ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፩
8me ANNE. № 1

ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፩ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ ም።
JEUDI 31 DECEMBRE 1951

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የብርሃንና ሰላም ዕድሜ ።

ብርሃንና ሰላም ከወጣ እነሆ ፯ዓመቱ፡ አልፎ የ፰ኛ ዓመት መጀመሪያው ቀን ነው።በዚሁ ቀን ምን ማሰብ ይገባን ይሆን? ለኔ እንደሚመስለኝ በዚህ በ፯ዓመት ውስጥ በብርሃንና ሰላም ተመርተን ምን አሻሽለን ይሆን?ማለት ይገባናል ምንም በነዚህ ዓመታት ብዙ ሥራ ብንሠራባቸው የበለጠ የቤተ ክርስቲያንን ነፃነት ጀምረንበታል።ለሰው ከነፃነት የበለጠ ዕድል የለውም።ነገር ግን ለአዋቂ እንጂ ለአለ አዋቂ ከፉ ደረሰበት ቃላል ይመስለዋል ። ነፃነት የሚጠበቀው በምን ነው ? ትለኝ እንደ ሆነ ምላሹ አጭር ነው ።

የነፃነት መጠበቂያ መጀመሪያው መስማማት ።

፪ኛው ወገን ወዳጅ ሳይመርጡ ሠራተኛውን በሥራ ማስቀመጥ ነው ።

፫ኛ የገበሬውን ግብር ማቅለል ነው

፬ኛ የራስን ጥቅም ብቻ ትቶ የሀገርን ጥቅም ማሰብ ነው። ይህስ እንዴት ነው? ትለኝ እንደሆነ ጥቅሜ ይቀራል ብሎ ብልሁን የታመነውን ሠራተኛ ወደ ታች አለመጫን ነው ። የሀገር ነፃነት ካልተጠበቀች ገንዘብን መሰብሰብ ወዴት ሁኖ ሊበላ ይሆን ?ሽማግሌ ሲተርት ይበላው ካጣ ይበላበት ያጣ ያሳዝናል ይላል። ይህም የሚተረተው ደባል በበዛበት ቤት ነው።

ሌባና ወምበዴ ባለቤቱን ለመግደል የሚፈልጉት ክብሩን ሊሹ ነው እንጂ ሰው መግደል ከማራቸው አለችግር ብቻውን በቀዳዳ ጎጆ የሚገኘው ድኃው ነበር። በቀድሞ ዘመን እንድ ወምበዴ ገንዘብ አለው መስሎት ድኃውን ገድሎ ፉጦ ሲዶ ቢአየው ገንዘብ አለመያዙን አይቶ ወይ እኔ ጥይቴን አበላሸኋት አለ ይባላል ። የጭፍራ አለቃ ከፋ የጦር ቀን በመጣ ጊዜ ተዋግቶ ለመንግሥቱ ይረዳል እኔንም በመልካም ስሜን ያስጠራዋል ብሎ መልካሙን ጀግና መምረጡን ትቶ ዕድሜውን የለከው ይመስል ይህስ ጕበዝ ዕንቅፋት የአገኘኝ ዕለት እኔን ማዕርግ ፈላጊ ነው ይልና ማር የሚአጭድለትን፡አጥር የሚአጥርለትን፤ ደንጊያ የሚፈልጥለትን ጅል ከፍ ከፍ ያደርግና እንደልቡ ኑሮ በጭንቀቱ ቀን ጌታውን አዋርዶ ይቀራል ። ይህም በሰገሌ ጦርነት ቀን ተመስክሮአል የንጉሥ ሚካኤል አሽከር የዘበኛ አለቃ አድርገው የሾሙት ተሰማ እርገቤ የሚባል ጀግና ነበረ። በጦሩ ቀን አንተ ዘበኛ ነህና ደጄን ሁነህ በኋላችን ጠብቀን ቢሉት፤ጌታዬ ስንት ቀን ላታልለዎ ምን ውታደር አለኝ እኔ የሰበሰብሁት ማር የሚያጭዱልኝን፤ አጥር የሚአጥሩልኝን፤ ደመወዙን ብቀማው የማይናገረኝን ባላገር ነው በኋላ ተሰለፍ ብለው ጥሎኝ ይሸሻልና እኔንስ ከነጭፍራዬ በፊት ያስቀድሙኝ ብሎ ቀደመና ከነልጁ በፊት ወደቀ ይባላል። እሱ ደግ ሰው ቢሆን ኃጢአቱን አውቆ በፊት ሞተ።ነገር ግን የጭፍራ አለቃ ብቻውን ረድቶ ምን ያህል ይጠቅማል ጀግኖችን መርጦ በደኅና ጊዜ አዘጋጅቶ ቢሆን ይህ ጀግና ጌታውን ምን ያህል ይጠቅም ነበር ?

ደስ የሚአሰኝ ወሬ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ከነበሩበት መኳንንቶቻቸው ጋራ ይመጣሉ ተብሎ ከተወራ ብዙ ቀን ሁኖ ነበርና የምስር ንጉሥ ፋዓድ ቀዳማዊ፣ ለመኳንንቶቻቸው የሰጡዋቸው ትእዛዝ እንዲህ ነው።የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጅ አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ሊመጡ ነውና ከምስር ቦታ ሁሉ በምትበልጥ ገዚራ በምትባል ቦታ እንዲአዘጋጅላቸው ዘማሊክ የማባለውን ፖሊስ(ዘ፡ኛ) በቶሎ አሰናዳላቸው ብለው ትእዛዝ ሰጡ። [illegible] ለጤንነትና ለዕረፍት ደስ የምታሰኝ ስለሆነች እንግሊዞች በምስራቅ ያን ሥራ ገብተው ይሠሩ በነበሩ ጊዜ ይኖሩበት ነበር።ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ ወደ ፖርት ሳዒድ መግባት እሑድ በኅዳር ፳፯ ቀን ገቡ።አቶ ጳውሎስ መናሞ የኢትዮጵያ ቆንስል ከኢየሩሳሌም መጥተው ወደ መርከብ ገብተው የተሸለሙትን ሽልማት ለብሰው ተገናኝዋቸው። ሌላ ሰው እንዳይገባ ባገረ ገዡ ተከለከለ በዝግታ አረፋ ዱና በ፱ት ሰዓት ወደ [illegible] የታጠቁ፡ ኒሻን የለበሱ፡ቍጥራቸው እጅግ የበዛ ፈረሰኞች ተሰልፈው ሙዚቃ እየተመታ ሰላምታ እየሰጡ ተቀበሏቸው ብዙ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ።ይህ ሁሉ ከተደረገ በኋላ ወደ [illegible] ገብተው ትንሽ ጊዜ ዐርፈው የዓባይን ውኃ የሚያጠራ

መኪና ያለበትን ቦታ አሳይዋቸውና ወደ አገረ ገዢው ቤት ከክቡራን መኳንንቶቻቸው ጋራ ተጠርተው ምሳ ተጋበዙ። ከዚህም በኋላ ወደ ኳስ መጫወቻ ቦታ ወሰዷቸው። ጨዋታውም ከተጨረሰ በኋላ መጀመሯ እቴጌ መነን ፥ ኋላም ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከገንጣሬ ወደ ፖርት ሳዒድ የመጡበትን ነጭ መርከብ አመጡላቸውና በ፲፭ ሰኞ በ፩ ሰዓት ተሡል ከፖርት ሳዒድ ወደ ገንጣሬ ሔዱ። በተለየ ባቡር ሲሔዱ አድረው ወደ ሀገረ ቅድስት ወደ ኢየሩሳሌም ገቡና ጎልጎታን የጌታችንን መቃብር እጅ ነሥተው ወጥተው ደር ሡልጣን መግቢያ ያለው በር ግርማዊት እቴጌ መነንና ንጉሡ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እናስገባም ብለው የከለከሉዋቸውን ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰንንና ክቡራን መኳንንቶቻቸውን ግብፃውያን ተቀብለው በሩን ከፍተው አስገቡዋቸው። በዚህ ጊዜ ለኢትዮጵያውያን ብዙ ደስታ ሆነላቸው። ከቅድስት ሀገርም የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግር ከረገጠበት ቦታ ደርሰው አይተው ታኅሣሥ ፩ቀን ዓርብ ማታ ወደ ገንጣሬ ገቡ። ከዚያም የፖርት ሳዒድ አገረ ገዢ መጥተው ልዑል አልጋ ወራሽንና ክቡራን መኳንንትን እንኳን በደኅና ተመለሳችሁ ብለው የሚሄዱበትንና የሚሳፈሩበትን ባቡር አሰናድተው ተመልሰው ወደ ፖርት ሳዒድ ሔዱ። ልዑል አልጋ ወራሽና ሰዎቻቸውም በተሰናዳላቸው ባቡር በ፩ ሰዓት ተነሥተው ሔዱ። በምስር የተደረገላቸው ሥራና አከባበር ከሁሉ የበለጠ ነው ።

ማርቆስ ወልደ ጊዮርጊስ ።

ስለ ብርሃንና ሰላም አወጣጥ ።

አባት ነጋዴ በንብያ የረከሰውን አንሥቶ ፤ የተወደደውን ከሩቅ አምጥቶ እህሉን ለወርቅ፥ ወርቁን ለጨርቅ እያለዋወጠ የሕዝብን ጥቅም እንዲያስገኝ የዚሁ ምሳሌ የሚሆን ብርሃንና ሰላምም የተሠወረውን ገልጦ ፤ የራቀውን አጉልቶ ብልሀን ትብልህ ፤ ሥራን ከሥራ እያገናኘና እያገናዘበ የራቀውን አቅርቦ ፤ የቀረበውንም አርቆ በማሰማት ከቆመ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለመሩዋቸው ቀና ቀና ሥራዎች ዓይነተኛው ረዳት እሱ መሆኑን ግንዛቤተኞቹ ሁሉ ይመሰክሩለታል ። ነገር ግን የረኸጥ (በሰር) ወጥ ለሠረው ጥፍጥ እንዲሉ አንዳንድ ሐሳባቸው ያልተቃናና ንግግራቸው ያልታረመ ሰዎች ለራሳቸው ብቻ ደግ መስሎ ስለታያቸውና ስማቸው ከመጽሐፍ ውስጥ ቢገኝ አዋቂዎች የሚባሉ ስለ መሰላቸው ቀዋሚነት የሌለውን ፈረሽ ነገር እየጻፉ ግድ ይታተምልን በማለት ሠራተኞቹን ያስቸግራሉ ለሚታተመውም ቋሚ ነገር ስፍራ በማጣበብና ጊዜ በማስተላለፍ ተቃዋሚዎች ይሆናሉ ። ነገር ግን አስቀድመው ላዋቂ ቢያሳዩት የሚያስፈልግ አለመሆኑን በነገሯቸውና እነሱ ደክመው ሰውን ከማድከም በዳኑ ነበር ። ሁለተኛም የብርሃንና ሰላም አነሣሡ ለቀዋሚ ሥራ ብቻ እንጂ ለግብዝ ነገርና ለከንቱ ውዳሴ አለመሆኑን ያላስተዋሉ ብዙ ሰዎች ባልሠሩት ሥራ መመስገን ኃጢአቱ እንዳይረሳ የማሰሰብ ያህል መሆኑን ባለማወቃቸው ላም ባልዋለችበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ አመስጋኞቻቸውን እያስነሡ ባልሠሩት ሥራ መመሰገኛ ሊያደርጉት ይፈልጋሉ። ይህም ከንቱ ነገር ነው ለምሳሌ ሌባ የሰረቀውን ገንዘብ ይዞ ከደኅና ሰው ቤት የገባ እንደሆነ ባይሆንስ ነገሩ እስኪመረመር ድረስ ያ ከቤቱ የገባበት ሰው ጥምር ይነቀፋል እንጂ ሌባው ከደኅና ሰው ቤት ቢገባ ሌባ መሆኑ ይቀራል ተብሎ አይጠረጠርም ። እንደዚሁም ሁሉ ሥራቸው ደግ ሳይሆን በበጎ ሠራተኛነት ስም የምስጋና ቃል እንዲጻፍላቸው የሚጣጣሩ ሰዎች በጎ ሥራ ሠርተው የሚገባ ምስጋና የተጻፈላቸውን የደጋግ ሰዎችንም ምስጋና ሐሰት ለማስመሰል ነው እንጂ እውነትስ ድንጊያውን ወርቅ ብር ፤ ሰገጨቱን ብረት ፤ አፈሩን እህል ቢሉት እንደማይሆን ፤ ፈሪውን ጀግና ፤ ንፉግን ለጋስ፤ ዋሾውን እውነተኛ ፤ ጨካኙን ርኅሩኅ ፤ አላዋቂውን ብልህ፤ ሥራ ፈቱን ሠራተኛ ብለው ቢጽፉለት ምስጋናው የሚጠጋው አይደለም ። እውነትና ንጋት እያደር ይገኛል እንዲሉ ይልቁንም ያለበቱን ላላወቁት ለማስታወቅ ነው። ነገር ግን እውነተኛ ምስጋና የተጻፈላቸውን ሰዎች ምስጋና መንቀፋችን አይደለም ። አሁንም ይህን የምታነቡ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ፤ እውነተኛ ምስጋናችሁ በእውነተኞች የታሪክ ጸሐፊዎች መጽሐፍ ውስጥ ይገኝ ዘንድ በየሥራችሁ እንድትጠነክሩ እንጂ እንደ ተውሶ ልብስ አድሮ በማይገኝ የሐሰት ምስጋና ከመመስገን እንድትርቁ አሳስባችኋለሁ ። በመንፈሳዊውማ ነገር ስንኳን ባልሠሩት ሥራ መመስገን የምንሠራት የበጐነት ሥራ ሁሉ የይዉልኝ ሥራ አይሁን ተብሎ ተጽፏል። ማቴ ፮ ። ሦስተኛም በኦሪቱ ሥርዓት ወንድ ልጅ በተወለደ በስምንተኛ ቀኑ ግዝረት ይደረግለታል (ግዝረትም ማለት) ግልተ ጽሩይ እንዲሆን በሰውነቱ ያለውን ቍልፈት ወይም ሰንኰፍ ቈርጦ መጣል ነው ። ሥራን በማስፋት፥ አገርን በማቅናት የወንድ ልጅ ምሳሌ የሚሆን ብርሃንና ሰላምም ከተወለደ (ከተጀመረ) ይኸው ስምንት ዓመቱ ነውና ዛሬ የመገረዣው ጊዜ ስለሆነ ለወደፊት በሚያትመው ቃል የሚያስፈልግ ንግግርና ከንቱ ውዳሴ ቀርቶ ቃሉ ሁሉ ምሥጢሩ የተደላደለ ፤ ንግግሩ የተካከለ፥ አንባቢዎች የሚወዱት ፤ ሰሚዎች የሚፈቅዱት ፤ ሥራን የሚያቋቁም ፤ ሀገርን የሚጠቅም ነውና ከሕፃንነቱ ወራት ይልቅ ዛሬ በጕልማስነቱ ጊዜ የበለጠ ሥራ ሠርቶ የአባቱ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ስም እንዲያስመሰግን እምነት ሳይጐድልባችሁ በመልካም ሐሳብ የምትረዱት ወዳጆቹ ሁሉ ለሀገር ጥቅም ፤ ለአንደበት ጣዕም ያለውን ቃል እየጻፋችሁ እርዳታችሁን እንዳታጐድሉበት አሳስባችኋለሁ ።

መኰንን ኢያቄም ።

ለጊዜው የተስማማ ጥያቄ ።

ከአንድ ጓደኛዬ ጋራ እየተጫወትን ስንሔድ በጫዋታችን መካከል እንዲህ ብሎ ጠየቀኝ ጥያቄውም እንዲህ ነበር።

፩ኛ፤ እረ በል ወንድሜ አገራችን የሥራ ጥቅም ያገኘችው የሌላ ቋንቋ በተማሩት ልጆችዋ ብቻ ነውን ወይስ በሀገራቸው ትምህርትና በተፈጥሮዋቸው ቅንነት እየተመሩ በሚሠሩት ልጆቿ ይሆን ? እስቲ የሚበልጠው ጥቅሟ ከማናቸው ወገን ይመስልሃል ? ።

O P BRITISH MUSEUM 21 JUL 36 B M

፪ተኛ፤ እግዚአብሔርንስ መፍራት ለማነው ? ።
፫ኛ፤ ንጉሥንስ መፍራት ለማነው ? ።
፬ኛ፤ መታመንስ ፡ ለማነው ? ።
፭ኛ፤ ትክክለኛነትስ ለማነው ? ።
፮ኛ፤ ቅንነትስ ለማነው ? ።
፯ኛ፤ ሕግ ተከታይነትስ ለማነው ? ።
፰ኛ፤ ያለ ቅርታ ማገልገልስ ለማነው ? ።
፱ኛ፤ የራስንስ ጥቅም አለመፈለግ (መጥላት) ለማነው?።
፲ኛ፤ አገርንስ መውደድ ለማነው ? ።

እንግዲህ ለነዚህ ለዓሥሩ ጥያቄዎቼ የሚበቃ ምላሽ ትስጠኝ ይሆን ቢለኝ ምላሹንስ አሁንም ለጊዜው በልቤ የታሰበኝንና ከዚሁም ቀደም ባይኔ ያየሁትንና የሰማሁትን አመልስልህ ነበር ነገር ግን ይኸውም ጥያቄህ ላሁን ድንገተኛ ነገር ስለሆነብኝ አሁን ብመልስልህም ምናልባት የድፍረት ታድርግብኛለህና ፈቃድህ ቢሆን የቀን ቀጠሮ ስጠኝና የሥራ ጓደኞቼ ለሆኑት ሁሉ ነገሩን አመልክቼ ለጥያቄህ የሚበቃ ምላሽ በኋላ እነግርሃለሁ ብዬው ቀጠሮ ተለያየን ።

ለዚሁ ጥያቄ ምሳሌ የሚሆን ጥቂት እንጉርጉሮ ።
ብርሃንና ሰላም ያሳብ መነጽር ።
ይህንን ጥያቄ አብክህ መሰክር ።
ብርሃንና ሰላም የሚያነብም ሁሉ ።
መች ይዘነጋዋል ይዞታል በቃሉ ።
እኔ በሐሳቤ እንደሚመስለኝ ።
የተፈጥሮ እውቀት ነው የሚያስገርመኝ ።
ተማሪ ቤት ሳይሔድ ገንዘብ ሳያሰኝ ።
የተፈጥሮን እውቀት እስቲ አድንቁልኝ ።
የቀድሞ ንጉሦች እንዴት ብልሆች ናቸው ።
መጥረቢያ መላጊያ ሞረድ ሳይኖራቸው ።
ዕንጨት አለስልሰው (አሳምረው)አልጋ መሥራታቸው።
በዕንጨት ሠራተኞች እናንት ሲደንቃችሁ ።
ብረት ሠራተኛ ንጉሥ መጣላችሁ ።
ይህም ለተፈጥሮ ማስረጃዬ ነው ።

በኃይለ ሥላሴ ስለ አገኘነው ። የብርሃንና ሰላም ተላላኪዎች የሥራ ጓደኞች የሆናችሁ ለዚህ ጥያቄ የሚያስረዳ ምላሽ እንድትረዱኝ እጄን ዘርግቼ እጠብቃለሁ። ለገሠ ቸሩ ።

የውጋዴን መንገደኞች ዜና።

ስለ ውጋዴን አውራጃ በመስከረም ፲፫ በተጻፈው ጋዜጣ ወደ ፊት መንገደኞቹ ሲመለሱ የነገሩን አኳኋን እንደንጽፈው ለአንባቢዎች ተስፋ ተሰጥቶ ነበር፤እነሆ የሐረር እንደራሴ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም ውጋዴን ለማቅናት በታቀደው አሳብ ከደራጁዋቸው መልካም ሥራዎች ዋና ዋናዎቹን ቀጥለንእንጽፋቸዋለን

፩ኛ ክቡር የሐረር እንደራሴ ደጃዝማች ገብረ ማርያም ሐዊያ ከሚባለው አውራጃ ሲደርሱ ኤልጉበያ በሚባለው ቦታ ላይ ከተማ ሠርተው አገሩን የሚጠብቅ ዳኛና የሚበቃ ዘበኛ አስቀምጠውበታል ይኸውም ስፍራ ለሐረር አቅራቢያው ስለሆነ ስሙን ጎረቤት ብለው ሰየሙት።

፪ኛ ፊቅ በሚባለው ቦታ ከተማ ተሠርቶ አገር የሚጠብቅ ዳኛና ዘበኞች እንዲቀመጡበት አድርገዋል ።

፫ኛ ጊሪባቤ ውሥጥ ገለልቻ በሚባለው ቦታ ላይ ከተማ ተሠርቶ አገር ጠባቂ ዳኛና ዘበኞች ተቀምጠውበታል ።

፬ኛ ማሊንጉር ውሥጥ ወረሒርሲ የሚባለው ቦታ እንደ ማቢያ ሁኖ ቤት ተሠርቶበት የሚበቃ ዘበኛ ተቀምጦበታል ።

፭ኛ ለጋሀመዶ ላይ ከተማ ተሠርቶ ገበያ ቁሞአል የአውቶሞቢል መንገድም ከዚያ እስከ ደጋሀቡር ተሠርቶ ከዚያም እስከ ጅጅጋ ድረስ በከሚዮን ይገናኛል።በዚህም ከተማ አገር የሚጠብቅ ዳኛና የሚበቃ ዘበኛ ተቀምጦበታል ክቡር የሐረር እንደራሴ ይህን ከተማ ሲቈረቍሩና ገበያውን ሲያቆሙ ስለ መንገዱም ሥራ ትእዛዝ ሲሰጡ የሰዎች ሐሳብ ሥራው ወደ ፍጻሜ እንደማይደርስ ተጠራጥሮ ነበሩና ሁሉም ተሠርቶ በፍጥነት ስለደረሰ የከተማውን ስም ታመነ ብለው ሰየሙት ።

፮ኛ አማዲን ውሥጥ በለምበል በሚባለው ቦታ ላይ ከተማ ተሠርቶ አገር ጠባቂ ዳኛና ዘበኞች ተቀምጠውበታል ገበያም ቁሞበታል። በዚህ ከተማ አጠገብ የቀድሞ ሰዎች ሕንፃ ፀሎቤት ተገኝቷል። ክቡር የሐረር እንደራሴም የጥንታውያን ሕንፃ ስለተገኘበት የከተማውን ስም ኦሬት ብለው ሰየሙት ።

፯ኛ ራር አብዶሌ ውሥጥ ጣናን በሚባለው ቦታ ላይ ከተማ ተሠርቶ ገበያ ቁሞበታል ስለ ሀገሩም ጥበቃ ዳኛ ተሾሞበታል ዘበኞችም እንደሚበቃ ያህል ተደርገውበታል ደግሞ የአቶሞቢል መንገድ ወደ ቈራሄ ተሠርቷል። ይህ ከተማ የተሠራው ከብዙ አገሮች ወሰን ላይ ስለሆነ በዙሪያው ያሉ የያውራጃው ሰዎች ሁሉ ይሰበሰቡበታልና ስለዚህ የስሙን መመሳሰል የምሳሌውን መተከከል አይተው ስሙን ጣና ብለው ሰየሙት ። በጣና ባሕር ብዙ ወንዞች እንደሚሰበሰቡበት የታወቀ ነው ።

፰ኛ በቈራሄና በደጋሀቡር መካከል ሰሰበኔ በሚባለው ቦታ ላይ እንደ ማብያ ሁኖ ቤት ተሠርቶበት የሚበቃ ዘበኛ እንዲቀመጥበት ተደርጓል። ይህም ማብያ ወደ ቈራሄ ለሚጓዘው ከሚዮን ተዳማዊ ምዕራፍ ይሆነዋል ።

፱ኛ ራር አብዶሌ ውሥጥ ቈራሄ ላይ ከተማ ተሠርቶ አገሩን የሚጠብቅ ዳኛና የሚበቃ ዘበኛ ተቀምጦበታል። ገበያም እንዲቆምበት ሁኗል። ይህ ስፍራ ከውጋዴን መሬት ሁሉ ይልቅ ነፋሻ ስለመሆኑና ውኃውም እጅግ ማለፊያ ስለሆነ የከተማው ስም እርጎ ተብሎ ተሰየመ።

፲ኛ ወደ ዳርቻ በኩል ሲል ቀልቀሎ በሚባለው ቦታ ላይ ባላባቱ እንዲከተምበትና ዘበኞች እንዲቀመጡበት ተደርጓል ።

፲፩ኛ ዋቢ ሸበሌ ላይ ቡስሌ በሚባለው ቦታ ከተማ ተሠርቶ፥ ገቢያም ቁሞበት አገሩን የሚጠብቅ ዳኛና የሚበቃ ዘበኛ ተቀምጦበታል። ክቡር የሐረር እንደራሴ ብዙ ቀን ሲጓዙ ሰንብተው በሌላው ስፍራ ምንም ሳይገኝ ከዚህ በደረሱ ጊዜ በሁሉም ነገር ተድላ ስለሆነና ስፍራውም ደስ የሚያሰኝ ስለሆነ የከተማውን ስም ፋሲካ ብለው ሰየሙት ።

፲፪ኛ በዚሁ በዋቢ ሸበሌ ላይ ጅድሌ በሚባለው አገር እንደ ማቢያ ሁኖ ተሠርቶ ያማራም የሱማሌም ዘበኞች ተቀምጠውበታል ይህ ማብያ ዋና ያገር መጠበቂያ ስፍራ ስለሆነ ስሙን መትረየስ በር ብለው ሰይመውታል። የጕዞአቸውም ፍጻሜ እስከዚሁ ሆነና በደኅና ተመለሱ።

ክቡር ደጃዝማች ገብረማርያም የሐረር እንደራሴ ያቆሙዋቸውን የ፲፪ቱን ከተሞች ስም በተራ ጽፈን እንደገና እንደግመዋለን ።

፩ኛ ። ጎረቤት ።(የቀድሞ ስሙ ኤልጐበያ ።)
፪ኛ ። ፈቅ ።
፫ኛ ። ገላልቻ ።
፬ኛ ። ወረሒርሲ ።
፭ኛ ። ታመነ ። (የቀድሞ ስሙ ለጋህመዶ ።)
፮ኛ ። አሬት ። (የቀሞ ስሙ በለምበል ።)
፯ኛ ። ጣና ። (የቀድሞ ስሙ ጣናን ።)
፰ኛ ። ሰሰበኔ ።
፱ኛ ። እርጎ ።(የቀድሞ ስሙ ቄሬሄ ።)
፲ኛ ። ቀልቀሎ ።
፲፩ኛ ። ፋሲካ።(የቀድሞ ስሙ ቡስቤ ።)
፲፪ኛ ። መትረየስ በር ።(የቀድሞ ስሙ ጅድሌ ።)

እነዚህ ከተሞች በቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በመመሥረታቸው ለኋላው ዘመን መልካም መታሰቢያን እንደሚያቆዩ እናምናለን። የቀረውን በሚከተለው እናትማለን።

መርስዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ

ስለመሬት ዓሥራት ማስታወሻ ።

ከዕለታት ፩ቀን ሁለት ባላገሮች ስለ መንግሥት ዓሥራት የተሰጠውን የመሬት ግምት ደምብ እንሥተው ሲጨቃጨቁ ድምፃቸው ስለተሰማኝ የተጣሉበትን ልጠይቃቸው አሳሰበኝ አንዱ ባለመሬት አንዱ ጢሰኛ ኑረው ጠባቸውን ቀጥሎ እንደተጻፈው አስታወቁኝ ።

(ጢሰኛ)እኔ ከዚህ ቀድሞ ለዚህ ለባለመሬት ጢሰኛ ሁኜ መሬቱን እያረስሁ ካሥር አንድ ለመንግሥት ዓሥራት፥ከአራት አንድ ለባለመሬቱ እርቦ እየሰጠሁ እኖር ነበር አሁን ግን ባለመሬቱ ባዲሱ ደምብ አንዱ ጋሻ በሙሉ ተገምቶ የመንግሥቱን ድርሻ እሰጣለሁ ። አንተ ግን የኔ ጢሰኛ ነህና እንደቀድሞው ካሥር አንድ ዓሥራቱን አውጥተህ ለኔ ስጠኝ ስላለኝ መንግሥቱ የሰጠን ደንብ ለሁላችን ነው ።እኔም ያረስሁት መሬት እንደድርሻዬ ተገምቶ እሰጣለሁ እንጂ እንደቀድሞው ደምብ ዓሥራት አልሰጥም በማለት ተጣልተናል አለኝ።

(ባለመሬት)ቀድሞ መሬታችን ያፈራውን የመንግሥት ዓሥራት እንሰጥ ነበር ። አሁን ግን ደጉ ንጉሣችን በሰጡን ሕግ መሬቴን በሙሉ አስገምቻለሁ ።ለመንግሥትም እንደግምቱ ድርሻውን እሰጣለሁ ከጢሰኛዬ ግን እንደቀድሞው ዓሥራት እቀበለዋለሁ ብሎ ነገረኝ ስለዚህ ሁለቱ ገላጋይ አጥተው ሲጨቃጨቁ ስላየኋቸው ለባለመሬትና ለጢሰኛ አስተዳደር ደምብ በርሻ ሚኒስቴር አስታዋሽነት ታገኛላችሁ ብያቸው መንገዴን ሔድሁ ። (የግልግል ሐሳብ)ባገር ላይ የተመረጡት የመሬት ገማቾች ባንድ ጋሻ መሬት በድምር ብቻ ይህን ያህል ብለው ገምተው ከመሔድ ባንድ ጋሻ ውሥጥ ያሉትን ማሳዎች በዝርዝር ገምተው ባለመሬትና ጢሰኛ እንዲያውቁት አድርገው ዝርዝር ከድምር ይገምቱ ጢሰኛም ያረሰውን ግምት ለባለመሬቱ እንዲከፍልና ባለመሬት በዝርዝር ተቀብሎ እንደተሰጠው ደምብ ድምሩን ለመንግሥት ቢከፍል ባለመሬትና ጢሰኛ ዕርቅ ያደርጉ ይመስለኛል ።

ደምሴ ወልደ ሐዋርያት ።

ሀብታምና ድኃ

ሁለት ሰዎች አንዱ ሀብታም አንዱ ድኃ በአንድ ወንድማችን ቤት ተገናኝተው ስለ ሀገር ፍቅር ጭውውት ተነሣና የድኃ ሰውዬ ዛሬ በፀሐዩ ንጉሣችን ጊዜ ለሀገራችን ጥቅም እንዲህ ብናደርግ ይሻል ነበር እያለ ልዩ ልዩ የሆነ እርባና ያለው ነገር እየጠቀሰ ሲያጫውተን ያሀብታሙ ሰውዬ የቤቱን ባለቤት በችኰላ አስጠራና በየጋዜጣው የሰለቸኝን ነገር ለምን ታስነዘንዘኛለህ አሁንም ይኸን ምናምንቴ ድኃ አስወጣልኝና ልጠጣ ያለዚያ ተነሥቼ መሔዴን እወቅ አለው ። ባለቤቱም ደነገጠና እየተንቀጠቀጠ ያንን ድኃ ሰውዬ ጌታ ተቈጥተዋልና ዝም ብለህ መጠጥህን ጠጣ ያለዚያ ከቤቴ ወግድልኝ አለው ፤ ያም ድኃ አንተው ጠርተህ አመጣኸኝ እንጂ በግዴታ አልመጣሁብህም ፤ ደግሞስ ከድኆች ወንድሞቼ ጋራ ተገናኝተን ጥያቄ ስለጠየቁኝ ለሀገራችን የሚያስፈልጋትን ጕዳይ እንዲህ ቢሆን ደግ እኮ ነበር እየተባባልን የሥራ ረገድ እንሥተን ተጨዋወትን እንጂ አገር የሚጐዳ መንግሥት የሚነካ ክፉ ነገር አላመጣሁም ፤ በዚያውስ ላይ የጠላ ቤት ለባለጌ ልጅ መማቻ ለጨዋ ልጅ መጫወቻ እየተባለ ይተረካል ለምን ትቈጣለህ ብሎ ቢመልስለት ፤ ያሀብታም ድኃውን ሰውዬ አንት መናጢ አሁን አንተ ለፈለፍህና ምን ሊደረግ ነው ከሰውስ የሚቈጥርህ ማነው አለና በጥፊ እየመታ ከድንኳኑ አስወጣው ድኃውም ጫፉን ታግሦ ከእግሩ ላይ አጐንብሶ ይቅርታ ቢለምነው በጫማው ረገጠው። (ጠቀጠቀው።)በድንኳኑ ከነበሩት ጥቂቶች ሐሳቡን ተሰቅቀውት ነበርና ሀብታሙን ሰውዬ እንደዚህ ነዋ እንኳን አስተነፈሱን እያሉ መረቁት ። እረ ምን ይገርም ምን ይደንቅ ጥቅም የሚሆን ሐሳብ ቢያከፍልና ቢያጫውት ብርቱ አደጋ የጣሉበት ሌላ ጸያፍ ቢናገር ምን ሊያደርጉት ኑሯል ። ክቡራን አንባቢዎች ይኸነን አርእስት አድርጌ እንድትመለከቱት ቀጥሎ የተጻፈውን ለመጻፍ አሳሰበኝ ቃሉም ይህ ነው ። አስተዋይ ድኃ ደግ ሐሳብ ከልቡናው ያነቃል ሊያደርጋትና ሊፈጽማትም ይጀምራታል ፤ ግን የሐሳቡን ፍጻሜ በቀጥታ ለማስኬድና ለማቆም ያቅተዋል አጋር ወይም ገንዘብ የሚባለው ምሰሶ (ደገፋ)የለውምና ትፈርስበታለች ። ግን ደገኛይቱ ሐሳብ (የሀገር ፍቅር) በልቡናው ሠርፃለችና እንደ እሳት ልሳን ስታቃጥለው ታድራለች ቅድም እንደ ተናገርነው አንድ ብልህ ድኃ ለሀገር የሚረባ ለመንግሥት የሚረዳ አሳብ ቢያነቃ ይኸነንም ለማስደረግ ቢቃተል ድኃ ነውና ምኞቱ የተናቀ ይሆናል ። ያም ብልህ ድኃ ሐሳቡን የሚቀበለው ሲያጣ ሁለተኛም ችግርና መጕላላት ሲበዛበት ከብስጭት የተነሣ ጥልቅ የሆነ እውቀቱ እየተጎደለ ይሔዳል ፣በኋላም ከደንቆሮች እንደ አንዱ ወይም እንደ ዕብድ ይቈጠራል የሥራውንም ጊዜያት በከንቱ ያሳልፋቸዋል ። በቀደሙት ዘመናት በራስ ቢትወደድ

ተሰማ እንደራሴነት ጊዜ የኢትዮጵያን መጻሕፍት የተማሩ፤የአውሮፓን ታሪክ የመረመሩ ብላታ ገብረ እግዚአብሔር የሚባሉ ሊቅ ነበሩ ፤ እንደ ዛሬ እንደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ብልህና አዋቂ በሥራው አልተጠቀመም ነበርና ለመንግሥትና ለሀገር የሚረዳ ነገር እየጻፉ ቢያቀርቡ የሚቀበላቸው ስለ አጡ ክንዴት የተነሣ መጠጥ ይጠጡ ጀመር።አንድ ወዳጃቸው የሆነ ሰው መጠጥ ሲጠጡ አይቶ መጠጥ አብዝተው ለምን ይጠጣሉ ብሎ ቢጠይቃቸው፤እኔ ሐሳቤ ለራሴ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለሀገሬ መንግሥትና ለሕዝቤ ነበር ግን ነገሬን የሚቀበለኝ ስለ አጣሁ አሁን ሐሳቤ ተለውጦ ጊዜ ለማሳለፍና ቀኑ እንዲመሽልኝ፤ ሌሊቱ እንዲነጋልኝ ብቻ ነውና ስለዚህ መጠጥ ግድ የሚያስፈልገኝ ሁኖ አጠጣለሁ ብለው መለሱለት ይባላል ። እሳቸውም ለሀገራቸው ቀናኢ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ ሁሉ ማንም አይስተውም ነገር ግን ከላይ እንደ ተባለው የብስጭት ንግግር ይመስላል ። ሰማችሁ መርከብ ያለ ውኃ፤ ባቡር ያለ ሐዲድ፤ካሚዮን ያለ መንገድ ለመሔድ እንደ እማይችል የብልህንም እውቀቱን የሚያስኬድለት ዕፁብ ድንቅ የሚያሰኝለት ማኅንት ነው ግን በድኅነትና በችግር ገመድ ክተያዘ ምንም ብልህ አዋቂ ቢሆን ሐሳቡ አይከናወንለትም፤ ለሀገር ጥቅም የሚሆን ነገር ቢናገርም ለብዙዎች ነገሩ አይጥምም፥ይኸውም ሊታወቅ የሀገራችን ልጃ ገረዶች በአበባ ተቀዳጅተው ለመስቀል(ለደመራ) በዓል እንዲህ እያሉ ሲዘፍኑ እንሰማለን ቃሉም ቀጥሎ ያለው ነው፤ አበባም አለኝ ያዘምር ሀብታም ሲናገር ምን ያምር ፤አበባም አለኝ የከስከሶ ድኃ ሲናገር ዕሬትና ኮሶ ብለው ይገጥማሉ እውነትም ይህ ቃል እርግጥ እንደሆነ ያስረዳናል።ሰሎሞን በተግሣፁ የድኃ ብልሀቱ የተናቀ ነው ብሏል ክብሩን ሆይ ከሆነማ ከድኆች ልቡና ለምለሚቱ የጥበብ ቡቃያ ትበቅል አልነበረችምን፤ነገር ግን ምን ይሆናል ችግር የሚባል ማዕበል እያነገለ ወደ ውጭ ይጥላታል። ይኸውም ሊታወቅ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ከድኆች ወንድሞቻችን የነቃ ለሀገር ጥቅም የሚሆን ማስታወሻ እየተጻፈበት በየሳምንቱ እናያለን ፤ ምናልባት በሥራ ብዛትም ይሁን ከተጻፈው ሁሉ የተደረገው ጥቂት ሳይሆን አይቀርም ስለዚህ ዋና አስታዋሽ ሊሆንበት ያስፈልጋል ፤ አሁንም ለአለፈው ክረምት ቤት አይሠራምና የአለፈውን ትተን ወደ ፊት ብንገፋ ይሻላል ፤ እንደዚህ ያለውን ለሀገርና ለመንግሥት የሚያስተዳድረውን፤ ወደ እውቀት ፍሬ የሚያደርሰውን ደኅና ደኅናውን ሐሳብ ከጋዜጣው ውሥጥ እየቀሰሙ በማስታወሻ ቢጽፉትና በአማካሪ ቤት እየተመረመረ ለጊዜው የሚቻለውን በፍጥነት ቢያቆሙት የሚዘገየውንም ከላይ እንደ ተባለው በማስታወሻ አቈይቶ በጊዜው እንዲሠራ ቢያደርጉት መልካም ይመስለኛል ። ሰሎሞን ለሁሉ ጊዜ አለው እንዳለ ኢትዮጵያም የእውቀትና የሥልጣኔዋ ጊዜ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ነውና ደማችንን ማስከበር፤ ሰንደቅ ዓላማችንን፤መጠበቅ፤ ሥራን ከነሠራተኞቿ፤እውቀትን ከነአዋቂዎችዋ መሻት ይገባናል ።

በቀለ አበዬ

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአቦካትነት ሥራ ይሠራሉ በአገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክ አገር የፍርድ ቤት ብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ናቸው ። ለዚሁም አቦካትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጅሮንድ ዘለቀ አግደው ግቢ ነው። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፯ት ሰዓት ይቀበላሉ ።

ማስታወቂያ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ድርሰትና ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው በአንድነት ተጠርዞ በ፲፭ ብር መሸጡን እናስታውቃለን ።

ደግሞ በአማርኛና በፈረንሳዊ ቋንቋ የታተመ ጥራዙ ጠንካራ ሁኖ የተጠረዘ (የሬኮማንዴ) ያደረ ወረቀት ማስፈረሚያ ደብተር በ፫ብር ይሸጣል ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።



ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሲንጀር ከቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሲንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ከታኅሣሥ ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመት ምሕረት ጀምሮ የምስር መንግሥት ቆንስላ ጃንሜዳ ወደ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ቤት መዛወሩን ለሕዝቡ እናስታወቃለን ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምሀርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር ፣ ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቲፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመመ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የከትበት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የከትበት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትበበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምባሳል ፡ የልብ፡ የደረት፡ የጉበት፡ የኩላሊት ፡ የጅማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቍቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፡ የርሻ የፋብሪክ ፡ የደን ፡ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።

አበከት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ቁአሩጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ላሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፤ ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂሰኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፪
8me ANNE. № 2

ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም።
JEUDI 7 JANVIER 1932

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የልደት በዓል።

የልደት በዓል በየዓመቱ በታኅሣሥ ፳፱ቀን እንዲሆን ሊቃውንት ወስነውታል። ነገር ግን በ፫ቱ ዓመት ደኅና ተሰማምተው ኑረው በ፬ኛው ዓመት በዘመነ ዮሐንስ በጳጕሜ ፮ መሆን ምክንያት በታኅሣሥ ፳፰ቀን የልደትን በዓል እናክብር በመጽሐፍም እንዲሁ ተጽፎአልና የሚሉት ሊቃውንት ኦርቶዶክሳውያን (ተዋሕዶዎች) ተባሉ ። በዓል ማድረግ በመብል በመጠጥ አይደለምና ፳፰ኛውን ጾመን እንዳለፋት ዓመታት በ፳፱ነኛው ቀን ፋሲካ እናድርግ የሚሉት ጸጎች፡ ቅባቶች ተባሉ። በዚህም ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ሁሉ ታላቅ ሁከት ሁኖ ሲኖር አቡነ ማቴዎስ እንብላ ከሚሉት ወገን ስለሆኑ ተዋሕዶ የሆኑት ረትተው ይኖሩ ነበር። ዘንድሮ ግን ፳፰ኛው ሐሙስ፡ ፳፱ነኛው ዓርብ ስለሆነ ሐሙስ ገድፈን ዓርብን እንጹም የሚሉ አሉ። በዓሉን በ፳፰ኛውስ ቀን ብናደርግ ፳፱ነኛውን ቀን ዓርብን ከጾምን በዓሉን መሻራችን አይደለምን በሁለቱም ቀን ፋሲካ ማድረግ ይገባናል የሚሉ አሉ ።

ይህ መሆኑ ረክበ ካህናት የሚባለው የካህናቱ መገናኘት በዓል በዓመት አንድ ቀን የሚደረገው ስለቀረ ነው። እንደተጻፈው በየዓመቱ ተሰብስበው ቢሆን አንድ ጊዜ ብቻ ተጣልተው ተከራክረው ብዙዎች ያሉት ተጽፎ በየቤተ ክርስቲያኑ ይገኝ ነበርና በየዓመቱ እንግዳ አድርጎ ከመከራከር ያድን ነበር። ምንም ጾም እንደኛ ባያጠቃቸው ኦርቶዶክሳውያን የተባሉት ግሪክና መስኮብ፡ግብፅ፡ ሶርያና እንጾኪያ የቀሩትም በዚህ ስም የሚጠሩ ብዙ አሉና ከነዚህ አንድነት አድርጎ ተስማምቶ አንድ ቁርጥ ነገር ማድረግ ነው እንጂ በየዓመቱ ተጣልቶ ነገሩ ሲአልፍ ዘንግቶ ዘለዓለም መቄየት ለቤተክርስቲያን የማይገባ መስሎ ስለታዩን ነገሩን መርምረው ብፁዓን አባቶቻችን እንዲፈጽሙት ተስፋ እናደርጋለን ። ይህንም ማሰባችን የጎረቤቶቻችንን ዕረፍት እያየን ነው።የልደትን በዓል በታኅሣሥ ፳፭ቀን በኛም አቈጣጠር በታኅሣሥ ፲፮ቀን በየዓመቱ ይውላሉና ምንም ሰውን የሚአጣላው መብልና ጾም ቢሆን በየዓመቱ ሳይከራከሩ ያሳልፉታል። ይኸም መደረጉ አንድ ጊዜ ስለ ወሰኑት ነው እንጂ ጠባያቸው ከእኛ ተሽሎ አይደለም ። ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ ግን ብሉ ብለው በይነዋል ።ነገር ግን ቤተክርስቲያን አንድ ሁና ወስና ካልጸፈችው ቀዋሚ አይሆንም። በብዙ ዓመት አንድ ቀን ዓርብ ቢገድፍ ብዙ የሚአስቀይመውን የሕግ መተላለፍ የሚችል አምላክ በዚህ ይከፋዋል ብለን አይደለም፡ በታናሽ ነገር የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዳይጠፋ ብለን ነው።ይበላ ያሉትም በዓሉን ስለማክበር ብለው ነው እንጂ የአንድ ቀን ምግብ ምን ያህል እንዳይጠቅም አጥተውት አይደለም። የሆነ ሁኖ ዘኒ በልዐ ለእግዚአብሔር በልዐ ወዘኒ ተሐረመ ለእግዚአብሔር ተሐረመ ይላልና ሁሉንም ተስማምታችሁ ብታደርጉት የሚሻል መሆኑን እናመለክታለን ።

በመሬትና በሴት ምክንት ይጕድላል በረከት።

እህል ካልተዋጠ ጥጋብ ፡ ወሬ ካልተደመጠ ጥበብ አይገኝምና ብላታ ጆሬሳ ስለእርሻ ምክንያት የጻፉትን በኢትዮጵያና በምስር መሬት መካከል ያለውን የሀብት መበላለጥ በብርሃንና ሰላም በ፯ኛ ዓመት በ፬፻፬ገጽ በተመለከትሁት ጊዜ ከዚህ በታች የጻፍሁትን ቃል ለማሳሰብ መሬ ሆነኝ።መሬትና ሴት ፡ ባልና ገበሬ እነዚህ አራቱ አንድ ናቸው። ገበሬና ባል ዘር በማቀበል፡ ሴትና መሬት ዘር በመቀበል ተስማምተው ይኖራሉ ። ከነሱም የተነሣ የዘር መራባት፡ የሀብት ብዛት፡ የሀገር ልማት፡የመንግሥት ክብረት ለዓለም ይተርፋታል ። ነገር ግን መሬትና ሴት በድንግልና ቢኖሩ መራባት ይጠፋል። የሰውም ትውልድ ከብዛቱ ይጕድላል ። ከዚህም የተነሣ አገር ምድረ በዳ ይሆናል።ከእህል ፍሬ እስከዱር አውሬ እንዳች ነገር አይገኝም ። በዚህም ምክንያት መንግሥት ወደመደኅየት ፡ ባላገር ወደስደት ይደርሳል ። አንዳንዱም ባላገር ዕርፉን ጥሎ ጠመንጃ አንጠልጥሎ ለየመኳንንቱ ተከታይ ሁኖ ለመኖር ወደከተማ ይገባል። ባላገሩ ካልጠገበ ከተማው አይጠግብምና ችጋሩ አይለቀውም ።

(የዋሁ ባላገር ሆይ ይልቁንስ ለመሬት አሽከርነት አድረህ የእርሻውን ትልም ብትከታተል በተሻለህ ነበር) እንዳንዱም ባላገር ራቅ ብሎ ሒዶ ዱር መንጥሮ ባጭር ታጥቆ ፤ ዕርፍ እርቆ ማረሱ ይቀርና የቤቱን ጓሮ ብቻ እየጫጫረ በማዳበሪያ መሬቱን ሳያዳብር መልሶ መልሶ ባመት በመቱ ያንኑ

ቢዘራው ቡቃያው እየኰሰሰ፡ ምርቱ እያነሰ ከመሔድ በቀር ምንም ትርፍ አይገኝበትም። መሬት ሲያረጅ መጭ ያፈራል እንዲሉ ከእርጅናው የተነሣ እህል የሚያደክም አረም እያበቀለ በባላገሩ ድኅነትን ያመጣበታል።ያባት ዕዳ ለልጅ ያፍንጫ እድፍ ለእጅ እንዲተርፍ ባላገሩ ደኅይቶ መንግሥቱን ያደኽያል።ባላገር ካልጠገበ ከተማውም ተራበ ።

ነገር ግን ቡርክት ኢትዮጵያ በመልካሙ ንጉሠ ነገሥት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሀብት ስለተባረከች በእህል ወገን ጉዳት የለባትም።ስለዚህም የሚሻል ነገር ለእኔ እንደሚመስለኝ የሚታረሰው መሬት በከተማው አውራጃና በየባላገሩ መንደር ኀሮ ያለው መሬት ብቻ ስለሆነ መሬታችን መላው ለም እንዲሆን ጠፍ በበዛበት አገር ላይና በየዳርቻው አገር ላይ አልፎ አልፎ ከተማ ቢመሠረት ከተማውን ሲፈልግ ብዙ ሰው ይሰበሰባል። በዚህም ምክንያት መሬቱ ውድ ሁኖ ይታረስና አገሩ ይከብራል።መንግሥትም ገቢ በዝቶለት ከመደሀየት ይድናል ።

በየዳር አገሩ ውሥጥ ያለው ጠፍ መሬትስ ትጽፎ አይልቅምና በየመሀሉ አገሩ ያለውን ጠፍ መሬት ቀጥሩን በጥቂቱ ጽፌ እገልጻለን በበጌምድር ከጐንደር እንሥቶ ፍርታ በርን አልፎ እስከ ውዶ፡በጐጃም ከሞጣ እንሥቶ እስከ ደብረ ወርቅ ያለው መሬት፡ከጋላ አገርም ክፍል የሚበልጠው መሬት ባለመታረሱ ለባላገሩና ለመንግሥቱ ምን ያህል ጥቅም እንደቀረበት እስኪ እናስተውለው ? በጭር ግምት እኔ የማውቀውን ብቻ ጠፍ መሬት ጻፍሁ እንጂ እንደምንሰማውስ ቢሆን ከሚታረሰው ለማይታረሰው ብልጫ አለው ለማለት ያደፋፍራል መሬት ስትመክን የሰውም ሀብት ይመክናል መሬት ወላድ ስትሆን የሰውም ሀብት ይወለዳል ።

ምንም አንዳንዱ ሰው በእርሻና በማናቸውም ገቢ ገንዘብ ቢከብር የግል ጥቅሙ ብቻ ስለሆነ ከመካከል ያለውን የባላገሩን ለሙን መሬት መርጦ ባላገሩን በወርቅ አባብሎ መሬቱን ይገዛና ከዚያ በኋላ ግራና ቀኝ ያለውን መሬት ለመደረብ ወንድሜ አቶ እገሌ የሚቸግርህ ነገር እንዳለ ብርም ብትል ብር እህልም ብትል እህል ውሰድ ዝም ብለህ ትመልስልኛለህ ።

ነገር ግን ምንም ባልጠረጥርህ ለደንቡ ግን ጥራልኝ ይለዋል ። ያም ድሀ ያዘነለት ይመስለውና እሺ ብሎ ጫማ ይስምና ጥንድ ዋስ ጠርቶ እየመረቀ ከብሩ በዛ ከእህሉም ገሩ አድርጎ ተበድሮ ይወስዳል።ያሀብታም ግን ወጥመዱ እንደ ያበት አውቆ ወሩን፡ቀኑን፡ዓመተ ምሕረቱን፡ጽፎ ተበዳሪውንና ዋሱን አስፈርሞ ደብተሩን በሣጥኑ ያኖራል ። እምጣም አይለውም ብቻ ወለዱን እያሰበ ዝም ብሎ ብዙ ዘመን ያኖራል።ነገር ግን ገንዘቡ በዛ ሲልና ድሀው ለመክፈል እንደማይቻለው ሲሆን አይቶ አቶ እገሌ ያንን ገንዘብ ብትሰጠኝ ደግ ነበር ይለዋል ያም ባላገር እሺ እያለ ሁለት ሦስት ቀን ያድራል ። ኋላ ዋሱ በታሠረ ጊዜ ምን አደርጋለሁ ብሎ ለዚያ ለሀብታም መሬቱን ተፈርሞ ይለቅለታል ። ይህንም እጅ ካደረገ በኋላ ደግሞ በወሰኑ ያለውን መሬት በዚሁ ዓይነት እጅ አድርጎ ይይዘዋል ።

ስለዚህም ሀብትና መሬት ወደሀብታም ቤት ይገባሉ፡ከድኃ ቤት ይርቃሉ ። ባላዋቂ ቤት አዋቂ እንግዳ ናኘበት እንዲሉ ድኃው በሞኝነቱ ርስቱን ለቆ ይሰደዳል ። ሀብታሙ በተንኰሉ ባለርስት ሁኖ ይኖራል ። ከዚህ በኋላ ሀብታሙ መሬቱ ስለበዛ ማረስ ይቸግረውና ከመሬቱ የሚበዛው ጠፍ ሁኖ እየኖረ የመሬት ሀብት ሳይታወቅ ይኖራል ።

ስለዚህም ነገር የሚሻል መስሎ የታየኝን ብጽፍ አይከፋም ። ሀብታም በቤቱ ሰው ልክ ለትዳሩ እንደሚበቃው እየተገመተ ይዛዝ እንጂ ብዙ ብር አለኝ ብሎ ብዙ መሬት እንዳይገዛ፡ድኃም ተቸገርሁ ብሎ መሬቱን በመሸጡ የሚጠቀምበት ካልሆነ በቀር በዕዳ ምክንያት አሳልፎ እንዳይሸጥ ግምቱን ለባለዕዳው መንግሥት ከፍሎ ባለርስቱ ቢችል እርሱ ወጥቶ ወርዶ ባይችል ከሱ በኋላ የሚነሱ ልጆቹ ወጥተው ወርደው ገንዘብ አፍርተው ለመንግሥት ዕዳቸውን ከፍለው መሬታቸውን እጅ እስኪ ያደርጉ ድረስ መሬቱ ለመንግሥት ኩዳድ ሁኖ ብዙ ጥቅም ቢያስገኝ ይሻል ይመስለኛል ።

በዚህም ሁለት ጥቅም አለበት አንደኛ መንግሥት የድኃ አባት ነውና ከሠራሽ ጠብቆ ርስት ለድኆች ልጆች ማቈየቱ ትልቅ እርዳታ ነው።ሁለተኛም መሬቱን መንግሥት ቢአሳርሰው በጥቂት ዘመን ከዋጋው አትርፎ ብዙ ዐጠፌታ ያስገኛል አገር ተባብሮ በመላው ቢከብር ነው እንጂ መልካምነቱ አልፎ አልፎ ከየወረዳው አንዳንድ ሰው ቢከብር ጥቅሙ አጭር ነው ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ።

የ፬ተኛ ገጽ ተከታይ ።

የጀግናውን መቃብር መጐብኘት ።

ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም በመትረየስ በር ላይ ሰፍረው ሳሉ በመከኔ ሚዳ የተቀበሩትን የፊታውራሪ ወልደ አማኑኤልን መቃብር ለመጐብኘት ሐሳባቸው ሆነና በ፲፫ መስከረም ከመቃብሩ ላይ አበባ አስቀምጠው ተመለሱ።መቃብሩም ከዋቢ ሸበሌ ወንዝ ማዶ ነበርና ውኃው ከብዛቱ የተነሣ ሚዳውን ሁሉ አጥለቅልቆት በታንኳ ሲሻገሩ አንድ ሰዓት ተኩል አቈያቸው ። ፊታውራሪ ወልደ አማኑኤልም የልዑል ራስ መኰንን የታመኑ አሽከርና መልካም አርበኛ ነበሩ ። የ፲፰፻፹፱ ዓመተ ምሕረት ከዋቢ ማዶ ያለውን የውጋዴንን ግዛት እንዲጠብቁ ከጌታቸው ታዝዘው ሔደው ሲጠብቁ አረማውያን ጠላቶች በድንገት ጦር አንስተው ገደሉዋቸውና እዚያው መከኔ ተቀበሩ ስለዚህ ያ ስፍራ የፊታውራሪ ወልደ አማኑኤል መቃብር እየተባለ ባለ ምልክት ሁኖ ሲጠራ ይኖራል ። አሁንም የሐረር እንደራሴ ይህን ማድረጋቸው የመታሰቢያውን ምልክት እንዳፀኑና ስለ ኢትዮጵያ የፈሰሰውም ደም እንዳከበሩ ይገልጻል ። ወይም እኮ በዚህ ስፍራ ያአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ይተከል ይሆናል ?

ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም ከዚህ ስፍራ ከተመለሱ በኋላ እርስ በርሳቸው ይዋጉ ለነበሩት ወገኖች በፍርድ ጉማ እየከፋፈሉና በመሐላ እያስተራረቁ ለወደፊቱም ሕግ እየሰጡ ጕዞአቸውን ወደ ኋላ አቀኑ ። ያገሩ ሽማግሌዎችም ለዘበኝነት ሥራ የሚሆኑት እየተመለመሉ ሰልፍ እንዲማሩ አድርገዋል። በሰልፍ ትምህርት እንዲያሠለጥኑ ተመርጠው የተሾሙትም

ቀድሞ ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል በጅጅጋ በሰልፍ ሥራ አሠልጥነዋቸው የተመሰገኑት ዘበኞች ናቸው ። ደግሞ በየጥናው ከተማ ፴ ፴ ጠያር ከነዘበኛው እንዲሠለጥን ተደርጓል ።

የሕዝብ ሙያ ።

ሱማሌዎች በአነጋገር የተራቀቁ ሁነው በእጅ ሥራ እምብዛም ያህል ናቸው ። እርሻ ከለማወቃቸውም የተነሣ መሬቱን በአንካሴ እየጠቁሙ አልፈው አልፈው አንዳንድ የማሽላ ፍሬ እንደ ችግኝ ይተክሉበታል ። ሀገሩ ግን ከሀብታምነቱና ከሙቀቱ የተነሣ እንደምንም አብቅሎ በሁለተኛው ወር ለምግብነት ያደርስላቸዋል ። ብዙ ፍሬም ያቀርጻቸዋል ። አሁንም ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም የእርሻን ሥራ በአገባቡ ለማስለመድ የበሬ ዕቃ አሠርተው እርሻ የሚያስተምር ገበሬ አስቀምጠውበት መጥተዋል ።

የጕዞ መመለስ ።

የሐረር እንደራሴ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም በመስከረም ፲፱ ከመትረየስ በር ተነሥተው በየስፍራው የተወጠኑትን ሥራዎች እየጐበኙና እያዩ መንገዶቹንም እያስጠረጉ በ፲፰ ኅዳር ቃመን ወደተባለው ከተማ ገቡ ። ከዚህም በኋላ በአውቶሞቢል ሁኖ በየስፍራው የተሠሩትን መንገዶች ለማየትና የጅጅጋን ከተማ ለመጐብኘት ስላሰቡ መጀመሪያ ደጋሀቡር ደረሱና ከተማውንና አዲሱን ቤተ ክርስቲያን ጐበኙ (፪ኛ) ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ ወደ እርጎ ከተማ ያሠሩትን መንገድ ጐበኙ ። (፫ኛ) ከደጋሀቡር ወደ ጅጅጋ መጥተው ባላምባራስ እሸቴ ያሠሩትን ቀጥ ያለውን የሐበርአወሉን መንገድና የአይሻውን ጥርጊያ ጐበኙ ። ቀጥሎም በጅጅጋ የተወጠኑትን ዋና ዋናዎቹን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አይተው ፥ ይልቁንም የልዑል ራስ መኰንንን ትምህርት ቤት ጐብኝተው ስለ እርዳታም አንድ መቶ ብር ሰጥተው ሠራዊቱ ወዳለበት ወደ ቃመን ከተማ ተመለሱ ። የብዙ ቀን ጕዞ የነበረውን አገር ሁሉ በጥቂት ቀን በአውቶሞቢል አዳርሰው መመለሳቸው ሥራ ለሠሪዋ እንደምትጠቅም የሚገልጽ ነው ። ቃመን ከተማ ከደረሱ በኋላም ሠራዊቱን አስከትለው በእግር ጕዞ ወደ ሐረር ገብተዋል ። የኢትዮጵያ አርበኞች በሰላም ወደ ቤታቸው በመግባታቸው ለእግዚአብሔር ታላቅ ምስጋና ይሁን ።

ለአንባቢዎች የሰጠነው ተስፋ እንዲፈጸም ስለ ውጋዴን መንገደኞች የሰማነውን እርግጠኛ ዜና በጭሩ ጽፈናል ። የቀረውንም ረዳቶቻችን እንዲመሉት ተስፋ እናደርጋለን ።

መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ።

የሒሳብ መረዳዳት ።

በቍጥር ፶፩ ብርሃንና ሰላም በገጽ ፬፻፪ የተጻፈውን ስመለከት አንድ ግሬኛ የዕርዕ (የግሬክ) ተወላጅ በንጹ የኢትዮጵያ ተወላጅ ላይ ያደረገውን የግፍ ግፍ ስላነበብሁና ይኸውም ንባብ የጥቍሮችን ክብር ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ቅሌት ስለ መሰለኝ ከዚህ የሚቀጥለውን ልጽፍ ጊዜ ፈቀደልኝ መጀመሪያ እግዚአብሔር ሲፈጥር እኩሉን ቀይ ፥ እኩሉን ዝንጕርጕር ፥ እኩሉን ጥቁር ፥ እኩሉን ነጭ እያደረገ ነው ። ይህም እኔ ላሁኑ የጻፍሁት በተሠራ በጨርቅና ባልተሠሩ በዕፀዋት ነው ። ነገር ግን ሰው በኑሮው አንዱ ለጌጥ ቀዩን ይመርጣል ። አንዱ አረንጓዴውን ይመርጣል፤ አንዱ ለጌጥ ነጩን ይመርጣል፤ አንዱ ለጌጥ ጥቁሩን ይመርጣል ፥ ጥቁርን በአጻጻፍ ወደኋላ በማስቀረቴ ተርታ አላበላሸሁም ወደፊት እንዲቀድም ስለ ተረዳሁት ነው ። በዚህ መከከል ዓለም በሙሉ ለክብር የመረጠው ጥቁሩን ነው ። ጥቁር የክብር ልብስ መሆኑን ዓለም መስክሯል ። ሮማውያን በደስታ ጊዜ ለምሳም ሲጠሩ፤ ለእራትም ሲጠሩ ጥቁር ልብሳቸውን ለብሰው ነው የሚሔዱ ። እንግዲህ ጥቁር የማዕርግ ልብስ ከሆነና በክብር ጊዜም የሚፈለግ ከሆነ ጥቁር ክቡር ነው ብዬ ከዓለም ሁሉ ማስረጃ ተቀብዬ ልመሰክር ተንጠራራሁ ። ሰሎሞንም በመጀመሪያው መኃልዩ እኔ ጥቁር ነኝ ውብ ነኝ ይላል ።

ነገር ግን ይህ ሰው የእግዚአብሔርን ፍጥረት ሳይመረምር ነው እንጂ ነጭና ጥቁር ከመሬት ያመጡት መልክ ነው ። ኋላም መሔጃቸው ወደ መሬት ነውና ነገ በሚጠፋው የሰውነት ቀለማቸው መኩራት አይገባቸውም ነበረ ።

ግብረ ድንግል ደበቤ ።

ማስረጃ ።

ሚስተር ፍራንክ ሐይተር በጥንት ዘመን የንግሥተ ሳባ የገንዘብ ቤት የነበረውን አግኝቶ ቍርጥራጭ ያልሆነ ሩብያና አልማዝ ፕላቲንና ወርቅ ይዞ አገሩ ገባ ብሎ ዋዬርሌስ ፕሬስ የጻፈውን እንዛቤ ከዚህ ቀደም በብርሃንና ሰላም የጻፍኩትን የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ስለተጠራጠረ በኅዳር ፬ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓም በቍጥር ፵፩ የጻፈው በቶሎ ስላልደረሰኝ የሚያስፈልገውን ነገር ሳልጽፍ የቀረሁት ስለዚህ ነው እንጂ በተቀር እውነቱን ደጋግሜ ለመጻፍ እንደማያስቸግረኝ አውቃለሁ ።

አሁንም መልስ ብሎ ከጻፈው ውሥጥ ከወዳጆቼ ጋራ ሁኜ ሳወጣ ሳወርድ ይህን ሰው የሚያውቁት ኑረው ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሔደበት ምክንያት ለሥራ ከተቀጠረ ባልንጀራው ጋራ ሁኖ የሔደ ነበረ አሉኝ ማለት ሚስተር ፍራንክ ሐይተር ወደ ኢትዮጵያ ለአደን መምጣቱንና ሥራውም ትልቅ አዳኝ መሆኑን ራሱ በእንግሊዝ ጋዜጣ የጻፈውን ሐሰት የማድረግ ያህል ነውና ደግሞም ከዚህ ይልቅ ይኸ ሰው ከአዲስ አበባ ፫፻፳ ማይል የሚርቅ ሰው ባልመረመረው አገር ያህን የከበረ ገንዘብ በተሸሸገ ስፍራ አገኘሁ ብሎ ግልጽ አድርጎ በጋዜጣ ላይ ሲያጽፍ የጥንቱን የንግሥተ ሳባን ገንዘብ ቤት በገዛ ራሱ መርምሮ አገኘ ለመባል ችሎት ያሰው ነው ብዬ እንደበቱ አይደፍርም ማለት ለሰውዬው የመርዳት ያህል ነው ።

የወርቅ ኰንሴስዩን ውል ካላቸው ሰዎች ስፍራ በልዩ ብልሃት ይህን የከበረ ገንዘብ አግኝቶ ይሆናል ማለትም የተገባ ምክንያት አይደለም የብርሃንና ሰላም ተላላኪ እኔ ስለ ጻፍሁት ነገር የሚበቃ ምስክር የሌለኝ መስሎት ጥርጣሬውን

ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች በማከፋፈሉ ለአገር መቈርቈር ያለባቸውን ወደ ፊት ማናቸውንም ለአገር ጥቅም የሚሆነውን ለመጻፍ ተስፋ ሲያስቈርጣቸው ይታየኛል ።

እውነትን ስለተጠራጠረ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፳ በቍጥር ፳፱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቶማስ ያለውን ጥቅስ ያሳስበኛል ።

ኢየሱስም አለው ። ቶማስ ሆይ ስላየኸኝን አመንህ ምስጋና ይገባቸዋል ሳያዩ ለሚያምኑ ።

እኔ የጻፍሁት ይህ ሰው ይህን የከበረ ገንዘብ እላይ እንደተጻፈው ሁሉ ወሰድሁ ብሎ የጻፈውን ጋዜጣና ዋዬርሌስ ፕሬስ አነበብሁ እንጂ ይህን ልዩ ልዩ ገንዘብ ሲወርድ አብሬ ነበርሁ ብዬ እንዳልጻፍሁ የታወቀ ነገር ነው ። ግን ይህ ነገር ሲወሰድ ብኖር ኑሮ ያገር ፍቅር የሚያዘኝን ትእዛዝ በደስታ እንደምፈጽም ወቃሽ ሕሊናዬ ይመሰክራል ።

ስለዚህ ጥርጣሬውን እምነት ሊያስወግደው ቢፈልግ የጋዜጣውን አድራሻና ስም የተጻፈበትን ቀን ከነዋጋው ከዚህ በታች ያገኘዋልና ገዝቶ ማንበብ ነው ።

እንዲሁም ይህን ጋዜጣ ከዚህ በታች እንዳለው አድራሻ አስመጥቶ አንብቦ እኔ እንደጻፍሁት ልክ ያልሆነ እንደሆነ በውነት ያገር ፍቅር የሌለብኝ ለአገሬ የማልቈረቈር መሆኔን ተረድቶ ሌሎችንም ለማስረዳት ያን ጊዜ ይችላል ።

ኃይለ ገብርኤል ነገሮ።

ከራስ ይልቅ የወንድምን ጥቅም መፈለግ።

በቀድሞ ዘመን ዳርዮስ የሚባል አንድ ንጉሥ ነበረ። ይኸውም ንጉሥ ራሱ እንዴት ብሎ እንዲጠራና እንዲታወቅ የበለጠ ስም ሲፈልግና ሲመረምር ጊዜዮቱን በዚህ ሲያሳልፍ ይኖር ነበር ። ስለዚህም ራሱን ንጉሠ ነገሥት ዳርዮስ ብሎ ጠራው የሃይማኖት ጠባቂ የሕዝብ ሁሉ ገዥ ሆነ የሚገዛቸውም አገሮች ከሕንድ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ መቶ ሀያ የመንግሥት አገሮች ነበሩ ይባላል ። ከሰምንት በሀለት ቀን የስሙን ማዕርግ ይለውጠው ነበር። አሽከሮቹንም በጣም የከበረና የተደነቀ ግብር ያበላቸው ነበር ። ይህነንም ማድረጉ ስለ አፈቀራቸው አይደለም ስሙን እንዲአስጠሩና እንዲመሰገን ነው። አንድ ጊዜ በቤተ መንግሥቱ በፊት ያልነበረ ተደርጎም የማይታወቅ ሌሎችም ነገሥታት ያላደረጉትን ግብር እንዲዘጋጅ በቤተ መንግሥቱ አዘዘ በቤተ መንግሥቱም በወጭም በውስጥም አጥሩም ግቢውም የቤቱ ግድግዳም ጣራውም ሁሉ በወርቅና በብር እንዲለጠፍ፤ በዝሆን ጥርስ በሐር እንዲጌጥ አዘዘ፤ በቢያውም ላይ ድል ያደረገውንና የማረከውን ነገር ሁሉ በሥዕልና በቅርጽ እያደረጉ ሣሉት የወይን ጠጅም ከይሁዳ፤ የማር ጠጅም ከሲቢየ፤ ፍሬም ከኢትዮጵያ አስመጣ።

ከዚህም በኋላ የንጉሥ መልእክተኞች ወደ እያገሩ ሁሉ ተላኩ በመንግሥቱ ያሉትን ታላላቆች ሁሉ ጠሩቸው የተላኩባቸውም ቃል ይህ ነው ከአፄ ዳርዮስ ከፔርሽ ንጉሠ ነገሥት ከመሳፍንቶቹና ከአሽከሮቹ ከአለቆችና ከባላባቶች ሁሉ ሰላም ላናንተ ይሁን ሁላችሁን በማክበር አጠራችሁአለሁ። የመንግሥቴን ኃይሉንና ክብሬን አሳያችሁ ዘንድ ከኔም ጋር ግብር መቶ ቀን ትበላላችሁ ከዋክብትንም መረመርሁ፤አዋቆችንም ጠየቅሁ ይህን አደርግ ዘንድ በዚሁም በተወሰነው ቀን የተጠሩት ሰዎች ሁሉ እንደጕርፍ ወደ ከተማው ይጐርፉ ጀመረ እነዚህም የተጠሩት ሰዎች ከገራቸው ሲመጡ ከብዙ መታያያና እጅ መንሻ ጋር መጡ። ለንጉሡም አበረከቱ ያበረከቱትም ዕንቍና ወርቅ፤ አልማዝ፤ ሐር ምንጣፍ፤ ሌላም በጣም የከበረ ነገር ሁሉ ነው የሹሻና ከተማም ዳር እስከ ዳር በማረ ሽቶ ተረጨች ንጉሡም በዙፋኑ ተቀምጦ መተያያውን ይቀበል ነበረ። ከዚህም በኋላ ተጠርተው የመጡትን ሰዎች እንደ ማዕርጋቸው ወደተዘጋጀላቸው ስፍራ አገቡአቸው። ጥሩምባ ነፊዎቹና መለከት ነፊዎቹ ከፍ ባለ ድምጥ ይነፉ ጀመሩ። ባለሙዚቀኞችም በሙዚቃ፤ ባለመሰንቆቹም በመሰንቆ በከበሮም ይጫወቱ ነበር ። የንጉሡም የመብያውና የመጠጫው እቃ ሁሉ ባዳራሹ ያለው ከከበረ ወርቅና ብር ነበር የተሠራ። ንጉሡም በግብር ላይ ሳለ እንዲህ አለ ባለፈው ሁለት ዓመት ለኔ አማካሪዎች የሚሆኑ ሦስት ሰዎች መርጬ ነበር ። አንደኛው የፔርሻ ሰው ፤ ሁለተኛው የሕንድ ሰው ፤ ሦስተኛው የአይሁድ ወገን ዘሩባቤል የሚባል እነዚህም አማካሪዎች በመንግሥቴ ካሉት ሰዎች ሁሉ ብልሆች ናቸው ።

ነገር ግን ከነዚህ ከሦስቱ የትኛው በብልሃትና በዕውቀት እንዲበልጥ አላውቅም ብሎ መኳንንቶቹን ጠየቃቸው የበለጠውን ብትነግሩኝ የሚፈልገውን እሰጠዋለሁ የመንግሥቴን እኩሌታ እንኳ ቢሆን አልከለክለውም ብሎ ተናገረ። ሰዎቹም አሰቡና አንደኛው መኰንን ተነስቶ እኛ ብልህነታቸውን የምናውቀው በንግግራቸው ነውና ስለዚህ ንጉሥ አንድ ጥያቄ ይጠይቁአቸውና ሦስቱም እንደንጉሥ ጥያቄ ይመልሱ አለ ንጉሡም ጥያቄ ጠየቃቸው እንዲህ ብሎ ከንጉሥ የበለጠ ኃይለኛ ምንድር ነው ብሎ ጠየቃቸው ። በመጀመሪያ ሊናገር የተፈቀደለት የፔርሻ ሰው ነበር ። ዕድሜውም አርባ አንድ ዓመት ነበረ ። እርሱም ተናገረ እንዲህ ሲል፤ እኔ የሚመስለኝ ከንጉሥ የሚበረታና ኃይለኛ የወይን ጠጅ ነው አለ። የወይን ጠጅ የሰዎቹን ነፍስ ይለውጣል ባርያውን አርነት የወጣ ያስመስለዋል ። አዘነተኛውንም ደስ ያሰኘዋል። ተማሪውንም ከአስተማሪው የበለጠ ያስመስለዋል ። ድሀውንም ሰው ከንጉሥ የበለጠና የከበረ ያስመስለዋል ። ፈሪውንም ደፋር፤ ዝምተኛውንም ተናጋሪ ያደርገዋል፤ ስለዚህ የወይን ጠጅ ጠንካራ ነው ብሎ በጨረሰ ጊዜ ከንጉሡ ጀምሮ ባዳራሹ ያሉት ሁሉ አጨበጨቡለት ፤

ሁለተኛ ሊናገር የተፈቀደለት የሕንድ ሰው ነበር ዕድሜውም ሰላሳ አንድ ዓመት ነበር፤ እርሱ እንዲህ አለ እኔ ከወይን ጠጅ የሚበረታ ንጉሥ ይመስለኛል ። ሰው ሁሉ ሞትን ይፈራል ንጉሥ ግን ሰዎቹን ለጦርነት ይሰዳቸዋል፤ እንዲወጉ እንዲዋጉ፤ ሊገድሉ ሊገደሉ፤ንጉሥ ተራራውን ሜዳ፤ሜዳውን ተራራ፤ ከተማውን በረሀ፤ በረሃውን ከተማ ሊአስደርግ ይችላል፤ንጉሥ የተመኘውን ሁሉ ያደርጋል ፤ የፈለገውም ይሆንለታል ስለዚህ የንጉሥ ኃይል ከወይን ጠጅ ይበረታል ብሎ በጨረሰ ጊዜ ዳር እስከ ዳር ድረስ ተጨበጨበለት ።

ሦስተኛውም ዘሩባቤል የሚባል የይሁዳ ባላባት ነበር ። በዕድሜውም የሀያ አንድ ዓመት ልጅ ነበር መልኩም ያማረ ነበር እሱም እንዲህ ብሎ ተናገረ እውነት ነው የወይን ጠጅም ኃይለኛ ነው ንጉሥም ኃይለኛ ነው።

ነገር ግን እንደኔው አሳብ ከዚህ ሁሉ የበለጠ የሴት ኃይል ነው አለ፡ሰዎቹም ከንግግሩ የተነሣ እርስ በእርሳቸው እየተያዩ ራሳቸውን እየነቀነቁ ያመሰግኑት ጀመር። የሚነግሡት ሰዎች ሁሉ ፥ ለጦርነት የሚሔዱት ፥ወይን የሚተክሉት የሚጠምቁትም ሴቶች ልጆች ናቸው፤ ሰውም ያለእናት ያለእኅት ያለሚስት ደስ ሊለው አይችልም ስለ ሴትም ብሎ እናቱንና አባቱን አገሩን ዘመዱን ትቶ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ ወደ እርሷ ይሔዳል ንጉሡም ስለሴት ብሎ መንግሥቱን ይለቃል ስለዚህ የሴት ኃይል ይበረታል ብሎ በተናገረ ጊዜ ለመኳንንትና ለአለቆች እርሱ የተናገረው ቃል እንደ ከበረ ዕንቍ መስሎ ታያቸው እንዲህ ያለ ብልህ ሰው አይተንም አናውቅ ብለው ተናገሩ። ዳርዮስም በጣም አጥብቆ ደስ አለውና እኅደህ አለ እናንተን ሦስታችሁን የኔ አማካሪዎች አድርጌ እኔና ሕዝቤ እውቀታችሁን አይተን መርጠናችሁ ነበር አሁንም ደግሞ ከናንተ ፤ ሦስታችሁ ብልህ ሁኖ የተገኘ እኔ ዳርዮስ የለመነኸኝን ሁሉ እሰጠዋለሁ እስከ መንግሥቴ እኩሌታ እንኳ ቢሆን ብዬ ቃል ኪዳን ገባሁላችሁ ስለዚህ ዘሩባቤል በልጦ ስለተገኘ የመንግሥቴን እኵሌታ ሰጥቼዋለሁ ብሎ ለዘሩባቤል ሰጠው።ዘሩባቤልም እንዲህ አለው የኔ ንጉሥ ሆይ የፈለግሁት ነገር ሁሉ በንተ ቸርነት ሁኖልኛል ነገር ግን የራሴን ጥቅም ብቻ ለማግኘት አልፈልግም የለመንኸውን ሁሉ እሰጥሃለሁ ብለህ ቃል ኪዳን ስለገባህልኝ ወንድሞቼን እስራኤላውያንን ብንተ አገር የተማረኩትን ወደ አገራቸው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱና ቤተ መቅደሳቸውን እንዲሠሩ አምላካቸውን እንዲያመልኩ ፍቀድላቸው አለው ንጉሡም በደስታ ፈቀደላቸው የዚያንጊዜ እስራኤል ወደ ባቢሎን ተማርከው ነበረ የሚጠብቃቸው ወታደርም አዘዘላቸው።ከግብርም ነፃ አወጣቸው ለቤተ መቅደስም እርዳታ ወርቅ ላከላቸው መኳንንቱም ሁሉ እንደተቻላቸው ረዱዋቸው ወደ አገራቸውም ተመለሱ ዘሩባቤል ግን ከራሱ ጥቅም የወገኖቹን ጥቅም ስለፈለገ ከባርነት ወደነፃነት ከድንቍርና ወደእውቀት መራቸው ። ይህችን አጭር ታሪክ ብናነብት የምታሳስበን ዋና ነገር ስለወገን ፍቅር ስለሆነ ለመጻፍ አሳሰበኝ እኛም ብንሆን ከራሳችን ደስታና ጥቅም የወገናችንና ያገራችንን ጥቅም ብንፈልግ ለስማችን ማስጠሪያ፥ ላገራችን ጥቅም፥ ለሕዝባችን ደስታ ጥለን እንሔዳለን ለወገን ለዘመድም ኵራትና መኳደጃ ይሆንለታል።ተገኘ ዮሴፍ።

መልካም ዕድል ።

ሙሴ ማቲክ ኪቦርኮፍ ከፈረንሳዊ መንግሥት ግራንድ ኦፊሴ ደ ኒሻን ኤፍቲከር የሚባለውን ኒሻን ደግሞ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በአንገት የሚታሠረውን የሁለተኛውን ማዕርግ የአፄ ምኒልክን ኒሻን ስለተሸለሙ ብርሃንና ሰላም እንኳን ደስ አለዎ ይላል ።

ስለ ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤ ከሮማ ወደ አዲስአበባ መግባት።

ክቡር ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤ በኢጣሊያ መንግሥት ከተማ በሮማ ዋና ባለሙሉ ሥልጣን የኢትዮጵያ ጉዳይ ፈጻሚ ሚኒስትር ሁነው ብዙ ጊዜ ቈይተው ነበር፡ የታማኝነታቸውን ሥራ ፈጽመው በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ ተጠርተው በታኅሣሥ ፲፱ ቀን በዓርብ ባቡር ከክብርት ባለቤታቸው ጋራ በደኅና ሰለ ገቡ ታላላቆች መኳንንትና ብዙ ሕዝብ በደስታ ተቀበላቸው ብርሃንና ሰላም እንኳን ደኅና ገቡ ይላል ።

የሚአሳዝን መርዶ ።

የናቴና የአባቴን ልጅ የወንድሜን፥ የሁለቱንም የታላቁንና የታናሹን ልጆቼን መርዶ በታኅሣሥ ፳፮ቀን በቴሌግራም ስለ ተረዳሁ መሪር ኃዘኔን ለወዳጆቼ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ለማካፈል ጽፌላችኋለሁ።በሩቅም የአሉትን አባቴንና እናቴን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እላለሁ ። ባላምባራስ በረኺ

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአቦካትነት ሥራ ይሠራሉ በአገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክ አገር የፍርድ ቤት ብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ናቸው ። ስለዚሁም አቦካትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጅሮንድ ዘለቀ አግዴው ግቢ ነው። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፯ት ሰዓት ይቀበላሉ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።
ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።
ፎርድ
ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።
ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሴንጀር ከቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፲ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክተ ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር ፤ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ. አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ከምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ክንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በቀመሙጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅኑ ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትበበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንጻ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፡ የልብ፡ የደረት፡ የጕበት፡ የኵላሊት ፡ የጆማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቋታ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዳሮውማዘጋጃ ቤት ^ ግንብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፡ የርሻ የፋብሪክ ፡ የደን ፡ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወዩም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም

ALEM



ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አበካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ጸአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙ ሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ፡ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፫
8me ANNE № 3

ሐሙስ ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም።
JEUDI 14 JANVIER 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል ባለግርማ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ወደ ፈረንሳዊ አገር መግባት ።

ልዑል ባለግርማ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን ከተከታዮቻቸው ጋራ የፈረንሳዊ ሕዝብ መንግሥት ፕሬዚዳን በታኅሣሥ ፳፫ ቀን በኤሊዜ (ቤተ መንግሥት) ተቀበሉዋቸው ።

ልዑል ባለግርማ አልጋ ወራሽ የጃንሆይን ደብዳቤ ለሙሴ ዱሜርግ ከደረሱና ከርሳቸውም ጋራ የወዳጅነት ቃል ከተነጋገሩ በኋላ በትከሻ የሚደረገውን የመጀመርያውን ማዕርግ ትልቁን የሰሎሞንን ኒሻን ሸለሙዋቸው ።

ክቡር ሙሴ ዱሜርግም ለልዑል ባለግርማ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን በትከሻ የሚደረገውን የመጀመርያውን ማዕርግ ትልቁን የሌጂዮን ዶኔርን ኒሻን ሸለሙዋቸው ።

ከዚህም በኋላ ልዑል ባለግርማ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን የፓሪስ ከተማ የማዘጋጃ ቤት ሹሞች በሆቴል ዴቪል (ማዘጋጃ ቤት) ተቀበሉዋቸው ።

ደግሞ የልዑል ባለግርማ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን መምጣትና አቀባበል አስቀድሞ የሚነግር ማስታወቂያ በቬርሳይ ቤተ መንግሥት ይቀበሉዋቸዋል፤ የሰንሲርን የጦር ትማሪ ቤትና የለማዩን ባቡር ሜዳ ለማየትም ይሔዳሉ ይላል ።

የንግድ ሥራ መሻሻል ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንግድን ሥራ ለማሻሻል አጥብቀው አስበውበታል። የንግድ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር አቶ መኰንን ሀብተ ወልድም ለዚሁ ለመልካሙ ሐሳባቸው ተከታይ ሁነው በትጋት ስለተነሡ እጅግ ተመስግነዋል ።

ንግድም እንዲሰፋ የነጋዴውም ችግር እንዲጠፋ ስለአሰቡ የነጋዴን ችግር መመርመርያ ለንግድም ማሻሻያ በተለየ የጽሕፈት ቤት አዘጋጅተዋል። ነጋዴውም የቸገረውን ነገር ሁሉ እያስታወቀ የተሻሻለ ነገር እንዲደረግለት ተስፋ ተደርጓል ። ነጋዴውም በአዲስ አበባ ዕቃው የሚሸጥበትን ልክ ሳያውቅ ገዝቶ በመጣ ጊዜ እንዳይረክስበት እዚህ የሚሸጥበትን ዋጋ የአዲስ አበባው ጕምሩክ እየጠየቀ በየሀገሩ ላሉት ነጋድራሶች በየጊዜው በቴሌግራም ሊአሳልፍላቸው ታዝዟል።የቀረጡም ነገር እንዲቀልለት ተወስኑዋል እንግዲህ የነጋዴና የገበሬ ነገር ታስቦ ከተሻሻለለት የሕዝብ ሀብት እየበዛ መሔዱ አይጠረጠርም።ነገር ግን ሰው እስበ ይህን ዓለም እንደእማይገፋው ታውቃላችሁና አገረ ገዢዎች ሁሉ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሐሳብ ተከትላችሁ የገበሬን ቀምበርና የነጋዴን ሸክም እንድታቀሉ የራሳችሁንም ጥቅም ብዛት ትታችሁ ለሕዝባችሁ ጥቅም እንድታስቡ ብርሃንና ሰላም ያሳስባችኋል ።

አስታዋሽንና አስታዋሽነትን መናቅ እንዳይገባ ማመልከቻ።

በማናቸውም ሥራ ላይ የቆመ ሠራተኛ በሚሠራው ሥራ ላይ እንደ ዕውቀቱ መጠን አሳመርሁ ብሎ በብዙ ትጋትና ጥንቃቄ የሠራው ሥራ ምንም ለራሱ መልካም መስሎ ቢታየው በያሉበት ሁነው ለሚአዩትና ለሚሰሙት ሁሉ ክፉ መስሎ የታያቸው እንደ ሆነ ከዚህ ላይ በጅተሃል፤ ከዚህ ላይ ተሳስተሃል፤ ከዚህ ላይ ተበላሽቶብሃል እያሉ የመቃወም ያይደለ የማስታወስ ምክራቸውን በቃልም በወረቀትም ቢያስታውቁት ያየሚሠራው ሥራ ለዘለዓለም ነዋሪ ነውና ለሥራው ርዳታ የሚሆነውን ምክር ከማግኘቱ የተነሣ ደስ ከመሰኘት በቀር የሚከፋው ሊኖር አይገባም።ደግሞም የዕውቀት ጕዳናዋ ልዩ ልዩ ነውና ያየተሠራው ሥራ ሳይሳሳት በምክር ከሚረዱት ሰዎች ለማናቸውም ቢሆን ሥራው የተሰናከለ መስሎት በታየው ጕዳና የምክር መልሱን ከሰጠ በኋላ ያው ሠራተኛ እደገና ምክንያቱን ገልጦ የሠራበትን ማስረጃ መልስ የሰጠ እንደ ሆነ ነገሩ እንዳልተሳሳተ ከተረዳው የሁሉም ድካማቸው ለሥራ ጕዳይ ነውና ነገሬ ተነቀፈብኝ ብሎ ሊያፍር አይገባውም። የዚህም ማስረጃ ሰው ሁሉ ለተነሣበት ነገር ማሰብ ልማድ ስለ ሆነ ምንም ዕውቀታችንና ሰውነታችን አነስተኛ ቢሆን ሥራችን መጻሕፍትን ማረም ሆነ የሥራ ሁሉ ምንጭ ነውና በለዚህም በግዕዝም በማርኛም በሚታተሙት መጻሕፍት ሁሉ የምሥጢሩን ተራ፤ የፊደላቱን ስፍራ፤ ያነጋገሩን ፋና (ፍለጋ) ጠንቅቆ ማወቅ እጅግ የሚያስፈልግ ስለሆነ ከኛ የተሠወረ-

ውን ከብዙ ሊቃውንት እየጠየቅንና መጻሕፍትን እየመረመርኝ ይልቁንም የግዕዙ ፊደላት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ስፍራ ስፍራቸው እየተሳሳተ ጸሓፊዎች ሁሉ የማይስማሙባቸው ስለሆነ የታተመ ነገር ለኋላ እንደ ምስክር ነው በማለትአርኄ መጽሐፍ እየተመለከትን ፤ ከየጠንቃቆቹ ጸሐፊዎች እየጠየቀን ከየግሡ አካሔድ በምሥጢር የሚለያይና የሚገናኘውንም እየመረመርን ደግሞ ከየስፍራው እየመጣ በጋዜጣ የሚገባውንም ቃል ባነጋገሩ እጅግ የሚለያይ ስለሆነ አማርኛው አንድ ዓይነት እንዲሆን ብማለት በብዙ መጨነቅና መቸገር እያቃናን ነው የምናርመው- ስለዚህም በእግዚአብሔር አጋዥነት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁብትና ለጋስነት የምናርማቸውን መጻሕፍት የምታነቡ ሁሉ ምሥጢሩ የተሳከረ ፤ ንግግሩ ያላማረ ፤ፊደሉ የተዛወረ መስሎ የታያችሁን ከላይ እንደ ተጻፈው የመቃወም ያይደለ የማስታወስ ምክራችሁን በቃልም በወረቀትም እንድታክፍሉን እንለምናችኋለን ። መኰንን ኢያቄም ።

የከምባታ ሕዝብ አማካሬ መምረጥ ።

በኢትዮጵያ መንግሥት ያገር ግዛት ሚኒስትር ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ ግዛት በከምባታና በሌም አውራጃ ያሉ መኳንንትና ሠራዊት በሆሣዕና ከተማ ተሰብስበው ታላቅ ጉባኤ ሁኖ ሐምሌ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም እንደወጣው ሕገ መንግሥት ደንብ ከየወረዳው አገር ተመርጠው መጥተው በተሠራው የምክር ቤት ውሥጥ ገብተው ከሚመክሩ አማካሪዎች ጋር ሁኖ የሚመክር ዕውቀት ያለው ደጓና ትክክለኛ ሰው ለመምረጥ የተደረገው ጉባኤ ከረጅሙ ባጭሩ ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች በተጻፈው ቃል ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እገልጽላችሁ ዘንድ ወደድሁ ።

በሀገሩ ክፍል ያለው መኳንንትና የሻምበል መቶ አለቃና አምሳ አለቃ የማዕርግ ልብሱን ለብሶ ጭፍራውን አስከትሎ ከጥዋቱ ባንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ ሦስት ሰዓት እጓቢ ድረስ እንዲሰበሰብ በጦሩ እንደራሴ በክቡር ፊታውራሪ አርገጤ በኩል አስቀድሞ የትእዛዝ ቃል አልፎለት ነበርና በተቀጠረው ሰዓት ሁሉም አንድ ሳይቀር ከሻምበል እስከ ወታደር ከባላባት እስከ ጭቃ ሹም ከትት ብሎ እንደተሰበሰበ በጸሓፊ ትእዛዝ በኩል ወዳገር ግዛት ሚኒስቴር የተጻፈውን ደብዳቤና ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው አባተ ወደ ፊታውራሪ ሽበሺና ወደ ፊታውራሪ አርገጤ የጻፉትን የትእዛዝ ደብዳቤ የጸሓፊዎቹ አለቃ አቶ መንግሥቱ በሕዝቡ መካከል ቁሞ በታላቅ ድምፅ አነበበ ።

ከዚህም ቀጥሎ ክቡር ፊታውራሪ አርገጤ ከተቀመጡበት ወንበር ተነሥተው ቁመው አሁን ጸሓፊው እፊታችን ቁሞ እንዳነበበው ቃል የያንዳንዳችንን ጥቅም ብቻ ሳይሆን የመላ ሕዝባችንን ጥቅም ለማስፋት በምክር ቤት ውሥጥ ገብተው ከሚመክሩ አማካሪዎች ጋር ሁኖ ለሀገር ስፋት ለሕዝብ ልማት የሚሆን ሥራ የሚሠራ አንድ ዕውቀት ከትዕግሥት ያደረበትን ሰው መርጠን እንድንልክ ስለታዘዝን ይህነኑ ትእዛዝ ለመፈጸም ተሰብስበናችኋልና እገሌና እገሌ የመረጡት ሰው ምርጫችን ነው ብላችሁ ከመኳንንትና ዕውቀት ካለው ተራ ሕዝብ ከባላባቶችም ጭምር መርጣችሁ እንድታስታውቁን እንለምናችኋለን ብለው ተናገሩ ።

የተሰበሰበው ሠራዊትም በቃል ብዛት ሁኖ ከዚህ በታች ስማቸው የተጻፈው መኳንንትና ባላባቶች የመረጡት ሰው ምርጫችን ነው ብሎ አጨብጭቦ ሰጠ ።

ሰብሳቢዎች ዳኞች ፊታውራሪ አርገጤና ፊታውራሪ ሽበሺ

መኳንንት ።

ፊታውራሪ ተሚኤ፡ ፊታውራሪ ደመር፤ ፊታውራሪ ተክሌ፤ ፊታውራሪ አይተንፍሱ ፤ ቀኛዝማች አድነው ፤ ፊታውራሪ ሳሙኤል ፤ ቀኛዝማች ደጄኔ ፤ ፊታውራሪ ወንድማገኘሁ ፤ ፊታውራሪ በላቸው ፤ ቀኛዝማች መኩሪያ ፤ ቀኛዝማች ወልደ ጻድቅ፤ ቀኛዝማች በቀለ ፤ ነጋድራስ ገርማነህ ፤ ቀኛዝማች ፈለቀ ፤ ቀኛዝማች ይግለጡ ፤ ቀኛዝማች ወልደ ማርያም ፤ ዳግም ቀኛዝማች ወልደ ማርያም ፤ ቀኛዝማች ኃይሌ፤ ግራዝማች እሸቴ፤ አለቃ ወልደ ሐና ቀኛዝማች ነጋሽ ቀኛዝማች ጣዉ (ፀሐዬ) ቀኛዝማች ደምሴ፡ ግራዝማች ደስታ፡ አቶ ሜጫ፡ አቶ ደጀኔ፡ ግራዝማች ተገኝ አባ ደፋር፡ ግራዝማች እጅጉ ፤ ግራዝማች ዘገየ ፤ አቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል

ባላባቶች ።

ፊታውራሪ ጋረዶ ፤ ቀኛዝማች አገዲስ፡ ግራዝማች በቾሬ፡ ጸሓፊው አቶ መንግሥቱና ገዛቱ ቆሞስ ፤ አባ ተክለ አረጋይ

ሠላሳ ሁለት መኳንንትና ሦስት ባላባቶች አንድ ጸሓፊና አንድ ቆሞስ ቄስ (ድምር ሠላሳ ሰባት)በልፍኝ አዳራሹ በቄይታ እንደተቀመጥን ቆሞሱ አባ ተክለ አረጋይ ከተቀመጡበት ተነሥተው ቁመው ወዳጅ ዘመዶችን ብላችሁ እንዳታደሉ ምሥጢር እንዳታወጡ ትክክለኛውን ሰው አይታችሁ መንፈስ ቅዱስ እንደገለጸላችሁ እንድትመርጡ ገዝቻለሁ በሥልጣነ ጴጥሮ ወጳውሎስ ውጉዝ ከመ አርዮስ ብለው ገዘቱ። እኛም ባንድ ቃል ሁነን ቃልዎ ይድረሰን ብለን በቃል ብዛት በትክክል ታማኝ የሆኑትን ሰው በሌሉበት ቦታ ቀኛዝማች ወርቄን መረጥን ።

ከዚህ በኋላ ልክ ለ፯ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ሥራችንን አጠናቀን ጨርሰን ቀኛዝማች ወርቄን የመረጥንበንትም ምክንያት በወረቀት ጽፈን ሠራዊቱ ወደተሰበሰበበት ቦታ ወጣንና ወዳዋጅ መንግርያው በር እንደደረስን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በሕዝቡ መሃከል በየረድፉ እየተውለበለበ ሠራዊቱ ሁሉም አደግድጎ እንደቆመ ከሕዝቡ ብዛት የተነሣም የአዋጁን ቃል አንድ ሰው አንብቦ አያሰማውምና አየተቀባበለ የሚነግር አራት ሰው በተራ ይቁም ተብሎ ታዞ በዚህ መሃከል ጸሓፊው አቶ መንግሥቱ በጸሓፊ ትእዛዝ በኩል የመጣውን ያመራረጡን አኳኋን የሚያስታውቀውን ደብዳቤ ታዘው በተራ ከቆሙት ሰዎች ጋር እንደስልክ ቃል እየተቀባበለ አነበበ ።

ቀጥሎም እንደዚሁ ሁሉ ቀኛዝማች ወርቄን የመረጥንበትን ምክንያት የሚያስረዳ ከዚህ በታች የተጻፈውን ቃል አነበበ ።

እኛ የሚመረጠውን ትክክለኛ ሰው ለመምረጥ የተመረጥን ሰዎች ቀይ፡ጥቁር፥ ረጅም፥ አጭር ብለን ሳናደላ ንጉሠ ነገሥቱን የሚያከብር ሀገሩን ኢትዮጵያን የሚያፈቅር የማይጠረጠር የታመነ ትዕግሥተኛ ሃይማኖቱ የፀና ባንድ ቃል ሁነን በነገሩ ተስማምተን ቀኛዝማች ወርቄን መምረጣችንን ሳይውል ሳያድር ለዚሁ ሥራ በተሰበሰብንበት ቀን በዚሁ ጉባኤ ፊት በግልጽ እናስታውቃችኋለን ብለው ሲጨርሱ ዳር እስከዳር የተሰበሰበው ሠራዊት ፫ጊዜ አጨብጭቦ እኛም ወደናል የሚበጅ ያድርገው ብሎ በደስታ ንጉሠ ነገሥቱን እየመረቀ በየቤቱ ሔደ ።

በሌሉበት ቦታ ይህን ለመሰለ ትልቅ ሥራ ከብዙ ጉባኤ ማኸል መመረጥ ትልቅ ዕድል ነውና እግዚአብሔርን የሚፈሩበት ንጉሣቸውን የሚያከብሩበት የመረጡዋቸውንም ሰዎች በሥራቸው የሚያኰሩበት ሐሳብ ያሳድርባቸው ብለን ለቀኛዝማች ወርቄ እንመኝላቸዋለን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ንጉሣችንን ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴን ሺሕ ዓመት ያንግሥልን መንግሥቱ ለልጅ ልጅ ትሁን ።

ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አክሱም ።

ጥቅም የሚገኝበት ታሪክ ።

ሰው በሕይወቱ ሳለ በዚህ ዓለም የሚያገኘው ነገር ሁሉ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የማይፈጸም ስለሆነ ለዚህ የሚያስረዳ ምሳሌ ከዚህ በታች እጽፍ ዘንድ አሳሰበኝ።አንድ ንጉሥና አንድ ፈላስፋ ሲጫወቱ፡ ንጉሡ ፈላስፋውን ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ ጠየቀው፤ ሰው ሁኖ በማስተዋልና በትክክለኝነት በሚሠራው ሥራ ሁሉ በጥንቃቄም የሚያገኘው ኑሮ በችግርና በጭንቀት ሁኖ ሳለ እነዚህ ያለማስተዋል (ያለመጠንቀቅ) የሚሠሩ ሰዎች ከፍ ያለ ደረጃ ማግኘታቸው በምን ምክንያት ይሆን ? ፈላስፋውም እንዲህ ብሎ መለሰለት፥ ዕድልና የእግዚአብሔር ስጦታ ከማናቸውም ሰው ጥበብና ጥንቃቄ ይበልጣሉ ነገር ግን ብልሀነት አስተዋይነትና መጠንቀቅ ሰው በሕይወቱ ሳለ ዓይን ለማየት ጆሮ ለመስማት እንደሚያስፈልጉ ሁሉ ለሰው በሕይወቱ ዘመን እነዚህ የተቈጠሩት የሚያስፈልጉ ናቸው።የዚህንም ነገር የሚያስረዳ የንጉሥ ልጅ ከነባልንጀሮቹ ታሪክ አለ ብሎ ፈላስፋው ቢነግረው ንጉሡ ምንድር ነበረ ንገረኝ አለው ከዚህ በኋላ ፈላስፋው እንዲህ ብሎ ተናገረ፤ አንድ ቀን አራት ሰዎች በመንገድ ላይ ተገናኙአንደኛው የንጉሥ ልጅ ነበር፥ ሁለተኛውም የነጋዴ ልጅ፥ ሦስተኛውም መልከ መልካም የመሳፍንት ልጅ፥አራተኛውም የገበሬ ልጅ ነበረ ከሚኖሩበት ስፍራ ርቀው ስለሔዱና ከለበሱት ልብስ በቀር ሌላ ነገር ስላልነበራቸው በጣም ተቸግረው ነበር ሲሄዱም የሚያደርጉትን ሲያስቡ ከዚህ እንደሚቀጠለው ነገር ተገለጸላቸው ።

የንጉሡ ልጅ እንዲህ አለ በዚህ ዓለም ያለ ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ስጦታ ተወስንዋል ይኸውም በእግዚአብሔር የተወሰነው ስጦታ ሁልጊዜ የሚፈጸም ስለሆነ ትዕግሥትና እግዚአብሔር መታመን ለሰው ኑሮ የተሻለ ነው ። የነጋዴውም ልጅ እንዲህ አለ ከማናቸውም ነገር ማስተዋል ይበልጣል የመሳፍንቱም ልጅ አሁን ከተናገራችሁት ሁሉ መልከመልካምነት ትበልጣለች ፤ አለ አራተኛውም የገበሬ ልጅ ሥራ መውደድ ከሁሉ ይበልጣል አለ ።

ይህንን ሲነጋገሩ ወደ አንድ ከተማ በደረሱ ጊዜ በዚያ ስፍራ ተቀምጠው ሐሳባቸውን ሲማከሩ ሦስቱ አንደኛውን የገበሬውን ልጅ እንዲህ አሉት፤ ለዛሬ የሚሆን የምንበላው መብል ሔደህ ሠርተህ አምጣልን የገበሬውም ልጅ ተነሥቶ ወደ ከተማ ገብቶ አራት ሰው የሚመገብበት ገንዘብ ሠርቶ ለማግኘት ሥራ ሲፈልግ ሳለ በከተማው ያሉ ሰዎች እንዲህ አሉት፤ ለሚነድ እሳት ዕንጨት ብታመጣ የሚበቃ ገንዘብ ታገኛለህ ከዚህ የሚበልጥ ዋጋ ግን የሚያወጣ ሌላ ነገር የለም ስላሉት ከዱር ሔዶ አንድ ሸክም ዕንጨት ይዞ ወደ ከተማ ውሥጥ መጥቶ ላንድ ብር ሸጦ ለባልንጀሮቹ የሚሆን መብል ከገዛ በኋላ በከተማው በር ላይ የአንድ ጠንካራ ሠራተኛ ሰው የአንድ ቀን ዋጋው አንድ ብር ነው ብሎ ጽፎ የገዛውን መብል ይዞ ወደ ባልንጀሮቹ ተመልሶ በልተው ጠገቡ ። በማግሥቱ ከመልከ መልካምነት የሚበልጥ ነገር የለም ያለው ሰው ዕድሉን ሒዶ እንዲሞክር ስለተስማሙ እንደዚሁ የመሳፍንቱ ልጅ ተነሥቶ ወደ ከተማ መሔድ ጀመረ በመንገድም ሳለ ማጕረምረም ጀመረ ሥራ ልሠራ አልችልም ወደ ከተማ የምሔድበት ጥቅሙ ምንድር ነው ? ነገር ግን ወደ ባልንጀሮቹ መብል ሳይዝ ለመመለስ ስለአፈረ በአንድ ዛፍ አጠገብ ተጠግቶ ከባልንጀሮቹ ተነጥሎ ወደ ሌላ አገር ለመሔድ ሲያስብ እንቅልፍ እንቀላፍቶት ተኛ ተኝቶም ሳለ የአንድ የታወቀ ሰው ሚስት በዚያ በተኛበት አጠገብ ስታልፍ ሳለች ተኝቶ መልኩን ባየችው ጊዜ በውበቱ ተደነቀችና ሥዕል አንሺ መልኩን እንዲያነሣው ፈቃዱ መሆኑን ለመጠየቅ ገረድዋን ላከችበት ገረዲቱም ወደ ሰውዬው ሒዳ ወደ እመቤትዋ ቤት ይመጣ ዘንድ ስለ ለመነችው እሱም ሒዶ ቀኑን በደስታ አሳልፎ ሥዕል አንሺው መልኩን ካነሣው በኋላ ወደ ማታ አምስት መቶ ብር ስጦታ ሰጥታ ሰደደችው ከዚህም በኋላ ወደ ከተማ መጥቶ በከተማው በር ላይ የመልከመልካምነት ዋጋው ላንድ ቀን አምስት መቶ ብር ነው ብሎ ጽፎ ወደ ባልንጀሮቹ ተመለሰ ።

በሦስተኛው ቀን ጥዋት የነጋዴው ልጅ ተነሥቶ በማስተዋሉና በእውቀቱ ሠርቶ የሚበሉት መብል እንደያመጣ ባልንጀሮቹ ስለፈቀዱ የነጋዴው ልጅ ተነሥቶ ሲሔድ በጠረፍ አጠገብ ሸቀጥ የተጫነች መርከብ ቆማ አየ ከዚያችም መርከብ ላይ ሸቀጡን ለመግዛት ያሰቡ ነጋዴዎች ወዲህና ወዲህ ይሔዱ ነበርና ወዲያው በአንድ ክፍል ውሥጥ ተቀምጠው እንዱ ላንዱ ሸቀጡን ዛሬ ሳንገዛ ብንሔድ የመርከቡ ጌታ እቃውን የሚገዛው ሰው ስላጣ ነገ በርካሽ ዋጋ ይሸጥልናል ብለው ይማከሩ ነበር የነጋዴውም ልጅ ይህንን ከሰማ በኋላ መንገዱን ለውጦ ወደ መርከቡ ጌታ ሒዶ ሁሉንም ሸቀጥ በዱቤ መቶ ብር ሊሰጥ ገዛው ከገዛውም በኋላ ወደ ሌላ አገር እቃውን ለመውሰድ አሰበ ነጋዴዎቹም ይህ-

ንን ከሰሙ በኋላ ሁለተኛ እቃ አይመጣልንም ብለው ፈርተው ከዋናው ገንዘቡና ከትርፉ ጋር መቶ ሺ ብር ሰጡት እሱም እቃውን የገዛበትን ዋጋ ለመርከቡ ባለቤት ከፍሎ የቀረውን ወደ ባልንጀሮቹ ይዞ ሲመለስ በከተማ በር ላይ የማስተዋል የአንድ ቀን ዋጋው መቶ ሺ ብር ነው ብሎ ጽፎ ተመለሰ ።

በአራተኛው ቀን የንጉሡ ልጅ ዕድልና ስጦታውን እንዲሞክር ተራው ነበርና የንጉሡ ልጅ ተነሥቶ ሔዶ ከከተማው በር መቀመጫ ላይ መጥቶ ተቀመጠ በዚያ ቀንም የአገሩ ንጉሥ ሙቶ ነበር ነገር ግን የሞተው ንጉሥ አልጋ ወራሽ አልነበረውም ሲለቀስም ሳለ የንጉሡ ልጅ እንደሌሎች ኀዘን አልገባውምና በዚያ በልቅሶ ያሉ ሰዎች ይህንን የንጉሥ ልጅ ተመልክተውት ነበር በር ጠባቂው በቁጣ ቃል እንዲህ ብሎ ተናገረው የማነህ አንተ ምስኪን ንጉሡ ሙቶ ከኀዘናችን ሳትካፈል ከበሩ መጥተህ ለመቀመጥ የደፈርህ ? ብሎ ከበሩ ላይ አባረረው ነገር ግን አልቃሾች ወደ መቃብር ከሔዱ በኋላ ከዚያው ከበሩ ላይ እንደገና መጥቶ ተቀመጠ አልቃሾቹም ከመቃብር በተመለሱ ጊዜ ያ በረኛው ከዚያ መቀመጡን ተመለከተና እንዲህ አለው እዚህ እንዳትቀመጥ ከዚህ በፊት አልከለከልሁህም ኑርዋልን ብሎ አለውና አስይዞ ከወህኒ እንዲታሠር አደረገ ። በማግስቱም የአገሩ መሳፍንት ንጉሥ ለመምረጥ ተሰብስበው ነበርና ሁሉም የእያንዳንዱን ሰው ሐሳብ በትዕግሥት ሲጠባበቁ ሳለ የሚቀጥለው ሐሳብ ተፈጸመ።

ከዚህ በኋላ በር ጠባቂው ለተሰበሰቡት ሰዎች እንዲህ ብሎ ተናገረ ትናትና ሰው ሁሉ ኀዘንተኛ ሁኖ ሳለ አንድ ጐልማሳ ደስ ያለው ሰው እበሩፍ አጠገብ ባየሁት ጊዜ አንድ ነገር ተናገርሁት ምላሽም ስላልሰጠኝ ከበሩ አበረርሁት ከመቃብር ከተመለስን በኋላ ሁለተኛ እዚያው ስፍራ ተቀምጦ ስላገኘሁት ሰላይ መስሎኝ እወህኒ አግብቼዋለሁ ከዚያ በኋላ የከተማው መሳፍንት የንጉሡ ልጅ ከወህኒ እንዲወጣ አዘዙና በፊታቸው በቀረበ ጊዜ ወደዚህ ከተማ የመጣበትን ምክንያቱን ጠየቁት እሱም እንደዚህ አለ እኔ የንጉሥ ሩሞፎን ልጅ ነኝ አባቴ ከሞተ በኋላ ወንድሜ ከመንግሥቱ አስወጣኝ ስለዚህ ሕይወቴን ለማዳን ከአገሬ ወጥቼ ወደዚህ እንደምታዩኝ መጣሁ ይህን ታሪኩን ከጨረሰ በኋላ አንድ መስፍን በአባቱ አገር በፊት የነበረ ከመሳፍንቱ መሐከል ተነሥቶ የዚያኑ የንጉሡን ልጅ ስም ያከብር ጀመር መሳፍንቱም በዚህ የተነሣ ንጉሣቸው እንዲሆን መረጡት በመመረጡም በጣም ደስ አላቸው ።

የአገሩ ልማድ አዲስ ንጉሥ ሲነግሥ በነጭ ዝሆን ላይ አስቀምጦ ከተማውን ማዞር ነበርና ይህንን አዲስ የተመረጠውን ንጉሥ እንደተለመደው ሁሉ በነጭ ዝሆን አስቀምጠው ሲያዞሩት ሳለ በከተማው በር ላይ ተጽፎ የነበረውን ተመለከተና በዚያ ቀን በተሰጠው ክብር እንዲህ ብሎ ተናገረ እንደተባለው በሥራ በማስተዋል በመልክ መልካምነት በማናቸውም በዚህ ዓለም ሰው በሚያገኘው ነገር ሁሉ አይደለም ነገር ግን እግዚአብሔር በቈረጠለት ነገር ይፈጸማል ብሎ በበሩ ላይ እንዲጻፍ አዘዘና ወደ ንጉሠ ነገሥቱ አዳራሽ ገብቶ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠ በኋላ እነዚያን ሦስቱን ጓደኞቹን ወደርሱ አስመጥቶ የሚገባቸውን ማዕርግ ሰጣቸው ።

የጕሬ ትምህርት ቤት ዲሬክተር ንጋቱ ማህሌ ።

የሚአስቸኰል ጥያቄ ።

በብርሃንና ሰላም በሰባተኛው ዓመት በ፵፩ ቍጥር በ፬፻፮ ገጽ የተጻፈውን የሚያሳዝነውን የግፍ ነገር አይተን እጅግ አዘን በዚሁ ነገር እየተከዝን ስንነጋገር ከመካከላችን አንዱ እንዲህ አለ ፤ የኢትዮጵያ ልጆች ቅሌት አያውቁምና ለቅሌቱ ቅሌት መመለስ አይችሉም እንጂ ምነው ይህ ግፍ የተዋለበት ሰውዩ ለጉሽሙ ጉሽም ሳይመልስ ቀረ ቢል አንዱ መለሰና ጻሓፊው የግፉን ብዛት አመዛዝኖ ጥቃቱ የበዛውን ወገን አይቶ ጽፎ ይሆናል እንጂ አለ ቢሆንም ወደ ዳኛ ተቃረቡ የሚል ቃል ተጽፏል የመጨረሻውን ፍርድ በምን እንሰማው ቢል በፍቅር መምህር በብርሃንና ሰላም በኰል ብንጠይቅ ልክ እስከ ፰ቀን መልሱ ይመጣል ተቀብለን ለልባችን ተስፋ ሰጥተነዋልና የውሻ ጌታ ሙሴ ሚከሊትያኖስ እዳኛ ዘንድ በግድ ቀርበው ፍጻሜው እንደምን ሆነ እያልን ይህንኑ የግፍ ነገር መጀመሪያ የጻፉልንን ወዳጃችንን በማክበር እየጠየቅን መልሱን እንጠብቃለን ። በግፉ ከተቈረቈሩት አንዱ ወ ድንህ ይነሡ።

ስለ ሥራ ረገድ ማስታወቂያና ማስታዋሻ ።

በብርሃንና ሰላም ፫ኛ ዓመት ቍጥር ፺፪ ክቡር ወንድማችን አቶ መኰንን ኢያቄም የሃገራችን ቋንቋ (አማርኛ) ቢጻፍና ቢታተም ለመላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብርሃን መሆኑን ተረድተውት የአማርኛ ቋንቋ (ዲክሲዮኔር) እንዲጻፍ ስለ አመልክቱንና ሐሳባቸውን ስላካፈሉን ይህ መልካም ምኞት እያደር እንደ ወርክ እየሰፋ የሚሔድ ነውና ከልብ እናመሰግናቸው ዘንድ ማስታወሻቸው ይቀሰቅሰናል እነሆ ስለ አማርኛ ቋንቋ ነገር የትምርት ምኒስቲር ካሰበበት ብዙ ጊዜ ነበር ነገር ግን የትምርት ቤትና ቢሮዎችን (የመጻፍያ ቤቶችን) ልዩ ልዩ የሆኑትንም ክፍላ ክፍሎች በማደራጀት አሁን የተባለው የቋንቋ መሰብሰብ ሥራ እንዲታሰብ ነገሩ ሳይቈረጥ ለጥቂት ጊዜ ዝግ አለ፣ ግን ፲፱፻፳፫ ዓመት ከግንቦት ወር ጀምሮ የትምርት ምኒስቴር አማርኛ ቃላትን እየሰበሰበ የሚጽፍ ሠራተኛ ስላደረገ እስከ ዛሬ ድረስ ሥራው አለማቋረጡን እናስረዳለን ስለሆነ አቶ መኰንን ኢያቄም እንዳሉት ከየአውራጃው ሁሉ አንድ ሰው ቢመረጥና የየአውራጃውን አማርኛ ቃላት ለመሰብሰብና ለማቃናት ረዳቶች ቢሆኑ በጎ ነገሩ ያከፋ አይመስልም፤አሁን እንኳ ከተጀመረበት ቀን አንስቶ እስካሁን ብዙዎች ቃላቶች ሳይጻፉ አይቀሩም ይሆናል፥ ወደ ፊትም በዕድላሙ በግርማዊ ኃይለ ሥላሴ ሀብት በትጉሁ ዲረክተ[illegible] ጋት ተከናውኖ እዲወጣና ፍጻሜውን ለማየት እንመኛለን ። በቀለ አበዬ።

የሚአሳዝን ሞት ።

የፌታውራሪ ኃይሌ በዛብህ ልጅ ከበደ የሚባል ከጦር ሚኒስትር ክቡር ፌታውራሪ ብሩ ልጅ ከወይዘሮ አየለች

ኖተወለደ እጅግ የሚአምር ልጅ ነበረ በታናሽ ቢስክሌት በአልፍኝ ውሥጥ ሲጫወት ወድቆ ጐኑን መሬት ስለመታው በዚህ ምክንያት ታሞበዶክተር ቦራ ሆስፒታል ፰ ቀን ያሀል ተኝቶ በታኅሣሥ ፳፫ ቀን ሙቶ በእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበረ ዕድሜውም ፫ ዓመት ከ፲ ወር ነበረ ።

ደግሞ የአፈንጉሥ መኰንን ደምሰው ልጅ እጅግ መልከም ሕፃን ነበረ ፩ ዓመት ከ፱ ወር ሲሆነው በሳል ሕማም ታሞ በታኅሣሥ ፴ ቀን ሙቶ በብዙ ክብር በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ ። ወላጆቻቸውን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጣል ።

ለ አቶ ገብረ ጻድቅ ሞት ።

አቶ ገብረ ጻድቅ (ባሻ ወልደ ማርያም ልጅ የነጋድራስ ደኅኔ ታላቅ ወንድም እጅግ መልከም ሰው እንግዳ ተቀባይ ነበሩ። አባታቸው ባሻ ወልደ ማርያም በነበሩበት በታ ተተክተው ለወንድሞቻቸው አባት ሁነው ሲኖሩ ወንድሞቻቸውን ለመጠየቅ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በድንገተኛ ሕማም ታመው በታኅሣሥ ፴ ቀን ሙተው በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ ዕድሜአቸውም ፶፱ ዓመት ነው ብርሃንና ሰላም ልጆቻቸውንና ወንድሞቻቸውን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ኀዘኑን ይገልጣል

ለ ልጅ ብቀለ ከበደ ዕረፍት ።

ልጅ በቀለ ከበደ የራስ ቢትወደድ ተሰማ የልጅ ልጅ በጥር ፩ ቀን በዶክቶር ላምቢ ሆፒታል ዐርፎ እናቱ ወይዘሮ አሰገደችና ክቡር ደጃዝማች ሀብቴ ሚካሌል ዘመድ ወዳጅም አዝኖ ቀበረው።እሱም በመልኩ ያማረ መልከም ጐበዝ ነበረ ነገር ግን እንደ አባቶቹ ጠባዩን ባለማሳመሩ ሕዝብ ሁሉ ያዝንበት ነበር እሱም ወደ ሴቶች ፍቅር ያዘነበለ ዋዛም ያቸነፈው ጐበዝ ነበረ፡በዚህም ምክንያት ያን ያሀል እንደ ባሕር አሸዋ የተከማቸውን የአባቶቹን ገንዘብና ለቍጥር የሚአስቸግረውን ርስት ሺጦ ጨርሶ በዕዳ ምክንያት በአቶ ደብጭ እጅ ፪ ዓመት ያሀል ታሥሮ በ[illegible]ሞቱ ለዘመዱ ሁሉ ታላቅ ኀዘን ሆነ። ዕድሜውም ፴፯ ዓመት ከመንፈቅ ነው ሌሎችን ወጣቶች ለማስጠንቀቅ ስንል [illegible] ታሰቢያውን በመጻፋችን እጅግ እናዝናለን።ወይ ሥጋ [illegible]ቸውን ሁሉ ጨርሶ ሺጦ ሲሞት የእናቱን የወይዘሮ አሰገደችን ከባድን ኀዘን አይተን እጅግ ተደነቅን

ሽማግሌ ሲተርት ጥቂት ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ ቢለው ምን እንደመርፌ ትወጋ እንደ ማረሻ ታርስ እንጂ ያለው ሰው መልከም ተናግሮአል ።

ማስታወቂያ ።

፩ኛ ፤ የክርስቲያን መንገድ ሁለተኛ መጽሐፍ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታትሞ ይሸጣልና ዋጋው አንድ ብር መሆኑን እናስታውቃለን ።

፪ኛ ፤ የቀን መቍጠሪ፡ የሒሳብና የመስፈሪ፡ የሚዛንም ልክ መግለጫ፡ የነገሥታት ታሪክና ዘመን፡አጽዋማትና በዓላት ከ፲፱፻፳፬ ዓ ም እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ ም ድረስ፡የተቀማጭ ገንዘብና የዕዳ ባጭሩ የሚያጽፍ መዝገብ ያለበት ትንሽ ያጌጠ መጽሐፍ በኪሳችሁ መያዝ ያስፈልጋችኋልና ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት በአሳድ ግዙ ።

ያማርኛ ትያትር ።

ጳጕሜ ፭ ቀን ከጃንሆይ አስፈቅደን ልዑል አልጋ ወራሽና ልዑላን መሳፍንት ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር ያዩት ብዙ ምሥጢር ያለበት ያማርኛ ትያትር እንዲደገም የብዙ ሰዎች ፈቃድ ስለሆነ አሻሽለንና ጨማምረን ጥር ፳ ቀን እሑድ ቦ፱ ሰዓት በዚያው በማጀስቲክ ሆቴል እንደግመዋለንና ይህን ብዙ ትምህርት ያለበት ጨዋታ ለማየት የምትፈልጉ የሀገራችሁ ፍቅር በልባችሁ የተፀነሰ ጌቶችና እመቤቶች ወጣቶችም ሁሉ የምትገቡበትን የስፍራ ወረቀት በዚሁ ሆቴል ብትጠይቁ እንደ የማዕርጋችሁ ታገኛላችሁ። ልጆቻችሁ የኢትዮጵያ ወጣቶች።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአቦካትነት ሥራ ይሠራሉ በአገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክ አገር የፍርድ ቤት ብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ናቸው ። ለዚሁም አቦካትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጅሮንድ ዘለቀ አገደው ግቢ ነው። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፫ት ሰዓት እስከ ፮ት ሰዓት ይቀበላሉ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።
ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።
ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሲንጀር በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ሕጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሲንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሸንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴን ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።



ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና አንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አጽቶው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ጩሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ካ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች እንዳ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም

ALEM

በያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።



ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።



የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኜይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ሞንሴኜ ደ ፋብሪክ አጠገብ ጴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት [illegible] ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፡ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ [illegible]ልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሴ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪና ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፬
8^me ANNE. № 4

ሐሙስ ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም።
JEUDI 21 JANVIER 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታላቅ የምስራች ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስለ ሥራና ጾም ብዛት ስምንት ቀን ያህል በታናሽ ሕመም ምክንያት ከእልፍኝ ሳይወጡ ስለሰነበቱ ሕዝቡ እጅግ ይወዳቸዋልና አዝኖ ሰነበተ ። ያዘነበትንም ነገር ማቅለል ለእግዚአብሔር ልማዱ ነውና በጎ ሁነው በታላቁ እልፍኝ ሕዝቡን ግባ ብለው በጥር ፱ቀን ስለታዩ ታላቅ ደስታ ተደረገ።ነገር ግን ከብርዱ ፅናት የተነሣ ሐኪሙ ወደ ውጪ መውጣት ስላልፈቀደላቸው እስከ አሁን ከግቢ አልወጡም እንጂ በጣም በጎ መሆናቸውን ለኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ ብርሃንና ሰላም ያስታውቃል። ይገርማል የጥምቀትና የቃና ዘገሊላ ዕለት መኳንንቱና ሠራዊቱ ሕዝቡም ልክ እንደቀድሞው ተሰብስበው ነበረ።ሊቃውንቱና ካህናቱም እንደቀድሞዋቸው ይዘምሩ ነበር ።

ነገር ግን እውራ የሌለው ንብ መስሎ ቀዝቅዞ ዋለ እንጂ ቢዘመር ቢዘፈንም እንደ ቀድሞው አልደመቀም ። በዮሐንስ ወንጌል እንደተጻፈው በጎቹ የራሱ የሆኑ የበጎች እረኛ ሕይወቱን ስለበጎቹ ይለውጣል የተባለው በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደርሶ የሥራ ኃላፊዎች ያስታጉሉትን ሥራ ሁሉ እሞላ እሞላ በማለት የዕረፍት ጊዜ አጥተው ጊዜውን ሁሉ በሥራ እያሳለፉ ስለ ሕዝባቸውና ስለ ሀገራቸው ራሳቸውን መጕዳታቸውን በሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ያውቀዋል ። ሲአስቡለት የማያስብ የለምና ሕዝቡ ሳያያቸው የዋለ እንደሆነ እጅግ የሚናፍቃቸው ስለሆነ ኃዘኑ በርትቶ ነበርና ስለ ዳኑለት ታላቅ ደስታ ያደረገበት ምክንያት ስለዚህ ነው ።

ስለ ሀገር ፍቅር የተሠራ ትያትር

በጥር ፰ቀን በዘጠኝ ሰዓት የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሕዝቡን አሳብ ለማነቃቃት እጅግ ደስ የሚያሰኝ ትያትር አድርገው ይህንም ድንቅ ለማየት ታላላቆች መኳንንትና ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ነበር፡ምንም በሙሉ ጽፈን ልናሳያችሁ ባንችል ከዚሁ ከፍለን ጽፈንላችኋል ።

መጀመሯ የኢትዮጵያን መዝሙር

፩ኛ ተነሡ ታጠቁ ኢትዮጵያውያን
እንጀምር ሥራ በስመ አብ ብለን
ርቀው ሒደዋል ጓደኞቻችን
እንድረስባቸው በጣም ተፋጥነን
አሁን በብርሃኑ ጨለማ ሳይሆን
ወደኋላ ቀርተን አውሬ እዳይበላን
ኢትዮጵያ አገራችን ስለነፃነትሽ ይፈሳል ደማችን
፪ኛ ምስጋና ይሁነው ለሰማዩ ጌታ
ጠብቆ ላቈየን በሰላም በደስታ
ውድ አገራችነን ከብዙ ወስላታ
እንግዲህ እንጠንክር በጣም እንበርታ
እንዳንወላውል እንዳናመነታ
ሕይወታችን ይለፍ ባገራችን ፈንታ
ኢትዮጵያ አገራችን ስለነፃነትሽ ይፈሳል ደማችን
፫ኛ እናት ኢትዮጵያ ውዲቱ ውዲቱ
በሦስቱ ቀለሞች የተሸለምሽቱ
ነፃነት የሚሸር ቢመጣብሽ ብርቱ
ደማችን ይፈሳል አይቀርም በከንቱ
ላንች የማይረዳ ሳለ በሕይወቱ
በረከትሽን ይንሣው እስከለተ ሞቱ
ኢትዮጵያ አገራችን ስለነፃነትሽ ይፈሳል ደማችን

ከዚህ ቀጥሎ ሰነፎች ሰዎች በተኙበት ስፍራ ሆድ አምላኩ የሚባል ሌባ ባታክልታቸው ውሥጥ ሊሰርቅ ገብቶ የሰረቀውን ፍሬ ሸጦ የሚያገኘውን ብርና የኋላውን ጌትነቱን እያሰበ ከደስታው የተነሣ ሲጮህ ባለቤቶቹ ነቅተው እንደደበደቡት የሚያሳይ ትያትር ተደረገ ።

ሦስተኛ ነጋድራስ ሰብስቤ የሚባል በቀን እፍኝ እፍኝ ሽንብራ ከነልጁ እየቈረጠመ ዕድሜውን ሙሉ ብር ሲያጠራቅም የኖረ ንፉግ ሽማግሌ ብሩ ፲ሺ ሊሞላ ፪ብር ጐድሎበት ነበርና ያነን ፈላልጎ ሊሞላ በወጣበት ዕድሜውን ሙሉ ሲያጠራቅመው የኖረውን ሁሉ ሌባ ወሰደበት፡እሱም ከዚያ ተመልሶ ገንዘቡን ቢያጣ የየዕነጪቱንና የየጠረጴዛውን እግር እየታቀፈ አባካችሁ ገንዘቤን መልሱልኝ ሲል ቈይቶ ሞተ ሙቶ በወደቀበትም

ቦታ ልጁ መጣና አባቴ አላስተማርኸኝ ሥርቼ አልተከልሁ ምን ላድርግልህ ወደ ብር ብሎ የብርን ስም ቢያነሣ ከሞተበት ብር? ብሎ ተነሣ። ነገር ግን ምንም ብር ብር ቢሉ ለጊዜው ነው እንጂ ለፍጻሜው አያድንምና ተመልሶ ሞተ ።

አራተኛ ያቶ ወደኋላ ሞት በኃይለ ሥላሴ የሚባለው ትያትር ተደረገ።በዚህ ትያትርም በመጀመርያው ክፍል ሐበሻ ከወደ ኋላ ጋር እንደተጋባችና ሁለት ዓይንዋን እንደታመመች ታዩ በኋላ መታመሟን ያዩ አእምሮ የሚባል ሰው ለልጆቿ ነግሮ ሊያይዋት በሔዱ ጊዜ የበከር ልጅዋን የመላከ ብርሃን ኃይለ ሥላሴን እጅ ይዛ ከዚህ በታች የሚከተለውን የልቅሶ ግጥም በዜማ ታለቅስ ጀመረች

ልጆቹ እያላችሁ እናንት ኃያላን።
እንዴ ብርሃን ሳላይ ይለፍብኝ ቀን ።
እወጣ ስል ወረድሁ መንገድ ተሳስቶኝ ።
እስቲ ልመላለስ ምንም ቢታክተኝ ።
የት ትደርስ ያሉኝ ሰው በኋላ ቀርቼ።
መሳቂያ ሆንኋቸው ለባልንጀሮቼ ።
ኃያላን ልጆቼ እርዱኝ እባካችሁ ።
ወልጄ እንዳልወለድሁ ሆንሁ እኔ እናታችሁ ።
እባካችሁ አጥቡኝ እንዳጠባኋችሁ ።
ጥቅማችሁ ምንድር ነው ሰው ቢፈርድባችሁ ።
ተው ምከሩበት አስቡ በፀና ።
እናት በብዙ ብር አትገኝምና
ልጄ አሳድጌ በብዙ መከራ ።
አሁን አላችሁኝ ሐጂ ደብላሽ አሞራ ።
እስቲ መልሱልኝ ልጠይቃችሁ ።
ከየት ነው የመጣ ጌትነታችሁ ።
ባልወልዳችሁ ኑሮ አምጨ በፅኑ ።
ባላሳድጋችሁ ለፍቼ በፅኑ ።
ከየት መጥታችሁ ነው ጌቶች የምትሆኑ ።
መጠንከር አሁን ነው ማለት በርታ በርታ ።
ለምንም አይጠቅም የኋላው ዋይታ ።
አሁን ነው እርዳታ አሁን በትኩሱ ።
ተሔድሁ አልመለስ ኋላ ብታለቅሱ
ያልወለድሁ ይመስል ጅግና ባለጋሻ ።
እንዲህ ሁኝ ቀረሁ ወይ እኔ ሐበሻ።አለች ።

በዚህ ጊዜ ከልጆቿዋ አንዱ የሚከተለውን ቃል ለወንድሞቹ ተናገረ ።

ወንድሞች ሆይ የኛ እናት እንደዚህ ባለ በረከሰና በተጐሳቈለ በሽታ ወድቃ ስትጨነቅ እያየን ነገራችንን በዕንባ ብቻ ብንወስነው የሰው መሳቂያና መቀለጃ መሆናችንን አታስተውሉምን?የሰው ሁሉ እናት በጥበብ ስትሽሞነሞን የኛ እናት እንደህ ሁና ተጐሳቍላ የልጅ የዘመድ ያለህ እያለች በደም እንባ ስትታጠብ የነማን እናት እንዲህ ሁና ሞተች በተባለ ጊዜ ውርደቱና ንቀቱ ስድቡስ ለማን ይመስላችኋል ለኛ አይደለምን እኛ ባለ ጸጎችና ጕልበታሞችሁነን እናታችን እንዲህ እንዳልሆነ ሁና ስትሞት እንደዶሮ ጫጩት ተንጫጭተን መለያየት የሚገባን አይመስለኝም። የራሳችንን ጥቅም ከመፈለግ ይልቅ ሁላችንም ተስማምተን ለርስዋ ጥቅም ብናስብ ጥቅማችን የበዛ ይሆን ነበር።እርስዋ ግን ከኛ ከልጆችዋ እንደማትጠቀምና እንደማትረባ ተስፋ ከቈረጠች በርስትዋና በጕልቷ ደኅና አድርጎ አሽከሞ እንደ ባልንጀሮችዋ በሴት ወይዘሮ ደንብ የሚያስቀምጣትን ልጅ ወራሽ አድርጋ መውለድዋ አይቀርም ። እኛም በርስታችንና በጕልታችን ባዕድ ከተወለደበት እንደዚህ እንደዛሬ ኵራትና ማዕርግ እንደሌለን እንወቅ። ከዚያ ወዲያ ተዋርደንና ዝቅ ብለን በገንዘባችን ፥ በርስታችንና በጕልታችን የሰው ፊት አይተን ማደራችንን አንርሳ ። አሁንም እንደዚህ ታላ መከራ ለመዳን ይህን ጊዜ ባለጸጎች በከብታችን ድሆች በጕልበታችን ተረዳድተን እናታችንን በእግዚአብሔር እርዳታ እናድን ።

እባካችሁ አስቡበት ሰው ጌጥና ፈንጠዝያ የሚያስፈልገው ራሱን ተቻለ ወዲያ መሆኑን ሁላችን አንስተውም ። ሀዲያውም በሰም ያጣበቁት ጥርስ ቢበሉበት አያደቅ ቢስቁበት አያደምቅ እንደሚሉ ተበድረን የምናጌጠው ጌጥ ምንም ያህል አያኰራንም ። ስለዚህ የሁሉም ማሠሪያ የእናታችን ደኅንነት መሆኑን አሳስባችኋለሁ ።

እንዲህ ብሎም ከተናገረ በኋላ መላከ ብርሃን ኃይለ ሥላሴ እጅዋን ይዞ ወደ ቤታቸው ጕዞ ሲጀምሩ ወደ ኋላ ዱላውን ይዞ ቤቴ የጐረምሳ መጫወቻ ሁኖ የለም ወይ ብሎ ተናዶ ሲመጣ ልጆችዋ ይዘው መግደልና አንዱ ጐራዴውን ይዞ ጕሮ ወሸባየ ማለትና መዝፈን ሌሎቹም መቀበል ።

ከዚህ ቀጥሎም መልአከ ብርሃን ኃይለሥላሴ ከጥቂቶቹ ወንድሞቹ ጋራ ዕውቀት የሚባል መድኃኒት ገዝቶ እንዳመጣላትና ትንሽ እንደተሻላት ።

ከዚያ ወዲያ እናታችንን አንረዳም ያሉትን ወንድሞቹን ባዬ ማስተዋል ከሶ እንዳስፈረደባቸው ተመልሶም ከወንድሞቹ ሁሉ ጋራ እናቱን ወይዘሮ ሐበሻንና አባቱን አለቃ ጥየቡን ለምነው አስታርቀው ሰርግና ፈንጠዝያ አደረጉ።

በመጨረሻም የብርሃኑ ልደት ከኢትዮጵያ የሚባል ቴያትሮ ተደረገ ።

ከዚህም ቀጥሎ አንዱ ተማሪ የሚከተለውን ዲስኩር አነበበ ።

ክቡራን መኳንንቱና ወይዛዝሩ በዚች ቀን ሥራችሁን እየተዋችሁ እዚህ ድረስ መድከማችሁ የሀገራችሁ ፍቅር በልባችሁ ስላደረና እኛን ልጆቻችሁን ለማፅናናት መሆኑን ስለተረዳነው በጣም እናመሰግናችኋለን ዛሬ የኛን የሕፃናቱን ሐሳብ ሳትንቁ እዚህ ድረስ መድከማችሁ ባለመናናቅና በመተባበር እናታችንን ኢትዮጵያን ከፍ ወዳለው ደረጃ ለማድረስ እንደሆነ ሐሳባችሁ ያስረዳናል ። የትያትሮ ጨዋታ በኛ አገር በጣም አልተለመደም እንጂ በውጭ አገር ሰዎች በጣም የተለመደ ነው ። እኛም ደግሞ የሀገራችንን የኢትዮጵያን ጕዳት በመጽሐፍና በንባቡ በሚያሰለች ነገር ከማሳሰብ እንደዚሁ ባጭሩ በዘፈንና በጨዋታ ለጌቶቻችንና ለእመቤቶቻችን ማሳሰብ የሚሻል ስለመሰለን ይህን ዘፈን ያለበትና ቀልድ የሚመስል ትያትሮ አሰናዳን ነገር ግን በውሥጡ ብዙ ቁም ነገርና ትምህርት እንዳለበት አትስቱትም ።

ጌቶቻችን እመቤቶችን ሆይ ሀገራችን ኢትዮጵያ ቀደምት ከሆኑ ገናናዎችና ኃይለኞች ነገሥታት አንደኛዋ እንደነበረች ብዙ መጻሕፍትና ብዙ መምህራን ይመሰክሩላታል ። ከኢትዮጵያ ሊቃውንት አንዱ አለቃ ታዬ በጻፉት በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ ብትመለከቱ ከዚሁ በታች የተጻፈውን ቃል ታገኛላችሁ ።

የኢትዮጵያ የጥንት ድንበር ከጂቡቲ ባሕር ዳር ጀምሮ እስከ ስናር፥እስከ ነጭ ዓባይ ድረስ ነበረ በሰሜንም ከሁለተኛው ሀገረ ናግራን ወዲያ በርበር የምስር ድንበር ይመልሰው ነበረ። የቀድሞ ታሪክ ጸሓፊ ሄሮዶቱስ የሚባል የግሪክ አገር ሰው ፬፻፳፬ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረ ከርሱ ዘመን በፊት ምስርን ጨምረው የገዙትን የኢትዮጵያን ነገሥታት ታሪክ ሲናገር ዓሥራ ስምንት ነገሥታት ምስርን ጨምረው ገዙ ሲል በታሪክ መጽሐፉ ጽፎአል ።

ነገር ግን ይህን ያህል ኃይልና ሥልጣን የነበራት ሀገር ኃይሏ እየደከመ ፍቅርና አንድነት እውቀትም እያደረ ቢጐድልባት ብዙ ጥቅም የሚገኝባቸውን ጠረፎቿን ሁሉ ከውጭ የመጡ ባዕዳን ሕዝብ ያዙባት ጥቡብንም ከብልሃተኞች መጠየቅ ናቀችና ቸል አለች የቀድሞ እውቀትዋን ትታ በኃይል ቆሜ እኖራለሁ ብላ ተመካች።ነገር ግን ይህ ይቅርና የቀድሞው እውቀቷ እጅግ እየጐደለ ሔዶ እንግዲህ በድንቁርናው ዘመን የገነነችና የሠለጠነች የነረበችው ሀገራችን አሁን የዚያን ጊዜ ስማቸው ያልተጠራና የት እንደ ነበሩ ያልታወቁ ሀገሮች ሁሉ ሠልጥነው ራሳቸውንም ችለው በተቀመጡበት ጊዜ እስዋ ወደኋላ ቀርታ እንደዚህ አሁን በትያትሮ እንደሰማነውና እንዳየነው የልጅ ያለህ የዘመድ ያለህ እያለች በደም እንባ ስትታጠብ እንኳን ለኛ ለልጆቿ ለባዕድም ያሳዝናል

ይህም ከኛ ከልጆችዋ ስንፍናና ቸል ማለት ነው እንጂ እኛ ብንረዳዳስ ሀገራችን ባንድ ጊዜ ጓደኞችዋ ከደረሱበት ደረጃ እንድትደርስ ጥርጥር የለበትም ።

መግሥት ነፃነትን ይሰጣል፤አርአያ ይሆናል፤ይረዳል እንጂ እሱ ብቻውን ሀገሩን ለማሠልጠንና ብቻውን ለመሥራት ይከብደዋል ስለዚህ አምሳ ሎሚ ላምሳ ሰው ጌጥ ነው ላንድ ሰው ሸክም ነው እንደሚሉት እኛ ብንረዳዳበት ነገሩ ሁሉ ቀላል ነው ለምሳሌ ባዲስ አበባ ውሥጥ የሚኖሩ ሠራተኞች ሁሉ በጨዋታና በማይረባ ነገር ከሚያጠፉት ገንዘባቸው በሳምንት አንዳንድ ሩብ ለሀገራቸው መርጃ ዓሥራት የሚያወጡ ቢሆኑ ለነሱ በጣም ቀላል ነው ለሀገራቸው ግን ባንድና በሁለት ዓመት ብዙ ደረጃ የሚያራምዳት መሆኑ የተገለጸ ነው ስለዚህ እናታችን ኢትዮጵያ ለባለጸጎችም ለድኆችም እናት ናትና ባለ ጸጋና ድኃ ሳንል እንደተቻለን እናታችንን ልንረዳ የሚያስፈልገን ነው በዚሁም መካከል ለሀገራቸው ፍቅር ልባቸው የማይቀዘቅዝና አሳባቸው የማይተኛ ክቡር አዛዥ ወርቅነህን ልናመሰግን የተገባ ነው በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት አለቃ ሳሉ ለተማሮች እንደ አባትና እንደ እናት ሁነው በብዙ ቸርነት ይጠነቀቁ ነበር ።

ደግሞ ስለሀገራችን ስለኢትዮጵያ ነፃነትና ደኅንነት ስለመንግሥታችንም ፅናት ብላችሁ ሌትና ቀን ጠንክራችሁ ልትሠሩ ይገባችኋል እንጂ በቀልድና በጨዋታ ጊዜያችሁን ልታሳልፉ አይገባችሁም እያሉ የሚያነቃቃ ምክርና ተግሣፅ ለመስጠት አልቦዘኑም ነበር ።

እንደዚህም የነፃን ትምህርት ቤት ያፅናኑ ነበረ ይህንም ትተው ወደ ዓሰበ ተፈሪ ቢሾሙ እዚያ በሔዱበት ተማሪ ቤት ከፍተው ብዙ ልጆች ያስተምራሉ።አስተማሪዎቹም በተፈሪ መኰንን ተማሪቤት የተማሩት ልጆች ናቸው አሁንም እንደዚህ አድርገው አገራቸውን ለመርዳት እንቅልፍ የሌላቸውን ያባታችንን በጎ ሥራ በመከከላችን ልናስበው የሚያስፈልገን ነው ። እንደዚሁም ጌቶቻችንና እመቤቶቻችን ሁሉ ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትሻሻልበትንና የምትረዳበትን መንገድ እንድታስቡ የሁላችን ተሰፋ ነው ። እኛም ልጆቻችሁ ይህን አሳብ ያሰብንበት መጀመሯ እንደዚህ በጨዋታ አድርገን የሀገራችንን ጉዳት ለማሳሰብ፤ ሁለተኛም ከሆቴልና ከሌላ ከግራ የሚተርፍ ገንዘብ ቢኖር ለሀገር የሚጠቅም አንድ ሥራ እንሠራበታለን ብለን ነው ። ይኸውም ደግሞ ጌቶቻችንንና እመቤቶቻችንን ታምነን ነው እንጂ በኛ ጉልበት የሚሠራ ሥራ አይደለም ከዚህ ቀድሞ ባደረግነው ጭዋታ ክቡር ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ በሚያስፈልገን ስለረዱን፥ ደግሞ ክቡር ፊታውራሪ ብሩ መቶ ብር ፥ ክቡር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ፲ ብር ለሥራችን እርዳታ ስለሰጡን እግዚአብሔር ዕድሜና ጤና ከብዙ ሀብት ጋራ ይስጥልን እያልን ምስጋናችንን እናቀርባለን ።

ኢትዮጵያውያን ሆይ ።

ለሀገራችን ደኅንነትና ልማት ለመንግሥታችንም ፅናት እንድናስብ እግዚአብሔር ኃይሉን ይስጠን፡ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ከነቤተሰቦቻቸው እግዚአብሔር በሰላም ይጠብቅልን። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም በነፃነትዋ ትኑር ብዬ ነገሬን እወስናለሁ ።

ሐዲስ ዓለም አየሁ ።

የክቡር አዛዥ ወርቅነህ መምጣት ።

ክቡር አዛዥ ወርቅነህ ወንዶችንና ሴቶች ልጆቻቸውን ወደ እንግሊዝ ከተማ ወደ ሎንዶን ልከዋቸው ብዙ ጊዜ ቈይተው የሚበቃቸውን ትምህርት ተምረው ስለጨረሱ ሴቶችን ልጆቻቸውን አስቴርን ፥ ኤልሳቤጥን ፤ ሳራን ፥ ለማምጣት በቅርብ ጊዜ ወደ እንግሊዝ አገር ሒደው በጥር ፮ ቀን በዓርብ ባቡር ወደ አዲስ አበባ ገቡ።መምጣታቸውን ያወቁ ዘመድ ወዳጆቻቸውም ወደ ባቡር መቈሚያ ወርደው ተቀበልዋቸው ። እነዚህ ወጣቶች ሴቶች ልጆች የሚበቃቸውን ትምህርት ተምረው ስለመጡ ቤተሰቦቻቸውንና ልጆቻቸውን በሥራት ይመራሉ ብሎ ተስፋ በማድረግ እንኳን በደኅና ወደ ሀገራችሁ ለመመለስ አበቃችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል

መልስ

ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል

አቶ ለገሠ ቸሩ በብርሃንና ሰላም የተፈጥሮ ዕውቀትን ማነቃቂያ ምስጋና ስመለከት የተፈጥሮ ዕውቀት ታላቅ የትምህርት ዕውቀት ታናሽ ብለው ስለ ጻፉት ነገር የሐሳባቸው

ተቃዋሚ ሳልሆን ጥቂት የተሳሳቱትን ነገር አቶ ለገሠ ቸሩን ይቅርታ እየጠየቅሁ ለመናገር እደፍራለሁ ።

፩) አቶ ለገሠ ቸሩ የተፈጥሮ ዕውቀት ታላቅ የትምህርት ዕውቀት ታናሽ ስላሉ ታላቅ ስሕተት ጽፈዋል እንደምን ቢሉኝ በተፈጥሮ ዕውቀት ከዚህ ቀደም ምን ዓይነት ለአገር የሚጠቅምና ለርስዎ የሚሆን የክብር ስም እንደ ፕሮፌሰር ወይም እንደ መሐንዲስ ወይም እንደ ሐኪም ይህን ከመሰሉት ከነዚህ አንዱን በተፈጥሮ ዕውቀትዎ አገኙ? ወይስ ያገኙ ይመስልዎታል ?

፪) የሀገራችን መንግሥት ከልክ ያለፈ ገንዘቡን እያወጣ የተማሪ ቤትና ደግሞ ልጆችን ወደ ሠለጠነው አገር እየላከ የእውቀትን ነገር እንዲማሩ መንግሥታችንና የትምህርት ሚኒስትሩ ተግተው የሚያስቡበትን ከሁሉ የሚበልጠውን ነገር የተፈጥሮ ዕውቀት ይበልጣል ብለው መጻፍዎ የኢትዮጵያ ወጣቶች ለወደፊት ምንም አይሠሩም ብሎ እንደ ነቢያት ትንቢት የመናገር ዓይነት መሆኑን ማንም አይስተውም።

፫) ከአንድ ጀምረው እስከ ዓሥር ድረስ የጻፏቸው ነገሮች በምን እንደተገኙና በምን እንደሚፈጸሙ ሳይመረምሩ የተፈጥሮ ዕውቀትን አድንቁልኝ ብለው በመጻፍዎና ይህነንም እንጕርጕሮ ያሰቡበት ጌዜዎ በከንቱ ስላለፈ እጅግ አዝናለሁ ጊዜ ወርቅ ናት የምትባለውን ምሳሌ አልሰሙም እንዳልል ከመንግሥቱ ሥራ በአንደኛው ክፍል ውሥጥ መሆንዎን ሰው ሁሉ ያውቀዋል ነገር ግን ጌዜ ወርቅ መሆንዋን ዘንግተው የተፈጥሮ ዕውቀትን በብርሃንና ሰላም ተራራ ላይ ቁመው ለመስበክ እንደምን ያለ መንፈስ አንቀሳቀሰዎት ?

(አስረጅ) አቶ ለገሠ ቸሩ ሆይ ሆድ እየቀደዱ የውሥጥ ሕመምን እየመረመሩ ልዩ ልዩ መድኃኒት የሚሆኑትን ነገሮች መርምረው ማወቅና መሥራትን፤ ወርቅና ብርን፤ ፕላቲንም እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎችም የሚገኙበትንና በየዓይነታቸው እየለዩ ማውጣት ትልቁ የአውሮፓ ሥራ ደቂይና በሃገራችን ያሉ ለቍስል፤ለሥራይ ለምች የሚሆኑ ቅጠላ ቅጠሎች የሚቈርጡና የሚቀምሙ ይህን የመሳሰለውን ነገር የሚያሰናዱ ሰዎች እንኳን ከነሱ በፊት ያውቁ ከነበሩ ሰዎች ካልተማሩ እንዲሁ በገዛ ራሳቸው ለማወቅ አይችሉም ትልልቁን ነገር ትቼ አንድ አንዱን አነስተኛ ነገር እጽፍልዎታለሁ ሸማ፥ ጥበብ፥ ድርብ፥ መሥራት መዝጊያ ጠርቦ ልጎ ማጋጠም ማቅ መፍተልና መሥራት፥ብራና ፍቆ አለስልሶ መጻፍ ይህ ሁሉ ያለትምህርት ይሠራ ይመስልዎታልን? ። እነዚህ የጻፍኩቸው ነገሮች በተማሪቤት የሚማሯቸው አይደሉም ቢሉኝ አኳኋኑንና አሠራሩን የሚያሳዩና የሚያስተምሯቸውን ሳይዙ በራሳቸው ለማወቅና ለመሥራት እንደማይችሉ የታወቀ ነገር ነው።

አቶ ለገሠ ቸሩ ሆይ አሁን ባሉባት በክብር ሥራዎ ውሥጥ የሚሠሩት ከውጭ አገር ቋንቋ በመጡ ሐሳቦች አይደለምን? አቶ ለገሠ ቸሩ ሆይ ይህን የሚሠሩበትን ልብ ሳያደርጉትና ሳይሰማዎት ቢቀር ነው እንጂ በትምህርት የተገኘ መሆኑን የሰው ሕሊና ሁሉ ያውቀዋል ወንድሞቻችን በተማሪቤት ለፍተው ተምረው አገራችንን እንዲረዱት እርስዎ ሲአውቁት ቅን የሚያስቡትን የወጣቶችን ሕሊና ዋጋ ማሳጣትዎ እረ በምን ምን ከንያት ነው የውጭ አገር ቋንቋ የሚያውቁ ሰዎች ሁሉ አገራቸውን እስከሁን ድረስ አልረዱም ማለት ነውና ይቅርታ መጠየቅ ይገባዎታል ስል በወጣቶች ስም ሆኜ አመለክትዎታለሁ ። ከኢትዮጵያ ወጣቶች አንዱ አበበ ገብሬ ።

የአኵስም ጽዮን በዓል ።

በኅዳር ፳፩ ቀን የእመቤታችን በዓል ነበር ጽዮን ማለት ፀወን ፤ አምባ መጠጊያ ነውና እመቤታችን ለዓለም ሁሉ የምሕረት አማላጅ ስለሆነች ጽዮን ትባላለች ስለዚህም ከአራቱ ማዕዝነ ኢትዮጵያ ብዙ ሕዝብ እየተሰበሰበ አኵስም ላይ የእመቤታችንን በዓል ያከብራል ። ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ እንደመጣው እኔም የእመቤታችንን በዓል ለማክበር በ፲፱፻፳፬ ዓ ም ኅዳር ፳ቀን አኵስም ጽዮን ደረስሁ ። በዚሁም ቀን ብፁዕ አባታችን አቡነ ይስሐቅ አኵስም የሚገቡበት ቀን ስለ ነበረ በዳግማዊ ምኒልክ ትእዛዝ አኵስምን ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ተሹመው ያሠሩት ቤተ መንግሥት በባንዲራ አጊጦ ይጠባበቃቸው ነበረ ። ክቡር ንቡረ እድ አረጋይም ተከተማው ወጥተው በሚያስደንቅ ሰልፍ በክብር ተቀብለዋቸው ሲገቡ የአሥመራውም ቆንስል ክቡር አቶ ወዳጆ አሊ በቆንስልነት ሥራቸው ላይ የክቡር ንቡረ እድ ዲሬክተር ሁነው በአኵስም በጥቅምት ወር ስለ ተሾሙ ቀደም ብለው መጥተው ነበርና አብረው ከንቡረ እድ ጋር ሁነው ተሰልፈው ተቀበሏቸው ካህናቱም ልብሰ ተክህኖአቸውን ለብሰው፤ መዘምራኑም የማዕርግ ልብሳቸውን እያጌጡ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ ብለው እየወረቡ ቈዩ።ቀጥለውም ይንእዳሁ አብያተ ክርስቲያናት ወይብላሁ ብፁዕ ጳጳስ ይስሐቅ ኀሩይ እያሉ ሲያሸበሽቡ እጅግ አምረው ይታዩ ነበር ። ወድያውም ስለ አባታችን ክብር መድፍ ተተኰሰ። ከዚህም በኋላ አፈ ንቡረ እድ ተፈሪ የተባሉ ሊቅ መወድስ ቅኔ ተቀኙ።ቅኔውም ቀጥሎ ያለው ነው ። አኃዜ ዓለም ፍትሐከ ወልደ ጊዮርጊስ ፤ እንዘ ውስተ ዓለም ምሉእ በጽዮን ተወሰነ ።

እስመ እብነ ክብራ ለጽዮን ርእሰ ማዕዘንት ኮነ ፨
ወፀንሰት መንታ ለይስሐቅ አቡነ ።
ማኅፀነ ርብቃ ሃይማኖትነ ፤
ምስለ እበ ዓለም ይስሐቅ እስመ ተዋሐደት ለነ ።
ለይስሐቅሂ ጽላሎቱ አድባረ ጽዮን ከደነ ።
ቃለ ማዕነቅ ኃይለ ሥላሴ እምከመ ተሰምዐ በምድርነ።
እምጣነ አፉሁ ከሡተ በደብረ ጽዮን እምነ ።
ኖላዌ እስራኤል ኃይለ ሥላሴ ሠረገላ ብርሃን ዘተዕዕነ ፨

ቅኔውም ከተጸፈ በኋላ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኋለ አባታችን አቡነ ይስሐቅ ወደ ማኅበረ አክሱም የተላከ ደብዳቤ ተነበበና ዳር እስከ ዳር ፫ጊዜ ተጨበጨበ ። ጳጳሱም ሕዝቡን ወደ መንፈሳዊ መንገድ የሚመራ ስብከት ሰብከው ባርከው አሳረጉና ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ ስምንት ሰዓት ተኩልም ሲሆን ቅዳሴ ገብተው በዓሥር ሰዓት ወጡ ብፁዕ አባታችንም ከንቡረ እድ አረጋይ ቤት ገብተው ግብዣ ተጋብዘው ሰፈራቸው ቤላይ እንዲመለከቱት ከቤተ መንግሥቱ

ኀበርና ከዚያ ገብተው እደሩ ከማታው በሁለት ሰዓት ተደወለና ማኅሌቱ በጣም ደምቆ አደረ ። ኅዳር ፳፩ቀን ከጥዋቱ በአራት ሰዓት ዑደት ተደርጎ ጳጳሱም እንደ ፀሐይ የሚአንፀበርቅ ልብሰ ተክህኖአቸውን ለብሰው የሀገራቸውን የኢትዮጵያን ባንዲራ በትከሻቸው አንግተው ከዋክብት ያረፉበት የመሰለ የወርቅ ጃንጥላ ተይዞላቸው፥ ክቡር ንቡረ እድ አረጋይም የወርቅ ካባ ላንቃ ለብሰው፥ የወርቅ አክሊል ደፍተው፥ ባምጃ ሱሬ ታጥቀው፥የወርቅ ጫማ ተጫምተው፥ነጭ ሐር ጥላ ተይዞላቸው፥ ክቡር መልአከ ብርሃናት ገብረ ሕይወትም እጅግ ያማረ ባለወርቅ ጥብጣብ ካባ ለብሰው፥ሐር ጃንጥላ ተይዞላቸው፥ቆንስሉም ክቡር አቶ ወዳጆ የወርቅ ኒሻኖቻቸውንና የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ሁሉም በተዘጋጀላቸው ወምበር ተቀመጡ። ሌሎችም ስማቸው በዚህ ያልተጻፈ ከየአውራጃው የመጡ ብዙ መኳንንት ነበሩ ። በዑደትም ጊዜ ከህናቱ ሙሴኒ ርእያ ሀገር ቅድስት ቃዝራኒ ተናገሩ ዳዊት ዘመረ ፪ተኛ እስመ እምጽዮን ይወፅእ ሕግ ወቃለ እግዚአብሔር እምኢየሩሳሌም ብለው በአማረ ድምፃቸው ወረቡን ወርበው እስመ ለዓለሙንና ሰላሙን ፀፍተው ሲጨርሱ ብፁዕ አባታችን አቡነ ይስሐቅ ከወምበራቸው ተነሡና የበዓሉን ምክንያት የሚያስረዳ መንፈሳዊ ስብከት ሰብከው ባርከው አሳረጉ ። ሕዝቡም እጅግ የጣፈጠ ስብከታቸውን ለመስማት ከደስታው ብዛት የተነሣ እርስ በርሱ ይቀዳደም ነበረ ። ያንጊዜም ስብከት በናት በአባት ቋንቋ ሲሰሙት እንደምን ያምር ብለው አቶ ማኅተመ ወርቅ እሼቴ የተናገሩት ቃል ብዙዎቹን ሰዎች እየታሰበን ፈጣሪያችንን ስናመሰግነው ዋልን አምስት ሰዓት ተኩል ሲሆን ዑደቱ ተመለሰና በ፮ሰዓት በሦስቱም መቅደስ ባንድ ጊዜ ቅዳሴ ገቡ ። በመከከለኛው በጽዮን መቅድስም ገባሬ ሠናይ ሁነው የቀደሱ አባታችን ነበሩ ቅዳሴ ማርያምን ቀድሰው ከቅዳሴ በኋላ በክብር ዘበኞች ታጅበው ወደ ቤተ መንግሥቱ ገቡ ። እንዲህም ሁኖ በዓሉ በደስታ ከተፈጸመ በኋላ በኅዳር ፳፫ቀን ብፁዕ አባታችን አቡነ ይስሐቅ ፲፩ ታቦት ባርከው ለ፰ሰው ቁምስና፥ለ፰ ሰው ቅስና፥ለ፻፶፯ሰው ዲቁና ሲሰጡ ውለው በ፳፬ተኛው ቀን ዓዲ አቡን ለመሔድ ስለ ተነሡ መኳንንቱንና ከህናቱን ሕዝቡንም ለማሰናበት ወደ ትልቁ ሐውልት ሥር ከለው ደረጃ ወጥተው ክርስቲያን ሁሉ ለወደፊቱ ጋብቻው በተክሊል እንዲሆን ወንድ ባንዲት ሴት ሴትም ባንድ ወንድ ተወስኖ እንዲኖር ሌላም ልዩ ልዩ የሆነ መንፈሳዊ ስብከት ሰብከው አስተምረው ባርከው ሔዱ። ንቡረ እድና ዲሬክተሩም፥ በብዙ መኳንንትና ሠራዊት ታጅበው ከከተማው ውጭ ሸኝተዋቸው ተመለሱ ። ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ለሁሉም ጊዜ አለው እንደተባለ ዓምና እንደዚሁ አኩስም ጽዮንን ለመሳለም ሒጄ ነበር ነገር ግን አገሪቱ ጸና በማጣቷ ድኖቹ ፍትሕ አጥተው በየመንገዱ ሲያለቅሱ ይታዩ ነበር ። አሁን ግን ይህ ሁሉ አልፎ ድኃው በፀጥታና በሰላም ሥራውን እየሠራ በደስታ በዓሉን አክብሮ ስለዋለ ሕዝቡ ፈጣሪውንና መንግሥቱን እያመሰገነ ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲለ ምን ብዙዎቹ ስንሰማና ስናይ ዋልን ። ይልቁንም አሁን ቤተ መንግሥቱን ዲሬክተሩ አቶ ወዳጆ አሊ ተረክበው በቤተ መንግሥቱ ግቢ ለመምህራን የሚሆን ቤት ለማሠራትና ያገራችንን የመንፈሳዊ ትምህርት የሚአስተምሩ መምህራን መፈለጋቸውንና በሥራውም ከንቡረ እድ እየተመከከሩ መፋጠናቸውን በመስማቴ ምስጋናዬን ለፈጣሪዬ አቀርባለሁ ።

ትንሹ ወንድማችሁ በላይ ሐጐስ።

ማስታወቂያ ።

፩ኛ ፤ የክርስቲያን መንገድ ሁለተኛ መጽሐፍ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታትሞ ይሸጣልና ዋጋው አንድ ብር መሆኑን እናስታውቃለን ።

፪ኛ ፤ የቀን መቍጠሪ፥ የሒሳብና የመስፈሪ፥ የሚዛንም ልክ መግለጫ፥ የነገሥታት ታሪክና ዘመን፥አጽዋማትና በዓላት ከ፲፱፻፳፬ ዓ ም እስከ ፲፱፻፷፰ ዓ ም ድረስ፥የተቀማጭ ገንዘብና የዕዳ ባጭሩ የሚያጽፍ መዝገብ ያለበት ትንሽ ያጌጠ መጽሐፍ በኪሳችሁ መያዝ ያስፈልጋችኋልና ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት በአላድ ግዙ ።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአቦካትነት ሥራ ይሠራሉ በአገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክ አገር የፍርድ ቤት ብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ናቸው ። ለዚሁም አቦካትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጅሮንድ ዘለቀ አግደው ግቢ ነው። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፯ት ሰዓት ይቀበላሉ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሲንጀር ከቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሲንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መስንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።



ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርደና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የከትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የከትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የቍላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስሬያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሙሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. A. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAZA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልክ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፭
8me ANNE. № 5

ሐሙስ ጥር ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም።
JEUDI 28 JANVIER 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታላቅ ደስታ ያለበት የምስራች ።

አስቀድመን እንዳስታወቅነው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በን ከሆኑ ቈይተዋል። ዛሬም በጥር ፲፭ቀን እሑድ በእልፍኙ አዳራሽ ግብር አድርገው ስለዋሉ፥ ይልቁንም በጥር ፲፰ቀን የስብረተዓፅሙ ጊዮርጊስ ዕለት ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ለክብረ በዓሉ ስለወጡ ሕዝቡን ሁሉ እጅግ ደስ ብሎታል። ይህን የምስራች ለማስማት ስለአበቃው ብርሃንና ሰላም እግዚአብሔርን ያመሰግናል ።

ተልክ ያለፈ እርዳታ ።

ሚስተርኬን የሚባሉ የአሜሪካ ሚሲዮን ሠራተኛ በሲዳሞ ሲኖሩ በፅኑ ሕማም ታመው እጅግ ተጨንቀው ነበረ።ወዳጆቻቸውም ኀዘናቸው ሰለፀና ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አስታውቀው ወዲያው አይሮፕላን እንዲአስመጡላቸውና ወደ ሆፒታል ገብተው እንዲመረመሩ የጃንሆይን ፈቃድ ለመኑ።ጃንሆይም ርኅሩኅ ናቸውና እሺ ብለው በአይሮፕላን ሒደው እንዲያመጧቸው የአይሮፕላኖችን አለቃ ሙሴ ኮርጂርን አዝዘውላቸው በጥር ፲ቀን ሒደው አገሩን ስለአላወቁት ተመለሱ።ደግሞ ሁለተኛ በጥር ፲፩ ቀን በ፫ሰዓት ወደ ሲዳሞ በአይሮፕላን ሒደው በሽተኛውን ሚስተርኬንን ይዘው በ፯ሰዓት ተመልሰው ወደ አዲስ አበባ ገቡ።ወዲያውም በፍጥነት ወደ ቤተሣይዳ ሆፒታል ገብተው ዶክቶር ሐነር አከመዋቸው አሁን ደኅና ሁነዋል እንኳን እሳቸውና ወዳጆቻቸው ይህን ነገር ያወቀ ሁሉ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እጅግ አመስግኑዋቸዋል ። የአሜሪካና የኢትዮጵያ ፍቅርም ዛሬ ተገለጠ ።

የሚያሳዝን የእሳት አደጋ ።

ሰላሌ ፍቼ ከተማ በታኅሣሥ ፲፫ቀን ከሌሊቱ በ፰ ሰዓት ከዋናው ግቢ ፊትለፊት ከአንድ ትንሽ ቤት እሳት ተነሥቶ ፩ ባለ ፫ ክፍል ሱቅና ፪ቤቶች ምንም እቃ ሳይወጣ ተቃጠሉ ጉምሩኩም ባጠገብ ነበርና ምንም ቆርቆሮና ግምብ ቢሆን እንቹ ተያያዘና እኩሉ ተቃጠለ ። በዚያው ቀን የነጋዴዎች እቃ ገብቶ ጊዜው ስለመሸ ሳይጻፍላቸው በመቅረቱ እቃው በጉምሩክ ውስጥ አድሮ ነበር። የከተማው ዘበኞች አለቃ ምክትል ሹም አቶ ተካ ዘረፋ መዝጊያውን ሰብሮ ገብቶ እቃውን አዳነ ቤቱም እኩሉ እንደተቃጠለ እኩሉን አዳነው። በዙሪያውም ወዳሉት ቤቶች እሳቱ እንዳያልፍ ወኃ እያስቀዳ አስጠፋው ።

፪ተኛ በታኅሣሥ ፲፮ ቀን በ፱ሰዓት ሽንኩርት በሚባለው ከተማ አጠገብ ወርጡ የወይዘሮ ስለሺ ቤት ከ፪ት ቤት በስተቀር ዘጠኝ ቤት ከነ እቃው ተቃጠለባቸው። ለጊዜው ነፋስ በርትቶ ነበርና እሳቱን እያነሳሳው እቃ ከሚያወጡት ፫ሰዎች ተቃጠሉ።ከነዚህም አንዲቱ አርጉዝ፥አንዲቱ መነኩሲት ናቸው። አራተኛይቱ ቄስላ ግን ዳነች ።

፫ተኛ በታኅሣሥ ፲፰ቀን በፍቼ ከተማ አንድ ቀን በ፰ና በ፲ሰዓት በየተራ ፪ ቤት ተቃጠለና በቶሎ ሳይጎዳ አጠፉት ባለ ቤቶቹም መላልሶ በመቃጠሉ ፈርተው እቃቸውን ወደሩቅ ቦታ አሸሽተው አሳደሩ። በማግሥቱ ባ፲፱ቀን ከቀኑ በ፫ ሰዓት አቶ አየለ የሚባል ሰው ሚስቱ ሒዳ እሱም ታዞ ሒዶ ፪ቱም በሌሉበት ቶሎ እመለሳለሁ በማለት በደኅና ቍልፍ ዘግቶት ኑሮ ቤቱ ተቃጠለ።ጎረቤትና ሌላም ሰው ጢስ እያየ ተሰብስቦ ለማጥፋት ጥቂት ሲቀር ፪ት ቀፎ ንብ ከቤቱ ጥግ ነበረና ሕዝቡ እሳቱን ለማጥፋት ሲጣደፍ ቀፎው ተደፍቶ ሰውን አንድ ሳይቀር እየነደፈ አባረረው።መቸም እግዚአብሔር ያዘዘው የማይቀር ነውና እንደገና የጠፋው እየጋለ ነፋሱም እየበረታ እነዚያን ትላንት የተረፉትን ሁለት ቤትና ሌላም ፫ ቤት አቃጠለ።ያቶ አየለ ቤት ከነእቃው እንደተዘጋ አመድ ሆኖ የቀረው ግን እቃው ወጥቷል። የነዚህ ቤቶች እሳት ተያይዞ ሲነድ ባሕርዛፉን በተያያዘው ጊዜ እንደ ባሩድ እየጮኸ ወደአየር ሲወረወር ላየው መላው ከተማ የተያያዘ ይመስል ነበር። ግን የእግዚአብሔር ምሕረቱ ቅርብ ነውና ነፋሱም ጸጥ አሉ ንቡም ተቃጠለ ሰውም እንደገና እየተመለሰ አጠፋው በውራጃው ከ፫የሚበልጥ መንደር እቃውን ለማውጣት በመጣደፍ የተሰበረና የተበላሸበት ብዙ ነው ።

እኔም ከዳር ቁሜ ላገሩ እንግዳ ነኝና ከነዋሪዎች ምን ይመስላችኋል ፬ቀን ሙሉ እንደዚህ ያለ የእሳት አደጋ መደ-

ረጉ ብዬ ብጠይቃቸው ተማሪ እንደርቢ (አስማት) አድርጎ ይሆናል አሉኝ። እኔም ይህን ከንቱ ወሬ የሚዘሩ ከታላዮች ወገን ሳይሆኑ አይቀሩም ከቤቱ ሁኖ የእሳት ሥልጣን እንደምን ተሰጠው ሐሰት ነው ለሕዝብ እንዲህ ያለውን ከንቱ ወሬ ሲሰጡት እውነት ሳይቀበል አይቀርም ብዬ አሰብሁ።ደግሞ በታኅሣሥ ፳ ቀን ከማታው በአንድ ሰዓት የልዑል ራስ ካሣ የፍርድ ጸሐፊዎች አለቃ የባላምባራስ ዝለቅ አገልጋይ በጥፋቷ የታሠረች ቤቱን ስታቃጥል ሰው አይቷት ኑሮ በጣም ሳይጎዳ ጣራውን እንዳጋመሰው በርትተው አጠፉት።ለምን እንዲህ አደረግሽ ቢሏት ነዶኝ ነበርና መቸም አልጠረጠር ብንደርቢ ይመኻኛል ብዬ ነው አለች።ከዚህ በኋላ ይህን ሁሉ ያቃጠለው ሰው ነውና ያየህ የሰማህ አውጣ ተብሎ ሕዝቡ ቃዘ ተሰብስቦ ይውላል ።

የፍቼ ከተማ ፖስታ ሹም ገብሩ ወ አ ።

ስለ አራቱ የችግር መሠረቶች ማመልከቻ ።

ከነዚሁ ከ፬ቱ የችግር መሠረቶች አንዱን የመሬትን ግብር በቍርጥ ማድረግ የተባለውን ባለፈው በ፺፪ ቍጥር ብርሃንና ሰላም ጽፈን ነበረ።ጥቂትም የቀረ ቃል ቢኖር አሁን እናስከትላለን።ይህን የቍርጥ ግብር በሐረር አውራጃ የጃንሆይ ማድቤት የሆኑትን አገሮች ጅጅጋንና ጨርጨርን በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት በተሾሙበት ጊዜ በጃንሆይ ፈቃድ የ፪ቱን አገሮች ግብር በብር በቍርጥ አድርገውላቸው ነበረ። እነዚህ ጨርጨርና ጅጅጋ የሚባሉት አገሮች ከዚያ በፊት በጣም ጠፍ ነበሩ ዛሬ ግን በጣም ለምተው ብዙ ግብር ይገብራሉ ። ሁለቱም አገሮች ግብራቸው በቍርጥ ስለሆነ በጣም ለም ሁነዋል ይህን ሥራ በተሾሙበት አገር ጀምረው ለኢትዮጵያ በማሳየታቸው።በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል። ቀጥሎም የሻለቃ ሁነው ለራሳቸው ማደሪያ አገር ግዛት ካላቸው መኳንንት ለሕዝቡ የመሬቱን ግብር ቍርጥ በብር ማድረግ የጀመሩ ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ናቸው።የቍርጡም አኳኋን ስለ ማር ግብር የኰዳድ እህል ዓሥራት ወፍጮ፡ ምራት ሌላውንም ይህን የመሰለ የጉልበት ግብር የሚባለውን ሁሉ ቀርቶ ባላገሩ ከዓመት ዓመት አርሻውን እያረሰ ከብቱን እያረባ በዋናው ለም ጋሻ ፵፫ብር፡ በመካከለኛው መሬት ፴ብር እንደ መሬቱ ተዋረድ ፳፫ብርም ባመት እንዲሰጥ በዚህ ተዋውለው ባላገሩም በትልቅ ደስታ ተቀብሎ ወደ ቤቱ ገባ ።

ፊታውራሪ ታፈሰ ይህን ያደረጉበት ምክንያት ምን ይሆን ምክንያቱን እንተርጉመው ። መጀመሪያ የሚበቃ እውቀትና ማስተዋል ስላላቸው ሰው ሟች ጠፊ መሆኑን የ፩፩ሰው ንብረት በትንሽ ትንሽ ምክንያት ጠፊ መሆኑን አገር ግን እስከ ኅልፈተ ዓለም ኑዋሪ መሆኑዋን ስለ አወቁ ነው ።

፪ኛም አገራቸውን በውነት ስለሚወዱ ከኔ ጥቅም አገሬ መልማቱ ይበልጣል ብለው ነው እንላለን።እነዚህ እውነተኛውን መሠረት ያለውን የአገር ጥቅም የሚሠሩ ሰዎች ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል ስማቸውንም የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች እንዳይረሱት ሙሉ ተስፋ አለኝ ።

ከዚህም አስከትለን የከብት ክትባት በመታጣት የሚገኘውን የችግር መሠረትና ይህም ችግር ቢጠፋ የምንጠቀመውን ጥቅም እናመለክታለን ። ይህ የከብት በሽታ ቀድሞ በኢትዮጵያ አልነበረም አሁን ቅርብ ጊዜ የዛሬ ፵፫ዓመት ከምጥዋ ተነሥቶ ወደ ኢትዮጵያ ገባና በትግሬ ባማራ በጋላ አገር ገብቶ እንኳን የቀንድ ከብት በየደኑ ያለው አውሬ አሳማ ድኩላ ሳይቀር አለቀ ። ከበረሀ ያለውም ጎሽ አለቀ ግን ያን ጊዜ የይናርያ አገር ከፋ፡ኩንታ፡ኰሎ፡ ጊሚራ፡ ጉራ ፋርዳ የሚባሉትና እነሱንም የመሰሉ አገሮች ሁሉ ዲና ስለነበሩ አገሩ ስላልቀና ነጋዴ አይሔድባቸውምና በሽታው ሳይደርስ ስለ ቀረ እነዚህ አገሮች ከቀኑ በኋላ ከዚያ ብዙ ከብቶች መጡና እንደገና ከብት ባገሩ ረባ ይህ ባይሆን ከብት በማጣት አገሩን ትልቅ ችግርና መከራ ለብዙ ጊዜ ያገኘው ነበረ ። ከዚያም ወዲህ ይህ በሽታ ባገሩ ውሥጥ እየተመላለሰ በያገሩ ሁሉ ከብቶችን ይፈጃቸዋል ።

ባላገሮቹም ነግደው የሞተውን ከብት ቆዳውን ሸጠው እህል ሸምተው ከብቶች ወዳሉበት አውራጃ ሒደው ደክመው ፩፪ጥምድ በሬ ፳፴ቁም ከብት ሲአገኙ እንደገና በ፩ወይም በ፪ት ዓመት ተመልሶ በዚሁ አውራጃ ይኸው በሽታ ይመጣና ከብቶቹን ፈጅቶ ባላገሮችን ያስለቅሳቸዋል።ከዚያም በሽታ የተረፉትን ከብቶች ደግሞ አባ ሰንጋ፡ዋንጉርባ የሚባሉና እነሱንም የመሰሉ በሽታዎች እየተመላለሱ ይለቅሟቸዋል ። በዚህም በሽታ ምክንያት ከብቱ እያለቀ በየዓመቱ ወደ ውጭ አገር ለመሸጥ የሚወጣ ቈዳ ከ፪ እስከ ፫ሚሊዮን ይሆናል ይኸውም በጉምሩክ እስታስቲክ ይታወቃል። ይህም ላገሩ ትልቅ ጉዳት ነው ።

ግን ለነዚህ በሽታዎች ሁሉ በሌላ አገር የክትባት መድኃኒት ስላለ ከብቶች አያልቁም። በዚሁ በኛ ጠረፍ በሐማሴን እንኳ የኢጣሊያን መንግሥት የክትባት ቤት አቁሞ የሐማሴንን ከብቶች ያስከትባል። ጎረቤቶች የሆኑትም የኢትዮጵያ ዜጎች የትግሬ ሕዝብ ከብቶቻቸውን ከ፫፬ቀን መንገድ ነድተው ወስደው አንዳንድ ብር ከፍለው ያስከትባሉ።ከብቶቹም ከእልቂት ይድናሉ እንደዚሁ ለአገራችን የከብትም የሰውም ክትባት ቤት ደምብ ቢቆም ጥቅሙ ትልቅ ነው ። እነዚህ ከላይ የጻፍኋቸው በየዓመቱ የሚያልቁት ፫ሚልዮን ከብቶች በክትባት ተጠብቀው ቢኖሩና ባያልቁ እስከ ፭ዓመት ፲፭ሚሊዮን የሚሆኑ ትርፍ ከብቶች በአገር ውሥጥ ሊገኙ ነው።በዚህም ጊዜ የከብት ዋጋ በጣም ሲረክስ አሁን ዛሬ ቤት መሥራት ሚስት ማግባት ትተው በየከተማ የነጋዴ ተሸካሚ ወይም የፈረንጅ አሽከር የቀን ሙያተኛ ሁነው በመኰላላት የሚያልቁት የኢትዮጵያ ወጣቶች በ፫፬ወር ድካም በሚአገኙት ገንዘብ በ፲ብር ቀንጃ በሬ ገዝተው እርሻ ይጀምራሉ። አንድ ጊደር ገዝተው ወተት ቅቤ ሲአገኙ ጉልበት አግኝተው እራሳቸውን ያሰፋሉ።ከብቶቻቸው በዝተው የበረከቱላቸውም ሰዎች ለሣር ፍለጋ ሲሉ እንደ አሩሲ እንደ ከፋ ያለውን ጫካ ሒደው ያቀናሉና በበሬ ብዛት የእርሻ ሥራም ይሰፋል ። ከዚያም ቀጥሎ ከብት በአገር ውሥጥ ሲበዛ ዋጋው ይረክሳልና በመርከሱ ምክንያት ነጋዶች

ከዚህ ገዝተው ወደ ውጭ አገር ወስደው ለመሸጥ ይችላሉ። በዚሁም አኳኋን ፫፱ሚሊዮን ከብት ወደ ውጭ አገር ወጥቶ ሲሸጥ በአንድ ጊዜ ፺፱፻ሚሊዮን ብር ወደ ኢትዮጵያ ይገባል መንግሥትም ወደ ውጭ በሚወጡት ከብቶች ቀረጥ ፲፲፭ሚሊዮን ብር በአንድ ዓመት ያገኛል።መንግሥትም ሆነ ሕዝብም ሆነ ትልቅ የሥራ ፋብሪካ ለማቆም የሥልጣኔ ትምህርት በጣም ለማስፋት የንግድ ሥራ ለመጀመር የሚቀናው በዚህ በከብት ርቢ የገንዘብ ሀብት በጣም ሲገኝ ነው ። ይህን ማለቴም የተጀመረው ዛሬ ባገሩ ያለው የሥልጣኔ ትምህርት ቤት እንዲቀር አይደለም ይህ ያለው ጠንክሮ በሰፊው ሌላ እንድንጨምር ነው።

ደግሞም ከብት ባገር ውስጥ በዝቶ ከዚህ በላይ እንደጸፍሁት የከብት ዋጋ ሲረክስ የባለከፍቶቹ ባላገሮች ጥቅም ይበዛል እንጂ አይጐድልም፤ምክንያቱም ዛሬ ፩ የሥጋ ከብት ኑሮት በ፴ ብር የሚሸጥ ባላገር ከብቱ ከበሽታ ድኖ ሲረባለት ፲በሬ አግኝቶ በ፲በ፲ ብር ቢሸጣቸው ፻ብር ያገኛል፡ዛሬ ዋና የኢትዮጵያ ጥቅም የንግድ ሥራ መሥራት ፋብሪካ አቁሞ በፋብሪካው መሥራት ማዕድን መቈፈር አይደለም እነዚህ ሁሉ ሰፌ ትምህርትና ብዙ ገንዘብ ይፈልጋሉ።እኛ ግን ዛሬ ለዚህ የሚበቃን ገንዘብና ትምህርት ስለሌለን ጥቅም አናገኝባቸውም ጥቅም ማለትም የየ፩አንዱ ሰው ማግኘት አይደለም ዋና ጥቅም የምንለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ የሚጠቀምበትን ጥቅም ነው ስለዚህ ዛሬ ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት ዋና ሀብቷ የከብት ርቢና እርሻ ነው።እርሻዋ እንኳ ከብት ረብቶ በሬ ከተገኘ በኋላ ነው የከብት ርቢና እርሻ ሥራ ትምህርትና እውቀት አያስፈልጉም ብዬ አይደለም ትልቅ ትምህርት ያስፈልጋሉ ግን እስከዚያውም ትምህርቱን እስትናገኝ ድረስ የአገራችን ሣር ለምለም በመሆኑና እብዛኙ የመሬታችን ዋጋ እርካሽ በመሆኑ በተፈጥሮ ልማድ የሚረቡት ከብቶች ትልቅ ጥቅም ይጠቅሙናልና የዛሬው ዋና ሀብታችን ጊዜው የሚፈቅድልን የከብት ርቢ ሥራ መሆኑን መረዳት ያስፈልገናል

ስለዚህ ይኸን ፪ተኛውን የችግር መሠረት በፍጥነት መንቀልና ማጥፋት ትልቅ ባላጋራ ድል ማድረግ ነው

ማስረጃ

ሰፊ ለምለም መሬት ባለበት አገር የከብት ርቢ ሥራ ትልቅ ጥቅም መሆኑን የሚያስረዳ በአሜሪካ ውስጥ አርጀንቲን የሚባል መንግሥት አለ ሕዝቡ ፲ሚሊዮን ይሆናል በዚያ አገር መሬታቸው ለምለምና ሰፊ ስለሆነ ሥራቸው ከብት ማርባት ነውና በ፩ዓመት ከዚያ አገር ወጥቶ የሚሸጠው ከብት ዋጋው ፸ሚሊዮን ጆኒ ነው።ይኸም በአዛጋር ወርቅነህ ጆግራፊ በ፫፻፳ ገጽ ይገኛል።የዚህም ሒሳብ በዛሬው በጆኒ ሽረፍ ፩ጆኒ ፲፮ብር በሚመነዘረው ሒሳብ ፩ሺ፩፻፳ሚሊዮን ብርነው።የአርጀንቲን ሕዝብም ይኸን የከብት ርቢ ሥራ ማስፋታቸው ሌላ ሥራ ባያውቁ አይደለም ሌላ ሥራ እንደ ኤውሮፓ እንደ አሜሪካ ያውቃሉ ግን መሬታቸው ጥቅም የሚሰጣቸው በከብት ርቢ መሆኑን ስለተረዱ ብዙ ሕዝብ የከብት ርቢ ሥራ መርጦ ከብት ያረባሉ የሥልጣኔ ትምህርት ያለው ሕዝብ ብዙ ጥቅም ማግኘቱ የአገሩ መሬት የሚሰጠውን ሀብትና ጥቅም መርምሮ መርጦ በመሥራቱ ነው። ኢትዮጵያም ወደፊት ትልቅ ጥቅም የምታገኘው በከብት ርቢ ነው።ከብት ማርባት የሚቻለውም የከብት ክትባት ቤት ቁሞ ከብቶቹ ተከትበው ከማለቅ ሲድኑ ነው። ከዚህም አስከትለን ፫ተኛውን የችግር መሠረት ነገር እንጽፋለን።

ብ ደሬሳ ።

ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም የሐረር እንደራሴ ውጋዴንን ጐብኝተው በየክፍሉ ገበያና ኬላ አቁመው ስለመጡ ግጥም አዋቂው ግራዝማች ውብቴ የገጠሙላቸውን እንድታነቡት አትመንላችኋል። ለሠራተኛ ዋጋ ይገባዋልና ።

ለመድፍ ለመትረየስ ዋጋ እንዳታወጡ ።
እንደ ገብረ ማርያም የጠራ ጦር አምጡ ።
ከቤት ተሸፍና ትኖር ነበረች ።
ውጋዴን በንት ቀንታ ገበያ ወጣች ።
አባ ንጠቅ ገብሬን ምን ትሉታላችሁ ።
ጣናን ከተማ አርጎ ሲዋኝ እያያችሁ ።
ከቤቱ ሰባቸው ሲጣሉ ሰዎቹ ።
አባ ንጠቅ ገብሬ ለጐረቤት ምቹ ።
ቈራ በውጋዴን አይጥልም ያሉታል ።
እንደ እርጎ የሚያበርድ ከተማ ተገኝቷል ።
የመድፍ መተኰሻ ሙኙ ታጣ ሐረር ።
አበጀ አባ ንጠቅ የመትረየስ በር ።
ውጋዴን ዲና ነው ተብሎ ሲወራ ።
ታመነ አባ ንጠቅ በከተማው ሥራ ።
ንጠቅ የወንጌል ሕግ አያውቅም ውጋዴን ።
አሬትን ሊያስተምር ሔደ ወደማዴን ።
ዘመቻ ዘመተ በጾም በፍልሰታ ።
ፋሲካ አደረገ በሸበሌ ቦታ ።
መከኒ እያምልጥህ አባ ንጠቅ በርታ
ሱማሌም ገባልህ በዘፈን በልልታ ።
ከተሾሙት ሁሉ ያንት እድል በረታ
አሰፈረው ንጠቅ ላሙን ከበረቱ ።
አቢላም ሆነ አሉ አጻና እንደ ጥንቱ ።
ጥንት እንደ ሰማነው በከብረ ነገሥቱ ።

ማስታወሻ ።

ክቡር ራስ ናደው ነፍሳቸውን ይማርና ለኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ እርዳታ አስበው በታላላቆች ወንዞች ክረምት በመጣ ቍጥር ሀገርን የሚያደክሙትን ለገንዘባቸው ሳይሳሱ በውነት አስበውበት ያሠሩት ድልድይ ሥራው ግብዝ ስለሆነ ፈቃድ አጥቶ ገንዘብ እንዳልወጣበት ሁሉ በከንቱ የትልቁን ሰው ሐሳብና ሥራ ጐርፍ በመውሰዱ የጌታቸውን ሐሳብና ድካም ለዚህ ሥራ ብለው የደከሙና የተከተሉ ኢትዮጵያውያን ይህን በከንቱ የፈረሰውን ድልድይ የጌታቸው ሐሳብና የሰው ጕልበት ገንዘብ የፈሰሰበትን ከታሰበለት ዕድሜ ወዲህ መፍረሱን እያዩ ከመኳንንት እስከ ሕዝብ ባይናቸውም ያዩበሮአቸውም የሰሙ ተላላፊዎች ነጋዴዎችም በዚህ መንገድ በተላለፉ ቍጥር እያዘኑ ይሔዳሉ ። ይህም የትልቁ ሰው

ሐሳብ እንደዚህ መሆኑ በወኅው ውስጥ የቆሙት የግምብ ምሰሶዎች ሥራቸው ግብዝ በመሆኑና እንደሚቆዩ ነገር ሁነው ስላልተመሠረቱ መሆናቸውን ከተሠራ ጀምሮ የፈረሰበትን ዓመት ላሰበው ሰው በጣም ያስረዳል ።

ይልቁንም እንደምንሰማው ለዚህ ሥራ ወጭ የሆነውን ገንዘብ ለሰማው ሰው እጅግ ያሳዝናል። አበበ ኃይሉ።

ስለ ክቡር ፊታውራሪ አልጃራ ዕረፍት ።

ፊታውራሪ አልጃራ የደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ወንድም የደጃዝማች ሀብተ ማርያም አጐት ነበሩ። ወለጋ ወረዳ በደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ጊዜ በግዛታቸው እንደራሴ ሁነው ለአገሩ የተመቹ ለድኃውም ፤ ኅሩኅ ምግባራቸው የቀና ሃይማኖታቸውም የፀና ለሀገሩና ለጌታቸውም ታማኝ ነበሩ። ደጃዝማች ገብረ እግዚአብሔር ከረፉ በኋላም ለደጃዝማች ሀብተ ማርያም እንደ አባት ያህል የሚያስቡላቸው ረዳታቸው ነበሩ። ምንጊዜም በዚህ ዓለም ምንም ደኅና ሰው ቢሆን ከሞት የሚቀር የለምና እንደ እብጭ እየሆነ ግራና ቀኝ በእጃቸው ላይ እያበጠ አንድ ጊዜም እየጠፋ በእንደዚህ ያለ በሽታ አንድ ወር ያህል ታመው ተኝተው ነበርና በሽታው በጣም እየዋለ እያደረም የሚጠናባቸው ስለሆነ ነቀምት ወዳለው ሐኪም ለመታከም አስበው ኪነጅ ወደ ነቀምት ለመነሣት ተሰናድተው ለድኃ ነገር በጣም ሐሳቢ ነበሩና ለተበደለ ደኃ ነገሩን ሮብን፥ ሐሙስን፥ ዓርብን ጨርሼለት ቅዳሜ እነሣለሁ ብለው ሮብ ኅዳር በ፳፱ ቀን ለድኃው ችሎት አድርገው እኩሉን በብይን የአምስት ሰው ያህል በፍርድ ጨርሰው ፮ተኛውን ጀምረው ነገሩ ብዙ ምርምር ያለበት ስለሆነ ይደርና ነገ መርምሬ እፈርዳለሁ ብለው ዱሮ እስከ ፰ ፱ ሰዓት ያስችሉ የነበሩ ሰውነታቸውን በሽታ ስላገዳው በ፯ ሰዓት ተነሥተው ወደ ቤት እገባለሁ ሲሉ የበሩ ምድራህ አንቀፋቸውና ለመውደቅ ሲሉ ግራና ቀኝ የነበሩ አሽከሮቻቸው ከብርቱ አወዳደቅ አዳኑአቸው። ጉልበታቸው ብቻ መሬት ወግቶ ተነሡ። ከዚህ በኋላ ወደ እልፍኝ መሔድ ቢያቅታቸው በአልጋ እልፍኝ ደረሱ። ከዚህ በኋላ ቄስ ተጠርቶ ፫ጊዜ ደፍቶኝ ካሉ በኋላ እንደበታቸው ተይዞ ምንም ሳይናገሩ ቈይተው በተወለዱ በ፶፰ ዓመት ኅዳር ፴ቀን ከምሽቱ በ፫ሰዓት አረፉ። በብዙ ማዕርግና ልቅሶ ነጆ ኪዳነ ምሕረት ተቀበሩ። ይህም ከሆነ በኋላ ትልቁ ልጃቸው ቀኛዝማች ቢራቱ አባቴ ፊታውራሪ አልጃራ አረፉ። እንዲህ ያለ ጕዳት ተጐዳሁ ብለው ለደጃዝማች ሀብተ ማርያም በወረቀት አስታውቆ በሰሙ ጊዜ ደጃዝማችም ስለሀዘናቸው ጽናት በነቀምት አድባራት ያሉ ካህናትን በሙሉ አስጠርተው ከቤታቸው እስከ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ድረስ በአጐበር የጕዝ ፍታት እየተፈታ ሕዝቡ በእንባ እየተራጨ ሲያለቅስ ጥሉ የማያውቃቸውም እንኳን ደግነትና ለሀገር መርዳትና ደኅና ሰውነት እንዲህ ደግነወይ እያለ ያልቅስላቸው ነበረ። ከላይ እንዳስታወቅሁት ሰውዬው ለፍርድ የተጠነቀቁ ደኃን የጠበቁ ለሀገሩም አሳቢ ስለነበሩ ምንም ቢአማቸው ፩ቀን በአልጋ ሳይተኙ ከችሎት ዕለቱን ገብተው ስለሞቱ ዳዊት ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር ያለው ታሰበኝና የብርሃንና ሰላም ወዳጆቻችው ዕረፍታቸውን እንዲሰሙት ማስታወቂ ነው።

ፊታውራሪ አስጢፋኖስ።

የሚያሳዝን ሞት።

ደመቀ ተጫኔ የሚባል ልጅ አሁን በቅርብ ቀን በመጣው ነፋስ (ግሪፕ)፯ ቀን ታሞ ሞተ ልጁም በ፫ተኛው ክፍል እንግሊዝ ተማሪ ነበር። በባሕሪውና በትምህርቱ በመልኩም ያማረ ነበር። በዕድሜው የ፲፯ ዓመት ወጣት ልጅ ነው።

እናቱንና ወንድሙን አቶ ኪዳኔን ብርሃንና ሰላም እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል።

ስካር ገንዘብን ያጠፋል ሕይወትንም ይቀሥፋል ።

አንድ አንድ ሰዎች በጥጋብ የጐለመሱ፥ እግዚአብሔርን የረሱ የሰው ተፈጥሮ ምን እንደሆነ የማያስታውሱ ሰው ቢመታ የሚያጐዳ ሕይወቱ ሊአልፍ የሞት ዕዳ እንዲመጣባቸው የማያውቁ ብዙዎች ያልከልባለሚሎች የመስቲክ ቅምጥሎች አያለሁ። አሁን ዛሬ በታኅሣሥ ወር ውሥጥ አንዱ ባልከል ስካር ራሱ ያበጠ ከወዳጁ ከረቂ ጋር ተባብረው አንዱን ሠራተኛ አመንገድ ጠብቀው ያለምክንያት ከኋላው አንቀው እንደተቻላቸው ደበደቡት። ምንም በከፋትና በጭከና ተረዳድተው አልከልና አልከሊስት አንድነት ቢደበድቡት ኃይሉ ያልከል ኃይል ነውና እኩሌታው ኃይል ስለተከፈለ ተደብዳቢው የበትሩ አደጋ ሳይጐዳው ሸሽቶ አምልጦ ሕይወቱን በትዕግሥት አተረፈ። እስኪ ባይሸሽና እግዚአብሔር ባያወጣው ያለእውቀቱ አውቆ የሰው ሕይወት አሳልፎ የራሱንም ሕይወት እንዲያሳልፍ አይጠረጠርም። ይህ ግፍ በተደረገ በ፪ለተኛው ቀን ተደብዳቢው ደብዳቢውን ከሶ አዳኛ አድርሶ መደብደቡ ተመስክሮ ቅጣቱን እንዲቀበል ለጊዜው በቀላል ቅጣት ተፈርዶበት ነገሩ በዚህ ላይ ቈይቷል። ይህ ሰው ስካርን በገንዘቡ ገዝቶ ቅጣትንም በስካር አጋርነት አምጥቶ ነውና እስከዚህ የደረሰው ስካር ገንዘብን ያጠፋል ሕይወትንም ይቀሥፋል ማለታችን ስለዚህ ነው። እስኪ የተደብዳቢው ሕይወት ቢአልፍ እንደዚሁ ሊመሰከርበትና በሕይወቱ እንዲቀጣ ይጠረጠር ኖሯልን። አትስከሩ ከከፋት ተከልከሉ በትዕግሥት ኑሩ እያለ ብርሃንና ሰላም ያወግዛል (ያውጃል)። ምነው ሰው መከሪውን አይወድ ? « ወዳጃችህ ገብረ ኢየሱስ ድሬዳዋ።

ማስታወቂያ ።

ስለ አቶሞቢል አካሔድ ደምብ ።

ከሁን ቀደም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የአቶሞቢል ነጂዎች አካሔዳቸው በልክ እንዲሆን የአዲስ አበባ ከተማ ሜ

ዘጋጃ ቤት በየጊዜው በማስታወቂያ እያወጀ ደምብ አድርጎ ነበር።ነገር ግን የታወጀውን አዋጅ ሳይጠብቁ ከሕግ የተላለፉ አቶሞቢል ነጂዎች በየጊዜው በደምቡ ይቀጣሉ።አሁንም ማዘጋጃ ቤት በ፲፱፻፲፯ ዓ ም በ፴ የካቲት እንዳወጣው ማስታወቂያ በ፲፰ተኛው ክፍልና ሁለተኛም በ፲፱፻፲፰ ዓ ም በጥር ፲፩ ቀን በ፳ተኛው ክፍል እንደታወጀው ፫ተኛም በ፲፱፻፲፰ ዓ ም በ፪ ሚያዝያ እንደ ወጣው አዋጅ ከዚህ በፊት የወጡትን ማስታወቂያዎች መሠረት እያደረገ ፬ተኛም በ፲፱፻፲፱ ዓ ም በ፩ ግንቦት እንደተደረገው ማስታወቂያ እየደጋገመ ማዘጋጃ ቤት ማስታወቂያውን አድርጓል ። ፭ተኛም ለአቶሞቢል ነጂዎች የእነዳዳቸውን ልክ የሚአመለክት ነጂነት በተፈቀደላቸው ጊዜ ከፈቃድ ወረቀታቸው ጋራ እንዲሰጣቸው ተደርጎ በተሰጣቸው ደምብ በ፲፪ተኛው ክፍል የተጻፈውን መከተል ትተው አንዳንዶቹ አቶሞቢል ነጂዎች ከደንብ በተላለፈ ፍጥነት አቶሞቢል መንዳታቸውን ስለ ተመለከትን አሁንም ከአሁንም ቀደም በየጊዜው እንደታወጀው ማስታወቂያ የአቶሞቢል አካሔድ ፍጥነቱን ቀንሶ በዝግታ እንዲአስኬድ አበርትተን እናስታውቃለን።ነገር ግን ማናቸውም አቶሞቢል ነጂ ቢሆን ከደምቡ ተላልፎ በከተማው ውስጥ በፍጥነት ሲነዳ ቢገኝ በዘበኛ እየተያዘ ብርቱ ቅጣት ይቀጣል።የዚህንም ዓይነት እየደጋገመ ለአቶሞቢል ነጂነት የተሰጠውን ደምብና የተደረጉትን ማስታወቂያዎች ሳይጠብቅ ቀርቶ የተገኘ አቶሞቢልነጂ በደምቡ ፫ጊዜ ከተቀጣ በኋላ በ፬ተኛው ለአቶሞቢል ነጂነት የተሰጠውን የፈቃድ ወረቀት ይወሰድበትና ነጂነቱ ይከለከላል።ደግሞ ከሁን ቀደም በአቶሞቢል ደረጃ ላይ ግራና ቀኝ በውጭው ሰው እንዳይቆም ብለን በጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም በማስታወቂያ አጥብቀን ክልክል አድርገን ነበር ። ነገር ግን በማስታወቂያ እንዳስታወቅነው ሁሉ በትክክል አለመፈጸሙን ስለ ተመለከትን ከዚህ ቀደም የወጣውን ማስታወቂያ እያፀናን አጥብቀን ክልክል ማድረጋችንን ደግመን እናስታውቃለን።ይኸውም ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንሥቶ የፀና ይሆናል።ታኅሣሥ ፴ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ። የአዲስ አበባ ከንቲባ ።

የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ማስታወቂያ ።

በከተማ ጥዳት በኩል በየወሩ ስለሚከፈለው ገንዘብ ቀጥሎ ያለውን ደምብ እናስታውቃለን ።

ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ወደፊት የከተማ ጥዳትን ግብር የሚከፍል ሰው ሁሉ በየወሩ እከተማ ጥዳት ቢሮ ድረስ እያመጣ እንዲከፍል ደምብ ሁኑዋል።ነገር ግን በየወሩ ይህነኑ የከተማ ጥዳት ግብር እከተማ ጥዳት ቢሮ ድረስ እያመጣ ሳይከፍል ቀርቶ ወሩን አሳልፎ የተገኘ ሰው በየወሩ የሚከፍለውን የወር ግብር በዐጠፌታ እየተያዘ ይከፍላል ።

ጥር ፩ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ። የአዲስ አበባ ከንቲባ ።

ማስታወቂያ ።

፩ኛ ፤ የክርስቲያን መንገድ ሁለተኛ መጽሐፍ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታትሞ ይሸጣልና ዋጋው አንድ ብር መሆኑን እናስታውቃለን ።

፪ኛ ፤ የቀን መቍጠሪያ፥ የሒሳብና የመስፈሪያ፥ የሚዛንም ልክ መግለጫ፥ የነገሥታት ታሪክና ዘመን፥ አጽዋማትና በዓላት ከ፲፱፻፳፩ ዓ ም እስከ ፲፱፻፷፫ ዓ ም ድረስ፥ የተቀማጭ ገንዘብና የዕዳ ባጭሩ የሚያጽፍ መዝገብ ያለበት ትንሽ ያጌጠ መጽሐፍ በኪሳችሁ መያዝ ያስፈልጋችኋልና ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት በአላድ ግዙ ።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአቦካትነት ሥራ ይሠራሉ በአገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክ አገር የፍርድ ቤት ብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ናቸው ። ለዚሁም አበካትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጅሮንድ ዘለቀ አግደው ግቢ ነው። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፲ት ሰዓት ይቀበላሉ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።



ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሲንጀር ከቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ካለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ሕጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሲንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፣ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፣ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላኒዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አጽድቀው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ቅኅሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከቋ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒቅ ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፡ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቤታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦርና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ ምብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሽክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።

አበካት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሙሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ደ.ሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፡ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ፡በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፌ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሉ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፮
8me ANNE. № 6

ሐሙስ ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም።
JEUDI 4 Fevrier 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊው ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

መልካም በዓል።

ሁላችሁእንደእምታውቁት በጥር ፳፩ ቀን የአስተርእዮ ማርያም በዓል ነው።በዚሁም ቀን ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ግርማዊት እቴጌ፥ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፥ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት በእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ተሰብስበው ካህናቱ ማኅሌታቸውን አድምቀው ከፈጸሙ በኋላ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ እጅግ ደስ የሚአሰኝ እነጋገር ተናግረው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱ ።

በዚሁም ቀን ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በታላቁ አዳራሽ ታላቅ ግብር አድርገው ነበረ፤ ከግብርም በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት፥ ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ተሰብስበው በተቀመጡበት ክቡር ብጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት የገንዘብ ሚኒስትር የሕገ መንግሥቱን ትርጓሜ አስታወቁ በዚሁም ትርጓሜ መሀል እያገቡ ለሀገር ጥቅም የሚሆነውን ነገር ሁሉ አስታወቁ የነበረውም ሰው ሁሉ በቃላቸው መተከከል እጅግ ተደነቀ ፩ሰዓት ተኩል የሚሆን ቁመው በቃላቸው ሲናገሩ የአንደበታቸው አለመላቀቅ ሕዝቡን በሙሉ አስደንቆታል ያነጋገር ስጦታ ያለው ሁሉ እንደዚሁ ቢፈቀድለት ብዙ ጥቅም ያገኝበታል።

የመልእክተኞች በደኅና መግባት።

አስቀድመን እንዳስታወቅነው ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ፥ ልጅ ተፈራ ገብረ ማርያም የጂቡቲ ቆንስል ፥ ልጅ አርአያ አበበ፥አቶ ዳባ ብሩ በመስከረም ወደ ጃፓን መንግሥት ተልከው ሔደው ነበሩና በጥር ፳ቀን በግርብ ባቡር በደኅና አዲስ አበባ ስለገቡ የኢትዮጵያና የሮፓ መኳንንት ተሰብስበው በብዙ ክብር ተቀበልዋቸው። ብርሃንና ሰላም እንኳን በደኅና ገባችሁ እያለ ደስታውን ይገልጻል ። የጃፓን መንግሥት ያደረገላቸውን አቀባበል በሚከተለው እናትማለን ።

የዓሣ ጠባይ ።

ታላላቁ ዓሣ ታናናሹን ዓሣ ይውጣል እንዲህ ዓሣ እርስ በርሱ ባይዋዋጥ ባሕሩ ሁሉ ዳር እስከ ዳር ዓሣ ብቻ በሞላው ነበረ ። እንዲሁ ጦርነትም ባይኖር እግዚአብሔር እንዳዘዘው ይህች ዓለም ዳር እስከ ዳር ሰው በሞላት ነበረ ።

ሰው ለሰው የመተላለቅ ነገር የተጀመረ ጥንት ይህች ዓለም ገና ሕፃን ወጣት ልጅ ሳለች ጀምሮ ነበረ ። የዚያን ጊዜ ያዳም ልጅ ዓይኑ ገና አልተከፈተ የዛሬው አእምሮ በልቡ አልተዘራ አልበቀለ እንዲአው እንደ እንስሳ ይኖር ነበረ ። ስለዚህ መጨከን መጨካከን፥መግደል መገዳደል ጥፋትና ኃጢአት ይሆን አይመስለውም ነበረ ። ስለዚህ ባለማወቅ ነበርና አይፈረድበትም ዛሬ ግን ዓለም አርጅታና ጐልምጣ በሕዝቡ ልብ የጠነከረና የጐለበተ ዕውቀት ከሥልጣኔ ጋራ ከደረበት በኋላ እንዲህ በጭካኔ አለርኅራኄ ኃይለኛው ሰነፉን፥ ብርቱው ደካማውን እየዘለለ እያነቀ እንደ ዓሣ ቢውጠውና እርስ በርሱ ቢተላለቅ እጅግ የሚአስደንቅ ያረመኔ ሥራ ነው። የሠለጠኑቱ ነገሥታት አገር ሁሉ ከብዙ ዓመታት ጀምረው እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረ ጊዜ የተናገረውን ቃል ለመፈጸም ሲሉ የሚአደርጉ መስለው ይህችን ዓለም የሰው ዘር እንዲሞላት ሲሉ በዕውቀታቸውና በጥበባቸው ብዛት ተግተው በዓለም የተዘራው ሁሉ በሽታ እንዲነቀልና እንዲጠፋ የሰው ዘር ሁሉ በጤናው እንዲአድግ እንዲኖር እንዲአረጅ እንዲዋለድ እንዲራባ እያሉ ሌት ተቀን ይማስናሉ ይጥራሉ ። ሕፃናቱንም በጅምናስቲክ፥ በትግል በእስፖርት ጉልበታቸው እንዲበረታ ጅማታቸው እንዲረታ ናላቸውም የጥበብና የብልሀት የዕውቀት ምንጭ እንዲሆን አለዞራት ትሕትና፥ ደግነት አለጭካእንደአድርባቸው እያደረጉ በብዙ ጭንቀት ያሳድጋሉ። ከዚህ ሁሉ ትምህርት በኋላ እኩሉ አለአገባብ የሰው ንብረት ለማጥፋት አገሩን ለመቀማት ሲሉ፥ እኩሉም በሚገባቸው ነፃነታቸውን ለማዳን አገራቸውን ለመጠበቅ ሲሉ እንደዚያ ተጨንቀው ተጨንቀው ያሳደጓቸውን ወጣቶች ልጆቻቸውን እንደበግ ወደሚታረዱበት የጦርነት ስፍራ ይሰድዋቸዋል ። እንዲህ እየሆኑ የአዳም ልጅ እርስ በርሱ እየተራረደ በደም ባሕር እየዋኘ እየተላለቀ ይህች ዓለም እንኳን እግዚአብሔር ባዘዘው ቃል የሰው ዘር ይሞላት ይልቁንም ዕራቁቷን እንድትቀር አደረጓት።

መቸም አገራቸውን ከኃይለኛ ወንዛቸውን ከወንጀለኛ ለማዳንና ነፃነታቸውን ለመጠበቅ ልጆቻቸውን እንደ አብር-

ሃም ለሞት ቢአሳልፉ ይገባቸዋል ላገሩ የሚሞት ሰማዕት ነው ። እነዚያ አለሥራት በገዛ ጕልበታቸው ኰርተው የሰውንብረት የሚአጠፉት፣ የሰው አገር የሚቀሙት የልጆቻቸውን ደም በከንቱ ማስፈሰሳቸው ነውና ከእግዚአብሔር ቃል መውጣታቸውን ይመሰክራሉ ። አረመኔ መሰደቡ ከዚህ የበለጠ ነገር መች ሠርቶ ነው ።

ይህን ግን እግዚአብሔር ቢረዳ ይኸው አሁን የኢጣልያ የውጭ አገር ጕዳይ ሚኒስትር በፊተኛው መንገድ በተለመው ፈሰስ የዕርቅና የፍቅር ምንጭ እንዲወርድበት ለማድረግ ዠኔብ የተሰበሰቡት የነገሥታቱ ሊቃውንት በትጋትና በቅንነት ይጨርሱት ዘንድ ዓለሙ ሁሉ ተስፋ አድርጓል ።

ይህ የፍቅር ነገር በውነት ቢደረግ ለጦርነት መሰናጃ የሚወጣው ሁሉ ገንዘብ ዛሬ ባለሙ ሁሉ የመጣውን ችጋር አጥፍቶ አሁን ከያገሩ በማጣት የሚያልቀውን ሕዝብና ደኀ ያድነው ነበረ ። እንዲህ ከሆነ ችጋር የሚሉት ሁሉ ከዚህ ዓለም እንዲጠፋ የታወቀ ነው ።

የጦር መሰናጃ በነድሮ ባንድ ዓመት ብቻ ፲፯ቱ ነገሥታት ያወጡት ብዛቱ በጣም ይገርማል ልኩንም በጋዜታ ተጽፎ እንዳየነው ከዚህ በታች ጽፈነዋል። ነገሩን በጣም ለማስረዳት ስንል የነዚህን አሀጉር ያምሳ ሰባቱንም መንግሥታት እየራሳቸው የሕዝባቸውንም ቍጥር ያገራቸውንም ስፋት ጨምረን ከየመጻሕፍቶቻቸው እያየን ጠንቅቀን ጽፈነዋል የሕዝቡ ቍጥር መቸም በየቀኑ ይለዋወጣል ይበዛል ያንሳል ። ለሁሉም ነገር የሁሉንም ከጦርነታቸው በኋላ የተለዋወጠውን መርምረን አይተን እንደልኩ ጽፈነዋል ። ያገራቸውም ስፋትና ጥበት ከጦርነታቸው በኋላ የሆነውን አይተን አድርገነዋል ።ስለምን ያንዳንዱ መንግሥት አገር ከጦርነቱ በኋላ የተጨመረለት የሰፋለት አለ ። ያንዳንዱም የተቀነሰበትና የጠበበበት አለና ሁሉንም አይተን በትክክል ጽፈነዋል ። ሁሉንም መጻፋችን ያገራችንን ወጣቶች ልጆች ለጂዖግራፊ ትምህርት ያግዛቸዋል ስለማለት ነው ።

አሜሪክ (ኤታዙኒ)።

የሕዝቡ ቍጥር ፻፳፪ሚሊዮን ፯፻፴ሺ.

ያገሩ ስፋት ፯ሚሊዮን ፰፻፹፱ሺ.፱፻፺፱ ኪሎሜትር ካሬ

አሁን በአለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፲፯ሚሊ.አርድ ፯፻፴፫ሚሊዮን ፯፻፹፫ሺ. ፍራንክ

የመስኮብ ሶቢየት መንግሥት ።

ሕዝቡ ፻፷፯ሚሊዮን

ያገሩ ስፋት ፳፩ሚሊዮን ፫፻፶፪ሺ. ፱ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፲፬ሚሊ.አርድ ፬፻፹፫ ሚሊዮን ፫፻፳፯ሺ. ፯፻፹፫ ፍራንክ ።

የፈረንሳዊ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፵ሚሊዮን ፯፻፵፫ሺ. ፺፻፹፬

ያገሩ ስፋት ፭፻፶ሺ. ፱፻፹፯ ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፲፩ሚሊ.አርድ ፯፻፹፬ሚሊዮን ፍራንክ

የግራንድ ብሬታኝ (እንግሊዝ)።

የሕዝቡ ቍጥር ፵፭ሚሊዮን ፯፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፪፻፵፪ሺ. ፯፻፴፩ ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፲፩ሚሊ.አርድ ፯፻፴፩ሚሊዮን ፫፻፸፫ሺ. ፍራንክ

የኢጣልያ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፵፪ ሚሊዮን ፫፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፫፻፲፬ሺ. ፪፻ ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፯ሚሊ.አርድ ፪፻፹፫ ሚሊዮን ፯፻፷፪ሺ. ፫፻ፍራንክ

የጀርመን መንግሥት ።

ሕዝቡ ዛሬ ከትልቁ ጦርነት ወዲህ ፷፫ሚሊዮን ፷፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ዛሬ ፬፻፷፱ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፬ሚሊ.አርድ ፪፻፺፰ሚሊዮን ፹፯ሺ. ፍራንክ

የጃፓን መንግሥት ።

ሕዝቡ ፹፯መሊዮን ፯፻ሺ. (፺መሊዮን ብለው የጻፉ ሰዎችም አሉ)

ያገሩ ስፋት ፫፻፹፩ሺ. ፫፻፹፯ ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፭ሚሊ.አርድ ፱፻፳፩ሚሊዮን ፫፻፴፯ሺ. ፫፻ፍራንክ

የቸኮስሎባክ መንግሥት።

ሕዝቡ ፲፬ ሚሊዮን ፬፻፴፫ሺ.

ያገሩ ስፋት ፻፵፫ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፩ሚሊ.አርድ ፪፻፹፱ ሚሊዮን ፯፻፹፫ሺ. ፍራንክ

የሩማኒ መንግሥት።

ሕዝቡ ፲፰ሚሊዮን

ያገሩ ስፋት ፪፻፺፫ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጕዳይ ያወጡት ገንዘብ ፩ሚሊ.አርድ ፫፻፺፩ሚሊዮን ፯፻፹ሺ. ፍራንክ

የሀንግሪ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፰ሚሊዮን ፯፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፺፫ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጕዳይ ያወጡት ገንዘብ ፫፻፷ ሚሊዮን ፫፻ሺ. ፍራንክ

የፖርቱጋል መንግሥት ።

ሕዝቡ ፮ሚሊዮን ፯፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፺፫ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፩፻፱ሚሊዮን ፱፻፺፩ሺ. ፍራንክ

የኤስፓኝ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፳፪ ሚሊዮን ፯፻፪ሺ.

ያገሩ ስፋት ፭፻፭ሺ. ፯፻፹፫ ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፪ሚሊ.ሕርድ ፫፻፲፬ ሚሊዮን ፫፻፹፬ሺ. ፫፻ፍራንክ

የሊቱአኒ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፪ ሚሊዮን ፫፻፲፯ ሺ.

ያገሩ ስፋት ፶፫ሺ. ፯፻፶፱ ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፻፶፪ ሚሊዮን ፍራንክ ።

የሌቶኒ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፩ሚሊዮን ፰፻፺፫ሺ. ።

ያገሩ ስፋት ፷፭ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፻፲፯ሚሊዮን ፫፻ሺ. ፍራንክ

የፊንላንድ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፫ሚሊዮን ፯፻፲፪ሺ.

ያገሩ ስፋት ፺፭ሺ.፪፻፺፫ ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፩፻፲፭ ሚሊዮን ፩፻፴፯ሺ. ፍራንክ

የሱይስ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፬ሚሊዮን ።

ያገሩ ስፋት ፵፩ሺ.፪፻፺፰ ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፩፻፺፮ ሚሊዮን ፫፻ሺ. ፍራንክ ።

የቱርክ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፲፫ ሚሊዮን ፯፻፷ሺ.

ያገሩ ስፋት ፯፻፹፪ሺ. ፫፻፺ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፩፻፵፬ ሚሊዮን ፪፻፸፱ሺ. ፪ፍራንክ

የቡልጋሬ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፭ሚሊዮን ፯፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፻፫ሺ. ፻፵፯ ኪሎሜትር

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፻፺ ሚሊዮን ፪፻፹፭ሺ. ፪፻፺ ፍራንክ

የግሪክ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፯ሚሊዮን ፪፻፴ሺ.

ያገሩ ስፋት ፻፳፯ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፫፻፴፫ ሚሊዮን ፭፻፳ሺ. ፍራንክ

የሆላንድ መንግሥት (ፓኤሲ. ባሴ.) ።

ሕዝቡ ፯ሚሊዮን ፯፻፴ሺ.

ያገሩ ስፋት ፴፬ሺ. ፪፻፲ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፯፻፹፪ሚሊዮን ፍራንክ

የቤልጅግ መንግሥት።

ሕዝቡ ፰ሚሊዮን

ያገሩ ስፋት ፴ሺ. ፭፻፺፬ ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፫፻፴፪ ሚሊዮን ፫፻፸ሺ. ፍራንክ

የኖርቤጋር መንግሥት ።

ሕዝቡ ፪ሚሊዮን ፰፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፫፻፳፬ሺ. ኪሎሜትር

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፪፻፸፫ሚሊዮን ፍራንክ

የኦስትራሊ.መንግሥት።

ሕዝቡ ፯ሚሊዮን ፯፻፲፬ሺ.

ያገሩ ስፋት ፯ሚሊዮን ፱፻፴፫ሺ. ፫፻፹፫ ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፬፻፷ ሚሊዮን ፬፻፺፪ሺ. ፫፻፺ ፍራንክ

የኤስቶኒ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፩ሚሊዮን ፪፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፵፫ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፻፴፫ሚሊዮን

የፓሎኝ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፴ ሚሊዮን ፬፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፫፻፹፰ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ያወጡት ገንዘብ ፪ሚሊ.አርድ ፫፻፩ሚሊዮን ፫፻፹፰ሺ. ፍራንክ

የፔርስ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፱ሚሊዮን

ያገሩ ስፋት ፩ሚሊዮን ፫፻፶፰ሺ. ፶፬ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፪፻፺፯ ሚሊዮን ፬፻ሺ. ፍራንክ

የፔሩ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፯ ሚሊዮን ፫፻ሺ. ።

ያገሩ ስፋት ፩ ሚሊዮን ፯፻፺፰ሺ. ኪሎሜትር ካሬ ።

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፪፻፺፬ ሚሊዮን ፱፻ሺ. ፍራንክ

የምስር መንግሥት (ኤጅፕት)።

ሕዝቡ ፲፬ ሚሊዮን ፪፻፲፫ሺ. ፫፻፴፬ ።

ያገሩ ስፋት ፱፻፲፬ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፪፻፴፩ ሚሊዮን ፯፻፸፪ሺ. ፱፻፺ ፍራንክ

የዳኔማርክ መንግሥት።

ሕዝቡ ፫ ሚሊዮን ፭፻፹ሺ.

ያገሩ ስፋት ፵፫ሺ. ፱፻፹፯ ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፫፻፯ ሚሊዮን ፯፻፺ሺ. ፍራንክ

የሊቤሪአ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፩ሚሊዮን ፯፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፺፰ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፫ሚሊዎን ፫፻፩ሺ. ፯፻፶ ፍራክን

የሉሴምቡርግ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፪፻፺፱ሺ. ።

ያገሩ ስፋት ፪ሺ. ፭፻፹፮ ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፯ ሚሊዎን ፱፻፴ሺ. ፍራንክ

የኑበል ዜላንድ መንግሥት።

ሕዝቡ ፩ ሚሊዎን ፬፻፹፫ሺ.

ያገሩ ስፋት ፪፻፸ሺ. ኪሎሜትር ካሬ ።

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፹፯ ሚሊዎን ፬፻፫ሺ. ፯፻፶ ፍራንክ

የፓናማ መንግሥት።

ሕዝቡ ፯፻፲፬ሺ.

ያገሩ ስፋት ፹፯ሺ. ፬፻፹ ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፲፭ ሚሊዎን ፬፻፴፫ሺ. ፭፻ ፍራንክ

የፓራጓይ መንግሥት።

ሕዝቡ ፰፻፴ሺ.

ያገሩ ስፋት ፬፻፶፱ሺ. ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፵፭ ሚሊዎን ፬፻፹፯ሺ. ፭፻ ፍራንክ

የሳንዶሚጎ መንግሥት።

ሕዝቡ ፩ሚሊዎን ፳፬ሺ.

ያገሩ ስፋት ፶ሺ. ፶ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፹፯ ሚሊዎን ፬፻፹ሺ. ፱፻፶ ፍራንክ

የሳን ሳልባዶር መንግሥት።

ሕዝቡ ፪ ሚሊዎን ፬፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፴ሺ. ፱፻፶፫ ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፶፬ ሚሊዎን ፹፱ሺ. ፍራንክ

የሲአም መንግሥት።

ሕዝቡ ፲፭ ሚሊዎን ፭፻፯ሺ.

ያገሩ ስፋት ፭፻፲፰ሺ. ኪሎሜትር ካሬ ።

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ያወጡት ገንዘብ ፪፻፵፫ ሚሊዎን ፮፻፫ሺ. ፯፻፶ ፍራንክ

የኡሩጓይ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፩ ሚሊዎን ፰፻፹፰ሺ.

ያገሩ ስፋት ፻፹፮ሺ. ፱፻፳፮ ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፻፲፭ ሚሊዎን ፱፻፶ሺ. ፍራንክ

የቦሊቢያ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፫ ሚሊዎን ፭፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፩ሚሊዎን ፬፻፴ሺ. ፴ ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፹፯ ሚሊዮን ፴ሺ. ፍራንክ ።

የብረዚል መንግሥት ።

ሕዝቡ ፴፱ ሚሊዎን ፯፻፳፭ሺ.

ያገሩ ስፋት ፰ ሚሊዎን ፬፻፹፭ሺ. ፯፻፷፯ ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ያወጡት ገንዘብ ፩ሚሊ. አርድ ፫፻፷፭ ሚሊዎን ፯፻፷፫ሺ. ፍራንክ

የአርጀንቲን መንግሥት።

ሕዝቡ ፲፪ ሚሊዎን

ያገሩ ስፋት ፪ሚሊዎን ፯፻ሺ. ኪሎ ሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፩ሚሊ.አርድ ፪፻፺፫ ሚሊዎን ፪፻፹፪ሺ. ፯፻፳፭ፍራንክ ።

የኮሎምቢያ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፯ሚሊዎን ፺፱ሺ. ፫፻

ያገሩ ስፋት ፩ሚሊዎን ፪፻፩ሺ. ፭፻፰ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፻፴፭ሚሊዎን ፫፻ሺ. ፍራንክ

የኮስታሪክ መንግሥት።

የሕዝቡ ቍጥር ፭፻ሺ. ፭፻

ያገሩ ስፋት ፴ሺ. ሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፲፯ሚሊዎን ፪፻ሺ. ፍራንክ

የኤኩአዳር መንግሥት ።

ሕዝቡ ፪ሚሊዎን ፭፻ሺ.

ያገሩ ስፋት ፫፻፯ሺ. ፫፻ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፵፭ሚሊዎን ፫፻፶፭ሺ. ፍራንክ

የአትሪሽ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፪ ሚሊዮን ፯፻ሺ. ።

ያገሩ ስፋት ፳፫ሺ. ፫፻፴፫ ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፫፻፴፱ ሚሊዎን ፯፻ ፳፫ሺ. ፍራንክ

የመክሲክ መንግሥት።

ሕዝቡ ፲፯ሚሊዎን ፬፻፬ሺ.

ያገሩ ስፋት ፩ሚሊዎን ፱፻፹፯ሺ. ፪፻፩ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ነገር ያወጡት ገንዘብ ፩ሚሊአርድ ፯፻፶፫ሚሊዎን ፫፻፹፯ሺ. ፭፻ ፍራንክ

የቬኔዙኤላ መንግሥት።

ሕዝቡ ፫መሊዎን

ያገሩ ስፋት ፩ሚሊዎን ፳ሺ. ፬፻ኪሎሜትር ካሬ

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፫፻፶፪ ሚሊዎን ፪፻፴ሺ. ፍራንክ

የዩጎስላቢያ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፲፫ሚሊዎን

ያገሩ ስፋት ፪፻፵፰ሺ. ፮፻፴፭ኪሎሜትር ካሬ

አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፩ሚሊአርድ ፪፻፳፩ሚሊዮን ፩፻፶ሺ ፍራንክ

የሆንዱራስ መንግሥት።

ሕዝቡ ፯፻ሺ
ያገሩ ስፋት ፪ሺ ፪፻፵፰ኪሎሜትር ካሬ
አሁንባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፳፬ሚሊዮን ፫፻፴፰ሺ ፍራንክ

የኩባ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፫ሚሊዮን ፭፻፹ሺ
ያገሩ ስፋት ፪፻፴ሺ ፭፻፳፬ ኪሎሜትር
ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፫፻ሚሊዮን ፯፻፸፭ሺ ፍራንክ

የጉቲማላ መንግሥት።

ሕዝቡ ፪ሚሊዮን ፭፻ሺ
አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ያወጡት ገንዘብ ፺፪ሚሊዮን ፭፻ሺ ፍራንክ
ያገሩ ስፋት ፻፲፫ሺ ፸፰ ኪሎሜትርካሬ

የሐይቲ መንግሥት ።

ሕዝቡ ፪ሚሊዮን ፫፻ሺ
ያገሩ ስፋት ፳፰ሺ ፯፻፸፯ኪሎሜትር ካሬ
ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፳፰ሚሊዮን ፰፻፵፰ሺ ፍራንክ

የኡኒዮን ሱድ አፍሪካ ።

ሕዝቡ ፯ሚሊዮን
ያገሩ ስፋት ፩ሚሊዮን ፪፻፳፫ሺ ኪሎ ሜትር ካሬ
አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፺፳፪ሚሊዮን ፯፻፹፪ሺ ፪፻፸፭ ፍራንክ

የኒካራጉአ መግሥት።

ሕዝቡ ፯፻፴፰ሺ ፪፻፰
ያገሩ ስፋት ፻፲፫ሺ ፩፻፵፫ኪሎሜትር
አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፯ሚሊዮን ፰፻፱ሺ ፯፻፸፭ፍራንክ

ሀ ን ድ ።

ሕዝቡ ፫፻፴፫ሚሊዮን
ያገሩ ስፋት ፩ሚሊዮን ፯፻፸፬ሺ ፯፻፲፬ ኪሎሜትር ካሬ
አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፭ሚሊአርድ ፪፻፹፩ ሚሊዮን ፱፻፹ሺ ፭፻፵ፍራንክ

ፖ ር ላ ድ ።

ሕዝቡ ፪ሚሊዮን ፱፻፸፩ሺ ፱፻፺፪
ያገሩ ስፋት ፫፻፹ሺ ፫፻፹፫ ኪሎሜትር ካሬ
አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፲፰፯ሚሊዮን ፯፻፲፪ሺ ፭፻ፍራንክ

አ ዝ ቤ ሲ አ ።

ሕዝቡ ፲ሚሊዮን ፻፭ሺ
ያገሩ ስፋት ፩፻፵፯ሺ ፩፻፸ኪሎሜትር ካሬ
አሁን ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፱፻፲፫ ሚሊዮን ፯፻፵ሺ ፍራንክ ነ አፈወርቅ ገ ዘብሔረ ዘጌ።

ማስታወቂያ

ከ፲፱፻፳፬ ዓ ም በፊት ስለከተማ ቦታቸው የሚከፍሉትን ያመት ግብር የ፩፡የ፪፡የ፫፡የ፬፡ የ፭ ዓመት ግብር እስካሁን አስታጕለው ሳይከፍሉ ስለቀሩ እንዲከፍሉ እያልን በየጊዜው በደብዳቤም በማስታወቂያም ካስረዳናቸው በኋላ ምንም የከፈሉት ነገር የለም ስለዚህ አሁንም ከ፲፱፻፳፬ ዓ ም በፊት ሳይከፍሉ ታጕለው የቈየውን ካ፩ እስከ ፭ዓመት ያህል ያለውን ግብር አቈበው በድምሩ እስከ የካቲት ፩ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም ድረስ ያልከፈሉ ሰዎች ባጠፌታ እንዲከፍሉ አድርገን በክፍል ዘበኛ ማስገደዳችንን እናስታውቃለን ይሁን እንጂ ከዚህ በኋላ ደግሞ ደህ የታጕለው ግብር ባሁኑ ዘመን ጨርሶ ሳይከፈል ቢቀር ወደፊት ማዘጋጃ ቤት የቦታውን ግብር አከፋፈል አሻሽሎ በቈረጠው ልክ አራት ዓጠፌታ አድርገው እንዲከፍሉ ማድረጋችንን አስቀድመን እናሳስባለን ጥር ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም

የአዲስ አበባ ክንቲባ።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአቦካትነት ሥራ ይሠራሉ በእገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክአገር የፍርድ ቤትብዙ ዘመን ሠርተዋል። ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ናቸው።ለዚሁም አቦካትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ ፣ ጊዮመጡብት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጅሮንድ ዘለቀ አግደው ግቢ ነው ። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፯ት ሰዓት ይቀበላሉ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሴንጀር ቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ሕጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዮ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውስጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮላታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላኒዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።



ባለነጭፈረስዊስኪ ።

ጤና እንድታገኙና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈል,ጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲለሙሴ ኤ አ ኃኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ሕሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መስከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርስቲያን በታች ከጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትክል የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዣና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ኣለም

ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኜይ።
አበካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአውጀይድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭው

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፯
8me ANNE. № 7

ሐሙስ የካቲት ፫ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም።
JEUDI 11 Fevrier 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጻፃት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ነፋስ መለወጥ ።

ከዚህ ቀደም እንዳስታወቅነው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፳ቀን ያህል በሥራ ብዛት ስለታመሙ ሕዝቡ ተጨንቆ ነበረ ። መቸም በሥራ ብዛት ፃ ክንያት መታመማቸውን ታላቁ ሐኪም ያውቀዋልና በአዲስ አበባ ብርድ እጅግ ስለበዛ ወደቄላ ሒደው ነፋስ እንዲለውጡ ሶለ አመለከተ ግርማዊት እቴጌ መነንን፥ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴን፥ ልዕልት ዘነበወርቅን፥ ልዕልት ፀሐይን፥ ልዑል ራስ ኃይሉን ፥ ልዑል ራስ ሥዩምን፥ ከሌሎችም ጥቂቶች መኳንንት አስከትለው በጥር ፳፫ቀን በጧት በልዩ ባቡር ተሳፍረው ከአዲስ አበባ ተነሡ ። በድሬደዋ ከተማ ሰንብተው በጥር ፳፬ ቀን ጂቡቲ መድረሳቸውን በስልክ ሰማን ። ነፋሱም እጅግ ተስማምቷቸዋል ስለተባለ እጅግ ደስ ብሎናል ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሔዱበትን ምክንያት ላላወቁ ሰዎች ይህን ማስታወቂያ ጽፈናል አሁን በቅርብ ቀን እንዲመጡ አውቀናልና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ ደስ ይበላችሁ።

ንቃትና ትጋት ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለከተማውዋና ታማኝ ጠባቂ የአደረጓቸው ክቡር ፊታውራሪ ብሩን የጦር ሚኒስትሩን ነው ። እሳቸውም ይህን ታላቅ እምነት ተቀብለው ንቃትና ትጋት ማብዛት እንዲገባ ስላወቁ ሌሊትና ቀን ተግተው በከተማው ዙሮ በአቶሞቢል እየዞሩ ዘበኞችን በማንቃታቸው እጅግ ተመስግነዋል ።

ስለ ጊዜው የገንዘብ ችግር።

አሁን ዛሬ በዓለም ሁሉ የገንዘብ ችግር ወሬ ይወራል በሁሉም አገር የገንዘብ ችግር በዝቷል ይባላል። ገንዘብ ማለትም በኤውሮፓና በአሜሪካ ሕዝብ የሚገበያይበት በነገሥታት መልክ የታተመ ወርቅ ነው ። ደግሞም በምሥራቅ መንግሥታት አገር እንደ አገራችን የብር ገንዘብ አለ ። ደግሞም ስለ ወርቅ ምትክ በወርቅ ዋስትና መገበያያ የሚሆን የኒኬል፥የናሐስ፥ የወረቀት ገንዘብ አለ። ይህም እንደ በንክኖት እንደ ቤሳ ማለት ነው።

ይህን ዛሬ በዓለም ላይ የሚወራውን የገንዘብ ችግር አስተውለን ስንመለከተው በጣም ይገርማል። ገንዘብ ማለት ወርቅና ብር ከሆኑ እንደ እንስሳ ታርደው እንደ እህል ተፈጭተው አልተበሉ። እንደ ጨርቅ አርጅተው ተቀዳደው አልወደቁ እንደ ሱካር እንደ ጨው ሟምተው አልተበሉ አልተጠጡ፥እንደ ብረት ዝገት የሚየበላሻቸው ሁነው አልዛጉ። ቀድሞ ወደ ወጡበት ቦታ አልተመለሱ ገንዘብ ጠፋ የሚባልበት ምክንያቱ ምን ይሆን፥መቸም ሌላ ምክንያት ይገኝለት አይመስለኝም ብቻ ዛሬ ሰው ሁሉ ጌትነት ብዙ ገንዘብ ብዙ ሀብት ስለ ፈለገ ሀብታሞቹ ባለገንዘቦች ሁሉ እየሰበሰቡ ዕላይ ቁጭ አደረጉት በየሰው እጅ የቀረውም ገንዘብ ለዓለም ጕዳይ የማይበቃ ሆነ በሌላው ዓለም እንኳ በሠለጠኑት በ፩፩አገር ፋብሪካ በዝቶ ከሚሠራው ዕቃ ብዙው የማይሸጥ ስለሆነ ብዙ ፋብሪካ እየተዘጋ ሠራተኞቹ የሚሠሩት ሥራ ስላጡ ብዙዎችን የገንዘብ ችግር ተሰማቸው። ከ፩፩አገርም ሁሉ ሥራ የሚሠራው በመኪና ስለሆነ ሰዎች ሥራ አጡ ይባላል። በኢትዮጵያ ግን ይህ ሁሉ የለም ግን በአገራችን ያለው ገንዘብ ብር ነውና ከዛሬ ፪ዓመት ጀምሮ በዓለም ላይ የጥሬ ብር ዋጋ ረከሷል» ይኸውም የኛ ብር ከምንለው የሚበዛው በንጉሠ ነገሥታችን መልክ ስላልታተመና ዋስ የሚሆነው ወርቅ ስላልነበረው ዋጋው ልክ እንደ ጠገራ ሁኖ ረከሰ፥ ዕቃ ከውጪ አገር ሲመጣ በጊኒ በፍራንክ ተገዝቶ ስለሚመጣ በዕቃ ግዢ ላይ የብር ዋጋ ማነሽ ጐደለና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፯ብር የነበረው ፺ብር፥ሺ ብር የነበረው ፭፻ብር፥ ሆነበት በዚህም ምክንያት ፪ዓመት ሙሉ በ፩ብር የሚገዛውን ዕቃ በ፪ብር በዕጥፍ ሲገዛ በአገር ውሥጥ የነበረው ብር ብዙው በእቃ ሻጮች እጅ ስለገባ አሁን ዛሬ ከባላገር ብር አንሷል

ይኸውም የብር ችግር ለከተማም ሕዝብ ይሰማው ጀምሯል በዚህ ስንገረም አሁን የቡን፥የቆዳ ዋጋ ረከሰ፥ ብዙውን ገንዘብ ወደ አገራችን የሚያገቡልን እነዚህ ፪ነበሩ ይልቁንም የዚህ የገንዘብ መታጣት ነገር ወደ ፊት የሚያሰጋን ነገር አለ አሁን ዛሬ የእንግሊዝ ጊኒ ዋጋ በጣም ወርዷል። ምናልባት እንደ ጊኒው ሁሉ ፍራንክና የአሜሪካ ዶላር የወረደ እንደሆኑ የቡንና የቆዳ ዋጋ ከአሁኑ የበለጠ በጣም የሚወድቅ ይመስላል። በአገር ውሥጥ የነበረው ብር የዕቃ ግዢ ዋጋ እጥፍ ስለሆኑ

በእቃ ሻጮች እጅ ገባ።የገሩ ወጭ ቡንና ቄዳ ተሸጦ ገንዘብ እንዳያገባልን ዋጋቸው ረክስ ሌላ ሀብት በፋብሪክ ተሠርቶ የሚሸጥ እቃ ኑሮን እንንዳንሸጥና ገንዘብ እንዳያመጣልን ይህን ማድረግ ገና አልቻልንም ወይም በያሌው እህል ፤ ጥጥ ፤ አታክልት ኑሮን እሱን ሸጠን ገንዘብ እንዳናገኝ በአገር ውሥጥ ዛሬ ተሠርቶ ያለው እርሻ ከኛም አይተርፍም ።

ወይም ብዙ ከብት አርብተን ከብት ወጭ አድርገን ሸጠን በሱ ገንዘብ እንዳናገኝ ከብቱን በየዓመቱ በሽታ ፈጅቶት ለዚህ የሚበቃ ከብት የለንም። ይህም የከትብት ሥራ ስላል ኖረ ነው። አሁን ደግሞ ይህን ሁሉ ጕዳታችንን ሳንመረምርና ሳንረዳው ወደፊት የሚመጣውንም ጕዳት ሳንገምተው እኛ በገዛ እጃችን ያመጣነው ትልቅ ጕዳት አለ ። አሁን ዛሬ የገንዘብ ወጭአችን በየቤታችን ሁሉ ፩እጥፍ ሁኑዋል ሁለቱ እጥፍ ከላይ እንደጻፍሁት በብር መርከስ ምክንያት ነው ። ፪ቱእጥፍ ደግሞ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየቤቱ ፪ት ዓይነት ኑሮ አለው ጸዱ ሰው እንደ ኢትዮጵያ ልማድ ከልብስ ወገን ጥበብ ኩታ፥ ቡልኮ፥ ሱሪ፥እጀጠባብ፥በርኖስ፥ ካባ አለው፥ አሽከሮች፥በቅሎዎች ፈረሶች፥ ለጓሚዎች፥ጥልፍ ኰርቻ፥ የብር ዶቃ፥የፈረስ ቤኔቻ ሌላም መጣሪያ አለጡ ። ደግሞም ከእቃ ወገን መሰብ፥ዋንጫ ብርሌ፥ሌማት፥ቢላዋ፥ ምንጣፍ፥መጋረጃ፥ይህንንም የመሰላ አለው እንደ አገሩ ልማድ ግብር ያበላል፥ ዝክር ይዘክራል፥ተስከር ያበላል ። ይህ ለአንድ ሰው ኑሮ ሙሉ ነውና በቂ ነበረ ። ግን ይኸው አንዱ ሰው እንደ ኤውሮፓውያን ኑሮ ደግሞ ከልብስ ወገን ኮት፥ወፍራም ሹራብ፥ሱፍ የብርድ ልብስ፥ፍራሽ፥ የአልጋ ልብስ፥የዝናም ልብስ፥ ጫማ፥ ገምባሌ፥ባርኔጣ፥ የባርኔጣ መስቀያ፥የቁም ሣጥን፥ሻንጣ፥ ሌላም የሮፓውያን እቃ አለው ከዕቃም ወገን የፈረንጅ ወምበር፥ ልዩ ልዩ ጠረጴዛ፥ ፋኖስ መብራት፥ የብረት አልጋ፥ ሣህን፥ብርጭቆ፥ ማንከና ሹካ የቻይ ጀበናና የፍንጃል ማቅረቢያ ፥ በየዓይነቱ የአበባ ማስቀመጫ ትልቅና ትንሽ ሰዓት ፥ መስታወት ፎቶግራፍ አቶሞቢል፥ሹፌር የአንድ ፈረንጅ ዕቃ በሙሉ አለው። ድግስም ሲደግስ ወይም በሌላ ዘወትር ቀን ቢሆን እንደ አገር ልማድ ነጭ እንጀራ ጠጅ፥ ጠላ የኢትዮጵያን ወጥ በየዓይነቱ፥ ቡን፥ ሰንጋ፥ ሙክት፥ ቃርዶ ይቀርባል። ደግሞም የፋርኖ ዳቦ የፈረንጅ ወጥ በየዓይነቱ፥ወይን ጠጅ፥ቢራ፥ ሻምፓኝ፥አረቂ በየዓይነቱ፥ ቢሺ ውኃና ፒሪ ውኃ ሰዳ ሳይቀር የፈረንጅ አገር ፍሬ በየዓይነቱ ቻይ ሎከር ፥ ሾኮሌት ሁለቱም ዓይነት ይቀርባል።የገንዘባችን ወጭ ፪እጥፍ ሁኑዋል ያልሁት መጀመሪያ ከብር መርከስ የተነሣ በአንድ ብር ይገዛ የነበረው ዕቃ ዋጋው ፪ብር ሆነ።ዳግመኛ የዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ የአንድ ሰው የ፪ ሰው ንብረት ሆነ። ይህ አኳኋን እንኳን ለሕዝብ ለድኃ ይቅርና ለመንግሥትም ቢሆን ችግር የሚያበዛ ይመስላል። ምክንያቱም መንግሥት ከቀድሞ እንደ ቈየው የኢትዮጵያ ደምብና ልማድ አገር ግዛቱን በነጋሬት ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት እንደሚገባ ሹሞ ሸልሞ አከፍሎ ሰጥቷቸዋል የአገሩ ግብር የበርና የገበያ ቀረጥ ሌላውንም ከአገር ግዛት የሚገኘውን ጥቅም ሁሉ ቀድሞ እንደ ቈየው ለመሳፍንትና ለመኳንንት ለትክለኛም ተሰጥቶ በቀድሞው አካሔድ ለእነሱ ሁኑዋል በአንድ ወገን ደግሞ መንግሥት እንደ ኤውሮፓ እንደ አዲሱ የሥልጣኔ አካሔድ የሚኒስቴር ቤቶች፥የትምህርት ቤቶች፥ ሆስፒታል የከተማ መንገድ በሥልጣኔ አካሔድ የሚሠለጥኑ ወታደሮችና ዘበኞች ሌሎችም እነዚህን የመሰሉ ትልልቅ ሥራዎች (አርጋኒዝ) ሁሉ አቁሞ ሥራውን ለማስኬድ ጀምሯል የ፪ቱም ወገን ሥራዎች ብዙ ወጭ ገንዘብ ያስፈልጋሉ ።

ይህንን አካሔድ ልብ አድርጎ ለተመለከተው ሰው ትልቅ ጕዳት መሆኑ በጕልህ ይታያል ። ጕዳት መሆኑም መንግሥት ሆነ ሕዝብም ሆነ ለቀድሞ ኑሮ ዓይነትም ለአዲሱ የሥላጤኔ ሥራ አካሔድ ማስሔጃ የሚሆነውንም ገንዘብ የሚያገኘው ከዚችው ካንዲት አገር ነው ለወጭነት የምንፈልገው ገንዘብ ግን አካሔዳችን ፪ ዓይነት ስለሆነ ለ፪አገር የሚበቃ ገንዘብ የሚያስፈልገን ሆነ ። ስለዚህ ይህ ፬ እጥፍ ወጭ ወደፊት ለአገሪቱ ትልቅ ጉዳት የሚሆናት ይመስለናልና ሁላችንም በዚህ ነገር ማሰብ ያስፈልገናል ። ተረት ስንሰማ ፪የሚያበርር በ፩ዱም አይደርስ ይበላል ። ይኸንም ማለቴ ዛሬ ልክ እንደ ኤውሮፓውያን ኑሮ ለማድረግ እንችላለንና የቀድሞው ይቅር ወይም የኤውሮፓን ሥልጣኔ መቀበልን እንተውና በቀድሞው ልማድ እንቆይ ማለቴ አይደለም አስቀድመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሥልጣኔ ማለት ምን እንደሆነ ለይተን እንወቅ ። ሥልጣኔ ማለት የሠለጠነ ሕዝብ ለንግድና ለትርፍ የሠራውን እቃ በብዙ ዋጋ ገዝቶ ከቤት ማኖር ወይም መልበስ አይመስለኝም ። ትምህርትና ሥልጣኔ ያላቸው ሰዎች በሠሩት ቤት መቀመጥ የሠሩትን ልብስ ገዝቶ መልበስ መልካም መልካሙን እቃቸውን ገዝቶ ከቤት ማስቀመጥ ጥቅምና ሥልጣኔ አይሆንልንም ። ይልቁንም ገንዘባችንን አበክኖ ክፉ ችግር ይመጣብናል እንጂ ሥልጣኔ ማለትስ እኛ የትምህርትን ሥራ አጠንክረን ባገሩ ችግርና ድኅነት በዝቶ እንዳንቸገር የገንዘብ (ኤኮኖሚክ) ቁጠባ ሥራ ሕዝቡን እየመከርን ልጆቻችንን የሥልጣኔ ትምህርትና የእጅ ሥራን ትምህርት እያስተማርን በአገራችን ብዙ ዓይነት ሥራ እየተሠራ ራሳችንን እንድችል ማድረግ ።

ደግሞ አሁን በቶሎ የከብት ርቢ ሥራና የእርሻ የአትክልት ሥራ ባገሩ እንዲለማ እንዲበዛ ከኛ ተርፎ ወደ ውጭ አገር በብዙ ተሸጦ ከውጭ አገር ገንዘብ እንዲያመጣልን ማድረግ ሌላውን የኤውሮፓ ሥልጣኔ እስትናገኝ ለጊዜው የሚሆን ሥልጣኔ ይህ ነው ።

ይህም ሐሳብ የአገር ታላላቆች ለዚህ ለማይረባ ለውጭ አገር ዕቃ ብዙ ወጭ ማድረግ ትተው ለሕዝባቸው የጥንቃቄ መንገድ ቢያሳዩት ይፈጸማል ። ብዙዎች የሥልጣኔ ትምህርት የሌላቸው የምሥራቅ አገሮች እንደዚሁ የሌላ አገር ዕቃ መግዛትና ብዙ የገንዘብ ወጭ ማድረግ ጌትነትና መከበር መስሎአቸው በዚህ አካሔድ ፍጻሜ ለሌለው ለትልቅ ጕዳትና ውርደት ደርሰዋልና ከዚህ መንገድ በቶሎ እንራቅ ።ሕዝቡም እየተስማማ ይህ የማይረባ አካሔድ የሥልጣኔ ሥራ መሥ-

ራትና ጌትነት መስሎት በሁለት ክፍል ኑሮ የሚያወጣውን የገንዘብ ወጭ ቢተወው ለሕዝቡ ይጠቅመዋል ።

ለዚሁም ማስረጃ ቀጥሎ ያለውን የአዲስ አበባ ጉምሩክ እስታትስቲክ በየዓመቱ የሚወጣውን ሂሳብ መመልከት ነው። በ፲፱፻፲፰ ዓ ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቡንና ቄዳ፥ ሰም፥ ከብት እህል፥ ሌላም ንግድ ለውጭ አገር የሸጠበት የገንዘብ ድምር ፱ሚሊዮን ፱፻፺፯ሺ ፯፻፺፩ ብር ነበረ።ደግሞ ከውጭ አገር የመጣውን እቃ ጨርቅሐር፥ድርና ማግ፥ ብረት፥ ሌላውንም የንግድ ዕቃ የገዛበት ዋጋ ፯ሚሊዮን ፱፻፳፱ሺ ፪፻፲፯ ብር ነውና በዚያ ዓመት ገቢና ወጭው ሲመዛዘን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፪ሚሊዮን ፱፻፺፰ሺ ፭፻፺፬ ብር አትርፎ ነበረ። ይህም መልካም ዕድል ነበረ አሁን ግን የብር ዋጋ ስለረከሰ ደግሞም ሕዝቡ ብዙ የውጭ አገር ዕቃ መግዛትን ልማድ ስላደረገና በብዙ ስለሚገዛው በ፲፱፻፲፱ ዓ ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለውጭ አገር ሰዎች የሸጠው የንግድ ዕቃ ዋጋ በአንድ ዓመት ፯ሚሊዮን ፭፻፹፩ሺ ፪፻፹፯ ብር ነው።ደግሞም የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚሁ ዓመት ከውጭ ሰዎች በአንድ ዓመት የገዛው የንግድ እቃ ዋጋ ፲፫ ሚሊዮን ፭፻፺፩ሺ ፩፻፹፭ ብር ነው በዚህ ዓመት ገቢና ወጭው ሲመዛዘን ከኢትዮጵያ በውጭ ሰው እጅ የሔደብን ገንዘብ ፮ሚሊዮን ፻፹ሺ ፩፻፲ብር ነው።ቀጥሎም በ፲፱፻፳ ዓ ም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለውጭ አገር ሰዎች የሸጠው የንግድ እቃዋጋ ፯ ሚሊዮን ፻፹፩ሺ ፱፻፺፯ብርነው ደግም የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚሁ ዓመት ከውጭ አገር ሰዎች የገዛው የንግድ ዕቃ ዋጋ ፲፩ ሚሊዮን ፻፺፯ሺ ፩፻፺፩ብር ነው። በዚህ ዓመት ከኢትዮጵያ ሰዎች በውጭ ሰዎች እጅ ትርፍ የሔደብን ብር ፫ሚሊዮን ፱፻፳፩ሺ ፫፻፳ብር ነው።በእቃ መወደድና በቡን በቄዳ መርከስ ምክንያት በዚህ በ፫ዓመት ንግዳችን ፲፫ሚሊዮን ፻፺፩ሺ ፪፻፳፫ብር ጐደለብን። ይኸውም ብር ከአገራችን ሕዝብ እጅ ወጥቶ በውጭ ሰዎች እጅ መግባቱ ነው ።

ይህም የሐረር፥የድሬደዋ፥የጅጅጋ፥የጋንቤላ፥የመተማ፥ የምጥዋ ሒሳብ ሳይጨመር የአዲስ አበባ ጉምሩክ ብቻ ነው።ይህ ለመላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ ጉዳት ነው። ይህ ትኳኳን ፫ዓመት የደጋገመን እንደሆነ የብር ዘር ከአገር መጥፋቱን ብንረዳው ይሻላል።ይህንም አውቀን ዝም ማለት አይደለም ልናስብበት በጣም የሚያስፈልግ ነው ።

ብ ደሬሳ ።

የተፈርዶ ሞት ።

ሽማግሌ ሲመርቅ ከተፈርዶ ሞት ያድንህ ይላል። ተረት ሲደርስ ቁም ነገር ይሆናልና የደረሰበትን ሰው ፍርድ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለገዳዮች ፍርድ በአደረጉበት በታኅሣሥ ፳፱ ቀን በዓርብ ችሎት ሰምቼ ለአሰማችሁ ወደድሁ። ነገሩም እንዲህ ነው ዝንጀሮ ውኃ በሚባል በጅሩ አውራጃ ጋሻው የሚባል በእርሻና በችግር የሚኖር ሰው አለ። በጎረቤቱ አሺኔ የሚባል ተንኰለኛ ሰው እግሩን እየጠበቀ ይህ ድኃ ችግረኛ ከቤቱ ሲወጣ ሚስቱን ለምዶበት ኑሮ ፩ ቀን የዚህ የችግረኛ ድኃ በሬው ደክሞበት ወዲያውም ማኅበሩ ነበረና ማኅበሩን ጠጥቶ አንዳንድ ቀን ረሱልኝ ብሎ ለመን ሲሔድ አይቶ ከሌሊቱ ፭ ሰዓት ሲሆን እንደ ልማዱ መዝጊያውን ገልብጦ ገብቶ ቢቆም ባለቤቲቱ እባክህ ወንድሜ ውጣልኝ ባለቤቱም ወደ ማኅበሩ ነው የሔደው በሬው ታሞበታልና አሁን ይመጣል ብትለው እምቢ ብሎ ሲጨቃጨቅ ባለቤቱ ደርሶ ይህን መዝጊያ ምን ከፈተው ብሎ ቢጠይቃት መቸም ሴቶች ምክንያት ለመስጠት ይቀናቸዋልና በሬው ይሆናል እንጂ ማን ይከፍተዋል ብላ መለሰችለትና ወደቤቱ ሲገባ ሌባው ባለቤቱንና ባለቤቲቱን በጐራዴ አቈሰላቸው ባለቤቱም ጠንካራ ነውና ከተመታ በኋላ ባላጋራውን አጠንክሮ ይዞ በጨለማ ወደቤቱ ሲመለስ ብቻውን እንዳይሆን ከማኅበሩ ሁለት ሰዎች ተከትለውት ነበሩና ከነሱ ፩ዱ በጦር ወግቶት የቈሰለውም ሌባ ሩጦ ከቤት ወጥቶ ሔዶ በሜዳ ወድቆ ዘመዶቹ ሸሽገው ወስደው ከቤት አስተኝተው ሞተ አሉ።ከዚህ በኋላ እነዚያ ረዳቶች ሁነው የወጉት ሰዎች ስለአልተገኙላቸው ባለቤቱን ዘመዶቹ ተቈራኝተውት መጥተው በገዛቤቱ አላስገባም ብሎ በጐራዴ ከነሚስቱ አቍስሎት በፊትም ሚስቱን ቀምቶት ቢገድለው አያስሞተውም ተብሎ ተፈረደ።ዘመዶቹም አፍረው ሔዱ። ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር የተባለው ተረት ተፈጸመ።

ለሚያስቸኵል ጥያቄ የተሰጠ መልስ ።

በብርሃንና ሰላም በ፫ኛው ዓመት በቍጥር ፫ በ፷ገጽ ስለ ሙሴ ሚክሊሲያኖስ ግፍ ፍጻሜው እንደምን ሆነ ብለው ተቈርቋሪው ወዳጃችን ስለጠየቁኝ መልስ ባጭሩ ሁኖ እንደሚከተለው ክርክር ነገሩ ቈሟል ።

ባዲሱ ሕግ ስለ ወንጀለኛ መቅጫ ም ፫ ቍ ፪፻፳፫ በፈቃዱ ሰው ስለመታና ስላቈሰለ የወንጀለኛ ቅጣት በሚባለው አንቀጽ መቀጫና ካሣ ፳ብር እንዲከፍሉ ሕጉ ፈርዶ ነበር፤ነገር ግን ለጊዜው ይሆን ፍርድ ለማስፈጸም የቀረቡ የቆንስሉ ወኪል ሙሴ ዛሬራኢዲስ የዚህ ግፍ ዋጋ ከ፲፫ ብር በላይ ከፍ ሊል አይሆንም ብለው በግሪክ ወይም በኤሮፓ ሕግ ያደደለ እንዲሁ በቃላቸው አሻሽለው ፲፫ ብር ቈርጠው ነበር ኋላም ዳኞቹ ያገር ሕግ የማትቀበሉ ከሆናችሁ ይኸን የተቈረጠውን ክፈሉና ነገሩን ወደ ላይ እናደርሳለን ቢሉ ፤ ነገሩ ወደ ላይ የሚደርስ ከሆነ ፲፫ ቱንም ብር አንከፍልም ብለው ደግሞ መልሰው የራሳቸውንም ፍርድ ነቀፈው በኩርፊያ ቈይተዋል ፍትሕ ተገኝቶለት ሕግ ተፈጽሞለት በሆነስ ብርሃንና ሰላም በ፫ኛ ዓመት በቁጥር ፺፭ በ፱፻፳ ገጽ ላይ የግፍ ግፍ ብየ ባልጻፍሁም ነበር።

ደግሞ ሌላው ጠያቂ ይህ ግፍ የተዋለበት ሰውዬ ለጉሽሙ ጉሽም ሳይመልስ ቀረ? ብሎ ስለጠየቀ ይህን የግፍ ግፍ የተቀበለ ሰው ከየዋሆቹ ባላገሮች አንዱ እርሱ ነው።ደግሞም ሰውነቱ የሸመገለ፥ጉልበቱ የተከፈለ፥ሁለንተናው የዛለ ስለሆነ ተጠቃ እንጂ ሌላውስ የማይቀመሰው ወንድ ያደረገውን ሙሴ እ ፒቲርስ ራፖር ያደረጉት ያስረዳናል። ለተጠየቅሁት ጥያቄ መልስ ከሰጠሁ በኋላ ሌላውን ከፍ ያለውን በደል ለመጻፍ ስሞክር ተቈርቋሪው ዘወትር የሚሠራውን ግፍ መላልሶ መስማት ሲበዛበት ግፈኞችን ለመገሠፅና በደልን ለማስወገድ ለክርክር እርሳሱን ቀርጾ ማዘጋጀት ያሰበበው ይሆናል እላለሁ ።

እነሆ ከነዚሁ ወገኖች ጥቂት ሰዎች ተከፍለው ግፍ ለማድረግ ማኅበር የሆኑ ይመስላሉ የቤሎቹን ወደ ኋላ አቈይተን ሙሴ በሎኒያስ ያደረጉትን ላሁን እንድንጽፈው የሚያስፈልገን ነው።አሁን ባለፈው በቅርቡ ሰሞን ከዕለታት አንድ ቀን ሙሴ በሎኒያስ ከቤታቸው እያይዘው አዲስ ሥራ ሲሠሩ ዘበኞች አይተው ይህን አዲስ ሥራ ለመሥራት ፈቃድ ተቀብለዋልን ወረቀት እንዳለዎ ያሳዩን ብለው ጠየቋቸው እሳቸውም መልሰው እናንተ ውሾች ናችሁ ለናንተ ለውሾች ወረቀቴን አላሳይም ልትጠይቁኝም አትችሉም ብለው ለመምታትም ገላምጠው መለሷቸው በዚህም ጊዜ ዘበኞቹ የዘበኝነት ሥራቸውን ለማሳየት ክሰቡ በኋላ በፊት እስኪ ነገሩን ወደ አለቆቻችን እናድርስ ብለው ራፖር አድርገው በመጅሊስ ሙሴ በሎኒያስ ቀርበው ቢጠየቁ እኔ በኢትዮጵያ አገር መጥቼ ከተቀመጥኩ ከ፳ዓመት ይበልጠኛል በዚሁ አገር የወለድሁ የከበድሁ (የከበርሁ) ነኝ ስለዚህ እንደዚህ የመሰለ ጸያፍ የምናገር አይደለሁም እሉ የተከሰሱበትን በደል ክሕደት አደረጉ እንጂ እውነትም ሙሴ በሎንያስ በኢትዮጵያ አገር ነው የከበሩትም ከፍ ከፍ ያሉትም ከዚህ በኋላ ከናንተ በቀር ሌላ ምስክር ታገኛላችሁ? ተብለው ዘበኞች ቢጠየቁ ሌሎችም እዚያው የነበሩ የውጭ ሰዎች እና ስመሰክሩስን ብለው ሦስት ምስክሮች ቈጥረው ምስክሮቹን የሚያስነቅፍ ምንም ምክንያት ሳየመጡ እንዳይመሰክሩና እንዳይረቱቱ ለማከላከያ እውነቱም እንዳይገለጽ ለማሰናከያ ብለው ቢሆን ሙሴ በሎንያስ አልተሳደብሁም ካሉ አለ መሳደባቸውን እሳቸው ምስክር ይቈጥራሉ እንጂ ዘበኞቹ በሥራቸው ላይ ቢሰደቡና ቢዋረዱም እነሱ ተሰደብን ብለው ቢናገሩም የነሱን ቃልና የነሱን ምስክር መቀበል አይበቃም ብለው የታመኑትን ዘበኞች እንዳልታመኑ አድርገው በፍርድ ቦታ ላይ ቆንሲሉ ሙሴ በሎላክስ በመናገራቸው አዘንን ።

ሙሴ በሎኒያስ ያደረጉትን ሐሰት ብለው ስለካዱ የዘበኞቹና የ፫ቱ ምስክሮች ቃል እውነቱ አንድ ላይ ሁኖ ተሰብስበ ቢመዘን በዚህ አካሔድ ያንዱ ግሪክ ክሕደት እውነትና የታመነ ቃል ሁኖ ከሁሉ የሚበልጥ መሰለ ፤ ይህን ግሩም ክርክር በመስማት ዳኞቹ በፍጹም ተደንቀው ራሳቸውን እየነቀነቁ እያንዳንዳቸው በኀዘን እንደ መሳቅ ይሉ ነበሩ። የዚሁ ምሳሌ ዓይነት አንዱ ግሪክ ካንዱ ኢትዮጵያዊ ጋራ ተሟግቶ ምስክር አምጣ ቢሉት የኔ ልጄ፥የኔ ሚስቱ ፤ እኔ ራሴ ብሎ ቈጠረ እያሉን ጨዋታና ቀልድ እንሰማ ነበር ፤ ይህም እንደዚሁ የመሰለ ቀልድ መሆኑ ትዝ ስላላቸው ዲሬክተሩ አቶ በሻህ ውረድ የሚከተለውን ተናግረው ነገሩን አቈዩት።የአውሮፓንም ሕግ እናውቀዋለን ዘበኛ ና ሲለው እምቢ ያለ እንደሆነ አንገቱን ጠምዞ ነው የሚወስደው ደግሞ አንዱ ዘበኛ እንኳ በመሰከረ የዘበኛው ቃል ብቻ ይበቃል እንጂ ምስክር ማምጣት የለበትም አሁን ሙሴ በሎኒያስ አልተሳደብሁም ሲሉ አለመሳደባቸውን ምስክር ቈጥረው ይርቱ ከተባለ በዚያን ሰዓት ከዚህ ቦታ የሌሉትን ሰዎች አምጥተው መስክሩ ቢሏቸው አልሰማንም በሰፈራውም የለንም ብለው ይመሰክራሉ እንደዚህ አድርገው ረትተው ይሔዱ ማለት አይቻልምና ነገሩ ይቈይ ተብሎ በዚህ ምክንያት ቈይቷል

በንጉሠ ነገሥቱ በተሳለ ምልክት በሙሉ እምነት ደምብና ሥርዓትን የሚጠብቅ አምሳለ መንግሥት የሆነው ዘበኛ ክብሩ መታፈሩ ቀርቶ ውሻ ተብሎ ሊሰደብ ላፍ ይቀፋል ለመናገርም ያስከፋል ። ግን ያንደበታቸውን ቈላፍነት ያልተገዘሩ አንዳንድ በኢትዮጵያ ሀብት የተነፉ፥ ንግግራቸው ሁሉ ስድ፥ሥርዓታቸው አለመንገድ ብልሃታቸው፥(ሐሳባቸው) እንደ ገመድ እየሆነ ሁከት በማድረጋቸው ያሳዝናል ።

ግን ግፉን ጽፌ በጋዜጣ ልበቀል ብዬ አይደለምና እውነቱን በግልጽ በመጻፌ ኃፊኞች እንዳትቀየሙኝ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ።

ጅማ ወልደ ገብሬል ።

ለፈራጅ ተጠንቅቆ መመርመር ይገባዋል ።

የምታደርገውን ሁሉ እስተውለህ አድርግ በልብ ሳያስተውሉ በችኰላ ያደረጉት ቈይቶ ጠጠት ይሆናል ። የ፲ሙም ምሳሌ በብርሃንና ሰላም መጀመሪያ ዓመት ፶፩ኛ ቍጥር ገጽ ፪፻፵፰ ለጻፍሁት ተከታይ ነውና ከዚህ በታች የተጻፈውን ያለመሰልቸት እንድትመለከቱልኝ እለምናለሁ።በምሥራቅ አገር ፩ ከበርቴ ሰው ሃይማኖተ ፅኑ፥እግዚአብሔርን የሚፈራ፥ ከክፉ ነገር ሁሉ የራቀ ነበረ ። ሚስቱም ደግ ሴት ነበረች ይባላል አንዲት ሴት ልጅ ብቻ ወልደው በእግዚአብሔር ፊት ያለነውር የሚሔዱ ነበሩ ። ሁልጊዜ በጾምና በጸሎት እግዚአብሔርን ብቻ የሚአገለግሉ ነበሩ ይህ ጻድቅ ሰው ከሚስቱና ከአንዲት ልጁ ጋራ በመልካም አኗዋወር ሲኖሩ ሰይጣን ካንድ ጉልማሳ ጐበዝ ልጅ ጋራ ሁኖ ፈተናቸው። አፉን አለስልሶ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ተናገረ ፡ ጌታዬ ሆይ ብዙ የእጅ ሥራና ጥበብ አውቃለሁና በጉልበቴ እያገለገልሁ የሚበቃኝን ገንዘብ እንደቸርነትዎ ይመዝኑ እየሰጡኝ ደስ ላሰኝዎ እለምናለሁ እያለ ለመልካሙ ጻድቅሰው ነገረው መልካሙም ጻድቅ ብዙ ደስ አለውና ይሁን ልጄ ለወር የሚበቃህን ይኸን ያህል ገንዘብ እሰጥሃለሁ ብሎ ነገረው ። ያ ክፉ መንፈስ ያለበት ጐልማሳ ልጅ አሽከርነት እንደተቀጠረ ስምህ ማነው ብሎ ጻድቁ ሰው ጠየቀው ። አሽከሩም ስሜ እኔ ይባላል ብሎ መለሰ አባትና እናቴ ያወጡልኝ ስም እኔ ነው ። ሁለተኛ ጥቂት ቈይተው ሚስቲቱ ስምህ ማነው ወዳጄ ብላ ጠየቀችው ክፉ መንፈስ ያለበትም ሎሌ እመቤቴ ስሜ እርሳቸው ነው ብሎ መለሰላት ሰው ሁሉ እርሳቸው እያለ ይጠራኛል አለ።ውለው አድረው ልጂቱ ስሙ ማን እንደሆነ ጠየቀችው ሎሌውም መለሰ ስሜ አባቴ ነው በሀገሬ አዋቂውም ልጁም አባቴ ይለኛል አላት ከዚህ በኋላ ያንን ክፉ ሎሌ ጌታው እኔ፥ሚስቲቱ እርሳቸው፥ ልጂቱ አባቴ እያሉት ተቀመጡ ። ነገር ግን ፩ወር ያህል እንደተቀመጠ እንደልጅ በቀለበት እንደድመት በወተት እንደሚሉ በማባበያ እሺ አሰኝና ያችን ልጅ አስነወራት ልጂቱም አድጋ ነበርና በቶሎ ፀነሰች ሰውነቷ እየሞላ፥ ሆድዋ እየገፋ ስለሔደ አባትና እናቷ ተጠራጠሩ ምናልባት ፀንሳ ይሆን ? እያሉ ይጨነቁ ነበር ። ከዚያ ወዲያ ፫ወር ያህል ቈይተው መፅነስዋን ደኅና አድርገው ባወቁት ጊዜ አጥብቀው ደነገጡ ብዙም አፈሩ ። አጥፊው ሎሌም ማፈርና ድንጋጤአቸውን አይቶ በፊታቸው ቁሞ እንዲህ ብሎ ተናገረ ። የተወደዳችሁ

ጌታዬና እመቤቴ ሆይ የእናንተን ደግነት የሃይማኖታችሁን ፅናት አይቶ በዚች ልጃችሁ ደረስሁባትና ፀነሰች አሁን ለኔው ስጡኝና ልጃችሁን አግቡኝ እየታዘዝኋችሁ ልቀመጥ አላቸው አባትና እናትም መቸስ ምን ይደረግ ፩ጊዜ የሆነ ሁኖአል ፈቅደንልሃል አሉት ሎሌውም ያችን ልጅ በለሰጡት ሚሚ-ቸውን ሳመና በጐጀው ከልጂቱ ጋራ ተቀመጠ ። ያክፉ መንፈስ ያለበት ጐልማሳ አንድ ወር ያህል እንደተቀመጠ በስ ድስተኛው ወር የአገር ሽማግሌዎችና ዳኛው አንድነት ተሰብስበው ሲጫወቱ ሔዶ አጠገባቸው በደረሰ ጊዜ ጌቶቹ ሰላም ለናንተ ይሁን አላቸው ሽማግሌዎቹና ዳኛውም መለሱ አሉትም ወዳጄ የፈጠረን አምላካችን ደብርክህ የዚያ የጻድቅ ሰው ሎሌ የአንተን ጌታ የመሰለ መልከም ባለሃይማኖት ሰው በዓለም ሁሉ ይገኝ አይመስለንም አሉት ። ሎሌውም እንዲህ ብሎ መለሰ እናንተ እንደመሰላችሁ ደግሰው ባለሃይማኖት ነው እያላችሁ ታወራላችሁ እርሱ ግን የወለዳትን ልጁን አስረግዟል ሃይማኖት ያለው ሰው ልጁን ያስረግዛልን እያለ ተናገረ ሽማግሌዎቹና ዳኛውም አጥብቀው ደነገጡ ክፋውንም ሎሌ ልጁን ማስረገዙን ማንይመሰክርልሃል አሉት አሽከሩም ጌታዬ ራሳቸው ። የጌታዬ ሚስት ይህች ልጂቱ እኒህ ሦስቱ ነየብቻቸው ይመርመሩና ነገሬ ሐሰት የሆነ እንደሆነ ልሰቀል ብሎ ተፈጠመ ከዚህ በኋላ እነዚያ የአገር ሽማግሌዎችና ዳኛ በፍጥነት ያንን ጻድቅ ሰው ጠርተው ልጅህ ከማነው ያረገዘችው ብለው ጠየቁት ጻድቁም ሰው ከኔ አለ ፡ ደግሞ እናቲቱን ይህች ልጅሽ እስከሁን ድረስ ሳታገባ በድንግልና ነው የተቀመጠች አሁን ከማን ፀነሰች አሏት ከርሳቸው አለች። ልጂቱንም ከማነው ያረገዝሽው እስቲ እውነቱን ንገሬን አሏት ልጂቱም ተአባቴ ነው ያረገዝሁት ብላ በተናገረች ጊዜ ነገሩን ሳይመረምሩ ዳኛውና የአገር ሽማግሌዎች ያንን ጻድቅ ወስደው ሰቀሉት በተሰቀለበትም ዕንጨት ላይ ወንጀሉን ጽፈው በራሱ አጠገብ ከቀኝ ወገን ለጥፈውት ነበር ጽፈቱም እንዲህ የሚል ነበር ይህ ነው የወለዳትን ልጁን ያስረገዘ ። የአገሩ ሕዝብ ሁሉ እያነበበ ይደነቅ ጀመር ። የሚአውቁትም ያዝኑ-ለት ነበር ከዚህ በኋላ የሀገር ሽማግሌዎችና ዳኛው ያንን ሎሌ ጌታው እኔ እመቤቱ እርሳቸው ልጂቱ አባቴ እንደሚሉት ተረዱና ያንን ንጹሕ ጻድቅ ሰው በከንቱ ስለሰቀሉት ዕንባ ለዕንባ ይራጩ ጀመር ነገር ግን ያሰው ሙቷልና ማዳን አል-ቻሉም ፩ቀን በሳቱ ዓመት ይፀፀቱ የተባለው ምሳሌ ስለዚህ ነው ያአታላይ ክፉ መንፈስ ያለበት ሰው የአፉን ንግግር እንደማር አጣፍጦ ሐሰቱን እውነት አድርጎ ጻድቁን አስገደለ ጃኖና ፈራጆችንም አሳተ ። በመጨረሻ አሰቱ ተገለጠበትና እሱም ተሰቀለ ። ዳሩ ግን ምንይሆናል ጻድቁ በከንቱ ሙቷልና ያሽከሩ መሰቀል ፈራጆቹን ደስ አላሰኛቸውም ባለመመ ርመራቸው እጅግ አሳዘናቸው ። ጌቶቼ ወንድሞቼ ሆይ እግዚ አብሔርን የፈጠረንን መፍራት ትልቅ ጥበብ ነው ። ከኃጢአ ትም መራቅ ማስተዋል ነው ። ኢዮብ ም ፳፰ ቍ ፳፰ ተመ ልከቱ ።

ሐ ዓ አ ሸሪፍ አፈንዲ።

የተሳሳተውን መግለጫ ።

ባለፈው ብርሃንና ሰላም ለሕፃናቱ የጂኦግራፊ ትምርት የሚረዳ ጽፌ ነበር አሁንም ከዚሁ የተሳሳተውን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አስታውቃለሁ ።

አሜሪክ (ኤታዡኒ)

የሕዝቡ ቁጥር ፻፳፪ ሚሊዮን ፯፻፴ሺ.

የፊንላንድ መንግሥት

ያገሩስፋት ፫፻፹፫ሺ. ፪፻፹፱ ኪሎ ሜትር ካሬ

ሊቤሪአ ።

ያገሩ ስፋት ፺፭ሺ. ፬፻ ኪሎሜትር ካሬ ።

ባለፈው ዓመት ለጦርነት ጉዳይ ያወጡት ገንዘብ ፫ሚሊዮን ፪፺፩ሺ. ፯፻፺ ፍራንክ ።

የፖሎኝ መንግሥት ።

ያገሩ ስፋት ፫፻፹፰ሺ. ፫፻፺ኪሎሜትር ካሬ ።

ነ አፈወርቅ ገ ዘብሔረ ዘጌ

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአበክትነት ሥራ ይሠራሉ በአ ገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክአገር የፍርድ ቤትብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ናቸው።ለዚሁም አበክትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃ ቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮ አቸው በፎሮንድ ዘለቀ አግደው ግቢ ነው ። ወደሳቸው የሚ መጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፯ት ሰዓት ይቀበላሉ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሴንጀር ከቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፭ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላኒዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ. አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚሀ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ሳንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርደና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጲያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የከትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትክል የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኩላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቴክ ኬዎርኪፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM

በያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብረል።

ፔር ዳኒይ ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኪልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጪ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፌ ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልቡ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ግቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፰
8me ANNE. № 8

ሐሙስ የካቲት ፲ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።
JEUDI 18 Fevrier 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ከጂቡቲ ወደ አዲስ አበባ በደኅና መመለስ።

አስቀድመን እንዳስታወቅናችሁ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ግርማዊት እቴጌ መነን፥ከልዑላን መሳፍንትና ወይዛዝርም ልዑል ራስ ኃይሉ፥ልዑል ራስ ሥዩም፥ ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ዐፀደ አስፋው ጋራ፥የጃንሆይ የወንድማቸው ልጅ ወይዘሮ የሻሸወርቅ ይልማ፥ከሌሎችም መኳንንትና ወይዛዝር ጥቂቶች ነበሩ ።

ከጂቡቲ ተመልሰው የየረር ጎታን ፍልውኃ አይተው የጨርጨርን ከተማ ዓሰበ ተፈሪን አይተው በየካቲት ፲፩ቀን ጧት ይገባሉ ተብሎ ከተማው ተዘጋጅቷል ። ወታደሩም ከባቡር መቆሚያ ጀምሮ እስከ ታላቁ ግቢ ድረስ መኳንንቱና ወታደሩ በሥርዓት ተሰልፎ ቁሞ እንዲቀበል የመንግሥቱ ዋና አጋፋሪ ከልከሌ ቦታውን አከፍለው አደራጅተዋል።የነገን ቀን ለማየት የከተማው ሰው ሁሉ ጐምጕጉቷል በደኅና ለመግባት ያብቃልን እያለ ብርሃንና ሰላምም ምኞቱን ያቀርባል።

በክብር መመለስ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ሮፓን ዞረው አይተው የክብር ክብር ተቀብለው በየካቲት ፬ ቀን ከማርሰይ ከተማ ወደ ኢትዮጵያ ሊመጡ በታላቁ መርከብ ዠኔራል ሚት ዚንጀር በሚባለው ተሳፍረው ጕዞ ጀምረዋል። በየካቲት ፲፬ ቀን ጂቡቲ ይደርሳሉ በደኅና ወደ አገራቸው ያድርስልን እያለ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ይገልጻል ።

የሚያስደንቅ ትጋት ።

የመርዕድ አዝማች አስፋወሰን እንደራሴ ክቡር ደጃዝማች ወዳጄ እጅግ ያማረ አዲስ ቤት በኖራ አሠርተው አስለስነው አስከደነው በጥቂት ጊዜ በመጨረሳቸው ትጋታቸውን ያየ ሁሉ አመስግኖአቸዋል ። የጌታውን መምጣት ተዘጋጅቶ በትጋት የሚጠብቅ ምስጉን ነው የሚለው ቃል ዛሬ በክቡር ደጃዝማች ወዳጄ መታየቱ እጅግ ያስደንቃል ።

የአይሮፕላን አደጋ።

ሙሴ ኮርጂ ፡ የአይሮፕላን ነጂዎች አለቃና የመኪናው ተመልካች ሙሴ በለዲ ወደ ጂቡቲ በአይሮፕላን ሔደው ሰንብተው በየካቲት ፭ ቀን ቅዳሜ ከጧቱ በ፫ ሰዓት ተኩል ከጂቡቲ ተነሥተው አዲስ አበባ ደረሱ ወዳጆቻቸውና ወገኖቻቸውም ደስ ብሏቸው ተቀበልዋቸው ። መቸም የዚህ ዓለም ደስታ አይፈጸምምና ከ፮ት ሰዓት በኋላ ተመልሰው በዚያው በመጡበት አይሮፕላን በ፱ሰዓት ወደ ጂቡቲ ሲወርዱ ገና ጂቡቲ ሳይደርሱ ከመንገድ አይሮፕላኑ ተሰናክሎ ከመንገድ ወደቀ።አይሮፕላኑ ተጐድቷል እንጂ ሰዎቹ ድነዋል ምንም ገንዘብ የሰው ነፍስ ቢሆን እንኳን ሰዎቹ ዳኑ እንጂ ይህን ያህል ገንዘብ ለመንግሥት ጕዳት መስሎ አይታየንም ።

የእቴጌ ጣይቱ መታሰቢያ ።

እቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ ለሀገራቸው ብርቱ ተከላካይ ዘበኛ እንደነበሩ የዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች መስክረዋል ። ነገር ግን ሞት የሚባል የማያደላ ዳኛ ነውና ጅግናውንና ደከማውን፥ብልሁንና ደንቆሮውን በየጊዜው የሚጠራ ስለሆነ እቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ ከሞቱ እነሆ ዛሬ ፲፬ኛ ዓመት ሆናቸው ። የሞቱበትም ቀን በየካቲት ፩ቀን በሺ፱፻፲ ዓመተ ምሕረት ነበረ ። ከሞቱ ጀምሮ በየዓመቱ መታሰቢያ (ተዝካር) ይደረግላቸዋል ። ዛሬም የካቲት ፩ቀን ዓርብ ስለነበረ በየካቲት ፫ቀን ቅዳሜ በታላቁ አዳራሽ ታላቅ ግብር ሁኖ ዋለ።በከተማ ካሉት አድባራት ያሉትና በከተማው ዙሪያ ባሉት አድባራት ያሉ ካህናት ተሰብስበው ነበረ።ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ ግርማዊት እቴጌ መነን አስቀድመን እንዳስታወቅነው ነፋስ ለመለወጥ ወደ ጂቡቲ ሔደው ነበሩና ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትር፥ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል የግቢ ሚኒስትር፥ ቢትወደድ ጌታቸው የአገር ግዛት ሚኒስትር የቀሩትም ታላላቅ መኳንንት ሁሉ በሥርዓት ተቀምጠው ካህናቱን ጋበዝዋቸው ። እቴጌ ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ ምንም መካን ቢሆኑ የሀገራቸው ፍቅር እጅግ ደፀናባቸው ነበርና ስለዚህ መታሰቢያቸው ለዘለዓለም ይኖራል።

ሰው ሁሉ አገሩን ይወዳል ። ነገር ግን እንደ አፄ ቴዎድሮስ፥ እንደ አፄ ዮሐንስ፥ እንደ እቴጌ ጣይቱ ፤ እንደ ራስ አሉላ የአገሩን ፍቅር የገለጠ ደገኛ አይመስለኝም።እንደነዚህ መታሰቢያውን ባገሩ ላይ ያስቀረውን ሰው ሞተ ማለት ያፍ ልማድ ነው እንጂ ሲመረምሩት በእውነት ሞቱ ያልነው ሰው እንደ ዓለም ልማድ ሞተ ብንል ስሰሕተት ይቈጠር መስሎ ይታያል

ስለሁለት ሽፍቶች ነገር ።

እነዚህም ፪ሽፍቶች በጫካ በደን ውሥጥ ሳይሆኑ ሜዳ ለሜዳ ሲዞሩ አለመጠየቃቸው ስላገረመኝ ነገሩን ለተመልካቾች አከፍላለሁ በሐረር አውራጃ ከኢቱ በታች እስከ ጅጅጋ ድረስ መጣጢስና ጫት የሚባሉ አሉ እነሱንም የሚተክል ሰው ለመልከኛው ያነኑ የሚገባውን ግብር ይሰጣል እንጂ ለመንግሥት ስለዓሥራት አንድም ቁና እህል አይሰጥ እነዚሁንም ጫትና መጣጢስ የሚተክሉ ሰዎች ፪ና፫፻ ዳውላ ያህል የሚያወጣውን የገበር መሬት በሙሉ እየተከሉ የመንግሥት ገቢ ይከላከላሉ።ለነሱ ጥቅም ግን ጫቱና መጣጢሱ ፬ና፭፻ብር ድረስ እያንዳንዳቸው ይሸጥዋቸዋል ለምግባቸውም ሙቼም እህል የሚዘራ ለመንግሥት አገልጋይ አንዳንድ ሰው አይጠፋምና ከዚያ እየሸመቱ ይበላሉ።በዚሁም ባልነው አገር ውሥጥ ከእህል ገበሬ የጫትና የመጣጢስ ገበሬ በልጧል ወደፊት ግን ከ፫ና ከ፬ዓመት በኋላ እህል ጠፍቶ ጫትና መጣጢስ ብቻ መሆኑ አይጠረጠርም።እንዲህ ቡና አይደሉ አይቀረጡ፤እህል አይደሉ ዓሥራት አልወጣባቸው እንዲያው በሜዳ ሙሉ እየተስፋፉ አንድ ነገር ሳይረዱ መንግሥት ስለጉዳ ማስታወቂ ነው እንጂ በጭራሽ ከገር ይጥፉ ማለቴ አይደለምና የሚገባቸውን ፍርድ እንድታደርጉላቸው ለተመልካቾችና ለደምብ አውጭዎች አመለክታለሁ ።

የብርሃንና ሰላም ደጅጠኚ ደስታ ሙሴ።

ከመልክም ሽቱ መልክም ስም

ምንኛ የታደለ ሰው ነው በዚህች በጭር ዘመኑ ነዋሪ ስም ተክቶ የሚሔድ ነዋሪ ስምስ መተው የሚችል እንዴት ያለ ሰው ነው።አሁን ነዋሪ ስም የምለው ሥራው ለዘለቃ ሁኖ ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ መሥራት ነውና ብዙዎች ከአንባቢዎች ይህን መሥራት የሚችሉ ሀብታሞች ወይም ባለ ማዕርግ ሰዎች ብቻ ናቸው ብለው የሚመልሱልኝ አይታጡም። እውነት ነው የዚህ ዓለም አንደኛ መሣሪያው ገንዘብ ነውና የሚበልጥ ጊዜ እነርሱ የሚሠሩት ይበልጣል።ነገር ግን አገርን ለማገልገል የተሰጠ ለሁሉ ነው ሁሉም በየዓቅሙ እስከል ድረስ አገሩን ሊረዳ ይገባዋል። ፈቃድ የሚባል ማንም የማያግደው ኃይለኛ መሣሪያ ከያዘ ማናቸውም ሰው ለሀገር ጥቅም ያለው ሥራ እንደሚሠራ ለማስረዳት ከዚህ በታች የሚከተሉትን ትንንሽ ታሪኮች እጽፋለሁ።

እንደምታውቁት ከኤሮጳ አንድ ክፍል ሆላንድ የተባለ አገር እንዳንዱ ቦታ ላይ ከባሕሩ በጣም ይዘቀዝቃልና የባሕሩ ሙላት ባገሩ ላይ እየፈሰሰ ቤታቸውንና እርሻቸውን እየናደ ሲያስቸግራቸውና ሲያጠፋባቸው ይኖር ነበር ከላይ እንዳልኩት ፈቃድ ካለ የማይሞከ ነገር የለምና ሕዝቡ በብዙ ድካም የባሕሩን ዳር ዳር እጅግ ስኑ የሆነ ግምብ ገብተው ከደጋው ለመዳን ችለው ተቀምጠዋል(ስለዚህ ዲዩስ ማሬ ባታቢስ ሊተራ ፌሲት የሚል የላቲን ምሳሌ አለ)ይህም እግዚአብሔር ባሕርን ፈጠረ፥ ሆላንድ ባሕርን አገደ ማለት ነው።

ከዕለታት አንድ ቀን እንደ ያሥራ አምስት ዓመት ልጅ ብቻውን ወደ ባሕሩ ዳር በጥዋት ሐዶ ሽርሽር እያለ እግምቡ አጠገብ ሲደርስ በንዱ በኩል ግምቡ ውኃ ሠርፆበት የመናድ ጊዜውን ሲጠባበቅ አየው ይህ ብቻ አልነበረም በግምቡ መካከል አንዲት ትንሽ ቀዳዳ አብጅታ ስትንቈረቈር አየ ልጁም ብልህ ነበርና ይህ ግምብ የተናደ እንደሆነ ቤተ ሰዎቹ አገሬ ሁሉ መጥፋታችን ነውና ምን ብደርግ ይሻለኝ ይሆን እያለ ያስብ ይተክዝ ጀመር፡ወደቤት ተመልሶ ሊናገርም አሰበ ነገር ግን እቤት እስኪደርስ ድረስ ቀዳዳው እንዳይሰፋ ፈራና የተቻለውን ያህል እንዲሠራ ቈረጠው እንዳሰበና አልቀረም ወደ ግምቡ ቀርቦ እጁን በላዩ በውል ጨቍኖ ያዘና በገዛ ግቱ ዘግቶ ነጠብጣቡን ለማቋረጥ ቻለ። ግን ጊዜው ብርድ ነበርና ሰዓቱ እያለፈ ሲሔድበት ጊዜ እጁ እየደነዘዘ ሔደ እንዲህ የሚል ሐሳብም ያዘው አሁን ትቸው ብሔድ ተንዶ ሕዝቡን ሁሉ ያጠፋል እኔም እንዲህ ሁኜ እንዳልገፋው ረዳት ካልደረሰልኝ አልችልም ቀዝቃዛውም ሰውነቱን ጕዳኝ እያለ ሥራውን ሳይፈታ ሐሳቡን ብቻ ያወጣ የወርድ ጀመር በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር ሰው ወዲህ እንዲመጣ ቢያደርግ ያደርጋል በተቀር ግን ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ እኔ አስቀድሜ ብጠፋ ይሻላል ብሎ መረጠና ባትዕግሥት ዝም ብሎ ያዘ። አሁንም ሰዓቱ እያለፈ ጉልበቱ እየራደ ሔደ እጅግም ሰነፈ በሰዶምና በገሞራ ጊዜ ለአብርሃም የተለመነ አምላክ ቅን ሐሳብ ላላቸውና የሰውን ደኅንነት ለሚያስቡ ይረዳልና ከቤተ ሰዎቹ ሁለት ሰዎች ሲፈልጉት ውለው አሁን ወዳለበት ቦታ ደረሱ ይህን ጊዜ እንዱ እርሱን ሲረዳ ቈዬ።ሁለተኛው ግን ቶሎ ወዳገር ሔዶ የሀገሩን ሰዎች ሰብስቦ መጣና ልጁን አሳርፈው ግንቡንም አጠነከሩ።

ልጁም ብዙቀን ታሞ ከተነሣ በኋላ ነፍሱን ስላገሩ መሥዋዕት አሳልፏልና በሀገሩ ብቻ ሳይሆን በመላ ዓለም እጅግ ክብር አገኘ ስሙ በታሪክ ስለተጻፈም ይኸው አገሩን ለሚወድ አርአያ ለመሆን በቃ ።

ደግሞም አንድ ጊዜ አገሩን በጦር ከሚሸዋት ባዕዳን ከተማ የሚቀመጥ አንድ ድኃ ነበረ። ይህ ደካ ደኃ በሚኖርበት አገር ንጉሡ አማካሪዎቹን ሰብስቦ እንዲህ አላቸው ጠላቶቻችንን አገኘናቸውም አጣናቸውም ዛሬ ነው ሁለት ሳምንት የሚያህል ከቤት የማይወጡበት በዓላቸው ይኸው ደረሰ ንጉሡም ስለበዓሉ ምክንያት ሠራዊቱን ያሰናብታልና ጊዜ ሳያልፍ አሁን ሔደን አደጋ እንድንጥልባቸው ትፈቅዱ እንደሆነ አስታውቁኝ እነርሱም ቀን በሐሳብ ሌሊት በሕልም የሚታያቸው ነገር ነውና ወዲያው ደቂቃ ሳይቈዩ እስከ ሦስት ቀን አገሪቱን እጅ እንዲያደርጉዋት ለንጉሡ ምሉ ተስፋ አበረከቱ ።

ያ ተጨንቆ በሰው አገር የሚኖር ስደተኛ ባገሩ ላይ እንዲህ ያለ አደጋ እንደመጣበት በምሥጢር ከሥራ ቤቱ ሰማ ሰውዬው

ከገሩ ወጥቶ በዚያ የተሻለ ኑሮ ይኖር ነበርና በነገሩ እጅግ ተጨንቀ አሁን እኔ ከአገሬ የበለጠ በዚህ ተመችቶኝ እኖራለሁ። የሔድሁ እንደሆነ ይዘው ቢገድሉኝ ወይም ቢመልሱኝ ይህችን ያሁንዋን እንጀራዬን አጣለሁ የቀረሁ እንደሆነም አገሬ ከበዕድ በታች ሁና መቅረትዋ ነው ምን ባደርግ ይሻለኛል ይሆን እያለ ሲያወላውል የሀገር ፍቅር የምትባል ሰውነት ስለ ሀገር መጦት ለሰው ክብሩ ማስትዋን አስከትላ በቅጽበት ዓይን አቋርጣው አለፈች፡እርሱም ወዲያው ተፋጥኖ ተነሣና ተከታተላት ሰው እንዳያየውም መንገዱን ትቶ ዱሩን እየጣሰ ቀንና ሌሊት ሳይለይ እህልና ውኃ ሳይቀምስ የአራቱን ቀን መንገድ በተነሣ በሦስት ሰዓት ደረሰ በጠላቶቻቸው ዘንድ የተመከረበቸውን ክፋት ሁሉ ለንጉሡ አደረሰ ንጉሡም በሽሽግ ተሰናዳ ሠራዊቱንም አስከተተ ከዚህ በኋላ ደጉን ሰውዬ አስጠርቶ አገርህን በደምህ ገዝተህታልና ማዕርግ ያንተ ነው ብሎ ደስ አሰኘው ። ጠላቶቹም ንጉሡ እንደሰማ በወቅ ጊዜ በመመከታው ተጸጸቱ፡አፈሩም፤ ሊሆን የነበረ ነገር በምክንያት ሳይሆን ቢቀር ሊሆን እንደነበረ አድርጎ ሰው አይረዳውም እንጂ ይህ ታማኝ ሰውዬ ባይኖር አገሪቱ ትጠፋ እንደነበረች አይጠረጠርም ነበር ።

ጊዜ እንዳይወስድብን እንተወዋለን እንጂ የሴቶችም ሳይቀር ብዙ አርአያ የሚሆን ታሪክ እንጽፍ ነበር።ይህን ሁሉም ማለቴ ሰው ሁሉ በተሰጠው ዓቅሙ አገሩን ማገልገል እንዲገባው ና ፈቃዱ ከሆነ ሁሉም ማገልገል እንዲችል በቀላል ማስረዳቴ ነው ።

እንባቢዎች ሆይ ፤ አገራችንን ከፍ ወዳለው ደረጃ በፍጥነት ለማድረስ ኃይለ ሥላሴን ጋሻ አድርገን ሀብታም በሀብቱ ድኃ በጕልበቱ እንረዳ ይልቁንም አሁን ከተልልቆች ወገኖቻችን የደግ ንጉሣችንን ሐሳብ ተከትለው በመላ ኃይላቸው ስለሀገራቸው የሚደክሙ እናያለን ።

ለምሳሌ ፦እንባቢዎችም አትስቱትም ክቡር ፊታውራሪ ብሩ አገራቸውን ለማገልገል በጭር ታጥቀው እንደተነሡ በልዩ ልዩ በታ የሠሩት ጥቅም የመላፎት ሥራቸው ያስረዳል። ከብዙው ጥቂቶችን ለማሳሰብ ከዚህ በታች አመለከታለሁ።

፩ኛ፥ ለኢትዮጵያ ልጆች የዕውቀት ምንጭ የሚፈልቅበት፡ የተፈሪ መኰንንን ትምህርት ቤት ለመጕብኘት ብዙ ጊዜ ሲመላለሱ በመጡበትቀን ቍጥር ብዙ ገንዘብ ለትምህርት ቤቱ እንደረዱ ተጽፏል ።

፪ኛ፥ ክቡር ፊ ብሩ በሚገዙት አገር ውስጥ በብዙ ክሳራ ከውጭ አገር ሐኪሞች አስመጥተው ሆስፒታል አቁመው የሕዝብ ጤና እንዲጠበቅ አድርገዋል ። ፫ኛ፥ እንዲሁም የተማሩ ኤውሮፓውያን አስተማሪዎች አስመጥተው ትምህርት ቤት ከፍተው የአውራጃቸውን ሕፃናት በዕውቀትና በጥበብ ያጐለምሳሉ ይህም ላገራቸው ጣሪ ለሕዝባቸው ተቈርቋሪ መሆናቸውን ያረጋግጥልናልና ለሀገሩ የሚጥር ለሕዝቡ የሚቈረቈር ሰው በዚህ ዓለም ከስም በተቀር ደመወዝ አይገኝለትም ማዕርጉም ከሁሉ ከፍ ያለ ነውና የንጉሣችንን ሐሳብ ተከትለው ለዚህ ሥራ ፈላጊ ሁነው በመገኘታቸው እጅግ ደስ ያሰኛል ። ፬ኛ፥ ባለፈው ጊዜ እኛ ትያትር ስናሳይ ትርፍ ገንዘብ ቢገኝ ለአገር በሚጠቅም ሥራ እናውለዋለን ስላልን በፊተኛው ፻ብር በሁለተኛው ፶ ብር መቶ አምሳ ብር እርዳታ ሰጡን ።

ይህን ሁሉ መሥራታቸው ከላይ እንዳልሁት አፍአዊ ያልሆነ እውነተኛ ውሣጣዊ የሀገር ፍቅር ቢያድርባቸው ነው እንጂ አበክሉ ድረስ ገንዘብ መሰብሰብ እንደሚያስመክ ዘንግተውት አይደለም።እውነተኛን የሀገር አገልግሎት የሚጠብቅ ሰው እንደዚህ በጋዜጣ ተጽፎ የሚልቅ አይደለምና ለሚመጣ ትውልድ ነዋሪ በሚሆን የታሪክ መጽሐፍ ሥራቸው ሁሉ በዝርዝር እንዲጻፍ እየታመንሁ በዚያ ቀን ችሮታ ያደረጉልንን ጌቶቻችንንም ከዚህ በታች አመለክታሁ ።

ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው ፺ብር

ክቡር አዛጋር ወርቅነህ ከብዙ ወርቅ ከሚመረጥ ምክራቸው ጋር ፶ ብር

ክቡር ከንቲባ መኰንን ፳ ብር

ከሰውዬው ይልቅ የሠራው ወይም ያሠራው ሥራ የሚበልጥ ዕድሜ ይኖራልና ለሰው ስሙን የሚያስጠራ ነዋሪ ጥቅም መተው መጀመሪያ ዕድል መሆኑን ቢረዳው በየዓይነቱ መታሰቢያ ለመተው ይቀዳደም ነበር።ኢትዮጵያውያን ሆይ ይህን ነገር በተለየ እኛ በጣም ዘንግተነዋልና ሩቅ ከለ መቻል አለ የሚቻል ምሳሌን ተመርኵዘን ስማችንን እስከ ኅልፈተ ዓለም በታሪክ ለማስጻፍ እንጣጣር።

ሰሎሞን ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ይበልጣል ብሎዋልና ።

ገብረ ኦብ ቢያድግልኝ በተፈሪ መኰንን ት ቤት ተማሪ ።

ግርማዊ ንጉሥ ነቀ ኃይለ ሥላሴ ከዘሩት አንዱ አፈራ

አያና ብሩ በሐያ አራት ዓመቱ ሁለት የማይሞቱ ሥራዎች ሠራ ።

የኢትዮጵያ ልጆች ንቁዎች ለአገራቸው አሳቢዎች መሆናቸውን የሚክድ ሰው ያለ አይመስለኝም ። ባለፉት ዘመናት ኢትዮጵያን ወደ ኋላ ያስቀሩት የልጆችዋ ስንፍና አይደለም ነገር ግን በአሁኑ ዘመን ሰዎች አዲስ ነገር ለማግኘት እንደሚጥሩ ባለፈውም ዘመን እንደሁ ድንበራቸውን ለማስፋት ሃይማኖታቸውን ለማጽናት ይዋጉና ይሞቱ ነበር ። እንዲሁም ኢትዮጵያ መጀመሪያ ድንበርዋን ለማስፋት ቀጥሎም መንግሥቷን ለማጽናት ስለነበረባት የሥልጣኔመንገድ ለመያዝ ጊዜ አላገኘችም ነበር ።

ኢትዮጵያና አዲሱ ሥልጣኔ ።

ከአፄ ቴዎድሮስ መንግሥት አንሥቶ እስከአሁን ድረስ ኢትዮጵያ አንገቷን ወደሥልጣኔ መልሳለች ሥራዬም ብላ የያዘችው ከአፄ ምኒልክ አንሥታ ነው ይሁን እንጂ በሠላሳ ዓመት ውስጥ የተራመደችው በጣም የሚያኰራ ነው አፄ ምኒልክ ወደ አውሮፓ ነገሥታት የጻፉት ወረቀት እንደዚህ ይላል ኢትዮጵያ በአረማዊ ባሕር ውስጥ ያለች የክርስቲያን ደሴት ነች ።

እነሆ በአፍሪቃ ክፍል የሠለጠነ ጎረቤት ስለሌለን ልንፈክክር አልቻልንም አውሮፓን ዛሬ የዓለም ሥልጣኔ መሪ ያደረገው የሕዝቦቹ መፈክክር ነው በውሮፓ ክሉት እገሌ ነው በብዙ ለሥልጣኔ የረዳ ለማለት አይቻልም ስለምን ሁሉ እንደዓቅሙ ረድቷልና።አንድ አገር የጀመረውን ሌላው ያሻሽላል የቀረውንም ሥራ ያሊዘዋል። ነገር ግን በኛ ክፍል የጀመረም አልተገኘም የተከተለም የለም ከተፈጥሮዋ ክፍላችን ለምለምና ሰፊ ስለሆነች ሕዝብዋ ችግር አልነበረበትም ከመፍለስም የሚያደርሰው ደግሞ ችግር ነው ሰንጠረጋርና ገበጣ የተፈለሰፉት በወሕኒ ቤት መሆኑ እሥረኞቹ የሚጫወቱት ጨወታ በማጣትና በመቸገር ነው ።

አያና ብሩ አኰራን።

ኢትዮጵያ ልጆቿን ታስተምራለች ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ለመድረስም ትጣጣራለች እያሉ ብዙ ሰዎች ሲጽፉ አይቻለሁ ግን ከተማሩት ይህን አደረጉለት ሲሉ አልሰማሁም እነሆ የምስራች ያገሬ ልጆች አያና ብሩ ለኢትዮጵያ ትልቅ ነገር ሠራ።

የዛሬ ሰባት ዓመት አያና ብሩን እንዲማር ወደ ግብፅ ሰደዱት እዚያ እንደሚገባ ከተማረ ወዲህ እንግሊዝ አገር መጥቶ የወርቅና የብር መሐንዲስነት ይማራል ጠባዩና እውቀቱ የተከከሉ መሆናቸው ተመስክሮአል። አሁን ገልጸዋል ከዚህ ቀጥዬ እናገረዋለሁ።ግን ሥራውን ሳልጀምር ሌላ ላገሩ የሠራውን አስቀድሜ መናገር እወዳለሁ።በዚህ አገር ያሉ ዩኒቬርሲቲዎች የኛን ቋንቋ አንቀበልም ብለው ሲኖሩ ነበር ነገር ግን ነገሩን ገንዛኖት ኢትዮጵያ የሠለጠነች ታላቅ መንግሥት ናት ከዚህም በላይ ያለም መንግሥት ማኅበርተኝነት አላት ቋንቋዋን ለምን አትቀበሉም ብሎ ቢጠይቃቸው ምክር ይዘው በሦስተኛው ቀን መቀበላቸውን አስታወቁ።አለጥርጥር ታላቅ ነገር ነው ስለምን ቢሉ የኢትዮጵያ ልጆች ለመማር ወደ አውሮፓ ሲመጡ ሁለት ሦስት ቋንቋ ለፈተና ሲያቀርቡ አንዱን አለችግር ያቀርባሉ ።

እኔም እንደዚሁ አማርኛ አቅርቤ ነው እውነተኛውን ሥራዬን የጀመርሁት ዕድሜ ለአያና እያልሁ እማረሰሁ ለምሳሌ አሁን ጀርመን አታውቅምና አንድ ዓመት ተማረው ቢሉኝ እኔ የምማረው የከብት ሐኪም ለመሆን ነው ይህንንም ለመማር ጀርመን ማወቅ አይጅግም አያስፈልግም እነሆ አማርኛ ባይቀበሉኝ አንድ ዓመት በከንቱ ላጠፋ ነበር ይህ እንግዲህ ለኢትዮጵያ ልጆች ያማረ መንገድ ነው ።

አሁን ያወጣው ።

የኢትዮጵያ ፊደል ለያመጠን ረጅምና ተስፋ የሚያስቈርጥ ስለሆነ የእጅ መጻፊያ መኪና ደስ የሚያሰኝ ሁኖ ሊወጣ አልተቻለም ነበር። አንድ እንኳ ቢወጣ ያለመጠን ትልቅና ከእጅ ጽሕፈት የማያፋጥን ነበር ይህን የእጅ ጽሕፈት መኪና ደስ አድርጎ እንዲሠራና እንዲያፋጥን ቢፈለግ የኛን ፊደል መለወጥ ነው እንጂ ሌላ ምንም መድኃኒት ያለው አልመሰለንም ነበረ።ይሁን እንጂ አያና ብሩ ፊዳላችንን ሳይለውጥ ያንን ሁሉ ጕጸጕጽ እጅግ በሚያስደንቅ መንገድ አገኝቶና አሰናድቶ እጅግ ያማረ መጻፊያ መኪና አውጥቶና አሠርቶ የፈለገ እንዲገዛ አገባያ ዘረጋው የመኪናውም ትልቅነት ያውሮፓዎቹን መኪና ያህላል።ወዲያም ወዲህም ሲሉ ለመሸከም የማይከብድ ነው። ደግሞ ከዚህ ሌላ በፍጥነት ሊጻፍበት ይቻላል ።

የብሩ ብልሃት

ብሩ ፊደሎቹን ሁሉ አልጻፈም በመኪናው ላይ ያሉት እነዚህ ናቸው

ሀሀ ለል መም ሰስ ረር ቀቅ በብ ተሬ ነን አእ ከክ ወዋ ዘዝ የይ ገግ ጠጥ ጨጭ ጸዩ ደዩ ሠጮ ዳዴ ዶፉ ማዮ ጋሬ ሃሥ ናኑ ቶሩ ሬዱ ፋኖ ፈፋ ፍሬ ትጫ ዐጨ ፐፖ ፡ ኘ ፰፱ ፲፬ ፳፱

ዓሥራሁለት ምልክቶች አሉት የቀሩትንም ፊደላት በእነርሱ ያገኛቸዋል ። የመኪናው ኩባንያ ሮያል ይባላል ይህነን በአማርኛ የወጣውን የሚሸጥ ኩባንያ በኢትዮጵያ ሊቆም ነው

አያና ይህነን ሥራ ሲያሰናዳ ነገሩን ቢያጫውተኝ መንገዱንና አሳቡንም ቢነግርኝ አላመንኩም ነበር ተማሪ ቤት ሲዘጋ መዝገቡን ጨርሶ አምጥቶ ቢያሳየኝ መገረምና ደስታ በድንገት ማረኩኝ መኪናውንም በቶሎ እንዲያሠራና እንዳየው እየናፈቀኝ ቈይቼ ትላንትና ማታ በዚህ አገር ያየነውን ወንድሞቼን ሁሉ ሰብስቦ ቢያሳየን ተደነቅን ።

እስከአሁን ድረስ በእጅ ጽሕፈት ብቻ ብዙ ነገሮች በድካም ሲሠሩ የነበሩ የመንግሥት ሠራተኞች ይህነን አፍጣኝ የሆነ መኪና ሲያገኙ ሥራቸው እንዲቀልላቸው አይጠረጠርም እኛም ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ለመድረስ የምንችለው እንደነዚህ ያሉትንና የበለጡትን ነገሮች ራሳቸው ለመሥራት በመቻል መሆኑ አይጠረጠርም ።

ዓለሙ ወርቅ ደ ።

በአዲስ አበባ ከተማ የቆመ የሕዝብ ወጥመድ።

ከዚህ ቀደም ሞሊና የሚባል የውጭ አገር ሰው አንድ ክፉ ወጥመድ ሩሊና የሚባል ጨዋታ በከተማችን አቁሞ ብዙ ሰው አደኅይቶ ወደ አገሩ ተመልሶ ሔደ ይኸውም ጨዋታ ሕዝብን መጕዳቱን አውቆ መንግሥት አጥብቆ ከልክሎ ነበር

አሁን ግን ከወዳጄ ከሙሴ ከስጣ ሮሰግሉ እንደሰማሁት ወሬው በጣም የሚያሳዝን ነው ።

ለዚሁ ማታለያ አምስት የውጭ አገር ሰዎች ተሻርከው ሙሴ ማብሬኮስ የሚባለውን ዋና አድርገው ሌሊቱን ሁሉ ሰው ሲያታልሉ ያድራሉ አሉ ። መጀመሬ የጨዋታውን መኪና መያዝ ያስፈልጋል። ሁለተኛ እነዚህን ሥራ ፈቶች ሥራቸውን ምን እንደሆነ መመርመር ያስፈልጋል ።

አገራችን ሥልጣኔ ጀመረች እያልን ዓይናችንን በገለጥንበት ጊዜ ዕንቅፋት የሚሆን ነገር ሁሉ መልሶ ያደነቁረናልና ስለዚህ ወንድሞቼ ወደ ወጥመዳቸው አትድረሱ የተጠመደልንም በማብሬኮስ ሆቴል ነው ።

በዚሁ ጨዋታ የከሰሩትን ሰዎቹ ዝርዝር ብጽፈው እግጅ ያስለቅሳችኋል ። አሁን በቅርብ ቀንም በጨዋታው ወገን ሳይቶው ለመጋደል የደረሱ ብዙ ናቸው ይልቁንም የውጭ አገር ሰዎች የሆኑ ።

ክቡር ከንቲባ የዚህን ነገር መርምረው የሕዝብን ጉዳት የከተማን ጥቃት ደህንን የመሰለውን ክፉውን ዕንቅፋት ይነቅሉታል ስል አስቀድሜ በጣሙን ምስጋና አቀርባለሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት አስተማሪ አልቤር መሱላምና ሙሴ ክስታ ሮሶግሉ ።

የሚሰሙ ጆሮች ያሉት ይስማ ። ማቴ ፲፫፥፱

የብርሃን መሪ በሆነው ብርሃንና ሰላም በ፫ኛው ዓመ. ብ፩ቁጥር አርእስቱንም ለጊዜው የተስማማ ጥያቄ ብዬ ከአንድ እስከ ፲ዓይነት አድርጌ የሥራ ጓደኞች ለሆናችሁ ለብርሃንና ሰላም ተላላኪዎች ስላቀረብሁት ጥያቄ ባ፩ኛው ቍር ብርሃንና ሰላም አቶ አበበ ገብሬ ለጥያቄዬ የሚገባ ምላሽነው ብሎ እኔን እየነቀፈ የጻፈውን ቃል አየሁት።

ሰማህ አቶ አበበ ገብሬ የኔ ጥያቄ አገራችን የሥራ ጥቅም ያገኘችው የሌላ ቋንቋ በተማሩት ልጆችዋ ብቻ ነውን ወይስ በአገራቸው ትምህርትና በተፈጥሮዋቸው ቅንነት እየተመሩ በሚሠሩት ልጆቿ ይሆን? እስቲ የሚበልጠው ጥቅሟ ከማናቸው ወገን ይመስላል የሚል በመሆኑ የሥራን ሚዛን ለማመዛዘን ስለ ነበረና ደግሞ ለዚሁም ጥያቄ እንዲሆን የሚገባው ነው ብለህ የተፈጥሮ እውቀትን አብልጬ የትምህርት እውቀትን ታናሽ አድርጌ የጻፍሁ አስመስለህ ምላሽ በመጻፍህ ጥያቄዬን ሳትመለከትና ሳትመረምር በወሬ ነው የጻፍኸው ለማት ይቻላል።ሰማህ አቶ አበበ ገብሬ ይኸውም የጻፍኸው ነገር ከንተ ልብ ለመውጣት የማይችል ስለሆነ የተመከር ሙግት ፡ ያን ተናገሮ ጉልት እንዳይሆንብህ እንጂ ለቀረውስ ነገር ግድ የለም ይልቅስ ይኸነን ጽፎ የሰጠህን ሰው ዋቢህን አሳልፈህልኝ ደግሞ ለዚያውም ላላከህ ሰው ከመናገር አሳሳቢው ቢከራከር ይበልጥ ነበር ።

አስረጅ ።

አነቀድሞ ሳይሰማ ነገር ለሚመልስ ስንፍና ኃፍረትም ይገባዋል ምሳ ፲፰ ፲፫ ሳትመረምር አትንቀፍ አስቀድመህ ነገሩን ጠይቀህ ተረዳው እንጂ ከተረዳህም በኋላ ትቈጣለህ ሲራ ፲፩ ፯ለጨዋታ ብለህ ልጆች እንደሚያነቡት አታንብ ። ለመማርም ብለህ ኩሩዎች እንደሚያነቡት አታንብ እንደ.ህ አይደለም ለመናገር ብለህ አንብ ለነፍስህ ከታላላቅ መናፍስት ነጥሮ የወጣ የዕውቀት መጕናጸፊያ አድርጋ ፈላስፋ ፍሎበር።

ሰማህ አቶ አበበ ገብሬ እንደዚህ የተባለውን ትእዛዝ ሳትገምት ነውና የጻፍህልኝ ስለዚህ ይቅርታ መለመን ይገባሃል እላለሁ

ለሚሳለቁ ሰዎች ፍርድ የተዘጋጀች ናት። ምሳ ፲፱ ፲፱

ለብርሃንና ሰላም ተላላኪዎች ለፍርድ የቀረበ አቤቱታ። አቶ አበበ ገብሬ ጥበብን የተቃወምሁ አስመስሎ በከንቱ የሰደበበትን ቃልና የቀድሞ ጥያቄዬን አይታችሁ ለጥያቄዬም የሚገባና የማይገባ ምላሽ መሆኑን ገምታችሁ ፍርድ እንድትሰጡን ለብርሃንና ሰላም ተላላኪዎች አቤቱታዬን አቀርባለሁ

መልካም ምክር ።

ሥራህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ አሳብህም ትፀናለች ምሳ ፲፯ ፫ ። ነገርን ከመጀመር መፈጸም ይሻላል ። ትዕግሥ ከደፋር ይሻላል ። መክ ፯ ፰ የተባለውን ገምቼ ይኸነን ነገሬን ለናንተ ለዳኞቼ ለፍርድ ማቅረቤ ስለዚህ ነው ለገሠ ቸሩ ።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ፔሽዲማልጂ የፈረንሳዊ ሌጋሲዮን ጥገኞች የሆኑ አርመኖች ጉዳይ ሰክሬቴር የሟቹ የሙሴ ክራፖስ ክራገዚያንን ዕቃና ገንዘብ ለጊዜው እንዲጠብቁና የወራሾቻቸውንም ጉዳይ እንዲጨርሱ የፈረንሳዊ ሌጋሲዮን አዘዋቸዋልና የሙሴ ክራፖስ ክራገዚያን ገንዘብ ያለባችሁና ከርሳቸውም ገንዘብ የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ ከጥር ፴ቀን አንሥቶ እስከአንድ ወር ድረስ ለምትከፍሉት ወይም ለምትፈልጉት ገንዘብ ምስክር የሚሆናችሁን ወረቀት ለሙሴ ፔሽዲማልጂ እንድታሳዩ አስቀድመን እናስታውቃችኋለን ይህ የተቈረጠው አንድ ወር ካለፈ በኋላ የምታመጡትን አቤቱታ አለመቀበላችንንም በሥርዓት እናስታውቃችኋለን የፈረንሳዊ ቆንስል ።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአቦካትነት ሥራ ይሠራሉ በአገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክአገር የፍርድ ቤት ብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍ[illegible] አዋቂ ናቸው።ለዚሁም አቦካትነታቸውና ፍትሐ ነገ[illegible] ቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጆርጊንድ ዘለቀ አግደው ግቢ ነው ። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፯ት ሰዓት ይቀበላሉ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

እነሆ በአፍሪቃ ክፍል የሠለጠነ ጎረቤት ስለሌለን ልንፈክክር አልቻልንም አውሮፓን ዛሬ የዓለም ሥልጣኔ መሪ ያደረገው የሕዝቦቹ መፈካከር ነው በውሮፓ ካሉት አገሌ ነው በብዙ ለሥልጣኔ የረዳ ለማለት አይቻልም ስለምን ሁሉ እንደዓቅሙ ረድቷልና።አንድ አገር የጀመረውን ሌላው ያሻሽላል የቀረውንም ሥራ ያሲዘዋል። ነገር ግን በኛ ክፍል የጀመረም አልተገኘም የተከተለም የለም ከተፈጥሮዋ ክፍላችን ለምለምና ሰፊ ስለሆነች ሕዝብዋ ችግር አልነበረባትም ከመፍለስም የሚያደርሰው ደግሞ ችግር ነው ሰንጠረጋርና ገበጣ የተፈለሰፉት በወሕኒ ቤት መሆኑ እሥረኞቹ የሚጫወቱት ጨወታ በማጣትና በመቸገር ነው ።

አያና ብሩ አኰራን።

ኢትዮጵያ ልጆቿን ታስተምራለች ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ለመድረስም ትጣጣራለች እያሉ ብዙ ሰዎች ሲጽፉ አይቻለሁ ግን ከተማሩት ይህን አደረጉስት ሲሉ አልሰማሁም እነሆ የምስራች ያገሬ ልጆች አያና ብሩ ለኢትዮጵያ ትልቅነገር ሠራ

የዛሬ ሰባት ዓመት አያና ብሩን እንዲማር ወደ ግብፅ ሰደዱት እዚያ እንደሚገባ ከተማረ ወዲህ እንግሊዝ አገር መጥቶ የወርቅና የብር መሐንዲስነት ይማራል ጠባዩና እውቀቱ የተከከለ መሆናቸው ተመስክሮአል። አሁን ገልጾዋል ከዚህ ቀጥዬ እናገረዋለሁ።ግን ሥራውን ሳልጀምር ሌላ ላገሩ የሠራውን አስቀድሜ መናገር እወዳለሁ።በዚህ አገር ያሉ ዩኒቬርሲቲዎች የኛን ቋንቋ አንቀበልም ብለው ሲኖሩ ነበር ነገር ግን ነገሩን ገንዝቦት ኢትዮጵያ የሠለጠነች ታላቅ መንግሥት ናት ከዚህም በላይ ያለም መንግሥት ማኅበርተኝነት አላት ቋንቋዋን ለምን አትቀበሉም ብሎ ቢጠይቃቸው ምክር ይዘው በሦስተኛው ቀን መቀበላቸውን አስታወቁ።አለጥርጥር ታላቅ ነገር ነው ስለምን ቢሉ የኢትዮጵያ ልጆች ለመማር ወደ አውሮፓ ሲመጡ ሁለት ሦስት ቋንቋ ለፈተና ሲያቀርቡ አንዱን አለችግር ያቀርባሉ ።

እኔም እንደዚሁ አማርኛ አቅርቤ ነው እውነተኛውን ሥራዬን የጀመርሁት ዕድሜ ለአያና እያልሁ እማራለሁ ለምሳሌ አሁን ጀርመን አታውቅምና አንድ ዓመት ተማረው ቢሉኝ እኔ የምማረው የከብት ሐኪም ለመሆን ነው ይህንንም ለመማር ጀርመን ማወቅ እጅግም አያስፈልግም እነሆ አማርኛ ባይቀበሉኝ አንድ ዓመት በከንቱ ላጠፋ ነበር ይህ እንግዲህ ለኢትዮጵያ ልጆች ያማረ መንገድ ነው ።

አሁን ያወጣው ።

የኢትዮጵያ ፊደል ለያመጠን ረጅምና ተስፋ የሚያስቴርጥ ለሆነ የእጅ መጻፊያ መኪና ደስ የሚያሰኝ ሁኖ ሊወጣ አልተቻለም ነበር። አንድ እንኳ ቢወጣ ያለመጠን ትልቅና ከእጅ ጽሕፈት የማያፋጥን ነበር ይህን የእጅ ጽሕፈት መኪና ደስ አድርጎ እንዲሠራና እንዲያፈጥን ቢፈለግ የኛን ፊደል መለወጥ ነው እንጂ ሌላ ምንም መድኃኒት ያለው አልመሰለንም ነበረ።ይሁን እንጂ አያና ብሩ ፊዳላችንን ሳይለውጥ ያነን ሁሉ ጕጻጕጽ እጅግ በሚያስደንቅ መንገድ አንኝቶና አሰናድቶ እጅግ ያማረ መጻፊያ መኪና አውጥቶና አሠርቶ የፈለገ እንዲገዛ እገባያ ዘረጋው የመኪናውም ትልቅነት ያውሮፓዎቹን መኪና ያህላል።ወዲያም ወዲህም ሲሉ ለመሸከም የማይከብድ ነው። ደግሞ ከዚህ ሌላ በፍጥነት ሊጻፍበት ይቻላል ።

የብሩ ብልሃት

ብሩ ፊደሎቹን ሁሉ አልጻፈም በመኪናው ላይ ያሉት እነዚህ ናቸው

ሀሀ ለል መም ሰስ ረር ቀቅ በብ ተፌ ነን እኢ ከክ ወዋ ዘዝ የይ ገግ ጠጥ ጨጭ ጸዪ ደዩ ሠጮ ዳዴ ዶቆ ማፐ ጋሬ ሃሥ ናኑ ቶሬ ሬዲ ፋኖ ፈፋ ፍሌ ትጫ ዐጩ፡ ፐዎ ፡ ኘ ፰፱ ፲፬ ፳፩

ዓሥራሁለት ምልክቶች አሉት የቀሩትንም ፊደላት በእነርሱ ያገኛቸዋል ። የመኪናው ኩባንያ ሮያል ይባላል ይህነን በአማርኛ የወጣውን የሚሸጥ ኩባንያ በኢትዮጵያ ሊቆም ነው

አያና ይህነን ሥራ ሲያሰናዳ ነገሩን ቢያጫውተኝ መንገዱንና አሳቡንም ቢነግርኝ አላመንኩም ነበር ተማሪ ቤት ሲዘጋ መዝገቡን ጨርሶ አምጥቶ ቢያሳየኝ መገረምና ደስታ በድንገት ማረከኝ መኪናውንም በቶሎ እንዲያሠራና እንዳየው እየናፈቀኝ ቄይቼ ትላንትና ማታ በዚህ አገር ያየነውን ወንድሞቼን ሁሉ ሰብስቦ ቢያሳየን ተደነቅን ።

እስከአሁን ድረስ በእጅ ጽሕፈት ብቻ ብዙ ነገሮች በድካም ሲሠሩ የነበሩ የመንግሥት ሠራተኞች ይህነን አፍጣኝ የሆነ መኪና ሲያገኙ ሥራቸው እንዲቀልላቸው አይጠረጠርም እኛም ወደ ሥልጣኔ ደረጃ ለመድረስ የምንችለው እንደነዚህ ያሉትንና የበለጡትን ነገሮች ራሳቸው ለመሥራት በመቻል መሆኑ አይጠረጠርም ።

ዓለሙ ወርቅ ደ ።

በአዲስ አበባ ከተማ የቆመ የሕዝብ ወጥመድ።

ከዚህ ቀደም ሞሊና የሚባል የውጭ አገር ሰው አንድ ክፉ ወጥመድ ሩሊና የሚባል ጨዋታ በከተማችን አቁሞ ብዙ ሰው አደኻይቶ ወደ አገሩ ተመልሶ ሔደ ይኸውም ጨዋታ ሕዝብን መጕዳቱን አውቆ መንግሥት አጥብቆ ከልክሎ ነበር

አሁን ግን ከወዳጀ ከሙሴ ክስጣ ሮሶግሉ እንደሰማሁት ወሬው በጣም የሚያሳዝን ነው ።

ለዚሁ ማታለያ አምስት የውጭ አገር ሰዎች ተሻርከው ሙሴ ማብሬክስ የሚበለውን ዋና አድርገው ሌሊቱን ሁሉ ሰው ሲያታልሉ ያድራሉ አሉ ። መጀመሪ የጨዋታውን መኪና መያዝ ያስፈልጋል። ሁለተኛ እነዚህን ሥራ ፈትዎች ሥራቸውን ምን እንደሆነ መመርመር ያስፈልጋል ።

አገራችን ሥልጣኔ ጀመረች እያልን ዓይናችንን በገለጥንበት ጊዜ ዕንቅፋት የሚሆን ነገር ሁሉ ሞልቶ ያደነቁረናልና ስለዚህ ወንድሞቼ ወደ ወጥመዳቸው አትድረሱ የተጠመደልንም በማብሬክስ ሆቴል ነው ።

በዚሁ ጨዋታ የከሰሩትን ሰዎች ዝርዝር ብጽፈው እግጅ ያስለቅሳችኋል ። አሁን በቅርብ ቀንም በጨዋታው ወገን ለይተው ለመጋደል የደረሱ ብዙ ናቸው ይልቁንም የውጭ አገር ሰዎች የሆኑ ።

ክቡር ክንቲባ የዚህን ነገር መርምረው የሕዝብን ጉዳት የከተማን ጥቃት ይህንን የመሰለውን ክፉውን ዕንቅፋት ይነቅሉታል ስል አስቀድሜ በጣሙን ምስጋና አቀርባለሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት አስተማሪ አልቤር መስላምና ሙሴ ክስታ ሮስግሉ ።

የሚሰሙ ጆሮች ያሉት ይስማ ። ማቴ ፲፫፱

የብርሃን መሬ በሆነው ብርሃንና ሰላም በ፫ኛው ዓመ ብ፩ቁጥር አርእስቱንም ለጊዜው የተስማማ ጥያቄ ብዬ ከአንድ እስከ ፲ ዓይነት አድርጌ የሥራ ጓደኞች ለሆናችሁ ለብርሃንና ሰላም ተላላኪዎች ስላቀረብሁት ጥያቄ በ፬ኛው ቍር ብርሃንና ሰላም አቶ አበበ ገብሬ ለጥያቄዬ የሚገባ ምላሽነው ብሎ እኔን እየነቀፈ የጻፈውን ቃል አየሁት።

ሰማህ አቶ አበበ ገብሬ የኔ ጥያቄ አገራችን የሥራ ጥቅም ያገኘችው የሌላ ቋንቋ በተማሩት ልጆችዋ ብቻ ነውን ወይስ በአገራቸው ትምህርትና በተፈጥሮዋቸው ቅንነት እየተመሩ በሚሠሩት ልጆቿ ይሆን? እስቲ የሚበልጠው ጥቅሟ ከማናቸው ወገን ይመስላል የሚል በመሆኑ የሥራን ሚዛን ለማመዛዘን ስለ ነበረና ደግሞ ለዚሁም ጥያቄ እንዲሆን የሚገባው ነው ብለህ የተፈጥሮ እውቀትን አብልጬ የትምህርት እውቀትን ታናሽ አድርጌ የጻፍሁ አስመስለህ ምላሽ በመጻፍህ ጥያቄዬን ሳትመለከትና ሳትመረምር በወሬ ነው የጻፍኸው ለማት ይቻላል።ሰማህ አቶ አበበ ገብሬ ይኸውም የጻፍኸው ነገር ከንቱ ልብ ለመውጣት የማይችል ስለሆነ የተመከሮ ሙግት ፣ ያን ተናግሮ ጕልት እንዳይሆንብህ እንጂ ለቀረውስ ነገር ግድ የለም ይልቅስ ይኸን ጽፎ የሰጠህን ሰው ዋቢህን አሳልፈህልኝ ደግሞ ለዚያውም ለላከህ ሰው ከመናገር አሳሳቢው ቢከራከር ይበልጥ ነበር ።

አስረጅ ።

አስቀድሞ ሳይሰማ ነገር ለሚመልስ ስንፍና ኃፍረትም ይገባዋል ምሳ ፲፰ ፲፫ ሳትመረምር አትንቀፍ አስቀድመህ ነገሩን ጠይቀህ ተረዳው እንጂ ከተረዳህም በኋላ ትቈጣለህ ሲራ ፲፩ ፯ ለጨዋታ ብለህ ልጆች እንደሚያነቡት አታንብ ። ለመማርም ብለህ ኩሩዎች እንደሚያነቡት አታንብ እንደዚህ አይደለም ለመናገር ብለህ አንብ ለነፍስህ ከታላላቅ መናፍስት ነጥሮ የወጣ የዕውቀት መጐናጸፊያ አድርጋ ፈላስፋ ፍሎበር።

ሰማህ አቶ አበበ ገብሬ እንደዚህ የተባለውን ትእዛዝ ሳትገምት ነውና የጻፍህልኝ ስለዚህ ይቅርታ መለመን ይገባሃል እላለሁ

ለሚሳለቁ ሰዎች ፍርድ የተዘጋጀች ናት። ምሳ ፲፱ ፳፱

ለብርሃንና ሰላም ተላላኪዎች ለፍርድ የቀረበ አቤቱታ። አቶ አበበ ገብሬ ጥበብን የተቃወምሁ አስመስሎ በከንቱ የሰደበበትን ቃልና የቀድሞ ጥያቄዬን አይታችሁ ለጥያቄዬም የሚገባና የማይገባ ምላሽ መሆኑን ገምታችሁ ፍርድ እንድትሰጡን ለብርሃንና ሰላም ተላላኪዎች አቤቱታዬን አቀርባለሁ

መልካም ምክር ።

ሥራህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ አሳብህም ትፀናለች ምሳ ፲፮ ፫ ። ነገርን ከመጀመር መፈጸም ይሻላል ። ታጋሽ ከደፋር ይሻላል ። መክ ፯ ፰ የተባለውን ገምቼ ይኸነን ነገሬን ለናንተ ለዳኞቼ ለፍርድ ማቅረቤ ስለዚህ ነው ለገሠ ቸሩ ።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ፔሽዲማልጂ የፈረንሳዊ ሌጋሲዮን ጥገኞች የሆኑ አርመኖች ጉዳይ ሰክሬቴር የሚቼ የሙሴ ክራፖስ ከራገዚያንን ዕቃና ገንዘብ ለጊዜው እንዲጠብቁና የወራሾቻቸውንም ጉዳይ እንዲጨርሱ የፈረንሳዊ ሌጋሲዮን አዘዋቸዋልና የሙሴ ክራፖስ ከራገዚያን ገንዘብ ያለባችሁና ከርሳቸውም ገንዘብ የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ ከጥር ፴ቀን አንሥቶ እስከአንድ ወር ድረስ ለምትከፍሉት ወይም ለምትፈልጉት ገንዘብ ምስክር የሚሆናችሁን ወረቀት ለሙሴ ፔሽዲማልጂ እንድታሳዩ አስቀድመን እናስታውቃችኋለን ይህ የተቈረጠው አንድ ወር ካለፈ በኋላ የምታመጡትን አቤቱታ አለመቀበላችንንም በሥርዓት እናስታውቃችኋለን የፈረንሳዊ ቆንስል ።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአቦካትነት ሥራ ይሠራሉ ባገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግ በግሪክአገር የፍርድ ቤት ብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍትሐ ነገሥ አዋቂ ናቸው።ለዚሁም አቦካትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጅሮንድ ዘለቀ አግደው ግቢ ነው ። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፯ት ሰዓት ይቀበላሉ።

የሚሸጥ ኦቶሞቢል ።
ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ ኦቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።
ፎርድ
ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።
ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሲንጀር ከቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጎበኙለት በማክበር ያመለክታል

በየይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሲንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ዘጣትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀም [illegible] ጥር ፲፬ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዮ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከሦስት፤ ጀምር እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላኒዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መስንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በክዚና በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

ቡብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ ቡብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደ መሰከረላት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የሴብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቡናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትክል የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምባሳል ፥ የልብ፡ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዲሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መበለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም
ALEM



ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄሰኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፌ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፱
8me ANNE. № 9

ሐሙስ የካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
JEUDI 25 Fevrier 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ፥
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረኽተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሕይወት መንገድ ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በታንሽ ሕመም መታመማቸውንና በጎ ሁነው ሥራ የመጀመራቸውንም የምስራች በስምንተኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም በ፰ኛ ቍጥር እንደተጻፈው አስታውቀናል ። ነገር ግን ነፋስ መለወጥና አሙቀት አገር ጥቂት ጊዜ መቈየት የሚያስፈልግ መሆኑን ሐኪሞች አስታውቀው ነበርና ስለዚህ ወደጅቡቲ ለመሔድ ስላሰቡ የመንገዳቸውን አኳኋን ቀጥለን ጽፈነዋል ።

ጥር ፳፫ቀን ከጧቱ በ፩ሰዓት ከግርማዊት እቴጌ መነንና ከተከተሏቸው መሳፍንትና መኳንንት ጋር ተነሡ ።

ከተከታዮችም ዋና ዋናዎቹ ቀጥሎ የተጻፉት ናቸው ።

ልዑል ራስ ኃይሉ

ልዑል ራስ ሥዩም

ልዕልት ፀሐይ ኃይለ ሥላሴ

ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ

ክብርት ወይዘሮ ዓፀደ አስፋው

ክብርት ወይዘሮ የሻሽ ወርቅ ይልማ

ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴና ሌሎችም ስማቸው ያልተጻፈ መኳንንት ነበሩ ።

ለመሸኘትም ከመጡት መኳንንት ክቡር ፊታውራሪ ብሩ አቃቂ ድረስ እንዲሸኙ ፈቃድ ለምነው ስለፈቀዱላቸው አቃቂ አድርሰው በኦቶሞቢል ተመለሱ ።

ከዚህ በኋላ በባቡሩ መንገድ ግራና ቀኝ በየጣቢያውም ላይ ለተገኙ ችግረኞች ለሆኑ ሁሉ የገንዘብ እርዳታ ሰጡ። በ፲፩ ሰዓት አዋሽ ገብተው በተለየ ከተሰናዳው ቤት አደሩ ።

በጥር ፳፬ በ፲፪ሰዓት አዋሽ ከተከሏት ከመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ሒደው ተሳልመው በ፪ሰዓት ወደድሬ ደዋ ለመሔድ ተነሡ ።

በዚሁም ቀን ፋርማንና ፖቴዝ የሚባሉ ሁለት አውሮፕላኖች ጅጅጋ ደርሰው ድሬ ደዋ ላይ ጃንሆይን ሊጠብቁ ታዘዝው ነበርና ከጧቱ ባንድ ሰዓት ከአዲስ አበባ ተነሥተው አዋሽ ላይ በቡሩ ሲነሣ ደረሱ ።

ከዚህም በላይ እንዳስታወቅነው በየመንገዱና በየጣቢያው ላይ የርኅራኄ ሥራቸውን ሳያቋርጡ በ፰ሰዓት አፍደም ደርሰው ምሳ ከተበላና ባቡሩ መሔድ ከጀመረ በላይ ከመንገዱ ግራና ቀኝ ከ፪፻ሜትር በሚርቅ ስፍራ አውሬዎች ስለ ታዩ ተኵሰው ፪ቱንም አውሬዎች ገደሏቸው ።

በዚሁም ምክንያት ባቡሩ ጥቂት ጊዜ በመቆሙና እንደ ዚሁም አዋሽ ላይ በማርፈዱ ድሬ ደዋ በጊዜ ለመድረስ መሽቶ ከማታው ባ፩ሰዓት ገቡ ።

አቡነ ቄርሎስም በሕመማቸው ምክንያት አስቀድመው ድሬ ደዋ ወርደው ነበርና የጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ድሬ ደዋ መምጣት ስለተሰማ ብፁዕ አባታችን አቡነቄርሎስና በድሬ ደዋ ከተማና በዙርያዋም ያሉ የሀገራችንና የውጭም ሀገር ሰዎች ተሰልፈው ይጠባበቁ ነበርና ባቡሩ እንደደረሰ ዳር እስከ ዳር ሦስት ጊዜ ተጨበጨበ።

ወዲያውም ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከባቡሩ ሣሎን እንደተቀመጡ ብፁዕ አባታችን አቡነ ቄርሎስና የውጭ አገርም ታላላቅ ሰዎች በተራ እየገቡ ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ ጃንሆይም ተከታዮቻቸውም ወደ ቤተ መንግሥቱ ባማረ አቶሞቢል ሔዱ

ከዚያም በኋላ ለመሳፍንቶችና በድሬ ደዋ ከተማም ላሉ ለውጭ አገር ሰዎች ከቤተ መንግሥቱ የራት ግብዣ ተደረገ።

በጥር፳፭ም ከጧቱ በ፩ሰዓት ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ግርማዊት እቴጌ መነን ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሒደው ተሳልመው ተመለሱ ።

በዚሁም ቀን በ፬ሰዓት አገር ለማልማት ለመንግሥትና ለሕዝብ ጥቅም ሲሉ ከድሬ ደዋ ወደ ሐረርጌ የኦቶሞቢል መንገድ እንዲሠራ አድርገው ነበረና የተሠራውን መንገድ ሐራማያ ድረስ አይተው በ፯ ሰዓት ተመለሱ ።

በዚሁም ቀን ከማታው በ፬ ሰዓት ተነሥተው በጥር ፳፰ ቀን በ፫ ሰዓት ጅቡቲ ገቡ ።

በዚሁም ሰዓት የጅቡቲ ገዥ ልዊ አንቷንና ባለቤታቸው በጅቡቲም ያሉ ታላላቅ የውጭ አገር ሰዎች ጃንሆይን ለመቀበል ይጠባበቁ ነበረና ባቡሩ እንደደረሰ እንደማዕርጋቸው

በተራ እየገቡ ሰላምታ ከቀረቡ በኋላ ጃንሆይና እቴጌ ከባቡሩ ማሎን ሲወጡ የሰላምታ ሙዚቃ ተነፍቶ ተዘጋጅቶ በሚጠብቀው አቶ ሞቢል ሁነው ወደ የጂቡቲ ጉበርኔር (ገገር) ቤት ሔዱ ።

በዚሁም ቀን ወደማታ አምቡሉ የሚባለውን አታክልት ያለበትንና ውኃ የሚወጣበትን መኪና ጐበኙ ።

በጥር ፳፱ ጅቡቲ የሚመጣ መርከብ እስከሚቆምበት ቦታ ማናቸውም ሰውና ዕቃ በጀልባ መሔዱ ቀርቶ በቀጥታ እመርከብ ላይ እንዲሣፈርና እንዲወርድ ለማድረግ የሚሠራውን ቦታ ጐበኙ ።

በዚሁም ቀን ከማታው በ፱ ሰዓት የጅቡቲ ገገር ለተከታዮቻቸው የራት ግብዣ አደረጉ ።

ጥር ፴ ቀን ፌልክስ ሩሲል የሚባለው ከተሠራ ቅርብ ጊዜ የሆነው አዲሱ የፈረንሣዊ መርከብ መጥቶ ነበረና ይህኑ መርከብ በ፬ሰዓት ሔደው ጐብኝተው ለመርከቡ ሹማምንቶች ሙታሰቢያ ሜዳይ ሰጡ ።

ከኩለቀንም ባኋላ ጅቡቲ ያለውን ሆስፒታል አይተው ዘመድ ለሌላቸው በሽተኞች እርዳታ አደረጉላቸው ።

በዚሁም ቀን የምድር ባቡር ኩፓንያ ራት ጋብዞ ነበርና ከመሳፍንቶቻቸው ጋራ በ፱ሰዓት ሔዱ ።

የካቲት ፩ ቀን ቢትሬ ለፍራንሷ በሚባለው በፈረንሣዊ የጦር መርከብ በ፫ ሰዓት ተነሥተው በባሕሩ ላይ ነፋስ ሲቀበሉ ውለው የአበከን ጠረፍ አይተው በ፲፩ ሰዓት ተኩል ገቡ።

በዚሁም ቀን ፪ተኛ እጂቡቲ ጉበርኔር ቤት የራት ግብዣ ተደረገ ።

የካቲት ፪ ቀን ጨው የሚሠራውን መኪና ጐበኙ።

የካቲት ፫ ቀን ያፍሪክ አሪያንታል ኩፓንያ በሁለት ጉንንሽ መርከብ የመስቀል ደሴት እስከሚባለው ሐደው የባሕሩን ነፋስ እንደተቀበሉ ዓሣ እንዲያጠምዱ ለምኖ ነበር።በ፪ ሰዓት ሐደው እስከ ፯ ሰዓት ሲናፈሱ ዋሉ።በዚሁም ቀን የጨው ማኅበር ኩባንያ ከመሳፍንቶቻቸው ጋር እራት ጋበዙ።

የካቲት ፬ ቀን አዋጅ የሚባለውን የፈረንሣዊና የእንግሊዝ ድንበር የሚገናኝበትን ጐበኙ ።

የካቲት ፭ ቀን ከዚህ ባላይ ስሙ በተጠራው በፈረንሣዊ የጦር መርከብ በ፪ ሰዓት ገብተው የተጐሬን ጠረፍና የሰይጣን ደሴት የሚባለውን አይተው በባሕሩ ላይ ውለው በ፲፩ ሰዓት ገቡ ። በዚህም ቀን ነፋስ በርትቶ ተናውጾ ነበር፡ ለመርከቡም ሠራተኞች እንደማዕርጋቸው ኒሻንና ሜዳይ ሸለሙአቸው።

በዚህም ቀን ሙሴ ኮርጂር የሚባለውን አውሮፕላን ነጂ ወደ አዲስ አበባ ሔዶ መመለስ መቻልና አለመቻሉን ቢጠይቁት ይቻላል ብሎ አስታውቆ ተልኮ አዲስ አበባ ፋርማን በሚባለው በፈረንሣዊ አይሮፕላን ሔዶ ነበረና ተመልሶ ጅቡቲ ሊገባ ፺፩ ኪሎ ሜትር ሲቀረው ነፋስ አባራ አስነሥቶ መኪናውን አላስኬድ ብሎት ስለተሰበረ ሙሴ ኮርጂር እጁንና ወደጐኑም ቈስሎ ኑሮ እመጣለሁ ካለበት ሰዓት በማስተላለፉና በስልክ ቢጠየቅ በየመንገዱ ያሉት ስልከኞች ሁሉ ደኅና መሔዱን አይተናል ብለው ሸበሌ በሚባለው ጣቢያ ቢጠየቅ አላየሁም ብሎ ስለአስታወቀ ጃንሆይ ባቡርና ዘበኛ እዘዝው ሲፈለግ ከባቡሩ መንገድ እርቆ አብሮት ያለ መከኒሲያን ደኅና ሁኖ ሙሴ ኮርጂር ቈስሎ ተገኝቶ በባቡር አስመጥተው ጅቡቲ ሆስፒታል አገቡት።

የካቲት ፮ ቀን አንኮል የሚባለው ታላቅ የጀርመን መርከብ ጅቡቲ መጥቶ ነበረና ሔደው ጐብኝተው ለመርከቡ ሹማምንቶች መታሰቢያ ሰጡ። በዚሁም ቀን እጅቡቲ ገገር ቤት ከመሳፍንቱ ጋር ፫ተኛ የራት ግብዣ ተደርጎ በ፬ ሰዓት ከጅቡቲ ወደድሬ ደዋ ለመሔድ ተሳፈሩ።

የካቲት ፯ ቀን በ፫ ሰዓት ከ፳ደቂቃ ድሬ ደዋ ገቡ። በዚሁም ጊዜ ብፁዕ አባታችን አቡነ ቄርሎስና በድሬ ደዋ ከተማ በዙሪያዋ ያሉ ያገራችንና የውጭ አገር ሰዎች ሲጠባበቁ ነበረና በክብር ተቀበሉ ።

በዚሁም ቀን በ፱ ሰዓት ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከድሬ ደዋ ወደሐረር ባሠሩት የአቶሞቢል መንገድ ወደ ሐረማያ ሔደው ነበረና ሐረማያ ደርሰው ወደ ድሬ ደዋ ለመመለስ ሲነሡ ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ ሐረርጌን ለማየት ስለለመኑ ማንም ሰው ሳያውቀው በድንገት ወደ ሐረርጌ ወርደው፡

መጀመሪያ አደሬ ጢቆ መከነ ሥላሴ።

ሁለተኛ የመድኃኔ ዓለምን ።

ሦስተኛ የጥምቀተ ባሕር ሚካኤልን ቤተክርስቲያን ተሳልመው።

አራተኛ የልዑል ራስ መኰንንን መቃብር።

አምስተኛ የተፈሪ መኰንንን ሆስፒታል ጐበኙ በዚሁም ቀን ልዑል ራስ ሥዩምና ወይዘሮ ዓፀደ ወይዘሮ የሺሽ ወርቅ ሐረርጌን ለማየት ተሰናብተው ሔደው ነበርና ስለዚህ የሐረርጌ ሹማምንቶችና ሠራዊቱም ጃንሆይን ሳይከተሉ አስቀድሞ በመሔዳቸው የጃንሆይን መምጣት አላሰቡም ነበረና በድንገት ቢደርሱ ሕዝቡ ከመጣበት ሳይታወቅ የብዛቱና የልልታው እኳኳን እጅግ ያስደንቅ ነበረ ወዲያውም ስለደስታው ብዙ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ።

ከዚህም በኋላ ወደ ድሬ ደዋ ተመልሰው አደሩ ።

የካቲት ፰ቀን ከሌሊቱ በ፲ሰዓት ተኩል ከድሬ ደዋ የረር ጐታ ጠበል ሔደው ጠበሉንም ተጠምቀው ለጠበልና ለሆቴልም የተሠሩትን ቤቶችና አታክልቱንም ጐብኝተው በ፯ሰዓት ወደ ድሬ ደዋ ተመለሱ ።

በዚሁም ቀን ከ፱ ሰዓት በኋላ ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ያቆሙት ተማሪ ቤት ነበረና እሱን ለመጐብኘት ሔደው ስሙን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ተማሪ ቤት ብለው ሰየሙት ።

ሁለተኛም በድሬ ደዋ ያለውን የሚሲዮን ተማሪ ቤት።

ሦስተኛ የአልያንስን ።

አራተኛ ሆስፒታሉን ።

አምስተኛ የባንያንን ተማሪ ቤት ጐበኙ ።

የካቲት ፱ቀን በ፲፪ሰዓት ከድሬደዋ ተነሥተው የረር ጐታ ባለው ጠበል ሲጠመቁ ቈይተው በ፳ሰዓት ከሩብ ከየረር ጣቢያ ተነሥተው በ፲፩ሰዓት ሚኤሶ ጣቢያ ደረሱ ።

ከዚህም በአቶሞቢል ሁነው የዓሰበ ተፈሪን ከተማ እንዲያዩላቸው አዛዥ ወርቅነህ ለምነው ነበረና ፲፩ ሰዓት ከሰፈ በኋላ ተነሥተው ማታ ዓሰበ ተፈሪ ገቡ ።

ከተሰለፈውም ወታደር በቀር በከተማው ያለ ሕዝብ ወንዱም ሴቱም ሳይታዘዝ በገዛ ፈቃዱ በየበታው አቅጣጫ ተሰልፎ ይጠባበቅ ነበረና አስቀድሞ የሔደው ከሚዎን ድምፅ ሲሰማ ጀምሮ የጃንሆይ አቶሞቢል እስኪመጣ ድረስ እልልታው ሳያቋርጥ ፩ሰዓት ድረስ ቈየ ዓሰበ ተፈሪም አድረው በማግሥቱ በየካቲት ፲ቀን በ፲፪ሰዓት የቅዱስ እግዚአብሔር አብን ቤተ ክርስቲያን ከተሳለሙና በየክፍሉም ያሉትን የሥራ ቤቶች ከጐበኙ በኋላ የእግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን ለከተማው ሕዝብ እጅግ ርቆት ነበርና እዲረከተሩ በታ ላይ ተዛውሮ እንዲሠራ አዘዙ ከዚህ በኋላ ወደሚኤሶ ጣቢያ ወርደው እንደገና በከ የሚባለውን ያባታቸውን የልዑል ራስ መኰንንን ርስት እንዲያዩለት ለዚሁ ሥራ የተሾመው አቶ ሰይፉ ለምኖ ነበረና ወደዚያው ሔደው የሠሩትን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ቤተ ክርስቲያን ከተሳለሙ በኋላ በዚሁ በርስታቸው ውሥጥ ያለውን ቡንና ልዩ ልዩ የሆነ ልምላሜውና ፍሬው የሚያስደንቀውን አትክልት ጐበኙ

ከዚህም በኋላ ለተከታዮቻቸው መሳፍንትና መኳንንት ሁሉ መልከም ግብዣ ተደርጎ ሁለተኛም አስቀድሞ ያልታየውን አትክልት ጐብኝተው ወደሚኤሶ ተመለሱ ።

ከሚኤሶ በ፲ሰዓት ተነሥተው ከማታው አዋሽ በ፫ሰዓት ገብተው አደሩ በየካቲት በ፲፩ሰዓት ተኩል ከአዋሽ ተነሥተው በ፯ሰዓት ሞጆ ገብተው ለተከተላቸው ሠራዊት ምሣ ተደርጎ በ[illegible]ሰዓት አዲስ አበባ ገቡ ።

ከጅቡቲ እንሥቶ አዲስ አበባ እስኪገቡ ድረስ በየጣቢያውና በየመንገዱ ዳር በጐበኙዋቸውም ቦታዎች ሁሉ ሕዝቡ እየተሰበሰበ እልልታው ከልክ ያልፍ ነበረ ።

አዲስ አበባም ሲገቡ ታላላቁ መኳንንት ለጋር የጦር አለቆችና ወታደሮችም በአቶሞቢሉ መንገድ ግራና ቀኝ ተሰልፈው ይጠብቁ ነበርና ባቡሩ እንደደረሰ ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ወደተዘጋጀው ስፍራ ከሆኑ በኋላ እንደማዕርጋቸው ሰላምታ አቀረቡ ።

ከዚህም ቀጥሎ በአቶሞቢሉ መንገድ ግራና ቀኝ የቆመው ሹማምንትና ሠራዊት ሰላምታ እያቀረበ ወደቤተ መንግሥቱ ገብተው ወዲያውም ከልፍኝ አዳራሽ ተገኝተው ከወታደር እስከ መኳንንትና መሳፍንት ጠጅና ሸምጋኝ ተጠጣ ።

ከዚያም ቀጥለው ወደሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሔደው ተሳልመው በ፲፪ የካቲትም በ፲፪ሰዓት አቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሔደው ተሳልመው የመንግሥታቸውን ሥራ ጀመሩ ።

አንባቢ ሆይ በወረቀት መጻፍና በዓይን ማየት ትክክል አለመሆኑ ከማንም ሰው የተሰወረ አይደለምና ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በመናፈስ ምክንያት ከአዲስ አበባ ወደ ጅቡቲ ከሔዱበት ቀን ጀምሮ የአንድ ሰዓት ስንኳ የዕረፍት ጊዜ አለመኖሩን ያየ ሰው እንዴት በተደነቀ ነበረ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽም በየካቲት ፲፱ ቀን ጂቡቲ ይደርሳሉ ። ስለዚህም ተቀባዮች በዚሁ ጃንሆይ በመጡበት ቀን ከሌሊቱ በ፫ ሰዓት ወደ ጂቡቲ ወርደዋል የተቀባዮችንም ስም እንዳንዱን ቀጥለን እንጽፋለን ።

ልዕልት ዘነበወርቅ ኃይለ ሥላሴ፣ ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው የአገር ግዛት ሚኒስትር፣ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ የጽሕፈት ዋና ዲሬክተር፣ የሻቃ በልሁ ሁለተኛው የአልፍኝ አስከልከይ የቀሩትም ብዙ ሰዎች አሉ በዚሁ ሰሞን ይገባሉ ብለን እንጠብቃለን ብርሃንና ሰላም በደኅና መግባታቸውን ይመኛል።

በሎንዶን ከተማ የተደረገላን ክብር

በጥር ፫ቀን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንና ልዕልት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ሎንዶን ገቡ ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ክቡር ደጃዝማች አበራ ካሣ ክቡር ልጅ ዮሐንስ ኃይሉና ብዙዎች ሌሎች መኳንንቶች ተከትለዋቸው ነበር።የኢትዮጵያ መላክተኞች ዶቬር እንግሊዝ ጠረፍ ሲቀርቡ ሐያ አንድ ጊዜ መድፍ ተተኰሰላቸው ከዶቬርም በልዩ በተሰናዳላቸው ባቡር ገብተው ወደሎንዶን ተነሡና ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስተር ለንግሡ በዓል ወደ አዲስ አበባ መጥተው የነበሩት የግርማዊ ጆርጅ ፭ተኛ ልጅና ክቡር ሰር ጆን ሳይሞን የእንግሊዝ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከብዙ ሹማምንቶች ጋራ በባቡር መቋሚያ ሆነው ይጠብቁ ነበር የልዑል አልጋ ወራሽ ባቡር ሊገባ ሁለት ደቂቃ ሲቀረው ለዓይን የሚያስፈራ ብርሃን ተጣለ።ባቡሩም በተቈረጠው ሰዓት ደረሰ ልዑል አልጋ ወራሽም እንደወረዱ ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስተር ቀርበው እንኳን በደህና ገቡ ብለው ሰላምታ አቀረቡላቸው ቀጥሎም መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ልዕልት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅንና የቀሩትን መኳንንቶች ከእንግሊዝ ንጉሥ ልጅ ጋር አስተዋወቁ ከዚያም በኋላ አቶ በቀለ የእንግሊዝን ሹማምንቶች እያቀረቡ ከአልጋ ወራሽ ጋር አገናኙ። በባቡሩ መቋሚያ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት ልጆች ለማየት የመጡ ብዙ ሰዎች ነበሩ ግፊያም እንዳይበዛ ዘበኛ ያግድ ነበር በሎንዶን ያሉ የኢትዮጵያ ተማሮች በደረጃው ላይ እንዲቆሙ ተፈቅዶላቸው ነበርና ከግፊያው ዳኑ

ወይዘሮ ተስፋ ይልማ ያዌ ቴዎድሮስ ዘመድ የኢትዮጵያን ባንዲራ በትልቁ አሰፍተው ለብሰው ወደ ጣብያ ሔዱ ኢትዮጵያን እንደዚህ አድርገው መውደዳቸው ልባችንን ነክን ሰውም ሁሉ በብዙ ደስ አለው የመንግሥትም መቀበያ ደንብ ከተፈጸመ በኋላ በኢትዮጵያ ባንዲራ ያጌጡ አቶሞቢሎች ቀረቡ የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽና መልክተኞች እንደማዕርጋቸው ተቀምጠው የእንግሊዝ መንግሥት ወደአሰናዳላቸው ሆቴል ተጓዙ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን የእንግሊዝ መንግሥት አልጋ ወራሽ ማታውን ሻይ ጋብዘውአቸው ነበር። በማግሥቱ የእንግሊዝ ንጉሥ ግርማዊ ጆርጅ ለምሳ ጋብዘዋቸው ከዚያ ቀን በኋላ እንደተሰናዳላቸው የኢትዮጵያ መልክተኞች ሎንዶንን እየዞሩ አዩ። በሎንዶን ያለ የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ ክብር የዲፕሎማቲክ ሰዎችንና ብዙዎችን የእን

ግሊዝ ታላላቅ ሰዎች ለእራት ጠርተው ነበር።ይህ ግብዣ በደኅና እንዲፈጸም አቶ በቀለ በብርቱ ሲለፉ ይታዩ ነበር። ስልሳ አንድ የሚያህሉ እንግዶች ነበሩ ። በእነዚህም መከከል የጀርመን አምባሳደርና ክቡር ሰር ጆን ሳይሞን ነበሩ። የውጭ አገር ምስለኔዎች የለበሱት የማዕርግ ልብስ በሌላ ጊዜ በጣም ይደነቅ የነበረው ከኢትዮጵያ መኳንንት ልብስ ጋር አጠገብ ለአጠገብ ሲታይ ትልቅ ልዩነት ተገለጸ ።

መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን በጣም መልከ መልካም ናቸው። ዝናቸው በሎንዶን አስቀድሞ ስለተሰማ በሐዲቡት ሁሉ ዓለም ይከተላቸው ነበር ። ከዚህም ስጦታ ጋር አልጋ ወራሽችን ግርማ ሞገስ አላቸው።አስተያየታቸውና አካሔዳቸው በማናቸውም ጊዜ የማስተዋልና የጥበብ ነበር ። በጣቢያ የተተከሉት መብራቶች በብዙ ከማንጸባረቅ የተነሣ በልዑል አልጋ ወራሽ አጠገብ የቆሙትን ሁሉ ሲያስቸግሩአቸው በእርሳቸው ላይ ምንም የመቸገር ምልክት ስላልታየባቸው አንድ ጋዜጣ ወትሮውንም ብርሃን ብርሃንን አይጎዳውም አለ።

ልዕልት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅም ልክ እንደ ወንድማቸው ሎንዶንን አስደነቁ፡ ሁለቱም ከባቡር ሲወርዱ የኢትዮጵያን ልብስ ለብሰው በጣም ያማረ ነጭ ካባ ደርበው ነበር።መልካቸው እንደ አልማዝ ጥሩ ስለሆነ የሎንዶንን ሰዎች አስደነቁ።የሔዱበትም ሁሉ ሰዉ ሊያያቸው ብዙ ሰዓት ይጠባበቅ ነበር ። ልዕልት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ በአነጋገራቸው ልክ እንደ ዲፕሎማቲክ ሰዎች ናቸው። የኢትዮጵያ መልእክተኞች ሁሉ በአካሔዳቸው አገራቸውን በጣም አስመሰገኑ። የእንግሊዝ መንግሥት እንደዚህ አድርጎ የንጉሠ ነገሥቱን ልጆችና መልእክተኞችን መቀበሉ በሁለቱ መንግሥቶች መካከል ያለውን የዝምድና ስፋት ይገልጻል።ይህም ዝምድና ለሁላችንም ጥቅም እየበረታ እንዲሔድ እምነት አለን ። የዓለምን ዋና ከተሞች በክብረት ዞረው ያዩት መልእክተኞች ያገራቸውን ችግር ልብ እያደረጉ የሚጠቅማትን ነገር ይዘው እንዲመለሱ ምኞታችን ነው ።

አ ብሩ ።

ማመልከቻ ለክቡራን የኢትዮጵያ ልጆች ።

ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ወደጥንት ማዕርጓ ተመልሳ ከታላላቅ ነገሥታት ጋር ትክክል ስለሆነች ለክቡራን ጌቶቼ ለኢትዮጵያ ልጆች የምስራች ብዬ በብርሃንና ሰላም አመልክቼ ነበር። አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ ለምለሚቱ ሀገራችሁ ከጥንት ማዕርጓ ስለበለጠች ለክቡራን ጌቶቼ ለኢትዮጵያ ልጆች የምስራች አላለሁ ። ኢትዮጵያም ከቀድሞ ማዕርጓ መብለጧ ምክንያቱ እንደዚህ ነው ሁላችሁም ታውቃላችሁ። ከኢትዮጵያ ነገሥታት አንድ ንጉሥ እንኳን ወደ አውሮፓ ሀገር የሔደ የለም።አሁን ግን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሁኖ ኢትዮጵያን ከጥንት ማዕርጓ ከፍ ከፍ ለማድረግ በቸርነቱ አስቦ የዓለምን ተስፋ የአፍሪካን ንጉሠ ነገሥት ምሥራቃዊ ንጉሥ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በቀኝ አስነሥቶ እነሆ መንግሥቱ ሰፍቶ ሕዝቡ ተስማምቶ የከተማው ፅዳት የሠራዊቱ ንቃት ይኸውና በግልጽ ይታያል ። ደግሞም በቀድሞ ንጉሦቻችን ጊዜ ቴሌግራፍ ማን ፌልና አይሮፕላን የለም ነበር።ከሁሉም ነገር የሚያስደንቀው የኢትዮጵያ ዋና ተአምሩ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥቱ በዳዊትና በሰሎሞን መንበረ ዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጠው የኋላው ንጉሠ ነገሥት የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ከተመሰገኑ ከኢትዮጵያ ነገሥታት ልጆችና ከክቡራን መኳንንት ጋር ሁነው ወደ አውሮፓ ጕዟቸው ቀጥሎ የተጻፈው ነው ። መጀመሪያ ልዑል መርዕድ አዝማች ከኢትዮጵያ ክቡራን መኳንንትና ከእኅታቸው ከልዕልት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ጋር ሁነው ወደ ምስር ከተማ ሲገቡ የምስር ንጉሥ ቀዳማዊ ሡልጣን ፉዓድ በክብክብና በብዙሓ ፈረስ ሰልፍ በደስታና በይባቤ ያለመጠን አክብረው ተቀበሏቸው ። ደግሞም በተለየ ሥራ የተሠራ ያለመጠን በተጌጠ በንጉሡ ቤት ተቀበሏቸው ከዚያም በኋላ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን ለመቀበያ በተዘጋጀው ቤት ንጉሡና ሊቀ ጳጳሱ እየሔዱ ጠየቁ ። ንጉሡም ለራሳቸው የፈረስ እሽቅድድም መመልከቻ በጌጥ የተሠራውን ሰገነታቸውን ለልዑል ፈቀዱላቸው ልዑልም እስከ ክቡራን መኳንንቶቻቸው አንድ ቀን የፈረሱትን መቀዳደም ሲመለከቱ ዋሉ ለልዑል የተሠራው ማዕርግ ክብር ብዙ ነበር። በነጋውም አራዊት ያሉበትን ደሴት ለመመልከት ሒደው ነበር ። በምስር ከተማ ከፈርዖን ዘመን ጀምሮ ያለውን አንቲካ ቤትም አይተዋል ። እንዲያው በጥቅሉ የምስር ንጉሥ ቀዳማዊ ሡልጣን ፉአድ ልዑል መርዕድ አዝማችን እንደአንድ ልጃቸው አድርገው በታላቅ ፍቅር ተቀብለዋል ። የኢትዮጵያና የምስር ፍቅር የጸና የበረታ መሆኑ በዓለም ላይ ሁሉ የታወቀ ሆነ ። ይኸውና የአይሮፓ ጋዜጣና መጻሕፍት በልዑል መርዕድ አዝማችና በመኳንንቶቻቸው ሥዕልና ታሪክ የመላ ሆነ ። ደግሞም ኢትዮጵያ ከቀድሞ ማዕርጓ በለጠች ያልኩበት ሌላም ምክንያት ይገኛል ። ዳዊት ከመንግሥቱ ቤት ሲወጣ ሕዝቡ ይናወጥ ነበር ። ደግሞም ሰሎሞን ሲወጣ እንደዚያው ይናወጥ ነበር ። ዳዊት ሲወጣ ሰሎሞን ነው ሰሎሞን ሲወጣ ዳዊት ነው ይባል ነበር።አሁንም በኢትዮጵያ መንግሥት እንደዚሁ ሁሉ ሁኑዋል ደግሞም የአጼ ሰይፈ አርዕድ ልጅ ዳግማዊ ዳዊት ሳዕላይ ግብጽ ድረስ ዘምተው የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ተቀብለው በወሎ ሀገር በአንባሰል አውራጃ ግሸን ተራራ ላይ አስቀመጡት ያችም ያንባሰል ተራራ እጅግ የተባረከች ቦታ ናት ይኸውና እንደዚህ ያለ አበባ ይገኝባታል ። ደግሞም ታላቁ ነገር የሚደንቀኝ ወሎ የእስላም አገር ነው መባሉ ነው ግማደ መስቀሉ ያለው ወሎ ላይ ነው ወሎ ዋና የክርስቲያን አገር ነው እንጂ የእስላም አገር አይደለም ።

ግራኝ ራሱ ግሸንንና መካነ ሥላሴን በታሪኩ ላይ ሲናገር የክርስቲያን አገር መሆኑን መስክሯል ወደመጀመሪያ ሐሳቤ ልመለስ የንጉሠ ነገሥታችንን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ልጆች ልዑል መርዕድ አዝማችንና ልዕልት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅን፥ አብረው ያሉትንም ክቡራን መኳንንትን በአይሮፓ እንደተከበሩ እንዳማሩ ታሪካቸው በየጋዜጣው ላይ ሁሉ

ተመስግኖ እንደተጻፈ አበባ እንደሆኑ ወደ መንግሥታቸው ወደ ኢትዮጵያ ሀገር በሰላም እንደመለሱ የነገሥታትን ሁሉ ንጉሥ የጌታን ሁሉ ጌታ አምላካችንን መድኃኔ ዓለምን እንለምናለን።

ታዛጋር አሽከራችሁ ዓረቢ አስተማሪ ወልደ ሥላሴ ።

የሚያሳዝን ሞት ።

አዲስ ያትክልት ቡቃያ የመሰለች ለጋ ወይዘሮ አሰገደች የቀኛዝማች አስፋው ልጅ የደጃዝማች ይልማ መኰንን የልጅ ልጅ አንድ ዓመት ሙሉ እንደሳል ያለ በሽታ ታማ ቢተወለደች በ፲፯ ኀመቷ በተዳረች በሁለተኛው ዓመት የካቲት ፲፩ ቀን ሙታ ወዳጅ ዘመዷዋ ሁሉ ተሰብስበ አልቅሰላት ብዙ መኳንንትና ሴት ወይዛዝር ተሰብስበው አዝነውላት በሚያስደንቅ የጉዞ ፍታት በብዙ ክብር በዚሁ በሞተችበት ቀን በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ባበትዋ መቃብር ተቀበረች ፤አዝነው እንደሚገባ አድርገው ከስቀበሩም መኳንንት ጥቂቶች ስማቸውን ያወቅናቸውን ከዚህ በታች እንጽፋለን ።

ክቡር ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል፣ ደጃዝማች ነሲቡ፣ ደጃዝማች ታፈረ፣ ደጃዝማች በላቸው፣ አዛጋር ደርሶው፣ ፊታውራሪ ሣህሉ ፤ ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ፣ ከንቲባ ገብሩ፣ፊታውራሪ ወልደ ጊዮርጊስ፣ ቀኛዝማች ቡኔ ፤ እነዚህ ናቸው ። ሌሎችም ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር ነበሩ። እጅግ የሚገርም ነገር አለ ዘር ከዛብ ይጠቅሳል እንደ ሚሉት ተረት የቀድሞ እያቶቿን ደግነት ይዛ የሕግንነት በሕርይ ሳያሸንፋት ከሕግ ባልዋ በሥጋ አምላክ ተወስና መሞቷ በጣም ይደንቃል ። ከዘመዶችዋም አንዱ ልጅ ሰይፉ ተሰማ ከዚህ በታች ያለውን የልቅሶ ግጥም ገጠመላት ።

ጥንቱን ባልተሠራሽ ዘመድ ባላየሺ ።
አሰገደች አስፋው ብቅ ብለሽ ጠፋሺ ።
ወጣት ቡቃያችን ብለን ስናያት ።
ሞት የሚያልፍ መስሎ ቀጥፍ አረጋት ።
ምን ያለው ጨካኝ ሞት በክፉ ዓይን አየብን ።
ቀምበጥ ቡቃያዋን ምን ሲል ቀጠፈብን ።

እንዲህ ያለች ቅን ልብ ያላት ወይዘሮ በሕፃንነትዋ ዘር ሳትተው ታይታ መጥፋቷ እጅግ ያሳዝናል።ወዳጅ ዘመዶችዋን እግዚአብሔር ያጥናችሁ፣ ይልቁንም እንዳባት ሁነው አሳድገው የዳሩ አጐትዋ ፊታውራሪ ባንተ ደደሩንና ባለቤቷን ቀኛዝማች ካሣን እግዚአብሔር ያጥናቸው።ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ዘ አ

የሚያስቅ ጨዋታ ።

አንድ ጂዖግራፊ የተማረ ሰውና ያቶ ውስኪ ምስክርነት ።

አቶ ውስኪ በትልቅ ሆቴል ውሥጥ ይኖራሉ ሲባል በሰማ ጊዜ ይህ ጂዖግራፊ የተማረ ሰው በትምህርት ቤት ሲማር ቅር ያለው ነገር ነበርና ሊጠይቃቸው ሔደ ።

ጤና ይስጥልኝ አቶ ውስኪ፣ ወዴት ከርመሃል ወዳጄ ምነው እስተዛሬ ጠፋህብኝ ። እስተዛሬ ድረስ መቼም አላውቅዎትም ነበር ከዝናዎ በተቀር። ትምህርት የሚሉት ዘበኛ ከልጅነቴ እስተዛሬ ድረስ እስሮኝ ዛሬ ጓን ቢለቀኝ ጂዖግራፊ የሚሉትን ትምህርት ጨርሼ ትንሽ ቅር ያለኝን መስመር እንዲያስረዱኝ ልጠይቅዎት መጣሁ ፈቃድዎ ቢሆን ።

ወዳጄ ሆይ እንኳን ልትጠጋኝ መጥተህ እኔው በአቶ ሽታ ብጋ ለመጠጋት እፈቅዳለሁ ነገሩ ምንድርነው በተማሪ ቤት ሳለሁ መሬት ትዞራለች እያሉ አስተማሩኝ ከተወለድሁ አንድ ጊዜም ስትዞር አላየኋትም እባክዎን ይህችን መስመር በጭሩ ያስረዱኝ

ዋ ዋ ወዳጄ እንኳን ይህን አጭሩን ነገርና ብዙውን የማስረዳ ነኝ ቁጭ በል ጥቂት ስንጫወት ያለውዴታህ ትረዳዋለህ ምንም አትቸገር።በዚያን ጊዜ ሰውዬው ከአቶ ውስኪ ጋራ ተቀምጦ ሲጫወት ጊዜው መሽቶበት አሁንስ ያሰናብቱኝ ብሎ ገና ሲነሣ እንደተባለው መሬቱ ሲዞር ታየው።ወይ ጉድ ከብልህ የዋለ ብልህ ነው እያለ ከቤቱ ሲወጣ የሰልኩን ምሰሶ አንቆ ቆመ። ወዲያው ዘበኛ ቀርቦ እንዲህ አለው ሰውዬው ጊዜው መሽቷልና ወደ ቤትህ አትገባምን? ቢለው ዋ ዋ ጌታዬ ባታውቅ ባትማር ነው እኔ ከተማሪ ቤት ሳለሁ መሬት ትዞራለች ብለው ሲያስተምሩኝ ቀልድ መስሎኝ ዛሬ ተረዳሁት።ስለዚህም የቤቴ ደጃፍ በዚህ እስኪታልፍ እጠብቃለሁ እንጂ አልሔድም ብሎ ሲጠብቅ አደረ ።አልቤር መሱላም።

ማስታወቂያ ።

ሙሴ ኤባንጀሎ ሐጂዋኑ መጀመሪያ በኢትዮጵያ የግሪክ ቆንስል ጄኔራል የነበሩት አሁን የአበከትነት ሥራ ይሠራሉ በአገራቸው ኪብሮስ በእንግሊዝ መንግሥት ፍርድ ቤትና ደግሞ በግሪክአገር የፍርድ ቤት ብዙ ዘመን ሠርተዋል ። ፍትሐ ነገሥት አዋቂ ናቸው።ለዚሁም አበከትነታቸውና ፍትሐ ነገሥት ማወቃቸው ዲፕሎም አላቸው ። ዛሬ የሚቀመጡበት ቤታቸውና ቢሮአቸው በጅሮንድ ዘለቀ አግደው ግቢ ነው ። ወደሳቸው የሚመጣ ሰው ከጥዋቱ ከ፪ት ሰዓት እስከ ፯ት ሰዓት ይቀበላሉ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ። ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አርጌ ሆና የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርደና የማዋለድ የሬብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርስቲያን ባታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሲንጀር ቅቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ሰጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም ብሲንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፭ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላኒዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።



ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኙና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲለሙሴ ኤ.አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም
ALEM



ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ አሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኜይ።

አበካት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም ዘአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S&E&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መድቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፲
8^me ANNE. № 10

ሐሙስ የካቲት ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
JEUDI 3 MARS 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ዜጣውንም የሚፈልጉ ለደሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት በፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያ መ አ ወ በደኅና መግባት ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ። በብርሃንና ሰላም ብዙ ጊዜ እንዳነበባችሁ ከእኅታቸው ከልዕልት ተናኘ ወርቅ ጋራ ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠውን፥ ክቡር ደጃዝማች አበራ ካሣን፥ክቡር ልጅ ዮሐንስ ኃይሉን ። የንግድ ሚኒስቴርን ክቡር ነጋድራስ ኃይሌ ወልደሩፌን፥ የአገር ግዛት ዲሬክቴር ክቡር ብላቴን ጌታ ወልደማርያምን፥ አቶ ማህለማርያምን ዋና አስተርጓሚና ጸሐፊ አድርገው፥ሌሎችንም የሚአገለግልዋቸውን አስከትለው ሮፓን ሁሉ ዞረው አይተው ነገሥታትም በብዙ ክብር ተቀብለዋቸው በየካቲት ፲፬ ቀን ጂቡቲ ደረሱ።የጂቡቲውም ገዢ በሥርዓት ተቀበሉዋቸው።በዚያን ጊዜም ክቡር ቢቶደድ ጌታቸው አብረዋቸው አልጋ ወራሽን ለመቀበል ከሔዱት ከክቡራን መኳንንት ጋራ ከመርከቡ ገብተው አልጋ ወራሽን ከተገናኙ በኋላ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ

ልዑል ሆይ ።

ዛሬ በዚች በዕድለኛዋ ቀን ከልዕልት እኅትዎ ጋር ከውሮፓ ጕዞዎ በሕይወት ተመልሰው በማየቴ ደስ ብሎኛል ይህ ክብር ያለው ታላቅ ጕዞዎ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከባትዎ ጕዞ በታሪክ ሁለተኛ ሁኖ ሊጻፍ የተገባ ነው ። ልዕልናዎም በኃይልና በዕውቀት የፀኑትን ነገሥታት መንግሥት በጕበኙ ጊዜ ለኢትዮጵያ በጥልቅ ሐሳብ እንደሚያስቡላት ይሰማኛል።

ልዑል ሆይ ።

በሃገርዎ ሳሉ በትምህርት ቤት በንባብና በጽሕፈት አስተከክለው ያወቁትን ዛሬ በዓይንዎ አይተው አስረግጠውታል የትምህርት ቤት በመክፈትም በንግድ ማስፋትም ቢሆን አጥብቀው ይረዱናል ስንል ታላቁ ተስፋችን ይህ ብቻ ነው ።

ልዑል ሆይ ።

ለኔም ይህ እንደዛሬው ያለ ክብር ሲአጋጥመኝ ሁለተኛ ጊዜ ነው ። እነሆ የዛሬ ፰ ዓመት ጃንሆይ አባትዎ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ እንደዚሁ ሁሉ ያውሮፓን መንግሥታት ጐብኝተው በተመለሱ ጊዜ በዚሁ በባሕር ጠረፍ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በክብር ተልኬ የተቀበልኋቸው እኔ ነኝ ደግሞ ዛሬ ይኸው ክብር ሁለተኛ ስላጋጠመኝ ደስታዬ መጠን የለውም ስለዚህ በታሪክ መጽሐፍ ውሥጥ እንደዚሁ ሁኖ ሲነበብ ለኋላ ለልጆቼና ለወገኖቼ ክብር ያለው መላከተኛነቴን የሚገልጽ ነውና ደስታችን አያቋርጥም።

ልዑል ሆይ ።

እነሆ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አባትዎና ፥ ከግርማዊት እናትዎ ከእቴጌ የተላከልዎን ደብዳቤ በእጅዎ እንዳስረክብና በክብር ልዕልናዎን ልቀበል ታዝዣለሁ በአዲስ አበባም ያሉት መሳፍንትና መኳንንት ሚኒስቴሮችና የጦር አለቆችም ሕዝቡም ሁሉ በደኅና በመመለስዎ ታላቅ ደስታ እንዳላቸው አሳስብዎ ዘንድ ይፍቀዱልኝ እኔም ራሴ እግዚአብሔር ወደ መልከሚቱ ሃገርዎ ወደ ኢትዮጵያ ከልዕልት እኅትዎና ከተከታዮችዎ ጋር እንኳን በደኅና የመለስዎ ስል ለልዕልናዎ የሚደርሰውን ከልብ የሆነ ሰላምታዬን ሳቀርብ እንዲቀበሉኝ አለምናለሁ ብለው ከጨረሱ በኋላ ልዑል አልጋ ወራሽ የሚከተለውን ቃል መለሱ ።

ክቡር ሆይ ።

በዲስኩርዎ እንደተናገሩት የገናኑን ያባቴን የንጉሠ ነገሥት መልእክት ለየታላላቁ መንግሥታት አድርሼ በደኅና ተመልሼ አገሬ በደኅና መግባቴና ከግርማውያንና ከተወደዱ ዘመዶቼ ለመገናኘት ሳበቃኝ አምላክ የማቀርበው ምስጋና ወሰን የለውም ።

እርስዎም ግርማዊ አባቴ እኔን ለመቀበል ስለላኩዎ እንደዚሁ የማቀርበው ምስጋና ወሰን የለውም።ይህነኑም መልእክት ስላደረሱልኝና በዲስኩርዎ ስለተናገሩት ቃል በፍጹም ልቤ አመሰግንዎታለሁ ብለው ጨረሱ ።

ከዚህ በኋላ በየካቲት ፲፰ ቀን በልዩ ባቡር ተሳፍረው በ፲፱ኛው ቀን በ፱ኝ ሰዓት አባቡር መቋሚያ ደረሱ።የባቡሩ መቋሚያም በኢትዮጵያና በፈረንሣዊ ሰንደቅ ዓላማ (ባንዲራ) አጊጦ እጅግ አምሮ ነበር ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን ሚኒስትሮች፥ መኳንንትና ሊቃውንት፤የውጪ መንግሥታት ሚኒስትሮችና፥ቆንስሎች፤በከተማም የሚኖሩ የሮፓ ሰዎች አጊጠው

የክብር ኒሻናቸውን ለብሰው በብዙ ክብርና ናፍቆት ተቀበልዋቸው።የባቡሩ መቋሚያ ውጪና ግቢው ሰልፍ በተማረ ወታደር ታጥሮ ነበር።ባቡር በደረሰ ጊዜ የኢትዮጵያ ማርሽ ተነፋ የቀረውም ወታደር ከባቡሩ ማረፊያ ጀምሮ እስከ ታላቁ ቤተ መንግሥት ድረስ በመንገዱ ግራና ቀኝ በአለቃ በአለቃው ተሰልፎ ነበር።እጅግ በአማረ አቶሞቢል ሁነው ሲአልፉ የሚገባ ሰላምታ እየሰጡ ያሳልፏቸው ነበር ።ከናፍቆትና ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ያብሩሁ ፊታቸው እንደ ሙሉ ጨረቃ ብርሃን ተጨምሮበት ሲአበራ ሕዝቡን ሁሉ እጅግ ደስአሰኘው።የከተማውም ሕዝብ ወንድ ወንዱ ጭብጨባውን ሴት ሴቱ እልልታውን ሲአቀልጠው ከተማው በሙሉ በደስታ ተንቃነቀ።

እንዲህ በሆነ ባማረ ሰልፍ ከታላቁ ግቢ ደረሱና ከግርማዊ ንጉሥ ነገሥት በተገናኙ ጊዜ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ።

ግርማዊ አባቴ ሆይ ፥

ወደ አውሮፓ ሒጄ የከበረውን መልእክትዎን አድርሼ፥ ከነገሥታቱም ጋራ ተዋውቄ፤ አውሮፓንም አይቼ በመመለሴ ለደስታዬ ወሰን የለውም ።

ይኸውም ያውሮፓ ጕዞዬ ግርማዊነትዎ በጀመሩት መንገድ ለኢትዮጵያ የሥልጣኔ እርምጃዋ የሥራ መሪዋ እየሆነ በታሪኳ ተጽፎ የሚገኝ እንዲሆን ተስፋ አደርጋለሁ ።

ዛሬም ተከትለውኝ ከሔዱት መኳንንት ጋራ በደኅና ተመልሼ አባባን ከመሳፍንቶችዎና ከመኳንንቶችዎ ጋራ በደኅና አግኝቼ በግርማዊነትዎ ፊት መቆሜ ለዘለዓለም መታሰቢያዬ ነውና ለዚህ ዕድል ያበቃኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ።

ወደፊትም እጅግ ለተወደዱ ግርማዊ አባቴ ረጅም ዕድሜ ከጤና ጋራ እንዲሰጥዎ ለኢትዮጵያም ልማትና ስፋት እንዲሆን ሳላቋርጥ ፈጣሪዬን እለምናለሁ ብለው ከጨረሱ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት የሚከተለውን ቃል መለሱ ።

የተወደድህ ልጄ ሆይ።

ገና በልጅነትህ የዕውቀትና የሥልጣኔ ምንጭ የምትሆን አውሮፓን በማየትህና ከታላላቁ ነገሥታት ጋራ እንድትተዋወቅ በማድረጌ እጅግ ደስ ብሎኛል

በልጅነት ያዩትና የተማሩት ፤ በልብ ተቀርጸ ይኖራልና፥ በዚህ አሁን ባየኸው የሥልጣኔና የዕውቀት ነገር ሁሉ ወደፊት ለኢትዮጵያ ልማት፤ ለሕዝቧ ሀብትና በረከት የሚሆን ሥራ ለመሥራት፥ እንደተማሬ ቤት እንዲሆንህ እመኝልሃለሁ

ዛሬም አንተና፤አንተንም ተከትለው የሔዱት መኳንንት በደኅና ስለመመለሳችሁና በፊቴ ቆማችሁ ስለማዬቴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ

እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜ እንዲሰጥህና መልካሙን ሥራ እየሠራህ ለኢትዮጵያ የምትጠቅም እንድትሆን የልቤን ምኞት እገልጻለሁ ብለው ጨረሱ ።

በሦስተኛውም ቀን በግቢአቸው ውስጥ ታላላቅ ድንኳኖች ተቀጣጥለው በሰፊው ቦታ ተተክለው ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለሊቃውንቱና ለወታደሩ ሙሉ ግብር አድርገው ዋሉ። በግብሩም ጊዜ የኢትዮጵያ መ አ ወ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን በተሰናዳው አጐበር ውሥጥ በተሰናዳው ዙፋን ተቀምጠው ከዙፋኑ እንዲቀርብ ከፍ ብሎ ተደልድሎ ልዑል ራስ ኃይሉና ልዑል ራስ ሥዩም በግራና በቀኝ ተቀምጠው በ፩ መሰብ ተጋበዙ ። የቀሩትም መኳንንትና ሊቃውንት በየማዕርጋቸው ተቀምጠው እጅግ የሚአምር ግብዣ ከተጋበዙ በኋላ መጋረጃው ተገለጠና በ፪ኛው ግብር የሽአምበሎች ገቡ።ከተጋበዙም በኋላ አርበኛ አርበኛው እየተነሣ ይፎክር ነበረ።በዚያም ቀን የኢትዮጵያ መ አ ወ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ለእንደራሴአቸውና ለሞግዚታቸው ለክቡር ደጃዝማች ወዳጄ እጅግ የሚአምር ሽልማት ሸለሟቸው።የሽልማቱም ዓይነት ቀጥሎ የተጻፈው ነው።ባለወርቅ ሰገጥ ቀሚስ፥ድርብ፥ ሙክሽ ጥልፍ ላንቃ የወርቅ ጋሻና ማለፊያ ጠመንጃ ይህን ሁሉ ተሸልመው ወደ ድንኳን መጥተው እጅ በነሡ ጊዜ የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ተነሥተው የሚነገተውን ታላቅ ክርዶን ኒሻን አደረጉላቸው በዚያ ጊዜ የደጃዝማች ወዳጄን አገልግሎት ያወቀ ሁሉ እጅግ ደስ አለው።እውነት ነው እኛም ከየናቸው ጀምረው እውነተኛ አገልጋይ መሆናቸውን እናውቃለን። ቀድሞ ተመርጠው የቤተ መንግሥት ዋና አጋፋሪ ሁነው በመልካም ፣ ለአገለገሉ ሊጋባ ተብለው የከፍተኛውን ደረጃ ማዕርግ ተቀብለው ሲኖሩ በዚሁ ብርታታቸውና አገልግሎታቸው ተመርጠው ለኢ መ አ ወ መርዕድ አዝማች ሞግዚትና እንደራሴ ሁነው ተሾሙ ወዲያውም እንደተሾሙ በመርዕድ አዝማች ግዛት ውሥጥ ካለው ለከተማ ቅርብ ወደሆነው አገር ሒደው አገር ያስቸገረውን ሌባና ወስላታ በምርምር ሰብስበው እያሠሩ ወደ ከተማ አስመጥተው የሚገባ ቅጣቱን ስለተቀበለ አሁን አገሩ ጸጥ በማለቱ የተቀበሉትን ምስጋና ከዚህ ቀድሞ በብርሃንና ሰላም አንብባችሁታል ዘንድሮም የኢ መ አ ወ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ወደ ሮፓ ከሔዱ ጀምረው ሌሊትና ቀን ተግተው ታላቅ ጥሩ ቤት በኖራና በጥርብ ድንጊያ በጥቂት ጊዜ ማሠራታቸውን አስቀድመን ጽፈንላችኋል የቤቱንም መሰናዶ ድግሱንም ስላሳመሩላቸው የኢ መ አ ወ ለሠራተኛ ዋጋ ይገባዋል የሚለውን የጳውሎስን ቃል ያውቃሉና የድካማቸውን ዋጋ ስለ ከፈልዋቸው ሰውን ሁሉ ደስ ያለው ስለዚህ ነው። እንዲሁም በልዩ ልዩ ሥራ የቆሙት ሠራተኞች ሁሉ እንደሥራቸው ዋጋቸውን ሳይቀበሉ አይቀሩምና በየሥራቸው እንዲተጉ ብርሃንና ሰላም ያሳስባል ።

እጅግ የሚያስደንቅ ግብር

ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ሚኒስትር ለሹመታቸው ማስመረቂያ እጅግ የሚያስደንቅ ድግስ ከጀመሩ ብዙ ቄይቶ ነበረ። የአደጋገሱን ዓይነት ለማየት ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ሁሉ እየሔዱ ያዩት ነበር።አሽከርና ገበር ሳያስቸግሩ ሥራውን ሁሉ የቀን ሠራተኛ እየቀጠሩ ያሠሩት ነበረ። በባቡር ማረፊያ ሁኖ ላየው ውኃ የሚቀዳው ሠራተኛው ብቻ ከቤታቸው እስከ ባቡር ማረፊያ በተራ ሲሔድ ደገርም ነበረ። ደልቁንም የሚሠሩት ቤቶች ማማር እጅግ ያስደንቅ ነበረ ግብሩ የሚደረግበትም ቀን ለሕዝቡ ሁሉ ናፍቆት ለማየት

ቸኵሉ ነበረ መቸም ቀን መድረሱና ማለፉ አይቀርምና ያ የተናፈቀው ቀን በየካቲት ፳ቀን ተጀመረ። ከጧቱ በ፫ ሰዓት ግርማዊት እቴጌ መነን ከልዑላት ልጆቻቸው ጋራ ባማረ አቶሞቢል ሁነው በጦር ዲሬክተር በክቡር ደጃዝማች ነሲቡና በታላላቅ መኳንንትና ወይዛዝር በብዙ አቶሞቢል ታጅበው ወደ ጦር ሚኒስትር ግቢ በደረሱ ጊዜ በታላቅ ደስታ በብዙ ክብር ተቀበልዋቸው ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትርም ለዓይን የሚያንጸበርቅ ጥሩ ላንቃ ለብሰው ታላላቆች የማዕርግ ኒሻኖቻቸውን በደረታቸው አድርገው፥ ታላቁን የሚነገተውን ንሽን አንግተው፥በወርቅ የጠለቀ ግምጃ ሱሪአቸውን ታጥቀው፥ የራስ ወርቃቸውን አሥረው እለመጠን አምሮባቸው ነበረ ። ፬ሰዓትም በሆነ ጊዜ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፍ ባለች በቅሎ ተቀምጠው በወርቅ የጠለቀ ግምጃ ጥላቸውን አሲዘው፥ልዑላን መሳፍንትንና መኳንንትንሚኒስትሮችን አስከትለው በብዙ ሠራዊት ታጅበው ብቅ ባሉ ጊዜ ፍልውኃ ሜዳ ሲደርሱ ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትር በላይኛው መስመር እንደጻፍነው በሚያስደንቅ ሽልማት ተሸልመው እጅ ነሥተው ተቀብለው ከፍ ባለች በወርቅ ዕቃ በአጌጠች በቅሎ ተቀምጠው በጃንሆይ ፊት ፊት ሰልፉን እየመሩ ዓጀቡ እጅግ አምሮ ነጋሪቱ እየተጐሰመ ወደጦር ሚኒስትር ቤት በደረሱ ጊዜ የኢትዮጵያ ማርሽ ተነፋ ገና በሩቁ ሲያዩት አጥሩ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ (ባንዲራ) አጊጦ የአጥር ግቢው፡ፊት እጅግ ያምር ነበረ ፫ቱ ታላላቅ ድንኳኖች በሰፊው ሜዳ ተተክለው ነበር ስፋቱም እጅግ የራቀ የጃን ሜዳ ተረክክሬ ነበረ ።

ለጃንሆይና ለግርማዊት እቴጌ መነን የተሰናዳው ቤት የቀለም አቀባቡና የቤቱ አሠራር ማማር ሕዝቡን ሁሉ አስደነቀው ።

ይልቁንም እቴጌ የነበሩበት በመስታዋት የተሠራው ፎቅ እጅግ ለመኖሯ የሚያስጐመጅ ቤት ነው የድግሱና የሥርዓቱ ነገር በዚህ ጊዜ ታይቶ ይታወቃል የሚል ሰው ቢኖር ዋሾ በተባለ ነበር ከመጋረጃ ውሥጥ ከተደረገው ከመኳንንቱ ግብር በኋላ የጦር ሚኒስትር ከመንግሥቱ ሊጋባ ከደጃዝማች ሀብተ ሚካኤልና ከዋናው አጋፋሪ ከልክሌ ጋራ ወጥተው የሺ አምበሎችን እየመሩ በአገቧቸው ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በሐሳባቸው ብርታት ተደነቀ የወጡ ዓይነትም ብዙ ነበረ።ይልቁንም ጮማው ሥጋ በወሳሳ ለሁለት ለሁለት እየተያዘ በቀረበ ጊዜ ከመረጠው ዓይነት እየቈረጠ ደስ እያለው አመሰግኖ መጠጥም የፈለገውን ዓይነት ሰው ሁሉ ያገኝ ነበረ ከተጋበዘም በኋላ አርበኛ አርበኛው ሲፎክር ጃንሆይንና መሳፍንቱን መኳንንቱን ሲአስደንቅ ዋለ ከ፬ት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዓሥር ሰዓት ድረስ በየተራ ሠራዊቱ ሲበላ ሲጠጣ ዋለ ዓሥር ሰዓት ሲሆን ጃንሆይ ከነበሩበት ዙፋን ተነሥተው ለሻይ ወደ ተዘጋጀው ወደ ታላቁ አዳራሽ ገብተው በአማረው ዙፋን ላይ ተቀመጡ የኢ አ ወራሽና ልዑላን መሳፍንት ሚኒስትሮችና መኳንንት ሊቃውንት በግራና በቀኝ በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር ከሻይም በኋላ ሺምፓኝ ቀረበና ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትር የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡና ዳር እስከዳር ፫ ጊዜ ተጨበጨበ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ።

እኔ አንደኛው አገልጋይዎ ዛሬ ታላቅ ዕድል ያገኘሁበት ቀን ስለሆነ ደስታዬን በግርማዊነትዎ ፊትና በሠራዊትዎ መካከል ልገልጸው እንዲፈቅዱልኝ እለምናለሁ ።

ጃንሆይ ።

በግርማዊነትዎ ቸርነት ዛሬ እኔ ያገኘሁት ዕድል እስከ መቼም ድረስ ከልቤ የማይጠፋ ስለሆነ ምስጋናዬን አላቋርጥም።

ይልቁንም ግርማዊነትዎ ልመናዬ እንዲፈጸምልኝ ለሠራዊትዎ ያሰናዳሁትን ግብር ለማየት በፍቅርና በትሕትናዎ ብዛት ከባሮዎ አዳራሽ ስለመጡልኝ የደጎቹን አባቶች የነአብርሃምን መልክም ዕድልና በረከት እንዳገኘሁ ያሀል እቈጥረዋለሁ ።

መቸውንም ግርማዊነትዎ በተቻለዎ ሁሉ እኛን ደስ ለማሰኘት አንድ ጊዜም አልበዘነም ይልቁንም ለኢትዮጵያ በሚጠቅመው መሠረት እኛን ለመምራትና ሕዝብዎን ከትልቁ የሥልጣኔ ደረጃ ለማድረስ ሐሳብዎ ጥልቅ መሆኑን በየጊዜው በሚገልጹልን በጎ ሥራዎ ላይ እንመለከተዋለን ።

ቅንነትን በፍጹም ገንዘብዎ ስላደረጉ ዕውቀትንና ፍቅርን አስተባብረው በነዚህ በሚታመኑ መሣሪያዎችዎ የሰውን ልብ ለመማረክና ለመግዛት ቻሉ ።

በቅንነት ሕገ መንግሥት አቆሙልን በዕውቀት ጥቅማችንን አሳመኑልን በፍቅር ኢትዮጵያን አስማሙልን ።

አሁንም ጃንሆይ እዚህ የተቀመጡልን እኛን ደስ ለማሰኘትና ለማስማማት ሲሉ እንደሆነ የሁሉ ልብ ይረዳዋል።

ለዓለም ሁሉ ትልቁ ጥቅሙ ፍቅርና መስማማት ብቻ ነው።

ግርማዊ ሆይ ።

የሰላምና የፍቅር አገራችን ከመላዋ አፍሪቃ በሥልጣንዋ ተለይታ የመንግሥታት ጓደኛ ሁና በነፃነትዋ ራሷን የቻለች በሃይማኖትና በፍቅር ያጌጠች ተወላጆችዋን የምታኰራ ባርበኞችዋ ወዳጆችዋን ደስ የምታሰኝ መሆንዋን በመረዳት ማንም ሳያስገድድዎ ከልጅነት እስከ ዛሬ ሕይወትዎን ሠውተውላታልና እስከ ኅልፈተ ዓለም የድካምዎን ፍሬ ከትውልድዎ ብቻ እንዳይወጣ ጥልቅ ምኞቴን ወደ እግዚአብሔር አላቋርጥም ።

ጃንሆይ ።

እኔም በዛሬው ቀን ዕድሌን ከሁሉ የበለጠ አድርጌ እቈጥረዋለሁ ስለዚህ ግርማዊነትዎ ባዘዙኝ ሥራ ላይ የማልሰንፍ በሚልኩኝ ሥፍራ የማላሳፍር ለሕይወቴ የማልሳሳ ባልጋዎ በለ ዘመኔ ሁሉ ጥርጣሬ የማላስገባ ቍርጠኛ ታማኝዎ መሆኔን ለመግለጽ እደፍራለሁ ለማለት አላፍርበትም ።

ነገር ግን ለግርማዊነትዎ የሚበቃና ደስ የሚያሰኝ ሥራ ምን ጊዜም ላገኝልዎ አልችልም ።

እግዚአብሔር በቸርነቱ በዕድሜዎ አቈይቶልኝ እነዚህን አርበኞችዎን ይዤ ለመንግሥትዎ ሕይወቴን አሳልፌ በደሜ ብድር ለመመለስ እንዲያበቃኝ እየተመኘሁ የማይረሳ የደስታ ምስጋናዬን ከዙፋንዎ ሥር አቀርባለሁ ።

ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለግርማዊት እቴጌ መነን ለመርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ሀብትና ጤና፥ለሠራዊቱ ፍቅርና ሰላም ይሁንልን ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ከዚህም በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡና የማያቋርጥ የጭብጨባ ድምጥ ከቤት ጀምሮ እስከውጪ ተሰማ ።

ደስታ በሁለት መንገድ ይደረጋል ። በይሉኝታና ከልብ በመሥራት፥ አንተ ግን በሚቻልህ ሁሉ እኔን ደስ ለማሰኘት ብለህ ከልብ ባደረግኸው እጅግ ደስ ብሎኛል ።

የአያትህም አገልግሎት ያንተም ቅንነት እንግዲህ ባንተ ላይ ተመስክሮአልና በሚቻልህ ሁሉ አሳቤን እየተከተልህ ከሥራህ ይህ መጀመሪያ ነው እንጂ መጨረሻው አይደለም ።

የሮፓ መጠጥ በየዓይነቱ እጅግ በዝቶ ነበር ። የጠጁማ ነገር ምን ይነገራል ጃንሆይና እቴጌ ከሔዱ በኋላ እንደገና ወደ ድንኳኑ ገብተው ግብር አድርገው አመሹ። በነጋው በየካቲት ፳፩ ቀን ለዘበኞች ግብር አድርገው ዋሉ ግብሩም እንደ ፊተኛው ቀን እጅግ ያማረ ነበረ ።

በየካቲት ፳፪ ቀን ከማታው በ፫ ሰዓት የኢትዮጵያ መኳንንት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን የኢትዮጵያ ሚኒስትሮችና ታላላቅ መኳንንት የውጭ አገር ዲፕሎማቲክ ሰዎች ተጠርተው ነበርና በዚያው በተጠሩበት ሰዓት ኒሻናቸውንና የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ መጥተው እንደ ሮፓ የሆነ ግብዣ ተጋብዘው የመጠጡንና የግብሩን ዓይነት ብዛትና መጣፈጡን አመስግነው የቤቱን ማዕርግና ሥራ እያደነቁ በ፭ ሰዓት ተሰነብተው በየቤታቸው ሔዱ ።

በየካቲት ፳፬ ቀን በየደብሩ ላሉ ካህናት ሁሉ ሙሉ ግብር ተደርጎ ዋለ ካህናቱም እጅግ አመስግነልዋ። በየካቲት ፳፮ ቀንም በየሥራ ክፍል ላሉ ዲሬክቴሮች ሁሉ ታላቅ ግብር ይደረጋል ።

ከዚህ በኋላ የግብሩ በዓል ይፈጸማል ይባላል ነገር ግን የለመደ ግብር ነውና ይለቃቸው አይመስለንም ።

ሐሳብ ።

የኢትዮጵያ የጦር ሚኒስትር በዚህ ግብር ምክንያት ያጠፋት ሁለት መቶ ሺሕ ብር ይሆናል በዚህም ድግስ ሙላት ምክንያት ብዙ ሰው ተንገላታብን ስለዚህ ይህ ግብር ቀርቶ በዚህ ገንዘብ አንድ ታላቅ መታሰቢያ በሠሩበት የሚሉ አሉ ።

እኛ ግን የጦር ሚኒስትር ሁነው ወታደር የማይወደውን መታሰቢያ ከማድረግ የሚወደውን አድርገውለታልና መልካም አስበዋል ብለን የክቡር ፊታውራሪ ብሩን የኢትዮጵያን የጦር ሚኒስትር አሳብ አመሰግንናል ።

ለመልካሚቱ አገር ጥንቃቄ ይገባል ፡

ባሌ ከላይ ከአሩሲና ከሲዳሞ፥ ከታች ከሐረርና ከበረና እየተዋሰነ ከጐረቤቶቻችን ጋር በፍጻሜው ያዋስነናል ። ሀገሩም ሜዳማ ደጋና ቈላ ስለሆነ ተወላጆቹ ሱማሌና ጋላ ናቸው በሃይማኖትም ደተበበራሉ ደሁን እንጂ ጥቂትም አጆዋዎች አሉባቸው። የዓለም ግብራቸውም ከብት ማርባት እንጂ ሌላ አያውቁም ማንኛውንም ተግባር አያውቁም ነበር። በሀገሩም የሚገኘውንና የሚረባውን እዱኛ ቀጥዬ ሳይበዛ በጥቂቱ ጽፌዋለሁ። ፈረስ፥በቅሎና ግመል፥ ላም በግና ፍየል፥ንብም አራዊት በያይነቱ ደረባበታል። ከመሬቱ ለአፍሪቃችን ሕዝብ የሚበቃ ጨው ይታፈስበታል ከመት ሁለት ጊዜ እሸትና ምርት ይበላበታል ከዛፉ ቡን ከርቤና ዕንሴ ይለቀምበታል። ይህም ዝናው እየደረሰላቸው በሹመትና በጌታ አዳር ምክንያት ብቻ ሳይሆን በሀገሩ መልካምነት እርሰን ነግደን ወጥተን ወርደን የጅ ሥራ ሠርተን ከብት አርብተን አግኝተን ተከብረን እንኖራለን እያሉ የዲፕሎማቲክም ሰዎች ከኢትዮጵያም ከየአውራጃዋ ብዙ ክርስቲያኖች መጥተው አብያተ ክርስቲያናትን አስተክለው ወልደው ስመውበት ከማጣት ወደ ማግኘት ከድኅነት ወደ ጌትነት ደርሰውበት ያለችግር ይኖሩበት ነበር። አገሬዎቹም የባይተዋሮቹን ተግባርና ትጋት እየተመለከቱ ሥራን ለምደው ነበር። የሀገሩን መልካምነት በስቀድሞው ወራት የዛሬውን ብርሃን ስላላገኘሁት የኔ አእምሮ ብርሃንና ሰላም ከሚባለው ከታላቁ ተራራ ላይ ቁሞ በፍጻሜ አስተካክሎ ሲናገረው አይችልም አሁንም ባልታረመው አእምሮየ ልጽፍ ያሳሰበኝ ይህ ነው ወስላታና ወምበዴ እንዳይበዛ መንግሥት የታመነ ሹምና ዘበኞች ቢአደርግበት የሚሻል መሆኑን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አስታውቃለሁ ። ደስታ አዳፍሬ ጊንር ።

ሥራ ለሠሪው እሾህ ለአጣሪው ።

በጊንር ከተማ አውራጃ በርበሬ በሚባል አገር መኰንን አስፋው የሚባል ወምበዴ ብቻውን እየሔደ በመንገድ አጠገብ እጫካ እየተቀመጠ በገበያ ቀንም ወጭ ወራጁን እየቀማ ብዙ ቀን ያስቸግር ነበረ ። ነድር አከፋፋዩ እግዚአብሔር የቈረጠው ቀን ሲደርስ ሐረር ምሥራቅ ፀሐይ ለኢትዮጵያ ማኅቶት ትጥዕም ፍሬሃ ለኵሉ ፍጥረት ። ከተባለችው ቡርክት ልዕልት ሀገር የመጣ ጊንር ከተማ በነጋዴ ሰፈር የሸኽ አንድሪስ ከዳሚ መሐመድ የሚባል ነበርና ጌታው ሸኽ አንድሪስ በርበሬ ወርደህ ጫት ገዝተህ ና ብሎው ሁለት መሐልቅ ሰጥተው ቢልኩት መሐመድም የጌታውን መልእክት ለመፈጸም መሐለቁን ተቀብሎ በርበሬ ወርዶ አለ እውቀት አህያ ገባች እጅብ ቤት እንደ ሚባለው ተረት ወምበዴው ባለበት ቤት ሳያውቅ ቢገባ ወምበዴውም በድንገት ስለገባበት ሰላይ የላከው መስሎት ከተቀመጠበት ተነሥቶ በሰደፍና በጥፊ ደብድቦ ወዲያው በግድ እየጐተተ ወደሚደበቅበት ዋሻ ወስዶ በኋላ አስምሎ አሽከርነት አሳድሮት ብረትና ዝናር ከነጥይቱ ሰጥቶት ፱ ቀን ያህል እየቀሙ አብረው ሰንብተው ነበርና በ፲ኛው ቀን መኰንን አስፋው የሚባለው የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ የተባለውን ተረት ዘንግተውና መድኃኒት ጠጥቶ ለበኑን ብረት ፱ ጥይት እንደጐረሰ ወደ ጓሮ ሲዞር ከአጠገቤ ቁም ድንገት ሰው የመጣ እንደሆነ ትሰጠኛለህ ብሎ ሰጥቶት ነበር ። መሐመድ የሚባለውም ያለፈቃድ በግድ ነበርና የወሰደው በገዛ ለበኑ በሁለት ጥይት ተኵሶ ገድሎት ወዲያውም መግደሉን ወደ ፊታውራሪ ይልማ እንደራሴ አቶ አበበ ወልደ ጊዮርጊስ ልከ ኋቶ አበበ ወልደ ጊዮርጊስም ለመላክተኛው ሰው በተሰናዳው ማዕርግ በታ ተቀምጬ አጠብቅሀለሁና ተሰልፈህ ወከዎ እያልህ እንድትገባ ብለው ለመላክተኛው ልከው ነበርና ፲፱፻፳፬ ዓመት ታኅሣሥ ፳ ቀን ከቀኑ ፱ ሰዓት ሲሆን የወምበዴውን ሬሳ በወሰሰ እፊት እፊት አስቀድሞ አሽከሞ ወከዎ እያለ ጥሩንባ እያስነፋ

እንደ አባቱ እየፈከረ ሲገባ እጅግ ያስደንቅ ነበረ እንዲያውም ክዚሁ ውሥጥ አንዳንዱ ሰው እኛም ሒደን ሽፍታ ፈልገን ገድለን እንሸለማለን እያለ ያስብ ነበረ ከዚህ በኋላ አቶ አበበ ወልደ ጊዮርጊስ ስለወምበዴው አሟሟትና ቀድሞ ሽፍታ ሁኖ መቀማቱን በጥንቃቄ መርምረው በእውነት ሽፍታ ወስታላ መሆኑ ከተመሰከረበት በኋላ ለመሐመድ ሽልማትም ሰጥተው የወስላታውን መሳሺ ሞርቀውለት ወኮዎ እያለ ወደ ቤቱ ሔደ የሽፍታውም ሬሳ ሕዝቡ እንዲያየው በከተማ ውሥጥ ፫ ቀን ወድቆ በ፬ቀን በከተማ ውጭ ተቀበረ ግን የዕድላሙ ንጉሥ የአፄ ኃይለ ሥላሴ አምላክ ቢረዳን ወደፊት ከወስላታና ከሽፍታ ሀገራችን ነፃ ትሆንልናለች ብለን ተስፋ አለን

ጊንር ጉምሩክ ፍርድ ጸሐፊ አበበ ተክሌ ዘብሔረ መንዝ ።

ስለዶክቶር ሩስ ሞት

ዶክቶር ሩስ የጀርመን ተወላጅ ከመጣ ቅርብ ጊዜ ነው በሕክምናው እጅግ ብልህ አወጣጡም ደማረ ጉበዝ ነበረ ይልቁንም በጠባዩ ማማር የከተማው ሕዝብ ሁሉ ይወደው ነበር ሰው ምንም ብልህ ቢሆን መጥፎአውን አያውቅምና ማሾ መብራት ሲአበራ ፩ ጣቱን ፈጅቶት እሱም ቀላል ነገር መስሎት ሳያስብበት ወደ ሰውነቱ ሁሉ መርዙ ተበትኖ ይልቁንም ወደ ልቡ ስለገባ ወዳጁ ዶክቶር ሐነር ቢደክሙ ሳይሆንላቸው ቀርቶ በየካቲት ፳፱ ቀን ብቤተ ሣይዳ ሆፒታል ሙቶ በጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበረ ዕድሜውም ገና ፴፮ ዓመት ነበረ ዘመዶቹንና ባለቤቲቱን መዳም ሩስን እግዚአብሔር ያጽናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል

ሊቁ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ።

የጃፓንን መንግሥትና የባሕር ወደቦች ደስያትን ሁሉ ጐብኝተው ነገሥታቱንና መሳፍንቱን ሊቃውንትና መኳንንትን ሕዝበና ሠራዊትን ደስ አሰኝተው ስለተመለሱ ጥቂቶች ምስጋናዎች በግዕዝ በዛ ያሉ አማርኛዎች እጽፋለሁ መቼም ቢሆን ግዕዝን አለመልቀቄ ሰውነታቸው ከጠና በኋላ የሰዋስው ምርመራ ያቃታቸው ትልቆች ሰዎች ሲያከፋፉት ሰምተው ወጣቶች እውነት መስሏቸው መሠረት ቋንቋ ለቀው እንዳይቃለሉ ነው እንጂ ላማርኛውስ ያማሬ ዘኢየሱስ ዘር እኔ ነኝ ዘላባም ለሚ ፈልጉ ቄጥሬ አስረክባለሁ ።

ኃይለ ሥላሴ ነግሠ ትትኀሠይ ምድር ወይትኀሠያ ደስያት ብዙኃት ።

ዓለም ጠቅልል ወንዱ ስማኝ ልንገርህ ። በሰው ፊት አደላክ ኅሩይ አሽከርህ ። እሱክ ብቻ ነው የሚያሳፍርህ ። የሚመክት የለም በፊትህ እንግዲህ ። ባሕረ ወጥ ከሆነ ያ ኅሩይ ሰይፍህ ። ብላቴን ጌታነው ለቁም ነገር ዋዛ ። ሰውን ሳያስቀይም በለዛ በለዛ ። ደም ማፍሰስ እንዲቀር ሰላም እንዲበዛ ። በኃይለ ሥላሴ ሁልጊዜ እንገዛ ። ፊደል መጀመሪያው አ እንደነበረ ። በጻያፍ የገባ ሀ ሁኖ እንደቀረ ። መኰንን ኢያቄም ፊደል የቈጠረ ። የፊደልን ብዙ ምሥጢር ተናገረ። ሁሉስ ምን ይረባል አራሚ ካልኖረ ። አለቃ መርሻ ዘ መ ኀ

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክቶር ጇ ኤ ማርቲኒ በፓሪስ ዩኒቬርሲቲ የተመሰከረላቸው።በዚሁ መታከሚያ ቤት የሴት በሽታ የልጆች በሽታ ፤ የዓይን በሽታ፤ የጆሮ በሽታ፤ የጒሮሮ በሽታ፤ ቂጥኝ ይህነን የመሰለውን ሁሉ በደኅና ያክማሉ። ቤታቸውም አራዳ ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ጧት ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ነው ። ከ፱ተኩል እስከ ፲፩ ሰዓት ያክማሉ ደክቶር ጇ ኤ ማርቲኒ ።

የንግድና የሥራ የኢትዮጵያ ማኅበር ።

ይህ ማኅበር ከዚህ ቀደም በያይነቱ የንግድ ሥራ የሚሠራ ስለሆነ አሁንም በንዚን፡ጋዝ ማዙትና ለመኪና ሁሉ የሚሆን ዘይትም ለማስመጣት ቍርጥ አድርጓልና ለማኅበሩ አማካሪዎች ደስታውን ያከፍላል እነዚህ ማኅበሩ የሚያስመጣቸው ዕቃዎች አሁን ባገር ውሥጥ ካለው በንዚን፡ጋዝ፡ማዙት፡ዘይትም ዓይነታቸው መብለጡ ብቻ ሳይሆን ዋጋውም በጣም እርካሽ ነው ።

ሐኪም አፊሊፕ በደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ አዲስ አበባ

ሐኪም አ ፊሊፕ በተለየ የሕክምና ሥራቸው በሎንዶን ከተማ በዋናው ሆፒታል የዓይኖች፡የጆሮዎች፡የአፍንጫ የጒሮሮ በሽተኞች ያክሙ የነበሩት አዲ አበባ ለማከም መጥተዋል

በዚሁ በከተማችን ውሥጥ አንድ ወር ብቻ ይቀመጣሉ ለመታከም የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ሁነው ዘወትር ይቀበላሉ ።

ሐኪም አ ፊሊፕ በሐኪምነታቸውና በመድኃኒቶቻቸው በዋናው የሕክምና ትምህርት ቤት ኢርላንድ አገር ደብላን ከተማ የምስክር ወረቀት (ዲፕሎም) ተቀብለዋል የምስክር ወረቀታቸውም ሕክምናቸውና መድኃኒቶቻቸው የሰው ራስ ፈዋሽ መሆኑን በሎንዶን ከተማ በታላቁ መንግሥታዊ ትምህርት ቤት የተመሰከረላቸው ናቸው።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጆማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዘ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሴንጀር ሕቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፣ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መስንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ናናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ ሕ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰጣ እሺቴ ሙዚቃ ሸከላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አበካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም ፀአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ጴልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፲፩
8me ANNE. № 11

ሐሙስ መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
JEUDI 10 MARS 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ሹምሽር ።

መምህር ተክሌ ራስ ወርቅ አሥረው ንቡረ እድ ተብለው አዲስ ዓለምን ተሾሙ ።

የላስታው መምህር ወልደ ሚካኤል ሊቀ ሊቃውንት ተብለው የራስ ወርቅ አሥረው መቃሰቢያ ቤትን ተሾሙ ።

መልአከ ገነት ወልደ ሐና መልአከ ሕይወት ተብለው የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትርነትን ተሾሙ ።

አለቃ ገብረ ክርስቶስ ባለፍትሐ ነገሥቱ ሊቄ (ሊቀየ) ተብለው ሊቀ ካህናትነትን ተሾሙ ። ወፈታሒስ ሊቀ ካህናት ውእቱ ያለው ተፈጸመ ።

የዓዲአንቀጠው መምህር ገብረ ሚካኤል ያዲስ አበባ ሥላሴን ተሾሙ።

መምህር ጽጌ ያዲስ አበባ ዑራኤልን ተሾሙ ።

መልአከ ገነት ክፍሌ አራዳ ጊዮርጊስን ተሾሙ ።

የመናገሻው መምህር ገብረ ጊዮርጊስ ያዲስ አበባ ገብርኤልን ተሾሙ ።

አለቃ ቀጸላ ያዲስ አበባ መድኃኔ ዓለምን አለቅነት ተሾሙ ።

ሊቀ ጠበብት ሀብተ ወልድ ያዲስ አበባ እስጢፋኖስን አለቅነት ተሾሙ ።

መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ዜና ማርቆስን ተሾሙ ።

እነዚህ ሊቃውንት የተሾሙ ዕለት እንደ የማዕርጋቸው የተሸለሙትን ለብሰው ከቤተ መንግሥቱ ብቅ ባሉ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እየተስፋፋች እንድትሔድ ተስፋ የሚያደርጉ ሁሉ እጅግ ደስ አላቸው ። እነዚህም የወንጌል ብርሃናት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብርሃን ስብከታቸውን እንዲያበሩላት እየተመኘ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል ።

ለጊዮርጊስ ሰንበቴዎች

ክቡራን ጌቶቼና ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ። አቶ ወልደ ሥላሴ አባቴ በዚህ ማኅበር ገብተው ሲኖሩ እሳቸው ለመንግሥታቸው ሥራና ለንብረታቸው ጉዳይ ዘወትር ወዲህና ወዲያ ይዞሩ ነበርና እኔ ባዬ ምኒልክ ተማሪቤት ነበርና ያለሁት በየሳምንቱ እየመጣሁ የደንባችንን ሁሉ እፈጽም ነበር አባቴም ባዲስ አበባችን ሲገኙ ሳያስታጕሉ ይመጡ ነበር ።

ጥቂት የፈረንጅ ትምህርት ከቀላወጥሁና በትምህርትና በመመርመር እንዲሁ ኤውሮፖች ለዚህ ሁሉ ብልሃት መብቃታቸውን ከተረዳሁ በኋላ አገራቸው ሒጄ እንዴት አድርገው እንዲማሩና እንዲመራመሩ ባይኔ ልይ ብልሃታቸውን ሁሉ በእጄ ልዳስ ስል ወደ ሰው አገር ልሔድባቸው የማይፈቅዱትን አባት ዘመዶቼን ሁሉ በድብቅ ተለይቼ ለመሔድ ቈረጥሁ።

ለመላ ኢትዮጵያችን ብርሃን የሆኑትንና የኢትዮጵያ ልጅ ይሁን እንጂ የእገሌ የገሊት የማይሉት ጃንሆይን ደጅ ጠንተን ከራት ባልንጀሮቼ ጋር ሁሉም አልቆ ልንነሣ ስንቀርብ ኃይለ ማርያም ተክሌ የሚባለው ጓደኛችንን የሰባት ቀን በሽታ እዚሁ አስቀረብን ።

የቀረነው ሦስታችን ድንጋጤው አሸንፎን ኃይላችን ሳያንስ መቼም የተፈጠርነው ለሞት ነውና ጊዜያችን እስቲደርስ ድረስ ወደፊት እንግፋ ስንል ኤሮፓ ለመሔድ በቃን ።

ከኤሮፓም አገሮች የኢጣልያን አገር ነክቶን ነበርና የዚህ አገር ነፋስና አየሩ ሙቀቱና ብርዱ ከኤሮፖች አገሮች ሁሉ በጣም ጥሩና ለጤና የተመቸ ነው ።

ይኸውም ቢሆን ወደ ጀርመንና ወደ ፈረንሳዊ አገር ያለው የኢጣልያንም አገር የነበርንበት የቶሪኖ ከተማ በጣም ብርዳም ስለሆነና የኰሌጅም ኑሮ በጣም ጠንካራና የልፋት ኑሮ ስለሆነ አንደኛው ጓደኛዬ ፈለቀ ወልደ ሐና የሚባለው በምኑም በምኑም ሰበብ የሳንባና የሳል በሽታ ይዞት ካንድ ዓመት በኋላ ለሞት ቢያደርሰው እዚሁ ተመልሶ እሆፒታላችን አረፈ ።

እኔና ሚካኤል ተሰማ የሚባለው አገሩን በቅጡ ካወቅነው በኋላ ነፋሱና አየሩ ወደሚስማማበት ቦታ አስለውጠን በሮም ከተማና በሌላ ከተማዎች ተዛውረን ዘጠኝ ዓመት ያህል ኖርን ።

የኢጣልያን አገር

መላ አገርዋ በጣም መልካምና እጅግ ደስ የምታሰኝ ናት ልምላሜዋ ሰብል አታክልቷ በበጋ ገነትን ነው የሚያስመስላት ። ያበባው ሽታ በየጐዳናው ያውዳል። መልካካም የሆኑ ሰፋፊ መንገዶቿ በትልልቅ አዳራሽ ተከበው በንጹሕ ተይዘዋል። ሕዝቧ ከየሥራው በቀር ለንዝንዝና ለጭቅጭቅ

አይሮጥም።ሁሉም በያኳያው በየወገኑ በየአውቀቱ በያቅሙ ይሠራል እንጂ ከቶ በዘን የለም። ቀላውጦና ለምኖ አውደልድሎ የሚበላ በነፃ ባገር ሊኖር አይችልም።ሕፃን ሆነ ሽማግሌ፡ ድውይ ሆነ ዓይነሥውር ሴት ወንዱ ሁሉም ሥራ አላቸው ።

በሁላችሁ ውቃቢ በዚች አገር ብዙ ዓመት ተቀምጬ ጥቂት እውቀትንና ሥራን ተምሬ ላገሬ ለመብቃት ቻልሁ ።

አያሌዎች እንደምታውቁት እንደሚሰማችሁም የወላድ አንጀት አይጨክንምና አባቴ ወዲያም ወዲህም ለዘመድ ወዳጆቻቸው ሁሉ አትርሱኝ ሲሉና ለየታቦቱ ሲሳሉ ነበር አሉኝ እንደዚሁ እዚህም እሰንበቴ ልጄ በሁላችሁ ጸሎት በጤና መጥቶ ላገሩና ዓይኑን ለማየት ብበቃ አንድ ሰንጋ እርዳለሁ ሲሉ ተስለው ነበር አሉኝ ።

እሳቸው ግን ለኔ ሲያስቡ ራሳቸው ሙተው ለመገናኘት ሳንበቃ ቀረን እንግዲህ ያ ስለት መድረሱ ነው ወይስ አልደረሰምን እንደኔ በግማሽ መድረሱ ነው ቢሆንም ሰው መፈጠሩ ሊሞትና ቦታ ሊለቅ ነውና የተሳሉት ቢሞቱ ለኔ ነውና የተሳሉት ለደኅ አገሬም በቅቻለሁና ይልቁንም ይህችን ሰንበቴአችንን አጥብቄ እወዳለሁና በጣም ጥሩ የሆነችና ላገራችን ደኅንነትና ለደኃው ሕዝባችን ጤና ለነፍስ ለሥጋችን የምትረዳ ነችና ስለዚህ ሁሉ ያገርና የነፍስ ጥቅም ስል ከማኅበሯ ሳልለይ ለመኖር እፈልጋለሁ ። አባቴም የተሳሉት ሰንጋ በምትሰጡኝ ቀጠሮ እኔው ላቀርብላችሁ የተሰናዳሁ ነኝ ።

ጥቂት ለማኅበራችን ምክር ።

ሰማችሁን ክቡራን ጌቶቼና ወንድሞቼ ። ማኅበራችን የመብልና የመጠጥ (ፍቀዱልኝና አንዲት ቃል ልናገር) የስካር ሁና ብቻ ትኑርስ ወይም ሌላ ብልሃት እንፈልግላትን ።

ከበረት የምትፀና ከኤሌትሪክ ይበልጥ የምታበራና ላገርና ለድኃ ዘለዓለም እየረዳች በኢትዮጵያችን የተለየ የድውይ ረጂ ማኅበር እንድናደርጋት ሁላችን እንፍቀድና ይኸንን ትልቅ ሥራ እንሥራ ስል አጥብቄ እለምናችኋለሁ ።

ክቡራን አባቶቼ ጌቶቼ ሆይ ።

ይህ እሑድ እሑድ ለት የምናዋጣው መብልና መጠጥ ገንዘብ የማያጸድቀን ነው የምል አይደለሁም ። እሱስ በእውነት ያጸድቀናል ። የምንሠራው ለነፍስ ስንል ነው እንጂ ለሌላ ስንል አይደለምና ።

ማናቸውም ለነፍስ ሲባል የተሠራ ሥራ ያጸድቃል እንጂ ከቶ አያስኰንንም ።

በምሳሌ መጀመርያ አንድ ወንበዴ ሰው በደን ተሸሽጎ ብዙ ደካሞች ሰዎች የሚቀማ የሚገድለውን አንድ ጨካኝ ጐበዝ ይህ ወንበዴ ብዙ ደካሞች ቀማ ነፍስ ገደለ ላጥፋው ሲል ተነሥቶ ቢገድለው ይጸድቃል ወይስ ይኰነናልን ።

ነፍስ በማጥፋቱ ይኰነናል ። ደካሞችን ለመርዳት ሲል ነውና የገደለው ይጸድቅ ይመስላል ።

፪ኛ፡ ሰው ያንን ወንበዴ ሳይገድል አባብሎ ወስዶ ወደ እሥራትና ወደመከራ ያደረሰው ሰው ይጸድቃል ወይስ ይኰነናልን ።

ይህንን ወንበዴ ወደመከራና ወደ እሥራት ስላደረሰው ይኰነናል ። ደካሞችን ለመርዳት ሲል ነውና ይህን በማድረጉ የሚጸድቅ ይመስላል ።

፫ኛ፡ ሰው ከወንበዴዎቹ ተወዳጅቶ በፍራት በምን የተነጣ በሥውር ጊዜ እየጠራ የሚጋብዛቸውና ከሌላም ጐበዛዝትና ቆንጆዎች እያስተዋወቀ አንድነት እንዲቀላቀሉ የሚያደርግና ተመልሶም ለዳኞችና ላገረገሮች የወንበዴዎቹን ኑሮና ምን ምን ያጫወቱና እንዲያዙ ያደረገ ሰው ይጸድቃል ወይስ ይኰነናል ይህ ሰው ወንበዴ ከታች ለጥቂትም ቀን ቢሆን ደጋፊና አብገር በመሆኑ ይኰነን ይመስላል ።

ደካሞችን የሚበድሉ እዚህ ናቸው በማለቱ ግን ይጸድቅ ይመስላል ።

፬ኛ ሰው ይኸንን ወንበዴ ሳይገድልም ፡ አባብሎም ወደ እሥራትና ወደመከራ ሳያገባ ተወዳጅቶም ሰብሳቢና ከጂ ሳይሆን መክሮ ዘክሮ ወደ ንስሓና ወደ ደኅንነት የመለሰው ሰው ግን ሰባት ጊዜ ይጸድቃል እንጂ በወንበዴው ረገድ ይኰነናል ሊባል አይጠረጠርም ።

እባካችሁ ይህችን ምሳሌ እንመልከት ። እኛ አሁን ሦስተኛውን ሰውዬ እንመስላለንና አዴራ አራተኛውን እንድንመስል ለወደፊቱ እንጣር ክቡራን ጌቶቼ ሆይ ።

ሁላችሁ እንደምታውቁት
በእሑድ ቀን ሁሉ ይመጸውታል ።
ያጠጣል ።
ያበላል ።
ይሰጣል ።
ያስከራል ።

በእሑድና ባውዳመት ቀን ከወዲያም ከወዲህም አያ ደኄ ሁሉ፡ ወይም አያ ሰነፍ ሁሉ ፡ ዓይነሥውሩ ሁሉ ፡ ቈማጣው ሁሉ ነፃ የወጣውና ጌታው የሞተበት አገልጋይ ሁሉ ነገሩን ሳይጨርስ ስንቁን የጨረሰው ሙግተኛ ሁሉ ሎሌነት ሊገባ የመጣው ተንከራታች ሁሉ አያምልጠኝ ሲሉ ከደጀ ሰላም ጀምረው እስከ ከተማው ጠረፍ ድረስ ከዝክር ከሰርግ ከተዝካር ከማኅበር ቤቱ ሁሉ ያለልክ እየጋፉ ይሰክራሉ ይሳከራሉ ።

ካንዱ ቤት አንድ ብርጭቆ ካንደኛው አንድ ኩባያ ፡ ካንደኛው አንድ ብርሌ ከነመለኪያው ሲል ሙሉ ማታ ጠግብዞ ተጠናብዞ ሴቱም ወንዱም ፡ ልጁም ሽማግሌውም ቈማጣውና ደኅናውም ወደ የመቃብር ቤቱና ወደ ማረፊያው በንድነት ከመልክም ግጦሽ እንደሚመለሱ ቁሞች በዚያ በቍስልና በመግል በተኰማተረው ከደኅናው እየተጓሸሙ ይመለሳሉ ።

እስቲ ከእንደዚህ ያለ ያለልክ ጥጋብና ስክር የሚመጣውን የሚወለደውን ጕዳት እባካችሁ ሁላችሁ በጥሞና አስቡት

እንደኔስ ሐሳብ ቢሆን ለድኆችና ለድውዮች ለማናቸውም ሰው ያለልክ እስቲጠግቡና ሕዋሳታቸው እስቲንቀሳቀሱ ሞቅ እስቲላቸው ድረስ ለደግነትና ለምጽዋት ሲል ያጠጣ ሰው ሰባት ጊዜ ይኰነናል እንጂ አይጸድቅም ስል እምናለሁ ።

ምነው ባበላና ባጠጣ ብትሉኝ ላስረዳችሁ የተሰናዳሁ ነኝና ክቡር ፈቃዳችሁ ሁኖ አዳምጡኝ ።

ሁላችን የታየንን ልናስብና መልካምና እውነተኛ ሁኖ ላገርና ለነፍስ የሚጠቅመውን ለሌሎች ወንድሞቻችን ሁሉ ልንገልጽ እንችላለን ። ሌሎችም ይህንን ሐሳብ መርምረው ከተረዱትና ላገርና ለነፍስ የሚጠቅመው ጥቅም ቢታያቸው ይህ እውነተኛ ጥቅም እንዲስፋፋና እንዲፈጸም እያሰቡን ላገራችንና ለነፍሳችን እንዲበጅ ለማድረግና ለመርዳት ለማገዝ በየወገናችን መታጠቅ እንዳለብን መልክም ኢትዮጵያዊና ለነፍሱ አሳቢ የሆነው ሁሉ እስቲ ያስበው ።

እንኳን በሽታ የጐዳቸው ድውዮችና ደኅናውንም ሰው መጠጥ እንዲረታውና ለማናቸውም መጥፎ ሥራ ሁሉ እንዲያበረታው የታወቀ ነውና ሴቱም ወንዱም በዚህ ከየቤቱ በሰበሰቡት የጌሾ ኃይል ተገፍተው ባንድነት እየተኙ በሽታቸውን ይካፈላሉ በሽተኞችም የሚሆኑ ሕፃናት ይወልዳሉ ።

ለነዚህ ለደከሙ ሰዎች የኃይላቸው መደገፊያ የሚሆነውን የዜያን የልዩ ልዩ በሽታ ክፋት አኳኋን የሚያስረሳውን ክፉ የብቀል ኃይል የሰጠ ሰው ነውና እነዚህ ፥ በችጋር ስም ሳያስቡ መከራ የሚወድቁትን ወንድሞቻችንን የበደለ ፣ ለዚህ ነገሩን ለመረዳት ከፈለግን ቀላል ነው ።

እስቲ እዚህ የተሰበሰቡትን በሽተኞች ተመልከቱአቸው ምን ምን በሽታ ነበረባቸው ።
አሁንስ ምን ምን ዓይነት በሽታ አለባቸው ።
እስቲ እናንተ ከኔ ይበልጥ የምታውቋቸው አስቡት ።
ሁሉን ነገር ልትረዱት ትችላላችሁ ።

በኢትዮጵያችን እንኳን ስድ ተለቆ ሰፍቶ ተስፋፍቶ በዘር ነው እየተባለ ሕዝባችንን ሁሉ የሚቈማምጠውን የታላቁን በሽታ ብቻ አገራችንን አገዛዝ እዩት ተመልከቱት እባካችሁ ።

ይህንን መድኃኒት የጠፋለትን በሽታ በመላ ኢትዮጵያችን እንደ ጤፍ ዘርተን እንዳትበቅልት እየኰተኰትን ክፋቱን ባለማወቃችንና ባለማስተዋላችን ብዛት የተነሣ ዘለዓለም እሱን በሽታውን እያከበርን እኛ እየተጐዳን እንኖራለን ።

ሰማችሁ ጌቶቼ አባቶቼ ። እንዴት የሚያይ ዓይን የሚሰማ ጆሮ ፥ የሚያስብ ራስ ፥ የሚናገር ምላስ ፥ እያለ እንዲህ ያለውን የሚቈማምጥ የሚበጣጥስ ፥ የሚሰብር ፥ የሚያንኳኰተውን ፥ የሚያስቀይመውንም በሽታ በመላው አገራችን ዓይናችንን እያየ እየዘራን ወንድሞቻችንን እንደ እህል እየወቃን እናምርት ።

ይቀጥላል ፑ፡ተ ጀኦሜትሪ መዠሯ ወልደ ሥላሴ

(ጂዮግራፊ)ዓለም ድቡልቡል ናት ።

ወይ ግሩም በቀደም እቶ ውስኪ ዘንድ ሒጄ ዓለምስትዞር አይቼ የቤቴ ደጃፍ እንኳን በፊቴ እያለፈ ከንዱ ግምብ ሌላው ግምብ የመዞሩ መጠን ያጋጨኛል ብዬ የስልኩን ምሰሶ እንቁ አደርኩኝ ብሎ ለባልንጀራውና ለኔ አዋየን ባልንጀራው መሬት ምን ትመስላለች ብሎ ጠየቀው ድቡልቡል ናት እጅም እግርም አፍንጫም ጆሮም አላት ዓይንዋን ግን አላየሁም አለው ወይ ግሩም ዋናውን ነገር ሳታይ ረስተሃልና ምን ይሻላል ። እንተው እስብና ወዳንዱ አስተማሪ ሒደን እንጠይቅ አለው። እንደ ተለመደው እቶ ውስኪ ዘንድ እንሒድ ወይ አይ እሱስ ይሰለቸናልና እያ ጠላ ከሰውም አይጣላ እሱ ዘንድ ሒደን እንጠይቀው ተባብለው ሔደ እያ ጠላንም አግኝተው የዚህኑ ጨዋታ እንደጀመሩ ነገሩን እንዲህ ሲል አስረዳቸው ዓለም ዓይኑዋ እናቷ ላይ ነውና ለማየት በጣም ያስቸግራል አላቸው እንደምን አሉት ተጋፊው ብዙ ነውና አላቸው እነዚህ ዓይኑዋን ያዩዋት እንደምን ሁነው ነው አሉት ። ተጋፍተው ገብተው ነው አለ መግቢያ በር አላት ወይ ብለው ጠየቁት አዎን ሁለት በር አለ አላቸው እነዚህም ስንፍና በርና ሥራ በር የሚባሉ ናቸው ስንፍና በር ሜዳ ነው ሥራ በር ግን ትልቅ ዳገት ነው ለመውጣትም ያደክማል አንድ ጊዜ ግን በዚያ የወጣ ሰው መመለሻ የለውም ዓይኑዋን ዘወትር ያያል በስንፍና በር የገባግን ዓይኑዋን አይቶ በቶሎ ይመለሳል አልደከመምና ብሎ አስረዳቸው እነሱም ዓይኑዋ እናቷ ላይ ከሆነ በስንፍና በር ወይም በሥራ በር የገባውን እንደምን አድርጋ ታውቀዋለች ብለው ጠየቁት በወሬ እንደምትሰማው በምልክት ታውቀዋለች ለጊዜው ግን ወደ እጇዋ የደረሰውን ታነሣለች እስከታየው ድረስ እናቷም በደረሰ ጊዜ የሥራ በርን ምልክት ስታጣበት መልሳ ወደ ያው ትወረውረዋለች ሁልጊዜም ሥራዋ ይኸው ነው ስታነሣ ስትጥል ትውላለች ስለዚህ አንድ ጊዜ ከደረሳችሁ እንዳትወረወሩ ጨክናችሁ ጊዜያችሁ ሳይጠፋ ዳገቱን ዛሬውን ጀምሩ አላቸው እነሱም ምክሩን ተቀብለው በተስፋ ጕዞዋቸውን ጀምረዋልና መዓበታቸውን በሰማሁ ጊዜ ወሬውን አካፍላችኋለሁ ።

አልቤር መሱላም ።

ማነቃቂያ ።

አሁን በዚህ ሰሞን በተደረገው የሊቃውንትና የመምህራን ሹመት ሽልማት ተሽዋሚዎቹና የነዚያውም ወዳጅ ዘመዶች ይቅሩና ከሩቅ ሁኖ ያየና የሰማውም ሁሉ ኢትዮጵያን የሚወድና ሥርዓቷ እንዲፀና፥ሀገርዋ እንዲቀና፥መንግሥትዋ እንዲሰፋ፥ ሕዝብዋ እንዲፋፋ፥ ሃይማኖትዋ እንዳይጠፋ፥ ልመናውን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርበው ሁሉ ደስታው ከልክ ያለፈ ሁኑዋል ነገር ግን ያለው ሰው ለሌለው ይሰጥ ዘንድ እንዲገባ ደስም ያለው ሰው ሌላውን ደስ ማሰኘት ይገባዋልና ለሥራ ረዳቶች የሚሆንዋቸውን ምሁራን በማቅረብና በቤተ ክርስቲያን ላይ ጕድለት የሚያመጣውን ነገር በማስወገድ በትልቅ ማዕርግ ያቆምዋቸውን ንጉሠ ነገሥትንና የተሾሙባቸውን ምእመናን ደስ እንዲያሰኙ በተስፋ እንጠብቃለን፡ ማናቸውም ሰው በሚሾመው ሹመት ላይ የሚቀበለው ሽልማትና የማዕርግ ልብስ ለሚሠራው ሥራ እንደ ልዩ ሰንደቅ ዓላማ ነውና፡ ከዚያውም ላይ እጁን ታጥቦ፡ከገበታ ቀርቦ ከተቀመጠ በኋላ የቀረበለትን ምግብ ለመብላት ንቆ የተወ ሰው አብረው በተቀመጡት ሰዎች ዘንድ ከክብር ያነሰ እንዲሆን ፤ የጦር መሣሪያም ይዞ ከተት ሠራዊት፥ምታ ነጋሪት፥ በተባለ ጊዜና አልጋ የሚነቀንቅ፡ድኃ የሚያስጨንቅ፡የሕዝብ ነፃነት ተቃዋሚ በተነሣ ጊዜ አፈሙዙን የማያዞር በጕራዴው የማይመትር፥ ጦር የማይወረውር፥

የሚደነዝር ከሕዝቡ አንድነት ተለይቶ፥ከሀገሩ በረከት አጥቶ፥በንጉሡ አደባባይ ተቀጥቶ ለወዳጆቹ ማዘኛ፥ለጠላቶቹ መዝፈኛሁኖ እንዲቀር፥በቤተክርስቲያንና በምእመናንም ላይየሚሾሙት መምህራንጉባኤ ዘርግተው፥የተነበበውንተርጕመው፥የተተረጐመውን መስለው ሕዝቡን ካላስተማሩና የቤተ ክርስቲያንንም ሥርዓት የጐደለውን መልተው ፤ የጠመመውን አቅንተው ካላሻሻሉና ካላስተካከሉት መናፍቃን ይበዛሉ፥ምእመናን ያንሳሉና፥የሕዝብ አንድነት፥ የሀገር ነፃነት፥ይጠፋልና ከላይ እንደተጻፈው እግዚአብሔር ኃይል ሰጥቶዋቸው ለሁላችን ጥቅም የሚሆነውን ሥራ በመሥራት እንዲበረቱ ተስፋ እናደርጋለን ። አንትሙ ውእቱ ጼው ለምድር፥አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም፥ኢትክል ተከብቶ ሀገር እንተ ተሐንፀት መልዕልተ ደብር ወኢያኅትው ማኅቶተ ከመ ያንብርዋ ታሕተ ከፈር አላ ያንብርዋ ዲበተቅዋማ ወታበርህ ለኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ቤት እንዲል ማቴ ምዕ ፭

መኰንን ኢያቄም

ስለ አማከሪዎች መምረጥ በቡና አውራጃ በጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፬ዓ ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ያደረጉት የበዓል ቀን ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴ ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ ልማት ለሕዝባቸው ጥቅም ሲሉ በመልካም ሐሳባቸው በሐምሌ ፱ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ም ስለ አቆሙት የሕግ መንግሥት መምሪያ የምክር ቤት ለክቡር ራስ ሙሉ ጌታ በእርስዎ ግዛት ውሥጥ ካሉት አገሮች ዋና ዋና ሽማግሌዎች ሰብስበው ለንጉሠ ነገሥት መንግሥት የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አማካሪዎች የሚሆኑ መታመንና እውቀት ያላቸው ሀገራቸውን ኢትዮጵያንና ንጉሠ ነገሥታቸውን የሚወዱ ሁለት ደግና ደግናሰዎች እንዲመረጡ እንዲያደርጉ፥የማስመረጫውንም ደምብ ከዚህ ደብዳቤ ጋር ልከንልዎታል የሚል በጽሕፈት ምንስቴር ማኅተም የታተመ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ትእዛዝ ስለመጣላቸው አስቀድመው በያውራጃው ያሉ መኳንንትና ባላባቶች እንዲሰበሰቡ ትእዛዛቸውን አሳልፈው ነበርና በጥር ፳፰ ቀን ልዩ ልዩ የሆኑ ፯ ድንኳኖችና ባንዲራዎችንም በሁለተኛው ቁጥር እንደተጻፈው ሲያዘጋጁ ውለው ለነገ ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ልክ በሦስት ሰዓት መኳንንትና ባላባቶች የማዕርግ ልብሳችሁን እየለበሳችሁ እንድትሰበሰቡ ብለው ቀጠሮ አደረጉላቸው ከዚህ በኋላ ጥር ፳፱ ቀን ከሌሊቱ በ፲፪ ሰዓት ሒደው ቤተ ክርስቲያን ስመው ከጧቱ በ፪ ሰዓት ተኩል ከመኳንንቱና ከባላባቶች ጋራ የማዕርግ ልብሳቸውን እንደለበሱ በአማረ ዓጀብ ተመልሰው ከተዘጋጀው ድንኳን ተቀምጠው ስለሚመረጡት አማካሪዎች ፊታውራሪ በፈቃዱን ሰብሳቢ ዳኛ፥ ጸሓፊ ፊታውራሪ ማኅፈዱን አድርጌላችኋለሁና እንደትእዛዙ ቃል ሥራውን በጥንቃቄ እንድትሠሩ ብለው ትእዛዝ አሳለፉላቸው።ከዚህ በኋላ መኳንንቱና ባላባቶች የማዕርግ ልብሳቸውን እንደለበሱ አምሮ በባንዲራ በተዘጋጀው ድንኳን እንደማዕርግ እንደማዕርጋቸው ተቀመጡ ።

ክቡር ራስ ሙሉ ጌታም ያማረ የማዕርግ ልብሳቸውን እንደለበሱ ልዩ በሆነ ወንበር ከአማካይ ቦታ ተቀምጠው ነበርና የመጣውን ማዘዣ በሥርዓት ቁመው አስነበቡት ከተነበበም በኋላ ክቡር ራስ ሙሉጌታ ቃላቸውን ከፍ አድርገው አሁን የተሰበሰባችሁት ይኸንን የኢትዮጵያን ልማት የሕዝባቸውን ጤንነት የሚፈልጉ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ያሰለፉልንን መልካም ሐሳባቸውን ለማካፈል ነውና ያመራረጡ ሥራ በውነት እንዲጀመር ሲሉ አስታወቋቸው። ከዚህ በኋላ ከዚያው ከተዘጋጀው ድንኳን ሳይወጡ መኳንንትና ባላባቶች ለየብቻ ተገልለው በየወረዳ በየወረዳው ተቀመጡ። ምክሩ ተጀመረና ከዚያው ከተዘጋጁት ድንኳኖች ውሥጥ የአማረ ልዩ ሆየን የጽሕፈት ጠረጴዛ ተዘጋጅቶ ተቀምጦ ነበርና ለዳኝነት የተመረጡት ፊታውራሪ በፈቃዱና ለጽሕፈቱ የተመረጡት ፊታውራሪ ማኅፈደ ከዚያው ከጠረጴዛው አጠገብ በወንበር ተቀምጠው ይጠባበቁ ነበርና የአማካሪነቱን ሥራ የሚችሉትን ሲያመዛዝኑ ቈይተው ከዚህ በኋላ መታመንና ዕውቀት ያላቸው ሀገራቸውን የሚወዱ ፥ መንግሥታቸውን የሚያከብሩና የአማካሪነት ሥራ የሚችሉ በኢሉባቦር ቀኛዝማች ኃይሌ ኢጀርሶን በጉማይ አባ ጀቢር ጉማን መርጠናል ብለው በማኅተማቸው የአታወ ፰ አምሳ ሦስት መኳንንትና ፳፫ ባላባቶች በድምሩ መቶ ሐያ አንድ ማኅተም መሆኑ ነው መኳንንቱና ባላባቶቹ በደብተር በማኅተማቸው አትመው ለዳኛው ለፊታውራሪ በፈቃዱና ለጸሓፊው ለፊታውራሪ ማኅፈዱ ለቀሰውስቱ ለአባ ሕፃኑና ለመምሬ ወርቅነህ በአንድነት አስረከቧቸው ከዚህ በኋላ እነዚህን ሁለት ሰዎች በወዳጅነትና በዝምድና ሳይሆን በውነት ለመንግሥታችን ሥራና ለሀገራችን ጥቅም የሚያገቡ ለመንግሥትም በውነት የሚረዱና መታመንና ዕውቀት ያላቸው መርጠናል የኃይለ ሥላሴ አምላክ ያጥፋን ወዳጅ ዘመድ አላልንም በውነት ነው ብለው ሥራ ከተፈጸመ በኋላ ክቡር ራስ ሙሉጌታ የማዕርግ ልብሳቸውን እንደለበሱ ከእልፍኝ አዳራሽ ወጥተው ከዚያው ከድንኳኑ ውሥጥ ከፍብሎ አምሮ በተነጠፈው ምንጣፍ ላይ ቆመው ከዚህ በኋላ በዳኛው በፊታውራሪ በፈቃዱና በጸሓፊው በፊታውራሪ ማኅፈዱ እጅ መኳንንቱና ባላባቶቹ መርጠው ያተሙበትን ደብተር ከዩ በኋላ ክቡር ራስ ሙሉጌታ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ለሀገራቸው ልማትና ለሕዝባቸው ጤንነት የሚፈልጉ ስለሆነ በሐምሌ ፱ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ም ባወጡት የሕግ መምሪያ አማካሪ ከዚህም ከኔ ግዛት እንዲመረጥ ስለ አዘዙኝና ስለሰበሰብኋችሁ በኢሉባቦር ቀኛዝማች ኃይሌ ጀርሶን በጉማይ አባ ደቢር ጉማን በመምረጣችሁና የመጣውን ትእዛዝ ስለፈጸማችሁልኝ በመላው ደስታዬን አከፍያችኋለሁና እናንተም የተመረጣችሁ የሕገ መንግሥት መምሪያ አማካሪዎች ሆይ የመንግሥቱን ሥራ በትክክል እንድትፈጽሙና ለሀገራችን ለኢትዮጵያ ረዳት እንድትሆንዋት ምኞቴን በቃላቅ ተስፋ እገልጻለሁ ከዚህም ያላችሁ ባላባቶች ሀገራችሁን በውነት እንድትጠብቁና ለመንግሥታችሁም እንድትረዱ እናንተ ሀገራችሁን ካልጠበቃችሁ ልጆቻችሁን ካልመከራችሁና ወንበዴ ወስላታ ሀገራችሁን ካጠፋው ለነዚህም አማካሪዎች ሐሳባቸውን ያጠፋዋል ሀገራችሁን ጠብቃችሁ ወንበዴ ሌባ ከአገራችሁ የጠፋ እንደሆነ አገራችሁ ለም ይሆናል አማካሪዎ-

ቹም ልበ ብርሃን ይሆናሉና አገራችሁን በውነት እንድትጠብቁና ለማንግሥታችሁ እንድትረዱ እያሳሰብሁ ፅድሜና ጤና ለቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ይስጥልን እያልን ጊዜ ሳንለይ እግዚአብሔርን እንለምን፤ይኸውም መኳንንትና ባላባቶች አትመው ያስታወቁበት ደብተር በሚመጣው ፖስታ ወደ ክቡር ጸሓፌ ትእዛዝ እንዲሔድ ብለው ከተናገሩ በኋላ ፫ጊዜ ተጨብጨበ የሰውም ብዛት ምንጊዜውንም በጣም ያስደንቅ ነበር ለመኳንንትና ለባላባቶች ምሳ ግብዣ አደረጉላቸው ከዚህ በኋላ የበዓሉ ቀን ተፈጸመ ።

ተድላ ታምራት ።

የወዳጅ መታሰቢያ

ሥላሴ ቅኔ

ዘከመዝኬ፡ ሊቀ ክህናት ይደልወነ አንጽሖተ ደም ይከል
አከኑ ቅድመ ገጸ ንጉሥ አልፋ ።
ወለቅቱላን ደሁበሙ ተስፋ ።
ወልብሰ መልከጼዴቅ እብ እንተ ኢተሠጠ ጽንፋ ።
ለንብረ ክርስቶስ ተላዌ ኬፋ።
መንጦላዕት ይእቲ ወበቲ ተጽሕፋ።
እፅዋፍ ዘትዓሬ ወክፋ።

የሥር ዳኛ አለቃ ዳኜ

መወድስ ።

በመንበረ ዳዊት ተከሥተ ወኢተሠወረ ።
ዘእምኅበ ምሥራቅ መጽአ ኃይለ ሥላሴ ቴዎድሮስ ።
እንዘ ቴስብያዊ ኤልያስ ገብረ ክርስቶስ ።
እስመ ያሬድ መልአከ ገነት ዘመልአ መንፈስ ።
ለብሉይ ወለሐዲስ
እመ ይቄስምዎ ወትረ በዔወ መለኮት መንፈስ ቅዱስ ።
ሚመትሂ ኅብስተ መና እመ ወረደ በርእሰ ።
ሰፍሐ እደዊሁ ሐሊናየ ዘካርያስ ።
ኃይለ ሥላሴ ፋኑኤል እስመ አርአየ በንግሥ ።
ትጽገብ እምኔሁ ድንግለ እስራኤል ቤተ መቅደስ ።

ሥርግው ዘደብረ ሰላም ።

ሐኪም አፊሊፕ በደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ አዲስ አባባ

ሐኪም አ ፊሊፕ በተለየ የሕክምና ሥራቸው በሎንዶን ከተማ በዋናው ሆፒታል የዓይኖች፡የጆሮዎች፡የአፍንጫ፡የጕሮሮ በሽተኞች ያከሙ የነበሩት አዲ አበባ ለማከም መጥተዋል በዚሁ በከተማችን ውሥጥ አንድ ወር ብቻ ይቀመጣሉ ለመታከም የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ሁነው ዘወትር ይቀበላሉ ።

ሐኪም አ ፊሊፕ በሐኪምነታቸውና በመድኃኒቶቻቸው በዋናው የሕክምና ትምህርት ቤት ኢርላንድ አገር ደብላን ከተማ የምስክር ወረቀት (ዲፕሎም) ተቀብለዋል የምስክር ወረቀታቸውም ሕክምናቸውና መድኃኒቶቻቸው የሰው ራስ ፈዋሽ መሆኑን በሎንዶን ከተማ በታላቁ መንግሥታዊ ትምህርት ቤት የተመሰከረላቸው ናቸው።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ብቻ ጠጡ ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክቶር ጂ ኤ ማርቲኒ በፓሪስ ዩኒቬርሲቲ የተመሰከረላቸው።በዚሁ መታከሚያ ቤት የሴት በሽታ የልጆች በሽታ፣ የዓይን በሽታ፣ የጆሮ በሽታ፣ የጕሮሮ በሽታ፣ ቁጥኝ ይህንን የመሰለውን ሁሉ በደኅና ያክማሉ። ቤታቸውም አራዳ ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ጧት ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ነው ። ከ፱ተኩል እስከ ፲፩ ሰዓት ያክማሉ ደክቶር ጂ ኤ ማርቲኒ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።
ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።
ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚሀ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒቅ ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጀማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዲሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።



ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሲንጀር ቅቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው።

ይኸንኳ የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክሰፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መስንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታው ቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ና ናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም

ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ አሸቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።

አበከት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ለአቡጂዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ጴልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለይ አስመጪ።

በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፲፪
8me ANNE. № 12

ሐሙስ መጋቢት ፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
JEUDI 17 MARS 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ልዑል አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ደኅና መግባት የተደረገ ክብር በፍቼ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ከነመኳንንቶቻቸው ወደአውሮፓ ከሔዱበት ቀን ጀምሮ የደኅንነታቸውን ወሬ ለመስማት የማይናፍቅና የማያስብላቸው ሰው አይገኝም ።

የካቲት ፲፯ ቀን ባ፲ ሰዓት ከነመኳንንቶቻቸው ደኅና መግባት ፍቼ ከተማ በስልክ በተሰማ ጊዜ ባማረ ክብር ሁነው ደስታውን ለሕዝብ ለመግለጥ ሐሳባቸው ሁኖ ልዑል ራስ ካሣ መድፍ እንዲተኰስ አዘዙና መድፍ ሲተኰስ በግቢው እልልታ ሆነ። ሰውም ናፍቋልና ይህን ሲሰማ ከተማው በእልልታ አመሸ ወደ ቤታቸውም የተመለሱ መኳንንትና ወታደሮች የመድፍና የዕልልታ ድምፅ ሰምተው ከልዑል ራስ ካሣ ደስታ ለመካፈል ወደ ግቢው ለመግባት በመጋፋት ሲሻሙ ይታይ ነበር።ልዑል ራስ ካሣም ወደ ፊታቸው ቀርበ እንኳን ደስ አለዎ ለሚል ሁሉ ከታላላቁ መኳንንት እስከ ተራ አሽከር ባአንገት እጅ ነሥተው አብሮ ደስ ይበለን እያሉ ደስ አሰኝተው ወደ እልፍኝ አዳራሽ ገቡና የሽምፓኝ ግብዣ ለመኳንንቱ አድርገው በደስታ ተመለሱ። እንዲሁም ከተማው ደስ ብሎት አመሸ ኢትዮጵያዊ ሆይ እንዲህ ሁኖ የፍቅር መተባበር ቢበዛ ጕልበት እየጠነከረ ዕውቀት እየሰፋ አገርና ሕዝብ በቶሎ እንዲሠለጥን ጥርጥር የለውም ።

ገብሩ ወ አ ፍቼ ሰላሌ።

ስለ ሕገጋት ተደጋጋፊነት ።

በእረኛ የሚጠበቁ እንስሳት ሣር ከየሚገኝበት መስክ እየተሰማሩና በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ውኃ እየጠጡ፥ በጊዜ ወጥተው በጊዜ እየገቡ በገደል በጕድጓድ ከመውደቅ በአውሬ ከመነጠቅ ከመዳናቸው በላይ ክረምት፥በቄላ፥ በጋ በደጋ የሚኖሩ ስለ ሆነ ጕዳት አያገኛቸውም።እረኛ የሌላቸው እንስሳት ግን አውሬ ነጣቂ፥ ሌባ ቀጣፊ እየተሻማቸውና በክረምት ቍር፥ በበጋ ሐሩር እየሠለጠኑባቸው ከዓምና ዘንድሮ ከዘንድሮ ከርሞ ክቍጥር የጐደሉ፥ ለዓይን የማይመሉ፥ ከቁም ነገር የማይውሉ ሁነው ይቀራሉ።እንደዚሁ ሁሉ ለባዊ እንስሳ (ሰውም) ምንም በተሰጠው አእምሮ መምጫውንና መሔጃውን መውጫና መግቢያውን፥ጕጂውንና ጠቃሚውን ቢያውቅ ትምህርት አሠልጣኝ ሕግ ወሳኝ፥ ዳኛ አወሳሳኝ የሚያስፈልገው ስለ ሆነ በየጊዜው የልዩ ልዩ አህጉር ነገሥታት የየሕዝባቸውን ማስተዳደርያ ሕግ ሲያቆሙ ይኖራሉ።ይህም የሕግ መቆም ለኢትዮጵያም የሚያስፈልጋት መሆኑን ስለ ተረዱት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የሕግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ብለው ሁለት የአማካሪዎች ቤት አቁመውላታል ይህም ሥጋዊ ሕግ ከመንፈሳዊው ሕግ ጋራ በመደጋገፍ የሕዝብን ጥቅም ሲያስገኝ ይኖራል። ጥቅምነቱ ምንም አንዱ በነፍስ አንዱ በሥጋ በኩል ቢሆን ውሥጡ የሁለቱም አንድ ነው ማለት ሥጋዊው ለመንፈሳዊው መንፈሳዊው ለሥጋዊው ረዳት ይሆናሉ።እንደምን ቢሉ ጾም፥ጸሎት፥ ምጽዋት፥ ሰጊድ ፥ ቁመት እነዚህንም የሚመስሉትን ሕገጋት ነፍስ በመፈጸም እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተን መንግሥተ ሰማያት እንድንገባ ተጽፋዋል የዚህም ምሥጢሩ በምንሠራው ሥራ በዚህ ዓለም፥ በወዲያኛውም ዓለም ራሳችንን ከመጥቀም በቀር ሥራውን ሠርተን የምንጠቀመውና ወይም ሥራውን ባለመሥራትና ሕጉን በመተላለፍ የምንጐዳው፥ሌላ የለም።ሥጋዊውም ሕግ ለመንፈሳዊው ረዳት መሆኑ ማናቸውም ሰው በሚሠራው ሥራ ሁሉ የሚያገኘውን ፍርድና ቅጣት ከማወቁ የተነሣ ክፉ ሥራ ብሠራ የዓይን መፍረጥ፥የእጅና የእግር መቈረጥ፥ የጅራፍ ግርፋት፥የገንዘብ ቅጣት፥ ከወህኒ መግባትና እሥራት ያገኘኛል ብሎ በመፍራት ክፉ ሥራ ከመሥራት ይታገሥና በሰው ላይ ከእርስበርሱ የሚመጣው ጕዳት ሁሉ ምንምን እንኳ ፈጽሞ ባይጠፋ እያነሰ መሔዱ አይቀርም ።

የተነሣንበትም የነገራችን ዓይነታው ጊዜው ስለ አጋጠመን ስለ ጾም ሕግነት ነው።ጾም ሕገ ነፍስ ሁኖ ምንም የነፍስ ጠቀሜታን የሚያስገኝ ስለ ሆነ መጀመርያ የሚጠቅም ሥጋን ነው እንደምን ቢሉ ማናቸውም ሰው ዓይነተኛ ሐሳቡን ወደ መብልና መጠጥ አዘንብሎ አላገባብ ለሆዱ ተገዝና የጾም ተቃዋሚ ቢሆን ከዚህ ቀጥለው የተጻፉት ጕዳቶች ያገኙታል። አንደኛ ልቡ ደንድኖና ደሙ ፈልቶ፥ አእምሮው ጐድሎ የማ-

ይገባ ሥራ በመሥራት እግዚአብሔርን አሳዝኖ የሚያገኘው ጕዳት ነው።ሁለተኛ አላገባብ ወፍሮ የማይወርድ ሸክም የተሸከመ ያሀል ሁኖ መኖር ነው ።

ሦስተኛ፤እንደ ተመቸ አይኖርምና የለመደውን በለመደው ሰዓት ሳያገኝ ቀርቶ ጥቂት ጊዜ በመተላለፍ የሚያደርስበት ደዌ ነው።ይህንም በሚመስለው ነገር ሕገ ነፍስና ሕገ ሥጋ ተደጋጋፊዎች መሆናቸው በብልሆች ዘንድ አይዘነጋም ።

መኰንን ኢያቄም ።

የጥር ሥላሴን በዓል አከባበር በደብረ ብርሃን

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በደብረ ብርሃን የጥር ሥላሴን በዓል ለማክበር አስበው ነበርና በሕመም ምክንያት ቀሩ ። ነገር ግን ለደብረ ብርሃን ሥላሴ የሠሩትን ቸርነታቸውንና የትሩፋታቸውን መጠን ከዚህ ቀጥዬ የምጽፈው ነው።የታኅሣሥ ሥላሴ ዕለት በቴሌግራፍ ለአለቃ ገብረ አጋእዝት እንዲህ የሚል ቃል አልፎላቸው ነበር።ይድረስ ለአለቃ ገብረ አጋእዝት የጥር ሥላሴን ለማክበር መምጣት አስቤአለሁና የምመጣውም በአቶመቢልና በካሚዎን ስለሆነ ጥቂት ሰው ነውና የሚመጣው በዚህ ምክንያት ድኃው እንዳይጉላላ ፩ም ነገር እንዳይታዘዝ ። እዚያም የማድረው ፪ቀን ነው የሚል ቃል አልፎ ነበር ከዚያም ቀን ጀምሮ አለቃ ገብረ አጋእዝት ቤተ መንግሥቱን በማደስ፤ከተማውን በማፅዳት በቤተ ክህነቱም በኩል ጃንሆይ በቸርነታቸው ደብረ ብርሃን እንዲአስተምሩ አድርገው ያቆሟቸው የ፲፪ቱ መምህራን ተማሪዎች በሥርዓት ሆሣዕና ሕፃናቱ ቡሩክ አንተ ንጉሥ እስራኤል እያሉ እንዲቀበሉ ፡በየመንገዱም ላይ ስለሚደረገው ነገር የተደራጀውንና ታስቦ የነበረውን ነገር ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕድሜ ሰጥቶልን የታሰበው እንዲፈጸም ያድርግልን እንጂ ብንጽፈው የሚጠቅመን አይደለም። በኋላ ግን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በሕመም ምክንያት ስለቀሩ ካህናቱም ሕዝቡም ሴቱም ወንዱም ወታደሩም ባላገሩም በጣም አዝነው ነበርና ጥር ፯ቀን ከጧቱ በአንድ ሰዓት ዘውድ፤ሙካሽ ወርቅ ጥልፍ፤ የእጃቸውን ጥላ፤ ጥሩ ወርቀዘቦ ካባ ላንቃ፤ባለወርቅ ጥብጣብ አብደላ ከኒቀሚስ የ፫ ልኡካን ልብስንጭ መብሩቅ ካባ ላንቃ ከመብሩቅ ቀሚስና ሱሪ ጭምር የ፫ልኡካን ልብስ ጥሩ ወርቀዘቦ መጐናጸፍያ፡ ጥሩ ወርቅ ቅብ ጽዋ ይኸንን በባሻ ወንድማገኘሁ እጅ ከጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማኅተም ጋራ ብደረሰ ጊዜ ክቡር አለቃ ገብረ አጋእዝት ከዕቃ ቤት አግብተው ተቀብለው ለጊዜው ሥላሴን ለማክበርና በጃንሆይ መቅረት እንዳያዝኑ ካህናቱን ለማፅናናት ክቡር ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ መጥተው እቅድስት ቁመው ነበርና የጃንሆይ ማኅተም በተነበበ ጊዜ የመጣውንም ልብስና ዘውዱን ካህናቱ አሳርገው እንዲቀበሉ እቅኔ ማኅሌት ግባና ወንድ ወንዱ በጭብጨባ፤ሴት ሴቱ በልልታ አክብረው በተቀበሉ ጊዜ ምድር የተናወጸች መሰለች።ካህናቱም አክሊል ንጹሕ ዘኃይለ ሥላሴ ተደለወ ለደብረ ብርሃን ጌራ ባሕርይ ወለተ ጊዮርጊስ ወቀጸላ ሥን እምኃ ሥላሴ እያሉ ዘውድን ከማህል አድርገው ዑደት ባደረጉ ጊዜ ክቡር ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ ሠራዊቱን አሰልፈው በተከተሉ ጊዜ ከ፻መቶ የሚበልጡ ዕድሜአቸው ከ፲፫ ዓመት በታች የሚሆኑ ሕፃናት ጃንሆይን ለመቀበል የተደራጀላቸውን ልብስ እየለበሱ የዘንባባ ቅጠል እየያዙ ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ሺሕ ዓመት ይንገሥ እያሉ እንደየመጠናቸው ትንንሽ ከበሮ እየመቱ በቀደመው ጊዜ ከማማራቸውና ከመተባበራቸው የተነሣ አንዲት ሴት እንዲህ ብላ ተናገረች መካን ሴት ልጅ ያልወለደች ባለመውለዷ ስታዝንና ስትፀፀት ትኖራለችና ዛሬ እዚህ ባልነበረች ደግ ነበር ብላ ተናገረች በዓሉም በመልካም አከባበር ከተፈጸመ በኋላ ለጃንሆይ መቀበያ የተሰናዳውን ድግስ አለቃ ገብረ አጋእዝት ለካህናቱና ለተሰበሰበው ሰው እንዲአበሉ ታዘው ነበርና በመልካም ተጋብዘው ሲጨርሱ በሳኒታው የዘውዱን በዓል በልዩ ለማክበር የእንጐለላንና የድንብሮን ካህናት እንዲጠሩ ወደአጋፋሪያቸው ትእዛዝ አሳልፈው ነበርና ከሌሊቱ በ፰ሰዓት ተደውሎ ማኅሌት ተቁሞ አድሮ ከቀኑ በ፫ሰዓት እንደዚያው ቀድሞ እንደጻፍነው ሕፃናቱም ሽማግሎቹም ወንዱም ሴቱም በሰልፍ ሁኖ ዑደት ከተደረገ በኋላ አለቃ ወልደ ኪዳን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቅኔ ተቀኙ።አክሊል ንጹሕ ዘኃይለ ሥላሴ።እመ ለካህናት ከነ ሰብሓት በአርያም። እስመ ቡሩኬሁ አክሊል ለደብረ ብርሃን ሄም ። ወገብረ አጋእዝት ተደለወ ይሚጥ ዲዋሁ ለያዕቆብ ስም።ዘሀሎ ቅድመ ዓለም።እምጣነ ወሬዛ በኃይሉ፤ገብረ አጋእዝት ብንያም። ከዕበዚ መዋዕሊሁ እመ ይከውን ሰላም፤ይሁዳ አማሌቃዊ ኢይቀንእ በኤፍሬም።ወኮላ ፍድፋዴ ሀብትን ዘይገብራ አዳም።እንበለ ፈቃዱ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኢትትፌጸም። ከዚህ በኋላ አለቃ መኰንን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቅኔ ተቀኙ። ሰብአ ደብረ ብርሃን ስእነ ጠይቆ ባሕርዩ፤ለደኃራዊ ሀብትን እምኃይለ ነፋስ ዘተፈጥረ ከመ ኢንስምዮ ሰብአ በይነ ምስሌን ነበረ። እመሬት እስመ ኢተፈጥረ ወኢለብሰ ምድረ።ወመልአክ ኢንስምዮ በሕገ መዋቲ አዳም ሞተ ወተቀበረ። እምግብዕሂ ኃጢአ ተስፋ እምድኅረ ሚጠት ተገብረ ። መቃብረ ሙሴ ሀብተ ዚአነ አይቴ ኑመ ተሠወረ። ወዘእንበለ ስንቅ ልብነ አመ ብሔረ በዕድ ሖረ ። በፀሐይ ኃይለ ሥላሴ የኅሥሥ ማኅደረ ።

ከዚህ በኋላ መሪ ጌታ ገብረ ጻድቅ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቅኔ ተቀኙ ። ሰማዕተ ብርሃን ዮሐንስ ደብረ ብርሃናት በመንፈስ ጥበብ ፀርኅ ርእኩ እንዘ ይብል።ከመ አንተ ርግብ ይወርድ መንፈስ እእምር አክሊል። አኮኑ ብዙኅ ሀብተ ዚአሁ እንዘ ፀሀሳዊ ፩አካል። ወንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ውእቱ ይሁብ ወውእቱ ኢይቀብል። ለጴጥሮስሂ ደብረ ብርሃን ፥ በይነ ሚመቱ ልዑል። በደጊመ ቃል ይደልዎ አክሊለ ሱራፌ ወኪሩቤል። ወመሐላሁ ዕኑዕ ለኃይለ ሥላሴ ባዕል፤አኮኑ ደብረ ብርሃን በስመ ካልኡ ኢይምሕል ። ይህን ሦስቱን ቅኔ ከተቀኙ በኋላ ቄሱ አሳርገው ከዳር እስከዳር ተጨብጭቦ በመልካም ከብሮ ገባ።ከዚህ በኋላ ስለዘውዱ በዓል በቤተ መንግሥቱ ግብር ተደራጅቶ ነበርና አለቃ ገብረ አጋእዝት ካህናቱ እንደዚሁ እንዳሉ እጣቢ እንዲገቡ ይሁን ብለው ለአጋፋሪያቸው ትእዛዝ አሳለፉ ካህናቱም አምረው ደምቀው አለቃ ገብረ አጋእዝትን አጅበው ወደቤተ መንግሥቱ ለግብር ገቡ።ግብሩም በጣም

እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነበር። ከዓብሩም ምላሽ የተደረገውን ቀኔ በሚመጣው ብርሃንና ሰላም እናስታውቃለን ።

ግራጌታ ተክለ ሥላሴ ዘደብረ ብርሃን

ስለ ዕድለኛይቱ ሀገራችን ።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ከጥንት ኑሮዋ ከ፲፱፻፱ ዓ ም ወደዚህ ብርሃን ሁና ለዓለም ሁሉ ስለታየች በዓለም ላይ ያለ ሕዝብ ሁሉ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ብርሃን የሰውቀች መሬ መንግሥታችንን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሺሕ ዓመት ያንግሥልን የማይል አይገኝም። ፩ኛም ጨርጨር አውራጃ ከጥንት አንዋኑዋሯ ከ፲፱፻፱ ዓመት ወደዚህ ክቡር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ከተሾሙ በጃንሆይ ፈቃድ በትጉህነታቸው ብዛት በሥልጣኔ ጎዳና በመራመዱዋ የሀገሩ ሕዝብና ሠራተኛውም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሺሕ ዓመት ያንግሥልን እያለ ይመኛል ፪ኛም ዕድለኛይቱ በማይረሳ ስም የተመሠረተችው ከተማ ዓሰበ ተፈሪ በ፲፱፻፲፰ ዓ ም ስለተቈረቈረች የተወጠነው ሳይፈጸም ሹም ሽር ስለሆነ አዝነን ነበር ። ነገር ግን እግዚአብሔር ዕውቀቱን የሚሰጠው ለቀባው ነውና አገራቸውን አስከባሪ መንግሥታቸውን አክባሪ የእውነት ምንጭ የሆኑትን ክቡር አዛጋር ወርቅነህን ስለሾሙልን በደስታ ተቀብለናቸው ነበርና ክቡር አዛጋር ወርቅነህ ዓሰበ ተፈሪ ከተማ እንደገቡ ሕዝቡን ለግብዣ አስጠርተው ግብዣው በመልካም ሁኖ ከተፈጸመ በኋላ ጥልቅ የሆነ ምክር መከረው በመጨረሻው መስመር ለመንግሥት የምትሠሩ ሠራተኞች በተሰጣችሁ ሥራ ለመንግሥታችሁና ለሀገራችሁ ብላችሁ ሥሩ እንጂ ለግል ጥቅማችሁ አትሥሩ ብለው ስለመከሩን እስከሁን ከልባችን ይሰማናል ።

፫ኛም ዓሰበ ተፈሪ ከተማ የተጀመረውን መንገድ ፈጽመው ሌላም ደስ የሚአሰኝ ሥራና የተማሪ ቤትም ስላቆሙልን እናመሰግናቸዋለን ።

፬ኛ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተወለዱበትን ቀንና የዘውዳቸውን በዓል አክብረው ሕዝቡን ሰብስበው ጋብዘው ለመንግሥት ጥቅም የሚሆን ምክር እየመከሩ ስለሚያሰናብቱት መንግሥት አክባሪ በመሆናቸው እናመሰግናቸዋለን

፭ኛም ሠራተኛውንና ሕዝቡን በተቀበሉት ደንብ በትክክል በማሳደራቸው እናመሰግናቸዋለን ።

ከዚህ በላይ የጻፍሁት የከተማዋን ዕድላምነት ለማስታወቅ ስለሆነ የጃንሆይን ዓሰበ ተፈሪ መጐብኘት ከዚህ ቀጥዬጽፌአለሁ። ከ፲፱፻፳፩ ዓ ም ከየካቲት ፩ቀን ወደዚህ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በማይረሳ ስም አሰበ ተፈሪ ተብላ የተመሠረተችዋን ከተማቸውን ለመጐብኘት ይመጣሉ ተብሎ ስለሚወራ በከተማ ያለ ሠራዊታቸው የኢትዮጵያን ብርሃን ለማየት የመጓጓቱ ብዛት ቀኑ አልመሽ ሌቱ አልነጋ ብሎት የሚመጡበትን ቀን ሲጠባበቅ በማህሉ የኦቶ ሞቢሉን መንገድ ለማሳደስ የከተማው ሕዝብ ስለታዘዘ የከተማው ነዋሪዎችና ሠራተኞቹ መንገዱን ሲደለድሉ ላያቸው ሰው የቆመ ሰብል ካንበጣ የሚሸሙ ይመስላሉ እንጂ እውነትስ ድንጋይና ጠጠር ያለበት ሥራው የሚአውክ አይመስልም ለዚሁም ጌታችን በመጡልን እንኳንስ ቀንና ሌት በሠራን እየተባባለ ይማከራል እንጂ አንድ የሚመረር ሰው አልነበረም ። በየካቲት ፱ ቀን የጃንሆይ መምጣት እርግጥ ስለሆነ የመንገዱም ሥራ ተፈጽሞ ነበርና የጨርጨር አውራጃ ዲሬክተር ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ለጌታቸው ሥራ ትጉህ ናቸውና የመንገዱን ሥራና የከተማውን ዕዳት በኦቶ ሞቢል ሲሰልሉ በከተማው ውሥጥ ሁለት መቶ የሚሆን ባንዲራ በየክፍሉ ተሰቅሎ ሲውለበለብ ላየው ሰው የመስከረምን አበባ ይመስል ነበር ወደዚያው ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ወደቤተ መንግሥት ሲመለሱ ክቡር አዛጋር ወርቅነህም የሠራተኛውን ሥልጣኔ መርምረውታልና ክቡር ልጅ መስፍን ሚኤነሶ ጣቢያ ወርደው እንዲቀበሉ ክቡር ቀኛዝማች በላቸው ቀድሞ የቤተ መንግሥት አጋፋሪ የነበሩት በከተማው ዳር በቀስት በተሰቀለው ባንዲራ አጠገብ ሠራዊቱን እንዲአሰልፉ ካህናቱም ልብሰ ተክህኖዋቸውን ለብሰው እንዲቀበሉ ግራዝማች ኃይሌና አቶ ኃይሌ መረን አቶ ፈለቀ ገድሌ አቶ መታፈሻ ውዴ ቤተ መንግሥቱን እንዲአዘጋጁ የማዘጋጃ ቤቱ ሹም አቶ ጸጋ ሥላሴ የከተማውን ዘበኞችና ነዋሪ እንዲአሰልፍ አዝዘው ነበረና ፱ ሰዓት ሲሆን ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ለመቀበል ሲሔዱ ሰልፍ ተጀምሮ እስላሙን ለብቻው ዓረቡን ለብቻው ፈረንጁን ለብቻ ዘበኞቹን ለብቻ የከተማውን ነዋሪ ለብቻ አሰልፈው ሰልፉ ካማረ በኋላ ክቡር አዛጋር ወርቅነህ በሰልፉ ማህል ተቀምጠው ሲጠባበቁ አሰበ ተፈሪ የደብረ ሰላም እግዚአብሔር አብ ካህናት የላሎ ሚካኤል ካህናት የዲንዲን ጊዮርጊስ ካህናት ሁነው በወረብ ሲአሸበሽቡ በቅኔ ሲዘሙ እጅግ ያምሩ ነበር አለቃ ማፈኛ የተቀኙትን ቅኔ በሚከተለው እንጽፋለን ወደዚያው ከማታው ባንድ ሰዓት ሦስት ኦቶሞቢል ተከታትለው ሲመጣ ሊትሪክ ፀሐይ መስሎ ሕዝቡ በየ ጊዜ የሠራዊቱ ደስታ ከልክ ያለፈ ሆነ ወደዚያው ጃንሆይ በመጀመሪያው ኦቶሞቢል ነበሩና ለሠራዊታቸው ሰላምታ ሰጥተው ካህናቱ ተዘጋጅተው ይጠብቁ ነበርና መስቀል ካሳለሟቸው በኋላ ለሠራዊታቸው ደስ የሚያሰኝ ሰላምታ ስለሰጡ ዳር እስከ ዳር ሶስት ጊዜ ተጨበጨበ

ከዚያ በኋላ ለማረፊያ ወደተዘጋጀው ቤተ መንግሥታቸው ሲሔዱ የሕዝቡ ሰልፍና በከተማው ውሥጥ ያሉት ሴቶች ዕልል ሲሉ ጋራ የተናደ ይመስላል እንጂ የሕዝብ አካሔድና የሰው ድምፅ አይመስልም ነበር ።ከተዘጋጀው ስፍራ ከደረሱ በኋላ ሠራዊቱን ግባ ብለውሃል ብሎ አጋፋሪ ፈቂበሉ ሲአሰናብተው የተሰበሰበው ሕዝብ እንኳን ደህና ገቡልን ዓሰበ ተፈሪ በምትባል ከተማዎ ነዋሪ ስለሆንን ግርማዊነትዎም አሰበው ከተማዎን ስለጐበኙልን ደስታችን ከልክ ያለፈ ሁኖአል ሺሕ ዓመት ያንግሥልን መንግሥትዎ ለዘለዓለም ትኑር ከነልጅ ልጅዎ ይግዙ ብሎ ዳር እስከ ዳር ሶስት ጊዜ አጨብጭቦ ሠራዊቱ ተሰናብቶ ተመለሰ የሰልፉንና የቤተ መንግሥቱን መዘጋጀት ሠራተኞችን አስቀድሜ ስለጻፍሁ እንደሚአምር ክቡራን አንባቢዎች አትስቱትምና ንባቡ እንዳይሰለች ትተነዋል ጃንሆይም ከተከተሏቸው መሳፍንት ጋራ በተሰናዳው ቤተ መንግሥታቸው አድረው በማግሥቱ በየካቲት ፲ ቀን ግርማዊ

ንጉሡ ነገሥትና እቴጌ፥ ልዑል መኰንን ልዕልት ፀሐይ ደብረ ሰላም እግዚአብሔር አብን ተሳልመው ከተመለሱ በኋላ ታላቅ ግብዣ ተደረገ ግብዣው ከተፈጸመ በኋላ ቢሮ ቤትን ሐርሽብን ግምጃ ቤቱን ጐብኝተው ልክ ሶስት ሰዓት ሲሆን ጃንሆይ ከተማውን ለመጐብኘት ፈቃዳቸው ስለሆነ በክቡር አዛጋር ወርቅነህ አመልካችነት ወደ(ማያ)ወሀው በአቶ መቢል ስለሔዱ የከተማውሕዝብ መጀመሯ የኢትዮጵያ ባንዲራዎች በቅስት አምረው ሠራዊቱ በተቀበላቸው በታ ተሰልፎ እንዲሸኝ ታዝዞ ነበርና ሕዝቡ ተሰብስቦ ሲጠባበቅ ልዑል ራስ ኃይሉ ። ልዑል ራስ ስዩም፥ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዓባይነህ ክቡር ፊታውራሪ ጣሰው ባንድ አቶሞቢል በከተማው ማህል የከተማውን ዕዳት አይተው ጃንሆይ ወዳሉበት ስለሔዱ በየካቲት ፱ ቀን የገቡት ከማታው በ፩ ሰአት ስለሆነ በደስታው ብዛት ሕዝቡ በግልጽ ለይቶ አላያቸውምና እንደገና ደስታና እልልታ ሆን ወደዚያው ሕዝቡ ተሰልፎ ሲጠብቅ በመጀመሯው በታላቁ አቶ ሞቢል ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት፥ግርማዊት እቴጌ ልዑል መኰንን፥ልዕልት ፀሐይ በሁለተኛው አቶሞቢል ልዑል ራስ ኃይሉ፥ልዑል ራስ ሥዩም፥ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ክቡር ፊታውራሪ ጣሰው ።

በሶስተኛው አቶ ሞቢል ክብርት ወይዘሮ ዓፀደ ክብርት ወይዘሮ የሻሽ ወርቅ ክቡር ደጃዝማች ከበደ ጎንጉል፥ክቡር አስፋወሰን ከሣ ሆነው ስለመጡ የከተማው ሴት እልል ሲል ሕዝቡም በግራ ወ ምበሩ ባቶ እረዴ አግር ተሰልፎ በአቶ ሞቢል ልክ ሲጓዝ የዕድለኛይቱ ከተማ ማማርና መድመቅ ክልክ ያለፈ ሆኖ ያስደንቃል ወደዚያው ዓሥር ደቂቃ ያህል ያስበ ተፈሪን ሆፒታልና ሙስተሬ በተቀበለው ፈቃድ ያቆመውን የእንጨትና የወፍጮ መኪና አይተው ጕዞ ሲመጀር በሀገሩ ያለ ሠራተኛና ሕዝብ የጌታችን ገጽ አይተን ሳንጠግብ ሔዱብን እያለ ያዝናል እንጂ አቤት ብለን ችግራችንን እናመልክት የሚል አንድ ሰው አልነበርም። ይኸውም የሆነው ጃንሆይ ይመጣሉ ተብሎ ተስፋ ስንመኝ ባስበ ተፈሪ ያሉ የጽሕፈት ሠራተኞች ጌታችን በተቀቡት ቅብዕ መንፈስ ቅዱስ ሥዩመ እግዚአብሔር ሁነው ከተማቸውንና ነፃነት የሰጡንን እኛን ባሮቻቸውን ለመጐብኘት ቢመጡ እናስቸግርምና ከንደበታችሁ ተጠበቁ ተበብለው ቁርጥ ምክር አድርገው ነበርና ስለዚህ አንድ አቤት ባይ ሳይኖር ሕዝቡ ጃንሆይን ሲሸኝ በከተማው ዳር ሲደርሱ ሠራዊታቸውን በደኅና ቃል ስላሰናበቱት ደስታችን ክልክ ያለፈ ሆኖ ዳር እስከ ዳር ሦስት ጊዜ ተጨብጭቦ መንግሥትዎ ለዘለዓለም ትኑር ከነልጅ ልጅዎ ይግዙ ሁለተኛም ብርሃን ገጽዎን ለማየት ያብቃን ብሎ ሕዝቡ ሲመለስ በየክፍሉ ሠራተኞቹ ያደረጉትን ፈንጠዝያ ላየው ሰው ይደንቃል ። ጠመሸትም ክቡር አዛጋር ወርቅነህ ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ አቶ ኃይሌ መረኑ ሒደው ነበርና የከተማውን ሕዝብ በ፱ ሰዓት ለግብር እንድትገባ ተብሎ ስለተለፈፈ ሕዝቡም ምነው ዛሬ የምናድረው ጃንሆይ በደሩበት በተቀደሰው በተባረከው ቦታ በሆነ እያለ እየተመኘ ሲጠባበቅ ክቡር ቀኛዝማች ይነሡ ዓባይነህ ለግብዣ ጠርተውኝ ሒጄ ነበርና ግብዣው ከተፈጸመ በኋላ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ጃንሆይ በዚች በዕድለኛይቱ አገር መጥተው ስላገኘኋቸውና ስላየኋቸው ደስታዬ ክልክ ያለፈ ሆኑእል የዚችም የዕድለኛይቱ ከተማ ሠራተኞች ይህንን ፎስሙኝ ይህንን ያድርጉልኝ ሳይሉ በደስታ ስለሸኙኣቸው ሠራተኞቹን አመስግኚ የሥልጣኔ ጕዳና መሪአቸውንም አመስግናለሁ ብለው ከፈጸሙ በኋላ ጌታችንን አመስግነን ተለያየን-

ወደዚያው ልክ ፲፪ ሰዓት ሲሆን ክቡር አዛጋር ወርቅነህ በአቶ ሞቢል ስለገቡ የከተማው ሠራተኛ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሔዶ ተቀበላቸው በቤተ መንግሥቱም ግብር እንዲዘጋጅ ባለቤታቸው ክብርት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ አዝዘው ነበርና በእልፍኝ አዳራሽ ክቡር አዛጋር ወርቅነህ ክፍ ባለው ማዕርጋቸው ላይ ተቀምጠው ግብር ገብቶ መኳንንቱና ሠራተኞቹ ሲጋበዙ አስተናባሪዎቹን አቶ መታፈሻ ውዴን አቶ ጸጋ ሥላሴን ሽፈራ ከፈላን ተሰማን ለተመለከታቸው ያፈጣጠናቸው ነገር ያስደንቃል ። ይልቁንም አሳላፊ ዘለለው የሚባሉት አስተናባሪ ባንድ እጅ ጣታቸው ፯ብርሌ ጠጅ ባንድ እጅ ጣታቸው ፯ብርሌ ጠጅ ይዘው ሲአሳልፉ የበሰለ ወይን መስሎ ይታይ ነበር ግብሩም ከተፈጸመ በኋላ እንዳማዕርጉ ነቢትና ቢራ ተከፍቶ ከተጋበዝን በኋላ አባቶቻችን ያላዩትን ይህን ያህል ዕድል እኛ ስላገኘን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሺህ ዓመት ያንግሥልን ይህችንም በማይረሳ ስም የተመሠረተችውን ከተማ ጃንሆይ ጐብኝተዋት ስለሔዱ እግዚአብሔር ፍጻሜዋን ለማየት ያብቃን አገራቸውን አስከባሪ መንግሥታቸውን አክባሪ የሆኑትን ክቡር አዛጋር ወርቅነህንም ከጌታቸው የተቀበሉትን ሐሳብ እምላክ ይፈጽምላቸው ብለን እየተሰናበትን ሒደን ሁለተኛም የካቲት ፲፪ቀን ለከተማው ሕዝብ ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ሲገቡ ግብር ተደረገ።ቃሉን ሳይተካከል ስለጻፍሁ በሁለተኛው በትምህርት ለመቀልጠፍ እመኛለሁ።ተኰላ መብራቱ ።

ስለተማሪ ቤቶች መጐብኘት ፣

ትጋትና ንቃት ይከተላል በሔዱበት እንዲሉ የትምርትና የጥበብ ሚኒስትር መልአከ ሕይወት ወልደ ሐና አሳቢና ትጉህ ስለሆኑ የተማሪ ቤቶችን ለመጐብኘት በሔዱ ጊዜ በየተማሪ ቤቱ ክፍል ደስ የሚአሰኝ ዲስኩር ተናገሩ ።

መጀመርያ መጋቢት ፫ቀን ባምስት ሰዓት የጥበብና የትምህርትንቢሮ ጐብኝተው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገሩ።

የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር ዲሬክተር ።

ጸሐፊዎችና ሠራተኞች ።

የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር በሥርዓት ሁኖ የተመሠረተ ጃንሆይ በአልጋ ወራሽነታቸው ጊዜ የዛሬ ፫ዓመት ነው ይኸውም ፫ዓመት ሚኒስቴሩ ስሙን አስጠርቶ በልዩ የቆመበት ዘመን ነው እንጂ ጅምሩስ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ነው ይልቁንም ስመ ጥሩው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በገንዘባቸው ብዙ ወጣቶች ለትምህርት ወደአውሮፓ በየጊዜው እየላኩ ለፍሬ ከአበቁአቸው በኋላ ለመንግሥታችን ሥራ በየክፍሉ የሚረዱና የሚአገለግሉ እነሆ ብዙዎች ናቸው።

ደግሞ ዕፁብ ሆኖ የተአነፀ የትምህርት ቤት በልዩ ገንዘባቸው አቁመው ብዙ ፍሬ እንዲአስገኝ አደረጉ አሁንም የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር በዚህ በ፳ዓመት ውሥጥ ደስ የሚአሰኝ አካሔድ ስለ ተራመደ በጣም እናደንቃለን።ይልቁንም በዲሬክተሩ በብላቴን ጌታ ማህሌ ፀዳሉ ትጋት ትምህርትና ጥበብ በስማቸው መልካም ቤት ስለተሠራላቸው ከልባችን እናመሰግናለን ። እንደዚሁም ጸሐፊዎችና ሠራተኞች በፍቅርና በአንድነት ለሥራ ረዳት በመሆናችሁ እናመሰግናችኋለን ።

ይኸውም ሚኒስቴር ገናና እዲሆን ሥራውም እንዲከናወንልት እተቻለ ድረስ መጣጣሬን አረጋግጥላችኋለሁ ።

ለጃንሆይ ለእቴጌ ና ለቤተ ሰዎችም ዕድሜ ከጤና ጋር ይስጥልን ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር።

ሁለተኛም መጋቢት ፲ቀን በ፱ሰዓት (ዳግማዊ ምኒልክን ተማሪ ቤት ጐብኝተው ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሆይ ።

ትምህርትና ቁልፍ አንድ ናቸው ቍልፍ የተዘጋውን በር እንደሚከፍት እንደዚሁም ትምህርት ድንቁርና የዘጋውን አእምሮ በጥበብ ከፍቶ በውቀት መሠረት እንዲከናወን ያደርገዋል ይኸንም ማለቴ የትምህርት ቤት ከቆመ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ መንግሥት ለመምህራንና ለትምህርት መሣሪያ ብዙ ገንዘብ ሳያቋርጥ እየከፈለ ብዙ ልጆች ለውቀት አድርሷል።ለወደፊትም ተማሪ ቤቱ እጅግ እየተሻሻለ እንዲሔድ መንግሥት ጠንክሮ አስበበታል።አሁንም ከዚህ የተሰበሰባችሁ ተማሪዎች ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ እነዋወር አስተዳዳሪ የሚሆናችሁ ትምህርት ነውና ውጥናችሁ ሁሉ ለዕውቀት ፍለጋና ለኢትዮጵያ እርዳታ እንዲሆን እንቃቃችሁ አለሁ ።

እኔም ታላቁን የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትርነት የተሾምሁበት ጊዜ ትምህርት በተወደደበት ሰዓት ነውና መልካም ዕድል ስለአጋጠመኝ ኢትዮጵያ ትምህርት እንዲስፋፋበት ጥበብ እንዲነግሥበት በብዙ ትጋት ማሰቤን ይልቁንም ከጃንሆይ የተቀበልሁትን ያለቀውን አደራ ለመፈጸም የጋለ ምኞት እንደአለኝ አገልጽላችኋለሁ ።

እናንተም መምህራን የምትዘሩት ለመልካም ፍሬ እንዲሆን በቅን ልቡና እንድትአስተምሩልን እናሳስባችኋለን ።

ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት።ዕድሜ ለግርማዊት እቴጌና ለንጉሣዊ ቤተ ዘመድ ለኢትዮጵያ ልማትና ስፋት ይሁን

ሦስተኛም ባሥር ሰዓት የተፈሪ መኰንንን ተማሪ ቤት ጐብኝተው ቀጥሎ የተጻፈውን ዲስኩር ተናገሩ ።

የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሆይ ።

ከሀብት ሁሉ ተቀዳሚ ጥበብ መሆንዋን ጥበብም የምትገኘው በትምህርት እንጂ በወርቅ እንዳይደለ ወርቅም የምትገኘው በጥበብ እንደሆነ በለባውያን ዘንድ የተገነዘበ ነው ስለ ዚህ ከወርቅ ሀብት ይልቅ የጥበብ ሀብት ያለው ሰው በጣም ደስ ይለዋል ያኰራዋልም እስመ ትኄይስ ጥበብ እምዕንቍ ዘብዙኅ ሤጡ ኵሉ ክብር ኢመጠና ላቲ ምሳሌ ም፫ ቍ ፲፭ በዚህ ሐሳብ መሠረት የማያልቀውን ሀብት ትምህርትን እንድታገኙ የታጫችሁ ተማሪዎች የጥበብ ናፍቆት እንድታድርባችሁ እንለምናችኋለን አኳኋናችሁም ሁሉ ተስፋ ያለው ስለ ሆነ ኢትዮጵያን ደስታ አልተለያትም እናንተም መምህራን ተማሪዎች ወደውቀት ደረጃ እየተራመዱ ቢሄዱ የናንተ ትጋት ይመሰከራልና ለስማችሁ መታሰቢያ እንዲሆን እንድትነቃቁ የከበደውን አደራ እንሰጣችኋለን ።

ዕድሜ ለግርማዊ ኃይለ ሥላሴ ።
ዕድሜ ለግርማዊት እቴጌ መነንና ለመንግሥት
ቤተ ዘመድ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

አራተኛ ባሥራ አንድ ሰዓት የእቴጌ መነንን ተማሪ ቤት ጐብኝተው ተማሪዎቹንም እጅግ ደስ የሚያሰኝ ምክር መክረው ወደቤታቸው ተመለሱ ።

በመታመን የሚገኘው የሹመት ዕድል

አቶ በዛብህ ረታ በግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በክብር ዘበኞች ክፍል የመቶ አለቃ ሁኖ በመታመንና በትጋት ሲያገለግል የቆየ ነበር። መታመንና መንግሥትን በቅንነት ማገልገል መጥቀሙ የታወቀ ስለሆነ። በዚሁ በእምነቱ ሳይለምን ተመርጦ ያቶ ኃይሌ ሮበ የነበረውን ሥራ ማግኘቱን እናስታውቃለን

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክቶር ጂ ኤ ማርቲኒ በፓሪስ ዩኒቤርሲቲ የተመሰከረላቸው።በዚሁ መታከሚያ ቤት የሴት በሽታ የልጆች በሽታ፤ የዓይን በሽታ፤ የጆሮ በሽታ፤ የጉሮሮ በሽታ፤ ቂጥኝ ይህነን የመሰለውን ሁሉ በደኅና ያክማሉ። ቤታቸውም አራዳ ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ጧት ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ነው። ከ፱ተኩል እስከ ፲፩ ሰዓት ያክማሉ ዶክቶር ጂ ኤ ማርቲኒ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ከምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚሀ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ሳንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ዶጓጦ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምባሳል ፤ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የሆላሊት ፤ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪክ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩባንያ ሲንጀር ቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጎበኙለት በማክበር ያመለክታል

በየይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሲንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ን ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ ።



ባለነጭፈረስዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር ፤ ግርማዊ ንጉሥ አሰናጁ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ከልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፲፫
8me ANNE. № 13

ሐሙስ መጋቢት ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
JEUDI 24 MARS 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጣት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres.

የአፈርሳታ መከልከል ቀርቧል ።

አፈርሳታ አገር ማስቸገሩን ብዙ ጊዜ ብርሃንና ሰላም አስታውቋል ። አፈርሳታ የመጣበት ምክንያት ሌባ ወምበዴ የሕዝቡን ገንዘብ አጥፍተው እንዳይቀሩ አጥፊዎችን አገር እየመረመረ እንዲያወጣቸው አገር በሰላም እንዲኖር ነበር። ነገር ግን ለሕዝብ ታላቅ ጉዳት መስሎ ታይቶናልና ብናስታውቅ ከነውር ይቈጠር አይመስለንም ። ይህንም ነገር ብርሃናዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አስተውለውታልና ከዚህ የሚሻል ደምብ ያደርጉልናል በማለት ተስፋ እናደርጋለን። እነሆ አሁንም በቅርብ ቀን በክቡር ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል ግዛት ወምበዴ የቀማቸው ነጋዴዎች ወደ አደባባይ ቀርበው ጮሁ። ጃንሆይም ነገሩን ጠይቀው የተዘረፋችሁት ዕቃ በብር ምን ያህል ሒሳብ ይሆናል ብለው ጠየቁ ። ነጋዴዎችም አስበው ፫ ሺህ ብር ይሆናል አሉ ። ጃንሆይም ቢትወደድን ዋስ ጥሩላቸውና አንተ ክፈል ዋሱን የንግድ ሚኒስቴር ነገረፈጅ አቶ ዓምደ መስቀል ይቆጠርላቸው ብለው በፈረዱ ጊዜ በአደባባይ የነበረው ሕዝብ ሁሉ እጅግ አመሰገነ ። እውነት ነው ሰው ሁሉ የሀገሩን ሰው ክፋትና ደግነቱን ያውቃል አገረ ገዢም የሕዝብ ሚዛን ነውና ደጉንና ክፉውን መመርመር ያገባዋል ። የበጎች እረኛ በጎችን በየስማቸው እንዲጠራ የተገባ መሆኑን በዮሐንስ ወንጌል ሰምተናል ። በማናቸውም ክፍል በአለአባት ከማዕርጉ አልተዋረደም በዳር አገርም ቆሮ ለጋ ። ገራዳ መላቃ ዶሚና ይባላል ። የአገራቸውን መሬት ከፍታውንና ዝቅታውን፥ ተራራውን፥ሜዳውን፥ ገደሉን ከልጅነቱ ጀምሮ የሚአውቀው ስለሆነ በምክንያት ተአገሩ የወጣ እንደሆነ ይህን በላይ የተጻፈውን ሁሉ እንደ እሚአየው አድርጎ ይቈጣጠራል። እንግዲህ በአለ አባት ሜዳና ገደሉን አገሩ የሚአበቅለውን ካወቀ ሌባውንና ወስላታውን አላውቅም ቢል ውሸት መስሎ ይታየናል ። እንግዲህ የድንቍርናውን ወራት እግዚአብሔር አሳለፈው እንደአለ ሐዋርያ ጳውሎስ ያ ጊዜ አልፎአልና ከእንግዲህ ወዲህ ሹማምትና በአለአባት ነገሩን እያወቃችሁ በጎችን በበረት ዘግታችሁ ብታስቸግሩ ልብ ዳኛ ነውና ይወቅሳችኋል።እንግዲህ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በብሩህ ልባቸው አሁን በቀደም የጀመሩት ነገር እንዲፈጸም ተስፋ አድርገናል ። በአላባት ነኝ ብሎ የአገሩን ሕዝብ ጠባይ ካላወቀ የሕዝብ ጠባይ መርምሮ የሚያውቀውን በአላባት ማድረግ ይቻላል ። አገረ ገዢም እንዲሁ ይሆናል ። የታወቀው ዋሾ ሌባሻይ ጊዜ እስቲገልጽበት ድረስ እውነተኛ የንጉሥ ቁና ተብሎ እንደ ኖረ ይህም አፈርሳታ የሚባል ክፉ ነገር መልካም መስሎ ቀርቧልና መከልከል የሚገባ መሆኑን በሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል ። የጠፋው የደኃ ገንዘብ እንዴት ሁኖ ይገኛልን? ትለኝ እንደሆነ እሥረኛ ቢጠፋ ዘበኛ ኃላፊ ሁኖ ይያዝ የለምን አገረ ገዥና በአላባትም የአገር ዘበኞች ናቸውና በጠፋው ገንዘብ ኃላፊ መሆን ይገባቸዋል ። የሆነ ሁኖ አገር አለ ምክር ቤት አለማገር አይፀናምና ሐሳባችንን ለአማካሪዎች እናቀርባለን ።

በጎ አድራጊ አበደረ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽነት ከታጩበት ቀን ጀምሮ የጊዜውን አኳኋን በመከተል የሕዝቡን ሀብት ለማሻሻልና በሕዝቡም ላይ የተጫነውን ከባድ የሆነ የጭለማን ቀንበር በብርሃኑ አእምሯቸው ለማቃለል በስንፍና ሳይሆን በትጋት እንደሚደክሙበት በፍጹም እናምናለን ። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ እነሆ አንድ ትጉህ እረኛ በጎቹን ተኵላ እንዳይነጥቀው ተጠንቅቆ ነቅቶ እንደሚጠብቅ እንዲሁም አደራ በተቀበሉት ሕዝባቸው ላይ የምሕረት ዓይናቸው ዘወትር ለመጐብኘት አይዘገይም ። እንደምን ትሉን እንደሆን ባለፉት የኢትዮጵያ ነገሥታትና መኳንንት በባለጸጎችም ቢሆን ከዳግማዊ ምኒልክና ከልዑል ራስ መኰንን በቀር ከዚያ ሁሉ ሀብትና ዕድል የተነሣ የሀገር ፍቅር አድሮባቸው ለሚመጡት ትውልድ ለሥራ መሪ የሚሆንና መታሰቢያ ሁኖ የሚኖር ፩ድ ፩ድ ቀዋሚ ነገር በዘመናቸው ባላተሠራ የሀገርዋን ሀብትና ክብር የሕዝቡን አእምሮና ብልጽግና እያጠበበ መሔዱን ያለጥርጥር እናምናለን፥ስለዚህ እነሆ በጎ ሐሳቢው ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወዘያበዝኅ ሥርናየ የኃድኅ ለአሕዛብ (ሲራክ ፲፩ ፳፮)የሚለውን ቃል መሠረት አድርገው አሁንም ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለታላላቆችም ባለጸጎች የበጎ ሕሊና

መምህር ስመሆን ሲሉ ኋላም ለሚመጡት ትውልድ የሥራ መሪነትን ለማፅናት የዚህንም ዓለም ድልብ በመናቅ ገንዘባቸውን አፍስሰው የመሠረቱልን ሥራዎች በእግአብሔር ፈቃድ አያሌ ፍሬዎችን አፍርተውልናል፡ከነዚሁም አንዱ የሕዝብን ዋና ጤና ጠባቂ የሆነው ሆፒታል ቤተሣይዳ ነው።ቤተ ሣይዳም ማለት የመዳኛ ቤት ማለት ነው። ማርቆስ ፰ ፳፪። ይኸውም ሆፒታል ከተመሠረተ ፱ኝ ዓመቱ ሆኖታል። ነገር ግን የሕክምናው ሥራ ከተጀመረ ፯ኛ ዓመቱ ነው በዚሁም በሆፒታል ልዩ ልዩ የሆኑ የሕክምና መሣሪዎች ስለሚገኙ ትጉሁ ዶክተር ሐነር በሥራቸውና በአንዋዋራቸው ፩ቀን ስንኳን ብስጭትና ቅሬታ ሳያገኛቸው በደስታና በትጋት ሥራቸውን ይሠራሉ ይልቁንም ለሐኪሞቹ በልታወቀ ጥልቅ በሆነ የውሥጥ በሽታ ለሚታመሙት በሽተኞች ራዲኦ የሚባለውን የውሥጥን በሽታ መርምሮ በጉልሕ የሚያሳየውን ታላቅ መሣሪ በነ አድራጊው ንጉሠ ነገሥት አደራ ለተቀበሉት ሕዝብ አስበው ስላስመጡት የሕዝቡ ልብ ያለመጠን በደስታ ተነክቷል።ታላቁ ውለታቸውንም ቸሩ እግዚአብሔር ከንቱ አያስቀርባቸው እያለ የጋለ ምስጋናውን ያቀርባል።በዚሁም ሆፒታል ገብተውና ተመላልሰው የታከሙትን በሽተኞች እስታትስቲክ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዝ እንገልጻለን ።

የሆፒታል ቤተ ሳይዳ ያዳሪ በሽተኞች እስታትስቲክ የስድስት ዓመት		፩ኛ ዓመት	፪ኛ ዓመት	፫ኛ ዓመት	፬ኛ ዓመት	፭ኛ ዓመት	፮ኛ ዓመት	የስድስት ዓመት	
		፲፱፻፲፰ ዓም ከ፳፫ / ፯ ፳፱/፱	፲፱፻፲፱ ዓም ከ፯ / ፯ ፳፬/፬	፲፱፻፳ ዓ ም ከ፳፫/፰ ፳፬ /፬	፲፱፻፳፩ ዓም ከ፳፫/፰ ፳፬/፬	፲፱፻፳፪ ዓም ከ፳፫ ፰/፳፪ / ፬	፲፱፻፳፫ ዓም ከ፳፫ / ፰ ፲ / ፬	የየዓይነቱ ድምር ።	ጠቅላላ ድምር ።
በሆፒታል ቤተ ሳይዳ	የአዳሪበሽተኞች ድምር	187	253	330	385	379	416	1950	1950
	የተኙበት ቀን ድምር	3702	5868	7052	6095	6451	5589	34757	34757
	ለየ፩ዳንዳቸው የቀኑ ልክ ሚዬን (መሐከለኛ)	19	23	21	16	17	13		
የሕክምናቸው ዓይነት	በኦፒራስዮን (በቅድ)	169	221	257	242	236	260	1375	1375
	በመድኃኒት።	18	32	73	143	143	156	565	565
	ድምር።	187	253	330	385	379	416	1950	
ሙዋቾች የሞቱበት ምክንያት	ከኦፒራስዮን በኋላ በቅድ	4	11	6	9	3	6	53	
	በ ድንገት አደጋ		1	4	3	3	3		
	በሌላ በሽታ	3	6	9	12	10	10	50	
	ድምር	7	18	19	24	16	19	103	103
የዳኑት ሰዎች	የታመሙት ሰዎች	187	253	330	385	379	416	1950	
	የሞቱት ሰዎች	7	18	19	24	16	19	103	
	የዳኑት ሰዎች ድምር	180	235	311	361	363	397		1847
የገንዘብ አከፋፈል ዓይነት	በገንዘባቸው የታከሙ	16	160	197	139	328	312	1152	
	በፋክቱር ያልከፈሉ					16	66	82	
	በነፃ የታከሙ	171	93	133	246	35	38	716	
	ድምር	187	253	330	385	379	416		1950

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጻፉት በሽተኞች በሆፒታሉ ውሥጥ ገብተው ፤ አዳሪ ሁነው የታከሙት ናቸው ። ተመላልሰው በክሊኒክ የታከሙት በሽተኞች ግን በ፩ዓመት ውሥጥ ከ፳እስከ ፱ሺ ያህል ይሆናሉ ።

መድኃኒተ ፈነወ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መዝ ፻፲ ያለው ቤተ ሣይዳ ሆፒታል መሆኑን በፍጹም ያሳስበናል እነሆ ዓቅሙን በማሳነስ በ፳፭ አልጋ ይህን ያህል የሕዝብ መድኃኒት ከወዴት ይገኛል ። በውኑ የሐኪሙን ብርታትና ትጋት ያስረዳል ። በሮፓ እንደምንሰማው አንድ አንዱ ሆፒታል ከ፫፻ እስከ ፭፻ አልጋ ያለው ነው ። በእንደዚህ ያለው ሆፒታል የሆነ እንደሆን ምናልባት የ፩ዓመት ሥራ ይሆናል ግርማዊነታቸው ይህን ሁሉ በማሰብ ቤተ ሣይዳ ሆፒታል ፳፭ አልጋ ብቻ በመሆኑ የግርማዊነታቸውን በጎ ሕሊና ለማጋነንና የሐኪሙንም ድካም ለማጉላት ስለሰነፈ ፤ የሕዝባቸውን ሕይ-

ወት የሚናፍቁ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆፒታሉን ለማስፋት ሙሉ ፈቃዳቸው ሁኖ ፤ ከሆፒታሉ የሚአዋስነውን የደጃች በላይነህ የነበረውን ቦታ በሙሉ እስከ ፊት በር ድረስ ተመርተነዋል ። ስለዚህ የግርማዊነታቸውንና የመሰፍንቶቻቸውን ችሮታ ተጠባብቀን በጥቂት ቀን ሥራው እንዲጀመር ሙሉ ተስፋ አለን ።

(ምክር)እላይ እንዳመለከትነው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ገንዘባቸውን አፍስሰው ፤ ለኢትዮጵያውያን መታሰቢያ የሚሆን በሮፓውያን ሕግ አኳኋን በመልከም አዘጋጅተው ሆፒታል ቤት ማይዳን በመመሥረት ብቻ አጊዜው ስናደንቅበየጊዜውም የገንዘባቸውን አሰጣጥ እውነተኛ ማስረጃ የሚሆነውንና ፤ በጎ ሥራ ተከታዮቻቸውም በመራራት የሰጡትን እርዳታ ፤ በሆፒታሉም ውሥጥ ሕሙማኑም የከፈሉት ገንዘብ ገቢና ወጭውን እስታትስቲክ ቀጥለን ለማስታወቅ እንደፍራለን ።

የሆፒታል ቤት ማይዳ የ፮ ዓመት ገቢ ገንዘብ		፩ኛ ዓመት		፪ኛ ዓመት		፫ኛዓመት		፬ኛ ዓመት		፭ኛ ዓመት		፮ኛ ዓመት		የስድስቱ ዓመት			
		፲፱፻፲፰ ዓም		፲፱፻፲፱ ዓም		፲፱፻፳ ዓ ም		፲፱፻፳፩ዓም		፲፱፻፳፪ ዓም		፲፱፻፳፫ ዓም		የየዓይነቱ ድምር		ጠቅላላ ድምር	
ያገባቡ ዓይነት		ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ
የግርማዊ ንጉ ነገ ቀ ኃይለ ሥላሴ ስጦታ	ለሆፒታሉ ለሐኪሙ ቤት ለማተሚያ ቤት ሥራ													73841	7		
	በጓዳ በኩል	500		29036	6	23806	18	15603	2	30501		67787	11	158234	5	265075	12
	ከማተሚያ ቤት ገቢ	17000		3500				3500				9000		33000			
እርዳታ	በጎ አድራጊዎች የሰጡት እርዳታ	2000		15000		500				3000		1000		21500		21500	
የሆፒታሉ ውስጥ ገቢ	ከአዳሪ በሽተኛ ገቢ	118		2290	16	2594		2533		5880		9682	14	23097	30		
	ከውጭ ተመላላሾች	129	21	259	16	245		593	24	941	2	885	25	3054	24		
	የመድኃኒት ሽያጭ	11		19				28	24	1058	16	994	15	2111	23	65955	10
	በየዓይነቱ ገቢ	8		16801	8	13203	4	5116	7	659	24	183	18	35971	29		
	የሬዲኦማራሬ ገቢ							629		380		710		1719			
	ድምር	19766	21	66906	14	40348	22	28003	25	42420	10	81243	19			352530	22
ማስረጃ	የግርማዊ ጃንሆይ ስጦታ													265075	12		
	የበጎ አድራጊዎች እርዳታ													21500			
	የሆፒታሉ ውሥጥ ገቢ													65955	10		
	ድምር															352530	22

የሆፒታል ቤት ማይዳ የ፮ ዓመት ወጭ ገንዘብ		፩ኛ ዓመት		፪ኛ ዓመት		፫ኛ ዓመት		፬ኛ ዓመት		፭ኛ ዓመት		፮ኛ ዓመት		የስድስቱ ዓመት			
		፲፱፻፲፰ ዓም		፲፱፻፲፱ ዓም		፲፱፻፳ ዓም		፲፱፻፳፩ዓም		፲፱፻፳፪ ዓም		፲፱፻፳፫ ዓም		የየዓይነቱ ድምር		ጠቅላላ ድምር	
ያወጣጡ ዓይነት		ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ	ብር	ቤ
ለሆፒታሉናለሐኪሞችለማቤትሥራ														73841	7		
ለመድኃኒት መግዣ		2000		2270	30	3048	8	4005	24	2505	4	2156	12	15986	14		
ለሆፒታል ሠራተኞች ቀለብ		5914	14	12783	14	14208	9	8217	16	14159		36793	24	92076	13		
ለወጥቤት		580	6	2743	22	4345	20	4601	20	1237	30	1790	16	15299	19		
በየዓይነቱ ወጭ		10416	12	42043	26	26310	27	11374	11	24150	18	39139	25	153435	22		
ድምር		18911		59841	28	47913	1	28199	6	42052	20	79880	13			350639	12
የ፮ዓመት ጠቅላላ	ገቢ													352530	22		
	ወጭ													350639	12		
በማጥንአዳፊ ገንዘብ																1891	10
ሚዛን ።																352530	22

ስለበጐ አድራጊዎች ።

የዚህ ዓለም ብዕል ኃላፊ ጠፊ ነው ። በጎ ሥራ ግን ለዘለዓለም ሕያው ነው ማቴ ፯ ፲፱ ። ሉቃ ፲፪ ፴፫ ።

ከዚህም ቀጥለን ለሆፒታሉ እርዳታ የሰጡትን ሰዎች እንጽፋለን ። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሪነት በጎ ሐሳባቸውን ተከትለው የሀገር ፍቅር ያደረባቸውን የኢትዮጵያ ተወላጆች

የሆኑትንና የውጭ አገር መኳንንት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በመራራት ያደረጉትን ዋና ውለታቸውን ባለመዘንጋት በሆፒታሉ ስም ሆነን ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እያቀረብን እነሆ ታላቅ እርዳታቸውን ልናስታውቅ እንወዳለን ።

	እርዳታ የሰጡ ሰዎች ስም ።		ብር	ቤ	የተገዛው ዕቃ ዓይነት ።
ኢትዮጵያውያን	ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ		2000		
	ግርማዊ ንጉ ነገ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ	በ	48421	4	በየዓይነቱ የመጻሕፍት ማተሚያ ገዝተው ሰጡ
	ግርማዊት እቴጌ መነን	በ	3000		ግሩም የሆነ የመቅደጃ ጠረጴዛ
	ወይዘሮ ሮማን ወርቅ ተፈሪ		1000		
	ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው	በ	2500		የኦፕራስዮን ቤት የኤሌትሪክ ብርጭቆ ሰጡ
	ደጃዝማች ዓምዴ	በ	500		ምንጣፍ ሰጡ ።
ሮፓውያን	ባሮ ሮሽልድ				፩(ዲያቴርሚ)የሙቀት ማሽ መኪና ።
	ዱክ ዴዛብሩዝ		1000		
	ሙሴ ኪሪኮር ሴፌሪያን		1000		
	ሙሴ ማርክአንትስ ጀርመናዊ		1000		
	መሐመድ አሊ		12000		
	ሎርድ ባክስቶን		50 ጊኒ		፳፫ የአማርኛ ሐዲስ ኪዳን
	ሙሴ ሻርኒ				፫የፈረንሳዊ ሐዲስ ኪዳን
					፫የእንግሊዝ ሐዲስ ኪዳን

ከቶ በጎ ሥራን አስተውሎ መሥራት ምንኛ ታላቅ ዕድል ነው ። እነዚህ ከዚህ በላይ እርዳታቸውን ያደረጉ ሰዎች ብዙውን ነገር በማስተዋልና በመመርመር በጎው ሕሊናቸው ቢወቅሳቸው ነው እንጂ ፈጽሞ ማንም ሰው ቢሆን እንዳላስገደዳቸው እናምናለን ። ኦብዑላን ወዓብዳነ ምድር በይነ ምንት ኢትቀንኡ ለእንተ ተዐቢ ጸጋ ፤ መድኀኒት ለነፍስ ወሥጋ እስመ ርቱዓት ፍናዊሃ ጻድቃን የሐውርዎን ፣ ወኃጥአን ይስእንዎን እናንት ሰነፎች የሆናችሁ የምድር ባለጸጎች ሆይ ፤ ለነፍስና ለሥጋ በሚበጀው በእንደዚህ ያለው ነገር ስለምን አትቀኑም ። ክፉ አድራጊዎች (ኃጥአን)የሚሰንፉበት ። በጎ አድራጊዎች (ጻድቃን)የሚበረቱበት የቀናች መንገድ ናት ማለት ነው ። በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፍርድ ቀን መጥቶ በጌትነቱ ዙፋን በተቀመጠ ጊዜ ለሰው የሃይማኖቱ ፈተና ሆነው ለጻድቃንም ሞገስ ለኃጥአንም ወቀሳ አርጎ የሚአቀርባቸውን ቃላት ከዕለተ ሞት አስቀድመን ዛሬ ባሕይወተ ሥጋ ሳለን ልንሠራቸውና ልንፈጽማቸው የሚገባን በመሆኑ ከ፩ኛው በተቀር ፫ቱም በ፩ነት ተዘጋጅተው ሆፒታልን በመጐብኘት እንደሚገኙ ያለጥርጥር እናረጋግጣለን ማቴ ፳፭ ፴፮ ቍ፤ብዕልክሙኒ ነቅዘ ወአልባሲክሙኒ ቈንቈነ ወርቅክሙኒ ዝሀለ፤ወዛሀሉኒ፤ስምዓ ይከውን ላዕሌክሙ ወይበልዖ ለሥጋክሙ ያለው ፣ ያዕቆብ ሐዋርያ እናስታውሳችኋለን ምዕ ፭ ቍ ፫። ይልቁንም የሚአሳዝነው ሲድኑ የሕመማቸውን ጭንቅ ይረሱና ጥለዉት እንደማይሔዱ ሁሉ ለሕይወታቸው የሚከፍሉት ገንዘብ ያቄጫቸዋል ። ወይም እንዳይከፍሉ ። ይለምናሉ ። ሆፒታል ለንግድ እንዳይደለ ከሣራና ትርፉ ይኸው በግልጽ ተጽፏል ። በሚገባ ቢከፍሉ ወይም አትርፈው ቢረዱ ለድኃ ወንድማቸው መርዳት መሆኑን ማን አያውቅም? ። ያዋቂ በዳይነት ክፉ ነው ።

የቤተ ሣይዳ ሆፒታልና የማተሚያ ቤት አድሚኒስትራሲዮን።

ቅንኡ ለእንተ ተዐቢ ጸጋ ።

ብዝኑ ወተባዝኑ ወምልእዋ ለሀገር እንዳለ መልካም የሆነች ሴት ሌላ እንግዳን ሳታውቅ ፀሕግ ባልዋ ፀንታ የተባረኩ ልጆችን በመውለድ፣ለልጆችዋም አባት በፍቅርና በውነት እየተገዛች ስትኖርና ልጆችዋም አባት እናታቸውን በማክበር እናታቸውን እየወደዱና ለአባታቸው እየታዘዙ እርስበርሳቸው በፍቅር ተስማምተው አንድነት ሲኖሩ የወላጆቻቸውንም ጥቅም በተለይ ሲያገኙ በዓለም ላይ ለሰው ልጆች ሁሉ ከዚህ የበለጠ ደስታ የለም።ስለዚህ ማንም ቢሆን ለንደዚህ ላለው የዓለም አክድሖ ቢቀና የሚገባ ነገር ነውና ምንም ነገሩ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ቢሆን ለዚሁ ያንድ አገር ሴት ስለባልዋና ስለልጆችዋ በሕግ ባልዋ ጸንታ ልጆችዋን የእንጀራ አባት ፊት ሳታሳይ መኖርዋን ምክንያት አድርጌ የታየኝን ጥቂት ቃል ለብርሃንና ሰላም ልጆች ለመጻፍ አሰብሁ።

እንደዚህም ማለቴ በዓለም ላይ በአንድ ባል ጸንታ የምትኖር አንዲት ሴት ብቻ ነች ለማለት አይደለም ነገር ግን ባንድ ታላቅ አገር ውሥጥ በዙሪያዋ ያሉ ጐረቤቶች ሁሉ የመጀመሪያ ባሎቻቸውን እየፈቱ የማያውቋቸውንና የማይመስሉዋቸውን እንግዶች እያገቡ ሲኖሩ በነዚያ መካከል ይህች ድንቀኛ ሴት ብቻ በሕግ ባልዋ ጸንታ ልጆችዋን በመልካም አስተዳደግ እየጠበቀች መኖርዋ ለብዙዎች እንዳስደነቀ የጽናትዋ ነገር ለሰሚው ሁሉ የሚያስቀና ነውና ከታሪክ ጥቂት ብጽፍ መልካም የሚሆን መስሎ ስለታየኝ ነው።

አስቀድሜም ለጐረቤቶችዋ ጥቂት ቃል ከዚህ አመለክታለሁ በዚች ታላቅ ሴት ዙሪያ የሚኖሩ ሴቶች የጥንት ባሎቻቸውን እየፈቱ ሌሎችን ለማግባት የደረሱበት ምክንያት መቸውንም ሴቶች ጌጥን ይወዳሉና ሁልጊዜምም ወንዶች በጌጥ

መሰይ ነገር ሲደልሉዋቸው ይኖራሉ እንደዚሁም የብዙ አገር ሴቶችን መሰብሰብ የሚወዱ ሰዎች መጀመሪያ እነዚያ ሴቶች አስቀድመው አይተውት የማያውቁትን ለጊዜው የሚብለጨለጭ ቆይቶ ግን የማይጠቅም የነበረ እንደዶቃና ዘነል እንደሻሽና ሱቲ እንደዘይትና ሽቱም የነበረ የጌጥ ዕቃን በመልክተኞቻቸው እጅ በመስጠትና እናገባችኋለን እያሉ አማጭ የንስሓ አባቶቻቸውን በመላክ እያባበሉ የባሎቻቸውን ምሥጢር ለማወቅና ለልጆቻቸው የሴቶቹን እንኳ ትገልጸ ያልነበረውን ጥቅም ለማግኘት በቂ ሁለተኛ ለልጆቻቸው እንደሱክር ያለ ጣፋጭ ነገር እየሰጡና እያታለሉ ደግሞም ነገርን በማስመሰል በልዩ ልዩ ዓይነት ምክንያት ወገን ከወገኑ በመለያየት ጥንታዊ ፍቅራቸውን አጥፍተው አባት ከልጁ ልጅም ከባቱ በመጣላት ዘመዳሞቹ ሐሳባቸው ተከፍሎ እርስበርሳቸው ስምምነትን ከጡ በኋላ በመጨረሻው እነዚያ እንግዶች የሴቶቹን የሕግ ባሎችና ዋና ዋና የነበሩ ልጆች ያለምሕረት አጥፍተው ሴቶቹን ለሚስቶቻቸው ገረዶች የተረፉትንም ልጆቻቸውን አሽከሮች አድርገዋቸው እነሆ ሁሉም ነፃነታቸውን አጥተው ለዘወትር ለእንጀራ አባት ሲገዙና ሲያገለግሉ ይኖራሉ ።

ነገር ግን ይህች ታላቅ ብልህ የሆነች ሴት ምንም ለድኆች ቸርነትዋ የበዛና ገበታዋ የተዘረጋ ቢሆን ስደተኞችንም ተቀብዳና እንግዶችን አክባሪ ብትሆን ሁልጊዜም ስታስብ ለምትወደው ባልዋ ወንዶችን መውለድ ደስታዋ ከማናቸውም ነገር ይልቅ ልጆችዋን ማየት ጌጥዋ ስለሆነ የባልዋና የልጆችዋም ዋነኛ ጌጥ የወንድ መሳሪያ ለወትሮም ጨዋታቸው ፍከራ ጠባያቸውም የጀግንነት ስራ ለችግረኞች ልቡናቸው የሚራራ ለተጠጋቸው ዝምድናቸው የሚአኮራ ለሚጠላቸው ግርማቸው የሚያስፈራ ይልቁንም ምንም የሰላም ጊዜ ቢሆን ከእጃቸው መሳሪያ ሳይጠፋ የወገባቸው ትጥቅ ሳይፈታ ካህናቶቻቸውና እናቶቻቸው እንኳ ቢሆኑ ሲጋዙ በብረት ታጥረው ለዘወትር በትጋት ስለሚኖሩ አባታቸውንም ያለመጠን ስለሚወዱና ስለሚያከብሩ እንደንብ ሲወጣ ከበው ሲገባም ተሰልፈው ሲጠብቁ ይኖራሉና እንደዚህ አንበሶች የአንበሳውንና የጉሺቱ ግልገሎች ከአባት ከናታቸው ሳይለዩ በመኖራቸው የስምምነታቸውና የአንድነታቸው ፍቅር እየበዛና እየበረታ ሲሔድ ይኖራል ደግሞም የኃይል መንፈስ በውሥጣቸው የድልም መንፈስ በላያቸው ስለሆነ ከጥንት ጀምረው በቍጣ በወጡበት ስፍራ ሁሉ አሸናፊን ሆነው ይኖራሉ ስለዚህ ሴትዮዋን ያስባት እንጂ ማንም ቢሆን ሊደፍራት የሚችል የለምና የጀግናው ሚስት የጐበዛዝት እናት መልካሚቱ ሴት በሐገርዋ ተወላጅ በመጀመሪያ ባልዋ ጸንታ ልጆችዋን እንደልባቸው ስታሳድግ ትኖራለች ።

እንግዲህ በዚህ ለመግለጽ ያሰብኩት ዋነኛው ሐሳቤ ባለቤቱና ባለቤቲቱ ልጆቻቸውም በቅርብ ጊዜ የተነጋገሩት የፍቅራቸውንና የአንድነታቸውን የትምክህታቸውንም መልካም ቃል ለማሳሰብ ነውና ነገሩን ሳላበዛ በትንሹ ቀጥዬ አጽፋለሁ.

መቼውንም እግዚአብሔር ለአምልኮቱ ንጉሥ ለመንግሥቱ ወንድ ለሚስቱ ቀናዒ ነውና መልካሚቱን ሴት ማን ያገኛታል ብሎ ሰሎሞን እንደተናገረ ከሴትዮዋ ውበት የተነሣ ሰዎች ከጥንት ጀምረው በብዙ እየተመኙ ይመለከትዋት ነበርና ባለቤቱ ስለተወደደች ሚስቱ ቀንቶ ከተመልካቾች በፍጹም ሊጠብቃት አሰበ አስቦም ሳይቀር ከዕለታት ፩ቀን ከሁሉ በበለጠው ታላቅ ተራራ ላይ በወጣ ጊዜ የቤቱንና የቦታውን ዙሪያ ሁሉ ተመለከተ ባስተያየቱም የበረኞቹን ወይም የከልካዮቹን እጅግ አለመትጋት ተመልክቶ ከአጥሩም ግቢ ወገኖቹ ያልሆኑ ገብተው ለመውሰድ የያዙትን ከብት አይቶ ከጀግኖቹ አንዱን ንጠቅ ሲል ላከና ለወደፊቱ ለዘወትር በየስፍራው ተግተው እንዲጠብቁ አደረገ ። መዓዛ ወልደ ሕይወት።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክቶር ጂ ኤ ማርቲኒ በፓሪስ ዩኒቬርሲቲ የተመሰከረላቸው።በዚሁ መታከሚያ ቤት የሴት በሽታ የልጆች በሽታ፤ የዓይን በሽታ፤ የጆሮ በሽታ፤ የጉሮሮ በሽታ፤ ቂጥኝ ይህነን የመሰለውን ሁሉ በደኅና ያክማሉ። ቤታቸውም አራዳ ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ጧት ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ነው ። ፱ተኩል እስከ ፲፩ ሰዓት ያክማሉ ደክቶር ጂ ኤ ማርቲኒ ።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀደም በሎተሪው ወረቀት ላይ ሎተሪው የሚደረገው መጋቢት ፲፭ቀን ነው ተብሎ ተጽፎ ነበር ። ግን ወረቀቱ ጨርሶ ስላልተሸጠልኝ በሚያዝያ ፴ቀን እንዲሆን ተፈቅዶልኛልና ያነኑ የሎተሪ ወረቀት ለገዙ ሰዎች አስታውቃለሁ ።

መጋቢት ፲፭ቀን ፲፱፻፳፬ ።

በፈቃደ ዘነበ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማከዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርስቲያን ባታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደይ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፤ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያጥልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪካ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሴንጀር ቅቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲስ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዮ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ካገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰሚ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኜ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ውሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበሳል ።(ቤታቸውም ፀአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሲ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፲፬
8me ANNE. № 14

ሐሙስ መጋቢት ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
JEUDI 31 MARS 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊተኛ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ ለኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

መልክም ታሪክ ።

ሙሴ ፓታፓን የአርመን ሰው የኢትዮጵያን ታሪክ ደኅና አድርገው ጽፈዋል ብሎ ኵሬር ዴ ኢትዮጲ ጽፎዋል። መጽሐፋንም አይተነዋል በመልክም ሁኖ የተጠረዘ ታላቅ መጽሐፍ ነው ። ፫ሺህ ከ፫፻ብር ለዚሁ መጽሐፍ ማሳተሚያ ከፍለዋል ይባላል ። በመጽሐፉም መጨረሻ በአማርኛና በአርመን የተጻፈ መዝገበ ቃላት አለበት።ይህም መዝገበ ቃላት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ደኅና ሁኖ ታትሞአል፡በመጽሐፉ ውሥጥም የኢትዮጵያ ነገሥታትና የታላላቅ መኳንንት የታላላቆች አርመኖችም ብዙ ሥዕል አለበት። ሙሴ ፓታፓንም ብዙ ጊዜ በኢትዮጵያ ኑረዋልና ደኅና መጻፋቸውን አንጠራጠረውም።ነገር ግን መጽሐፉ የታተመው በአርመን ቋንቋ ስለ ሆነ የኢትዮጵያ ልጆች ለማንበብና ለመተርጐም ባለመቻላቸው እናዝናለን።

ሙሴ ፓታፓንም ሑስፐር በእሚባለው በግብፅ ጋዜጣ የኢትዮጵያን ደግነት ብዙ ጊዜ ጽፈዋል ይባላል ኵሬር ዴ ኢትዮጲ እንደ እሚለው ይህን ቃል በአማርኛና በፈረንሳዊ ቋንቋ አስተርጕመው ቢአሳትሙት መልካም ነበረ ግን ብዙ ዋጋ የሚአስፈልግ ስለሆነ ረዳት ቢአገኙ ሳያሳትሙት አይቀሩም በማለት ተስፋ እናደርጋለ ።

መልክም ማየት ታላቅ ጥቅም ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሴንጀር ኩባንያ የጥልፍ ቤትና ብዙ ልዩ ልዩ ባመኪና የተሠሩ ሥራዎች መጐብኘት ።የካቲት ፴ቀን በለዚሁ ቀን ክቡር ሙሴ ባንኩል የሴንጀር ኩባንያ ዲሬክተር ተዘጋጅተው ይጠብቁ ነበር።ክቡር ሙሴ ሥማከ የኢጣልያን ሌጋስዮን ጕዳይ ፈጻሚና ሙሴ ሞሬኖ የዚሁ ሌጋስዮን የኮሎኒ አማካሪ ሌሎችም የተጠሩ ነበሩ ።

ግርማዊ ን ነ ቀ ኃይለ ሥላሴ ልክ በ፲ሰዓት መጡ ሙሴ ሥማከ ሙሴ ሞሬኖና ሙሴ ባንኩል በሉበት ተቀበሏቸው። ጃንሆይን ተከትለው የመጡ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን።ክ ደጃዝማች ወልደጻድቅ ክ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ፡ክ ከንቲባ መኰንን ናቸው፡ወዲያው የተዘጋጁትን ብዙ ልዩ ልዩ ሥራዎች በሴንጀር ኩባንያ መኪና የተሠሩትን ማየት ጀመሩ ግርማዊም በኢትጵዮያ ሠራተኞች ተነድፈው የተጠለፉትን በመኪና የተሠሩትን ምንጣፎች አይተው አመሰገኑ። እዚህም እሳሎኑ ውሥጥ ሙሴ ፕሬንገ አሚራል ጂቢ ልዩን ሯያል በሚባል መሥሪአቸው በሴንጀር ልዩ መኪና የተሠሩ የጕሬዛ ቆዳ ምንጣፎች ተነጥፈው አምረው ይታዩ ነበር ።

ደግሞም ፮የሐር የኢትዮጵያ ባንዲራዎች ባንድ በኩል የቅዱስ ጊዮርጊስ ባንድ ባኩል፥የአንበሳ ሥዕል ሙሴ ባንኰል ነድፈው በመኪና በሐር የተሣሉ ተሰቅለው ይታዩ ነበር።በባንዲራዎቹም ጃንሆይ በጣም ደስ አላቸው ።

ግርማዊ ን ነ ቀ ኃይለ ሥላሴ ይህንኑ መጥተው ስለጐበኙላቸው የማይረሳ መታሰቢያ ፎተግራፍ ተነሡ ።

ከዚሁ በላይ ሻምፓኝ ተከፈተና ሙሴ ባንኩል ስለ ጃንሆይና ስለቤተሰባቸው ብዙ ዕድሜና ጤንነት ብለው ሻምፓኝ ተጠጣ ። ሙሴ ባንኩል ጃንሆይን አስፈቅደው ተማሪ ቤቱን ግምጃ ቤቱንና ሱቁን ለማሳየት ጀመሩ ። መጀመሪያ የኢትዮጵያ ሴቶች ልጆች በመኪና መስፋት፥መቍረጥ፥መጥለፍና ብዙ ልዩ ልዩ በመኪና የሚሠራ ሥራ ሁሉ በየመኪናቸው ላይ ቍጭ ብለው ተማሪዎቹ ሲማሩ አይተው በጣም ደስ አላቸው ቀጥለው ብዙ ልዩ ልዩ መኪናዎችና የመኪና መሣሪያዎች ያሉበትን ግምጃ ቤቱን ለማሳየት ጀመሩ።በዚሁም ግምጃ ቤት ብዙ ገንዘብ የሚአጣ መኪናዎችና የመኪና መሣሪያዎች መኖሩን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በመኪና ረገድ የተዘጋጁ መሆናቸውንና የኩባንያውን ባለጠግነት አስረዱ ። ወደ ሱቅ አልፈው ብዙ ልዩ መኪናዎችና የመኪና መሥሪአዎች እሚሸጡበት ገብተው ጫማ፥ድንኳን፥ ቈዳ የጕሬዛና ሌላም የተሰፉ የአውሬ ቈዳ ሁሉ የሚሰፉና የቤተሰብ መኪናዎችና ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነቶች ቁመው ይታዩ ነበር ።

ግርማዊ ን ነ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህንን ሁሉ ካዩ በኋላ ሙሴ ባንኩል በየክፍሉ ስለ አሳዩና ስለአስረዱዋቸው በጣም አመስግነው በ፲፩ ሰዓት ሔዱ ።

ያልታወቀ በደል ።

ማንም ሰው ቢሆን ደጉንም ክፉውንም ስጦታ የሚያገኘው ከባትና ከእናቱ መሆኑ የታወቀ ነውና አንት ቆማጣ አንት ጠይብ አንት ባሻ ተብለው የሚሰደቡት በባትና በእናታቸው በዘራቸው አለባቸው በማለት ነው እንጂ ግድ ራሳቸው እጅ እግራቸው ተቆምጦ ወይም ጠይብ ሆነው ብረት ቢሠሩ ብር ቢያነጥሩ ነውር ሁኖ አይደለም፤ ወይም ባሮች ሁነው ሲሸጡ ሲለወጡ ታይተው አይደለም።ነገር ግን ወደ አያት ወደ ቅድም አያታቸው እየተመለሱ ዘር እየቈጠሩ ሲያሰድቧቸው ይኖሩ ነበር። ይሁን እንጂ በወሬም መሆኑ ቀርቶ እራሳቸውም ሁነው ቢገኙ መነቀብ የተገባ አልነበረም።ቆማጣም ቢሆን ከእግዚአብሔር የተፈረደበት በሽታ ነውና ሊታዘንለት እንጂ ሊሰደብበት አይገባም ጠይብም ቢሆን በትምህርት ጎክሞ ያገኘው እውቀት ነው እንጂ እንደ ርስትና እንደ ከብት ከአያት ከቅድም አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በውርስ ወይም በተፈጥሮ የሚገኝ ዕውቀት አይደለም። አሁን ከባት ከእናት መልክና ደም ግባት በተፈጥሮ ይገኝ እንደሆነ ነው እንጂ ሙያ በትውልድ ሊወረስና ሊገኝ አይቻልም። በተፈጥሮም ዕውቀትን የሚሰጥ ዘር ቢኖር ተፈልጎ የሚጋቡትና የሚዋለዱት በሆነ ነበረ እንጂ ባላሰደበም ነበር። ነገር ግን በትምህርት እንጂ በተፈጥሮ ዕውቀቱ እንዳይሰጥ ይታወቅ ዘንድ ብዙዎች የብረት ሠሪዎች፤ የብር አንጣሪዎች ልጆች ያባቶቻቸውን ሥራ ባለመማራቸው ምክንያት እንኳንስ ብረት ሊሠሩ ብር ሊያነጥሩ ማጭድ እንኳ ሊዘረዝሩ አይችሉም። ዳግም ሌሎች ሰዎች ለብረት ሠሪዎች ለብር አንጣሪዎችአገልጋይዎች የሆኑ ሥራውን ከመመልከታቸው የተነሣ ብዙ ዓይነት ሥራ ይሠራሉ ። ስለ ጠይብነት ስድብነት ብዙም አያደክመኝም ስድብነቱ ቀርቶ ወደጥንቱ ስሙ ጠቢብ ወደ መባሉ ሊመለስ ቀርቧል። ባሻ ስለመባል። ነገሩ አጭር ነው ። ጥንቱንም ባርያ ማለት ፈንጋይ አታላይ ከሀገራቸው ፈንግለው አታለው ያወጧቸው ወይም በሀገራቸው የጦር አደጋ ወድቆባቸው ከሀገራቸው የወጡ ናቸው እንጂ ከአዳምና ከሔዋን የተለዩ ትውልድ አይደሉም።ዳግም አንዳንዶች ሰዎች ከባሮችም በተለየ የባርነት ዘር ያላቸው አሉ ይላሉ። ይኸነኑ ቢመረምሩት መሠረቱ ከዚሁ አሁን ከልነው አይወጣምና ባርያ ብሎ መሳደብ የተገባ አይደለም። ይኸውም ቢሆን ጥንት በነበረው ዳኝነት እየተሰደቡ ቢከሱም ዘራችሁን ቈጥሮ ይርታችሁ ይባሉ ነበር ዛሬ ግን መልካም ሕግ ቆሞ መሳደብ ከልክል ሁኖአል ስለ ስድብነቱ አያሳስበኝም ነገር ግን አሁን ለጊዜው ያሳሰበኝ ቆማጣም ጠይብም ባርያም እርስበራሳቸው እየተጋቡ ይዋለዳሉ። ቆማጣም ከጥንት ከአያት ከቅድም አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ርስትና ከብት አለው ራሱም እየሰራም እየለመነም የጨመረበት አያጣም ጠይብም እንደዚሁ ሁሉ አለው። ባርያም ጉልማ እያረሰ ዶሮ እያረባ ያጠራቀመው ገንዘብ ጌታውም ሲሞት በኑዛዜ የተከፈለው ርስት አያጣም። እነዚህ አሁን የቈጠርናቸው ቆማጣና ጠይብ ባርያ በዕድል በተገኘው ልጆቻቸውን ሲያሰድቡ ይኖሩና ሲሞቱ ከልጆቻቸው አንዱን ሁለቱን ረግመው ግማሾቹን መርቀው ወይም በጭራሽ ልጆቻቸውን ረግመው ለባዕድ ከብቶቻቸውን ሰጥተው የሚሞቱ አሉ። ይህ እንደምን ይሆናል ጠይብና ባርያስ ቢሳደቡም ቢረገሙም ሙሉ አካላታቸውን ይዘው ነውና ግድየለም። የቆማጣ ልጁ ግን እሱ ራሱ ልጁ የልጅ ልጁ እጅ እግራቸውን የሚገብሩበትን ርስትና ከብታቸውን እንደዚሁ እንደቆምጥናው ከአያት ከቅድማያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣላቸውን ርስትና ከብታቸውን እንደምን ሊነቀሉና ሊከለከሉ ይቻላል ርስቱና ከብቱ ከያት ከቅድምአያት ያልመጣ ነውና በራሱ ድካም ያገኘውን ለወደደው ቢሰጥ የወለደውን ቢከለክል ምንአለበት ለማለትስ ከአያት ከቅድምአያት ያልመጣ ከባትና ከእናት የሚገኝ ቁምጥና አለ አይደለምን? ይልቁንስ ቂጥኝና ጨብጥ ከባት ከእናት አይደለምን? እንደዚህ ልጆች በተፈጥሮ ከባት ከናታቸው በሽታን ከወረሱ በተፈጥሮ የሚያገኟቸውንም ደዌና ነውር አባት እናታቸው በእርግማን ሊያቀሉላቸው አይችሉምና ያባት የናቱን ደዌና ነውር በተፈጥሮ እንደሚወርስ ሁሉ ርስትና ከብቱንም በዓይ በተፈጥሮ ሊወርስ ይገባዋል ይላል ሕሊናዬ።

ተገኝ የተሻ ወርቅ

የትምህርት ቤቶችን ማበርታት ።

የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር መልአከ ሕይወት ወልደ ሐና የትምህርት ቤቶችን ለማበርታት በመጋቢት ፲፫ ቀን መጀመሪያ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪቤት ሔደው የትምርት ቤቱን ክፍል ዞረው ካዩ በኋላ የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ።

በንግድና በመንግሥት ሥራ በዓለም የሠለጠኑትን ቋንቋዎች ተምረው ከፍ ላለ እውቀት እንዲደርሱ ይልቁንም ጥበብ አግኝተው ለአገር አገልግሎትና ረዳትነት እንዲበቁ ብሎ መንግሥት ባያለበት ብዙ ትምህርት ቤቶች ቢያቆም ልዩ ልዩ መምህራንንም ቢያስመጣ፡

መጀመሪያ የሚኰሩበትን ያገራቸውን ቋንቋና ትምህርት እንዲማሩ የሚያስፈልግ ስለሆነ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ተመርጠው የሚአስተምሩበት ይህን ተማሬ ቤት መንግሥት ማቆሙ ለጥቅማችሁ ነው ።

ከዚህ ትምህርት ቤት ያላችሁ ተማሪዎች የገር ፍቅር የሚአድርባችሁ አስቀድማችሁ ያገራችሁን ቋንቋና ትምህርት አጥርታችሁ ስታውቁ ነውና ለመማር እንድትተጉ አጠንክረን እናሳስባችኋለን ።

መምህራንም የኢትዮጵያን ልጆች በተወለዱበት ቋንቋና ትምህርት ቢጉለምሱ ምንም ጥቅሙ ለኢትዮጵያ ቢሆን ክብሩ የናንተ ነውና ለማስተማር ሙሉ ፈቃድና ትጋት እንዲኖራችሁ እንለምናችኋለን ።

ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት።ዕድሜ ለግርማዊት እቴጌ መነንና ለመንግሥታችን ቤተ ዘመድ ሁሉ ይስጥልን

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ብለው ሲጨርሱ ዳር እስከ ዳር ተጨበጨበ።

ቀጥለውም ግርማዊት እቴጌ መነን ወደ አሠሩት ወደ ሴቶች ልጆች ትምህርት ቤት ሔደው ነበረ።ዲስኩሩም ቀጥሎ የሚመጣው ነው ።

የአቴጌ መነን ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሆይ ።

እስከ አሁን ድረስ በኢትዮጵያ የተመሠረቱ ተማሪ ቤቶች ለወንዶች እንጂ ለሴቶች ትምህርት ቤት አልነበረም ። ነገር ግን ወንዱ በትምህርት ሠልጥኖ ሴቲቱ ሳትማር ብትቀር የኑሮአቸው ጥቅም ጉዶሎ መሆኑን ገናናይቱ እቴጌ መነን ስለተረዱትና የጃንሆይንም አብነት ተከታይ ለመሆን የግርማዊትነታቸው ፈቃድ ስለሆነ በተለየ ገንዘባቸው ሕንፃው የሚያስደንቅ ተማሪ ቤት ለኢትዮጵያ ቆነጃጅቶች ስለ አሠሩላችሁ በትምህርትም ሥልጣኔ እንድትበቁ ስለ አሰቡላችሁ መላዋ ኢትዮጵያ ታመሰግናቸዋለች ።

እንደዚሁም የወንድና የሴት አኗኗር እንደ ሰንሰለት የተያያዘ ስለ ሆነና የእግዚአብሔርም ቃል ስለ አለበት ጋብቻ እንዲጸና ትዳር እንዲቀና ሲሉ የጐደለውን ነገር በማስተካከላቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አሳቢ መሆናቸውን ደግ አድራጎታቸው ይመሰክራል። ለግርማዊት እቴጌና ለወገኖቻቸው ሁሉ የሚያኰራ ውለታቸው ለመታሰቢያ ይሆናል። ግርማዊት እቴጌ መነን የብርሃን መሪ ሁነው፥ በቀደሙበት መንገድ የኢትዮጵያም ወይዛዝር ተከታዮች እንዲሆንዋቸው ባለተስፋይቱ ተማሪ ቤት ታሳስባቸዋለች። መምህራኑም ተግታችሁ እንድታስተምሩ ተማሪዎችም ነቅታችሁ እንድትማሩ አደራ እንለምናችኋለን ።

ዕድሜ ለጃንሆይ፡ዕድሜ ለእቴጌና ለቤተ ዘመድ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

(ምሳሌ)ማመልከቻ ለክቡር አቶ ዳኛነት ።

በዚህ በርስዎ ግዛት ውስጥ ፩በድኅነት የሚኖር ባላጋራ የበዛበት ሰው ነበር ለሱውም አንዲት ልጁ ገረድ ከእግር ጥፍሯ እስከ ራስ ጠጒሯ ድረስ ቀራት የማትባል የተዋበች ቆንጆ ግብረ መልካም ልጅ ነበረችው። ነገር ግን ምንም የደሀ ልጅ ብትሆን ከቍንጅናዋ የተነሣ በንጉሡም በመኰንኑም በሀብታሙም ዘንድ የተመረጠች ሆና ሁሉም ለጋብቻ ይፈልጓት ጀመር። መጀመሪያም ንጉሡ ያማላጅነት ደብዳቤ ወደአባቷ ላከ ቃሉም ይህ ነው ወራሽ ቈራሽ ይሆነኛል ያልሁት ፩የጐበዝ ልጅ ነበረኝ እሱውም ለመንግሥት ስለ ደረሰ ዘሩዋንና ሁኗዋን ጠይቄ ለጋብቻ የምትሆን ፈልጌ አገባዋለሁ ስል መቼም የዛሬ ዘመን ልጅ እንዳሻው በራሱ ፈቃድ ስለሆነ ግድ ያንተን ልጅ ካላገባሁ ሙቼ እገኛለሁ ብሎ አስቸገረኛልና ልጅህን ለልጄ ስጥ ብሎ ላከበት። ፪ተኛም አንዱ መኰንን የላከው ደብዳቤ ይህ ነው የኔ ማዕድ ተዘርግቶ የሚበላው ጠፍቶ አንተ ብቻ በችግር እየተጉላላህና ባላጋራም እያጠቃህ በመኖርህ በጣም አዝናለሁ። አሁንም ለእኔ የምትሆን በጣም ደም ግባቷ ያማረ ቆንጆ ልጅ አቤትህ አይቻለሁና ጋብቻውን ፈቅደህልኝ ድግሱን ደግሼ ሥጋውንና ጠጁን አዘጋጅቼ መጥቼ እንድወስዳት ፈቃድህ ይሁን አንተንም ከባላጋራህ እጅ አወጣሀለሁ ሹመትም አገዝ ም እሰጥሀለሁ ብሎ ላከበት። ፫ተኛም አንዱ ሀብታም የላከው ደብዳቤ ይህ ነው በየጊዜው እህል ባስወቃሁ ቍጥር ለማንም ድሀ ምርቱን እያፈሰሁ ስሰጠው አንተ ብቻ እስከ ግርዱም ሳታገኝ መቅረትህ ይጸጸተኛል አሁንም ድሀን ያረባሁትን የቀንድ ከብትና በግና ፍየል ወራሽ ያደረግሁት ልጅ ነበረ ። መዳኛው ጊዜ ስለደረሰ እንደኔ ከለው ሀብታም አጋብዋለሁ ስል እሱ ያንተን ልጅ ወይ ሊሞት ነውና እንድትሰጥልኝ ይሁን ብሎ ላከበት ያም ድሀ የሶስቱንም ወረቀት ተቀብሎ አይቶ የኔን ልጅ ለማጋባት የፈለገ ሰው ቢኖር ያ፲ ዓመት መንገድ ሒዶ ፲ዓመት ተምሮ በጥበብ የበለጠ ሰው ይውሰዳት እንጂ ምንም ድሀ ብሆን የሰው ገንዘብና ጌትነት አይቼ አልሰጥም አለ እነዚያም ልጆች ይህን ቃል ሰምተው እንዳታመልጣቸው ፫ቱም ተነሥተው ያ፲ዓመት መንገድ ሒደው ፲ዓመት እንደተማሩ ከ፫ቱ አንደኛው ተማሪ ጋራና ተራራ ጨለማና ደመና ሳይከለክለው ዓለሙ ሁሉ እንደመስተዋት ባ፩ ጊዜ የሚታይ እውቀት ተገለጸለት ፪ተኛውም ተማሪ ሰው ከሞተ በኋላ ፫ሰዓት ሳይሞላው ከሞት የሚያስነሣ እውቀት ተገለጸለት ፫ተኛውም ተማሪ ያ፲ሩን ዓመት መንገድ ባ፩ደቂቃ አገሩ የሚያደርስ እውቀት ተገለጸለት በዚህ መካከል ጥቂት ቈይተን እንቀጽላለን ሲሉ ከዕለታት ፩ቀን ዓለሙ ሁሉ የሚታየው ተማሪ ወደሀገሩ ቢመለከት ያቺ አጩዋቸው ልጅ በድንገት ሙታ እየተላቀሱ ወደመቃብር ይዘዋት ሲሔዱ አይቶ ለሁለቱ ጓደኞቹ ነገራቸው ፫ቱም ከተላቀሱ በኋላ ዓለሙ ሁሉ የሚታየው ተማሪ እንዲህ አድርገን የደከምንበት ልጅ ልትመልጠን ነው ምን ይሻላል ቢል ከሞት የሚያስነሣው ተማሪ ፫ሰዓት ሳይሞላት የሚያደርሰኝ ቢገኝ እኔ አስነሣት ነበር አለ። ፫ተኛውም ያ፲ሩን ዓመት መንገድ ባ፩ደቂቃ አገራቸው የሚያደርሰው ተማሪ ተሆነማ እኔ አልወስዳችሁምን ብሎ ሁለቱንም ተሸክሞ ባ፩ደቂቃ እመቃብርዋ ላይ አደረሳቸው። ያም ከሞት የሚያስነሣው ተማሪ መድኃኒቱን በቀመሳት ጊዜ ቶሎ ብላ ተነሥታ እንደቀድሞዋ በቍንጅናዋ ተቀመጠች ከዚህ በኋላ መሞቷን አይቶ የተናገረው የመጀመሪያው ተማሪ እኔ በትክሱ መሞቷን አይቼ ባልናገር አትድንም ነበርና እኔ አገባለሁ አለ። ፪ተኛውም ከሞት ያስነሣት ተማሪ እኔ ከሞት ባላስነሣት አትገኝም ነበርና እኔ አገባለሁ አለ። ፫ተኛውም ያ፲ሩን ዓመት መንገድ ባ፩ደቂቃ ያደረሳቸው ተማሪ አንተም መሞቷን አይተህ ብትናገር አንተም ከሞት ብታስነሣት እኔ በጊዜው ባላደርሳችሁ እዚያው ሁናችሁ ስታለቅሱ ቀንዋ ተላልፎ እንደሞተች ትቀር ነበርና እኔ አገባለሁ አለ የልጂቱም አባት ለገሌ ሰጥቻለሁ እንዳይል የ፫ቱም እውቀት ትክክል ስለሆነ ወደሽማግሌ ሒዱና ሽማግሌ አይቶ ለሰጠው ይስጥ ብሎ ሰደዳቸው ሽማግሌዎቹም መሞቷን አይቶ የተናገረው ይውሰድ እንዳይሉ ከሞት ያስነሣት ሊቀርበት ሆነ ከሞት ያስነሣት ይውሰድ እንዳይሉ ያ፲ሩን ዓመት መንገድ ባ፩ደቂቃ ያደረሰው ሊቀርበት ሆነ ነገሩን አውጥተው አውርደው የነዚህ የ፫ቱም ልጆች እውቀታቸው ትክክል ነው ለ፩ኛውም ብንሰጠው የሁለቱን እውቀት ማቅለላችን ነው አንተ በዳኝነትህ አይላቸው እንጂ ለግልግል አይቻልም ብለው ወደኔ ሰደዷቸው እኔም ሥራዬ ጽሕፈት ስለሆነ የተነጋገሩትን ሰምቼ አጽፋለሁ እንጂ ለማነጋገር ሥልጣን አልተሰጠኝም ብዬ ወደርስዎ ሰድጃቼዋለሁና ዛሬውኑ ጨርሰውላቸው ለተበየነላት ሰው ግልባጩን እንዲሰጡት ይሁን ነገር ግን እነዚህ ልጆች ከ፫ቱ ሁለቱ ቢበየንባቸው እጠቅላላው ዳኛ ላይሳይደርሱ አይተውምና ምናልባት ብይኑ የተገለበጠብዎ እንደሆነ ኀፍረት እንዳይሆንብዎ ተመልክተው እንዲፈርዱ አመለክትዎታለሁ። ትስብእተ ወልድ አግዴ።

እስታራቂ ።

አቶ ለገሰ ቸሩ የተፈጥሮ ዕውቀት ታላቅ የትምህርት ዕውቀት ታናሽ ብለው ለጻፉት ከኢትዮጵያ ወጣቶች አንዱ አቶ አበበ ገብሬ አቶ ለገሰ ቸሩ የጻፉት ስሕተት አለበት ብለው የጻፉትን ቃል ስላየሁ ጠበቆቻቸው በሌሉበት የተፈጥሮ ዕውቀትን ከንድ ፊት የትምህርት ዕውቀትን ከንድ ፊት አድርጌ ቀጥሎ እንደተጻፈው መረመርሁ ።

መጀመሯ የተፈጥሮ ዕውቀት እንዲህ ሲል ተናገረ የትምህርት ዕውቀት የተገኘው ከኔ ነው፤ ነገር ከሥሩ ውኃ ከጥሩ እንዲሉ ከአዳም ጋራ የተፈጠርሁ እኔ ነበርሁ ያን ጊዜ ምን ዓይነት የተማሪ ቤት ኑሮአል ? አስረጅ አብርሃም በየትኛው ተማሪ ቤት ገብቶ ተማረና ተመራምሮ ፈጣሪውን አወቀ ይላሉ?ዮሐንስበከርሥ(ማኅፀን)ለጌታ ሰግዷልበከርሥ(ማኅፀን) ምን ዓይነት ተማሪ ቤት ነበር? የሰውን ልብ እያንቃቃሁ በፍልስፍና የተገኘውን ትምህርት ያመጣሁ እኔ አይደለሁምን ? ይህ የትምህርት ዕውቀት በየሀገሩ ሁሉ ገብቶ የሠለጠነና የተስፋፋ ስለሆነ ጊዜው ከተመቸኝ ብሎ በኔ እንደተገኘ ሳይታሰበው ቀርቶ ከኔ ልተካከል ሲል የተፈጥሮ ዕውቀት ይበልጣል ብለው መጻፍዎ እንደነቢያት ትንቢት የመናገር ዓይነት ነው ብለው አቶ አበበ ገብሬን ጠበቃ አድርገው አቤቱታቸውን ለብርሃንና ሰላም ዳኝነት አመልክተዋል ።

ዛሬ በመጽሐፍ ተጽፎ ከምናነበው በተቀር ነቢያት በትንቢት እንደተናገሩ የወደፊቱን የሚያናግር ምን ዓይነት የትምህርት ዕውቀት ነበረ? ወይስ ዛሬ የቆመበት የተማሪ ቤቱ ስፍራ ከወዴት ነው ይላሉ?።

በሀገራችን ያሉ ለቍስል ለሥራይ የሚሆኑ ቅጠላ ቅጠሎች የሚቈርጡና የሚቀምሙ ከነሱ በፊት ያውቁ ከነበሩ ሰዎች ካልተማሩ በገዛ ራሳቸው ለማወቅ አይችሉም ያሉት እነዚያ የቀድሞዎቹ ሰዎች ከወዴት አመጡት ይላሉ?

የትምህርት ዕውቀት የተገኘው በተፈጥሮ ዕውቀት መሆኑ ባይታሰባቸው ነው እንጂ የሰው ሕሊና እየመረመረ የተፈጥሮ ዕውቀት ካላስገኘው በተቀር ቀድሞ ለተፈጠሩት ሰዎች ሁሉ የጥበብ ትምህርት ተመሥርቶ እንዳልቈዩቻቸው ማንም አይስተውም ። በተፈጥሮ ዕውቀት የትምህርት ዕውቀትን ያስገኙ ባለፋብሪካዎች እነዚህ ናቸው።ያሬድ ዜማን፣ዳዊትበገናን፣ ሰሎሞንም እንደዚሁ ይህን የመሰሰሉ የጅ ሥራዎች ያስገኙ ባለፋብሪካዎች ብዙ ናቸው ።

የውጭ አገር ቋንቋ የሚያውቁ ሰዎች ሁሉ አገራቸውን እስከሁን አልረዱም ማለት ነውና ይቅርታ መጠየቅ ይገባዎታል ብለው ጽፈዋል። ይህስ ቢሆን ችግሩ ጥንት ነበር እንጂ ዛሬ ግን ዕድሜ ለንጉሣችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የውጭ አገር ፍቅር ወደ ኢትዮጵያ ስለተሳበች ብዙ የውጭ አገር ሰዎች በኢትዮጵያ ላይ ነዋሪ ሁነዋልና ከመለመድ የተነሣ ቋንቋ ለቋንቋ ለመናገር ብዙ የሚያስቸግር ነገር ያለ አይመስለኝም። ይልቅስ ከዚህ የሚበልጡትን ስህገር ጥቅም የሚሆኑትን በጅ ሥራ የሚገኙትን ጥበቦች ቢያደንቁ የተገባቸው ነው ።

በማናቸውም ነገር ታላቅ መባል ይገኛል አሉ ።

የትምህርት ዕውቀት ይህን ተናገረ እኔ የተገኘሁት ምንም ከተፈጥሮ ዕውቀት ቢሆን የሱ ዕድሉ ለያንዳንዱ ሰው ቢሆን እንጂ ለሁሉ አይሆንም የኔ የትምህርት ቤቱ በየሀገሩ ሁሉ የተስፋፋ ስለሆነ የተፈጥሮ ዕውቀት እንዴት ታላቅ ተብሎ ሊደነቅ ይገባዋል ያልኩት ስለዚህ ነው ብለው ነገራቸውን በጭሩ አመለከቱ ።

ከዚህ በኋላ ቀጥሎ እንደተጻፈው እስታርቂያለሁ አቶ የትምህርት ዕውቀት የጠበቃዎ ክርክር መሠረት ሳይገዝ በመሆኑ አዝናለሁ እርስዎስ የተገኙት ከተፈጥሮ ዕውቀት መሆኑን አልሳቱትም ያሬድ የዜማን ፋብሪካ ስላስገኘ ድጓው በምልክት እየተዜመ ይህን የመሰለው ሁሉ ዛሬ ለመምህራን ዋጋ ሲያሰጣቸው የሚኖረው የተፈጥሮ ዕውቀቱ ካልመራው ያሬድ ማኅሌታይ በየትኛው ተማሪ ቤት የተማረው ነው ይላሉ።

ክፉውን ትቶ ወደ ደጉ የሚመራው ደገኛው የተፈጥሮ ዕውቀት ነው የትምህርት ዕውቀትን ሁሉ የሚከተሉ ከሆነማ የትምህርት ዕውቀቱ ብዙ ልዩነት አለው ወንጌልንና ቍራንን ፩ አድርጎ ለመያዝ እንደምን ይቻላል ?

የኢትዮጵያ ልጆች አርበኛ ሁነው ይወለዳሉ፣ጠበቃ ሁነው ይሟገታሉ፣ዳኛው ሁነው ሲፈርዱ ይሞታሉ ተብሎ የተጻፈውን አላነበቡም ኑሮዋልን ?።

ይልቅስ ልጆችዎ ተምረን ቋንቋ አውቀናል እያሉ በተምረናል ብቻ እንዳይቀሩና ጊዜያቸው በከንቱ እንዳያልፍ ሥራ ለመሥራት የማይተጉትን እየመረመሩ ለሥራ እንዲተጉ ቢያደርጓቸው መልካም በሆነ የተፈጥሮ ዕውቀት ታላቅ መሆን አይገባውም ብለው ለጠበቃዎ ያወጡት ዋጋ በከንቱ ነውና በደለኛነዎት ስለዚህ የሽማግሌ ካሣ ይካሡ ብየ አስክሼአለሁ።ወደፊትም በዚህ ነገር ክርክር እንዳያነሡ በሽማግሌ ጨርሰዋል። አሸኔ ወልደ ዮሐንስ።

ስለ አማረውና ስላ ትልቁ የክቡር ፊታውራሪ ብሩ ዓብር ።

መወድስ ።

ፊታውራሪ ብሩ አብርሃም ቅድመ ሆሣዕና ፣ ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ፣ ሕዝበ እንቲአከ ይዘምሩ ።
አዕሩቀ ሥጋ በቀልት በበዓልከ መተሩ ።
ወበፈለገ ወይን አልባሲሆሙ እንዘ የሐፅቡ ነጸሩ በምድሩ። ማር ፲፩ ፯ ፱
ወአእባኒከ ተናገሩ ።
ምስለ እእጋረ ሰብእ ደቂቅ እንዘ በፍኖት የሐውሩ ።
ብሩሂ ፊታውራሪ እምሀበተ ጊዮርጊስ መምሁሩ ።
ግብረ ዘየዐቢ በዓመተ ገብረ ኢታንከሩ ።ዮሐ ፲፬ ፲፪
ሊቃውንቲነ መጽሐፈ እለ ትሬከሩ ።
ዝንቱ ከመ ጽሑፍ፣ እምጣነ ለሊከሙ ተአምሩ ።

አለቃ ዳንኤል ደስታ።

ሲመጣ ይጨንቃል ሲቄይ የቀረ ይመስላል

ክብርት ወይዘሮ ማርታ ያዩ ወልደ ሚካኤል የጅጅጋው ነጋዴ ባለቤት እጅግ የተመሰገኑ ጠባየ መልካም ባላቸውን አክባሪ ቤተሰው አስማምቶ አሳዳሪ የተማሩ ሴት ነበሩ ከቀረውም ሞያቸው ሁሉ የክርስቶስን ሕግ ፈጽመው ከባላቸው ጋራ በሕግ ፀንተው በተክሊል መኖራቸው እጅግ ያስመሰግናቸዋል። ይልቁንም በሕመማቸው ሰዓት እንደበሽተኛ ሳይሆኑ የክርስቶስን ስም እየጠሩ እኔ እንደሐሳቤ እግዚአብሔር የሰጠኝ ቀን ደህቿው ተመስለኝአለች ለኔ አትዘኑ እናንተም ትከተሉኝ አላችሁ እያሉ ልጆቻቸውንና ባለቤታቸውን እያስናኑ ወደ እውነተኛው ቤታ ሔዱ ጥር ፲፯ ቀን ታመው የካቲት ፯ቀን ዐረፉ ጥንቱንም የክርስቶስን ስም ከሕፃንነት ጀምረው ይዘውት ቈይተው ነበርና እንደ ክርስቲያን ሕግ ቄስ አስጠርተው የታዘዘውን ቀንዲል ተቀብለው አሬሳቸውም ካረፉበት ቦታ ከመረር በከሚዮን ጅጅጋ መጥቶ አቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን ፀማሪ ፍታት ተፈትተው ተቀበሩ። ሬሳቸውም እስኪመጣ በከትማ የሚኖረው ሕዝብ ሁሉ ማረፋቸውን ሰምቶ ነበርና ከሹማምንት እስከ ድኃ አልቅሰው ቀበርዋቸው።

መንገሻ ጅጅጋ ከተማ ።

የሚያሳዝን ሞት ።

ፍሬሣ መርጋ የሚባል ወጣት ልጅ ጐሬ በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ተማሪ ቤት የፈረንሣዊ ቋንቋ ይማር ነበረ እሱም በትምህርቱ የበረታ ትጉህና ንቁህ የልጅ አዋቂ ነበር ። መቸም የዚህ ዓለም ኑሮ መጨረሻው እንደማያምር የታወቀ ነው ያጠፋፉም ምክንያት ቀን አተማሪ ቤት ውሎ ማታ ወደ ቤቱ እንደገባ ሆዴን ቆረጠኝ ብሎ ሶስት ቀን ያህል ተኝቶ በአራት ቀኑ ሙቶ ፀገነተ ማርያም ተቀበረ። ምንም ሞት የሰው ነገድ ቢሆን እንደዚህ ያለው ወጣት ልጅ ሲቀነዘፍ በጣም ያሳዝናል ።

ለአባቱና ለዘመዶቹ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያሉ አስተማሪዎቹና በተማሪ ቤት ያሉ ሕፃናቶች ኀዘናቸውን ይገልጻሉ ።

ሥዩም ወልደ ሙስቀል ጐሬ ።

እጅግ የሚያሳዝን ሞት ።

አቶ ኃይሌ እጓለ ጽዮን የሚባል የርሻና የመሥሪያ ሚኒስቴር የፍርድ ጽሕፈት ቤት ክፍል ጸሐፊ የካቲት ፳፯ ቀን በድንገተኛ በሽታ ታሞ መጋቢት ፫ቀን ሙቶ በአዲስ አበባ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ።ሚኒስቴሩም ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አፈወርቅና የሥራ አለቃችም የሆኑ ዋና ዋና ሠራተኞች ሁሉ ተሰብስበው በክብር ተቀበረ ይልቁንም የሥራ ጓደኞቹ ሲያለቅሱ ላያቸው በጣም ያሳዝናል። ዕድሜውም ፴፰ ዓመት ነው

ትኒሽ የልቅሶ እንጉርጉሮ ።

መጋቢት ፫ቀን የሆነው ጉዳቴ ።
ኃይሌ ደከመብኝ አንሰ ጉልበቴ ።
ኃይሌ እንዲበረታ ነበረ ምኞቴ።
አሁን በስንት ቀን አጣሁት ከፊቴ ።
ኃይሌ እጓለ ጽዮን የሥራው ጥበብ ።
ጥለኸው አረፍህ ወደ የፍርዱን መዝገብ ።
ከሰዎች ሊሚገት ተፈጣጥሞ ሳለ ።
እስማኒያው ሳይደርስ አሁን ለምን ቀረ ። ፈለቀ ዳኜ።

ስለ ቀኛዝማች ሺፍኔ ሞት።

ቀኛዝማች ሺፍኔ የልጅ ባንጃው ወንድም የአፈንጉሥ ጥላሁን ልጅ የወይዘሮ ሀብትሽ ይመር በአለቤት እጅግ የሚአምር ደኅና ጉበዝ ጠባየ መልካም ሰው ነበረ ። አማቱ አፈንጉሥ ጥላሁን ከልጆቻቸው አብልጠው ይወዱት ነበር ። በድንገተኛ ሕማም ታሞ በዳግማዊ ምኒልክ ሆፒታል በመጋቢት ፲፩ቀን ሙቶ አፈንጉሥ ጥላሁን በአሠሩት በአቡነ ገብረ ሕይወት ቤተክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበረ።ዕድሜውም ፴፱ ዓመት ነበረ ኀዘንተኞችን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክቶር ጄ ኤ ማርቲኒ በፓሪስ ዩኒቬርሲቲ የተመሰከረላቸው።በዚሁ መታከሚያ ቤት የሴት በሽታ የልጆች በሽታ፤ የዓይን በሽታ፤ የጆሮ በሽታ፤ የጉሮሮ በሽታ ቂጥኝ ይህንን የመሰለውን ሁሉ በደኅና ያክማሉ። ቤታቸውም አራዳ ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ጧት ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ነው ። ፱ተኩል እስከ ፲፩ ሰዓት ያክማሉ ደክቶር ጄ ኤ ማርቲኒ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።
ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።
ዋናውን አ ቤስን ጠይቅ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ጽሮኜ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርደና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኩላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መበለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩባንያ ሲንጀር ከቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በየይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሲንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል እስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ባናው አሰናጂ ባዚል እስላኒዲስ

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውስጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፣ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድ ትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም (ሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ እ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በክቢና በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሸቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፌ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.& E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፲፰፡
8me ANNE. № 18

ሐሙስ መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ ም
JEUDI 7 AVRIL 1952

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታላቅ መታሰብያ።

ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ከሞቱ ፳፪ዓመት ሆነ የሞቱበትም ቀን በመጋቢት ፳፬ቀን ስለሆነ ከሞቱ እስከአሁን መታሰቢያ (ተዝካራቸው) እስከ ዛሬ በሚገኘው ቀን ቀርቶ አያውቅም።ዘንድሮም እንደተለመደው በመጋቢት ፳፬ቀን በአዲስ አበባ አድባራት ያሉ ካህናትና ተከተማ ውጭ ያሉ በየምክንያቱ የመጡ ብዙ ካህናት ተጠርተው በታላቁ አዳራሽ ጃንሆይ ተቀምጠው ታላቅ ግብር ተደረገ።ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እጅግ ደግ ነበሩ ደግነታቸውም እነሆ ዛሬ መሰከረ መከን ሲባሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ መርቆ በሺ፱፻፱ ዓመተምሕረት የሰጣቸው ልጅ የሥጋ ወንድማቸው ግርማዊ ንጉሠነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከልጅ የተሻሉ ስለሆኑላቸው በሕይወታቸውም በመንግሥት ሥራቸው ሁሉ ዋና ኀላፊ ሁነው ስለ አስመሰገኑዋቸው ታላቅ ዕድለኛ መሆናቸው በዚህ ይታወቃል ። በዘመናቸው የተሠሩ ብዙ መታሰቢያዎች አሉ ከነዚህም ታላላቆች ሁለት ናቸው መጀመሯ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ለጳጳስነት መመረጣቸው።፪ኛ ዓለምን ያስቸገረ የሌባ ሻይ መቅረት እነዚህ ሁለቱ ታላላቆች መታሰቢያዎች በዘመናቸው መደረጋቸው ከላይ እንደተጻፈው ደግ ልጅ በማግኘታቸው እነርሱም ከልጃቸው ፈቃድ በአለመውጣታቸው ስለሆነ መታሰቢያቸው ለዘለዓለም ይኖራልና መከን መባል አይገባቸውም።ልጅ መፈለጉ መታሰቢያው እንዳይጠፋ ነው ቢሆን ደግ ልጅ ማግኘት ለደግ ሰው ታላቅ ዕድል ነው ባይሆንም ደግና ሥራ ሠርቶ የሞተ ሰው ሥራው እንደ ልጁ መታሰቢያው ነውና በመልካም ሲጠሩ መኖሩ መልካም ዕድል ነው ስለዚህም መከን አይበልም። መከን መባል የሚገባውስ ሰው ክፉ ልጅ ወልዶ ወይም ክፉ ሥራ ሠርቶ የሞተ ሰው ነው ።

ይደልዎ ዓስቦ ለዘይትቀነይ።

ለሠራተኛና ለሎሌ ለንብረቱ የሚበቃ ያህል አስበ ቀለብና ደሞዝ መስጠት ይገባል ያለዚያ በብዙ ገንዘብ ላይ ሹሞ ቀለቡን አሳንሶ እሱን ታማኝ ሰራተኛ ሁን ማለት የሌብነት መክፈቻ ሰጥቶ ሒድ ስረቅ እንደ ማለት ያለ ነው።ይኸንኑ የሚያስረዳ ምሳሌ ጥንት ፩ድ ንጉሥ ነበር እሱም ልጁን ተማሪ ቤት እንዲማርልኝ ብሎ ወደ ምዕራብ አገር ሰደደው ያም የምዕራብ አገር መምህር እጅግ የተማረ መምህር ስለሆነ ከሩቅ አገር ድረስ ሁሉ እየመጣ እሱ ዘንድ የማይማር ሰው የለም።ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ሲሆን ያመምህር የዕለት ራት እንኳ ጠግቦ አያድርም ነበር የበቃ ልብስም ለብሶ አያውቅም ነበር ይላሉ ከማጣቱም ብዛት የተነሣ ዘወትር ከሚስቱ ጋራ እንደተጣሉና እንደተፋቱ ዘወትርም እንደታረቁ እንዲሁ በጭቅጭቅ በንዝንዝ ይኖራሉ የሚያስተምርላቸውም ሰዎች የጠም ቆሎ የዓመት ባል ዶሮ ብቻ ይሰጡታል እንጂ ሌላ የሚጠቅም ቀለብ አይሰጡትም ነበርና ስለዚህ በብዙ ችግር ላይ ይኖራል።ከዕለታት አንድ ቀን ከሩቅ አገር አንድ የባሯ ነጋዴ መጥቶ ያመምህር መቶ ያህል ተማሪ ግራና ቀኝ ጉባኤ አድርጎ ሲያስተምር አገኘው፡ነጋዴው በትሕትና ቃል ቁሞ መምህር ሆይ ሰላም ለርስዎ ይሁን እንዴት ዋሉ ሲል ሰላምታ አቀረበ ። መምህሩም እግዚአብሔር ይመስገን ከየት መጥተሃል አለው ነጋዴውም ከሩቅ አገር የመጣሁ የባሯ ነጋዴ ነኝ ግን ዕውርና እንግዳ አንድ ነውና ባሯ የሚሸጥበትን ቦታ የሚጠቁመኝ ሰው አጥቼ እንዲያው እንከራተታለሁ አሁንም የተማረ ሰው ቅን ነውና እባክዎ የሚሸጥበትን ቦታ ያሳዩኝ አለው ከላይ እንደጻፍኩት ሰው ሁሉ በሥራው ላይ ከተቸገረ መስረቁ አይቀርምና መምህሩም ከተማሪዎቹ አንዱን ሰርቆ ለመሸጥ አሰበና በምን ያህል ብር ትገዛለህ አለው ነጋዴውም አንስተኛ ባሯ እንደሆን በሥር ብር፥ ደኅና ባሯ እንደሆነ በ፳ ብርም ቢሆን እገዛለሁ አለ መምህሩም ከነዚህ ከመቶ ልጆች መርጠህ ግዛ አለውና ቢመርጥ የንጉሡን ልጅ በቁመትም በደም ግባትም መርጦ በ፳ ብር ገዝቶ ይዞ ሲሔድ በ፲፬ቀን እልጁ አባት ከንጉሡ አገር ደረሰና ከ፩ድ መንደር አሳድሩኝ አለ ጊዜው መሽቶ ነበርና እደር አሉት በኋላ መብራት ተበራና ቢያዩ የንጉሡ ልጅ ነው ባለቤቱም እረ ይኸን ልጅ ከየት አመጣኸው ብሎ ቢጠይቀው የገዛሁት ባሯ ነው አለ ዝም ብሎ አድሮ ሲነጋ ያባለቤት የንጉሥ ልጅ መሆኑን ያውቃልና እጁን አንጠልጥሎ ከንጉሥ ዘንድ አደረሰው። ንጉሡም ልጁን ባየ ጊዜ ደነገጠና ልጄ ምን አመጣህ አለው ልጁም አስተማሪዬ ለዚህ ሰው ሸጠኝ ነው አለው ነጋዴው

ቢጠየቅ አዎን ገዝቼው ነው አለ፡ ከዚህ በኋላ ንጉሡ ነጋዴውንና ልጁን በጓዳ ውስጥ ቈለፈና እዚያ መምህር ዘንድ ፫ ፈረሰኞች ናፍቆኛልና ልጄን በቶሎ ላክልኝ ሲል ላከበት መምህሩም ወደሩቅ አገር ልኬዋለሁ አሁን የለም ሲል መልሶ ላከ ንጉሡም ፪ኛ ከለበት አገር አስመጥተህ ላክልኝ ሲል ላከበት ። መምህሩም ላመጣው ብሔድ ሙቶ አገኘሁት ሲል መልሶ ላከ።

፫ኛ ንጉሡ ቢሞትም ሬሳውን ላክልኝ ሲል ላከበት መምህሩም ቀበርኩት ሲል መልሶ ላከ ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ እኔ ሳላየውና እኔ ሳልሰማው ማን ቀበር አለህ ብሎ እጁን አሲዞ አስመጣውና ቢጠይቀው እንደ ቀድሞ ሙቶ ቀበርኩት አለ ንጉሡም እንደ ቀበርከው ምስክር አለህ ወይ ቢለው ከዚያ ከላኩበት አገር ሒጄ ሳመጣው ከመንገድ እዳር ቢሞት ብቻዬን ነውና የቀበርኩት ምስክር የለኝም አዬ ይሙቱ አለ ንጉሡም ትምላለህ ወይ ቢሉት አዎን እሰምሬ እምላለሁ አለ። ከዚህ በኋላ ከቤተ ክርስቲያን ወስዶ ያንን መምህር ድርገት ሲወርድ በሥጋው በደሙ አስማለው ንጉሡም ይኸ ሐሰተኛ መምህር በሐሰት ምሏልና እሳት ከሰማይ ወርዶ አሁኑን ያቃጥለዋል ብሎ ሲመለከት ፈጣሪ እንደ ፍጡር አይቸኩልምና ቢዘገይበት ንጉሡ ስለ ልጁ መሸጥ እጅግ ተናዶአልና ቸኩሎ እንደ ተናደደ እቤቱ ሒዶ ልጁንና ነጋዴውን ከጓዳ ውስጥ አውጥቶ የማለውንም መምህር ፪ኛ አስጠርቶ ሙቶ የቀበርከው ልጅ ይኸ አይደለም ወይ የሸጥከለትስ ነጋዴ ይኸ አይደለም ወይ ብል እውነቱን አውጣ ቢለው አዎን ሸጬዋለሁ አለ።ከዚህ በኋላ አንተን በቶሎ ያልገደለ አምላክ ምን አምላክ ይባላል ይልቅስ ያንን የወደድከውን ብር ጠጣው ብሎ አስፈልቶ ቢየጠጣው ልቡን ሰንጥቆ ገደለው ንጉሡም በቶሎ ስለሞተለት ደስ አላውና አምላክስ ማለት ብር ነው ብሎ አምላኩን ክዶ የብር ጣዖት ሠርቶ ያመልክ ጀመረ ከዚህ በኋላ አብያተ ክርስቲያናት ይትዐፀዋ አብያተ ጣዖታት ይትረኃዋ ብሎ አዋጅ ነግሮ አብያተ ክርስቲያናትን አፈረሰ ምዕመናንም አሳደደ ክህናቱንና ሊቀውንቱንም ሁሉ በሰይፍ ጨረሰ ይባላል ። ማጣት እንዲህ ሰው ያሸጣል ።

ስለዚህ አሁንም ወደፊት ለሠራተኛ ሎሌ ፲ብር ፲፭ ብር ፳ ብር ። ለትዳሩ የማይበቃ ቀለብ ሰጥቶ በ፱፻ ሺ ብር በሚሊዮን ብር ላይ ኀላፊ አድርጎ እሱን መሾም የሚያበራየውን በሬ አፉን እንደ ማሠር ያለ ነው ። ወይም ከሽምብራ እሸት ውስጥ ሁነህ ወፍ ጠብቅ አንተ አትብላ ማለት ነው ። ፲፭ብር ፳ብር ቀለብ ለ፩፩ ሰው ትዳር ጮቹ ያንሳል ትሉኝ እንደ ሆነ እውነት ነው በዱሮው ዘመን ብር ስለተወደደ በአዲስ አበባ ከተማ እንኳን በብር የሚገዛው እቃ ሁሉ ርካሽ ነበረ ። በ፩ብር ብዙ ጨው ይመነዘር ነበር በ፩ብር ፩ ዳውላ ጤፍ ይሸመት ነበር ስለዚህ ለ፩ ፩ ሰው ትዳር ይበቃ ነበር አሁን ግን ብር ስለረከሰና በብር የሚገዛው እቃ ሁሉ ስለተወደደ ይኸውም በ፩ ብር ፱ጨው ይመነዘራል በ፩ ብር በበጋ ፱ቁና ጤፍ በክረምት ፩ ቁናጤፍ ይሸመታል በዚህም ላይ የወር ጨው የቤት ኪራይ ለጋዝ ለዕንጨት ለልብስ ወጭ አለበትና ለ፩፩ ሰው ትዳር ይበቃ አይመስለኝም ። የብር መርከስንም የሚያስረዳ አለ ጥንት ብር ስለ ተወደደ የሰው ሁሉ ካሣው ፲፭ ብር ነበር አሁን ግን ብር ስለረከሰ ፴ብር ሁኑአል ሁሉም ሲሻሻል ይህ ብቻ ሳይሻሻል ይኖራል ወደፊት ማሻሻል ይገባዋል።በዘ፻ ወበ፷ ወበዘ፴ እንዲል ከፍ ያለውን መቶ ዝቅ ያለውን ፷ መጨረሻውን ፴ አድርጎ መወሰን ይገባ ይመስላል ። ይህ ካልሆነስ አማትና ምሬት ራትና መብራት ሳይሰማሙ ሠሬት እንዲሉ ። እንደዚሁ ጌታና ሎሌ ሳይስማሙ መኖራቸውን ማንም አይስተውም እኔ ባለማወቅ የጻፍሁላችሁን እናንት ግን የእውቀት መስታዋት ላለው ልቡናችሁ አይታችሁ እንድትፈጽሙት አመለክታለሁ ።

ይህንኑ በግዕዝ የሚያስረዳ

መወድስ ቅኔ

ለቤተ መንግሥት ያዕነዕ ሥርዓተ ርኅራኄ፤እግዚአብሔር
በዕል ትምህርተ ርኅራኄ መሀረ ።
ለገብእተ ሠርክ ደኃርት ምስለ ገብእተ ነግህ ቀቡረ ።
እከኑ በኢተፈልጦ ፡ወሀበሙ ናሁ ሠላሰ ዲናረ ።
ወኅደገ ማዕተበ፤ከመ ንትሉ ንሕነ እንተ ዚአሁ እሠረ።
ዳዊትሂ ንጉሠ ኵሉ አመ ሙስተ ረኃብ ነበረ ።
ሐባውዘ ቍርባን ተሴሰዮ ተመይጠ ወተድኅረ ።
ዕንዐ ረኃበሂ ወጽምእ እንተ ኢየኀብእ ነውረ ።
ለዔሳው አስተርአዮ ፍኖተ አሕዛብ መቃብረ ።
ዘሙግ ወልደ ጻድቅ የመሐመድ ዓሊ ኩባንያ ቤት ጸሐፊ።

ለደባ አድራጊዎች የሚገባ ምስጋና ።

በርስት ነገር ተከስሼ ፫ዓመት ሙሉ ከወለጋ አዲስ አበባ በብዙ ድሞዝ ነገረ ፈጅ እየገዛሁ ሁለት ጊዜ ሰድጄ ስምዋገት ሥር ነገሩ ተበላሽቶብኝ አላልቅልህ ቢለኝ ፫ተኛ እኔ ሥራዬን ሁሉ ትቼ አዲስ አበባ መጣሁ ነገሩ አለጃንሆይ የማይፈጸምልኝ ስለሆነና የጃንሆይን ፍርድ የሚፈልግ ሕዝብ ስለበዛ አላገኛቸው ብዬ በወትን ወይስ በመንፈቅ ይሆን የማገኛቸው እያልሁ ሳዝን ከዕለታት አንድ ቀን በድንገት ወደጉምሩክ ብገባ የነጋዴ ችግር መመርመሪያ የሚሏ ጽሕፈት አነበብሁና ከቢሮው ውስጥ ገብቼ ሠራተኞቹን ተዋወቅኋቸውና ችግሬንና የመጣሁበትን ሁሉ ብነግራቸው በነገሩ አዘኑብትና ከንግድ ሚኒስቴር ዲሬክተር ከክቡር አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ ዘንድ ወስደው አገናኙኝ። እሳቸውም ወዲያው እፊታቸው እንደቆምሁ የተበደልኸውን ነገር ጽፈህ አምጣና ለጃንሆይ አሳይልሃለሁ አሉኝና ሥራዬን እየፈታሁ ፫ዓመት ሙሉ ነገሬ አላልቅ ብሎ እንደደከምሁ ጽፌ ቅዳሜ ቀን ብሰጣቸው ወዲያው ሰኞ ቀን እግዚአብሔር ባርኮ ለኢትዮጵያ ተስፋ የሰጣት ሕዝቦቸውን በመጠበቅ ቀን ዕረፍት ሌት እንቅልፍ ከሌላቸው ንጉሣችን ፊት አቆሙኝ የዚያኑ ዕለት እንደኔው የነጋዴ ችግር መመርመሪያ ጽሕፈት ቤት መቆሙን የሰሙ ነጋዴዎች አኵሎቹ ቱሉ በርጩማ ግቢ የተቀመ እንዱ ከትግሬ አገር የተቀማ ነበሩና ሁላችንም በጃንሆይ ፊት በቆምን ጊዜ ሩብ ሰዓት እንኳ ሳንቆይ የሁላችንም እግዚአብሔርን ደስ እንደሚለው

እድርገው ጨረሱልን ጓቢ ለተቀሙት ያንጊዜውኑ ሽለቃውን ሁለት ዋስ አስጠርተው የተቀሙትን ገንዘብ አሰጧቸው ከትጓሬ አገር የተቀማው ሰው ለቀማኛው መንግሥት ምሕረት አድርጎለታል ስለተባለ ካለበት ስፍራ ይምጣና ይጠየቅ ተባለ ለኔም በልዩ ነገሬ በመጅሊስ እንዲታይ አድርገውልኝ ፭ዓመት ሙሉ የደከምሁበትን ነገር በእኩል ሰዓት ጨርሰውልኝ በደስታ ፀሐይ ንጉሣችንን ኃይለ ሥላሴን ከነዘር ዘሩ ዓለም እስከታልፍ ያንግሥልን በጎ አድራጊና ቅን ፍርድ ፈራጆች ከኢትዮጵያ ለንጓቅ ዓላማ ሥር አንጣ ከኢትዮጵያ ልጆች ከወንድሞቻችንና ከወገኖቻችን እንደ አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ የመንግሥቱን እንበ ጠበቂ በርኅሬኄና በፍጥነት ወገኖቻቸውን የሚረዱ ይስጠን እያልን ልመናችንን ለዘወትር አናቋርጥም። ጃንሆይም ይኸነን የነጋዴ ችግር መመርመሪያ ጽሕፈት ቤት ሲአቆሙ በብዙ ሐሳብና ማስተዋል እንደሆነ ለአንባቢዎች አይሰታችሁም ። ለገላ ሁሉ ሰብሳቢው ራስ እንደሆነ እንዲሁም የአልጋ ደጋፊው የሕዝብን ግፍና ጥቃት መጠበቅ ነው ። ይኸውም በደጉ ንጉሣችን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተደረገልን ለጃንሆይም ዕድሜና ጤና ሰጥቷቸው ይኸነን በጎ ሥራቸውን ተከትለው የሚረዱቸው ጀግኖች ይስጣቸው በማለት ወደ እግዚአብሔር እንለምናለን ።

ኢትዮጵያ አገሬ ሎጋ ቆንጆ ናት፤ ታላቁ ታናሹ አሻግሮ ሲያጪት፤ መልከም መሬጭ አገር መልምሎ ዳሬት፤ ከማህለ ሥላሴ ከምኒልክ ቤት ።

እህመድ አፈንዲ ።

የንቡረ እድ አቀባበል ባዲስዓለም

በ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት የከቲት ፳፯ቀን እሑድ በ፬ሰዓት ወደ ዳግሚት ጽዮን ርእሰ አድባራት ዘደብረ ጽዮን ንቡረ ዕድ ተክለ ሃይማኖት ተብለው ስለ መጡ መጀመሮ በከበረ አቶሞቢል ከገነት አውራጃ ገዢ ከአዛጋር ገብሬና ከክቡራን መኳንንቶቻቸው የክብር ልብስና የራስ ወርቃቸውን አድርገው በክብር ስለመጡ ወታደሩም ተሰልፎ ካህናቱም ልብሰ ተክህኖ እንደለበሱ ከትልቁ ሜዳ ወርደው ንሴብሖ እያሉ ቄይተው ከአቶሞቢሉ ወርደው በተዘጋጀው ጥሩ ባለ መስተዋት ወንበር ላይ ተቀምጠው በግራና በቀኝ መኳንንቱ የተፈቀደላቸው ተቀምጠው ካህናቱም እንደሚከተለው ቃል ወረቡ ሐፁር የዐውዳ ዉጽጌ ረዳ ለደብረ ጽዮን ብእሲ ተወልደ በውስቴታ ሀየ ደብረ ጽዮን ማኅደረ ስሙ ለተክለ ሃይማኖት አልበ ማኅለቅት ለመንግሥቱ፡ መድኃኔ ዓለም እግዚአብሔር ኅደረ ላዕሌሃ ኪያሃ ዘሠያረ ኃይለ ሥላሴ ብለው ከወረቡ በኋላ ፪ተኛ ደብተራ ወልደ ዮሐንስ የሚባል ባለ ቅኔ ከዚህ ቀጥሎ እንደሚከተለው ቃል ተቀኘ ።

ይበዝኅ ከመ ዘግባ ለተክለ ሃይማኖት ክብረ ቤቱ ። ወይፈሪ ክዕበ ከመ ዕፀ ሠናይ ዓርዝ ። አዕዋፈ ዘአስተጋብአ በፍሬ ሐዋዝ ። ወእመ ውስተ ጽዮን ወዕአ መዐርገ ክብሩ ትእዛዝ ። ቤዛ ሰብእ ይኩን ጊዜ ትካዝ ። ወኅዙናነ ጽዮን ቆብአ ከመ ይናዝዝ ። ውሉድ ወሉድ እም አእላፍ ርእሱ ወርቀ ቄፋዝ ብሎ ቅኔውን ከሰጠ በኋላ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ወደ ካህናቱ የመልእክት ወረቀት ከተነበበ በኋላ ጥፍሑ እደዊከሙ እንሥዖው ቃል የተሰበሰበው ሕዝብ በጊዜ ተጨበጨበ ። ዕለቱም ዕለተ እሑድ ስለ ሆነ ከልጅ እስከ ሽማግሌ ከሴቶችም ከሴት ወይዘሮ እስከ መበለት ልክ የሌለው ሰው ተሰብስቦ ነበር። ሴቱም በዕልልታ ዕልል እያለ ተቀበለ።ከዚህ በኋላ ቄሱ አሳርገው በፊት በኋላ በቀኝ በግራ እንደ ንብ አውሬ ወደ ትልቁ ቤተ ክርስቲያን አግብተው ትንሽ ጸሎት አድርሰው ወደ አዳራሹ ወረዱ።ከዳራሹም ውሥጥ የተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ይልቁንም ዕሰፍ ዕሰፍ እየሆነ ሥጋው ቢቀርብ ያመት ድግስ ይመስላል እንጂ የዕለት ድግስ አይመስልም ነበር።የኔም ዝማሬ ደስ ስለ አለኝ ቀጥሎ እንደሚለው ነው፡ ቄሱም ደብተራውም ሕዝቡም ደስ ይበለን ። ስጦታው ካማረ ደጉ ንጉሣችን። እንደ በትረ አሮን ሠርፆ ከሙሐከላችን ። እጅግ ደስ የሚያሰኝ ተክለ ሃይማኖት ካህን አዝመራው አማረ አፈሩ ተክላችን። በኃይለ ሥላሴ ሰፍሬ ደረሰ እግዚአብሔር ይመስገን። ስል በዲስኩር አቀርባለሁ ምረቃዬን።

አንባቢ ሆይ ሥራዬ እርሻ ነው ነገር ግን የኢትዮጵያ ታሪክ ሳይጻፍ የነበሩ ሰዎች ስማቸውና ሞያቸው እንዴት ይታወቅ፥ ኑሮአቸው እንዴት እንደ ነበረ በዘመናቸውስ የሆነው የአየርና የመሬት የሹመትና የሽረት መለዋወጥ በምርምር ተለይቶ ይታወቃል ሲሉ ብርሃንና ሰላም ብለው ፀሐዩ ንጉሣችን በሰየሙልን ትልቅ ምስጋና ይጓባቸው ለቀደመው ምስክር በሀገራችን ከብዙ ሰው አፍ ዕድሜውን ስጠይቀው በእገሌ መንግሥት እገሌ ይኸን አገር ሲገዛ በእገሌ ዘመቻ በከብት እልቂት በክፉ ቀን ተወለድሁ እያለ ሲመልስልኝ ብዙ ጉዳት እየመሰለኝ በዓይኔ ያየሁትን በዘመኔ የሠራሁትን ለማቅረብ እመኛለሁ ። በቀለ ተክለ ሃይማኖት የአዲስ ዓለም ገበር ዘብሔረ ጀር ።

የደስታ ምላሽ ።

ብርሃንና ሰላም ፳፫ኛ ዓመት ቍጥር ፲፫ ገጽ ፴፰ ክቡር አቶ መዓዛ ወልደ ሕይወት የጻፈውን በየሁ ጊዜ ሆድ ቍርጠት በየጊዜው ፀንቶ አሞኝ ነበረና ጥቂት ተከፈለልኝ ስለዚሁ ወደ ሆስፒታል ሳልሔድ በመዳኔ ይህነን ልገልጽላችሁ እሰብሁ። አስቤም አልቀረሁ ይኸው ጀመርሁ ይህች የሕግ ባሏን እነሱ ኰሰሰ፥ አጠረ፥ ቀጠነ፡ ጠቈረ ነጣ ሳትል በወንጌል የተጻፈውን ቃል ተመልክታ ይህነኑ መሠረት አድርጋ ከቀዳማዊ እስከ ቀዳማዊ በሕግዋ ፀንታ በመኖርዋ ጎረቤቶችዋን ሳታስቀና ትቀር አይመስለኝም ። አንዳንዶቹ ለማግባት እንኳ ባይሆን ለጨዋታ ሳያስብዋት አይቀሩም የዚያን ኅፍረት ልጆችዋ በዩ ጊዜ ብርግግ ብርግግ እንዳሉ ናቸው ይህንም ልብ ሳታደርገው ትቀር አይመስለኝም ። እንዳልኸው ሁሉ ሴቶች ጌጽ በሚሆን ማታለያ ነገር ይደለላሉና እንዲያውም በመላ ባሏ ጉማህ ይመስለኛል ስለዚህ ከቀድሞው ሐሳቡ ጥቂት እንዳይቀንስ እንዲበረታ አዕናናው እስዋንም አስጠንቅቃት

ሰው እንደ ቤቱ እንጂ እንደ ጎረቤቱ አያድርም የሚባለውን ከመጽሐፈ ጨዋ የተገኘውን ዘወትር ታስብ ስል ሐሳቤን ከሐሳብህ አስጠጋለሁ ።

ተከታይህ ግብረ ድንግል ድባቤ ።

ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የልዕልት ስኒንን ተማሪ ቤት እንደ ጎበኙ።

በየካቲት ፲፱ቀን የልዕልት ስኒን ተማሪ ቤት አለቃ አቶ መንገሻ ብሩ ተማሪዎቹን አሰልፈው ተማሪ ቤቱንም በሰንደቅ ዓላማ አስጊጠው ሲጠባበቁ እኔም ለድንገት እተማሪ ቤት መጥቼ ነበርና በዚሁ ቀን ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የልዕልት ስኒንንተማሪ ቤት የሚጎበኙበትና የሚያነቃቁበት ቀን መሆኑን ስለተረዳሁ አብሬ እጠባበቅ ጀመር ልክ ፫ሰዓት ሲሆን ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ መጥተው በተሰናዳላቸው ወምበር ተቀመጡ ።

ስለሺ ደምሴ የሚባል ተማሪ በተማሪ ቤቱና በተማሪዎቹ ስም ሁኖ ቀጥሎ ያለውን የሰላምታ ቃል ተናገረ ።

ብፁዕ አባታችን ሆይ ስለ ራሴና ስለ ባልንጀሮቼ በመምህራንም ስም ሆኜ የከበረ ሰላምታ ለብፁዕነትዎ ለማቅረብ ተመርጫለሁና በዛሬው ቀን እመቤታችን ልዕልት ስኒን ያቆሙልንን ተማሪ ቤት በመጎብኘትዎ ተማሪ ቤታችን ትልቅ ክብር ያገኘበት ጊዜ ስለ ሆነ የብፁዕነትዎን ዕድሜ ያርዝምልን በየጊዜውም የተባረከውን መጎብኘትዎን አይንሳን ብሎ ጨረሰ

ከዚያም ቀጥሎ የግዕዝና ያማርኛ ንባብ ፈተና ሆነ ቀጥሎም እየደበተራቸው የጻፉትን አሳዩ ፫ተኛም ቍጥር በየተራ በጥቁር ሳንቃ ላይ ሲደምሩና ሲያካፍሉ ካዩ በኋላ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገሩ በዛሬው ቀን የልዕልት ስኒን ተማሪ ቤት አጀማመሩን በማየታችን ለደስታችን ልክ የለውም፡ከግራኝ ዘመን ጀምሮ ወሎ የእስላም አገር ሁኖ በዓረቦች አስተማሪዎች ሲማር ነበር ከአጤ ዮሐንስ ጊዜ ጀምሮ በኋላም በንጉሥ ሚካኤል ብርታት በአገሩ ክርስትና እገቡበት ልዕልት ስኒንም ከአባታቸው የነበረውን ሐሳብ ለማበርታትና በሕይወታቸው ሳሉም ለአገራቸው ሕዝብ ጥቅም በክርስትና ሃይማኖቱ እንዲጠና ፍላጎታቸው ስለ ነበረ ከዚህ ዓለም ወደ ሰማያዊ አገር በተጠሩበት ጊዜ ከዘመድ ከልጅም የአገርን ፍቅር ስለ መረጡ ልጄ አልጋ ወራሽ ሆይ ያለ ገንዘቤን ሁሉ ቢሆን ከባቴ አገር አለዚያ ለዚህ አገር ተማሪ ቤት ያስፈልገዋል ከምትለው አገር ተማሪ ቤት እንድታቆምልኝ ብለው እኔም እየሰማሁ ተናዘው ነበርና ደግ የሥልጣኔ መሪ የሆኑ ንጉሣችን ኑዛዜ አቸውን ስለ ፈጸሙላቸው ዕድሜአቸውን ያርዝምልን እናንተም በዚህ ልዕልት ስኒን ባቆሙላችሁ ተማሪ ቤት ለመማር ያበቃችሁ ሕፃናቱም አእምሮ ይግለጥላችሁ ተምራችሁም ንጉሣችሁንና አገራችሁን ለማገልገልና ለማክበር ያብቃችሁ አቶ መንገሻ ብሩም በትጋት ለጀመሩት ሥራ ፍጻሜው ብዙ ፍሬ እንዲያፈራ እመኛለሁ። ለወሎ ክርትና ለማስገባት ተጣጥረው ሃይማኖቱን ከበረታቱ ከልጅ ልጅ ተወልደው ከኢትዮጵየ ዙፋን ለተቀመጡ ግርማዊት እቴጌ መነን ረጅም ዕድሜና ጤና ይስጥልን የልዕልት ስኒንን ነፍስም ይማር የኢትዮጵያም ነፃነት ለዘላለም ይሁን ብለው በጨረሱ ጊዜ ከዳር እስከ ዳር ተጨበጨበ ።

ቀጥሎ የተማሪ ቤቱ አለቃ አቶ መንገሻ ብሩ የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ብፁዕ አባታችን ሆይ ዛሬ የልዕልት ስኒንን ትምህርት ቤት በመጎብኘትዎ የደስታውን ልክ ማናቸውም ቢያስበው አይደርስበትም ።የዛሬው ደስታ ለተማሪ ቤታችን መከን የነበረች ሴት የወለደች ጊዜ የደስታዋ ልክ እንደ ሌላው እንዲሁ ደስታው ለተማሪና ለተማሪ ቤታችን ሆነልን።

ደግሞም የበለጠ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እናመሰግናለን ስለ ቅዱሱ ሥራቸውና አሳባቸው ለገዛ አገራቸው ቅን መሪዎች ከገዛ ወንድሞቻቸው ስለ መረጡ ብፁዓን ጳጳሳትን በየገሩ መስደድ ታላቅ ሥራ ነው። በዚሁም በተደረገው ነገር ለኢትዮጵያ ላገራችን የነፃነት መንገድ ስላሳዩን በቡሩኩ ንጉሣችን በኃይለ ሥላሴ ወደ ነፃነት ደረጃ እየተመሩን ነፃነታችንን ለማግኘት ጀምረናል እንዲሁም ወደ ፊት እየታየ ወደ ተሻለው ሥልጣኔ ለመድረስ ብዙ ተስፋ እናደርጋለን ።

ከሁን ቀደም አንድ አቡን ብቻ ስለ ነበረ ከየሀገሩ ለክህነትና ለዲቁና ብዙ ችግር ነበረ ከመንገዱ መራቅ በችግርም ዓሥሩ ባንድ ቢነሡ ከበሽታና ከድካም የተነሣ ወይም በጉርፍ ይሞቱ ነበሩ በኃዘን ወደሀገራቸው የሚመለሱ ሁለት ወይም ሦስት ይሆኑ ነበሩ ።

ዛሬ ግን ይህን ሁሉ ችግር ለማስቀረት ይኸው ብፁዓን አባቶቻችን ለያገሩ የሰጠን እግዚአብሔር ይመስገን ።

ደግሞም እግዚአብሔርን እናመሰግናለን እንዲህ የተባረኩ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ብርሃን ልቡና ላገራቸውና ለሕዝባቸው በታማኝነት የተቀበሉ ደግ አሳቢ ንጉሥ ስለ ሰጠን ለወደ ፊቱም ብዙ ተስፋ አለን ከፍ ካለው ደረጃ ከሚታፈሩቱ መንግሥታት ትክክለኞች ለመሆን እንዲያደርሱን ስለዚህም እንዲህ ለሕዝባቸው ለሚያስቡ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ከነቤተሰዎቻቸው ሺህ ዓመት ያኑርልን በምሉው ረጅምም ዕድሜ ይስጥልን ለብፁዕ አባታችን አቡነ ጴጥሮስ ባራኪያችንና ቀዳሻችንን ያሰንብትልን የደጊቱ እመቤታችን የልዕልትስኒንንም ነፍስ ይማርልን ደጃዝማች እምሩን ገዢችንን በጤና ለብዙ ዘመን ያኑርልን የኢትዮጵያም ባንዴራ ለዘለዓለም ትታይ ። ኢትዮጵያም እንደ ከራች ትኑር ብለው በጨረሱ ጊዜ ዳር እስከ ዳር ተጨበጨበ ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ አባታችን ተነሥተው ተማሪ ቤቱን ዞረው አይተው ወደ ጽሕፈት ቤት ገቡ ተማሪ ቤቱ ገና እንደሚገባ ባለ መሠራቱም ከአቶ መንገሻ ጋራ ከተነጋገሩ በኋላም መቶ ብር ለተማሪ ቤት እርዳታ ሰጡና ለመሰናበት ተነሡ ሲነሡም አንድ ትንሽ ተማሪ ይሙር በላቸው የሚባል ለስንብቻ የሚከተለውን ቃል ተናገረ ።

ብፁዕ አባታችን ሆይ እኛ የልዕልት ስኒን ተማሮች ለትምህርት ብርቱ ፈቃድ ያለን ተማሮች ነን በእግዚአብሔርና በጸሎትዎም ኃይል እውነተኞች ኦርቶዶክሳውያን ሁነን አገራችንና ባንዴራችንን እያከበርን ንጉሣችንንም እየወደድንና እየ-

ታዘዝን ለመኖር ፈቃዳችን ነው ስለዚህ በጸሎተዎ አይርሱን ያባት በረከት ለልጆች ጤናና ሕይወት ይሰጠናል ለዚኸውም ሁሉ እግዚአብሔር ይርዳዎ ዕድሜዎን ያርዝም ጤናም ይስጠዎ ብለን እግዚአብሔርን እንለምናለን ጤና ይስጥልን ብለው ተሰነባበቱ

ይህን መጸፌ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ተማሪ ቤት ስለ ጐበኙ ማድነቄ አይደለም በየጊዜውም ስለ ሚሠሩት ሥራና ትጋት ክረድሙ በጭሩ ከብዙ በጥቂቱ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሳልገልጽላቸው ብቀር ሰውነቴ ይወቅሰኛል ብዬ ነው እንጂ። ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ከአዲስ አበባ እንደ መጡ በየአድባራቱ ልክው የመንፈሳዊ ተማሪ ቤት ቁሞ ሕዝቡ ትምህርት እንዲያገኝ ስላደረጉ በቅርብ ጊዜ የወሎ ሰው ፈጽሞ ክርስትና እንዲነሣ ጥርጣሬ የለውም ከዚህ ቀድሞ በሰንበትና በበዓል ቀን ሲሠራ የነበረውን በኋላቱ እንዲከብር ተደርጓል ሕዝቡም ብጥንቃቄ በዓላቱን ማክበር ጀምሯል።የብርሃንና ሰላም ተላላኪ።

ማስታወቂያ ።

የፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን አድሚኒስትራሲዮን የአድሚኒስትራሲዮኑን መሥሪያ ቤቶች ለሥራ የሚከፈቱበት ሰዓት ስንለውጥ የፈተኛውን መሠረት አድርገን ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው እናስታውቃለን።

፩ኛ፥ ፖስታ ቤት ።

የፖስታ ቤት ክፍል ሠራተኞች ከጧቱ በ፪ሰዓት ገብተው እስከ ፯ሰዓት ይሠራሉ ከእኩለ ቀን በኋላ በ፱ሰዓት ገብተው እስከ ፲፩ ሰዓት ይገኛሉ ግን ፖስታው በጧት በሚደርስበት ቀን ፖስታውን ለማደል ጊሼዎቹ እስከ ፯ሰዓት ድረስ ተከፍተው ይቈያሉ ማታ ከ፲፩ሰዓት በኋላ ፖስታ በሚገባበት ቀን ሁሉ ቧት ላላቸው ሰዎችና ፖስታውን ለማደል ከምሽቱ እስከ ፩ሰዓት ተኩል ድረስ ይታደላል በማንኛውም ምክንያት ቢሆን ፖስታውን አድለው ሳይጨርሱ አይሔዱም።

፪ኛ ቴሌግራም ቤት ።

የቴሌግራም ቤት ያለ ማቋረጥ ዘወትር ከጧቱ ከ፪ሰዓት ጀምረው እስከ ማታ ፲፪ ሰዓት ድረስ ይሠራሉ ከየዓመቱም ውሥጥ በታላላቅ በዓላቶችም ቢሆን ሥራውን ከጧቱ ከ፪ሰዓት ጀምሮ እስከ ፰ሰዓት ድረስ ይሠራሉ እንጂ አያቋርጡም ።

፫ኛ ቴሌፎን ቤት ።

የቴሌፎን ቤት ሠራተኞች ከጧቱ በ፩ሰዓት ገብተው እስከ ፯ሰዓት ይሠራሉ ከእኩለ ቀን በኋላ በ፰ሰዓት ተመልሰው ገብተው እስከ ፲፪ ሰዓት ድረስ ይሠራሉ በትልቅ በዓልም ቀን ቢሆን ከጧቱ በ፪ሰዓት ገብተው እስከ ፯ሰዓት ድረስ ይሠራሉ እንጂ ከዓመቱ ውሥጥ በማናቸውም ቀን ቢሆን ከጧት እስከ ማታ አይዘጋም ።

፬ኛ ማስጠንቀቂያ ።

ሕዝቡና አድሚኒስትራሲዮኖቹ የሚያመጡላቸውን ሪኮማንዴ ሁሉ ሥራውን በጊዜ እንዲያደርሱላቸውና ለነሱም ጊዜ እንዳያልፍባቸው የሚልኩትን ፖስታና ሪኮማንዴ ሁሉ የመጨረሻውን ሰዓት ሳይጠብቁ በጊዜ ማምጣትና ፖስታውን አሳጥን ማግባት አለባቸው ።

፭ኛ ተጨማሪ ቃል ።

በላጋር የቆመው የሬኮማንዴዎች መቀበያ ጽሕፈት ቤት ባቡሩ ሊነሣ እኩል ሰዓት እስኪቀረው ክፍት ነውና ለመቀበል ይችላል ሪኮማንዴ ላልሆነው የተራ ደብዳቤ ሁሉ ግን እስከ መጨረሻው ደቂቃ ሊቀበል ይችላል መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ።

የፖስታ ቴሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስቴር ።

ማስታወቂያ ።

ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊቱ በግሪክ ዜጎችና በኢትዮጵያ ዜጎች መከከል የሚደረገው ውል በማናቸውም ዓይነት ሥራ ማለት በሥራ መቋረጥ በብድር ነገር በቤት ወይም በመሬት ክራይ ነገር ይህኑ በመሰለው ሁሉ ስለ ፈላጊዮቹ ጥቢቃ (አሱራንስ) እንዲደረግላቸው የግሪክ ቆንስላ በቆመበት አገር ተዋዋዮቹ እየቀረቡ ውላቸውን እንዲያጻድቁ እንዲሆን ግድ ያስፈልጋል የግሪክ መንግሥት ቆንስላ የቆመበት አገር በአዲስ አበባ በድሬ ዳዋ በጅማና በሰዮ ነው ። ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት መጋቢት ፳፫ ቀን ተጻፈ አ አ

በግሪክ ሌጋስዮን ።

የግሪክ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ዶክቶር ዜርቦስ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠደቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ሳንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምበርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መስከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቊረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፣ የልብ፣ የደረት፣ የጉበት፣ የኩላሊት ፣ የጅማት፣ የጨብጥ፣ የቂጥኝና፣ የቋቍቻ፣የሚያዋልድ፣ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፣ የርሻ የፋብሪካ ፣ የደን ፣ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሴንጀር ቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ሐጋጻዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው

ይኽንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጇ ሙሴ ባዚል እስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ ብሙሴ ነ ሀልኩሰ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ጥናው አሰናጇ ባዚል እስላኒዲስ

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ
ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን
የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ
ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ
ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጇ በኢትዮጵ-
ያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዜና በቡና
ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም

ALEM

ባያይነቱ የኪ.ስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይ-ነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሽክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔ.ዮ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ፀአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ደ.ሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፡ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሂበኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊ.ን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢ.ትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሶ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፲፮
8^me ANNE. № 16

ሐሙስ ሚያዝያ ፮ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ ም
JEUDI 14 AVRIL 1952

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሚያስደንቅ አይሮፕላን ።

የወዳጃችን የጐረቤታችን የኢጣልያን መንግሥት እጅግ ታላቅ ፫ሞተር ያለው አይሮፕላን ከምጥዋ ተነሥቶ በ፯ሰዓት በአዲስ አበባ ላይ ላዩን አልፎ በገነት ከተማ ዐረፈ ። በነጋውም ተዚያ ተነሥቶ የአዲስ አበባን ዙሪያ ጐብኝቶ አቃቂ በመንግሥት ኩዳድ አጠገብ ዐረፈ ። ይገርማል የጐረቤቶቹን መጐብኘት ያልተመለከተ ሰው እክ ይኖራል?አዎን የምን አይሮፕላን ነው ሳያርፍ የተመለሰ የሚሉ ሰዎች አይተናል ። ስለዚህም የጐረቤቶቻችን መጐብኘት መሆኑን ለመግለጽ ጽፈነዋል ።

ስለ ባርያዎች ነፃነት

ምንም በየሌላው አገር ሁሉ ባርያ በጥኑ ግዞት መኖሩንና የባርያን ግዞት ለማጥፋት የሚጥሩ መንግሥቶች ፈጽመው ለማጥፋት ያልተቻላቸው ቢሆን ኢትዮጵያ ባርያ የሚገዛበትና የሚነገድበት አገር ናት እየተባለ ስለሚወራ ከሌላው አገር ሁሉ ስሟን ስለሚያጠፋዋት የባርያንም ግዞት ከምድር ላይ ለማስወገድ ከመቶ ዓመት ጀምሮ ባርያን ከሚገዙ ሕዝቦች ጋራ የሚከራከርና የሚታገል የእንግሊዝ ማኅበር የኢትዮጵያን መንግሥት በመንግሥታት ማኅበር በየጊዜው ስለሚከሰት አሁንም በቅርብ ጊዜ ሁለት ሚሊዮን ባሮች በኢትዮጵያ ይገኛሉ ብሎ አንዱ ባለዡርናል ስለጻፈ፡ በኢትዮጵያ የባርያን አኳኋን በሚያውቀው መጠን አስተካክሎ ለማስረዳት ሲል ይህነን አጭር ቃል ጽፎዋል ።

በኢትዮጵያ ባርያ መግዛት የተጀመረበትና የአሁንም የባሮች አኳኋንና ኑሮ በርግጡ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

፩ኛ በኢትዮጵያ ባሮች የሚባሉት ሰዎች በዚሁ በኢትዮጵያ ምዕራብና በደቡብ ምዕራብ በሰሜንም ምዕራብ የሚኖሩ ልዩ ልዩ የሕዝብ ነገዶች በፍጥረታቸው ዕድላቸው ሳይፈቅድላቸው ቀርቶ እንደ ሰው ኑሮ የማይኖሩ እንደ ዱር አውሬ ልብስና ቤት አልባ፡ ዕርቃን ሥጋቸውን በዱር በጫካ በውድማ በዛፍ ላይ የዱር ቅጠልና ፍሬ ሥር ቀቅለው እየበሉ የሚኖሩ ናቸውና በግራኝ መሐመድ የተሰበኩ በኢትዮጵያ ዳር ዳር ዙርያዋን ይልቁንም በምሥራቁና በሰሜንዋ የሚኖሩ በውስጥዋም አልፎ አልፎ በነጋዴነት የሚኖሩ ሕዝብም ወርጅ የሚላቸው እስላሞች እነዚህን መከረኞች የሕዝብ ነገዶች እንደ ከብት እያነቁ የክርስቲያኑንም ልጅ እየፈነገሉ ወደ ሱዳንና ምስር ወደ ጊዳና መካ ወደ ዓረብ አገር እየወሰዱ መሸጥ በጥቂት በጥቂት እያሉ ጀምረው ባባርያ መነገድን ለመዱ። ይህም ከተለመደ ዘንድ የኢትዮጵያም ሕዝብ ስራሱ የሚረዳውንና የሚያገለግለውን አንድና ሁለት ባርያ መግዛት ስለጀመረ ይኸው እየተለመደ ሔደ።በኢትዮጵያ የባርያ ግዞት ገባ ይህም ስለተለመደ የኢትዮጵያን ክርስቲያን ሕዝብ የሚገዛውን ባርያ ክርስትና እያስነሣ በመዋለድም እየተዛመደ አብሮ እየኖረ በሞት ይለያያል። ከሞት የተረፈውም ከክርስቲያኑ ሕዝብ ተቀላቅሎ ተጣጥቶ ይቀራል እንጂ ክርስቲያኑ የገዛውን ባርያ ሽጦ ለውጦ አያውቅም እነዚያም ባሮች እየሆኑ ለኢትዮጵያ ለክርስቲያኑ ሕዝብ የተሸጡት በመሸጣቸው ሕዝብ የሚኖሩበትን የሥልጥንናና የተሻለ ለሰው ዘር የሚገባ ኑሮ አገኙ ከቀድሞ ኑሮዋቸው የከፋ ኑሮ እንዳላገኛቸው ለማንም የተረዳ ነው። በፍርድም ቢሆን በዳኛ ፊት ከጌቶቻቸውም ከሌላም ሰው ጋራ ቢሆን ግራና ቀኝ ተቋቁመው ይፋረዳሉ እንጂ ባሮች ሆኑ ተብለው ፍርድ ሳይጐድልባቸው እስከዚህ ደርሰዋል። ከዚህም ሁሉ ይልቅ በኢትዮጵያ የባርያ ግዞት መሠረት የሌለው መሆኑን የሚያስረዳው ባለባርያ የሆነ ሰው ከሁለት ትውልድ በኋላ ባለባርያ የሆነ ሰው ባለመኖሩ ነው መሠረተኛ የባርያ ግዞት ኑሮ ቢሆን ግን የባለባርያና የባርያ ዘር ተለይቶ በየወገኑ እየኖረ ገዢም በገዢነቱ በባርያ ላይ እንደፈቃዱ ሲሸጠው ሲለውጠው ይኖር ነበር ባርያም በተገዢነት ከአባት ወደ አባት ሲተላለፍ ሲገዛ ይኖር ነበር ።

በኢትዮጵያ የባርነት ደንብ ግን የመጀመሪያ ጌታው ሲሞት ወይም እጅግ ቢበዛ በሁለተኛው ትውልድ አርነቱን አግኝቶ ከክርስቲያኑ ሕዝብ ተቀላቅሎ ይቀራል እንጂ እንደ ከብት እየረባ ሲገዛ አይኖርም ባሮች ተብለውም የሚገዙ ሰዎች የአገሩ ሕዝብ የሚኖርበትን ምግብና ልብስ በትክክል የሚበቃቸውን ያህል ተመግበውና ለብሰው ይኖራሉ እንጂ ከአገሩ ሕዝብ የተለዩ የግፍና የጉዳት ኑሮ አይኖሩም ይልቁንም ሐሳባቸውን በጌቶቻቸው ላይ ጥለው በመኖራቸው ዕድላቸውን የሚ

ያመሰገኑ ብዙዎች ናቸው።ደግሞም በዛሬው ሰዓት ባለባሮች የሚባሉት ሰዎች ባሮቹ ሠርተው የሚያተርፉላቸውን ጥቅም እደላድለው ሳያውቁት ሰብስበው በየቤታቸው አስቀምጠው የሚቀልቡና የሚያለብሱ ይልቃሉ ።ነገር ግን የነዚህ አገልግሎት ጌቶቻቸውን እያጀቡ ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ ሲነዱና አዋሩ ሲያለብሱ እየዋሉ ማታ በገበታቸው ዙርያ እየተደራረቡ መቀመጥና በዚህ ኑሮ ዕድሜያቸውን መግፋት ነው። ነገር ግን ባሮች ጌቶቻቸውን ከማገልገላቸው ይልቅ ማሳዘናቸውና ማናደዳቸው በጣም ስለሚበልጥ ብዙዎቹ ባለባሮች የሆኑ ሰዎች በባሮቻቸው ሲያዝኑና ሲመረሩ እናያለን እንሰማለን እነዚህም ጥቅሙን እደላድለው ሳያውቁት ባሮች ሰብስበው የሚያኖሩ ሰዎች ባለባርነት ጉዳት እንጂ ጥቅም አለመሆኑን ተረድተውት ባሮቻቸውን ቢያሰናብቱ ለአገሩ እጅግ የሚከፋ ነገር የሚያመጣ ይሆናል፥ስለዚህ ለጊዜው ባሮች በጌቶቻቸው ዘንድ ቢቄዩ ለሁሉም መልካም ነው ።

፪ኛዎቹ በኢትዮጵያ ባሮች የሚባሉት ዓይነታቸው ይህ ነው ። ኢትዮጵያን እስላም ከባላሸበትና ኃይልዋን ከቀነሰበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ መንግሥት የሔደበትን አገር እየመለሰ ለመያዝ ሲል በዙርያው ከአሉት ልዩ ልዩ የአረመኔ ሕዝብ ጋራ ሲዋጋ በጦርነት ውስጥ የተማረኩት ምርኮኞች በንጉሡ ፈቃድና ትእዛዝ በአዋጅ ወደ አገራቸው ሲመለሱ አንዳንዶች መመለሳቸውን እየጠሉ ንጉሡም ስለነገዳቸው ክፋት ባዋጅ ወደ አገራቸው ሳያሰናብታቸው ቀርቶ ከማረኪዎቻቸው ጋራ የሚኖሩት የምርኮ ባሮች ይባላሉ ። ነገር ግን የነዚህ ባርነት እኩሌቶቹ ወደ አገራቸው ተመልሰው ይገባሉ እኩሌቶቹም የማረኳቸው ጌታቸው በሕይወቱ እያለ ድረስ አገልግለው በሞቱ ሰዓት አርነት ይወጣሉ እንጂ ለልጅ መገዛት የለባቸውም ጠባያቸውና ባሕሬቸው መልካም ሁኖ ጌቶቻቸውን በቅን ያገለገሉ እንደሆነ የጌቶቻቸውን ገንዘብና ርስት ይወርሳሉ ።

ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግሥት አገሩን ከአሁኖቹ ጎረቤቶቹ ጋራ የጊዜ ወሰኑን ከተዋሰነበት ጊዜ ጀምሮ መዘመቱን ስለተወ የምርኮ ባርያ የሚገኘው አንዳንድ በዕድሜው የሸመገለ ባንዳንድ ቦታ ይገኝ እንደሆ ነው እንጂ ዘመቻና አገር መያዝ ቀርቷልና በአሁኑ ሰዓት ብዙ የምርኮ ባርያ በኢትዮጵያ የለም ወደትሬም አይገኝም ከነዚሁም ከምርኮ ባሮች ብዙዎቹን ማረኪዎቻቸው እንደ ልጅ አድርገው እያሳደጉዋቸው ጌቶቻቸውን እየወረሱ ከዚሁም ከክርስቲያኑ ሕዝብ እየተጋቡ ተቀላቅለው የቀሩ ናቸው።ብዙዎቹም በእውቀታቸውና በመታመናቸው የንጉሡና የመኳንንቱ አገልጋይ ሁነው እየተሾሙ እየተሸለሙ ደጃዝማች ፊታውራሪ እየተባሉ ለመንግሥቱና ለመኳንንቱ እንደራሴ እየሆኑ የገዙ የነዱ የከበሩ ናቸው ከነዚሁም አንደኛው በእውቀታቸውና በመታመናቸው ሹመታቸው ከደጃዝማች ሹመት አልፎ ከራሶች ሹመትና ማዕርግ ተካክሎ የጦር ሚኒስቴርና እንደራሴ ሁነው የነበሩት አንድ ታላቅ ሰው ምርኮኛ ነበሩና በመማረካቸውም ምክንያት ወደ ትልቅ ማዕርግ መድረሳቸውን ለማመስገን ሲሉ አብረው ከተማረኩት ከአንዱ ወዳጃቸው ጋራ የምርኮነታቸውን ወግ አንሥተው ሲያወጉ ከዚህ በታች ያለውን ቃል ተናገሩ ይባላል። አብረው የተማረኩት ወዳጃቸው ይህንኑ ነገር አንሥተው ወዳጄ ሆይ በዚያ በተማረክንበት ቀን አባቶቻችን ከደበቁን ስፍራ ተነሥተን ወደ ሌላ ስፍራ ስንዛወር አማራ አግኝቶን ባይማርከን አሁን በአለንበት ጌትነት ባልደረስንም ነበር ብለው ሲናገሯቸው ያንን ቀን የተባረክንበት ማለት ነው እንጂ የተማረክንበት ማለት አይገባም ብለው ተናገሩ ይባላል።

ይህን ሁሉ መጻፋችን በኢትዮጵያ ባርያ የሚባል ሁሉ እውቀቱና ታማኝነቱ የተገለጠና የተመሰከረለት ከሆነ በባርነት ውስጥ ተጨቁኖ ባርያ ሁኖ አለመኖሩንና የኢትዮጵያ ሕዝብ በጭከኔና በጥኑ ግፍ ባርያ የማይገዛ ሕዝብ መሆኑንና መንግሥትም ባለባሮች ባሮቻቸውን በጥኑ ግፍ እንዲገዙዋቸው የማይፈቅድ መሆኑን ለማሳየት ስንል ነው። በአሁኑም ሰዓት ሁለት ሚሊዮን ባሮች በኢትዮጵያ አሉ ስለሚባለው ግን ባርያ የሚገዛበትና የሚነገድበት አገር ብዙ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ከጥንት ጀምሮ ሃይማኖተኛ ስለ ሆነ ተርታው ሕዝብ ከባርያው ጋራ ባንድነት ሠርቶ ባንድነት ተመግቦና ለብሶ ሕይወቱን ይገፋል እንጂ እንደሌላው አገር ባርያ ጥኑ አገዛዝ አይገዛውም።በአሁኑም ሰዓት በኢትዮጵያ በእውነተኛ ባርነት የሚገዛ እንኳንስ ሁለት ሚሊዮን መቶ ሺ ባርያ ይገኝ አይመስለንም በዚሁም ሁሉ ላይ ብዙዎች ባለባርያ የሆኑ ሰዎች በሞታቸው ጊዜ ባሮቻቸውን በኑዛዜ እየለቀቁ የተለቀቀው ባርያ ከሕዝብ ጋራ አንድ እየሆነ ይቀራል እንጂ በሌላው አገር በድሮው ዘመን እንደ ነበረው ጥኑ አገዛዝ አይገዛም ባሪያ የሚባሉትም ሰዎች ከጌቶቻቸው ጋራ በመዋለድም በክርስትናም ለጌቶቻቸውም ታማኞች በመሆን እየተዛመዱ ነፃነታቸውን እያገኙ ከክርስቲያኑ ዘር ተቀላቅለው አንድ እየሆኑ ይኖራሉ ።

ባለባሮች የሆኑም ብዙ ሰዎች ለባሮቻቸው ነፃነት እየሰጡ አንዳንዶችም ገንዘባቸውን እያወረሱዋቸው ይሞታሉ ይህንንም ነገር አደላድሎ ለማስረዳት እነሆ አቶ እንዳለ የሚባሉ ታላቅ ሰው በአንኮበር ወረዳ ነበሩ በሞታቸው ጊዜ ለባሮቻቸው ሁሉ ነፃነት ሰጥተው ሞቱ ። ነፃ የተለቀቁትም ሰዎች ቍጥራቸውና ስማቸው ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

፩፡ እቶ ቡላ ፡
፪፡ ሚስቱ ትርንጎ ።
፫፡ ልጆቷ ወልደ መድኅን
፬፡ ድንቅነሽ
፭፡ ውቤቴ
፮፡ ገብረ ጻድቅ
፯፡ ወለተ ጻድቅ
፰፡ ወለተ ኪዳን
፱፡ አመተ ማርያም
፲፡ ልጆቿ ወለተ መድኅን
፲፩፡ ወለተ አማኑኤል
፲፪፡ ተክለ ሥላሴ
፲፫፡ ሞላ
፲፬፡ ደማነሽ
፲፭፡ እኅተ ጊዮርጊስ
፲፮፡ አሻግሬ
፲፯፡ አመተ ሕይወት
፲፰፡ ልጆቿ ወልደ ማርያም
፲፱፡ ኪዳኔ
፳፡ ወልደ ዮሐንስ
፳፩፡ ተክለ ወልድ
፳፪፡ ፈቃደ ማርያም

፷፫፡ ጎይሌ
፷፬፡ ወለተ ሰማዕት
፷፭፡ በረሃ
፷፮፡ ልጁ ወለተ መስቀል
፷፯፡ መልክ
፷፰፡ ሚስቱ ወለተ መስቀል
፷፱፡ ልጁ ገብረ ዮሐንስ
፸፡ ደማሚ
፸፩፡ ብሩ
፸፪፡ ሚስቱ ዕርገቱ
፸፫፡ ልጅዋ በቀለ
፸፬፡ ገመችስ
፸፭፡ ቶላ
፸፮፡ ልጆቹ መኩሪያ
፸፯፡ ዘነበች
፸፰፡ ወልደ አብ
፸፱፡ ረታ
፹፡ ሰጠኝ
፹፩፡ ወልደ ትንሣኤ
፹፪፡ ሚስቱ አበራሽ
፹፫፡ ልጆቻቸው ማሚቱ
፹፬፡ ሙሉነሽ
፹፭፡ ማሞ
፹፮፡ ተዋበች
፹፯፡ ድባቤ

በድምሩ ፹፯ መሆናቸው ነው

ለነዚሁ ለየባልና ሚስቶቹ ዓሥር ዓሥር ብር እየሰጥዋቸው ሞቱ በየአገሩና በየወረዳውም እንደዚሁ የሚያደርጉ ብዙ ሰዎች ናቸው

የቀረውን በሚከተለው እናትማለን

ስለ አለቃ በዛብህ ዕረፍት ።

በአፄ ምኒልክ ጊዜ ጀምረው በቤተ መንግሥቱ የታወቁ በሕዝብና በመኳንንት ዘንድ እጅግ የተወደዱ ነበሩ ይልቁንም የአነጋገራቸውና ያማርኛ ግጥም ማወቃቸው እጅግ ያስደንቅ ነበረ የግጥማቸውም አነጋገር እንደዛሬው የምክር ቤት ቢኖር ለአማካሪዎች ይረዳ ነበረ ምንም የአማርኛ ግጥማቸው ዋና ዋናው እጅግ ብዙ ቢሆን ለጊዜው ትዝ ያለንን እንጽፋለን በግብር ቀን ወደ ጃንሆይ ግቢ ሔደው መሳፍንቱና መኳንንቱ ቀደም ብለው ከጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ አዳራሽ ገብተው ሲበሉ ሲጠጡ የተከተላቸው ሠራዊት ርቦት ጠምቶት መቼ ይወጡልን ይሆን እያለ ሲጨነቅ የጃንሆይም ሠራዊት እኔ ልግባ እያለ ሲተናነቅ አይተው እንዲህ ብለው ገጠሙ

አንድ ጊዜ ብትገቡ ስፍራ አልጠበባችሁ
በተራ በተራ ምነው መብላታችሁ

ይህንም ማለታቸው ለጊዜው በአዩት ግብር አስመስለው የተራበውን አሰቡ እንጂ እድምብሬ ላይ የአገሌ አገር አለችና ይጨምሩልኝ ማለታችሁን ትታችሁ ደጅ የሚጠናውን ድኻ አትርሱት ማለታቸው ይመስላል ነገር ግን ያማርኛ ትርጓሜው ብዙ ነውና በየተቻላችሁ ተርጕሙት እኛ የጻፍነው መቸም የታላቁን ሽማግሌ መታሰቢያ ነው ። መቸውንም ቢሆን መንግሥትና ሕዝብ የወደዳቸው ነበሩና ከሹመት ተለይተው አያውቁም ነበረ ። አሁንም ከሸመገሉ ወዲህ ወደ ከተማ መምጣት የማይችሉ ስለሆኑ በተሾሙበት አገር ሲኖሩ የከተማው ሰው እጅግ ይናፍቃቸው ነበር ። በሚገዙት አገር ያለ ሕዝብ እንደ አባት እንጂ እንደ ሹም አይቈጥራቸውም ነበር ነገር ግን ሰው ምንም ቢወድ ከሞት አያድንምና በመጋቢት ፲፯ ቀን ዐረፈው ሕዝቡም እጅግ አዝኖላቸው በዚያው በተሾሙበት አገር በብዙ ክብር ተቀበሩ ዕድሜአቸውም ፸፰ ዓመት ነበረ ።

ለአንባቢዎች ማመልከቻ

ከዕለታት ፩ቀን ወደ ከተማ ለትንሽ ጕዳዬ ወጥቼ ያየሁትን ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ላካፍላቸው ወደድሁ

አንድ ባላገር ሰው በፈረስ ሰምሰማ ሲሔድ የከተማ ደንብ ጠባቂ ዘበኞች ያዙት እኔም የዚህን የድኻ መጨረሻ እያለሁ ብዬ ቆሜ ሳለሁ ደግሞ አንድ የከተማ ነዋሪ የሆነ ሰው ሽምጥ እስነሥቶ ሲጋልብ መጣ በዚያን ጊዜ እኔም ይህን ሰምሰማ ሔድክ ብለው እንዲህ ያደረጉት ይህን ባለሽምጡን እንዴት ሊአደርጉት ነው እያልኩ በሱ ፈንታ እኔ ሰፈራለት እንኳንስ ሊጠይቁትና በክፉ ዓይን ሳያዩት አለፈ ።

እኔም ከዚያ በኋላ ይህን ጥያቄ ጠየቅኋቸው ያን በሽምጥ ያለፈውን ትታችሁ ይህን ድኻ ለምን ታስለቅሱታላችሁ? ብላቸው እንዲህ ብለው መለሱልኝ እሱ የከተማ ሰው ስለሆነ ቁም ብንለውም አይቆምልን ብለን ነው ብለው ያለኃፍረት መለሱልኝ። በዚያን ጊዜ በመልሳቸው ተገርሜ ዳግም እንደዚህ አልኋቸው እሺ ያላችሁን እንደዚህ ልትጨክኑበት እንቢ ያላችሁን ልትለቁ ብዬ ጭካኔ በሚገባው ላይ ርኅራኄ ርኅራኄ በሚገባው ላይ ጭካኔ ያደረጉበትን ድኻ ፍጻሜውን ሳላይ የሥራ ሰዓት ስለደረሰብኝ ሔድኩ ግፍ የሚባለው ሁሉ እንደዚህ እንደሆነ በጣም የሚያስገርም ነው

ፈለቀ ዕርገቱ ።

የያንዳንዳችን አሳብ ።

ስለ አገር ፍቅር ።

እኔ አገሌ አገሬን እወዳታለሁ ማለቴ እምጣ ወልዳ በተራሮችዋ ሸፍና ከብርቱ ቅዝቃዜና ሙቀት ጠብቃ አቀማጥላ ስላሳደገችን ነውን ወይስ ከደረስኩ በኋላ እርስዋን በመርዳት።

ሁላችንም እያንዳንዳችን አገራችንን ኢትዮጵያን እንወዳታለን እንላለን ነገር ግን አንድ ሰው ተነሥቶ አገርህን ወደህ ምን አደረግህላት ብሎ ሲጠይቀን መልስ እንዳናጣ ወቃሽ ሕሊናችን ለመልከም ሥራ ያነቃቃን ።

እነሆ ሁሉን የሚችል አምላክ አእምሮን ያህል መሣሪያ ሰጥቶ በመልኩ ፈጥሮን ሳለ ለውዲቱ እናታችን መጦሪዋን ሳንሠራላት በከንቱ ጊዜያችንን ብናሳልፈው ከስንፍና ወይም ከንፍገት ይቈጥርብናል ስለዚህ መርምሮ መሥራትን ለያንዳንዳችን አድሉናል ።

የሁላችን አባት አዳም ትእዛዙን በተላለፈ ጊዜ ጌታችን እንዲህ አለው ወደ ምድር እስክትመለስ ድረስ እንጀራህን በፊትህ ላብ ብላ መሬት ነህና ወደ መሬትም ትመለሳለህ» እንዲህ ማለቱ ሠርተህ አደር ሲለው ነው ።

ነገር ግን ይኸን ያላስተዋሉ (ያልተማሩ) ወጣቶች ሐሳ ተላላፊዎች ሁነው ሳይሠሩ መብላትን ይለምዱና ባሉበት ዘመን ሁሉ የሕዝብ ዕንቅፋት ሁነው ይኖራሉ ። ይኸም በየጊዜው የምናየው ነው ።

ለምለም ማር ሲፈልግ በገደል የሚወድቅ መንጋ በረኞቹ ዝንጋታ እንዲሆን እንዲሁም ወጣቶች አገራችንን እንወዳለን በምንልና በሊቃውንት ስለዚህ የደማቸው አላፊ መሆናችን ነው ።

መልክምን ሥራ መፈጸም እንጂ ማዘግየትስ ከባድን ነገር በትከሻ ተሸክሞ ከመንከራተት ይብሳል ይኸን ማለት ሥራን ባንድ ጊዜ መፈጸም ይገባል ማለት አይደለም ነገር ግን አለ መዘንጋትን ያስከብል አለመዘንጋቱም ፈጥኖ ለማከናወን ይበቃል ።

፩ኛ አስረጅ፦ አንድ ገናና ንጉሥ ደን መንጥረህ ፥ አገር አቅንተህ ወታደር መርተህ እህል አብቅለህ ተመለስ ብሎ ወዳንድ ክፍል አርበኛውን ላከው አርበኛውም ንጉሡን ደስ ለማሰኘት ሲል ዝንጋታን አስወግዶ በርትቶ በመሥራት የጌታውን ትእዛዝ ሁሉ ፈጽሞ ከበቀለው እህል ፍሬውን ይዞ በቀረበ ጊዜ ያማረ ሽልማት ተሸልሞ በቀድሞው ማዕርግ ላይ ማዕርግ አስጨመረ በባልንጀሮቹም ፊት ክብር ሆነለት ።

፪ኛ አስረጅ፦ አንድ ተማሪ ይችላል ብለው አምነው መምህሩ የሰጡትን ትምርት ነገ አጠናዋሁ በማለት ዘንግቶ ጨዋታ ወዳለበት ቤት ሒዶ አመሸ በተመለሰም ጊዜ ድካም ተሰምቶታልና ፈጥኖ ተኛ ። በማግሥቱም ሰዓት ደርሶበት ወደ ተማሪ ቤት ወጣ መምህሩም አጥና ብለው ከሰጡት ትምርት አንዲት ጥያቄ አቀረቡለት ነገር ግን አንዳች መልስ ሊሰጥ አልቻለም ስለዚህ ጓደኞቹ ስቀውበት አፈረ ይልቁንም መምህሩ ባማረ ሽልማት ፋንታ ብርቱ ቅጣት ሰጡት እንዲሁም እኛ ቈይ ለነገ ለትናንት ጠዊያ እያልን እድንሠራበትና እንድናሠራበት የሰጠንን አእምሮ ሥራ አስፈትተን ብናዝገው ለድንቍርና መታዘዛችን ይሆናል ስለዚህ መሳቂያ ሁነን ብርቱ ቅጣት ያገኘናል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሐዋርያት ሥራና ትሕትና ሲያስተምረን እንዲህ አለ ። እነሆ እኔ ተቀምጦ የሚበላ ጌታ ስሆን ቁሜ አገለግላችኋለሁ ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደ ቀኝ እያልሁ ።

ዳግም ባጭር ታጥቆ ተንበርክኮ የደቀ መዛሙርቱን እግር እንዳጠበ ሌላም ልዩ ልዩ ሥራ እንደሠራ በቅዱስ ወንጌል እንብበን አምነናል። እንግዲያስ እኛ ታዛገርች ስንሆን ሥራና ሠሪን መናቅ አይገባንም ስለዚህ ለያንዳንዳችን ጥቅም ብቻ ሳይሆን ሕይወታችንን ስለኢትዮጵያ መሥዋዕት ማቅረብ ይገባናል ።

ብርሃን መስቅል አየለ

ስለ አኑዋኑዋር ጥያቄ ።

ከቡራን አንባቢዎችና ተመልካቾች ሆይ ከሥራ ሐሳብ የተነሣ አቶ ጠብቄ የሚባሉትን ሰውዬ ጥቂቶችን ነገሮች ብጠይቃቸው እንደዚህ ያሉትን ነገሮች በብርሃንና ሰላም ዳኝነት ጠይቀኝና የብርሃንን ሊቃውንት እርዳታ ይገፔ እመልስልሀለሁ እንጂ መልሴን በከንቱ አላጠፋም ስላሉኝ እነሆ ሁለታችንንም በተተከከለው አእምሮአችሁና እውቀታችሁ እንድትገላግሉን በማለት ጥያቄዎቹን ቀጥዬ ጽፌአለሁ ። ፩ኛ ከረጅምና ከአጭር የሥራ ጊዜያቶች ማናቸው የተሻሻሉና ተሰብስበው ተከናውነው የተመረጡ ጊዜያቶች የሆናሉ። ፪ኛም የሀገርንስ ልማድ ለማደስና ዓለም ሁሉ ወደሚጓዝበት የሥልጣኔ ጐዳና ለመምራት የሚአስፈልገው ምክንያቱ ከቶ ምን ይሆን ፫ኛ ባለ ሙሉ ሥልጣን የሆነውን ሰው በታዘዘው ሥራ የሚአግደውና የሚወስነውስ ነገር ምንድርነው ። ፬ኛም ገቢ እየተከዘ ወጭ እየፈነጠዘ መንዘቸው ምን ዓይነት ነገር ነው ብዬ ብጠይቃቸው እንደዚህ ያለውን ጥያቄ የብርሃን ሊቃውንት ይስሙትና በደንቡ ልመልስልህ ስላሉኝ ባለመሰልቸት በትጋት አስተዋይ የብርሃን ሊቃውንት የሆናችሁ ሁሉ በዚህ ጥያቄዎች የሽምግልና ግልግላችሁ እንዲገላግሉን ልመናዬን ከማክበር ጋራ አቀርብላችኋለሁ።ትጉህ አክባሪአችሁ ደነቀ ተክለ ጊዮርጊስ ።

በአፈርሳታ ስለሚሠራ ሐሰት

በጨርጨር አውራጃ የሌብነትና የድብቅ ወንጀል የሚሠራውን ሁሉ የወንጀሉን ሥራ ሲሠራ ወደዚያው ካልተያዘ በቀር የሚመረመረው በአፈርሳታ ስለሆነ ሦስት ሐሰት ነገር ስላየሁ ልጽፈው አሳሰበኝ ነገሩም እንደዚህ ነው

፩ኛ በሐረዋጫ ወረዳ አመድ ጳሜ የሚባል ለሊት በጩቤ ስለተወጋ የልጁ ባል አማቹ አመድ አብዲ የሚባል ለወምበሮች አመልክቶ አፈርሳታ ይውጣለት ስለተባለ በፈርሳታው ውስጥ በስውሩ ቋንቋ ወፍ የሚባሉ (ሰዎች) የወጋው የልጁ ባል አመድ አብዲ ነው ብለው ስለመሰከሩበትና አመድ አብዲ ስለታሰረ ወምበሮቹ ነገሩን መርምረው ደም ፈላጊውን ማውጣታቸው ያጠራጥራልና ወሮቹ ይምጡ ብለው ቃል ቢአልፍ ከዘበኛ አምልጠው ስለጠፉ የተወጋውም ድንዋልና ነገሩ ሳይፈጸም ቆይቶ የወረዳው ምስለኔ አቶ መኰሸ ወልደ ሚካኤል ጅብራኤልና ኢብሮ ኢለም የሚባሉትን ሁለት ሐሰተኞች ይዞ ስለላከቸው ቢመረመሩ በሐሰት ነው ያወጣነው ብለው አምነው የሐሰተኛ ቅጣት ተቀብለዋል

፪ኛ አሰን ወዳይ የሚባል ቤቱ ተቃጥሎ አፈርሳታ ሀገር ወጥቶ ተክለ ሥላሴ ነው ያቃጠለው ብለው አውጥተውት ፍርዱ ተፈጽሞ ሀገሩ ዪማልለት ቢባል አታስምለን የወጣህ የወረድክበትን እንክፈል ብለው በገንዘብ ታርቀው በኋላም በዚሁ በገንዘብ ተካከደው እፍርድ ቤት ስለደረሱ የታረቁት ሁሉ ቀርበው ቢመረመሩ አታስምለን ብለን ታርቀናል ብለው እኩሎቹ ስላመኑ ፍርድ ለመቀበል ታስረዋል

፫ኛ ሞሐመድ ሞአለፋ የሚባል ሌባ ስሙን እየለወጠ የሚያታልል አንድ ጊዜ ወልደ ሚካኤል አንድ ጊዜ ታደሰ ፩ጊዜ ሞሐመድ ሞአለፋ እየተባለ ሲዘዋወር በሌብነቱ ተይዞ ሐረር ደርሶ ተገርፎ ተለቆ ነበር ። ነገር ግን የለመደ አመል አይለቅምና በሐረዋጫ ወረዳ ሸጉጥ ሲሰርቅ ተይዞ የወረዳው ምስለኔ አቶ መኰሸ ይዞ አቅርቦትነገሩ ተመርምሮ ክቡር አዛጋ

ወርቅነህ ባስቻሉበት ቀርበ አምኖ መቀጫ ተቆርጦበት ታስሮ ነበር። በኋላም ከወህኒ አታሎ ሰብሮ ስለጠፋ ዘበኞቹ ተቀጥተው በጥንክር ሲፈለግ አታላይ ለጊዜው ያስመስላልና እስላም ነኝ አደም አሊ እባላለሁ ኩሊ እሠራለሁ ብሎ ስሙን ለውጦ ወላ ቂኒ ከሚባል አገር ሙመድ አሊ ፋራ እሚባል ሰው ቤት በኩሊነት ሲሠራ ቆይቶ ኑሮ በኋላ ነገሩ የሚገለጽበት ቢሆን ቢጠፋ የዚህ እርሶ ሠርቶ የሚኖር የሙመድ አሊ ጉረቤቶች ምቀኞች ሁነው ገድሎታል ብለው ኡስማን ሐሺ የሚባለው ዋና ሁኖ በሐሰት አሳስረውት ነበር ነገር ግን ነገሩ ተመርምሮ የማይበቃ ቢሆን አፍርሳታ እንዲወጣ ወምበሩ ቀኛዝማች በላቸው አስበውበት ነበርና ለበላይም አስታውቀው አፍርሳታ እንዲወጣ በለታዘዘ ሀገር ተሰብስቦ አደም አሊን የገደለው ሙመድ አሊ ፋራ ነው ። እሬሳውን አብሮ የጐተተው አብዲ ሐሺ ነው እሬሳው የተጐተተበትን ደሙ እንዳይታይ የአቃጠለው አብስዬ ነው ብለው ፱ ወኗ (ሰው) ሀገሩም ስላወጧቸው ነገሩ ታይቶ አየን የሚል ምስክር ከተገኘ ግልባጩ ሐረር ታይቶ እስረኞቹ አዲስ አበባ ይወጣሉ ተብሎ ፍርዲ ተፍጽሞ ግልባጩ ሲዘጋጅ ምን ጊዜም እውነት ለሐሰት አይለወጥምና እነዚህ የታሰሩት እስረኞች ወደ ክርስቶስ ሲአመለክ፥ እምላኬ ሲለምኑት ቅሩብ ነውና ይኸው ሞተ የተባለው አደም አሊ የሚባለው ግዛው ተብሎ የሰው ጊደር ሠርቆ አቢብ ከሚባለው እረዳቱ ጋራ እርዶ ሲበላ በጩኸት ተይዞ በውላ ቂኒ ጉልት ሹም በልጅ ፈረደ ዳኝነት ተመርምሮ በእጁም የተገኘው ጠመንጃ ከሾሮ አሊ የሰረቀው ሆኖ ስለተገኘ የጊደሩዋንቆዳ አሸክሞ በሰንሰለት በዘበኛ ልኳቸው በወህኒ እንዲታሰር ቢሔድ ሙመድ አሊ ፋራ ከነወገኖቹ አደም አሊ መጣልን ብለው ደስታቸው ከልክ ያለፈ ሆኖ ለፍርድ ቤት ማመልከቻውን ስለላከ ጊዜው የቀላጤ ሰዓት ስለሆነ ሳይመረመር አድሮ በማግሥቱ በ፩ሰዓት የባሬወምበሩ አቶ ረዴ በትጋት ተነሥተው በችሎት ተቀምጠው አቅርበው ቢመረምሩአቸው አደም አሊም በኩሊነት እሙመድ አሊ ፋራ ቤት የተቀመጥኩት እኔ ነኝ ብሎ አምኖ ሙመድ አሊ ፋራም ሞተ ብለው በገዳይነት ሀገር ያወጣኝ አደም አሊ እቤቴ የተቀመጠው ይህ ነው ብሎ ስለአመለከተ ወሮቹና ይህንን ነገር የወጠኑት ውሥጠ ወጊዎች እንዲያዙና እንዲመጡ በተሰጣቸው ሥልጣን የጠነከረ ትእዛዝ አሳልፈው ወደዚያው በሰበር አቅርበው ያሰቡት ተፈቅዶላቸው የወረዳው ምስለኔ አቶ በቀለ ወርቄ በጥንክር ይዘ ስለአቀረቡቸው ያውሬጃው ዲሬክተር ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ቢመረምሩአቸው እውነቱን የማያወጡ ስለሆኑ ለየብቻቸው ታስረው አድረው በማግሥቱ የጨርጨር አውራጃ ዲሬክተር ልጅ መስፍን ባስቻሉበት የግራ ወንበሩ አቶ ረዴ በተቀመጡበት ወሮቹ ቀርበው ቢመረመሩ መጀመሪያም ሞተ ያልነው አደም አሊ ይህ ነው ሙመድ አሊ ፋራ ነው የገደለው ያልነውም እናንተን እናወጣችኋለን ቢሉን ፈርተን ነው እንጂ በሐሰት ነው ትናንትም ብንጠየቅ የሸፈጥነው ቃላችሁን ፩አድርጋችሁ ይህ አይደለም በሉ እኛንም የሀገሩን ሰዎች ቢጠዩቁን እንመሰክርላችኋለን ስላሉን ነው ብለው ስላመኑ ተንኰል መካሪዎቹም ቢጠየቁ ቃላችሁን አንድ አድርጉ እኛንም ቢጠይቁን ይህ አይደለም የሞተው እንላለን ማለታችን እውነት ነው ግን ሞተ የተባለው አደም አሊ ይህ ነው ብለው ስላመኑ ገደሉ የተባሉት በዋስ ተፈትተው ተንኰል ሰሪዎቹና ሐሰተኞቹ ወሮች ታስረዋል የክዱትም ተመስክሮባቸው ታስረዋል ይህንንም ለመጻፍ ያሰሰኘኝ አንድም ሞተ የተባለው ሰው ሲገኝ ዘረ አደም ነውና ምንም በእውነት ሞቶ ባይመለስ በወሬም ሞቶ ከተገኘ የምስራች ነው ፪ኛም በልሁሩት ሥራ ገዳዮች ሆነው ሕይወታቸውን የሚያሳልፉት ስለዳኙ ምንም ቢሆን ደስ ያሰኛልና በጉባኤ ማህል ለመናገር ደፈርሁ ስለዚህ ሀገር ተሰብስቦ ሞተ የተባለው ከተገኘ ወንጀለኛው በቃሉ ካላመነ በቀር ሀገር ባፍርሳታ አውጥቶሃልና ተቀጣ በቃ ለማለት ለፈራጆች ቅርታ ሳይሆን አይቀርምና ከመንግሥት አደራ የተቀበሉ ዳኞች ወደፊት በፈርሳታ ነገር ይጠነቀቁበታል በማለት ተስፋ አለኝ በዚህም አስተያየት ግን በጭራሽ በአፈርሳታ ነገር እንዲታሰብበት አመለክታለሁ ተኩላ መብራቱ

ማስታወቂያ ።

ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊቱ በግሪክ ዜጎችና በኢትዮጵያ ዜጎች መከከል የሚደረገው ውል በማናቸውም ዓይነት ሥራ ማለት በሥራ መቋረጥ በብድር ነገር በቤት ወይም በመሬት ክራይ ነገር ይሁኑ በመሰለው ሁሉ ስለ ፈላጊዮቹ ጥበቃ (እሱራንስ) እንዲደረግላቸው የግሪክ ቆንስላ በቆመበት አገር ተዋዋዮቹ እየቀረቡ ውላቸውን እንዲያጸድቁ እንዲሆን ግድ ያስፈልጋል የግሪክ መንግሥት ቆንስላ የቆመበት አገር በአዲስ አበባ በድሬዳዋ በጅማና በሰዮ ነው ። ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት መጋቢት ፳፫ ቀን ተጻፈ አ አ

በግሪክ ሌጋስዮን ።

የግሪክ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ዶክቶር ዜርቦስ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኪት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዣና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩባንያ ሴንጀር በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ፍናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ኣለም

ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።





ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኜይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ጴልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፌ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልኩ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙሱ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፲፯
8me ANNE. № 17

ሐሙስ ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ ም
JEUDI 21 AVRIL 1952

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የማያውቁትን ማውራት ታላቅ ቅለት

ይህን ያሰኘን የቤተመንግሥቱ ገቢ ገንዘብ ከቀድሞው ገቢ እያነሰ ሔደ እያሉ የሚአወሩትን የሐሰተኞች ወሬ ስለ ሰማን ነው። እነሱም በሐሰት ወሬ አፋቸውን አጠፉ እንጂ የቤተመንግሥቱስ ገቢ ገንዘብ ከቀድሞው ይልቅ እየበዛ ከመሔድ በቀር አላነሰም። ለዚህም ማስረጃ እንዲሆን ከአዲስአበባ ጉምሩክ ብቻ የተገኘውን ገቢ ገንዘብ ቀጥሎ በሚታየው መስመር ጽፈናል ። ከመስከረም ፩ቀን ጀምሮ እስከ ሚያዝያ ፩ቀን የ፯ወር ገቢ ፪ሚሊዮን ፱፻ ፳፯ሺ ፳፯ ብ፲፫ መሐለቅ ሆነ።

ከአምናው ገቢ የዘንድሮው ገቢ ብልጫ ፻፲፩ሺ ፱፻ ፺፫ብር ፲፪ መሐለቅ ሆነ ። እግዚአብሔር ይመስገን የቤተመንግሥቱ ገቢ እየተጨመረ ሔደ እንጂ እየጐደለ አልሔደም የቤተመንግሥቱ ገቢ ከቀድሞው እያነሰ ሔደ ማለት የጠላት ወሬ ነው ።

የመቶ ፲፱ ገጽ ተከታይ

እነዚህ ባሮች የተባሉ ከጌታቸው ተስማምተው በፍቅር ይኖሩ የነበሩ ሰዎች በጌታቸው መሞትና ሰብሳቢ በማጣታቸው ታላቅ ችግር ስለ አገኛቸው ያለ መጠን አዝነው የእግዚአብሔርን ስም እያማረሩ እያለቀሱ ወደ መከራ አዘቅት ወድቀው በማያውቁት አገር ተበራሪ ሁነው ቀሩ እንጂ በጌታቸው ሞት ነፃነት ስለአገኙ ደስታና ተድላ አላገኙም። ጌታቸውም ሲሞቱ ለልጆቻቸው በአወረሱት መሬታቸው ላይ በጢሰኝነት ተቀምጠው እያረሱ እንዲበሉ ተናዘውላቸው ነበርና ጥቂት ጥቂት ጊዜ የጌታቸውን መሬት እያረሱ ሲበሉ ቈይተው ነበር። ነገር ግን በዚህ ትዳራቸውን አከናውነው ራሳቸውን ችለው ለመኖር የማይሆንላቸው ሁኖ የሚልቁት ከዘመዶቻቸው እየተለዩ ያነን አገር እየለቀቁ በየአገሩ ተሰደዱ።ከነዚሁም ሠርተው የሚያድሩበት ስፍራ እያጡ እየተመለሱ የጌታቸውን ልጆች እየተጠጉ ይኖራሉ አንዳንዶቹም በየስፍራው እየተባረሩ በችግር ውሥጥ እንደሆኑ ሞቱ ።

እንግዲህ እነዚህ ባርያ ተብለው ከጌታቸው ጋራ በስምምነትና በፍቅር በጌታቸው መሪነት ባንድነት እየሠሩ ሕይወታቸውን ይገፉ ነበሩ ከጌታቸው መሞት የተነሣ ግን ተጐዱ እንጂ ከቀድሞ ኑሮዋቸው የተሻለ ኑሮ ከቶ እንዳላገኙ በግልጥ ይታያል።በዚሁም አቶ እንዳለ ባሮቻቸውን በገዙበት አገዛዝ ሲገዙ እየኖሩ ሲሞቱም በመልካም ኑዛዜ ለባሮቻቸው ነፃነት እየሰጡ የሚሞቱ ብዙ ሰዎች በኢትዮጵያ በብዙ ወረዳ መኖራቸው በግልጥ የታወቀ ነው ።

በሌላም በኩል ከዚህ በላይ እንደተባለው በአበልጅነት በመዋለድ ከጌቶቻቸው እየተዛመዱ ነፃነታቸውን የሚያገኙ ብዙ ናቸው እኔም ራሴ ባሮቼ ከእኔ ዘንድ ካሁን በፊት መሔድ የፈለጉትን ሁሉ እንዳላገድኋቸው ብዙ ሰው ያውቃል።ከሔዱትም እኩሌቶቹ ተመልሰው እኔው ዘንድ ይኖራሉ። አሁንም መሔድ የፈለገ ቢኖር ነፃ ነው እንጂ አልከለክለውም ስለዚህ በኢትዮጵያ የባርያ ግዞት በሌላው አገር ቀድሞ ዘመን እንደ ነበረው ግፍ የመላበት ጥኑ አገዛዝ ይገዛል ለማለት አይቻልም። ይልቁንም ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከብዙ ዘመን ዠምሮ በእግዚአብሔር የሚያመልክና የሠለጠነ ሕዝብ ነውና ባርያ መግዛት በዓለም ሁሉ ላይ የተጠላና ለመከልከል የሚገባው መሆኑን ፈጽሞ ያላወቀው ቢሆን ነው እንጂ የባርያ ግዞት በሌለው አገር ሁሉ ተከልክሎ ቀርቶ በኢትዮጵያ ብቻ መኖሩና ይኸውም መነቀፊያውና ወደ ክፉ ነገር የሚወስደው መሆኑን እያደር ሲረዳው ከዚህ በላይ እንደተጻፈው አገሩን ከማስነቀፍና ከማሳማት ባርያውን አርነት መልቀቅ ሳይመርጥ ይቀራል ተብሎ አይጠረጠርምና በሌላው በክርስቲያን አገር ሁሉ የባርያ ግዞት ቀርቶ በኢትዮጵያ ሳይጠፋ እስከሁን መቈየቱ ኢትዮጵያ በጂኦግራፊ አቀማመጥዋ በበረሃና በአረመኔ ሕዝብ የተከበበች ስለሆነች በኤውሮጳ የፈለቀው አዲስ ጥበብና ሥልጥንና በጊዜያቱ ወደርስዋ ለመግባት መንገድ አጥቶ ስለዘገየ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትምርቱ ሳይደርስለት ከመቈየቱ የተነሣ ነው እንጂ የክርስትና ወንድሞቹ የሆኑ መንግሥታት ተባብረው የጠሉትንና ከየአገራቸው ያጠፉትን፥ በዓለምም ሁሉ ፊት ታላቅ ነውር ሁኖ የተቈጠረውን የባርያ ግዞት ለወደፊቱ በጥቂቱ ጊዜ ከአገሩ ሳያጠፋው አይቀርም ።

ይህንንም ለማደላደል እነሆ ባለ ባርያ የሚባሉት ሰዎች ብዙዎቹ ባሮቻቸውን በየመሬታቸው እያስቀመጡ ለየአንዳንዱ

አንድ አንድ ጥማድ በሬ እየሰጡ አርሰው ከሚያገኙት ከማናቸውም ነገር እኩል ይካፈላሉ። ሌሎችም አንዳንዶች አሥርና አሥራ አምስት ጋሻ በሚሆን መሬታቸው ላይ በርከት ያሉ ባሮች እያስቀመጡ መሬቱን አርሰው ከሚገኘው በየቤተሰባቸው ፪ና ፫ዳውላ እህል ለጌቶቻቸው እያከፈሉዋቸው የቀረውን ለራሳቸው እንዲያስቀሩ የሚያደርጉ አሉ። የመሬቱን ግብር ግን ባለቤቱ እየቻለ ነው። ይህም ሁሉ በኢትዮጵያ የባሮች ግዞች ፅኑ ነው ለማለት የሚያስቸግር ይመስለናል ።

ጸሐፊውም ይህነን ቃል መናገሩ በኢትዮጵያ የባርያን ግዞት በቶሎ ለማስቀረት በሕዝቡም ባሮች በተባሉትም በመንግሥቱም ያለበትንና የሚየመጣውን ብዙኅ ችግርና ሕውከት አጥልቀው ለማወቅ ያልተመቻቸው ሰዎች ሰው ሁኖ ለሰው መሸጥና መገዛት ብርቱ ግፍ መሆኑን ብቻ በቅን ልቦናቸው እያሰቡ የልባቸው ኃዘን ዕረፍት ስለማይሰጣቸው በኢትዮጵያ የባርያ ግዞት በቶሎ እንዲቀር እያሉ በመንግሥቱ፡ ስለሚጮሁበትና ስለሚያጣድፉት መንግሥትም በ፲፱፻፲፮ ዓ ም በአቆመው የባርያ ነፃ ማውጫ ደንብ የተጻፉትን ክፍሎች በዝግታ እያስፈጸመ የባርያን ግዞት በጭራሽ ለማጥፋት እንዲመቸው ጊዜ ያስፈልገዋልና በሌላም በኩል እነዚሁ ሰዎች የባርያ ግዞት በቶሎ ካለመጥፋቱ የተነሣ የባሮች ግፍ የሚረዝምባቸው ስለሚመስላቸው ከዚህ በላይ የተጻፉት የባለባሮችና የባሮች የርኅራኄ አስተዳደር ዓይነት በኢትዮጵያ መኖሩን ለነዚሁ ሰዎች ለማሳየት በማለት ነው እንጂ ባሮች ነፃ ለመውጣት የሚገባቸው መሆኑን ለመቃወም ምክንያት መፈለጉ አይደለም ።

ባሮችንም ነፃ ለማውጣት የሚመቸው ሁለት ነገር ነው። ከነዚሁም አንዱ መንግሥት አስቦ ያቆመውን የነፃ ማውጫ ሕግ ያስፈጸመ እንደሆን ነው ይህነን ማለት ፲፱፻፲፮ ዓ ም በአቆመው ደንብ በ፲፮ኛው ክፍል የዚሁ ደንብ አዋጅ ከተነገረበት ቀን አንሥቶ ወደፊት የሚወለዱ የባርያ ልጆች ሁሉ ባርነት የለባቸውም ይላል ። ደግሞ በ፲፯ኛው ክፍል ባርያ ያለው ሰው ሲሞት ባርያው ነፃ ይወጣል ይላል ። እንግዲህ የሚሞት እያነሰ የሚወለድ እየበዛ መሔዱን የሚስተው የለም። እንደዚሁም ባለባሮች በተወሰነላቸው ዕድሜያቸው እያለቁ ሲሔዱ የሚወለዱትም ባሮች ነፃነታቸውን እያገኙ መሔዳቸው ከማንም እውቀት ያልተሠወረ ነገር ነው ። በዚሁም በሕግ ላይ በ፫ኛውና በ፭ኛው ክፍል በክርስትና በመወለድ ባርያ ነፃነቱን እንዲያገኝ ተጽፍዋል ። ይህም የባሮችን ግዞት እያቃለለ የሚሔድ ነው።

ከዚህ ሁሉ የሚልቀው የባርያን ግዞት ፈጽሞ ከአገር የሚያጠፋና ኢትዮጵያን ከባርያ መነገጃነት ሐሜት የሚያድናት መንገድ ፈንጋይን ከአገር ማጥፋት ነውና መንግሥት የተከከለ የምሥጢር ዘበኛውን አቁሞ እያስጠበቀ ባቆመው ደንብ በ፴፩ኛውና በ፴፪ኛው በ፴፫ኛው ክፍሎች በተጻፈው ቅጣት እየቀጣ ፈንጋይን ከአገሩ ቢያጠፉ የባርያ ግዞት በጥቂት ጊዜ ከኢትዮጵያ እንዲጠፉ የታወቀ ነገር ነው ። መንግሥትም በመልካም ዘበኛና ፈታሽ አስጠብቆ ፈንጋይን ከአገር ለማጥፋት መጣጣሩ ከታየለትና ከታወቀለት በኋላ መጠየቅና መታማት መነቀፍ የለበትም። በአዋጅ የአቆመውን ደንብ አስጠብቆ ለማስፈጸምና እስከ ፲፭ና ፳ዓመት የባርያን ግዞት በጭራሽ ለማጥፋት የማይሆንለት ሁኖ በገሩ ባርያ ሲሸጥና ሲገዛ ቢገኝ ግን በዓለም ሁሉ ሕዝብ ፊት ነቀፌታ እንዳያገኘው ያሠጋዋል ። ሁለተኛውም የነፃ መውጫ መንገድ ኢትዮጵያ ወደ አዲሱ ጥበብ መራመድ ጀምራለችና እየገፋች ስትሔድና በዚሁ በጥበብ የሚጀመረው የመንገድና የእርሻ ማናቸውም ለአገር ብልጽግና የሚሆን እንደ መዘውር ወፍጮ የሆነ ልዩ ልዩና ዋና ዋና እንዱስትሪ የሚባል ሥራ ሁሉ በየዓይነቱ በውሥጥዋ ሲቋቋምና እየሰፋ ሲሔድ ባለ ባርያም የሚያስፈልገውን ሥራ ቢትንሽ ዋጋ አሠርቶ ወይም ገዝቶ ያድራል እንጂ አሳባቸውን በጌቶቻቸው ላይ ጥለው ከሚኖሩ ባሮች ጋራ ንዝንዝና ጭቅጭቅ አያገኛቸውም ባሪያም በየእንዱስትሪውና በየመንገዱ ሥራ እየገባ ሠርቶ ያድራል። በዚህ የባርያ ግዞት ፈጽሞ ይጠፋል

የባርያ ግዞት ይቅር የሚሉ ሰዎች እንደሚሉት ባሮች ሁሉ በቶሎ እንዲለቀቁ ማስገደድ ግን ለባርያም፥ለባለባርያም፥ ለመንግሥትም እጅግ የሚያስቸግር ነገር ያመጣል። እንደምን? ቢሉ መጀመርያ ከጥንት ጠንቶ በቄየው ያገር ልማድና ኑሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ ሠርቶ አዳሪ ስለሆነ ከዚህ በመጀመርያው አንቀጽ እንደተባለው የባርያ መግዛት ሲጀመር ለራሱ ኑሮ የሚረዳውንና የሚያገለግለውን ባርያ መግዛት በጥቂት በጥቂት ኋላ ለምዶ እስከሁን የቈየ ስለሆነ አሁንም በዚያው በቀድሞው ልማድ የድኃ ገንዘቡን እያወጣ የሚረዳውን አንድ ወይ ሁለት ባርያ እየገዛ ክርስትና እያስነሣ በስምምነትና በፍቅር የሚኖረውን ባርያ የሚባል ረዳቱን በድንገት ባንድ ጊዜ ልቀቅ ብሎ ያለ አንድ ካሣ ማስለቀቅ የተከከለ ፍርድ አይመስልምና መንግሥት ቢያስገድድ ሕዝቡን ማሳዘንና መጕዳት ይሆንበታል ። ሁለተኛ ባርያ የተባሉት በአንድ ጊዜ አርነት ቢወጡ የሚገቡበት ቤት ወይም ማረፊያ ሊያገኙ ስለማይችሉ መስረቅና መዝረፍ የግድ ይሆንባቸዋል ። ከዚህ የሚከተለውን መናገር አያስፈልግም ። ስለዚህም ምሳሌ እንሆ ራስ ቢትወደድ ተሰማና ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ሲሞቱ ለባሮቻቸው አርነት ሰጥተው ቢሞቱ በመላው በአዲስ አበባ ከተማ ሌባ ብቻ ሁኖ ሕዝቡ ለጥቂት ጊዜ እንደተቸገረ እነዚያም በቅጣትና በረኃብ እንዳለቁ እናውቃለን ።

ሦስተኛ መንግሥት ይህነን ለማስታረቅና አገሩን በጸጥታ ለማኖር ብዙ ችግር እንዲሆንበት አእምሮ ያለው ሰው ሁሉ አይስተውም ። ስለሆነ ግን ከሁሉም ነገር የሚያስፈልገው ከዚህ በላይ እንደተነገረው ፈንጋይን ከአገር ማጥፋት ባርያን ነፃ ለማውጣትና የባርያን ግዞት ከአገር ለማጥፋት ግድ የሆነ ዋና መሠረትነቱን ማንም የሚስተው የለም መንግሥት ግን ፈንጋይን ከአገሩ ለማጥፋት የማይሆንለት ቢሆን መታማትና መነቀፉ የማይቀርለት ነገር መሆኑ የታወቀ ነው ።

ደግሞ መንግሥት ይህነን የባርያ ፍንገላ ለማጥፋት ረዳት የሚሆነው ዋና ነገር ገዢ ከሌለ ሻጭ አይገኝምና የኢትዮጵያ ጐረቤቶች የሆኑትም አገረ ገዢዎች ከኢትዮጵያ

የሚመጣ ባርያ ወደ አገራቸው እንዳይገቡና ከነርሱም ወሰን አልፎ እንዳይሔድ በወሰናቸው ና ባገራቸው እንዲያስጠብቁለት መነጋገርና መስማማት ያስፈልገዋል ። ምስክር ዓይኔ

ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትር የአቆሙት የትምህርት ቤት በሰዳሞ ።

ምንም ይህ ተማሪ ቤት በ፲፱፻፳፩ ዓ ም ኅዳር ፳፩ቀን ቢከፈት ከዚሁ ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ለተማሪ ቤቱ የዕረፍት ጊዜ አልተደረገለትም ነበር ። ምክንያቱም የሀገሩ ልጆች የትምህርትን ጣዕም ስለ አላወቁ በዕረፍቱ ጊዜያት እንደሔዱ እንዳይቀሩ ነው ። ዛሬ ግን የትምህርትን ጣዕም ለአወቁት ይኸው በ፲፱፻፳፬ ዓ ም በመጋቢት ፩ቀን ለተማሪ ቤቱ የመጀመሪያው ዕረፍት እንዲደረግ የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ምኒስትር ክቡር ፊታውራሪ ብሩ ፈቅደው ነበረና ስለዚህ የተማሪ ቤቱ ዲሬክተር ክቡር ሙሴ እግዞፒር ለዋናው እንደራሴ ለክቡር ፊታውራሪ ጥላዬ በዚሁ ቀን መጥተው የተማሪዎቹን አሠለጣጠንና አኳኋን እንዲያዩ ስለ አስታወቋቸው እሳቸውም በተወሰነው ቀን ከመኳንንቱ ጋር በመጡ ጊዜ መጀመሪያ ከበሩ ሲደርሱ ተማሪዎቹ(አክሴር ደላሉን) የሚባለውን የፈረንሳይ መዝሙር በመልክም ድምፅ እዘመሩ በደስታ ተቀበሏቸው ። ከዚህም በኋላ ወዲያው ገብተው በተሰናዳላቸው ስፍራ በተቀመጡ ጊዜ የመጀመሪያው ክፍል ተማሪ ሙሉጌታ ቡሊ የሚባለው ልጅ በፈረንሳይ ቋንቋ የተጻፈውን ዲስኩር አነበበ ። ቀጥሎም በተማሪዎቹ ሁሉ ስም ለብቻው በማርኛ የተጻፈውን የ፫ተኛ ክፍል ተማሪ አመኑ ገብረሐና የሚባለው ልጅ አነበበ ። ቃሉም ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ለክቡር ፊታውራሪ ጥላዬ የኢ መ የጦ ሚ ክቡር ፊታውራሪ ብሩ እንደራሴ ክቡር ሆይ ዛሬ ክቡር ጌታችን ፊታውራሪ ብሩ ለኛ ለወገኖቻቸው ወጣቶች ልጆች ለሕይወታችን መጠቀሚያ ለሀገራችን ልማት እንዲሆን አስበው በገንዘባቸው ያቆሙልን ተማሪ ቤታችን ወደፊት የዕረፍት ጊዜአችን ፪ወር የሚዘጋበት ቀን ስለሆነ በዚሁ ቀን ያስተማሪዎቻችንን ድካምና ትርፍ የኛንም በትምህርት እየተሻሻልን አስተዳደጋችንንና ከሥልጣኔ ደረጃ መድረሳችንን ለማየት ስለመጡ እጅግ እናመሰግንዎታለን ለኛም የሕፃንነታችን ወራት የማይረባንን ነገር በመከተል ከሚያልፍብን ይልቅ በትምህርት መጻመዳችን በጣም የታደልን ነን።ደግሞ ደግ አድራጊያችን ክቡር ፊታውራሪ ብሩ አዲስ አበባ ተቀማጭ ከሆኑ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በንደራሴነትዎ ችሮታ ለተማሪ ቤታችን ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በትምህርታችንም እንዳንሰናከል በትክክል ፈጻሚ ለኛ እንዳባት ጠባቂ ላስተማሪዎቻችንም ረዳት ሁነው በመቈየትዎ ያለ ጥርጥር የጌታዎን መልካም ሐሳብ ተከታይ መሆንዎን ያስረዳናል ለደጉ ንጉሣችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የደስታ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን፤ እንደዚሁ ለሀገራችን የማይረሳ ውለታ ለዋሉላት ለክቡር ፊታውራሪ ብሩ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን፤ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር፤ፊታውራሪ ጥላዬን ያኑርልን ብሎ በጨረሰ ጊዜ ፫ጊዜ ተጨበጨበ።ከዚህም በኋላ የየ፩፩ዱ ክፍል ተማሮች በየተራ እየቀረቡ ሲጠየቁ በሒሳብ በንባብም የፈረንሣዊን ቋንቋን ወደ አማርኛ መተርጐማቸውና በማናቸውም ለተጠየቁት ነገር ሁሉ በቀጥታ መመለሳቸውና አቀለጣጠፉቸው ለተሰበሰቡት መኳንንት ሁሉ የሕፃንነታችን ወራት እንደዛሬ ሁኖ ምነው እንደነዚህ ሕፃናት ተምረን በሆን የሚያሰኝ ነው ይልቁንም ትምህርትን ከጨረሱ በኋላ ይማሩት የነበረውን (አልፋቢ ምርስ) የቴሌግራፍን ሥራ በየቀኑ በየጥቂቱ በትንሽዋ ኤሌትሪክ መኪና ያጠኑትን አስተማሪአቸው ክቡር ሙሴ እግዞፒር መኪናዋን እየተጫጫኑ ሲጠይቋቸው ከማነኛው ነገር ያለ የማይመስለን የቃጭል ድምፅ የፈረንሳይን ቋንቋ ወደ አማርኛ እየዘወሩ እንዲህ ማለቱ ነው ብለው ተርጉመው ሲናገሩ ላያቸውና ለሰማቸው የሚገርምና በጣም የሚያስደንቅ ነው እረ እንደዚህ ያለውን ውለታ ለሀገራቸው ለዋሉ ለክቡር ፊታውራሪ ብሩ ዋጋቸው ምን ያህል ይሆን ከቶ ሊገመት አይቻልም ። ከዚህም በኋላ በትምህርት የቀደሙ ተማሪዎች እያንዳንዳቸው በጽፈት መኪና የጻፉትንና በዓለም ጂዮግራፊ ሁሉ የታተመውን ካርታ እንደሚቻላቸው መጠን በጃቸው የሣሉትን ለክቡር ፊታውራሪ ጥላዬ እያቀረቡ አሳዩ ስለዚህ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ያዩት የተማሪዎቹ ሥራ ሁሉ እጅግ አድርጎ ደስ ስለ አሰኛቸው ከራሳቸው ለተማሪዎቹ እርዳታ መቶ ብር ሰጡ ። ደግሞ ከተማሪዎቹ አንዱ አባቱና እናቱ ርቀው ታርዞ ስለ አገኙት ከጓምጃ ቤታቸው ፪ሙሉ ልብስ እንዲቀበል አዘዙለትና ወዲያውም ላስተማሪዎች ምስጋና የሚሆንና ለተማሪቹ የምክር ቃል ቀጥሎ የተጻፈውን ተናገሩ ። ክቡር ሙሴ እግዞፒር ሆይ በአስተማሪነት ከሚረዱዎ ከቶ አስፋው አብዲና ከቶ ምሥራቅ ተፈሪ ጋራ በመተባበርና በስምምነት ሥራችሁን በጥንቃቄ እየሠራችሁ የልጆችን ዝንጉ መሆንና ጥፋታቸውን ሁሉ ያለ ብሽጭት በመቻል ትምህርታቸውን እያሻሻላችሁ ለንደዚህ ያለ ደረጃ ልጆቹን ስለ አደረሳችኋቸው እኔም እራሴ በጌታዬም ስም ሁኜ ፈጽሜ አመስግናችኋለሁ ። በዚሁም ሥራችሁ በማናቸውም ቢሆን ውለታችሁ እንዳይቀር አምናለሁ ። ፪ተኛ እናንተ ወጣቶች ልጆች ሆይ ባለፈው በሁለቱ ዓመት ውሥ ለተማሪ ቤት የዕረፍት ጊዜያት የነበረውን ክቡር ጌታዬ ተማሪ ቤቱ የተዘጋ እንደሆነ ልጆቹ የትምህርትን ጥቅም ስለአላወቁና ስለ አለመዱት በየዘመዶቻቸው ቤት እንደሔዱ ይቀሩና እንደመጀመሪያው ጊዜ መሰብሰብ ይሆንብናል ብለው ላስተማሪዎቹ ስለ አስታወቋቸው እነሱም የጌታዬን ፈቃድ ተቀብለው እስታሁን ፪ዓመት ዕረፍት አልተደረገም ነበር አሁን ግን ይኸው የዕረፍቱ ጊዜያት ስለተቈረጠ እናንተንም በዚሁ ቀን መጥቼ ባያችሁ በትምህርት አቀዳደማችሁና ሥልጣኔአችሁ በጣም ደስ ብሎኛል እንግዲህ የትምህርት ጥቅምንና ትርፉን ስለ አገኛችሁ ለወደፊት በተቈረጠው ቀን የጀመራችሁትን ትምህርት በመናፈቅ ተመልሳችሁ ተግታችሁ እንድትማሩና የሚበቃችሁን ትምህርት አግኝታችሁ የጌታዬን ውለታ መላሽና መንግሥታችንን ወዳጆች አገራችንን ረዳቶችና ጠቃሚዎች እንድትሆኑ እመክራችኋለሁ እንዲሁም ለናንተ በትምህርት ለቀደማችሁ ልጆች ከጌታዬ ሽልማታችሁን አላስቀርባችሁም እግዚአብሔር ልቡናችሁን ብሩሃን አድርጎ የጀመራችኋትን መልካሟን ትምህርት

ለመፈጸም ያብቃችሁ ብለው በደስታ ተሰነባብተው ሔዱ ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ከዚህ በላይ በተጻፈው ሁሉ ለሰውነቱ የተሰማኝን በምሳሌ አገልጽ ዘንድ ስለ ፈቀድሁ ባለመሰልቸት ትመለከቱልኝ ዘንድ እለምናለሁ ። ፩ብርቱ ብልህ ሰው ነበር የሚኖርበት አገሩ የሰጪትን ፍሬ ሁሉ የምታበቅል ሁና በወኃ ምክንያት እንደተሰናከለች ያውቅ ነበረና ያሰው ካሩቅ አገር ከትልቅ ድረት በብዙ ኪሣራና ድካም ወኃ መልሶ ባገሩ አጕረፈበት ባለው ዓቅሙ እሱ ብቻ ይጥራል እንጂ ግን ያልታደሉ የሃገሩ ሰዎች በዚህ ወሀ አትክልት ተክለን ከፍሬው እንመገባለን የሚል አንድ ሰው አልነበረም እንዲያውም ሳፅዱ ሰውነት የታጠቡበት እንደሆነ ያነጣል እሉ እያሉ የተለየ ወሬአቸውን እያወሩ ሲጕርፍ እንደዘርቅ ያዩት ነበረ ተመልሰውም ያንኑ ዱሮ የተጠራቀመ የቈሬ ወሀ (ሚክሮባቸውን)ይጠጣሉ በዚህ ተደንቄ ስኖር ሳለሁ እንደዚሁ የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ሚኒስትር ክቡር ፊታውራሪ ብሩ ለሀገራቸው ልማትና ስፋት ሲሉ በብዙ ኪሣራና ድካም የውጭ አገር ጥበብና እውቀት (ቋንቋ)የሚያስተምሩ የርከፍል አስተማሪዎች ቀጥረው ፪ተኛም እነዚሁ ተማሪዎች በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተሰብከው እንዲያድጉ ከተማሪ ቤቱ የማይለዩ ግዕዝና አማርኛ የሚያስተምሩ ፪መምህራን ቀጥረው የእውቀትና የጥበብ ትምህርት ይጕርፋል ነገር ግን የሃገሩ ሰዎች ራሳቸው ብርቱና ብሉያት ስላሆኑ የስንፍና ወሬአቸውን እያወሩ ልጆቻቸውን ወደዚሁ ተማሪ ቤት የሚያስገድዱና ያዘነበሉ እጅግም አላየሁ ስለዚህ ለወላጆቻቸው የግዴታ አዋጅ ያስፈልግ ይመስለኛል ። በነዚህ በጥቂቶቹ ከ፪ንመት ወዲህ በሠለጠኑት ወጣቶች ፍቅር ተነድፌ ብዛታቸውን በመናፈቅ ደፍሬ ጽፌአለሁና ይቅርታችሁን እለምናለሁ ።

ተመልካች አድማሱ ወልደ ሥላሴ

ስለ ወይዘሮ ብዙነሽ ገብረ ሕይወት ሞት ።

ወይዘሮ ብዙነሽ የፊታውራሪ ማህሉ ባለቤት የራስ ገብረ ሕይወት ሚካኤል ልጅ የንጉሥ ሚካኤል የልጅ ልጅ እጅግ የተዋቡ መልከ መልካም በጠባያቸውና በሙያቸው የተመሰገኑ ነበሩ በሳል ሕማም ምክንያት ብዙ ጊዜ ታመው ቈይተው በሚያዝያ ፱ቀን ሙተው እኅታቸው እቴጌ መነን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን የቀሩትም ቤተዘመዶቻቸው ሁሉ አልቅሰውላቸው ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ወይዛዝር ተሰብስበው ታላቅ ኀዘን ተደርጎላቸው የኀዘን ጥሩምባና እምቢልታ መለከት ድምፅ ልብ እያቃለለ በብዙ ክብር በአዲስ አበባ መድኀኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ዕድሜአቸውም ፴፪ ዓመት ነው ።

ብርሃንና ሰላም ኀዘንተኞችን ሁሉ እግዚአብብሔር ያጽናችሁ እያለ ኀዘኑን ይገልጻል ።

ስለ አቶ በጋለ ሠርፁ ዕረፍት ።

አቶ በጋለ ሠርፀ አገራቸው ጕንደር ከተማ ልደታ ነበር በልጅነታቸው መጥተው በንግድ ሥራ ተመችቶአቸው ይኖሩ ነበር መቸም ይህ ዓለም ወደመጨረሻው ለጥቂቶች ሰዎች በቀር በብዙዎቹ ሰዎች ዘንድ እያምርምና በምኑም በምኑም ምክንያት ኑሮአቸው ተሰናኝሎባቸው ነገር በዝቶባቸው ነበር ይልቁንም በመዋስ ምክንያት ሙግት በዝቶባቸው ብዙ ጊዜ በሙግት ብዛት ኀዘንና ብስጭት በዝቶባቸው ሲኖሩ እንደልማዳቸው ለሙግት ወደ ማዘጋጃቤት ሔደው ፫ሰዓት ሲሆን ወደቤታቸው ተመልሰው እንደ እውከታ አድርጎ አሟቸው እኩል ሰዓት ያህል ቈይተው በሚያዝያ ፯ቀን ሙተው በነጋው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ።

ዕድሜአቸውም ፷፪ ዓመት ነው መከረኛይቱን ሴት ባለ ቤታቸውን ወይዘሮ ላቀችንና ልጆቻቸውን እግዚአብሔር ያጥናቸው ።

(እጅግ የሚያምር የጋብቻ ኑሮና የሚያሳዝን ሞት)

ክብርት እናቴ ወይዘሮ ዓፀደ ማርያምን ያባቴ ያለቃ ደስታን ባለቤት የሕይወታቸውን ታሪክ ትንሽ እጽፋለሁና ቃልም ቢረዝምብኝ ነገርም ባላስተካክል ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎችን ይቅርታ እለምናለሁ ።

ወይዘሮ ዓፀደ ማርያም በአባታቸው ባቶ ወንድማገኘሁ መንዝ ጌራ የአቶ ሰማኝ የልጅ ልጅ የወይዘሮ አቻሜለሽ የልጅ ልጅ ናቸው በናታቸው ቡልጋ ከፈልቱ ዘአንቅዓ ወልዳ የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አቅኚዎች የመምህር ዓርከ ኢየሱስ የመምህር ወልደ ኪሮስ የመምህር ዓምዱ የመምህር ገብረሕይወት የልጅ ልጅ የወይዘሮ ብርቄ ልጅ ናቸው ወይዘሮ ብርቄ ከናታቸው ጋራ ተቡልጋ በጋብቻ ምክንያት ምንጃር መጥተው ሰቀላ ሲኖሩ ያቶ ወንድማገኘሁ እናት በርስት የተነሣ ከዘመዶቻቸው ተጣልተው ተመንዝ ምንጃር መጥተው ይኖሩ ነበር አቶ ወንድማገኘሁ ወይዘሮ ብርቄን አግብተው በክራቸውን ወይዘሮ ሙላቷን በ፲፰፻፷፪ ዓ ም ወለዱ ደግም በ፲፰፻፸፱ ዓም መጋቢት ፱ ቀን ወይዘሮ ዓፀደ ማርያምን ወለዱ አቶ ወንድማገኘሁ በወታደርነት ሐረር አውራጃ ጊሬ ሲኖሩ በ፲፰፻፹፪ ዓ ም ዐረፉ ወይዘሮ ብርቄም መሐመድ ጣሒርን ክርስትም አግብተው ሲኖሩ ልጃቸውን ወይዘሮ ዓፀደ ማርያምን ለደባው ላቶ ይጥና አባየሉስ ልጅ ላቶ አበጀ ዳሩ ወይዘሮ ዓፀደ ማርያም በ፲፰፻፺፪ ዓ ም አስፋው አበጀን ወለዱና አቶ አበጀ በ፲፱፻፮ ዓ ም በነሐሴ ፳፬ ቀን ስላረፉ ቡብርቱ ኀዘን ተቀምጠው አባቴ አለቃ ደስታ ወላጅ እናቱ ወይዘሮ ዠርማነሽ አስታጥቀ በ፲፱፻፪ ዓ ም እኔ የሦስት ዓመት ልጅ ሁኜ ጥለውባቸው ነበርና ፲፱፻፫ ዓ ም ዘመድ ወዳጃቸው መክሮ ኀዘንዋም መከራዋም እንዳንተው የሆነ ልጅህን (ምታሳድግልህ የታመነች ግብረ መልካም ሴት አግኝተንልሃል ብለው በቃል ኪዳን አጋቧቸው የጋብቻውም ኑሮ በፍቅር በሃይማኖት የተስማሙ እጅግ የሚያምር የሚያስቀና ነበር (መቸም ነበር ነው) እኔንም

ብመልከም አድርገው እያስተማሩ እስከዚህ ዕድሜዬ ድረስ አሳደጉኝ እናቴ ወይዘሮ ዓፀደ ማርያም ከባእቴ ከተጋቡ እስከ ፳፩ ዓመት ድረስ ፲፩ ወለዱ ፭ሲሞቱባቸው አሁን ፬ ወንዶች ፪ሴቶች አሉ ከነዲቱ ሴት ልጅ በቀር ፫ቱ ራስ በራስ (ከ፩ ዓመት ልጅ እስከ ፲፫ ዓመት ልጅ ድረስ ናቸው)ይህ በጣም የሚያሳዝን ነው ።

ከዚህ በኋላ አባቴ ወደ ውጪ አገር ተልከው ቢሔዱ ፍጹም ጤና የላቸውምና በጃኅና አይመለሱም በማለት እጅግ አድርገው አዝነው ሳሉ ወዲያው እንደምታት አድርጎ አሟቸው ሰነበተና ያስላቸው ጀመር ሳሉም ለጊዜው ብሮንሺት ነበር በኋላ ግን ቲቤርኪሎዝ ሆነ ፩ወር ድሬ ደዋ ታክመ ፫ሐኪሞች ፯ ወር ከደከሙላቸው በኋላ የፍጥረት ሁሉ ሕይወት በእጁ የሆነ የሐኪሞቹ ሁሉ በላይ ታላቁ ሐኪም ጠርቷቸዋልና በማናቸውም ብልሃት እሳቸውን ለማስቀረት አልተቻለም።ከዚህ በኋላ ፲፱፻፳፬ ዓ ም መጋቢት ፪ ቀን በተወለዱበት ቀን በ፵፫ ዓመታቸው አባቴን ባገቡ በ፳፩ ዓመት ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር አደራ ሰጥተው ከዚህ ዓለም ድካም ዐረፉ ።

እጅግ የሚያሳዝነው የልጆቹ ትንንሽነት አባቴስ በስተ ሽምግልና በ፷፯ ዓመታቸው እንዲህ ያለው ከባድ ኃዘን ሲጫናቸው እንዴት ይችሉታል አዬ በዚህ ቀን አባቴን ያየ ሰው ጋብቻም አያስመኝ እናቴ አሳዳጊዬ እግዚአብሔርን ፈሪ ሕጋቸውን አጥባቂ ባላቸውን አክባሪ በጠቅላላው በጎ ሥራ ለመሥራት ብርቱ ነበሩ ።

እናቴ ሆይ ሰላም ከነፍስዎ ጋራ ።

ከዚህ ቀጥዬ አባቴ ያንጐራጐሩትን የትኩስ እንባቸውን ተከታይ እጽፋለሁ አንገቴን በላሽው አንገቴን በላሽው እነማለሁ ስትይ ወድቀሽ የቀረሽው።

እንደ ሰማዕታት የበዛነው ገድልሽ።በ፱ሰዓት ዓርብ የሆነው ዕረፍትሽ።ከማኮደሉ በቀር ሞትሽ ለማን ቤዛ የሚሆን መሰለሽ። ለኔም ለልጆቹም ተስፋ ሕይወት ነበርሽ። ደግሞ እንደ መላእክት የረቀቀው ግብርሽ በሞትሽ ታወቀ የሰው ልጅነትሽ። ይህ አይቀርምና ከአዳም ተወልደሽ። ስንታገል ነበር ከጧት እስከማታ።ሲመሽ ጥላኝ ሔደች መዳከሜን አይታ፡ምነው ወዳጄ ሆይ እንደዚህ አድርገሽ ጣልሽኝ ። ሲመሽ በጨለማ ማን አይቶ ሊያነሣኝ።ተረዳችውና ድካሜን በውነት ። ቁልፏን ይዛው ሔደች የኑሮዬን ብልሃት። በወላድነቷ ሰነፍ ስትመስለኝ።ከልጆቿ ጋራ አንድ አርጋ ጣለችኝ።

ሚስቱ ናት ይላሉ የማያውቋት ሰዎች ። ዓፀደ ማርያም የባል እንጀራ ነች ። በወሩ ባመቱ ሥራ የሌለበት ። ዓፀደ ማርያም ባል አክባሪ በውነት ። አትፍታት ይሉኛል እሰዋ ጠልቃ ባሳር ። ወዴት ተስማምተን በኑሮስ በነገር።እኔ የከተማ እበዋ የባላገር ። ለምለሚቱ ዓፀደ እርጥቧ ታጨደች ። የባላገር እሸት እዝመራ ነበረች።እንደማያጉድል ሥራ እንደሌለበት ያን መልከሙን ጣቷን አጠንክሬ አሠርሁት ። ወስዶ እንደሚመልስ ለመሬት ሰጠኋት።አንገቴን በላሽው አንገቴን በላሽው እነማለሁ ስትይ ወድቀሽ የቀረሽው ።

ከሁለት መልክክም እናት አንድ ያጣሁት ጥ ደ ።

በለ አቶ ተክለ ሚካኤል ሞት ።

አቶ ተክለሚካኤል አገራቸው ሐማሴን ነበረ ። ከሀገራቸው በወንጌላዊት ሚስዮን ፈቃድ ተልከው ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከዚሁም በፈቃድ ተሰናብተው በአገራቸው በኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ ሥራ ይዘው ብዙ ጊዜ ቈይተው ነበር ። ጠባያቸው እጅግ መልካም ፍቅር አዋቂ እንግዳ ተቀባይ ነበሩ።በትምህርታቸውም እጅግ የተመሰገኑ ነበሩ ። ብዙ ጊዜ ታመው ዳኑ ብለን ተስፋ ታደረግን በኋላ እንደ ገና ታመው በሁለተኛ ቀናቸው በኤተ ማይዳ ሆፒታል በሚያዝያ ፲፩ቀን ሙተው እንደሮፓ ሕግ አድረው በነጋው በሚያዝያ ፲፪ቀን በጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበሩ።ባመቃብራቸውም ከወይዛዝርና ከመኳንንት ብዙ ሰዎች ነበሩ ።የሚአውቃቸው ሕዝብ ሁሉ እጅግ አዘነላቸው ዕድሜአቸውም ፵፫ዓመት ነው።ባለቤታቸውን ወይዘሮ ኤልሳቤጥንና ልጃቸውን ዘመድ ወዳጆቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክቶር ጄ ኤ ማርቲኒ በፓሪስ ዩኒቬርሲቲ የተመሰከረላቸው።በዚሁ መታከሚያ ቤት የሴት በሽታ የልጆች በሽታ፤ የዓይን በሽታ፤ የጆሮ በሽታ፤ የጕሮሮ በሽታ ቂጥኝ ይህነን የመሰለውን ሁሉ በደኅና ያክማሉ። ቤታቸውም አራዳ ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ሱቅ ነው የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ጧት ከአራት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ነው ። ፱ተኩል እስከ ፲፩ ሰዓት ያክማሉ ዶክቶር ጄ ኤ ማርቲኒ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማከዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ክንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ካ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንጻ የመጀመሪያው ነው ።

ማስ|ታ ወቂ ያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት ኦ ጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ.

የስፌት መኪና ኩምፓንያ ሴንጀር በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ብለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ሰጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ኒ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ባናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

ባለነጭፈረስዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም
ALEM

ባያይነቱ፡ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ፤ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አበካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም የአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ፡

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,



COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀቅ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፲፰
8me ANNE № 18

ሐሙስ ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
JEUDI 28 AVRIL 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረሰተኑ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የመጨረሻ ፍርድ ቀን

ከማ ብሩ የሚባል ዕድሜው ገና የሐያ ስምንት ዓመት የሚሆን ገና ወጣት ጕበዝ ፳፯ዓመት ያህል በትሪፖሊ ለወታደርነት ተቀጥሮ ሔዶ ሲኖር ነበረ። ከዚያ ተመልሶ ወደ አገሩ በጌምድር በፋርጣ ውስጥ ስምና በሚባል አገር ሲኖር በአለመታደሉ ሐሳቡ ወደ ክፋት ተለውጦ ወምበዴ ሁኖ ወደ ዱር ገብቶ ከወንድሙና ከባልንጀሮቹ ጋራ አገር አስቸግሮ ሲኖር ፩ቀን አቶ አልጣህ የሚባለውን ሰው ገድለው ጠመንጃውን ሊነጥቁ ተመካክረው የቤቱን አጥር ከበው ተኰሱበት። ባለቤቱ አቶ አልጣህም ቢተኵስ የከማ ብሩን ታናሽ ወንድም ገደለው። ወምበዴዎችም ቢተኵሱ አቶ አልጣህን የማያገኙት ቢሆን ራቅ ካለ የሚኖሩ መልካም ቄስ ወንድም ነበሩትና በፍልሰታ ጾም ሱባዔ አድርገው ከመቃብርቤት ሰንብተው ሌሊት ሲደወል ለጸሎት ወደ ቤተክርስቲያን ሲሔዱ ከቤተ ክርስቲያን በር ላይ ገደሏቸው። የአባታቸውን መሞት ሰምተው ሁለቱ ሴቶች ልጆቻቸው ቢመጡ ታላቂቱን እርጉዚቱን ልጃቸውን ተኵሶ ገደላት ታናሺቱን ገና ለጋብቻ የታጨችቱን ልጅ ተኵሶ ክንዷን ሰበራት። ከዚህ በኋላ እንደ ልማዱ ወደ በረሃ ገብቶ ብትታረቁኝ ታረቁኝ ካልታረቃችሁኝ ሁላችሁንም አፈጃችኋለሁ እያለ ቢልክ ፈራራቸው እሺ እንታረቃለን ብለው ላኩበት ከዚህ በኋላ ወደ አለበት ዱር ሔዱና ሺማግሎችም እየተንቀጠቀጡ ታራቂዎችም እየአማጡ ጌታው ከማ ብሩ አቶ አልጣህ ወንድምህን ቢገድለው አንተም ወንድሙን ገድለሃል የሁለቱ ደም ተከፋፈለ ማለት ነው። በትርፍ ለገደልሃት ለርጉዚቱ ሴት ሰማንያ ብር ክስ ብለውት የሟቾቹም ወገኖች ፈርተዋልና እሺ ብለው ከሰማንያው ብር ፴ውን ብር ለእናቲቱ ሰጥቶ ቆይቶ በኋላ አንቺ የእኔን ገንዘብ ወስደሽ ልታቀሪ ነውን ብሎ አምጪ ብሎ መቸም ለጊዜው ገዢ ነበርና አንድ ቄስ ቢልክ ጥንቱንም ገንዘቡን መቀበልዋ ፈርታ ነው እንጂ በአማራ አገር የደም ዋጋ ተቀብሎ መብላት ነውር ስለሆነ በጥንቃቄ አስቀምጣው ነበርና እሺ ብላ መለሰችለት ከዚህ በኋላ አገር ጠልቷቸዋልና አንዳንድ እያለ ባልንጀሮቹን የአገሩ ሰው ፈጃቸው ከማ ብሩም ብቻውን ስለ ቀረ ፈራና እርቅ ፍለጋ ጀመረ። ፩ቀንም ፩ካህናት ይዞ ሔዶ እሹሙ ቤት ለእርቅ ወደ ሹሙ ቤት ገባ ሹሙም ጥንቱንም እርቅ አልፈለገምና እጁን አሲዞ ደመኞቹን ጠርቶ ትቈረጡ እንደሆነ ደመኛችሁ ይኸውላችሁ አላቸው፡ወዲያው ወደ ዋናው ገዢ ወደ ደጃዝማች ወንድ በወሰን ችሎት ቀርበው የተነጋገሩበትን የመዝገብ ግልባጭ ጨምረው ወደ አዲስ አበባ ሰደዋቸው በሚያዝያ ፲፬ ቀን በጃንሆይ ችሎት ቀርበው እርቅ አለኝ ብሎ ስለተከራከረ የሚበልጠው ክፍል እርቅህ ድርድር ነው እንጂ የተፈጸመ እርቅ አይደለምና ትሞታለህ ብሎ ፈረደ። ጥቂቶችም ሰዎች እርቁ ይፈጸምለታል እንጂ አያስሞተውም ብለው ፈረዱ። ከዚህ በኋላ ወደ ፍትሐነገሥቱ ሲደርስ በአለ ፍትሐነገሥቱ ሊቁ ገብረክርስቶስ አስተዋይ ሊቅ ናቸውና ይደርልኝ ስላሉ ለሰኞ ተቀጥሮ በዚያው በተቀጠረው ቀን በጃንሆይ ችሎት ቀርቦ ይሙት በቃ ተብሎ በፍትሐነገሥት ተፈርዶበት ሲወጣ የናቱን ኀዘንና ጭንቀት ያየ ሰው ወንድ ልጅ መውለድ አይመኝም።ቀርበንም አገርዋን ብንጠይቃት እኔ የሸዋ ሰው ነኝ እነ ቀኛዝማች ክፍለው እነ ቀኛዝማች ናቄ ዘመዶቼ ነበሩ የበጌምድር ሰው አግብቼ ብዙ ልጆች ወልጄ ስኖር በሁለቱ ልጆች እንዲህ ያለ ክፉ አሳብ አሳድሮባቸው ፩በፊት ሞተ ይህ ደግሞ ይኸው ተፈረደበት እያለች ከዚህ በኋላ የንባዋ ጕርፍ ለመናገር ከለከላት ልጅዋም በዚሁ ቀን ተደበደበ።ሰውን ሰው መግደሉ በዓለም ሁሉ የሚደረግ ነው። ነገር ግን እንደ በጌምድር የሚሆን የለም ።

ምኞት

በበጌምድር በሬውን ሺጦ ጠመንጃ የማይገዛ ሰው ከወንድ አይቈጠርም። ስለ ዚህም ሁሉ በእለ ጠመንጃ ነውና በምኑ በምኑ ሲጣላ እንደተጋደለ ይኖራል ለዚህ መድኃኒቱ ከዘበኛ በቀር ማንም ሰው ጠመንጃ እንዳይዝ በጽኑ አዋጅ መከልከል የገዛውንም ጠመንጃ ተቀብሎ ዋጋውን እየከፈሉ ማስቀመጥና በሚአስፈልግ ጊዜ መስጠት ነበር። ይህን ደምብ በባላገር ጀምሮ መልካም ቢሆን በከተማውም ማድረግ ይሻል የመሰለውን ምኞት ብርሃንና ሰላም ለመንግሥት አማካሪዎች ያቀርባል ።

ከመሥዋዕት መታዘዝ ይበልጣል ።

አይሙት ኪዱ የሚባል የዋጅራት ሰው በወምበዴነቱ አገር የሚአስቸግር እጅግ ጨካኝ ሰው በልዑል ራስ ጉግሣ አር-

እያ ግዛት ክፍል የነበረ በዚሁ ጥፋቱ ታሥሮ ወደ አዲስአበባ መጥቶ ከታሠረበት ቤት አምልጦ ሒዶ እዚያው አገሩ ገብቶ ነበር።ጃንሆይ ደጃዝማች ከበደ ኀንጐልን ጠርተው ይህን አገር የሚያስቸግር ሰው ከሔደበት ቦታ አስፈልገህ በሰውም አገር ቢኖር አሲዘህ አምጣ ብለው አዝዘዋቸው ደጃዝማች ከበደ ኀንጐልም ዕለቱን ወደ ሹማምቶቻቸው በጃንሆይ ቃል የጠነከረ ትእዛዛቸውን አሳልፈው ነበርና በደጃዝማች ቃል ብርታትና በሹማምቶቻቸው ትጋት በመጋቢት ፲፰ ቀን አጋምቴ ከሚባል አገር ተያዘ ብለው አሽከሮቻቸው የስልክ ቃል ቢአሳልፉላቸው ደጃዝማችም ወዲያው ሒደው የምስራቹን ለጃንሆይ ቢነግሩ ደጃዝማች ከበደ ኀንጐልን ጃንሆይ እጅግ አመሰገኑዋቸው።ክፉን መያዝ ለሀገር ደኅንነት መስጠት ነውና በሀገሩ ሕዝብና በመንገደኞች ስም ሁኖ ብርሃንና ሰላም ለደጃዝማች ከበደ ኀንጐል ምስጋናውን ያቀርባል የሀገር ገዥ ሁና ደህን ምስጋና መቀበል ታላቅ ዕድል ነው ።

ነገር በዋና ዘሬን በገና፥ ባለነገር ከቤት ጠበቃከዱለት የተላከ ካቶ የተፈጥሮ እውቀት ።

ይድረስ ከክቡር ልጄ ወዳጄ አቶ አሸኔ ወልደ ዮሐንስ ልጄ ሆይ የኔ ጥቃት አሳዝኖህ ስለረዳኸኝ በብዙህ አመሰግንሃለሁ ። ነገር ግን ጡቺም የባለጋራዎቼን ብዛት ተመልክተኸዋል ይልቁንም ባለጋራዎቼ ከውጭ የመጡ አይደሉም ከኔው ውሥጥ የወጡ ናቸውና ምሥጢሬን ሁሉ ያውቃሉ ። ለቄጠርኋቸውም ምስክሮች ምክንያት ሳይፈልጉብኝ አይቀሩም ለኔም ያላደረግሁትን አድርጌአለሁ ማለት ብርቱ ነውሬ ነውና አንተ በመለከትህልኝ ማመልከቻ ውሥጥ ቃሌ አይደለም የምለውንነገር በምሥጢር ላመለክትህ እወድአለሁ ። ፩ኛ ከአዳም ጋር የተፈጠርሁ ነኝ ላማለት ትንሽ ያሳፍረኛል ብናገርም መጽሐፍ ቅዱስን ያህል ምስክር አለብኝና አይሆንም ። ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፪ ቍ ፱። ፲፮ ፲፯ ፳፫ ።ምዕራ ፫ ቍጥር ፩ እስከ ፳፬ ያለውን ተመልከት፥ የኔ ተፈጥሮ ከዚህ ይገኛል ።

፪ኛ ለአብርሃም የጣዖትን ከንቱነት የነገርሁ አንተ እንዳልኸው እኔ ነኝ ። ለኢሳይያስም እንደዚሁ ነግሬጽፎታልና ባ፵፬ ምዕራፍ ከ፱ቁጥር እስከ ፳ ቍጥር ተመልከት ። ፫ኛ ዮሐንስ በማኅፀን ሳለ ለፈጣሪው እንዲሰግድ ያደረግሁ እኔ ነኝ ብዬ ነበር ። ነገር ግን በዚሁ ነገር ብዙ ጠብ ተነሥቶ ሊቃውንቱ ሁሉ ጣማሾቹ ወደኔ ሁነው ተከራክረው ነገሩ በጌታ ትእምራት ይሁን ተብሎ የኔ ወገኖች ተረትተው እኔንም ደግመኛ ይህነን ነገር አታንሣ ይኸግ ያረፈ ሰይጣን መቀስቀስ አይደለምን ከዚህቀድሞ ከበለስ ስር ተቀምጠህ የሠራኸውን ሥራ ታውቀዋለህ ብለውኛ ትቼውአለሁ ባለቅኔም እንዲህ ብሎ ሰድቦኛል የዋሃ፣ ለአስሕቶ ነቢየ ሐሰት እእምሮ መምህረ የዋሂት ነፍስ፥መሀርከዎ ትቤ ለዮሐንስ በከርሥ።ወምንተ ትብል በይነ ጢስ ዕጣን ዮቡስ፤እስመ ኅበ ሀለወ ሀየ መስቀለ ክርስቶስ፥ እንፈርዓፀ ወሰገደ ጢስ ብሎኛል ፬ኛ፥ ስለ ቅዱስ ያሬድ ነገር የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደሚሉት እንደዚሁ የትእምራት ይመስላል እንጂ ለኔ ምኔም አይደል ነገር ግን የነገሩ እውነተኛ ብላቴን ጌታ ኅሩይ የሕይወት ታሪክ ሲጽፉ እንደጻፉት ሳይሆን አይቀርም ። ልጄ ሆይ ይኸንን ሁሉ ያሳሰበኝ ያላንተ በስተቀር እውነተኛውን ነገር የሚያስብልኝ ስላጣሁ ነው እንግዲያውማ ተምረናል የሚሉን ሰዎች በትምህርት እኩል ከሚዴክሙ ባልደረቦቻቸው የኔ ልጆች በመሆናቸው በልጠው የብዙውን ዓመት ትምህርት በጥቂት ዘመን ጨርሰው በመውጣታቸው ሙለታዬን ባላወቁትም ነበር። ነገር ግን እንዚህን የትምህርት እውቀት ይበልጣል የተፈጥሮ ዕውቀት ያንሳል ብለው ተናግረው አናጋሪዎች ልኩን እነግራቸው ነበር ዳሩ ግን ያምራል ብሎ ከመናገር ይከፋል ብሎ መተው ብዬ ያስተማርሁ እኔ ነኝና አይገባም ።

የተፈጥሮ እውቀት ሥራ ጸሐፊ ተገኘ የተሻ ወርቅ ።

መርምሮ መፍረድ ለሀገር ጥቅም ነው ።

የነጋዴዎች ችግር መመርመሪያ ቤት ሹም አቶ ለማ ወልደ ገብርኤል ለደኞች ያደረጉትን የቀና ፍርድ የማይታለፍ ስለሆነ ከዚህ በታች ልጽፈው ጀመርሁ ።

ሚያዝያ ፰ ቀን በስድስት ሰዓት ወደገበያ ሒጄ ዕቃ ለመግዛት ወደ አንድ ፈረንጅ ቤት ገብሁ ወደዚያው ከባላገር የመጡ ሰዎች ከአቶ ለማ ወልደ ገብርኤል ፊት ቁመው አቤት ተበደልን ንጉሠ ነገሥቱ መርጦ የነጋዴዎችን ችግር እንዲመረምሩ አዝዘዎታልና ይህ ፈረንጅ በማይገባ በሥር ብር የሚሸጠውን በሐያ ብር ስለሸጠልን ይህን ግፋችንን አይተው ብራችንን ያስመልሱልን እያሉ ቢአመለከቷቸው እሳቸውም አንተ ሽጠህላቸው የለምን ብለው ፈረንጁን ቢጠይቁት አልሸጥሁም አለና እየተቈጣ ችክችክ አይፈልጉም እኛ እይዋሹም እያለ ያጉረመርም ጀመር አቶ ለማ ግን በትዕግሥት ሁነው እምቢ ካሉ አሽከሮችዎ ይያዙ ስለርስዎም ወደቆንሲልዎ እናስታውቃለን ብለው አስጨንቀው ቢይዙት ያነን ሐያ ብር ቈጥሮ ሰጣቸው ። አቶ ለማም ተቀብለው ለደኞቹ ሰጧቸው በጣም ይገርማል ደኃ ተበድሎ እንዲህ ያለውን ፍርድ ማግኘቱ ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እያሉ ጃንሆይን እያመሰገኑና አቶ ለማንም ይህን መልካም አድራጎት ስላደረጉላቸው እየመረቁ ሔዱ። እኔም ይህን መጻፌ ነገሩ ደግ ስለሆነ የማይታለፍ ነውና የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እንድትመለከቱት ነው ።

ከተመልካቾች አንዱ የማተሚያ ቤት ሠራተኛ ብርሃኑ ገላጋሌ ።

ዓረፋ

ዓረፋ ማለት አወቀ ማለት ነው ዓረፋም የተባለበት እንደ ዓረብ ታሪክ አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን በገነት ሲኖሩ በደይነቱ የዛፍን ፍሬሁሉ ፈቅዶላቸው ከሁለት ዛፎች ብቻ አትብሉ ብሎ አምላክከለከላቸው ያምላክን ቃል ጥሰው ከተከለከሉት ዛፎች ስለበሉ ተገነት አወጣቸው ፥ከወጡም በኋላ ተለያይተው ሲኖሩ በዓረብ ቋንቋ ጆበል ዓረፋት በኛ በኢትዮጵያ ቋንቋ ደብረ ፋራን በሚባለው ቦታ ተገናኝተው ስለተዋወቁ ዓረፋ ተባለ ይህም ቦታ መካ ለሚባል አገር ቅርብ ነው በዓረብ ዝልሕጃ

በሚባለው ወር በዘጠነኛው ቀን ጀበል ዓረፋት (ደብረ ፋራን) በሚባል ቦታ ላይ በሰዓት ፩ጊዜ እዚያ ብዙ ሕዝብ እየተሰበሰበ ይጸልያሉ ።

ይኸም በቀድሞ ዘመን የነበሩ አባቶቻችን ለስማቸውና ለትውልዳቸው መታሰቢያ እንዲሆን ያምላክ፥ ቃል መሰረት አድርገው ይህን ቀን ያከብራሉ። ዘፍ ምዕ ፳፩ ቍ ፩ እስከ ፳ ተመልከት።ደብረ ፋራንም የተባለበት ምክንያቱ የዓማሌቃውያን ንጉሥታት መሬቱ፥ ሲአድሉ ለንጉሥ ፋራን ስለደረሰ መሬቱም በፋራን ስም ተጠራ በላዩ እንደተጻፈው እስላም የሆነ ወገን ሁሉ ከተቻለው በዕድሜው ፩ጊዜ ጀበል ዓረፋት ሒዶ በዘጠነኛው ቀን እዚያው መገኘት አለበት ያንቀን እዚያው የተገኘ ሰው ሖጂ ይባላል እዚያ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ይጸልያል ሚክያስ ምዕ ፬ ቍ ፩ና ፪ ተመልከት።በዚሁ ወር በ፲ኛው ቀን ዒዱል አድሐ ወይም ዒድ አነህር ይባላል ይህም ቀንበጣም ክቡር ነው እስላም ባለበት አገር ሁሉ የዚያን ቀን ከጥዋቱ በ፫ሰዓት ተሰብስበው ይጸልያሉ ከዚያ ሲመለሱ ፩አንድ በግ አርደው ለድሃ ይሰጣሉ ይህም መሆኑ አባታችን አብርሃም ፩ልጁን ለመሥዋዕት አቅርቦ በልጁ ፋንታ መላኩ ታምላክ ዘንድ በግ ተለውጦለት አምጥቶ አብርሃም በጉን እንዳረደ እስላሞቹም ይኸን መታሰቢያ አድርገው ያርዳሉ የአብርሃም ልጆች እስማኤልና ይስሐቅ ፪ቱም የተባረኩ ናቸው ዘፍ ምዕ ፲፯ ቍ ፲፰ ፳፩ ተመልከት።የቀረውን የታሪክ አከታተል ወደፊትእጽፋለሁ በኢትዮጵያም ያሉት እስላሞች ከዚህ ፊት እንደ ተለመደው መድፍ እያስተኰሱ ይህን በዓል ያከብራሉ መድፍ ሲተኰስ የኢትዮጵያ መንግሥት ዘላለም በሰላም ባዲስ ይኑር። የግርማዊ የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴን የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት ዕድሜ ከነ ዘመዳቸውና ከነቤተ ሰቡ ያርዝምልን የደስታ ዘውድ ስለሰጣቸው በየዓመቱ ደስታቸው እየታደሰ ይኑሩ፤ኢትዮጵያ ከነልጆቿ ዘለዓለም ትኑር ንጉሥዋ ሕያው ይሁን እያሉ ወደ አምላክ ይለምናሉ በዓላቸውም ሚያዝያ ፰ቀንና ፱ ቀን ነው ።

ሐ ዓ አ ሸሪፍ አፈንዲ

የምሳሌ ፍርድ ማመልከቻ ።

በ፲፱፻፳፬ ዓ ም መጋቢት ፳፬ቀን በታተመው በ፳ተኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም በ፲፬ቍጥር በ፻፳ገጽ ስለ መልከሚቱ ቆንጆ ባልንት ከ፫ቱ ብልሆች ጐልማሶች ማናቸው ሊያገቧት እንዲገባ ፍርድዎን ይስጡ ብሎ አቶ ትስብእተ ወልድ ኣባዩ ላቶ ዳኝነት የጻፈውን ማመልከቻ ቃል ስላነበብሁ ሲጠየቁ መፍረድ የሚገባ ስለሆነ ይልቁንም ነገሩ ከማንም ከማን የማያጋጭና የማያከራክር የአስተዋይ አእምሮ መመዘኛ የፍርድ አከሔድ ማስታወቂያ ብቻ በመሆኑ ደስ ስላለኝ በተሰጠኝ እውቀቱ የመሰለኝን ፍርድ ከዚህ ቀጥዬ እጽፈዋለሁና ፍርዱ ቢስማማ ይቀበሉኝ አለዚያም ከኔ የሚበልጡ ብዙ ፈራጆች አሉና የነዚያን ፍርድ ሰምተው ግልባጫቸውን ተቀብለው ለበላይ ዳኛ ያሰሙ እንጂ በዚህ ነገር የሆነ የኔ ፍርድ የማያከራክርና ለይግባኝም ግልባጭ የማያስፈልግ መሆኑን አስቀድሜ አስታውቃለሁና ስለዚህ ብሳሳትም እንዳትነቅፉኝ እለምንሃለሁ ።

በፍርድ መንገድ የኔ አሳብ ይህ ነው ፡ መጀመሪያ የነዚህ ልጆች አባቶች ይህችን ልጅ ለልጆቻቸው ለማጋባት ሲያጩ በሀብታቸውና በሥልጣናቸው እየተመኩ ቢጠይቁት የልጅቱ አባት ሀብትና ሥልጣንን ንቆ ትምህርትንና እውቀትን አክብሮ የኔን ልጅ ለማግባት የፈለገ ያ፲ዓመት መንገድ ሒዶ ፯ዓመት ተምሮ በጥበብ የበለጠ ሰው ነው የኔን ልጅ የሚያገባት ብሎ ቢመልስላቸው የሀብትና የሥልጣን ትምክህታቸውን እንደናቀባቸው አይተው ፫ቱም ልጆች አገር ጥለው ሒደው የኔ ይበልጥ የኔ ይበልጥ ብላው ልዩ ልዩ ሟያ(ጥበብ)ሲማሩ መቸም የጠያቂው ተአምር አያልቅምና ሦስቱም ከሩቅ አገር ከተማ ቤት ሳሉ ይህች ልጅ ሞተች አለ መሞቷንም ሙት አንሺውና በራሪው ሳያውቁ በሩቅ ተመልካቹ አይቶ ነገራቸውና ሦስቱም ተማክረው ተመልካቹንና ሙት አንሺውን ይዞ በራሪው ሟችቱ ካለችበት አደረሳቸውና ሙት አንሺው ሟችቱን ከሙታን አስነሣት፤ ስለዚህ ተመልካቹ ባይናገር፤ በራሪው ባያፈጥን ሙት አንሣው ባያድናት እንደሞተች ልትቀር ነበርና ከነዚህ ከሦስቱ ማንኛው የበለጠ ሥራ ሠርቷል ማንኛውስ ሊያገባት ይገባል ብሎ ነውና የጠየቀው እንደኔ ሐሳብና በዕድሜዬም እንዳየሁት በታሪክም እንዳነበብሁት የሙት አንሺው ጥበብ ከሁሉ የበለጠ ይመስለኛል ። በዕድሜዬም እንዳየሁት በታሪክም እንዳነበብሁት የሙት አንሺው ጥበብ ይበልጣል ያልሁበት ምክንያት እንደሚከተለው ነው ። ፩ኛ ከሩቅ ተመልካቹ ይበልጣልና ያግባት እንዳንል ከሩቅ የሆነውን የሚያዩና የሚሰሙ የቴሌስኮፕና የቴአይላይት የሳንፊልና የቴሌፎን ጠቢባን አሉ ምንም ሥራቸው ታላቅ ጥቅም ያለበት ቢሆን ደስታና መከራንም ለሰው እያቀባበሉ ቢኖሩ ይልቁንም በጦርነት ጊዜ የጠላትን አመጣጥ እያስታወቁ ወገናቸውን ከሞት ቢያድኑ ነገር ግን ከሞተ ወዲያ ሰውን ከሙታን አላስነሡምና ጥበባቸው ከሙት አንሣው ጋራ ሊወዳደር አይቻልም ለዚህም ማስረጃ ምሳሌ በጦርነት ጊዜ ደጀን ሆኖ የተቀመጠ ጦር አለ ከደጀኑ ጦር ውሥጥ አንዱ ባለመነጽር ነበርና ከሩቅ ሲመለከት አንዱን ጀግና ጠላት ሲያሳድደው አይቶ ላንዱ ጀግና ቢነግረውና ጀግናው ጦር ነቅንቆ ጥይት አውልቆ ፈክሮ ሒዶ አባራሪውን ጠላት ገድሎ ያንን ጀግና ከሞት ቢያድነው ጀግንነቱ የሚበልጠው የባለ መነጽሩ ነውን ወይስ ጠላቱን ገድሎ ከሞት ያዳነው ጀግና ነው እንደኔ ሐሳብስ ጀብዱው ጠላቱን ገድሎ ወገኑን ያዳነው ጀግና ነውና እንደዚሁ ሁሉ ከሩቅ ተመልካቹ ጥበብ የሙት አንሣው ጥበብ ይበልጣል ።

፪ተኛ በራሪው ይበልጣል ያግባት እንዳንል ብዙ ሰዎች በአውሮፕላን በሴፕላን በዘፔሊን እየበረሩ የፀብና የሰላም ጥበብ ይሠሩበታል የብዙውንም ጊዜ ጐዳና በሰዓት ይነጉዱታል ይልቁንም በእግር መንገድ የማይከጀሉትን ውቅያኖሶችና ምድረበዳዎች ባንዳፍታ እያቋረጡ እየተሻገሩ ጠላት ያጠቃሉ ወገ፥ ይጠቅማሉ ከነዚህም ስመ ጥሩ የሆኑትን የአትላንቲክን ውቅያኖስ የበረሩ ከኒውዮርክ ፓሪስ የገባው ሊንድምበርግ ከኒውዮርክ ቤርሌን የገባው ቻምበርሌን ናቸው እነዚህና ሌሎቹም ሁሉ ሆኑ ቢበሩ ቢፈጥኑ ከሞተ ወዲያ ሰው ከሙታን አላስነሡምና ስለዚህ የነሱ ጥበብ ከሙት አንሣው ጥበብ ሊወ

ዳደር አይችልም ለዚህም ማስረጃ ምሳሌ ብዙ ስመጥሩዎች ልዩ ሐኪሞች ስፔሲያሊስቶች አሉ እነዚህ ሰዎች በሳንፈል ሰምተው በአውሮፕላን በረው ሒደው ሕመሙን አክመው ቢያድኑ ያንን ሕመምተኛ ሐኪሙ አዳነው ይባላል እንጂ ባለሳንፈሉና ባለአውሮፕላኑ አዳኑት ለማለት አይቻልምና እንደዚሁም ምንም በራሪው በፍጥነት ቢያደርሰው ተመልካቹም ቢነግረው ከበራሪውና ከሩቅ ተመልካቹ ጥበብ ከሙት ያስነሣት ጥበብ ይበልጣልና ከሙታን ያስነሣት ያግባት ። ነገር ግን ከሩቅ ተመልካቹና ከበራሪው ጥበብ የሙት አንሣው ጥበብ ይበልጣል ስላልንም ከክብር ክብር እንዲልቅ እንዲሁ ከጥበብ ጥበብ መብለጡን አስረዳን እንጂ የሩቅ ተመልካቹንና የበረረውን ጥበብ ለመንቀፍ አይደለም ። ደግሞ ምነው ተመልካቹ አስቀድሞ ተናግሮ በራሪውም አፋጥኖ አድርሶ ውለታቸው ምን ሊሆን ነው የሚል ጠያቂ ቢኖር ጥንቱንም የልጅቱ አባት በጥበብ የበለጠ ልጁን ያግባት አለ እንጂ መልካም ውለታ የዋለላት ያግባት ብሎ ቃሉን አልሰጠምና ስለዚህ ነገር እንደግቡ ጋሻ እንደንግቡ ነውና በጥበብ የበለጠ ያግባት ካለ ዕኛ በዚህ ዓለም ለፍጡር ከሞት ማስነሣት የበለጠ ጥበብ የለም ለዚህም ማስረጃ ስለ ተመልካቹ ጥበብ ያለፈውንና የሚመጣውን ስንኳ በምድርና በሰማይ የሆነውንና የሚሆነውን የተናገሩ ከፍጡር ወገን ብዙ አሉ ሁለተኛ ስለበራሪው ጥበብ ባሕር እየከፈሉ በአየር እየበረሩ የብዙ ቀን ጕዳና በቅጽበት የደረሱ ከፍጡር ወገን ብዙ አሉ ። ከሞት የማንሣት ሥልጣን ጥበብ ግን ሁሉን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር እንጂ ለፍጡር ያልተሰጠ ሥልጣን ነውና በውነት እንደጥያቄው ቃል ሙት ማንሣት የሚችል ጥበበኛ ፍጡር ከተገኘ ከሁሉ የምትበልጥ የፈጣሪ ሥልጣን ያደረችበት መሆኑ ነው ስለዚህ ከበራሪውና ከሩቅ ተመልካቹ ጥበብ የሙት አንሣው ጥበብ ይበልጣልና ሙት አንሣው ያግባት ስል ፈርጃለሁ ።

መስፍን ቀለመ ወርቅ ።

የትጉህ ሰው አሳብ ያስገኛል መልካም ደምብ።

ቀኛዝማች ተክለማርቆስ ዋና የጽሕፈት ሚኒስቴር ዴሬክተር የሥራ መሪ የሚሆን የጽሕፈት ሚኒስቴር አስቀድሞ ለራሱ ደምብ እንዲያስፈልገው ስለተረዱት ፲፪ ክፍል የሚሆን የደምብ መጽሐፍ ጽፈው ለጽሕፈት ሚኒስትር ቢያሳዩአቸው መጽሐፉን አንብበው ምንም የሚታረም ነገር የለበትም በዚህ የሥራህ ብዛት ላይ ይህን ደምብ አስበህ በመጻፍህ አመሰግንሃለሁ ብለው ታላቅ ምስጋና አቀረቡላቸውና በጽሕፈት ሚኒስትር ክፍል ያሉ ጸሐፊዎች ሁሉ ተሰብስበው አንድነት በተቀመጡ ጊዜ ቀኛዝማች ተክለማርቆስ የጽሕፈት ሚኒስቴር ዋና ዲረክቴር የሚከተለውን ዲስኩር አንብበው የነበሩትን ሰዎች ሁሉ እጅግ ደስ አሰኝተዋቸዋል።

ለሥራ ጓደኞቼና ለድካም ተካፋዮቼ ቀጥሎ ያለውን ምክር አነባለሁ ።

ወንድሞቼ ሆይ

በዓለም የታወቀውና ከሌሎቹ መሥሪያ ቤቶች ሁሉ መጀመሪያ ሆኖ የሚጠራው የጽሕፈት ሚኒስትር ቢሮአችን ከጥንት የቆየ የሥራ ደንብ እንዳለው የታወቀ ነው። ነገር ግን ጊዜና መቆየት የሚያሻሽለው አንድ ፩ አገባብና ጥቅም ስላለ ያንኑ የጥንቱን መሠረት ሳንለቅ ጥቂት ጥቂት ማስረጃ እየጨመርን ለየአንዱ እንዳችሁም ያላፈነታችሁን ሥራና የሚያስፈልጉትን ሠራተኞች እየለየን ደንብ ጽፈንላችኋልና ይህንን መሪ እያደረጋችሁ በቅንነትና በትሕትና መስራት ነው። እንደምታውቁትም የጽሕፈት ሚኒስትር ቢሮ ለሌሎች ቢሮዎች ደንብና ሕግ ሰጪ ሲሆን እኛ ደንብ ባለመጠበቅና ባለመተባበር ሥራችን እንዳያድፍና ጉድለት እንዳያገኘን ማሰብ ነው ።

ይልቁንም ደንብን መጠበቅ እንጂ ማቆሙ አይቸግርምና በዚህም እንዳንሳሳት መጠንቀቅ ያስፈልገናል ።

ክቡር የጽሕፈት ሚኒስትርና እኔም እራሱ ብሆን ደሥራሉ የምንበለውና የምንመሰገነው እናንተ በታማኝነታችሁና በድካማችሁ የምታስናዱትን ይዘን ነው እንጂ ሁሉ በኛ ልብ ታስቦና ተሠርቶ አይደለምና አሁንም እንደዚሁ መታመንን መትጋትንና ቅንነትን ገንዘብ አድርጋችሁ የዕለት ጥቅምን ሳትፈልጉ እርዱን ።

እነዚህንም ገንዘብ አድርጎ የያዘ ሰው ሳይጠይቅ ዋጋውን እንዲያገኝ፥ ምረጡኝ ሳይል እንዲመረጥ በብዙ ሰዎች ላይ ታይቷልና ማስረጃ አያስፈልግም ።

ክፉን ማረቅ ይገባል ።

በንግድም በሥራም ምክንያት ኢትዮጵያን ጠቅመን እኛም ተጠቅመን እንኖራለን ብለው በአዲስ አበባ ኑአሪዎች ከነበሩ የውጪ አገር ሰዎች መንግሥት የአልፈቀደላቸውን መኪና አስመጥተው በከተማው ዳርቻ አጠገብ በስውር አረቂ ሲአወጡ በመጋቢት ፫ቀን የአልኮል ተጠባባቂዎች ዘበኞች ይዘዋቸው ያልተመረመረ ሕዝቡንም የሚጎዳ አልኮል ማምጣታቸውን በቃላቸው አምነው በልዩ በቆመው የፍርድ ቤት አንዳንዱ ሁለት ሺህ ከዓሥር ብር እንዲከፍሉ መኪናቸውንም ለመንግሥት ውርስ አድርገው እንዲለቁ ተፈርዶባቸው የአገር ግዛት ሚኒስትርም ነገሩን የሚጠባበቅ ሹም አስቀምጦ ነበረና የፍርዱ ነገር ከተፈጸመ በኋላ እስከ ሚያዝያ ፳፫ቀን ከኢትዮጵያ እንዲለቁ ጽፎላቸዋል እነሱም የትንሣኤ ዕለት ይለቃሉ ስማቸውና ነገዳቸውም ቀጥሎ የተጻፈው ነው።ሳላንት መንደል የፓለስቲን ይሁዲ ቆንሲል የለውም ።

ፐትሬትሲስ ኒኮላ ግሪክ የፈረንሣዊ ጥገኛ ነው ።
ፍለባልማን ሞረስ ማርቲን የሩማኒ ፓሎኝ ሰዎች ናቸው
ኮላንቶስ ዩኒስ ግሪክ
ታሶማንጂካስ ግሪክ
ደባንጂሻ ግሪክ

የነዚህ ሰዎች መሔድ ቍርጥ ነውና ገንዘብ አለኝ ነገር አለኝ የሚል ሰው መያዝ የሚፈልግ ከዚያ ወዲህ ነው ።

ስለእውቀት ማበላለጥ።

ረእዮ ኅቡኣት ኤልሳዕ መንቅሔ ምውት
እምርኁቅ ነጸረ ለእመ መዋቲ ፍኖታ ።

ወበኃይለ ኤልያስ በጽሐ እስከ ሰራ ፕታ ።
ወአንቀሐ መዋቲ በብዙኅ ያታ ።
አሐዱ ኃይለ ኤልሳዕ ።
ለእለ ይትሜየኑ ሕዝብ እስከ ይመስሎሙ መንታ ።
ዳንኤልሂ በጥበቡ እንዘ የሐትት ሐተታ ።
ሐሰተ ረበናት ይፈልጥ ለጽድቀ ሰስና እምሃይማኖታ ።
የሀበኒ ለኤልሳዕ ። ለወለተ ነዳይ ንብረታ ።
ዘጸሐፈ ተመያኒ ለመጽሐፈ ብርሃን በውስቴታ
አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን።

ስለ ሆሣዕና መወድስ ቅኔ

በወልደ ጌራ ልብሙ እምኢተሠወሮ ፤
መሥገርተ ነጋሢ ሰሎሞን ዘአሥገሮ መከረ ።
ኀሢሠ እእዱግ ዘጠፍኡ እመ ልቡናሁ ኢሠምረ ።
ወአእዱጊሁ እመኢጠፍኡ፤እምኢኮነ ማኒ በክህደት ሰክረ።
እኮኑ ልቡናሆሙ ሕይወተ እእዱግ ቢጸ፤ ከመ ነፍሶሙ ኢፍቀረ ።
በዓለምሰ ለእመኮነ አፍቅሮ እእዱግ ነውረ ።
በመንግሥተ ሳኦል ወልደ ቂስ፤ ኀሢሠ እእዱግ እምኢተነግረ ።
ወእምረዋፅያን አፍራስ እመከበረ እእዱግ ኀሥረ ።
ንጉሠ ነገሥት ሆሣዕና በዘባነ እእዱግ እምኢነበረ ።
ሊቀ ጠበብት ድንቄ ዘራጉኤል ።

የሚያሳዝን ሞት

ወይዘሮ ደመቀች የቀኛዝማች ተሰማ ቡኔ ባለቤት ገና ፳፰ ዓመት የሆናቸው ወጣት ነበሩ ቀኛዝማች ተሰማ ቡኔ ከአገቧቸው ገና ፪ወር ሊሆን ፲ቀን ሲቀረው በድንገተኛ ሕማም ታመው በሚያዝያ ፲፫ ቀን ሙተው በመድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበሩ እንዲህ ያለው አሟሟት እጅግ ያሳዝናል ነገር ግን ተላይ መጣ መቱስ ምን ይደረጋል ኀዘንተኞችን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናቸው

የሚያሳዝን ሞት ።

ልጅ መንገሻ ማሞ የማዘጋጃ ቤት ክፍል ሙዚቃ ተማሪ ገና ወጣት የሚያሳዝን ልጅ ነበረ በትምርቱም ላይ በትክክል እውቀት ገብቶት ከ፬ ባልንጀሮቹ ጋር በምልምል ሊአወጡት የሙዚቃ አስተማሪዎች አስበውለት ሳሉ በድንገት በውጋት በሽታ ታሞ ስለሞተ በልጁ ሎጋነትና መልከም ባሕርይ ስላየሁበት ለባልንጀሮቹና ለዘመዶቹ ኀዘኔን ልገልጽላቸው ፈቀድኩ በተወለደ በ፳፫ ዓመቱ በ፲፱፻፳፬ ዓም በሚያዝያ ፭ ቀን ከማታው በ፱ ሰዓት ተኩል አርፎ እሑድ በ፯ ሰዓት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ በዚህ ጊዜ እናቱ በዜማ ልቅሶ ሲአለቅሱ ሰማኋቸው ።

ባጭር መንገድ ልሒድ ድካሙን ልየው ።ረጅሙንማ መንገሽ ሔደው ። አረ ያ ልጅ ሔዶ ወምበዴ በላው ። ይቻለን እንደ ሆን ሔደን እንርዳው ።ልጅ መንገሻ ማሞ አጥንትም የለው ። ሥጋውንም እንደሁ አፈሩ በላው ። ብለው ሲአለቅሱ በጣም ያሳዝኑ ነበር ለባልንጀሮቹና ለቤተ ዘመዶቹ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል አድምቄ።

ማስታወቂያ

ሙሴ ዛኪ ሲድራክ ሳዳላ። የባለቦታውን የብላታ ጳውሎስ ሳዳላን ወራሾች የከዳማ ሳዳላ የበኪታ ሳዳላ የዳንቱካ ሳዳላ። የሲድራክ ሳዳላ፡ ወኪል ሙሴ ባስታ ሳዳላ የነዚህን ወራሾች ወኪልነት መተዉን ያስታውቃል። የውርሱም ቦታዎች ፪መሬቶች በአዲስ አበባ ከተማ ፮ሺ ሜትር ካሬ የሚሆኑት የሚሸጡ ናቸውና ለመግዛት የሚፈልጉ ሁሉ በዚህ ሳምንት ውስጥ ወደ ጠበቃው ሙሴ ክቦስቶፍና ሙሴ ዘሀቢብ ቢሮ መጥተው የዋጋውን ነገር ለመነጋገር ይችላሉ።

AVIS

Mr. Zakki Cidrak **SAADALA** mandataire de Khedama Saadala,Bekhita Saadala, Dentucha Saadala et Cidrak Saadala, heritiers de la Succession de Balata Bowlos **SAADALA** fait savoir que le sieur **BASTA SAADALA** n'est plus le mandataire des dit heritiers.

Les proprietés de la succession à Addis Abeba deux terrains environ 6.000 m. c. sont mis en vente.

Toutes propostions et offres d'achat doivent être faits dans le courant de huit jours au Bureau de l'avocat Khvostof et Mr. J. Habib chez qui les personnes interessées peuvent recevoir de meme tous les renseignements. Zaki Sedrak Saadall.

የሚሸጥ አቶሞቢል ።
ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።
ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚሁ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ባንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቀን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩፓንያ ሴንጀር በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ባለው ዕቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ዕቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ስጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጇ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ዋናው አሰናጇ ባዚል አስላኒዲስ

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኙና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር ፤ግርማዊ ንጉሥ አሰናጅ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም
ALEM

ባያይነቱ፡ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።





ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገፍረል።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ፀአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፡፡ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ጫልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።ብጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ እስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሴ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፲፱
8ᵉ ANNE № 19

ሐሙስ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 5 AVRIL 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ፡ ዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ·

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ።

ቅዳሜ ሥዑር በሚባለው ቀን ካህናት ቄጠማቸውን ይዘው በየዓመቱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ አደባባይ እየሔዱ ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሀደ እያሉ ይዘምራሉ። ዘንድሮም በዚሁ ልማድ እንዲሁ አደረጉ ይህንም የምስራች ቃል ለመቀበል ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለዓይን በሚያንጸባርቅ ምንጣፍ በተነጠፈው ከፍ ባለው ዙፋን ላይ ተቀምጠው ነበር። ብፁዓን ጳጳሳት ልዑላን መሳፍንት ክቡራን የኢትዮጵያና የውጪ አገር ሚኒስትሮች መኳንንትና ቆንስሎች በግራና በቀኝ በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር። የኢትዮጵያ ኃያላንም በግራና በቀኝ ቁመው ነበር ሊቃውንቱና ካህናቱ ጥሩ ጥሩ የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው በላይ እንደተጻፈው ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሀደ እያሉ መዝሙራቸውን ከጨረሱ በኋላ ከጐጃም ክፍል ዲማ ጊዮርጊስ የሚባለው የስመ ጥሩው የታላቁ ደብር ካህናት የሚከተለውን ወረብ ወረቡና እጅግ አማረባቸው። ይቤ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ እግዚሃ ለደብረ ድማህ ወኢያርኅቅ ምሕረትየ እምኔኪ ለዓለመ ዓለም ወይቤ ብፁዕ አባ ጊዮርጊስ ትከውኒ ከመቀዲሙ ወትገብኢ ከመትካት አንሰሱ ማእከሌኪ ደብረ ሊባኖስ ።

፪ኛ ፤ ዘመልዕልተ ዘመልዕልተ አድባር ይነብር ዘእምቅድመ ዘእምቅድመ ዓለም መንግሥቱ ዘእምቅድመ ዘእቅድመ ዓለም መንግሥቱ ለኃይለ ሥላሴ መንግሥቱ ብለው ወረቡ በኋላ ቀድሞ ልዑል ራስ መኰንን በሐረር መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በደብተርነት ተክለዋቸው የሚኖሩ ማለፊያ ደቀመዝሙር ቄስ ገብዝ ተድላ የሚባሉ ካህን መወድስ ቅኔ እሰጣለሁ ብለው ተመሪው ፍታሕ ሊተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልየ ብሎ ተጀመረ በኋላ ሰዓቱ ስለ አለፈ በወረቀት ጽፈው እንዲአቀርቡ በሊቀ ካህናቱ በሊቄ ገብረ ክርስቶስ ቃል ታዘዙ ቅኔውም ቀጥሎ የተጻፈው ነው

መወድስ ።

ምስለ ኃያላን አእላፍ አመ ትመጽእ በንጥረ መብርቅት
ግሩም ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ፥
ወሞጣሕተ በቀል አንተ አመ ትለብስ ፣
ይርዕድ ኵሉ እንተ ባሕር ወየብስ ።
ወእም መንግሥተ ባዕድ፡ ኢትሰምዕ ምንተ አውያተ ወለታ
መንግሥተ ፋርስ ።
ይትቀነያሂ ከመ ተነግረ ሰዓተ መንግሥትከ ዕንስ ።
ዘየዓቢ ሕዝበ ባዕድ ለኢትዮጵያ ዘይንዕስ።ወእምግርማከ
ትርዕድ ኢየሩሳሌም ነፍስ ።
እስመ በዮርዳኖስ አርሰስከ ኵሉ ይደመሰስ ።

የፋሲካ በዓል ።

ይህ የፋሲካ በዓል በቤተክርስቲያን ሁሉ ታላቅ በዓል ነው ። ነገር ግን ቤተክርስቲያን ሁሉ በክርስቶስ እምነት አንድ ስለች ውሥጥ ውሥጡን ብዙ መለያየት ታደርጋለች ። የዓመቱ አቈጣጠር ልዩ ስለሆነ የዓመት በዓሉ ቀን ይለያያል ። እንዲህም ስላልን የግብፅና የሶርያ የአርመን አብያተ ክርስቲያን የዓመት ቍጥራቸውና በዓላቸው ትኛ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት ጋራ አንድ ናቸው ። አንድ ናቸውም ስላ አልን ጥቂት ጥቂት የሚለያዩበት ነገር አለ ። ምንም ቢሆን ይቀራረባሉና አንድ ናቸው ማለት ይቻላል ። እንግዲህ ወደ በዓሉ ነገር እንመለስ ።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ፍቅር ይፀናባታልና በየጊዜው መታሰቢያውን አታቋርጥም ። ዛሬም በዚሁ ልማድ ከቅዳሜ ማታ ጀምሮ እስከ ፲ሰዓት ድረስ በየቤተክርስቲያኑ ሌሊቱ ቀን መስሎ የቤተክርስቲያንም ብርሃን እጅግ አብርቶ ከብርሃኑ በላይ ብርሃን ጨምሮ ይታይ ነበር ። ፲ሰዓት ሲሆን ቤተክርስቲያን ሥርዓቷን ጨረሰች። ከዚያም በኋላ ስለ በዓሉ ብዙ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ። ያም የተናፈቀው ፋሲካ ደርሶ አለፈ ። ምን ይሆናል? የወደዱት ቀን ማለፉ እያሳዝምና ነገር ግን ማለፍ በይኖር የጠላት ቀንም ነዋሪ ይሆን ነበርና ማለፉ ይሻል ይመስለናል ። ዘመናይ (ዘመናዊ) ግን ይህን ሲሰማ አዲስ አስመስሎ ይነቅፈው ይሆናል ። ምንም ዘመን የተመቸው ሰው ዓይኑ በይገለጥ በፊተኞቹ ማለፍ ከዚህ እንደደረሰ ማወቅን ይረሳ ይሆን? አዎን ምንም ብዙዎቹ ቢያውቁ ጥቂቶች ሳይረሱት አይቀሩም። አስተዋዮችማ እንኳንስ እውቀት በበዛበት በዛሬው ጊዜ ይቅርና በቀድሞው

ዘመን እንኳን ያውቁት ነበር የዚህንም ማስረጃ በሚከተለው መንመር እንገልጻለን። ደጃዝማች ውቤ የሚባሉ የስሜንና የወገራ የትግሬና የአስመራ ገጋር በመሳፍንት ዘመን አንደኛው ገጋር ነበሩ፤ የአደባባያቸውን ስፋት የሠራዊታቸውን ብዛት እያዩ አንዱ አወደድ ብይ ይህች ዓለም ማታልፍ ብትሆን እጅግ መልካም ነበረ ቢላቸው ትለፍ እንጂ ባታልፍማ እኛ ዘንድ መቼ ትደርስ ነበር አሉት ይባላል። ዘመናይ በዘመኑ ጊዜ ማለፍን ቢአስብ ኃጢአት ከዓለም ትጠፋ ነበረ፣ አሁን ይህን ሁሉ ያሳነበነ የዚህን የጥጋቡን ቀን የፋሲካን ማለፍ ስለአየን ነው

በበጌምድር አውራጃ የተደረገ በጣም የሚያስደንቅ የተአምራት ሥራ።

በክቡር ደጃዝማች ካሣ መሸሻ ጉልት እንፍራዝ በሚባለው አገር ውስጥ ምጥርሃ ማርያም የምትባል ደብር ከጣና ከባሕሩ ውስጥ አለች። ያብሬቱም ትልቅ ደብር ናት ፫ ነገሥታት ተቀብረውባታል ስማቸውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ዓለም ሰገድ ኢያሱ። ጻድቁ ዮሐንስ፣ ሳልሣይ ዳዊት እነዚህ ናቸው። ንግባእኬ ኀበ ጥንት ነገር ነውና ወደመጀመሪያው እንመለስ በዚች ምጥርሃ ማርያም በምትባለው ያሉ የሚያገለግሉት ካህናት ደንገል የሚባል ታንኳ የሚሆነው የሚበቅለው በጐጃም አውራጃ በባሕሩ ድምበር ከዚያ ስለሆነ የሚበቅለው በሰው አገር ያለ እቃ መሣሪያ መክበሩ አይቀርምና የአንዱ ታንኳ መግዣ ፲፫ና ፳ ብር ስለሆነ ከውጭ ሰው በሞቱና በዓመት በዓልም ጊዜ ከሰው ብዛት የተነሣ የሚገቡበት ታንኳ እያጣ ደብሬቱ እንደሰማይ ርቆው እንጋጦ እያየ ይቀር ነበር ከባሕሩ ድምበር እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ንጉሥ ለሰራዊቱ አዝማች ነውና ደጉ ንጉሣችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የባሕር ጀልባ ያመጡልናል በማለት ሕዝቡ በሙሉ ተስፋ ነው አሁንም የደጉ ንጉሣችን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ደግነታቸውን ለማስረዳት በጐጃም አውራጃ የበቀለው ታንኳ የሚሆነው ደንገል እስከነመሬቱ በዙርያውና በውስጡ የበቀለው ትልልቅ ዛፍ እንዳለ ተነቅሎ መጥለቅ የሚገባውን ትልልቅ ዛፍና መሬት እንዲያዘ በባሕሩ ላይ እንደ መርከብ እየበፈፈ ከጐጃም ዳር ተነቅሎ መጣ ከባሕሩም መካከል በደረሰ ጊዜ ሲታይ ከዛፉና ከደንገሉ መርዘም የተነሣ እንደ ትልቅ ተራራ መስሎ ይታይ ነበር ሕዝቡም እንደ ትልቅ ተራራ መስሎ ባታየው ጊዜ ዓሣ ነበረ ይሆን ወይስ ሌላ ነገር ይሆን ከኃጢአታችን ብዛት የተነሣ ምን መጣብን እያለ ይጨነቅ ጀመር በታንኳም ሔዶ እንዳያየው ሥጋ ፈሪ ናትና ወይስ መንፈስ ጋኔን እንደሆን እያለ ፈርቶ ቀረ ኢየኃድጋ ለሀገር ዘእንበለ ኖዱኄር እንዳለ ክቡር ደጃዝማች ካሣ መሸሻ በሰሙ ጊዜ መንግሥታቸውንና ንጉሣቸውን አክባሪ ስለሆኑ ደህና ደህና ጕበዛዝቶች ታንኳ የሚያውቁትን አሽከሮቻቸውን ገብታችሁ እዩት ብለው በፍጥነት አዘዙ የተአዘዙትም አሽከሮች የጌታቸው ቃል ለማጓደል አይችሉምና ሰው ሁሉ ለመግባት የፈራውን አስራ ስምንቱ በርት ታንኳ ፪በአንድ መሮጫ ታንኳ ሁነው ብረታቸውን እንደያዙ ማልደው በ፩ሰዓት ገቡና በ፬ት ሰዓት ደረሱ ደንገል መሆኑንም ካዩት በኋላ ደህና ወላዲተ አምላክ በፈቃዷ ያመጣችው ነው ብለው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ መመለስ ጀመሩ ሕዝቡም የነሱን መመለስ እየተጨነቀ ምን ያገኛቸው ይሆን እያለ ሲጠብቃቸው ነበርና ደስታውን ለሌላ ነገር እኔ እቀድም እኔ እቀድም እየተባባሉ በታንኳው መቀዳደም ጀመሩ በመሮጫ ታንኳ የተቀመጡ ሁለቱ ቀድመው ለሕዝቡ ሁሉ ደስታውን ገለጡ ደጃዝማች ካሣ መሸሻም ቀጥሎ የተጻፈውን ተናገሩ ለደጉ ንጉሣችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለደጊቱ ንግሥታችን ለማርማዊት እቴጌ መነን ረጅሙን ዕድሜና ጤና ሰጥቶ መንግሥታቸውን ሺህ ዓመት ያድርግልን ብለው በጨረሱ ጊዜ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ እንደቃልም ያድርግልን ብሎ በአንድ ቃል ተናገረ የመሬቱም ስፋት ፱፻፳ ክንድ ነው በኅዳር ፰ቀን የተነቀለ ከዛፉና ከመሬቱ ብዛት የተነሣ በኅዳር ፳፩ቀን ከተበረከችው ምጥርሃ ማርያም ደረሰና ከባሕሩ ድንበር ተተከለ ይህንም ልጽፍ ያሳሰበኝ በቀድሞ ነገሥታት ያልሆነውን ዛሬ በደጉ ንጉሣችን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ስለ ተደረገ ኢሰማዕነ ወኢርኢነ ወኢነገሩነ አበዊነ የለው ቃል ደረሰ የደጉ ንጉሣችን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ምሳሌ መሆኑን ስለተረዳሁት ለመጻፍ አሳሰበኝ ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ የበዛውን አሳጥራችሁ ያልጠራውን አርማችሁ እንድታነቡልኝ እለምናችሁአለሁ።

ታናሽ ወንድማችሁ ከንፈ ርግብ ተድላ ዘብሔረ እንፍራዝ

የጥያቄ መልስ።

መጋቢት ፳፱ ቀን ከደባባይ ውጭ ወደ ማረፊያ ቤቴ ስሔድ ፫ልጆች እርስ በርሳቸው እየተጨቃጨቁ ሲሔዱ አገኘኋቸው ምነው ምን ያጣላችኋል ወዴትስ ትሔዳላችሁ ብላቸው ባንዲት ልጃ ገረድ ምክንያት እኔ ላግባ እኔ ላግባ በማለት ተጣልተን ከቶ ትስብእት ወልድ አግዴ ብንሔድ እኔ ሥራዬ ጽሕፈት ስለሆነ የተነጋገራችሁትን ሰምቼ እጽፋለሁ እንጂ ለማነጋገር ሥልጣን አልተሰጠኝም ብለው ንግግራቸውን ጽፈው ወደ አቶ ዳኘነት ሰደው ነበርና አቶ ዳኘነትን አጥተን እንበክናለን ምናልባት ታውቃቸው እንደሆን ያሉበትን አመልክተን አሉኝ እርሳቸውስ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አደባባይ አይጠፉም ፍርዳቸውም እጅግ ደብ ያሰኛል። እነሆ እኔ ብርቱ ሰው ርስቴን ልውሰድብህ ብሎኝ ጭቅጭቅ ተጀመርሁ ፲፯ ዘመኔ ነው እርሳቸውም ዘወትር በቀጥታ ይፈርዱልኛል ነገር ግን ባላጋራዬ ኃይለኛ ስለሆነ ፍርድዎን እየጣሰ እምቢ አለኝ ብላቸው ፭ ቀን በችሎት ተገኝተው የፈረዱትን ነገር አልቁርጥልኝ ብለው የከተማ ረኃብ ይጫወትብኛል እኔን ያገኘ እንዳያገኛችሁ ምናልባት ብትታረቁ ነገራችሁን አላይላችሁምን አልኋቸው ምን ከፋና ተሆነልህ ይህን ወረቀት እያየህ ገላግለን ብለው ወረቀቱን ሰጡኝ እኔም ወአዕይንትየኒ ደክማ በተፅናስ ያለው ከኔ እጅግ አይርቅምና ረቆ አልታየኝ አለ መራቀቅ የሚባል መነጽር ከኪሴ አውጥቼ ብመለከት ጥቂት ጥቂት ስለታየኝ ወንድሞቼ ደህስ ነገራችሁ ከቶ ትስብእት ወልድ

ሕስቀድመው የነበሩት ሰዎች የተናገሩትን ይመስላል ባላጋራ የፀዘበት ፩ ድኃ የተባለ አዳም ነው። ደም ግባቷ ያማረ ልጅ የተባለች የአዳም ነፍስ ናት። ንጉሡም አብ ነው ወራሽ ቴራሽ ይሆነኛል ያልሁት ፩ የበኩር ልጅ ነበረኝ የዛሬ ዘመን ልጅ አዳኑ በራሱ ፈቃድ ስለሆነ ያንተን ልጅ ታላገባው ሙቼ እገኛለሁ ብሏልና ልጅህን ለልጄ ስጥ ማለት ዕብ ፩፫ ነገረን በወልዱ ዘረሰዮ ወራሲ ለኵሉ። ቈላስ ፩ ፲፫ በኵሩ ዘላዕለ ኵሉ ተግባሩ። ኤፌ ፩ ፲፩ ወረድአነ በከመ ምክረ ፈቃዱ የሚባል የልጄ ሥጋዌን ማዘጋጀቱን መናገር ነው። መኰንንም የተባለ ወልድ ነው የኔ ማዕድ ተዘርግቶ የሚበላው ጠፍቶ ማለት ዮሐ ፮፶፩ ወዝኒ ኅብስት ዘአሁብ አነ ሥጋየ ውእቱ በእንተ ሕይወት ተለዓለም ቢላቸው እሮ ይክል ዝንቱ የሀበነ ሥጋሁ ንብላዕ ማለታቸውን መናገር ነው። አንተ በችግር እየተጐሳቈልህና ባላጋራ እየጠቃህ በመኖርህ በጣም አዝናለሁ አንተንም ከባላጋራህ እጅ አወጣህለሁ ማለት ማቴ ፳፮፴፰ ተከዘት ነፍስየ እስከ ለሞት መጽአ ወረድአሙ ለእለ ይትዔገሉሙ ሰይጣን ያለውን ይመስላል። አሁንም ለትዳር የምትሆን ደም ግባቷ ያማረ ልጃ ገረድ ከቤትህ አይቻለሁና ጋብቻውን ፈቅደህልኝ ድግሱን ደግሼ ሥጋውንና ጠጁን አዘጋጅቼ መጥቼ እንድወስዳት ፈቃድህ ይሁን ማለት፣ ምሳ ፱ ጥበብ ዘበሐት ዘቢአሃ፣ ጥብሐ ወቶስሐት ውስተ ሰያሐ ዘቢአሃ ወይነ እንዲል ያንተን ሥጋ ተዋሕጄ ሥጋዬን ቊርባን ደሜን አፍሰሼ አድንሃለሁ ማለቱን መናገር ነው። ሽልማት አስሙ አልባስከኒ ልብሰ ሕይወት ወልብሰ መድኃኒት ያለውን፣ ሀገር ወበኡ ውስተ ሀገር ቅድስት ያለውን ይመስላል።

አንድ ሀብታምም የተባለ መንፈስ ቅዱስ ነው ሀብትኬ ሡናይ መንፈስ ቅዱስ እንዲል በየጊዜው አህል ባስወፃሁ ቀኖጥር ለማንም ድኃ ምርቱን እያፈሰሰ ሰጠው አንተ ብቻ እስከ ግርዱ አለማግኘትህ ያጸጸተኛል አሁንም ያሀን ያረቡሁትን የቀንድ ከብትና በግና ፍየል ወራሽ ያደረግሁት ልጅ ነበረ። ያንተን ልጅ ወዶ ሊሞት ነውና እንድትሰጥልኝ ይሁን ማለቱ በተፈጥሯቸው ድኖች ለሚሆኑ መላእክት በየጊዜው ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ሲሰጣቸው ለአዳም ስንኳን ደገሮው ሀብት የዓረበኑ ሀብተ ተከልክሎበት ስለኖረ ወኵሎ አግረርከ ሎቱ ታሕተ እገሪሁ አባግዐ ወኵሎ አልሕምተ ተብሎ የተነገረለት የወልድ ሥጋዌን መንፈስ ቅዱስም ማዘጋጀቱን መናገር ነው ወገብረሁስ ለውእቱ ሥጋ መንፈስ ቅዱስ እንዲል ያም ድኃ የሦስቱንም ወረቀት አይቶ የኔን ልጅ ለማግባት የፈለገ የዓሥ፣ ዓመት መንገድ ሔዶ ስድስት ዓመት ተምሮ በጥበብ የበለጠ ይውሰዳት አለ ማለት አዳም ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልድ ዓሠርቱ ቃላተ ኦሪትን አጽንቶ ስድስቱን ቃላተ ወንጌልን ሠርቶ ያድናኛል ብሎ ተስፋ አደረገ እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ ሰው ሁነው ያድኑኛል ብሎ ተስፋ አለማድረጉን መናገር ነው። ከዚህ ስደርስ አስቀድሜ እንደ ተናገርሁ ያይኔም ድካም እንደሆነ ወይም ከጽሕፈቱ ላይ ሕፀፀ ምሳሌ የሚባል ወኃ ነጥበ አጥፍቶትም እንደሆነ አላውቅ አልታየኝ ብሎ ስቸገር አኒያ ልጆች አንተ ሰው ሦስቱም የዓሥር ዓመት መንገድ ሔደው ስድስት ዓመት ተምረው ለአንዱ ጋራና ተረፈ ጨለማና ደመና ሳይከለክለው ዓለሙን ሁሉ እንደ መስተዋት የሚያሳይ ወረቀት ተገለጸለት። ለሁለተኛውም ሰው ከሞተ በኋላ ሦስት ሰዓት ሳይሞላው ከሞት የሚያስነሣ ዕውቀት ተገለጸለት ለሦስተኛውም የአሥሩን ዓመት መንገድ በአምስት ደቂቃ የሚያደርስ እውቀት ተገለጸለት ማለትና እኔ ላግባ እኔ ላግባ በማለት ሦስቱም ተጣሉ ማለት በሥላሴ ላይ ተምሮ ጥበብ መጎኘትና ባንድ ባንድ ጥበብ መወሰንን እኔ ሰው ልሁን በማለት መጣላትንም ያመጣየሀልኝ ያህንስ ትተህ እኛ የተጣላንበትን ፍረድልን አሉኝ የናንተስ ነገር እጅግም አያጥረኝ የሦስታችሁም ጥበብ የተተካከለ ስለሆነ ምንም ጥበቡ ከጥበባችሁ ባይበልጥ አስቀድሞ መርኹ ብልጫው ነውና አስቀድሞ ያጩ ሲያገባት ይታየኛል ስል ፈረደሁ ብዬ ሳልፀጨን ለብርሃንና ሰላም አስታውቃለሁ።

ደብተራ አድማሱ ዘዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ።

ጅማ ሀብታሙና ለምለሙ ሀገር

እስካሁን ሲደነቅና ሲመሰገን ይኖር ነበር ባ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ልምላሜው እየደረቀ ሀብቱ እየጐደለ መሔድ ጀመረ የረማኋቸውንና ያየኋቸውን ምክንያቶች ከዚህ ቀጥለው ባሉት መስመሮች ጽፌአቸዋለሁ። መጀመሪያ የልምላሚዋና የሀብቷ መሰረት ብልሁ አባ ጅፋር በየ ጊዜው አዋሳኞቻቸው ባላባቶች ለትልቁ ንጉሥ ነገሥት ለዳግማዊ አፄ ምኒልክ አንገዛም ብለው እየተዋጉ ሀገራቸውን በጦር ሲያስጠፉ ብልሁ አባጅፋር ግን ዓቅማቸውን ገምተው ልዋጋ ሳይሉ ሀገራቸውን ሳያስጠፉ በሰላም ተገናኝተው በፍቅር ተጠምደው አኖሩት። (፪ኛ) ይህንኑ ሀገራቸውን ለመጠበቅ ጃንሆይን አስፈቅደው ሶስት መቶ ብረት ተቀብለው ያማረ ወታደር አሳድረው የሀገራቸውን ጠረፍ አስጠበቁ ከመጀመሪያውም ማዕርግ እስከ ፊታውራሪ ለመሾም ፈቃድ ተቀብለው ስም መስጠት ጀመሩ።

ይኸውም ሀገራቸው ከሊሙ ከጉማ ተጌራ ተከፋ ተኵሎ ተኰንታ ተጃንጅሮ ተጠደሌ ተዋሳኝ ስለ ሆነ በነዚሁም ጠረፎች አቅራቢያ ያሉ ሀገራቸው ምድረ በዳና ያራዊት መኖሪያ ስለ ሆነ ጥንት በጋላ ዘመን የነበረ ኬላቸው እማህል አገር ውሥጥ ስለነበረ ያማረ ወታደር እያበረከቱ ብረት እየሰጡ ሀገራቸውን ማልማት ጀመሩ። ግብር የለችህ ሁሉ ተኬላ ውጭ እየሔድህ አቅና ያቀናኸውንም ርስት አድርጌልሃለሁ። ግብርህንም እስከ ሦስት ዓመት ምሬሃለሁ ብለው አዋጅ አደረጉለት። የሀገራቸውም የጐረቤታቸውም ሕዝብ መሬት የሌለውና ግብር የሌለቸው እየገባ ማቅናት ጀመረ ጠረፋቸውንም ሁሉ ለም አድርጎ የጅማን ሀብት እያሰፋ ቡን ተክላና ጥጥና [illegible] በሬ አበርክቶ ይሠራ ጀመረ። ይኸውም ሊታወቅ በጅማ ብዙ ቡን የሚገኘው በከፋ ወገን ቃንቀቱ በጌራ ወገን ሳዮር በጉማ ወገን ጉሬዶ በሊሙና በጉማ ማህል ማና ነው በዙሪያው ያለ ቆላው ግን በርበሬና ጥጥ ይበዛዋል ማህሉ ጅማ ግን እህል እንጂ የቡና ሀብት የለውም ሕዝቡም የሚበዛው በዚሁ በዱሉ ቅኝ ላይ ነው የጐረቤቶቻቸውንም ሀብት በብልሃታቸው

ዘመን እንኳን ያውቁት ነበር የዚህንም ማስረጃ በሚከተለው መንመር እንገልጻለን፡ ደጃዝማች ውቤ የሚባሉ የስሜንና የወገራ የትግሬና የአስመራ ገዢ በመሳፍንት ዘመን አንደኛው ገዢ ነበሩ፤ የአደባባያቸውን ስፋት የሠራዊታቸውን ብዛት አይቶ አንዱ አወደድ ባይ ይህች ዓለም ፥ማታልፍ ብትሆን እጅግ መልካም ነበረ ቢላቸው ትለፍ እንጂ ባታልፍማ እኛ ዘንድ መቼ ትደርስ ነበር አሉት ይባላል ። ዘመናይ በዘመኑ ጊዜ ማለፍን ቢአስብ ኃጢአት ከዓለም ትጠፋ ነበረ ፡ አሁን ይህን ሁሉ ያስነበብን የዚህን የጥጋቡን ቀን የፋሲካን ማለፍ ስለአየን ነው።

በበጌምድር አውራጃ የተደረገ በጣም
የሚያስደንቅ የተአምራት ሥራ ።

በክቡር ደጃዝማች ካሣ መሸሻ ጉልት እንፍራዝ በሚባለው አገር ውስጥ ምጥርሃ ማሪያም የምትባል ደብር ከጣና ከባሕሩ ውስጥ አለች ። ያብሬቱም ትልቅ ደብር ናት፤ ነገሥታቱ ተቀብረውበታል ስማቸውም ቀጥሎ እንደተጻፈ ነው ዓለም ሰገድ ኢያሱ ። ጻድቁ ዮሐንስ ፡ ሰልጣይ ዳዊት እነዚህ ናቸው። ንግበእኬ ኀበ ጥንተ ነገር ነውና ወደመጀመሬው እንመለስ በዚች ምጥርሃ ማርያም በምትባለው ያሉ የሚያገለግሏት ካህናት ደንገል የሚባል ታንኳ የሚሆነው የሚበቅለው በጉጃም አውራጃ በባሕሩ ድምበር ከዚያ ስለሆነ የሚበቅለው በሰው አገር ያለ እቃ፤ መሣሪያ መክበሩ አይቀርምና ፥አንዱ ታንኳ መግዣ ፲፭ና ፳ ብር ስለሆነ ከውጭ ሰው በሞተና በዓመት በዓልም ጊዜ ከሰው ብዛት የተነሣ የሚገቡበት ታንኳ እያጣ ደብሬቱ እንደሰማይ ርቃው አንጋጦ እያየ ይቀር ነበር ከባሕሩ ድምበር እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ንጉሥ ለሰራዊቱ አዛኝ ነውና ደጉ ንጉሣችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የባሕር ጀልባ ያመጡልናል በማለት ሕዝቡ በሙሉ ተስፋ ነው አሁንም የደጉ ንጉሣችን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ደግነታቸውን ለማስረዳት በጉጃም አውራጃ የበቀለው ታንኳ የሚሆነው ደንገል እስከነመሬቱ በዙርያውና በውስጡ የበቀለው ትልልቅ ዛፍ እንዳለ ተነቅሎ መጥለቅ የሚገባውን ትልልቅ ዛፍና መሬት እንደያዘ በባሕሩ ላይ እንደ መርከብ እየበረረ ከጉጃም ዳር ተነቅሎ መጣ ከባሕሩም መካከል በደረሰ ጊዜ ሲታይ ከዛፉና ከደንገሉ መርዘም የተነሣ እንደ ትልቅ ተራራ መስሎ ይታይ ነበር ሕዝቡም እንደ ትልቅ ተራራ መስሎ ባታየው ጊዜ ዓሣ ነባሪ ይሆን ወይስ ሌላ ነገር ይሆን ከኃጢአታችን ብዛት የተነሣ ምን መጣብን እያለ ይጨነቅ ጀመር በታንኳም ሔዶ እንዳያየው ሥጋ ፈሪ ናትና ወይስ መንፈስ ጋኔን እንደሆን እያለ ፈርቶ ቀረ ኢየኃድጋ ለሀገር ዘእንበለ ኄር እንዳለ ክቡር ደጃዝማች ካሣ መሸሻ በሰሙ ጊዜ መንግሥታቸውንና ንጉሣቸውን አክባሪ ስለሆኑ ደህና ደህና ጉበዛዝቶች ታንኳ የሚያውቁትን አሽከሮቻቸውን ገብታችሁ እዩት ብለው በፍጥነት አዘዙ የተአዘዙትም አሽከሮች ፥ጌታቸው፡ ቃል ለማጎደል አይችሉምና ሰው ሁሉ ለመግባት የፈራውን አበራ ስምንቱ በ፫ት ታንኳ ፪በአንድ መርጫ ታንኳ ሁነው ብረታቸውን እንደያዙ ማልደው በ፩ሰዓት ገቡና በ፬ት ሰዓት ደረሱ ደንገል መሆኑንም ካዩት በኋላ ይህስ ወላዲተ አምላክ በፈቃዷ ያመጣችው ነው ብለው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ መመለስ ጀመሩ ሕዝቡም የነሱን መመለስ እየተጨነቀ ምን ያገኛቸው ይሆን እያለ ሲጠብቃቸው ነበርና ደስታውን ለመናገር እኔ እቀድም እኔ እቀድም እየተባባሉ በታንኳው መቀዳደም ጀመሩ በመርጫ ተንኳ የተቀመጡ ሁለቱ ቀደሙና ለሕዝቡ ሁሉ ደስታውን ገለጡ ደጃዝማች ካሣ መሸሻም ቀጥሎ የተጻፈውን ተናገሩ ለደጉ ንጉሣችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለደጊቱ ንግሥታችን ለዳግማዊት እቴጌ መነን ረጅሙን ዕድሜና ጤና ሰጥቶ መንግሥታቸውን ሺህ ዓመት ያድርግልን ብለው በጨረሱ ጊዜ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ እንደቃልዎ ያድርግልን ብሎ በአንድ ቃል ተናገረ የመሬቱም ስፋት ፴፫ ክንድ ነው በኅዳር ፯ቀን የተነቀለ ከዛፉና ከመሬቱ ብዛት የተነሣ በኅዳር ፳፩ቀን ስተበረከችው ምጥርሃ ማርያም ደረሰና ከባሕሩ ድንበር ተተከለ ይህንም ልጽፍ ያሳሰበኝ በቀድሞ ነገሥታት ያልሆነውን ዛሬ በደጉ ንጉሣችን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ስለ ተደረገ ኢሰማዕነ ወኢርኢነ ወኢነገሩነ አበዊነ ያለው ቃል ደረሰ የደጉ ንጉሣችን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ምሳሌ መሆኑን ስለተረዳሁት ለመጻፍ አሳሰበኝ ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ የበዛውን አሳጥራችሁ ያልጠራውን አርማችሁ እንድታነቡልኝ እለምናችሁአለሁ ።

ታናሽ ወንድማችሁ ክነፈ ርግብ ተድላ ዘብሔረ እንፍራዝ

የጥያቄ መልስ።

መጋቢት ፳፱ ቀን ከደባባይ ውዬ ወደ ማረፊያ ቤቴ ስሔድ ፫ልጆች እርስ በርሳቸው እየተጨቃጨቁ ሲሔዱ አገኘኋቸው ምነው ምን ያጣላችኋል ወዴትስ ትሔዳላችሁ ብላቸው ባንዲት ልጃ ገረድ ምክንያት እኔ ላግባ እኔ ላግባ በማለት ተጣልተን ክቶ ትስብእተ ወልድ አግዴ ብንሔድ እኔ ሥራዬ ጽሕፈት ስለሆነ የተነጋገራችሁትን ሰምቼ እጽፋለሁ እንጂ ለማነጋገር ሥልጣን አልተሰጠኝም ብለው ንግግራቸውን ጽፈው ወደ አቶ ዳኝነት ሰደው ነበርና አቶ ዳኝነትን አጥተን እንባክናለን ምናልባት ታውቃቸው እንደሆነ ያሉበትን አመልክተን አሉኝ እርሳቸውስ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አደባባይ አይጠፉም ፍርዳቸውም እጅግ ደስ ያሰኛል። እነሆ እኔ ብርቱ ሰው ፥ስቴን ልውሰድብህ ብሎኝ ጭቅጭቅ ተጀመርሁ ፲፯ ዘመኔ ነው እርሳቸውም ዘወትር በቀጥታ ይፈርዱልኛል ነገር ግን ባላጋራዬ ኃይለኛ ስለሆን ፍርድዎን እየጣሰ እምቢ አለኝ ብላቸው ፩ ቀን በችሎት ተገኝተው የፈረዱትን ነገር አልቄርጥልኝ ብለው የከተማ ረኃብ ይጫወትብኛል እኔን ያገኘ እንዳያገኛችሁ ምናልባት ብትታረቁ ነገራችሁን አላይላችሁምን አልኳቸው ምን ከፋና ተሆነልህ ይህን ወረቀት እያየህ ገላግለን ብለው ወረቀቱን ሰጡኝ እኔም ወእዕይንትየኒ ደክማ በተዕናስ ያለው ከኔ እጅግ አይርቅምና ረቆ አልታየኝ አለ መራቀቅ የሚባል መነጽር ከኪሴ አውጥቼ ብመለከት ጥቂት፤ጥቂት ስለታየኝ ወንድሞቼ ይህስ ነገራችሁ ክቶ ትስብእተ ወልድ

እስቀድመው የነበሩት ሰዎች የተናገሩትን ይመስላል ባላጋራ የበዛበት ፩ ድኃ የተባለ አዳም ነው። ደም ግባቷ ያማረ ልጅ የተባለች የአዳም ነፍስ ናት። ንጉሡም አብ ነው ወራሽ ቄራሽ ይሆነኛል ያልሁት ፩ የበኵር ልጅ ነበረኝ የዛሬ ዘመን ልጅ አዳሩ በራሱ ፈቃድ በሆነ ያንተን ልጅ ታባገባው ሙቼ እገኛለሁ ብሏልና ልጅህን ለልጄ ስጥ ማለት ዕብ ፩ ፪ ነገረን በወልዱ ዘረሰዮ ወራሴ ለኵሉ። ቈላስ ፩ ፲፭ በኵሩ ዘላዕለ ኵሉ ተካበሩ። ኤፌ ፩ ፲፩ ወረድአነ በከመ ምክረ ፈቃዱ የሚባል የልጁ ሥጋዌን ማዘጋጀቱን መናገር ነው። መኰንንም የተባለ ወልድ ነው የኔ ማዕድ ተዘርግቶ የሚበላው ጠፍቶ ማለት ዮሐ ፮፶፩ ወዝኒ ኅብስት ዘእሁብ እኔ ሥጋየ ውእቱ በእንተ ሕይወተ ዓለም ቢላቸው እፎ ይክል ዝንቱ የሀበነ ሥጋሁ ንብላዕ ማለታቸውን መናገር ነው። አንተ በችግር እየተጐላላህና ባላጋራ እየጠፋህ በመኖርህ በጣም አዝናለሁ አንተንም ከባላጋራህ እጅ አወጣሃለሁ ማለት ማቴ ፳፮፴፰ ተከዘት ነፍስየ እስከ ለሞት መጽአ ወረድአሙ ለአለ ሀትዔገሉሙ ሰይጣን ያለውን ይመስላል። አሁንም ለትዳር የምትሆን ደም ግባቷ ያማረ ልጃ ገረድ ከቤትህ አይቻለሁና ጋብቻውን ፈቅደህልኝ ድግሱን ደግሼ ሥጋውንና ጠጁን አዘጋጅቼ መጥቼ እንድወስዳት ፈቃድህ ይሁን ማለት፣ ምሳ ፱ ጥበብ ዘብሐት ዘቢአሃ፣ ጥብሐ ወቶስሐት ውስተ ሰያሐ ዘዚአሃ ወይነ እንዲል ያንተን ሥጋ ተዋሕጄ ሥጋዬን ቈርሼ ደሜን አፍሼ አድንሃለሁ ማለቱን መናገር ነው። ሽልማት አስመ አልባሰከኒ ልብሰ ሕይወት ወልብሰ መድኃኒት ያለውን፣ ሀገር ወበኡ ውስተ ሀገር ቅድስት ያለውን ይመስላል።

አንድ ሀብታምም የተባለ መንፈስ ቅዱስ ነው ሀብትከ ሠናይ መንፈስ ቅዱስ እንዲል በየጊዜው እህል በስወፃሁ ቀጥር ለማንም ድኃ ምርቱን እያፈሰስሁ ስሰጠው አንተ ብቻ እስከ ግርዱ አለማግኘትህ ያጸጽተኛል አሁንም ያህን ያረባሁትን የቀንድ ከብትና በግና ፍየል ወራሽ ያደረግሁት ልጅ ነበረ። ያንተን ልጅ ወዶ ሊሞት ነውና እንድትሰጥልኝ ይሁን ማለት በተፈጥሯቸው ድኖች ለሚሆኑ መላእክት በየጊዜው ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ሲሰጣቸው ለአዳም ስንኳን ደገኛው ሀብት የዓረቡኑ ሀብት ተከልክሎበት ስለኖረ ወኵሎ አግረርከ ሎቱ ታሕተ እገሪሁ አባግዐኒ ወኵሎ አልሕምተ ተብሎ የተነገረለት የወልድ ሥጋዌን መንፈስ ቅዱስም ማዘጋጀቱን መናገር ነው ወገብረሁስ ለውእቱ ሥጋ መንፈስ ቅዱስ እንዲል ያም ድኃ የሦስቱንም ወረቀት አይቶ የኔን ልጅ ለማግባት የፈለገ የዓሥር ዓመት መንገድ ሒዶ ስድስት ዓመት ተምሮ በጥበብ የበለጠ ይውሰዳት አለ ማለት አዳም ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልድ ዓሥርቱ ቃላተ ኦሪትን አጽንቶ በድስቱን ቃላተ ወንጌልን ሠርቶ ያድናኛል ብሎ ተስፋ አደረገ እንጂ አብ መንፈስ ቅዱስ ሰው ሁነው ያድኑኛል ብሎ ተስፋ አለማድረጉን መናገር ነው። ከዚህ ስደርስ አስቀድሜ እንደ ተናገርሁ ያይኔም ድካም እንደሆነ ወይም ከጽሕፈቱ ላይ ሕፀፅ ምሳሌ የሚባል ወኃ ነጥብ አጥፍቶትም እንደሆነ ኣላውቅ አልታየኝ ብሎ ስቸገር እኒያ ልጆች አንተ ሰው ሦስቱም የዓሥር ዓመት መንገድ ሒደው ስድስት ዓመት ተምረው ለአንዱ ጋራና ተረረ ጨለማና ደመና ሳይከለክለው ዓለሙን ሁሉ እንደ መስተዋት የሚያሳይ ዕወቀት ተገለጸለት። ለሁለተኛውም ሰው ከሞተ በኋላ ሦስት ሰዓት ሳይሞላው ከሞት የሚአስነሣ ዕወቀት ተገለጸለት ለሦስተኛውም የአሥሩን ዓመት መንገድ በአምስት ደቂቃ የሚአደርስ እውቀት ተገለጸለት ማለትና እኔ ላገባ እኔ ላገባ በማለት ሦስቱም ተጣሉ ማለት በሥላሴ ላይ ተምሮ ጥቦብ መኳንትንና በንድ ብንድ ጥበብ መወሰንን እኔ ሰው ልሁን በማለት መጣላትንም ያመጣብሀልና ይህንስ ትተህ እኛ የተጣላንበትን ፍረድልን አሉኝ የናንተስ ነገር እጅግም አያጥረኝ የሦስታችሁም ጥበብ የተተካከለ ስለሆነ ምንም ጥበቡ ከጥበባችሁ ባይበልጥ አስቀድሞ መረኹ ብልጫው ነውና አስተደሞ ያጩ ሲያገባት ይታየኛል ስል ፈረደሁ ብዬ ሳልጨርስ ለብርሃንና ሰላም አስታውቃለሁ።

ደብተራ አድማሱ ዘዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ።

ጅማ ሀብታሙና ለምለሙ ሀገር

እስከሁን ሲደነቅና ሲመሰገን ይኖር ነበር በ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ልምላሜው እየደረቀ ሀብቱ እየጐደለ መሔድ ጀመረ የሰማኋቸውንና ያየኋቸውን ምክንያቶች ከዚህ ቀጥለው ባሉት መስመሮች ጽፌአቸዋለሁ። መጀመሪያ የልምላሜዋና የሀብቷ መሰረት ብልሁ አባ ጅፋር በየ ጊዜው አዋሳኞቻቸው ባላባቶች ለትልቁ ንጉሠ ነገሥት ለዳግማዊ አፄ ምኒልክ አንገዛም ብለው እየተዋጉ ሀገራቸውን በጦር ሲያስጠፉ ብልሁ አባጅፋር ግን ዓቅማቸውን ገምተው ልዋጋ ሳያሉ ሀገራቸውን ሳያስጠፉ በሰላም ተገናኝተው በፍቅር ተጠምደው አኖሩት። (፬፻) ይህንኑ ሀገራቸውን ለመጠበቅ ጃንሆይን አስፈቅደው ሶስት መቶ ብረት ተቀብለው ያማረ ወታደር አሰድረው የሀገራቸውን ጠረፍ አስጠበቁ ከመጀመሪያውም ማዕርግ እስከ ፊታውራሪ ለመሾም ፈቃድ ተቀብለው ስም መስጠት ጀመሩ።

ይኸውም ሀገራቸው ከሊሙ ከጐማ ተጌራ ተከፋ ተኰሎ ተኩንቻ ተጃንጅሮ ተጣደሌ ተዋሳኝ ስለ ሆነ በነዚሁም ጠረፎች አቅራቢያ ያሉ ሀገራቸው ምድረ በዳና ያራዊት መኖሪያ ስለ ሆነ ጥንት በኋላ ዘመን የነበረ ኬላቸው እማህል አገር ውሥጥ ስለነበረ ያማረ ወታደር እያበረከቱ ብረት እየሰጡ ሀገራቸውን ማልማት ጀመሩ። ግብር የሰለቸህ ሁሉ ተኬላ ውጭ እየሔድህ አቅና ያቀናኸውንም ርስት አድርጌልሃለሁ። ግብርህንም እስከ ሦስት ዓመት ምሬሃለሁ ብለው አዋጅ አደረጉለት። የሀገራቸውም የጐረቤታቸውም ሕዝብ መሬት የሌለውና ግብር የሰለቸው እየገባ ማቅናት ጀመረ ጠረፋቸውንም ሁሉ ለም አድርጎ የጅማን ሀብት እያሰፋ ቡን ተክላና ጥጥና [illegible] በሬ አበርክቶ ይሠራ ጀመረ። ይኸውም ሊታወቅ በጅማ ብዙ ቡን የሚገኘው በከፋ ወገን ቃንቀቲ በጌራ ወገን ሳዶር በጐማ ወገን ጉሬዶ በሊሙና በጐማ ማህል ማና ነው በዙሪያው ያለ ቆላው ግን በርበሬና ጥጥ ይበዛዋል ማህሉ ጅማ ግን እህል እንጂ የቡና ሀብት የለውም ሕዝቡም የሚበዛው በዚሁ ባዱሉ ቅኝ ላይ ነው የጐረቤቶቻቸውንም ሀብት በብልሃታቸው

ወደ ሃገራቸው አገቡት ሀገራቸውንም ሀብቱንና ልምላሜውን አበረከቱለት የሀገራቸውንም ጋላ አረስ ነግድ የሚጠብቅሀ ያማሬ ዘበኛ አድርጌልሃለሁ አሉት ባላገሩም በጅ ሥራና በንግድ በቡን ተኮላና በርሻ የሠለጠነ ሆነ በዙሪያቸውም ያሉ ጕረቤቶቻቸው ባላባቶች ገባሬችንን ወሰዱብን ሀብታችንን ተከፈሉን ቢሉ በዚህ አባ ጅፋር አይታሙም የራሱን ቤት ያልጠበቀ የሌላውን ሊያድን አይችልም እንደተባለው ነው አንድ አንድም የሚተሙበት ነገር ቢኖር ሰጪ ባልኖሬቸው ተቀባይ አይሆኑም ነበርና ደጉን ሥራቸውን በዚህ አንለውጠውም ።

ነገር ግን ምንም ብልህ ቢሆኑ ሽምግልናና ደዌ ከሰው የማይለዩ ስለሆኑ ከ፲፱፻፲፮ ዓመት ጀምሮ እስከ ፲፱፻፳፫ ዓም ሕመማቸው እየበዛ ስለ ሔደ ለዘውድ በዓል ክብር ቢጠሩ መሔድ ስላልቻሉ የልጃቸውን ያባ ዱላ ጐይታን ልጅ አባ ጆቢርን ላኩ ከዘውድ በዓልም በኋላ እንደራሴነትን ሰጥተው ወደ አዲስ አበባ ላኩት ። ፫ኛ አባ ጆቢር ከአዲስ አበባ ተመልሶ የሳቸውን ስራ ያሻሻለ መስሎት ጠረፍ ጠባቂ ነደረጉዋቸውን ያማሬ ወታደሮች ጣል ጣል እያደረገ የጅማን ተወላጅ ወጣቶች ብረት እያደለ ኰት እያለበሰ ባገር ውሥጥና በጠረፍ ዘበኛ እያደረገ በየአውራጃው እየሾመ መላክ ጀመረ. እነዚሁም አዲስ ወታደሮች ያገር ፍቅር ያልተማሩ ስለ ሆኑ የማያውቁትን ጠመንጃ ያዙና ከነዚሁም አንዱ ባልንጀራውን ና ወንድሜ ሥጋ አምሮኛልና ድኩላ እንግደል ቢለው ሁለተኛ ባልንጀራው ግን ወንድሜ ተኵስ መቼ ተማርን እንዲያው ብና ጮህበት ይሞት ይመስልሃል? ሮጦ እጫካ ይገባል እንጂ አንተ ሞኝ ይልቁንስ እኔ ልምከርህ የማይሸሽ ለማዳ በሬ ላም ፍየል በግ ሞልቷል ሌሊት ጭር ሲል ከንድ ባላገር ቤት እምስት ጥይት ተኵሰን በሬኦችንን ነድተን እጫካ አርደን ሥጋውን በልተን ቆዳውን ለደላላ ብንሰጠው ጥይት ያመጣልናል ብሎ ቢመክረው ይኸውም ምክር ለአዲሱ ወታደር የተስማማ ሆነለት እነዚሁንም የማይሸሹ ለማዳ እንስሶች ማደን ጀመሩ ከዚህ በኋላ የመከረኛው ባላገር ጭንቅ በየጊዜው እየጠናበት ሔደ ይኸንኑም ትምህርት አዲሶቹ ዘበኞች በጥቂት ጊዜ አጥንተውት ዋናው ኃይላቸው ማና በሚባለው ሀገር ላይ ስለ ወደቀበት ባንድ ጊዜ ግብር ሃያ ስድስት ሺህ ብር የሚያወጣው አገር ጠፍ ሆኖ ከሞት የተረፉት ባላገሮች ወደ ጐማና ወደ ሊሙ ሸሹ። ክቡር ጅማ አባጅፋር ግን መንግሥታቸውን በቅን እንዳገለገሉ እግዚአብሔርን በድለው አስቀይመውት እንደሆነ ነው እንጂ በብዙ ድካም ያለሙትን ሀገራቸውን ዓይናቸው እያየ ጆሮአቸው እየሰማ በሕይወታቸው ሳሉ ጥፋቱን እያሳያቸውም ነበር።የጥንቱ አሽከሮቻቸውን አማሮቹ ለጋላ ወታደሮች በታቸውን ለመስጠት እርስ በራሳቸው መፋጀታቸው ያሳዝናል። ይኸንን በፋክክር ከክብረት ወደውርደት ከለምነት ወደ ጠፍነት ከልምላሜ ወደ ድርቀት የተለወጠው ሀገር በጭራሽ ሳይጠፋ ከዚህ ከደዌ የሚፈውሰው ሐኪም ካላገኘ ወደ መራራ ሞት እንዳይደርስ ያሳስባል ጥፋቱን ግን ባንድ ጊዜ ለመግለጽ ላንባቢዎች አሰለቻለሁ ብዬ ተውሁት እንጂ የጥፋቱ ምክንያት ይህ ብቻ አይደለም ። ያገሉ አባወሉ ።

የተሳሳተውን መግለጫ ።

የቤተ መንግሥቱ ገቢ ገንዘብ ከቀድሞው ይልቅ እየበረከተ መሔዱን ባዲስ አበባ ጉምሩክ ገቢ ብቻ ለማስረዳት ተብሎ ሚያዝያ ፲፫ ቀን በቍጥር ፲፮ በብርሃንና ሰላም በመጀመሪያው ገጽ ተጽፎ ያነበብነው የ፯ ወር ገቢ ፪ሚሊዮን ፪፻፷፯ሺ ፷፮ ብር ከ፲፭ «ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሥልሳ ሰባት ሺህ ሥልሳ ስድስት ብር ከአሥራ አምስት መሐለቅ» በድምር መሳሳቱን ተመልክተን ከምናው ገቢ የዘንድሮው ብልጫ ተብሎ የተጻፈውም እንኳ አንባቢዎች ከታክሱ ጋራ እንዳይመስላቸው ብለን ቀጥሎ እንዳለው ባጭሩ ልናስረዳቸው እሰቡን ።

፩ኛ ፤ አምና ከመስከረም ፩ ቀን እስከ መጋቢት ፴ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ድረስ የአዲስ አበባ ጉምሩክ ጠቅላላ ገቢ ልክ ፩ሚ፯፻፹፭ሺ.፱፻፴ ብር ከ፲፬ መሐለቅ «አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ብር ከአሥራ አራት መሐለቅ» ሆኖ ከዚሁ ፳፱ሺ.፱፻፺፬ ብር ከ፱ መሐለቅ«ሐያ ዘጠኝሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ብር ከዘጠኝ መሐለቅ» የታክስ ዳክሲጊና ደክንሲማሲዮን ገቢ በውሥጡ ነበረበትና ያለታክስ የቀረው ዓይነት ገቢ ሲታሰብ ልክ ፩ሚ፯፻፶፭ሺ.፱፻፴፮ ብር ከ፭ መሐለቅ « አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ አምሳ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ስድስት ብር ከአምስት መሐለቅ»ብቻ ነበረ ።

፪ተኛ ፤ ዘንድሮ ከመስከረም ፩ ቀን እስከ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም ድረስ የአዲስ አበባ ጉምሩክ በጠቅላላው የገባው ገንዘብ ሲታሰብ ፪ሚ፪፻፷፯ሺ.፰፻፮ ብር ከ፲፭ መሐለቅ «ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሥልሳ ሰባትሺህ ስምንት መቶ ስድስት ብር ከአሥራ አምስት መሐለቅ » ሆኖ ከዚሁ በ፬፻ሺ.፭፻፸፮ ብር ከ፲፬ መሐለቅ የታክስ ገቢ በውሥጡ አለበት ዳሩ ግን የታክሱን ገቢ ከጠቅላላው ገቢ ላይ ስናነሣለት ፩ ሚ፰፻፷፯ሺ.፪፻፴ ብር ከ፩መሐለቅ «አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሥልሳ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሠላሳ ብር ከአንድ መሐለቅ» ይተርፋል ። ይሁን እንጂ የታክሱን ገቢ ሳይታሰብ በ፲፱፻፳፫ ዓ ም በ፯ ወር ውሥጥ የገባውን ፩ሚ፯፻፶፭ሺ.፱፻፴፮ ብር ከ፭ መሐለቅ « አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ አምሳ አምስትሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ስድስት ብር ከአምስት መሐለቅ» በ፲፱፻፳፬ ዓ ም እንደዚሁ በ፯ ወር ውሥጥ ከገባው ፩ሚ፰፻፷፯ሺ.፪፻፴ ብር ከ፩ መሐለቅ ላይ እርግጠኛው ብልጫ ንለማግኘት አመዛዝነን ስናጐልለት የዘንድሮ ገቢ ከምናው ገቢ በ፯ ወር ውሥጥ ኖር ብሎ ያለ ታክስ ልክ ፩፻፲፩ሺ.፪፻፺፫ ብር ከ፺፮ መሐለቅ በልጧል ነገር ግን ብልጫው ከነታክሱ የሆን እንደሆነ በ፬፻፹፩ሺ.፰፻፸፮ ብር ፩ መሐለቅ «አራት መቶ ሰማንያ አንድሺህ ስምንት መቶ ሰባ ስድስት ብር ከአንድ መሐለቅ» ይሆናል ። ይኸውም በዓለም ሁሉ የገንዘብ ችግር ጸንቶ ንግድ እንደቀድሞው በማይንቀሳቀስበት ሰዓት የታክሱ ገቢ ሳይጨመር ይህን ያህል በመብለጡ ታላቅ ዕድል ነውና በዚህ ዓይነት

ዋመንግሥቱ ገቢ ደስ ያሰኛል በገል ላንባቢዎች እናዋያለን ።

የአዲስ አበባ ጉምሩክ የመጀመሪ ማዕርግ ዋና ኤ ር
ብርሃን ሥላሴ አበዩሬ ።



ጨካኝ ሞት

ወይዘሮ ሐመረ ሥላሴ የምትባል በሬት የመድኃኔ ዓለም አጋፋሪ የነበረው አሁ፤ም እማዘጋጃ ቤት በፍርድ ሥራ ክፍል በዋና ሥራ ላይ የቆመው ያጋፋሪ በየነ ባለቤት ጠበየ መልክም ቆንጆ ባለሟያ ሁሉንም አሟልቶ የሰጣት ገና ወጣት ልጅ ነበረች እንደወንጌሉ ቃል ከባሏ ጋራ በሕግ ተጋብተው በሥጋ አምላክ ተወስነው እግዚአብሔርም ንብረታቸውን አቃንቶ ፍሬም ሰጥቷቸው ሬን ባሩስ እየወለደች ከባሏ ጋራ በሰምምነት ደስ ብሏቸው ሲኖሩ መቼም የዚህ ዓለም ነገር በደስታ አይፈጸምምና መጀመሪ በመንግሥተ ሰማያት እጠቀምበታለሁ ብላ ደመቀች የምትባለዋን ያባ ሀብተ ማርያምን ልጅ እንደ ጡት ልጅ አድርጋ አሳድጋ ድራት በተዳረች ባመቷ በዕንስ ምክንያት ታማ በተወለደች ባ፲፮ ዓመቷ መጋቢት ፳፫ ቀን በድንገት ስላሞተች ለሷ ደረቷን ጥላ አለመጠን አዝና ሙሉ ሳለ መቼም ሙት ለሙት ያለቅሳል እንደ ሚባለው እሱዋ ደግሞ ብ፲፱ኛው ቀን በሚያዝያ ፳ ቀን በድንገት ታማ የ፱ ወር ሕፃን ጥላ ሙታ የሴት ወይዘዝሩና የወንድ መኳንንቱ ተሰብስበ ብግሬ ፍታት፣ በብዙ ክብር በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተቀበረች። ዕድሜዋም ፳፱ ዓመት ነበር ልጆቿም ጥበቡ፥ ተናኝ ግርማ፥ እንባዳ ወርቅ፥ ላቀች ይባላሉ መቼም እኅቶቿና ባልንጀሮቿ ወዳጆቿ ሌላውም አላሬ አግዳሚው ሁሉ ሲያለቅስ ላየው ሰው እጅግ ያስገርማል።

ልቤም ይህን አይቶ እንዲህ ሲል በኀዘን እንጕራጕረ ።
መውለድ ቀጭን ፈትልን እንደሱዋ ማን ያውቃል ።
ጥበቡን እያየ ሰው ሁሉ ያደንቃል ።
እንደሱዋ ማን አለ ዕድልን ያገኘ ።
መልክም ሥራነቷ በሁሉም ተናኘ ።
ምን ጥላ ነበረው እቶ በየነማ ።
በሱዋ ተገኘ እንጂ ይኸ መልክም ግርማ ።
አሁን ባጉል ሰዓት የት ትሔጃለሽ ።
እንዲያው በባዶ ቤት እንግዳ ጥለሽ ።
መልክም አስተዳደሩ ይዛ ነበረች ።
አሁንማ በቃ ከሁሉም ላቀች ።
ትኵስ ወተት ነበር ለልጆቿማ ደጉ ።
ጥገቷ ከቆመች በባዶ ይደጉ ።
አቶ መቃብርን በምን ወደደችው ።
በኔ ሞት እያለች ሥጋ ጋበዘችው ።
እንደዚሁ እያለች ጋበዘችው በውል ።
የጁን ሥጋ ጕረስ ለኔ ፍቅር ስትል ።
አፈር ስሆንልህ ዓይኔ ፍስስ ሲል ።
አቶ ሞትም መጣ አፉን አሾትሎ ።
የሥጋ ዕዳ አላባት አስከፍሉኝ ብሎ ።
ተሟገታ ተረታች ሰማኒያውን ከዳ ።
ወደዚያው ተያዘች በዚያው በሥጋ ዕዳ ።
ሰማኒያውን ቢሆን አስቀረው ጨፍጭፎ ።
የሥጋውን ዕዳ ተቀበለ አትርፎ ።
ለኛ እንዘን እንጂ ባለነግበኔዎች ።
እሱዋስ ተወጣችው ዕዳዋን ከፈለች ።
አጋፋሪ እንግዲህ እግዚአብሔር ያጥናህ ።
ከሁሉም ከሁሉም አንተ ተጐዳህ ።

ትሰብእተ ወልድ አግዴ ።

ማስታወቂያ ።

አርስባለብ የተባለ መጽሐፍ ዋጋው አንድ ሩብ ።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያና የግርማዊት እቴጌ መነን ባለ ዘውድ ሥዕል ። ደግሞ የንግሥ ቸው መታሰቢያ ሥዕል በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት በአንዳንድ ሩብ ይሸጣል ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አዳመቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍቶዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ክንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመመጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቀን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር እምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምበሳል ፥ የልብ፡ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግጋርና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።



ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

የስፌት መኪና ኩባንያ ሴንጀር በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ አጠገብ ብለው ሰቃ መሸጫቤት የተሰናዱትን ጥቅም ያላቸውን ሰቃዎች መጥተው እንዲጐበኙለት በማክበር ያመለክታል

በያይነቱ የተሠሩትን ጥልፎችና ብጋጃዎች ዳንቴል በአንድ ቃል ጥቅም ያላቸውን የእጅ ሥራዎች ሁሉም በሴንጀር የስፌት መኪና የተሠሩ ናቸው

ይኸንን የእጅ ሥራ ለማየት እንዳይቀሩ ።

(ኤክስፖዚሲዮን) የሚታይበት ቀን ዘወትር ከታኅሣሥ ፳፩ ቀን ጀምሮ እስከ ጥር ፫ ቀን ድረስ ነው ።

ለማየት ዋጋ አይከፈልም ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል እስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል ።

ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ፕናው አሰናጂ ባዚል እስላኒዲስ

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውስጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮላታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅደስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድ ትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም
ALEM

በያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።





ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፒር ዳኔዮ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ውሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(በታችውም ዘአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዴር አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት ከወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፤ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ጆልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን በርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ፦

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፌ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፳
8^{me} ANNE. № 20

ሐሙስ ሚንበት ፬ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 12 AVRIL 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሚአስ ደንቅ ሠርግ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን የልዑል ራስ ሥዩምን ልጅ ልዕልት ወለተ እስራኤልን በሚንበት ፩ቀን እንዲያገቡ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ ታደረጉ ቈይተዋል። በመርዕድ አዝማችም ቤት ለእንጀራውና ለወጡ ፥ ለጠላውና ለጠጁ ለሚሰናዳውም ምግብ ሁሉ ታላቅ እኅታቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ በሚያስደንቅ ትጋት ሲያሰናዱ ሰነበቱ ። በውጭም ለሚሰናዳው ነገር ሁሉ ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው፤ክቡር ደጅ አዝማች ወዳጄ ናቸው። የሁለቱም ቤት እጅግ የሚያስደንቅ ሁኖ ከተዘጋጀ በኋላ በሚያዝያ ፴ቀን የሕግ መወሰኛ የምክር ቤት አለቃ ክቡር ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ የቃል ኪዳን አባት ነበሩና ለማጫ የሚሆነውን ወርቁን፥ ብሩን፥ፈረሱን፥ በቅሎውን ልዩ ልዩ የሆነውንም የሽልማት ጌጥ ሁሉ አሲዘው ሔዱ።አብረዋቸውም ብዙ ታላላቅ መኳንንት ሔደው ነበር።መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ግን በቤታቸው ሁነው የዘመድ እንግዳ ሲቀበሉ አምሽተው ማታ ወደ ቤተ መንግሥቱ ወረዱ።ሠርገኞቹም በደረሱ ጊዜ የልዑል ራስ ሥዩም ግቢ እጅግ አምሮ ተዘጋጅቶ ቈየ ። ልዑል ራስ ሥዩምም በአዲሱ ባሰደርብ ቤት ደረጃ ላይ አስነጥፈው ከፍ ባለው በረንዳ ላይ ወምበር አስዘርግተው ታላላቆችን መኳንንት በግራና በቀኝ አስቀምጠው እሳቸው በመሐል ተቀምጠው ነበር። እንደደረስን እነሱም ያንን የማይጠቅም አሮጌ ልማድ እንደ መናቅ አድርገውት ለምን ቈማችኋል አላሉም።ክቡር ቢትወደድ ወልደ ጻድቅም ፈሊጥ አዋቂ ሰው ናቸውና አሁን የቆምንበት ምክንያት ልጃችሁን ለልጃችን ሰጥታችሁ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አንድ እንዲሆኑ ብለን ነው ይህንንም ቃል ኪዳን ነገ በቤተ ክርስቲያን እንድንፈጽመው የከበረ ፈቃዳችሁን እንለምናለን አሉ።የሙሽራይቱም የቃል ኪዳን አባት ክቡር ደጅ አዝማች ማሩ ነበሩና እሺ ልጃችንን ልዕልት ወለተ እስራኤልን ለጌታችን ለልጃችን ለኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ሰጥተናል አሉ።ክቡር ቢት ወደድ ወልደ ጻድቅም ልዕልት ወለተ እስራኤልን ለልጃችን ለጌታችን ለኢ. አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ተቀብለናል አሉ።የማጫውን፥ የልብሱን፥የጌጡን ዓይነት በወረቀት ጽፎ ለማስረዳት እጅግ ችግር ነው።የአባት ልብስና የእናት ልብስ የሙሽራይቱ ልብስ በወርቅ የጠለቀ ነው ባንጽፍላችሁም ታውቁታላችሁ። የሞግዚት ልብስ የተባለው እንኳ እጅግ የሚያስደንቅ ነው የጥላውን ጌጥና የሴቶችን መሣሾማ ምን ይነገራል የሆነ ሁኖ በጠቅላላው መሣሾው ወርቅ ብቻ ልብሱ በወርቅ የጠለቀ ነው።ለመቶ ደንገጥሮች የተሰጠው ልብስ እጅግ ጥሩ ነው የተሰጡ ፈረሶች ፸፥በቅሎች ፲ ናቸው።ከነዚሁ ፲በጥሩ ወርቅና በብር ወርቅ ቅብ ቤነቻ የተጫኑ፥ ፳ው በነሐስ ቤነቻ የተጫኑ ናቸው። ፲ሺህ ብር ተሰጥቷል ቁጥሩን ብቻ በወረቀት ለማንበብ ብዙ ጊዜ የሚያስፈልግ ስለሆነ ወረቀቱን ጨምረው ሠራተኞች እንዲያስረክቡ ታዘዙ እንጂ ተቈጥሮ ታይቶ ቢሆን ጊዜውም አይበቃ ነበርና አይደረስም ነበር። ከዚህ በኋላ ለማደርያ ወደ ተሰናዳው ድንኳን አገቡን የድንኳኑም ስፋት እጅግ የሚያስደንቅ ነበረ።የምንጣፉ አነጣጠፍ፥ የመሰቡ አቀማመጥ መቼም የወይዘሮ ዓፀደ አስፋው ሙያ የታወቀነው። የወጡ ዓይነት ብዛትና ማማር፥የነጩ መለሳለስ፥ የጠጁ ማማር ሕዝቡን ሁሉ አስደነቀው። በነጋውም ብዙ ሽልማት አቅርበው በየማዕርጉ ለመኳንንቱና ለወታደሩ ሸለሙ።ጃንሆይም እቴጌም በመታሰቢያ ቤት ቤተክርስቲያን ገብተው የተክሊሉ ሥርዓት እስቲፈጸም ይጠባበቁ ነበር።ለመኳንንቱና ለወይዛዝሩ ማረፊያ ታላላቅ ድንኳኖች ተተክለው ነበር ። ቢትወደድ ወልደ ጻድቅና የቀሩት መኳንንት ሙሽራይቱን ወደ መታሰቢያ ቤት ይዘው ወጡ ። ልዑል አልጋ ወራሽም እቤተ ክርርቲያን ነበሩና ሊቀጳጳሳቱ አቡነ ቄርሎስ ለእውነተኞች ክርስቲያን የሚገባውን የተክሊል ሥርዓት አድርሰው ቃልኪዳን አጋብተው ሥርዓተ ቍርባኑን አድርሰው ሙሽሮቹ ሥጋውን ደሙን ከተቀበሉ በኋላ የግርማዊት እቴጌ መነን ተማሪዎች ወደ ቤተክርስቲያን ውሥጥ ገብተው አበባውን ሙሽሮቹ ወደ ተቀመጡበት እየበተኑ እንኳን ደስ አላችሁ የዘለዓለም ጋብቻ ያድርግላችሁ አልዋቸው።ክር ዲፕሎማቲኮችም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትንና ግርማዊት እቴጌን ለዚህ በዓል በመጠራታችን ደስ ብሎናል ፍጻሜውን ያሳምረው ብለው ለሙሽሮቹም ሰላምታ

ሰጥተው ሔዱ። ወደ ቤተ መንግሥቱ በሚወስደው መንገድ ወገንም ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ የሮማን ትምህርት የሚማሩ ወንዶች ተማሪዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር ዘመሩ። ከተማሪዎች ውሥጥ ሙዚቃ የሚነፉ ልጆች ሙዚቃውን ያሰሙሩት ነበር ። ከዚህ በኋላ ሙሽራይቱ እጅግ በሚአምረው ፮ ፈረሶች በሚስቡት ሠረገላ ተቀምጠው አክሊላቸውን ደፍተው ልብሰ ፀሐይ ለብሰው እጅግ ያምሩ ነበር ።ከሙሽራይቱ በግራ ወገን ሚዜው ደጃዝማች አበራ ካሣ ለዓይን የሚአንጸበርቅ የወርቅ ላንቃቸውን ለብሰው ተቀምጠው ነበር ። የኢትዮጵያ አልጋወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰንም ፮ ፈረሶች በሚስቡት በጥሩ ሠረገላ ተቀምጠው ጉዞ በጀመሩ ጊዜ መኳንንትና ሠራዊት ፈረሰኛና እግረኛ ሁሉ በመንገዱ ግራና ቀኝ ተሰልፈው የሚገባ ሰላምታ እየሰጡ ያሳልፉአቸው ነበር ። ሙዚቃና ጥሩምባው እምቢልታውና መለከቱ ሲነፋ ዓለም ያለፈ ይመስል ነበር ። ወደ ቤታቸውም በር በደረሱ ጊዜ ፲፮ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ በልፍኛቸው አጠገብ እነዚሁ አስቀድመን የጠራናቸው ተማሪዎች አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ያዘጋጀውን መልከም ምሥጢር ያለበትን መዝሙር ዘመሩ ።

የሴቶች ተማሪዎችም ነጭ ነጭ ርግቦች ይዘው ቆይተው ነበሩና ሙሽሮቹ ከሠረገላ ሲወርዱ ለቀቀዋቸው ።

ከዳራሽም በገቡ ጊዜ መሳፍንቱም መኳንንቱም ገብተው በሽምፓኝ ሲመርቁ ክቡር ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ሆይ።

ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለመላውም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደስ የሚያሰኘውን ትልቁን ሥጋዊና መንፈሳዊ ዕድል ያገኙበትን የዛሬውን ቀን ታላቅ የመታሰቢያ በዓል አድርገን ልናኖረው ይገባናል ።

በአባትዎ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በኢትዮጵያ የሚሠራው ሥራ ሁሉ ምንም አዲስና ጥቅም ያለው ቢሆን ባለፈውና በዛሬው ዓመት ለልዑልነትዎ የሠሩልዎ ሥራ ከሁሉ የበለጠ አዲስና ጥቅም ነው ።

ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት በገዛ ልጆቻቸው ይቀኑ ነበርና፣ ሲሞቱ ወይም በእርጅና ደክመው በቤት ሲውሉ አልጋ ወራሽ እገሌ ነው፤ እያሉ በኑዛዜ ያስታውቁ ነበር፤ ደጉ አባትዎ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጭነው በነገሡበት ዘመን ወዲያው የልዑልነትዎን አልጋ ወራሽነት ገልጠው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማስታወቃቸው ከተፈጥሮአቸው ቅናት የሌለባቸው መሆናቸውን ያስረዳናልና ትልቅ አዲስ ነገር ነው ።

ሁለተኛም ከዚህ አስቀድሞ በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት ልጃቸውን ሲድሩ ሙሽራይቱ ባለወገን እንድትሆንና ሠርጉ እንዲያምር ብቻ ያስቡ ነበር እንጂ በተክሊልና በቍርባን ለመኖር ማሰባቸውንና ማድረጋቸውንም አልሰማንም በታሪክም ተጽፎ አላገኘንም ደጉ አባትዎ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን ሙሽራዎ ባለወገን እንድትሆንና ሠርጉ እንዲያምር በማሰባቸው ላይ በመንፈሳዊም ወገን ክብርዎና ማዕርግዎ እንዳይጐድል በተክሊልና በቁርባን መዳራቸው ከሁሉ የበለጠ አዲስ ነገር ነው ።

ልዑል ሆይ

ይህ የዛሬው ጋብቻዎ የተባረከ ሁኖ ጃንሆይና እቴጌ እንደ አብርሃምና እንደ ሣራ፣ልዑልነትዎና ሙሽራይቱም እንደ ይስሐቅና እንደርብቃ ሁናችሁ እኔም እንደ አብርሃም ሎሌ እንደ ኢያቡር ሁኜ የምድር ሕዝብ ሁሉ በአብርሃም ዘር በይስሐቅ እንደተባረኩ የኢትዮጵያም ሕዝብ ሁሉ በጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘር በልዑልነትዎ የተባረኩ እንዲሆኑ የልቤን ምኞት እገልጻለሁ ።

ደግሞ ግርማዊ አባትዎ ይህን ሁሉ መልከም ሥራ እንደ ሠሩልዎ እርስዎም በቅን ልቡና ፈቃድ ፈጻሚና አገልጋይ ሁነው ዉረታቸውን እንዲመልሱ ልዑልነትዎን እለምናለሁ

እኛም ከዚህ ከዛሬው ከትልቁ የደስታ ዘመንና ቀን መድረሳችን ዕድለኞች መሆናችንን ያስረዳናል ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ሆይ

የደጉንና የብልሁን አባትዎን መንገድ ተከታይና ለኢትዮጵያ መልከም አሳቢ እንዲሆኑ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አባትዎና ለግርማዊት እናትዎ እቴጌ ለቤተ ዘመዶችዎም ሁሉ ረጅም ዕድሜ ከጤና ጋራ እንዲሰጣችሁ እየተመኘሁ ኢትዮጵያም ለዘለዓለም ትኑር እያልኩ ጽዋዬን እነሣለሁ ብለው በጨረሱ ጊዜ ከዳር እስከ ዳር ተጨበጨበ ።

የሰው ብድር አይቀር በምድር ።

ቀድሞ አፄ ዮሐንስ ኢትዮጵያን በሙሉ ሲገዙ የተከከለ ጋብቻዬ ንጉሥ ምኒልክ ነው ብለው ለአንዱ ልጃቸው ለራስ አርአያ ሥላሴ ንግሥት ዘውዲቱን መርጠው በሕግ በቃል ኪዳን አጋብተዋቸው ነበር ። አሁንም ሁሉ የሚቻላቸው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የአፄ ዮሐንስን መልከም ብድራቸውን ስለከፈሉ ሕዝብ ሁሉ እጅግ አመስግኑዋል ።

ለዚሁ በዓል ክብር ማክሰኞ በማግሥቱ ከግርማዊ ጃንሆይና ከግርማዊት እቴጌ በተለየ የተደገሰው በልዑል አልጋ ወራሽ ቤት በቢቶደድ ቀርበ ሠራዊቱ በሊጋባው ታዘ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ግብርና በዓል ሁኖ የበላውም የጠጣውም በደስታ እየመረቀ ሔደ ።

ከዚህም በኋላ በልዕልት ተናኘ ወርቅ የተሰናዳው ድግስ ለካህን ለነጋዴ ለተማሪዎች ለዘበኞች እንደዚህ ሁኖ እስከ ቅዳሚት ድረስ ሳምንቱን በተራ በተራው ይበላል ። አንባቢ ሆይ በዚህ ዕለት የተደረገው በዓል ፫ ታላላቅ ፍሬ ነገሮች ተገኝተውበታል ።

፩ኛ፡ለሕዝባቸው ሁሉ ምሳሌ እንዲሆን ጃንሆይና እቴጌ ልጃቸውን በተክሊል በቁርባን ሥጋዊንም መንፈሳዊንም ክብር ፈጽመውበታል ።

፪ተኛ፡ ሙሽሮቹ ለዚህ ዓለም ክብር ዓረበን የወዲያኛውን ዓለም ክብር እንዲወርሱ ተስፋውን አሳይተዋል ።

፫ኛ፡ ይመለከበት የነበረው የግንቦት ሦርግ አይገበም የሚባለው የክፉ ልማድ ገመድ ተቆርጦበታል ።

፬ኛ፡ የንጉሠ ነገሥቱ ዘር ግቢ በዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥትና ባዔዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት እንደተደረገው የማዕርጉና የክብሩ ልክ ታይቶበታል ።

፭ኛ፡ እንደ ዓለም ሕግ በዓለም ያሉ ነገሥታት ሁሉ እግዚአብሔርን አባት አድርገው አንዳንድ ሰው ልጆች ስለሚቈጠሩ ወዳውሮጳ ነገሥታት ከንጉሠ ነገሥቱ ያለፈው ቴሌግራምና ከነገሥታቱም የተመለሰው ደስ የሚያሰኝ ቴሌግራም ቤተ ዘመድ መሆናቸውን የሚገልጠው የመቀራረቢና ያንድነት የወዳጅነትም ሥርዓት ታይቶበታል።

እግዚአብሔር በቸርነቱ ለበጎ ሥራ መሪያችን የሆኑትን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን አቈይቶ የሙሽራውንና የሙሽራይቱን ግቢ የአብርሃምንና የሣራን ግቢ የባረከ አምላክ ባርኮ እንዲያሳየን ምኞታችንን በብርሃንና ሰላም እንገልጻለን ።

የጥበብና የትምህርት ሚኒስቴር ለሠርጉ በዓል ያደረገው ፕሮግራም ቀጥሎ የተጻፈው ነው

በኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ ሠርግ ሕዝቡ ሁሉ ደስ እንዳለው ተማሪዎቹም ደስታቸውን ለመግለጽ ምኞት ስለነበራቸው የትምህርት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር እንደራሴ አቶ ኪዳነ ማርያም አበራ ከሚኒስትር መልአከ ሕይወት ወልደ ሐና ጋር እየተማከሩ የተማሪዎቹን ሰልፍ አኳኋን አዘጋጅቶ ነበር የሰልፉና የተማሪዎቹ ደስታ መግለጥም ቀጥሎ ያለው ነው ።

፩፻ የሚያህሉ ተማሪዎች ከዲሬክተሮቻቸውና ከአስተማሪዎቻቸው ጋር በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ተሰብስበው ነበርና ሰንደቅ ዓላማቸውን አስቀድመው ሙዚቃቸውን እየመቱ ተሰልፈው አምሮባቸው ከጧቱ በ፪ሰዓት ወደ መታሰቢያ ቤት ቤተ ክርስቲያን ጉዞ ጀመሩ።በመንገዱ ያያቸው ሕዝብ ሁሉ በሰልፋቸው አኳኋንና በሙዚቃቸው ይልቁንም ሕፃናት በመሆናቸው በጣም ደስ ብሎት ፊቱ ፍግግ ፍግግ ይል ነበር። ተማሪዎቹ ሙዚቃቸውን እየመቱ ከመታሰቢያ ቤት በር በደረሱ ጊዜ አቶ ኪዳነ ማርያም ሒዶ ተቀብሎ እየመራቸው ሲመጣ የክብር ዘበኞች ሙዚቃቸውን እየነፉ ሰላምታ ስለ ሰጧቸው መኳንንቱና ሕዝቡ ልቡ በደስታ ተነክቶ፡ የእቴጌ መነን ተማሪዎች ለሙሽሮቹ የሚሰጥ አበባ ሰብስበው ነበርና እነሱ በስተፊት ሆነው ተማሪዎቹ ሁሉ በደምብ ተሰልፈው በመታሰቢያ ቤት ደጃፍ ቀጥ ብለው ቆመው ነበር ። ቅዳሴ ተቀድሶ የውጭ አገር ሚኒስትሮችና የኢትዮጵያ ሚኒስትሮች ለሙሽሮች ሰላምታቸውን ከቀረቡ በኋላ አበባ የያዙት አበባ የመሰሉት ሕፃናት ገብተው ለሙሽሮቹ አበባቸውን ሰጥተው የቀረውን አበባ ደግሞ በወይዛዝሩና በመኳንንቱ ላይ እየበተኑ ሲያልፉ ላያቸው ሰው በጣም ደስ አሰኙ።ቀጥሎም ፪ወንዶች ተማሪዎች ገብተው ግሩም የሆነ የወርቅ ብዕርና ግሩም የሆነ ፀጌጥ የተሠራ የብዕሩ ሥዕል ለልዑል አልጋ ወራሽ ሰጡ።በብዕሩ ሥዕል ላይ የተጻፈ ቀለም ቀጥሎ ያለው ነው፡ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን፤ ከብዕሩ ሥዕል በታች ደግሞ ዘጸሐፍኩ ጸሐፍኩ የሚል ነው። ስለዚህ ከሥዕሉ ቃሉ ከቃሉ ሥዕሉና ትርጉሙ የተስማማ ስለሆነ ያየ ሁሉ በጣም ደስ አለው። ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹ የኢትዮጵያን መዝሙር እያዜሙ ሙዚቃ መቱና መኳንንቱና ወታደሩ ቀጥ ብሎ ሰላምታ ከሰጠ በኋላ መኳንንቱና የውጭ አገር ሚኒስትሮች እየተሰናበቱ መሄድ ጀመሩ።ተማሪዎቹም እንደፊተኛው ተሰልፈው በፊት በፊታቸው መልአከ ሕይወት ወልደ ሐና ሰንደቅ ዓላማ አሲዘው በአቶሞቢል ቀስ ብለው እየሄዱ ሰልፉ አምሮባቸው ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ ግቢ አስቀድመው አልፈው ቆዩ። አቶ ኪዳነ ማርያምም ቀደም ብሎ አልፎ ነጫጭ ርግቦች ሰብስቦ በሕፃናቱ እጅ አስይዞ ነበርና ሙሽሮቹ የመጡ ጊዜ ወንዶቹ ተማሪዎች አቶ ዮፍታሔ የገጠመውን የሠርግ ሙዚቃ እየመቱ ሲያዜሙ ሴቶቹ ሕፃናት ርግቦቹን ቢለቊዋቸው በሙሽሮቹ ላይ ሲንሳፈፉ በጣም ደስ አሰኙ ይልቁንም አንዲቱ ነጭ ርግብ በልዑል አልጋ ወራሽ አክሊል ስላረፈች አንደቱ ነጭ ርግብ ደግሞ ሙሽራይቱ ወደ ነበሩበት ሠረገላ ገብታ እላያቸው ስላረፈች ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘኪያሁ ሠመርኩ ወሎቱ ስምዕዎ ከሚለው ቃል በመስማማቱ ሰው ሁሉ እጅግ ደስ አለው ።

ላገርና ለሕዝብ የተደረገ ርኅራኄ።

የጅማው ባላባት አባጅፋር ሕመምተኛም ሆነው እርጅናም ተጭኗቸው እቤት ከመዋላቸው የተነሣ ያገሩ ሕዝብና የሚተላለፈውም ነጋዴ በደሉ የበዛ መሆኑ ስለተሰማ ተሻሽሎ የቆመውንም ደንብ ተቀብሎ የንጉሡን ሥራ እንዲሠራና የአገሩንም አኳኋን እንዲመለከት ነጋድራስ ሣህሌ ታዞ መሄዱን ሰምታችሁታል ። ይኸውም ስለሆነ ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባላባት እንዳይጠፉ የሚያስቡ ስለሆኑ አባቱና ያገር ቀሮ ያሳድረናል ብሎ የመረጠው ያባጅፋር የልጅ ልጅ አባጆቢር አባዱላ የሚባለው ባላባትነቱን ይዞ እየሠራ አገሩንና ሕዝቡን በመልካም እንዲጠብቅ ታዞ ነበር ነገር ግን ባለፈው ጊዜ ሁሉ የጅማ ሕዝብ ሠርቶና ነግዶ በማደር በጣም ስሙ ሲመሰገን የነበረውን ይህንኑ እያሰፋና እያጸና በመሄድ ፈንታ ባገሩ ያልተወለደ ገጋ ሳይደረግበት ያልተለመደ ግብር ሳይቀጠልበት ያለችግር እንዲኖር የታሰበሎትን ለማሰንከክልና በገዛ እጁ ወደ ጉዳት ለመድረስ እርስ በርሱ እየተጋደለ መሰንበቱን ሰማን በዚህም ምክንያት አገር የሚጠፋ ቢሆን በዳኝነትና በምርማሪ ለሚሠራው ግራዝማች አበበ ናቂ ታዞ ያባጅፋርም የልጅ ልጅ አባጆቢር እዚሁ አገር ነበርና ላገሩ አሳፊ በመሆኑ እንዲያረጋጋ ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት የሚያስፈልገውን ትእዛዝ ጨምረው ወደ ጅማ ባይሮፕላን ላኩዋቸው ። እዚያም ከደረሱ በኋላ በኃይል ለሚሠራው ሥራ ሊቀ መኳስ መኰንን ዋልቴ ራሳቸውና ከሌሎም የደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ፫፻ ሰው ታዞ ጅማ ገብቷል ።

አይሮፕላኑም ካዲስ አባበ ጅማ በ፩ ሰዓት ደረሰ ። በዚያውም አድሮ በማግሥቱ ወደዚህ ሲመለስ ፖስታና በዚያውም ካሉት ከውጭ አገር ሰዎች ሙሴ እንድርያስን ከነሚስቱና ከነ፪ልጆቹ፥ ሙሴ ሰይድ ካራም የሚባሉትን ነጋዴዎች ከኢትዮጵያም ሰው አቶ ሙልሴ የሚባለውን ይዞ መጣ እዚያም አይሮፕላኑ ሲያርፍና ሲነሣ ለማየት የተሰበሰበው ሕዝብ ብዛቱ ልክ የለውም ነበር ብለው ስልከኞችና ባይሮፕላንም ከመጡ ሰዎች አጫወቱን ። ወንድሞቼ ሆይ ተገጋር የሆነ ሁሉ ምነው እንደ ገጋር ተጨንቆ ቢያስብ ያውም ለገዛ ሕይወቱና ለኑሮው ነበር እንጂ ለሌላ እንኳ አልነበረም ።እንግዲህ ሲያስቡለትና ሲጠብቁት ጥፋቱን በገዛ እጁ ለሚጠቅስ አገር ወዮለት እንጂ ሊታዘንለት አይገባም ።

መልክም ግብር ።

የሠረገላ ሳቢዎችና የጃንሆይ አቶሞቢል ነጂዎች የበዮችም አለቃ ልጅ አበፋው ከበደ አርባ ጾም ሲጀመር ጀምሮ የትንሣኤ ዕለት ለአከፋዮች የሚስማማ ብዙ ዓይነት ምግብና መጠጥ በየዓይነቱ ሲአስደግሱና ሲአዘጋጁ ስላሰነበቱ የድግሱን መሰናዶ ያየና የሰማ ሁሉ በመናፈቅና በመጕምጀት መቼ ቀኑ ደርሶልን እያለ ሲመኝ ነበር። መቼም ወደፊት ያለ ነገር ሁሉ ደርሶ ማለፉ አይቀርምና ያች የሰው ሁሉ ምኞት የቸኰለላት ቀን ስለደረሰች በማናቸውም ጉዳይ ምክንያት ከያውራጃው ሁሉ የመጡትን ካህናት አስቀድመው በሰሙን ሕማማት ከየሰፈራቸው ጠርተው ነበርና በዚሁ በትንሣኤ ሌሊት መነኰሳቱና መዘምራኑ በላይኛዋ ግቢ በሥዕል ቤት ማርቆስ ተሰብስበው ሲጸልዩ አድረው ቅዳሴው ከተቀደሰ በኋላ ከቡርአባ ሐና ቁመው አስገቢዎቹን በአክፍለት የተጕዳ ሰውነት እንዳይንገላታ በዝግታ አስገቡ እያሉ ሲአስገቡ ከሰው ብዛት የተነሣ ጕዴ የሚባለው ድንኳን አልበቃ ብሎት ሦስት ጊዜ እየተኰለኰለ ገባ ። ከገባም በኋላ ለሰውነት ልምላሜ የሚሰጥ መጠጥ በፊት ተሰጠና ወዲያውም ግቡ በያይነቱ ተከታትሎ ወጡም በየስልቱ ተቀጣጥሎ መጠጡም በየወገኑ ተጋርጕድጕዶ ስለቀረበ ያሰዓት ምን ጊዜ ደርሶልን ከእህል ተገናኝተን እያለ ይመኝ የነበረው አክፋይ ሁሉ የሚአሻውን እያማረጠ ሲመገብ ነበር ። ይህ ሁሉ ሲሆን ልጅ አበፋው ከበደ ዙሪያውን እየዞሩ ነጩን ዶራርቡበት ፤ መጠጡንም ሞላሉበት እያሉ አሳላፊዎቹን ሲያነቃቁና ተጋባዦዎቹንም በሉ እኮ አባቶቼ ተጋበዙልኝ እያሉ ሲጋብዙ ደስ ያሰኙ ነበር ። ባለቤታቸውም ወይዘሮ ዲነግዴ በዚያ ድካም በበዛበት ሰዓት ድካም ሳይኖርባቸው ሥራውን ሲአከናውኑ የሚቀርበውንም ሲአፋጥኑ እጅግ ያስደንቁ ነበር ። እንግዶቹም ካህናት ከተጋበዙ በኋላ ለንጉሣችን ዕድሜ፤ ለሀገራችን ልምላሜ ይስጥልን የጾማችንንም ልጓም የፈቱልንን ልጅ አበፋውን ከጌታቸው ጋራ ያኑርልን እያሉ እየመረቁ ሔዱ ። ሁለተኛም ሚያዝያ ፳፭ ቀን ጭፍሮቻቸውንና ሌሎችንም መኳንንት ጠርተው መልክም ግብዣ ጋብዘው ተጠሪዎቹን ደስ አሰኝተዋቸዋል። ሦስተኛም ሚያዝያ ፳፮ ቀን ብዙ የኢትዮጵያ መኳንንትና ከውጭ አገርም ብዙ ሰዎች ለራት ግብዣ ጠርተው ነበርና ለዚሁ ግብዣ የተሠራው የቤቱ ሥራት ልክ እንዳውሮፓ በሥልጣኔ የተከናወነ ፤ በውበት የታፈነ ነበር ። ነገር ግን ሰው ካላየው ይልቅ ያየውን ማድነቅ ልማዱ ነውና ባይኑ ላላየው ሰው ተረት እንዳይመስለው እንዴት አድርጌ ብጽፍለት ለመረዳት ይችል ይሆን። የምግቡና የመጠጡም ዓይነት እጅግ ደስ የሚአሰኝ ለሰው የሚስማማ የሥራውም አኳኋን በጣም የሚአስደንቅ ነበርና ስለዚህ ያይነቱን ብዛት ቈጥሮ የጣዕሙን ጥፍጥንት አስተናብሮ ለመጻፍ ብዙ ጊዜ የሚያስፈልግ ስለሆነ የድንቅነቱን ታሪክ አሳጥሬዋለሁ ። መኳንንቱም እጅግ አመሰገኑ። ይልቁንም ከተጠሩት መኳንንት ክቡር ፊታውራሪ ጣሰው ደስ የሚያሰኝ ዲስኩር ቁመው አነበቡና ሦስት ጊዜ ተጨበጨበ ዲስኩሩን ግን በታ ስለጠበበ ትተነዋል ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ።

ያልሰማ ጆሮ ከጕረቤት ያጣላል ።

ሚያዝያ ፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም በወጣው ብርሃንና ሰላም በሙቶ ሐያ አንድ ገጽ አቶ ፈለቀ ዕርገቱ ከዕለታት ፩ ቀን ወደ ከተማ ለትንሽ ጉዳይ ወጥተው የከተማ ዘበኞች ግፍ ሰሩ በማለት ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች የጻፉትን ስለ ተመለከትኩና የተገነዘብኩትን ነገር ልጽፍ ስላሳሰበኝ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች እንዲመለከቱልኝ ይፈርሁ ።

፩ የባላገር ሰው በፈረስ ሰምሰማ ሲሔድ የከተማ ደምብ ጠባቂዎች ዘበኞች ያዙት ወዲያው ፪ተኛ ደግሞ ፩ የከተማነዋሪ የሆነ ሰው ሽምጥ አስነሥቶ ሲጋልብ ቢመጣ ሰምሰማ ሲሔድ የተያዘው ይህን እንዴት ያደርጉት ይሆን ብዬ ስፈራለት እንኳንስ ሊጠይቁትና በክፉ ዓይን ሳያዩት አለፈ ብለው ለጻፉት ለጊዜው መመርመር የሚባለው ጓደኛዎ አብሮዎት ባይኖር ይሆናል እንጂ ከርስዎ ጋራ ያን ጊዜ ኖሮ ቢሆን በምክንያት መሆኑን ይገልጽልዎ ነበረ ምክንያቱም ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ከንቲባና ዲሬክተር በአዲስ አበባ ከተማ ውሥጥ ስለሚተላለፉት አቶሞቢሎችና ከሚአን ኦቶ ቢስክሌት ቢስክሌት እነዚህንም የመሳሰሉ በፍጥነት የሚተላለፉትን መኪናዎችና ከብቶች አቶሞቢል ነጂዎቹ ጥንት እንደፈቃዳቸው በፍጥነት እየነዱ ሲተላለፉ በመከከል ብዙ አቶሞቢሎች እየተጋጩ ብዙ ሰዎች እየተዳጡ ለሕዝብ ጉዳት የሚያመጡ መሆኑን ስለተለመለከቱት ሁል ጊዜ አቶሞቢልና ከሚአን ኦቶ ቢስክሌት ቢስክሌት የሚያስኬዱ ሠራተኞች ግራና ቀኝ ሳይወላውል ቀኝ ቀኙን ያስኪዱ እንጂ እንደፈቀደው ወዲያና ወዲህ ሲነዳ የተገኘ ሠራተኛ መቀጫ ይከፍላል ተብሎ ደምብ ሆኑአል ስለዚህ አሁን ከቅርብ ቀን ወዲህ በቀጥታው ቀኝ ቀኙን እየተላለፉ ብዙ መኪናዎች ከመጋጨት ብዙ ሕዝቦች ከመዳጥ ድነዋል ።

ደግሞ ፩ምሳሌ አንድ ሰው ከደቡብ ወደ ሰሜን ደግሞ አንድ ሰው ከሰሜን ወደ ደቡብ ለየጉዳያቸው በፍጥነት (በሩጫ) ሲተላለፉ ሁለቱም ሳያስቡት በኃይል ይጋጫሉ በመከከል በነዚህ ሁለት ሰዎች መጋጨት ዓይን በመፍሰስ ጥርስ በመርገፍ ጉዳት ይመጣባቸዋል በማለት እንደ አቶሞቢልና ሌሎች መኪ

ኛዎች አካሔድ ዓይነት እግረኛና ባለ ከብት ሁል ጊዜ ቀኝ ቀኙን እለፍ ይህንን ያልጠበቀ ሰው ግን ይቀጣል የሚሉ የማዘጋጃ ቤት ማመልከቻዎች በየጐዳናው ዳር በአንዳንድ ቦታ ይታያሉ ስለዚህ የከተማ ደምብ ጠባቂዎች ዘበኞች በየሰንተሊያቸው ላይ ቁመው ሲጠብቁ የዚህን ማመልከቻ ቃል ጥሰው በግራ በግራ የሚተላለፉትን ሰዎች ከመከላከል አላቋረጡም

ነገር ግን ሕዝባቹ ለጊዜው የከተማ ደምብ ጠባቂዎች ዘበኞች በሚቆሙበት ሰንተሊያ ሲደርሱ እንደ ማመመልከቻው ቃል ቀኝ ቀኙን ይተላለፋሉ ሰንተሊያውን ካለፉ በኋላ ግን ግራና ቀኝ እንደፈቃዳቸው ደምብ ባለመጠበቅ ይሔዳሉ ይህም ትልቅ ጥፋት ነው አሁን ይህን ሁሉ ነገር ለምሳሌ ጻፍሁት እንጂ ወደ ሥር ነገሩ እንመለስ ።

ከዚህ በላይ እንደጻፍሁት ሁሉ ይህ ባላገር የተባለ ሰው ሕግ ተላልፎ ግራ ግራውን ሲሔድ የተያዘ መሆኑ ጥርጥር የለበትም የከተማ ነዋሪ ነው የተባለው ሰው ጳን በፍጥነትም እንኳ ቢሔድ ቀኝ ቀኙን ስለተላለፈ በዚህ ምክንያት ያልተያዘ መሆኑን ያስረዳል ። ዳግም የከተማ ነዋሪ የሆነውን ሰው ሲቃችሁ ደህን ድሀ ባላገር ታስለቅሱታላችሁ ብዬ ብጠይቃቸው እሱ የከተማ ሰው ስለሆነ ቁም ብንለውም አይቆምልንም እሉ ለተባለበት ነገር የከተማ ደምብ ጠባቂዎች ዘበኞች ኃይለኛ ሕግ ተላልፎ በፍርሃት ይለቁታል ተብሎ አይጠረጠርም ።

ዳግም ምሳሌ ሁለት ሰዎች ባንድ ነገር ተከሰው በዳኛ ፊት ቁመው የተካሰሱበትን ነገር ሲያመለክቱ ተጠበቅ ብሎ በዳኛው ቃል ከተጠበቀበት በላይ ያ መጀመሬ የሚያመለክተው ነገሩን ጨርሶ ፍጆታ እስኪሰጠው ድረስ እንደኛው ዝም ብሎ ይቆያል ነገር ግን ከተጠበቀበት በላይ እንደ መጀመሬው አመልካች ድምጹን ከፍ አድርጎ ባይናገር እንኳ ዝግ ብሎ ፍጆታ ሳይሰጠው ቢናገር ጥብቅ ኀብቶ የሚገባውን መቀጫ ይከፍላል

ይህም የባላገር ሰው የተባለው ሕግ ተላልፎ ግራ ግራውን በፈረስ ሶምሶማ ሲጋልብና እያዘገመም ቢሔድ የከተማ ደምብ ጠባቂዎች ዘበኞችን ያስመሰግናል እንጂ ግፍ በማድረግ ስማቸው ሊጠፋና ሊያሰድባቸው የሚበቃ ነገር አለመሆኑን የብርሃንና ሰላም ተመልካቾች ይረዱታል ።

የማዘጋጃ ቤት ሠራተኛ ተፈራ ገብረ ማርያም ።

ማስታወቂያ ።

አርስጣላብ የተባለ መጽሐፍ ዋጋው አንድ ሩብ ።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያና የግርማዊት እቴጌ መነን ባለ ዘውድ ሥዕል ፣ ደግሞ የንግሣቸው መታሰቢያ ሥዕል በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት በአንዳንድ ሩብ ይሸጣል ።

በቤኒዳስ ኤምቻንድ ነገር ።

ባንክሩፕትሲ ቍጥር ፫ ፲፱፻፴፩ ዓ ም በእንግሊዝ

መንግሥት ቆንስላ የፍርድ ቤት ።

ከዚህ በላይ በተጻፈው ከሣራ የባለዕዳዎቹ ድርሻ እንዲታወቅ በማለት የመጀመሪያው ክፍያ ግንቦት ፳፬ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም እንዲሆን መታሰቡን እናስታውቃለን ።

ለሚፈልጉት ገንዘብ ማስረጃ የአላቀረቡ አበዳሪዎች ሁሉ ማስረጃቸውን ከዚህ በታች በግርጌው ፊርማውን አፈረመው ዘንድ አረቡ ግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም የአላቀረቡ እንደሆነ በክፍያው ውሥጥ የማይገቡ መሆናቸውን እናስታውቃለን ።

ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም አዲስ አበባ ተጻፈ ።

ቲ ዲ አየር ።

አፊሲዩል አሲኜ

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ካ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

ሀዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሸሹአት የተዘጋጀች ናት።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቁረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጎበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል። ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ገናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ካገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ያቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ።

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ጥንኪ አንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር ፣ ግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለ90

ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እቼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ፀአቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ጱልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ፦ በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስምንተኛ ዓመት ቊጥር ፳፩
8ᵐᵉ ANNE. № 21

ሐሙስ ግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 19 AVRIL 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታላቅ ግብር ።

የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን የሥርግበዓል እስከ ፰ቀን ድረስ ግብሩ አላቋረጠም ነበር። በግንቦት ፬ ቀን የካህናት ግብር ነበር ። በግንቦት ፰ቀን የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር መልእክ ሕይወት ወልደሐና የሮፓን ትምህርት የሚአስተምሩ መምህራንና ተማሪዎችን በትምህርት ቤት ያሉትንም ሠራተኞችን ሁሉ ጨምረው ወደ መርዕድ አዝማች ግቢ እንዲመጡ ተጠርተው ነበሩና በዚሁ በታዘዘው ሰዓት ሁሉንም ሰብስበው ሒደው ነበሩ ። የኢትዮጵያን ልብስ የለበሱ መምህራንና ተማሪዎች በአንድ አዳራሽ፥ እንደሮፓ የለበሱ ኢትዮጵያውያንና ከውጪ አገር የመጡ መምህራን ጥሩ ሁኖ በተሠራው በአዲሱ አልፍኝ ተጋበዙ እኔም በአዲሱ ቤት ካሉት ጋራ ነበርሁ ። የአቀማመጡና የግብዣውም ሥርዓት ልክ እንደሮፓ ሥርዓት ነበረ ምግቡም መጠጡም እጅግ የተመሰገነ ነበረ ። ስለ መርዕድ አዝማች ሁነው በመሐከል ተቀምጠው ይጋብዙ የነበሩትም ደጃዝማች አበራ ካሣ ነበሩ።ከምግብም በኋላ የሙዚቃ አስተማሪው ሙሴ ናልባድያን የሮፓውያንን መሰንቆ እየመቱ በኢትዮጵያ ቋንቋ እየዘመሩ ተቀማጮችን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙ።ሙሴ አልቤርም እንዲሁ መሰንቆውን እየመቱ ሰሚዎችን ደስ አሰኙ ከዚህ በኋላ ሸምፓኝ ተጋብዘን ተነበርንበት ተነሥተን ወደሌላው ክፍል ሒደን ቄይተን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን በታላቁ ሳሎን (አዳራሽ) ተቀምጠው እንደገና አስጠርተውን ገብተን እጅ ነሥተን በየማዕርጋችን እንድንቀመጥ ተፈቅዶልን በሌላው አዳራሽ የነበሩትም ወደ እኛ መጥተው ተቀመጥን ። ደግሞ እንደገና ሸምፓኝ ቀረበና የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር መልአከ ሕይወት ወልደ ሐና የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡና ተጨበጨበ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ሆይ።

ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የተመሰረተውን ጋብቻ በእግዚአብሔር ፈቃድ በልዑልነትዎና በልዕልት ወለተ እስራኤል መካከል በተፈጸመበት ቀን ዛሬ እኛ ባዳራሽዎ ተሰብስበን ለደስታዎ ተካፋዮች በመሆናችን የልባችንን ደስታ በአፍ ልንገልጸው አንችልም ።

ልዑል ሆይ ።

የቀደሙት በዝና ከዚያም ወዲህ በዘመናችን ያየናቸው ነገሥታት ምንም ሀብታቸው የገነነ ቢሆን የበለጠው የልጅ ሀብት የዘር ዕድል አልተሰጣቸውም ነበርና ስለዚህ ሀብታቸው የደመቀ ነበር ለማለት አልተቻለም ይኸንኑም ልዑልነትዎ አይስተውም።

ነገር ግን ግርማዊ ጃንሆይ አባትዎና ግርማዊት እቴጌ እናትዎ እግዚአብሔር አሟልቶ የዕድልና የሀብት ምንጭ ሰጥቶአቸዋል። ምስክሩም ይኸውና ልዑልነትዎ ተወልደው አድገው ለኢትዮጵያ አልጋ ታጭተው ለአካለ መጠን ደርሰው የመጋባትን ሕግ ፈጽመው ለሁላችን መሰብሰቢያ ስለሆኑን ያስረዳናል ።

ይኸው ሀብትና ዕድል የጋራችን ስለሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንድ ድምጽ ሁኖ እግዚአብሔርን ያመሰግናል ይልቁንም የትምህርት መንጋ የጥበብ ግልገሎች የሆኑ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ወጣቶች በልዑልነትዎ ዙፋን ፊት ቁመው በብዙ ዓይነት አደራረግ ደስታቸውን እየገለጹ ምስጋናቸውን ያቀርቡልዎታል ።

ልዑል ሆይ

በራሴ፥ በሹማምንቶቼና በአስተማሪዎች ፥ በተማሪዎችም ስም ሁሉ ጋብቻዎ እንደ አብርሃምና እንደ ሣራ እንዲሆንልዎ እየተመኘሁ ጽዋዬን አንሥቼ እጠጣለሁ ።

ከዚህም በኋላ ቢትወደድ ጌታቸው አባተ ስለ መርዕድ አዝማች ሁነው የሚከተለውን ዲስኩር መለሱ በአነጋገራቸውም ጣዕም ሰው ሁሉ ተደነቀ ።

ክቡር ሚኒስትር ሆይ

አሁን በተናገሩት ዲስኩርዎ በጣም ልባችን ተነክቷል ይልቁንም ከዲስኩሩ መሐል እንደተናገሩት ግርማዊ ጃንሆይና ግርማዊት እቴጌ ምንም በየጊዜው ልዩ ልዩ ዕድል ቢኖራቸው ዛሬ ደግሞ ይህንን ወሰን የሌለውን መታደል በማየታቸው ፍጹም ዕድለኞች ናቸው ለማለት ተቻለ ይህን ማለታችን እንደዚህ ያለ ከፍ ያለ ጋብቻ የተጀመረው ዛሬ ብቻ ነው ለማለት አይደለም።ነገር ግን ልዑል አልጋ ወራሻችን በትምህርትና በዕውቀት አድገው ይኸው እንዳየነው

በሕግ በሥርዓት በግርማዊና በግርማዊት ፈቃድ የከበረውን ጋብቻ ተቀበሉ ስለዚህ ይህ ጋብቻ ምንም ለጊዜው ለልዑል አልጋ ወራሽና ለልዕልት ወለተ እስራኤል ብቻ ቢሆን ጥቅሙና የመልካም አርአያነቱ ለነዚህም ለሕፃናቱና ለመላ ኢትዮጵያ በመሆኑ ለደስታችን ወሰን የለውም አሁንም ይህንን ጋብቻ እግዚአብሔር ወደፍጻሜ ደስታ ያደርሰዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ዳግም ክቡር ሚኒስቴርና መምህራኑም ተማሪዎቹም የደስታችን ተካፋይ ሆናችሁ በዚህ ቀን ስለመጣችሁ እናመሰግናችሁአለን ።

ከዚህ በኋላ ሙሴ ማለም የቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት አስተማሪ በፈረንሣዊ ቋንቋ የተጻፈ ዲስኩር አነበቡ።

ቀጥለውም ሙሴ ሽክሬ የዳግማዊምኒልክ ትምህርት ቤት ዲሬክተር መልካም ዲስኩር አነበቡ ።

ቀጥለውም ሙሴ ጋሪኮይክስ የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ዲሬክተር ከፍ ባለ አንደበታቸው መልካም ዲስኩር አነበቡ ።

ከዚህ በኋላ አለቃ ዳንኤል ደስታ እጅግ ደስ የሚአሰኝ እንጋገር ተናግረው መወድስ ቅኔ በወረቀት አነበቡ ።

ከዚህም በኋላ ብላታ ኀይለማርያም የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

በእግዚአብሔር ጸጋ በሀገሬቱም ሕዝብ ሁሉ ፈቃድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ።

ግርማዊ ሆይ።

ልዑል እምልዑላን ራስ ሥዩምና በዚሁ ያሉ ሌሎች ልዑላንና ክቡራን መኳንንትም ክቡራት ወይዛዝርም በየማዕርጉ ያለ ወታደርና ሕዝብ ሁሉ ሆይ ።

ሌላ ሌላውስ ይቅርና ፥ ስፋቱ የኢትዮጵያ ግማሽ ስለመሆኑ በሚያሳስብ በሸዋ ከጥንት የወረደ ነጋሢነት የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቀጥሎም የኢትዮጵያ ሲሶ ስለመሆኑ በሚያሳስብ በወሎም የንጉሥ ሚካኤል ዘር የሆነው ልዑል እምልዑላን መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን ፥ በስፋቱ ከነዚሁ ክፍሎች ክንደ እንደማታንስ በምታሳስብ በትግሬ ሀገር ላይ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲነግሡ ተርብ የሆነ ሠራዊታቸውን አስከትለው በአርግማን ተልከበት በነበረ የግራኝ ጊዜ በተዘሩበት አረመኔዎች በመጕሳቈሏ ተጣበ የነበረውን ሁኔታዋን እያስፋፉላት እስከኀልቀታቸው ድረስ ጠላት እንዳይገበባት ለኢትዮጵያ ሲከላከሉላት ለነበሩ ለንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ዋና ልጃቸው የሆኑ የራስ ሥዩምን ልጅ በተቀደሰ ጋብቻ ሰጡት ሲባል ማር እቅቤ ላይ ፈሰሰ ስለማለት ነውና ይህን ያህል ታልቅ ቁም ነገር ያለውን ጉዳይ እስበ ለመፈጸም የተወሰነባትን ዕለት ለዘለዓለም የተባረከች ትሁን ።

ግርማዊ ሆይ ።

ልዑል እምልዑላን ክቡራንም ሆይ የቀረውን ሌላውን ሁሉ በወገኑ አስቀምጬ አፄ ቴዎድሮስና አፄ ዮሐንስ በግዙፍነት አፄ ምኒልክና ራስ መኰንን በመንፈሳዊነት በሚታይ ሥራቸው ደማቸውን አፍስሰው በተሠዉባት በአግዓዚቱ ሀገር ውሥጥ ዋና ዋና ሁነው ከሚታዩቱ ከኒያ ከሶስት ሀገር ክፍሎችም በዘር ትልልቅ ከሆኑቱ ነገዶች እንደ ወርቅ ተነጥረው የወጡ እኒህ ሁለት ልጆች እስካሁን ድረስ ተይዞ ይታይ እንደነበረው እንዳገር ልማድ ግዙፍነት ባለበት አሳብ ሳይሆን ስለ ኢትዮጵያይቱ ነፃነታዊ አንድነት የሚያሳይ መንፈሳዊ አሳብ ባለበት ምኞት በተቀደሰው ሥርዓት ተጋብተው የሚቀላቀሉበት የዛሬይቱን ዕለት በእጅጉ ከፍ ከፍ እያደረግሁ ይኸነን ጉዳይ ተፈጽሞ ለማየት ያበቃንን አምላክ በኢትዮጵያ ስም ሁኜ ያቅሜን ያህል ሳመሰግን ከደስታዬ ብዛት የተነሣ ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት ስል የበለጠ ምርቃቴን አቀርባለሁ።

ግርማዊ ሆይ ።

ልዑል እምልዑላን ክቡራንም ሆይ ።

ይህን የተቀደሰውን ጋብቻ ሰነማው በደስታ ባሕር ተሰጥሜ አለሁ መስጠሜንም ጋብቻውን ምንም እንኳ እኒህ ልዑል መርዕድ አዝማች አልጋ ወራሽችን ተነጥረው ወጡባቸው ብለን ከተናገርናቸው ከሁለት ሀገር ክፍሎች ውሥጥ አንዱዋን በስሕተቷ ነው ከማለት ይልቅ ይህን ስለምን አድርገህ ለመባል የማይቻልበት በፈጣሪ ፈቃድ ስለመሆኑ በሚያሳስብ ሁኔታ ፍጻሜዋን እንዳላማረ ሳያሳስብባት ባልቀረ ምክንያት በድንገት ሳይነሣ ባልቀረው ጠብ የተነሣ በሌሎች ሁለት ክፍሎች መካከል ሁና ስለነሱ ያለውን ጥንታዊ ወንድምነት ሳያሰጋው ስላለመቅረቱ ያሳስብ ከነበረ ነገር ሁሉ በጥቂቱ የቀረውን የጓብዝነትን እርሾ አስረስቶ እኒህ ዋና ዋና የሆኑትን ሶስት ያገር ክፍሎች አንዲም ሌላዋንም ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት በኀይለ ሥላሴ ተወጥኖ እያስፋፋ ከሚሔድ ባዲሱ ሕግ ሥርዓት አካሔድ አራምዶ እንደገና እርስ በርሳቸው በፍቅር ገመድ እያስተሳሠረ በማዛመዱ ቀጥሎም የቀሩትንም ሌላ ሌላ ክፍሎች በዚህ በፍቅራቸው ማስተሳሰሪያ ገመድ በኩል በወዳጅነት አቈራኝተው የሚሰቡበትን ለነርሱ ሀብት እየሰጠ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ እንዳንድ አካል ሁኖ አገሪቱን ለመጠበቅ የሚበቃውን ጸጋ የሚሰጥ ጋብቻ ሁኖ ስለ ታየኝ ነው ። በቃና ዘገሊላ ሠርግ በመጠራቱ በርኅርኅት እናቱ አማላጅነት ጋኖቹን ውሀ አስመልቶ በመባረክ ጠጁን ወደ ወይን ለውጦ የባለ ሠርጉን ድግስ ያሳመረ ክርስቶስ ዛሬም በቅድስናና በመንፈሳዊነት አሳብ ተመስርቶ ወዳለው ወዳሁኑ ሠርጋችን ከርኅርኅት እናቱ ጋር ቀርቦ በርስዋ አማላጅነት ሠርጋችንን ባርኮ ድግሳችንንም አሳምሮ ግርማዊ ኀይለ ሥላሴንና ልዑል ራስ ሥዩምን በቀን በቀኑ ከግማሽ እንጀራ የበለጠ ስላለመብላታቸው እያሳሰበ አባቶቻቸው ስለተሠዉባት ኢትዮጵያ ጥበቃ በመንፈሳዊ ፍቅር ተሳስረው የሚኖሩበትን ጸጋ ሰጥቶ ሙሽሮቹንም የወላጆቻቸውን ፈቃድ እየፈጸሙ ከሕዝብም ጋራ እየተስማሙ ዕድሜአቸውን አርዝሞ ስለ ኢትዮጵያ አንድነትና ስለነፃነቷ የሚጣጣሩ ልጆች እየወለዱ የሚኖሩበትን ሕይወት እየሰጠ አብረው ለመኖር ያብቃቸው ። ግርማዊ ንጉሣችንንም ከነቤተ ሰባቸውና ከመኳንንቶቻቸው ከሠራዊታቸውም ከሕዝባቸውም በሰላም እያኖረ ዕድሜአቸውን ያርዝም መንግሥታቸውንም ያስፋ ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኑር ስል ጽዋየን እጠጣለሁ።

ቀጥሎ አቶ ኪዳነማርያም አበራ የትምህርትና የጥበብ ዲሬክተር እንደራሴ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ሆይ ።

በዚችው በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ሕዝብ ሁሉ ብዙ ደስታ በተቀበለበት በተባረከችው ሰምንት ከሁሉ የበለጠ ተማሪዎቹ በጣም ደስ እንዳላቸው ተረድቼዋለሁና ከልዕልናዎ ፊት ቀርቤ ለመመስከር ይፈቀድልኝ ።

ልዑል ሆይ

እኒህ ደስታቸውን ለመግለጥ ሲዘጋጁ የሰነበቱ አሁንም እሬትዎ የተሰበሰቡት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው አድገው ልዕልናዎን ለማገልገልና አገራቸውን ለማስከበር የተዘጋጁ መሆናቸውን እመሰክራለሁ ።

ልዑል ሆይ የልዕልናዎ ፈቃድ ሁኖ የደስታዎን ተካፋዮች እንድንሆን ስለጠሩን በትምህርት ሚኒስቴርና በአስተማሪዎቹ በተማሪዎቹ ስም ሁኜ የጠለቀ የልብ ምስጋናችንን ለልዕልናዎ አቀርባለሁ ።

ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት፡ዕድሜ ለግርማዊት እቴጌ፡ ዕድሜ ለልዑል አልጋወራሽና ለልዕልት ወለተ እስራኤል ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ።

ይህ ሁሉ ዲስኩር በየተራ ሲነበብ ጭብጨባው ሲደምቅ ከቤቱ ታላቅነት የተነሣ የቤቱ ቀበሌ አብሮ ሲጮህ የደስታ ተከፋይ ቤት መሆኑን አስረዳ ።

በዚሁም ቀን ለዘበኛ ሁሉ በታላቁ አዳራሽ ግብር ሁኖ ነበረ ። ዙሪያውን በመርዕድ አዝማች ግቢ በየቤቱ ጥጋብ ብቻ ነበረ ። ሙሽራይቱም በሙሽራው ቀኝ ተገልጠው ተቀምጠው ያያቸው ሁሉ በሥልጣኔ ደረጃ ላይ መውጣታቸውን ተረዳው።

በማግስቱም ሙሽሮቹ ወደ ታላቁ ግቢ ተጠርተው ነበሩና በወርቅ በወርቅ በጠለቀ መሣርያ በተጫኑ በቅሎች ተቀምጠው በወርቅ በወርቅ የጠለቀ ጥላቸውን አሲዘው በፊትና በኋላ መኳንንትና ሠራዊት አጀበዋቸው በሥራተ መንግሥት ሲሔዱ እጅግ ያምሩ ነበር።ስለ ሙሽሮቹም ደስታ መሳፍንትና መኳንንት ወይዛዝርና ሊቃውንት ተጠርተው ታላቅ ግብር ተደርጎ ዋለ ።

በእራትም ጊዜ የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ሚኒስትሮችም ጥሩ ሽልማታቸውን ለብሰው።የክቡር ዲፕሎማቲክና የውጭ አገር ሰዎች እንዲመጡ ተጠርተው ነበር ከእራትም በኋላ ዳንስ ሲቀልጥ ነግሁ እስቲቀርብ ቄየ የጣፋጩ ምግብና የሸምፓኝ ብዛት ላየው ሰው እጅግ ያስደንቅ ነበረ ። እንዲህ እያማረ የሠርጉ በዓል በደኅና ተፈጸመ ።

መልካም ዘር ይስጣቸው መጨረሻውንም ያሳምርላቸው እያለ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ይገልጻል ።

ዕድለኛው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን።

የዕድሉንም መጀመሪ ሁላችሁ ታውቁታላችሁና ዘርዝረን ለመጻፍ አያስፈልገንም።የሁለተኛው ዕድሉ ዋና የአዲስ አበባ ገበያ በአጠገቡ በመሆኑ ከውጪ አገር ሰዎች በመገናኘታቸው ምክንያት ካህናቱ እጅግ የሠለጠኑ ናቸው ለማብገር እንኳን የተጠሩ እንደሆነ ሙላልን ጨምርልን ማለትን ሳያበዙ ፈጥነው በመመለሳቸው ሕዝቡ እጅጓ ያመሰግናቸዋል፫ተኛም ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ተቀብተው ነግሠውበት ነበር።፬ተኛም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተቀብተው ንጉሠ ነገሥት የተባሉበት ስለሆነ የአራዳው ጊዮርጊስ መባሉ ቀርቶ መናገሻ ጊዮርጊስ ተብሎ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቃል ስለተሰየመ ሕዝቡን ሁሉ እጅግ ደስ ብሎ ቃል። የደብር ክብር ለማኅበሩ ክብር ነውና የመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስን ማኅበር እንኳን ደስ አላችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል ።

የጨካኞች ሴቶች ታሪክ ።

ውዴ የምትባል ሴት ደላንታ በሚባል አገር ነበረች እርሷም መካን ነበረችና ባልዋ ልጅ መፈለጉን አውቃ የፈለገውን በያገኝ ለጊዜው አረገዝሁ ብዬ ላታለውና አማረኝያልሁትን ሁሉ ይመግበኝ ከዘጠኝ ወር በኋላ ሌላ አስባለሁ ብላ አረገዝሁ ብላ እያታለለች የፈለገችውን እያገኘች ደስ ብሏት ቈይታ ዘጠኙ ወር ሲደርስ ሐሳብ ጀመረች።መቸም የሐሰት ነገር መጨረሻው ጥፋት ነውና ከወለደች ፭ዓመት የሚሆናት እቴቴ የምትባል ሴት በጐረቤቷ ነበረችና ወደ ዱር በሔደችበት ጊዜ ገደለቻትና ልጅዋን ታቅፋ ወደ ቤቷ ሒዳ ልብስዋን በዶሮ ደም ነክራ ወለድሁ ብላ የዋሁን ባልዋን ለጊዜው ደስ አሰኘታ ልጅቱ እናትዋ እንዳልሆነች አውቃ ልቅሶ ስታበዛ ጊዜ ከመታቀፉ እንርዳሽ ብለው ዘመዶችዋ ሲቀበልዋት ልጂቱ ጥርስ አብቅላ ነበረችና ጥርስዋን አይተው ሐሰትዋን እንዳያውቁበት ጥርስዋን በደንጊያ አወለቀቻት ልጂቱም ሕማምዋ ሲሰማት ጊዜ እማማእያለች ስታለቅስ አሁንስ እንዲያውም ልታሲዘኝ ነው ብላ መላስዋን ቈረጠቻት ያልታደለችቱም ሕፃን ስቃይዋን ተቀብላ ሞተች ይህች ጨካኝቱ ሴት በእንስራ ውስጥ አግብታ ከተተቻት ምንም ቢጨነቁ የተደረገ ነገር ሳይገለጥ አይቀርምና ነገሩ ተሰምቶ ይህንም ታላቅ ኃጢአት መሥራቷን በዳኛው ፊት እምና በዳኛው ትእዛዝ ታሥራ ብዙ ጊዜ ስለ ቈየች ያኑ የፈለገ

ችውን እርግዝና አረገዘችና ብትወልድ እጅና እግር የሌለው የተድበለበለ ሕይወት የሌለው ፍጥረት ወለደች ይህቺስ እግዚአብሔር የፈረደባት ሴት ናት ብለው ወደ አዲስ አበባ አምጥተዋት በወንጀለኞች ቅጣት ፍርድ ቤት ዳኞች በቀኛዝማች አጥናፌና በሌሎችም ፊት ተመርምራ ይህንም ማድረጓን አምና የተናገረችውም ቃል በወረቀት ተጽፎ ጃንሆይ ባስቻሉበት በታላቁ ችሎት ቀርባ ተመርምራ ይህን ሁሉ መስራቷን አምና በመጋቢት ፴ ቀን የሞት ፍርድ ተፈረደባት ከዚህ ሁሉ የሚአስደንቀው አብሯት የሚአድረው ባሏ የሆዷን አለማወቁ ነው።

ዘፈን ።

ያውና እዚያ ማዶ በግ ይነዳል ሰው ።

ለተመለሰተው ባላህያ (ባል አህያ) ነው ።

ብላ ዘፋኝቱ ገጠመች ሲሉን የድፍረት ቃል ይመስለን ነበር፡ለካስ በእንደዚህ ያለ ሰው የተገጠመ ኑሮአል?ተረትላልደረሰው ወሬ ቢመስል እንዲህ ሲደርስ እውነት መሆኑ ይታወቃል

ሁለተኛይቱ ጨካኝ ሴት ።

አበበች የምትባል የወረይሉ ሴት ዘነበች የምትባል እናትዋን ገድላ መግደልዋንም በቃልዋ አምና በጃንሆይ ችሎት ቀርባ ሞት ተፈረደባት በምን ምክንያት ገደልሻት ብለው ዳኞች ቢጠይቋት ምንም የበደለችኝ ነገር የለም ነገር ግን ጠላ ጠጥቼ ሰክሬ ነው አለች አገዳደልዋም እንዲህ ነው በካራ አንገቷን ቈርጣ በገለባ ውስጥ ሸሽጋት ሬሳዋን ውሻ ሲጐትተው በጠፋች በ፭ኛው ቀን የጐረቤት ሰዎች አይተው ይህ የናትሽ ሬሳ አይደለምን ብለው ቢጠይቋት ደንግጣ ዝም በማለቷ ጠርጥረው ይዘው ወደ ዳኛ ቢወስዷት እናትዋን መግደልዋን ቶሎ አመነች።ወይ የልጅ ነገር እናቴ እንደቀድሞዋ አትጨክንብኝም ብላ ይሆን ? ወይ አለመታደል? እውነት ነው እናቲቱ ለኑዛዜ በቅታ ብትሆን ልጄን አትግደሉብኝ ሳትል አትቀርም ነበር የናት ርኅራኄ ዘለዓለም ነው አሁን በቅርብ ጊዜ ሁለት ሶስት ዓመት ይሆን ይሆናል ሽጉጥ ተባርቆበት ልጅዋ እናቱን ቢአቈስላት እኔ ሰክሬ በልጄ ሽጉጥ ራሴን መታሁት እንጂ ልጄ አልነካኝም ብላ ተናዛ ይመርመርልኝ ሳትል ሞተች ሲባል ሰምተናልና አትግደሉብኝ ሳትል አትቀርም ነበር ያልነው ስለዚህ ነው።

ስለ ክቡር አፈንጉሥ ከተማ ዕረፍት

ክቡር አፈንጉሥ ከተማ ጌታ አዳምን ብላዕ በሐፈ ገጽከ ብሎ የተናገረውን ቃል ተከትለው ለንጉሣቸው በቅን ማገልገልና እውነት መውደድን ልማድ ያደረጉ እጅግ መልካም ክርስቲያን ነበሩ ያገልግሎታቸውንም ነገር ዓለም ያውቀዋል ስለዚህ የታወቀን ነገር ዘርዝሮ መጻፍ አያስፈልግም ደጅ ጥናትና ጌታ መከተል በማንም ላይ አያምር ያልተፈቀደ ነገር ሆኖ ሌሊት በቤታቸው ያድሩበታል እንጂ ሲቻላቸው እንዳልተቻለው ድኃ የጧትና የማታውን ውርጭ ሳይሰቀቁ እቤተ መንግሥቱ የሚገቡበትንና ወደቤታቸው የሚመለሱበትን ሰዓት ለተመለከተው ብዙ ይገርማል ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ዛሬ እስከ አፄ ኃይለ ሥላሴ ድረስ እንደበታቸውን እንቅፋት ሳይነካውና ሳይሰናከሉ ውርደት ሳያገኛቸው በየጊዜው አገልግሎታቸው እየታሰበ ካቶ ጀምሮ እስከ አፈ ንጉሥነት ድረስ በሹመት ላይ ሹመት እየደረበ የክብር ክብር ተቀብለው ነበረ በተሾሙበትም አገር ላይ ገና ሳይገቡና ያገሩን አኳኋን ሳይመለከቱ በሀገሩ ላይ ያለውን ጉድለት መርምሮ በሃገሩ ላይ የሕዝቡን ጉዳት የሚፈልግ ሽፍታ ቢኖር ሽፍታ ማጥፋት መንገድ ባይኖረው መንገድ ድልድይ የውኃ መሻገሪያ ባይኖር ድልድይ ቤተ ክርስቲያን ቢፈርስ ቤተ ክርስቲያን አስቀድሞ ማሠራት እንጂ የራሳቸውን ጥቅም ለማግኘት በፍጹም ሐሳብ የላቸውም ከሠሯቸውም ሥራዎች ከብዙ በጥቂቱ ጽፈን እንተዋለን በድልድይ በኩል ግቤንና ወሞን ያህል ወሃ ድልድይ አሠርተዋል ደግሞ እውነት እንጂ ሐሰት እንዳይፈልጉ ዓለም ሁሉ ስለተረዳው ከፋን ሲገዙ ኃጢአተኛውን ይዘው እንደኃጢአቱ መጠን የሚገረፈውን ለመግረፍ የሚሰቀለውን ለመስቀል ተፈቅዶላቸው ብዙ ሽፍታ ሰቅለው ለሀገር ጤንነት ለሕዝብ ዕረፍት ሰጥተዋል እንዲያውም ሽፍታው መድረሻ ቢያጣ በደፋር ከተማ ፊት ከመቅረብ በባሕር ጠልቆ መቅረትን መርጦ እግቤ ባሕር ብዙ ሽፍታ ጠልቆ ቀረ ይባላል ይህ የዕድል ዕድል ነው ያሠሩት ቤተ ክርስቲያንና መንገድ ግን ልክ መጠን የለውም ምን ይሆናል ጌታን ቢወዱ የክርስቶስንም መንገድ ቢፈልጉ ጧት ማታ ላገልግሎት ቢፋጠኑ ከሞት መቅረት የለምና በዚሁ ውርጭ በመዳፈራቸው ምክንያት በሽታ በሰውነታቸው ላይ አድሮ ሁለት ዓመት ያህል በሕመም ምክንያት ያንን የሚወዱትን ቤተ መንግሥት ተለይተው እቤት ስለዋሉ መቃብራቸውን ራሳቸው አሳንፀው በድንጋይ ገጥመው ጊዜ ሞታቸውን ይጠባበቁ ነበረ ዳሩ ግን ልምድህ ያሉት በሽታ ተብሎ እንደሚነገረው ሁሉ ደህና ናቸው ሲባል ሳይታሰብ በድንገት በተወለዱ በሰማንያ አንድ ዓመታቸው በሚያዝያ ፳፯ ቀን ረቡዕ ከማታው ሁለት ሰዓት አረፈው በማግሥቱ ፳፰ ሐሙስ ጃንሆይና እቴጌ፥ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስና ክቡራን መኳንንቶች ተሰብስበው ራሳቸው በገንዘባቸው ባሰሩት በቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ

እንዲህ ያለ ታማኝና እውነት የሚወድ ሰው ሲሞት ጉዳቱ የመንግሥት ነው ቢሆንም መሰል ልጃቸውን ተከተው መሄዳቸው ከኃዘኑ የሚከፍል ይሆናል እንዲያው ለልማዱ ግን ክብርት ባለቤታቸውንና ልጃቸውን ክቡር በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴን የቀሩትንም ልጆቻቸውንና ቤተ ሰባቸውን ጭምር እግዚአብሔር ያጥናችሁ እላለሁ ።

ምን ያለው ጉበዝ ነው ክፉ መቃብር። ይቅርታ የሌለው አንድ ጊዜ ሲያመር ። በከተማ መሃል ገብቶ በምሥጢር።ቀስ ቀስ እያለ አታሎ ሲኖር። የኋላ የኋላ አመጣ ነገር ። ቲኒሽም አይፈራ ሲደፍር ደፋር። ዝም በል አለና እንዳይናገር ። በላዩ ዘጋበት ደባለቀው አፈር ። ያለውድ በግድ ከቤት ሲወስደው። ለኛ እንደሠራልን እንደወረታው ። ይገባን ነበረ ብዙም ብንረዳው ።አንድጊዜ ከያዘ መቼም ላይለቀው ። በፍጹም ልባችን እየተረዳው፡ የኛ እርዳታ ማድረግ ምንም አይጠቅመው።ቀኙን መንገድ ይምራው ብለን ታገሥነው ። አብልተህ አጠጥተህ እንዲያውም አሳድገህ እኛ ስንል ችላ አብሮ አደግህ እውነት አልተውህም ብላ።ዛሬም ከንተ ጋራ ሄደች ተከትላ። አልለይም ካለች እውነት ትከተልህ ። በልቶ ዘውር ብቻ ምንም አንሠራልህ።በርግጥ ተረዳነው እኛ ምን እንበልህ፣ የምታምነው ጸላት ኢየሱስ ይሁንህ ።

ደግሞ ከዚህቀጥዬ የሚከተለውን የበገና ዓጥም እጽፋለሁ

መፍረሱ ባልነበረማ ። ደግ ነበር ከተማ ። የከተማ ኑሮ ብዙ ሲመቸን በመፍረሱ ብቻ እኛ ተጐዳን ። መፍረሱ ባልነበረማ ። ደግ ነበር ከተማ ። እየጠነከሩ እንደመታደስ ። ብዙ ያሳዝናል ከተማ ሲፈርስ ። ገበያችን ጠፋ አጣን ልብስ ጉርስ፣ ምንእንሁን እኛ ወዴት እንድረስ፣ ዓቅማችን ይኸው ነው እማልቀስ ድረስ ። መፍረሱ ባልነበረማ ደግ ነበር ከተማ፣ ከታች መሠረቱ እጅግ የዘለቀ ። ከላይም ማገሩ በጣም የጠበቀ መንገዱ ቀጥታ ለሰው የታወቀ። ነበረን ከተማ ብዙ የደመቀ፣ ዳሩ ምንይሆናል ፈረሰ ወደቀ ። መፍረሱ ባልነበረማ ። ደግ ነበር ከተማ ። አሁን ምንይባላል ከተማ መፍረሱ ፤ እዚያ የሚኖሩ ወዴት እንዲደርሱ። ከተማን ሲመኙ ይኑሩ ሲያለቅሱ።

ካሳደጉኝ አንደኛው እኔ ፍ ጸ ደምሴ ወልደየስ።

ስለሙሴ ባላኖስ ሞት ።

ሙሴ ባላኖስ የዮናኒ (የግሪክ) ሰው እጅግ ብልህ ሰው ነበሩ። በመሐንድስነታቸውም የተመሰገኑ ነበሩ የፌያት አቶሞቢል ማኅበር አለቃ ነበሩ በዚሁም በአለቃነታቸው እጅግ ከብረው ሲኖሩ በድንገተኛ ሕማም ታመው በ፫ኛ ቀናቸው በግንቦት ፫ቀን ሙተው እንደሮፓ ሕግ አድረው ከሞቱ ፳፬ ሰዓት ሲሆን በጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያና የሮፓ ታላላቅ መኳንንት ሁሉ በመቃብራቸው ተሰብስበው አዝነውላቸው በብዙ ክብር ተቀበሩ ።

ስለ ወይዘሮ በላይነሽ ወልደ አረጋይ ሞት ።

፲፱፻፳፬ ዓመተ ም ግንቦት ፬ቀን አረፈችና በአዲስ አበባ ከተማ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተክርስቲያን ተቀበረች እንኳን ለተወላጅ ዘመዶችዋና አንድ ቀን ላየት ሰው ፀፀቷ ከልብ የሚጠፋ አይደለም ይልቁንም የመልከም ዕድልዋንና ሐሳቧን ያየና የሰማ ሰው በጣም አድርጎ ያዝናል ። በእንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ያሉትን ነዳያንና ደካሞች የተረከበትን ያህል ምጽዋት መጽውታ የኪዳነ ምሕረት ጠበል ጠጥታ ሥጋወ ደሙን ተቀብላ ሙሞቷ በክርስቶስ በኩል ጥቅም የምታገኝበትን ሃሣብ ማሰቧ በጣም ታላቅ ዕድል መታደሏ የሚያስደንቅ ነው ። ነገር ግን አፍላዋን ሳትጨርስ መሞቷ ነው እንጂ የሚአስቈጨው ሞትማ ሲወርድ ሲዋረድ የቈየ ርስታችን መሆኑን ማንም ሰው ቢሆን አይስተውም።

ስለልቅሶ ዜማ ።

እኔ ላልቅስ እንጂ እያልሁ ዋዬ ዋዬ ። ረገፈችብኝ የኔማ አበባዬ ። ታፈራለች ብዬ ብዙውን ስመኝ ። የድንገት በረዶ ቆርጦ ጣለብኝ ። እሔዳለሁ ብዬ መንገድ ብጉበኝ ። እጣሁኝ ብርሃኔን ቀን ጨለመብኝ ። እኖራለሁ ብዬ ስፍራ ሳመቻች ። ፈቃዱ ሆነና በላይ ወደቀች ። አባዬ በላይነሽ ገንዘብ ስጭኝ ብዙ። እርስት ስጪኝ ብዙ ጨምረሽ አትክልት። ለኔ ለወንድምሽ ብርሃን ላጣሁት። ወንድሜ ወልደጻድቅ ምን ያደርግልሃል ርስትና ጉልት ። ወይኔ ይበቃሃል ላንተማ ንብረት ። ከለመንሽኝ ርስት ስጪኝ ካልከኝ ምድር ። እሰጥሃለሁ ሦስትክንድ ከስንዝር።ሰብል መሰብሰቢያው ነበር በበጋው። ገና በመስከረም ታጨደ አበባው ። አዝመራ አዝምሬ በሰኔ ዘሬን እጣሁ ዋኔ ዋኔ ።

ወልደ ጻድቅ ወልደአረጋይ

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አ ይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርስቲያን በታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩል የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ።

ዘዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፡ የልብ፡ የደረት፡ የጉበት፡ የሆላሊት ፡ የጅማት፡ የጨብጥ፡ የቂጥኝና፡ የቋቋቻ፡የሚያዋልድ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፡ የርሻ የፋብሪካ ፡ የደን ፡ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።



ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም እንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቊረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። እትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል እስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴን ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል። ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ባናው አሰናጂ ባዚል እስላኒዲስ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



በለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና ፀጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም

ALEM



ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኜይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሙሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ጴልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፌ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ
S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ከልዑ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፳፪
8^me ANNE. № 22

ሐሙስ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም
Jeudi 26 MAI 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል፡
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ ለኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres.

ስለ ኢትዮጵያ ባንክ አኳኋን ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ይህ ስለ ባንክ የወጣው አዋጅ እንዲፀና መታዘዙን አስታውቃለሁ

በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የተቈረጠው ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

አዋጅ ።

ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ በ፲፰፻፺፯ (በአውሮፓ ቍጥር ሺ፱፻ ፭) ዓመ ም በተቀበለው በኢትዮጵያ ሞኖፖል አድርጎ ይሠራበት በነበረው ውል እንደተፈቀደለት ያወጣውን ገንዘብ ወረቀት ዛሬ በፈቃዱ ሒሳቡን ያጣራልና ሒሳቡን አጣርቶ ለመጨረስ ቀድሞ ያወጣውን በብር የሚከፈለውን የወረቀት ገንዘብ ዋጋውን በብር እየከፈለ እንዲሰበስብ የሚያስፈልገው ስለሆነ በነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት የኢትዮጵያ ባንክ አዋጅ የተመሠረተበትን ሳናፋልስ የወርቅ መሠረት ያለው የኢትዮጵያ ገንዘብ እስኪወጣ ድረስ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ አውጥቶት በነበረው የገንዘብ ወረቀት የሚተካ ሌላ የገንዘብ ወረቀት ማውጣት የሚያስፈልግ መሆኑን አይተን ከዚህ የሚከተለውን አውጀናል ።

አንደኛ

የኢትዮጵያ ባንክ በተጠየቀ ጊዜ ዋጋው በብር የሚከፈል የገንዘብ ወረቀት እንዲያወጣ ተፈቅዶለታል ያከፋፈሉም አኳኋን እንደሚከተለው ተወስንዋል ።

ሁለተኛ

የገንዘብ ወረቀቶችን ይዞ ለሚያቀርብና ለሚጠይቅ ያለ ንቃሽና ያለ ከሳራ በባንኩ ዋና ቤት፥ወይም በማናቸውም ምክትል ቤት (ሰኩርሳል) ወይም የውክልና ቤት (አዣንስ) በኢትዮጵያ መገበያያውን ብር ወይም በውጭ አገር ላምጭው ለትሬቱ ቅናሽ እንዲደረግ በሚከፈል ትሬት በሚባል የገንዘብ ወረቀት ዋጋቸው ይከፈላል።የገንዘብ ወረቀቶቹ ዋጋ በውጭ አገር ላምጭው በሚከፈል ትሬት የሚከፈል የሆነ እንደሆነ ትሬቱ የሚሰጠው በቀኑ ሽረፍ ሒሳብ ስለ እንደዚህ ያለ ዓይነት ገንዘብ ሽያጭ ተብሎ ነው፤ምናልበት ባንድ በባንክ ምክትል ቤት (ሱኩርሳል) ወይም የውክልና ቤት (አዣንስ) ከሚቀመጠው ገንዘብ የበለጠ ወረቀት ዋጋ የተጠየቀ እንደሆነ የወረቀቱ ዋጋ አዲስ አበባ ላይ ከባንኩ ዋና ቤት ላምጭው በሚከፈል ትሬት ይከፈላል ወይም የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከአዲስ አበባ ለማምጣት የሚበቃ የቀን ቀጠሮ አድርጎ ይከፈላል። በዚሁም ምክንያት ወረቀት የያዘ ሰው ማናቸውንም ዋጋ ወይም ኪሣራ መክፈል የለበትም በማናቸውም ምክንያት ግን የወረቀቱ ዋጋ የሚከፈልበትን መንገድ ባንክ ሊመርጥ ይችላል ።

ሦስተኛ

ለነዚህ የገንዘብ ወረቀቶች የባንኩ መሥሬ ገንዘብ ሁሉ በተለይ የቀደምትነት መያዣ ይሆናል። ዳግም እውጭ በየሰው እጅ ባለው በገንዘብ ወረቀት ልክ በመቶው መቶ ሁኖ በነዚህ ወረቀቶች ዋስትና ስም በባንክ ውሥጥ ተቀማጭ ይሆናል፤ ይሽውም በዋስትና ስም ተቀማጭ የሚሆነው የገንዘብ ዓይነት እንደሚከተለው ነው ።

፩) የብር ገንዘብ ወይም በሌሎች ባንኮች ውሥጥ ባደራ ስም የተቀመጠ የብር ገንዘብ ሁሉ።

፪) የኢትዮጵያ መንግሥት ኦብሌጋሲዮን የሚባል የብድር ወረቀት ዋጋው በብር የሚከፈል ስለ ገንዘብወረቀት ዋስትና ተቀማጭ ከሚሆነው የገንዘብ ድምር ከመቶው ዓሥር በላይ የዚህ የኦብሌጋሲዮን ዋጋ በማናቸውም ጊዜ ሊሆን አይችልም።

፫) ኤፌ. እበ. የሚባል ላምጭው ዋጋው የሚከፈል ወረቀት ስለዋስትናው በንግድ ምክንያት የሚተላለፍና የሚሸጥ

ወረቀት ወይም በባንክ ውሥጥ ወይም በዕቃ ቤቱ ውሥጥ ተቀማጭ የሆነ ሸቀጥ መያዣ ያለው ነገር ግን ይህ ዋስትና የሚረጋው ባንክ መያዣ አድርጎ የተቀበለው ነገር ስለሚፈልገው ገንዘብ ዋስትና ለመቶው ዋጋው መቶ ሐያ አምስት የሚያወጣ የሆነ እንደሆነ ነው በዋስትና የተያዘውም ዕቃ ግምት ለመቶው መቶ ሐያ አምስት ሳይሞላ የቀረ እንደሆነ ስለሚመጣው የገንዘብ ወረቀት ዋስትና ሰም ተቀማጭ ሁኖ ሊመረጥ አይችልም ።

፱) ኤፈ ኮሚርሲያል የሚባሉ የንግድ ወረቀቶች ቢያንስ ሁለት ነጋዴዎች ከፋይነታቸው የታወቀ የፈረሙበት ገንዘቡም ተመልሶ የሚከፈልበት ጊዜ ቢበዛ ፫ ሦስት ወር ውሥጥ የሆነ እነዚሁም ኤፈ የተባሉት ስለሚወጣው የገንዘብ ወረቀቶች ዋስትና ሁነው በተቀማጩ ገንዘብ ቍጥር ውሥጥ የሚቈጠሩት በዋስትና ሰም የተቀመጠውን ገንዘብ ድምር ከመቶው ሠላሳ ምን ጊዜም ሳይበልጡ ነው ።

አራተኛ ።

በእንዚህ በገንዘብ ወረቀቶች የተከፈለ ዕዳ ምንጊዜም ዋጋው የተከፈለላትና ዕዳ የሚያስወርድ ይሆናል።በማናቸውም በመንግሥት ገንዘብ ቤት በነዚህ በወረቀቶች የተከፈለ ዕዳ ቀረጥናማናቸውም ዓይነት በብር የሚከፈል ሁሉ ይረጋል። ይኸውም የሚሆነው ባንክ የነዚህን የገንዘብ ወረቀቶች ዋጋ ያለንቃሽ ሲከፍል እቈየ ድረስ ነው ባንክ ግን በዚህ ባሁኑ ሕግ እንደተወሰነው የገንዘቡን ወረቀት ይዞ ለቀረበ ሰው ዋጋውን መክፈል የተወ እንደሆነ ባንክ የተጠየቀውን ገንዘብ ሳይከፍል በመቅረቱ ከሥርዋል ተብሎ ሒሣቡን ያጣራል።

አምስተኛ

ባንክ በቀን በቀኑ ሙጪ የሚያወጣቸው በብር የሚለወጡ የገንዘብ ወረቀቶች መካከለኛ ዋጋቸው ተገምቶ ከዋጋቸው በመቶ በመቶ አንድ ሒሳብ እየታሰበ በወር በወሩ ለመንግሥት ገንዘብ ቤት ታክስ ይከፈላል ።

ስድስተኛ

በ፳፱ነሐሴ በ፲፱፻፳፩ ዓመት በተደረገው አዋጅ በ፵፫ ፵፬ ፵፭ ፵፮ ክፍሎች የተወሰነው ነገር ሁሉ በዚህ በአሁኑ ሕግ ተፈቅዶ ለወጣው የገንዘብ ወረቀትም የጸና ይሆናል ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የጽሕፈት ሚኒስቴር ።

የሠርግ በዓል ።

የሠርጉ በዓል በ፫ኛው ቀን ተፈጸመ ብለን በብርሃንና ሰላም አስቀድመን ጽፈን ነበር ።ነገር ግን የበዓል ደንብ ከ፫ ቀን አያልፍም በማለት ነው እንጂ የወጣቶች ደስታ በጥቂት ቀን ይፈጸማል ለማለት አይደለም ። ፫ቱ ቀን በተለየ ሌላ ሥራ አልተሠራበትምና የሠርግ በዓል ተባለ።ሌላ ሥራ አልተፈታም እንዲሁ በዓሉስ እስከ ዛሬም አላቋረጠም ።

በግንቦት ፫ቀን ከ፯ሰዓት ጀምሮ እስከማታ ድረስ በታላቁ ቤተመንግሥት በዳግማዊ ምኒልክና በተፈሪ መኰንን ትምርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች የሚያስደንቅ ትያትር አድርገው ጃንሆይንና እቴጌን ፥ መኳንንቱንና ወይዛዝሩን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙ።ትያትሩንም አዘጋጅዎች ለዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ነው። ለተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ሐዲስ ዓለም አየሁና ዘርይሁን ወግአየሁ ናቸው።

የትያትሩን ነገር ለመጻፍ ብዙ ስፍራ የሚይዝ ስለሆነ ከአቶ ዮፍታሔ ንጉሤ የተገጠሙትን ድንቅ አማርኛ ያለባቸውን ግጥሞች በሚከተለው መስመር ጽፈናቸዋል ።

፩ ፤ ፍሬውንም አየን በሠላው አምሮ ።
እጅግ መልከም ነበር አበባው ተድሮ ።
፪ ፤ የሰው ወርቅ አያደምቅ ይላል ሰው ተላላ ።
የእኛ ወርቅ ምነው ታደምቃለች ሌላ ።
፫ ፤ ኀፍረት የሌለው ሰው እንደዚህ ልጅ የታል ፤
ምን አባቱን ሁኖ ሰው ይመለከታል ።
፬ ፤ ምን አስፈራው ያንልጅ በጥቂት ሰው ፊት ።
ብዙ ሰው መሃል ገናና ሲሉት ።
፭ ፤ መቋሚያ ነው ስንል ሲቀበል ከአባቱ ።
ከዘራ አደለምወይ የያዘው በጣቱ ።
፮ ፤ ውቢቱ ሙሽራ ከሰፋችልን ።
መሰብና አገልግል እናቀርባለን ።
ሙሽራችን ምረጥ የምትገዛውን ።
ሁለቱን አገልግል ትገዛ እንደሆን ።

በግንቦት ፲፩ቀንም በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ግቢ ለሮፓውያን የራት ግብዣ ነበረ።የተጠሩትም የክቡር ዲፕሎማቲክ ሰዎችና በከተማ ከሚኖሩ ታላላቅ ሰዎች ነበሩ።ቍጥራቸውም ከስልሳ ይበልጣል ። ግብዣውንም እጅግ አመስግነዋል ።

ከራት በኋላም ለመጠጥ ግብዣ(ለስዋሬ)የተጠሩት ሰዎች ከመቶ ይበልጡ ነበር ።

ምላሽ ።

የሙሽራይቱ የልዕልት ወለተ እስራኤል አባት ልዑል ራስ ሥዩም ሙሽሮችን በግንቦት ፲፩ቀን ጠርተው ነበር።በዚሁም ቀን ልዑላን የኢትዮጵያ መሳፍንትና ክቡራን ሚኒስትሮች፥ መኳንንትና የክቡር ዲፕሎማቲክ ሰዎች ፥ በከተማ ከሚኖሩ ሮፓውያንም ብዙ ሰዎች ተጠርተው ነበሩ።

የልዑል ራስ ሥዩምም ቤት እጅግ አምሮ ተዘጋጅቶ የቤቱ ውጭና ግቢው በኤሌትሪክ ብርሃን ጨለማው ርቆ የማለዳ ፀሐይ መስሎ ይታይ ነበር ። የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንና ልዕልት ወለተ እስራኤል ባማረ አቶሞቢል ሁነው ሚዜዎች ቢትወደድ ጌታቸውና ደጃዝማች አበራ ከሣ በጥሩ በጥሩ አቶሞቢል ተከትለዋቸው ቀደም ብለው በደረሱ ጊዜ የሴቶች ዕልልታ አለልክ ደመቀ ። የተጠሩትም ሰዎች የቀጠሮው ሰዓታቸው ከማታው በ፪ሰዓት ነበርና ጥቂቶች በዚሁ ሰዓት ደረሱ የሆነ ሁኖ ሁሉም እስከ ሁለት ሰዓት ተኩል ድረስ ጨርሰው የተጠሩት ሁሉ ገቡ ። የቤቱ ሥርዓት የወምበሩና የምንጣፉ አኳኋን እጅግ የሚያምር ነበረ ።ልዑል

ራስ ከማ ፣ ልዑል ራስ ኃይሉ ፣ ልዕልት ተናኘ ወርቅ ከባለቤታቸው ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ጋራ ባማረ አቶሞቢል ሁነው የሚያንጸበርቅ ነጭ ሐር ልብስ ለብሰው ብቅ ባሉ ጊዜ ከኤሌትሪክ መብራት ጋራ በአንድነት አበሩ ። የሚመጡትንም እንግዶች ወደ በረንዳው ላይ ወጥተው የሚቀበሉ ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻና ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነበሩ ። ግብዣውም ልክ እንደ ሮፓ ሥርዓት ነበረ ። የአቀማመጡን ተራ የሚአዘጋጅ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ጸሐፊ ነበረ ። ግብዣውም እጅግ የተመሰገነ ከሮፓ መጠጥ ይልቅ ጠጅና ወጡን የኢትዮጵያን የመረጡ የሮፓ ሰዎች ነበሩ።የልግሥናውም ነገር መጠን አልነበረውም። ከግብዣውም በኋላ ደስ የሚአሰኝ ፒያኖ እየተመታ ዳንስ ተደረገ ። በዚህም ጊዜ ጣፋጭ ምግብና የሮፓ መጠጥ በየዓይነቱ ተዘጋጅቶ ሰው ሁሉ የወደደውን ይጋበዝ ነበረ ። ሰዓቱ ሳይታወቅ በደስታና በጨዋታ ፯ሰዓት ሆነ። ከዚህ በኋላ የፈጠኑ ሰዎች እያመሰገኑ መሔድ ጀመሩ። ያልቸኰሉም ገና አልተመለሱም ነበር ። ከሠርጉ ምላሹ በማማሩ ያየ ሁሉ እጅግ ደስ አለው አበባው እንዳማረ ፍሬውን አሳምሮ ለማየት ያብቃን እያለ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ይገልጻል ።

ደብ ራሱን ስለት ድጉሱን

ማና እሚባለው ክፍል ጅማ አውራጃ አንድ አባቡልጉ አባመጋል የሚባል ያገር ጨዋ (ሹሬሳ) ነበረ። ጨዋ መባሉም በልምድ ነው እንጂ በምግባሩስ ባሌጌ መሆኑ ቀጥዬ በጻፍኳቸው መስመሮች ይታያል። በዚሁ በማና ክፍል አባቅደም የሚባል የሌቃ ሰው ሽፍታ አገር አጥፊ አለ። ይሁ አባ ቡልጉ አባ መጋል የሚባለው አባቅደምን ከነአሽከሮቹ ጋብዞአቸው ሲበሉ ሲጠጡ ቈዩና ሲሰክሩ ቀረርቶ ተጀመረ ይኸ ጋባዥ ያገሩ ጠላት ወንድሞቼ የጋበዝሁአችሁ በሥውር በልታችሁ ጠጥታችሁ ልትሔዱ ነበረ አሁን ግን ሰው እንዲሰማ ሆነ ተዉ ቀረርቶውና ተኵሱ ይቅር ቢል ከዚሁ ከሽፍታው አሽከር አንዱ ፌት አልሆነ ስፍራ አስቀምጠኸኝ አሁን ደግሞ ጨዋታ ትከለክለኛለህ ብሎ ያባ ቡልጉ አባመጋልን ወንድም አባዲጋ የሚባለውን በጥይት ገደለው ባለቤቱንም አቍስሎት ይታከማል። ፪ኛ አሕመድ የሚባል የዚህ የማና ክፍል ዘበኛ ሁኖ ይጠብቅ የነበረ እሱው አጥፊ ስለሆነ አባጆቢር አባዱላ ይዞ ገርፎ ጥቂት ጊዜ አወህኔ አሥሮት ነበረ አባጆቢር አዲስ አበባ ሲወጣ ከወህኒ አመለጠ ተብሎ እዚያው አለመደበት ማና ገብቶ አገር ያጠፋል።በጅማም አውራጃ በየክፍሉ ሽፍታ እየሆኑ አገሩን የሚያጠፉት እነዚያው ያገሩ ተወላጆች የየሰፈሩ ልጆችና ባሮቻቸው አገረ ገዥው እየሾመ ዘበኛ እያለ ያስቀመጣቸው ናቸው ለገዛ አገሩ ጠላት ሁኖ ማጥፋት ግን እጅግ የሚገርም ነው። ፫ኛ ዘበኞቻቸውና የአገሩ ተወላጆች የገዛ አገራቸውን ማጥፋታቸውን የሚያስረዳ መጋቢት ፳፩ቀን ከማታው በ፩ሰዓት በዶና ቆሬ በሚባለው ክፍል የሚጠብቁ ዘበኞቻቸው ጅሬን ውለው ሲመለሱ ሐርማታ እነጋዴው ሰፈር አምሽተው ጠጅና አረቄ ጠጥተው ሲሰክሩ ተመሽታ ቤት ወጥተው እመንገድ ላይ ተቀምጠው ሳሉ አንድ የከተማ ዘበኛ በቅሉ ው ጠፍቶበት ሲፈልግ አጠገባቸው ደረሰ፡ብረት ሳቲዝ ለምን መጣህ ብለው በጥይት ሮምታ ተኵሰው ገደሉት ።ያ ኸንኑም ተኩስ ሰምተው የክቡር ነጋድራስ ሣህሌ ባልደረባች ባለመለዮ ዘበኞች ደረሱ እነዚሁ ይኸን ወሬ የሚባለውን የገደሉ አባሕር ዛፍ ውሥጥ ተሸሽገው ነበሩና በዘበኞቹ ተኰሱባቸውና ስንታየሁ የሚባለውን የጠመንጃውን በምባ ገሸለጠው አያኖ የሚባለውን ዓይነስቡን ጨረፍታ መትቶት ቈሰለ።ይኸንንም የሠሩት እነማን እንደሆኑ አውቀናቸዋል ጊዜው ሲደርስ ስማቸው ይገለጣል። ፬ኛ አፈሳ የሚባል የነጋድራስ ሙሴ ጸሐፊ አባጅፋርና አባጆቢርም ያወቁት ምሥጢርም ተካፋይ ታማኛቸው ነበረ። የጅማም ጉምሩክ ሲቆም በጸሐፊነት ሰጥተውት ሲሠራ ቈየ። አንድ አሽከር ነበረው ግዛው የሚባል ጠመንጃም ገዝቶ ሰጥቶት ነበረ ይኸ ግዛው ተነዚሁ ተውጭ ስመ ዘበኞች ጋራ ጓደኛ ሁኖ ከነሱ ጋራ መዋል ጀምሮ ነበረ መጋቢት ፳፯ቀን ተጓደኞቹ ጋራ ሲሔድ አገኘውና እኔ ጠመንጃ መስጠቴ እኔን ልትጠብቀኝ ነበረ ውሎህ ግን ከነዚህ ከሆነ ጠመንጃዬን ስጠኝ ብሎ ተቀበለው።ግዛውም ጠመንጃውንም ቢወስድበት ጌታውን ተከትሎ ነበረ መጋቢት ፳፯ቀን የመድኃኔዓለም በዓል ነግሦ ስለሆነ በጠዋት አፈሳ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጣ ግዛውም ጀሌውን ተከትሎት ነበረ ተቤተ ክርስቲያንም ምላሽ ወደ ጉምሩክ ደረሰና ተማታው በ፲፪ሰዓት ቆጭ እሚባለው ሙንደር ዘውዲቱ እምትባል ሴት ቤት ገዝቶ ነበረና ፲፰ደቂቃ ቈይቶ አደኤባ እምትባል መሸተኛ ቤት አምሽቶ ጊንጆ እሚባለው ክፍል ሲደርስ በ፪ጥይት አፈሳ ግዛውን ገድሎ እቤቱ ጅሬን ገብቶ አደረ። ተሱ በኋላ የመጡ ሰዎች አሬሳውን አይተው ለነጋድራስ ሣህሌ በነግሩአቸው ነጋሬዎቹን ይዘው ዘበኛ ልከው አሬሳውን አስነሥተው በአቅራቢያው እጋላ ቤት አሳድረው ወደ አፈሳ አሽከርህ ሙቶአል ብለው ላኩበት እሱም ሚስቱም የኃዘን ልብስ ለብሰው እየጮሁ ሬሳውን ከነጋድራስ ሣህሌ ጋራ አስነሥተው እቤተ ክርስቲያን መጡ። ነጋድራስ ሣህሌ ግን ጠርጥረው ነበርና ጸሐፊና ሽማግሌ ይዘው ምርምር ጀመሩ፤ ምልክትም ስለአገኙ በምርምሩ ጠንክሩ እሱ መግደሉ፡ የሚያስረዳ ብዙ ምክንያት ከተገኘ በኋላ እራሱ አምኖ ገድየአለሁ አለ በጅማ እንደዚህ በየመንገዱ እየሞቱ የቀሩ ብዙ ናቸው አንድም ሰው የሞቱበትን ምክንያት የፈለገላቸው አልነበረም የሰውም ደም እንደ እንስሳ ደም ነበረ ዕድሜ ለብርሃኑ ንጉሠ ነገሥታችን ደማችን ተከበረ ብሎ ክርስቲያኑም እስላሙም ንጉሠ ነገሥቱን መረቀ በነጋድራስ ሣህሌ ብርታት ስለተገለጠ

ያጋሉ አባወሎ።

መልስ ።

ስለአንዲት ልጅ አገረድና ስለ፫ ተማሪዎች ጋብቻ ክርክር በመጋቢት ፳፪ ቀን ባ፲፰ ቍጥር በ፺፫ ገጽ አቶ ትስብእተወልድ አግዴ በመጀመሪ መጥቷን በሩቅ ያየው ያግባት ወይስ ያሥሩን ዓመት መንገድ ባ፳ደቂቃ የደረሰው ያግባት ደግሞስ ከሞት ያስነሣት ያግባት ብሎ አርእስቱን ምሳሌ አድርጎ ወደ አቶ ዳኝነት ስለጻፈው ማመልከቻ ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ

፩ኛ ከሩቅ የሚሆነውን የሚያዩና የሚሰሙ የቴሌስኮፕና የቴ እደላንት የሳንሬልና የቴሌፎን ጠቢባን እሉ ፪ኛ በራሪው ያግባት እንዳንል ያውሮፕላኑና የሲጤላን የዘፕሌን ጠቢባን እሉ ከሞሞት የሚያስነሣ ግን ሁሉን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር እንጂ ለፍጡር ያልተሰጠ ሥልጣን ነውና በውነት ሙት ለማንሣት የሚችል ፍጡር ከተገኘ ሙት እንሺው ያጣባት ብለው የፈረዱትን ቃል እይቼ በንግግሩ መቀልጠፍ እጅግ አመሰገንሁ ነገር ግን በሩቅ ተመልክቼ ይቀርበት እንዳይባል ከአካል ሁሉ ዓይንን ለማብለጥ ማኅቶቱ ለሥጋከ ዓይንከ ውእቱ እንደተባለ የሥጋ መብራቱ ዓይን ስለሆነ ምንም በሩቅ የሚያዩና የሚሰሙ እንቴሌስኮፕና እንቴሌፎን ቢኖሩ የቴሌስኮፑም ዓይን የሌለው ሰው ሊአይበትና በቴሌፎኑም የሚሰማ ጆሮ የሌለው ሰው ሊሰማበት የማይቻል መሆኑን የሚስተው ሰው የለም ፪ኛም ያሥሩን ዓመት መንገድ በደቂቃ ያደረሰው ይቅርበት እንዳይባል ምንም አየሮፕላንና ሲፕላን ቢኖሩ መኪናዎቹን ለማስኬድ የሚረግጥበት እግር የሚጨብጥበት እጅ የሚመለከትበት ዓይን ያለው ሰው ካልነዳቸው አውቀው በርረው እንዳይሔዱ የታወቀ ነው።፫ኛም ከክርስቶስ በቀር ፍጡር የሆነ ሰው ከሞት ለማስነሣት አይችልምና ከሞት ያስነሣት ያግባት እንዳይባል ፍጡር የሆኑ ነቢያት ሙታን ሲአነሡ እንደቈዩና ሐዋርያትም ሐሩ ወመሀሩ ሕሙማነ ፈወሱ እለ ለምፅ እንጽሑ ወሙታነ እንሥኡ እንደተባሉ የሚስተው ሰው የለም ስንኳን ለ እነዚህ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸውና ወሀለዎ እንዶሬውያት ዘያቅነሐ ምውተ እንደተባለ አንዲት የእንዶሬውያን ሴት ሙት እንሥታለች እየተባለ ሲነገር ይኖራል።አሁንም ስንኳንስ ታናሺቱ ልጅ አገረድና ታላቂቱ እመቤታችን ብትሆን በጠበቄንት ለዮሴፍ በጣ ደርሳለችና ይህችንም በጣ የደረሰው ሰው ይውለዳት እንጂ ከነዚህ ከሦስቱ ልጆች የውቀት ብልጫ ያለበቱው አይመስለኝም። ነገር ግን አቶ ትስብእቶ ወልድ አግዴ መጀመሪ ሲጽፉአርእስቱን ምሳሌ ማለቱ ምሥጢር ነገር ቢኖርበት ነውና ሌላው ሰው ምሳሌውን ለማግኘት የማይቻለን ከሆነ ዋናው አቶ ትስብእት ወልድ አግዴ ምሳሌ ያለበት ምክንያት እንዲአስረዳን ተስፋ ማድረግ ይሻል ይመስለኛል ።

ዓይን ዓለም ገብረማርያም ።

ስለ ደግ ሥራ ዋጋ ማግኘት ።

እነሆ ክቡራን አንባቢና ተመልካቾች ሆይ ክፉ የሠራ ፍዳ፡ ደግ የሠራ ምንዳ እንዳያጡ የታወቀ ነውና በምሥራቅ ጅጅጋ የተደረገውን የደስታ ነገር ላከፍላችሁ ሙልእም (መስለኝ) ጽፌላችኋለሁ እንግዲህ ከቅንነት የተገኘው ዋጋ ቀጥሎ ያለው መሆኑን አስረዳለሁ ።

ክቡር ደጃዝማች ገብሬ የሐረርና ያውራጃዋ እንደራሴ ሁነው ከልዑል ራስ መኰንን ጀምረው እስከ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ እስኪዘወር ድረስ ያለአንድ ቀያሜ ኑረው ነበረና ትንሹም ትልቁም የሐረርም ሠራዊት እንዳባት በፍቅር፡ እንደጌታ በክብር ሲአመሰግኟቸው የዳማጪን ልብ ደስታ ያሰምጠውና ይመስጠው ነበረ።ፍሩ ግን የደግ ልጅ ዘሩ የክፉ ሰው በሩ ይመሰክራል እንደተባለው የክቡር ደጃዝማች ገብሬ ልጆች በፍጹም መንግሥታቸውን አክብሬ ፈጣሬአቸውን ፈሪ ለችግረኛ ተዘከሪ የቅንነት መሪ ሁነው ከመኖር በቀር በማነኛውም ነገር ቢሆን እስከሁን በጥፋት ው ሥዋ አልተገኙም ስለሆነም ከልጆቻቸው መሀከል ክቡር ፊታውራሪ መዝለቂያ ገብሬ ባተለይ የዘሬውን ሥልጣኔ የሚከተሉና የመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር እያሻሻሉ የሚሠሩና ደግሞም ፩ተኛ በውጋዴን አውራጃ የሱማሌን ባህል አውቀው መዘረፍንና የመጋደል ግጭትን በማስቀረታቸው ፪ኛም ከሰጋሀመዶው እንሥቶ እስከ ጅጅጋና ከጅጅጋም ቀጥሎ አይሻ ጣቢያ ድረስ የመንግሥት ገንዘብ ወጭ ሳይሆን የአውቶሞቢል መንገድ አሠርተው ውጋዴንና ጅጅጋን ከጅቡቲና ከድሬ ደዋ ባቡርን በማገናኘታቸው በሐረር አውራጃ ያለ ሠራዊትና የሥራውንም አኳኋን የተመለከተው ሁሉ የማያመሰግናቸው የለም እንደዚሁም ደግሞ ከጅጅጋ ደጋሀቡር ስልክ በማስተከላቸውና የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተክርስቲያን ማሰራታቸው የስማቸው መታሰቢያ ሳይሆን አይቀርም በማለት ያሳስባል ።

ስለዚህ ይህንኑ የመሰለውን የቅንነት ሐሳባቸውን ሁሉ የውጭ ሀገር ነገሥታትና የሮም ፓፓም ስለሰሙላቸው የደስታ ምልክት ከፍተኛ የወርቅ መስቀል ኒሻን አባ ዮአሺን በሚባሉት መነኵሴ እጅ በ፳፯ የካቲት ልከውላቸው ስለኒሻኑ በዓል ብዙ ሠራዊት ተሰብስቦ ነበርና አባ ዮአሺን ቀጥሎ የተጻፈውን ዲስኩር ስለፓፓው ሁነው ተናገሩ።

ክቡር ፊታውራሪ ሆይ ፣ በዚህ ከፍ ባለው ማዕርግዎና ሕዝቡም በተሰበሰበበት ቀን ለዚህ ማዕርግ ተመርጩ የከበረውን [illegible] ለማልበስ ስለመጣሁ ለኔም ደስታ ወሰን የለውም ለዚ [illegible] ዓል ለመግለጽ ክቡር አባታችን አሀዙኝ ሥልጣናቸው [illegible] ስለርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፲፩ኛ ፒዮስ ሆኜ የቅዱስ ሲሊቪስተር የሺቢልዩ በተለይ ከፍተኛ የወርቅ መ መስቀል ኒሻን የላኩልዎትን እንዳለብሰዎ መፈቀዱ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ትክክለኛነትና ታማኝነትዎን ያስረዳልና ክቡር ፓፓም ከፍተኛውን የወርቅ ኒሻን የላኩልዎትን ለከፍተኛ ማዕርግ የታመኑ መሆንዎን ስለሰሙና ስለተረዱት ነው ። እነሆ ይህ የቅዱስ ስቪለቴር የክብር ኒሻን መስቀል በደረትዎ ላይ እንደሰማይ ከዋክብትና እንደጧት ጎህ ፀሐይ ያብራልዎ ። ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰውም ፊት የከበረ ይሁንልዎት ብለው ምርቃታቸውን በጨረሱ ጊዜ የተሰበሰበው ሠራዊት በሙሉ ልብ በደስታ ቃል የደስታ በዓል ያድርግልን ብሎ ዳር እስከዳር ፫ ጊዜ አጨበጨበ ።

፪ኛም ስለበዓሉ ታላቅ ግብርና በየዓይነቱ መጠጥ ተደርጎ ሳለ የዲሬክተሩ የበላንባራስ እሺቱ ዲስኩርና ያቶ ደነቀ ተክለጊዮርስ እንደዚሁም ያቶ ኃይለ ማርያም ቢሮና ያቶ ተ ማ ሀብተ ማርያም ምርቃት በየተራ እየተነበበ በታላቅ ደስታ ተጨበጨበ የተሰበሰበውም ሰራዊት እጅግ ጣፋጮችን በያይነቱ የሀገራችንን ምግቦችና መጠጦችንም በፍቅር ጠጥተውና ተጋብዘው በሽምፓኝና በውስኪ ተመራርቀው እያ

መሰገኑ ሐዱ እያችሁን ክቡራን አንባቢዎችና ተመልካቾች ሆይ ከደግ ሥራ የሚገኘውን ዋጋ ማንም ሰው ቢሆን በቅንነት የመንግሥቱን ሥራ ከሠራ መልኩን የማያውቁት ሁሉ እንዲያመሰግኑትና እንዲረዱት የታወቀ ነውና ምናልባት ሰው ሁኖ ብተሾመበት ስፍራ ሕዝቡንና ሀገሩን የሚበድል ተንኰል ነገር የሚሠሩ ሰዎች ቢኖሩ የሚቀበሉት ዋጋ ክፉ ምን ይሆን በማለት እናስባለን ። ለደግ ሰው ቀብ ለክፉ ሰው ልብ እግዚአብሔር ይስጥልን ክቡር ፊታውራሪ መዝለቂያም አሁን ሁለተኛ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ውጋዴንን በየክፍሉ ለመጐብኘት በመጋቢት ወር ስለወረዱ የኢትዮጵያ አምላክ በደኅና ይመልሳቸው አሜን የብርሃንና ሰላም ተመልካች ደ ተ ጊ ።

ስለ ብርሃንና ሰላም ምስጋና ።

ብርሃንና ሰላም ወዳጄ ከተገናኘን ጀምሮ ከኔ ጋራ ፍቅራችን ፅኑ ነው ፡ ከመውደዱም የተነሣ ሁለት ተእምራት አይቶ እጅግ አጥብቆ ደስ አለኝ። መጀመሪያ ከዲስአበባ በተሸሸገ በታቆነበረ ይሁዳ ከተቀበረበት በታ ሚያዝያ ፳፫ ቀን የትንሣኤ ለት ከኢትዮጵያ ተነሣ ማለትን ብሰማ እሑድ መነሣቱ ደስ አለኝ።

ሁለተኛ በገንዘብ እየተፈለገ ለታንኳ የሚፈለገው ደንገል ብዙዎች ከባዶች ዛፎች እንደየዘ ምድርሃ ገብቶ በተአምራት በኅዳር ፯ቀን ተተከለ ማለትን ሰምቼ እመቤታችን ንጽሕት ማርያም በነሐሴ ፳፫ ቀን የሙታ ችግር ያለበትን ደብረ ፅቆናን አፍልሳ በኢያሪኮ ዳርቻ ለመትከሏና በኅዳር በ፯ቀን ጌታችን ሕዓለም ሐዋርያትን፤ ከጽርሐ አርያም መላእክትን ይዞ በርስተ ሐዋርያት ቍስቋም መቅደሱን ያሳሰበል፤የይሁዲውም መነሣት እሑድ ስለ ሆነ አንድ መወድስ ሰጠሁ ።

እምኀልኅታሁ ኅብእት ዘኢትዮጵያ።
ይሁዲ ትንሥአ በዕለተ ትንሣኤ እሑድ፥
ወትንሣኤሁ ኢእምኑ እጽራሪ ትንሣኤ አይሁድ ።
ከመ ትንሣኤሁ ለዘወርኀ ወልድ።
ወተአምራት ይተልዋሁ፡ ለእግረ ይሁዲ ቀሊል በፍርሃት
መበረዓድ።
ብንኢኒ ወመጺሀ ዘቤተ ይሁዲ ልማድ።
አበየ ወኢሰተየ ኢትዮጵያ በውስተ ዓውድ።
ለእምልከ ሐዲሰ ስልክል እንተ ኢይትአመር በሰዶ።
አከኑ ኢትዮጵያ ለዓለመ ዓለም ኢይሰግድ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርሪዔ ኅዘን



ስለ ደጃዝማች መኰሮ ገርማሜ ሞት ·

ጀግናው ደጃዝማች መኰሮ ገርማሜ ጀግንነትንና ቅንነትን አጥብቀው ይዘው ይኖሩ ነበር ። በልጅነታቸው ጀምረው ለአንበሳና ለዝሆን ለቀሩትም አራዊት ሁሉ መልአከ ሞታቸው ነበሩ። በተላኩበትም ጦርነት ሁሉ ድል ማድረግ እሳቸው ባሉበት ወገን ነበረ ። በልጅ ኢያሱ ጦርነት ሁሉ ከሚኤስ ጀምረው እስከ ደሴ ድረስ ድል ከማድረግ አልተመለሱም ነበር ። ይልቁንም በራስ ጉግሣ ወሌ ጦርነት ጊዜ በፊት ተሰልፈው በመትረየስ ሰልፉን በትነው የተላኩበትን ፈጽመው ጌታቸውን ደስ አሰኝተው ተመለሱ ። በዚህም ምክንያት ታላቅ ማዕርግና ሽልማት ተቀብለው ነበር ። ነገር ግን በላይ እንደተናገርነው በረኃ በማዘውተር ምክንያት የገዳይ ደዌ መርዝአቸው መንሸ እየሆነ ሁልጊዜ ያማቸው ነበርና ከራስ ጉግሣ ወሌ ጦርነት ከተመለሱ እየበረታ ስለሔደ ወደ ሆፒታልም ቢመላለሱ መዳን ሳይሆንላቸው ቀረ ። ከሆፒታል ወደቤታቸው ተመልሰው ፲፫ቀን ያህል ቈይተው በግንቦት ፲፫ቀን ሙተው ጃንሆይና እቴጌ መጥተው አዝነውላቸው፤ ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ወይዛዝር አልቅሰውላቸው፤ሊቃውንትና ካህናት ፍታቱን አሰምረውላቸው፤ ልክ የሌለው ሠራዊት አዝኖላቸው በአዲስ አበባ ከተማ ባለው በመናገሻ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበሩ። ዕድሜአቸውም ፵፰ ዓመት ነው የጀግና የብልህ ሞት ምንም ጕዳቱ ለአገር ቢሆን ባለቤታቸውን ክብርት ወይዘሮ አሰለፈችንና አሽከሮቻቸውን ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል።

የመኰሮን መሣሪያ እነማን ወረሱ ።
ሚስቱን ያስለቀሳት የጁ መትረየሱ፡
ልጅ በማጣቱ ነው ሕዝቡ ያዘነለት ።
ለመታሰቢያማ የጁ ጦር አለለት ።

የልብ ወዳጃቸው አቶ ተሰማ እሼቴ ከዚህ በላይ የተጻፈውን የልቅሶ ዜማ ግጥም ጻፉላቸው ። ወይ ወዳጅ እንዴት ወዳጅ ይቅር ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።
ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶመቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።
ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ሳንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርደና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከቌ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቀን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች [illegible] የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።



ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከነድ ቀን አንድ ቀን እየተዋዉት ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መከ ና ብዱ፲ እስከ ፴ወር እንዲወለዱ ይፈትዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቁረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የነበሩ መኪኖችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት ለንዲጎበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን ማቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል እስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ለ
አጠገብ መሆኑ

በማክበር ያስታውቃል። ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ናሙ አሰናጂ ባዚል እስላኒዲስ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቀውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፤ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ አንድ ትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለት ልቅ ምልክቱ ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር ፣ የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወኪሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በከዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አበከት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሙሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ለአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ጫልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. & E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በተዳማዊ ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፳፪
8me ANNE. № 22

ሐሙስ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 26 MAI 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የፈረሶች መቀዳደም ።

በግንቦት ፲፪ቀን የፈረሶች መቀዳደም በጃንሜዳ ተደርጎ ነበረ ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዑላን መሳፍንትንና መኳንንትን አስከትለው ፱ሰዓት ሲሆን መጥተው በተዘጋጀው መንበረ ዳዊት ላይ ተቀመጡ ።ልዑላን መሳፍንትና መኳንንትም በየማዕርጋቸው ተቀመጡ ። የውጪ አገር ሰዎችም የፈረሶችን መቀዳደም ለማየት የመጡ ብዙ ነበሩ ። ፱ሰዓት ተኩል ሲሆን መቀዳደም ተጀመረ ።

የመጀመሪያው መቀዳደም ኖቢስ ክብ የሚባለው የሜዳው ርኅቀት ፩ሺህ ሜትር ነበረ ። መጀመሪያ የቀደመ ዋንጫና አርባ ብር፥ ፪ኛው ፴፭ብር፥ ፫ኛው ፳፭ ብር ፥እንዲቀበል ደምብ ተደርጎ ነበረ ።

በዚሁ መቀዳደም ።

፩ኛ ዳምጠው የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነ ።
፪ኛ ዳንት የኢጣልያ ሌጋሲዮን ፈረስ ሆነ ።
፫ኛ ዳመና የመርዕድ አዝማች አስፋወሰን ፈረስ ሆነ ።

የሁለተኛው መቀዳደም ።

የሜዳው ርኅቀት ፩ሺሕ ፳፪ ሜትር ነበረ። በዚሁ መቀዳደም የመጀመሪያው ሰማንያ ብር።
፪ኛው ፵ብር።
፫ኛው ፳፭ብር እንዲያገኝ ደምብ ተደርጎ ነበረ።
በዚሁ መቀዳደም ሐረር የመርዕድ አዝማች አስፋወሰን ፈረስ መጀመሪያ ሆነ ።
፪ኛ ጉራ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነ።
፫ኛውን አልቈጠሩትም

የ፫ተኛው መቀዳደም ።

የሜዳው ርኅቀት ፩ሺ ፭፻ሜትር ነበረ በዚሁ መቀዳደም
የመጀመሪያው ፪ የኢጣልያ የወርቅ ዋንጮች ።
፪ኛው የመታሰቢያ ዕቃ እንዲአገኝ ደምብ ተደርጎ ነበረ።
በዚሁ መቀዳደም ቡልቲሞ የኮንት ዲቸለሬ ፈረስ ሆነ
፪ኛ የማዳም እንብሮድሜድ ፈረስ ቲፎን ሆነ።

ያ፬ኛው መቀዳደም ።

የሜዳው ርኅቀት ፪ሺሕ ሜትር ነበረ በዚሁ መቀዳደም
፩ኛው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የወርቅ ዋንጫና ዓርባ ብር
፪ኛው ፴፭ብር
፫ኛው ፳፭ብር እንዲአገኝ ደምብ ተደርጎ ነበረ።

በዚሁ መቀዳደም

፩ኛ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሩብር ሆነ
፪ የመርዕድ አዝማች አስፋወሰን ፈረስ አውራሪስ ሆነ።
፫ኛውን አልቈጠሩትም

ያ፭ኛው መቀዳደም ።

የሜዳው ርኅቀት ፫ሺሕ ፪፻ሜትር ነበረ ። በዚሁ መቀዳደም
፩ኛው የልዑል ዱክ ዴዝአብሩዝን የወርቅ ዋንጫና ፵ብር፥
፪ኛው ፴፭ብር ፫ኛው ፳፭ብር እንዲአገኝ ደምብ ተደርጎ ነበረ

በዚሁ መቀዳደም

፩ኛ ጐንደር የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ጥርኝ ሆነ
፪ኛ ቡሎ የልዑል መኰንን ፈረስ ሆነ
፫ኛውን አልቈጠሩትም
የ፮ኛው መቀዳደም ለወታደር አለቆች ተሰጥቶ ነበረ
የሜዳው ርኅቀት ፩ሺሕ ሜትር ነበረ

በዚሁ መቀዳደም ።

፩ኛው ሠላሳ ብር
፪ኛው ፲፭ብር ።
፫ኛው ፲ብር ከጃንሆይ እንዲቀበል ደምብ ተደርጎ ነበረ።

በዚሁ መቀዳደም ።

፩ኛ የጁ የትርፌ ዱባለ ፈረስ ሆነ ።
፪ኛ ጊዳ የልጅ አበበ ደገፉ ፈረስ ሆነ ።
፫ኛ ቄንጆ የልጅ ተሰማ አያኔ ፈረስ ሆነ ።

የ፯ኛው መቀዳደም ።

የሜዳው ርኅቀት ፩ሺሕ ፪፻ሜትር ነበረ።በዚሁ መቀዳደም
፩ኛው የሐሪንቶን የወርቅ ዋንጫና አርባ ብር ፥
፪ኛው ፴፭ብር ።

፫ኛው ፳፭ብር እንዲአገኝ ደምብ ተደርጎ ነበረ ።
በዚሁ መቀዳደም ።
፩ኛ ማሳውድ የሙሴ ጋሌብ ፈረስ ሆነ ።
፪ኛ አኬን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነ።
፫ኛ ሲልባኖ የኢጣልያ ሌጋሲዮን ፈረስ ሆነ።
የ፲ኛው መቀዳደም ። በ፱ሰዓት ተኩል ነበረ ።
የሜዳው ርኅቀት ፩ሺሕ ፭፻ሜትርነበረ በዚሁ መቀዳደም።
፩ኛ የግርማዊት እቴጌ መነንን የወርቅ ዋንጫና አርባ ብር ።
፪ኛው ፴፭ብር ።
፫ኛው ፳፭ ብር እንዲአገኝ ደምብ ተደርጎ ነበረ።
በዚሁ መቀዳደም ።
፩ኛ ጋ`ቶ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነ።
፪ተኛ ሰገሌ የግርማዊት እቴጌ መነን ፈረስ ሆነ ።
፫ኛውን አልቈጠሩትም ።

ደግሞ ከውርርድ ያልገቡ ፈረሰኞች ተቀዳደሙና የሙሴ ክስሮፍ አሽከር በቀለ ቀድሞ ከጃንሆይ ፳፭ብር ተቀበለ ።

እንዲሁ ይህ ቀን እስከ ፲ሰዓት ድረስ አለሐሳብ ዋለ ። ነገር ግን የኛን አልን እንጂ እንቀድማለን በዮችማ ከሐሳብ እንዳያርፉ አይጠረጠርም ።

ይህም የሽልማቱ ዕቃ ሁሉ በጃንሆይ ፊት ቀርበ የቀደሙት ሲታደሉ ወደ ኋላ የቀሩት ፊታቸው ተለውጦ እጅግ ያሳዝኑ ነበር ። ምን ይሆናል ምን ቢጣጣሩ አለዕድል መቀደም አይቻልምና ።

ትውልደ ጻድቃን ይትባረኩ ።

የልዑል ራስመንገሻና የልዑል ራስ መኰንን ወዳጅነት ስለታሰበኝ ከሙሉ በከፍሉ ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች እጽፋለሁ ። በዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ ልዑል ራስ መኰንን የኢትዮጵያን ሰሜን ለመጐብኘት ከብዙ ሠራዊት ጋራ ወደ ትግሬ በሔዱ ጊዜ ልዑል ራስ መንገሻ ትግሬን በመላ ይገዙ ነበረና ሕዝቡና ሠራዊቱ ባልዑል ራስ መኰንን አመጣጥና በልዑል ራስ መንገሻ መቈየት ተጨንቆ ተጠበ ጸጥታ እንዳያጣ ያለ ልክ ፈርቶ ነበር ። ምንም አንዳንድ ሰዎች የማያስፈልገውን የከፋትና የመለያየት መገናኘት ቢሞክሩ የእግዚአብሔር ጥበቡ ረቂቅ ነውና ከዝምድናና ከወዳጅነት ለማራራቅ ከሚያሳስቧቸው ርቀው ያለጠብ በፍቅር ያለጥመም በቅንነት ሁለቱ ተገናኝተው የወዳጅነት ዝምድና በተባረኩ ልጆቻቸው መታሰቢያን ትተው ለማለፍ በቁ ። ይኸውም ከዚህስ የበለጠ መበረክና መዘማመድ ምን ይገኛል ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ለኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰንና ለልዕልት ወለተ እስራኤል የሰሎሞንንና የንግሥተሳባን በረከት ያሳድርባቸው ብዬ ምኞቴን እገልጻለሁ ።

ባላምባራስ በርሄ ዘደብረ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ ።

ዲስኩር ።

የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል መምህር ገብረ ጊዮርጊስ ላደረጉት ለካህናቱ ግብዣ በሚያዝያ ፳፰ ቀን

ክቡር ጌታችን መምህር ሆይ ።

እኛን ደስ ለማሰኘት ለታላቁ ክብር ለሆነው ግብዣዎ ተከታይ ምስጋናዬን አቀርብልዎታለሁ ክቡር ሆይ እንዲሁ ይህ ታላቁ የዛሬ ክብርዎና ግብዣዎ ለአባቶቼ ደስ እንደሚአሰኛቸው የታወቀ ነው ክቡር ሆይ እኔም ምንም በሰውነቴ የልጅነት ባሕርይ ቢኖርብኝና ከነገሩ ብጓድፍ ከታላቁ ንጉሠ ነገሥት ከአፄ ምኒልክ ጀምረው አንድ ተብለው የተቀመጡት አባቶቼ ባጠፋሁት ነገር እኔን ለመገሠፅና ለመቈጣት የተዘጋጁ ናቸው ። ክቡር ሆይ ይልቁንም የጌታችን ግብዣ በዚሁ ብቻ እንዳይቀርብን በምሉ በአባቶቼ ስም ሁኜ ምስጋናዎን አቀርባለሁ ። ክቡር ሆይ ነገር ግን ሥልጣኔና ትምህርት ከትውልድ እስከ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ ይኖራል ጌታም ተማሪዎቹንና መምህር ሁነው የሚአስተምሩትን መምሮችን ከፍ ወደ አለው የዕድል ተራራ ድረስ ያሳድጋል መምህር ሆይ ለዚሁ ዛሬ ላደረጉልን ለታላቁ ምሳ እርስዎን ሲሉ ለመጡት እንግዶችዎ ታላቅ በማይረሳ ምስጋናና ክብር የሚገባው ነው መምህር ሆይ እንዲሁም አምላክ በኢትዮጵያ ላይ እጁን እንደ ዘረጋበት ለእርስዎም ለጌታችን ትልቁን ሕይወትና ረጅም ዕድሜ ይስጥልን መምህር ሆይ ይኸውም የሚአስደንቀው ሐሳብዎና ግብዣዎ እኔን የመሳሰሉ ወንድሞቼምንም እየተነሡ ባይናገሩ ደስታው በሰውነታቸው ጥልቅ እንደሆነ ማንም አይስተውም አሁንም ጌታችንን ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ለዘለዓለም ያኑርልን ።

ይህ የዛሬ ግብዣዎ ስሙ እንደሐውልት ተተክሎ ለመቸም ተጠሪ መሆን የተገባው ነው እኛም ታዛዥ የሆንን ልጆችዎ ጌታችንን በቅን ለማገልገልና ደስ ለማሰኘት የተዘጋጀንነን እንዲሁም አባታችን ምሉ እምርቃትዎን እንዲሰጡን እንለምንዎታለን ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሺሕ ዓመት ይንገሡ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ተብሎ ተነበበና ከተጨበጨበ በኋላ ጠጁ በማንቈርቈሪያና በብረት ገንቦ ለካህናቱና ከዚያውም ለነበሩት ሁሉ ሲቀዳ የነሐሴን ጕርፍ ይመስል ነበረ እንዲሁም ሲበላ ሲጠጣ ተውሎ በሰላም መርቀን ወጣን ።

ያራዳ ማዘሮ ቤት ሠራተኛ ምናሴ ካ ።

በወለጋ አውራጃ ስለ የንግድ መንገድ መከልከል ።

ወለጋ አውራጃ በክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ግዛት ቡና ጭኖ ወይም ተሸክሞ የሚነግድ ነጋዴ የመንግሥት ጕምሩክ በቆመበት ሰዮ ድረስ አምጥቶ በጕምሩኩ ጕርድ አስቀረጠ እንዲነግድ እንጂ በረብ ወይም በሌላ መንገድ ወስዶ እንዳይሸጥ ስለ ተከለከለ ለጊዜው ደኅና ምክር መሆኑ ታይቶን ነበር ። አሁን ግን በ፲፱፻፳፬ ዓ ም ከጥቂት ቀን በፊት ከጕሬና ከሰዮ አሜሪካን ሚስዮኖች ሦስት ልጃገረዶች በሺሆጀሌ አልሃሰን አገር አድርገው ወደ ከርቱም ሲወርዱ እኔም አገር ለማየት አብሬ ሔጄ ነበርና ስንሔድም ስንመለስም ነጋዴዎች ብዙ ጭነት ቡና ሲያወርዱ አይቼ ለቈረቈር አንድ ቀን ኩርሙክ

ላይ አንዱን ነጋዴ ቡና ..በዚህ በኩል እንዳይወርድ ክልክል አይደለምን እደምን አመጣችሁት ብዬ ብጠይቀው ስለ መንገዱም በጋልኛ የሚገጥም ትንሽ ተረት ጨምሮ ወዲያውም አከታትሎ ስላገራችን ጉዳት እያስተዛዘነ የሚከተለውን ቃል መለሰልኝ ። እየ ወንድሜ ሆይ ድኃና ጅብ መንገድ ያጣልን ግን መንገዳችን በዱርና በጨለማ ስለሆነ ለመንፈቅ ያሰብነው ሱሬ በንድ ወር ያልቅብናል እንጂ ሙሹለኪያ መንገድስ እናጣም ይልቅስ ስላገራችን ጉዳት እጅግ የሚአሳዝነውን ነገር ልንገርህ ማለት በሰዮ አውራጃ ያሉ ግሪኮች ከኛ ትርፍ ለማግኘት እንጂ ለመንግሥታችን ወይም ለሕዝባችን ጥቅም እንዳል ተቀመጡ የታወቀ ነውና ሙቼም መንገዱ ክልክል ነው እንደ ፈቃዳችን እንገዛለን እንጂ ወዴት ያደርሱታል ሲሉ የቡናው ዋጋ ከዚህ አይለፍ ያቡጂዲው ያሽበው ዋጋ ከዚህ አይነስ እያሉ በንዲት ሰዓት ወረቀት ተላልከው ከዳር እስከ ዳር አድመው ይቈዩና ነጋዴው ጭነቱን አምጥቶ ከንዱ ሱቅ ሲያራግፈው መዝና አይቶ ሙሉውን ቁንጣር ጉደሎ ትርፍ ያለበትን አንድ ቁንጣር ነው ዋጋውም ይህን ያህል ነው ይለዋል ። ሕዝባችንም ከተማረ ያልተማረ ይበዛልና ቍጥሩን ካለማወቁ የተንኣሚዛኑ ይህን ያህል ነው ብሎ መከራከር ስላልተቻለው አንዱ አብልጦ ይሰጠኝ መስሎት ወዳንዱ ሱቅ ይወስደዋል ። መቼም ነገሩ የተመከረ ነውና ከዳር እስከ ዳርም ቢያዞረው ቃላቸው አንድ ሁኖ ይገኛል ። ይልቁንም ቀድም ከወጣበት ቤት የተመለሰ እንደ ሆነ ከፊተኛው ቀንሶ ሊገዛው ይፈልጋል ይኸን ጊዜ ድኃው ነጋዴ ወደ ገምቤላ አውርዶ በመርከብ ወደ ውጪ አገር ወስዶ እንዳይሸጥ ዓቅም አጥቶ፥ በከብቱ ጭኖ ወደሌላ አገር እንዳይወስድ መንገድ አጥቶ በይኑ አልቅሶ በጁ አብሶ ሲቸግረው እነሱው በቈረጡለት ዋጋ ሊሸጥ የግድ ይሆንበታል ብሎ የኋዊኞቹንና የራሱን ችግር ስላዋየኝ እኔም ደግሞ ብርሃንና ሰላም የሁሉም ሐሳብ መግለጫ ነው የሚለውን ቃል ከጋዜጣ ስላነበብሁ በዚህ መካከል የታየኝን ሁለት ጉዳት በደካማው ሐሳቤ ጽፌ ለማስታወስ ፈቀድሁ ። ፩ኛ ድኃው ነጋዴ በተደለደለው በንጉሡ ጕሥና ቀን ለቀን ቀረጥ እየከፈለ ወደ ወደደበት ሒዶ እንደ መነገድ ሴሊት ዱር ጥሶ ጨለማ ለብሶ እግሩን እንቅፋት ልብሱን ጋሬጣ እየፈጀው ወይም ጅኒያው ተቀዶ ቡናው ፈሶ ያከስረዋል ። ፪ኛም ድኃው ነጋዴ ተሸክሞ ወይም ጭኖ ያለመንገዱ ሲሔድ የመሸታ መጠጫ ፈላጊው ወምበዴ ኬላ ሰብረሃል ሲል ይዞት በዕጥፍ እየተቀበለው ወደ መንግሥቱ ገቢ ተጨምሮ ለተማሬ ቤት ወይም ላገር ጥቅም ለሚሆነው ሁነኛ ሥራ ይረዳ የነበረውን ገንዘብ ወደ መሸታ ቤት ያገባዋል ። ስለዚህም መንግሥት መክሮ ድኃው ቀረጥ ከፍሎ ጉርዱን ተቀብሎ ወደ ወደደበት ሒዶ እንዲነግድ ቢያደርግ ለድኃውም ለመንግሥቱም የሚሻል መስሎ ቢታየኝ ስለ የብርሃን መንገድ መሪ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ስለ ለምለምዋ አገራችን ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር ያለ ዕውቀት በሞኝነት፥ ያለ ፍርሃት በድፍረት አመለከታለሁ ፩ ዮሐ ፬ ፲፰ ።

ማሞ ሙርቃ ።

ጥንቁቅ አይሮፕላን ነጂ

፪ት አይሮፕላኖች ወደ ደሴ ሒደው ነበር ያንዱ አይሮፕላን ነጂ ሙሴ ሚሽካ ባብቼፍ ነበርና ከደሴ በሚነሡበት ጊዜ ከአይሮፕላኑ መኣሮዎች አንዱ ታናሹ መኣሮ መበላሸቱን መርምሮ ሳይነሣ መሰናከሉን አስታውቆ ቀረ ። ፪ኛው ቀን ያን የሚአስፈልገውን መኣሮ ሌላው አይሮፕላን ይዞለት ሒዶ በደኅና ወደ አዲስ አበባ ደረሰ። አይሮፕላን ነጂዎች ሁሉ እንዲህ ቢጠነቀቁ አደጋ አይበዛም ነበር ለጥንቁቁ ለሙሴ ሚሽካ ባብቼፍ ብርሃንና ሰላም ምስጋናውን ያቀርባል ።

የሚአስደንቅ ድፍረት

ክብርት ወይዘሮ ጽጌ ማርያም የክቡር ደጃዝማች እምሩ ባለቤት በግንቦት ፳ቀን በአይሮፕላን ተሳፍረው ከደሴ አዲስ አበባ ገቡ በድፍረታቸው ሕዝብ ሁሉ ተደነቀ ። እንድሽማግሌ ይህን ድንቅ ሰምተው እንዲህ የምታደንቋት የማን ልጅናት ብለው ጠየቁ የራስ ጉበና የልጅ ልጅ ናቸው ቢሏቸው ይህችማ የዘር ጀግንነት አለባት አይደለምን ይህስ አያስደንቅም ብለው የራስ ጉበናን የጀግንነታቸውን ታሪክ ሲአነቡት እንኳን የተኛና የሞተ ይቀሰቅስ ይመስል ነበረ ።

የጨካኝ ሞት

ከዋጀ ደሚት ጋሊ ተርዜ የግብዕ ሰው ከት ሰሬ ነበረ ። አንዳንድ ቀንም በዲቁና ማዕርግ በሊቀ ጳጳሱ ቤተክርስቲያን ያገለግል ነበረ ። የተበሳጨባት ምክንያት ሳይታወቅ በግንቦት ፯ ቀን በገዛ ሽጕጡ ራሱን ገደለ ።

ስለክቡር አለቃ ይግዛው ዕረፍት ።

አለቃ ይግዛው የደብረ ወርቅ አለቃ ነበሩ ከልዑል ራስ ኃይሉ ጋራ ተጣልተው ደብሩ ሁሉ አለቃቸውን ተከትለው መጥተው እጃንሆይ ላይ ቀርበው ነገራቸውን አሳይተው ጃንሆይም የነገራቸውን መብዛትና የበደላቸውን መበርታት ተመልክተው ነገራቸው በቶሎ እንዲፈጸም ዳኛ ተቀብለው ሳለ መቼም ነገር ያለቀኑ አይቈረጥምና ቢዘገይባቸው እዚሁ ጃንሚዳ እደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ዘንድ ሰፈራቸውን እዚያ አድርገው ደጅ ሲጠኑ፥ ወሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት እንደሚሉ ሞት አይቀርምና በታመሙ በሰባት ቀናቸው በሚያዝያ ፲፱ ቀን ዐርፈው በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ደጃዝማች መሸሻ ወልዴና ክብርት ባለቤታቸው ወይዘሮ ማናለብሽ ጋረደው በክብር አስቀበሯቸው የካህናቱን ኃዘንና ልቅሶ ላየው ሰው በጣም ያሳዝናል እናት አባታቸው የሞቱባቸው ይመስላሉ እንጂ ገዣአቸውና አለቃቸው የሞቱባቸው አይመስሉም ነበር መቼም በዚህ ዓለም ምን ቢማሩ ምንደኛ ቢሆኑ ከሞት መቅረት የለምና እሳቸውም እንደደግነታቸውና እንደ ምሁርነታቸው ሞት የሚገባቸው አልነበረም ዕድሜአቸውም ፷ ዓመት ነው ይልቁንም የሚያሳዝነው ለነገር መጥተው ነገራቸው በቶሎ ሳይፈጸም ቀጠሮ የማይሰጠው ሞት ያዘ—

ቸው በመሔዱ ያሳዝናል ካህናቱንም ሆድ እንዳይብሳቸው ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ከቡራን አባቶቼ ሆይ አይዟችሁ አትዘኑ ሞት መቸም ለማንም አይቀር ዋንጫ ተራ ነው በተራ ለሁሉም ይደርሳል እሳቸውስ አባታችን እስከሁን በነ ሥራ ሠርተው ያልተማረ አስተምረው አብያተ ክርስቲያናትን በየደረሱበት አገልግለው ብዙኅ ልጅ ከለማወቅ ወደማወቅ መልሰው ነውና ያረፉት አትዘኑ ብለው የካህናቱን ልብ የሚያፅናና ቃል ተናገሩአቸው። ካህናቱም እንዲህ የሚል ቃል ተናገሩ። ጌታችን ሆይ እኛ ብናዝንና ብንበሳጭ አባታችንን አናገኛቸውም ብቻ ኀዘናችን ሞት ለማን ይቀራል ነገር ግን ለነገር መጥተን መከበራችንና መታፈራችን በሳቸው ነበር እንዲያው በጉሉ አውራ የሌለው ንብ መስለን ተንከራተን በመቅረታችን እድላችን ይህ ሁኖ በመቅረቱ ለዘለዓለም ኀዘኑና ፀፀቱ ከልቡናችን ለመቸም አይወጣልን። ነገር ግን እንግዲህ ሐሳቡና መከራው የርስዎ ነው ፊትም ያባትዎ የራስ ወልዴ ነው ግብዝናው አሁንም ከርስዎ እጅ ነውና ለመንግሥትዎና ለባትዎ ደብር ሲሉ ይርዱን እንጂ የውህ ላይ ኩበት ሁነን ቀርተን የለም ብለው ተላቀሱ ደጃዝማች መሸሻ ወልዴም እሺ ምን ከፋኝ አባቶቼ በሚቻለኝ አቅሜ እረዳችኋለሁ ብለው ኀዘናቸውን የሚያስታግሥ ቃል ተናገሯቸው ቀባሪ በፈጣሪ የተባለው ቃል በደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ተፈጸመ ኀዘናቸውን ላየው ሰው በጣም ያሳዝናል ከነበረ ቤታቸው። በዚህ ጊዜ መዘመድና መዋለድ ቋንቋ ሁኖአል በድሮው ጊዜ ግን ይጠቅም ነበር ዛሬ ግን መታደል ነው ደጉ ቀባሪ አታሳጣኝ ብሎ ልመና ማቅረብ የተገባ ነው ።

የትንሣኤለትም ካህናቱን ጠርተው ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ግብር በሚገባ አርገው አበሏቸው ካህናቱም ለንጉሣችን ዕድሜ ለጌታችንም ሀብት ለዘለዓለም አይለይብን እያልን ልመናችንን አናቋርጥም ብለው በየተራ እየተነሡ እየመረቁ በየበዓታቸው ተመለሱ ። በቀለ አደራ።

ስለጥሩነሽ ወልደ ኪሮስ ዕረፍት

ጥሩነሽ ወልደ ኪሮስ በጠባይዋ የተመሰገነች ለናት ላባቷ የተመቸች በቅን የምታገለግል እጅግ አወጣጡ መልክም ነበረች የጊዜው ባለቤት ይበቃል ከለ ከባለቤቱ ለመከራከር አይቻልምና በተወለደች በዓሥራ ሰስት ዓመት ከሰስት ወሯ ግንቦት ፲፮ ቀን ከቀኑ አምስት ሰዓት ሙታ የገነተ ማርያም ካህናት ጉዞ ፍታት ሲፈቱ ውሎው በ፲፩ ሰዓት ገነተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቀበረች አባቷም አቶ ወልደ ኪሮስ ሀብተ ገብሬኤል እንዲህ ብሎ አለቀሰላት ልጄ ምን አስኬደሽ በአምስት ሰዓት ምንም ብትቸኩይ ገነት ለመግባት ። ስትጨነቅ ክርማ የኔ ቤት ጠፏት ። ሰፊ ሁኖ ታያት አዳራሹ ሞት ። አበበና ዘውዴ ጥሩነሽ ማለዱ ። ምንም እሩቅ ቢሆን የገነት መንገዱ ። የዛሬ ልጆችስ ይሉኝም አይሉ። ካባት ከናት በፊት ልጆች ያቀድማሉ ። ነገር አዋቂ ነው ብልህ ነው ይኸ ሞት ። አንድ ዓመት ሰልሎ ነጥቆ ወሰዳት ። ልጆች ያሉሁ ጉበዝ ተጠንቀቁኝ ጠብቅ ። ሞት ያለሰማንያ ጀምሯል መናጠቅ ። ዘመድ ሳይጠራ ሳንሰማው ውሉን ። ሰርገኛው ወሰዳት መጥቶ ብቻውን።

አላንቃና ወላነጣ መሥሪያ ቤት አጠገብ ባለው ሱቅ ከ፲፱፻፳፬ ዓ ከሰኔ ፩ ቀን ጀምሮ ከቀድሞው ዋጋ ተሻሽሎ የሚሸጥ ዕቃ ማስታወቂያ ።

የዕቃው ቍጥር	የዕቃው ስምና ዓይነቱ	ያንዱ የጥንት ዋጋ		ያንዱ የዛሬ ዋጋ	
		ብር	ቤ	ብር	ቤ
፪፻፫፡	መጀመሪያ ሱፍ ከበርት ደኅና	፲፫		፲	
፫፳፡	ሁለተኛ።			፮	
፮፻፬፡	ጥቁር መልክ ሱፍ ከበርት ደኅና	፳		፮	
፹፫፡	ሁለተኛ።	፭		፪	፶
፫፡	ባለወርቅ ጥብጣብ ገበርዲን ሱፍ ኰት ደኅና።	፴፫		፲፫	
፫፡	ገበርዲን ሱፍ ሱሪ ደኅና።	፲		፮	
፮፡	መጀመሪያ ሱፍ ሰማያዊ ኰት ።	፲		፪	፶
፻፫፳፡	መጀመሪያ ሱፍ አጭር ኰት ደኅና	፮		፫	
፺፫፡	ሁለተኛ ።			፬	፶
፭፻፫፡	ጥቁር መልክ ሱፍ ኰት ደኅና	፮		፭	
፳፮፡	ሁለተኛ			፬	
፶፡	መጀመሪያ ሱፍ ባለቆዳ ሱሪ ደኅና	፯		፫	
፶፭፡	ሁለተኛ ።			፬	
፺፫፡	ባለቁልፍ ነጭ የተልባ እግር ባለሌ ሱሪ ደኅና ።	፰		፫	፶
፳፪፡	ሁለተኛ ሱፍ ኰት ።	፭	፶	፪	፶
፶፳፡	ሁለተኛ ።			፬	
፶፡	ሱፍ ሱሪ።	፭		፬	፶
፶፪፡	ሁለተኛ ።				፸፭
፵፳፡	ሁለተኛ ሰማያዊ ኰት ።	፭	፶	፬	
፮፻፫፡	ሸራ ዓይነት ጥንድ ገምባሌ ደኅና	፪		፬	
፲፬፡	ሁለተኛ ።				፳
፯፳፪፡	የጠቅደር ባርኔጣ	፬			፶
፲፡	ሁለተኛ።	፬			፭
፳፻፡	መንጠልያ አጭር ካባ።	፬			፭
፳፻፲፱፡	ጥቁር መልክ ሱፍ ሱሪ ደኅና	፫		፬	፶
፴፱፡	ሁለተኛ ።	፬			፶
፩፻፳፪፡	ጥንድ ሱፍ ገምባሌ ።	፬			፳
፻፮፡	የራስ መለዮ ሱፍ ።		፶		፱
፲፪፡	ነጭ መርዱፋ ሱሪ ።		፶		፭
፳፡	ሱፍ ብርድ ልብስ ደኅና ።			፲፳	
፲፫፡	ሁለተኛ ።			፲፪	፶
፮፡	ዝቅተኛ ሱፍ ብርድ ልብስ ደኅና			፳	
፲፭፡	ሁለተኛ ።			፯	
፭፹፫፻፳፫፡	ጥቁር መልክ ሱፍ ብርድ ልብስ ።	፴		፲፱	
፶፱፡	ላንቃ ቅድ ሌጣ እንበሳ ።	፵		፲፯	
፫፡	ሐር የጠረጼዛ ልብስ ደኅና ።	፶፭	፶	፲፰	
፳፫፡	ሁለተኛ ።			፲	

ባለ አቶ ወልደ ሥላሴ ተክለ ሃይማኖት ሞት

አቶ ወልደ ሥላሴ በጣም የተማሩ ደግ ሰው ነበሩ ። አባታቸውም አለቃ ተክለ ሃይማኖት ናቸው አገራቸው ቡልጋ፤ መኖሪያ ቤታቸው ሉሜ ውሥጥ ቱሉ ርኤ መድኃኔ ዓለም (ጣሬ) ስለሆነ ያለቃ ተክለ ሃይማኖትንም አስተማሪነት አገሩ ሁሉ ስላወቀው ባስተማሪነታቸውም ስለተመሰገኑ በውሬጃው ያሉትን ሕፃናትና ከሩቅም አገር የሚመጡላቸውን ልጆች እያስተማሩ ግማሾቹም በቅስና እኩሌቶቹም በጽሕፈት ሥራ እየያዙ መንግሥትን ያገለግላሉ ከተማሪዎቻቸውም አንደኛው እኔ ነኝ ።

አቶ ወልደ ሥላሴ ግን ቀድሞ የደጃዝማች ኃይለ ማርያም ለማ የጽሕፈት ሹም ነበሩ ። ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ሚኤሶ፥ ሰገሌ፡ መቅደላ ታዘው የዘመቱ ጊዜ አብረው እየዘመቱ ጌታቸውንና መንግሥትን አገልግለው ነበር በኋላ ከጌታቸው ስለ ተጣሉ ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ሸዋ ጊሚራን ተሹመው ሲሔዱ ስለጠብ ብለው አንድ ላይ አልሔድም በማለት ቀርተው ጃንሆይ ካውሮፓ የተመለሱ ጊዜ አመልክተው በልደረብነታቸው ለክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ሁኖ ሥራ ግን በማግረጥ አላያዙም ነበርና በደጅ ጥናት ጥቂት ቀለብ ተፈቅዶላቸው አገልግሎት የሚያስመሰግን ሥራ ይገኝ መንግሥቴን አገልግዬ አለቆቼን ደስ አሰኛለሁ እያሉ ዘወትር ሲመኙ ሐሳባቸው ሁሉ ሳይጠቀለልላቸው አሁን በመጋቢት ፲፯ ቀን ሙጋትና ሳል ሕመም አንድነት ተነሥቶባቸው በጠና ስለታመሙ ብሞትም በአባቴ መቃብር እንድቀበር ወደ ቤቴ አውርዱኝ ብለው በመጋቢት ሐያ አራት ቀን በባቡር ተሳፍረው ሞጆ ጣቢያ ወርደው እቤታቸው ከደረሱ በኋላ ከሌሊቱ በሦስት ሰዓት ሙተው ከህናቱ በጕዞ ያማረ ፍታት እየፈቱ እያለቀሱላቸውም ያገሩም ሰው ሁሉ ይወዳቸው ነበርና ያለመጠን አልቅሶላቸው በ፳፰ቀን ባባታቸው መቃብር ቤት ሉሜ ውሥጥ (በጣሬ) ቱሉ ርኤ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ቀብር ተቀበሩ ።

ሞቱም ተመሬት ተፈጥሮ ሞት የማይቀር ሁኖ ከምላክ ቦለታዘዘን ነው እንጂ በደግነታቸውና ስለጠባያቸውም መልካምነት ሰውም ሁሉ እንደሚወዳቸው ቢሆንማ እንደመላእክት አይሞቱም ነበር ። ሰው ከሆኑ የመሬት ተፈጥሮአችን የማናገኘውን በመመኘት መከራን አብበን ሞትን እንድናፈራ ስላደረገን ደግም ቢሆኑ ወይም ክፉ አካታቹ ሞት ነውና ይህንኑ የሚያሳዝን ያቶ ወልደ ሥላሴ ተክለ ሃይማኖትን ሞት በሩቅ አገር ያሉ ዘመድ ወዳጆቻቸው በብርሃንና ሰላም እሰዲሙት ብዬ ጻፍኩት እንጂ ስለጠባያቸው መልካምነትና ለሥራትም ደግ ሥራቸው ሁሉ የተስማማ ታሪክ ሁኖኛል ብዬ አይደለም።

ናቁ ይፍሩ ።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።

ማስታወቂያ ።

ስለ በሽታው ምክንያት ከዚህ ቀደም በከተማ ውሥጥ ባየመንገዱ የሚገኙትን ውሾች የማዘጋጃ ቤት ስለሚያጠፋቸው አሁንም ከግንቦት ፴ ቀን በኋላ እንደተለመደው ሁሉ ውሾችን ለማጥፋት አስበናልና ከግንቦት ፴ ቀን ጀምሮ የከተማው ሕዝብ ደኅና ውሻውን እስከ ፲፫ ቀን ድረስ ከቤቱ ውሥጥ አሥሮ እንዲያቈይ እናስታውቃለን። ይህም ማስታወቂያ ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ እንደተጻፈው ሁሉ ውሻውን ሳያሥር ቀርቶ ውሻው አንድ አደጋ ቢያገኘው የማዘጋጃ ቤት አለመጠየቁን አስቀድመን እናስጠነቅቃለን ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ።

የአዲስ አበባ ከንቲባ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም ልርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማከዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የከትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የከትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትደዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንጻ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን እንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው። ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል ሕስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል። ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ.

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም
ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አበካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም [illegible] ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ያኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሚልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ፣በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭው በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S&E&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልክል የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኮኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፳፬
8^me ANNE. № 24

ሐሙስ ሰኔ ፪ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 9-JUIN 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ማስረጃ ።

የምድር ባቡር ኩባንያ ሠራተኞች አድማ፤ ሰኞ በ፳፪ ግንቦት ፲፱፻፳፬ ዓ ም ጀምሮ እስከ ሐሙስ ግንቦት ፳፭ ቀን አለቀ ።

በአንዳንድ የውጭ አገር ሰዎችና በድሬ ደዋ ማዘጋጃ ቤት አንዳንድ ዘበኞች መካከል እሑድ ጧት ግንቦት ፳፩ቀን የተደረገውን ለአድማው ምክንያት የሆነውን አምባጓሮ፤ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም የሐረር አውራጃ እንደራሴ ከቶ ሎሬንዞ ትእዛዝ የፍርድ ሚኒስቴር አማካሪ ጋራ ሁነው ምርመራ አደረጉ ።

ክቡር የፈረንሣዊ ሚኒስትር ሙሴ ደረፌ ወደድሬ ደዋ ወርደው ነበረና የምርመራውን አካሔድ በፍጥነትና አለ አድልዎ መደረጉን ተመልክተዋል ።

የመጀመሪያው አድሚኒስትራቲፍ ምርመራ አልቋል ።

በዚህ በአምባጓሮው የተነሣ የተመቱት ሰዎች በትር ባንዳንድ ሰፍራ እንደተወረው በጣም የሚያሰጋ ብርቱ በትር አይደለም ።

ይህነን ነገር በመላው መርምሮ እንደሕጉ አድርጎ ለመፍረድ በድሬ ደዋ በልዩ ከቆመው የፍርድ ቤት ልዩ ዳኛ በቅርቡ ይታዘዛል ።

COMMUNIQUE

La grève du personnel de la Compagnie du Chemin de Fer, commencée le lundi 30 mai 1932 à pris fin le jeudi 2 juin 1932.

Les incidents survenus le dimanche matin 29 mai entre quelques ressortissants étrangers et quelques policiers de la Municipalité de Diré-Daoua qui ont constitué le prétexte de cette grève, ont fait l'objet d'une enquête conduite par S. E. le Dejazmatce Guébré Mariam, Gouverneur de Harrar avec l'assistance d'Ato Lorenzo Taezaz, Conseiller au Ministère de la Justice.

S. E. le Ministre de France Mr. De Reffye qui s'était rendu à Dire- Daoua, a suivi la marche de l'enquête, qui s'est déroulée de façon impartiale et rapide.

L'enquête administrative préliminaire est close.

L'état des personnes contusionnées aux cours de ces incidents est satisfaisant, et n'a, à aucun moment, revêtu un caractère de gravité telle que le bruit en a couru dans certains milieux.

Un Juge ad hoc du Tribunal Spécial siégeant à Dire- Daoua sera incessamment chargé de statuer conformément à la loi sur l'ensemble de l'affaire.

አዋጅ ።

በነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት በተደረገው አዋጅ በ፪ኛው ክፍል የኢትዮጵያ ባንክ መተዳደሪ ደምብ ለኢትዮጵያ መንግሥት ቀርቦ ይፈቀዳል፤የኢትዮጵያ መንግሥትም መፍቀዱን የመንግሥት ማስታወቂያ በሚታተምበት ጋዜታ ውሥጥ አሳትሞ ያስታውቃል የሚለውን ተመልክተን ፤ የኢትዮጵያ ባንክ አማካሪዎች ያዘጋጁትን የባንክ መተዳደሪ ደምብ ለባንኩ ባለአክሲዮኖች ዋና ጉባኤ አቀርበው ፤ የባንኩም ባለአክሲዮኖች ዋና ጉባኤ ይሁን ብሎ መቀበሉን ተመልክተን ይኸውም የባንክ መተዳደሪ ደምብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ መፍቀዳቸውን ተመልክተን እንደሚከተለው እናውጃለን።

፩ኛ ክፍል

በሮፓ ቍጥር በየካቲት ፳፱ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓመት የተሰበሰበው የባለ አክሲዮኖች ዋና ጉባኤ ተቀብሎት የነበረው የኢትዮጵያ ባንክ መተዳደሪ ደምብ ተፈቅዷል ።

፪ኛ ክፍል

ይህ አዋጅ የመንግሥት ማስታወቂያ በሚታተምበት ጋዜታ ውሥጥ ታትሞ ከወጣ በኋላ በፍጹም የሚፀና ይሆናል

ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ። የገንዘብ ሚኒስትር ።

ስላቶ ሥራ ፈትና አቶ ሥራ ወዳድ።

ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ሥራዬ ለመግባት ከቤቴ ተነሥቼ ወደ መንገድ ስገባ ይህ አቶ ሥራ ወዳድ የሚባለው የችግር ጠላት የሆነ ይህነን አቶ ሥራ ፈትን እማላይበት ወዴት ልሒድ አሁን እኮ ይህንን በሩን መውጫ መግቢያውን እንደሁ ቍጥቋጦው ዛፉ ቅጠላ ቅጠሉ ሲያጠልቀው ዕንጨቱን ቈርጦ ቍጥቋጠውን መንጥሮ በጊዜያቱ የሚሆነውን እህል ቢዘራው እንኳን ለሱ ቤተሰብና ለጎረቤቱ ሁሉ ይበቃ ነበረ ዳግም ይህችን አንዲት ላሙን እንደዚህ አድርጎ ለጥጃዋ እንዳይተርፍ አድርጎ ወተቷን ከማለብና ከማከሳት ወተቷን ለጥጃዋም አከፍሎ ዝም ብሎ ሣሩን ካለበት ፈልጎ ቢያበላት ውሀውን በጊዜያቱ ቢያጠጣት ይህች አንዲት ላሙ እሚአርስበት በሬ እሚጠጣውም ወተት ታተርፍለት ነበረች ምንይሆናል መከፉ አቶ ችግር የዓይኔ ጠላት ነው እኔ አሁን ይህ አቶ ችግር እንዲህ የጠላኝ የገዛ ሥራዬን በጊዜያቱ በሠራሁና ከብቶቼን እየጠበቅሁ ምግባቸውንም ሳላስርብ ሣሩንም ካለበት እያጨድሁ እያበላሁ ውኃውንም በጊዜያቱ እያጠጣሁ ከብቶቼ ስለረቡና እህሌንም በጊዜያቱ በጕተራዬ ስለከተትሁ ይኸው ችግር የሚባል አጥሬ ስር ሳይደርስ እንደጠላኝ ይኖራል ይልቁንም የአቶ ሡራትና አቶ ውርደት መጨረሻቸው ይኸው አቶ ችግር የሚባለው ነው ዳግም ለነዚህ ሁሉ ዋና ዘመዳቸው አቶ ስንፍና ነው እነዚህ ሁሉ እንኳን እቤቴ ሊገቡና በመንገድም ቢአገኙኝ እንዴት ዋልህ አይሉኝም ነበር።አሁንማ መጥፎአቸው መጥቷል ይልቁንም በየሀገር ቤቱ ነው እንጂ ያሉት በከተማ በከተማውማ ዕድሜ ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህ ችግር የሚባል እንዳይደርስ ትጋት የሚባል መርማሪ ሹመውበታል አሁን ይኸው በየዳር አገሩ እንኳን ይኸው አቶ ትጋት አቶ እውቀትን ወንድሙን ጨምሮ አቶ ሡራትንና እናቶ ስንፍናንና ችግርን ለማጥፋት መጥተው ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ በቆሙላቸው የተማሪ ቤት በሚባለው ዳኛ እየከሰሱ የተፈታውን ድንቍርና በሚባለው ጭለማ ወህኔ እያገቡ ማሰር ጀምረዋል።እኔማ ምንቸገረኝ ጥንትም ቢሆን አይወዱኝ ጠላቶቼ ናቸው ይልቅ የኔዘመዶች በመኾማቸው ለደስታዬ ወሰን አይገኝለትም እያለ ይህ አቶ ሥራ ወዳድ የችግር ጠላት ሲጫወት ባለመስልቸት ዝም ብዬ ሳዳምጥ ቈይቸ ለካ ሹም ተሹሞበታል እኔን እዚህ እመንገድ ላይ ቁሜ ቢያገኙኝ ምን ልመልስ ነው ብዬ በፍጥነት ወደሥራዬ ገባሁ የሰማሁትን ለብርሃንና ሰላም ላመለክት ስለጻፍሁት በጕደለ ሞልታችሁ የበዛውን ቀንሳችሁ እንድታነቡልኝ እያሳሰብሁ አመለክታችኋለሁ።የብርሃንና ሰላም ደጅ ጠኚ ተድላ ታምራት ጐሬ አሊ ግንት ከተማ ።

የክቡር ደጃዝማች አምባቸው ትጋት።

በዋድላ ወረዳ ማዲጋዛ በሚባለው አገር አለቃ አስፋው የሚባል ሰው ከበጌምድር መጥቶ ሚስት አግብቶ ወልዶ ይኖር ነበር ። ጠባቸው ሳይታወቅ አማቶቹ ለማስገደል አሰቡት ። አስበውም አልቀሩ ጋርደው መኰንንና በጋለ መኰንን የሚባሉ በጫካ የሚኖሩ ወምበዶች ነበሩና ወንዱ አማቱ ጣርዳት ከሚባለው አገር ግደሉልኝ ብሎ ይዞአቸው ተሸገረ። ውኾች ነበሩትና እንዳይጮሁ ሴቲቱ አማቱ አሥራ ቈይታ ወምበዶቹን በከበሬታ ተቀብላ ከንፉ ልጅዋ ጋር ይዛ ገብታ እረዱልኝ አለቻቸው ወምበዶቹም በገንዘብ ተገዝተው የሔዱ ናቸውና አንዱ በሽመል አንዱ በጕራዴ መቱት አልሞትላቸው ቢል ሴት ጨካኝ ናትና አማቱ ቢላዋ ስላ አንገቱን አርዳ ጨረሰችው እሷም ንዟን ይዛ ጠፋች ወምበዶቹም የተገዙበትን አድርገው ሔዱ ወንዱ አማቱ ግን ደኅና ሰው ለመምሰል ወምበዴዎችን ሸኝቶ ልጄን ወምበዴ ገደለው ብሎ እየጮኸ ወደ ዳኛ ሔደ ዳኛውም ሬሳውን ለማስነሣት በሔደ ጊዜ የዚህ የሰውዬ ሚስት ንዟን ይዛ መጥፋቷን ሰማ ሚስትህ ንዟን ይዛ ከጠፋች መንግሥት ይመረምርሃል ብሎ አለቃ አስፋው ከሌላ የወለዳት ልጅ ነበረችውና ወደ ክቡር ደጃዝማች አምባቸው ሰደዳት አዝነው መንግሥታቸውን በመውደድ ይህችን ሕፃን ጥቃት ማታ እያየሁ ወምበዴዎቹን በጥንካሬ አስፈልጋቸዋለሁ ብለው ከእልፍኛቸው አስገብተው አስቀምጠው ወምበዴዎችን ቢያስፈልጓቸው ወደ ሰቆጣ ሔዱ አሏቸው ጌታዬም የሰው ደም የማያስቀረው እምላክ የዚህን ሰው ደም አያስቀርበት እያሉ ይህ ሰው በግፍ ስለ መሞቱ በጣም አዝነውበት ነበርና የገዳይዎቹ ጓደኛ የሚሆን አንድ ሰው መጥቶ

ይህንንነገር ካሰቡበትማ እኔን የሚሸልሙኝእንደሆነ እነዚያን ገዳዮች/ከሔዱበት አምጥቼ አላሲዝምትምን አላቸው እነሱንማ ከስያዝኸኝ ለመንግሥቱም እርዳታ ነው እኔም ያልኸኝን አደርግልሀለሁ አሉት እሱም እሽ ብሎ እጅ ነስቶ ተመልሶ ሔዶ የጓደኞቹን ባሕሪ ያውቃልና ያለቃ ኣሳፋው ሞት ተረስቶአልና ከዚያው ከለመድነው አገራችን ሔደን እንቀመጥ ብሎ ክክቡር ደጃዝማች አምባቸው አገር ይዟቸው መጣ ከመጡም በኋላ አምጥቻቸዋለሁና ያስይዟቸው ብሎ ቢነግራቸው እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ጌታ ለሠራዊቱ ተጨናቂ ነውና በጫከ ያሉ ብዙ ሰው ብሰድ ነፍስ የገደለ ሰው አውሬ ነውና አልያዝም በማለት ከወደዚህ ንጹሕ ደም የፈሰሰ እንደሆነ ሁለተኛ እጎዳለሁ ብለው በብርሃን ልቡናቸው አስበው ከግራዝማች አበጋዝ ቤት ብዙ ንዝ አለና እንስረቅ ብለህ ይዘሃቸው ግባ አሉት እሱም እንደአዘዙት ይዟአቸው መጥቶ አስቀድሞ በሩን ከፍቶ ይዞአቸው ገባ። ግራዝማች አበጋዝም የታመነ አሽከራቸው ነውና ተጠንቅቆ ቆይቶ ከሌሊቱ በሰባት ሰዓት አንድ ጥይት ሳይጮህ አንድ አሽከር ሳይቈስል በሩን ዘግቶ ይዞ የፊጥኝ በተላድ አስሮ አሳድሮ ከጥዋቱ በሁለት ሰዓት ክቡር ደጃዝማች አምባቸው ከተቀመጡበት ችሎት ይዞአቸው ቀርቦ ቢመረምሩ መጀመሪያ እንደተጻፈው ቃል አወን የሚስቱ እናትና አባት ገደሉልን ብለው ወስደውን ገድለነዋል ብለው ስለአመኑ ፈትም በአገዳደላቸው በኋላም ክቡር ደጃዝማች አምባቸው ለመንግሥት አስበው ለደሃቸው ተጨንቀው አንድ አሽከር ሳይሞት አንድ ጥይት ሳይጮህ በመያዛቸው ነው ሁሉ እጅግ የተደነቀ። ሁለተኛ ወንዱ አማቱ በጥርጣሬ ተይዞ ቆይቶ ነበረና እነዚህ ገዳዮች ተይዘው ከተመረመሩ በኋላ ክቡር ደጃዝማች አምባቸው ከታሠረበት አስመጥተው አለቃ አሰፋውን ያስገደልኸው አንተ ከነሚስትህ መክረህ አይደለምን ቢሉት አዎን ከሚስቴ ጋራ መክሬ እኔ ተሸግሬ እነዚህን ገዳዮች ከማርዳት አምጥቼ ሚስቴ ውሾቹን አስራ ቈየች።ከዚህ በኋላ እኔ ወደኋላ ቀረሁ ሚስቴ ከንዱ ልጇ ጋራ ወምበዶችን ይዛ ገብታ አስገደለችው እየተጠራሞተ አልሞት ቢል እሷ በቢላዋ ጨርሰው ጓዟን ይዛ ሔደች እኔ ግን ገዳይዎችም አይያዙ ብዬ እየጮሁ የደም ሽማ ይገኝ ወደ ዳኛ ስለሔድሁ በጥርጣሬ ተይዤ ቆይቼ ነበር ። አሁን ግን ገዳዮቹ ከተያዙ እግዚአብሔር ፈረደብኝ ብሎ የእግዚአብሔርን ፍርድ ተረዳው ። የገዳዮቹና ያስገዳዩ ቃል ስለገጠመ በፅኑ ታሥረው ቈይተዋል ።

የክቡር ደጃዝማች አምባቸውን ብርታት አይቶ ሌባና ወምበዴ ከግዛታቸው ጠፍቷል ሌባንና ወምበዴን በማጥፋታቸው ስለ ንጹሑ ደምም በመበቀላቸው ክቡር ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠን ብርሃንና ሰላም እጅግ ያመሰግናቸዋል ።

የጥያቄ መልስ

አቶ ትስብእተ ወልድ አግዴ በብርሃንና ሰላም ፲፬ ቍጥር ከድጎው ሰውዬ የተወለደችውን ብላቴና ከሶስት ብልሖች ተማሮች ማንኛው እንዲያገባት ፍረዱ የሚል ጥያቄ አቅርበዋል ። ብዙ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎችም እንደ ታያቸው መጠን መልስ ሰጥተዋል። እኔም ከዚህ ቀጥዬ የታየኝን መልስ አቀርባለሁ ።

በመጀመርያ የብላቴናዋ አባት በተጠየቀ ጊዜ ልጄን የሚአገባ በእውቀት የበለጠ ነው ብሎአል።ስለዚህም ሶስቱ ጠያቂዎች በብላቴናዋ ውበት ጐምጅተዋልና ሩቅ መንገድ ሔደው ብዙ ስንቅ ፈጅተው ስንኳ ቢማሩ ከነዚሁ በእውቀት የበለጠ ታጣ። አቶ ትስብእተ ወልድም በዚህ ጥያቄአቸው ውስጥ ሶስቱም ልጆች እውቀታቸው ትክክል ነው ብለዋል ።

እውነት ነው የሶስቱ ተማሮች እንደ አንድ ሰው ሥራ ነው ማለት አንድ ሰው በዓይኑ ያያል ፤ በእግሩ ይሔዳል በጉልበቱ ይሠራል። እንደዚሁም ሶስቱ ተማሮች አዩታው ቢአይ፥ ፈጣኑ ቢደርስ፥ ሙት አንሺው ቢአድ፣ ሥራው አንድ ነው እውቀቱም እኩል ነው፥ መበላለጥም የለውም ።

አሁንም እንደ አቶ ትስብእተ ወልድ አጠያየቅ ጥንት አባትዋ በእውቀት የበለጠ ልጄን ያገባል ከአለ እነዚህ ሶስት ተማሮች በእውቀት አልተበላለጡምና ከነእርሱ አንድ ስንኳ ሊአገባት አይችልም። ስለዚህም ይህች ብላቴና ቍንጅናዋን ይዛ ከአባትዋ ቤት ትኑር ስል የታየኝን ፍርድ ገለጽሁ ።

አ ተ መ ።

ፍርድና ፍትፍት በየፊት።

እንደታየ ይፈርዷል፥በተሳለ ያርዷል እንደተባለው ሁሉ ወንድማችን አቶ ትስብእተ ወልድ አግዴ ያቀረቡልንን ፍርድ እንደታየን መስጠት እንጂ መልስ ፍርድ የጠየቀ ሰው ረቂቅ ምሥጢር ይኖረው ይሆን ብሎ መጠራጠር የማያስፈልግ ስለመሰለኝ ተመልካች ይውሰድ ብያለሁ ማለት መመልከት ባልኖረ እንደኛው ፈጥኖ ማድረስ ሁለተኛውም ማዳን ባልቻሉም ነበር እንዲያውም እውቀታቸው የተለየ ይሆናል ላዋቂዎቹም የመጀመሪ መሠረታቸው መመልከት እንደሆነ ማንም ሰው አይስተውም ስለዚህ ዕድለኛይቱ እጮኛ መልካሚቱ ሙሽራ የምትገባው ለተመልካች ነው ስል ፈርጃለሁ።ዳሩ ግን የራሱን ሐሳብ እንደመጻፍ የኔን ፍርድ መቃወም የሚፈልግ ሰው ቢኖር ለጊዜው ሥራ ስለ በዛብኝ ከብዙ በጥቂቱ ነውና የጻፍሁት በፍርዴ ላይ ተመልካች ይውሰድ ያልሁበት ምክንያት ምን እንደሆነ ብጠየቅ ምክንያቱን ለማስረዳት ዝግጁ መሆኔን አስቀድሜ አስታውቃለሁ ።

ፍ ጸ ደምሴ ወልደየስ ።

ፍሬው የሚያጠግብ የጠራ ሐሳብ

ብርሃንና ሰላም ብዙ ጊዜ ለሰው ደስ የሚያሰኝ ስለ ምናይበት እኔም ይህን ሰጥቸው ለብልሆቹ አንባቢዎች እንዲያቀርባቸው ይህን ጥያቄ አቀርባለሁ ። ማቅረቤም ለራሴ የሚገባውን ምላሽ ከብልሆቹ አግኝቼ በዚያ ሰውነቴን እንዳቆመው ነው ። ደግሞም ይህ ሐሳቤ ለብዙዎች ደስ ሳይል አይቀርምና ለነዚያም ጥቅም ይሆናል ስል ነው ።

፩ኛ ጥያቄ፡ ትምህርት በራሱ ምንድርነው ?

፪ኛ፡ የትምህርት ዓይነታው ፍሬ የቱ ነው?

፫ኛ፡ ሰው መማሩ ለምንድር ነው? ለማን ሲል ነው? ትምህርት አነጣጥሮ የሚነግረን ነገሮች እነማናቸው?አእምሮ ተዟሮ የሚያየው የትምህርት ዋና ይላማው ምንድርነው?።

፬ኛ ጥያቄ፡ሰው በመማሩ በማወቁ ምንሁኖ እንዲታይ ነው?

፭ኛ ጥያቄ ፥ እውነት ስለእውነትነቷ መፈለግ መታወቅ ይገባታልን ወይስ ለሰው ጥቅም በመሆንዋ ብቻ ሰው ይወቃት? ወይ ይፈልጋት?

፮ኛ፡እውነት ምንድርነው? እውነት በራሱ አለወይ? ወይስ ሰው ሠራሽ ነውን ።

፯ኛ፡ ሰው ለሥራ ይሻልን ወይስ ሥራ ለሰው ይፈልጋል?

፰ኛ፡ ከሀብት ከኃይል ከጥሩነት ከውነት የሚያምር ነገር ከሁሉ ምንድር ነው?ከነዚህስ ማናቸው ያምራል?ቈንጆ ውብ የሚያምር ደስየሚያሰኝ ከነዚህ ውስጥ ለአእምሮ የሚበልጥበት የቱ ነው? የሚመርጥበትስ ምክንያት ግድ የሚለው ምንድር ነው? ።

፱ኛ፡ሥራ ከትምህርት ጋር ኅብረት እንዲኖረው ግድ ይላልን ወይስ ትምህርት ከሥራ ጋር አንድ መሆን ይገባዋል ?

፲ኛ፡ ደምብ በሁሉ ላይ ሥልጣኑን አጥምዶ ይይዛልን ወይስ ሕግ ነውን ። ስለሁሉ የሚገኝ ማንኛው ነው ሥልጣኑ ወሰን የሌለው? ።

፲፩ኛ፡ ሰው ሕግን ይጠብቃልን ወይስ ሕግ ሰውን የሚጠብቅ ነው? ።

፲፪ኛ፡ ሰው ጊዜን ይወስነዋልን ወይስ ጊዜ ሰውን ይወስነዋል ። ሰው በጊዜ ውስጥ ይገኛልን ወይስ ጊዜ በሰው ውስጥ ይገኛል ።

ክቡራን አንባቢዎች ማሰብና ማስተዋል ልምዱ የሆነው አእምሮዋችሁ ሐሳቡን እንደኔው ሁናችሁ ለምታችሁ የተገባ ምላሽ ከአንደበታችሁ ለማግኘት ተስፋ አለኝ ነገሩን በራሱ መርምሩት እንጂ የኔ ተራ ሰውነት አስቀድሞ በመታወቁ ጥያቄውን ፍሬ አልባ እንዳያስቀረው ይህን አሳስባለሁ የጸሐፊው ወይም የደራሲው ማነስና ማደግ ለነገሩ ከፍታና ዝቅታ አይሰጠውም ፍሬና ጣዕም እንዳለበት ማየት ብቻ ይበቃል ።

ሞገሴ ዳ ።

የሚያስደንቅ ሥራና ለዘለዓለም የሚኖር መታሰቢያ።

ከኔው ይልቅ አባቶቻችሁ እንደምታውቁት ከ፲፰፻፺፩ ዓመተ ምሕረት በፊት ያዘቦና የራያ ወረዳ አገር ጠፍ ያውሬ መፈንጫ የሽፍታና የወምበዴ መቀመጫ ብርቱ ተጋድሎ የሚያልፍ ጀግና ካልሆነ በቀር ደካማ መንገደኛ በዘበት ቀን የማያልፍበት በረሃ መኖሩን በፊታችን ከነበሩ ሽማግሌች አፍ ሰምተን ተረድተነዋል። በላይኛው መስመር ካመለከትነው ዘመን ወዲህ ግን እንደዚሁ ሁሉ በበረሃው ተሰራጭቶ የሚኖር ዘላን ጋላ ተላላፊውን ሰው እየገደለ ቢያስቸግራቸው አጼ ዮሐንስ የዘቡልን ከተማ ሲያሠሩ አበረሃው መሃከል ቆቦ የሚባል ከተማ ቈርቈረው ቤተ ክርስቲያን አሠርተው መንገደኛው አላገባብ እንዳይሆን የሚጠብቁ ክርስቲያኖች አስቀምጠውበት ነበር ይሉናል።ይሁን እንጂ ይህ አዘቦ የሚባል በረሃ ከቈላነቱና ከሃሩሩ በላይ ከኰረም ወረዳ ጨለማ ዱር ከሚባል ስፍራ ተነሥቶ ያላማጣን ቍልቍለት ወርዶ የዋጃን በረሃ አልፎ ማይሸምበቆ ከሚሉት ቦታ በመጋደያ ጫካ ላይ ከምትገኘው ብርቱ እንጂ ደካማ የማያገኛትየጉድጓድ ውሃ በቀር ሌላ ውሃ ስለሌለ የሚበዛው ሕዝብ በዚያ በረሞጫ በረሃ ውሃ አገኛለሁ መስሎት ሲፈልግ በዋለበት ቀልጦ የሚቀር እጅግ ብዙ ነው። እንዳንዱም ያንን ሁሉ በረሃ ተጕዞ አልፎ ቆቦ ከተማ ሲደርስ የከተማው ሰው የሚጠጣው ውሃ የሰባት ሰዓት መንገድ ሔዶ ኰርማት ከሚባል ወንዝ ቀድቶ ነውና መንገደኛ ሕዝብ ከተማ እንደገባ ውሃ ለምኖ ስለማያገኝ ከተማውን አልፎ ጊዜ አለጊዜ ተጕዞ ውሃ ጠግቦ እንዲያድር ኰርማት ወይም ጕፈማ ከሚባል ወንዝ ይሰፍራል ። ከዚያም ቦታ በሰላም አድሮ ከሚተላለፈው ይልቅ እዚያ ቀልጦ የሚቀር ሳይበዛ አይቀርም ለማለት እንደፍራለን። ይህ ሁሉ ግን ውሃ ከማጣት የተነሣ ነው ።

አሁን ግን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለንጉሣዊ ቤተ ዘመድዎ ረጅም ዕድሜ ከሕይወት ጋር ይስጥልንና የሕዝባቸውን ችግር ለማቃለል አስበው ብልህ ስመጥሩ የሆኑ አሽከራቸውን የወሎና ያውራጃዋ እንደራሴ ክቡር ደጃዝማች እምሩን ረዓይኬ አበጋዕየ ብለው የዘቡልን ኃላፊነት ከሰጡዋቸው ወዲህ ጥንታዊ የሆነ ታማኝነታቸውን ለማጠንከር አደራ በተቀበሉት አገር ላይ ታማኝ የሆኑ ጭፍራቸውን ፊታውራሪ በየነን ስለሾሙበት አደራ ከተቀበሉት አገር ላይ ያለውን የሕዝቡን ችግር ለማቃለል አስበው በሚያስደንቅ ትጋትና ብርታት የጕሊማን ወንዝ በበይ ቀደው በቆቦ ከተማ መሃከል ፈሳሽ አደረጉት ። ተላላፊ የሆነ መንገደኛም በከተማው እርፈት አድርጎ ውሎ ውሃ እንደልቡ ጠጥቶ ልብሱን አናጥቶ ንጉሠ ነገሥቱን እየመረቀ በሰላም ያልፋል ብለው በዚያ በከተማ አልፈው የመጡ መንገደኞች ቢያጫውቱን ከደስታችን ብዛት የተነሣ ምንም ቢውል ቢያድር የደስታ አሮጌ የለውምና ለደስታችን ተከፋዮች ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ጽፈን አቅርበንላችኋል። ይህም ሥራ በወሃ ፍለጋ ምክንያት የሚፈሰውን ንጹሕ ደም የሚያስቀር ነውና እንዲህ ያለውን መልካም ሥራ የሠሩት ሰው መታሰቢያቸው ለዘለዓለም አይረሳም ከጕሊማ ቆቦ ከተማ ድረስ በይ(ፈለግ) ቀደው ያመጡትንም ውሃ ምንም እንኳ ከተሠራ ወዲህ ባናየው አገሩን በጣም እናውቀዋለንና ወደላይ ከፍ ብለው ካልጀመሩት በቀር በመሻገርያው ላይ ቢመልሱት ቦታው ዘባጣ ስለሆነ ፈሳሽ ወሃም ምንም ቢበረታ ወደታች እንጂ ወደላይ አይፈስምና በጣም ስለሚያስቸግር በዚህ ግምት ርቀቱ ከራት እስከአምስት ሰዓት ድረስ የሚያስኬድ ጐዳና ሳይሆን አይቀርም ይህን የመሰለ ለዘለዓለም መታሰቢያ የሚሆን ሥራ ለሚሠራ አሽከርም ምኞቱን ሁሉ ቢፈጽሙለት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አገብር ምእመን ዘበውሑድ ምእመነ ኮንከ ዲበ ብዙኅ እሠይመከ ባዕ ውስተ ፍሥሓሁ ለእግዚእከ ተብሎ የተጻፈውን ቃል ተፈጸመ ያሰኛል። ንጉሣችን ልጅ እስከ

ልጅ ልጅ ይግዛ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር። ይህን የመሰለውን መታሰቢያ ያለውን ሥራ በየጊዜው እንዲሠሩልን የኢትዮጵያን ኃያላን ያበርታልን ።

ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አክሱም ።

የሚያሳዝን ሞት

ልጅ ማመጫ ሀብተማርያም የወንጀለኛ ቅጣት ፍርድ ቤት ሁለተኛ አጋፋሪ ግብረ መልካም ጠባዩ እጅግ ደግ በታዘዘው ሥራ ሁሉ ሰው የማያስተሐቅር ነበር በ፲፱፻፳፬ ዓ ም በሚያዝያ ፳፫ቀን ዐርፎ በተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በብዙ ክብር ተፈቶ ተቀበረ ስድሜውም ገና ወጣት ጐልማሳ ፴፬ ዓመቱ ነበር ። ወይዘሮ ላቀች ቸርነት ያደሩ ልጃቸው ነበርና እንዲህ ብለው አለቀሱ ።

እንድ ወንድም ነበረኝ ማመጫሚሉት። ይዚት መሬት ገባ ያችን እንደበት። ተነሡ አሽከሮቼ ጥሩት ማመጫን።እንደ-ወትሮ ልምዱ ወይ ይል እንደሆን። ለሸቱ ስጓን ሰው በዘራው ግብስ፡ ዕድሌ አጭዶት ሔደ ቡቃያው ሳይደርስ ።

በላይነህ አሸበረው

የባሰ ሞት ።

ወዳጆ ካሣ የሚባል የሙሴ ወዘኪስ አሽከር ጠባየ መልካም ሰውም ወዳጅ ነበረ። ነገር ግን የዚች ዓለም መጨረሻዋ ሞት ስለሆነ ፯ቀን ታሞ ፲፱፻፳፬ ዓ ም ግንቦት ፲፫ ቀን ዐርፎ በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበረ። ዋ እንኳን ለዘመድ ወዳጁ ይቅርና ላየው ሰው ሁሉ የሚአሳዝን ውብ የሆነ መልክ መልካም ነበረ። በዚች በትንሽ በሽታ ስለተቀሠፈ የባሰ ሞት ያሰኘኝ ምክንያቱ ይህ ነው። ዋ ዋ ዋ ምን ይደረጋል ዘመድ ወዳጆቹን እግዚአብሔር ያጥናቸው ።

ከጎረቤቶቹ አንደ. ወዳጅነህ ገብረ ኢየሱስ ዳሬዳዋ ።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ በፊት እንዳስታወቅነው በክሣራ ስም በተጠራው ብቢኒዳስ ኔምቻንድ ነገር የመጀመሪያው ክፍያ ተደርጎ በመቶ ብር ፳፪ ብር ከ፳፻፬ ሳንቲም የሚደርስ መሆኑ ታውቋልና ማስረጃቸውን እየአቀረቡ በክፍያው ውሥጥ የገቡት ባለገንዘቦች ከግንቦት ፳፬ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ጀምሮ ከጧቱ ባራት ሰዓትና ከኩላ ቀን በኋላ በ፲ ሰዓት ወደ እንግሊዝ ቆንስላ የፍርድ ቤት እየመጡ ድርሻ ድርሻቸውን ለመቀበል የሚችሉ መሆናቸውን እናስታውቃለን ።

ግንቦት ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ተጻፈ አዲስ አበባ ።

ቲ ዲ አየር አፊሲዩል አሲኜ ።

ማስታወቂያ ።

ስለኤሶሉብ (ማርክ)ምልክት የሥራው መሣለጫ ።

ለሕዝብና ለነጋዴ የተሰጠ ማስታወቂያ ። ይህ የስታንዳርድ አይል ከምፓኒ ስም የሌለው ኩባንያ በአሜሪካ በኤታዙኒ በኒዩ ዠርዚይ ያገር ክፍል በደላዋር የኤታዙኒ ሰፈር ደምብ የሚኖረው ዓለም ሁሉ ያውቀዋል ሥራውንም የሚያስኬድበት መኖሪያው በሚልዊንቶን ከተማ ነው ።

ይህ ኩባንያ ከዚህ በታች የተጻፈውን (ማርክ)ምልክት ባለቤት ነው ።

ESSOLUBE

ኤ ሶ ሉ ብ ።

ይህ ማርክ ከዚህ በታች የተጻፈውን ያመለክታል ። የተነጠረ ዘይት በጣም ያልተነጠረ ዘይት፤ ያልተነጠረ ዘይት ከጋዝ (ፔትሮል)ስብና ሌላ ብዙ ዓይነት ይወጣበታል ። ተእንስሳና ተቡታያ ከምድር ከሚመነጭ ስብ ጋር ቢቀላቀልም ባይቀላቀልም ለብርሃን ለጉልበት ለእሳት ለሙቀት ለቅባት ለማለስለስ (አስፋልት)የቅጥራን ሸህላ የቤርኒስ ፈሳሽ የሰንታ ቤርኒሽ የፓራፊን ማጠብያ የፈረስ መሣሪያ መወልወያ የሚሆን ይህ ሁሉ ነገር ይወጣበታል ።

ይህ ከዚህ በላይ ስለኤሶሉብ (ማርክ)ምልክት የተጻፈው ማስታወቂያ በዚሁ ዓይነት በሌላ ሰው እጅ በሌላም አገር እንዳይሠራ የሚከለክል ነው። ነገር ግን በዚሁ ዓይነት (ማርኩ) ምልክቱን ኤሶሉብ ብሎ ሲሠራ ወይም ሲሸጥ የተገኘ ሰው ተከሶ በኤውሮፓና በአሜሪካ አገር በቆመው ደምብ በብርቱ ተፈርዶበት መቀጣቱን ኩባንያው ያስታውቃል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ። ስለስታንዳርድ አይል ከምፓኒ አፍ ገርዘይ ወኪልነት ።

ፓል ሻንዋ አበከ አደስ አበባ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ግርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ግርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት ።

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክቶር እንደመሰከረለት ተመልከት። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አርጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች ሕንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም እንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዶች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱሬ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዷል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቀኁረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኙት ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች

በማክበር ያስታውቃል። ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ጎናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም

ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል።

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ቫልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፳፭
8me ANNE. № 25

ሐሙስ ሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 16 JUI [illegible] 32

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጻዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

በቀድሞ ዘመን እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ነገሥታት የሠራላቸውንና የረዳቸውን በታሪክ ስንሰማ እንኖር ነበረና ዛሬም ለንጉሠ ነገሥታችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደፊት በታሪክ ተጽፎ ለሚመጣው ትውልድ ሲነገር የሚኖር ሥራ ስለሠራላቸውና በዓይናችንም ስለአየን የፈጣሪያችን ስሙ ለዘላለም የተባረከ ይሁንና ቸርነቱ ለፍጥረቱ ሁሉ የእውነት ረዳት የሐሰት ጠላት እየሆነ መሥራቱን ለማመን ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ይበቃናል ፦

ልጅ ኢያሱ ከሚጠበቁበት ከፍቼ ከተማ ስለ ማምለጣቸውና ከጐጃም እንደገና ስለመያዛቸው ።

ልጅ ኢያሱ እግዚአብሔር ሳይለምኑት የኢትዮጵያን መንግሥት ቢሰጣቸው አልቀበልም ብለው ከፈቃዱ ወጥተው ሕዝቡን ጠልተው የክርስቲያንን ሃይማኖት ለውጠው ደም የሚያፋስስና መንግሥታችንን የሚጐዳ ሥራ ሲሠሩ ቢገኙ መሳፍንቱና መኳንንቱ ከሠራዊቱ ጋራ ባንድነት ሁነው ከመንግሥት እንዳስወጧቸውና በመንፈሳዊም ወገን ጳጳሱና እጨጌው ከካህናቱ ጋራ ባንድነት ሁነው አውግዘው ከምእመናን እንደለዩዋቸው የማያውቅ ሰው የለም ።

ልጅ ኢያሱም ይህ ሁሉ እንደ ተደረገባቸው በሰሙ ጊዜ ለጊዜው በሐረር አውራጃ ነበሩና የሱማሌውንና የአዳሉን እስላም ሁሉ እርዳኝ ብለው ስለሰበሰቡት በሐረር ከተማ ውስጥ ክርስቲያኑና እስላሙ ወገን ለይቶ ተጋጥሞ በእግዚአብሔር ኃይል ክርስቲያኑ ጉልበት አግኝቶ ልጅ ኢያሱን ሊረዳ የመጣ እስላም ሁሉ ታረደና እሳቸው አምልጠው ሔዱ። የታረደውም እስላም ምንም በሃይማኖት አንድ ባንሆን የኢትዮጵያ ተወላጅ ነውና በልጅ ኢያሱ ምክንያት ደሙ መፍሰሱ እጅግ ያሳዝናል።

ሁለተኛም፥ በድሬዳዋ ሳሉ ከሸዋ ወደ ሐረር ጦር ሊመጣ ነው የሚባል ወሬ ቢሰሙ እርሳቸው ድሬዳዋ ሁነው ከወሎም ከሌላም አገር እየተሰበሰበ ከርሳቸው ጋራ ያለውን ወታደር ባንድ ደጃዝማች አበጋዝነት አድርገው በባቡር አሳፍረው ሰደዱትና ሚኤሶ ሲደርስ ከአዲስ አበባ ከወረደው ሠራዊት ጋራ ተጋጠመና የጦር አበጋዝ ሁኖ የመጣው ደጃዝማች ብቻ ሲያመልጥ ሁሉም በሚኤሶ ላይ እንደቅጠል ረግፈው ቀሩ ።

ልጅ ኢያሱም ይህን በሰሙ ጊዜ ከድሬ ዳዋ ግምጃቤት ያገኙትን ገንዘብ ለተከታዮቻቸው እያካፈሉ ሰጥተው ኢድልቢም የተቻለውን ያህል ወደ ጅቡቲ ይዞ እንዲወርድ አዝዘው አዳል በረሃ ገቡ ።

ሶስተኛም አባታቸው ንጉሥ ሚካኤል ከወሎ ገስግሰው መጥተው ከሸዋ ጦር ጋራ ሊዋጉ ነው ሲባል ቢሰሙ በአዳል በረሃ አቋርጠው መጥተው አንኮበር ሲደርሱ ንጉሥ ሚካኤል ሰገሌ ላይ ተዋግተው ድል ሁነው ተማረኩ የሚባል ወሬ ቢሰሙ ወደኋላቸው ተመልሰው አምልጠው ሔዱ። የተከተላቸውን ሡራዊት ግን መደዴ የሚባለው በይፋት አውራጃ ያለው ጦር እያሳደደ እየተከታተለ ፈጀው ።

አራተኛ፡ የራስ ገብረ ሕይወት ሰው ወረይሉ ድረስ ሲን ቀዋለል መጥቶ ደጃች መኰንን ተወንድ በላይ ድል አድርገው ነጋሪቱን ይዘው ገቡ ብዙ ሰው አለቀ ።

አምስተኛ፡ በአዳል አገር ዞረው በቦሩ አድርገው ወደ ወሎ ስለገቡ ከሰገሌ ጦርነት እየሸሸ ወደ ወሎ የገባውን የንጉሥ ሚካኤልን ወታደር ሰብስበው ከአንዱ ወደአንዱ ስፍራ እየተዘዋወሩ ቆይተው በኋላ መቅደላ ገቡ ተብሎ ቢወራ በጦር ሚኒስትሩ በፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አበጋዝነት የሸዋ ጦር ወደ ወሎ ዘመተ ።

ልጅ ኢያሱም በመቅደላ ዙሪያ ከራስ አባተ ጋራ ተዋግተው ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰዎች ከሞቱ በኋላ አምልጠው ወደ የጁ ሲሔዱ በመንገድ ላይ ከደጃዝማች አመዴ ወሌ ጋራ ተጋጥመው የብዙ ሰዎች ደም ከፈሰሰ በኋላ ደጃች አመዴን ድል አድርገዋቸው ነበረ ።

ስድስተኛ፡ የንጉሥ ሚካኤል ጀግኖች እነራስ ይመር፥ እነ ፊታውራሪ ሥራህ ብዙ አብረዋቸው ነበሩና የወሎን ባላገር ሁሉ በከተት ሰብስበው የጦር ሚኒስትሩን ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስንና ሌሎችንም የሸዋን መኳንንት ሁሉ ብዙ ቀን ከከበቧቸው በኋላ በነሐሴ ፳፩ ቀን ተጋጠሙና ልጅ ኢያሱ ድል ሁነው ራስ ይመር ተማረኩ፥ፊታውራሪ ሥራህ ብዙ በጦርነት ውስጥ ሞቱ፡ ልጅ ኢያሱ ግን ሸሽተው አመለጡ ።

ሰባተኛ፡ ከደሴ ሸሽተው በአውሳ በረሃ ገብተው ከንዱ ስፍራ ወደ አንዱ ስፍራ እየተዘዋወሩ ሶስት ዓመት ያህል ቆይተው በዚያ ወራት የልዑል ራስ ሥዩም ሚስት የንጉሥ ሚካኤል ልጅ ወይዘሮ ተዋበች ነበሩና ራስ ሥዩም ስለአማችነታቸው በጦርነት የሚረዱዋቸው መስሏቸው ወደ ትግሬ ሔደው ገቡ ። ከልዑል ራስ ሥዩምም በጦርነት እርዳታ አለማግኘታቸውን ባወቁ ጊዜ ከልዑል ራስ ሥዩም ግዛት ወጥተው ወደ ልዑል ራስ ጉግሣ ግዛት መግባታቸው ተሰማና ልዑል ራስ ጉግሣ አስከብበው ያዙዋቸው። ወዲያውም እስከ ደሴ ድረስ አምጥተው ያን ጊዜ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለነበሩት ለዛሬው ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አስረከቡ ።

ከዚህም በኋላ በልዑል ራስ ካሣ እጅ ተጠብቀው እንዲኖሩ ተመከረና ልዑል ራስ ካሣ ተቀብለው ሰላሌ ውሥጥ በፍቼ ከተማ አግብተው እየጠበቋቸው ፲፩ ዓመት ከኖሩ በኋላ ልዑል ራስ ካሣ በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ በልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ሠርግ ምክንያት ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሳሉ ልጅ ኢያሱ ዘበኞቹን በገንዘብ አታለው ከሚጠበቁበት ቦታ ወጥተው አመለጡ ።

ያወጣጣቸውም ነገር የውጭው ዘበኛ ሳይሰማ የቤቱ በር ሳይከፈት ቅዮሩን ሰርስረው እጅግ በተሰወረና በረቀቀ አደራረግ ነበረና መውጣታቸው ሳይታወቅና ሳይሰማ ስምንት ቀን ያህል ቆየ ።

ከስምንት ቀን በኋላ ግን ስለ መውጣታቸው በገንዘብም በምክርም ለረዱዋቸው ለራስ ኃይሉና ለሌሎችም ለአንዳንድ የቀድሞ አሽከሮቻቸው ደብዳቤ ጽፈውላቸው ኑሮ አምስቱ ያህል ሲያመልጡ የቀሩት ሁሉም ተይዘው ቢመረመሩ የልጅ ኢያሱ ማምለጥ እርግጥ መሆኑንና ለሁሉም እረዳታቸውና መከሪያቸው ራስ ኃይሉ መሆናቸውን ተናገሩ ።

ራስ ኃይሉ ግን የልጅ ኢያሱን ደብዳቤ ከተቀበሉ በኋላ ፊታውራሪ ጊንዶ የሚባለውን የጓንደ በረት ተወላጅ የሆነ አሽከራቸውን ልጅ ኢያሱ ተደብቀው ወደ ተቀመጡበት ወደ ሜጫ ልከው ሰደዱና እሳቸው እንዳይጠረጠሩ ወዲያውም በማታለል ወዳጅ ለመምሰል ከልጅ ኢያሱ የተላከላቸውን ደብዳቤ ለጃንሆይ አሳዩዋቸው ።

ጃንሆይም ደብዳቤውን አይተው ለራስ ኃይሉ የተላከውንና ተይዘው የተመረመሩትን የልጅ ኢያሱን አሽከሮች ቃል መጋጠሙን አይተው ራስ ኃይሉ በነገሩ ውስጥ መኖራቸውን የሚአስረዳ ነገር ስለ አገኙ በግንቦት ፲፱ ቀን ራስ ኃይሉን አስያዙዋቸው ። በማግስቱም የራስ ኃይሉ መላክተኛ ፊታውራሪ ጊንዶ ሜጫ ደርሶ ከልጅ ኢያሱ ጋራ ተገናኝቶ የራስ ኃይሉን መልእክት ነግሮ ምላሹንም በጽሕፈት ተቀብሎ ሲመለስ ተልኮ መውረዱ ተሰምቶ ነበርና በጠቋሚ ከነደብዳቤው ተይዞ በተመረመረ ጊዜ ከራስ ኃይሉ ወደ ልጅ ኢያሱ የተላከውን ሁሉ ገልጦ ተናገረ። ከራስ ኃይሉ አሽከሮች እንደ አንተ ይህን ምሥጢር የሚያውቅ ማነው ብለው ቢጠይቁት ቀኛዝማች መርሻ የሚባለው ነው ብሎ ተናገረና ቀኛዝማች መርሻ ቀርቦ ቢጠየቅ ቃሉ ሁሉ ከፊታውራሪ ጊንዶ ቃል ጋራ ተጋጥሞ ተገኘ ።

ከዚህም በኋላ ደጃዝማች ደስታ ዳምጠውና ሌሎችም መኳንንት ልጅ ኢያሱን ለመፈለግ እየታዘዙ ወደ ሜጫ በወረዱ ጊዜ ልጅ ኢያሱ ከዚያ ሸሽተው ወደ ጓንደበረት መግባታቸው ተሰማና ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ግንደበረትን ከበው ብዙ ቀን ቀመጡ። ከበውም የተቀመጡበት ምክንያቱ በጦርነት ኃይል የሆነ እንደሆነ ልጅ ኢያሱ ሳይሞቱ አይቀሩምና በፊቃዳቸው እጃቸውን እስኪሰጡ ድረስ ከበችሁ ተቀመጡ እንጂ አትታኰሱ የሚል ትእዛዝ ከጃንሆይ ስለታዘዙ ነው ።

ነገር ግን ልጅ ኢያሱ ላይጠቀሙ ደም ማፍሰስ ዕድላቸው ነውና በንድ ቤት ተቀምጠው ምሳ ሲበሉ ለመፈለግ ከልዑል ራስ ካሣ ታዘው የመጡ የሰላሌ ወታደሮች በደረሱባቸው ጊዜ እሳቸው በቤት ውስጥ እንደሆኑ ተታኰሱና ከልዑል ራስ ካሣ ወታደሮች ፊታውራሪ ዓባዩና ሌሎች ሰዎች ሞቱ ።

ከእሳቸውም ወገን ለተከታዮቻቸው ዋና ያደረጉት ዘውዱ እርገጤና ሌሎችም አምስት ሰዎች ሞቱባቸውና እርሳቸው በፈረስ ሁነው ወደ ጉድሩ ሸሽተው አመለጡ። አብረዋቸውም ያሉት ጥቂቶች ሰዎች ተለያይተው ሲሸሹ ተቋርጠው ሳይገናኙ ስለቀሩ አንድ ወምበዴ ብቻ አስከትለው

ወደ ጐጃም መሻገራቸው ተሰማ።ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ልጅ ኢያሱ ከግንደበረት ሾልከው ወደ ጐጃም መሻገራቸውን በሰሙ ጊዜ የአዋጅ ቃል አስጽፈው በከንቲባ ማተቤ እጅ ወደ ጐጃም እንዲላክና ደብረ ማርቆስ ላይ በመኳንንትና በሠራዊቱ ፊት የአዋጁ ቃል እንዲነገር አደረጉ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

አዋጅ

ስማ የጐጃም ሰው ።

ራስ ኃይሉ ከጃንሆይ ከአፄ ምኒልክ ጀምሮ እስከ እኛ ድረስ ሲአደርጉት የኖሩትን እንደምታውቀው ፡ አሁንም በራስ ጉግሣ ጦርነት ጊዜ ለሁላችንም ዘመድ መስለው ለኛም ለሳቸውም አለሁ እያሉ ያንን ሁሉ ደም ከማፍሰስ ያደረሱትን ከኛም ይልቅ አንተው ታውቀዋለህ ። ያንን ሁሉ የተክለሃይማኖት ልጅ ናቸውና ይመከሩልናል በማለት የኛን በደል ብዙ ጊዜ ብናሳልፍ እሳቸው የደሀውን በደል የማይተውልን ሆነ ። እንኳን በባላገሩ በቤተ እግዚአብሔር በሾል እየተጋፉ የሠሩት እጅግ የበዛ በመሆኑ የሚገባውን ሙሉ ቅጣት ፍርድ ከፍለን እሳቸው ለወረሱት ደሀ ገንዘብ መክፈያ ብለን አገውምድርንና የበርና የገበያውን ቀረጥ ይዘን የቀረውን እንደያዙ ይሁኑ ብለን ብንምራቸው እያጠፉ መማር ሲበዛባቸው ጊዜ እጅግ ከልክ አልፈው ፪ት ወር እንኳ ሳይሞላ ከለፈው ሥራቸው የባሰ ደግሞ ሸዋና ጐጃምን አዋግተው አገር ለማስጠፋት ሃይማኖት ያናወጹትን ፡ ከምእመናን የተለዩትን ፡ ልጅ ኢያሱን ከታሠሩበት ስፍራ ለማስወጣት የተላላኩት ወረቀት ከራሳቸው ከእጃቸው ላይ ተገኝቶ ፡ ለማስወጊያም የጦር መሣሪያ መስደዳቸው ተመስክሮ ይኸው እጃቸውን ይዘናቸዋልና ከጐጃም የበደሉን እሳቸው ብቻ ናቸው እንጂ ከወታደሩም ከባላገሩም ጠብ የለኝምና ዳኛህን እስትሰድልህ ድረስ ባለህ እርጋ ። ለጊዜውም የሚጠብቅህ ዳኛ ይኸው ሰድጀልሃለሁ ። እሳቸውም በሚሠሩት ተንኰል የኔ ጠላት የሆነ ከገርህ ላይ የገባ እንደሆነ ጠላቴን ስፈልግ አንተን እንዳላጠፋ ተጠንቅቀህ ጠብቀህ ያዝ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

አዋጅ ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ ባላገር ፡ ባለርስት ፡ ባላባትም የሆንከ፡ በገርህ ላይ ልጅ ኢያሱን ያሳለፍክ፡ ያሳደርክ ፡ ይዘህ ያላመጣህ፡ ጠላቴን ስፈልግ ርስትህ ከብትህ አገርህ ቢጠፋ እኔን እንዳትጠላኝ ጠላቴን እንዳያመልጥህ ያዝ። ገንዘብ፡በመስጠትም በመስለልም የረዳህ ጥፋትህን በራስህ አንተው መፍረድህ ነው።

ግንቦት ፳፬ ቀን።

የጐጃምም መኳንንትና ሠራዊቱ ሊቃውንትና ካህናቱም የጃንሆይን የአዋጅ ቃል በሰሙ ጊዜ ባንድ ልብና ባንድ አሳብ ሁነው የግርማዊን የአዋጅ ቃል በከንቲባ ማተቤ እጅ በገኘነው ጊዜ ልባችን በደስታ ሙቀት የጋለ ሆነ ።

ከአሁንም በፊት ማጣት ማግኘታችንን መድከም መበርታታችንን ጃንሆይ እንዲያውቁልን ብናስብ መጮጫ ቀዳዳ መሮጫ ሜዳና ነፃነት አጥተን በባርነት ቀምበር ተይዘን ነዋሪዎች ስለ መሆናችን አሳባችን ሳይፈጸምልን ቀረ ። አሁን ግን እንኳን የክርስቲያን ጠላት ልጅ ኢያሱን የሀገራችንን መሬት ማስረገጣችን ይቀርና በሌላም አገር ቢሔዱ ጃንሆይ ታዘዙን ተከታትለን ሔደን ደማችንን እስከ ማፍሰስ ደርሰን ለመያዝ እኛ ባሮችዎ የተዘጋጀንነን ።

በማናቸውም በጃንሆይ ላይ ለሚመጣው ክፉ ነገር ሁሉ አስቀድመን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ እንሞታለን የሚል ቃል ጽፈው ስልሣ የሚሆኑ መኳንንት እያተሙ እየፈረሙ በአይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ላኩ ።

ከዚህም በኋላ የልጅ ኢያሱ ጐጃም መሻገር በተወራ ጊዜ የጐጃም መኳንንት የተናገሩትን የክርስቲያንነት ቃላቸውን ለማፅናት ሲሉ ልጅ ኢያሱን ፈልገው ለመያዝ ተነሡ ከመከከላቸውም እንዱ ፊታውራሪ ገሠሠ በለው የሚባለው የራስ ኃይሉ የወንድም ልጅ ግዛቱ ወደ ዓባይ ወገን ሊበን በሚባለው አገር ነበርና ልጅ ኢያሱን ከተከተላቸው ወምበዴ ጋራ ሲሔዱ አግኝቶ ቁም ብሎ ያዛቸው ። ልጅ ኢያሱም አልያዝም ብለው ሳያንገራግሩና አንድ ጥይት እንኳ ሳይተኰሱ እጃቸውን ሰጥተው ተያዙ ወዲያውም የምሥራቹንና ዓባይ ድረስ ይዘው ወርደው ለማስረከብ ማሰባቸውን በስልክ አስታውቀው ነበርና ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ከግንደ በረት ገሥግሰው ወደ ዓባይ ድረስ ወርደው እንዲቀበሉ ታዘዙና በሰኔ ፫ ቀን ተቀብለው ወደ ግንደበረት ተመልሰዋል።

እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ለኢትዮጵያና ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚሠራው የቸርነት ሥራ ተጽፎና ተነግሮ አያልቅም ።

ከ፲፱፻፱ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ እስከሁን እስከ ፲፱፻፳፬ ዓመት ድረስ በልጅ ኢያሱ ምክንያት የፈሰሰውን ደምና የፈረሰውን ትዳርና ቤት ለመቍጠር እጅግ ይበዛልና ወገኑ የሞተበትና ትዳሩ የፈረሰበት በየቤቱ ይቍጠረው ።ስለዚህ በየመንገዱና በየባላገሩ ከተደረገው ጥፋት በቀር ጦርነት እየተደረገ ሕዝቡ ያለቀበት አገር ብቻ ብዛቱ ከዚህ ቀጥሎ እንዳለው ነው።

፩ኛ፡ በሐረር ከተማ ከነደጃች ባልቻ ጋራ ።
፪ኛ፤ በሚኤሶ ጣቢያ ከነደጃች አያሌው ጋራ ።
፫ኛ፤ በሰገሌና በደፋት አውራጃ ።
፬ኛ፤ በደሴ ከንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ጋራ ።
፭ኛ፡ በደሴ ከወይዘሮ የሺመቤት ጋራ ።
፮ኛ ፤በመቅደላ ዙሪያ ከራስ አባተ ጋራ ።

፺ኛ፤ በየጁ አውራጃ ከደጃች አመዴ ጋራ።
፺፩፤ በደሴ ከፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ጋራ ።

ይህም ሁሉ የፈሰሰ ደም በእግዚአብሔር ፊት እያስፈረደብኝም ብለው ሳይዋረዱ በመልከምና በክብር ከተቀመጡበት ስፍራ ወጥተው እንደገና ሽማግሌውንና ባልቴቱን ፤ ሕፃናቱን ለማስለቀስ ተደላድሎ የቆመውን መንግሥት ለማናወጽና እርስ በርሳችን አዋግተው የክርስቲያኑን ደም ለማፍሰስ የእስላሙን ጉልበት ለማጉልመስ ማሰባቸው እጅግ የሚያስደንቅ ነው ።

ቢሆን እንደዚህ ያለ መከራ ያገኘው ሰው ባለፈው ሥራው ተጸጽቶ ንስሓ ገብቶ ክርስቲያንነትን ማጽናት ነበር እንጂ ዉንድምና ወንድም ፤ ባልንጀራና ባልንጀራ የሚያጋድል ሥራ መሥራት አይገባም ነበር ።

ልጅ ኢያሱ ከእስላሞች ጋራ አንድነት እንዳላቸው የሚያስረዳ ነገር ከነጋድራስ አበከር ልጅ አንድ ወንድ ልጅ ስለ ወለዱ የእናቱ ዘመዶች ከኢትዮጵያ ግዛት አሸሽተው በሌላ መንግሥት ቀኝ አገር ስለ አኖሩት አሁን በቅርቡ ጊዜ ከእስላሞች ጋራ ያለው ልጅዎ ወደዚህ መጥቶ ክርስትና ተነስሥቶ ማደሪያም ሰጥተነው ቢቀመጥ ይሻላል ብለው ጃንሆይ ቢልኩባቸው ምንም ቢሆን ልጄን ክርስትና አላስነሣም ብለው እምቢ አሉ ይህም ሁሉ ባለፈው ሥራቸው አለመጸጸታቸውን ያስረዳል ።

አዲስ ዓለም ላይ ለደብረ ጽዮን የተሠራው ሕግ በተነበበ ጊዜ ስለ ተደረገው በዓል ።

ተፈሥሑ በእግዚአብሔር ዘረድአነ ወየብቡ ለአምላከ ያዕቆብ ንሥኡ መዝሙረ ወሀቡ ከበሮ መዝሙር ሐዋዝ ዘምስለ መሰንቆ ንፍሑ ቀርነ በዕለተ ሠርቅ በእምርት ዕለት በዓልነ እስመ ሥርዓቱ ለእሥራኤል ውእቱ እያልሁ እምርት ዕለት የተባለች ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥትነት የደረሡባት ቀን እንደሆነች እናገራለሁ ይህችም ቀን አምስት ሺሕ ከምስት ፻ዘመን ተጠብቆ የነበረ የአዳም ተስፋ የተፈጸመባትን ዕለት ትመስላለች ሰማያዊው ንጉሥ አዳምን ፈጥሮ በገነት ካኖረው በኋላ ቢበድለው ከቦታው አውጥቶ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ወደ ቀደመ ቦታህ እመልስሀለሁ ብሎ የሰጠውን ተስፋ ዕለት ሰዓት ሳያሳልፍ እንደፈጸመለት ምድራዊው ንጉሥ አፄ ምኒልክም ደብረ ጽዮንን በከበረች ቦታ በሐዲስ ዓለም ተክለው እሠራላታለሁ ብለው የሰጥዋትን የሕግ ተስፋ ለመፈጸም ዓረፍተ ዘመን ገትቷቸው ስለ ቆየ ልጃቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጊዜው ጊዜ ዕለት ሰዓት ሳያሳልፉ ፈጽመውላታልና ስለ ፈጸሙላት ።

ዳግመኛም እምርት ዕለት ዘመነ ወንጌል እንደ ሆነች ይህችም ዕለት ዘመነ ወንጌልን ትመስላለች ወንጌል በመልከ ጼዴቅ ጊዜ ታይታ ጠፍታ ውሥጥ ለውሥጥ ስትነገር ቈይታ በአማናዊው ካህን በክርስቶስ ጊዜ ፈጽማ እንደ ተገለጸች ይህችም ሕግ በከበሩ አባታችን ባለታ ኪዳነ ወልድ ጊዜ ተጀምራ ውሥጥ ለውሥጥ ስትነገር ቈይታ ይነብር ክህነቱ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ በሚያሰኙ በአማናዊው ካህን በንቡረ እድ ተክለ ሃይማኖት ጊዜ ተፈጸማለችና ።

ፈጽሞም የሚያስደንቀው የሥራውና የዕለቱ መተባበር ነው እኛ ተፈሥሑ በእግዚአብሔር ዘረድአነ እምርት ዕለት በዓላነ እያልን በምናመሰግንበት በዕለተ ሆሣዕና ልኡካኑ ግብር ይዘው አርኅዉ ኆኃተ መኳንንት ብለው ቅዳሴ የሚገቡበት ጊዜ ሲደርስ የደጉ ንጉሣችን የማትሻር ወንጌላዊት ሕግዎ ቀርባ ተነባ ስትፈጸም ተጋጠመና ካህናቱም ጨዋውም ከዳር እስከ ዳር አጨብጭበን ንሴብሖ ብለን ሥጋውን ደሙን በመሃል አድርገን በመቅደሱ ውሥጥ ዑደት ስናደርግ ዋናውን በዓላችንን አስተ፡እዮን መሰሉ ነበርና ።

የቅዳሴው ሰዓት ባልደረሰብንስ ብዙ በዓል ለማድረግ ተዘጋጅተን ነበረ ። ዳሩ ግን የቅዳሴው ሰዓት ሊተላለፍ አይቻልምና ተወት አድርገነው እውቀት ያላቸው ቆሞስ ተመርጠው ቀርበው ላባትዎ ዳዊት ታቦተ ጽዮንን ወደ ኢሎፍሊ ተማርከ ኑራ ስትመለስ በፍጹም ምስጋና ቢያከብሩት መንግሥትን ከዘርህ አላወጣብህም ብሎ የማለለት እግዚአብሔር የዳዊት መሳይ ልጁ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም በመቸገር ምርኮ የምትኖር ደብረ ጽዮንን በፍጹም ክብር ስላከበሯት መንግሥትን ከልጅ ልጅዎ አያናውጽብዎ ላባትዎ ለዳዊት የማለውን መሐላ ያፅናልዎ ብለው አሳርገው ዲያቆኑ በታላቅ ቃል አርኅዉ ኆኃተ መኳንንት ብሎ ተጣራ ።

አርኅዉም በብዙ ወገን ይተረጐማል ለዚች ዕለትና ሕግ ያጋጠማት ዋናው ምሥጢር ግን እንዲህ ነው አርኅዉ ኆኃተ መኳንንት ማለት መኳንንተ ትንቢት ነቢያት መኳንንተ ትምህርት ካህናት ኆኃተ ትንቢትን ኆኃተ ትምህርትን ክፈቱ፤ ወይትረኃዎ ኆኃት እለ እምፍጥረት ከጥንት ጀምሮ ተከፍተው የማያውቁ ኆኃተ ትንቢት ኆኃተ ትምህርት (ወይንም አእዛነ ሰማዕያነ አልባበ ሰማዕያን) ይከፈቱ ወይባእ ንጉሠ ስብሐት፤ የክብር ባለቤት ጌታ በአእዛነ ሰማዕያን በአልባበ ሰማዕያን ይደር ማለት እንደሆነ ይህን ሥራ የሠሩ የክብር ባለቤት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በመምራን አንደበት ይመስገኑ በደቀ መዛሙርት ልቡና ይታመኑ ማለት ነውና ቄሱም ሰምቶ የክብር ባለቤት ማን ነው ብሎ ጠየቀ ቸሩ ለጋሱ ኃያል ፅኑዕ ያርበኞች ጌታ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነዋ ብሎ መለሰለት እንኪያስ ይባእ፤ በመምራን አንደበት ሲመሰገን በደቀመዛሙርት ልቡና ሲታመን ይኑር ብሎ ከፈተለት እኛም በዚሁ ቃል ጽፋቱን እንደወረብ አድርገን እየመላለስን ይባእ ንጉሠ ስብሐት ብለን ብዙ ጊዜ አመስገንንና ወዲያው ቅዳሴ ተጀመረ ።

ይህም ይህ ነው ከዚህ ጋራ የሚያስደንቀው አጋጣሚ ነገር በዚህ ቀን የሚሰበከው ተፈሥሑ ባእግዚአብሔር ዘረድአነ የሚለው መዝሙር ፍጻሜ ዳዊቱ ወአዕገበሙ መዓረ እምኰኵሕ መሆኑ ነው ሲያስቡት ሆነ ተብሎ የተደረገ ይመስላል እንጂ የድንገት አጋጣሚ አይመስልም (ማለት) ወኰኵሕሰ ክርስቶስ ውእቱ ባለው አንጻር አንተ ኰኵሕ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ አሐንፃ ለቤተ ክርስቲያን ወአናቅጸ ሲኦል ኢይኄይልዋ በተባሉ በንቡረ እድ ተክለሃይማኖት መሠረትነት የማትናወፅ

ሁና ለታነፀች ምእመን የተሠራችላት ሕግ ክህናቱ የሹመት ማዕርግና የማር ግብር ይቀበሉ ተፈቅዶላቸዋል የምትል ናትና ለካ ወእፅገቦሙ መዓረ እምኰኵሕ ታሰኝ ዘንድ አገባብ ነው።

ዳግመኛም እናቅጸ ሲኦል ኢይኄይልዋ ያላት ሀገሪቱንም ነው እንጂ ምእመንን ብቻ አይደለም (ማለት) ከዚህ ቀድሞ የነበሩ አለቆቻችን ይህች ተስፋ እንድትፈጸም ያለመትጋታቸው ምክንያቱ ገባር ይቀነሳል ወታደር (ሎሌ) ያንሳል የማለት ሐሳብ እያሸነፋቸው ይመስላልና በሊህ ግን ይህ ሁሉ ሐሳብ እንደሌለባቸው ደጉ ንጉሣችን ተረድተው በዘመናቸው ይህችን ሕግ ሠርተው ጽፈው በላኩላቸውና በተነበበች ጊዜ ከኛ ይደረግላችሁ ከተባልነው ይልቅ የሳቸው ይከፈሉብዎ የተዮሉት ደስታ በዝቶ ተርፎ ይታይ ነበርና ደስታቸውንም ለመግለጽ አሠሩ ለልብ ብሩህ ገጽ እንዲል ። ንሴብሖ በተባለ ጊዜ በጎድጓት የቆሙትን ሰዎች እየዘሩ ያነቃቅዋቸው ነበርና ።

ከቅዳሴም በኋላ ከቤታቸው ገብተን ቊርስ ጋብዘውን ሳለ ይህን የተሰጣችሁን ነገር እየተሳሰባችሁ በፍቅር ያደረጋችሁት እንደሆነ ከዚህ የበለጠ ታገኛላችሁ ብለው ምክር ቢሰጡን ልቡናችን በደስታ ተነክቶ ለካ ወእናቅጸ ሲኦል ኢይኄይልዋ ያሰኘው ይህ ነው ብለን አደነቅን። እንደሕጉም የዓበይት በዓላት መወደስ የሚገባው ለንቡረ እዱ ስለሆነ እንዲህ ብለው ተቀኙ።

መኑ ይትረሰይ ለቀትለ ፀላኢ፥ቀዉ.መ ዓውደ ቀትል ዕኑዕ ለእመ ቆመ ዕሬቆ

ወመኑ የእምር (ይሰምዕ)ቃለ መሰንቆ ።
ለእመ በትእምርት ኢነበቡ ፤
እለ ሰምዑ ቃሎ ወርእዩ መብረቆ ።
እስመ ለቃለ እብ ባሕረ ተዓውቆ
ዘኢለመዱ ፀቢተ፥ ኢይሜጥኑ ዕመቆ ።
እመ ዐርገ፤ ሆሣዕና ምዕራገ ተዓዉቆ ።
ለህንባበ ዳዊት ዕፀ ክርካዕ፥እምዓፅቀ ዘከርያስ ኢያርኃቆ።
መኢመ ይሁዳ ኢሰምዐ ለቃለ ዳዊት ጽድቆ ።
ነበልባለ ሄኖክ ነበልባል ለሐቅለ ይሁዳ ያድለቀልቆ ።

እንግዲህሳ ምንተኑ እዐሥዮ ለእግዚአብሔር በእንተ ኵሉ ዘገብረ ሊተ እንዲል እንዲህ ያሉ ለዓለም ሁሉ የሚያበሩ ርኅሩኅ ቸር ንጉሥ አስነሥቶ ሁሉን በሥራ ፤ሥራው እንዲያሰማሩ ላደረገ ዳግመኛ የትሩፋት አበጋዝ የሚሆኑ ንቡረ እድ ተክለ ሃይማኖትን አስነሥቶ በዘመናቸው እንዲህ ያለ ሕግ እንዲሠራልን ላደረገ ለእግዚአብሔር ምን ስጦታ እንሰጠዋለን ምን ዋጋ እንከፍለዋለን ። ዳሩ ግን እም ዘብየሰ እሁበከ እንዲል የኛ ገንዘብ ስሙን ማመስገን ዕድሜና ሕይወት መለመን ነውና ራትዕ ንጉሣችነን ድንት ለድነት ያኑርልን መንግሥትን ከዘርዎ አያውጣብን እያልን ስንገባ ስንወጣ ስንበላ ስንጠጣ ለፈጣሪችን ማመልከት ይገባናል ብዬ ነገሬን እጨርሳለሁ ።

ከተማሪዎቹ አንዱ ሞገስ ዓምደ ሚካኤል።

የማዕድን መገኘት በሐረር አውራጃ

በክቡር ደጃዝማች እምሩ ም ክርና ፈቃድ ኰንፓኒ አምፔርየል ዴሚን ዴትዮጲ ፲፱ኛ ቊጥር የኮንቲና ገኦሎገክ ሚኔራሎገክ ኰሌክስዮ ስልሳ ዓይነት ሚኔሮ በሣጥን እንደአለነ ተነማስረጃው የሰጡኝን ተከትዬ በሶስት ዓመት ተመንፈቅ ውሥጥ በፔሮስፔክቴርነት ፍጥነት የአገኘሁትን ማዕድንና ድንጋዩ ለኢትዮጵያ ልጆች አስታውቃለሁ ።

፩(ሚጊሮ ሐጨና አው ሙሳ በሐረር አውራጃ ሺ፰፻ አልቲትድ ላይ በግራኒቲክና በፔግማቲት ድንጋይ ውሥጥ ለሥራ የሚበቃ ትክቡር ድንጋይ ቤሪል ዛፊር ቱርማሊን ኰሬንዶ የቊት እጠገቡም (በሚከሺስትና በሚተምርፊክ ድንጋይ ውሥጥ ግሬንና የብረት ማዕድን ይገኛል በማዊናና በዓሊ ሺራ መካከል ሺ፻፻ አልትቱድ ላይ በግራኒቲክና በከልሲት ውሥጥ ሆኖ ቶፓዝ ቱርመሊን አገትም በትራሺት ውሥጥ ይገኛል ውልራም ፔሬትም ይገኛል አሉብዬን ኰንግሎሜራ ውሥጥ አሜቲስት ይገኛል ። በደቻኦ ። ሺ፮፻ አልትቱድ ላይ ኤሚሮድና ኤፒዶት ተማዕድንም ሞሊብዴኒት ይገኛል ። በጋራ ጃቤና በጋራ በራድ ሺ፭፻ እስከ ሺ፭፻፶ አልትቱድ ላይ ተፈርጥም ተማዕድንም ታልክ ወይም ሴርፓንቲን ቱርማሊን ክልሴድዎን አሜትስት ኮሬንዶ ተማዕድንም የዝንክ ከለሚን የሊርሰሳ ጋሌኒ ገርንዬሪት ኔኬል መኜቲት ጋራ ሚኔራ ሆኖ ብርና ወርቅ ይገኛል በለቁሉና አውሶፌ መካከል ሺ፱፻ አልትቱድ ላይ የድንጋይ ከሰል ይገኛል የቀረውንም እስከታትለን በጋዜጣ እናስታውቃለን ለአንባቢዎችም እንዳይቸግር የገኦሎገክን የሚኔራሎ ዢክን የፓሌአንቶሎ ዢክን በአማርኛ ባረብኛ በፈረንሳዊኛ ምሥራቅ ብለን በጠራነው መጽሐፍ ሲታተም ያገኙታል ።

አሕመድ አሊ ሻሚ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሸሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሬ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል። ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ጎናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



ማስታወቂያ ።

ወይን ጠጅ ።

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባየሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ግለፈያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የከምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ ።

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአደስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባህ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧት ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፷ እስከ ፲ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን ዮሁን አዲስ የከትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የከትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ ፥ የደረት የጉበት ፥ የኩላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቁቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት ኣጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

አለም

ALEM

በያይነቱ የኪስናየእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሸቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል ።

የምትፈልጉ ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል ።

ፔር ዳኔይ ።

አበካት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክተር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል። ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው ።

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳዊ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂኒልያን ቤት ይገኛል ።

☞ የሚከራይ ። ☜

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፳፮
8me ANNE. № 26

ሐሙስ ሰኔ ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 23 JUIN 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ ለኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ራስ ኃይሉ መያዝና መታሠር

ተረት ቢሰነብት ፤ ይሆናል እውነት ።

ሽማግሌ ሲተርት ከተራብ ለጠገበ አዝናለሁ ይላል ። ይህንም ያሳሰበን የራስኃይሉ ሐሳብ ነው። ራስ ኃይሉ የጐጃም ባላባት የንጉሥ ተክለሃይማኖት ልጅ ናቸው።አባታቸው ንጉሥ ተክለሃይማኖት ደጃች ሥዩም ብለው አገር ሹመዋቸው ይኖሩ ነበር።አባታቸው ንጉሥ ተክለሃይማኖት ከሞቱ በኋላ ግን ሁለቱ ታላላቆች ልጆቻቸው ራስ በዛብህና ደጃዝማች በለው አባታቸውን ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ከድተው ወደ አፄ ምኒልክ ቢመጡ አፄ ምኒልክ መቸም አዋቂ ነበሩና ለአባታቸው ያልሆኑ ልጆች ለኔም አይሆኑኝ ብለው አሥረው ወደ አባታቸው መለሱዋቸው።ንጉሥ ተክለሃይማኖትም ብዙ ዘመን አሠሩዋቸው አፄ ምኒልክም አባታቸው እንደጨከኑባቸው ባዩ ጊዜ ፍታልኝ እባክህ ብለው አማልደው ቢአስፈቷቸው እንግዲህ ልጆች አይሆኑኝምና ወደ እርሶዎ ይሁኑ ብለው ወደ አፄ ምኒልክ ሰደዋቸው በግዞት ይኖሩ ነበር ። ደጃዝማች ሥዩም ግን ከአባታቸው ፈቃድ ሳይወጡ አብረው ይኖሩ ነበርና ንጉሥ ተክለሃይማኖት በሞቱ ጊዜ ምንም ኑዛዜ ባይኖረው ከአባቱ ፈቃድ ላልወጣው ይገባል ብለው የአባታቸውን ሙት ዓመት ለደጃዝማች ሥዩም ሰጧቸው ። ወዲያው ተንኰል ሥራ ጀመሩ። የአባታቸውንም መኳንንት ለማጥፋት ሲሉ የመኳንንቱን ማኅተም እያስመሰሉ ቀርጸው አፄ ምኒልክን እንክዳና ራስ ቢትወደድ መንገሻን እንውጋ የሚል ቃል የነሱ ሐሳብ አስመስለው ጽፈው አትመው ወደ አፄ ምኒልክ ቢልኩ በዚያ ጊዜ ከማኅተም ጋራ ፊርማ አልነበረምና አፄ ምኒልክ እውነት ስለመሰላቸው እንዱ እንኳ እንዳያመልጥህ ሁሉንም ያዝ ብለው ስለፈቀዱላቸው ሁሉንም አሠሩዋቸው ጊዜውም ክረምት ነበረና የዓባይ ውኃ እስቲጐድል ድረስ ብዙ ቈይተው እሥረኞች አቤቱታቸውን ስለአበዙ እሥረኞችን ይዘው ወደ አዲስአበባ እንዲመጡ አፄ ምኒልክ አዘዋቸው ከመጡ በኋላ ማኅተሙ ቢመረመር የራሳቸው ተንኰል ሁኖ ተገኘ።እውነት እውጣ ብለው በብርቱ ቢመረምሯቸው አዎን የኔ ተንኰል ነው እንጂ እነሱ አልጻፉልኝም ማኅተማቸውንም ያስቀረጽሁ እኔ ነኝ ብለው ስለአመኑ ይቀጣ በቃ ተብሎ ተፈርዶባቸው ፳ዓመት ያህል እፍቀራ አምባው ላይ ታሥረው ኖሩ። ደግሞ የንጉሥ ተክለሃይማኖትን ታላቁን ልጃቸውን ራስ በዛብህን ሾመው ቢሰዱዋቸው እሳቸውም ክዳት አስበዋል ተብለው ተከሰውና ተረትተው እንደ ታሠሩ ሞቱ፡በጐጃምም ግራዝማች ወልደ ዮሐንስን ምስለኔ አድርገው ሲአስጠብቁት ነበርና ጉዳት አለባችሁን ብለው የጐጃምን መኳንንት ቢጠይቋቸው ጃንሆይ ጉዳትስ ምንም የለብንም ነገር ግን አውራ አውራ ሸተተን ስለ አልዋቸው ከተሻላችሁማ ምን ቸገረኝ ብለው ደጃዝማች ሥዩምን ከእሥር ቤት ፈትተው እንደገና ያባታቸውን አገር ሾሟቸው።እንዲፈቱ የጣሩላቸውም እቴጌ ጣይቱ ነበሩና የእኅታቸውን ልጅ ክብርት ወይዘሮ አሰለፈችን አጋብተው ራስ ቢትወደድ መንገሻን አስከስሰው አስረትተው ስም እንሰጥሀለንና ከአባቶችህ ስም ምረጥ ብለው ቢፈቅዱላቸው ኃይሉ መባልን እመርጣለሁ አሉ።እቴጌ ጣይቱም ለተነሡበት ነገር እጅግ ይተጉ ነበርና ራስ ኃይሉ አሰኝተው ጐጃምንና ዳሞትን አሾሙዋቸው ከዚህ በኋላ አፄ ምኒልክ በብርቱ ታመው ከቤት ዋሉ በዚያም ጊዜ እቴጌ ጣይቱ በጃንሆይ ቃል እያሳተሙ የመንግሥት ሥራ ይሠሩ ነበርና የኢትዮጵያ መኳንንት በአንድነት መክረው እቴጌ ጣይቱ ከመንግሥት ሥራ ይውጡልን የመንግሥቱን ሥራ ግን የልጅ ኢያሱ ሞግዚት ራስ ቢትወደድ ተሰማ ይሥሩ ብለው እቴጌ ጣይቱን ከመንግሥት ሥራ በአስወጡ ጊዜ ሚስቱን ካልፈታሁ አልታመንም ብለው ወይዘሮ አሰለፈችን ፈትተው ሰደዱዋቸው።መቸም ሰው በራሱ ካልደረሰበት የኔም ቀን ይህ ነው አይልምና ራስ ቢትወደድ ተሰማ አመንዋቸው ።

ከዚህም በኋላ ራስ ቢትወደድ ተሰማ ሞቱና ልጅ ኢያሱ መንግሥት በያዙ ጊዜ ዘመዳቸውን ደጃች ተረፈ አምባዬን አስገድለዋል ስለ ተባሉ የሟቹ ዘመዶች ወደ ልጅ ኢያሱ መጥተው አቤቱታቸውን ባቀረቡ ጊዜ ንጉሥ ሚካኤልን የሀገሬ ቍራጭ ይሁኑልኝ ብለው ለምነው ወደ ወሎ ተሻገሩ። ይህንም ማድረጋቸው የሸዋ ሰው ኃጢአቴን ያውቃልና ይፈርድብኛል የወሎ ሰው ግን አያውቀብኝም እንግዳ ነውና እታልለዋለሁ ብለው ነው ። ደግሞ በብዙ ብልሀት አድርገው ልጃ

ቸውን ወይዘሮ ሰብለወንጌልን በግርድና አይበል በሚስትነት አይበል እንዲያው ለልጅ ኢያሱ ሰጡ፡ወይዘሮ ሰብለ ወንጌልም ከልጅ ኢያሱ ሴት ልጅ ወለዱ፡ከዚህ በኋላ የልጅ ኢያሱና የንጉሥ ሚካኤል ልብ እጅግ ታመነባቸው ። ነገር ግን ልጅ ኢያሱን ጊዜ በጣላቸው ጊዜ አስቀድመው ከዱ ። ከዚያ በኋላ ንግሥት ዘውዲቱ ሲነግሡ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም አልጋ ወራሽ በሆኑ ጊዜ የሁለት ሰው ቤት እንዲህ ላለ ሰው ይመቻልና አንድ ጊዜ ከንዱ አንድ ጊዜ ከንደ እያሉ ለሁሉም ወዳጅ መስለው ኖሩ።ራስ ጉግሣ ወሌም በከዱ ጊዜ እኔ አለሁ በገንዘቡና በመጓጓዥ እኔ እረዳለሁ ብለው እሳቸውን አስነሥተው ጥይትና ገንዘብ ለራስ ጉግሣ ወሌ ሰጥተዋል ተብለው ቢከሰሱ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትዕግሥቱን ያበዙ ቃልና እንዳልሰሙ ሁነው ነገሩን አስቀሩላቸው፡በቀን በቀኑም የሚከሰሱበት ነገር ሁሉ ለሰሚው የሚያሰዝን ነበረ። ነገር ግን ጃንሆይ በቀን በቀኑ ይቅርታ እያደረጉላቸው በክብር ላይ ክብር እየጨመሩላቸው ቢይተው ራስ ኃይሉ የተቀበሉበት መቸም ተንኰል ነውና ገንዘቤ ሳለ ሰው ምን ያደርገኛል እግዚአብሔርስ እንዴት ይፈርድብኛል ብለው አፋቸውን ወደ ግቢ ልባቸውን ወደ ውጪ አድርገው በመንግሥቱና በኢትዮጵያ ላይ ክፉ አሳብ እያሰቡ እርስ በርሱ ደም የሚያፋስስ ሥራ ሲሠሩ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና የኢትዮጵያ አምላክ ገልጾባቸው በግንቦት ፲፱ቀን ተያዙ።ራስ ኃይሉን ፳፰ ዓመት ያህል እያንቀባረረ ያስገዛቸውንና ያጠገባቸውን መንግሥት፡ ኢትዮጵያን የመሰለች በግር በወትት ያሳደገች እናት መክዳታቸው በጥጋብ ስለሆነ ከተራብ ፤ ለጠገበ አዝናለሁ የተባለውን ተረት ያሰብንበት ምክንያት ስለዚህ ነው ። ድሀ ቢጠግብ የሚወድቀው ተመሬት፤ ሀብታም ቢጠግብ የሚወድቀው ተሰገነት ነውና ስብራቱም እንደማዕርጉ ስለሆነ ሽማግሌው ከተራበው የጠገበው ያሳዝነው ስለዚህ ነው ። አሁንም ራስ ኃይሉ የሠሩት የተንኰል ሥራ አገራችንን ኢትዮጵያን የሚያጠፋ ስለ ሆነ የተበደለውም ሙሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው እንጂ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብቻ አይደሉምና ሁላችንም እንፋረዳቸዋለን ።

ታላቅ ክብር ያለው ሠርግ።

በሰኔ ፱ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጃቸውን ልዕልት ዘነበ ወርቅን ለልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ ልጅ ለደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ የሚድሩበት ቀን ነበረ። ከዚሁም ቀን አስቀድሞ አቃቂ ከልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ ቤት አጠገብ ያለውን መልካም ሁኖ የተሠራውን የልዕልት ስኂንን ቤት ሰጥተዋቸው ነበርና የታዘዙት ሠራተኞች ቤቱን ያድሱ ነበር።ለአቶሞቢል የሚመች መንገድ አልነበረምና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሠራዊቱን አዝዘው ከማኑኤል ቤተክርስቲያን ጀምሮ እስከ ልዕልት ስኂን ቤት በጥቂት ቀን አፋጥነው የሚያምር መንገድ ተሠራ።መልካም መልካም ድልድዮችም በኖራ ተሠርተዋል፡አንዱን ድልድይ ያሠሩ ቀኛዝማች ወልደዮሐንስ ወልደአብ ነበሩ፡በፍጥነት በማሠራታቸው ምክንያት ፩አቶሞቢል ተጃንሆይ ተሸለሙ። የቀሩትን ድልድዮችና የአፈሩን ድልድል ያሠራ ማዘጋጃ ቤት ነው ይህም መንገድ ብዙ ጊዜ የታሰበበት ይመስላል እንጂ በጥቂት ጊዜ የተሠራ አይመስልም ጃንሆይም በየቀኑ እየተመላለሱ ሠራተኞችን ያተጉ ነበር።ችሎቱም የሚያደርጉት እዚያው ከሚሠራው መንገድ አጠገብ ነበር።

እንግዲህ ወደ ሠርጉ ነገር እንመለስ በዚሁ በሰኔ ፱ቀን ከሌሊቱ ቀደም ብለው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊት እቴጌ መነን ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስና ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፡መሳፍንትና መኳንንት ሊቃውንትና ካህናት በመታሰቢያ ቤተ ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ነበር ከሕዝቡም ብዛት የተነሣ ቦታ አልበቃው ብሎ ለሕዝቡ ማረፊያ ታላቅ ድንኳን ተተክሎ ነበር። ጳጳሳትና ካህናቱ እንደ መጽሐፉ ሕግ የተክሊሉን ሥርዓት ከፈጸሙ በኋላ ሥርዓተ ቍርባኑን አድርሰው ሙሽሮቹ የአንድነታቸውን ምልክት ሥጋውን ደሙን ተቀብለው ሲወጡ እጅግ አማሩ። ይልቁንም ሙሽራይቱ ልዕልት ዘነበ ወርቅ ከአክሊላቸው ጋራ ተባብረው ተፀሐይ ብርሃን ጋራ ተስማምተው ሲአበሩ፡ ሙሽራው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣም ይህ ቀረህ የማይባሉ መልከመልካም ጉልማሳ ናቸውና በሁለቱም መልክ ማማር ሕዝቡ ሁሉ ተደነቀ። ይልቁንም የሰው ሐሳብ ረጅም ነውና ከሁለቱ የሚወለዱ ልጆች እንዴት ያሉ መልከመልካሞች ይሆኑ ይሆን እያሉ ገና የሚገኙትን ሕፃናት የሚናፍቁ ሰዎች ነበሩ።ሥርዓት ሲሆን ጃንሆይና እቴጌ ታላላቅ ወይዛዝርና መኳንንት ሙሽሮቹን አጅበው ወደታላቁ ቤተመንግሥት ገብተው ጃንሆይና እቴጌ በመንበረ ዳዊት ተቀመጡ መንበረ ዳዊቱም አጐበሩም በወርቅና በሐር ያጌጠ ነበር። ሙሽሮችም በወርቅ በወርቅ ወምበር ተቀምጠው ነበር። ወይዛዝሩና መኳንንቱም የዲፕሎማቲክ ሰዎችም በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር። በአዲስ አበባ ከሉት የውጪ አገር ቋንቋ ከሚማሩት ከወንዶችና ከሴቶች ተማሪዎች መርጦ የትምህርትና የጥበብ ዲሬክተር እንደራሴ አቶ ኪዳነ ማርያም አበራ ይዞ ገብቶ ነበርና ሴቶች ተማሪዎች አስቀድመው ገብተው አበባውን እየረጩ ሙሽሮቹን ደስ አሰኙ። ሙዚቃ መንፋት የተማሩትና ሌሎችም ተማሪዎች መዝሙሩን እየዘመሩ በሙዚቃ አስተማሪው በሙሴ ናል ባንድያን እየተመሩ ሙዚቃውን በማሳመራቸው ሰሚውን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙ።ከዚህ በኋላ በሸምፓኝ ጊዜ የፈረንሳዊ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ሚኒስትር በውጪ ጉዳይ ዋና ጸሐፊ በአቶ ወልደጊዮርጊስ አስተርጓሚነት መልካም ዲስኩር ተናገሩ። ከዚህም በኋላ ሸምፓኝ ተጋብዘው የክር ዲፕሎማቲክሰዎች ሁሉ ሙሽሮችንና ጃንሆይን እየመረቁ ተሰነባብተው ከወጡ በኋላ የልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ ፻፶የሚሆኑ መኳንንት በየማዕርጋቸው ተሸልመው እጅ በነሱ ጊዜ ግራዝማች ገረአሴ የሚባለው ጅግና ፎከረ። ምክንያቱም እንደጅግንነቱ መጠን ብልጫዬን ሰው ወሰደብኝ ማለቱ ይመስላል።ወዲያውም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ማለፊያ ጐፈርና ጉሜ ወርቅ ጣፋ ጋሻ ባለጫሜ ጐራዴ ለወጡለት። ከዚህ በኋላ የተሸለሙት ሰዎች እጅ እየነሱ ወጡ። ሙሽሮችም የሙሽራ ልብሳቸውን ለብሰው ወጡ። ጃንሆይና እቴጌ በዘውዱ በዓል ቀን በተቀመጡበት ፬ፈረሶች በሚስቡት

በወርቅ ሠረገላ ተቀምጠው ጕዞ በጀመሩ ጊዜ በግቢ ያለው ሕዝብ ቢያጨበጭብ እየተቀባበለ እስከ አራዳ ድረስ ጭብጨባው ደመቀ ሚዚዎቹና ደንገጥሮችም የተሸለሙት ሽልማት እጅግ የሚያምር ነበር ለሙሽራውም የተሰጡት ፈረሶችና በቅሎዎች ብዙዎች ነበሩ፡፡የተጫኑትም በወርቅና በብር ዕቃ ነበር ወታደሩም ከታላቁ ቤተ መንግሥት ጀምሮ እስከ ፩ኪሎ ድረስ በግራ በቀኝ ተሰልፎ ነበረ። ሙሽሮቹም ሲጓዙ የክብር ዘበኞች የሚባሉት ፈረሰኞች ተሠረገላው በፊት በፊት ሲሔዱ በግራና በቀኝ የተሰለፈው ወታደር የሚገባ ሰላምታ እየሰጠ ያሳልፍ ነበር። እንዲህም ሁነው በከተማው ሁሉ እልል እየተባለ በዓለም ወደቤታቸው ደረሱ ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያም በድግሱ ተጠንቅቀውበት ነበሩና ተቀጣጥሎ በተተከለው ሰፊ ድንኳን ያንን ሁሉ ሕዝብ ደኅና አድርገው በመጋበዛቸው ሕዝብ ሁሉ ተደነቀ በማግሥቱም ዓርብ ብዙ እንግዳ ጠርተው ታላቅ ግብር አድርገው ዋሉ የድግሱም ማማር እጅግ ተደነቀ ተገቢ ሙሽራይቱን ተከትለው ለሔዱት መኳንንትም የሚያስደንቅ ሽልማት ሸልመዋቸው። ይልቁንም ሊጋባ ሀብተሚካኤል የተሸለሙት ሽልማት እጅግ የሚያስደንቅ ነው እንኳን ንጉሥ አገር የሚገዛ ጌታ ያሰየውን ሕዝብ ይቀበለዋል ዘመን ያመጣው ነገር ማለት ወይም ጊዜ የወደደው ነገር ማለት ንጉሡ ወይም አገረ ገዥው የወደደው ማለት ነው። የደግ መሪ ንጉሣችን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጆቻቸውን እንደ መጽሐፍ ሕግ በተክሊል በቁርባን መዳራቸው ለሕዝብ ሁሉ መልካም አርአያ ማሳየታቸው ነውና ይህን ትምህርት ሕዝብ ሁሉ እንዲማረው ተስፋ እናደርጋለን።ለመልካም አስተማሪያችን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ታላቅ ሠርግ

ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትር የክቡር ደጃዝማች አበበ ዳምጠውን ልጅ ወይዘሮ ቀለመ ወርቅን ከተስማሙ ብዙ ቀን አልፎ ነበር ። ይኸውም በሰኔ ፯ ቀን ተፈጸመ። የአኳኋኑም ነገር እጅግ የሚያስደንቅ ነበረ ። በሰኔ ፰ ቀን ሠራዊቱን ሁሉ ሲጋብዙ ውለው ከምሳ በኋላ ወደ ታላቁ ቤተመንግሥት ጉዞ ጀመሩ ። ለማጌጫ የሚሰጠው ብዙ በቅሎና ፈረስ በጥሩ ዕቃ ተጨኖ ጥሩ ጥሩ ቀሚሱን ለብሶ ሲሳብ በወርቅና በብር በሐር ጥልፍም የተሠራው የጌጥ ልብስ በወሳሳ ተይዞ ተይዞ ሲሔድ የከተማማው ሰው ሁሉ እያየ እጅግ ይደነቅ ነበር ልጂቱን እንደአባት ሁነው የሚድሩ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነበሩና በዚያው በተቈረጠው ሰዓት ታላላቆችን መኳንንት አዝዘው የታዘዙትም መኳንንት የውሉን መፈጸሚያ ቦታ አሳምረው አስነጥፈው ወምበሩን በሥርዓት አስደርድረው ቈዩና እንደ ደምቡ የውሉን ነገር ጨርሰው ወደታላቁ አዳራሽ ገብተው ታላቅ ግብር ተደርጎላቸው በታላቅ ደስታ አድረው በማግሥቱም እንዲሁ ታላቅ ግብር ተደርጎላቸው ውለው ሙሽራውና ሚዜዎቹ የነገር አባቱ ከደጃዝማች ይገዙ ታላላቅ መኳንንትና ታናናሽ መኳንንት በየማዕርጋቸው ተሸልመው ከ፮ት ሰዓት በኋላ ወደቤታቸው ጉዞ ጀመሩ ። የነጋሪቱና የጥሩምባው የእምቢልታው የመለከቱ ድምጥ ፀደ ሰማይ የደረሰ ይመስል ነበር።የተከተላቸውም ሠራዊት እጅግ ብዙ ነበር የዕልልታውም ድምጥ እጅግ ከፍ ብሎ ይሰማ ነበር።እንዲሁ ወደቤታቸው በደረሱ ጊዜ የቤታቸው ሹማምት የቤታቸውን ሥርዓት አሳምረው ቈይተዋቸው ነበር።ሹመታቸውን ያስመረቁ ጊዜ ግብር ካደረጉበት ድንኳን አነስ ያለ ድንኳን ተቀጣጥሎ ተተክሎ ነበርና ወዲያው እንደገቡ ለመኳንንቱና ለሠራዊቱ ታላቅ ግብር አደረጉ ። በማግሥቱም ሙሽራይቱን ተከትለው ለሔዱ መኳንንት ለደንገጥሮች ብዙ ሽልማት ሸለሙ ። እንዲሁ የሠርጉ በዓል በደስታ ተፈጸመ ። የመልካም ጋብቻ ያድርግላችሁ። እያለ ብርሃንና ሰላም ለክቡር ፊታውራሪ ብሩና ለክብርት ወይዘሮ ቀለመ ወርቅ ምኞቱን ያቀርባል ።

ሠርግ ።

አቶ አየለ ስብሐት የአገር ግዛት ሚኒስቴር ዋና ጸሐፊ የነጋድራስ ዘውገን ልጅ ከፈይ ዘውገን በሕግ በተክሊል በሰኔ ፰ ቀን አገባ ሕዝቡም እጅግ ይወደዋልና በዚያ ቀን ምንም የሠርግ ጥሪ በየስፍራው ቢበዛበት ወደ እሱ ቤት አድልቶ የሔደው እጅግ ብዙ ነበረ ። ይልቁንም በዚያው ቀን በቤቱ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ በሙሽራው በአቶ አየለ ስብሐት ቤት የልጅ ኢያሱን መያዝ ስለ ሰማ እነዚህ ሙሽሮች ዕድለኞች በመሆናቸው እጅግ ተደነቀ የደኅና ጋብቻ እንዲሆንላቸው ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ይገልጻል ።

ስለ ጋብቻ ምሥጢር።

በዛሬው ወራት ውሥጥ በኢትዮጵያ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በጉባኤ ሙሉ ተክሊል ተደረገ።

ለዚሁም በሙሉ ሥርዓት ተክሊል ለተደረገው መጀመሪያ ዋና ክብር የተቀበሉ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ናቸው ። እለዚህን በሁኑ ወራት ውሥጥ በተክሊል የተጋቡትን እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ። እኔም በዚሁ ብዙ ደስ ብሎኛልና እላንተም የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ክቡራን የኢትዮጵያ ልጆች የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የጋብቻን ሥርዓት ወደፊት የምጽፈውን ቃል እንድትቀበሉት በማክበር እለምናችኋለሁ ።

ዓለምን የፈጠረ እምላክ ጋብቻን ሠርቶታል ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያኑ በተቀደሰው ከ፯ አዕማደ ምሥጢር ቈጥሮታል ።

በሱም በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ወንድና ሴት አንድ ይሆናሉ ልጆችን ለማግኘትና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለማሳደግ ። ጥቅሙም መጀመሪያ የሰውን ጐሣ ለመጠበቅና ለማብዛት ነው በዚሁም ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን ተጋድለውና ድል የሚነሱ የቤተ ክርስቲያን አካሎች ይበዙ ዘንድ ነው ይህም የሆነው በእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው ብዙም ተባዙም ምድርንም ምልዋት ሲል ዘፍጥ ፱ ፩

ሁለተኛ ሁለቱ እርስ በራሳቸው ሊተጋገዙና ሊረዳዱ ነው እግዚአብሔር እምላክም አለ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ

መልካም አይደለም የምትረዳውን አጠገቡም የምትሆን የምትስማማውን ልፍጠርለት ዘፍጥ ፪ ፲፰ ።

ሶስተኛ ሰው ከሥጋዊ ፃኞቱና ከኃጢአት እንዲጠበቅ ነው ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው ግን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን ተናግሬያለሁ ብሏል ኤፌ. ፭ ፴፪

ሥልጣን ያለው ካህን በግልጥ በሚሠራው ሥራ ምክንያት ኢየሱስ ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን አንድ እንደ ሚሆን ምሳሌ ሁሉ የእግዚአብሔር ጸጋ የባሕርይ ጋብቻ ወደ ተቀደሰው ታላቅ ምሥጢር ትለውጠዋለች ። ስለዚሁም የቤተ ክርስቲያን አባቶች በፍትሐ ነገሥት ፱፳፬ አንቀጽ ምዕራፍ ፭ መጅ፩ የመጋባት ማሠሪያ ግን አይሆንም አይፈጸም ም ክህናት ከሌኖሩ ጸሎትም ካላደረጉበት ቍርባንም ካልሰጧቸው በተክሊል ጊዜ ሁለቱ የሚዋሐዱበትና አንድ ሥጋ የሚሆኑበት ጌታችን እንደተናገረ ምስጋና ይገባዋልና ያለዚያ መጋባት አይቆጠርላቸውም ሴቶቹን ለወንዶቹ ወንዶቹንም ለሴቶች የሚገባ የሚያደርግ ጸሎት ነውና የእግዚአብሔር ጸጋ በዚህ ምሥጢር እንደሚመጣው ቃል ትሠራለች መጀመሯ የጋብቻን መተሣሰር ትቀድሳለች የመንፈሳዊ መተሳሰብ ታደርገዋለች ኢየሱስ ክርስቶስም ከቤተ ክርስቲያን አንድነት እንደዚህ ነውና ስለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል መጋባት የከበረ ይሁን መኝታውም ንጹሕ ዕብ ፲፫ ፬ ። ሁለተኛ የጋብቻ መተሣሰር ላይቋረጥ ለዘላለም ትረዳለች እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ለመለያየት አይችልምና ማቴ ፲፱ ፮ ።

ሶስተኛ በጽሬትና በንጽሕና በቅድስና የተፈጸመ ፍቅር ታደርገዋለች ስለዚህም ቅዱስ አጎስጢኖስ በጋብቻ የሚገኝ በጎነት ነገር ሁሉ መልካም ነው ሲል ተናግሯል ። እንደዚሁ ሁሉ ሐርተሊያኖስ የጋብቻን ሀብት እንደምን አድርገን ለመተርጐም ይመቸናል ቤተክርስቲያን የምታስበውን ቍርባን የሚጸናውን በረከት ብለዋል በፊታችን በግልጽ ሥርዓቱ የተፈጸመው ታላቅ ምሥጢር ይህ ነው ወደፊት የሙሽሮችን ሕይወት እግዚአብሔር የምሥጢሩን ሥራ የተፈጸመ እንዲያደርገው ምሉ ተስፋ እናደርጋል ።

የኦርቶዶክሳዊን ሃይማኖት ጠባቂ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጥላ ውሥጥና በኢትዮጵያ መንግሥት ሊቀ ጳጳስት አቡነ ቄርሎስ ጸሎትና በረከት ወደፊትም የሚያገቡ ሰዎች ሁሉ የልዑል አልጋ ወራሽን መንገድ እንዲከተሉና በሃይማኖታቸው እንዲቀኑ እንመኛለን ጥቂት አርሾሊጡን ሁሉ ያመጣል ተብሎ ተጽፎአልና ገላት ፭ ፱።

በአባታችን አቡነ ቄርሎስ ግቢ የቅዱስ እንጦንዮስ ቤተ ክርስቲያን ቄስ ማርቆስ ።

ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው ።

ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው እየተባለ ሲተረትና የሚሩትም እሳት ይፈጃል እየተባለ ሲነገር ከአፈ ጩዋ የተገኘ ተረት ይመስለኝ ነበር አሁን ግን መጽሐፍ ስመለከት ከቀድሞ የተጻፈ ሆኖ ስላገኘሁት ያልተረዱት ሰዎች ቢኖሩ ልብ አድርገው እንዲረዱት በማለት ከዚህ ቀጥዬ ጻፍሁት ምሳ ፱ ምዕራፍ አቤሜሌክ የይሩብ በዓል ልጅ ወደሴኬም ወደናቱ ወንድሞች አገር ሒዶ ሴሎቹ ሰዎች ከሚገዟችሁ እኔ ያጥንታችሁ ፍላጭ የሥጋችሁ ቁራጭ በናንተ ላይ ጌታ ብሆን (ብነግሥ) ይሻላችኋል አሁንም ለሴኬም ሰዎች ማለት (ላድመኞች) ንገሩ እናንተም ፍቀዱ አላቸው እነሱም እሱን ለመከተል ልባቸውን አዘነበሉ ለሴኬም ሰዎችም (በሉቲከን) ነገሩ ከበዓል ብሪትም ቤት ማለት (በምክር ፬ ከሆነ ባለጠጋ) ፸ ቢትቃልብር ወስደው ሰጡት በዚያውም ምናምኖችንና ተግባረ ፈቶችን ሰዎች ገዝቶ አስከትሎ ሒዶ ያባቱን ልጆች ሰባውን ወንድሞቹን በአንድ ድንጋይ ላይ አሳርዶ እነዚያኑ በገንዘብ የተገዙትን የሴኬምን ሰዎች (አድመኞችን) ይዞ ሒዶ በንጉሥ ዛፍ ሥር አነገሡት ከዚህ በኋላ ከወንድሞቹ መታረድ ያመለጠው ታናሹ ዮናታንም በተራራው ራስ ላይ ወጥቶ ቃሉንም ከፍ አድርጎ ጮሆ አሰምቶ እንዲህ ሲል ተናገረ እናንተ የሴኬ ምሰዎች (አድመኞች) እናንተንም እግዚአብሔር እንዲሰማችሁ እኔንም ስሙኝ ዛፎች ተከማችተው (ተሰብስበው)ንጉሥ በላያቸው ሊያነግሡ ሔዱ መጀመሯም ወይራን በላያችን ንገሥ አሉት ወይራም እንዴት አድርጌ ቅባቴን አማልክትና ሰዎች የሚያከብሩትን (ቀ ኃ ን) ትቼ በናንተ በዛፎች ላይ ልሰፈፍ (ልንገሥ ይኸስ አይሆንልኝም አላቸው ሁለተኛም በለስንና በላያችን ንገሥ አሉት እሱም በውኑ እንዴት አድርጌ ጣዕም ያለውን ጣፋጭነቴንና መልካሙን ፍሬዬን ቀ ኃ ን ትቼ በናንተ በዛፎች ላይ ልሰፈፍ (እነግሣለሁ) ይኸስ አይሆንልኝም አላቸው ፫ኛም ወይንን መጥተህ በላያችን ንገሥ አሉት እሱም እንዴት አድርጌ አምላክንና ሰውን ደስ የሚያሰኘውን ጠጄን (ቀ ኃ ን) ትቼ በናንተ በዛፎች ላይ እነግሣለሁ ይኸስ አይሆንልኝም አላቸው ፬ኛም እሾህን መጥተህ በኛ ላይ ንገሥ አሉት እሱም በውነት እኔን በናንተ ላይ ልነግሥ ትቀቡኝ ዘንድ ተፈቅዳችሁ ኑ ከጥላዬ በታች አረፉ እንዲህም ባይሆን እሳት ከሾሁ ውሥጥ ይውጣ የሊባኖስን ዛፎች (ራሳችሁን) ያቃጥላችሁ አላቸው አሁንም አባቴ (ንጉሤ ቀ ኃ) የላንዳች በደል እናንተን ከምድያን እጅ (ማለት ከችግር) ስላወጣና ተጋድሎ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶ ሀገሪቱን ነፃ ባወጣ ፈንታ አቤሜሌክን ለማንገሥ ፈቅዳችሁ ባባቱ ቤት (በጌታዬ) ተነሥታችሁ ሕዝብ ለማጥፋት ስለፈለጋችሁ የውነትና የቅንነት አምላክ እንደሥራችሁ መጠን ይስጣችሁ በሥራችሁም አከፋታችሁ እንደሆነ እሳት ከአቤሜሌክ ትውጣ ታቃጥላችሁም ብሎ ተናገረ ይላል ይኸውም ነገር ይፈጸም ዘንድ ጥቂት ጊዜ ተቆየ በኋላ አቤሜሌክ እሳት ይዞ መንደሩንና ሕዝቡን ሲአቃጥል እስከ ሞት ድረስ ያገኘውን መከራና የተደረገውን ነገር ሁሉ እስከ መጨረሻው እንዳልጽፈው ጊዜ ሳላገኝ ቦለቀረሁ ሰዓት ባጋጠመኝ ጊዜ እጽፈዋለሁ ብዬ ተውሁት አሁን ላስፈለገኝ ለተረቱ መጓጠም ቢሆን ሥራ ለሠሪው ያሰኘው አላይ እንደተጻፈው ቃል ሳትበደሉ አቤሜሌክን ስለፈለጋችሁ የውነትና የቅንነት አምላክ እንደሥራችሁ መጠን ይስጣችሁ ለተባለው ነው እሾህ ላጣ-

ሬው ያሰኘው አሾህ እኔን በላያችሁ ለማንገሥ ከፈቀዳችሁት በጥላዬ እረፉ እሳትም ከኔ ይውጣ ያቃጥላችሁም ለተባለው ነው የሚሩት እሳት ይፈጃል ያሰኘው። ዛፎች በገዛ ራሳቸው እሾህን በላያቸው ለማንገሥ ፈልገው ለሾሁ ሲባል እነሱም አብረው መቃጠላቸውን መናገር ነው ነገር ግን እነዚህ ግብረ መሬርነት ያላቸው ዛፎች ከያለበት ተጠራቅመው መልክም ጣዕም ያላቸውን ደጋጎችን ዛፎች ግብረ አበር አድርገው ለማጥፋት መነሣታቸው እጅግ ያሳዝናል እኔም እነዚሁ ክፉዎቹ ዛፎች መጨረሻውን ምን እንደሆኑ መምህራኖችን ብጠይቅ ሥራቸው (እንጀታቸው) አሮ ሚፋቸው (ከንፈራቸው) ተንጨብሮ አበባቸውና ፍሬአቸው ረግፎ በከንቱ ደርቀው ቀሩ አሉኝ እነዚያስ ደጋጎቹ ዛፎች እንደምን ሆኑ ብዬ ብጠይቅ ወይራም ቅባቱን አማልክትና ሰዎች የሚያከብሩትን (ቀ ኃ ን) ይዞ በለስም ጣፋጩንና መልካሙን ፍሬ (ቀ ኃ ን ይዞ ወይንም እምላክንና ሰውን ደስ የሚአሰኘውን (ቀ ኃ ን) ይዞ እነሱማ ምን አለባቸው እምነት የሚባለውን የመስኖ ውሀ ጧት ማታ እየጠጡ ተድላና ደስታ የሚባሉትን ለውዝ ገውዝ አብበው አፍርተው ይኖራሉ አሉኝ እኔም እነዚያ ክፉዎቹ ቅጠላቅጠሎች ዛፎች በከንቱ ረግፈው ለመቅረት አሁን ክፉ ሐሳብ ለምን አደረባቸው በማለት እየገራረመኝ ሰነበትሁ ነገር ግን ኅዘኑ ላይለቀኝ ተድላው አያምልጠኝ የሚባለው ተረት እንደነዚሁ እላይ እንደተጻፉት ተረቶች ከመጽሐፍ ይገኝ እንደሆን ብዬ እያገላበጥሁ ብፈልግ ለጊዜው ባክኜ ባክኜ አጣሁት ለኋላው ግን ሳይገኝ አይቀርምና ወደፊት እንጽፈዋለን ዘበ እዝን ሰሚዐ ለይስማዕ ።

ትስብእት ወልድ አግዴ ።

የጥያቄ መልስ ።

በብርሃንና ሰላም በ፳፬ኛ ቍጥር በ፻፹፯ ገጽ አቶ ሞገሴ ከጠየቁት ፩ኛው ጥያቄ እንዲህ ይላል።ትምህርት በራሱ ምንድር ነው ? ። ትምህርት በራሱ ከመጀመርያ አንድ ቀዋሚ ሁኖ ተወስኖ የተገኘ ነገር አልነበረም።ግን ከብዙ ዘመን በኋላ ታርሞ ለሰው ወገኖች ሁሉ ተሰጠ ። የትምህርት ዓይነተኛ ስሙ ኑዛዜ ነው ልለው እደፍራለሁ ። በድሮ ዘመን ፊደላት አልተገኙም ነበሩና ከፊደላት በፊት የነበሩ ሰዎች ሐሳባቸውና ኑዛዜያቸውን በብዙ ችግር ለወገኖቻቸው እንዲያመለክቱ ይጥሩ ነበሩ ። ጥረታቸውም አጥርቶ ገልጾ በማያስረዳ ነገር ስለሆነ ማስተዋሉ ብዙ አስቸገረ ። ብዙ ነገርም ሳይታወቅ ቀረ ። ከብዙ ዘመን በኋላ ግን ባሰው ትጋትና በእግዚአብሔር ቸርነት በምድር ካለው ጥበብ ሁሉ የሚበልጥ የፊደላት ቅርጽ ተገኝና ሐሳብን ሁሉ ለመግለጽ የሚበቃ መሣርያ ሆነ ።

በትምህርት የሚወረሰው እውቀት ከልዩ ልዩ ሰዎች ባሕርይ ይመነጫል ። እያንዳንዱ ሰው ካራክተር (የጠባይ ዓላማ) አለው ። በተለየም ባንዳንድ ሰዎች በብዙ ነገር ጥቅም ብቻ የሚያስገኝ ጠባይ አላቸው ። እነሱ ራሳቸው ይኖሩበታል ሰዎችንም ይመክሩበታል ። ደግሞም ለሚመጣው ትውልድ መሪ እንዲሆን ጽፈው ይተውታል ። ባንዱ በሽተኛን መመርመርና በሽታን ለመፈወስ ምን እንዲያስፈልግ ስጦታ አለው ። በሌላውም መሬት እንዴት እንደምታፈራና እንዴት ባለ መንገድም ማፍራት እንዲሆንላት ። እንስሶችም እንዴት እንዲረቡ በጥሩ ለማርባትም ምን እንዲያስፈልግ፣ ባሕርያትንም መመርመር ። በፖለቲካም ማስተዳደር የቍጥር ዓይነት ቀጥታን መመልከት የጦር ስልት ላገር መቅናት የባሕርይ ደግነት የሰውንም ባሕርይ በመመራመር እውቀት ሌላም ይህንን የሚመስል ሁሉ ተሰብስቦ በመጽሐፍ ተጽፎ ለሰዎች ተሰጥቶ ሲነገር ትምህርት ይባላል ትምህርትንም ለመቀበል ባሕርይ ያስፈልጋል ። ባሕርይ ማለት ጥሩ ብረት ማለት ነው ትምህርት ግን መሳል ነው እንደዚህ በመሰለ መንገድ ሁሉ ትምህርት በራሱ ምን እንደሆነ ይገለጽ ይመስለኛል ስል የወዳጅነቴን መልስ አቀርባለሁ ። ክፍለ እግዚእ ይኅደጎ ።

ሹምሽር ።

ፊታውራሪ ገሠሠ በለው የደጃዝማች በለው ተክለሃይማኖት ልጅ ደጃዝማች ተብለው ለደጃዝማቾች የሚገባውን የማዕርግ ሽልማት ተሸልመው ላንቃ ለብሰው ቀድሞ የያዙትን አገር ሊበንን እንደያዙ አነሴንና አነብሴን ጐንቻን በራስ ኃይሉ አገር በነበረው በሙሉ የጦር እንደራሴነቱን ጨምረው በነጋሪት ተሾሙ።

ብላታ መኰንን በመጀመሪያ ልጅ ኢያሱን የያዘ ቀኛዝማች ተብሎ ቀድሞ ምስሌኔ ሁኖ ይገዛው የነበረውን አገሩን ሽመለ ገበ የሚባለውን ተሾመ ።

አብረዋቸውም ከመጡ ዋና ዋናዎቹ እስከ ፭ አምስት የሚሆኑ ሰዎች እንደ የማዕርጋቸው ካባ ቀሚስ ለምድ ሙሉ የሰልፍ ልብስና ፶፫ ጠመንጃ ከነጥይቱ ፲፰ በቅሎ አሥር ፈረስ ሽልማት ተቀበሉ ደግሞ ከዚህም በቀር ለስንቃቸው ለደጃዝማች ገሠሠ በለው ፪ሺ ብር ለተከታዮቻቸው ፫ሺ ብር በድምሩ ፭ሺ ብር ተሰጡ ።

ለእግዚአብሔርና ለመንግሥት በቅን ያገለገለ ሰው ዋጋው እንዳይቀርበት እርግጥ መሆኑ በነዚህ ሰዎች ታወቀ እነዚህም ሰዎች መርማሪዎች እንደ እምታውቁት ሊፈስ ተዘንብሎ የነበረውን የኢትዮጵያን ደም ያቀኑ ናቸውና በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፊት ሞገስ አግኝተው የድካማቸውን ዋጋ በማግኘታቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ደስ ሊለው ይገባል።ደጃዝማች ገሠሠ በለውም አሁን የተሾሙበት አገር አባታቸው ደጃዝማች በለው በመጀመሪያ ደጃዝማች ተብለው የተሾሙበት አገር ስለሆነ ደስታቸው እጥፍ መሆኑ አይጠረጠርም ። እንኳን ደስ አላችሁ በዕድሜአችሁ ልክ ከመንግሥት ፈቃድ አያውጣችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ይገልጻል ።

በጋብቻ ነገር ስለተጣሉ ተማሪዎች የመሰለንን ፈርደን እናቀርባለን

ወንድማችን አቶ ትስብእት ወልድ አግዴ መጋቢት ፳፱ ቀን ፳፬ በቍጥር ፲፬በታተመው ብርሃንና ሰላም የደሃ ልጅ ስትሆን በመልክዋና በጠባይዋ ለተመሰገነችው ልጃ ገረድ ከሶስቱ

አዋቂዎች ማንኛው በእውቀቱ በልጦ እንዲያገባት ፍረዱ ብለው ያቀረቡትን ጥያቄ አ፣ ተን ከሁን በፊት ሐሳባቸውን በፍርድ ለገለጹ ወንድሞቻችን መቃወም ሳይሆን እኛም ከዚህ በታች መስሎ የታየንን ፍርድ በጭሩ እንገልጻለን ።

እውነትም እነዚህ ሶስት ተማሪዎች ሁሉም ተምረዋልና የሶስቱንም ዕውቀት ረቂቅና ጥልቅ ቢሆን ላዋቂዎች አዋቂ ለፈላስፎች ፈላስፋ እንዳላቸው እውቀን ከሶስቱ ብልሆች አንድ ብልሀ በብልሀነቱ ብልጫ መርጠን መልከ መልከምዋን ቈንጆ ያግባ ብለን እንድ"ፈርድ የሁሉም መምህር ብርሃንና ሰላም ባዶ ትስብእት ወልድ አግዴ አስታዋሽነት አስገድዶናልና በላይኛው መስመር ቀኑንና ቁጥሩን ለይተን በመለከትነው ብርሃንና ሰላም እንዳነበባችሁት ሁሉ ከሶስቱ ተማሪዎች አንደኛውን ተማሪ ጋራና ተራራ ደመናና ጨለማ ሳይጋርደው ዓለሙን ሁሉ ባንድ ጊዜ የሚያሳይ ዕውቀት ለሱ ሲገለጽለት ዓለሙን ሁሉ ባንድ ጊዜ ለማየት ከሁን ቀደም ለፈጣሪ ከልሆነ በቀር ለፍጡር ተገልጾ ታ፣ው ሲባል ከቶ አልሰማንምና የዚህ የተማሪ ዕውቀት በዚህ ፡ተገለጸለት ዕውቀት ውስጥ ምልዓት ብቻ ነው እንጂ ሕፀፅ የለበትም ብንል ጸያፍ አይሆንብንም ።

ለሁለተኛውም ተማሪ ሰው ከሞተ በኋላ ሶስት ሰዓት ሳይሞላው ከሞት የሚያድን ዕውቀት ሲገለጽለት ከዚህ ከተወሰነው ሰዓት አልፎበት ያገኘውን ምውት ሊያድን አለመቻሉን የተወሰነውን ሰዓት እያስረዳን ያሁኑም ምውት አነሳስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር አልዓዛርን ከመቃብር ሲያስነሣ ሳለ እምድኅረ ጌዐ ወአፀየ ብሎ እንዳስረዳን ሁሉ ኃይል አላገኘንበትም በማለት የዛሬም ዘመን ሐኪሞች በዚህ ነገር ተጠራጥረው ሰው ከነፍሱ እንዳይቀበር ሲሉ ከሞተ በኋላ ሐያ አራት ሰዓት ሳያልፍበት እንዳይቀበር መከልከላቸውን የተማሪውን ዕውቀት መመዘኛ አድርገን ይህ የተገለጸለት ዕውቀት ሕፀፅ የተፈረቀው ነው ለማለት እንፈረም ።

ሶስተኛውም ተማሪ ያሥሩን ዓመት መንገድ በ፭ደቂቃ የሚያደርስ ዕውቀት ስለተገለጸለት ለጊዜው በዛሬ ዘመን ተሰርተው ከሚበሩ አይሮፕላኖችና በኤሌክትሪክ ኃይል ከሚራወጡ የብረት ተንቀሳቃሾች (ባቡሮች) የበለጠ ፍጥነት በማግኘቱ የሚገባውን ክብር እየሰጠን ዓለም በሙሉ በእግር ለመዞር ባጭር ግምት ፳፻ዘመን የሚያስኬዝ ቢሆን ይህነን መንገድ ለመሄድ ፬፻፺ደቂቃ ወይም ፰ሰዓት ከ፲ደቂቃ ሊያስፈልገው ነውና ይህም ሶስተኛው ተማሪ ያገኘውን ዕውቀት ሕፀፅ ያለበት ሆኖ ስለታየኝ ሐሳቤን ወደተመልካቹ እመልሳለሁ ።

በዛሬ ዘመን ያሉ መነጽሮችና መነጽርን የሚመስሉ መመልከቻዎች ዓለምን ሁሉ ለማሳየት ባንድ ጊዜ ቀርቶ በሥር ዓመትም ቢሆን አልተቻላቸውም ይህም ተመልካች የሆነ ተማሪ ባንድ ጊዜ የሚያየው ያሥሩን ዓመት መንገድ ብቻ ሳይሆን አኃዝያን ዓለም ሥላሴን ይመስላል ባንድ ጊዜ መመልከቱ ዓለምን በመላዋ ስላየ ከሁን ቀደም ለፍጡር ያልተገለጸለት ሥራ ተገልጾለታልና ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ ሊባል ነው የሚገባው የተማሪውም ብልጫ አስቀድሞ መሞቷን አይቶ በመንገሩ ብቻ ያደደለ የሁለቱ ሥራ ከሁን በፊት የነበሩ ጠቢባኖች ጀምረውት የቈየ ሥራ ሲሆን የሱ ጥበብ ከፈጣሪ በቀር ፍጡር ያልሠራው ሥራ ሁኖ ተገኝቶለታልና በሁሉም ነገር እሱ በልጠዋቸዋል መልከ መልካምዋን ቆንጆ ያለ ቅርታ ረአዩ ኀቡዓት የሆነ ተመልካች ሲያገባት ይታየኛል ስል ፈርጃለሁ

ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አኩስም

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ከ፲ዓመት ጀምሮ እስከሁን ድረስ ከሃይማኖታችን ተለይተው ከቤተ ክርስቲያናችን ወጥተው ወደ ቡርስታንቶች ሃይማኖት መግባታቸውን አስታወቀው የሚኖሩ ሰዎች የካቲት ፲፰ቀን ቀርበው እንመለሳለን ቢለኝ ጉባኤ እየሰማችሁ ቈዩና በጉባኤ እቀበላችኋለሁ ብዬ አቆይቻቸው ነበር አሁን ግን ግንቦት ፲፯ ቀን የረከበ ካህናት ዕለት በትግሬ አውራጃ ያሉትን ገዳማት አድባራትን ጠርተን እንመለስ ያሉትን ሰዎች እንዳይደክሙ አምለን አስገዝተን ስለተመለሱልን ከመለየታችን ፩መንገድ መሆናችን ደስ ብሎን ሕዝቡ በዕልልታ ሊቃውንቱ በማኅሌት ጃንሆይን እየመረቅን ፈጣሪያችንን እያመሰገንን ጉባኤ አድርገን ውለናል የተመለሱትም ሰዎች በእስመራ የነበሩ ኣለቃ ተወልደ መድኅን ፣ አድዋ የነበሩ ጕበዚ ጕሹና አለቃ ገዛኸኝ ፣ ወልደ አረጋይ አብርሃ ይባላሉ። የሚመስላቸውም ብዙ ነበሩ ይህነን ያደረገ የጃንሆይ ሁብት ነውና ሁሉ እንዲሰሙት አመለክታለሁ ።

አቡነ ይስሐቅ ።

የሚሸጥ አቶሞቢል ።

ባለ መስተዋት ጥሩ አቶሞቢል
የሥራና የእርሻ አቶሞቢል ።
አዲስ ላስቲክም ይገኛል ።

ፎርድ

ስለሁሉም ነገር ኀላፊነቱ
በኛ ላይ ነው ።

ዋናውን አ ቤስን ጠይቁ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቊረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመንብኝት ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል እስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ነ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች

በማክበር ያስታውቃል። ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ባለ ፋብሪካው አሰናጂ ባዚል እስላኒዲስ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ

ይህ ግሩም የሆነመጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

አለም

ALEM

ባያይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት ይገኛል ።

ODEON

ዓለም ሱቅ በየዓይነቱ የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሽከላ ይገኛል።

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ገብሬል።

ፔር ዳኔይ።
አቦካት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሙሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም ቆአቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማስታወቂያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

☞ የሚከራይ ። ☜

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፳፰
8me ANNE. № 28

ሐሙስ ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 7 JUILLET 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሴቶች ተማሪዎች ዕድል ።

የእቴጌ መነን ተማሪ ቤት በሰኔ ፲፰ ቀን ስለ ክረምት ዕረፍት ለማድረግ የሚዘጋበት ቀን ነበርና በዚሁ ቀን በትምህርታቸው የበለጡ ተማሪዎች ሽልማታቸውን ሲቀበሉ ለማየት የመጡ ሰዎች ብዙ ነበሩ ። ከታላላቆች ሰዎችም ጥቂቶችን እንጽፋለን ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ሊቀጳጳሳት፤የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋወሰን። ከወይዛዝሩም ልዕልት ዓፀደ አስፋው፥ ልዕልት የሻሽ ወርቅ ይልማ፥ ልዕልት ተናኘ ወርቅኩበርት ወይዘሮ አሰቴር መንገሻ ሌሎችም ስማቸው ያልተጻፈ ብዙ ሰዎች ነበሩ።በመጀመሪያ ወይዛዝርና መኳንንት በተቀመጡ ጊዜ ዲሬክቴሪቱ የሚከተለውን ዲስኩር በፈረንሣዊ ቋንቋ አነበቡ። በአማርኛ የተተረጐመውን ጽፈንላችኋል ።

ልዑል ሆይ

የእቴጌ ተማሪ ቤት ተማሪዎች፥አስተማሪዎች፤ሠራተኞችም ለመጀመሪያ ጊዜ ሽልማት የሚሰጥበት ቀን ተሰብስበው በልዕልናዎ ፊት በመቆማቸው ታላቅ ክብርና ኵራት ሁኖ ስለተሰማቸው የጠለቀውን ምስጋናቸውን ለማቅረብ ይጣደፋሉ።

ካንድ ዓመት ሥራ ይበልጥ ከሠራን ወዲህ የተገባነን ለዕረፍታችን ከምናስበው ይልቅ በሥራችን ደስ ያለን ደስታ ይበልጣል። ይህም ተማሪዎቹ በገዛ ራሳቸው መጣጣርና ብርታት በሥራቸው መበርታታቸውን መመስከር ግዴታ አለብኝ

ጀማሪዎቹ በሚያታክተው ፊደል የፈረንሳይ ቋንቋና ሒሳብ መሠረት የሆነውን፤ሲማሩ፥ በትምህርታቸው ከፍ ከፍ ያሉት ተማሪዎች ጠንከር ያለ ትምህርት ለመማር ጀማመሩ ።

በቀጥታ በትምህርት ፕሮግራም ያለውን ሳልዘረዝር እኔው ራሴ በምወስነው በፈረንሳይ አገር ከሚማሩት የዓሥር ዓመት ዕድሜ ካላቸው ልጆች ያንሱ አይመስለኝም ።

እንዳንዶችስ እንኳ በዕድሜአቸውና ከዚህ በፊት ባገኙት እውቀት ምክንያት በትምህርታቸው በጣም በርትተው ላስተማሪዎቻቸው በጣም ደስ አሰኙ ።

ለባልንጀሮቻቸው እንደ ታላላቅ የተወደዱ እኅትማማቾች የሆኑት እኛም ብዙ የምናፈቅራቸው የነበሩ የተለዩን ጊዜ በጣም አዘንን- የድካማችን ፍሬ መልካም ባለቤቶችና እናቶች ለመሆን የበቁ እንዲሆኑልን ነው። የእቴጌ ተማሪቤት በጃንሆይና በግርማዊት እቴጌ ደግነት ሲከፈትላቸው ለሚመጡ የሴቶች ትውልድ ትልቅ እርዳታ መሆኑን ተማሪዎቹ ማሰብ ይገባቸዋል ።

ከትምህርቱ አካሄድ ሌላ ደግሞ ልዩ ልዩ የዕዳትና የምቾት ነገር ለነዚሁ ለተወደዱት ሕፃኖች የተደረገላቸውን ማመልከት እፈቅዳለሁ በየክፍሉ የተተከለው የወሃ ባምቧ፥ የገላ መታጠብያ ወሃ፥ የኤሌክትሪኩ መብራት በትክክል በመሠራቱ ብዙ ችግር አላገኘንም ።

የምግባቸውም አኳኋን ሁሉ በትክክል የተዘጋጀ ነው። ለጧት ቍርሳቸው፤ለምሳቸው፤ለ፲ ሰዓት ሻያቸውም እንደፈረንጅ ይመገባሉ። ማታ ደግሞ እኛ ዘንድ ሳይመጡ በቤታቸው ይመገቡት የነበረውን ያገራቸውን ምግብ ይመገባሉ ።

የተማሪዎቹ ቍጥርና የተማሪ ቤቱን መስፋፋት ለልዕልናዎ ማመልከት ደስ ይለኛል። ልጆቻቸውን አደራ ብለው የሰጡን ቤተ ሰቦች ብዙ ናቸው ለዚሁም እያመሰገናቸው በሙሉ ኃይላችን ለልጆቻቸው እንደምንደክምላቸው እናረጋግጥላቸዋለን። በዚህ ዓመት በመዝገብ የተጻፉት ተማሪዎች ቍጥራቸው ስድሳ ነው ከነዚሁ ፲፯ አዳሪዎች ፲፩ በ፮ ሰዓት ምሳ የሚበሉ ፴፪ ተመላላሾች ናቸው።የተማሪ ቤቱ ሠራተኞችም ይልቁንም የተማሪ ቤቱ ዋና ሹም ባላምባራስ በየነና አስተማሪዎቹ ልጆቹን በሚገባ በብዙ ጥንቃቄ በመልካም አስተዳደግ ነው የያዟቸው ።

ለክቡር የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር ለመላከ ሕይወት ወልደ ሐና፤ለክቡር ዋና ዲሬክተር ለብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉና ለትጉህ ምትካቸው ላቶ ኪዳነ ማርያም አባራ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እነሱም ይህ ተማሪ ቤት ከተከፈተ ገና ፩ዓመት ሳለ ማለፊያ አካሄድና የደስታ ምንጭ ሁኖ እንዲራመድ በተሰጣቸው መንገድ ሁሉ ተጣጥረውለታል ።

ዛሬ የግርማዊት ተማሪ ቤት ተማሪዎች ሽማልት በሚቀበሉበት ቀን ከኛ ጋራ ደስታችንን ለመካፈል ብለው እዚህ ለተሰበሰቡ ለልዑላንና ለብፁዓን ጳጳሳት፥ ለክቡራን መኳንንትና ለወይዛዝር ልዩ የሆነውን ምስጋናዬን እቀርብ ዘንድ ልዕልናዎ እንዲፈቅድልኝ እለምናለሁ ።

ልዕልናዎ የጠለቀውን የከበረ ምስጋናችንን እንዲቀበሉልን እየለመን እግዚአብሔር ለልዕልናዎ ረጅም ዕድሜና ተድላ ደስታም ጭምር ያልተለየው መንግሥት እንዲያደርግልዎ ለመላ ኢትዮጵያ መልካም ዕድል እንዲሆንላት እየተመኘሁ ነገሬን እወሳናለሁ ።

ቀጥሎም አቶ ኪዳነማርያም አበራ የትምህርትና የጥበብ ዲረክቴር እንደራሴ የሚከተለውን ዲስኩር አነበበ ።

ልዑል አልጋ ወራሽ ሆይ ።

ወንዶቹ የተማሩ ሲሆኑ እንዲስማሟቸው የተማሩ ሴቶች ያስፈልጓቸዋል ብለው ግርማዊት እቴጌ ልክ የሌለው ገንዘባቸውን አፍሰው ይህን ተማሪ ቤት በመክፈታቸው ትምህርት የሚወድ ሰው ሁሉ በሙሉ ልቡ እያመሰገነ ይመርቃቸዋል ይህ ተማሪ ቤት ከተጀመረ አንድ ዓመት ሁኗል ። ስለሆነም በግርማዊነታቸው እርዳታና በዲሬክትሯ በማዳም ጋሪኩይክስ እንዲሁም ባስተማሪዎቹ ብርታት የተገኘው ፍሬ የብዙ ዓመት ይመስላልና ግርማዊት እቴጌን በጣም ደስ ይበላቸው ። ስለዚህ ለክቡር መልአከ ሕይወትና ሌት ተቀን እየሠሩ ተማሪ ቤቱን ሁሉ ላሠሩ ለክቡር ብላቴን ጌታ ሣህሌ ምስጋና ይገባቸዋል እንዲሁም የእቴጌ ተማሪ አድሚኒስትራቶር ባላምባራስ በየነ አመሰግናቸው ዘንድ ይገባኛል ይህ ተማሪ ቤት ገና በመጀመሪያው እንዲህ የሆነ ብዙ ዓመት ከሠራ በኋላ ለመላው ኢትዮጵያ የሚጠቅም ፍሬ እንደሚሰጥ ጥርጥር የለውም ። ሴት የወንድ ደጋፊ ስለ ሆነች ወንድ አለሴት ሕይወት አለው ለማለት አይቻልም ስለዚህ ሴት የወንድ ዋና ምሰሶ ከሆነች እንደባልዋ የተማረች ልትሆን ይገባታል ይልቁንም ሕፃናትን የምታሳድግ ሴት ናትና በጣም ልትማር ያስፈልጋታል ሴት የተማረች እንደሆን እንደወንድ ላገር የሚጠቅም ልዩ ልዩ ጥሩ ሥራ ለመሥራት ትችላለች ያልተማረች እንደሆነች ግን አንድም ነገር ስንኳ ለመሥራት አትችልም ስለዚህ ግርማዊት ይህን ሁሉ አስበው ይህን እንዲህ ያለ ተማሪ ቤት በመክፈታቸው ሴቶቹ ሁሉ እያመሰገኑ ለዘለዓለም እንደሚያስቧቸው ጥርጥር የለውም ሐዋርያ ጳውሎስ በሁለተኛው የጢሞቴዎስ መልእክቱ በምዕራፍ ፬በቁጥር ፯እንደጻፈው ግርማዊነታቸው መልካም ገድል ተጋደሉ ሩጫቸውንም ጨረሱ ሃይማኖትንም ጠበቁ እንግዲህም ያጸድቅ ፈራጅ እግዚአብሔር በዚያች ቀን የሚሰጣቸው የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶላቸዋል ለማት ቻልን ።

ግርማዊት እቴጌ የጀመሩት ሥራ ፍሬ አፍርቶ ይህን መንገድ መከተል የሚፈልጉ ሰዎች እንዲገኙ ተስፋ እናደርጋለን ከልተማሩ መኰንን አለና የኢትዮጵያ መኳንንትና ሕዝብ ለትምህርት እንዲተጋ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊት እቴጌ መንገዱን ጠርገውልናል ስለዚህ ልዑላንና ክቡራን መኳንንት ይህን መንገድ ተከትለው በየገራቸው የወንድና የሴት ተማሪ ቤት እንዲከፍቱ ሞላው ሕዝባችን በተስፋ ይጠባበቃል አገሩን ለመጥቀም ነፍሱን ለማዳን የሚፈልግ ሰው ገንዘብን አያስብም ገንዘብን ካላሰበ ተማሪ ቤት እንዳይከፈት የሚያግደው ምንድን ነው? በዚህ ዓለም ችግርና ጭንቅ አይጠፋም ነገር ግን ችግሩንና ጭንቁን አሸንፎ ላገርና ለነፍስ የሚጠቅም ሥራ መሥራት ያስፈልጋል ያን ጊዜ በራእየ ዮሐንስ እንደተባለው በም ፯ ፲፬ ከታላቅ መከራ የወጡ ልብሳቸውን በበጉ ደም አጥበው ያነጹ እኒህ ናቸው ለማለት ይቻላል እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይጠብቅ ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዕድሜ ለግርማዊት እቴጌ ዕድሜ ለልዑል አልጋ ወራሽ ።

ከዚህ በኋላ ደህና ደህና ትያትርና መዝሙር ተደረገ ተማሪዎችም በየማዕርጋቸው ተሸለሙ ።የክፍሉም አቈጣጠር ከላይኛው ከመጨረሻው ክፍል ጀምሮ ነው ።በዚሁ በመጀመሪያው ክፍል ።

፩ኛ ወይዘሮ የምስራች እምሩ ሆነችና የሚገባትን ሽልማት ተቀበለች ።

፪ኛ ማሬ ኤኒ ጋሪ ኩይክስ ሆነችና የሚገባትን ሽልማት ተቀበለች ።

፫ኛ ሬሞ ጊዮሙ ሆነችና የሚገባትን ሽልማት ተቀበለች

በ፪ኛው ክፍል

፩ኛ ሲሲል ላሬቤር ሆነችና የሚገባትን ሽልማት ተቀበቀበች ።

፪ኛ ሮዝ ሳልሐብ ሆነችና የሚገባትን ሽልማት ተቀበለች

፫ኛ ሸፈናወርቅ ሆነችና የሚገባትን ሽልማት ተቀበለች

በ፫ኛው ክፍል ።

፩ኛ ክብረት

በ፬ኛው ክፍል

አቲሉላ ከሬብ ትሲያኒስ ናቸው እነዚህ ተማሪዎች በማዕርግ የበለጡ ናቸው እንጂ ሽልማትስ የተቀበሉ ብዙ ናቸው እነዚህ ሴቶች ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጨርሰው ላልተማሩት ሴቶች ሁሉ የመልካም መሪዎች እንዲሆኑ ብርሃንና ሰላም ምኞቹን ይገልጻል ።

የተማሪዎች ዕድል

በሰኔ ፳፩ ቀን ስለ ክረምቱ ዕረፍት ለማድረግ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ከሚማሩ ተማሪዎች በትምህርት የበለጡ ልጆች ሽልማት የሚቀበሉበት ቀን ነበረ ። በዚሁም ቀን የተማሪዎችን ዕድል ለማየት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ግርማዊት እቴጌ መነን፣የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፣ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት ልዑላን መሳፍንት ክቡራን መኳንንት ክቡራት ወይዛዝር ሊቃውንትና የኮር ዲፕሎማቲክ ሰዎች ሁሉ ሌሎችም በከተማ የሚኖሩ የውጪ አገር ሰዎች ተጠርተው ነበር ።ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በገቡ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ከሙዚቃ ድምፅ እየተስማማ ተዘመረ ቀጥሎ አቶ ኪዳነ ማርያም አበራ የጥበብና የትምህርት ዲረክቴር እንደራሴ የሚከተለውን ዲስኩር አነበበ ።

ጃንሆይ ።

ግርማዊነትዎ አላንዳች ቅሬታ ብዙ ገንዘብ አፍስሰው ያቆሙት የትምህርት ቤት ሲዘጋ በመሀከላችን ስለተገኙልን

በትምህርት ሚኒስቴርና በሕፃናቱ ስም ሁኜ ለከፍተኛው ግርማዊነትዎ የሚገባ ምስጋና አቀርብ ዘንድ እንዲፈቀድልኝ እለምናለሁ ።

ብፁዓን ጳጳሳትና ልዑላን መሳፍንት ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር ክቡራን የኢትዮጵያና የውጭ አገር ሚኒስትሮችም ሕፃናቱን ደስ ለማሰኘትና ለማበረታታት ፍጹም ፈቃዳችሁ ሁኖ ስለመጣችሁልን የልብ ምስጋናችንን ለማቅረብ በጣም ደስ ይለናል ።

ጃንሆይ ።

ብፁዓን ጳጳሳትና ልዑላን መሳፍንት፡ክቡራን መኳንንትና ሚኒስትሮች፡ የተፈሪ መኰንን ተማሪቤት ከቆመ ጀምሮ እስከሁን ድረስ ያሉትን ዓመታት ብንቈጥራቸው እጅግ ጥቂቶች መሆናቸውን ልንረዳ እንችላለን።ይሁን እንጂ ዓመታቱ ጥቂቶች ሁነው ቢገኙ የተገኘባቸው ፍሬ በጣም የሚያስደንቅ ነው በዚሁ በተፈሪ መኰንን ተማሪቤት ተምረው ወደውጭ አገር ሂደው ትምህርታቸውን ጨርሰው መጥተው ለቁም ነገር የበቁ የኢትዮጵያ ልጆች እያሌ ናቸው፡ደግሞም እዚሁ የሚገባቸውን ትምህርት ጨርሰው ወጥተው ከፍ ከፍ ያለ የመንግሥት ሥራ ይዘው በትክክል የሚሰሩ ብዙዎች ወጣቶች እንዳሉ ማንም አይስተውም። ተማሪቤቱ ከቆመ ጀምሮ እስከሁን ድረስ በየዓመቱ ከሁለት መቶ አምሳ የሚበልጡ ተማሪዎች ተምረውበታል ዘንድሮም በጠባያቸውና በሥራቸው የተመሰገኑ ፫፻ ተማሪዎች አሉን ይኸም የኢትዮጵያ ሕዝብ የግርማዊነትዎ ዋና ምኞትና ሐሳብ ትምህርትን ለማስፋት መሆኑን እንደተረዳና ረቂቁን ሐሳብዎን አክብሮ እንደተቀበለ ይገልጽልናል ለወደፊቱም ከሁኑ የበለጡ ተማሪዎች እንድናገኝ ሙሉ ተስፋ አለን ።

ይህ ተስፋችንም እንዲፈጸም እላንት ወጣቶች የትምህርትን ጥቅም የእውቀትን ጣዕም ታውቃላችሁና ለጓደኞቻችሁ ለምታውቋቸውም ሁሉ በዚሁ በዕረፍታችሁ ጊዜ በሚቻላችሁ መንገድ የትምህርትን ጥቅም እንድትገልጹላቸው እናሳስባችኋለን ።

ግርማዊ ሆይ ።

የኢትዮጵያ ልጆች ከድንቁርና ወደ ዕውቀት ብርሃን እንዲሻገሩበት ብለው ገንዘብዎን እንዳሸዋ አፍሰው ያቆሙት የትምህርት ቤትዎ ስሙ በሞላው ኢትዮጵያና በውጭ አገር የታወቀ የተመሰገነም ሁኖ ያን ሁሉ ድካምዎን በከንቱ ሳይቀር የሚገባውን ፍሬ በመስጠቱ ኢትዮጵያውያን ሁላችን በጣም ደስ ሊለን ይገባናል።

ሙሴ አቤርሶን የፍትሐ ነገሥት ትምህርት በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት በብዙ ትጋት ያስተምሩ ነበርና ልጆች በትምህርታቸው በጣም ስለበረቱ የኢትዮጵያ ልጆች ትምህርትን በፍጥነት ተቀባዮች መሆናቸውን የሚያስረዳ ወረቀት ጽፈውልናልና ግርማዊነትዎ በጣም ደስ እንደሚልዎ እርግጠኛ ነኝ።

ግርማዊነትዎ የሠራልንን ድንቅና ጥቅም ያለው ሥራ እያየን ንጉሠ ነገሥታችንን ለዘለዓለም ያኑርልን እያልን እንደምንመርቅ እንዲሁም የልጅ ልጆቻችን ገናናውን ስምዎን ማመስገናቸውና ለዘለዓለም እንደማይረሳ ማድረጋቸው አይጠረጠርም ።

እኒህ አሁን የተሰበሰቡትም ህፃናት ግርማዊነትዎ ያደረጉላቸውን ውለታ ለጊዜው ለመመለስ ባይችሉ ከደጉና ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ በታማኝነት እያገለገሉ ይህነን ውለታ በማይረሱ በታሪክ መጻሕፍቶች እንዲመልሱልዎ ጥርጥር የለውም ።

ይህ ተማሪቤት እንዲህ ያለ ገናና ስም ለማግኘት የበቃ ግርማዊነትዎ መርጦ የሾሟቸው ሹማምት ሌትና ቀን በትጋት መሥራታቸውን ይገልጽልናል አስተማሪዎቹም ከተማሪዎቹ ተስማምተው ከልብ እንዳስተማሩ ያስረዳናል ስለዚህ ለክቡር መልአከ ሕይወትና በሙሉ ልባቸው ለትምህርት ለሚደክሙ ለክቡር ብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን ልናቀርብላቸው ይገባናል ። የተማሪቤቱ ዲረክተር ሙሴ ጋሬኰኤክስ እንደ አባት ሁነው ተማሪዎቹን እያስተማሩ የተቀበሉትን ሥራ በትክክል ስላስኬዱ ለትጋታቸው የሚገባ ምስጋናችንን እናቀርብላቸዋለን ።

መምህራኑም ከትልቁና ከትንሹ ተስማምተው በትጋት ስላስተማሩልን እናመሰግናቸዋለን ።

ጃንሆይ

ግርማዊነትዎ ለኢትዮጵያ ነፃነትና ታላቅነት የሚሠሩት ጥቅም ያለው ሥራ ይህ ነው ብለን ወስነን ለመናገር ብዙ ጊዜ ይወስድብናልና የሚውሉልን ውለታ እንደ ባሕር አሸዋ ብዙ ስለሆነ ባጭሩ እግዚአብሔር ውለታዎን ይመልስልዎ እያልን በፍጹም ልባችን እንለምናለን ።

በራእየ ዮሐንስ ፊቱንም ያዩታል ስሙም በግምባራቸው ተጽፎአል መብራትና የፀሐይ ብርሃን አይፈልጉም። እግዚአብሔር አምላክ ያበራላቸዋልና ለዘለዓለሙም ይነግሣሉ እንደተባለው አገር የሚጠቅመውን የግርማዊነትዎን መንገድ ለማሰናከል የተነሡ ሰዎች ሁሉ ሰው ያይደለ እግዚአብሔር እየገለጻልዎ በክፉሥራቸው እንደጠፉ ሰው ሁሉ ተረድቶታል ። ስለዚህ በእውነተኛ መንገድ የሚሔደውን ሰው ለማሰናከል የሚነሣ ሰው ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው አልተዋጋም ። ግርማዊነትዎ ኢትዮጵያን ለመጥቀም የያዙት መንገድ የእግዚአብሔር መንገድ መሆኑን በጣም ተረድተነዋልና በዚሁ መንገድ እየሔዱ ኢትዮጵያን ከፍ ወደአለ ደረጃ አድርሰው የሃብትና የሰላም አገር እንደሚያደርጉዋት የተረገጠ ነገር ነው።

ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ኢትዮጵያ አገራችንን ከፍ ወደአለ ደረጃ ለማድረስ ከሠለጠኑት መንግሥታት ጋርም ለማስተካከል መጀመሪያ የሚያስፈልገን ትምህርትን በሞላው አገራችን መዘርጋት ነውና የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን መልካም አርአያ ተከትላችሁ በያውራጃችሁ የትምህርት ቤቶችን ከፍታችሁ በጨለማ ለሚኖሩት ሕፃናት የእውቀትን ብርሃን ልታበሩላቸው እየደጋገምን ልመናችንን እናቀርባለን ።

እኒህ (ልዕልናችሁ) ለወደፊቱ ያቆሟቸዋል ብለን በተስፋ የምንጠባበቃቸው ተማሪቤቶች ለትውልደ ትውልድ ስማችሁን

እንደሚያስጠሩና እንደሚያስመሰግኑ ጥርጥር የለውምና ይህነኑ ምኞታችንን እንድትፈጽሙልን አጥብቀን እንለምናለን ።

ኢትዮጵያውያን ሆይ። ጠቢቡ ሰሎሞን ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ይሻላል ብሎአልና እናታችን ኢትዮጵያን ለማሠልጠንና ስምዋን ለማስጠራት የእውቀት መሪያችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ምርኩዝ አድርገን በሚቻለን መንገድ ሁሉ ልንደክምላት ይገባናል ።

ኢትዮጵያ በጥበብ እያደገች በነፃነትዋ ለዘለዓለም ትኑር። ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ለግርማዊት እቴጌ ለቤተ ሰዎቻቸውም የማያቋርጥ ደስታና ተድላ ይስጥልን ፡

ቀጥሎ የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ዲሬክቴር ሙሴ ጋሪኰዲክስ የሚከተለውን ዲስኩር አነበበ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ

በተፈሪ መኰንን ተማሪቤት ተማሪዎችና መምህራን ስም ሁኜ ጥልቅ የሆነና የከበረ ምስጋናችንን እንዲቀበሉን ግርማዊነትዎን እንለምናለን ። ፊዲያውም ደግሞ ይኸን ተማሪ ቤት በሚገባ አካሔድ ስለያዙት መሠረት ያለው ውለታችንን አስተባብረን ሁላችንም እናቀርባለን ።

የሽልማቱን ማመልከቻ ንባብ ሳልጨርስ አስቀድሜ በ፲ወር ውሥጥ በተደረገው ሥራ የተገኘውን የተማሪዎቹን ንቃትና ትጋት የመምህራኑን ብርታት ማመልከት አለብኝ።

በመጀመሪያ ላይ በተማሪ ቤት አካሔድ ሁለት አዲስ ነገር አመለከታለሁ ። ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ ላሉትና ከ፯ወር ወዲህ የሕግን ትምህርት ለጀመሩ የትምህርት የምስክር ወረቀት ለመስጠት የተደረገውን ዋና ፈተና ነው ።

በ፲፱፻፳፬ ዓ በጥቅምት ወር ውሥጥ ከተማሪዎቻችን በውጭ አገር በፈረንሣይ ተማሪ ቤት በ፰ተኛው ክፍል ያሉት የሚፈተኑትን የኛዎቹ በ፬ቱ ቋንቋዎች ተፈትነው በተደነበው ፕሮግራም ፈተናውን በትጋት አለፉት ። ደግሞ በልዩ ልዩ አካሔድ ያ፬ኛው ክፍል እንደዚሁ ተስፋፍተው በደረጃው ደረሱ

በዚህ ወራት በፈረንሣዊ ሌጋሲዮን እርዳታ አዲስ የትምህርት አያያዝ ቁሞ ነበር ከቀረቡት ከ፲፱ኙ ተማሪዎች ፲፯ቱ የሚበልጡት ወገን ደህና ሁነው ተገኙ ።

ስለዚህ እነዚህን ተማሪዎች በተለይ ስለረድዋቸው ለፈረንሣይ ሌጋሲዮን ለሕግ አካሔድ አስተማሪዎች ለረዳቶቻቸውም ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

አስቀድሞ ተመስርቶ የሚታይ የነበረውን ችግር ሳላፈርስ የትምህርቱን ምስክር ወረቀት ነገሩን ለመግለጽ አይቻለም።

ለመጀመሪያው ደረጃ ፈተና የሚዘጋጅ ተማሪ ቤት እጅግም ስሙን አያስነሳም ።

ስለዚህ ረቢ በሚባለው በውጭ አገር ስለሆነው ትምህርት የሚጻፈው ጋዜጣ ሙሴ ሔሪዎ ፍራንስዋ አልቤር ማሪዎ ፉስታን የተባሉ የኢኒቤርሲቴ ታላላቅ መምህራን፤የእስክንድርያ የፈረንሣይ ተማሪ ቤት፥ የቤይሩት፥ የማሎኒክ፥ ቱሔሮ ከቡል ተማሪ ቤቶች ብዙ ተማሪዎች የትምህርት ደረጃ የምስክር ወረቀት የሚቀበሉ አሉ ሲሉ በዚሁ በረቢ ጋዜጣ ጽፈዋል ።

ዋናው ዋናውም የትምህርት አካሔድ ተገልጾዋል ። ስለዚህ ብዙ የተማሩ ልጆች በልዩ ልዩ ስፍራ አሉ ፡

አሁንም ጃንሆይ ታላቁ እርዳታዎ ሳይለየው የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት የቀርቡን የምሥራቃዊ ሁለተኛ ተማሪ ቤትን ደረጃ የሚይዝበት ቀን ይደርሳል ።

በሕግ ትምህርት ክፍል በዚሁ ተማሪ ቤት የተመሰገኑ ተማሪዎች አሉ ይኸነኑ ትምርት የመንግሥት አማካሪ ሜትር አቤርሰን በጥንቃቄና በትጋት ይዘው ስለቄዩ ለዚሁ ትምርት ሜትር አቤርሰን አቶ ሎሬንሶ ትእዛዝ ሙሴ ከልሰን ፈርመው ለትምህርት ሚኒስቴር ያቀረቡት የተማሪዎቹን ትጋት በሰፊው የሚያስረዳ ቀጥሎ እንደመሰከሩት ቃል ነው ።

ይህ ከተማሪዎቹ ትጋት የተገኘ ማመልከቻ በኢትዮጵያዊ ተማሪ ቤት በትልቁ ደረጃ ያሉት ተማሪዎች የሕግን ትምህርት ለመማር የሚችሉ ናቸውና መንግሥት ከነዚሁ ተማሪዎች ለሥራ ቤቱ ማስኬጃና ለፍርድ ክፍል የሚያስፈልግ ትልቅ ጥቅም ያገኝባቸዋል። በዚህ በተሰጣቸው የሕግ ትምህርት ደስ የሚያሰኝ ማስረጃ ስለተገኘበት ይኸው ትምርት ሳያቋርጥ እንዲከሄድና እንዲስፋፋ የሚያስመኝ ነው።

ይህ ራፖር ለተማሪዎቹ ምስጋና የተሰጠበት ስለሆነ ለተወደዱ መምህራን ልዩ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

በተማሪ ቤቱ ክፍል ሁሉ ሥራው በትክክል ስለመሄዱ ተስፋፍቷል። ደግሞ ተማሪዎቹ ጉልበት በማጣታቸው የቤተ ዘመዶቻቸውን ድጋፍ ስላላገኙ በተማሪ ቤቱ አዘውትረው ባለመምጣታቸው ያሳዝናል ።

የሆነው ሁኖ ካለፉት መልካም ዘመናት ይልቅ በዛሬው ዓመት የተማሪዎቹ ቁጥር በዝቷል ።

ደግሞ ተማሪዎቹ በደምብ መሆናቸውና በመታዘዛቸው መልካም መንፈስ እንዳደረባቸው ስለጓደኞቹ ሁኜ ለግርማዊነትዎ አመለከታለሁ ።

ይኸን ሳልፈጽም አስቀድሜ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴርን ጥሬ አክብረው የተፈሪ መኰንንን ተማሪ ቤት መስፋፋት ለማሞገስ እዚህ ለተሰበሰቡት ለልዑላንና ለክቡራን መኳንንት ምስጋናዬን አቀርብ ዘንድ ግርማዊነትዎ ይፍቀዱልኝ ስል እለምናለሁ ።

ወዲያውም ትምርት እንዲነቃና እንዲስፋፋ መልካም አበትነታቸውንና ረዳትነታቸውን ሳያቋርጡ በደግነትና በትጋት ሥራቸውን ለሚፈጽሙ ለክቡር የትምህርት ሚኒስትር፥ ለዋናው ዲሬክተር ለክቡር ብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ፥ለትጉህ ምትክቸው ላቶ ኪዳነ ማርያም አበራ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

ጃንሆይ ።

ልዑል እግዚአብሔር ለግርማዊነትዎና ለግርማዊት እቴጌ ረጅም ዕድሜ ተድላና ደስታ የማያቋርጥበት ክብር ጭምር ለመንግሥትዎና ለሕዝብዎ ይስጠው ቤተ ሰብዎንም ይጠብቀው ስል ጥልቅ የሆነ ምኞቴን እገልጻለሁ ።

ዕድሜ ለግርማዊነታችሁ ።
ዕድሜ ለኢትዮጵያ ።

ከዚህም በኋላ ታናናሽ ሕፃናት የወታደር ሰልፍ አሳዩ። ከዚህም በኋላ የሰባተኛና የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ተሸለሙ እንዲሁም ትያትሩን በመሐል እያደረጉ ተማሪዎች በተራ በተራ በየክፍላቸው ይሸለሙ ነበር። የተማሪዎች ስምና የሽልማቱ ዓይነት ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

በታላቁ የ፰ኛው ክፍል ።

፩ኛ አሰፋ ኃይለ ሥላሴ አንድ የወርቅ ሰዓት ከጃንሆይ፥ አንድ የወርቅ መስቀል ከቡነ ቄርሎስና ሁለት መጻሕፍት ከፈረንሳይ ሌጋስዮን ተሸለመ

፪ኛ ዋቅጅራ ሰርዳ የብር ሰዓት ከጃንሆይ የወርቅ መስቀል ከአቡነ ቄርሎስና አንድ መጽሐፍ ከፈረንሳይ ሌጋስዮን ተሸለመ ።

፫ኛ ሞሪስ ጋሌብ የብር ሰዓት ከጃንሆይና አንድ መጽሐፍ ከሙሴ ዶሮብያር የኩሬር ደኢትዮጲ ዲሬክተር ተሸለመ

፯ኛ ክፍል ።

፩ኛ ኢያሱ መንገሻ አንድ የወርቅ ሰዓት ከጃንሆይ ተሸለመ
፪ኛ ያሰቆብ ገብረ ልዑል የብር ። - - - -
፫ኛ ለማ ኃይለ ሥላሴ - - - - - - - -

፮ኛ ክፍል ሀ ።

፩ኛ እሸቱ ቂርቆስ የወርቅ ሰዓት ከጃንሆይ ተሸለመ
፪ኛ ከንፈ ሚክኤል አባታቦር የብር - - - -
፫ኛ ከሳቢያን ማርዲሮስ - - - -

፮ኛ ክፍል በ ።

፩ኛ አበበ ዘለቀ የወርቅ ሰዓት ከጃንሆይ ተሸለመ
፪ኛ መኰንን መንገሽ የብር - -
፫ኛ ተድላ ደስታ

፬ኛ ክፍል	፫ኛ ክፍል	፪ኛ ክፍል
አንደኛ መርዕድ መንገሻ	አንደኛንዋየ ማርያም አፈወርቅ	አንደኛ ዘውዴ መሸሻ
፪ኛ አያሌው ደብዛ	፪ኛ ዳኛቸው በሻ	፪ኛ ከበደ በሻ
፫ኛ አረጋ ደስታ	፫ኛ ክፍለ ማርቆስ ተክሎት	፫ኛ ሥዩም ነጋሽ

፭ኛ ክፍል ሀ ።	፭ኛ ክፍል በ
፩ኛ በኩር አክለ ሕይወት	፩ኛኃይሉ ደግለጡ
፪ ዘውዴ ተክለ ጊዮርጊስ	፪ኛ አድማሱ ሽፈራ
፫ኛ መለሰ ኪዳነ	፫ኛ ገብሩ ዘወልደ ማርያም

የትያትሩ ማማርና የልጆች መሠልጠን የተሰበሰቡትን ሰዎች ሁሉ እጅግ ደስ አሰኘ።

ለምንት አንገለጉ አሕዛብ ።
ወሕዝብኒ ነበቡ ከንቶ ።
ሀገሩንና መንግሥቱን የሚወድ የሚጽፈውን ይጻፍ ወይም ይመልከት።

ለአድለኛዋ ኢትዮጵያ በባሕርዩ ሞት በመንግሥቱ ሕልፈት የሌለበት የባሕርይ አምላክ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከሁን ድረስ በልዩ ልዩ ፈተና ጠላት በተነሣበት ጊዜ በየጊዜው በማይታወቅ ጥበቡና ቸርነቱ እየደገፈ ረድኤቱን ከንጉሠ ነገሥቷና ከርበኞቿ ሳይለይ ከብዙ ፈተና ጠብቋታል አድንዋታልም ።

ይኸም መሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ በማናቸውም ሥራው ላይ ተቀዳሚ የሚያደርገው እግዚአብሔርን መፍራት ሃይማኖቱን ማጽናት መንግሥቱን መውደድ አገሩን መጠበቅ ከዚህ ሌላ ያለውየትሩፋቱ ሥራማ ስንቱ ይቆጠራል ይህን በመሰለ ሥራ ሁሉ የፈጣሪያቸውን ሕግ ጠብቀው ስለሚኖሩ በኢትዮጵያና በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ክፉ ለመምከር የሚያስቡትን ሁሉ ሳይታሰብ በድንገት ማጥፋቱ ብዙ ጊዜ ታውቋል ።

ስለዚህ ብርሃኑ ንጉሣችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን አደራነት ከፈጣሪያቸው የተቀበሉበት አኳኋን በማይታወቀው በማይመረመረው በረቀቀው በእግዚአብሔር ሐሳብ ነው እንጂ እነጋዲያውማ ተጀምሮ የነበረው ሐሣብ ለእግዚአብሔርና ለኢትዮጵያ ለሕዝቡም የማይስማማ ሁኖ በፍጹም ቀርቶ የለምን ? ዳሩ ግና አደራነቷን ከተቀበሉ ጀምሮ እስከሁን ድረስ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የሠሩትን ውለታ ስንቱን ጽፈን ስንቱን ቆጥረን እንጨርሰዋለን ። አሁንም ከሠለጠኑት ከሌሎች አገሮች እንዳቃረቧት ሁሉ ወደፊትም ሳያስተካክሏት አይቀሩም ብለን በማይጠረጠር ተስፋ ቁመናል እርግጥ ነው ሥራቸውና ሐሳባቸው ሁሉ ያስረዳናል ነገር ግን ከዚህ ተሥፋ የሚወጣ ተጠራጣሪ የራሱን ክብር ብቻ የሚያስብ የሀገሩንና የሕዝቡን ጥቅም የማይመለከት ጸጥታን ባገኘው በውነተኛው መንግሥታችን ላይ በሐሰት ነገር ቢነሣ ራሱን ከማጥፋትና ሐሳቡ ከመሰናከል በተቀር ምን ጊዜም ቢሆን የተጠቀመ አለመሆኑ ብዙ ጊዜ ተረግጧል ።

ይሁን እንጂ አሁን ራስ ኃይሉ ይህን ያሰቡበት ነገር እኮ ድኃን ታላኰላላሁና ታልበደልሁ የጠላሁትን በድዬ የወደድሁትን ጠቅሜ በፈቃዴ ካልኖርሁ በእግዚአብሔርና በመንግሥት ሕግ ተወስኜ የምኖር ከሆነ ኢትዮጵያን እርስ በርሷ አጋጭቼ የሆነው ይሁን ። ደግሞስ ከራሴ ክብር በተቀር ለሀገርና ለመንግሥት ለምን አስባለሁ ማለት ነው እንጂ እውነት በጃንሆይ ዘንድ ቸርነት ባይደረግላቸው ኑሮ እንደምንሰማው በሕዝቡ ላይ በየጊዜው ለሚያደርጉት ግፍ የአገው ምድርና የጎባያው መቀነስ የሚበቃ ካሣ ሁኖ አልነበረም ። በዚህስ ቸርነት ለበደሌ ሁሉ መንግሥት ይቅርታ እያደረገ ብዙ ዘመን ታግሦ እስካሁን አስገዝቶኛል ። ስለሆነ ግን በኔ አለመታገሥ የተነሣ በደሌ በምገዛው አገር ከዳር እስከዳር ሞልቶ ሕዝቡ እየተጯጯኸ በእግዚአብሔርና በንጉሠ ነገሥቱ በሕዝቡም ፊት ተገልጾ የሚፈረድብኝ ከሆነ ከዚህ ቀደም በሠራሁት ጥፋት ይቅርታን አግኝቼ ወደፊት በነፃነት እንድኖር ይፈቀድልኝ ብለው ይቅርታን እንደመለመን ሁሉ ጕዳምን የበደሉት አንሶ በሙሉ ኢትዮጵያን ለመበደል ማሰባቸው ታላቅ የበደል በደል ሆነ። ዳሩ ግን በርኅራኄና በቸርነት በእውቀትና በሀብት ይልቁንም በትዕግሥት አጕናጽፎ የፈጠራቸውን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ የሆነው ገናናው አምላካችን ስለሰጠን ኢትዮጵያን ለመበደል የተነሣው ሰው የጀ

መረውን የከፉ ምክር ሳይፈጽም እሱን ራሱን አስመስክሮ በጠመደው ወጥመድ ላይ እንዲወድቅ ማድረጉ የጃንሆይም አድራጎታቸው ለኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ከሠሩላት ውለታ ይበልጣል እንጂ አያንስም ። እንደዚሁ ሁሉ ጢት ማታ ሳያቋርጡ ከራሳቸው አስበልጠው ለሚወዱት ለከበረው ሕዝብና ለውድ ሀገራቸው ለኢትዮጵያ ሲሉ የሚሠሩትን የንጉሣዊ ሐሳባቸውን ሳያስተውል ከንቱን ወሬ እያወራ የሐሰት ስብከት የሚናገር ሰው ምናልባት ቢኖር ይህ ያሁኑ አኳኋን ያስረዳዋልና ሥራ ከማይዘው ሐሳቡ ተመልሶ የኢትዮጵያና የሕዝቡ ሥልጣኔ እርምጃ ከምን እንደሚደርስ ቢመለከት ይሻለዋል ። የጐጃም ሕዝብስ ለብርሃኑ ንጉሠ ነገሥት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወረታቸውን ምን ጊዜም ቢሆን መልሶም አይጨርሰውም መቸም ያሁኑ የራስ ኃይሉ ሐሳብ ለምን የተበደለውን የድኃ ጩኸት ሰሙብኝ ብለው በማይገባ ሐሳብ እንደተነሡ ታውቋል። ስለዚህ ለጐጃም የተሠራውን ውለታ የተመለከተና የሰማ የሌላ የኢትዮጵያ ክፍል አገር ሁሉ ይህን ምሳሌ አድርጎ ከቀድሞው ይልቅ ዛሬ በንጉሠ ነገሥቱ ፍቅር ተባብሮ ባንድነት የተስማማ መሆኑ ጐልቶ ይታያል ጐጃምም ውለታውን መልሷል ። እንግዲህስ ሐሳቡን በስሕተት ለማንቀሳቀስ የሚያራምድ ሰው አለመኖሩን ስለተረዳነው የኢትዮጵያ ዕድል ከንጉሠ ነገሥቱ ጋራ እየገነነ መሔዱ አይጠረጠርም በማለት ተስፋፍተናል ። ደጉ ደመር።

የበደል በደል ።

ይህ የበደል በደል የተባለውን እንደኔ ለሀገራችሁና ለመንግሥታችሁ ለምትቆረቆሩ ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ከዚህ በታች የሚከተለውን ቃል ጽፌላችኋለሁ ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ከተቀበሏት ጀምረው ድንቁርና የሚባል የፈሪ ጋሻን አስጥለው ፥ ጥበብ የሚባል መቀነትን እንዳስታጠቁን በሁላችን ጐን መታሰቢያ መሆኑን ማንም አይስተውም ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ከሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንደኛው ይሁዳ ከጌታ ፊት ንጹሕ መስሎ ቀርቦ ከድስቱ ውሥጥ እጁን ከቶ ሲሠርቅ እንደታየ ራስ ኃይሉም ሥራቸው ሁሉ ከመኳንንት ልዩ ሁኖ የሐሰት ወረቀታቸውን ንጹሕ መስለው ቀርበው በመያዛቸው የማን ወገን መስለው ይታዩ ይመስላችኋል።ነገር ግን እግዚአብሔር ወሀበ ወእግዚአብሔር ነሥአ የሚለውን ቃል ሳይመለከቱ ቀርተው የኢትዮጵያን ጀግኖች ደም በከንቱ ለማፍሰስ ስለነበረ ሐሳባቸው ወደሳቸው ብመዛወሩ በጣም ያስደንቃል ።

እነሆ የዱር አባቶች ሲተርቱ ትንሽ ልጅ እንቁላል ሰረቀና እናቱ እያመሰገነችው ስትኖር አእምሮ አውቆ ወደ ትልቁ ሌብነት ደርሶ በተያዘ ጊዜ ምነው እናቴ የእንቁላሉ ጊዜ በቀጣሽኝ ብሎ ተናገረ ይላሉ ። አሁንም ራስ ኃይሉ ጐጃምን ከወንጌል ሕግ አልፈው መከራና ሥቃይ ባሳዩት ጊዜ መቅደላ ወይንም አፍቀራ ሒደው ቢሆን ሁለተኛ ለፍርድ አያሳስቡም ነበር ። ልሳነ ወርቅ ቸርነት ዘብሔረ እንጦጦ ።

ስለ ልጅ ኢያሱ መያዝ አለቃ ዳንኤል የተቀኙት መወድስ።

አባሲ ይብለከ በቃለ ኃዘን።
አይቴኑ አሐውርሰበ ኪያየ ኅሠሥከ ።
ወአይቴ እጐይይ እምቅድመ ገጽከ ።
እስመ እመ ዐረጉ ሰማያተ ።
ወወረድኩ ከርሠ ቀላያት ዘየኒ ሀሎከ ።
ወበውስተ መከን ዘፈቀድከ ።
ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ዘታንበረኒ የማንከ።(መዝ ፻፴፱ ወይም ፻፴፰ ቍ ፯-፲፩።)
በገዳምኒ ኢይትኀባእ እንተ አበሰ ዮርከ ።
እስመ ውስተ ኵሉሙ በሐውርት ኃይለ ሥላሴ መለከትከ።
ወበእደ ባዕዳን ኢይደቅ እንተ አበሰ ላዕሌከ ።
እስመ ለዘአበሰ ይኄይሶ ወዲቅ ውስተ እዴከ ።(ሳሙ-ካልእ ፳፬ ፲፬።)

መወድስ ቅኔ ።

ስለ ራስ እምሩ መሾም ደስ ስለአለው የተቀኘውን መወድስ እንድትመለከቱት አትመንላችኋል ።

እሮ ጸለዩ በአንቀዕድዎ
መንግለ ፈጣሪ ሕያው ምእመናን ሰብአ ጐጃም ።
በኃዘን ልብ መሪር ወበአንብዐ ገጽ ደም ።
ፀሐየ ዓለም ራስ እምሩ ፥ ላዕሌሆሙ እምጣነ ሠረቀ ለይድኀን ዓለም ።
ወሀገረ ጐጃም ተፈወሰ ፥
ፍትሐ እምሩ ሰሎሞን እስመ ወርቀ ያዘንም ።
ባዕደሰ ኢይምሰልክሙ ራስ እምሩ አዳም ።
እምጣነ ጐጃም ጥንተ ሀገሩ ለተክለ ሃይማኖት አብርሃም ።
መኃይለ ሥላሴ ፍርሁ ምስለ እምሩ ግሩም ።
እምጣነ ድኩመ ያፀንዖ ወኃያለ ያደክም ።
ደብተራ ወልደ ኪዳን ዘሐረር መድኃኔዓለም ።



የሚአሳዝን ሞት ።

ዓሥር ዓመት የሆነው አወጣጡ መልካም ለትምህርት የተጋ የአቶ አየለ ገብሬ ልጅ ነበረ።በድንገተኛ ሕማም ታሞ በ፩ቀን ሞተ የሞተበትም ቀን በሰኔ ፳፫ቀን ነው።ብርሃንና ሰላም አቶ አየለ ገብሬንና ባለቤታቸውን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ኃዘኑን ይገልጻል ።

የሚያሳዝን ሞት ።

ክቡር አቶ ደስታ አደራ በጣም የተማሩ ዜማ፡ ጽሕፈትና ሒሳብ አዋቂ ለመንግሥታቸውና ለዘመዳቸው አሳቢ እጅግ መልካም ሰው ነበሩ መጀመሪያም የንቡረ እድ ገብ

ረሥላሴ ባልደረባ ሁነው ቀለብ ደመወዝ ጸሐፊ ነበሩ። ፪ኛም በክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅ ጊዜ ንግግርና ጽሕፈት ያውቃል ፍርድ ጽሕፈት ይችላል ብለው መርጠው ፍርድ ጸሐፊነት ሰጥተዋቸው ባላጋራና ባላጋራ የተነጋገሩትን ዳኞች የጠየቁትን በገባብ ጽፈው ሲአነቡላቸው ከሥር ጀምሮ ባለ ነገሩ ጽፎ ያመጣላቸው ይመስሉ ነበር እንጂ ከነገረተኞች እፍ ሰምተው የጻፉት አይመስልም ነበር።፫ኛም በመታመናቸውና ሒሳብ በማወቃቸው በገንዘብ ምኒስቴር ክፍል የሒሳብ ሹም ተብለው እንደ አንድ ክፍል የሥራውን ደምብ ተቀብለው የጌታቸውን ገንዘብ በትክክል ጠብቀው ብዙ ዘመን ይኖሩ ነበር

፬ኛም ከሰው መርጦ ለሹመት እንደሚባለው የሐረርጌ ጓምጃ ቤትን ተሹመው በ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ጓንቦት ፲፱ቀን ከዚህ ተነሥተው ወርደው በ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት ግንቦት ፳፰ቀን አርፈው በክብር ተቀበሩ። ዕድሜያቸውም ፵፰ ዓመት ነበረ እኛም ቤተ ዘመዳቸው ግንቦት ፴ቀን ተረድተን አልቃሽ ቁማ እንባ ለንባ ስንራጭ ዋልን። ይልቁንም ምትኬ ደስታና ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ኃዘናቸውንና እንባቸውን ያየ በጣም ያዝናል ግን ምንም እንባ ቢበዛ የሞተ ለመመለስ አይቻልም ።

ከነዚህም መካከል እያንጐራጐሩ በጣም ቢያስለቅሱኝ ከዚህ የሚከተለውን ልጽፈው አስብሁኝ ።

ተቀመጥ በምቹ ጥልፍ እቃ ጭነህ ። መርገፍ አይረባህም ምክር ተሰማህ ። የደስታ ምድር ሀገሩ መልቶለት ። ገዝቶ ተቀበረ የሰው አገር መሬት ። ወይዘሮ አፀደ ይስሙኝ ልንገረዎ ። ማለፉ አይደለምወይ ደስታ በርስዎ። ምትኬን አደራ ብሎ ሲሔድ ቢያውቁት ። መቃብር ሰጡና በማጥን ከተቱት። እመጣለሁ ብሎ ቀጠሮ ነበረኝ ። ጊዜውን ሳላውቀው አለፈ መሰለኝ ።

ልጃቸውን ምትኬ ደስታንና ባለቤታቸውን ወይዘሮ ዓፀደን እግዚአብሔር ያጥናቸው ።

ደስአለኝ ቸርነት

ማስታወቂያ ።

የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ።

የዋና ምርመራ ጽሕፈት ቤት ክፍል ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ያስታውቃል ።

፩ኛ፥ የአቶሞቢላቸውን ታክስ ላልከፈሉ አቶሞቢል ላላቸው ሰዎች ።

፪ተኛ፥ አቶሞቢል ለመንዳት የፈቃድ ወረቀታቸውን ላላሳደሱ ለአቶሞቢል ነጂዎች ።

የአቶሞቢላቸውን ታክስ ለመክፈልና አቶሞቢል ለመንዳት የፈቃድ ወረቀታቸውን ለማሳደስ እስከ ሐምሌ ፴ቀን ድረስ ከአቶሞቢል መጠባበቂያ ጽሕፈት ቤት ድረስ እንዲቀርቡ እናስታውቃለን ይህ ቀን ያለፈ እንደሆነ ግን በዘበኛ እየተያዙ ሀያ ሀያ ብር መቀጫ ይከፍላሉ ። የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት

ያገር ግዛት ሚኒስቴር ።

ማስታወቂያ ።

ከሁን ቀደም በመጋቢት ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት በጻፍነው ማዘዣችን ስለሀገሩ ጥቅም ብለን ከብዙ ዘመን በፊት ጀምሮ የበቀለ ታላላቅ ዛፍ እንዲያው ያለጥቅምና ያለ ሥራ እየቈረጠ ቢጥለው በእሳትም ቢያቃጥለው በኋላ ጉዳት ይሆናል ብለን ይህን የመሰለ እንጨት ሁሉ እንዲያው ያለጥቅም እንዳይቆረጥ ዱሩ ሁሉ ይጠበቅ ይከልከል ብለን በየአገሩ ገዦው ጽፈን አስታውቀን ነበረና ። አሁን ግን ይከልከል የተባለው ቃል ቀርቶ እንደዚያው እንደቀድሞው ባላገሩ ለሥራው የሚያስፈልገውን ማናቸውንም እንጨት ቢቆርጥ አይከልከል መባሉን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እናስታውቃለን ። ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት ።

ያገር ግዛት ሚኒስቴር ።

ማስታወቂያ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከሪያሌት ማህበር ላይ የገዛቸውን የአረቄ ማውጫ መኪናዎች ለመሸጥና ወይም ለማከራየት ስለፈቀደ ይህነን የአረቄ መኪና ለመግዛት ወይም ለመከራየት የሚፈልግ ሰው ጥያቄውን ከንግድ ሚኒስትር ለመነጋገር ይችላል ገዢ ወይም ተከራይ የሆነ ሰው ፈቃድን ከንግድ ሚኒስቴር ተቀብሎ አልኮልን ለመሥራት ይችላል ።

ሰኔ ፴ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም የንግድ ሚኒስቴር

AVIS

Les destilleries sachetées de la Sociète Anonyme Rialet par le Gouvernement Ethiopien sont offertes en vente ou en location avec faculte d'obtenir des liceces pour la fabrication d'alcol.

Pour tous renseignement' s'adresses au Ministère du Commerce.

Addis-Abeba le. 7 Juillet 1932

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው· ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቊረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጎበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመነበናት ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መሰንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ሀልኩሲ ሳሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች በማክበር ያስታውቃል። ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ጎናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፣ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፣ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ።

ስምንተኛ ዓመት ቊጥር ፳፱
8me ANNE. № 29

ሐሙስ ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 14 JUILLET 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ በጸሬኽተሩ ስእቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres.

የተማሪዎች ሰድል ።

በሰኔ ፴ ቀን የዳኅማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ስለ ክረምቱ ዕረፍት ለማድረግ የሚዘጋበት ቀን ነበረ ። በዚሁም ቀን በት ምሀርት የበለጡትን ተማሪዎች ሽልማት ለማየት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፥ ግርማዊት እቴጌ መነን፥ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት ፥ የኢትዮጵያ መ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ፥ ልዑላን መሳፍንትና ልዑላት ወይዛዝር፥ የኢትዮጵያ ሚኒስትሮችና መኳንንት፥ የክር ዲፕሎማቲክ ሰዎች ሌሎችም ከኢትዮጵያና ከውጪ አገር ሰዎች ብዙ ነበሩ ። የተማሪቤቱም ግቢ በሰንደቅ ዓላማና በአበባ አጊጦ ለማየት እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር አዳራሹም እንደሚገባ ተነጥፎ አምሮ ነበር በመጀመርያ ጃንሆይ ሲገቡ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ከሚአምር ሙዚቃ ጋራ ተዘመረ ። ከዚህ በኋላ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር መልአከ ሕይወት ወልዴ ሐና የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ።

ጃንሆይ ።

ምንም በግርማዊነትዎ ፊት የሚያኰራ ነገር ይገኛ ባልቀርብና ሐሳቤን የምገልጽበት አንደበት ባይኖረኝ በዚህ ምክንያት ያጋጠመኝን መልካም ዕድሌን አልዘለውም ።

ጃንሆይ፥ ለኢትዮጵያ ልማት ለሕዝብዎ ሰላም አዘውትረው ከሚያስቡላትና ከሚሠሩላት ጊዜዎችዎ ውሥጥ ይህችን ሰዓት ለዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የድካማቸውን ዋጋ መቀበያ በተለይ እንድትሰጣቸው በደግኛው ፈቃድዎ መስነው ከልዑላን መሳፍንትዎችዎና ከክቡራን ሚኳንንቶችዎ ጋር ስለ መጡልን ደስታችንን በሰውነታችን ላይ እንገልጻለን።

ጃንሆይ።እንደሚውያቁትና በየዓመቱ እንደተለመደው ዛሬ የ፲፱፻፳፬ ዓ ም የተማሪዎች ፈተና ነው ይኸውም የተማሪዎች ፈተና ከአምናው ይልቅ ዘንድሮ የሚያኰራ የእውቀት እርምጃ ማድረጋቸውን ከሁሉ በፊት ለግርማዊነትዎ አረጋግጣለሁ። ይልቁንም የሥልጣኔ አዋኪ የእውቀትን አሰናከይ ማስወገጃ የአገርና የሕዝብ ጥቅም መግለጫ የሚሆን በማይሰለች ማስረጃ በሚያስደንቅ ጨዋታ በማሳየታቸው የግርማዊነትዎን ክብር እንዲያገኙ የጋለ ተስፋ አለን።በዚሁ ላይ አንደበታቸው የሰላ ንግግራቸው የጣፈጠ ሐሳባቸው የረቀቀ አእምሮዋቸው በእውቀት የጐለመሰ መሆኑንና ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ፍሬ በሰፊው ጕተራዋ ለማከማቸት ትበቃለች ተብሎ ሲነገርላት የነበረው ተስፋ መድረሱን እንረዳለን።ይህም ሁሉ በግርማዊነትዎ ገበሬነት በትምህርት ቤቱ እርሻነት መሆኑን በሕዝብ መካከል ለመመስከር ምክንያት በማግኘቴ ክብር አለኝ ።

ጃንሆይ፡ ንግግሬን ባይሰለቹኝ መቸውንም የዛሬ ወጣቶች ጊዜ ስለ አጋጠማቸው እያስደንቀምና የነእሱን ተወት አድርገን የዱሮ ሰዎች ይልቁንም የቤተ ክህነትን ሰዎች ብንመለከት የኑሮ መከበሪያ የስም መጠሪያ ጥበብ መሆኑዋን ጥበብ የምትገኘው በትምህርት እንደሆነ ጣዕሙ ተሰምቶአቸው ብዙ ልጆቻቸው በተማሪ ቤቶቻችን አሉ ለዚህ ሁሉ እያተጋጋ የረዳንንና የጥበብን ጣዕም የሰበከልንን ብርሃንና ሰላምን እያነሳሁ ባዚህ ምክንያት የግርማዊነትዎን ምስጋና አላቋርጥም።

ጃንሆይ፥ ጥበብማ በዘመነ መንግሥትዎ ዋጋ ማግኘቷን ብዙ ወጣቶች በእርስዎ እምነት የወርና የሁለት ወር ጕዳና ከዘመዶቻቸው ተለይተው በዝማም ወርቅ ሲገበያዩአት አይተን ተረድተን የለምን።ስለሆነም ገበያተኛዋ ከሚበዛላት፥ትርፍ ዋጋ ከምታገኝበት በታ ሁሉ ጕጆ ያስፈልጋታልና ግርማዊነትዎ ያስለመዳት ችሮታ ሳያቋርጥ በየጊዜው እንዲፈጸምላት ባስታውስ በጃንሆይ ልቡና የታሰበውንና የተወደደውን ደግኛውን ፈቃድ እንደ ትንቢት ማወቅ ይሆንልኛልና እንደዚህ ያለ ዕንቊ ነገር ሲያሳስበኝ ተስጥዎየን አደንቃለሁ ።

ጃንሆይ

የግርማዊነትዎ ሐሳብ ተባባሪ የሥራዎ አጋዥ ለስቶችም የሞያቸውን ጉድለት አስተካካይ የትዳራቸው ጠጋኝ የሆኑትን የስመ ጥሩዋን የግብረ መልካሟ የገናናይቱ የእቴጌ መነንን ስም ምንም ዘወትር በምስጋና ብናነሳው ለደግ አድራጐታቸው ወሮታ የሚሆን ምሳሌ አናገኝም።ቢሆንም ወሮታቸው ባተለየ ገንዘባቸው ባሠሩት በሚያስደንቅ ተማሪ ቤታቸው ውሥጥ በሚያስተምሩአቸው ወጣት ልጆች ላይ ባለፈው ሳምንት እንደአዩት ለወደፊቱም በብዙ ያገኙታልና ታላቅ ሥራቸውን የምስራች ብል የሚያሳፍረኝ አይደለም።

ጃንሆይ የመጨረሻው ቃሌ ሐሳቤን በክብር የምገልጥበት መልካም አጋጣሚ አግኝቼ በዚህ ምክንያት ጊዜ ስለአሳለፍሁ ይቅርታ እየለመንሁ ወዲያውም ነገሬን ከትልቅ ጉዳይ ቈጥረው በደስታ ስለ አደመጡኝ እያመሰገንሁ ጥሪአችንን አክብረው ለመጡልን ለልዑላን መሳፍንቶችና ለክቡራን መኳንንቶች ለወይዛዝሮችም ደግሞ ለክቡራን የዲፕሎማቲክም ሰዎች በትምህርትና በጥበብ ሚኒስትር ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለግርማዊነትዎና ለንጉሣዊ ቤተሰብዎ ዕድሜና ጤና ለመንግሥትዎ ጽናት ለአገርዎ ልማት እመኛለሁ ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ቀጥሎ የትምህርትና የጥበብ ዲረክቴር ዋና እንደራሴ አቶ ኪዳነ ማርያም አበራ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት፥ ግርማዊት እቴጌ ሆይ ።

ሕዝባችሁን ደስ ማሰኘትና ማበረታታት ልማዳችሁ ነውና የደጉ ንጉሠ ነገሥት የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ተማሪዎች በትምህርታቸው ተፈትነው በሚሸለሙበት ቀን፥ ሕፃናቱን ደስ ለማሰኘትና ከፍተኛውን ተስፋችሁን ለመስጠት በመክከላችን ስለተገኛችሁልን ለገናናው ግርማዊነታችሁ የሚገባ ምስጋና ለማቅረብ እንዲፈቀድልን እንለምናለን ።

ብፁዓን ጳጳሳትና ልዑላን መሳፍንት ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር ክቡራን የኢትዮጵያና የውጭ አገር ሚኒስትሮች እነዚህ ሕፃናት በግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና በግርማዊት እቴጌ ፊት ቀርበው እንደ የስራቸው በሚሸለሙበት ቀን ስለመጣችሁልን የልብ ምስጋናችንን እናቀርብላችሁ ዘንድ ይገባናል ።

ጃንሆይ፥ እቴጌ ሆይ ፤

ብልሁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ለኢትዮጵያ ልጆች የሥልጣኔን መንገድ ለመክፈት ዋና ምኞታቸውና ሐሳባቸው ስለ ነበር ብዙ ገንዘብ አፍሰው ይህንን ተማሪ ቤት አቆሙ። ይህም ተማሪ ቤት ከቆመ ጀምሮ እስታሁን ድረስ ብዙ ሕፃናት የማይረሳውን ያፄ ምኒልክን ስም እያመሰገኑ ተምረውበታል። አሁን በተማሪ ቤቱ ያሉ ተማሪዎችም እግዚአብሔር በመንግሥቱ ሰማያት የማያቋርጥ ተድላና ደስታ ይስጥልን እያሉ ሌትና ቀን መለመናቸው ጥርጥር የለውም ።

ማናቸውም ሕዝብ ያለመደውን አዲስ ነገር ተቀበል ያሉት እንደሆን ምንም እንኳ ነገሩ የሚጠቅመው መሆኑን ቢረዳው አዲስ ነገር በመሆኑ ብቻ ቅር እንደሚለው የታወቀ ነገር ነው ብልሁ አፄ ምኒልክ በዘመናቸውና በዘመናችን፥ ለወደፊቱም ባለው ዘመናት የኢትዮጵያን ነጻነት ለመጠበቅ ዋና መሣሪያ የሚሆነው ትምህርት መሆኑን በጣም ስለተረዱት የሥልጣኔ ተማሪ ቤት ከፈቱ። በከፈቱም ጊዜ ነገሩ አዲስ ስለሆነ ደስ ያላቸው ሰዎች በጣም ብዙዎች አይደሉም ስለሆነም ጥቅሙ እየታየ ፍሬው ከተገለጸ በኋላ ብዙ ሰው ደስ አለው ስለዚህ እንዲህ ያለውን ትልቅ መንገድ ስለጠረጉልን ስማቸው እስከ ዘለዓለም በየልባችን ተጽፎ ይኖራል ።

ይህ መጀመሪያ የኢትዮጵያ የዕውቀት ተማሪ ቤት ከቆመ ጀምሮ እያደረ ከፍ ከፍ ማለት እንጂ ዝቅ አለማለቱ የሹማምቱን ብርታትና ትጋት ያስረዳናልና ለትጋታቸው የሚገባ ምስጋና ልናቀርብላቸው ይገባናል። የተማሪ ቤቱ ዲሬክተር ሙሴ ሹክሪ ባለፉት ዓመታትና በዚህ ዓመት ከስተማሪዎቹና ከተማሪዎቹ ተስማምተው እየሠሩ የተቀበሉትን ሥራ በትክክል ስላስኬዱ እናመሰግናቸዋለን። አስተማሪዎቹም ከተማሪዎቹ ተስማምተው በደስታ ስላስተማሩልን ልናመሰግናቸው ይገባናል።

የአፄ ምኒልክ ስም የትምህርትን ጥቅም በሚያውቁ ኢትዮጵያውያንና በመላው ኤውሮፓ የተመሰገነና የተከበረ ሆነ።

ጃንሆይ ።

ግርማዊነትዎ ጉልቍ የሌለውን ገንዘብዎን እያፈሰሱ ብዙ ልጆች ወደ ውጭ አገር ከመላክዎ በላይ እንዲሁም በኢትዮጵያ ብዙ ተማሪ ቤት ከማቆምዎ በላይ የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት እንዳይደክም የሚያስፈልገውን ሰጥተው ለሹማምንቱ የሚያተጋ ትእዛዝ በማስለፍዎ ያፄ ምኒልክ ነፍስ እንደምትመርቅዎ የታወቀ ነገር ነው ።

ይህ ተማሪ ቤት ባለፉት ዓመታት የብልሁ የዳግማዊ ምኒልክን ስም እንዳስጠራና እንዳስመሰገነ እንዲሁም ለትውልደ ትውልድ ገናናውን ስማቸውን ማስመስገኑ ጥርጥር የለውም። ስለዚህ ገንዘቡን ለተማሪ ቤት የሚያወጣ ሰው በጣም ደስ ይበለው ገንዘቡን ቢያጠፋ ስሙን ለዘለዓለም እንደማይረሳ አድርጓልና ግርማዊነታችሁ ብዙ ገንዘብ አፍሰው ያቆሟቸው ተማሪ ቤቶችም ለትውልደ ትውልድ ምስጉኑን ስማችሁ እንደሚያስጠሩ የታወቀ ነገር ነው ።

ማናቸውንም አገር ነፃነቱን ጠብቆ ለመኖር የሕዝቡ አንድነት ያስፈልገዋል። የሕዝቡን አንድነት ለማፅናት ደግሞ የሚያስፈልገው ትምህርት ነው ስለዚህ ሞላው ኢትዮጵያ ለትምህርት እንዲተጋ እግዚአብሔር ይርዳው ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር፥ ረጅም ዕድሜ ለጃንሆይ ዕድሜ ለእቴጌ፥ዕድሜ ለልዑል አልጋ ወራሽ ።

ቀጥሎ የትምህርት ቤቱ ዲረክቴር ሙሴ ሹክሪ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ጃንሆይ « በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች ስም ሁኜ ይህን ትንሽ በዓል ለማክበር ብለው ስለመጡልን ለግርማዊነትዎ ዋናውን የክብር ሰላምታችንንና እውነተኛ የሆነውን ወሮታ አለመርሳታችንን አቀርባለሁ ።

ደግሞም ለልዑል አልጋ ወራሽና ለልዑል መኰንን፥ ለልዑላት ወይዛዝር ለብፁዕ የኢትዮጵያ አቡን ለሚኒስትሮች ለሊቃውንቱና ለመኳንንትም ምስጋናችንን እናቀርባለን ለበዓሉ መምጣታቸው ተማሪዎቻችንን ለትምህርት ለማነቃቃት መስሎ ይታየናል ። መምጣታቸውም ለሥራ ያተጋቸዋል ጠንክርነትና ትዕግሥት ይሰጣቸዋል ።

የትምህርት ዓመት ፲፱፻፳፬ አሁን ተፈጸመ የዘጠኝ ወር ተኩል ሥራ ፍሬ ዛሬ እንናገራለን ይህ ተማሪ ቤት ብዙ ተማሪዎች አሉበት ይህን ዓመት ምንም ትምህርት ቤቶች ስለተለዋወጡ የተማሪዎቹ ቍጥር ፪፻፴ ነው።ይህ ቍጥር ምንም ትንሽ ቢሆን ትልቅ እንደሆነ ሊያዩት ይገባል ። ስለምን ቢሉ ይህን ዓመት ተማሪ ቤቱ የንግሊዝ ብቻ ስለሆነ ነው። ባለፈው ዓመት የፈረንሣዊና የንግሊዝ ክፍል ነበረው።የፈረንሣዊ ክፍል የነበረው ብዙ ተማሪዎች ነበሩበት የንግሊዝ ክፍል ግን

በጣም ጥቂት ነበሩ ተማሪዎቹ ። ስለዚህ ባለፈው ዓመት የተማሪዎቹ ቍጥር ፫፻፳፫ ነበር ።

የትምህርት ሚኒስቴር ከ፩፻ ለበለጡ ተማሪዎች የወር ቀለብ ይሰጥ ነበር ። ከነዚህም ልጆች የሚበልጡት ገንዘብን ለመቀበል ወሩ ሲደርስ ብቻ ነበር የሚመጡት ። ይህ ደመወዝ ስለቀረ ዛሬ ሠራተኞችና ትምህርት አፍቃሪ የሆኑ ተማሪዎች መጡልን ።

ምንም ይህ ሁሉ ስለተለዋወጠ የተማሪ ቤቱ ደግ ስም ጥቂትም አልተዋረደ ። ሁልጊዜ በሕዝቡ እንደተደነቀና እንደተመሰገነ ይኖራል ።

ይህ ሁሉ በመጨረሻው ደጋግ ዘመዶች ለውድ ልጆቻቸው ለኋላ ኑሮ የሚያዮቡ ይህን ተማሪ ቤት በመልካም መቀበላቸውና ማመስገናቸው ስለምን እንደሆነ ያስረዳል ።

በዚህ ዓመት ብዙ የሆኑ የኛ ተማሪዎች በትምህርት ቤትና በየሚኒስቴሩ ደጋግ ሥራ አግኝተዋል ከነዚህም ተማሪዎች ውሥጥ አቶ በላዮ ገብረ ሕይወትን የትምህርት ሚኒስቴር ኢንስፔክተር (ትምህርት የሚጐበኝ) የሆነውን ንጋቱ ማህሌንና ብዙ ወርቅ ማህሌን በውጪ አገር ክፍል ተማሪ ቤቶች ዲሬክተር የሆኑትን እንጠራለን ።

በሙሉ ልቦናችን እነዚህን ተማሪዎች እናመሰግናለን ። እውቀታቸውንም አይተው ሥራ ለሰጧቸው ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እናቀርባለን ። ዛሬ ይህንን ተማሪ ቤት ትተው ለሚወጡ ልጆችም ደግ የሆነ ቦታ እንዲያገኙ እንመኝላቸዋለን።

መንግሥታቸውም ደጋግ ሥራ እየሰጠ የተማሩትን ልጆች ብቁም ነገር ቦታ ማዋሉን ስላተረዳነ በጣም ደስ ይለናል ። ሕዝቡም አሁን ደግሞ ትምህርት የሚያአስፈልግ መሆኑን ተረዳው ። ልጆቹንም ወደተማሪ ቤት የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት ከተመረጡና ለሥራቸው እየሰጉ ሁል ጊዜ ለልጆቹ የሚያስቡ አስተማሪዎች ዘንድ እንዲማሩ ለመላክ ይፋጠናል ።

የተማሪዎቹ ቍጥር ሁልጊዜ ያድጋል ይልቁንም የጅማሪዎቹ ። ይህም ነገር ሁለት አዳዲስ ክፍሎች ለመክፈት አስገደደን፡ ለንግሊዝ ተማሪዎች የሚበዙት እነሱ ናቸውና ፫ክፍል ለኢጣልያ ተማሪዎች ግን ፪ክፍል እናደርጋለን።ከዚህ ቀደም የዛሬ ዓመት የኢትዮጵያን መንግሥት እንደለመንን ዛሬም አዳዲስ ክፍሎች እንዲሠሩልን ልመናችንን ለማስታወስ ደፈርን ።

የትምህርቱ ፕሮግራም በ፲፱፻፳፫ ዓ ም የተጻፈውን ይህን ዓመት አሻሽለነው ዘንድሮ እሱን እየተከተልን አስተማርን ለ፯ኛ ክፍል የሁለተኛ ዓይነት የመጨረሻ ክፍል ትምህርት አለበት ብዙ ከዚህ የወጡ ልጆች በየተማሪ ቤቶቹ አስተማሪ መሆናቸውን አይተን ላስተማሪነት የሚያስፈልግ ትምህርት ለ፯ኛ ክፍል ተማሪዎች ለማስተማር ይህ ዓመት ሲጀምር አስበን ከንግዲህም ወዲያ እያሰፋፋን ይህን የሚያስፈልግ ትምህርት እንድንቀጽልና ከንግዴህ ወዲያ ጃንሆይ በቶሎ ለሚከፍቷቸው ትምህርት ቤቶች ብዙ አስተማሪዎች እንድናቆይ ተስፋ እናደርጋለን ።

ከትምህርታቸውም በላይ እነዚህ የመጨረሻ ክፍል ተማሪዎች ሙሴ አቤርሶን የሚያስተምሩትን የደንብ ትምህርት ከባልንጀሮቻቸው ከተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋራ ይማሩ ነበር ።

ለመጨረሻ ክፍል ተማሪዎች ከ፱ ቍጥር ላይ ፳፰ ላገኙት የውቀታቸውን ደረጃ የሚነግር ወረቀት ሰጥተናቸዋል።ይህም የቀሩትን ባልንጀሮቻቸውን ያተጋቸዋል ። የሚመጣው ዓመት ሲያልቅ የትምህርት ሚኒስቴር ለኢትዮጵያውያን የመንግሥት ሴርቲፊክ ዲቱድ (የትምህርት ደረጃ መመስከሪያ ወረቀት) የሚባል የምስክር ወረቀት እንደውጪ አገር ሴርቲፊክ የሚሆን ለተማሪዎች ይሰጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

ከዚህ ቀደም በተማሪ ቤቱ የሌለውን የጅምናስቲክ መማሪያ አሠርተን ነበር ።

ሰኔ ሲገባም የጅምናስቲክ በዓል እናደርጋለን ብለን ተሰናድተን ነበር። ነገር ግን ለማድረግ የማይቻል ስለሆነ ቀረ ይህን ዓመት ተማሪዎቹ በትጋት አንድ ቀን ሳይቀሩ በመምጣታቸው በጣም ደስ ብሎናል። ይህም ትምህርት በግድ የሚያስፈልግና ዋጋ ያለው ነገር መሆኑን መረዳታቸውን ይነግረናል በቅኑ ልቦና እየታዘዙና መልካም ጠባይ እያሳዩን ከረሙ ይህም እነዚህ ተስፋ ያላቸው ልጆች ለኋላ ደጋግ ሥራ ማግኘታቸው ጥርጥር እንደሌለው ያሳየናል ።

ጃንሆይ ።

ይህም ሁሉ በእውቀት ከፍ ከፍ ማለትና የትምህርትን ጐዳና እውቀት እየዘራ ይህ ተማሪ ቤት መከተሉ ግርማዊነትዎ ትልቅ አጋርና አዳሽ ድጋፍ ስለሆነለት ነው ።

ዲሬክተሩ የክቡር የትምህርት ሚኒስቴር መልአከ ሕይወት ወልደሖና የደግነት ሥራና የሥራ ወዳዱን የክቡር ብላቴን ጌታ ማህሌ ፀዳሉ የትምህርት ዲሬክተር ዢኔራል ምትክ ያቶ ኪዳነ ማርያም አበራን ማጽናናት ሳያመሰግን ለማለፍ አይችልም።

ዲሬክተሩ በትጋትና በቅንነት ሥራቸውን የሚፈጽሙ አስተማሪዎቹን ደግ ሥራ ለመርሳት አይችልም። ለትምህርትና ለሥልጣኔ ስለለፉ ምስጋና ያቀርብላቸዋል። አንድ ጊዜ ስንኳ ቢሆን ከሰጠናቸው ሥራ ባልሆነ ጊዜ ውፎፊት ሳይሉ ይህን ዓመት ፈጸሙ ። ሁሉ ጊዜ ደከመን ሳይሉ በትጋትና በትዕግሥት የሚገባቸውን ሥራ ሠሩ ።

ጃንሆይ

ይህ ተማሪ ቤት በዕድሜ ከሁሉ የሚበልጠው ዋናው የብርሃን ምንጭ ሆነ ከዚህም የሚፈልቁ ብርሃናት ለዘለዓለም ሳይጠፉ ያበራሉ። በከበረውም አጋርነትዎ ይህ ተማሪ ቤት ትልቁ መሥራቹ ያሳየውን የእውቀት ጐዳና አልለቀቀም።ወደፊትም ከዚህ መንገድ አይወጣም። እዚህ ኢትዮጵያውያን ትልቅ መንግሥት ውስጥ እውቀትንና ጥበብን ለሕዝቡ እየሰጠ ለራሳቸውና ለውድ አገራቸው የሚጠቅሙ ሰዎች እያስተማረ የትልቁን የዳግማዊ ምኒልክን ሐሳብ ይከተላል።

ቀጥሎ የትምህርትና የጥበብ አማካሪ ፕሮፌሰር ምርክ የአሜሪካው ሰው የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ጃንሆይ

የመንግሥትዎ አገልጋይ ሁኜ ከምሠራው ሥራ በላይ ደግሞ ባለፉት ስድስት ወራት አንድ ትንሽ ክፍል ላስተማሪነት ሥራ የሚዘጋጁ ተማሪዎች አስተማርሁ ። በተማሪ ቤቶቻችን የውጭ አገር ሰዎች ሊያስተምሩ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልግና የሚቻል አይደለም ነገር ግን የገዛ ልጆቻችን የገዛ አገራቸውን እንዲያገለግሉ ማበረታታትና ሥራ መስጠት በጣም የሚያስፈልግ ነው ።

እርግጥ ነው በንደዚህ ያለ አጭር ጊዜ እኒህ ልጆች በሁሉ ክፍል የኢትዮጵያን ተማሪ ቤቶች ሊያስተምሩ ይችላሉ ብለን ለመመስከር አንደፍርም ስለሆነ ግን በዝቅተኞች ክፍሎች ሊያስተምሩ ይችላሉ ። የግርማዊነትዎ መንግሥትም ላስተማሪነት የሚያዘጋጅና የሚያሰናዳ ተማሪቤት እንዲቋቋምና እነዚህ ልጆችም እንደገና እዚያ ተመልሰው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ እንዲሁም ብዙ ሌሎች ተማሪዎች የተገባ ትምህርት እዚያ እንዲያገኙበት ትንዲደረግላቸው ምሉ ተስፋችን ነው ። ይህም ከቀን ብዛት ለመላ ኢትዮጵያ የገዛ ራስዋ ልጆች አስተማሪዎች ሁነው እንዲያገለግሉዋት የሚያበቃ መንገድ መሆኑ አይጠረጠርም ።

ስለዚህ እነዚህ ተማሪዎች ደበሳ ሳይዳ ደስታሁን አበራ ተወልደ ብርሃን ሐዲስ ኪዳነ ማርያም ለይኩን ማኅተመ ወርቅ አበተ ቀንአ ኔንቾ ኢጀታ ገብረ መስቀል ተገኝ ዮሴፍ ገብረ እብ ቢያድግልኝ ዳግም አበበ ብንቴ የሚባል ለጊዜው ከነርሱ ሲማር ኖሮ በመጨረሻ ግን ላስተማሪነት ሥራ ተፈልጎ የሔደ በግርማዊነትዎ ፊት ላቀርባቸው ስለ ተፈቀደልኝ ትልቅ ክብረት ሁኖ ይሰማኛል ። እነርሱም ለግርማዊነትዎና ለተወደደች አገራቸው ለኢትዮጵያም እውነተኞች አገልጋዮች እንዲሆኑ እየተመኘሁላቸው ነገሬን እወስናለሁ ።

ከዚህ በኋላ በትምህርት ለበለጡ ተማሮች ሽልማት ተሰጠ መጀመሪያ በ፯ኛው ክፍል ደስታሁን አበራ ፩ኛ ሆነና ከትምህርት ቤቱ መጻሕፍት። ከጃንሆይ የወርቅ ሰዓት ፤ ከቢትወደድ ጌታቸው አባተ ክብ የሚዞር የዓለም ካርታ ተሸለመ ።

ተወልደ ብርሃን ገብረ መድኅን ፪ኛ ሆነና ከትምህርት ቤቱ መጻሕፍት፤ ከጃንሆይ የብር ሰዓት ተሸለመ ።

ለይኩን ማኅተመወርቅ ፫ኛ ሆነና ከትምህርት ቤቱ መጻሕፍት። ከጃንሆይ የብር ሰዓት ተሸለመ ።

በ፮ኛው ክፍል

ጋድ ገብረ ክርስቶስ ፩ኛ ሆነና ከትምህርት ቤቱ መጻሕፍት፤ ከጃንሆይ የወርቅ ሰዓት ተሸለመ ።

መስፍን የበጋእሼት ፪ኛ ሆነና ከትምህርትቤቱ መጻሕፍት፤ ከጃንሆይ የብር ሰዓት ተሸለመ ።

ጣሰው አይችሉህም ፫ኛ ሆነና ከትምህርት ቤቱ መጻሕፍት፤ ከጃንሆይ የብር ሰዓት ተሸለመ።

በ፭ተኛው ክፍል ።

ጥበቡ ይገበሃል ፩ኛ ሆነና ከትምህርት ቤቱ መጻሕፍት ከጃንሆይ የወርቅ ሰዓት ተሸለመ ።

ቀጸላ ወልደሐዋርያት ፪ኛ ሆነና ከትምህርት ቤቱ መጻሕፍት፤ ከጃንሆይ የብር ሰዓት ተሸለመ።

ጌታቸው በላይነህ ፫ኛ ሆነና ከትምህርት ቤቱ መጻሕፍት ከጃንሆይ የብር ሰዓት ተሸለመ

በጅምናስቲክ ብልጫ ሽልማት ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጅምናስቲክ ለበጡ ተማሪዎች ደስ የሚያሰኝ ሽልማት ሰጡ የተማሪዎችም ስም ቀጥሎ የተጻፈው ነው

ተረፈ ነገሬ

ስለሺ ድፋባቸው ።

ጋድ ገብረ ክርስቶስ ።

ኃይሉ ኪዳነ ማርያም የታደሉት ልጆች እነዚህ ናቸው። ይልቁንም በማስተማር አገራቸውን ይረዳሉ ብለው ፕሮፌሰር ዎርክ የመሰከሩላቸው ልጆች ፲፪ ናቸው ። ስማቸውንም ፕሮፌሰር ዎርክ በአነበቡት ዲስኩር ጽፈናልና ሁለተኛ መጻፍ አያስፈልገንም ።

የትያትሩም ነገር እጅግ የሚያምር ነበር። ይልቁንም ትምህርት የሌላቸው በአላገርዎች በአለመሰማማት የአገኛቸውን ጉዳት ገልጾ በምሳሌ ሲአሳይ እጅግ ደስያሰኝ ነበር ጊዜውም እጅግ ብዙ ነበር የሌላውን እንጃ እንጂ ለእኛ ግን በተማሪ ቤት ጊዜ ማሳለፍ ብርቅ ሁኖብን ደስ እያለን ሳናውቀው ጊዜው አለፈ ጊዜአቸውን በተማሪቤት የሚአሳልፉ እንዴት የታደሉ ናቸው።

ዕድሜ ለዕድላሙ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ።

ትጥቃችንን ፈታን፤እንቅልፍ ጠገብን በየከተትና በመጋቢት እስከ ሚያዚያ ወር ጅማ ላሙንና በሬውን እየሸጠ የጦር መሣሪ መግዛት ገንዘብም ያጣ ብረት እየተከራየ እርስ በርሱ መጠፋፋት መንገደኛ መቀማት በከተማና በሀገር ቤትም ከሚጠብቁት ዘበኞች መግደል ሁኖ ነበረ ።

እኛም ይህ ሕዝብ በጠረኝነት ያልኖረ በርሸና በቡን መትከልና በንግድ ስመ ጥሩ የሆነ ባላባቱም እስከሕመማቸው ድረስ አምሳ አምስት ዓመት በታማኝነት ለመንግሥቱ ገበርሁ አገለገልሁ ይሉ ነበረ ከሕመማቸው ወዲህ ሦስት ዓመት መሆኑ ነው በድምር አምሳ ስምንት ዓመት ። ይልቁንም አገር ሳይሠለጥን የጋላ ነገድ ላማራ አንገዛም በማለት እየተዋጋ አገሩን ሲያስጠፋ የጅማው ባላባት በጐረቤታቸው ሐሳብና ምክር ሳይተበበሩ በሰላም የኖረ አገር አሁን በሰላሙ ዘመን አዳልና ሱማሌ እሩያና ዓዘብ ባረፈበት ጊዜ ባልተጠራበት ስም ስለተጠራ የጅማ ባላገር ሽፈተ ብለን ለማስታወቅ አፍረት ሆኖብን ከዛሬ ነገ ይሻለዋል በማለት ነጋድራስ ሣህሌም የሀገሩን ዋናዎችና እንደራሴውን አባ ቡሽን ጣቢን በየጊዜው በመምከር ብዙ ጊዜ አሳለፉ በኋላ ግን ነገሩ እየበዛ ስለ ሔደና ሒርማታ ከተማ ገብተው ተከተማው ዘበኞች አንድ ገድለው ሁለተኛውን አቍስለው ፪ኛም በዴዶ ክፍልም ከሚጠብቁት ዘበኞች ቤት ሲከድኑ ከገደሏቸው በኋላ እንደራሴውም አባ ቡሽን ጣቢ አገሩ መሸፈቱን ለከተማውና ለራሳቸውም ለነጋድራስ ሣህሌ ማስፈራቱን አስታውቀን ጃንሆይም ለሕዝባቸው ርኅራኄ

ያበዛሉና ከሊሙ ጦር ሦስት መቶ ወታደር አሳዝዘው የትንሣኤ ዕለት ተቤቱ ተነሥቶ በማግሥቱ ደረሰልን ከዛሬ ከነገ ከተማውን ሊመታው ነው ሲባል የትንሣኤ ዕለት እንኳን ሴትና ሽማሌ እንጂ ለርዳታ የሚችል ሁሉ በየደጃፍ መሣሯውን ይዞ ይጠባበቅ ነበጋ እንጂ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሔደ አልነበረም።ኋላም ጅጅቀን ሚያዝያ በአይሮፕላን የባላባቱን የልጅ ልጅና ግራዝማች አበበ ናቁን ላኩ ከዚህም በኋላ ሊቀመኳስ መኰንን ዋልቴ በነጦራቸው ሙጡ ባላባቱም በመጣ በ፬ኛው ቀን ውሻኔ ወደሚባለው ክፍል ሔዶ ሳምንት ሳይሞላው ሰማኒያ አምስት ሽፍታ መያዙንና ከነዚሁም አንዱን መስቀሉን እስታውቆአል፡ከ፡ዚሁም ከተያዙት ሰባ ያህል መጥተዋል ፈትም ያው ባላባቱ መርምሮአቸዋል ኋላም በግራዝማች አበበ ናቂ ተመርምረዋል በችሎትም ከተመረመሩት የየአንዳንዷን ቃል ሰምተነዋል ደሁን እንጂ ከዚህ በላይ እንደ ጻፍኩት ድማ ወትሮ ባልተጠራበት ስሙ ተለውጦ መጠራቱ እስከሁን አልተገለጸልንም ና እነዚህ የተያዙት አሥረኞች ሽፍቶች የተባሉት በብልሁ ንጉሥ ነገሥት ፊት ሲደርሱ ሦስተኛ ምርምር ሳይደረግ ይቀራል ብዬ አልጠረጥርምና እነዚህ ሽፍቶች የተባሉት አዲስ አበባ ደርሰው ይኸ የተሠወረው ምሥጢር መገለጫውን ለማየት እጥብቄ እመኛለሁ። ፪ኛም የሚገርመኝ ከዚህ በላይ ስማቸውን በጻፍኳቸው ወርዎች የሚጤ፥ የውሻኔ ፥ የዱዶ፥ የመንቾ ፥ የቤየም፥ የአክፈሌ ፥ የማና ባላገሮች ቤታችንን፥ እህላችንን ሽፍታ አቃጠለብን ላማችንን፥ በሬያችንን፥ በጋችንን አረደብን ሚስታችንን ልጃችንን ማረከብን ያድኑን እያለ ወደ ነጋድራስ ማህሌ ሁለትና ሦስት መቶ እየሆኑ ጥፋታችንን ይዩልን ለመንግሥትም ያስታውቁልን ሲሉ ከርመው ጃንሆይም ይኸንን ሁሉ ስለ ሰሙና ለድኃቸው ስለ አዘኑ ለኃይል ጥበቃ የሊሙን ጦርና ሊቀመኳስ መኰንን ዋልቴን ለምርምርና ላፍርሳታ ግራዝማች አበበ ናቄን ቢልኩ እንኳን እግራዝማች አበበ ችሎት አለመድዋቸውም እነጋድራስ ማህሌ ደጃፍ ጉዳቱንና ጥፋቱን ለማመልከት አንድ እንኳን ጋላ ባለ መምጣቱ እንደ አቶ ተሰማ እሸቴ ሙዚቃ ይህ ነገር ረቂቅ እኔ ዓጥሙ ጠፋብኝ እነዚህ የተያዙት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ችሎት መድረሳቸውን አስመኘኝ ይኸነንም ጠንካራ ሕመም መርምሮ ለማወቅ የሚችል ባለ ዲፕሎም ሐኪም ነው ባለ ዲፕሎሙም ሐኪም ሀብታቸውና ጥበባቸው እንደ ሰሎሞን የሆኑት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ናቸው እንጂ ሌላውስ ማነኛውም የፋርማሲ ሐኪም (መድኃኒት ሻጭ) መርምሮ ሊያገኘው አይችልም።

ያግሉ አባ ወሎ ።

ያገር ጉዳት ።

እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ትልቁ ሀብታችን እርሻና የከብት እርቢ ነበር ከርባ ሦስት ዓመት ወዲህ የመጣው ጉመደው ወተቴ የሚባል በሽታ የቀንዱን ከብት ስለፈጀው የእህል ሀብትም አብሮ አነሰ ። በተረፉት ከብቶችና በመቈፈሪያ (ዶማ) የበቀለውን እህልም ከ፫ ዓመት ወዲህ አንበጣ ስላጠፋው ትልቅ ጉዳት ሆነ ። በወሬ ስንሰማው የነበር ነውን አንበጣ አሁን በገሩ ሁሉ ተዘርቶ ባይናችን አየነው ። ወልቃይት፥ ጠገዴ፥ቀብቲያ፥ጃን ፈቀራ ፥ አርማጨሆ ዳዋ እስከ ጭልጋ ከመተማ በላይ ያለው አገር ሁሉ አውራ እህላቸው ማሽላ ነው ። ከሱ የሚበቅል ጥጥም ከማራ እስከ ትግሬ ፥ ደግሞ እስከ ሸዋ ድረስ አልብሰ ይኖራል የማሽላውም ስም ጅሄላ፥ ዙርዙራ (ዋንዚ)ቡሴ (ነጭ ማሽላ) ይባላል ። ምንም ምድሩ እህል አብቃይ ቢሆን ለተራበው አገር ተነግዶ ለነጋዴውና ለገበሬው ትርፍ ተገኝቶበት አያውቅም ። ስለዚህም ገበሮቹ ያመት ቀለብ ይበቃናል ብለው መጥነው ያርሳሉ ባለፈው ታኅሣሥ ትንግርት ያለው ወፍ ከዓረብ አገር ተነሥቶ በላይ የጠራናቸውን አገሮች ማሽላ አጠፋው ይህም ወፍ ድምቢጥ ያህላል መልኩ ቡላ፥ አፉ ቀይ ነው። ብዛቱም እንደአንበጣ ይሆናል ግን ያላየ አያምነኝም። ውኃ ጠጥቶ እህል በልቶ ሲነሣ ሰማይ የነጐድ ምድር የተናደ ይመስላል ። ስሙንም የዓረብ ወፍ ብለውታል ይህም ወፍ እንዳንበጣ በንድ ላይ ነውና የሚሔድ የሚያጠፋው መሣሪያ ባልጠፋም ይመስለኛል ።

በጥር ፯ ቀን እግር ጥሎኝ አርማጨሆ ላይ የዚህን ወፍ መዓት አየሁ ሴት ወንዱ ትልቅ ትንሹ ከበ ማሽላውን ሲከላከል ነበር ። እኛም የበሰለ የበሰለውን ብትቈርጡ ይልቅ አይሻልምን ብንላቸው ዛሬ ቅዳሜ አይደለምን አሉን ። ቀዳም ሥዑር ተብላ ከብሯ በትንሣኤ ወይም ሰንበተ ክርስቲያን መለወጡን እንደምታውቁት ነው ። በፍትሐ ነገሥት መሻሯን ስላወቅን ፥ ጌታችንም ዘበ አሐቲ በግዕት ወእመ ይእቲ ወድቀት በሰንበት ውሥተ ግብ አኮኑ ያእኅዛ ወያነሥኣ (ማቴ ምዕ ፲፪ ቍ ፲፩) አልፎም ሰንበትሰ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት ወአኮ ሰብእ በእንተ ሰንበት (ማር ፫ ።፳፯ ።) ያለውን አስበን እንዲህ አልናቸው ከንበጣ ከሳት የባሰ አጥፊ ሲመጣ ሰንበተ አይሁድና የወር ባል ስትቈጣጥሩ ቤተ ሰባችሁ በራብ ማለቁን አታውቁምን ወንድሞቼ አልኋቸው ። እነሱም ይህን ሰሙና ማጭድ ማጭዳቸውን ይዘው ከወፉ ጋራ መሻማት ጀመሩ በጥር ፰ቀን ስንከማር ሲነበብ የቅዳሚን መሻር ሰምተን ነበርና በነገታው ይህን በመምከራችን ቅር አላለነም ። ሀቡ ወይሁቡክሙ ወበመስፈርት ዘሰፈርክሙ ይሰፍሩ ለክሙ ሉቃ ፮ ፴፰ ወልቃይት ጠገዴ አርማጨሆ ዳር አገር በመሆናቸው እህል ከሩቅ አገር ባህያና በአጋሰስ ጭኖ መውሰድ አስቸጋሪ ስለሆነ ይኸው ከሌሎች ጋር በራብ መጨነቅ ይዘዋል።የኢትዮጵያን ጥቅሟን እንጂ ችጋሯን የማትሹ ሰዎች የነዚህን አገሮች ጭንቅ ልጽፍላችሁ ያሳሰበኝ ምክንያት ይህ ወፍ ተመልሶ አልሔደምና ከርሞ ሌላውን አገር ጨምሮ ያጠፋ እንደሆነ የባሰ ጉዳት እንዳይመጣብን ፍርሃት ስላደረብኝ ነው ።

ከ፫ ዓመት ወዲህ ቅጣት የበዛብን ምክንያቱ ምንድር ነው ብዬ ሽማግሎችን ብጠይቅ ዘከመ ፈቀደ ይገብር ወበከመ ሐለየ ይፌጽም።አልቦ ዘይክል ተዋሥኦቶ እኩሉም እስመ ዘአፍቀረ ይጌሥፅ ይሉኛል ደግሞ አንድ ሰው ዳኞቻችን ዘመቻ ሒደውሳሉ አገሩ ደፍርሶ እንደ ነበረ ታውቃላችሁ ኋላም ዳኛ እገኘኔ ብለን ደስ ብሎን ሳለ በሞተው ሰውና በጠፋው ዕቃ አፍርሳታ ይውጣ ተባለ ሰውም አንተ ደንጊያ እኔ ወፍ እሆናለሁ

እያለ እውነቱን ቀብረው በሐሰት ሰው አልቷልና የተገባ ቅጣታችንን ተቀብለናል።ወፍ ነን ላሉት ወፍ ሰድዋልና ደንጊያ ላሉት ደንጊያ ይሰዳል እኔም በልዋልሁበት ያማቹን በሬ በልቷል ብለው ስለአወጡኝ አሜቴ አገር ከወጣሀ እንዴት አደርጋለሁ ብለው አለከፈሉኝ።ተመስገን እግዚአብሔር ሁላችንን አስተካክለን እያለ አምርሮ ተናገረ ባልንጀራውም እውነትህ ነው ወደ ጋላዝመቱ ብለውን ሂደን ብዙዎች ሙተው ቀሩ የቀረነውም ገንዘባችን አልቆ ተመለስን ከቤትም በሬው ታርዶ ሰዋችን ሙቶ ቄዩን እኒያ በሰው ገንዘብ የከበሩትም ሰጋር በቅሎ ጭነው ከኖሩ ልብስ ላይ መልከም በርኖስ ደርበው ከደባባይ ዋሉ ሰውም እነሱን ብናጠጣ ከምን እንገባለን ሲል ድኖችን አበፈጀ ብሎ ተናገረ ። ይሄን ሰምተን ሲገርመን ሲደንቀን ሰነበተ በሰሞኑም የጥምቀት በዓል ነበረና ዕውር በመሬ እንከሚ በምርኩዝ አሽከር ዶጉ ከተሰበሰበበት ደረስሁ ከተቀደሰ በኋላ ሰው ሁሉ በደጅ ሰላሙ ተቀምጦ ሳለ ፎሰዎች ቄመው የእገሌን አገልጋይ ሰርቀን ሽጠን እንደሆን እናንተን ደጣላችሁ አለዚያ በሰት ያወጣነን ይጣልላችሁ ብላችሁ አጨብጭቡልን ብለው ተናገሩ ። ያለው ሁሉም በአንድ ቢያጨበጭብ ዛፉ የተሰበረ ቅጠሉም የረገፈ መሰለ ከነሱ አንዱን እንዴት አርገው በሐሰት አወጡህ ብለው ቢጠይቁት ከባለቤትየው ጋር ጠብ ነበረን የሰረቀው አገሩ ቢርቅ እነሱን አውጡልኝ ብሎ ስላባበላቸው በሐሰት አወጡን ብሎ መለሰልኝ ።

ይኸን ያህል ለተጨነቀ ሕዝብ የሚበጅ ነገር ለመጻፍ ዓቅም ስላጠረኝ ለብርሃንና ሰላም እንባቢች አበረክታለሁ ።

ጀምበር ቻላቸው በጥቃ ጎንደር ።

ሕገ መንግሥት የቆመበት በዓል መታሰቢያ

ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለሀገራቸው ለኢትዮጵያና ለሕዝባቸውም ከሠሩዋቸው ልዩ ልዩ መታሰቢያዎች እንደኛው ሐምሌ ፱ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት የቆመው ሕገ መንግሥት ነው።ይህም ሕገ መንግሥት ከቆመ ዘንድሮ ፲፱፻፳፬ ዓመ ምሕ ሐምሌ ፱ቀን አንድ ዓመት ሞላ ። ይህ ሕገ መንግሥት የቆመበትንም በዓል እኛ ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ ልናከብረውና መታሰብያነቱንም ከሁሉ ልናበልጠው የተገባ ዋና በዓል መሆኑን፤ዘንድሮም ሐምሌ፱ቀን በቤተ መንግሥቱና በሕዝቡ ዘንድ መከበሩን በበዓሉም ምክንያት ማተሚያ ቤት መዘጋቱን ለአንባቢዎች እናስታውቃለን ።

መልስ ።

ሰኔ ፪ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመት ብርሃንና ሰላም ቁጥር ፳፬ ገጽ ፻፹፫ እስከ ፻፹፯ ለተጻፈው ፍሬው ለሚያጠግብ ለጠራ ሐሳብ ሞገሴ ዳ ለጻፉቱ ከብዙ በጥቂቱ በሐሳቤ የመሰለኝን መልስ ከዚህ ቀጥዬ በማክበር አገልጣለሁ ።

፩ኛ ትምህርት በራሱ ምንድርነው? አእምሮ (እውቀት) ነው ።

፪ኛ የትምህርት ዓይነተኛው ፍሬ የቱ ነው? በእውቀትና በአእምሮው ሥራ መሥራት ነው ።

፫ኛ ሰው መማሩ ለምንድር ነው? ለማወቅና በዕውቀቱ ለመሥራት ነው ።

ለማን ሲል ነው መማሩ? ለራሱ ጥቅም ሲል ነው

ትምህርት አነጣጥሮ የሚነጣረን ነገሮች እነማን ናቸው? አእምሮንና (እውቀትን)

አእምሮ ተኵሮ የሚያየው የትምርት ዋና ይላማው ምንድር ነው? የልማትንና የጥፋትን መንገዳቸውን ለይቶ ማወቅ ነው

፬ኛ ሰው በመማሩና በማወቁ ምን ሁኖ እንዲታይ ነው? አዋቂ ሁኖ እንዲታይና እንዲከበር ነው ።

፭ኛ እውነት ስለ እውነትነቷ መፈለግ ይገባታልን ወይስ ለሰው ጥቅም በመሆንዋ ብቻ ሰው ይወቃት? ወይስ ይፈልጋት እውነትን ሰው ሁሉ ያውቃታልና እውነትን መፈለግ ይገባዋል ጥቅም ግን በድል ትገኛለች እንጂ በእውነት አትገኝም ።

፮ኛ እውነት ምንድ፡ ነው? እውነት በራሱ አለወይ እውነት ከሰው ከባሕርዩ ጋር የተፈጠረች ረቂቅ የዳኝነት መንፈስ ናት እንጂ እውነት በራሷ የለችም ።

፯ኛ ሰው ለሥራ ያሻልን ወይስ ሥራ ለሰው ይፈለጋል የሰው የተምርቱ የእውቀቱ መፈተኛ ሥራ ስለሆነ ሥራ ለሰው በግድ ያስፈልጋል። እንደዚሁ ሥራ መገለጫው በሰው ስለ ሆነ መገለጫ ሰው ያስፈልጋል ። ፪ቱም ትክክል ናቸው ሰው ያለሥራ ሰው አይደለም ሥራም ያለሰው ሥራ አይደለም ።

፰ኛ ከሀብት ከኃይል ከቸርነት ከውነት የሚያምር ነገር ከሁሉ ምንድርነው ከነዚህስ ማናቸው ያምራል ከነዚህ የሚያምር ነገር ኃይል ነው ቆንጆ ውብ የሚያምር ደስ የሚያሰኝ ከነዚህ ውስጥ ለአእምሮ የሚበልጥበት የቱ ነው የሚመረጥበት ምክንያት ዓይ የሚለው ምንድርነው? ለአእምሮ የሚበልጥበት እውነት ነው ዓይ የሚያስመርጠውም እውነት ከሰው ባሕርይ ጋር የተፈጠረች ረቂቅ የዳኝነት መንፈስ ስለሆነች የዓይ አእምሮ እውነትን አብልጣ ትመርጣለች ።

፱ኛ ሥራ ከትምህርት ጋር ኅብረት እንዲኖረው ግድ ይላል ? ወይስ ለትምህርት ከሥራ ጋር አንድ መሆን ይገባዋልን ሥራም ከትምህርት ጋር ትምህርትም ከሥራ ጋር አንድ ኅብረት መሆን ይገባቸዋል አንድም ናቸው እንዲሁ ሥራ ሠሪውን ባለቤቱ ከሌለበት ቦታ ያስመሰግነዋል ያስነቅፈዋልና ያለትምህርት የተሠራ ሁሉ ስሕተት አያጣም ስሕተትም የተነቀፈ ነው በትምህርት የተሠራ ይመሰገናል ።

፲ኛ ደምብ በሁሉ ላይ ሥልጣኑን አጥምዶ ይይዛልን ወይስ ሕግ ነውን ለሁሉ የሚገኝ ማናቸው ነው ሥልጣኑ ወሰን የሌለው ደንብና ሕግ አንድ ናቸው እነሱም ሀብታምና ድኃ ሳይለዩ በውስጣቸው የሚኖረውን ይጠብቃሉ ከነሱ የሚመጣውን አጥምደው ይይዛሉ የተያዘውም ሕግ ውጡ (እንባጡ) ተብሎ ይሰደባል ሥልጣኑ ወሰን የሌለው እግዚአብሔር ብቻ ነው

፲፩ኛ ሰው ሕግን ይጠብቃልን ወይስ ሕግ ሰውን ይጠብል? ሕግ (ደምብ) እንዳጥር እንደ ቤት ነው ሰው አጥሩን አጥሮ አጥብቆ ቤቱን አጥብቆ መሥርቶ ሠርቶ በውስጡ ሲኖር አጥሩ ከሌባ ከውሬ ቤቱ ከብርድ ከዝናብ እንደሚጠብቀው እንደዚሁ ሕግን ከጠበቁት ሰውን የሚጠብቅ ይሆናል ሰውም ሕግን እንደ አጥሩ ይጠብቀው ።

፫ኛ ሰው ጊዜን ይወስናልን ወይስ ጊዜ ሰውን ይወስነዋል ሰው በጊዜ ውስጥ ይገኛልን ወይስ ጊዜ በሰው ውስጥ ይገኛል እንደዚሁ ሰው ሲናገር ለሰሚው እንደሚሰሙት ሰው ጊዜዬን አደረስኩ ጊዜዬን ጨረስኩ ጊዜ አላሳልፍም ሲል ሰው በጊዜውላይ ጊዜን ለመወሰን ይችል ይመስላል እውነቱ ጊዜ ሰውን ይወስነዋል ሰው ከጊዜ አያልፍም ጊዜ ወስኖታልና ሰውም በጊዜ ውስጥ ተገኘ በጊዜ ውስጥ ተወልዶ በጊዜ ውስጥ ሞቷልና ጊዜም በሰው ሕይወት ውስጥ ይገኝ ነበር ይኸን የምሰራበት ጊዜ አገኘሁ ጊዜ አጣሁ ሲል ይሰማልና ።

የብርሃንና ሰላም ክቡራን አንባቢዎችና ተመልካቾች ሆይ ይኸ የጥያቄ መልስ ለኔ እንግዳ ሁኖ ለፈላስፎች የታወቀ መሆኑን አውቃለሁ የመልሱን አለመቀልጠፍ አይታችሁ አትፍረዱ ለሰው ሐሳቡ ወሰን የለውምና ይቅርታ እለምናለሁ ።

ኃይለ ጊዮርጊስ ።

ማስታወቂያ ።

ወይን ጠጅ ።



በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባየሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ዊስኪ ካምቤል ማለፊያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው ።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አሁን አዲስ የክትባት ክፍል አቁሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የክትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ ፥ የደረት የጕበት ፥ የኩላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቁቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የድን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርክፍ ቤት ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም አንዱ አርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን እንድ ቀን እየተዋበች ሔዶች ቀጥሎም እንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቀረጥ መስፋትና መጥለፍ፡ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙ፣ ደምቡንና ትምህርቱ፣ እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ግዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ላመንበኝ ።

ማስታወቂያ ።

የዕንጨት አሰናጂ ሙሴ ባዚል አስላንዲስ የዕንጨት ማስቀመጫና የዕንጨት መለንጠቂያ ያለበት አዲሱ ቤታቸው በቅዱስ ጊዮርጊስ መንገድ በሙሴ ሀልኩሲ ሰሙና መሸጫ ቤት አጠገብ መሆኑን ለሚፈልጉ ሰዎች

በማክበር ያስታውቃል። ዋጋው ቀላል የሆነ ማለፊያነቱ የበለጠ ነው ።

ገናው አሰናጂ ባዚል አስላኒዲስ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድዩ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቊጥር ፴
8me ANNE. № 30

ሐሙስ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 21 JUILLET 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣጥት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የጃንሆይ የልደት በዓል ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተወለዱበት በሐምሌ ፲፮ ቀን ስለሆነ እንኳን ከዚህ አደረስዎ ለማለት የሚመጡትን የውጭ አገር ሰዎች በዚሁ ቀን ቀዳሚት በ፭ት ሰዓት ከሦስት ሩብ በቤተ መንግሥት ይቀበላሉ። ዕድሜአቸውም ፵ ዓመት መልቶ ፵፩ኛው ዓመት መጀመሩ ነው።

A l'ocasion de l'Anniversaire de Sa Majesté l Empereur Haïle-Sellassié Ier une reception officielle aura lieu au Palais Impérial le 23 courant samedi à 11 h. 45 du matin.

ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ልደት።

በ፲፰፻፹፬ ዓ ም መስከረም ፩ቀን ቅዱስ ዮሐንስ ዓርብ ውሎ ነበረ ። ፩ዓበቅቴ ፳፱ መጥቅዕ ፲ሌሊት ፯ ጨረቃ ሁኖ ውሎ ነበረ ።

የሐምሌ ልደታ ሐሙስ ነበረች ። ሐሙስ ለሐሙስ ፳ ሐሙስ ለሐሙስ ፲፭ ዓርብ ፲፮ ቀን ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን በተቀበለችበት ቀን አዳም አባታችን በተፈጠረበት ዕለት ለኢትዮጵያ ብርሃኑዋ ለሕዝቧ ረዳት የሚሆኑ ተወለዱልን። አሁን ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ዮሐንስ ፵ዓመት ሆነ ተፈጸመ ። ይህን ፵ዓመት መፈጸሙን ያሳየን አምላክ ይክበር ይመስገን ።

ዳግም እንደዛሬው ሁሉ የዘውዱን በዓል ፵ዓመት ለማየት ያብቃን ስል ምኞቴን እገልጻለሁ ።

ቁም ጸሐፊ ገብረጻድቅ።

ያማረ ምላሽ ።

አስቀድመን እንዳስታወቅናችሁ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጃቸውን ልዕልት ዘነበ ወርቅን ለደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ በሕግ በሥርዓት ድረው ነበርና የምላሹ ቀን ዋናው በሐምሌ ፲፩ቀን ስለሆነ በዚሁ ቀን የትያትር ጨዋታ እንዲያሳዩ የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎችና የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪዎች የቀጠሮ ሰዓት ተቀብለው ነበሩና በዚያው በተቀጠረው ሰዓት የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር መልአክ ሕይወት ወልደሐና ለትያትር ጨዋታ የተሰናዱትን ተማሪዎች ሰብስበው በታላቁ ቤተ መንግሥት ይጠባበቁ ነበር ። የቀጠሮውም ሰዓት ከማታው በ፪ት ሰዓት ነበርና ልክ በተቀጠረው ሰዓት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ ግርማዊት እቴጌ መነን በተዘጋጀው መንበረ ዳዊት ተቀመጡ። ሙሽሮችና ልዑላን መሳፍንት፥ ልዑላት ወይዛዝር፥ ክቡራን መኳንንት ገብተው በየማዕርጋቸው ተቀመጡ ። ከዚህ በኋላ አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ያዘጋጀውን ትያትር የሠለጠኑ ተማሪዎች ጀመሩ። የትያትሩንም አኳኋን ከፍለን ጽፈነዋል

አባት ፥ የተወደድኸ ልጄ መስፍን ሆይ እግዚአብሔር ብዙ ተባዙ ብሎ በተናገረው ቃል ኪዳን አባቴ እኔን ከወለዱኝ በኋላ እንዳይርበኝ አብልተው እንዳይጠማኝ አጠጥተው እንዳይበርደኝ አልብሰው በሕፃንነቴ ወራት የሚአስፈልገኝን ሁሉ ሰጥተው ይልቁንም ከአደግሁ በኋላ ሰውነቴን ረድቼ ለወዳጆቼ የምጠቀምበትን የንባብና የጽሕፈት ትምህርት እያስተማሩ ስለ አሳደጉኝ እኔም በእርጅናቸው ወራት እየረዳሁና እየጦርሁ በሚፈልጉት ነገር ሁሉ ደስ እያሰኘሁ ብድራቸውን መመለስ ይገባኝ ነበረ ።

ነገር ግን ምንም ሕፃን አእምሮ ባልሆን እኔ ከሕፃንነት ወደ ጉልማስነት ሳልደርስ እርሳቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ወደ ወዲያኛው ዓለም ስለ መሔዳቸው ብድራቸውን ሳልመልስ ቀረሁ ።

የተወደድህ ልጄ ሆይ

አባቴ እስከአሁን ቈይተው ቢሆን አንተንና እኅትህን ደስታን ከመውለድ አስቀድሜ እናታችሁን ወይዘሮ መታፈሻዬን ሳገባ ንብረት ስይዝና ለዚህ እናንተ ለምታዩት ሁሉ ስበቃ እናንተን ስወልድም አባቴ አይተውኝ ቢሆን ያ በዕድሜ የአረጀው ሰውነታቸው አንተንና ደስታን በማየት ይታደስ ነበረ ። መስፍን ሰማህ ?

መስፍን ፡ አቤት

አባት ፡ ደስታን ብትጠብቃት ትጠብቅሃለችና አትለያት።

ደስታ

ደስታ ፡ አቤት

አባት ፡ መስፍን ወደ ፊት ሥራ ሳይበዛበት አይቀርምና ከቤትሽ ሳይመጣ ውሎ የአደረ እንደሆነ ምን ሆነና ሳይጠይቀኝ ቀረ ብለሽ አስቢ እንጂ ችላ አትበይው ። ብትጠብቂው ይጠብቅሻል ። አንተም እንዲሁ ብትጠብቃት ትጠብቅሃለችና በበጎ ነገር ተጠባበቁ ። እንግዲህ ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስ ። የእናንተ ፍቅር አዘነጋኝና የትልቅ አባቴን የአቶ ደጉን ነገር አስረሳኝ ።

መስፍን ፡ አባት ሆይ አሁን እንደ ነገሩን ቃል ትልቅ አባትዎ አቶ ደጉ ስቅቅ ብለው ተጨንቀው የአሳደጉዎ መሆናቸውን ምንም ለጊዜው ባንኖር በአሳባችን እናውቀዋለን ። ሲአሳድጉዎ ቢመችዎ እኛንም እንዲሁ ሲአሳድጉን በመመቸትዎ እንረዳዋለን አባት ሆይ አባት ሳለ ለልጅ ተረት አይገባውም ።

ወ መታፈሪያ ፡ እኔ ከዚህ የበለጠ ምን እመክራችኋለሁ ወንድ ልጅ በትምህርቱ ጥቂት እውቀት የአገኘ እንደሆነ ከባሕርዩ በንጹሕ ጠባይዕ የአገኘው እውቀቱ ይረዳዋልና ከወንዱ ልጄ ከመስፍን ይልቅ ለሴቲቱ ልጄ በምክር ብዙ ልረዳት ይገባኛል ።

ልጄ ሆይ ደስታ አካላችሁና ልብሳችሁም ሁሉ ዘወትር ንጹሕ ይሁን ። እጃችሁን ለሥራ ዓይናችሁን ለማየት ጆሮዋችሁን ለመስማት ፈጣኖች አድርጉ ። አንቺ ያልነገሩሽን አትስሚ ያልጠየቁሽን አትመልሺ ንብረትሽ ሁሉ ጠቅላላ ይሁን የምትተኚበት አልጋና የምትቀመጭበት ስፍራ ሁሉ ከእድፍና ከጉድፍ ሁሉ ንጹሕ ይሁን ። በእውነትና በሚገባ ነገር ሁሉ ይሉኝታ አትፍሪ ።

ልጆቼ ሆይ እግዚአብሔር የሚቀየምበት ንጉሥ የሚቈጣበት ሰው የሚጠሉበት ነገር ካልሆነ በቀር ያሰባችሁትንነገር ለማድረግ አትመለሱ።ነገር ግን በዚህ ዓለም ለሥጋችሁጥቅም በወዲያኛው ዓለም ለነፍሳችሁ ጥቅም የሚሆን ነገር ካልሆነ በቀር ሰውነታችሁን ብዙ አታድክሙ።

ልጄ ሆይ ሚስትህና ልጆችህ ቤተ ሰዎችህም ያለ ሥርዓት ሲኖሩ ዝም አትበላቸው ። ነገር ግን ጨካኝና ቁጡ አትሁን ። ሚስትህ ልባም የሆነች እንደሆነ የቤትህን ሥርዓት ሁሉ ለእርሷ ልቀቅና አንተ በውጭ ሥራህን አሳምር ። አንተ የውጭውን እርስዋ የውስጡን የሠራችሁ እንደሆነ ንብረታችሁ ይቀናል ያሰባችሁትም ሁሉ ይፈጸማል ።

ደስታ ፡ በእናንተው በአባትና በእናቴ ፈቃድ ተማሪ ቤት ከገባሁ ጀምሬ እስከ ዛሬ በተማሪ ቤት ብዙ የተሻለ ነገር አገኘሁ ።

የብልህ ልቡና እውቀት ሲሻ አባትና እናቱን ሲአከብር ሕይቱ አጥንቱ ለመለመ ።

፪ተኛ ወርቅን ዕንቍን በብዙ ገንዘብ ከመግዛት ጥበብን መግዛት ይበልጣል ሲል ሰማሁት ።

፫ኛ ምክር ከሌላ ዘንድ አሳብ ይበተናል ልቡ የሚያሳዝንና አሳብ የሚያበዛ ሰውም ሁሉ ዘመኑ የከፋች እንዳትሆን ምንም ቢከፋው ሁል ጊዜ ደስታ የተመላ ሁኖ መገኘት ማለፊያ ነው ሲል ሰምቼ እጅግ ደስ አለኝ ።

መስፍን ፡ እውነት ነው ይህነን ያህል ማስተዋል ከአገኘሽ በዚህ ላይ ምንም ብዙ ትምህርት ባይኖርሽ የሚበቃ እውቀት አለሽና እግዚአብሔር በቸርነቱ መልካም አካሔድ የሚራመድ ባል የሰጠሽ እንደሆነ ደህና ንብረት ትይዣለሽ ይልቁንም ዘርቼ ለመቃም ወልጄ ለመሳም እንጂ የሚገባው ቢሆንስ አባት የአበጀው ለልጅ ይበጀው ማለቱን ለመናገር በደፈርሁ ነበር ። በዕድሜአቸውማ ቈይተውልን ቢሆን ፡ ከአባት በላይ አባት ስናገኝ አዬ ደስታ ድንቅ የሆነ ደስታ ነበረ። ደስታ አንቺ እንዴት በሆንሽ ።

ደስታ ፡ እኔማ ደስታ በዘመኔ ኑረውልኝ ቢሆን ሌላም በአልፈለግሁ ነበር ጠዋት ስወጣ ማታ ስገባ በረከታቸውን እየተቀበልሁ እንኳን ራሴን እናንተንም በአስጠቀምኋችሁ ነበረ ። ልቤም እንደ መልካም አምባ በታመነባቸው ነበረ ።

አባት፡አዎን የእግዚአብሔር አሳብና የሰው አሳብ እንደ ሰማይና እንደ ምድር የተራራቀ ነውና እርሱ የተቀደሰውን አሳቡን አድርጎ በኋለኛው ቀን እስትንገናኝድረስ በዚህ ዓለም የእኔን ደስታ ሳያዩ እኔም አሳቸውን ደስ ሳላሰኛቸው ተለያይተን ቀረን ።

የተወደዳችሁ ልጆቼ ሆይ አባቴ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ስለ እኔ በደከሙት ድካም ሁሉ እኔ አሁን በሰማይ ወሮታቸውን ለመመለስ የማይቻለኝ ሆነ ።

ስለዚህ ቀድሞ በርሳቸው ብርታትና ድካም ተምሬ በአገኘሁት እውቀት የሚጠቅም ምክሬን ሰጥቻችኋለሁ ።

እማከሬ፡ስለ እናንተም ይህን ምክር አስበው መስጠታቸው እግዚአብሔር ያሰበላችሁ ዘመን በአጭሩም እንደሆነ በረጅሙም እንደሆነ አውቀዉት አደለም ነገር ግን አሳቸው ያሰቡትን ያድርጉላችሁና እግዚአብሔር ደግሞ ያሰበውን ያድርግላችሁ ።

ሰው አሳቢ ነው ። እግዚአብሔር ግን አድራጊ ነው ። ሰው ጀማሪ ነው እግዚአብሔር ግን ፈጻሚ ነው ።

አባት ፡ ልጆቼ ሆይ በወዳጆቻችሁ ላይ ነውር ያገኛችሁበት እንደሆነ ለብቻው አድርጋችሁ ንገሩት ለሌላ ሰው ግን አትንገሩበት ። ብዙ ተድላ ለማድረግ አትጨነቁ ። ይህነን ለማድረግ የፈለጋችሁ እንደሆነ ግን ለሰው መራራትን ደግነትን አታገኙዋቸውም ።

እማከሬ ፡ ልጆቼ ሆይ በየጊዜውም በሰውነታችሁ ውሥጥ የሚነሣውን አሳብ ደግና ክፉ መሆኑን ሳትመረምሩ ። የአሰባችሁትን ሁሉ ለመፈጸም አትቸኩሉ ። ለዚህ ያልቸኰላችሁ እንደሆነ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁ በረከት እጅግ መልካም ይሆናል ። ከስጦታውም ሁሉ ሚስትና ልጆች መስጠቱ እንዲበልጥ እወቁ ።

አባት ፡ በተረፈ እናታችሁ ትንገራችሁ አብቃኝ ብለሽ ፈጣሪሽን ለምኝው ለንስሐ ሞት አብቃኝ በይው ዕድሜ ለንስሐ ስጠኝ ብትይው ይሻል ይመስለኛል ።

አማክሪ ፡ አደለም አደለም። ልጄ ሆይ ለንስሐ ዕድሜ ስጠኝ ብሎ ወደ እግዚአብሔር መለመን ደግነት እንዳይመስልህ አስብና ተናገር ፤

ነገር ግን ለንስሐ ዕድሜ ስጠኝ ብሎ መለመን በሕፃንነቱ ወራት እንደ ልቤ ያሰብሁትን ሁሉ ስሠራ ኑሬ፤ ስሽመግልና ኃጢአትን ለመሥራት ጉልበቴ ሲደክም ያን ጊዜ ንስሓ እገባለሁ ማለት ነው ፤

ትርጓሜውንም ገልጩ ብነግርህ ለንስሓ ዕድሜ ስጠኝ ብሎ መለመን የዚህን ዓለም ተድላና ደስታ ፍትወቱንም ሁሉ ሳልጠግበው አትግደለኝ ማለት ነው ፤

ወ መታፈሪያ ፤ ልጄ ሆይ አሁን እሳቸው እንደነገሩህ ከሚስትህና ከልጆችህ ከወዳጅህና ከዘመድህ ጋራ በዚህ ዓለም ደስ ብሎህ እንድትኖር፡ ዕድሜ ስጠኝ ብለህ ለምን እንጂ ለንስሓ ዕድሜ ስጠኝ ብለህ አትለምን ፤

ሲሽመግሉና ሲደክሙም ኃጢአት መሥራትን መተው የሚያጸድቅ አይምሰልህ ፤

ሰውም ተወልዶ እስቲሞት ድረስ ምንም ቢሆን ከኃጢአት ንጹሕ ሁኖ አይገኝምና በየጊዜው ንስሓ ግባ እንጂ፤ ለንስሓ የሽምግልና ጊዜ ብቻ አትጠብቅ ፤

አሽከር ፡ መዝጊያ መታ ፤

መስፍን ፡ ማነህ? ግባ ፡

ትእዛዝ ፡ አሽከር ገባና ወረቀቱን ለመስፍን ሰጠው፡

መስፍን ፡ በደብዳቤ አምበሎጥ ላይ የተጻፈ የርስዎ ስም ነው ፤

አባት ፡ እሱ አምጥቶ ለእኔ ሰጠኝ ከየት መጥተሃል? ወዳጄ ፤

አሽከር ፡ ከምድያም ነው የመጣሁት ፤

አባት ፡ ምነው በደኅና ትጠይቀኛለህ ?

አሽከር ፡ የእንበረም ልጅ ሙሴ ይህን ደብዳቤ ወስደህ ስጥ ብሎኝ መጣሁ ፤

አባት ፡ ከብትም ልጆችም ቤትም ሁሉ ደኅና ናቸው ?

አሽከር ፡ ደኅና ናቸው። እግዚአብሔር ይመስገን ።

ትእዛዝ ፡ አባት ወረቀቱን ቀደደና አየ ፤

አባት ፡ እረ በል ?

አሽከር ፡ አቤት ፤

አባት ፡ የሠርግ በዓል አድርገን ሰነበትን ይለኛል። የማን ሠርግ ኑሩዋል ?

አሽከር ፡ ወይዘሮ ትስብእት ወልድን ድረን እንዲሁ በተድላ በደስታ ሰነበትን ፤

አባት ፡ ለማን ዳራችኋት ወዳጄ?

አሽከር ፡ መለከት አካላዊ ቃል አገባት ፤

አባት ፡ አይ አጅሬ አገባትና አረፈ ? በዚህ ነገር እንዴት እንዴት ደክሟል መሰለሽሰላይ ያልሆነ ሰው ያልተላከ ሽማግሌ አይገኝም። እነኢሳይያስ ትያለሽ ዳንኤል እነ ናታን ትያለሽ ምን ስንቱን ልቍጠረው? የቀረውስ ይቆይና ንጉሡ ዳዊት እንኳ አልቀረም። እነ ሕዝቅኤል ትያለሽ ማን ቀርቷል

ወ መታፈሪያ ፡ ዳዊትም ንጉሡ ተልኮ ኑሩዋል

አባት ፡ ሰሎሞንም ልጁ አልቀረም፤ ራሱ ሙሴ ይህን ደብዳቤ የጻፈልኝ ሰው እንደ ወተወተ ይኖር ነበር ። ዘካርያስ ሳይቀር ተቈጥሮ ፡ የአፉ መፍቻ አደረጋት ወይ ታሪክ ወይ ግሩም ድንቅ ነውከ ።

ደግሞ የሚላከው ሽማግሌ ሁሉ አቤት ሲደርስ እኩሉ በአሽሙር ተናግሮ ይሸሻል፡ እኩሉ ደግሞ ባይደፍርም እንደ ነገሩ ተናግሮ ይመለሳል፡ ከተላከው ሽማግሌ ሁሉ እንደ ኢሳይያስ ደፍሮ እውነቱን የተናገረ የለም ፡

አባት ፡ እህ ወዳጄ ፡

አሽከር ፡ እንዲህ ሆነ ጌታዬ ።

አባት ፡ የሚጠጣው አምጣለት ፡

ሠርገኛው ብዙ ኑሩዋል ወይስ በልክ ነው ?

አሽከር ፡ ቤቱን ሞልቶ የሰነበተ የእኛው የሴት ወገን ነው እንጂ፡ ሙሽራው መለከትስ ምንም አላስከተለም። ፩ድ አሽከር ብቻ ተከትሎ መጥቶ በጆሮም በምንም ይነጋገር ነበር አየ ሙሽራ ዓይነ ደረቅ እንዲህ የአለ አላየሁም፡ አባቱ ብዙ ቤት አለኝ እያለ እየተናገረ እሱ መጥቶ ቄጣስር ገባና እኛ ቤት ቁጭ አለ፤ ምንም አያፍርም ፤

አባት ፡ የሠርጉ ቀን ከተደረገ ስንት ቀን ሆነ ?

አሽከር ፡ ፩ድ ዓመት ከ፱ወር ከ፳፬ቀን ሆነ ፡

አባት ፡ ታድያስ እስከ ዛሬ እዚሁ እናንተው ቤት ቄጣስር እንደገባ ነው ፩ድ ዓመት ከ፱ወር ከ፳፬ቀን ሙሉ ፡

አሽከር ፤ ወንዴ አባቱ ከሣራ አይወድም። ልጁም እሱ አባቱን አክባሪ ነው፡ ይህ የድግስ ቀን ሲአልፍለት ወይዘሮ ትስብእት ወልድን ያዘና ወደ አባቱ ቤት ተጓዘ። ለጊዜውማ አባቱ በእግሬ የረገጥሁትን በእጄ የጨበጥሁትን ለልጄ ሰጥቼዋለሁ አለ። ልጁም የአባቴ ገንዘብ ሁሉ የእኔ ነው አለ። ይህን ሁሉ ወደ ኋላው አስቀመጠና የእኛን ሲበላ ከርሞ ሔደ። ቢያዩት ብልጥ ነው ።

አባት ፡ እሱ መቼም አለ አንድ አሽከር አልተከተለውም የጋብቻውን ምሥጢር ቃል በቃል ተነጋገሩት እንጂ ለማንም አላወራም ተብሎ ተጽፎ ደብዳቤውን አነበብሁት። አንተም ነገርኸኝ ።

አባቱ ሰማይን ያህል አገር ሲገዛ ያ፩ድ አለቃ ጭፍራ እንዴት ከለከለውና ብቻውን መጥቶ ተስማማ ወይስ አሽከር የለው ይሆን እንዴት ነው ጥበቡ ፡

አሽከር፤ ፺፱ የሚሆኑ ቱርክ ባሾች አሉት። ያውስ እነዚህ ፺፱ኙ፻ቱርክ ባሾች እሳት ለብሰው እሳት ጐርሰው ብቅ ሲሉ አንዱን አንዱ እየሰነጠቀው ሲተላለፉ የማይተያዩ ያዘዙአቸውን ከዓይን ጥቅሻ ፈጥነው የሚያዘጋጁ ናቸዋ እንዲህ መሰለም ።

መስፍን ፤ የወታደር ቤት ነው ተውሸቱም ትንሽ ትንሽ ትቀላቅላላችሁ መሰለኝ። ለአንድ የጭፍራ አለቃ ብሎ ምን አሳፈረው ፺፱ ከማድረጉ መቶ አይሞላቸውም ኑሩዋል እውነት ተሆን እስቲ ።

አሽከር፤ አንተም እውነትህ ነው አይተማመኑምና ተቍጥር ባያገባው ነው እንጂ መኖሩን አለ ማጥፋት ያሰበ እንደሆነ

አንድ አንድ ቀን እሱን ይልከዋል እልም አድርጎ አጥፍቶ ይመለሳል እሱ የሚታመን አደለም በአስቀመጡት ቦታ አይገኝም ። ከዳተኛ ነው ። ስለዚህ ከቀኖር አይገባም ይላሉ ። እሱ ቢቄጠር መቶ ይሆናሉ ፡ እኔ ወንድሚ የሴት ወገን ነኝ ነገራቸውንም ሁሉ አላሙቀውም ትፈልጉ እንደሆን የእኛን ቤት ወሬ ጠይቁኝና ልመልስላችሁ ። በተረፈ እማላውቀው ቤት አግቡታችሁ አታስቀባጥሩኝ ።

ወ መታፈሪያ፤ እውነቱ ነው የእናንተ ወገን የትስብእተ ወልድ ዘመድ በሙሉ ተጠርቶ ኑሩዋልን ።

አሽከር፤ እንዴታ መቶ ሐያ ሰው ተጠርቶ ነበረ ። ከዚሁ ከመቶ ሐያ ሰው ፴፪ቱ ሴቶች ነበሩ ። አሸበል ና ገዳሚ ሲሉ ሰነበቱ ። ወደ አለማየት አሁን እክ ከናንተ ጋራ ያለሁ ይመስላችኋል ። እናንተ ባታዩት ነው እንጂ ልቤ ሐዷል ።

አባት፤የወይዘሮ ትስብእተ ወልድ የነገር አባት ማኑሩእል።

አሽከር፡የወይዘሮ ትስብእተ ወልድ የነገር አባት የእኔ ጌታ ሙሴ ነበረ ። የአካላዊ ቃል የነገር አባት ማነው? አምጣልኝ አባክህ ።

አሽከር ዳንኤል ነው ዳንኤል ።

አሽከር አዎን ዳንኤል ነው ዳንኤል ዳንኤል መቼም ጎልፈተ ዓለም መሰለ ሠርግ እንዲህ አድርጎ ሲደምቅ አይቼ አላውቅም ለደኅንነት ያድርጋላቸው ።

ደግሞ ያ ጳውሎስ የሚሉ ሰው ነበረ ። በሽምፓኝ ጊዜ ዲስኩሩን ለቀቀና ቢተወው የተሰበሰበው ሁሉ አፉን እየከፈተ መመልከት ሆነ የሚመልስ ጠፋ ።

መስፍን ፡ እስቲ የተናገረውን ዲስኩር ንገረን ።

አሽከር ፡ ምን ቸገረኝ። ይሀቺማ የምናውቅበት አደለችም።

ልጆቼ ሆይ ብሎ ጀመረ ።

እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋራ ሥራችሁን በትሕትና ጀምሩ ። ምእመናን ለክርስቶስ እንደሚገዙ እናንተም ሴቶች ለባሎቻችሁ ተገዙ አለ። አውቃችኋልን ለመርዓዊና ለመርዓት ነውኮ ይህ ዲስኩር ።

ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ራስዋ እንደሆነ ለሴትም ራስዋ ባሏ ነውና እናንተም ሴቶች ለባሎቻችሁ ተገዙ ብሎ በየነ ።

እህህ ወይ ዋዛ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን እንደ ወደዳት እናንተም ወንዶች ልጆቼ ሚስታችሁን ውደዱ ብሎ ደግሞ በወንዶቹ ዘወር አለባቸው ሚስቱን የወደደ ራሱን ወደደ። ከቶ ምን ቢሆን ራሱን መጥላት የሚቻለው ሰው የለም ።

ሆሆይ ይህ የመርዓዊና የመርዓት ተዋሕዶ እንዴት ያለ ታላቅ ምሥጢር ነው ግን ለክርስቶስና ለምእመናን ምሳሌ አደርገዋለሁ ።

እናንተ ልጆችም ለአባትና ለእናታችሁ ተገዙ ። ለአባት ለእናታችሁ መገዛት የሚጠቅም ሥርዓት ነው በአሪት የመጀመሪያው ሥርዓት አባት እናትህን ማክበር ነው ብሎ ሲናገር የኤፌሶን ሰዎች በሙሉ ተቀምጠው ይሰሙት ነበርና የነገሩ መከናወን ፡ የአንደበቱ መቀልጠፍ ፡ መቼም ሌላ ነው ፡ በዚህ ጊዜ ዳር እስከ ዳር ጭብጨባው ቀለጠ ።

አሽከር ፡ ይህስ አሁንም ያስጨበጭባል ።

ትእዛዝ ተጨበጨበ ።

አሽከር ፡ እንዲህ ተሆነ በኋላ የተዘፈነውን ዘፈን ብትሰሙት ልብ ይሠርቃል አዬ ለዛ አዬ ውበት እኔ አይቼ አላውቅም ።

መስፍን ፡ እንዴት ያለኸው እፈ ጮማ ነህ ወንድሜ እስቲ እስቲ ተዘፈኒቱ ጥቂት አክፍለን ።

አሽከር፡ ምን ቸገረኝ፡ ይቺማ የምናውቅበት አይደለችምን።

የውድ አዝመራዬ እቴ ሙሽራዬ ።

ተቀባይ ፡ የውድ አዝመራዬ እቴ ሙሽራዬ ።

አሽከር ፡ የውድ ውዲቱ እቴ ሙሽራይቱ።

ተቀባይ ፡ የ ው እ ሙ ።

ብቻዬን አታስለፍልፉኝ ትቀበሉኝ እንደሆን ተቀበሉኝ በአንድ እጅ ማጨብጨብ ሆነና ምነው ጎበዝ ።

አሽከር ፡ የውድ ውድዬ አያ ሙሽራዬ ።

ተቀባይ ፡ የ ው አ ሙ ።

ዋ ዋ ያልነበረሰው ያላየ ሰውኮ ምንም ቢሆን አያምንም ።

አሽከር ፡ የኛማ ሙሽራ የኛማ ሙሽራ የኛ ሙሽራ

ተ ድልድል ።

አሽከር ፡ የኛ ሙሽራ ድልድል ወሰደሽ ባለድል ።

ተ የኛማ ሙሽራ የኛማ ሙሽራ የኛ ሙሽራ ።

አሽከር ፡ ድልድል ።

ተ የኛ ሙሽራ ድልድል ወሰደሽ ባለድል ።

አሽከር ፡ ሥራ የማይገባ

ተቀባዩ ፡ ድልድል

አ ፡ ብዙ እንጨቶች ሳሉ

ተ ፡ ድልድል

አ ፡ ዝግባ ለምን ይሆን እንቆረጠው ያሉ

የኛ፡ ሙሽራ ድልድ ወሰደሽ ባለድል

የኛ ሙሽራ ድልድል ወሰደሽ ባለድል

ተ ፡ የኛማ ሙሽራ የኛማ ሙሽራ የኛ ሙሽራ

አ ፡ ድልድል

ተ ፡ የኛ ሙሽራ ድልድል ወሰደሽ ባለድል

አ ፡ እያበጠ ልቡ፡ ድልድል ለአመመውሆዱን

ተ ፡ ድልድል

አ ፡ ዘንጋዳ ማብላት ነው መተው ሌላውን

አ ፡ የኛ ሙሽራ ድልድል ወሰደሽ ባለድል

ተ ፡ የኛማ ሙሽራ የኛማ ሙሽራ የኛ ሙሽራ

አ ፡ ድልድል

ተቀባዩ ፡ የኛ ሙሽራ ድልድል ወሰደሽ ባለድል

አሽከር ፡ ለለመነው ሰጠ

ተ ፡ ድልድል

አ ፡ ባለሙሉ ተስፋ

ተ ድልድል

አ ፡ ጉሬ ላለው ጉሬን ከፋ ላለው ከፋ

ተመልካች ፡ ደብረሲና ሒደን ብንገዛ ጠበቃ

በአንድ ጊዜ አልቀረም እስከ ዛሬ በቃ

ነቢያትን ሙሴ በጉች ሲአስመራ
ነበልባለ እሳት ከሐመልማል ጋራ
ውዕየትና ርጥበት ሁለቱ በተራ
ተዋሕደው አየ በዚችው ተራራ
እሳቱ ሳይጠፋ ሐመልማል አይሉ
ሐመልማል እሳቱን ሳያጠፋ ውሉ
ከግንብ አስገብቶ በንቱን ቀላቅሎ
ይህንን ድንቅ አየ ሙሴ ተከታትሎ
ዘመን እንዲህ አርጎ ሰላምን ሲአስረዳ
ሰው እንግዳ አይሆንም ጊዜ ነው እንግዳ
ወሀ የባሕርዩን ሲመጣ ሊአጠፋ ።
ወሀ ሲመጣ አይቶ እሳት ቢአንቀላፋ
ምን በመጣ ነበር ከዚህ የሚከፋ
አጥፊ እንዳያጠፋ ፤ ጠፊም እንዳይጠፋ
የመለከት ግርማ
ይህን ተዋሕዶ መልከም አርጎ አስማማ
አሮጌውን ተውት ለልብስ አትሳሱ
ከሙሽሮቹ ልብስ አዲሱን ልበሱ

ቀጥለውም የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሐሳባቸው ያዘጋጁትን ትያትር የሠለጠኑ ተማሪዎች ጀመሩ ከትያትሩም ቃል ከፍለን ጽፈነዋል መከፈላችንም ስፍራ ባይ በቃን ነው እንጂ የሚታረም ጉሮት አይደለም ቃሉም የሚከተለው ነው ።

፪ኛ ትያትር

የፍቅርና እማሬ በለጠ ጋብቻ ።

ፊታውራሪ በለጠ፤እረ የዚያ የልጃችን ነገር ግራ ገባኝ።ወሬውንም አጣን ወረቀትም አልጻፈልን።ከቶ ምን አግኝቶትይሆን።

ወይዘሮ አስተዋለች፤እኔም ሌትና ቀን ሌላ ሐሳብ የለኝም ይልቁንም ይኸን ሰሞን ሆዴ ሁሉእየተሸበረ በጣሙ ጨንቆኛል ደኅና ቢሆን ነው እንጂ እውነት ይኸን ያህል ቀን አንድ ነገር ሳንሰማ አንቀርም ነበር ።

ፊ በለጠ፤ አይ ጊዜ እያነሰው ይሆናል እንጂ ለጤንነቱ የሚያሰጋ ነገር የለም ።

ወ አስተዋለች ፤ እስቲ እግዚአብሔር እውነት ያድርገው

አገፋሪ ፤ አንድ ሰው ከልጅ እማሬ ዘንድ መጥቻለሁና ወደ ጌቶችና ወደመየቴ አስታውቁልኝ ይላል

ወ አስተዋለች ፤ ግባ በለው ግባ በለው ።

ፊ በለጠ ፤ እንዴት ሰንበትህ

ወ አስተዋለች ፤ ልጄ ደህና ነውን። እረ እሱን ትመስላለህ ና ሳመኝ ና ሳመኝ ደስ አለኝ እውነት ነፍሱ አለ ከሱ ዘንድ ነው የመጣኸው

መልክተኛ፤ ደህና ነው እግዚአብሔር ይመስገን ።እሱም ወደዚህ ለመምጣት ተነሥቷል። እኔ ግን ቀድሜው የመጣሁኝ ወደ በረሃ ለአደን ስለ ሔደ ነው ።(ወረቀቱን ይሰጣል)

ፊ በለጠ ፤ ይድረስ(ንሳ አንተ መነጽሬን አምጣ) ለክቡር አባቴ ፊታውራሪ በለጠ ለክብርት እናቴ ወይዘሮ አሰተዋለች ከተለያየን እስከሁን ለጤናችሁ እንደምን ከርማችኋል እኔ ከናንተ ናፍቆት በስተቀር እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ እስከ ዛሬ ድረስ ወረቀት ሳልጽፍላችሁ የቀረሁት ጊዜ ስላጣሁ ነውና ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እለምናችኋለሁ ።

አሁንም በናንተ ውቃቢ በሥላሴ ቸርነት የጀመርሁትን ትምህርት ፈጽሜ ከመምህራኖቼ የምስክር ወረቀት ተቀብዬ ወደ ሀገሬ ለመግባት ተነሥቻለሁና በግንቦት ፴ ቀን ለወዳጅ ዘመዶችን ሁሉ ንግራችሁ እንድትቀበሉኝ ስል በማክበር አመለክታችኋለሁ ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመት

ይላል ታዛዥ ልጃችሁ እማሬ በለጠ

ወይዘሮ አስተዋለች ፤ እሰይ እሰይ ተመስገን አምላኬ እልል

ፊ በለጠ ፤ ይልቅ ለሱ የሚጠጣው አስመጭለት እልልታው በመጣ ጊዜ ይሆናል ።

መልክተኛ ፤ ጤና ይስጥልኝ

ፊ በለጠ ፤ ደህና ዋል ደስ የሚያሰኝ ነገር እንዳሰማኸኝ ቸር ያሰማህ እግዚአብሔር ያን ለት እንዳትቀር አደራ ።

መልክተኛ ፤ እሺ አልቀርም ።

ፊ በለጠ ሰማህ አንተ ።

አሽከር ፤ አቤት

ፊ በለጠ ፤ ሒድና አሁን እንደሰማኸው ለነቀኛዝማች ደስታና ለነቀኛዝማች ግዛው ለዘመዶቻችንም ሁሉ ንገር

አሽከር ፤ እሺ እጅ ነስቶ ይወጣል ።

ቀኛዝማች ፤ እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን ደስ አለን መቼ ነው የሚገባው ።

ፊ በለጠ ፤ ግንቦት ፴ቀን ነው እገባለሁ ያለን ዛሬ መሆኑ ነው እንግዲህ ።

አጋፋሪ ፤ መንገደኞቹ መጡ ።

ጉሮ ወሸባዬ ።

ቀኛዝማች ደስታ፤ በቃ በቃ አረፍ አረፍ በሉ ።

ክቡር ፊታውራሪ በለጠና የተሰበሰባችሁትም ቤተ ዘመዶች ሆይ ።

ይህቺን የዛሬን ቀን ስለ ሶስት ነገሮች በጣም ልናከብራት ይገባናል ፩ኛ ይህ ልጃችን በትምህርት ምክንያት ብዙ ዓመት ተለይቶ ኑሮ ዛሬ በመሀከላችን በመገኘቱ ነው

፪ኛ ፤ ጨለማ የሚባለውን ጫካ ተገን አድርገው ይኖሩ ከነበሩ አጋሚዶች እነድንቁርናን በጥበብ መሣሪያ ተዋግቶ ብዙዎቹን ገድሎ እኛን ወገኖቹን ስለ ረዳንና ለልጆቻችን መልካም አርአያ ስለ አሳየልን ፫ኛ ብድር የማያስቀሩት ገናናው ንጉሣችን ይኸን ድንቅ የሆነ የሚያስመሰግን ሥራ በመሥራቱ ደስ ስለ አላቸውና ልቡን ለማነቃቃት ይኸን ያማረ ሽልማት ስለ ሰጡት ነው ።

ክቡራን ሆይ ።

ክቡር ፊታውራሪ በለጠ ጥበብ ዓይነተኛ ነገር ናት ጥበብን ግዛ በከብትህም ሁሉ ማስተዋልን አትርፍ አትተዋት ትደግፍሀለች ውደዳትም ተጠብቅህማለች ያለው የሰሎሞንን ቃል ተከትለው ልጃቸውን ለእንዲሃለው ማዕርግ በማብቃታቸው ወሰን የሌለው ምስጋናችንን እናቀርብላቸዋለን ።

እኛም ቅንኡ ለእንተ ተዐቢ ጸጋ ያለውን ምሳሌ ተመር ኩዘን ልጆቻችንን ብርሃን ለማሳየትና ኢትዮጵያ አገራችንን ከፍ ወዳለው ደረጃ ለማድረስ እግዚአብሔር ይርዳን ።

አማረ ፡ ክቡራን አባቶቼና እናቶቼ ወንድሞቼ ሆይ ።

ብዙ ዘመን ተለያይተን ኑረን ዛሬ እፊታችሁ በመታየቴ ጥልቅ የሆነ ደስታዬን እየገለጽሁ ያላንድ ቅሬታ በብዙ ገንዘብ ከከበረ ዕንቍ የምትበልጥ እውቀትን ያወረሱኝን አባቴን በፊታችሁ አመሰግናቸው ዘንድ ይገባኛል ።

እኔም ትምርቴን ጨርሼ ዲፕሎም የሚባል የምስክር ወረቀት ከትልልቆች መምህራን እጅ ተቀብዬ በመምጣቴ ለቸርነቱ ወሰን የሌለውን አምላክ እያመሰገንሁ ከሁሉ የምትበልጥ ትምርቴን የሀገር ፍቅርን ለኢትዮጵያ ወጣቶች ለማከፈል የተሰናዳሁ መሆኔን እገልጻለሁ ።

አገራችንንም በነፃነት ለመጠበቅ ብንፈልግ ከሁሉ በፊት አስቀድመን ድንቁርና የተባሉትን አጋሚዶች ማጥፋት እንደሚያስፈልግ አታጡትምና ለዚሁ ተማሬ ቤት የተባለውን ምሽግ ማጠንከር አለብን ።

አሁንም ሁሉን አክብሩ አንድነትን ውደዱ እግዚአብሔርን ፍሩ ንጉሥን አክብሩ የሚለውን የሽማግሌውን የዓለም መሪ የጴጥሮስን ቃል መሠረት አድርገን ሌሊትና ቀን አገራችንን ልናገለግላትና በንጹሕ ደማችን ልንከላከልላት የሚገባን ነው።

ለግርማዊ ንጉሠነገሥታችንና ለግርማዊት እቴጌእችን ረጅም ዕድሜና ጤና ለኢትዮጵያ ሰላምና ነፃነትን ይስጥልን(ጭብጨባ)

ገዳይ አሸ በሉ ገዳይ አሼ በሉ

ግዳዩ ማማሩ

ማየ ኢፌሶን

ቀ ደስታ፥ ልጄ ሐሳብህን ለመፈጸም እግዚአብሔር ይርዳህ እንዲሁ በሠርግህ ጊዜ ተሰብስበን ለመብላት ለመጠጣት ለመጫወት ያብቃን ።

መጋረጃ

ፊ በለጠ፥ ልጄ ወዳጄ ሆይ ያባትህን ትእዛዝ ጠብቅ የናትህንም ምክር አትተው ሁል ጊዜ በንገትህ አንጠልጥላት በልብህም አኑራት ወዴትም ብትሔድ ትመራሃለችና ።

አሁንም ሰው ሆኖ ተፈጥሮ እንደተጻፈ ረዳት የምትሆነው ሴት ታስፈልገዋለችና ስለዚህ አንተም ላከለ መጠን ከደረስህልን የደጃዝማች ፍሥሓንና የወይዘሮ ጥበብን ልጅ ፍቅርን እንድታገባ ፈቃዳችን ሆኖ አባትና እናቷን ብንጠይቅ ሁለቱ ናቸውና አብረው የሚኖሩ እነሱ ይስማሙ እኛ ግን ፈቃዳችን ነው ብለዋልና ፈቃድህ ሆኖ ነገርህን እንድትጨርስ ይሁን ።

አማረ ፡ ክቡር አባቴ ።

እንዲህ ያለችውን በምግባሯ የምትመስለኝን የደጃዝማች ፍሥሓንና የወይዘሮ ጥበብን ልጅ ስለመረጣችሁልኝ ደስታዬ ከልክ ያለፈ ነው አሁንም ሴት ያገኘ በረከት አገኘ ከእግዚአብሔርም ዘንድ ጸጋ ተቀበለ እንዳለ ሰሎሞን በደስታ ሐጄ ፈቃዱን እለምንአለሁ ።

ዐወቀ ፡ እህ ፡ እህ

አማረ ፡ ግባ እረ ተመጣህስ አንድ የማማክርህ ጉዳይ አለኝ

ዐወቀ ፡ ምንድነው ወንድሜ የምታማክረኝ ።

አማረ ፡ አባቴና እናቴ ፍቅር የምትባለውን የደጃዝማች ፍሥሓንና የወይዘሮ ጥበብን ልጅ አግባ ብለውኝ ነበር አሁን ከስዋ ጋር ለመነጋገር እፈቅዳለሁና የሚመቻትን ሰዓት እንድትጠይቅልኝ ነው ።

ዐወቀ ፡ ይኸማ ከሆነልህ በጣም ጥሩ ነው መልከሚቱን ሴት ማን ያገኛታል ከክቡር ድንጋይ ሁሉ ይልቅ ዋጋዋ ይበልጣል የባሏ ልብም ይታመንባታል የተባለው ቃል በንተ መፈጸሙ ነው አሁንም ሄጄ ጠይቄልህ እመጣለሁና እንድትጠብቀኝ ።

አማረ ፡ እሺ እጠብቅሃለሁ ።

ዐወቀ ፡(ኳ ኳ ኳ)

ፍቅር ፡ ግባ

ዐወቀ ፡ ጤና ይስጥልኝ ወይዘሮ ፍቅር ።

ፍቅር ፡ ጤና ይስጥልኝ ልጅ ዐወቀ ምነው በደኅናህ መጣህ

ዐወቀ ፡ ደኅናስ ደኅና ነኝ ልጅ አማረ በለጠ ከወይዘሮ ፍቅር ጋራ የምነጋገረው ጉዳይ አለኝና የሚመቻትን ሰዓት ጠይቅልኝ ስለ አለኝ ይኸን ልጠይቅሽ ነው የመጣሁ ።

ፍቅር ፡ እህህ ሰዓቱን አልነገሩኝም እንጂ እናቴ እንኳ ይመጣል ብለውኝ ነበር አሁንም በተመቸው ጊዜ ቢመጣ ሊያገኘኝ ይችላል ደኅና ዋል ።

አማረ ፡ እንዴት ዋልሽ እኅቴ ወይዘሮ ፍቅር ።

ፍቅር ፡ እግዚአብሔር ይመስገን ወንድሜ ።

አማረ ፡ እንደማለዳ ብርሃን የምትገባኚ እንደ ጨረቃ የተዋብሽ እንደፀሐይ የጠራሽ ወዳጄ ሆይ የመጣሁበትን ነገር ሳትሰሚውና ሳታውቂው ትቀሪያለሽ ብዬ አልጠራጠርም ።

የተመሰገንሽና የተወደድሽ መሆንሽን ወላጆቼ ስላወቁ ለኔ ሚስት እንድትሆኚ ብለው ዘመዶችሽን ቢለምኑ እኛ እሷ ከፈቀደች ፈቃዳችን ነው ስላሉ ፈቃድሽ እንዲሆንልኝ ስል ልለምንሽ መጥቻለሁ ።

ፍቅር ፡ እስከ ዛሬ ድረስ በአገራችን እንዲህ ያለ ልማድ የለም አባትና እናቴን መጠየቅ ነው እንጂ ፈቃዴ ነው ፈቃዴም አይደል ለማለት ለኔ እንዴት ይገባኛል ።

አማረ ፡ የኔ ርግቤ ፍቅር ሆይ እንኳን ካባትሽና ከናትሽ እንዲህ ያለውን ሥልጣን አግኝተሽና ራስሽም የምታደርጊው ነገር ነበር ። ይልቁንም አብረን የምንኖር እኔና አንቺ ነንና የምስማማሽና የማልስማማሽ መሆኔን ብትናገሪ ምን የሚያስፈራ ነው ።

ፍቅር ፡ ነገሩማ እርግጥ ነው ግን

አማረ ፡ አይዘሽ ምን ያስፈራሻል ፈቃድሽም እንደሆነ አሁኑኑ ንገሪኝ ፈቃድሽም እንዳልሆነ ልሂድልሽ በወረቀት አስታውቂኝ ።

ፍቅር፥ወዳጄ ሆይ እንዲያው ለወጉ ብዬ ነው እንጂ መግደርደሬ እንተን እምቢ ብዬ ካንተ የበለጠ ማንን ላገኝነው አሁንም እኔም ያንተ አንተም የኔ ነህና ፈቃዴ መሆኑን ለወላጆችህ ንገር እኔም እነግራለሁ ።ደኅና ዋል ።

አማረ ፡ አሜን ደኅና ዋይ ደሞ እየመጣሁ እጠይቅሻለሁ።

አማረ ፡ ከቡራን አባቴና እናቴ ።

ከዚህ ቀደም እንደነገርኋችሁኝ ወይዘሮ ፍቅር ዘንድ ሔጄ ብነግራት እሺ ፈቃዴ ነው ሔደህ ለዘመዶችህ ንገር ትኔም እነግራለሁ ብላኝ መጣሁ ።

ወ አበትዋለች ፡ ልጄ ሆይ

ለምታስበው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር መሪ ይሁንህ ዘርህ የተባረከ ይሁን ከጕብዝናህ ሚስትህ ጋራ እስከ ሕይወትህ መጨረሻ ድረስ ደስ ይበልህ ከወላጆችህና ከባለቤትህ ፈቃድ እንዳትወጣ ይጠብቅህ

መጋረጃ

ልጅ አገረዶች ፡ እኅታችን ፍቅር ሆይ ባል ልታገቢ ነው አሉ አጮኛሽን ታውቂዋለሽ ወይ ማነንስ ይመስላል ። እባክሽ ንገሪን ።

ፍቅር ፡ የመጣ ጊዜ ታዩት የለም ምን አስቸኰላችሁ

ልጅ አገረዶች፡ብዙዎችን እምቢ ብለሽ ይኸንን በመምረጥሽ በጣም ተደንቀናልና እባክሽ ንገሪን ።

ፍቅር፡ሙሽራዬ ከአልፍ የተመረጠ አንገቱ የወርቅ ምዝምዝ ቁንዳላው የተዘረፈረፈ ልብሱ ቀይና ነጭ ሐር አካሉ በብልሃት የታነፀ እጆቹ እንደ ወርቅ ቀለበት ናቸው ጥርሶቹ እንደ በረዶ የነጹ እኔ የወደድሁት ወዳጄ ይህ ነው ።

አማረ ፡ እቴ መርዓት ሆይ እንደምን ዋልሽ ባይኖችሽና ባንገትሽ ድሪ በምግባርሽም ልቤን የማረክሽው

ፍቅር ፡ የኔ ጽጌ ረዳ የኔ አበባዬ እንኳን ደኅና መጣህ የድግሡብ ሥራ ተከናወነልህን

አማረ ፡ ወዳጄ ሁሉም ተሰናድቶ ይጠብቅሻል።

ፍቅር ፡ የናቱን ጡት እንደጠባ እንደ እንድ ወንድሜ የምወድህ ሙሽራዬ ፈቃድህ ሆኖ ከሥርጋችን ጠጅ ትጠጣ እንደሆነ ላምጣልህ ።

አማረ ፡ ጠጁን ነገ እንጠጣዋለን አሁን ግን እቸኵላለሁና እንዳትቀየሚኝ እለምንሻለሁ ደኅና ዋይ ።

መጋረጃ ።

አጋፋሪ ፡ ሙሽሮች መጡ ።

ደጃዝማች ፍሥሓ፡ ግቡ በላቸው ።

አጋፋሪ፡ እንዴት ዋላችሁ ፡

ደጃዝማች ፡ ተቀመጡ ሙሽራዋን አምጡ ይበሉ አባቴ ሥርዓተ ጋብቻውን ያድርጉላቸው ።

ቄስ ፡ በል አንተ እኔ አማረ ወይዘሮ ፍቅርን እጄ በጨበጠው እግሬ በረገጠው ባለ እኩል አድርጌ ወድጄና አፍቅሬ በጽኑ ቃል ኪዳን አግብቻለሁ በል ።

አማረ ፡ እኔ አማረ ወይዘሮ ፍቅርን እጄ በጨበጠው እግሬ በረገጠው ባለ እኩል አድርጌ ወድጄና አፍቅሬ በጽኑ ቃል ኪዳን አግብቻለሁ ።

ቄስ ፡ በይ አንችም እኔም ፍቅር ልጅ አማረን እግሬ በረገጠው እጄ በጨበጠው ባለ እኩል አድርጌ በጽኑ ቃል ኪዳን አግብቻለሁ በይ

ፍቅር ፡ እኔ ፍቅር ልጅ አማረን እጄ በጨበጠው እግሬ በረገጠው ባለ እኩል አድርጌ በጽኑ ቃል ኪዳን አግብቻለሁ

ቄስ ፡ ያስምረው ይቀበለው እግዚአብሔር የአዳምንና የሔዋንን፡ የአብርሃምንና የሣራን፡ የይስሐቅንና የርብቃን፡ ጋብቻ የባረከ አምላክ ጋብቻችሁን ይባርክ ውለዱ ክበዱ ባባታችሁ ቦታ እንድትተኩ ያድርጋችሁ ብዙኁ ወተባዝኁ ወምልዕዋ ለምድር የተባለው ምርቃት በናንተ ይፈጸም አገራችሁን አፍቃሪ ፡ አባትና እናታችሁን አክባሪ፡ንጉሣችሁን ወዳጅ ሕዝባችሁን ጠቃሚ አድርጎ በስምም በሰላም ያኑርልን አሜን እንበል አቡነ ዘበሰማያት ።

አእምሮ ፡ ከቡራን ጌቶቼና አባቶቼ

ጋብቻ በሁለት መንገድ ይከፈላል ።

፩ኛ ልጃችን የገሌን ልጅ ያገባ እንደሆነ ጌቶች ናቸውና ገንዘብ ያተርፈናል ብለው የሁለቱን ጋብቻዎች ኑሮ ሳያስቡ የሚደረገው ነው ትርፉም ጠብና ንዝነዝ ነው ።

፪ኛው ግን በገንዘብ ፍላጐት ሳይሆን ምንም እንኳ እጮኛዎቹ ተገናኝተው ነገሩን ባይጨርሱ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው የልጆቻቸውን ጠባይ አይተው ትክክለኛ ጋብቻ መሆኑን መርምረው በተክሊል የሚፈጽሙት ሥርዓተ ጋብቻ ነው ። ወደፊትም ልጆቻችሁን የምትድሩ ሰዎች ሁሉ ትዳራቸው ጸንቶ እንዲኖር እንደዚህ እንዳሁኑ ዓይነት ጋብቻ እንድታደርጉ እንጂ በገንዘብ ፍላጐት ብቻ እንዳታደርጉት ስል አሳስባችኋለሁ ።

ቄስ ፡ ማዕደ አብርሃምን ማዕደ አበውን የባረከ እግዚአብሔር ማእዳችንን ይባርክ ።

አያ ወሸቤ

ዐወቀ ፡ ርግብ (አውርድ ማዴ)

ቀኛ ደስታ ፡ ምነው አግዙት እንጂ ጨዋታውንም ለወጥ አድርጉት ።

የትግርኛ ዘፈን

ዐወቀ ፡ እስቲ ደሞ እንዳገዙኝ እኔም ላግዛቸው

ማየ ረሰየ ወይነ

ከሥርጉ ይልቅ ምላሹ ሲአምር ደስ ያሰኛል ነገር ግን ምላሹ የሚያምርላቸው ሰዎች ጥቂቶች በመሆናቸው እጅግ ያሳዝናል ዛሬ ግን በሙሽሮቻችን ምላሽ ማማር ደስ ብሎናል እነሱንም በልጆቻቸው ደስ እንዲላቸው ተስፋ እናደርጋለን ።

ማመልከቻ ።

ሰኔ ፳፫ ቀን በወጣው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በራስ ኃይሉና በጓደኞቻቸው ስለ ተፈረደባቸው ፍርድ መሻሻል ስንናገር በሁለተኛው ማሻሻል ላይ የአካል ቅጣት ተቀጥተው እስከ ዕድሜ ልካቸው እንዲታሠሩ ተደረገ የሚል ቃል ጽፈን ነበርና ይህን ቃል የፍርድ ሚኒስትር አይተው ጃንሆይ በቸርነታቸው እነዚህ ወንጀለኞች ከተገረፉ በኋላ እስከ ዕድሜ ልካቸው እንዲታሠሩ አደረጉ እንጂ የአካል ቅጣት ባንድ ሰው እንኳ አልተፈረደም፡ብለው ስላስረዱን የአካል ቅጣት እንዲቀጡ ተደረገ ተብሎ የተጻፈው በስሕተት መሆኑን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እናስታውቃለን ። የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች። ከዚሁም አንዱ አርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዳች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሹሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመንብኑት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል።

ማስታወቂያ ።

በሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪል ነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፴፩
8^{me} ANNE. № 31

ሐሙስ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 28 JUILLET 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታላቅ ክብር ያለው ቀን ።

በሐምሌ ፲፮ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተወለዱበት ቀን ስለሆነ አስቀድሞ ማስታወቂያ ተደርጎ ነበርና ገና በጧት ስለቀኑ ክብር ፳፩ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ከጧቱ በ፩ሰዓት ጀምሮ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የክብር ዘበኞች በአለቃ በአለቃቸው ከ፬ኪሎ ጀምረው እስከ ቤተመንግሥቱ ደረጃ ድረስ በመንገዱ ግራና ቀኝ በሚአምር ሰልፍ ተሰልፈው ለሚገባው ሰው ሁሉ የሚገባ ሰላምታ እየሰጡ ያሳልፉ ነበር።ከነዚህም ከተሰለፉት ዘበኞች ከመጀመሪያው ከ፬ኪሎ ወገን የተሰለፉት ከከተማ ዘበኞች ከአለቆቻቸውና ከጠቅላይ አለቃቸው ከግራዝማች አማረ ጋር ነበሩ ።

፬ሰዓት ተኩል ሲሆን የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ሚኒስትሮችም ወደቤተመንግሥቱ በመጡ ጊዜ የደጅ አጋፋሪዎች እየተቀበሉ ወደዋናው አጋፋሪ ከልክሉ ያቀርቡ ነበር።አጋፋሪ ከልክሉም ወደቤተመንግሥቱ ሊጋባ ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል ያቀርቡ ነበር ። ከዚያም በኋላ የልፍኝ አስከልካዩ ፊታውራሪ ጣሰውና ሁለተኛው የልፍኝ አስከልካይ የሻቃ በልሁ እየተቀበሉ አግብተው በየማዕርጋቸው ያስቀምጡ ነበር። ፭ሰዓትም ሲሆን የውጪ አገር ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ያግረ ያማረ የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ መጡ። አጋፋሪዎችም እንዲሁ በማዕርግ ተቀበልዋቸው የቤተ መንግሥቱ ሊጋባ ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል በወርቅ የጠለቀ ላንቃ ለብሰው በወርቅ የተንቆጠቆጠ ጐራዴ ታጥቀው የወርቅ ጋሻና ጠመንጃ ይዘው አጋፋሪ ከልክሉም የአንበሳ ጋማ አሥረው አንፋሮ ለብሰው በወርቅ ያጌጠ ጐራዴ ታጥቀው የወርቅ ጋሻቸውንና ጠመንጃ ይዘው ፊታቸውን ብርሃን አድርገው እንግዶችን ሲቀበሉ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር። አጋፋሪዎችሁሉ በየማዕርጋቸው ተሸልመው በየመልእክታቸው ሲፋጠኑ የሙሉ ከዋክብት ብርሃን መስለው ይታዩ ነበር።የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጪ አገር መኳንንት ገብተው በየማዕርጋቸው ከተቀመጡ በኋላ በሽምፓኝ ጊዜ የሚኒስትሮች ተቀዳሚ ዲስኩር ተናገሩ።ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር በሙዚቃ ድምጽ ተዘመረ።የውጪ አገር ሚኒስትሮችና ቆንስሎች ከጃንሆይ እየተሰናበቱ ወጡ። ከዚህ በኋላ በልዩ ልዩ ሥራ ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚያገለግሉትና በከተማ ኑዋሪዎች የውጪ አገር ሰዎች ገብተው እንኳን ከዚህ ዓመት አደረሰዎ እያሉ እየተሰናበቱ ወጡ ። ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ አርበኞችና በየክፍሉ ያሉ ሹማምንት እንኳን ከዚህ አደረሰዎ ደግሞ ብዙ ዘመን ያኑርዎ እያሉ እጅ እየነሡ ወጡ።ከዚህ በኋላ ከ፮ ሰዓት ጀምሮ እስከ ዓሥር ሰዓት በታላቁ አዳራሽ ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ለሠራዊትና ለሊቃውንት ታላቅ ግብር አድርገው ዋሉ። ደግሞ በ፲ ሰዓት ስለ በዓሉ ደስታ የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎችና የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ዲሬክተር አቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ያሰናዱትን መልክም ትያትር ለማየት ወደ ታላቁ ቤተ መንግሥት ጃንሆይና እቴጌ መጥተው በመንበረ ዳዊት ተቀመጡ። ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ሚኒስትሮች ልዑላት ወይዛዝር በግራና በቀኝ ተቀምጠው ነበር። ከትያትርም ቃል የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከአወጡት ከፍለን ጽፈናል። ቃሉም የሚከተለው ነው የቀረውን ስፍራ ጠበን ትተነዋል ።

የሆድ አምላኩ ቅጣት ።

አቶ በነ ሰውና ወይዘሮ አትጠገብ በቤታቸው እንደተቀመጡ ሆዱ አምላኩ ዱላውንና ኰፊያውን ይዞ ዳባውን ለብሶ ይመጣል ።

ሆዱ አምላኩ በእንተ ስማ ለማርያም ስለቸሩ እግዚአብሔር እመ አምላክ ትቁምልዎ እኔ ሆዱ አምላኩ ሙተዋል እንዴ እመ አምላክ ትቁምልዎ ።

ወይዘሮ አትጠገብ አትቁም ።

ሆዱ አምላኩ እሺ ግድ የለም እቀመጣለሁ ።

አቶ በነ ሰው ወደ ግሩም ምን ያለው ቀልደኛ ተማሪ ነው ሰዎች እባክሽ ተነሽ ተዘከሪው።

ወ አትጠገብ፡ ምጣድ አልጣድኩምና ዟዙሮ ይምጣ

በነ ሰው፡ እሺ እንግዲያስ ንገሪው

ወ አትጠገብ፡ ዙረህና

ሆዱ አምላኩ፡ ምን ከፋኝ እመቤቴ (ዙሮ)ጀርባውን አዙሮ ይመጣል)በነ ሰው ወየው ጉድ እባክሽ ጥሬ እንኳ ቢሆን ተዘከሪው

አንተ ተማሪ ፥

ሆዱ አምላኩ ፡ አቤት ጌታዬ

በጎ ሰው ፥ የውጋት መድኃኒት ታውቃለህ ።

ሆዱ አምላኩ ፥ ግናም አድርጌ እንዲያውስ እንደኔ አድርጎ ማን ያውቃል

በጎ ሰው ፥ እረ እንግዲያስ እባክህ ባለቤቴን አንዳንድ ቀን ያማታልና እንድታደርግላት ።

ሆደ አምላኩ፥ እሺ እንጂ ምን ከፋኝ ።

በጎ ሰው ፥ በል እንግዲያስ በኋላ እርስዋን ይገር መጥቸ እዚያው አንተ ዘንድ ታደርግላታለህ

ሆዱ አምላኩ ፥ እረ ግድ የለም እርስዎ አይድከሙ እመየቴን ብቻ ይላኳቸውና ቶሎ አድርጌላቸው ይመለሳሉ ወዲያውም መድኃኒቱ እሚሰምረው እርስዎ ባለቤታቸው በሌሉበት ሲደረግ ነው

በጎ ሰው፥ከድከሙ ምን አለኝ ተዳኝችልኝ ወንድሜ እንግዲያው ያዳንሀልኝ እንደሆን ዋጋህ ወሰን የለውም አገርህ የት ነው

ሆዱ ፥ አምላኩ ፥ ምን የኔ አገሬ ኰፈዳየና የማምላክ ስም ናቸው እንጂ ምን አገር አለኝ ጌታዬ

በጎ ሰው ፥ አዬ የኔ ልጅ በል ግድ የለህም ዘመድ እንሆንሃለን በይ ተነሽ ተሀከሪው አትጠገብ ። (አትጠገብ እንጀራውን ይዛው ወደተማሪው መሔድ)

(ተማሪው እየሳቀ እንጀራውን ትቶ እጅዋን መያዝ)

(አትጠገብ)ምን ማድረግህ ነዋ)

ሆዱ አምላኩ ፥ ምንም አይደል እይዝዎ ከከብዎን ለመቁጠር ነው (እየሳቀ

አትጠገብ ፥ አንተ ነህ ኮከቤን የምትቆጥርልኝ በል አሁን ሰማሁህ ዝም በልና ልቀቀኝ ባለቤቱ ያዩህ እንደሆነ በዱላ ነው ልብህን የሚያጠፉህ የኔን ኮከብ መቍጠር ትተህ ሒድና ይልቅ ከቸርህን ቍጠር

ሆድ አምላኩ እረግ በዛኝቱ ምኑን አመጡታ እንኳን የር ስዎ ባል ይህ ኰሳሳው እንደሱ እንደሱ ዓሥር ቢመጡስ እም በጠቅ ሰው ነኝ ምነው እንዲህ ናቁኝ ዳባዬን አይዩ እኔን ማየት ነው ዓይኔ እንደንጋት ኮከብ የሚያበራ ልጅ

አትጠገብ ፥ አከ ልቀቀኝ አሁን ከርፋፋ ተማሪ እኔ የከክህ ማራገፊያ ነኝ አንተ አከክም

በጎ ሰው ፥ (ዱላውን ይዞ ዝግ እያለ መጥቶ ምሽቴን ምን ትላታለህ አንተ ቆርንጮአም ተማሪ

ሆ አምላኩ እረ እኔስ ምንም አላልኋቸው ጌታዬ የውጋቱን መድኃኒት ላድርግላቸው ብዬ ነው እንጂ እኔ ማን ወልዶ ማን አሳድጎኝ የሰው ሚስት እይዛለሁ

በጎ ሰው ፥ ይውጋባችሁና የሚወጋ ሙጋትስ አንተ መንፈሳዊ መስለህ መጥትህ የሰው ቤት የምታፈርስ (በዱላ ገርግፎ

ሆ አምላኩ ፥ እረ እዛኘን ምንም አላልኋቸው እንዲሁ ነው የሚለፈልፉ እኔ መድኃኒቱን ላድርግልዎ ከማለት በቀር እስቲ አሁን ምን አልኋቸው

በጎ ሰው ፥ እረ ያንተን መድኃኒት አይተነዋል አንተ ቀጣፊ (በዱላ ተማሪው እየተሳደበ መሮጥ

በጎ ሰው ፥ ወደ ተማሪ ወይተማሪ እኔማ ቆርንጮውን ለብሶ እምሽክ ድቅቅ ሲል ሳየው ጊዜ ዋና መንፈሳዊ መስሎኛል እሱስ ነጣቂው ኑሩዋል እንግዲህ ሁለተኛ አልሞኝም (ወደሚስቱ ዘወር ብሎ በንቀት)ይህች ደሞ ልክስክስ እንዲያው እንደሰፈደ ቶሎ ማንም እንዳፈሳት ዕድሜዋን ገፋችው ከቶ ምን ባደርግሽ ይሻለኛል ።ምን ብትመከሪ ባንቺ የተነሣ ከንደኞቼ ሁሉ ተቆራረጥሁ አገሩንም ጥየልሽ ልሒድ ።

ወ አትጠገብ እስቲ አሁን ለምን መልክሽ አማረ ብለው ነው እንጂ ምን ከሰው የተለየ ሥራ ስሠራ አዩኝ ከኔስ ወዲያ ባሉን የሚወድና የሚያከብር ማነው

በጎ ሰው፥ እረ ይህም ሲያንስሽ ነው ይገባሻል እኔ እየጠነፈርሁ የማመጣውን አንች እዚህ ቁጭ ብለሽ መልክሽን እየወለወልሽ የጐረምሳ መቃጠሪያ አረግሽው ሲያንስሽ ነው (እያጕረመረመ መሔድ እስዋም መከተል)

ሆ አምላኩ ፥ ከረጢቱን ይዞ ዝግ እያለ ግራና ቀኝ እያየ ወዳታክልቱ መግባት ቀና ብሎ ወደፍሬው ይመለከታል ። እረግ እረግ እረግ እንዲህ ነው እንጂ አሁን ጌትነት መጣች ጓዚን ጠቅልላ ሒጂ እንግዲህ አንቺ ዳባ የሚሆንሽን ፈልጊ እኔ ግን እንግዲህ በጥበብ ኩታ በነጭ ሐር እጀ ጠባብ በባለ መስታዋት ጫማ መኰፈስ ነው እንጂ ከእንግዲህ አንችን እንኳን ልለብስሽ አልቀመጥብሽም (ብሎ ዳባውን አውልቆ መጣል)

አሁን እንግዲህ ከዚህ ወይን በከረጢቴ ሞልቸ እወስድና ነገ ገበያ አውጥቸ አንዱን ባንድ ብር አንዱን ባንድ ብር እንኳ ኳዋለሁ እስቲ ፫ሺህ ፍሬ የወሰድሁ እንደሆን ፫ሺህ ባንድ ጊዜ ማግኘቴ ነው ከዚያ ወዲያስ በሰጋር በቅሎ እየተንፈሰስሁ ማንም እጅ ሲነሳኝ የጕድን እያየሁ መሔድ ነው ።ደግሞ ከዚህ አምስት ስድስት ጊዜ የሚበልጥ ቦታ አገዛና በዚያ ሙሉ ወይኑንም ሎሚውንም ትርንጎውንም ሽንኰር አገዳውንም ቡኑንም እተክልና በሽቦ አፍን አድርጌ አሳጥሬ ሌባ እንዳይሰርቀኝ ዙሯሙን በዘበኛ አስጠብቀዋለሁ። ደግሞ እኔ እንደነዚህ ሰነፎች ሰዎች ተኝቸ እንቅልፌን ሳሳድድ አላድርም ። ሌሊት እነሳና ዘበኞች ተጠንቀቁ ሁለ ጊዜ ንቁ አትክልቴን እንዳታሰርቁ እላቸው ነበር ። ግድ የለም ይህ ሁሉ አይቀርም እንግዲህ ሳይነጋብኝ ልሒድ ቶሎ ቶሎ መልቀም በፍጥነት ይወጣል ።

በጎ ሰው ፥ እረ ግሩም ነው ግሩም ነው ምን ነካብኝ እኔ ዘመትር ፍሬው እንዲበዛልኝ ብዬ እከባከበዋለሁ እርሱ ግን እያደረ ያንሳል እኔ ባለብዙ ሥራ ነኝ እሱን እዚህ ቁጭ ብዬ ልጠብቀው አልችል አምላክ ይጠብቅልኝ እንጂ ምንአደርጋለሁ

ሆዱ አምላኩ ፥ እሰይ እሰዩ አሁንም አልተነሡ ተመስገን ጌታዬ እንዲህ አድርጌ በቁመናዬ መንግሥተ ሰማያት ልግባ እኔ ብሆን ይህችን አይተዋት የማትጠገብ ለምለም ቦታ ትቸ መቸ እተኛለኋ ዘበኛ ዘበኛ አንተ ዘበኛ ነቃ ብለህ ጠብቅ ተጠንቀቅ እለው ነበር ።

በጐ ሰው ፥ከእንቅልፉ በሌባው ጩኸት ነቅቶ ዱላውን ይዞ ከሌላ ሰው ጋር ይመጣል ዝግ ብሎ መጥቶ በዱላ ብሎ መያዝ ።

ሆ አምላኩ ፡ አረ ልሰርቅም አይደል አህያ ቍለጋ ነው የመጣሁ አረ ባዛኝቱ የዛሬን ይማሩኝ አይለምደኝም ።

በነ ሰው ፡ አንት ቀጣሬ በቀደም ሚስቴን ስትጐትት አገኘሁህ ደግሞ ዛሬ ይኸው ስትሰርቅ አገኘሁህ አሁን ቢገድሉህ ለሰው ዕዳ ለመሆን ነው ።

ሆድ አምላኩ ፡ ጌታዬ የቸርነትዎን ሥራ ይሠሩልኝ እንጂ ይህ እንደሚመጣብኝ አላወቅሁም ነበር ።

በነ ሰው፡ አረረ ጠላቱ ።

አረረ ጠላቱ እያደገ ሀብቱ ።

በነ ሰው ፡ ንሳ ይህን አታላይ ሌባ ቀጣሬ ለዘበኛ ስጥ

አረረ ጠላቱ፡ አንተ እንዴት እንዴት ጠግበሻል ስቆጥር ቆጥረሻል መጥተሽ አሰርቃል መጤፎ ክፉ (በጥፊ በጥፊ)።

በነ ሰው ፡ አያችሁት እናቶ ሌትና ቀን ለፍቶ ያሳደኩትን አትክልቴን ሹልክ ብሎ መጥቶ እንዲህ አድርጎ ይጫወትብኝ ግን እግዚአብሔር አሳየኝ ። ለወደፊቱም ዘበኞቹ እንዲጠነክሩ አደርጋለሁ ። እኔም ጸሎት ጋሻን አንግቤ ድፍረት ጦርን ይዤ እጠባበቀዋለሁ ባገኘውም እንዲህ በዋዛ አልለቀውም ።

(መጋረጃ)

በነ ሰው፡ እኔ ወንድሜ ስንት አገር የፈታህ ሰው በሰረቅህ ቁጥር ከንተ ጋራ ተደባድቤ አልዘልቅህምና ና ወደ ዳኛ እንሒድ ።

እግዚአብሔር ያሳይዎ መላኩ ያመልክትዎ ይኸ ሰውዬ መጀመሪያ ተማሬ መስሎ ደበሎውን ለብሶ ተዘከሩኝ ሲል መጣ ባሌቤቱም ልትዘክረው ብትመጣ ሲጐትታት ያዝኩት ። ሁለተኛ እኔ ሌሊትና ቀን ላቤን እያንጠፈጠፍኩ ያለማሁትን አትክልቴንድንበሬን አልፎ አጥሬን ጥሶ ሌት በጨለማ ሰርቆ ዳባውን ጥሎ ሔደ ። ሶስተኛ የፊት ስርቆቱ አንሶት በሰማይ ምን እግዜር አለ በምድር ምን ሰው አለ ብሎ እየፈነጠዘ ንየጮኸ ሲሰርቅ ይገኝ ይኸው ወደ ክቡርነትዎ አመጣሁት

አፈ ንጉሥ ሰሎምን፡ በላ አንተስ ምን ትላለህ።

ሆድ አምላኩ፡ እግዚአብሔር ያሳይዎ መላኩ ይንገርዎ አሁን ከተወራው ወሬ ሁሉ አንድም እውነት የለ መጀመሪያ ሚስቴን ጐተታት ላለው እኔ ለራሴ የሰው አገር ሰው ችጋር ያንገላታኝ የሱን ሚስት እንኳን ጐተታ ጨርቋንም አልነካሁ ። ሁለተኛ አትክልቱ ውሥጥ ገብቶ ሰረቀ ላለው ። እውነት ነው ሁላችሁ እንደምታውቁት ቅኔ የሚቆጥር ሰው ከሰዋሬ ቦታ ሒዶ ነውና ስለዚህ ልቈጥር ገብቻለሁ እንጂ መስረቅ ይቅርና በልቤም አላሰብኩ ። ሶስተኛም ሲሰርቅ አገኘኹ ወደ ክቡርነትዎ አመጣሁት ላለው አህያ ጠፍቶብኝ ስፈልግ ቢያገኘኝ ሌባ ነህ ብሎ ከናሽከሩ ደበደበኝ እኔ

በነ ሰው፡ ጌታዬ እኔ ማረስ መቆፈር ነው እንጂ ሙግትና ነገር አላውቅምና በነገሬ ሁሉ እርቱም እርቴ ምቱም ምቴ ሆኖ እንዲነጋገርልኝ አቶ ዓወቀን ወልጃለሁ

ዓወቀ፡ እኔም ተወለድሁ መንግሥት ይሙት

ሆድ አምላኩ፡ እኔም ተቀብያለሁ ።

ዓወቀ፡ እግዚአብሔር ያሳይዎ የዚህ ሰውዬ ነገር አልሸሹም ዘወር አሉ ነው እንዲያው ለነገሩ መጨረሻ ይኸ ደበሎ የማነው ብለው ይጠይቁት ።

አፈ ንጉሥ፡ እውነቱን እኮ ነው በሉ ። አንተ ልጅ እረ ይኸ ዳባ የማነው ።

ሆድ አምላኩ፡ የኔ ነው ዓለሜ ።

አፈ ንጉሥ፡ ማለፊያ ጸፍለት

ዓወቀ፡ ማን ይሙት ያንተ ነው ።

ሆድ አምላኩ፡ ባንተ ቃል አልፈጠምም

አፈ ንጉሥ፡ ጭቅጭቁን ተውና ተፈጠም ።

ሆድ አምላኩ፡ እንዲያው እሱ ቢያናድደኝ ነው እንጂ በገንዘቤ ያልተፈጠምኩ ምን ልሆን ነው መንግሥት ይሙት የኔ ነው ።

ዓወቀ ፡ እንዲያ እንዲያ ሲል ይመጣል ። ንጉሥ ከሞቱ በማን ይሚገቱ ከንዳ ሰማኒያ

ሆድ አምላኩ፡ የምን ሰማኒያ አልከንዳም ።

ዓወቀ ፡ እየው መጀመሪያ በሁለተኛ ማመልከቻዬ ደበሎውን ጥሎ ሔደ ብል ሾላ ድፍኑን ሁሉም ውሸት ነው ብለህ ተፈጠምህ አሁን ደግሞ መልሰህ የኔ ነው ካልህ ሰማኒያ እንዲያስከነዳህ ከፊቱ የሚዳምጥ ከኋላው የሚያፈናጥጥ ሐመር ፈረስ አስጥ ።

ሆድ አምላኩ፡ ዝቅ አርግ ባለ ፈረስ

ዓወቀ ፡ ነጭ ማር አስጥ ።

ሆድ አምላኩ፡ አሁን አገባ ብልህነገር ይረዝማል በኋላ አስጠቀልል የለ አጉራህ ጠናኝ ከነዳሁ።

ዓወቀ እኔም አስከነዳሁ ተጠየቅ ልጠይቅህ

ሆድአምላኩ ፡ ልጠየቅ ።

ዓወቀ ፡ አንድ ስጠይቅህ ግማሽ ሁለት ስጠይቅህ አንድ ከዚህ አልፍ ዝንፍ ያለ እንደሆነ ከፍ ከፉ ነጭ ማር ቅዳለት ተጠየቅ ሆድ ፡ አምላኩ ልጠየቅ ።

ዓወቀ ፡ ተጠየቅ ሥራት ልክ ነው ።

ሆድ አምላኩ፡ እንጃ

ዓወቀ ፡ ተጠየቅ አቤቱ ልትለምን መጥተህ ነበር ።

ሆድ አምላኩ፡ መጥቻለሁ

ዓወቀ፡ ተጠየቅ ልትዘክርህ ብትመጣ ሚስቴን ጐትተሃል

ሆድ አምላኩ፡ አልነካሁም ።

ዓወቀ፡ ተጠየቅ ልጠይቅህ ድንበሬን አልፈህ አጥሬን ጥሰህ ከርስቴ ገብተሃል ።

ሆድ አምላኩ፡ መግባቱን ገብቻለሁ ድንበርህንም አልፌ አለሁ ። ነገር ግን አጥር ያልከው ውሸት ነው እንኳን እኔ ልጥሰው በቦታውም የለ ።

ዓወቀ ፡ ዋስ በለው ገባ ።

ሆድ አምላኩ ፡ አዎን ገባሁ ይዋሱኝ ጌታዬ

ዘመዴ፡ ደግሞ ይዋሱኝ ተየቱ የመጣህ የት አውቅሃለሁ ገና እንዲያው ብልሃተኛ ነኝ እያልክ ታወራለህና ልዋስህ ነው አንድ ቀን በጠፍ ጨረቃ ቆዳህን ለብሰህ በጠፍ ጨረቃ እልም ያልክ እንደሆነ የማን ያለህ ልል ነው አልዋስም

ሆድ አምላኩ፡ ይህን ሁሉ ነገር ከመዘብዘብ እንዲያው በጭሩ አልዋስም አይሉም ነበር ። ምን አለፉዎ መቸስ ምን አደርጋለሁ የንታ ጌታ ይዋሱኝ ።

ብሥራት ፥ ምነው ወዳጄ ዓይኑ አያይም ጆሮው አይሰማም ሲሉ ሰምተሃል ዓይኔ እያየ ጆሮዬ እየሰማ መምጫህ ላልታወቀ ላንተ እዋሳለሁ አልነከውም ።

ሆድ አምላኩ፥ዋስ ታጣሁ ምን ምን አደርጋለሁ ዳባዬ ትዋሰዋኝ ።

አፈ ንጉሥ፥ ደግሞ ዳባዬ ትዋሰኝ አንተ ንቀህ ጥለሃት የሔድህ ለኛ ምን ታደርግልናለች ። ግዴሌም የዚህ አያስቸግርም ወደ ስር ነገራችሁ ተመለሱ ።

ዓወቀ ፥ እየው ወንድሜ ታያት ተቅድማያቴ ታብቴም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣልኝን በጂ ጨብጬ በግሬ ረግጬ የያዝኩትን የወገኖቼ ደማቸው በፈሰሰበት አጥንታቸው በተከሰከሰበት ርስቴ ውሥጥ ድንበር አልፈህ ወሰን ገፍተህ ከተገኘህ ሌባ ሲሰርቅ በምስክር አይደለምና ምስክር አግኝቼ ። ሌብነትህን ባላነጥር የጠፋ ገንዘቤን ክፍለህ አንተም ተቀጥተህ ታገር ውጣ እንዲሉህ ጉራቻ ማር እሰጥ ።

ሆድ አምላኩ ፥ ባያት በቅድማያትህ ባንተም ርስት ድንበርህን አልፌ ወሰንህን ገፍቼ ብገባ በሌብነቴ ካልተረታሁ ገንዘብህን ከወሰድብህፈልግ ይሉሃል እንጂ እኔን ክፈል ታገርም ውጣ አይሉኝም ። ይልቅ አንተ በሰማይ ምን እግዜር አለ በምድር ምን ሰው አለ ብለህ ምንም ሳላጠፋ ምንም ሳላደርግ ስለደበደብከኝ እኔን ክሰህ ለዳኛም ተቀጥተህ ሒድ ይሉሃል አንተ ምን ጉራቻ ማር ትሰጥ እኔ በራሬ በቅሎ እሰጥ

በላ ልበልሃ ያጤ ሥራቱን ያብርሃም እራቱን አልናገር ሐሰቱን ሁልጊዜ እውነት እውነቱን እሥር እመሠረት በለርስትነቴን ከመንህ ሁለተኛም ድንበሬን አልፈህ ወሰኔን ገፍተህ ርስቴ ውሥጥ መገኘትህን አምን ካልክ ዳባህም እዚያው ወድቆ ከተገኘ የጠፋ ገንዘቤን ክፈል ። አንተም ተቀጥተህ ታገር ውጣ ይሉሃል ብዬ ውርርድ ትክዬ እግር ዘንጥዬ ብረታ ባልመታ አማረ በሉ ፍረዱልኝ ከፋ ስደዱኝ ሲል ይሙዋገታል ወንድማችሁ ዐወቀ ነገረ መልከም አፈ ደማም ።

ሆድ አምላኩ ፥ በላ ልበላሃ ያጤ ሥራቱን ያብርሃም ራቱን ያገራችንን የጌታችንን ጠላት ከምበል ፈሰስ ያድርገው አልኩሃ እየው ድምበርም ባልፍ ወሰንም ብገፋ ርስትህም ውሥጥ ብገባ ገንዘብም ቢጠፋህ በሌብነቴ ካላነጠርክ የጠፋውን ክፈል አንተም ታገርውጣ አይሉኝም በጀበሉ ፍረዱልኝ ጠፋ በሉ ስደዱኝ ሲል ይሟገታል የሰው አገር ሰው ሆድ አምላኩ።አፈ ንጉሥ በል እንጂ አጋፋሬ አስፈርድ አንተም ለራስህ ፍረድ ።

ሆድ አምላኩ ፥ አቶ ዐወቀ ተው አንጣላ እንገላገል የተደበደብኩ እኔ ክሳችሁኝ ብሔድ አይሻልም ሰዎቹንስ ለምን ታደክማቸዋለህ ።

ዐወቀ ፥ አዬ ሆድ አምላኩ ግልግልማ ቀረ አመለጠህ ይልቅ ጌቶቼ ፍረዱንና ሞት ሽረታችንን እንወቀው አጋፋሬ ይፍረድብኝ ባደላም ያድላብኝ በሐሰተኛ ሰይፍ ሞት ይፈረድበት የአገራችንን የጌታችንን ጠላቶ የራቀውን በመድፍ የቀረበውን በሰይፍ ቆርጦ ቆራርጦ ይጣለው የሌባ ዓይኑ ደረቅ ተመልሶ ልብ ያደርቅ እንደሚሉት እርስትህ ውሥጥ ድንበርህን አልፌ ወሰንህን ገፍቼ ገብቻለሁ ብሦርቅም ምስክር ካልነገረብኝ አልከፍልም አልቀጣም የት ይሆናል የጠፋውን ክፍለህ ተቀጥተህ ታገር ስትወጣ ይታዩኛል ።

ደባልቄ ፥ ይፍረድብኝ ባደላም ያድላብኝ ጠላታችንን የራቀውን በጸሎት የቀረበውን በስለት አርዶ ፈራርዶ ይጣለው እኔ እጸድቃለሁ ሰው አስኰንናለሁ ከቶ ተብሎ አይታወቅምገና ድኃነው ተብሎ እንዲህያለ ፍርድ ይፈረዳል ነቅቶ መጠበቅ ነበር እንጂ አሁን እሱ ምን ያድርግህ እንዲያውም በደበደብክበት አንተ ትክሰዋለህ ።

ዘመዴ ፥ ይፍረድብኝ ወንድሜ ባደላም ያድላብኝ ጠማ ባለቤቱን ያስወጣ እንደሚሉ አርሶ ቆፍሮ ወጥቶ ወርዶ ያለማውን ቦታ ውሥጥ ገብተህ ከተገኘህ አንተ ያልተቀጣህ ማን ሊቀጣ ነው ።

በጥባጤ ፥ ይፍረድብኝ ባደላም ያድላብኝ ባሰተኛ ሰይፍ ሞት ይፈረድበት ያገራችንን የጌታችንን ያድበሩን ያውጋሩን ጠላት የራቀውን በመድፍ የቀረበውን በሰይፍ አርዶ ፈራርዶ ቆርጦ ቈራርጦ ይጣለው ፍትሐ ንጉሥን እሀል ቅዱስን እያጥፋብን ምነው ጠብያ እንዴት እንዴት ያለው ፍርድ ይፈረድ ጀመራ ባደባበያችን አይዘህ አንተ ወግኅ አገባብን አለው ለነዚህ ለደሀ ጉዳት ፀሐይ ቢፈጀው ጥላ ፈልጎ እዛፍ ሥር ቢያርፍ ምን አርግ ነው የምትሉት የግፍ ግፍ በብርሌ ድፍድፍ አንተው ደብድበህ አንተው መልሰህ መክሰስ ከየት አገር የመጣ ደንብ ነው እንኳን ቅጣትና ቁንጢጥም አይነካው እንዲያውም በተደባደበበት ክሰህ በደበደብክበት ተቀጥተህ ስትሄድ ይታየኛል ።

አፈ ንጉሥ ፍትን ይጠብቅ ወንጀለኛን ያውድቅ ሰማህ ወዳጄ ጐልማሳ በሚስቱ ደሀ በርስቱ ሲባል ሰምተህም አታውቅ አንተ አፈ ጮሌ ነገረ ደማም ነኝ ብለህ እሱ ለፍቶ ማስኖ ባቀናው መሬት ውሥጥ አልፈህ ተርፈህ ድንበር ረግጠህ ወሰን ገፍተህ ያውም በጨለማ አንድ ቀን ነውና የስሕተት ነው አይባል አንድዬ ዜማ ቈጠራ አንድዬ አህያ እፈልጋለሁ እያልክ ስትመላለስ ኖርክ ዳባሎህም እዚያ ከተገኘ አንተ ያላጠፋህ ማን ያጥፋ አሁንም ለእሱ ገንዘቡን ክፍለህ ለኛ ባከልህ ተቀጥተህ ታገር ትወጣለህ ።

ዓወቀ ፥ እሰይ የኔ ጌታ የዕድሜ ደሀ አያርግብኝ አንሣ ሙርርድህን ።

ሆድ አምላኩ ፥ እነሣሁ ።

ዓወቀ ፥ እኔም አስነሣሁ መንግሥት ይሙት ጥሬ ዋስ ለገንዘቤ

ሆድ አምላኩ ፥ እኔ የሰው አገር ሰው ባይተዋር ማንን አውቄ ማንን እጠራለሁ ተቀጠርክ ዋስ በራሴ ።

ዓወቀ ፥ ስደተኛ ደሀ አንተን እስሬ ምን ላገኝ ነው ቀለብ ትርፉ አልችልም የኔንም ፈንታ መንግሥት ይቅጣልኝ ።

አፈ ንጉሥ ታዲያ ምን ከፋ ሰማህ አንተ ውሰድናእወህኔ ቤት አሳድሩትና ነገ ቅጣቱን ይቀበላል(ዳኛው ይወጣል)።

በጎ ሰው ፥ ድፍረት አይሁንብኝና ስለ ደስታዬ ቤቴን እንድታዩልኝ እለምናችኋለሁ ። በስመ አብ በዬ ።

(ከንግግር በኋላ)የዛሬ ደስታዬ ከልክ ያለፈ ነውና ትንሽ ዘፈን እንድዘፍን ፍቀዱልኝ ደግሞ አማሪኛ ለመዝፈን ይቸግረኛልና በትግሪኛ ስለሆነ እንዳትፈርዱብኝ ።

የትያትሩም ጨዋታ ጃንሆይንና እቴጌን፣ የተቀመጡትን መሳፍንትና መኳንንት ወይዛዝር እጅግ ደስ ስለ አሰኝ ከዚሁ አንዱን ክፍል ለአዘጋጁ ለአቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ፫፻ብር ጉርሻ ደግሞ በቀለባቸው ላይ የቀለብ ጭማሪ፣ ለተማሪዎችም የወርቅ የወርቅ ሰዓትና ፶፶ብር፣ ሰላሳ ሰላሳ ብርና የብር የብር ሰዓት ከጃንሆይ የተቀበሉ ብዙ ልጆች አሉ፡፡ለቀሩትም የሚከፋፈሉት ገንዘብ የተቀበሉ አሉ፣ ሰዓት ያገኙት ልጆች ከሰዓቱ ይልቅ ከጃንሆይ እጅ በመቀበላቸው እጅግ ደስ ብሏቸዋል። ሰዓት ያላገኙ ሲአዝኑ ከመከከላቸው የነበረ አንዱ አዋቂ እንዲህ ብሎ አጽናናቸው በ፩ጊዜ ሁሉ ሰዓት ያገኘ እንደሆነ አይስማማምና የተቀበላችሁትን አመስግኑ እንጂ ግድ ሰዓት ካላገኘን ብላችሁ አትዘኑ። ብታዝኑም ሰዓት አለሰዓቱ እንዳይገኝ አወቁ አለ።የትያትሩም ጨዋታ ከ፲ ሰዓት ጀምሮ ከማታው እስከ ፩ሰዓት አመሻ ለነበረው ሰው ግን ምንም የቆየ አልመሰለውም ነበር።

የተማሪ ቤት በዓል ።

በሐምሌ ፲፬ ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ስለክረምቱ ዕረፍት ለማድረግ የሚዘጋበት ቀን ነበረ በዚሁም ቀን የተማሪዎችን ዕድል ለማየት የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፣ ልዑል ራስ ሥዩምሌሎችም የኢትዮጵያ ሕዝብ መኳንንትና የውጪ አገር ሰዎች ነበሩ በመጀመሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ከሙዚቃ ጋራ ተዘመረ ከዚህ በኋላ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር መልአከ ሕይወት ወልደሐና የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ።
ልዑላን መሳፍንት፣ ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር ሆይ።

ስለክረምቱ ዕረፍት ምክንያት የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ተማሪዎች የሚሰናበቱበት ጊዜ ስለ ደረሰና እንደተለመደው በትምህርት የበለጡት ተማሪዎች በሚሸለሙበት ቀን ልዑል አልጋ ወራሽ፣ልዑላን መሳፍንትና፣ክቡራን መኳንንት ጥሪአችንን አክብራችሁ ስለመጣችሁ እንደዚሁም የውጭ አገር ሰዎች ለደስታችን ተባባሪ ለመሆን ከዚህ ስለ ተገኙልን በራሴ በሹማምንቶቹና በተማሪዎችም ስም ሁሉ ምስጋናዬን ከብዙ ማክበር ጋራ አቀርባለሁ ።

ይኸውም መጐብኘታችሁ ለተማሪ ቤታችን የሚአስከብር ለተማሪዎች የሚአተጋጋ ለሴቶች ልጆች ኃፍረት የሚከላ ስለ ሆነልን እጅግ ደስ ብሎናል ።

በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ ይህ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ከተመሰረተ በኋላ ትምህርቱ የተጀመረው በ፲፱፻፳፩ ዓም ነው ከዚያ ወዲህ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ለከፍተኛ ትምህርት ከሚዘወሩትበቀር ፫፻፲፯ ተማሪዎች አሉ ከነዚሁም ውሥጥ ፶፭ቱ ሴቶች፣ የቀሩት ወንዶች ናቸው። ደግሞ ፲፭ የኢትዮጵያ አስተማሪዎች አሉን ከነዚሁም ፫ቱ ሴቶች፣ የቀሩት ወንዶች ናቸው። ስለትምህርቱ አኳኋንና ዓይነት ከሁለት ላይ ተከፍሏል ፩ደኛ የቋንቋና የትምህርት አገባብ ሁሉ፣ ሁለተኛ የጥበብ ሥራ ነው የቋንቋና የትምህርት አገባብ ከሁለት ተከፍሏል ያል ነው አንደኛ የኢትዮጵያ ትምህርት፣ ሁለተኛ ያውሮፓ ትምህርት ነው ።

ስለ ጥበብ ሥራ ።

ሴቶች ልጆች ከዚህ ከመለከትነው ትምህርት በላይ ጥልፍ ስፌትና ይህን የመሰለ የጅ ሥራ ይሠራሉ ይኸንኑም በግርማዊነታቸው ፊት ለማስመስከር የተዘጋጀን ነን ግን ለወንዶቹ ተማሪዎች ያዘዝነው የጥበብ መሣሪያ ሳይደርስልን ስለ ቀረ በእረፍቱ ውሥጥ ተዘጋጅቶ ለሚመጣው አዲስ ዓመት እንዲጀምሩ ቊርጥ ሐሳብ አድርገናል ።

እስከ አሁን ድረስ ያቆምናቸው ተማሪ ቤቶች ተምሮ ለማወቅ አውቆ ለመራቀቅ ከዚያም ወዲያ ለሊቅነት የሚያደርሱ ጉዳዮች ስለሆኑልን የትምህርት ወገን ደህና ተካሂዶልናል ለሚቸግረን ጉዳይ ሁሉ የሚገቡልን ብዙ ልጆች አድርሰናል ነገር ግን አሁን ለኛ በጣም የሚያስፈልገንና በተውሶ እቃ ተወስኖ ተመኖር የሚያስጥለን የትምህርት ወንድም ጥበብ ነውና ምንም እንኳን በየተማሪ ቤቱ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ትጋት የተዘጋጀ መሣሪያ ቢኖር ከፍ ያለ የጥበብ ሥራ ለማቆም እንድንችል ከ፲፱፻፳፫ ዓ ም ጀምሮ ወደፊት ለልጆች መማሪ ለሕዝብ መጥቀሚያ የሚሆን ፋብሪካና ለዚህ የሚገቡ መምህራን እንዲፈቀድልን ግርማዊነታቸውን እንለምናለን።

ምንም የሰው ተፈጥሮው አንድ አይነት ቢሆን ስጦታው እየቅሉ ነውና ተማሪዎቻችንን ያየ አንድ አንዱ ስጦታቸው በከንቱ እንዳይቀርብን ከዚህ በላይ የመለከትነው የጥበብ ሥራ በቶሎ ተጀምሮልን በትጋት እንድናስፋፋው በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቸርነት ተመርኩዘን የጸና ተስፋ እናደርጋለን ።

ዕድሜ ለጃንሆይ ። ዕድሜ ለእቴጌ ። ዕድሜ ለልዑል አልጋ ወራሽ፣ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

እጅግ የሚአምር ትያትርም ተደርጎ ነበር ።

መልክም ስጦታ

እስከ ዛሬ የተለየ ለንጉሠ ነገሥቱ ልዩ የባቡር ሠረገላ አልነበረም። አሁን ግን እንዲያስፈልግ ስለተረዳው ኩባንያው አውቆ ስለ ጃንሆይ ዘውድ በዓል መታሰቢያ የሚሆን በጥሩ የተሠራ በባቡር የሚሳብ ሠረገላ ለጃንሆይ ስላሰጠ ይህኑ ሠረገላ ለመረከብ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ሚኒስትሮችም ወደ ባቡር መቆሚያ በሐምሌ ፲፰ቀን በ፱ ሰዓት ተኩል ወርደው ሠረገላውን ተቀበሉ። የፈረንሣዊ ሚኒስትርም ከዚያው ነበሩ ሠረገላውንም አይተው ተመልሰው በተዘጋጀላቸው ቦታ ተቀምጠው ሸምፓኝ ቀርቦ የባቡሩ ኩባንያ ሹም የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ጃንሆይ

የዛሬ ሐያ ወር ጃንሆይ በነገሡበት ጊዜ ፲፫መንግሥታት ልዩ የሆኑትን አምባሳደሮች ጃንሆይን ለማመንገና ደስታዎን ለመካፈል በላኩ ጊዜ ፕሬዚዳናችን ሙሴ ማክሲም ዡቴጂ

በፍራንኮ ኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩፓንያ ስም ሁነው ጃንሆይ ለነገሡበት ቀን መታሰቢያ እንዲሆን ጥልቅ የሆነ አክብሮታቸውንና የፍቅር ምልክት ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥትለመግለጽና ለወደ ፊት መንግሥትዎ የሚሠራውን መንገድ ሥራ እንዳለፉት ጊዜያት በቅንነት ከዚህ በፊት እንደሠራነው ለመረዳት ምኞታቸውን ለማሳየት ይህን ስጦታ ሰጡ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አንድ አንድ ጊዜ ምክንያት አግኝተው በብረት መንገድ በሔዱ ጊዜ አንድ የተለየ ጋሪ ለጃንሆይ ያቀረብን እንደሆን ለዚህ ለተመኘነው ሁሉ የሚስማማ መስሎ ታየን ።

ይህን ጋሪ ለግርማዊነትዎ ለመስጠት ቊርጥ አሳብ ካደረግን በኋላ ደስ የሚያሰኝና የሚያምር ሁኖ በቶሎ ተሠርቶ የማለቁ ነገር ሥጋት ሁኖብን ነበር ።

አሁንም በዚህ በጋሪው ላይ ያለው ዕቃና ራሱ ጋሪው ተስማምቶ እንዲሠራ ተተጣቆበት የነበረው ሥራና ጌጡ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን በፍጹም ደስ ያሰኝዎታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። አሁንም ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በምድር ባቡር ኩምፓንያ አማካሪዎች ማኅበረተኞች ሁሉ ሠራተኞቻችንና በፍራንኮ ኢትዮጵያ የምድርባቡር ኩምፓንያ ስም ሆኜ ባንድ አሳብ ይህን ቢጎን ሳሎን በማክበር አስረክባለሁ ።

ቀጥለውም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የሚከተለውን ዲስኩር መለሱ ።

የምድር ባቡር ኩምፓንያ ወኪል

ለነገሥንበትቀን መታሰቢያ የምድር ባቡር ኩምፓንያ ወዳጅነቱን ሊገልጽልን ሲል የሰጠንን ልዩ ጋሪ እኛን ደስ ለማሰኘት የእውነት ፈቃድ እንዳለው ገልጾ ያሳየናል ።

ይኸውም ልዩ ጋሪ አሠራር በጥንቃቄ በመሠራቱና በመዘጋጀቱ የምድር ባቡር ኩምፓንያ የሥራ አማካሪዎች ነገሩን በመቍረጣቸው ያሰቡባቸው ፍቅር በጣም ተሰምቶናል።

አሁንም ለተመሰገኑ ፕሬዚዳንቾሁ ለሙሴ ማክሲም ገርቱን ከፍ ያለ ምስጋናችንንና ደስታችንን ገልጸው እንዲነግሩልን እንለምንዎታለን ።

የምድር ባቡር ኩምፓንያ ሥራ ከመንግሥታችን ጋር እየተስማማ ሥራው እየተስፋፋ እንዲሔድለት ፈቃዳችንን እናረጋግጥለታለን ብለው ጨረሱ ።

ከዚህ በኋላ ሙሴ ሐዘር የባቡር ሹም የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

የኤክስፕሎታስዮን ዲሬክተር በመታመማቸው የምድር ባቡር ኩምፓንያ ለጃንሆይ ለመስጠት የቆረጠውን ቢጎን ሳሎን ለማቅረብ ስላልተቻላቸው እኔ ስለሳቸው ሁኜ እንዳቀርብልዎ በመታዘዜ እጅግ ክብር አገኘሁ ።

ጃንሆይ፣ በዚህ በጌጠኛ ቢጎን ለወደፊት በብረት መንገዱ በመልካም ምኞት እየተመላለሱ አገርዎ ለኛ ሁለተኛ አገራችን የሆነውን እንዲለማ ለማድረግ የሚሰሩትን የምድር ባቡር ሠራተኞች በሥራቸው እንዲጠነክሩ የሚያበረታታቸው ነገር ነውና ስለዚህ በምድር ባቡር ሠራተኞች ሁሉ ስም ሁኜ ከፍ ያለ ደስታችንን ለግርማዊነትዎ እገልጻለሁ ።

ትልቁ የማህበሩ ሥላሴ ትውልድ ኢትዮጵያን እንግዳ ተቀባይ አገር ለማድረግና በኢትዮጵያ የሚኖሩት እንግዶች ሁሉ እንደ አገራቸው እንዲኖሩ ከልብ መሥራታቸውንና ደግሞ አሁንም ጃንሆይ አገርዎ ለዚሁ እንዲተጋ ዛሬ የሚሠሩት እጅግ ይሰማናል ይህንኑ ምክንያት ይዤ በምድር ባቡር ኩምፓንያ ሠራተኞች ሁሉ ስም ሁኜ ይህ የጀመሩት ሥራ ሁሉ ያለችግር እንዲከናወንልዎ ዋና ምኞታችንን ሳቀርብ በበኩላችን ላገልግሎታችን እምነት እንዲያደርጉ ለጃንሆይ አረጋግጥልዎ ዘንድ ይፈቀድልኝ ፤ ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ያኑራት ።

የመስኮብ ጋዝና ቤንዚን በኢትዮጵያ ስለመግባት።

ከዚህ ቀደም ጋዝና ቤንዚን በኢትዮጵያ የሚያገቡ ጥቂት ሰዎች ነበሩ ። እነሱም ለመሮከከር ትንሽ ቀን ዋጋ እያዋረዱ መሸጥ ዠምረው ነበር ። ይህም መሮከከራቸው ለሕዝቡ ታላቅ ጥቅም ሁኖለት ነበር። ነገር ግን እነዚህ ጋዝና ቤንዚን የሚያመጡት ሰዎች ቊጥራቸው ያልበዛ ስለሆነ ፤ አንድነት ተስማምተን ከዋጋው በላይ ሕዝቡን እያስከፈልን ከልክ ያለፈ ትርፍ ብናገኝ ይሻላል እንጂ የኛ ትርፍ በምን ምክንያት ያንስብናል ብለው ቆረጡ ከዚህ በኋላ የምንዛሪና ሌላም ልዩ ልዩ የሆኑ ምክንያቶች እየሰጡ የራሳቸውን ከልክ ያለፈ ትርፍ ብቻ በመፈለግ የሕዝቡን መጐዳት ሳያስቡ ከብዙ ጊዜ ጀምረው እስከ ዛሬ ድረስ ሲሰሩ ቆዩ ይህንንም ሲያደርጉ ከኛ በቀር ሌላ ሰው የሚሮከከረን የለም ብለው ነበር ነገር ግን የሕዝቡን መጠቀምና ልማት የሚፈልጉ ንጉሠ ነገሥታችን ይህን አደራረግ ወዶ ዝም ብሎ ለማየት አይጨክኑምና ሕዝቡ ጋዝና ቤንዚን በውነተኛው ዋጋ እንዲገዛ አሰቡ ከዚህ በኋላ በመጠየቅ ብዛት የተነሳ ሱኢዝናፍ ኤክስፖርት የሚባል የመስኮብ ጋዝና ቤንዚን የሚያወጣ ሴንዲካ እኔ በርካሽ አሸጣለሁና ግዙኝ ሲል ጥያቄውን አቀረበ ። መንግሥታችንም የሚመኘው ይህንኑ ነበርና የዋጋውን ነገር እንዲነጋገሩ ሠራተኞቹን አዘዘ ንግግሩ ካለቀ በኋላ ጋዝና ቤንዚኑ እንዲመጣ ተደርጎ ይኸው እነሆ በሀገራችን መግባት ጀምሯል ።

የመስኮብ ጋዝና ቤንዚን ሊመጣ ነው ሲባል ገና በወሬ የጋዝና የቤንዚን ዋጋው ወረደ ። እንግዲህ በውድ ይሸጡ የነበሩት ሰዎች ከዋጋቸው አውርደው መሸጥ የግድ ሊሆንባቸው ነው ። ከዚህ ቀደም የመስኮብ ጋዝና ቤንዚን የመምጣቱ ወሬ ሳይሰማ አንድ ማጥን ቤንዚን እስከ ፳፰ ብር መሸጡን ሰው ሁሉ ያውቃል ። ጋዝም አንዱ ማጥን እስከ አሥራ ስድስት ብር ተሸጧል ። ስለዚህ ከጥር ፲፱፻፳፫ ዓ ም እስከ ታኅሣሥ ፲፱፻፳፬ ዓ ም ባንድ ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ ፺፫ሺ ፭፻ ማጥን ጋዝ ያህል መጥቷል። ይህም የተሸጠበት ዋጋ ፳፻፶፯ሺ ብር ያህል ይሆናል። ዛሬ ግን ይህኑ የሚያህል ጋዝ ከ፯፻፵፰ሺ ብር የበለጠ አያወጣም ። እንዲሁ ደግሞ ከዚህ በላይ ባስታወቅነው ዓመት ውስጥ ፳፬ሺ ፬፻ ማጥን ቤንዚን ያህል መጥቷል የተሸጠበትም ዋጋ ፯፻፳፩ሺ ፯፻ ብር ያህል ይሆናል ። ዛሬ ግን ይህኑ የሚያህል ቤንዚን ከ፬፻፹፯ሺ ፫፻ ብር የበለጠ አያወጣም እንግዲህ የዛሬው ዋጋ ሲታይ ሕዝቡ ሊከፍለው ከሚገበው

ዋጋ በላይ የ፱፻፳፰ ፫፻ ብር ያህል ትርፍ ገንዘብ ሲከፍል መቆየቱን ይገልጻል።

አባት ለልጁ እንደሚያስብ ንጉሠ ነገሥታችንም የኢትዮጵያን የንግድና የሥራ ማኅበር በመርዳት የሚያስፈልገንን ጋዝና ቤንዚል በርካሽ ዋጋ እንድንገዛ ስላደረጉልን ምስጋና ይገባቸዋል ። ከዚህ ቀደም ጋዝና ቤንዚን የሚሸጡ ሰዎች ከዋጋቸው ቢያወርዱም ከመስኩብ አገር በመጣው ጋዝና ቤንዚን ምክንያት ነው እንጂ ዱሮ በትክክለኛ ዋጋ ቢሸጡ የከለከላቸው ሰው አልነበረም ። ስለዚህ አሁን ጋዙ ቤንዚኑም የተጠቀለለበት ጣሣን መጥፎ ነው ። ዓይነቱም መልከም አይደለም እያሉ የፖሊቲክም ነገር እያቀላቀሉ የምቀኝነት ወሬ ብያወሩ ይሻላቸዋል ። ስለምን ማለት የራሱን ጥቅም የማያውቅ ሰው አይገኝም ። በውድ ከመግዛት በርካሽ መግዛት መሻሉን ዓለም ሁሉ ያውቀዋል ። ስለዚህ የምቀኝነት ወሬ ያቀላል እንጂ አያስከብርምና መጠንቀቅ ይሻላቸዋል ስንል እንደገና እናመለክታለን ።

የጋዙንና የቤንዚኑንም ጥሬት ለማወቅ የሚፈቅዱ ሰዎች እንዳሉ የጂቡቲ የመንግሥት ሆፒታል ላቦራቷር በአፊሲዬል መርምሮ የመስከረባቸው ወረቀቶች፣ በንግድና በሥራ በኢትዮጵያ ማኅበር ዘንድ አሉና መጥቶ ለማየት ይችላል ስንል ለሕዝብ እናስታውቃለን ።

ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም

ማስታወቂያ ።

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባህ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ ።

ማስታወቂያ

ዶክቶር አምባር ለሕዝብ ጥቅም እንዲሆን ዮሁን አዲስ የከትባት ክፍል አቋሞአል የፈንጣጣ ትኩስ የከትባት መድኃኒት አሰናድቶ ይከትባል ደግሞ ያበደ ውሻ የነከሰውን የሚያድን መድኃኒት እንደዚሁ አሰናድቶ ይከትባል የሚከትብበት ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምባሳል ፥ የልብ ፥ የደረት የጉበት ፥ የኩላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቁቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ (ቤትና የመሬት ግዢና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ያ ፣ ገን ብ ማበደር

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዶች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቀረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጎበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ግዙታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመንበኛት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል።

ማስታወቂያ ።

በሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፴፱
8me ANNE. № 39

ሐሙስ ሐምሌ ፳፪ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 28 AOUT 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ፡ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለኡቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ፡ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ዕድል ወይም ስጦታ ።

በዓለም ላይ ለሰው ልጆች የተሰጡ ልዩ ልዩ ዕድሎች አሉ ፤ ከነዚሁም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

፩ኛ፤ አንድ አንድ ሰው፥ ልበ ብሩህና ተመልካች ሁኖ ሳለ የልቡን ብልህነት በሥራ ገልጦ ለማሳየት፥ በቃ ተናግሮ ለማስረዳት፥ የሚቸግረው አለ።

፪ኛ፤ደግሞ አንድ አንድ ሰው ልበ ብሩህና አስተዋይ ሁኖ ለመሥራት የሚችለውን ሥራ፥ በቃ ለማስረዳት የሚያውከው፥ ሥራውን ግን አሳምሮ ሠርቶ የሚያሳይና ደስ የሚያሰኝ አለ።

፫ኛ፡ ደጋሞ አንዳንድ ሰው ልቡም አፉም ብልህ ሁኖ የልቡን አስተዋይነት፥ በቃ ገልጦ የሚያስረዳ ንግግር የሚያሳምር ከፉውን መልከም፥ መልካሙን ክፉ አስመስሎ ሲጽፍ የሚመስልለት፥ ራሱ ግን ሠርቶ ለማሳየት ከቶ ጭራሽ የማይሆንለት አለ። የልብ ብልህነትን ፥ ያንደበት ቀናነትን፥ ሠርቶ ማሳየትን፥ እነዚህን ሦስቱንአንድነት ይዘው የሚገኙ ዕድለኞች ሰዎች ጥቂቶች ናቸው።

ይህንንም ለመናገር ያሳሰበኝ በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በ፯ተኛው ዓመት በቍጥር ፯ ከ፵፱ እስከ ፶፭ ገጽ ብላታ ዴሬሳ ስለ ገንዘብ ችግር ብለው የጻፉትን ተመልክቼ አነሳስቶኝ ነው። ብላታ ዴሬሳ እንደ ዛሬ በመንግሥት ሥራ ላይ ሳይሆኑ ቀድሞ በየጊዜው የሚጽፏቸውንጋዜጣዎች እየተመለከትን ይልቁንም ስለርሻና ስለከብት ማርባት ነገር የጻፉትን እያየን እዩ ይኸን የመሰለ ሰው ባንድ መንግሥት አድሚኒስትራሲዮን ላይ ቢሆን እንዴት ያለውን ሥራ ሠርቶ ባሳየና ባተደነቀ እያልን ስንመኝ ነበር። ኋላ ግን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴ እንደ ሕዝቡ ሁሉ ተመልክተዋቸው ኑሮ የርሻ ሚኒስቴር ዲሬክተርነትን ስለሾሟቸው እጅግ ደስ አለን። ደስታችንም ብላታ ዴሬሳ ፊት ሥራውን ሳይዙ ስለ እርሻ ስፋትና ስለከብት ማርባት በየጊዜው በጋዜጣ ይጽፉት የነበረውን ቃል ዛሬ ለዚህ ለሥራ ዲሬክተር በመሆናቸው ሥራውን አከናውነው ወሬ የነበረው ቀርቶ ሥራ ሁኖ ሲታይ ታላቅ ጥቅም የሚያፈራ መስሎ ስለታየን ስንጠባበቅ ቈይተን ነበር።

አሁን ግን እንደሚሰማው የተሾሙበት ክፍል ሥራ፥ ከቀድሞው እያገደለ እንጂ መሻሻሉ ስለ ቀረ ብላታ ዴሬሳ ስጦታቸው ከዚህ በላይ በሦስተኛው ክፍል እንደተጻፈው ዓይነት መሰለን።

ይህንንም ማለት ምንም ቢሆን ሰው ተመርጦ እንዲሠራ የታዘዘውን ሥራ ሠርቶ ማሳየቱን ለሕዝብ ምሳሌ መሆኑን ትቶ ለገዛ ሥራው እንደ ጐረቤት ሁኖ እንደዚህ ቢሠሩት እንደዚህ ቢያደርጉት እጅግ መልካም ነበር እያለ የምኞቱን ወሬ ብቻ በየጊዜው ለሰው ሁሉ ቢያካፍል ጥቅሙ ምንድንነው? ይልቁንም ደግሞ ብላታ ዴሬሳ በገር ግዛት ሚኒስቴር ክፍል ስለ አገር ግዛት፥ በገንዘብ ሚኒስቴር ክፍል ስለ ገንዘብ ነገር በንግድ ሚኒስቴር ክፍል ስለ ንግድ ነገር፥ በርሻና በመሥሪያ ሚኒስቴር ክፍል ስለ እርሻና ስለ ከብት ማርባት ነገር ጽፈዋል፥ ለሦስቱ ሚኒስቴር ክፍል ሥራ ምክር ከመስጠት ይልቅ አስቀድሞ ክፍላቸው ለሆነ፥ በኃላፊነት ለተቀበሉት ሥራቸው ለርሻ ሚኒስቴር፥ ይህን በጋዜጣ ብቻ የሚያጠጣቡንን ምክር ምነው ራሳቸው ሥራውን ሠርተው አያሳዩን?

ስለዚህም ስለጻፉት ጋዜጣ መልሱን በዝርዝር አድርጌ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እገልጻለሁ።

መጀመሪ በሮፓ ያሉት ሀብታሞች አንድ ላይ፥ ገንዘባቸውን ሰብስበው ቈጭ ስላደረጉት፤ በየሰው እጅ ያለው ገንዘብ ለዓለም ጉዳይ የማይበቃ ሆነ ላሉት ፤ እነዚህ ሀብታሞች የቈ ባሉት ገንዘባቸው እየተዘዋወረ ቢያተርፍላቸውና ጥቅም ቢያገኙበት ጠልተው አይደለም ፤በሁኑ ጊዜ በሮፓ ንግድ ስለተዋረደና ከሬዝ ስለሆነ፤ ግድ ሁኖባቸው ነው እንጂ ገንዘባቸው እንደተከማቸ ሥራ ፈትቶ ያለ ጥቅም ቢቀመጥ ፈቃዳቸው ሁኖ አይደለም ፤ ይኸንኑም ብላታ ዴሬሳ በሀብታሞች ፋብሪክ የተሠራው ዕቃ ገዢ አጥቶ ፋብሪካቸው መዘጋቱን በመናገራቸው አስረድተዋል ።

ባገራችን ያለው ገንዘብ ብር ነውና የጥሬ ብር ዋጋ ረከሷል ላሉት ብር የረከሰው በሮፓ ነው እንጂ ለኛ አገር ዕቃ አይደለም ፤ ብር በኢትዮጵያ ውሥጥ ከቀድሞው ይልቅ ዛሬ ሥራውን ይሠራል።

የኛ ብር የምንለው በንጉሠ ነገሥቱ መልክ ስላልታተመና የወርቅ ዋስትና ስለሌለው ዋጋው እንደጠገራ ሁኖ ረከሰ ላሉት በዚህም ነገር ብላታ ዴሬሳ ፈጽሞ ተሳስተዋል ፤ ዛሬ

በውሮፓም ቢሆን የወርቅ ዋስትና ያለው በንጉሡ መልክ የታተመው ገንዘብ በብዙ አገር ውሥጥ ዋጋው ረክሶ ችግር ሁኑዋል፤ ብላታ ዴሬሳም ይህንን የተናገሩትን ቃል ለውጠው በዚሁ ጋዜጣ ላይ የእንግሊዝ ጊኒ ዋጋው በጣም ተዋርዷል ሲሉ ጽፈዋል፤ ይህንንም ካሉ በኋላ እንደገና ደግሞ የወርቅ ዋስትና ያለው ገንዘብ ስለሌለን ብራችን ረክሰ ብለው ወዲያው መልሰው የወርቅ ዋስትና ያለው የእንግሊዝ ጊኒ ዋጋው በጣም ተዋርዷል ብለዋልና፤ አንዱን ነገር አንድ ጊዜ መልካም አንድ ጊዜ መጥፎ ብሎ መጻፍ ባንድ ራስ ሁለት መላስ ተብሎ የተነገረው ተረት ለካ እሳቸውን ለመሰለ ሰው ኑሯል ያሰኛል፤ለጻፉት ጋዜጣ መልስ በመስጠት ነገሩን ለማስረዳት ነው እንጂ እንደ ሌሎቹ መንግሥታት ሁሉ የወርቅ ዋስትና ያለው በንጉሡ መልክ የታተመ ገንዘብ ለማውጣት የኢትዮጵያ ብርሃን የሆኑ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ገና ከብዙ ዓመት በፊት ማሰባቸውን ከብላታ ዴሬሳ በቀር ያልተረዳው የለም ይህንንም በማሰባቸው ምክንያት የወርቅ ዋስትና ያለው ገንዘብ ለማውጣት እንዲመቻቸው አዲስ አበባ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ተብሎ ይጠራ የነበረውን የእንግሊዝ ባንክ ገዝተው ገንዘቡንም ባንኩንም፤ በታውንና ቤቱንም ሁሉ፤ ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት አዙረው ስሙን የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንክ ብለው ሰይመውታል የወርቅ ዋስትና ያለው ገንዘብ ለማውጣት በእርግጥ ማሰባቸውን የሚያስረዳም ፊት የእንግሊዝ ባንክ አውጥቶ ይገበያይበት የነበረውን ባንክ ኖት አስቀርተው የኢትዮጵያ ባንክ ተብሎ የታተመበት አዲስ ባንክ ኖት (የገንዘብ ወረቀት) አውጥተው እነሆ ዛሬ ፈረንጁም ሕዝቡም የሚገበያየው በዚህ ባንክ ኖት ነው፤ ይኸውም ባሁኑ ጊዜ ላለን ለኢትዮጵያ ልጆች ዋና እድገታችንና ዕድላችን ነው ።

ብርሃናችን አፄ ኃይለ ሥላሴ በታላቅ ትጋት ለሀገራቸው ልማት በማሰባቸው ፤ ደሀ ለኛ ለሕዝባቸው ጥቅም ሲሉ ያዞሩልን የኢትዮጵያ ባንክ ፤ለብዙ ነጋዲዎችና አራሾች ገንዘብ እያበደረ መርዳቱንና ማገልገሉን ባንኩንም እየሠራ ለመንግሥት ብዙ ትርፍ መስጠቱን ብዙዎች አዋቂዎች በእርግጥ ተደንቀውበታል ።

የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ፤ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ስንኳንስ ለነጋዴና ለገበሬ እያበደረ የሚያገለግልና የሚረዳ ለመንግሥትም ትርፍ የሚሰጥ ባንክ ማግኘታችን ይቅርና እንዲያውም ቢሆን ትርፍም ባናገኝበት ግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ስለ ሕዝባቸው ጥቅም በመቅናት ስለ ሀገራቸው ጉዳት በማሰብ ፩ኛ ጥቅማችንን ይወስድብን የነበረውን የውጭ አገር ባንክ ነቅለው፤ ገንዘቡንም ርስትነቱንም ለኛ ለኢትዮጵያ ልጆች መትከላቸው ፤፪ኛ የእንግሊዝ ባንክ ተብሎ ሲጠራ የነበረውን ባንክ ፤ አሁን ወደኛ አዛውረውልን የኢትዮጵያ ሕዝብ ባንክ ተብሎ መጠራቱ፡ የኢትዮጵያን ገናናነቷን የሚገልጽ የልጆቿንም ዕድል የሚያሳይና የሚያኮራ ስለሆነ በዚህ በአሁኑ ሥራቸው ብቻ የሰውን ድካም ዋጋ በማያስቀር በታላቁ እግዚአብሔር ዘንድ ዋጋቸው ምን ያህል ይሆን ? እኛስ የኢትዮጵያ ልጆች ይኸንን መልካም ወሮታቸውን በምን ዓይነት መንገድ ይሆን የምንመልሰው? የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ አንባቢዎችና ሰሚዎች፤ በየጊዜው የሚሠሩልንን በጎ ሥራ ብሩህ ልባችሁ ያመዛዝነው ።

ብላታ ዴሬሳ በስሕተት ብር በኢትዮጵያ ረክሰ ብለው የጻፉት የማይታመን መሆኑን ለማስረዳት ጻፍሁ እንጂ የኤኮኖሚክ ፖለቲክ ወይም የፊናንስ ሥራ እጅግ ጠሊቅና ረቂቅ ስለሆነ በተለየ ለዚሁ ሥራ አዋቂ (እስፔሲያል)ያልሆነ ሰው እንዲያው አፉ እንዳመጣ ዛሬ ገንዘብን ረክሰ ብሎ እርግጠኛና ቁርጥ ነገር አድርጎ ፤በጋዜጣ አውጥቶ ለማስረዳት ስንኳንስ ብላታ ዴሬሳ ፤ በውሮፓና በሚሪካም ቢሆን ብዙ ሰዎች የገንዘብን ጥቅምና አኳኋን(የፊናንስ ሥራ) ለመማር ብዙ ጊዜ ዘመናቸውን በትምህርት ቤት አሳልፈው ፤ ኋላም በገንዘብ ሥራ ላይና በታላላቅ ባንኮች ላይ ተቀምጠው የሠሩና ፕራቲክ ያደረጉ ዋና የገንዘብ አዋቂዎች ተብለው የተጠሩ ሊቃውንቶች እንኳ በሮፓ ያለውን የገንዘብ ችግር ለማዳን ተቸግረው ከብዙ ዘመን ጀምረው እስከሁን ይደክማሉ ዛሬ በዓለም ላይ ያለውን የገንዘብ ችግር(ክሪዝ ሞንዲያል) መድኃኒቱንና ፍጻሜውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው ።

በዕቃ ግዢ ላይ የብር ዳግመኛ ዋጋ ጉደለና የኢትዮጵያ ሕዝብ ፲ብር የነበረው ፶ብር ሺብር የነበረው ፩፻ብር ሆነበት ባገር ውሥጥ የነበረውም ብር በዕቃ ሻጮች እጅ ገባ ላሉት እነዚህ ዕቃ ሻጮች ብሩን ወዴት ወሰዱት ማለታቸው ነው?፥ ብር ፈላጊ ዕቃውን ለብር ይሸጣል፥ ዕቃ ፈላጊ ብሩን ለዕቃ ይሸጣል እንጂ፥ ዱሮውንስ ቢሆን ብርና ዕቃ አንድነት መቼ ይቀመጣሉ? ገበያ ማለት እንደዚሁ እየተዘዋወረና እየተለዋወጠ አይደለምን? በተቀረጣ ብርም፥ ዕቃም፥ ሽቀጥም፥ ባንድ ሰው እጅ የሚገኝ ቢሆን፤ መለዋወጥስ ገበያስ መቼ ያስፈልግ ነበር፥? እነዚህ ዕቃ ሻጭዎች ዕቃቸውን ለባላገር በሸጡ ጊዜያት ብር ቢወስዱ፥ ዳግም መልሰው በዚሁ በብር ቆዳና ቡና ሰም ዝባድ ሌላም ይኸን የመሰለ ዕቃ ከሕዝቡ ላይ ሲገዙ፥ ያሁ የወሰዱት ብር ተመልሶ በባላገሩ እጅ መግባቱ አይደለምን? ዳግም ዕቃ ሻጭዎች ኢትዮጵያ ያለውን ብር ጭነው ወደ ፈረንጅ አገር ወሰዱት እንዳይባል ብላታ ዴሬሳ ብር በፈረንጅ አገር እጅግ ረክሶ እንደ ጠገራ ሁኑአል ብለው ጽፈዋልና ምን ሊያደርግላቸው ይወሰዱት ይሆን? እንደ ብላታ ዴሬሳ ሐሳብስ ቢሆን ብር በዕቃ ሻጭዎች እጅ ገብቶ እነሱ ብሩን እየጫኑ ከወሰዱት፥ አገሩ ውስጥ ያለው ብር ያንሰና መርከሱ ቀርቶ ይወደድ ነበር እንጂ መቼ የሚያረክሰው ነገር ነው? አንድ አንድ ጊዜ እንኳ ብር ቢሔድም ወደ አደንና ወደ ዓረብ አገር ነው፤ይህንኑም እስታትስቲኩ ገልጦ እንደሚያስረዳው ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር የወጣው እንደ ሮፓ ቍጥር በ፲፱፻፲፱ ዓመት ፪፻፶፬ሺ ብር፥ በ፲፱፻፳፩ ዓመት ፩ሚሊዮን ፬፻፶፯ሺ ፪፻ ብር ስለሆነ፤ ብላታ ዴሬሳ በመለከቱት በ፪ዓመት ውስጥ የወጣው በድምሩ ፩ሚልዮን ፯፻፲፩ሺ፪፻ብር መሆኑ ነው፥ እንግዲህ ከኢትዮጵያ በ፪ ዓመት ውሥጥ ፩ሚሊዮን ፯፻፲፩ሺ፪፻ብር ሲወጣ፤ብር በዕቃ ሻጭዎች እጅ ገብቶ ከባላገሩ እጅ ብር አነሰ ብሎ ለመጻፍ ያስደፍራልን ይህንንስ ለማለት ያደፋፈራቸው ከቶ በመላው ኢትዮጵያ ያለው ብር ሁሉ፥ ምን ያህል መስሎ ቢታያቸው ይሆን? የወርቅ ዋስትና ስላለው ገንዘብ በስሕተት

እንደተናገሩት ሁሉ፤ እንደዚሁ ስለ ብርም ፩ጊዜ ብር ረክሰና ባላድ ይገዛ የነበረው በብር ሆነ ብለዋል፡ ወዲያው መልሰው አፍርሰው ብር በዕቃ ሻጭዎች እጅ ገባና በባላገር ብር እንዷል (ተወደል) ብለዋል ፤

እንባቢዎች፤በማያውቁት ሥራ በመግባታቸው እንጂ በለማወቃቸው አትፍረዱባቸው፤ የእንግሊዝ ጊኒ በጣም ተዋርዷል ምናልባት እንደ ጊኒው ሁሉ ፍራንክና የአሜሪካን ዶላር የወረደ እንደሆነ፤ የቡንና የቆዳ ዋጋ ከሁኑ የበለጠ በጣም የሚወድቅ ይመስላል ስላሉት እስከሁን ድረስ እንደተመለከትነው ገንዘብ ሲረክስ ዕቃ ይወደዳል፤ ዕቃ ሲረክስ ገንዘብ ይወደዳልና ፍራንክና ዶላር ዋጋው የተዋረደ እንደሆነ ይልቅ፥ ለቡንና ለቆዳ መልካም ነው እንጂ ጉዳት አይሆንበትም ።

በፋብሪካ ተሠርቶ የሚሸጥ ዕቃ ኑሮን እንዳንሸጥና ገንዘብ እንዳያመጣልን፡ ይህን ለማድረግ ገና አልቻልንም ስላሉትም፥ በዚህም እጅግ ተሳስተዋል፤ በአሁኑ ጊዜያት እንደሌላው አገር ሁሉ ፋብሪካ ኑሮን ዕቃ የምንሠራ ብንሆን፥ ብዙ ጉዳትና ከሥራ ባገኘን ነበር፡ አሁን ላውሮፓና ላሜሪካ ዋና ጉዳት ሆኖ የተሰማው ፋብሪካ ተስፋፍቶ የተሠራው ዕቃ ያለመጠን በዝቶ፥ ገገር በማጣቱ ነው፥ ብዙዎችም ባለ ፋብሪካዎች ዕቃቸውን የሚገዛቸው ስላጡ ሠራተኞቻቸውን አሰናብተው ፋብሪካቸውን ዘግተዋል፤ የተሰናበቱትም ሠራተኞች ሥራ ስለፈቱ በኑሮአቸው ችግረኛ ሆነው ለመንግሥታቸው ታላቅ ሐሳብ ሆነውበታል፤ብላታ ዴሬሳም እንደዚሁ በዚሁ ጋዜጣ፤ በሮፓ ፋብሪካ በዝቶ፤ ዕቃው የማይሸጥ ሁኖ፥ ብዙ ፋብሪካ ተዘግቷል ሠራተኞቹም የሚሠሩት አጥተዋል ብለው ጽፈዋል፡ ከዚህ በላይ የወርቅ ዋስትና ስላለው ገንዘብና፥ ስለ ብርም ነገር፤ በስሕተት እንደጻፉት ሁሉ ስለ ፋብሪካም እንደዚሁ፥ ፩ጊዜ ፋብሪካ ያስበራል፥ ፩ጊዜ ፋብሪካ መልካም ነው ሲሉ ጽፈዋልና ልማዳቸው ስለሆነ እንላፈው ፥ እንመልከታቸው፥ ብዙ ከብት እርብተን ወደ ውጭ አገር ሸጠን፤ ገንዘብ እንድናገኝ፤ የክትባት ሥራ ስላልኖረ ከብቱን በሽታ ፈጅቶብናል፤ እህል እንዳንሸጥ ከኛው አይተርፍም ላሉት፤ ባያስተውሉ ነው እንጂ ከገር የሚተርፍ እህልና ከብት ስላለን፤ ብርሃናችን አፄ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ባላገር እህሉንና ከብቱን በብዙ ዋጋ ሸጦ እንዲጠቀምላቸው አስበው፤ እህልና ከብት ማንም ሰው ቢሆን ወደ ውጭ አገር አውጥቶ እንዲሸጥ ፈቃድ አድርገው፤ ማስታወቂያ ተደርጎ ሳለ፤ በውጭ አገር ገጋ ስላልተገኘ የከብትና የእህል ኤክስፖርታሲዮን ሳይደረግ ቀረ እንጂ፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተርፍ እህልና ከብት በመታጣቱ አይደለም ፤

ወደ ውጭ አገር እህልና ከብት ያልወጣበትን ምክንያት ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ከስረዳሁ በኋላ ፥ እንደ ብላታ ዴሬሳ ሐሳብ እውነት አይደለም እንጂ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተርፍ እህልና ከብት ባይኖር እንኳ ፥ ከገር እንዲተርፍ ለማድረግ ሚያስፈልገውን ነገር ማዘጋጀት የሚገባው ፥ የርሻ ሚኒስቴር ዲሬክተር ይኸን በማድረግ ፋንታ ለግዛ ሥራቸው እንደጉረቤት ሁነው መከርና ጋዜጣ ጸሐፊ መሆናቸው እጅግ ይደንቃል ፥ የክትባት ሥራ ስላልኖረ ከብቱን በሽታ ፈጀው ላሉትም የኢትዮጵያ ዋና ሥራዋ የከብት ማርባት ስለሆነ ፥ በያውራጃው አገርና በባላገሩ ያለውን ከብት እየዞሩ እንዲከትቡና የከብቱን በሽታ በመከላከል የሕዝባቸውን ሀብት ለመጠበቅ ፥ በማሰባቸው ብርሃናችን አፄ ኃይለ ሥላሴ ከ፰ዓመት በፊት ፥ ከታላላቅ ኩፓንዮች ጋር ተነጋግረው እነዚህ የክትባት ሥራ ኩፓንዮች በያገሩ እየዞሩ ብዙ ከብቶች ከትበው አድነዋል ። እንደሰማነው ከሌላው አገር በተቀር በሐረር አውራጃ ብቻ እንኳ ፲፰ሺ ከብት የሚያህል ከትበዋል ይላሉ ፥ ይህም ኩፓንያ ውሉን የተዋዋለው እንደሚገባው በርሻ ሚኒስቴር በኩል ነው አሉ ፥ እንግዲህ እዚህ ላይ የሚደንቅ ሁለት ነገር አለ አንደኛው ፥ ብላታ ዴሬሳ በክፍል ሥራቸው በርሻ ሚኒስቴር ስለ ክትባት ሥራ የተዋዋለውን ኩፓንያና የሚሠራውንም ሥራ እስከሁን ሳያውቁ ቀርተው የክትባት ሥራ ስላልኖረ ከብቱን በሽታ ፈጀው ብለው ጋዜጣ በመጻፋቸው ።

፪ኛው ፤ በክፍላቸው ያለውን ሥራ ስንኳንስ ለመስራት ያለውንና የሌለውን ለማወቅ ሳይችሉ ፥ በኤኮኖሚክ ፖሊቲክ ሥራ ገብተው ባልተረዱት ጉዳይ ምክር ሰጭ መሆናቸው ነው ።

ደግሞ ቀጥለው ፥ አሁን ደግሞ በገዛ እጃችን ያመጣነው ትልቅ ጉዳት አለ ፤ የገንዘብ ወጭአችን በየቤታችን ፪እጥፍ ሆኑዋል ፤ ሁለቱ እጥፍ ስለ ብር መርከስ ፤ ሁለቱ እጥፍ ግን ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየቤቱ ሁለት ዓይነት ኑሮ አለው አንዱ ሰው እንደ ኢትዮጵያ ልማድ ልብስ ፥ የቤት ዕቃ፥ የምግብ ዕቃ ሌላም ዓይነት ዕቃ አለው ግን ይኸውም አንዱ ሰው እንደ ሮፓውያን የቤት ዕቃ፥ ልብስ፥የምግብ ዕቃ ሌላም ዓይነት ዕቃ አለው፤የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ የሁለት ሰው ንብረት ሆነ ይህ አኳኋን ስንኳንስ ለደኃ ለመንግሥትም ያስፈራል ብለው ጽፈዋል ፤ አሁን እንደ ብላታ ዴሬሳ አሳብ እንኳን ብንሔድ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በግምት ፳ሚሊዮን ቢሆን ከዚሁ ከ፳ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ ብላታ ዴሬሳ ሁለት ንብረት ይዘዋል የሚሏቸው ሰዎች ከ፻ ስንት ይሆናሉ ? በግምት በሺህ ቤት ለመቁጠር እንኳን ይቻል አይመስለኝም ለዚሁስ ለኑሮአቸው ባመት የምን ያህል ገንዘብ ዕቃ ቢገዙ ይሆን ጉዳት አገኛቸው ያሉን ? ይኸንን በመመርመር ጊዜ ከማሳለፍ ሁለት ንብረት ላሉት መልሱ የሚከተለው ነው ፤ አንድ ሰው አሮጌ ኑሮውን ለማሻሻልና ለመተው ፤ ወደ አዲሱ ሥልጣኔም ለመዛወር ሲያስብ ጥቂት በጥቂት እያለ በየጊዜያቱ እየተሻሻለ ፤ ወደ ዋናው ሥልጣኔ ደረጃ ላይ ይደርሳል እንጂ ፤ ሕዝብም መንግሥትም ቢሆን የሚጎዳውን ነገር ባንድ ጊዜ ለመተው ፤ ወይም የሚጠቅመውን ነገር በአንድ ጊዜ ለመያዝ ባንድ እርምጃ ተሻግሮ በዋናው ደረጃ ለመድረስ በውሮፓም ባሜሪካም ፤ በሌላውም አገር ቢሆን መቼም ሆኖ መቼም ተደርጎ አያውቅ ።

ስንመለከተው ከላይ ጀምሮ እስከታችኛው ፍጥረት ድረስ ማናቸውም ቢሆን ዕለቱን የደረሰ የለም፤ ለምሳሌም ሰው ዕለቱን ተወልዶ ዕለቱን አያድግም፤ ዛፍም ዕለቱን በቅሎ፤ ዕለቱን ፍሬ አይሰጥም፤ እንደዚሁም መንግሥት ወይም አንድ ሰው ቢሆን ኑሮውን ለማሻሻል በሰበ ጊዜያት እላይ እንደተና

ገርሁት ጥቂት በጥቂት እያለ እየተሻሻለ ሲሔድ ፍጻሜው እንዲያምር የሥልጣኔን ደረጃ ባንድ እርምጃ ለመያዝ የሚያስብ ግን ታላቅ ጉዳት እንዲያገኘው ያለፈው ታሪክ ሁሉ ያስረዳናል፤ ስለዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ የወትሮውን ኑሮ መሠረት አድርጎ ከዲሱ ሥልጣኔ ጋር የተያያዘውን መልክሙን ኑሮ ቢከተል ጉዳት ይሆንበታል ማለት በፍጹም ስሕተት ነው።

በተቀረ እንደ ብላታ ዴሬሳ ሐሳብ የኢትዮጵያ ሕዝብ በኑሮው ለማሻሻል የፈለገ እንደሆነ የሁለት ንብረት ወጭ ይሆንበታል ብሎ በማሰብ፤ በሮጌ ኑሮው ይቆይ የተባለ እንደ ሆነ፣ ኢትዮጵያ ከዓለም ሁሉ ተለይታ ወደኋላ መቅረቷ ነው፤ አሮጌውን ኑሮ ፈጽሞ ትቶ አዲሱን የኑሮ መሻሻል ባንድ ጊዜ እርምጃ ተሻግሮ ይያዝ የተባለ እንደሆነም፤ ይህ የማይቻልና ጉዳት አምጭ ነው፣ በማናቸውም አገር ቢሆን ወጭ ሳይደረግ መልካም አኑዋኑዋርን ለማግኘት የማይቻል ነው።

ይልቁንስ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ለጤና በሚስማማ አሳብ ተመርቶ፤መልካም አኑዋኑዋርን በመሻት፡ጉዳት የሚያመጣበት ነው ብሎ ከመስበክ፣ ብላታ ዴሬሳ የርሻና የመሥሪያ (የእንዱስትሪ) ዲሬክተር በመሆናቸው ምክንያት ለዚሁ ለመልካም አኑዋኑዋር የሚያስፈልገውን ነገር ባገር ውሥጥ እንዲዘጋጅና ያገር ሰው ከውጭ እንዳይገዛ፣ የሚበቃውን እዚሁ ለማግኘት እንዲችል፤ሥራው እንዲስፋፋ ለማድረግ ችላ ማለታቸው፣ጥፋት መሆኑን ማሰብ በተሻላቸው ነበር።

ሁለት የሚያበርር በአንዱም አይደረስ የሚባል ተረት አለ ላሉትም፥ ብላታ ዴሬሳ የርሻ ሚኒስቴርን ሥራ መሥሪያቸውን ትተው፥ ለሦስቱ ሚኒስቴር ክፍል ሥራ መክር ልሁን ማለት፥ እንግዲህ እሳቸው እንዳሉት፥ ሁለት የሚያበርር አንድ መያዝ ካቃተው ፥ ይልቁንም አራት የሚያበርርማ ከቶውንም የመያዝ ተስፋ የለውምና ተረቱ የተፈጸመው በሳቸው ነው።

ያዲስ አበባን ጉምሩክ እስታትስቲክ በየመቱ የሚወጣውን መመልከት ነው። በዕቃ መወደድና በቡን በቆዳ መርከስ ምክንያት፥ በዚህ በሁለት ዓመት ንግዳችን ፲፫ሚሊዮን ፻፵፬ሺ ፮፻፺፫ ብር ጉደለብን ይኸውም ብር ከአገራችን ሕዝብ እጅ ወጥቶ በውጭ ሰዎች እጅ መግባቱ ነው፥ ይህም አኳኋን ፪ት ፫ት ዓመት የደገመን እንደሆነ የብር ዘር ከገር መጥፋቱን ብንረዳው ይሻላል ላሉት፥ መቸም ስለ ብር መርከስ ነገር ከዚህ በላይ የጻፍሁት የሚበቃ ይመስለኛል ፲፫ ሚሊዮን ፻፵፬ሺ ፮፻፺፫ ብር በ፪ ዓመት ውሥጥ ጉደለብን ላሉት ግን፥ ይህን ግምት ያደረጉት ባዲስ አበባ ጉምሩክ እስታትስቲክ ብቻ ነው እንጂ በሐረር፥ በድሬ ደዋ፤በጅጅጋ፤በአስመራ፥ በመተማ፥ በምጽዋ፥ በጋንቤላና ይህን በመሳሰሉ በነዚህ በቄጠርናቸው በሮች ከኢትዮጵያ ብዙ የሚወጣ ዕቃ ስላለ፥ የዚህን ሁሉ ጠቅላላ እስታትስቲክ ሳያገኙና እርግጠኛውን ሒሳብ ሳይዙ በሐሰት ከ፲፫ ሚሊዮን የሚበልጥ ገንዘብ ሔደብን ማለታቸው ያስገርማል፤ስለምን በአንድ በር እምፖርታሲዮን ቢበዛ በነዚህ በተቈጠሩት በሮች ያለው ኤክስፖርታሲዮን፥ ሲመዛዘን ያጉድለዋልና፥ ይልቁንም ይኸንን ከ፲፫ ሚሊዮንየሚበልጥ ብር ወጥቷል ላሉት ሐሰት መሁኑን ማስረጃ፥ ከዚህ በላይ እንደተናገርሁት እሳቸው በሚሉት ሁለት ዓመት ውሥጥ ከኢትዮጵያ የወጣው ብር በድምሩ ፩ ሚሊዮን ፯፻፲፩ሺ ፪፻ ብር ነውና ነገሩን አስፋፍቶ መደጋገም አያስፈልገንም። እንግዲህ ከ፲፫ ሚሊዮን የሚበልጥ ብር ወጣ ያሉት በየት በኩል ነው? እንደዚህ እንደ ብላታ ዴሬሳ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት ባዲስ አበባ ጉምሩክ እስታትስቲክ ብቻ የሚገመትና ግምቱም እውነት ሁኖ ቢሆን እስከሁን ድረስ በጭራሽ ከገራችን ብር ይታጣ ነበር።

ብላታ ዴሬሳ የኢትዮጵያን ኤክስፖርታሲዮንና እምፖርታሲዮን ለማመዛዘን የነቁት ከ፪ ዓመት ወዲህ ስለሆነ፥ እንግዳ ነገር መስሏቸው ቸኩለው ጽፈዋል እንጂ ኤክስፖርታሲዮንና እምፖርታሲዮንን የምናመዛዝነው ባዲስ አበባ ጉምሩክ እስታትስቲክ ብቻ ቢሆንስ፥ ከ፲፱፻፲፩ ዓመት ጀምሮ እስከ ፲፱፻፳፩ ዓመት መጨረሻ ያለው ኤክስፖርታሲዮንና እምፖርታሲዮን፤ ከዚህ እሳቸው ከሚሉት ከ፪ ዓመት ይልቅ የባሰ ነበር፤ ነገር ግን ከዚህ በላይ እንዳስረዳሁት፤ በኢትዮጵያ ጠረፍ ዙሪያ፣ ወደ ውጭ አገር የንግድ ዕቃ የሚወጣባቸው ብዙዎች በር ስላሉ፤ በጅቡቲ በኩል በዝቶ የሚታየውን እምፖርታሲዮን እነዚህ ተመዛዝነው ያጉድሉታል።

ይልቅስ እንደሚመስለኝ ብላታ ዴሬሳ ወደ ውጭ አገር ወጣብን የሚሉት ብር ፥ እዚህ አገር ያሉት ፈረንጆች ለኢትዮጵያ ባላገር ዕቃ ሲሸጡ ፥ ስለ ዕቃቸው ዋጋ የተቀበሉትን ብር ይሆናል ይህማ ከሆነ እነዚህ ፈረንጆች ለባላገሩ ዕቃ ሲሸጡ የተቀበሉትን ብር ፥ ቆዳና ቡና ከባላገሩ ሲገዙ ፥ መልሰው ለባላገሩ ይሰጡት የለምን ? ወይስ ብላታ ዴሬሳ የሚሉት ፥ ፈረንጆች ለሕዝቡ ዕቃ ሲሸጡ ዕቃውን ብቻ ይስጡና ብሩን አይቀበሉ ማለታቸው ነውን? ከቶ ምን ይሆን ? ።

ማስረጃ

ብላታ ዴሬሳ ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ፥ በዓለም ላይ ሁሉ የገንዘብ ችግር በዝቷልና እንዲሁም በኢትዮጵያ ሳይሆን አይቀርም ብለው ፤ የገንዘብንና የንግድን ፤ ችግር እጅግ አለመጠን አስፋፍተው፤ ሐሰቱን እውነት አስመስለው ስለጻፉ ለብርሃንና ሰላም ጋዜጣ አንባቢዎችና ሰሚዎች ለመግለጽ የተገባ ይመስለኛል ።

ብልሆችና አዋቂዎች እንደሚመዝኑት በውጭ አገርስ እንዳለው ገንዘብ ችግር አኳኋን ዛሬ ለኛ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ አጋጣሚ ሁኖልን ያሁኑ ኑሮአችን ከነሱ የተሻለና የታደልን ሆነናል፤ ማለት ዛሬ በአውሮፓና በአሜሪካን በጣም ሥልጣኔ በዝቶ ብዙ ፋብሪክ በየዓይነቱ በመሠራቱ፤ የሕዝቡን ሥራ መኪና ነጠቀው በዚሁም ምክንያት ብዙዎች ሰዎች ሥራ ፈት ሆነው ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ ለማግኘት ሥራ እያጡ ወደ ታላቅ ጉዳት ደርሰዋል፤እነዚህም ያለ ሥራ የተቀመጡ ሾመር የሚባሉት ሰዎች ቍጥራቸው ባጭሩ ከ፳ ሚሊዮን ይበልጣል ይባላል፤ደግሞ ባለብዙ ገንዘብ ካፒታሊስቶች የሆኑ ታላላቆች ሰዎች በየፋብሪካቸው የሠሩት ዕቃ አልሸጥ ስላላቸው በታላቅ ከግሬ ላይ የወደቁ ብዙዎች ናቸው በውጭ አገር ባሁኑ ጊዜያት የተነሣው የገንዘብ ችግር እጅግ አስጨንቋል።

በኛማ በኢትዮጵያ እንደነሱ ያለ ችግር ስንኳንስ ብዙ ቀን አንዲት ቀን ቢደርስብን፤ ታላቅ አደጋ ይሆንብን ነበር፤ እግዚአብሔር ይመስገን በኛ አገር ከቀድሞው ይልቅ ዛሬ ንግድም እርሻም ደኅና ዋጋ ስላገኘ በርሻና በንግድ በሌላም ሥራ ላይ ያለ ሕዝባችን ሁሉ እጅግ ተጠቅሟል፤ ለዚሁም ጥቂቱ ማስረጃ አቀርባለሁ፤ ቀድሞ አራሹ ገበሬ የእህሉን ዋጋ ያውም እህሉ ውድ ሲሆን፥ በ፩ ዳውላ ጤፍ ፬ ብር፥ በ፲ ዳውላ ጤፍ ፵፪ ብር ያገኝ ነበር፤ ዛሬ ግን በ፩ ዳውላ ጤፍ ፳ ብር፥ በ፲ ዳውላ ጤፍ ፪፻ ብር ድረስ ያገኛል፤ እንደዚሁ ማናቸውንም ዓይነት እህል ሁሉ የቀድሞውንና የዛሬውን ዋጋ ቢያመዛዝኑት የዛሬው ዋጋ ከፍ ብሎ አራሹ ገበሬ የድካሙን ዋጋ አግኝቶ ተጠቅሞ ይታያል፤ ደግሞ ባዝራና በቅሎ፤ በሬና ላም፤ በግና ፍየል፤ ከቀድሞው ዛሬ ደኅና ዋጋ አግኝቶአልና ከብት አርቢዎች ተጠቅመዋል፤ ከዚህም በቀር ማር፤ ቅቤ፤ ቡና፤ ቆዳ፤ ሰም፤ ዝባድ፤ ሸማ፤ በርኖስ፤ ሌላውም የንግድ ዕቃ ሁሉ ከቀድሞው ይልቅ ዛሬ አራት አምስት እጥፍ ዋጋ አግኝተዋልና በነዚህ ዕቃዎች የሚነግዱ ሰዎች እጅግ ተጠቅመዋል፤ ንግድ ጠፍቶ ተበላሸ የሚያሰኘው ገበሬ ላረሰው እህል፤ ከብት አርቢ ላረባው ከብት ነጋዴ ለሚነው ማርና ቅቤ፤ ቡናና ሰም ለሌላውም የንግድ ዕቃው ሁሉ ዋጋ ባያገኝና ባይሸጥለት ነበር፤ የሰው ተፈጥሮ ምን ጊዜም ቢሆን በዓለም ላይ በቀን ሚሊዮን ገንዘብ ቢያገኝ ከቶ ማግኘትንና ሀብትን ይበቃኛል የሚል ፍጡር የለም እንጂ፤ እንግዲያውስ እናታችንን ኢትዮጵያን ሁል ጊዜ ለሚጠብቃት ቸሩ አምላካችን ክብር ምስጋና ይግባውና ዛሬ ከሌላው አገር ይልቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለ ችግር ይኖራል፤ ገበሬና ነጋዴ ከቀድሞው ዛሬ ለህሉና ለንግድ ዕቃው በእርግጥ ትርፍ ማግኘቱን ለማወቅና ለመረዳት የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ ከ፲ ወይም ከ፲፭ ዓመት በፊት እህልና ከብት፤ ቡናና ቆዳ፤ ማርና ቅቤ፤ ሌላም ይህን የመሰሉ የንግድ ዕቃዎች የሚሸጡበትን፤ ዋጋ ዛሬ ብላታ ዴሬሳ ንግድ ጠኝ፤ ገንዘብ ታጣ፤ ከሚሉበት ጊዜ ገበያ ዋጋ ጋር ብታመዛዝኑት ፍሬውን እውቃችሁ፤ ጥቅማችሁ በቶሎ ይገባችኋል ።

ከዚህም በቀር እንደሰማነው ፤ በመላ ኢትዮጵያ ጉምሩኮች ገቢ ሳይጨመር ባዲስ አበባ ጉምሩክ ብቻ በዚህ ባየነው ዓመት የጥር ወር ገቢ ፬፻ሺ ብር ድረስ ገባ ይላሉ ። ይኸውም ባለፉት ዓመታት ውሥጥ ባንድ ወር ይኸንን ያህል ፩ጊዜም ገብቶም አያውቅ ይባላልና የኢትዮጵያ ንግድ ሁሉ ከቀድሞው ይልቅ ዛሬ እየተሻለ ለመሔዱ ይህም ዋና ማስረጃ ነው ። ገበሬና ነጋዴስ በእህሉና በከብቱ በንግድ ዕቃውም ከቀድሞው ይልቅ ዛሬ በእርግጥ ደኅና ዋጋ አግኝቷል ። እንደነሱ በንግድና በእርሻ ሥራ ላይ ያልሆኑ በሌላ በየዓይነቱ ሥራ ላይ ያሉ የመንግሥት ሰዎች እህልና ከብት ዕቃም ሲገዙ ይወደድባቸዋልና ዕቃ ሸጮች ይጠቀማሉ ፤ ዕቃ ገዥዎች ግን ዕቃ በመወደዱ ይጐዳሉ እንዳይባልም ከ፲ ወይም ከ፲፭ዓመት በፊት እህልና ከብት ዕቃም በርካሽ በሚገዛበት ጊዜያት የመንግሥት ሰዎች የሆኑ ይቀበሉት የነበረው ቀለብና ደመወዝ እጅግ ጥቂት መሆኑን ያን ጊዜ ለነበረው ያንድ ሰው የወር ቀለብ ልክ ይልቁንም የተራው ሰው ቀለብ እንዴት እንደነበረና ያለመጠንም አነስተኛ መሆኑን ማንም አይስተውም አሁን ግን ዛሬ እህልና ከብት ዕቃም ደህና ከፍ ያለ ዋጋ በሚያገኙበት ጊዜያት የመንግሥትም ሰዎች ከፍ ያለ ቀለብና ደመወዝ ስለሚያገኙ ዕቃ ሻጭዎችና ዕቃ ገዥዎች ምንም ያህል በጥቅም አይበላለጡምና በዕቃ ገዥዎችም ላይ ቢሆን ምንም ጉዳት አይደርስባቸውም ።

ደግሞ እንደነጋዴና እንደ አራሹ ገበሬ ለመጠቀም ብናስብና የነርሱንም ፍለጋ ብንከተል ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑርልን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለአፄ ኃይለ ሥላሴ ረጅም ዕድሜና ጤና ይስጥልን እንጂ ለኢትዮጵያ ዋና ሥራዋ እርሻና ከብት ማርባት ንግድም ስለሆነ በደስታ ለመኖር እንችላለን ።

ኃላፊውን የማይመረምር ታሪክ የማይመለከት የፊቱን ብቻ የሚያይ ሕዝብ ጥቅሙ እየተሻሻለ ወይም እያጐደለ መሔዱን ገምቶ ለመረዳት አይቻልምና ያለፈውን ንግድ ጉዳት አውቃችሁ ያሁኑን ትርፋችሁን ተረድታችሁ ይህንን ሰፊ ችሮታ ላደረገልን አምላካችን ወሰን የሌለውን ምስጋና እናቅርብለት ።

የብርሃንና ሰላም ወዳጅ ።

ማስረጃ

ከአሁን ቀድሞ በኢትዮጵያ አገር በወርቅና በጽላቲን ይህነንም በመሰለ ሚኔሬ በሚባል ነገር የሚነግድ ነጋዴ ቀረጥ ወይም ግብር ለመንግሥት ሳይከፍል በስውር ሲነግድ ይኖር ነበር የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግን ለሰው ሕይወት ግድ የሚያስፈልግ እህልና ጉመን ሲሸጥ ቀረጥና ግብር እየተከፈለበት ማጌጫና ለንግድ እንጂ ለሰው ሕይወት ግዴታ የማይሆነው ወርቅና ጽላቲን የከበረ ማዕድን ሁሉ ሲሸጥ ግብርና ቀረጥ የማይከፈልበትን ምክንያት ስላላገኘ ለወደፊቱ በወርቅና በጽላቲን ሚኔሬ የሚነግድ ሰው ሁሉ ቀረጡን ወይም ግብሩን እየከፈለ በግልጥ እንዲነግድና ወደውጭም አገር እንዲያወጣ በውል ያልተፈቀደለት ሰው ግን ማናቸውንም ማዕድን የተባለ ነገር ሁሉ ከመሬት እንዳያወጣና በማናቸውም ማዕድን የሚነግድ ሰው ግብሩንና ቀረጡን ሳይከፍል ወደውጭ አገር እንዳያወጣ በኅዳር ፳፯ቀን ፲፱፻፳፪ ና ጥቅምት ፳፯ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ምሕረት በታወጁት በሁለት አዋጆች ክልክሉ ነበርና በ፲፱፻፳፫ ዓ ም ይህነኑ አዋጅ ተላልፈው ሐያ የሚሆኑ ነጋዴዎች የወለጋ ሰዎች አባ ጉጂ ከሚባል አዲስ አበባ ከሚኖር ነጋዴ ጋራ ሆነው ወርቅና ጽላቲን በሥውር ሲሸጡ ተገኝተው ማዕድናቸውን እየተወረሱ የደንቡን መቀጫ ከፍለው ብዙ ብዙ ወራት ታስረው ተለቀቁ ። እንደዚሁም ሙሴ ዛፓ የሚባል የኢጣልያን ዜጋ ወለጋ የሚኖር ልጁ ወርቅና ጽላቲን ሲሸጥ ተገኝቶ ወርቁንና ጽላቲኑን ተወርሶ እርሱ ለኢጣልያ ሌጋስዮን ተሰጥቶ ታስሮ ቆይቶ ተለቀቀ ። ከዚያም ወዲህ አሁን በአለፈው ሰኔ የደጃች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር አሽከር ቀኛዝማች አባይ ካባ የሚባል ሰባ ወቄት ተኩል ወርቅ ሲሸጥ ተገኝቶ በዘበኛ ተይዞ ወርቁን ተወርሶ አምስት መቶ ብር መቀጫ ከፍሎ ተለቀቀ ። የማዕድንም ሥራ ቤት አዋጅ አፍራሹን

ለአገኙት ሰላዮችና ለያዙት ዘበኞች ፫፻ውን ብር ስለ ሽልማት አከፋላቸው። ለወደፊቱም ቢሆን የማዕድን ሥራ ቤት ሰላዮችንና መርማሪዎቹን በየቦታው እያደረገ አዋጅ አፍራሹንና በር ሰባሪውን እያስያዘ እንደ አዋጁ ቃል ለማድረግ መጣሩን አይተውም። ከዚህም ሌላ ደግሞ የንግድ ዕቃ ለሆነ ነገር ሁሉ አዋጅ አፍራሽና በር ሰባሪ በጥንቃቄ ለመጠበቅና ለመያዝ የሚገባቸው መጀመርያ የጉምሩክ ሠራተኞች ሁለተኛ የፖስታ ሠራተኞች ስለሆኑ ለነዚህ ለሁለት ሥራ ቤቶች ከአሁን በፊት እንደለመናቸው በየበኩላቸው የፖስታ ሠራተኞች በኮሊ ፖስቶ የሚሄደውን ዕቃ የጉምሩክም ሠራተኞች በሽቀጥ ኮሊ (ጥቅል)በጥንቃቄ ያስጠብቁልናል የማለት ብርቱ ተስፋ አለን ።

መንግሥትም ይህነን የደንብ አዋጅና አዋጅ አፍራሽ በብርቱ ቅጣት እንዲቀጣ ማድረጉ ማዕድን የሚባል ነገር ሁሉ ያለ እርሱ ፈቃድ ከመሬት እንዳይወጣና ግብር ወይም ቀረጥ ሳይከፈልበት እንዳይነገድበት ለመከልከል ነው እንጂ የደንቡን እየፈጸመ በወርቅ ወይም በሌላው ዓይነት ማዕድን የሚነግድን ሰው ንግዱን ለማሰናከል ፈቃድ የለውም ።

ይህነንም በአዋጅ የተነገረውን ደንብ እየፈጸመ በማናቸውም ዓይነት ማዕድን ለመነገድ የፈቀደ ሰው ሁሉ ደንቡን ከማዕድን ሥራ ቤት እየጠየቀ ፈቃድ እየተቀበለ በፈቀደው ማዕድን እንደልቡ መነገድ ይችለዋል ።

የባሮች ነፃነት ሥራ እየተሻሻለና እየሰፋ ስለ መሔዱ ።

ባገራችን በኢትዮጵያ የባርነት ነገር አለ ማለት ስሙ ብቻ ነው እንጂ በቀድሞ ዘመን በሌሎች አገሮች እንደ ነበረው በጽኑ አገዛዝ የሚገዛ ባርያ እንደሌለ የታወቀ ነው ። ቢሆንም ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የባርነት ነገር ጥቂት በጥቂት እየተሻሻለ እንዲሔድና ሕዝቡ የባርነት ነገር ጥቅም የሌለው መሆኑን እንዲያውቅ ለማድረግ ስለ አሰቡና ስለ ፈቀዱ ከዚህ ቀድሞ በ፲፱፻፲፮ ዓ ም አንድ ደንብ አቁመው ነበርና ደግሞ ባለፈው ዓመት ሌላ ተጨማሪ የተባለ ደንብ አውጥተው ስለ አወጁ የባርነት ነገር በጣም እየተሻሻለ የሚሔድ ሁኑዋል።

አሁን ደግሞ በዚሁ በያዝነው በሐምሌ ወር ውሥጥ በባርያ ነፃነት ሥራ የሚሆን አዲስ ደንብ አውጥተው በያውራጃው ያለውን የባርያ ነፃነት ዳኝነት ቤት ለሚቆጣጠረውና ለሚመረምረው አዲስ አበባ ላይ ለቆመው ለዋናው የባርያ ነፃ ጽሕፈት ቤት በተለይ አንድ ዋና የበላይ ሹም። አንድ ዋና ዳኛ። አንድ ዋና ጸሐፊ ሹመዋል ።

የነዚሁም ሹሞች ስማቸው የዛሬ ሳምንት በሚወጣው ብርሃንና ሰላም በአፈሴል ሳይታተም አይቀርም ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት
ጃንሆይ እነሆ መወድስ ቅኔ

ኃይለ ሥላሴ ዳዊት ክቡደ መዝሙራት ሰይፈ መንግሥትከ ምላሕ ወዕግቶሙ ለፀር።
ንጉሠ ኢሎፍሊ ወጌት ከመ ይትኃፈር።
አኮኑ ዳዊት ኃይለ ሥላሴ በዓለ ሀብታት ሰብዓቱ እህጉር ።
ወድንግለ ዕበይ መንግሥትከ ትትሌዐል ወትረ እምነገሥተ ዓለም አድባር ።
ዮምሂ እመ ተሐውከ ማእበለ ፀርከ ባሕር ።
ሐመረ እድኅኖ ኃይለ ሥላሴ፤ ለዓለመ ዓለም ኢትሰበር።
እስመ አዶንያስ ወልድ ዘአምሐግከ ነኪር ።
ከመ ያፍ ባሕታዊ ውስተ ናሕሰ ሞት ይነብር ።

አለቃ ተስፋ ሁነኝ ዘብሔረ አኩስም ።

ስለ አዛጋር ደገፌ ዕረፍት

አዛጋር ደገፌ በአፄ ምኒልክ ጊዜ ጀምረው ከማዕርጋቸው ላይ ማዕርግ እየተጨመረላቸው በደኅና ሲኖሩ መቸም የዚህ ዓለም መጨረሻው ይህ ነውና በድንገተኛ ሕማም ታመው በሐምሌ ፳ ቀን ዐርፈው በአቡነ ተክለሃይማኖት ቤት ክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበሩ ።

ጨካኙ ሞት

በኑ ለከንቱ ፈጠርኮ ለኵሉ ለእጓለ እመሕያው

ብሉየ መዋዕልነት ያለው በየለቱም ሐዲስ የሚሆነው ጨካኙ ሞት ከጭካኔው ብዛት የተነሣ እጅግ የተዋበውን ያቶ ትስብእት ወልደ አግዴን ልጅ ነጋሹ የሚባለውን በተወለዶ በ፪ዓመት ከዘጠኝ ወር ከ፭ ቀን ፯ ቀን ያህል እንደታመመ በሐምሌ ፪ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም ከምሽቱ እኩል ሰዓት ሲሆን ሳይታሰብ በድንገት መጥቶ ከአባቱና ከናቱ መከከል ስለነጠቀው በአባቱና በናቱ በቤተ ዘመዶቹም መከከል የተደረገውን ጽኑ ኃዘን ያየ ሰው እስከመቸው ድረስ ልጅ ስጠኝ ብሎ ለመመኘት አይችልም ነበረ ። ይልቁንም አባቱና እናቱ የኃዘናቸው ጽናት በመላው ሰውነታቸው ስለተሰራጨ አንድ ጊዜ እንኳ ሳይታገሡ በልዩ ልዩ ምክንያት እየመሰሉ የራሳቸውን ሞት ብቻ በቁርጥ እየተመኙ በፅኑ ያለቅሱ ነበረ። ኃዘናቸውንም ተካፋይ የሆኑት ወዳጅ ዘመዶቻቸውና በፍቅር ሰንሰለት የተሣሠሩት ባልንጀሮቻቸው የኃዘናቸውንም ፅናት እያዩ አቶ ትስብእት ወልድንና ወይዘሮ ሙሉነሽን አፅናንተው ከኃዘናቸው ለማስታገሥ ሳይቻላቸው ቀርቶ አንዳንድ ጊዜ እንደነሱ ተባብረው ሲያለቅሱ እናትና አባቱን ከማያውቁ ወገኖች ለጊዜው ለመለየት የቻለ አልነበረም ። ነጋሹ ተብሎ የተሰየመበትም ምክንያቱ በ፲፱፻፳፩ ዓም በመስከረም ፳፯ ቀን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴና አልጋ ወራሽ ንጉሥ ተፈሪ ተብለው መጀመሪያ የዘውድ ክብር ተቀብለው በነገሡበት ቀን ስለተወለደ ጊዜ ለማጋጠሙ መታሰቢያ ይሆናል በማለት ነጋሹ ተብሎ ተሰየመ የነጋሹን አወጣጥና ብልህነት የሚያውቅ ሰው ሁሉ እንደ ትልቅ ሰው ያህል አድርጎ ይገምተዋል እንጂ ከሰውነቱ ማነስ በቀር በንግግሩ የልጅ አመል አልነበረበትም ።

እንደዚህ ያለው ልጅ እንኳን ለእናት አባቱ ለአየው ሁሉ ጸጸት ነው አባቱንና እናቱን እግዚአብሔር ያጥናቸው

የኃዘናቸው ተካፋይ ደጉ ይመር ።

WHITE HORSE WHISKY

ባለንጭ ፈረስ ዊስኪ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በከዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ ያሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ ፥ የደረት የጉበት ፥ የኩላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቁቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዳሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት።ከዚሁም እንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዶች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፉና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዘዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙባታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ካገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ.

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ የጃሜሊና ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪል ነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለሰንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፴፫
8me ANNE. № 33

ሐሙስ ነሐሴ ፭ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 11 AOUT 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጠውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የተማሪዎች ዕድል ።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተማሪ ቤት ተብሎ ማለፊያ የትምህርት ቤት ቆሟል ይኸውም የትምህርት ቤት በትምህርታቸው የበለጡ ተማሪዎች ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ወጥተው የገቡ ታላላቆች ተማሪዎች አሉበት፡የሚማሩትም የመሐድስነት ትምህርት ነው ይኸውም የትምህርት ቤት ስለ ክረምቱ ዕረፍት ለማድረግ በሐምሌ ፳፩ ቀን የሚዘጋ ስለሆነ በትምህርታቸው ተፈትነው የበለጡትን ተማሪዎች ሽልማት ለማየት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ ግርማዊት እቴጌ መነን ። ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንትና ሚኒስትሮች ልዑላት ወይዛዝርና የውጪ አገር የክቡር ዲፕሎማቲክ ሰዎችም ነበሩ።በከተማ ኑዋሪዎች ከኢትዮጵያና ከሮፓም ብዙ ሰዎች ነበሩ።የቀጠሮውም ሰዓት በ፰ሰዓት ተኩል ነበርና በዚሁ በተቀጠረው ሰዓት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊትእቴጌ የቀሩትም በላይ የተጻፉት ሁሉ በመጡ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ተዘመረ ። ከዚህ በኋላ የትምህርትና የጥበብ ሚኒስትር መልአከ ሕይወት ወልደሐና የሚከተለውን ዲስኩር አነበበ ።

ጃንሆይ

በንጉሠ ነገሥቱ ከተማ ከቆሙት ተማሪቤቶች ዝቅተኞቹን ዘለን፤የከፍተኞቹን ፭ኛ የሆነውን በጃንሆይ አሳቢነት በ፲፱፻፳፬ ዓም የቆመውን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተብሎ በገናናው ስምዎ የተሰየመውን ተማሪቤት ለመጐብኘት ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ ፥ ከልዑላን መሳፍንትና ከክቡራን መኳንንቶች ጋር ስለመጡልን ከር ዲፕሎማቲኮችም በዚህ መካከል ስለተገኙልን የደስታ ፋና በልባችን በርቷልና ምስጋናችንን እናቀርባለን እንደዚሁም የአንድነት ደስታችን መሆኑን ተረድተው ጥሪያችንን አክብረው ለመጡልን ሰዎች ሁሉ ጥልቅ ምስጋናችንን እናስቀድምላቸዋለን ።

ጃንሆይ

ከብዙ በጥቂቱ ከሙሉ በከፍሉ አድርገን ዘሬቍጥር የወጠነው ተማሪቤት ስም ።

፩ኛ የዳግማዊ ምኒልክ። ፪ኛ የተፈሪ መኰንን
፫ኛ የመነን አስፋው። ፬ኛ የጊዮርጊስ። ፭ኛ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነው ።

ስለ ፭ኛው ተማሪቤት አቋቋም ይህ ፭ኛ የሆነው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተማሪቤት ከቆመ ፩ዓመት ሆነው ይኸውም ተማሪቤት ምንም እንኳን ከዚህ በላይ ከቈጠርናቸው ተማሪቤቶች አምሳያ የሚሆን ሕንፃ ለጊዜው ባይሠራለት በትምህርት ከፍ ከፍ ላሉት በእውቀት ለበሰሉት ተማሪዎች የቆመ የተለየ ትልቅ የመሐንድስነትና የሥነ ፍጥረት ትምህርት ቤትነው የተማሪዎቹም ቍጥር በዚሁ በአንድ ዓመት ውሥጥ ፻፴ ያህል ሁነዋል። ይኸውም የዲሬክተሩ ሙሴ መልሐሚ ትጋት እንደሆነ ይሰማናል።

የትምህርቱ አኳኋን ።

ይህ ተማሪቤት ከሁለት ላይ ተከፍሏል ።

አንደኛ የአስተማሪነት ።
ሁለተኛ የመሐንድስነት ትምህርት ነው ።

ስለ ትምህርትና ስለ ጥበብ እርምጃ ።

፩ኛ ፥ የአስተማሪነት ትምህርት ከሚማሩ ልጆች ውሥጥ ወደ ፲የሚሆኑ ለመምህርነት ተመርጠው በትምህርት በጣም ስለተሻሻሉ ለሚመጣው ዓመት ከሚያስፈልጓ ደረጃ እንዲደርሱና ከመምህራን ቍጥር ተርታ እንዲገቡ እንታመናለን ።

፪ኛ ፥ የመሐንድስነት ትምህርት ከሚማሩት ልጆች ውሥጥ ፯ቱ ለመሐንድስነት ሥራ ተመርጠው መልካም አጀማመር አሳይተዋልና ለመሐንድስነት ሥራ ረዳት ለመሆን የሚችሉ ለወደፊቱም አሉን ብለን የምንቆጥራቸውና የምንታመንባቸው ናቸው።የነዚሁም ተማሪዎች ምርጫና ብልጫ በስጦታ መሆኑን ያሳስበናልና ለስጦታቸው ማስፈጸሚያና ማተጋጊያ በያይነቱ የጥበብ ተማሪቤት ማቆም የሚያስፈልጓ መሆኑን ለግርማዊነትዎ ሳላስታውስ ይህንን ምክንያት አልዘለውም ።

ጃንሆይ ።

በዘመኑ መንግሥትዎ የትምህርት ስብከት በአገራችን እየገነነ የሔደበት ምክንያት በከተማውና በያውራጃው በብዙ

ወጭ ገንዘብ በየመቱ ተማሪ ቤት እንዲቆም ስለፈቀዱ ነው እስከሁን ድረስ የቆመው ተማሪ ቤት ለ፩ሚሊዮን ፪፹ሺህ ኪሎሜትር ካሬ ስፋትና ፳፫ ሚሊዮን ሕዝብ ላላት ለኢትዮጵያ የሚዳረስ አይደለምና ለትምህርት ያጨነውና ትጋት ያየንበት አውራጃ ሁሉ ተማሪ ቤት እንዲቆምበት ለትምህርትና ለጥበብ ሚኒስቴር በተወሰነው ቀጠሮ ቀን የሥራ ማመልከቻ ለግርማዊነትዎ እያቀረብን በደገኛው ፈቃድ በ፲፱፻፳፫ ዓ ም የተማሪቤቱን ቁጥር እንድና በረከተውና እንድናስፋፋው የተረጋገጠ ተስፋ አለን።

ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንት ሆይ ።

አንድ ሰው ብዙ ገንዘብ ቢኖረው በገንዘቡም ብዙ ነገር ለመሥራት ቢችል ረዳት ከሌለው ጥቅሙ የጐደለ ይሆናል ። እንደዚህ ሁሉ መንግሥት ተማሪቤት ለማቋቋም ቢጣጣር በውስጡ ያሉት ባለሥልጣኖች መሳፍንቶችና መኳንንቶች በየበኩላቸው ካልረዱት አገር ለመጥቀምና ለማሠልጠን አይቻልምና ። እላንት ልዑላን መሳፍንትና ክቡራን መኳንንት ወይዛዝሮችም ። የጋራ ጥቅማችን እንዳይጐድልብን እንድትረዱልንና የተወደደች አገራችን ኢትዮጵያን ከሠለጠኑት መንግሥታት ጋር እንድናስተካክላት በትምህርትና በጥበብ ሚኒስቴር ስም ሁኜ እለምናችኋለሁ ። ይኸውም ልመና ያገር ፍቅር ላደረበት ሰው ሁሉ ግዴታ መሆኑን አስታዋይ እንዲገነዘብልን ጥርጥር የለውም ።

የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ

ገበሬ በፀሐይና በዝናም ወጥቶ ወርዶ አርሶ አለስልሶ በተሰፋ ትንሽ ዘር ዘርቶ ብድሩን አብልጦ በመውሰዱ ወሮታው እንዲመለስ እንደዚሁም ተማሪቤት ወሮታዋን በአጥፍ ትመልሳለችና ሁላችንም በአንድነት እንድንተጋገዝ እናተጋጋችኋለን

ጃንሆይ

ለግርማዊነትዎ ክብር ይግባውና የትምህርት ጣዕም ታውቆልናል ስለሆነም ከሁንም በፊት ሰባት ዓመት የሞላው የኢትዮጵያ ልጅ አተማሪቤት እንዲገባ በዋጅ ያስነገሩት ግዴታ ለሚመጣው ዓመት እንዲታደስልን የግርማዊነትዎን ፈቃድ እለምናለሁ

ስለሹማምንቶችና ስለ አስተማሪዎች ትጋት

ጃንሆይ ።

በትምህርትና በጥበብ ሚኒስቴር ውሥጥ ያሉት ሹማምንቶችና አስተማሪዎች በየክፍሉ ያለውን ተማሪቤት እያተጉ በጣም ረድተውልናል ።

ይልቁንም የዲሬክተሩ እንደራሴ ያቶ ኪዳነ ማርያም አበራ ትጋትና አገልግሎት ደስ የሚያሰኝ መሆኑን ለግርማዊነትዎ አረጋግጣለሁ

ደግሞ አቶ በላይ ገብረሕይወት በሥራውና በጠባዩ አጅ ማመር ደስ አሰኝቶናል ። እንደዚሁ የአቶ ዮፍታሔ ንጉሤንና የአቶ ዳዊት ዕቁበ እግዚእን እርዳታቸውን ለግርማዊነትዎ አስታውቃለሁ

ጃንሆይ ።

እዚህ የተሰበሰባችሁ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች የመንግሥት ሹማምንቶችና የጦር አለቆች ወታደሮችም ሁሉ የማይማርና የማይሠራ ሰው ክንፍ ሳለው እንደማይበር አሞራ ወይም ክንፍ አግኝቶ እንደማይዋኝ ዓሣ ነውና እግዚአብሔር ሳያደላ የፈጠረውን አእምሮ ሥራ ማስፈታት ለድንቁርና መግዛት እንዳይሆንብን የትምህርት ፍቅርና የሥራ መውደድ በሁላችን ላይ ይደር።

የንጉሡ ነገሥቱና የእቴጌይቱ ዕድሜ ይርዘምልን ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ቀጥለውም የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ሙሴ መልሐሜ የአነበቡትን የዲስኩር ትርጓሜ ስፍራ ጠበን ትተነዋልና በሚከተለው እናትመዋለን ተያትሩም ማለፊያ ነበረ።ይልቁንም በሰሎሞንና በንግሥተ ሳባ ምሳሌ ሁነው በፈረንሳዊ ቋንቋ የተናገሩት ተማሪዎች ተቀማጮችን ሁሉ ደስ አሰኙ ። እነዚህም ልጆች ከጃንሆይ ሽልማት ተቀበሉ ፤ ሥራ ሚኒስትር ፊታውራሪ ታፈሰ የመሐንድሶች ሙሣሪ ልጅ ተድላ ኃይሌ ብዙ መጻሕፍት ሸለሟቸው ።

የትያትሩንም ማስታወቂያ ፩ተማሪ በአማሪኛ ከአነበበ በኋላ ልጅ መንበረ ያየህ ይራድ በፈረንሳዊ ቋንቋ ይህኑ ማስታወቂያ አስተካክሎ በማንበቡ ሰውን ሁሉ እጅግ አስደነቀው ከጃንሆይም የወርቅ ሰዓትና የወርቅ ሜዳይ ተሸለመ ።

የወንድማማቾች ሠርግ ።

የክቡር ደጃዝማች ገብረማርያም ልጆች ልጅ ተፈራ ገብረማርያምና ልጅ ለገሰ ገብረ ማርያም በሐምሌ ፳፬ቀን በተክሊል ስለአገቡ የሥርዓት ወዳጆችን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኝተዋል የአገቡዋቸውም ወይዛዝር ስም ቀጥሎ የተጻፈው ነው ታላቁ ልጅ ተፈራ ገብረማርያም የፊታውራሪ ሽፈራው ባልቻን ልጅ ወይዘሮ ዕፀገነትን አገባ ። ታናሹ ልጅ ለገሰ ገብረ ማርያም የብላቴን ጌታ ኅሩይን ልጅ ወይዘሮ አምሳለ ኅሩይን አገባ ። በዚሁም ቀን በወዳጆቻቸውና በዘመዶቻቸው ዘንድ ታላቅ ደስታ ተደርጎ ነበረ ታናሹ ልጅ ለገሰ ገብረማርያም ጉለሌ በሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ተክሊሉን ፈጽሞ በሙሽራይቱ ቤት ታላቅ ግብዣ ተደርጎለት ወደቤቱ ተመለሰ ።

ታላቁ ልጅ ተፈራ ገብረ ማርያም በላይኛው ጊቢ አጠገብ ባለው በማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ተክሊሉን ፈጽሞ ልጂቱን እንደ አባትና እንደ እናት ሁነው የሚድሩ ጃንሆይና እቴጌ ስለሆኑ የተደገሰው በላይኛው ጊቢ ነበረና በልጂቱ ወገን የጋብቻውን ውል ፈጻሚ አዛዥ ይርዳው በሥርዓት ተቀብለው በታላቁ የእልፍኝ አዳራሽ ታላቅ ግብዣ አድርገውላቸው በታላቅ ደስታ ዋሉ በዚሁ ቀን ጃንሆይና እቴጌ በታላቁ ግቢ ግብር አድርገው ውለው ነበርና ማታ ወደ ላይኛው ግቢ ወጥተው ለሙሽራይው የጋብቻ ውል ፈጻሚ ለነጋድራስ ኃይሌ ወልደሩፌና ለሚዜዎች ለግራዝማች

ኃይለ ማርያም ወልደ ገብርኤልና ለልጅ ዓለምአየሁ ደርቤ ከሠርገኞችም ለተመረጡት ሰዎች ያማረ ያማረ ሽልማት ሰጧቸው ከዚህ በኋላ ሙሽሮቹ ወደ ቤታቸው ተመልሰው ታላቅ ግብዣ ተደረገ ። ሙሽሮቹ ዕለቱን ሒደው ሳያድሩ በመመለሳቸው አስተዋዮችን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኝቷል ። እውነት ነው ለሙሽሮች የሚጠቅማቸው ማደሯቸውን እቤታቸው ቢአዘጋጁላቸው ነው እንዲ የሠርጉ ጃጃታ ምንም እንዳይጠቅማቸው የታወቀ ነው የተስማማ ጋብቻ ያድርግላቸው እያለ ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ይገልጻል ።

ሹም ሽር

ልጅ ሰይፉ ሚካኤል የጨርጨርን አውራጃ ዲረክተርነት የልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ ሹመት የነበረውን ተሾሙ።

ልጅ አንዳርጋቸው መሳይ የልጅ ተፈራ ገብረ ማርያም ሹመት የነበረውን የጂቡቲን ቆንስልነት ተሾሙ ።

እንኳን ደስአላችሁ ከጌታችሁ ፈቃድ አያውጣችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል ።

ማስረጃ

ሕዋሳት በተፈጥሮ በየወገናቸው አንድ ዓይነት ስለ ሆኑና አንዱ ከንዱ የማይለይ ስለ ሆነ ።

ጉድ እኮ ነው ሰዎች ። በን ሰው ተብሎ ለማኝ መጥላት፥ ምእመን መስሎ የእመአምላክን ስም መዘበቻ ማድረግ ተማሬ ለነበረ ሰው እጅግ ያሳዝናል ። በኃይለ ሥላሴ በዋቂው ንጉሥ ። ትምርቱ ሲፈለግ ፊደሉ ሲነግሥ ። መች ይገባሃል ተማሬ ማርከስ ። አዋቂም አይደለ አላዋቂ ዓብደላ። እርኩሙን ቍራውን እርሙን የሚበላ። የሙብላችን ሥራ ክሱ ሙብል ሌላ በፋሲካ ፍየል በጾሙ ባቄላ ። ተማሬ ያልሆነ ዳባ ያልለበሰ ። ብበቱ ሙት ዓመት የተክበሰበሰ ። አህያ መፈለግ ከህዮች አጠገብ ። ነውር መስሎሻልወይ እንኮየ አትጠገብ ። አህያ እንዳይፈልግ በክሕደት የኰራ ። ማኒስንኳ ተጣላ ከፈጣሪው ጋራ ፍየል አትጠገብ ተይ እሪያ ተይ እሪያ። አሁን ቢደጋገፍ አንጣሪያ ላንጣሪያ ። ሁሉም ዘፍ ባይነው እንደ ጣለው በሾያ ተማሬ ሴት ወዶ እጅግስ ቢሰስት ። እንዴት ቆንጆ ሞልቷ ይገኙትታል እስስት ። ሰው ከስስት ጋራ እንዴት ይታገላል ። በኔስ አገር ታንቆ በጉድፍ ይጣላል ። ቅኔ መቈጣጠር ዜማ ማንጐራጐር ነውር ሆነ ወይ ። ከከብ የማይገባ ድብልብል ድንጋይ ። በዓት መለየትም ነውር ሆነ ወይ ። መቶ ጋለሞታ ሽርሙጣ ፈንጋይ ። ፲፮ አግር ያንተ ሰበተኛ፥ በንድ ትንሽ ጓዳ ይዘህ የምተኛ ‹ደሞም ነቃፊ ሆንህ አንተ እንጉል ጋኛ፥ ለየበረንትቻው ዙሮ ከመስገድ ። ቢያመልኩስ ቢሰግዱስ አይ ቀርብም ወይ ሆድ

ለዚህ መደገፍያ ቅኔ

ከርሥ ኢያዕቆ ለጥበበ አብ ወልደ ባሕርይ። አምጣነ እምከርሥ ወፅአ ምክንያተ ድኂን ክርስቶስ ።

ወለቃየል ምክንያተ ሞት ፀአቱ እምከርሥ ።
ወከመ ኢትበል አፍ በቃለ ረዋዒ ነፋስ ።
ዓበየ ከርሠ ኢየኅሥሥ ።
ኢጸግበት ደመ እስከ አድማስ ።
ውርዝልያ በከርሣ ነዓስ

ፊት ዳባ ኋላ ካባ
ለባሽ ተማሬ

የሲኒማ የቴአትር የዜማና የዱለት ጨዋታ ማሳያ ቤት ደንብና ሕግ ።

፩ኛ ፡ የሲኒማ የቴአትር የዜማና የዱለት ጨዋታ ማሳያ ቤት ባለቤትና ወይም ወኪል የሆኑት ሲኒማ ቴአትር የዜማና የዱለት ጨዋታ ለማሳየት ሕዝቡን ሳይሰበስቡ አስቀድመው ከስምንት ቀን በፊት የሚያሳዩትን ጨዋታ ዓይነትና ሕዝቡን የሚሰበስቡበትን ምክንያት ጭምር ጽፈው ከማዘጋጃ ቤት ከዋና ምርመራ ጽሕፈት ቤት ክፍል የማሳያ የፈቃድ ወረቀት ይጠይቃሉ የዋና ምርመራ ጽሕፈት ቤት ሕዝብ እንዲሰበሰብ የፈቃዱን ወረቀት ሳይሰጥ አስቀድሞ በጨዋታው ቤት ባለቤቶች የተባሉትን ጨዋታ ዓይነት ወኪሉን ልኮ ያስመረምራል።

የሚታየውን ጨዋታ ዓይነት የዋና ምርመራ ጽሕፈት ቤት አስመርምሮ ይህ የሚታየው ጨዋታ ዓይነት ለሕዝብ ጸጥታና ምግባር የሚስማማ ከሆነ ለማዘጋጃ ቤት ዲሬክሰዮን አመልክቶ ፈቃድ ከተቀበለ በኋላ ለጠያቂዎቹ ሊያሳዩ የጠየቁትን ጨዋታ ዓይነት እንዲያሳዩ የፈቃድ ወረቀት ይሰጧቸዋል ነገር ግን ይህ የሚታየው ጨዋታ ዓይነት ለሕዝብ ጸጥታና ምግባር የሚቃወም ሁኖ የታየው እንደሆን ለመርማሪው ለጨዋታ ማሳያ ቤት ባለቤቶች እንዲያሳዩ የፈቃድ ወረቀት አይሰጣቸውም ።

፪ተኛ ፤ የጨዋታ ማሳያ የፈቃድ ወረቀት መጠየቂያው ዱብዳቤ ሕዝብ በሚሰበሰብበት ቤት ባለቤትና በወኪሉ ወይም በዲሬክተሩ ይፈርማል ነገር ግን ስብሰባው ለመልካም ሥራ የሆነ እንደሆን ሕዝቡን በሚሰበስበው ማኅበር ሹም (ፕሬዚዳን) ይፈረማል ።

፫ተኛ ፡ ቴአትር የዜማና የዱለት ጨዋታ ለማሳየት ወይም በሌላ ምክንያት ለገዛ ጥቅማቸው ሲሉ ሕዝብን የሚሰበስቡ የማሳያ የፈቃድ ወረቀት ሲቀበሉ ስለፈቃዱ ወረቀት ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው በሦስት አኳኋን ይከፍላሉ ።

ሀ ፤ መቶ ብር ።
ለ ፥ ሰባ አምስት ብር ።
ሐ ፥ አምሳ ብር ።

፬ተኛ ፤ የጨዋታ ማሳያ ቤቶች ለመልካም ሥራ ሲሉ ማለት መሬት በመቀጥቀጥ አደጋ ላገኛቸው ስለሆፒታል እርዳታ ሕዝብን በሚሰበስቡት ጊዜ የጨዋታ ማሳያው የፈቃድ ወረቀት በነፃ ይሰጣቸዋል ።

፭ተኛ ፥ የሕዝብ መሰብሰቢያ ቤት ባለቤቶችና ወይም ሌሎች ቢሆኑ ከዚህ በላይ የተባለውን ሳይፈጽሙ የጨዋታ ማሳያ የታተመ ማስታወቂያ ለሕዝብ ሊያቀርቡ አይችሉም ።

፮ተኛ፥ ምናልባት አንድ የሕዝብ መሰብሰቢያ ቤት ባለቤት ከዚህ በላይ የተባለውን ሳይፈጽም ቀርቶ ፈቃድ ሳይቀበል ሕዝብ የሰበሰበ እንደሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለት መቶ ብር፥ ለሁለተኛ ጊዜ ስድስት መቶ ብር መቀጮ ይከፍላል።ለሦስተኛ

ጊዜ ግን በባለ ሥልጣን የሕዝብ መሰብሰቢያ ቤቱ ፈጽሞ ይዘጋል ።

፱ተኛ ፤ የሕዝብ መሰብሰቢያ ቤት ባለቤቶች ሲኒማ በሚያሳዩበት ጊዜ ሁሉ በመጀመሪያ ምዕራፍ የተመለከተውን በትክክል መፈጸም አለባቸው።የማሳያ የፈቃድ ወረቀትም በተቀበሉ ጊዜ ሁሉ ዓሥር ዓሥር ብር ይከፍላሉ ምናልባት ይህን ደንብ ያልፈጸሙ እንደሆነ ግን በስድስተኛው ምዕራፍ የተባለውን መቀጫ ሊከፍሉ ይፈረድባቸዋል ።

፲ተኛ ፤ የሕዝብ መሰብሰቢያ ቤት ባለቤቶች ሁሉ ቴአትር ሲኒማ የዜማና የዱለት ጨዋታ በሚያሳዩበት ጊዜ ሁሉ ሁለት የመጀመሪያ ማዕርግ ቦታ ለማዘጋጃ ቤት መርማሪዎች ያዘጋጃሉ ይህም የቴአትር የሲኒማ ፤ዜማና የዱለት ጨዋታ ማሳያ ቤት ደንብና ሕግ ከታወጀበት ቀን ጀምሮ ይቆማል ።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት ።

የአዲስ አበባ ከተማ ክንቲባ ።

ሥላሴ ።

ንጉሠ ሰላም ።
ክሂል ንድቁ ለዕበይከ
ዓረፍተ ኀፉትከ ቅጽር አኮኑ በአምጣነ ጸሕቀየ ዓምድ ።
ወነዋኀ ጥቅማ እምነዊ ማኅፈድ ።
ታሕተ ጽላሎትከ አዕርፍ ባሕቱ፤ከመ ኢይክልአኒ በዕድ።
ወፍሬ ኢ.ደኅማአ ጊዜ ገሚድ ።
እንቲአከ ይእቲ ምድር፤ ውሂበ መፍቅድ ።
ወዚአከ ይእቲ ልማድ ።

መወድስ ።

ሥሪዐ ዜና ግብር ደምሀሩ እምእለ አኀዙ
ሡስተ መጻልው ዓለመ አመ አንበሩ ለፍጻ ።
ወእመ ጠቢባን ፈደዩ፤ እምእምሮቶሙ ዕዳ ።
ክርቤ ወወርቀ ጠበብተ ዕርዕ ።
ወሰሎሞንሃ አምኃ ወጋዳ ።
ኃይለ ሥላሴ ዘአልአሜዳ ።
ትሬእዮሙ ለእሉ፤ ከመ ብርዐ ባሕሩስ ወፍሬ ተቅዳ ።
አኮኑ ከመ ራእዩ፤ ለበዓለ ፈረሰ ፀዓዳ ።
ከይሴ ወአቃርብተ አመ አእጋሬከ ይከይዳ ።
ትቤለከ ነያ ድንግል፤ ኢትዮጵያ ሳይዳ ።
ውስተ ርእሰ አድባር እሬእዮ፤ወእሌብዎ ውስተ ይሁዳ ።

አርኦያ ሥላሴ ወረታ ።

የዋና ምርመራ ዘበኞች
በሥራቸው ላይ መትጋታቸውን የሚያሳይ

እንዳውሮፓ ደንብ ሁሉ ተመስርቶ የቆመውን የከተማ ጥበቃ የዘበኝነትን ሥራ የሚያትጋጉና የከተማ ዘበኞችንም ዘወትር በሥራቸው ላይ እንዲበረቱና እንዲጠበቁ ተብሎ የዋና ምርመራ ዘበኞች በተለይ ከቆሙ ጀምሮ በየጊዜው የሚሠሩትን የትጋት ሥራ አስተዋይ ሰው ሳይገነዘበው አይቀርም

፩ኛ ማስረጃ፥ አሁን በሰኔ ወር ውስጥ ጽኑ የሆነውን የመንግሥት አዋጅ ተላልፎ በሥውር ወርቅ ይሸጥ የነበረውን የወለጋ ሰው በረቂቅ ብልሐት ይዘው ግፋቱን አሳምነው ለቅጣት ማሳለፋቸውን ሰምተን ትጋታቸውን ስናመሰግን ነበረ ።

፪ኛ ማስረጃ፥ ደግሞ እነዚህ የዋና ምርመራ ዘበኞች ዘወትር ማታ ማታ በየበሩ እየሆኑ ማቋረጫ ማቋረጫውን ስፍራ እየያዙ ጥፋተኞችን እንዲጠባበቁ ከለቃቸው ዘንድ የበረታ ትእዛዝ ተቀብለው ነበርና እንደዚሁ ሁሉ ያለቃቸውን ትእዛዝ ተቀብለው ከመሥራታቸው የተነሣ በ፲፱፻፳፬ ዓ ም ሐምሌ ፳ቀን ከሌሊቱ በ፰ሰዓት ወደፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ሰፈር በሚያሻግረው ድልድይ አጠገብ ሆነው ሲመለከቱ መሬት እየቆፈሩ የሚሰርቁ ከ፲ የሚበልጡ ሌቦች የስርቆት መሣሪያቸውን እንደያዙ ከንዱ ወዳንዱ ክፍል ሲተላለፉ አግኝተዋቸው በደምቡ ቁሙና ተያዙ ቢሏቸው ሌቦቹ አንያዝም በማለት በኃይል ሲሸሹ እየተሯሯጡ ብዙ መንገድ ሰሰሐዱ ይልቁንም የሚሯሯጡበት ስፍራ በወንዝ ውስጥ ሆኖ እየተበታተኑ ለማምለጥ ስፍራው ስለረዳቸው ሌቦቹ ማምለጣቸውንና ጥፋተኛ መሆናቸውን የዋና ምርመራ ዘበኞች በፍጹም ተረድተው ጠመንጃ ተኰሱባቸው፡ከዚህ በኋላ ከመካከላቸው አንዱ ነገዎ የሚባለው ሌባ መቈፈሪያውን እንደያዘ በጥይት ተመቶ ወድቆ አገኙት ይልቁነም ደግሞ በሌላ ክፍል ቦኩል ይመረምሩ የነበሩት የዋና ምርመራ ዘበኞችና በገበያው መካከል ይጠብቁ የነበሩት የከተማ ዘበኞች ተኵሱን ሰምተው እየተሯሯጡ ከዚሁ ስፍራ ላይ ጥፋተኛው እንደወደቀ ገና ሳይነሣ ወድያው በፍጥነት ደርሰዋልና የነዚህንም ትጋት ማሳሰብ ይገባናል። ከነገዎም ጋራ ከነበሩት ሌቦች ለጊዜው ሸሽተው ተሰውረው ስለነበረ በማግሥቱ በሰላይ ፪ቱ ሌቦች ተይዘው ከነገዎ ጋራ ሊሰርቁ መሔዳቸውን አምነው ወደ እስር ቤት ተላልፈው ቅጣታቸውን ለመቀበል የፍርዱን ቀን ይጠባበቃሉ ።

፫ኛ ማስረጃ፥በሐምሌ ፳ቀን መተኪያ የሚባል ሰው ልብሱ በደም እንደተነከረ ባከሔዱ እንደማይታወቅበት ሆኖ ሲሸሽ ይህ ሰው ያለምክንያት ልብሱ ደም አልሆነምና ብለው በጥርጣሬ የዋና ምርመራ ዘበኞች ይዘው ከበላይ አለቆቻቸው ስላቀረቡት አለቃቸው ምናልባት ሰው ገድሎ እንደሆነ የያዛችሁበትን ስፍራ መሰረት አድርጋችሁ በከተማው አዙሩት ብሎ ትእዛዙን ሰጠ። ዘበኞችም እንደትእዛዙ ቃል ሁሉ ይዘውት ሲዞሩ ከደጃዝማች ወልዳማኤል ቤት አጠገብ ከወንዙ ዳር ፩ሰው በሰንጢ ተወግቶ ወድቆ ሲንፈራፈር አገኙት ከዚህ በኋላ በዋና ምርመራ ዘበኞች እጅ የተያዘው መተኪያ የተወጋውን ሰው እንድሪስ እንድሪስ ብሎ ጠርቶ እስካሁን ድረስ ነፍስህ አልወጣችምና እያለ እየተከዘ እሱ መውጋቱን ለዘበኞቹ ገለጻላቸው፡ዘበኞቹም ወዲያው ወደ ክንቲባ ችሎት ይዘውት ቀርበው የገደለበትን ምክንያት ቢጠየቅ የሁለታችንም አገር ጃማ ነው ይህ እንድሪስ የሚባለው ሰው ምትኬ የሚባለውን ወንድሜን ገድሎብኝ ነበርና በጉማ ታርቀን ገንዘቡንም ተቀብለን ዕርቁን ለማፍሰስ የደጃዝማች ወልዳማኤል ወንበር አቈራኝቶን መጥቶ ነገሩ በቶሎ የማይፈጸምልኝ ቢሆን ልብስ እንጠብ ብዬ በጧት ወደ ወንዝ ይዤው ወርደን ሳለ ነገሩን በምክ-

ንያት እነሣሥቹ ከመጣላት ደረስንና በሰንጢ ወጋሁት ብሎ ከመነ ብኋላ የሥርምሩን ቃል ጽፈው ወደ ወንጀለኛ ቅጣት ፍርድ ቤት ወዲያው ሰለቱን አሳልፈውታል እንድሪሰም በከተማ ዘበኞች እጅ ወደዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ሔዶ ጥቂት ቀን ሲታከም ሰንብቶ በሐምሌ ፲፫ቀን ሞተ ።

፩ኛ ማስረጃ፡ በሐምሌ ፲፫ቀን ደሳለኝ ሐበሻ የሚባለው ታመነ ዋሴ የሚባለውን ሰው ከሴትኛ አዳሪ ቤት አግኝቶ በማይገባ ምክንያት ጥል አንሥቶ በሽጉጥ መትቶት አጥር ዘሎ እሔዳለሁ ሲል የዋና ምርመራ ዘበኞች አለቃ ከመ ቅጽበተ ዓይን ደርሶ ከያዘው በኋላ ወደ ቢሮ አቅርቦ ነገሩን ቢመረምረው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ የተጣሉበትንና በሽጉጥም እስከመምታት የደረሰበትን ምክንያት አስረድቶ በእስር ቤት ቆይቷል ታመነ ዋሴም ወደሆስፒታል እየተመላለሰ ይታከማል ።

ይህን የመሰለ የትጋት ሥራ የሚሠሩትን የዋና ምርመራና የከተማ ዘበኞችን ሥራ የሚቃወም ሰው እንደዚሁ ሁሉ ጥፋቱ ተገልጾበት የቅጣት ፍርዱን የተቀበለ በደለኛ ይመስላል እንጂ እንግዲያውማ ከዚህ ቀደም በብርሃንና ሰላም እንደተነገረውና ይልቁንም በየጊዜው በማናቸውም ጥፋት በዘበኞቹ እጅ እየተያዘ የሚቀጣው ጥፋተኛ ሁሉ ባደባባይ ቀርቦ ጥፋቱን ከመነ በኋላ ፍርዱን እየተቀበለ መሔዱን ማንም አይስተውምና ስለዚህ በትጋት መሥራታቸውንና በእምነት ላይ እምነት ማግኘታቸውን ያስረዳል።

እንግዲህ ወደፊት የዘበኞቹ ሥራ ለከተማው ሕዝብ መመኪያ ሳይሆነው አይቀርም በማለት ተስፋ እናደርጋለን ።

በዳኝነት ክፍል ለሚሠሩ ሰዎች አስረጅ ያለው ምሳሌ

አንድ በባላገር ውስጥ የሚኖር ሰው ከእህሉ ምርት፥ከጥጡ ዝሪት፥ከከብቱ ርቢት፥ ከቡናው ከጌሾው አትክልት ሽጦ ለውጦ ከዘመን ወደዘመን ሲያጠራቅም አራት ሺ ከምስት መቶ ብር ተቀማጭ ገንዘብ አገኘ ። ይህ የዋህ የባላገር ሰው ይህችን በድካሙ ፍሬ ያከማቻትን ገንዘብ ወደባንክ ወስዶ አደራ እንዳይከት ባንክ መኖሩን አያውቅም እገዛ ቤቱም ከሣጥን አግብቶ ወይም እመሬት ቀብሮ እንዳያስቀምጥ የገሩ ሰው ገንዘብ ማጠራቀሙን ያውቃልና የቀን ድካም ተሰምቶኝ የሌሊት ንዋም በሸነፈኝ ጊዜ ሌባ አጥር ሰብሮ መሬት ቈፍሮ ገብቶ የወሰደብኝስ እንደሁ? ወይስ በባላገር ውስጥ የሚኖር ሽፍታና ወምበዴ በሌት በሰኑ ጨለማ እቤቴ ድረስ መጥቶ ደጃፌን በማስፈራራት አስከፍቶ እኔንና ቤተ ሰቤን አላገባብ ሠርቶ (ገድሎ) ብር ያስቀመጥሁበትን ሣጥን ሰብሮ ከፍቶ የዘረፈኝስ እንደሁ? እያለ ሲጨነቅ የሰማው ዘመዱ በዚህ ነገር አትጨነቅ የውጭ አገር ሰዎች የታመኑ ናቸው አሁንም እዚህ አጠገባችን አንድ የውጭ አገር ሰው ሱቅ አሠርተው ዕቃ ገዝተው ንግድ ጀምረዋልና ለሳቸው ወስደህ አደራ ያስቀምጡልኝ ብለህ ብትሰጣቸው ስጡኝ ባልካቸው ቀን ነገ ሠልስት እንዳይሉህ እኔ እታመንልሃለሁ ብሎ ምክር ቢያከፍለው ያም የዋህ የባላገር ሰው ልጆቹን አሸከሞ ሔዶ አደራ ያስቀምጡልኝ ብሎ ቈጥሮ አስረከበና አደራ አስቀምጫለሁ የሚል የምስክር ወረቀት አስፈርሞ ሳይቀበል እንዲያው ተመልሶ እቤቱ ገባ ።

በማቴዎስ ወንጌል በስድስተኛው ምዕራፍ በሐያ አንደኛው ቍጥር ኀበ ሀሎ መዝገብከ ህየ ሀሎ ልብከ ብሎ የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ በዓላት በሆነ ቀን ቍጥር አደራ ወዳስቀመጠበት ሰው ቤት ሔዶ ሙሴ እገሌ እንዴት ሰነበቱ? ይለዋል እሱም እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ብሎ አንድ ሁለት መለኪያ አረቂ ጋበዘ ይሸኘዋል እንደዚሁ ሁሉ በዚሁ ባደራ ገንዘብ ምክንያት ጠያቂ ተጠያቂ ጋባዥ ተጋባዥ እንደሆኑ ብዙ ዘመን አለፈና ከነጋዴው ጋር በመወዳጀቱ ምክንያት የተነሣ ይህ የዋህ የባላገር ሰው አንድ ዓይነት ዕቃ ሲረከስ በጅምላ ገዝቶ አስቀምጦ ያነን የረከሰ ዕቃ በተወደደ ጊዜ ሽጦ ለውጦ ብዙ ትርፍ ገንዘብ እንዲገኝ ስለተረዳ በዚያ በተቀማጭ ገንዘቡ ነግዶ እንዲያተርፍበት አሰበና ከዕለታቱ ባንደኛው ቀን አደራ አስቀመጠለት ሰው ዘንድ ሔዶ ያነን ገንዘብ ፈልጌዋለሁና እንዲሰጡኝ እፈቅዳለሁ ብሎ ጥያቄውን ቢያቀርብለት ያ በብዙ ታማኝ ነው የተባለ ሰው መቸ ቀን የሰጠኸኝ ገንዘብ ነው ብሎ ያለይሉኝታ ክህደቱን ገለጸለት ያም የዋህ የባላገር ሰው በብዙ ደንገጠና ሲፈር ሲቸር በእገሌ ዘመን እንዲህ ባለሰዓት አራት ሺ ከምስት መቶ ብር ቈጥሬ አደራ ያስቀምጡልኝ ብዬ አልሰጠሁዎትም ወይ? ቢለው አንኳን ይህን ያህል ገንዘብ አንድም ብር አላየሁ ምናልባት ተሳስተህ ይሆናል ሲል መለሰለት የክህደቱ ፍጻሜ ጭራሽ አላየሁም ማስረጃ እንዳለህ ፊርማዬን አምጣ ሆነ ምን ይሁን ሰማይ ቢወጡ በአየር ቢሮጡ እመሬት ቢፈርጡ ያራት ሺ አምስት መቶ ብር የደረሰኝ ፊርማ ካላመጣ ገንዘቡን አለማግኘቱን ተረዳና ሲያዝን ሲተክዝ ወደቤቱ ተመለሰ እቤቱም እንደደረሰ እህል አልበላ ወሀ አልጠጣ ስላለው በዳኛ ፍርድ የተቈረጠ እጅ ያቈጠቈጠ ያህል ነው ብሎ ወዳገረ ገዣው እንደራሴ ገሥግሦ ችሎት እንደተቀመጠ ደርሶ አቤት አቤት እግዚአብሔር ያሳይዎ ጌታዬ እህል ሸምቱ ከብት ሽጬ ጥቂት ገንዘብ ባጠራቅም እገዛ ቤቴ እንዳላስቀምጥ ሌባ ፈርቼ የውጭ አገር ሰዎች የታመኑ ናቸው ሲሉ ሰምቼ ላንድ የውጭ አገር ሰው አደራ አስቀምጥልኝ ብዬ አራት ሺ አምስት መቶ ብር ሰጠሁት አሁን ጅብ ፈርቶ እዛፍ ለወጣ ሰው ነብር እዚያ አድፍጦ ቈየው እንደሚሉት ተረት ታማኝ ነው ሲሉ ሰምቼ አደራ አስቀምጥልኝ ብዬ የሰጠሁት ሰው ጭራሽ አላየሁም ብሎ ካደኝ እባክዎ ጌታዬ የተሠወረ ነገር ለዳኛ ይገለጽለታልና እንደቸርነትዎ ሥራ ሠርተው የደሃ ገንዘቤን ያሰጡኝ ሲል አቤቱታውን አቀረበ ።

የዳኛው ጥያቄ) ይህን ያህል ገንዘብ አደራ ስታስቀምጥ የደረሰኝ ፊርማ ተቀብለሃልንስ ወይስ ስትሰጠው ያዩልህ ምስክሮች አሉህ ብሎ ቢጠይቀው ፊርማም አልተቀበልሁም ምስክርም የለኝ እንዲያው በእምነት ነው የሰጠሁት ሲል መለሰለት ዳኛውም እንግዲያ እኔ ምን ላርግህ የዳኛ ሥራ ፊርማ ተገኝቶ ያንተ ፊርማ ነው የኔ አይደለም ብሎው የተጣላ እንደሆነ ወይም ምስክር በገንዘብ ተገዝቶ እውነቱን እጥ

ፍቶ አብሎ የመሰከረበት እንደሆነ የነገሩን እውነት ለማግኘት እግዚአብሔር እንደገለጸለት ጥበብ እስከተቻለው ድረስ ይደክማል እንጂ ይህን ለመሰለ ነገር ምን መድኃኒት ይገኝለታል አይሆንልኝም ሂድ እቤትህ ቢለው ሦስት ቀን ሙሉ እቤቱ ሳይሔድ እቤት እቤት እያለ ከቤት አላስገባም ወደ ደጅ አላስወጣም እህል አላስበላ ወሃ አላስጠጣ ብሎ ቢያስቸግረው ዳኛውም ጭምር ከመጨነቁ የተነሣ የነገር ምሥጢር ተገለጸለትና ያ እቤት እቤት ባይ ደሃ ሳያየው በስርቆሽ በር ወጥቶ አደራ አስቀመጠ እተባለው ሰው ዘንድ ሒዶ ለብቻው በግል አደረገና ከዚህ በታች ያለውን ቃል ምሥጢር ብሎ አከፈለው።

ጌታ ሙሴ እገሌ አንድ የከበደ ነገር አገኘሁ ጌታዬ የኔን ሹመት ለሌላ ሰው ሊሰጡትም እንደሆነአላውቅም በቶሎ እንድትመጣ ብለው የትእዛዝ ደብዳቤ ላኩብኝ ከኔና ከርስዎ በቀር ማን ይህችን ምሥጢር ያወቃት ሰው የለም አሁን እንደምንም ብዬ ያጠራቀምሁት አንድ ፶ሺ ብር የሚሆን ገንዘብ ነበረኝ እጌታዬ ግምጃ ቤት አግብቼ እንዳልተወው ከኔ አገር የዘረፈው ነውእንጂ ከባቱ አገር ይዞት አልመጣ ብለው የወሰዱብኝስ እንደሆንብዬ ፈራሁ ላንዱ ጨዋ ሽማግሌ ያገሬ ሰውም አደራ አስቀምጥልኝ ብዬ ብሰጠው ምናልባት ሹመቴን የወሰዱብኝ እንደሆነ ለተሻረ ሰው ዘመድ የለውምና ምሥጢር አውጥቶ ከሳሽ ያስነሳብኛል ብዬ ተጠራጠርሁ ፤ እባክዎ ጌታዬ ከናንተ በቀር ለንደዚህ ያለ ነገር የሚታመን ሰው የለምና ይላኩልኝ ባልኩዎት ቀን ይልኩልኛል ነገ በጨለማ ልጆች አስይዤ እመጣለሁ አደራ እንዲያስቀምጡልኝ እለምንዎታለሁ አለው። አደራ አስቀማጩም እሺ ይሁን ብሎ ነገሩ በእሺታ ቆመ ዳኛውም ወደቤቱ ተመለሰ እቤቱም እንደደረሰ እቤት እቤት እያለ የሚያስቸግረውን ሰው ለብቻው አስጠራና በቁይታ አድርጎ አሁን ዝም ብለህ እቤትህ ሒድና እደር ነገ ጥዋት አደራ አስቀምጥልኝ ብዬ ብሰጠው አላየሁም ብሎ ከደኝ ወደምትለው ሰውጋ ሒደህ እባክህ ጌታዬ ስለእግዚአብሔር ብለህ ገንዘቤን ስጠኝ በለው አላየሁም ቢልህ መላልሰህ ለምነውና ቢሰጥ ይስጥህ ባይሰጥህ ግን ሌላ ነገር ሳትናገር ብቻ እንዲህ በለው ደግ ይሁን እኔማ ምንአደርጋለሁ የደሃ ጉልበት ዳኛ ነው ለዳኛ እመልከቼ ዳኛ የሚሉኝን እሰማለሁ ብለህ ተመልሰህ ውጣ አለና መክሮ ሰደደው ። እሱም እንደመከረው ሒዶ ገንዘቤን ስለ እግዚአብሔር ብለው ይስጡኝ ቢለው መቼ ያበደርኸኝ ገንዘብ ነው የለም አላውቅም አለና መለሰለት ።

ያም የዋህ የባላገር ሰው እንደተመከረው ቃል እሺ ይሁን ደግ ነው ካላወቁም ይህን ያህል ገንዘብ ተዘርፌ ለዳኛ ሳላመለክት አልቀር ወዳገሩ ዳኛ ሒጄ አቤት እላለሁ እንጂ ምን አደርጋለሁ ብሎ ወጥቶ ቢሔድ ለዳኛማ ከጮኸ ያነን አምሳ ሺ ብር አምኖ አስቀምጥልኝ ያለኝን ይጠረጥርና ያስቀርብኛል የሚበዛውን ገንዘብ መብላት ይሻላል ብሎ አስቦ ሰውዬውን ከመንገድ ጠርቶ መልሶ አላስቀመጥኩም ያልሁህ ተሳስቶኝ ነው እንጂ አሁን መዝገብ ሳገለባብጥ አንተ አምጥተህ ስትሰጠኝ የተጻፈበትን ቀን አገኘሁት ብሎ ገንዘቡን ቈጥሮ ሰጠው።ሰውዬውም ከደስታው ብዛት የተነሣ እልልታውን እያቀለጠ እዳኛው ቤት ሒዶ ደስታውን ገለጸ ዳኛውም ላንተ አራት ሺ አምስት መቶ ብር ለውጥ አምሳ ሺ ብር አገኘሁ መስሎት ነው የሰጠህ ብሎ ሳቀ ያም ደኃ ዳኛውን እየመረቀ ገንዘቡን አሸክሞ በደስታ ተመልሶ ወደቤቱ ገባ ።

ከስምንት ቀን በኋላ ብልህና አስተዋይ የሆነ ያገሩ ዳኛ አምሳ ሺ ብር ታስቀምጥልኛለህ ወዳለው ሰው ዘንድ ልኮ ያ በቀደም የተነጋገርነው ነገር ሰንባች ሁኑአል ቀጠሮ አፈረስህ እንዳይሉኝ ምክንያት አግኝቼ ነው የቀረሁ ሁሉንም እኔ መጥቼ እንጫወተዋለን ብለህ ንገር ብሎ ልጅ ልኮ ነገሩን በሥውር አስቀረው ።አሁንም ይህን የመሰለ ከዚህም የሚብስ ነገር አይጠፋምና በዳኝነት ክፍል የተቀመጣችሁ መኳንንት ለተሠወረ ነገር ሁሉ በረቀቀ ጥበባችሁ እንድትመረምሩትና ይህን የመሰለ ምክንያት እንድትፈልጉበት ማሳሰቢያ እንዲሆን ብለን ጽፈነዋል። ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አክሱም።

የባሯ ነፃነት ሥራ እየተሻሻለና እየሰፋ ስለ መሔዱ ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በአዲስ አበባ ላይ ለቆመው ለዋናው የባሯ ነፃነት ጽሕፈት ቤት በተለይ አንድ ዋና የበላይ ሹም ፤ አንድ ዋና ዳኛ፥ አንድ ዋና ጸሓፊ ሹመዋል ማለትን በወሬ ሰምተን ባለፈው ሳምንት አትመን ነበር።

አሁን ግን በኦፊሲዬል የሆነውን እርግጠኛውን ነገር ስለ ሰማን ለዚህ ሥራ የበላይ ሹም ሆነው የተሾሙት ክቡር ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤ፥ ዋና ዳኛ ሆነው የተሾሙት ፊታውራሪ ግዛው በየነ፥ ዋና ጸሐፊ ሆነው የተሾሙት ልጅ ዓለማየሁ ጠና መሆናቸውን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሁሉ እናስታውቃለን

ማስታወቂያ ።

በልዩ የቆመው የፍርድ ቤት ዋና ጽሕፈት ቤት በሐምሌ ፳፩ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም በተፈረደው ፍርድ ሄርማን ካርል እሽቱርሜር ጸሐፊ የፍልስፍና ሊቅ ቀድሞ የጀርመን ዜጋ የነበረ ዛሬ ግን የውጭ አገር ዜግነት የሌለው የሆነ ቀድሞ የጀርመን ዜጋ ከነበረች ዛሬ ግን የውጭ አገር ዜግነት ከሌላት ከማድሟዜል ገሬት ክሩገር ጋራ ቤርሊን ሽማርዣንዶርፍ ላይ በ፳፫ ኅዳር ፲፱፻፳፫ ዓ ም ከተጋቡት ጋብቻቸው በጀርመን ፍትሐ ነገሥት በ፩ሺ፭፻፷፭፣፷፮ተኛውና በ፩ሺ፭፻፷፰ተኛው ቍጥር እንደተወሰነው እንዲፋቱና ሁለቱም ወገኖች ከሣራውን ሁሉና የዳኝነቱንም እንዲከፍሉ መፈረዱን ያስታውቃል ።

ይኸውም ፍርድ በጋዜታ እንዲወጣ የሆነው ሙሴ እሽቱርሜር ከዚህ ቀደም ኑሮው አዲስ አበባ ነበር ዛሬ ግን ያለበት ስፍራ ስላልታወቀ ፍርዱን እንዲያውቀው ከጋዜጣ ውሥጥ ይግባልኝ ብላ ማዳም እሽቱርሜር ስላስታወቀች መሆኑን እያሳሰበን በፍርዱ ላይ ደግሞ ሙሴ እሽቱርሜር ይግባኝ የሚል የሆነ እንደሆነ ፍርዱ በጋዜጣ ውሥጥ ከገባበት ጀምሮ እስከ ሦስት ወር ድረስ የፍርዱን ግልባጭ ከልዩ ፍርድ ጽሕፈት ቤት ወስዶ ይግባኝ ለማለት ተፈቅዶለታል ስንል እናስታውቃለን ። ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።

የልዩ ፍሬድ ዋና ጽሕፈት ቤት በቀለ ሣህሌ ።

LE GREFFE
du
Tribunal Spécial fait savoir

Que par jugement contradictoir rendu par le Tribunal en date du 21 juillet 1932 le mariage contracté par Hersan Karl Stürmer, écrivin, Docteur en Philosophie, alors de nationalité allemande, mais actuellement heimatlos, avec Mademoiselle Gräte Krüger, alors de nationalité allemande mais actuellement heimatlon, à Berlin, Schmargendorf, le 20 novembre 1925 a été déclaré dissous par le divorce prononcé tant contre l'un que contre l'autre des époux en application des articles 1567 et 1568 du Code Civil Allemand et les dépens et autre frais de justice ont été laissés à la Charge de chacune des parties qui les a exposés.

La présente publication est faite en vertu d'un-ordonnance rendue par Monsieur le Président de ce Tribunal en date du 2 Août 1932 à la requête de Madame Stürmer-Krüger, pour savoir lieu de signification à la personne de sieur Herman Karl Stürmer ci-dessus designé et qualifié lequel précedemment domicilié à Addis-Abeba est actuellement sans domicile ni résidende connus.

Par la même ordonnance, un délai de trois mois francs à compter du jour de la présente publication a été imparti à sieur Herman Karl Stürmer pour former appel du jugement sus rappelé dont une copie est tenue à sa disposition au Greffe du Tribunal Spécial.

Le Greffier Chef du Tribunal Spécial

BACALLA SAHLÉ

ማስታወቂያ ።

አዲስ አበባ በአለው በእንግሊዝ መንግሥት ቆንስላ የፍርድ ቤት በከሣራ ስም ከተጠራው ከመሀሙድ ዩሱፍ የእንግሊዝ ሶማሌ ከሐብር ዩኒስ ጎሳ ላይ ገንዘብ የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ እስከሰኞ መስከረም ፴ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም ድረስ ከዚህ በታች በግርጌው ፊርማውን አፈረመው ሰው ዘንድ እየ መጡ ለሚጠይቁት ገንዘብ ማስረጃቸውን እንዲአቀርቡ እንአስታውቃለን ።

ከዚሁ በከሣራ ስም ከተጠራው ሶማሌ ዘንድ የተገኘው ገንዘብ ጥቂት በመሆኑ የተነሣ ያነኑ የተገኘውን እንደሆነ በቅርብ ቀን ለማከፋፈል ታስቧልና ስለዚህ ከዚህ በላይ እስከ ተወሰነው ቀን ድረስ ማስረጃቸውን የአላቀረቡ ሰዎች በክፍያው ውስጥ ለመግባት አይችሉም ።

ሐምሌ ፴ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ተጻፈ ።

ቲ ። ዲ አየር   አፊሲዩል አሲኚ

Japanise Dentist
ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።



ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቁ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፈቃዳቸው ሕገ መንግሥት ስለማቆማቸው የገንዘብ ሚኒስቴር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት በ፲፱፻፳፬ ዓ ም ለመሰፍንቱና ለመኳንንቱ የተናገሩት የስብከት ቃል በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታትሞ በዕሩብ መሸጡን እናስታውቃለን ።



ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱሬ እስከ ፴ወር እንዲወርዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመገብየት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፒሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ካገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሴና ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዘር የተመቸ መጋዝና ስዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፴፬
8me ANNE. № 34

ሐሙስ ነሐሴ ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 18 AOUT 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ፡ መጣት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

መግፋትን የታገሠ ቢወድቅም ይነሣል ።

መገፋት አይጠቅምም የሚሉ ቍጡዎች ሰዎች ቢኖሩ ወትትን መርምረው መረዳት ይችላሉ ። ስለም፥ ቢሉ ወተት ባይገፋ ቅቤ ሁኖ በሰው ራስ ላይ አይወጣም ነበር ። ይህንም ያሳሰበን ምክንያት የጐጃም ሕዝብ በራስ ኃይሉ አገዛዝ አጥብቆ ባይበደል በተክክለ ደምብ የሚገዙ ለመንግሥት ከልብ አሳቢ እውነተኛውን ዳኛ ራስ እምሩን የመሰለ ዳኛ አያገኝም ነበር ። ከነዚህም በላይ ከተጸፉት ሕዝብ ወገን የሆኑ አለቃ ፈንታ ገብርዬ የሚባሉ መልካም ትምህርትና የእጅ ሥራ የተሰጣቸው ንጉሥ ተክለሃይማኖት ያሳደጓቸው በማያስፈልግ ነገር ራስ ኃይሉ ተጣልተው አበርረዋቸው ፳ዓመት ሙሉ አዲስ አበባ መጥተው በደጅ ጥናት ሲኖሩ በባለቤቱ ፈቃድ ራስ ኃይሉ ተሽረው የተበደሉትና የበደሉት ሁሉ ዋጋቸውን በተቀበሉ ጊዜ አለቃ ፈንታ ገብርዬም ሳያስቡት በጃንሆይ ቃል ተጠርተው መልአከ ብርሃናት ተብለው በማዕርግ ተሸልመው የብቸና ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን አለቅነት በተሾሙ ጊዜ መቸም ከተማረ ሰው መልካም አነጋገር አይጠፋምና የተናገሩትን ቃል ስፍራ ጠቦን አቆይተነዋል እንጂ ታትሞ ቢሆን ምን ያህል ደስ የሚአሰኝ ይመስላችኋል? ለሰው ከላይ የታዘዘለት በጊዜ ብዛት አይቀርምና ደጅ ጠኚ ሆይ የጊዜውን ብዛት አይተህ ተስፋ እንዳትቆርጥ ማስረጃ ይሆንሀልና ተመልከተው ።

በአስበ ተፈሪ የተደረገ ትልቅ በዓል ።

ሐምሌ ፲፮ ቀን የጃንሆይቀ ኃ ልደት ስለ ሆነና ይህንንም የልደት ቀን መላ ኢትዮጵያ ሊያከብረው የሚገባ ስለሆነ የጨርጨር አውራጃ ገዥ ክቡር አዛዥ ወርቅነህ በአዲስ አበባም ሳሉ የተፈሪ መኰንንን ትምህርት ቤት ተማሮች እያተጉ በየጊዜው ይህንን በዓል ለማክበር በዓመት በዓመት አላቋረጡም ነበርና አሁንም በአስበ ተፈሪ ፲፱፻፳፬ ዓ ም ኅዳር ፳፩ ቀን የከፈቱት ተማሪ ቤት በዚሁ በጃንሆይ ቀ ኃ ልደት ቀን ብለ ዕረፍት እንዲዘጋና በዓሉም ደኅና ሁኖ እንዲከበር ብለው በአስበ ተፈሪ ከተማ የሚኖሩ ታላላቆች ሹማምትና መኳንንት የውጭ ሀገርም ሰዎች የመንግሥት ጸሐፊና ሠራተኛ ሁሉ በመላው አንድ ሳይቀር አለቃ ያለው በአለቃው አለቃ የሌለው በየራሱ ስም እንዲጠራ አዝዘው ነበርና በዚሁ ቀን የተጠራው ሰው ሁሉ አንድ ሳይቀር በስምንት ሰዓት ተዘል የተሰበሰበው ሲታይ የአስበ ተፈሪ ከተማ ይህንን ያህል ሕዝብ በመያዝዋ ብዙ ሰዎች ይደነቁ ነበር ። ክቡር አዛዥ ወርቅነህም የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ወደ ተሰናዳው ቦታ ከመኳንንቶች ጋራ ሲገቡ ተማሪዎች የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር በዘመሩ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ከአዛዥ ወርቅነህ ጋራ ቀጥ ብሎ ቆመ ከዚህ በኋላ ክቡር አዛዥ ወርቅነህ ስለ ጃንሆይ ልደት የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ወዳጆቼና ልጆቼ ሆይ ።

ይሄው ዛሬ ሁለተኛ ዓመቱ ነው ከአላንት ከወንድሞቼ ጋራ ሆኜ የተወደዱና የተመሰገኑ ንጉሣችን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የልደት ቀን ማክበሬ ለዚህ ስላበቃኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ። ባለፈው ዓመት እንደምታውቁት ጃንሆይ ስለታመሙ በጣም አዝነን ነበር እግዚአብሔር በምሕረቱ ስለ አዳናቸውና መጥተው ከተማችንን ስለ ጐበኙልን ደስ ብሎን ሳለ በንጉሣችንና በኢትዮጵያ ላይ ክፉኛ ችግር መጥቶብን ነበር ግን ኃጢአታችን ምንም ቢበዛ መሐሪ አምላካችን በቸርነቱ የክፋዎችንና የሞኞችን ሰዎች ክፉ ምክር አፈረሰልን ። የወንድሞቻችንን ብዙ ደም ከማፍሰስና በዓለም ላይ መሳቂያ ከመሆን አዳነን ። ስለዚህ ለታላቅ ቸር አምላካችን በሙሉና በጥሩ ልባችን ማመስገን ይገባናል እግዚአብሔር መርጦ በእርግጥ መንግሥትን ለሰጣቸውና ለቀባቸው ለንጉሠ ነገሥታችን ፍጹም ጤናና ረጅም ዕድሜ እንዲሰጣቸው በሙሉና በጥሩ ልባችን እንለምን። ለግርማዊት እቴጌ፣ ለልዑል አልጋ ወራሻችን፣ ለሌሎችም ልጆቻቸው ሁሉ ጤናና ዕድሜ እንዲሰጣቸው እየለመን ጽዋችንን አንሥተን እንድንጠጣ እለምናችኋለሁ።ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ያኑርልን ብለው ሲጨርሱ ሶስት ጊዜ ዳር እስተዳር ተጨበጨበ። ቀጥሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር እንደገና ተማሪዎች ዘመሩና የቻይ ግብዣ ተጀመረ ቻይ ሲጠጣ ሦስት ተማሪዎች በየተራ ቀርበው ጃንሆይ ከልጋ ወራሽነታቸው ከ፲፱፻፱ ዓ ም ጀምረው ለኢትዮጵያ የሠሩትንና የኢትዮጵያን የዱሮ ታሪኳን ባጭሩ ለሕዝቡ

ገለጸ። ከነዚህም አንዱ አያሌው ዘለለው የተባለው ተማሪ በሕዝቡ ፊት ለተማሪዎች የሚከተለውን ተናገረ ። ወንድሞቼ ሆይ ይህችን ቀን የምናከብርበት ዋና ምክንያቱን ምንም ብታውቁት አገልጽላችኋለሁ ። ጃንሆይ ቀ ኃ ሥላሴ በዚህች ቀን ተወለዱ ። በዚህች ቀን ስለተወለዱ ብቻ አይደለም ደግሞም በዚህች ወራት መንግሥታችንን የሚያረጋና ደስታ የሚሰጠን ሥራ ተሠርቷል ። ዛሬ እንደዚህ አንሳ የምናያት ኢትዮጵያ ሀገራችን በዱሮ ዘመን አሁን በታሪኳ እንደሰማን ከሁሉም የምትበልጥ እጅግ ታላቅ ሀገር ነበረች።ያነሰችበትም ምክንያት ከዚህ ቀደም የተነሡ ነገሥታቱዋ እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ በማለት ስለ ተለያዩ ባንድነት ሁነው ስለ አልረዱዋት አንድነታቸውን ስለ አላወቁ ችላ በማለታቸው እያዩ በዕዳን ያዙባት እንጂ ስምምነት ቢኖራቸውና ቢረዱዋት ኑረው ማንም ሊደፍራት ባልቻለም ነበር። አሁን ግን ጃንሆይ ቀ ኃ ሥላሴ ለቆላ ለደጋው ለግራ ለቀኙ ሳይሉ ኢትዮጵያ ሀገራችንን ለመርዳት ፍጹም ሐሳባቸው ስለሆነ በመንግሥታችን እስከ የልጅ ልጃቸው ጸንተው እንዲኖሩ ሕፃናቱ ሁሉ ፍጹም ምኞታችን ነው። ከአልጋ ወራሽነታቸው ጀምረው እስከ አሁን ለኢትዮጵያ የሚጠቅመውን ሥራ ከመሥራት አላቋረጡም። የውጭን ሀገሮች መንግሥታት ጐብኝተው ሲመለሱ በ፲፱፻፲፯ ዓ ም የአውሮፓውያንን ሥልጣኔና አኳኋን አይተው ተቈርቍረው ለሀገሬ ለኢትዮጵያ ወጣቶች እንደዚህ የሥልጣኔ ትምህርት ቤት ማቆም ይገባኛል ሲሉ የተፈሪ መኰንንን ትምህርት ቤት አዲስ አበባ ላይ አቆሙ ለዚህም ሥራ ዋና ሆነው ያስኬዱ የነበሩ ክቡር አዛዥ ወርቅነህ ነበሩ ።

አሁንም ክቡር ጌታችን አዛዥ ወርቅነህ ጃንሆይ ቀ ኃ ሥላሴን ለመርዳትና የጃንሆይ የሀገራቸውን ሕፃናት ለመጥቀም ሲሉ ይህነን ተማሪ ቤት ከፈቱልን ። ይህም ረዳት ቢያገኙ በየሁሉ ስፍራ ተማሪ ቤት ተከፍቶ ሕፃናቱ ሁሉ እንድንሠለጥን የደጉ ንጉሠ ነገሥታችን ምኞት መሆኑን ያስረዳናል ። እኛም እንደዚህ ያለ ደግ ውለታ የሚውሉልንን የብርሃናችንን የልደት በዓል ልናከብረው ይገባናል ። ለኢትዮጵያ ደግ ሥራ የሚሠሩላትን ጌቶቻችንንና አባቶቻችንን ከደጉ ንጉሠ ነገሥታችን ጋራ አምላክ ይጠብቅልን ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ባለ ጊዜ ተጨበጨበለት ።

ከዚህ በኋላ አምላክ እስራኤል ታማኝ ጌታችን ብሎ የሚጀምረውን መዝሙር ተማሪዎች በጥሩ ድምጥ አስተካክለው ዘመሩት ከዚህ በኋላ ኒቆዲሞስ ኢየሱስን በሌት ሒዶ የጠየቀውን ጥያቄና ኢየሱስ ያስተማረውን ትምርት እንደ ቲያትር አድርገው ለሕዝቡ ሰባኩና ሰውን ሁሉ አስገረሙ። ቀጥሎ ስለኢየሱስ ሁለት መዝሙሮች ዘመሩ ከነሱ አንዱ የሚከተለው ነው ።

የልደት መዝሙር ።

፩ኛ፥ በሰማይ ለሚኖር ለሁላችን አባት
ከመላእክት ጋራ ዛሬ እንበል ስብሐት
ለዓለም የሚበቃ ላከልን መድኃኒት
ለኛ ክብር የሚሆን ለሰይጣናትም ሞት
ለካዱት ጨለማ ላመኑበት መብራት
ይታደጋቸዋል ለቀረቡት
መድኃኒታችን የኛ ትምክህት ለካዱት ጥፋት ነው ላመኑበት ሕይወት ።

፪ኛ፥ ጥግ አጣን ላሉት ጥግን መስጠት ሲችል
ለደካማዎችም ሲጨምር ጉልበት ኃይል ።
ቸግሮት አይደለም የወደቀ በጎል ።
ለኛ ሲል ነው እንጂ ሸክማችንን ሊያቀል ።
ሰይጣን የጫነንን በበለሱ ቅጠል፣
ሁላችንም እርሱን እርዳን እንበል ።
መድኃኒታችን የኛ ትምክህት ለካዱት ጥፋት ነው ላመኑበት ሕይወት ።

፫ኛ፥ ውለታውን ከቶ እንዴት እንመልስ ።
እኛ ድሆች ችለን ለዚህ ታላቅ ንጉሥ ።
ለኛ ሲል ተዋርዶ መጥቶ እስከዚህ ድረስ ።
የሰይጣንን ምክር ወዲያ ሊያፈራርስ ።
እርሱንም አጥፍቶ ሊሆነን ሞገስ ።
መንግሥቱንም ቶሎ ለኛ ሊያወርስ ።
መድኃኒታችን የኛ ትምክህት ለካዱት ጥፋት ነው።ላመኑበት ሕይወት

ኢሊባቦር አሌ ገነት ከተማ ሕገ መንግሥት ስለቆመበት ቀንና ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ስለተወለዱበት ቀን የተደረገበዓል።

ሐምሌ ፱ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ጃንሆይ ሕገ መንግሥትዎን የመሠረቱበትና ያፀኑበት የመጀመሪያው ዓመት ስለሆነ ይህነኑ በዓል ለማክበር ክቡር ራስ ሙሉጌታ በገነት ከተማ የሚኖሩትን የመንግሥት ሠራተኞችና የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሰዎችንና ታላላቅ ነጋዴዎችን ሁሉ ከጧቱ ባራት ሰዓት ተኩል የማዕርግ ልብሳችሁን እየለበሳችሁ መጥታችሁ የደስታችን ተካፋይ እንድትሆኑ ብለው ገና በዓሉ ፫ቀን ሲቀረው በጽሕፈት አስታውቀው ነበርና በዚሁ በተወሰነው ቀንና ሰዓት መኳንንቱ ሁሉ የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው እንዲመጡ ለበዓሉ ማክበሻ በዘምባባ፥ ባበባና በኢትዮጵያ ባንዲራ ባጌጠው ቤት ሁሉም እንደ ማዕርግ እንደ ማዕርጉ ተቀመጠ። ወዲያው ብፁዕ አባታችን አቡነ ሚካኤል ከርዶን ኒሻናቸውን ለብሰው መጥተው በተሰናዳላቸው ቦታ እንደተቀመጡና የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ካፒቴን ኢ ኤን ኤርስኪን የማዕርግ ልብሳቸውን የክብር ኒሻናቸውን ለብሰው ከመጡና በገነት ከተማም የሚኖሩ አውሮፓውያን ነጋዴዎች ሁሉ መጥተው በየማዕርጋቸው ከተቀመጡ በኋላ በያይነቱ መጠጥ ቀረበና የደስታ ጨዋታ ሲጫወቱ ጥቂት ቈይተው ወዲያው ሻምፓኝ ቀረበና ክቡር ራስ ሙሉጌታ የጻፉት ዲስኩር ለኢሉባቦር አውራጃ ጉምሩክ ዲሬክተር ላቶ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልዳማኑኤል ተሰጥቶ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ቃል ተነበበ ።

ብፁዕ አባታችን፥ ክቡራን መኳንንት ሆይ፥ ዛሬ የኃያላን ኃያል የነገሥታት ንጉሥ የሆኑ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ሕዝቡና መኳንንቱ ሳያስገድዷቸው ማስፈለጉን በሰፊውና በጤ

ራው አእምሮአቸው መርምረው በገዛ ፈቃዳቸው ሕገ መንግሥትን የመሠረቱበትና ያጸኑበት ቀን ስለሆነ መላ ኢትዮጵያ ይህን የተባረከና የተቀደሰውን ቀን በየመቱ ለማክበር ለዘለዓለም አይዘነጋውም እንዲሁም አሁን እኛ ይኸን የመጀመሯውን ዓመት የሕገ መንግሥት በዓል ለማክበር ምቹ ጊዜና ዕድል ብማግኘታችን ደስታችን ከልክ ያለፈ መሆኑን ለብፁዕ አባታችንና ለላንት ለክቡራን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ ።

ክቡራን ሆይ፥የዚህን የሕገ መንግሥት አመሠራረት ለተመለከተው ሰው ዕድላሙ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ እንደ ቀድሞው አባታችን እንደ ዳዊት ትንቢት የተገለጸላቸው ናቸው ለማለት ያስደፍራል ማለት እስከ ዛሬ ድረስ በማንላቸው ዓለም ቢሆን ሕዝቡና መኳንንቱ ሳያስገድዱትና ሳያሰቡት እንደዚህ ያለውን የሰላም መሪ የሆነ ሕግ ንጉሠ ነገሥቱ በራሱ ሐሳብና ፈቃድ አቆመ ሲባል አልሰማንም።ለዚሁም ማስረጃ የሚሆን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስም ብንመለከት እናጣም ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር እስራኤልን ከምድረ ግብፅ በወጣቸው ጊዜ ሕዝቡ ተሰብስበው ሙሴንና አሮንን ሕግ ስጡን ብለው እንዳስገደዷቸውና ሙሴም በዚሁ ተቸግሮ ወደ እግዚአብሔር አመልክቶ ሕግ እንደ ተቀበለና እንደ ሰጣቸው እንብበናል ከዚያም ወዲህ ብዙ የዓለም ነገሥታት ሁሉ በሕዝቡ ማስገደድ ምክንያት ብዙ ልዩ ልዩ ሕግ እንዳወጡ በብዙ ታሪክ አንብበናል ግን እኒህ አስተዋዩ ንጉሠ ነገሥታችን ወደ ፊቱ የሚሆነውን አውቀው ያለ ግዴታ በውዴታ ይህን ሕገ መንግሥት በማቆማቸው ከታላላቆቹና ከስመ ጥሩዎቹ ከዓለም መንግሥታት ጋራ ያስተካክላቸዋል ለማለት እንደፍራለን

ክቡር የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ካፒቴን ኤ. ኤን ኤርስኪን የዛሬውን በዓል ታሪክ እንደተቻለኝ ከበረዳሁ በኋላ ይኸንኑ በዓል ለማክበር በደስታ ስለመጣችሁ በኔ በራሴና ክፍ ባሉ መንግሥቴ ስም ሆኘ የሚገባችሁን ምስጋና አቀርባለሁ ዕድሜ ለቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ፥ዕድሜ ለዕድለኛይቱ እቴጌ መነን፥ ለልዑል አልጋ ወራሻችንና ለልዑላን መሳፍንቶች ሁሉ እየተመኘሁ ስለሀገራችን ሰላምንት ስለሁላችሁ ጤንነት ጽዋዩን እንሣለሁ ብለው ሲጨርሱ ፫ጊዜ እየተደጋገመ ተጨበጨበ። ቀጥሎም የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ካፒቴን ኤ. ኤን ኤርስኪን ድንቅ የሆነ ዲስኩር ተናገሩ።ቀጥሎም የገነት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ተማሪ ቤት ዲሬክተር ልጅ ንጋቱ ማህሌ ደስ የሚያሰኝ ዲስኩር ተናገረ።ቀጥሎ ከኢሉባቦር ለምክር ቤቱ እንደታዘዘው ተመርጦ አዲስ አበባ ወጥቶ የነበረ ቀኛዝማች ኃይሌ ኤጀርሶ ዲስኩር ተናገረና በመጨረሻ ብፁዕ አባታችን አቡነ ሚካኤል የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴን የደግነት ታሪክ ዘርዝረው ተናገረውና ባርከው አሰረጉ። ከዚህም በኋላ ሕዝቡ ሁሉ መንግሥቱን እያመሰገነ የውጭ አገርም ሰዎች ከክቡር ራስ ሙሉጌታ እየተሰናበቱ ሄዱ ወዲያው ክቡር ራስ ሙሉጌታ ለሕዝቡና ለመኳንንቱ በልፍኝ አዳራሽ ደስ የሚያሰኝ ግብር አድርገው ዋሉ ።

፪ኛ፥በስምንተኛው ቀን ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም የጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ልደትዎ ስለሆነ በመጀመሯ እንደ ተጻፈው ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ስለ ልደቱ በዓል ከጧቱ በ፩ ሰዓት ተኩል የማዕርግ ልብሳችሁን ለብሳችሁ አግቢ ድረስ መጥታችሁ የደስታችን ተካፋይ እንድትሆኑ ብለው ከ፫ቀን በፊት ለመንግሥት ሠራተኞችና ለአውሮፓውያን መኳንንቶችና ለታላላቆች አስታውቀው ነበርና በነጋው ከጧቱ በ፲፪ ሰዓት ስለልደቱ በዓል ፯ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ወዲያው የአምቢልታውና የመለከቱ የነጋሪቱ ቃል ተቀጣጥሎ ሲያጓራ የከተማውን ሰው ሁሉ ልቡን በደስታ ያናውጠው ጀመር።በዚሁም በተቀጠረው ሰዓት መኳንንቱ የማዕርግ ልብሱን ለብሶ ተቀጣጥሎ ወደ ግቢ ሲገባ ላየው ድምቀቱ ከጧት ጀምበር ጋራ ተጋጥሞ ሲያንጸባርቅ እጅግ ያስደንቅ ነበር።ምድረ ግቢውም ከሳምንቱ ይልቅ ውጭው ሁሉ በለመለመ ዘምባባ ባበባና በኢትዮጵያ ባንዴራ አጊጦ የኢትዮጵያም ባንዲራ በያለበት ተደርጎ በነፋስ ላይ ሲያንዣብብ ለሚያዩው ሁሉ ልብን በደስታ ይሠውር ነበር።ወዲያው ብፁዕ አባታችን የአውሮፓውያን መኳንንቶችና ታላላቆች የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው መጥተው በየማዕርጋቸው ከተቀመጡ በኋላ ከሳምንቱ የሚበልጥ በያይነቱ መጠጥ እጅግ ከሚጣፍጥና ደስ ከሚያሰኝ(ሚዜ) ለመጠጡ የሚስማማ ምግብ በያይነቱ ቀረበና(ግራማፎን)ሙዚቃው ባንድ ፊት፥አዝማሪዎች ባንድ ፊት እጅግ ደስ የሚያሰኝ ጨዋታ ሲጫወቱ ቆይተው ስድስት ሰዓት ተኩል ሲሆን ሻምፓኝ ቀረበና ከዚህ ቀጥሎ ያለው የክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ዲስኩር ተነበበ ።

ብፁዕ አባታችን፥ ክቡር የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል።

ክቡራን ወይዛዝርና መኳንንት ከሁሉ በፊት አስቀድሜ የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ልደትዎ ስለሆነ በዓሉን ስናከብር የደስታችን ተካፋይ ለመሆን ስለመጣችሁ ከፍ ባሉ መንግሥቴና በኔም በራሴ ስም ሆኜ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባላችኋለሁ ።

ክቡራን ሆይ፥ እንደምታውቁት ሰው ከጨለማ ወደ ብርሃን ከለመኖር ወደ መኖር የወጣበት ስለሆነ የተወለደበትን የልደቱን ቀን በየመቱ ሊያከብረውና ሊያስበው የሚገባው ነው። እኛም ይኸን የዛሬውን ታላቅ የሆነ በዓል የምናከብረው የዛሬ ዓርባ አንድ ዘመን በዚህ በዛሬው ቀን የሀገራችን ነፃነት መዳበሯ፥ለኛ ለመኳንንቱ መከበሯና መታፈሯ፥ ለወጣቶች በውቀት መጠንከሯ የሆነ አብነት ስላገኘንበት ነው እንጂ እላይ እንደተናገርኩት ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከለመኖር ወደመኖር የመጡበት ቀን ነው ብለን ብቻ አይደለም ። ስለዚህ ልባችን በዚህ ሁሉ ደስታ ተፍና ስለሚያነቃቃንና ስለሚገፋፋን በየመቱ ይህን በዓል ስናከብር ደስታችን ከልክ ያለፈ ነው።

ክቡራን ሆይ እላይ እንደተናገርኩት ሰው ከጨለማ ወደ ብርሃን ከለመኖር ወደ መኖር የወጣበትን ቀን ሲያከብረው እኛ ከዚህ ዘርዝሬ እንደተናገርኩት ብዙውን ነገር ባንድነት ያገኘንበትን ቀን ለማክበር ደስታችን እንደምን እጽፍ ድርብ ይመስላችኋል ይህን ደስታችንን ለማስረዳ በቂ ቃል አላገኘም እንጂ ቢቻለኝ ገልጬ ላስረዳችሁ ደስ ይለኝ ነበር ።

ክቡራን ሆይ እኒህ ቸር ጠባቂ የሕሙማንና የድሆች ረዳት የወጣቶች አባት ለኛ ለመኳንንቱ የጉልበታችን ብርታት የጌቶች ጌታ የመሳፍንት ንጉሥ የሆኑ ጌታችን ለኛና ለኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸው ስጦታችን እንደሆኑ ብዙ ማስረጃ አገኛለሁ ይኸውም መጀመሪያ ገና በሕፃንነታቸው የደጉ አባታቸውን የልዑል ራስ መኰንን ግዛት የነበረውን ሐረርን ይገዙ በነበሩ ጊዜ በጀልባ ነፋስ ለመቀበል በዓረምያ ባሕር ገብተው በድንገት ጀልባው ተነድሎ ብዙ ሰዎች በባሕሩ ሲሰጥሙ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን መድኃኒት አያጠፋምና በሚያስደንቅ ታምራት ከባሕሩ አወጣቸው ከዚያም ወዲህ ከብዙ መከራ የጠበቃቸውና ያዳናቸው ታሪኩ ብዙ ነው ። ጊዜ ይወስድብኛል እንጂ ሁሉንም በዝርዝር ለመናገር ደስ ይለኝ ነበር ይኸነኑም የተናገርሁት የመጀመሪያውን ነው እንጂ ከዚያ ወዲህ ለወራሲ መንግሥት ከታጩበት ቀን አንሥቶ እስከ ንጉሠ ነገሥትነታቸው እስከሁን ድረስ በየጊዜው ልዑል እምላክ ከስንት ክልዩ ልዩ መከራ ያዳናቸውን እርሳቸውም በእግዚአብሔር ረዳትነት ለኢትዮጵያና ለሕዝቡዋም የሠሩትን ወሮታ ቆጥሮና ዘርዝሮ ለመናገር የሚችል አንደበት ይገኝ አይመስለኝም ስለዚህ እኒህን ታላቅ መድኃኒታችንን ያገኘንበትን ቀን በደስታ ብናከብር የሚያስደንቅ አይደለም ክቡራን ሆይ አሁን የሁላችንም ምኞት እኒህ አስተዋዩ ንጉሠ ነገሥታችን ዕድሜያቸው እንዲረዝም መንግሥታቸው እንዲሰፋ ጠላታቸው እንዲጠፋ ነውና ስለዚህ እኔም ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከተወለዱ እስከ ዛሬ ድረስ ከልዩ ልዩ መከራ ያዳናቸውና የጠበቃቸው ልዑል እምላክ እንዲሁም ወደፊት በየጊዜው እንዲጠብቃቸውና እንዳይለያቸው ዕድሜያቸው እንዲረዝም መንግሥታቸው ከልጅ ልጃቸው እንዳያልፍ እየተመኘሁና ለዕድለኛይቱ ለግርማዊት እቴጌ መነንና ለልዑል አልጋ ወራሻችን ለልዑላን መሳፍንቶች ሁሉ ዕድሜና ጤና እየለመንሁ ስለ ኢትዮጵያ ሰላምነት ስለ ሁላችሁ ጤንነት ጽዋዩን እነሣለሁ ኢትዮጵያ በነፃነት ለዘለዓለም ትኑር ብለው ሲጨርሱ ፫ ጊዜ ተጨበጨበ ቀጥሎ የገነት ከተማ የንጉሠ ነገሥት መንግሥት ተማሪቤት ዲሬክተር ልጅ ንጋቱ ሣህሌ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገረና ሕዝቡን ደስ አሰኝ ።

ክቡር የክቡራን ክቡር ጌታዩ ራስ ሙሉጌታ

ክቡር ሆይ

ዕድለኛይቱ የዛሬ ቀን የኢትዮጵያ ብርሃን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የተወለዱበት ለምለሚቱም ሀገራችን ኢትዮጵያ የተመኘችውን እውቀት ያገኘችበት ቀን ስለሆነ እነሆ ከታላቅ እስከ ታናሽ በዓል አድርጎ የብርሃን ንጉሡን መታሰቢያ ለዘለዓለም አዲስ አድርጎ የማያከብርና በዚህ ቀን ለኢትዮጵያ ብርሃን እንደተገኘላት የማያውቅና ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና የማያቀርብ የለም ።

ክቡር ሆይ ።

ከዓለም መንግሥታት አንደኛዋ ራስዋን የቻለች ነፃነቷን ያጸናች ሀገራችን ለምለሟ ኢትዮጵያ ከዚህ አስቀድሞ ንግርዋን ስትጠብቅ እስከ ዛሬ ድረስ እጆዋን ዘርግታ ወደ ፈጣሪዋ ልመናዋን ስታደርስ ሳለች እነሆ በዛሬ ቀን ግርማዊ ባለ ግርማ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ከጠላቶችዋ እንድትታፈር ነፃነቷ በፍጹም እንዲጠበቅላት ልጆቿ እውቀትን እንዲያገኙላት አስበና አደላድሎ ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ከሰጣት ቀን አንሥቶ ኢትዮጵያ ያለ አንድ መሰናክል እርምጃዋን አሳምራለች ።

ክቡር ሆይ ።

ለምለሟ ሀገራችን ኢትዮጵያ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጠባቂና መታፈሪያ ከሆኑበት ቀን እንስቶ ከደስታዋና ካገኘችው ብርሃን ብዛት ያለልክ ዳብራ ፍሬዋ ለሚያየው ሰው በጣም ደስ የሚያሰኝ ሆኑዋል ይኸውም ባለፈው ሳምንት እንዳከበርነው በዓል ያለ ታላላቅ የሥልጣኔ እርምጃ ያገኘችው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜያት ስለሆነ የብርሃን ንጉሡን ሥራ ከታላቅ እስከ ታናሽ የዘለዓለም መታሰቢያ አድርጎ በልቡ የማያኖራት ሰው አይገኝም ለማለት እደፍራለሁ ።

ክቡር ሆይ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የተወለዱበትን ቀን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከትልቁ ድንቁርና የዳነበት ወጣቶች እውቀትን ያገኙበት ከጨለማ ወደብርሃን የደረሱበት ቀን ስለሆነ ይህ የዛሬ ቀን የተባረከና የተቀደሰ ይሁን።

ክቡር ሆይ

ምንጊዜም ቢሆን ለመንግሥትዎ ታዛዥና አገርዎን ኢትዮጵያን በመውደድዎ እነሆ የዕድልዎ ብዛት በማናቸውም ጊዜ ሰላምንና ደስታን ለሕዝብዎ ክብርን ለመንግሥትዎ የሚሆን ሥራ ስላጋጠመዎት ስምዎ የገነነ ሥራዎ የደመቀና የደከሙበት ሥራ ሳይጐድልብዎ እየተስፋፋ ሒዷል ይኸንንም የዛሬን ቀን በማክበርዎ እውነተኛ የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ፍቅር በልብዎ እንደተቀረጸ ያስረዳል ።

ክቡር የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ዘወትር ከደስታችን ሳይለዩ ደስታችንን ተካፋይ በመሆንዎ እዚህ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ደስታው ከልክ ያለፈ ሆኑዋል እንዲሁም ጤንነትዎን ሰጥቶዎት ከኛ ሳይለዩ ንጉሣችን የተወለዱበትን መታሰቢያ ቀን በያመቱ እንድናከብር እመኝልዎታለሁ ዕድሜ ለቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴና ለግርማዊት እቴጌ መነን ኢትዮጵያ በነፃነት ለዘለዓለም ትኑር ከዚህ በኋላ ሰባት ሰዓት ተሩብ ሲሆን የውጭ አገር ሰዎች ክቡር ራስ ሙሉጌታን እየተሰናበቱ ሔዱ ወዲያው ክቡር ራስ ሙሉጌታ ለብፁዕ አባታችን ለአቡነ ሚካኤል ለምሳ መጋበዣ የተለየ ክፍል አደራጅተው ነበርና ብፁዕ አባታችንን በተሰናዳላቸው ስፍራ አስገብተው እሳቸውም በልፍኝ አዳራሽ ተቀምጠው ሕዝቡንና መኳንንቱን እስከ ፲፩ ሰዓት ድረስ ደስ የሚያሰኝ ግብር አድርገውለት ዋሉ የግብሩን አኳኋን በዝርዝሩ ለማስረዳት ቃል ይበዛብኛል እንጂ እንደምን ደስ ባሰኝ ነበር ። በዚሁም በሁለቱ ቀን የየመኳንንቱን ሁሉ ደስታ ዘርዝሮ ለማስረዳት የሚቻል አይደለም ብፁዕ ብእሲ ዘኢሖረ በምክረ ረሲዓን እንዳለው ክቡር ዳዊት የክፉዎችን ሐሳብ ሳይከተል በጎ ሥራን ተከትሎ የጌታውን ክብ

ሩና ፍቅር በሰው ፊት ከፍ ከፍ የሚያደረጋና የሚገልጽ ምስጉን ነው ምስጋና ይገባዋል ክቡር ራስ ሙሉጌታ ኢሉብበር ከመጡ ጀምሮ የንጉሠ ነገሥታቸውን ክብር በሰው ፊት ለመግለጽ ያለመዘንጋት ጥንቃቄአቸውን ለድኃም ማዘናቸውን ፍርድ ማደላደላቸውን ለሥራ ትጋታቸውን ሰላየንና ክብርት ባላቤታቸውም ወይዘሮ በለጥሻቸው የንጉሠ ነገሥቱ በዓል በሚሆንበት ጊዜ ለሚደረገው ግብዣ ተጨንቀው ተጠበው በማዘጋጀታቸው ሁለቱም የሀገራቸውና የንጉሠ ነገሥታቸው የፀና ፍቅር እንዳለባቸው ያልተረዳው የለም ስለዚህ ክቡር ራስ ሙሉ ጌታንና ክብርት ወይዘሮ በለጥሻቸውን ለበጎ ሥራቸው የሚገባቸውን ምስጋና እያቀረብን ለደጉ ንጉሠ ነገሥታችን ለቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ረጅም ዕድሜ ለሀገራችን ልምላሜ እንመኛለን ።

ፍቅሬ ሕይወት ተክለ አብ ።

መልስ ።

አገሩንና እውነትን የሚፈልግ ሰው በራሱ ፍቅር ምክንያት ሰውን በምሉ አያመሰግንም እንዲሁም በምሉ አይነቅፍም ። በሚነቀፍበት ስፍራ መንቀፍ በሚመሰገንበትም ማመስገን ይገባል ። የተጻፈውን ነገር ሁሉ ባነበብን ጊዜ መቀበልና መንቀፍ በሕይወታችን ውሥጥ ዘወትር ሲፈራረቅ ይኖራል በብርሃንና ሰላም በ፴፱ኛው ቁጥር የተጻፈውን አይቼ የሚከተለውን ቃል ለመጻፍ እነሳሳኝ ።

መጀመሪያ እውነት ነው በኤውሮጳና በአሜሪካ ያሉ ሀብታሞች ገንዘባቸው ሥራ ፈትቶ ሊቀመጥ ፈቃዳቸው አይደለም ገንዘብ የሚያተርፈውን ነገር ያውቁታልና ከተቻለስ ወዲህና ወዲያ እያለ ትርፉን ይዞ እንዲመለስ ይወዳሉ። ገንዘብ ያለ ትርፍ ሲኖር ዋና ነገር አይደለም ። ትርፍ የሚሰጥበትንም መንገድ አይተው ይመራርጣሉ ።

ለምሳሌ አሁን ባገራችን መሬት ለውጭ ሰዎች ክልክል ነው ። ዱሮ ከያዙ የውጭ ሰዎች ግን ማናቸውም የውጭ የሆነ ሰው ሁሉ ከነሱ ለመግዛት ሲቻለው መሬት የሚያተርፈውንና ንግድ የሚያተርፈውን አመዘገዝኖ መሬት መግዛትትቶ ገንዘቡን በልዩ ልዩ የንግድ ሥራ ሲያስቀምጠው እናያለን ። የኛ ሕዝብ ግን ቢያተርፈውም ባያተርፈውም ልቡ ብመሬት ፍቅር ብቻ የታሠረ ነው ።

ባገራችን ያለው ጥሬ ብር ባገራችን ውስጥ ባይረክስ በኤውሮጳ ቢረክስ እኛን የሚጎዳን በየትኛው መንገድ ቢረክስ ነው? እርስ በርሳችን በሚሆን መርከስና መወደድ ለያንዳንዳችን ለልዩ ልዩ ሰዎች ይሆናል እንጂ ጉንዲያው በጠቅላላው ላገር ሁሉ አይደለም። አገሩን ሁሉ የሚጎዳ ገንዘባችን በኤውሮጳ ቢረክስ ነው ። እኛ ለኤውሮጳና ላሜሪካ ስንከፍል ጉዳት ይሆንብናል ። ከሶስት ዓመት ወዲህ እንኳ ከኤውሮጳ ወደኛ ገቢ በሆነው ነገር ሁሉ ከመቶ ሰባ አምስት ያህል ጨምሮ መክፈል ሁኖብናል የምንከፍለው ማለትም ዕቃ የምንገዛበት ነው ።

ለምሳሌ ከሶስት ዓመት በፊት አንድ ጆንያ ሱካር በሀያ ስድስት ብር ገዝቼ ነበር ዛሬ ግን ፵፯ ብር ያህል ነው ከፈረንሳይ አገር በመጣው ባንድ ካታሎግ ጫማ እንዲሁም ሌላ ዕቃ ነበር ። ላንድ ጫማ ሰማንያ አንድ ፍራንክ ተጽፎበት የፍራንክ ምንዛሬም ባንድ ብር ፲፪ መሆኑን አይቼ ባመጣ ፯ ብር ከ፴ ፍራንክ ሆነ።አሁን ግን ሰማንያ አንድ ፍራንክ በምስት ፍራንክ ላንድ ብር ቢታሰብ ዓሥራ ስድስት ብር ካንድ ፍራንክ ሆነና ለጊዜው ብር ይወደድልኝና ኪሣራው ያነሶልኛል ስል ጎቼዋለሁ ሳይወደድ የቀረ እንደሆነ ግን መግዛቴና መክሰሬ አይቀርም በማናቸውም ነገር ሁሉ በሊሬ።በጀኔ በዶላር እንዲሁ ነው ። ማመዛዘንም ከውጭ ጋራ ነው እንጂ በገር ውሥጥ እርስ በርሳችን በሚሆን ዓይነተኛ ነገር አይደለም ።

የወርቅ ሙስትና የሌለሙ ገንዘብ እንዲረክስ እርግጥ ነው ። ብሩር በዓለም ሁሉ አለ ። ልዩ ልዩ የወርቅ ገንዘብ ያላቸው መንግሥታት እንዲሁም የብርና ክብርም ያነሰ ገንዘብ አላቸው የነሱም ብር ዋጋው የብራችንን ያህል አልረከስም ።

ለምሳሌ የብር ሩብያ አለ አንድ ሩብያ ከ፲፭ ግራም አይበልጥም አንድ የኛ ብርም ከ፳፰ ግራም አያንስም። ስለዚህም አንድ መቶ ብር ፳፭ ሩብያ ብቻ ሲሆን እናያለን ፴፪ ቤሳም በሚዛን ዋጋ ብርን አያህሉም ። የብር ውስትና ስላላቸው ልክ ስለ ብር ሁነው ያገበያያሉ ። የ፲ ብር የ፶ ብር የማናቸውም ቁጥር ምልክት ያለው ባንክ ኖት ብርን ያህል እባንክ ቁጭ ብሎ እኔ አለሁ የሚል ዋስ ስላለው ከቁጥር ሳይጎድል ይኖራል ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም ይህነን ሁሉ አይተው ነው በብዙ ገንዘብ ባንኩን የገዙት ሁሉም ሲረክስ ከበላይ ሁኖ የሚኖር የወርቅ ገንዘብ በንጉሠ ነገሥታችን መልክ ሳይሠራ የቄየበት ምክንያት ይኖረዋል እንጂ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በብርቱ እንዳሰቡልን ባንኩን መግዛታቸው ያስረዳናል ።

ባገራችን በኢትዮጵያ በ፳፫ ሚሊዮን ሕዝብ መካከል (እስፔሲያል) የሆኑ ሰዎች ከመቶ ስንት ቫለን ለመቁጠር እንችላለን?ያልተማርሁ ሰው ነኝ ብሎ መልከሙን ምክር መተው አይገባም ። እውነት ነው ምክር ከሥራ ጋራ ሲሆን እጅግ መልክም ነው ። መሥራት ባይቻልም መምከርን አለመተው ይሻል ይመስለኛል ።

ሌሎች አገሮች ለማናቸውም ሥራ ሁሉ ፋብሪካ ስላላቸው ፋብሪካው በዝቶ ከሰሩ፥ እኛም ለኛ የሚበቃ ፋብሪካ ስለሌለን ከሰርን ። ላንዲት ሴት ሁለት ልጆች ነበሩዋት ይባላል ። አንደኛው ሲዋኝ ወኃ አብዝቶ ጠጥቶ ሞተ ። ሁለተኛው ደግሞ በወኃ ጥም ሞተና ሴትዩዋ ሁለቱ ልጆቼ አንዱ ወኃ አብዝቶ ጠጥቶ ሁለተኛው ደግሞ በውኃ ጥም ሞቱብኝ አለች ይባላል ። እንደኔ ሐሳብስ ፋብሪካ አብዝተን አሁን በአሜሪካ እንዳለ እኛም ብንሆን ይሻል ይመስለኛል ።

ከብት አርብተን እህል አብዝተንም ወደ ውጭ መሸጥና ሀብትን ማከማቸት ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላ ያወጡት ማስታወቂያ ብቻ አይደለም ። እረ ገና አልጋ ወራሽ ሳሉ ሕዝባቸው እንዲበለጥግ ወደውጭ አውጥቶ እንዲሸጥና ከሚገዛው ይልቅ የሚሸጠው በዝቶ በገንዘብ እንዲከብር ማሰባቸውና መጣራቸውን አስተዋይ የሆኑ ሁሉ ያውቁላቸዋል ።

ስለ እህል መወደድ እውነት ነው ፩ብር የነበረው ፫ብር ሁኑዋል ፫ የሆነም ለከተማና ለባቡር የቀረበ አገር ብቻ ነው ለሁሉ እንዲሆንና ትርፍንም አብረው እንዲካፈሉ ዓይነተኛው አጋጣሚ ባቡር ቢኖር ነው ። ባቡሩም ካዲስ አበባ ተነስቶ ባሌ ድረስ። አሲዳሞ ዳርቻ ድረስ፡ጅማ ድረሰ ነቀምቴ ድረስ ጐጃምና በጌምድር ጫፍ ድረስ፤ ላስታና እንደርታ ድረስ ቢሆን ለንግድ ብቻ አይደለም ለሌላም ለብዙ ነገር የሚረዳ ይመስላል ። ባቡር መሥራትም በዓለም ሁሉ የመንግሥት ብቻ አይደለም ። ልዩ ልዩ ሀብት ያላቸው ያገሩ ልጆች ኩምፓኚ እየሆኑ ያሠሩታል እንጂ እንዲሁም የአገራችን ልጆች ኩምፓኚ እየሆኑ ቢያሰሩ ገንዘባቸው አሁን ይዘውት ካለ ንግድ ይልቅ የሚበልጥና መሰረት ያለው ጥቅም ምስጋናና ለዘላለም ከማይረሳ መታሰቢያ ጋራ ለራሳቸውና ለሚያከብሩቸው ለተወደደ ሕዝባቸው የማያልቅ በረከት ሰጥቶ ይመለስላቸው ነበር ። ደግሞ አገርን መርዳት በጦርነት ብቻ አይደለም ። እንደዚህ በመሰለ ነገር ሁሉ እንጂ ። አገር ቢከብር የተከበሩ ሰዎች ደግሞ እጅግ እንዲከብሩ አንርሳ ።

አሮጌ ኑሮ ሲታደስ የቤት ወጭ እንዲበዛና ሰው ሁሉም በማስተዋል ከሆነ አብዝቶ ሲያወጣ አብዝቶ ለማግኘት እንዲጣጣርም እርግጥ ነው።አብዝቶ ማውጣትም የሥልጣኔ ምልክት ነው ወጭው ግን ለሸምፓኝ ። ለውስኪ ። ለካራምቦላ እንዲሁም ለመሰለ ነገር ቢሆን ከጉዳት ሌላ ትርፍ የለውም።ገንዘብ የሰዎችን ጉልበት ወይም እውቀት መለኪያ ነውና እንደዚህ ከሆነ በጥቂት ደቂቃ ኃይል ለማይሰጥ ሕይወትንም ለማያበረታ ነገር የብዙ ሰዎች ጉልበት መለወጥ ማለት ነው

ሰው በመጀመርያ ቅጠል እንደ ለበሰና በዋሻም እንደ ኖረ እናስባለን ከዚያም በኋላ በቅጠላ ቅጠል በተሠራ ዳስ በኋላም በሣርና በገለባ መሳይም በተዘጋጀ ጐጆ ዕውቀቱ ከበዛ መጠን ግን ወጭ አብዝቶ ልዩ ልዩ ወደ ሆኑ አዳራሾች ተሻገረ

ክፍለ እግዚእ ደሳደን

መልስ ።

በስምንተኛው ዓመት ቊጥር ፴፫ በገጽ ፪፻፶፯ ነሐሴ ፯ ቀን በተጻፈው ብርሃንና ሰላም ሳይረዳ አስረጅ ሳያውቅ ፈራጅ ለሆነውና ፊት ዳባ ኋላ ካባ ለለበሰው ተማሪ መልስ ስጽፍ የጥበብ ምንጭ ለሆናችሁ ሊቃውንትና ወደ ትልቅ ማዕርግ የሚያደርሰውን ዕውቀት ተምራችሁ አገራችሁን ለመርዳት ወደ ፊት ለምትፋጠኑ ወንድሞቼ ለሆናችሁ ተማሮች ። ይህ ሳይማር ተማርሁ ሳያውቅ አወቅሁ ብሎ የሊቃውንትን ልብስና ማዕርግ ወስዶ ፊት ዳባ ኋላ ካባ ለባሽ ያለውንና እንድነታችንን ለመለየት የሚጣጣረውን ጥራዝ ነጠቅ ተማሪ ለማግኘት እንደሆነ የምፈልገው እንደርሱ ትስቱታላችሁ ብዬ ሳልጠራጠር ብሩህ የሆነ ልቦናችሁ በቅንነት እንዲመለከትልኝ እሳስባችኋለሁ ። ፊት ደባ ኋላ ካባ ለባሽ ተማሪ ሆይ ምንም እንኳ ባታስተውለው ስድብ ሳይሆን ምክር መሆኑን ትንሽ እንድትሰማኝ መርማሪው ዕውቀትህም እንዲያስተውልልኝ እስታውቅሃለሁ ። ከመጠምጠም መማር ይቅደም የተባለውን ምሳሌ አታውቅምን ? ዳባ ለብሰህ የተማርኸው በየት አገር ደሆን ? እንዴትስ እንኳን ልትማር ሲማሩም የሰማህ አትመስለኝም ። የተማርክበትን አገር የማታውቅ ስትሆን ሰውን ለመስደብ ማን አስተማረህ ? ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የስድብ አስተማሪ እንዳልነበረ የታወቀ ነው ። ባለማወቅህ አይፈረድብህም ነበር ። ነገር ግን አውቃለሁ መስሎህ ወንድና ሴት ሳትለይ ሰባራ ግጥምህን ይዘህ በብርሃንና ሰላም ተራራ ወጥተህ መጮህህ እጅግ ያሳዝናል ። በተለየ ዕውቀትህ የጮሀሃቸውን በዝርዝር ካንድ ታናሽ ብላቴና እንድትረዳቸው በሚከተሉት መስመሮች ጥያቄዎቼን አጽፍልሃለሁ ።

፩ኛ፡በጎ ሰው የተገለ ማነው ? ፪ኛ፥ አትጠገብ የተባለች ማን ናት ፫ኛ ፤ አንተ ጠባቃ የሆንህለትና የምታመልከው ሆድ አምላኩ ማን ነው።ነገር ግን የመጀመርያውን ከሚያውቅ ልጅ ተጭነኸዋል። እርሱም ሕዋሳት በተፈጥሮ በየወገናቸው አንድ ይነት ስለሆኑ ብለህ አንድነታችንን ስላወቅህ ነው ። ይሁን እንጂ ልጁ ስለ ሕዋሳት ቢጭንህ አንተ ማስረጃ ቀርቦታን ደረብህበት ምን ያለኸው ሸክም ወዳጅ ነህ የውቀትህ ብዛት በሁለቱ አርእስቶችህ ይታወቃል።

በጎ ሰው ተብሎ ለማኝ መጥላት ምእመን መስሎ የእመ አምላክን ስም መዘባበቻ ማድረግ ተማሪ ለነበረ ሰው እጅግ ያሳዝናል ላልኸው ለምን ተዘከረው ብሎ የእመአምላክን ስም መዘባበቻ አደረገው ብለህ ታዝናለህ ይልቅስ ተቀብሎ የሚሰርቅ አንተ የነገር አባት የሆንህለት ሆድ አምላኩ እንደሆነ የእመ አምላክን ስም ያረከሰው ካንተ በቀር የማያውቀው የለም ። አትጠገብ ማን መሆንዋን ሳታውቅ አህያ ካልሃት አንተም የርሷን ወተት ጠጭ ውርንጫ መሆንህን አገልጽልሃለሁ ። ዳሩ ግን ስምህን እስክትገልጽልኝና ሞልቼ እስክሞግስህ ድረስ ምንም ላንተ በይሰማማህ ለጊዜው በግጥምህ ግጥም በቅኔህ ቅኔ ጽፌ አቀርብልሃለሁ ።

ብልህ ቅኔ አዋቂ የሆድ አምላኩ አባት ። አንተም ትሞት ይሆን ይዘህ ይህን እውቀት ። ነውርስ አልነበረም ዚማ ማንጐራጐር። አንተ ጣልኸው እንጂ አድርገህ ስብርብር። እንዴት ያለ ሰው ነው ምንም የማይሰማ ። እናቱን በእስለት አስመስሎ እሚያማ ። ከራሱ የሞላ ሞኝነት ሳያንሰው አውጥቶ ይሰጣል የራሱን ስም ለሰው ። ሰምንና ወርቅን ለይቶ የማያውቅ ። ቅኔ ሊጽፍ ገባ በጣሙን ሊራቀቅ። ወርቁንም ለማግኘት ያን ያህል ተጉዞ ። እንዲያው ፈዞ ቀረ ሰሙን ብቻ ይዞ ። ይኸ የማያፍር አዋቂ እኔ ነኝ ባይ። እንደ ትንሽ ሕፃን እህል ከፈር ሳይለይ።የነገሬን ወርቁን አንተ መች አየኸው።በሰም ባሕር ገብተህ ጠልቀህ የቀረኸው ።

ሥላሴ ።

ለጥበበ አብ ወልደ ባሕርይ፤ እመ ነገረ ከርሥ ኢያዕዓቆ
እምግብርናተ ከርሥ አዓዓዘ ባሕርየ ሥጋሁ ዳዕሙ ።
መርዓዌ ውላጤ ዘተረስዓ ስሙ ።
ዘይሜኒ ወይነ ጠይቆ አስተደኃረ እምዓቅሙ ።
ወእለ ከርሦሙ አምላኮሙ ።
ለሕርትምና ይከውን ደኃሪቶሙ ።
ይቤለነ ጳውሎስ ቀዲሙ ።

ዘይእዜ ።

ረሲዕ ረስየ ሀገሪተከ ለእንተ ምሳሌ ጥበብ ፍቅርተ ንጋሢ አእምሮ ፡

እስመ ተፀዲዎ ቃለ ጳውሊ፤ ለብርሃን ዘምስለ ጽልመት ልብከ ደመሮ ።

ወማእከለ እሳት ወማይ ኢትኅልፍ በተድኅሮ ።
ንውም እንተ በጊዜ ፈከሮ ፡
ወንቁሐ ልሳን ወአፍ በዘዘለፉ ዘምሮ ።
ንውም እንተ በጊዜ ፈከሮ ።

መወድስ ፡

ዓፀደ ፍሬ ኢይኩን በዓተ ሰረቅት
መሠረተ ፍትሕ ቆመ በገነተ ተድላ ሠናይት ሥን ።
ንግኤ ፍሬ ወይን ይሰደድ አፍአ መከን ።
ወበዓፀደ ወይን ዘናቡቴ ፤
በዘበአ እንበለ ድልወቱ አክአብ መስፍን ።
ኤልያስ ቴስብያዊ ፤
በደሙ እንስት ከመ ይትሐፀብ ይኄንን ።
ዓይንኒ ከመ ትሬኢ ወከመ ትስምዕ እዝን።
ክፍለ ቄናጽል ለይኩኑ በዓውደ ዳዊት ወሰሎሞን ።
ዘበዓለ ቤት ኄር አዕፃዳተ ወይን ።
እለ ያማስኑ በአኀብሮ አርድእተ ኢሰሚዕ ንዑሳን ።

የኡትጠገብ ልጅ የሀድ አምላኩ ተቃዋሚ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም በለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፺ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቆሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወከሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በክዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፈቃዳቸው ሕገ መንግሥት ስለማቆማቸው የገንዘብ ሚኒስቴር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት በ፲፱፻፳፬ ዓ ም ለመሰፍንቱና ለመኳንንቱ የተናገሩት የስብከት ቃል በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታትሞ በዕሩብ መሸጡን እናስታውቃለን ።



ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዳች ቀጥሎም እንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን ብቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሴና ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፴፭
8me ANNE. № 35

ሐሙስ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም
Jeudi 25 AOUT 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጣቱ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሚአሳዝን ሞት ።

ጃንጥራር ገብረ እግዚአብሔር የግርማዊት እቴጌ መነን ልጅ ገና ወጣት ልጅ መልከ ቀና ። ሰው ወዳጅ ጠባየ መልካም ነበሩ ። አምባሰልን የእያታቸውን አገር ተሹመው ጥቂት ጊዜ በደስታ ቈይተው በድንገተኛ ሕማም ታመው ሐኪም ወደ አለበት ወደደሴ መጥተው በደሴ ሆስፒታል በሐምሌ ፳፰ቀን ሙተው አሽከሮቻቸውና ዘመድ ወዳጆቻቸው ከደሴ ወደ ግሸን ወስደው በአያቶቻቸው መቃብር ቀበሩዋቸው። እናታቸው ግርማዊት እቴጌም በፍልሰታ ጾም ምክንያት ከብዙ ሰው ተከልክለው በላይኛው ግቢ አጠገብ ባለው በማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ጸሎት ይዘው ሰንብተው ነበርና ይህ የፍልሰታ ጾም ሲፈጸም በነሐሴ ፲፯ቀን ተረድተው ታላቅ ኀዘን ተደርጎ ዋለ።ዕድሜአቸውም ገና ፳፫ ዓመት ነበረ ።

ደግሞ የአቶ አየለወርቅ ልጅ የልዑል ራስ መኰንን የእኅታቸው ልጅ የፊታውራሪ አሸናፊ ባለቤት ወይዘሮ አሳመነች አየለወርቅ ባለቤታቸው ፊታውራሪ አሸናፊ በረናን ተሹመው ሲሔዱ እሳቸውንም ይዘዋቸው ሒደው ፊታውራሪ አሸናፊ ድንገት በሚአስቸኵል ጉዳይ ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው ስለመጡ ባለቤቲቱን ወይዘሮ አሳመነችን እዚያው በተሾሙበት አገር በረና ጥለዋቸው መጥተው ነበርና በድንገተኛ ሕማም ታመው በሰኔ ፩ቀን ሙተው በዚያው በረና ባለው ቤተክርስቲያን ተቀብረው በዚሁ በነሐሴ ፲፯ቀን ለጃንሆይና ለባለቤታቸው ለፊታውራሪ አሸናፊ፥ ለልጃቸው ለልጅ ልብሰ ወርቅና ለወንድሞቻቸው ለፊታውራሪ አበበ አየለወርቅና ለፊታውራሪ ማህሉ አየለወርቅ፥ለቀሩትም ዘመድ ወዳጆች ሁሉ አርድተዋቸው ታላቅ ልቅሶ ተደረገ። የመርዶውም አኳኋን እጅግ የሚያስደንቅ ነበረ።ጊዜ መድፍ ተተኰሰ።ነጋሪቱ ሲመታ የእምቢልታውና የመለከቱ ድምጽ ለከተማው ሰው ሁሉ መርዶውን ነገረ ዕድሜአቸውም ፵፩ ዓመት ነው ። የጃንጥራር ገብረ እግዚአብሔርና የወይዘሮ አሳመነች የሞት መርዶ በአንድ ጊዜ ስለሆነ የከተማው ሕዝብ ሁሉ እጅግ አዘነ አቡነ ሳዊሮስና ልዑላን መሳፍንት፥ ካህናትና ሊቃውንት፥ ወይዛዝርና ሠራዊት ተሰብስበው በላይኛው ግቢ ታላቅ ድንኳን ተተክሎ ፎቶግራፎቻቸውና መጣኛቸው ልብሳቸውና ጌጣቸው ተይዞ ሲለቀስ እንግዳ ነገር መሰለ።የልጅ ኀዘን በግርማዊት እቴጌ መነን ስለተመላለሰባቸው ሰው ሁሉ እጅግ አዝኖአል።ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴንና ግርማዊት እቴጌ መነንን፥ ፊታውራሪ አሸናፊንና ልጆቻቸውን የቀሩትንም ኀዘንተኞች ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል ።

ስለ አያና ብሩ ከትምህርት ቤት መመለስ ።

የግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዋናው አሳባቸው አገራቸውን ለማልማትና ሕዝባቸውን በጥበብ መንገድ ለመምራት ስለሆነ በትምህርታቸው ከፍ ያሉትን ልጆች እየመረጡ የጥበብ ሥራ እንዲማሩ ወደ አውሮፓ ሰደዱ።ወደ አውሮፓ ከሔዱትም ልጆች አንዱ አያና ብሩ ሦስት ዓመት በእስክንድርያ ቪክቶርያ ኮሌጅ ከተማረ በኋላ ወደ እንግሊዝ አገር አልፎ የመዓድን ሥራ ትምህርት በትጋት ይማር ነበርና ዘንድሮ በሰኔ ወር የመጨረሻ ፈተናውን ስላለፈ ለመዓድንና ለሰርቤይንግ የልዩ ልዩ መሐንድስነት ሥራ እውቀቱ ዲፕሎማና(የምስክር ወረቀት) ተቀብሎ በማክሰኞ ባቡር ነሐሴ ፲ቀን አዲስ አበባ ገባ ።

በዚሁም ቀን በባቡር ማቆሚያ መድረሱን በናፍቆት ይጠባበቁ የነበሩት ዘመዶቹ በደህና ስለመጣላቸው የደስታቸው ብዛት ከልክ ያለፈ ነበር ።

በማግሥቱም ረቡዕ ከጧቱ በ፬ሰዓት ተኩል ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተገናኘ ጊዜ የትምህርቱን አኳኋን ገልጾ እያመለከተ የትምህርቱን ፈተናዎች በማለፉ የተቀበለውን ዲፕሎማ ስለ አቀረበ ጃንሆይን እጅግ ደስ አሰኘ። ከዚህም በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ወሰን በሌው ቸርነትዎ የድሆችን ልጆች ሰብስበው ለትምህርት ስላበቁን ውለታዎን ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር እንደ ቅንነትዎ ይመልስልዎ እንጂ እኛ ልንመልስልዎ አንችልም።ስለሆነ ግን ኢትዮጵያን

በጽኑ መሠረት መሥርተው ወደ ከፍተኛው ደረጃ ለማድረስ ፍጹም ፈቃድዎ በመሆኑ ለሥልጣኔ ትምህርት ክበቡን ዘንድ ይህን ታላቁን ውለታዎን ከልባችን ሳናጠፋ መንገድዎን እየተከተልን እያንዳንዳችን በተቀበልነው ሾጦታ ለክብርት ሀገርዎና ለመንግሥትዎ በምናደርገው አገልግሎታችን የተለመደ እርዳታዎን እንደማያጓድሉብን ፍጹም እምነት አለን ብሎ ስለተናገረ ግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ውበትና ጥበብ በተመላው ቃል አውሮፓ ድረስ ሔዳችሁ እንድትማሩ ያደረጓንበት ዋናው አሳባችን ተምራችሁ ለሀገራችሁ እንድታገለግሉ ነውና በምትሠሩት ሥራ ሁሉ የሚያስፈልገውን እርዳታችንን አናጓድልባችሁም ብለው የሚያነቃቃ ቃላቸውን አሰምተው ታላቅ ተስፋ ሰጡት። አያና ብሩ በላይ ከአመለከትነው ትምህርቱ በቀር በየጊዜው ለአገሩ ጥቅም የሠራው የብልሃት ሥራ ሁሉ እጅግ ያስመሰግነዋል ። ወደፊትም እንደዚሁ ለአገሩ በሚያደርገው አገልግሎቱ መልካም ፍሬ እንዲያሳይ ተስፋ እናደርጋለን ።

የሆስፒታል መሠረት ምረቃ

የኢጣልያ ሚሲዮን ታላቅ ሆስፒታል ለመሥራት ኮለጅ መረች መሠረቱ በሚጀመርበት በነሐሴ ፯ ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተጠርተው ሒደው ነበር ከኢትዮጵያ ታላላቅ መኳንንትም ተጠርተው ጃንሆይን ተከትለው ከሔዱት ጥቂቶችን እንጽፋለን።የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፥ ልዑል ራስ ካሣ፥ ልዑል ራስ ሥዩም፥ ልዑል ራስ ጉግሣ፥ክቡር ራስ ደስታ፥ ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትር፥ ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው የአገር ግዛት ሚኒስትር፥ ክቡር አፈንጉሥ መኰንን የፍርድ ሚኒስትር፥ ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደመስቀል የጽሕፈት ሚኒስትር፥ ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅ የርሻ ሚኒስትር፥ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር፥ክቡር በጅሮንድ ተክለሐዋርያት የገንዘብ ሚኒስትር፥ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ የሥራ ሚኒስትር፥ክቡር ከንቲባ መኰንን የከተማ ዳኛ ናቸው። በላይኛው መስመር እንዳስታወቅነው ስማቸውን ያልጻፍነው ብዙ መኳንንት ነበሩ ።

በከተማ የሚኖሩትም የኢጣልያ ሰዎች ነበሩ የከበሩ የከንሰላታ ክህናትና ደናግል ነበሩ።በዚሁም በሆስፒታሉ መሠረት አጠገብ ታላቅ ድንኳን ተተክሎ ለጃንሆይና ለመሳፍንቱ ለመኳንንቱም መቀመጫ ጥሩ ጥሩ ወምበሮች ተዘጋጅተው ነበር። በምዕራብ ኢትዮጵያ ሁሉ የታወቁት ሙሴ ባርላሲና የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ጃንሆይ

በኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከአሁን በፊት ተሠርቶ ባለው ታላላቅ የሥራ ቤት ላይ እንደገና እየተሠራ የሚጨመረው የቤት ሥራ ሁሉ የዚህኑ የአዲሱን አበባ መልኩን እያሳመረና ብዛቱንም እያሳደገ የሚሔድ መሆኑን ያስረዳል ነገር ግን ታላላቅ ከተማ ሁሉ ስመ ጥሩ የሚሆነው የሰው ዘር ለሆነ ሁሉ ብዙ እርዳታ የሚሆንና በጎ ሥራ የሚሠራበት ብዙ ቤት ሲሠራበት ነው እንጂ የታላላቅ ቤተ መንግሥትና ታላላቅም ሐውልት ቆሞ በመታየቱ ብቻ አይደለም ስለዚህ የሕዝብን ችግር ለመጠገንና ለመፈወስ የሚሠራ ሥራ ሁሉ ለከተማው ታላቅነትና ለመንግሥቱ አዋቂነት ምስክር ይሆናል ።

ስለዚህ አንድ አዲስ የሕክምና ቤት ተሠርቶ ሲያልቅና ለሕመምተኞች ሲከፈት ደግሞ ሌላው ተከትሎ ቢሠራ ከልክ ያለፈ ሆነ ተብሎ አይታሰብም ። ይህንንም የግርማዊነትዎ ዓይኖች ሥራው ሲጀመር የሚያዩት የሕክምና ቤት የሚያሠራው የኢትዮጵያ ፍቅር በልባቸው አድሮ የነበሩ ፕሮፌሰር ሻፔሬሊ መሥራች ሆነው ሚሲዮኖችን ለመርዳት ያቆሙት የሕዝብ ማህበር ነው ። ለፕሮፌሰር ሻፔሬሊም በሌላው አገር ሁሉ እንዳደረጉት እርዳታ ለዚህም ለከበረ አገር እንዲያደርጉት ብዬ የዛሬ አሥር ዓመት አመልክቻቸው ነበርና ይህኑ የሕክምና ቤት ለማቆም በዚያኑ ጊዜ ፈቅደው ቁርጥ አደረጉ ። የዚህኑም የሕክምና ቤት ሥራ ለማስኬድ የዶክተር በራ ቅንነትና የሕክምናም ሰፊ እውቀት ያላቸው መሆናቸውን እኒሁ ፕሮፌሰር አውቀው በሳቸው ዲሬክተርነት ቢሠራ ፍሬው እንዲያምርና ታላቅ እንዲሆን ሲሉ ዲሬክተርነቱን ለዶክተር በራ ሰጡ ።

እኒሁ ፕሮፌሰር ሻፔሬሊ ከሞቱ አራት ዓመት አለፈ ነገር ግን ለዚህ ታላቅ በጎ ሥራ የቆመ ማኅበር መሥራች የሆኑ ፕሮፌሰር ሻፔሬሊ ሰፊ እውቀታቸውንና ታላቅ ለጋስነታቸውን እየደሰ ያስታውሰላቸዋል እንጂ ማኅበረተኝነታቸው ከሰው ልብ ለዘለዓለሙ አይጠፋም ። ይኸም የሕክምና ቤት የፕሮፌሰር ሻፔሬሊን መታሰቢያ ለዘወትር እየጠበቀ ለብዙ ሕመምተኞች ታላቅ ፈውስ ሁኖ ይኖራል። ግርማዊነትዎም ለዘወትር ላገሩ ደህንነት የሚመኙና የሚተጉ ወደ ልማትም የሚሔድበትን መንገድ ለማግኘት በጥንቃቄ የሚፈልግ ስለ ሆነ ይኸነን አዲስ በጎ ሥራ ለመርዳት አልበዘኑም ያለመበዘንዎም ምስክር ለዚሁ ለሕክምና ቤት የሚያስፈልገውን መሣሪያ ስናስመጣ ችግር እንዳያገኘን የግርማዊነትዎ ፈቃድዎ ሆኖ ያደረጉልን እርዳታ ነው ።

አሁንም ጃንሆይ ይኸነን ሥራ መጥተው በመገኘትዎ ስላደረጉልን ክብርና ማበረታታት እኛን ለመጠበቅ ከፍ ያለ ፈቃድዎ ለመሆኑ አዲስ ምስክር ሆኑልን አሁንም ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን ለግርማዊነትዎ እያቀረብን በብዙ ጥንቃቄና በመጨነቅ ለመጠበቅ ለሚተጉለት ሕዝብዎ ጥቅም እንዲሆን ይኸነን የቆመ በጎ ሥራ በምሉ ፈቃዳችን ጠብቀን ለመኖር እራሳችንን የሰጠን መሆናችንን በዚህ መሠረት እንገልጥልዎታለን።

ይህነን የተጀመረውን በጎ ሥራችንን ጨርሶ ቸርነቱንና ጸጋውን በግርማዊ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና በተወዳጁ ቤተ ዘመድም በገርዎም ሕዝብ ላይ እንደዚህ ያለውን ሥራ ሁሉ እየጨመረ እንዲሔድ ቸሩ አምላክ ፈቃዱን ይፈጽምልን እያልን እንመኛለን ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥትም እጅግ ደስ የሚያሰኝ መልስ መለሱ፥ ይህም የተመሠረተው ሆስፒታል ለሕዝባቸው እርዳታ ነውና በብዙ ምስጋና ደስታቸውን ገለጡ

ፕሮፌሰር ኤሜልዮ አስኪያፖሬሊ የኢጣልያን ሚስዮን ማህበር ዋና ሁነው ያቆሙት ይህን ሆስፒታል በአዲስአበባ ለማሥራት ስለአስጀመሩ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሁነው ምስጋናቸውን አቀረቡ ፕሮፌሶር ኤሜልዮ ስኪያፖሬሊ ዶክቶር ቦራን ለዚሁ ሆስፒታል ዲሬክተር ስለሾሙአቸው የሕዝቡን ጠባይ ያውቃሉና እንደቀድሞአቸው በፍቅርና በትሕትና ይቀበላሉ ማለትን ተስፋ አድርገው እጅግ ደስአላቸው። የሥራውንም መጨረሻ ለማየት ተመኙ። ከዲስኩሩም በኋላ ጃንሆይና የተጠሩትም መሳፍንትና መኳንንት የክፍሉን መሰረቶች ሁሉ አዩ የአልተረዱትንም ነገር ሁሉ ከመሐንዲሶች ቸርዮና በዮ እየጠየቁ ይረዱ ነበር። ከዚህም በኋላ መታሰቢያ ቃል ጋደተጻፈበት ድንጊያ ቀርበው የጃንሆይና የአልጋወራሽ የቤአ ኤቼለንሳ ባሮኒ ሰከልማከ የኢጣልያ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ የኢትዮጵያና የኢጣልያ መኳንንት ማኅተም በብራና ታትሞ ጃንሆይ ለመታሰቢያ የሰጡት የወርቅ ገንዘብ በብራና ተጠቅልሎ በጠርሙስ ገብቶ ጠርሙሱ በመልክም ተዘግቶ በመሰረቱ ውስጥ አግብተው በታላቅ ደንጊያ ገጠሙት ከዚህ በኋላ ጃንሆይ የብር መዶሻና የብር መንከ አንስተው በመዶሻው ደንጊያውን መትተው በመንከውም ስሚንቶውን አንስተው እንደ ነገሥታት ሕግ መሠረቱ። ከዚህ በኋላ ወደ ድንኳኑ ተመልሰው ሻምፓኝ ተጋበዙ ።

የሆስፒታሉ ጽላን

ሶስት ፎቅ አለው ስፋቱ ፪ሺ ፪መቶ ሄሜትር ከሬ ነው።የቤቱም ክፍሎች ፷፪ይሆናሉ ወደ ፎቁም መውጫ ሁለት በኤሌክትሪክ የሚሳቡ መኪናዎች አሉት ክፍሉን ሁሉ የኤሌክትሪክ ብርሃን ይሞሉታል። ደግሞ በሽተኞች የሚተኙበትን ክፍል ሁሉ የሚአሞቅ የኤሌክትሪክ መኪና ይደረግበታል ይህን የተሰጠውን ተስፋ ተፈጽሞ ለማየት እየተመኘ ይህን ሆስፒታል ለመሰረቱ ለታላቁ ሚሲዮን ብርሃንና ሰላም ምስጋናውን ያቀርባል።

የሞት ሞት ።

በባሌ አውራጃ ጊንር ከተማ ደስታ ጊርጊሶና ደሳለኝ ወርቁ የሚባሉ ወጣቶች ከነአሽከሮቻቸው ሆነው ቀን እመሸታ ቤት ሲጠጡ ውለው ነበርና ሐምሌ ፲ቀን ከምሽቱ በ፩ሰዓት ጀማነሽ ተሰማ የምትባል ሴት አዳሪ መሸታ ሻጭ ነበረችና ከዚቹ ከጀማነሽ ቤት ገብተው እንደ ገና መሸታ ገዝተው ሰውነታቸውን እስቲሰቱ ድረስ ሲጠጡ ቆይተው ነበርና ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ሲሆን ከቤቱ ላይ እሳት ተነሥቶ ሲነድ ጀማነሽ ተሰማ የምትባለው ሕሊናዋን አውቃ ሸሽታ ወጣች ደስታ ጊርጊሶና ደሳለኝ ወርቁ የሚባሉት ከነአሽከሮቻቸው መጠጥ ስለእገዛቸው እሳት መሆኑን ሳያውቁት እቤቱ ውስጥ አራቱም ተቃጠሉ ። ሲቃጠሉ ጩኸት ሰምቶ የከተማው ሰው ቢረዳ ደስታ ጊርጊሶና ደሳለኝ ወርቁ የሚባሉት የታጠቁት ድርብ ዝናር የረጅም ለበን ነበርና ስለጥይቱ ብዛት እሳት በነካው ጊዜ ተኩሱ ስለበዛ ሰው አላስቀርብ ብሎ በዚሁ ምክንያት ሶስት ቤት ተቃጠለ።ሐምሌ ፲፩ቀን ከንጋቱ ሁለት ሰዓት ሲሆንእሳቱ በበረደ ጊዜ ሥጋቸው እየተቆራረሰ ከየአመዱ ውስጥ ቢፈለግ ደስታ ጊርጊስ እሚባለው የጠጁን ማንቆርቆሪ ተንተርሶ ተገኘ አራቱም ሁሉ በአንድነት ተቃጥለው አጽማቸው ተለቅሞ በደብረ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ተቀበሩ።ሀገራቸውም ባሌ ጉለልቻ ከሚባል አገር ነበርና ይልቁንም ጊንር ያመጣጣቸው ምክንያት ሳይታወቅ ሐምሌ ፱ቀን መጥተው ሐምሌ ፲ቀን ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ተቃጥለው በመቅረታቸው እጅግ ያሰደንቃል።አባቶቼ ወንድሞቼ ሆይ ከመጠጥና ከሴት ደጅ ሰውነታችንን ብናስጠነቅቅ ሕይወታችን በከንቱ አያልፍም ነበርና ያለፈውን እያየን ለሚከተለው ለሰውነታችን ከመጠጥና ከሴት ደጅ እንድንታገሥለት በብርሃንና ሰላም አሳስባችኋለሁ። ጊንር ጉምሩክ ፍ[illegible] ጸሐፊ አበበ ተከሴ ዘብሔረ ደንገዚ ።

ስለ ወይዘሮ ወለተየስ ዕረፍት ።

ወይዘሮ ወለተየስ (ወለተኢየሱስ)በእናታቸው የኢትዮጵያ በአባታቸው የጀርመን ተወላጅ መልክና እውቀት የተሰጣቸው ነበሩ በአፄ ምኒልክ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ነበር። ለእቴጌ ጣይቱም እጅግ ባለሙዋል ሁነው ነበር ደህና ደህና ልጆችም ነበሯቸው ፩ልጃቸው ሙሴ ያዕቆብ የአዲስ አበባን ጉምሩክ ሥራ በደህና አድርገው የመሩ እሳቸው ነበሩ አሁንም በአዲስ አበባ ያሉት ሙሴ ዳዊት ሐልና ሴቶች ልጆቻቸው በታላቅ ሥራ ላይ ናቸው ወደ አዲስ አበባ ከመጡም ብዙ ጊዜ ሁናቸው ነበር። በዕድሚአቸውም ሸምግለው ሳሉ ነገር አያሳስቱም ነበር። መቼም የሰው መጨረሻው ይህ ነውና በነሐሴ ፲ቀን አርፈው እንደሮፓ ልማድ አድረው በማግሥቱ በነሐሴ ፲፩ቀን በብዙ ክብር መኳንንትና ወይዛዝር አልቅሰውላቸው ጉለሌ በሮፓውያን መቃብር ተቀበሩ ዕድሜአቸውም ፹፬ ዓመትይሆናል ።

የሚአሳዝን አደጋ ።

ክቡራን ጌቶቼና አባቶቼ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎችና ተመልካቾች ሆይ ። ለሕዝባችንና ለሀገራችን ጥቅም የሚሆን ልዩ የሆነ ሐሳብና ምኞት ነበረኝ ገና ልጅ መሆኔ ያግደኛል እንጂ ። ይኸንንም ማለቴ በያንዳንዱ ወገናችን (ሰዎችን) ላይ የሚሠራውን ግፍ ሥራና የሚያገኘውን የድንገት አደጋ ተመልክቼ ነው ይኸንንም ለመጻፍ ያነሳሳኝ በሐምሌ ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ከቤቴ ተነስቼ በትልቁ ጐዳና ስሔድ አራት ኪሎ ላይ ስደርስ ብዙ ሰው አስከትለው ፩ መኰንን እንደ ልማዳችን ሁሉ እየተጨዋወቱ ሲሔዱ አንድ የውጭ አገር ሰው በአቶ ቢሲክሌት እንደ ነፋስ ሲሮጥ መጣ እኔን አለፍ ሲል እፊቴ መኰንኑን ከሚከተሏቸው አንዱን ሽማግሌ በድንገት ጩኸት አስደንግጦ ሽማግሌውም አካሔዱ ከልክ ያለፈ መሆኑን አውቀው በፍርሃትና በድንጋጤ አመልጣለሁ ሲሉ በቅጽበት ደርሶ ዳመጣቸውና ያንጊዜውን ሞቱ ይህንም በየሁ ጊዜ በጣም ሐዘን ገባኝና እኒህ ሰው ማንን ያጐድላሉ ብዬ የልቤን ጥያቄ የማቅርብለት ቸገረኝ ።

ከሊያንስ ተማሪዎች አንዱ ሲሞን አደፍርሴ ።

ሹም ሽር ።

የወረገኑ ዲሬክተር የነበሩት ልጅ ዘለቀ ባንቲዋሉ በሐምሌ ፳፱ ቀን ባላምባራስ ተብለው ወላሞ የባሻ ሽበሺ የነበረውን ፳ገበር አሩሲ ፲ገባር የልጅ ተረፈ ሽበሺ የነበረውን ደግሞ ተዚሁ ባሩሲ ውሥጥ ፱ገባር ግምብቱ ፩ጋሻ መሬት በድምሩ ፴፱ ገባር ፩ጋሻ መሬት አድርገው የማዕርግ ልብስ አልብሰው ሾሙአቸው ። በቀን ልቡና ማገልገልን የመሰለ መልካም ነገር የለም የወረገኑን ዲረክተርነት ከተሾሙ እንኳን ብዙኋ ጊዜአቸው ነው በየሌላ ሥራ ላይ እንደቆሙት ዲሬክተሮች ሁሉ እንኳ የሚበቃ ቀለብ የላቸውም ነበር የሚበቃኝን ቀለብ አላገኘሁምና ብለው በሥራቸው ውሥጥ የዝንጋታና የቸልታ ሐሳብ የለባቸውም ነበር ። ዝንጋታና ቸልታ እንደሌለባቸው የሥራ ጓደኞቻቸው ሁሉ አይስቱትም ተስፋቸውን ሁሉ በጌታቸው ላይ ጥለው ጠዋት በውርጭ ከምሽቱ በጭለማ በየጊዜው ሁሉ ባለመሰልቸትና ባለ መበሳጨት ሲወጡና ሲወርዱ ለተመለከታቸው ሰው ትጋታቸው እንዴት ያስደንቅ ይመስላችኋል ተግቶ ሥራን መሥራት እንደሚጠቅም ተረዳነው የዚያን ዕለት ተስፋ የሌለን ሰዎችሁሉ ። ለሁሉም ጊዜ አለው እንደሚባለው ሁሉ ተስፋ አደረብን አባታቸውንም ግራዝማች ባንቲዋሉን ላያቸው ሰው እንዴት ደስ ያሰኙ ነበር ባላምባራስ ዘለቀንና ትንሹን ልጃቸውን ልጅ ተረፈ ባንቲዋሉን ግራና ቀኝ አስቀምጠው ደስታ ልባቸውን በጣም ተሰምቶት ነበርና ከደስታቸው የተነሣ ለቆመው አዝማሪ እንዲህ ብለው ነገሩት ቃሉም ቀጥሎ ያለው ነው ።

ስንጸልይ ኑረን መዓልቱን በዳዊት ሌቱን በውዳሴ ።
ይኸ የተገኘው በኃይለ ሥላሴ ።
እኔን የሻለቃ ልጄን እንደራሴ ።
ወድቆ ይነሱ በጅ ይታደሱ በልዩ ሲሉ እየሰማሁ ።
ሐሰት እንዳይመስለኝ በጌታዬ አየሁ ።
መንግሥትህ አይጥበብ ያሰፋው አላለሁ ።

በቀለ አደራ

ስለ ዓመፀኞች መዋረድ

ሳምኬት ብሂል ሰፋኒ እግዚአብሔር
ሳምኬት ኃይለ ሥላሴ
ዐማፅያነ ጸላዕኩ ፡ ሕገከሰ አፍቀርኩ ።

በገንዘባቸው የተመኩ እግዚአብሔርን የማይፈሩ ንጉሥን የማያከብሩ ከውርደት በቀር ሌላ እንዳያገኙ ይህ የሚከተለው ቃሌ ከመጻሕፍት ቃላት እየተጠቀሰ ያስረዳናል ።

መወድስ ።

ለምንት ይዜህር እንበለ መጠን ልቡና ብእሲ ኃያል ፤
በብዝኀ እከዩ ወዕንዐ ኃይሉ ። (መዝ ፶፩ ፩ ፱)
ወለምንት ይትሜካሕ በብዝኀ ብዕሉ ። ሳሙ ቀዳ ፪ ፫ ፫
ዘሰ ይትሜካሕ፡ ለይትመካሕ በእግዚአብሔር ዘሀሎ በላዕሉ ። ኤርምያስ ፱ ፳፫ ፳፬
ወያክብሮ ለንጉሥ ፡ እስመ ለንጉሥ አምላክ ዘአኰነኖ መልዕልተ ኵሉ ። ፩ኛ ጴጥ ፪ ፲፫ ፲፯ ።
ትምክሕትሂ ውስተ ዓለም ፤ እመ ለፍጡር ይደሉ ።
ለይትመካሕ ብንዴቱ ነዳየ ሥጋ በመዋዕሉ ።
እንዘ በእሳት ይነድድ ፤ ለብዓለ ጺጋ አከሉ ።
አልዓዛር ነዳየ ሥጋ በገነተ ትፍሥሕት እስመ ይሄሉ ።
(ሉቃ ፮ ፳ ፳፭)ሉቃ ፲፮ ፲፱ ፴፩ ።

አለቃ ዳንኤል

የኢጣልያን ሌጋስዮን በኢትዮጵያ ።
ማስታወቂያ ።

የየመን አገር ዜጎች የሆኑ ሰዎች የኢጣልያን ጥገኝነት የምስክር ወረቀት የያዙ ሰዎች ሁሉ እንደደምቡ በየዓመቱ የተመደበውን መለወጥ ለማድረግ በአንድ ወር ውሥጥ በኢትዮጵያ ካለ የኢጣልያን ሌጋስዮን ዘንድ እንዲቀርቡ እናስታውቃለን ።

ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ የምስክር ወረቀታቸውን ያላሳደሱ የየመን ዜጎች ሁሉ የኢጣልያን ጥገኝነት ይቀርባቸዋል ።

የምስክር ወረቀቱንም ስለማሳደስ የሚከፈለው ዋጋ ባለገንዘብ የሆኑት ሰዎች ፷የወርቅ ሊሬ (፵፰ብር) ሀብታም ያልሆኑት ሰዎች ፲፪ የወርቅ ሊሬ (፱ብር ከ፲መሐለቅ) አዲስ አበባ ነሐሴ ፲ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመት ።

የኢጣልያን መንግሥት ቆንስል ።
ፍራንቼስኮ ዲ ቼሌሬ

LEGAZIONE D'ITALIA IN ETIOPIA
CIRCOLARE

Si invitano tutti i sudditi Yemeniti possessori di certificato italiano di protezione a presentarsi entro un mese alla R° Legazione d'Italia in Etiopia per la regolare ed annuale rinnovazione di essi.

Informasi che alla scadenza del suddetto periodo, tutti i sudditi yemeniti che non avranno rinnovato il certificato, perderanno la protezione italiana.

Si rammenta che la tassa di rinnovazione del certificato di protezione e di Lire oro 60.- per persone agiate (Talleri 48.-) e di Lire oro 12.- per persone non agiate (Talleri 9,10/16).

Addis-Abeba, li 16 Agosto 1932 *X°*

IL R° CONSOLE
Ft° Francesco Di Cellere

Per Copia Conforme all'Originale
Addis-Abeba,li 17 Agosto 1932 X°

ከሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመት አንስቶ ወደፊት በፖስታ ለመላክ የሚከፈለው ዋና ዋና ዋጋ ማስታወቂያ ።

ክፍሉ	መጀመሪያ አኳሆን ለአገር ውስጥና ለጂቡቲ	ሁለተኛ አኳሆን ለውጭ አገር ። ኢንቴርናሲዮናል
ደብዳቤ	ለመጀመሪያው ፳ ግራም ፪ ግርሽ ከዚያ በላይ በ፳ ወይም በ፳ ግራም ቅናሽ ፩ ግርሽ እየጨመረ ይሄዳል	ለመጀመሪያው ፳ ግራም ፭ግርሽ ከዚያ በላይ በ፳ ግራም ወይም በ፳ግራም ቅናሽ ፫ግርሽ እየጨመረ ይሔዳል
የፓስቶ ካርታ ።(ካርት ፖስታል)	፩ ግርሽ	፫ግርሽ
የታተሙ ወረቀቶች	በ፶ግራም የግርሽ አላድ	በ፶ ግራም ፩ ግርሽ
ለሥራ ጉዳይ የሚሆኑ ወረቀቶች	በ፶ ግራም ፩ግርሽ ፶ግራም ብቻ የሆነ እንደሆነ በአነስተኛነቱ ፪ግርሽ	በ፶ግራም ፩ግርሽ ፶ ግራም ብቻ የሆነ እንደሆነ የሚከፈለው ገንዘብ ከ፭ግርሽ አያንስም
በእጅ የሚዳሰሱ ለዕውራን የሚታተሙ	በ፩ሺ ግራም የግርሽ አላድ	በሺ ግራም ፩ግርሽ
የንግድ ዕቃ ለማስመጫ ስላይነት ለሚላኩ	በ፶ ግራም ፩ግርሽ ፶ግራም ብቻ የሆነ እንደሆነ በአነስተኛነቱ ፪ግርሽ	በ፶ግራም ፩ግርሽ ፶ግራም ብቻ የሆነ እንደሆነ የሚከፈለው ገንዘብ ከ፪ግርሽ አያንስም
ቲንንሽ ጥቅል	በ፶ ግራም ፪ግርሽ ፶ግራም ብቻ የሆ. እንደሆነ በአነስተኛነቱ ፬ ግርሽ	በ፶ ግራም ፫ግርሽ ፶ግራም ብቻ የሆነ እንደሆነ የሚከፈለው ገንዘብ ከ፰ግርሽ አያንስም
ለጋዜታና ለግዜ ታሪክ ለሚታተሙ	በቍጥር የግርሽ ሩብሚዛኑም ፶ግራም ድረስ ነው	እስከ ፶ ግራም ድረስ በቍጥር ፩ግርሽ በፖስታ አንድነት ማኅበር ከዋጋው ግሚሱ እንዲከፈል ፈቅደው ለተቀበሉ ሀገሮች የግርሽ አላድ
ለአደራ	በአንድ አደራ ወረቀት ፬ግርሽ	በአንድ አደራ ፮ግርሽ
በውሥጡ ያለው ገንዘብ ልክ በላዩ ተጽፎ ዋጋው ለታወቀ ደብዳቤ ።	ለአንድ አደራ ደብዳቤ ላደራውና ለሚዛኑም እንደሚከፈለው ልክ ይከፈልበታል ከዚያ በላይ ስለአሱራንስ በ፫፻ የወርቅ ፍራንክ ፬ግርሽ ይከፈላል	ለአንድ አደራ ደብዳቤ ላደራውና ለሚዛኑም እንደሚከፈለው ልክ ይከፈልበታል ከዚያ በላይ ስለአሱራንስ በ፫፻ የወርቅ ፍራንክ ፰ ግርሽ ይከፈላል
በውሥጡ ያለው ገንዘብ ልክ በላዩ ተጽፎ ዋጋው ለታወቀለቲንንሽ ሣጥን	በ፶ ግራም ፫ግርሽ ይከፈላል ፶ግራም ብቻ የሆነ እንደሆነ በአነስተኛነቱ ፮ ግርሽ ይከፈላል ። ስለአሱራንስም ዋጋው በታወቀው ደብዳቤ ይከፈልበታል እንደተባለው ልክ ይከፈላል	በ፶ግራም ፩ብር ይከፈላል ከ፶ግራም በላይ ላለው በ፶፶ ግራም ፫፫ግርሽ ይከፈላል አሱራንሱም ዋጋው በታወቀው ይከፈልበታል የተባለው ዋጋ ይከፈልበታል
ደብዳቤው መድረሱን ለማስታወቂያ ።	ደብዳቤውን ሲልክ ለጠየቀ ፫ ግርሽ በኋላ ለጠየቀ ፮ ግርሽ ይከፈላል ።	ደብዳቤውን ሲልክ ለጠየቀ ፮ ግርሽ በኋላ ለጠየቀ ፲፪ ግርሽ
ለአቤቱታ ማቅረቢያ የሚሆን ወረቀት።	፮ግርሽ	፲፪ ግርሽ
በፍጥነት እቤት ድረስ ለሚሰጡ ደብዳቤዎች	ለአንድ አደራ ደብዳቤ የሚከፈለው ዋጋ ይከፈልበታል በፍጥነት ስለመሄዱም ፪ ግርሽ	የመልስ መቀበያ ፮ ግርሽ
ወደፊት ለሚታይ ነገር። ለሽያጭ ለሲኒማ ማያ ቀደም አድርጎ ለሚታተሙ ማስታወቂያዎች ።	እሁለት ታጥፎ ብቻ የፖስታ ሳጥን ለተከራዩ በማጥናቸው የተጣለ እንደሆነ የግርሽ አሩብ ይከፈላል አድራሻ ወይም መጠቅለያ ያለው እንደሆነ የግርሽ አላድ ይከፈልበታል	እንደታተሙት ወረቀቶች ዋጋ ልክ ይከፈልበታል

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት

ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
የቅዮ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
,, ,, ,, ትግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፭ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲ ብር
፫ቱ መጻሕፍተ መነኮሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፴፪ ብር
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪ ብር
ደስታና ክብር የአውሮጳ ሙ ታሪክ	፱ ብር
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጅዖግራፊ ከነከርታው	፯ ብር
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፯ ብር
ድርሳነ ሚካኤል	፯ ብር
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኅሀ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪ ብር ፳መ
የእርሻ ትምህርት	፩ ብር ፳መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ አጅግ ያማረ	፪ ብር
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
የቁጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የነጻ ደንብ ከነተጨማሪው	፩ ብር ፳መ
የብድር ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ አዲስ	፩ ብር ፳መ
የገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
ዮሐንስ ቡንያን	፩ ብር
፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፴፭ ብር
የ፪ኛ	፴ ብር
የ፫ኛ	፲፭ ብር
የ፬ኛ	፲ ብር
የ፭ ኛ	፯ ብር
የ፮ኛ	፯ ብር
የ፯ኛ	፯ ብር
፴፬ ካርት ፖስታል	፩ ብር
የረከማንዴ ደብተር	፫ ብር
ሕገ መንግሥት	፭ ብር
የአቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን ነገ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተስማማ	፳ መሐ
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፳ መሐ
ያማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
የፍቅር መላክት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የምሕረት አዋጅ	፬ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የንቁጣጣሽ ግጥም	፪ መሐ
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፪ መሐ
፩ ጋዜጣ	፪ መሐ
አርስጣላብ	፬ መሐ
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፬ መሐ
የአቴጌ ፎቶግራፍ ባለውዘድ	፬ መሐ
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፩ መሐ
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፩ መሐ
ካላንድሬ	
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪ	፩ መሐ
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፰ መሐ
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፬ መሐ

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት አጥፍ ። ነጠላ በያይነቱ ። እርሳስ መንጉልና ብረት ብርዕ ቀለም በያይነቱ፡የካርት ቢዚት አንቦልብና ካርት ቢዚት በያይነቱ ። አንቦልብ ትልቅና ትንሹ በያይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር አ ብሩንስ በፊት በድሬ ዳዋ ማዘጋጃ ቤት የመንግሥት ሐኪም የነበረ ዛሬ በአዲስ አበባ መጥቶ የሕክምና ሥራ መሥራት መጀመሩን ለሕዝብ ሁሉ ያስታውቃል። ማከሚያ ቤቱም አራዳ እሙሴ ዛኅን ጐን ቀድሞ ዶክተር ማየ ቤርዠር እሚሰራበት ቤት ውሥጥ ነው የሚገኘውም ጧት ከ፫ ጀምሮ እስከ ፬ ሰዓት ከእኩል ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲ ሰዓት ነው ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፡ የልብ ፡ የደረት የጉበት ፡ የኩላሊት ፡ የጅማት ፡ የጨብጥ የቂጥኝና ፡ የቋቍቻ ፡ የሚያጥልድ ፡ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፡ የርሻ የፋብሪካ ፡ የደን ፡ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቆሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋናታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፈቃዳቸው ሕገ መንግሥት ስለማቆማቸው የገንዘብ ሚኒስቴር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት በ፲፱፻፳፬ ዓ ም ለመሰፍንቱና ለመኳንንቱ የተናገሩት የስብከት ቃል በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታትሞ በዕሩብ መሸጡን እናስታውቃለን ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዳች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመንበናት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፴፮
8me ANNE. № 36

ሐሙስ ነሐሴ ፳፮ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ ም
Jeudi 1 Septembre 1952

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
አ ዋ ጅ ።

በራስ ኃይሉ እጅ የነበርኸውን ባርያ ሁሉ ነፃ አውጥተንሃል። በራስ ኃይሉ ቤት በርስታቸውና በጉልታቸውም የምትኖር ሹም ሁሉ ባንተ ዘንድ የተቀመጡትን የራስ ኃይሉን ባሮች እስከ ኅዳር ሚካኤል ድረስ ጐጃም ደብረ ማርቆስ ላይ ለዚሁ ለባርያ ነፃነት ለተሾመው ዳኛ እያስረከብህ የደረሰኝ ተቀበል። የሩቁ የቅርቡ እስከ ጥቅምት ሚካኤል አስረክብ። ለባሪያ ነፃነትም ዳኛ ሆነህ የተሾምኸው የራስ ኃይሉ ባሮች በመጡልህ ጊዜ ስማቸውንና አገራቸውን በመዝገብ እያጻፍህ የምስክሩን ወረቀት እየሰጠህ ወደ አገራቸው ለመመለስም ወይም በደመወዝም እየተቀጠሩ በወደዱበት ስፍራ ለመኖር ቢፈልጉ እንዳይከለከሉ አድርግ ።

ዕድሜያችሁ ከ፲ዓመት በታች የሆናችሁ የባሮች ልጆች ቀለብና ልብስ እየተቀበላችሁ በያድባራቱ ትምህርት ቤት እየገባችሁ እንድትማሩ አድርገናል ።

አንተም የነፃ ዳኛ ለትምህርቱ ቤት አለቃ በደረሰኝ እያስረከብህ በመንፈቅ በመንፈቅ የትምህርታቸውን አኳኋንና የሕይወታቸውን መጠበቅ እየመረመርህ ባመት ባመቱ አዲስ አበባ ላቆምነው ለነፃ ጽሕፈት ቤት ላክ። ዳግም ከራስ ኃይሉ ባሮች መካከል ሠርቶ ለመብላት የማይችሉ በዕድሜ ያረጁና በሽተኞች የሆኑ የተገኙ እንደሆነ መጦሻቸውን እየተቀበሉ እንዲጦሩ ይሁን ።

የራስ ኃይሉም ባሪያ የሆንህ ሁሉ ነፃ ወጥቻለሁ ብለህ ስምህንና አገርህን በመዝገብ ሳታጽፍና የነፃነትህን ምስክር ሳትቀበል የሚመጣብህን ጉዳት ባለማወቅ ወዲያ ወዲህ እንዳትል። ነሐሴ ፳፫ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ።

ኅሡ ሰላማ ለብሔር ።

አገር ደኅና ሆነ ፤ አገር ደኅና ይሁን ማለት ንጉሥ ከዙፋኑ፣ጳጳስ ከምእመናኑ፣ታቦት ከመንበሩ፣ አንበሳ ከዱሩ፣ ሳይናወጡ በየስፍራቸው ቢፀኑ ነው እንጂ አለዚያስ እረኞች ላሞችን በመጠበቅ፣ነጋዶች ስንቅን በመሰነቅ፣ ፈራጆች ፍርድን በመጠንቀቅ ፤ መምህራን ምሥጢርን በማራቀቅ ፤ ገበሮች መሬትን በመሰንጠቅ ፤ ሕፃናት ትምሮ በማወቅ ፤ አርበኞች ወሰናቸውን ባለመልቀቅ፣ ምእመናን በሃይማኖትና በምግባር ፍጹማን ሁነው መጽደቅ አይገኝምና ማናቸውም ሰው ሁሉ የብልህ ሞኝ ከመሆን ይልቅ የሞኝ ብልህ መሆንን ቢመርጥ ይሻላል ማለትን እናዘወትራለን። ማለት ሆዳም ሰው ላንድ ቀን ምሳ ቅልውጥ በመሔዱ ምክንያት የራሱንና የቤተሰቡን የዓመት ልብስና ጕርሰ ከማጣት እንዲደርስ ብዙ ሰዎችም የጥቂት ጊዜ የአንዳንድራሳቸውን ብቻ ጥቅም ሲሹ በመታመን ክዳትን ፤ በውነት ሐሰትን ምትክ እያደረጉ እስከ ብዙ ዘመን ድረስ ለልጅ ልጅ የሚሆነውን የራሳቸውንና የወገኖቻቸውን ብዙ ጥቅም ከማጕደላቸው የተነሣ መታሰቢያቸው ክፉ ይሆንና በሥጋም በነፍስም እንደተረገሙና የነሱቸው ወገን የሆኑትም እንዳፈሩ ይኖራሉ። ለይሁዳ ወልዱ ወውሉደ ውሉዱ ይደምሰስ እንዲሉ አሁን የአስቆሮታዊ ይሁዳ በዘር የወረደ የልጅ ልጅ ቢኖረው በክርስቲያን ዘንድ እንዴት ሲአፍር በኖረ?። ነገር ግን የሀገርን ደኅንነት ለሚያስቡና አሳበውም መሥራት ለሚቻላቸው ሰዎች ከዚህ ቀጥዬ ትንሽ ማስታወሻ እጽፍላቸዋለሁ።መናብርት ቤተ ዳዊት ተዚያነዉ ዳኅናሃ ለኢየሩሳሌም ይትናገሩ ሰላመ ብእንቲአኪ ወበእንተ ቤተ እግዚአብሔር አምላኪየ ኃሠሥኩ ሠናይተኪ እንዲል መዝ ፻፳፩ ።

ላገሬ እሞትላታለሁ፣ስለ ሀገሬ ሕይወቴን አሳልፋለሁ፣ስለ ሀገሬ ደሜን አፈሳለሁ የሚል ሰው እንኳን ዛሬ ብዙ ትምህርት ባለበትና ፍቅረ ሀገር ባያሌው በተሰበከበት ዘመን ከዚህ በፊት ትምህርት ባልሰፋበትና ፍቅረ ሀገር ባልተሰበከበት ዘመን በተፈጥሮ ዕውቀት ተመርተውና በአእምሮ ጠባይዕ ተመራምረው ስለ ሀገራቸው ፍቅር ደማቸውን አፍስሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው፣ ሕይወታቸውን አሳልፈው በድንበራቸው ላይ የወደቁ ብዙዎች እንደ ሆኑ ማንም አይስተውም ።

ነገር ግን በወንድማማች መካከል የሚሆነው ፍቅረ ሀገር ሕይወትን በማሳለፍ ደምን በማፍሰስ ሳይሆን ሊያደርጉላችሁ የምትሹትን አድርጉላቸው ቢያደርጉባችሁ የምትጠሉትን አታድርጉባቸው ያለውን በመፈጸምና ሁለተኛም ለሀገር ጥቅም የሚሆነው እንዲፋፋ፥ ጕዳት የሚያመጣው እንዲጠፋ፥ ያንድራሱን ብቻ ጥቅምና ያንድራሱን ብቻ ጥቃት ለመወጣት ሲሹ የብዙዎችን ጥቅም ማጥፋቱ ና የብዞዎችን ጥቃት አለመበቀል። ያንድ ራሱን ጥቃት ለመወጣትና ያንድ ራሱን ጥቅም ብቻ ለማግኘት ሲሉና ለደም ጥልቀት ለሥጋ ልደት ረድቶ ለብዙ ነገር ጥቅም ሲሆን በትንሽ ነገር የሚጐዳውን አጥፍቶ ጕዳትነቱ በገዛ ትንሽ ጠቀሜታ የሚገኝበትን ፈማልማት የሚነሣሣ ሰው እንዳይኖር አስታዋሽነቴን አበረታለሁ ።

መኰንን ኢያቄም ።

የአቶሞቢል መሰናከል

በነሐሴ ፲፱ ቀን ወይዘሮ ዓፀደ አስፋውና ወይዘሮ አስቴር መንገሻ ተላይኛው ግቢ በ፩አቶሞቢል ሁነው ወደቤታቸው ሲሔዱ በነጂው አለመጠንቀቅ ምክንያት ከጀርመኖች ሰፈር አጠገብ ሲደርሱ አቶሞቢሉ ተገልብጦ ከነአሽከሮቻቸው ወድቀው ነበር። ሰዎቹ ተጐዳት ድነዋል።ያ መከራ ያልለመደው ለስላሳው ሰውነታቸው ከዚህ አደጋ መዳኑ እጅግ ያስደንቃል ። መሬት የመታውም ሰውነታቸው የረጋው ደም እንዲበትን በሐኪም ፈቃድ ፍልውኃ ገብተው ሰንብተዋል ። ብርሃንና ሰላም እንኳን እግዚአብሔር አተረፋችሁ ይላል ።

ጥቂት ወቀሣ ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ከዚህ ቀጥዬ የጻፍኳቸውን ቃሎች አላወቃችኋቸውም አልሰማችኋቸውም ብዬ አይደለም እንዲያው ማሳሰቢያ እንዲሆኑ እንጂ ።

፩ኛ ፤ የዕውራን ብርሃናችን፣የደካሞች ምርኩዛችን፣ለጕልዳፎች መላሳችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያ እናታችን ከእግዚአብሔር ባይላኩላት እንዴት በሆን ነበር ፍጻሜያችን?።

፪ኛ፥ ሐሳቡን ለሕዝቡ ደሙን ለሀገሩ በግልጽ ያሰናዳ ንጉሠ ነገሥት ባይኖረን ከድንጋጤ ማን ሊያፅናናን ኑሯል ይሆን

፫ኛ፥ሰው እግዜር፥ እግዚአብሔር ሰው የሆነ በሥጋ ብቻ ባይሆን እውነት የዘንድሮውን ሐሳብ እግዚአብሔር የመረጠው ንጉሠ ነገሥታችን ከመፍሰስ አዳነው ደማችንን።

፬ኛ፥ ያንዱ ወዳጅ በጥፋቱ ከሥራ ይወጣና ላንዱ ሲሰጥ ስለ ወዳጅ እርዳታ አላወቀበትም ብሎ በስወራበት ጊዜ የሀገር ፍቅርና አእምሮ ያላቸው ሰሚዎች እንዲታዘቡት አይገምተው ይሆን ? አድልዎና ምቀኝነትን ከስንት ዘመን በፊት ግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ እንደገደሉት አልታወሰው ይሆን? ፍቅርና ሥራ ለየብቻው መሆኑንስ ያለመስበት ይሆን ? ይልቅ የቀድሞ ሠራተኞች በብዙ ዘመናት ውሥጥ በየሥራው ላይ ኑረው በመሥራታቸው መልካም ምስጋና ይገባቸዋል።ደግሞ የዛሬው ልጆች በቀድሞ ባባቶቻቸው ልክ በጥቂት ጊዜ በመሥራታቸው አያስደንቅምን ? ።

ጥቂት አንጉርጉሮ ቀድሞ የነበረ ላሁን የሚስማማልጨምር።

መመቀኛኘትን ቢተው ሐሳባችን ።
እያደላደለ ይሰጣል ጌታችን ።
ቢተዉት አይተውም የዛሬው ቂመኛ ።
እስክንደርስ ድረስ እትልቁ ዳኛ። የብርሃንና ሰላም ተላላኪ።

መልስ ።

የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል እንደሚባለው ሁሉ ቀድሞ ወደ ጅማ ታዝዤ እንደመጣሁ ለኔ ዘመዴ የሆንና የሚያስብልኝ ሰው ሁሉ ያቶ ያግሉ አባወሉን ነገር ተጠንቀቅ እያሉ ይመክሩኝ ነበር ። በጆሮ የሰሙትን በዓይን ያሳያል ቤታቸውን እመንገድ ዳር ሂርማታ እጥናው ገበያ ላይ ሰርተው በወጭና በወራጅ የሆነውን ነገር ይጽፋሉ ማለትን እሰማ ነበር ያንኑ የለመዱትን መስተንግዶ እንዳይቀርበት ብለው በሐምሌ ፯ቀን በ፲፱፻፳፬ ገጽ በጻፉት ብርሃንና ሰላም ተመልክቻችሁታል።ይልቁንም የሚደንቀው ባላዩትና በችሎቱ ሳይኖሩ የእስሩን ቍጥርና ከምርመራ የቀረውን ነገር ሳያውቁ ሦስተኛ ይመረመራሉ እስረኞቹም ስባ ያህል ናቸው ማለታቸው የነገሩን ልክ ምን እንደሆነ አውቀው ነው?የተያዙትም አጥፊዎች ሁሉም በሰሩት የኃጢአት ሥራ የቍጥራቸውን ልክ ጠንቅቆ የሚአውቅ ባለ መዝገብ ስለሆነ በግምት ከዘጠና እያንስም።ይህ ሁሉ ሲሆን አራት ሰዎች በነፍስ ገዳይነትና በመቀማት አፈርማታ ሲወጡ የቀረው ከዚህ በላይ እንደጻፍኩት ሁሉም በየሥራው በቃሉ ያመነ ነው እንደዚህ ያለ ጥፋት የሠራ ፈትቼ ለቀቁ ቢሆን በተናገሩ እኔ በታዘዝሁበት ሥራ እሥረኛውንና መዝገቡን ይዤ ለፍርድ ሚኒስትር አቅርቤ የዘበውን አቅንተው የጐደለውን ሞልተው የፍርድ ሚኒስትሩ አይተው በንጉሠ ነገሥቱ ችሎት ይቀርባሉ እንጂ አቶ ያግሉ አልታዘዙበት ሥፍራ መግባት አያስፈልጋቸውም ነበር ።

ሁለተኛስ ሁለትና ሦስት መቶ ሰዎች እየሆኑ ለነጋድራስ ማህሌ ጥፋታችንን ይዩልን ለመንግሥትም ያስታውቁልን ሲሉ ቴይተው ዳኛ ቢልኩላቸው እንኳን እግራዝማች አበበ ዘንድ አለመዷቸው እነጋድራስ ማህሌ ደጃፍ ሳይደርሱ ቀሩ ላሉት ነገር ቀድሞ እችሎት በዋሉና ባዩት ቅር ባላለኝ ደልቅ ተናግሮ ከቀረው ደኃና ከሳቸው ጕዳቱ ለማን ይሆናል?ሥራ አነሣቸው እንዳይባል በነጋድራስ ማህሌ ውሥጥ ለገባያና ለኬላ ወምበር ናቸው ሁለተኛም ለክቡር ራስ ደስታ ዳምጠው ጅማ ውሥጥ ላለ ገንዘባቸው ወኪል ናቸው ።

ሦስተኛም ተዋውለው የተማሬ ቤት ያሠራሉ ይህ ሁሉ ሥራ እያላቸው እሰው ሥራ መግባት ምን ይመስላል?የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች እንደሚሉት ሁሉ ሂርማታ ከተማ አንድ ዘበኛ ገድለው ሁለተኛውን አቍስለው ሄዱ ላሉትም ከተማ ለመጠበቅ መቶ ዘበኛ ከነጋድራስ ማህሌ ጋር ታዞ እንደመጣ ሁላችሁም ታውቃላችሁ ደግሞ የቁጥራቸውን ልክ አላወቅሁትም እንጂ ቀድሞ ከተማ ይጠብቁ የነበሩ የአባ ጅፋር ዘበኛ ወደነጋድራስ ማህሌ የሆኑ አሉ።አቶ ያግሉም በነጋድራስ ማህሌ ውሥጥ ዋና ወምበር ሁነው ዘበኞቹን ሁሉ የሚአዝዙና ከነጋድራስ ማህሌ በምክርም በሥራም የማይለያዩ ናቸው።ዘበኛው የሞተ ለት ተከታትሎ እንደመያዝና ቢያመልጥ አፈርሳታ

እስወጥቶ ደመኛውን እንደመፈለግ የራሳቸውን ጥፋት ይጽፉሉ የአፈርሳታ ፈቃድ የላቸውም እንዳይባል እንኳንስ በራሳቸው ሥራና በነጋድራስ ማህሌ አገረ ገጋርውንና ቆሮዎቹን ሲያዙ እንደቆዩ ጆሮ ያለው ሰው ሁሉ ያውቀዋል እነሱ ከተጡት የዘበኛውን ደመኛ እኔ እስፈልጌዋለሁ እኔን የነቀፍሁ መስሏቸው ጠንከራ ሕመም መርምሮ ለማወቅ የሚችል ባለዲፕሎም ሐኪም ነው እንጂ ማንኛውም የፋርማሲ ሐኪም (መድኃኒት ሻጭ) መርምሮ ለማወቅ አይችልም ማለታቸው እውነት ነው ብሮ እንደጌታው ለማወቅ እንደምን ይችላል ሐኪም ሁኖ መድኃኒት መሸጡም ጌታው በሰጠው ሥራ መሥራቱ ነው እሳቸውኳን ማንኛውም መድኃኒት ሻጭ ማለታቸው ዘለፋ አድርገውት ነው ይኸነን ሁሉ ያሳዩትን መናገራቸው ሰው የላከቸው ይመስለኛል እንጂ ብቻቸውን የሰሩት አይመስለኝም። ቀድሞም የሃገሩን ጥፋት ያስታወቁ ነጋድራስ ማህሌና አቶ ያግሉ ናቸው አሁን እንደምስክር ሁነው ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ማስታወቃቸው ከሳሽ በባላጋራውና በዳኛው ምስክር አለመሆኑን ባለማወቅ ያሳስባቸዋል አሁንም ክቡራን አንባቢዎች ሆይ የተናገርሁት ነገር ከልሆነልኝ እኔው ምስክር ሁኜ ልመስክር ቀድሞ በነገሩ መግባቴን የሚያውቅብኝ ሰው የለምና እውነት ይመስላል ብለው ነው እንጂ ይኸነን አውቀውት ቢሆን አይጽፉም ነበር እሳቸውም ጻፉ እኔም መልስ ሰጠሁ ከንግዲህ ወዲህ ይህኑ ሥራ አድርጌ ሁለተኛ ልጻፍ ቢሉ እኔን የሚያስፈልጋቸው ነገር እንዳለ በፍርድ ሚኒስቴር በኩል ይጠይቁኝ እንጂ ብርሃንና ሰላም የጸብ መከራከሪ አይደለምና ቢተውት ይሻላል።እንዲሁ ያላየሁትን እናገራለሁ አልተውም ቢሉ እኔም ለመልሱ የተዘጋጀሁ ነኝ ። ግራዝማች አበበ ናቄ።

በ፰ኛ ዓመት ቊጥር ፳፱ ሰኔ ፪ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት በወጣው በብርሃንና ሰላም ጋዜጣ የአቶ ሞገሴ ፭ ጥያቄ መልስ ባጭር ቃል ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው

፩ኛ ጥያቄ፡ትምህርት ምንድርነው ለተባለው መልስ ትምህርት መማር ነው ተማረ ተማረ ማለት ነው።ያልተማረ ሰው ግን ነፃነት የሌለው ዕዳው ያልተወሰነ በምቀኝነት ሰንሰለት የታሰረ በስንፍና የወደቀ በድንቁርና የተጨቈነ ነው።በ፪ኛው ጥያቄ የትምህርት ዓይነታው ፍሬ የቱ ነው ለሚለው ጥያቄ መልሱ ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር ተብሎ ተጽፎ ቈይቶናል። የትምህርት መጀመሪያና መጨረሻው እግዚአብሔርን መፍራት ባልንጀራን መውደድ ነው ተብሏል። በ፫ኛው ጥያቄ ሰው መማሩ ለምንድርነው ለሚለው መልስ ሰው መማሩ ሰው ለመሆን ነው። መጀመሪያ ራሱን አንፆ ሠርቶ ደግሞ ባልንጀራውን ለማነፅና ሰው ለማድረግ ነው በዚህ መልስ ያልተማረ ሰው ሰው አይባልም ማለቴ አይደለም ያልተማረ ሰው እርእያው የሰው መልክ ነው ጠባዩና አስተዳደሩ አነዋወሩ ግን ከተማሩት ሰዎች ልዩ ነው የትምህርት ዋና ዓላማው የተማረውን በማሻሻል በመመልከት የትምህርትን ቃል ሰሚና አድራጊ መሆን ነው።፬ኛ ጥያቄ ሰው በመማሩ ምን ሁኖ እንዲታይ ነው ለሚለው መልስ መልካሙን ግብራችሁን ለአሕዛብ አሳዩ መልካሙን ሥራችሁን አይተው የሰማይ አባታችሁን እንዲአመሰግኑት ተብሎ የተጻፈውን የመጽሐፉን ቃል መፈጸም ነው የተማረ ሰው የተማረውን በማድረግና በቃልም ባልንጀራውን ወደተሻለው ኑሮ ወደ ደኅንነት ሲመራው እንዲታይ ነው። አቶ ሞገሴ በዚህ ጥያቄዎ በውሥጥዎ ያለውን መልካሙን አሳብዎን ለመናገር አልደፈሩም እንጂ በውሥጣዎ መልካም ነገር የተመለከቱ ይመስለኛል።ፈሪ ነቢይ በውሥጡ ያለውን በመላሱ መናገር አይደፍርም እንደተባለው መሰለኝ ምናልባት ከተማረ ሰው ውሥጥ ትምህርቱን ያልተከተለ ልማዱን ያልተወ ሰው አይተው የታዘቡት ይኖራል እንጂ በከንቱ ይህነን ያህል ጥያቄ አይጠይቁም ነበረ። ከ፭ኛው ጥያቄ እስከ ፲፪ኛው ጥያቄ የጠየቁትን መልስ በዝርዝር ለመጻፍ የሚበዛ ስለሆነ በአጭር ቃል እመልሳለሁ። ከ፭ እስከ ፲፪የተጻፉት ጥያቄዎች ለሰው ለኑሮውና ለሕይወቱ ለጥቅሙ ሁሉ የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ በትምህርት መንገድ የሚገኙ ናቸው እነዚህ በጥያቄዎ ውሥጥ ከተጻፉት ሁሉ አንድ ቢጐድል ሁሉም እንደጠፉ ይቈጠራሉ። እነዚህ ለሰው የተሰጡ ደንብ ናቸው እንደ ሰንሰለት ተያይዘው እርስ በራሳቸው ተቃቅፈው በሰውነት ላይ ካልተገኙ የሰው ልጅ ሕፃን እንደሆነ ሳያድግ አዋቂ ሳይባል ሳይጠቀም ሳይጠቅም ጐጅና ተጐጂ እንደሆነ ዘመኑን ጨርሶ ያልፋል ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ያቶ ሞገሴ ጥያቄ ስለ አነሣሣኝ ጥቂት ቃል ከዚህ ቀጥሎ ልጽፍላችሁ የኢትዮጵያ ፍቅር ያስገድደኛል ።ኢትዮጵያ ዘገምተኛ ሁና በረግመድ ሳትቀለጥፍ ትኖር ነበረ አሁን ግን በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ መሪነት አካሔድ አወቀች እርምጃዋ እየተፋጠነ ትገሠግሣለች እኛም በደስታ እንከተላታለን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የሰው ልጆችን ኑሮ በታሪክ ስንሰማው ከባድ ከባድ የልማድ ቀንበር ተጭኖአቸው ይኖሩ እንደነበረ ያስረዳናል ። አሁን ግን የሰው ልጆች የቀድሞ ዘመን ኑሮአቸውን ታዝበውታል ። ይልቁንም የአውሮፓ አዋቂዎች የጦር መሣሪያ እንዳይሠራ የመከላከል አሳባቸውን በየጋዜጦች በየጊዜው ይጽፉታል ። እኛም ብናስበው ታሪክም ብናነብ በጸላትነት ምንም ጥቅም አልተገኘበትም ለማለት እንደፍራለን ። መጀመሪ ቃየል አቤልን ወንድሙን በጸላትነት ተነሥቶ ገደለው ከጸጸት በቀር ምን ጥቅም አገኘ?ከዚያም ወዲህ ከየትውልዱ ተከታትሎ የተደረገውን የጸላትነት ታሪክ ከዚህ ቀጥሎ በተጻፉት በጥቂቶች ቃሎች እንረዳዋለን።በሙሴ ዳታን አቤሮን ተነሡበት ። በዳዊትም ሳኦልና አቤሴሎም ተነሡበት። በኤርምያስ ጳስሁር በጸላትነት ተነሣበት። በመርዶክዮስ ሐማ ተነሣበት፤ በሰምሶን ፍልስጥኤማውያን ተነሡበት ። በዮሐንስ ሄሮድያዳ ተነሣችበት፤በማርያም የእስራኤል ሊቃውንት ተነሡበት በኢየሱስና በሕፃናቱ ሄሮድስ ተነሣ።ለተነሡት ጸላቶች ሁሉ ከጸጸት በቀር ምን ጥቅም አገኙበት።አሁንም ዓለም በደኅንነት እንዲኖር የሚጠቅመው ጸላትነትን መንቀፍ ወዳጅነትን መውደድ ነው። ጸላትነት የሚጸነስበትን ማኅፀን ማፍረስ ፤ በግድ ለሰው ልጆች ያስቸግራል።ጸላትነት የሚጸነስባቸውን ማኅፀኖች የጥቂቶቹን ስም ከዚህ ቀጥሎ ጽፌዋለሁ መጀመሪያ ፍትወትን አለማሸነፍ የራሱ ብቻ አገልጋይ መሆን የጸላትነት ምንጭ ነው።

፪ኛ በሕግ አለመወሰን፤ ፫ኛ በቃኝ አለማለት የራሱ ያልሆነውን ባልንጀራው የደከመበትን መመኘት ጸላትነትን

ይወልዳል።በላይኛው መስመር እንደተጻፈው አዋቂዎች የጦር መሣሪያ እንዳይሠራ ተመኙ ይህን የጦር መሣሪያ መሥራት ከመተው በፊት ጦር የሚነሣበትን ምክንያት ሁሉ በስምምነት ቢመለከቱት ጦር የሚመጣበትን መንገድ በሕግ ቢዘጉት የጦር መሣሪያ መሥራት ለመንግሥት ጉዳት እንዳለበት ይታወቃል ። መንግሥት የሚአገኘውን ገንዘቡን ሁሉ ለጦር መሣሪያ መክፈሉ ይቀራል ይልቁንም የጦር መሣሪያ በመሥራት ፈንታ ሌላ ለሀገር ሀብት የሚሰጥ ሥራ ይሠራል የጦርነት ነገር በዓለም ሁሉ ለዓለም እንደጠባይ ሁኖ በየምክንያቱ ሁሉ ሲዋጉ በውጊት ሲተላለቁና ደም ሲፋሰሱ ገንዘባቸውን ሲከስሩ ይኖሩ ነበረ ። በጐሣና በቋንቋ በሃይማኖት በግዛት በሥርዓት አንድ ወገን ያልሆኑ የዓለም ልጆች ሁሉ መንፈሳቸው ለጦር የሚቸኩል ነበረ ። በየትውልዱ ሁሉ ጦርነት ከዓለም ላይ አልቀረም ነበረ እየቄዩ ግን የተዋጉበትን ምክንያት ሁሉ አዋቂዎቹ እየታዘቡት የስምምነት ነገር እየተጀመረ የጦርነት ነገር እያነሰ ይሔዳል። መጀመሪያ አገሮች ሁሉ በጐሣና በቋንቋ የተለያዩትን ሁሉ በመንግሥት ሥልጣን አንድነት ሲአገኙ ጊዜ እርስ በራሳቸው መዋጋታቸው ቀርቶ እየተጋቡ ተዛመዱ በንጉሥ መገዛት እርስ በራሳቸው ከመጋደል አዳናቸው ለማስረጃ በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ባላገሮች ከየጐረቤቶቻቸው ሲዋጉ ይኖሩ የነበሩት ስማቸው ከዚህ በታች ተጽፎአል።ሱሉልታ ከበዲ ይዋጋ ነበረ፥ በዲ ከሙሎ ይዋጋ ነበረ ። ሙሎ ከሜታ ይዋጋ ነበረ።ገላን ከጉለሌ ይዋጋ ነበረ በዚህ ዓይነት ጥቃቅኖቹ አገሮች ሁሉ እርስበርሳቸው ዘወትር ውጊትና መዛረፍ ያደርጉ ነበረ ይህነን ኑሮአቸውን ከዛሬው ኑሮ ጋራ ቢአስተያዩት ከመከራ ድነው ወደ ደኅንነት መድረሳቸውን ይረዱታል።በዚህ አምሳል ዓለም ሁሉ በየአቅራቢያው እርስ በርሱ መዋጋትን እየተወ ራቅ ራቅ ካለው ወገን አንድ አንድ ጊዜ መዋጋት ይጀምራል ዓለም ከሕፃንነት ወደ አዋቂነት ሲደርስ ጦርነትን መንቀፍ ጀመረ የዛሬው ኑሮ ለሕይወት የታመነ ከቀድሞ ኑሮ የተሻለ ከሆነ ወደፊትም በስምምነት ከዚህ የበለጠ የተሻለ ኑሮ እንዲገኝ ተስፋ አለን ። ከዓለም ላይ ጦር እየቀለለ እርስበርሱ ከመዋጋት እርስበርሱ መዛመድ እየበዛ መሔዱ በታላላቁ አገር ሁሉ በአንድ መንግሥት ተጠቅሎ በመገዛቱ ነው ። አሁን ደግሞ ምኞታችን መንግሥታቱ ሁሉ ገንዘባቸው አንድ ዓይነት ቢሆን በገንዘብ መስማማት ቢኖር በፍትሐ ነገሥቱም አንድ ብቻ ቢሆን ለዓለም ሁሉ አንድ ሕግ በላያቸው ደምላሽ ቢሆን የዓለም ኑሮ ደስ የሚያሰኝ ኑሮ ይሆናል ይህነንም ምኞት መጻፌ በዓለም ላይ እንዲደረግ ከታሰበው ጉዳይ ሁሉ ለማድረግ የማይቻል የለም። እንደምታውቁት ዓለም ሁሉ ተራርቆ ይኖር የነበረው አሁን እንዲህ የተቀራረበው መልካም ነገር በማሰብና በመሥራት በመስማማት ነው። አሁን ከ፲፱፻፳፪ ዓመት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በገንዘብ ችግር ዓለም ሁሉ ያዝናል ችግር ሲበዛ ማስፈራቱ አይቀርም።ችግር የሚወልደውማነን እንደሆነ ገና አላወቅነውም ይህም የሚያስፈራ ችግር ዓለምን ሁሉ እንዲአስጨንቅ ሥልጣን ያገኘበት ምክንያት በሁለቱ ከዚህ ቀጥለው በተጻፉት ምክንያቶች ነው ።

፩ኛ በገንዘብና በምንዛሬ ባለመስማማት ነው ። ፪ኛ በየሀገሩ ያሉት ገንዘቦች ልዩ ልዩ ስለሆኑ አንዱ አገር ብር እንዲወደድለት ይሻል፥ ደግሞ ፪ኛው አገር ወርቅ እንዲወደድ ይሻል። ፫ኛው አገር ፍራንክ እንዲወደድ ይሻል በዚህ ምክንያት እነዚህ ገንዘቦች በዋጋ ስምምነት ያልተወሰኑ ስለሆኑ እርስ በራሳቸው ተቃዋሚነት አለባቸው ደልቁንም ደግሞ ገንዘብ ሁሉ ፈሪ ጠርጣሪ የሆነ ይመስላል ገንዘብ ከልፈራ ለምን እየተዘዋወረ ሥራውን አይሠራም ገንዘብ ሁሉ ስለፈራ በአንድ ፩ቤት እየተዘጋበት ቢቀመጥ ሲዘዋወር ባለመታየቱ ገንዘብ በየሀገሩ የሌለ ይመስላል ችግርን ለማቅለል በገንዘብና በሕግ መስማማትን እመኛለሁ አቶ ሞገሴ ለጠየቁት መልስ መማር ምን ለመሆን ነው ለሚሉት መማር ችግርን ሁሉ ለማቅለል ኑሮን ለማሻሻል ከዚህ በላይ የተመኘነውን ሕግና ስምምነት ለማግኘት እንዲረዳ ነው ብዬ የመሰለኝን በመጻፌ ይቅርታ እለምናለሁ ።

ነጋድራስ ደስታ ምትኬ ።

የብልህ ሐሳብ ስላለመገታት ።

ትምህርት መቸም እንቅልፍ አያስወስድምና የሥጋዊ ትምህርት ያለው የሥጋዊን ኑሮ አሳብ፥መንፈሳዊም ትምህርት የተማረ ሰው የመንፈሳዊ፥አሳብ ሲአስብ ያድራል።ስለዚህ በመንፈሳዊ ትምህርት በጣም የተመሰገነው ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ለመድኃኔ ዓለም የተቀኘውን ቅኔ ቀጥለን ጽፈነዋል።

መወድስ።

ደመ ቅቱለ ግፍዕ አቤል ወዘካርያስ ፥ ለተበቅሎ ፀር ተጋህ ፥ ወስእነ ተዐግሦ ።
እስከ ደመ ፍዳ ይትከዐው እምዘቀደመ አብሶ ።
ወውእቱ ያኅሥሮ ለሰብእ በምክሐ ተፈጥሮ ዘአዕበየ ነፍሶ፥
እንዘበአእምሮ ልብ፥አስመ ከመ ጠቢብ ኢገብረ፥በዘያበዕዕ ርእሶ።
ባሕቱ በድነ አንበሳ፥ እምተፈጥሮተ ሰብእ ኅይሶ ።
ዲበሕተ መዓር አስተዳለወ ለዘገብረ ተባእሶ ።
ወእምአንክሮዝ ነገር ለልቡናነ ናግዓሥ ።
እስመ ደመ ወልድ ለከዓዊሁ ዓለመ ሕይወት ያወርሶ።

ስለ ጐጃም ሕዝብ መታደል ።

እውነተኛ ዳኛና ትክክለኛ ገጋር ለሕዝብ ጥቅምና ደኅንነት፤ ለሀገር ልማት መሆኑ፥ እውነተኛ ያልሆነ ዳኛና ትክክለኛ ያልሆነ ገጋር ግን ለሕዝብ ጉዳት ለሀገር ጥፋት መሆኑ የታወቀ ነው ስለዚህ ገናናው ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አባት የተወደደች ሕፃን ልጁን ከሳች ጠቁረችብኝ ብሎ አዝኖ ተከባክቦ እንዲያሳድጋት ከሞግዚት ሞግዚት አሻሽሎ እንዲያደርጋላት እንዲሁ ለሕዝባቸው እንደእናት እንደ አባት የሚያስቡ ጃንሆይም ብሔረ ጐጃም በከባድና በጠባብ ቀምበር ተይዞ ነፃነት አጥታ በጭንቅ መኖርዋን አይተው ስለ አዘኑላት ይህነን ከባድ የሆነ ቀምበር በግርማዊነታቸው ሰባብረው ጥለው ቀምበሩ ቀላል ሥራው ትክክል የሆነ እውነተኛ ዳኛና ገጋር ክቡር ራስ እምሩን መርጠው ሹመው ሸልመው ስለ ሰደዱላት ፍጹም ደስታን ተመልታ ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ። የመንግሥትዎ ዘሩን እስከ ልጅ ልጅዎ ፀንቶ.

ጅኑርልን እያለች ምስጋናዋን አታቋርጥም ። ይህም መንግሥት እውነተኛና ሕዝቡን ታዳጊ ነውና በእውነትና በእምነት የሚያገለግለውን ሰው ሁሉ በጊዜው ጊዜ ዋጋውን እጽፍ አድርጎ እንዲከፍለው የማይጠረጠር ነው ። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ እነሆ ባለፉትም ዛሬም በተሾሙት ሹማምቶች ሁሉ ላይ ስለ አገልግሎታቸው ያደረገውን የቸርነቱን ሥራ ስንመለከት ከዚህ በላይ የተጻፉት ቃላት ሁሉ እርግጥ መሆናቸውን የሚያስረዳ እንደሆነ አስተዋይ ሕሊና አመዛዛኝ ልቡና ያለው ሰው ሊስተው አይችልም ። ስለዚህም ከሕዝብ ወገን የሆነ ሁሉ ማንም ሰው ቢሆን በሥራው ተግቶ ሀገሩንና መንግሥቱን በመውደድ ፀንቶ መኖር ነው እንጂ ሁለ ልብ ሁኖ መበከንና ማንከስ የማይገባ መሆኑን አውቆ መጠንቀቅ ያስፈልገዋል ።

ዕድለኛይቱ ጐጃም ሆይ።ሕዝቡን ባንቺ አንቺን በሕዝቡ ሰይሚ እናገሬለሁና ልብ አድርገሽ ስሚ ጥላ ለሐሩር ቡልኮ ለቍር ቤዛ እንደሆነ ለግፍና ለበደልም እውነተኛ ፍርድቤዛው ነው። ስለዚህ ግፍ ከሚባል ሐሩርና በደል ከሚባል ቍር የምትድኚበት እውነተኛ ፍርድ የሚባል ጥላና ቡሉኮውን ልቡና ከሚባል ግምጃ ቤቱ እያወጣ የሚያጐናጽፍሽ እውነተኛ ገጋር ክቡር ራስ እምሩን ስላገኘሽ ከሀገር ተለይተሽ በጽኑ ዓዘት መቀጥቀጥሽን እያዩ ያዝኑ የነበረ ግራ ቀኝ ጐረቤቶችሽ ሁሉ በቅናት በምቀኝነት ሳይሆን በፍቅር በትሕትና ሁነው ደስ ይበልሽ ደስታ ይገባሻልእያሉ የደስታሽ ተካፋይ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

የተወደድሽ ጐጃም ሆይ፡ እንግዲህም ሥልጣኔ በሚባለው ደረጃ ቀኝ እጅሽን ይዞ የሚአወጣሽ ብልህ ትጉህ ገጋር ከማግኘትሽ የተነሣ ሥልጣኔን አብበሽ ጥቅምን አፍርተሽ እንድትኖሪ ጥርጥር የለውምና ይህንን ሁሉ ውለታ ላደረገልሽ ንጉሥ የምታቀርቢው ምስጋና ከቶ ምን ይበዛ? ደግሞስ ምን አንቺ ብቻ እኛም እንጂ ለመላ ኢትዮጵያ አባትነት ለሆነ ለታላቁ ንጉሠ ነገሥት የምናቀርበው ምስጋና መጠን የለውም።አበበ መኩሪ።

የሚአሳዝን ሞት

የቀኛዝማች ወልደአብ ልጅ ኪዳነማርያም ወልደአብ ጠባዩና አወጣጡ ያማረ ልጅ ነበረ ። የአንጀት በሽታ ነበረበትና ከዚህ ቀደም ዶክቶር ሐነር በቤተሣይዳ ሆስፒታል ቀደው አድነውት ነበር ። ደግሞ ሁለተኛ ስለተነሣበት እንደ ቀድሞው ያድኑኛል መስሎት በዚያው ሆስፒታል ሒዶ ተቀዶ ነበር ምንም ቢሆን ቀኑ የደረሰውን ለማዳን አይቻልምና በነሐሴ ፳ ቀን በዚሁ በቤተሣይዳ ሆስፒታል ሙቶ በመድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ተቀበረ። ዕድሜውም ገና ፲፱ ዓመትነበረ። ቀኛዝማች ወልደ ዮሐንስንና ሌሎችን ወንድሞቹንና እኅቶቹን እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል

ስለ አቶ ደገፋ ሞት

አቶ ደገፋ በንግድ ሥራ ራሳቸውን ችለው የሚኖሩ ትዕቢትና ትምክሕት የሌላቸው ሀብታም ፡ የረጉ ፡ ጠባየ መልካም ሰው ነበሩ። በሳል ሕማም ምክንያት ታመው ዓሥር ቀን ያህል በዶክቶር በራ ሆስፒታል ተኝተው ሰንብተው በነሐሴ ፳፫ ቀን ሙተው ጉለሌ በሮፓውያን መቃብር በብዙ ክብር ተቀበሩ። ዕድሜአቸውም ፳፫ ዓመት ነው ።ልጆቻቸውንና ዘመድ ወዳጆቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል።

Chaussures Bata Chaussures

La plus grande fabrique de chaussures du monde entier

የባታ ጫማ ።

በዓለም ከሁሉ የሚበልጥ ትልቁ የጫማ ፋብሪካ ለወንድና ለሴት ለልጆችም የሚሆን ጫማ በየዓይነቱ ይገኛል ።



ባንዳንድም ሆነ በጅምላ ብትፈልጉ
በጣም ባነሰ ዋጋ ታገኛላችሁ።



ይህም የሚሸጥበት ቤት በማዳም ሐርዲ ቤት ፊት ለፊት ባለው ሱቅ ነው አንድ ጊዜ መጥታችሁ ብታዩት ደስ ሳይላችሁ አይቀርም ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት

ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር	
የቅዱ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር	
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፭ ብር	
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር	
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲ ብር	
፫ቱ መጻሕፍተ መነኰሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪ ብር	
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪ ብር	
ደብታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፱ ብር	
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር	
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር	
የዓለም ጂዮግራፊ ከነካርታው	፯ ብር	
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፮ ብር	
ድርሳነ ሚካኤል	፯ ብር	
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር	
ጎህ ጽባሕ	፭ ብር	
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር	
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ ብር	
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪ ብር	፶መ
የእርሻ ትምህርት	፩ ብር	፶መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ እጅግ ያማረ	፪ ብር	
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር	
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር	
የቍጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩ ብር	
የአማርኛ ሰዋሰው	፩ ብር	
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር	
የነፃ ደንብ ከነተጨማሪው	፩ ብር	፶መ
የብድር ደንብ	፩ ብር	
የጠር መሣሪያ ደንብ አዲስ	፩ ብር	፶መ
የገዳም ደንብ	፩ ብር	
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር	
ዮሐንስ ቡንያን	፩ ብር	
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፭ ብር	
የ፪ኛ	፳ ብር	
የ፫ኛ	፲፭ ብር	
የ፬ኛ	፲ ብር	
የ፭ ኛ	፯ ብር	
የ፮ኛ	፯ ብር	
የ፯ኛ	፯ ብር	
፳፬ ካርት ፖስታል	፩ ብር	
የረኮማንዴ ደብተር	፫ ብር	
ሕገ መንግሥት	፭ ብር	
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፶ መሐ	
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን ነገ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፶ መሐ	
አጭር የዓለም ታሪክ	፶ መሐ	
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተስማማ	፶ መሐ	
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፶ መሐ	
ያማርኛ ም[illegible]	፶ መሐ	
አሳብና ምኞት	፴ መሐ	
የፍቅር መላክት	፴ መሐ	
ትምህርተ ሕፃናት	፴ መሐ	
የምሕረት አዋጅ	፴ መሐ	
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፳ መሐ	
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፳ መሐ	
የንቍጣጣሽ ግጥም	፳ መሐ	
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፳ መሐ	
፩ ጋዜጣ	፳ መሐ	
አርስጣላብ	፴ መሐ	
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፴ መሐ	
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለውዘድ	፴ መሐ	
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፩ መሐ	
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፩ መሐ	
ክላንድሬ		
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪ	፩ መሐ	
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፶ መሐ	
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፴ መሐ	

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት አጥፍ ። ነጠላ በየይነቱ ። እርሳስ መንኰልና ብረት ብርዕ ቀለም በየይነቱ።የካርት ቢዚት እንቦልብና ካርት ቢዚት በየይነቱ ። እንቦልብ ትልቅና ትንሽ በየይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር እ ብሩንስ በፊት በድሬ ዳዋ ማዘጋጃ ቤት የመንግሥት ሐኪም የነበረ ዛሬ በአዲስ ኣበባ መጥቶ የሕክምና ሥራ መሥራት መጀመሩን ለሕዝብ ሁሉ ያስታውቃል። ማከሚያ ቤቱም አራዳ እሙሴ ዛኳን ጉን ቀድሞ ዶክተር ማየ ቤርዠር እሚሰራበት ቤት ውሥጥ ነው የሚገኘውም ጧት ከ፫ ጀምሮ እስከ ፬ ሰዓት ከእኩል ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲ ሰዓት ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፤ የደረት የጕበት ፤ የኲላሊት ፤ የጆማት ፤ የጨብጥ የቂጥኝና ፤ የቋቍቻ ፤ የሚያዋልድ ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

* * *

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪክ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወከሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች፡፡ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዶች ቀጥሎም እንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፉና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመንገብኝት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ያቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።



በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሉር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንጨቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለፅንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፴፯
8me ANNE. № 37

ሐሙስ ጳጕሜን ፫ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓም
Jeudi 8 Septembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ትንቢት ይቀድሞ ለነገር ።

መንፈሰ እግዚአብሔር ያደረባቸው ደጋጎቹ ቅዱሳን የተናገሩት ነገር በአካለ ነፍስ ይቅርና በአካለ ሥጋ በግልጽ ሳይደርስ ይቀራል ተብሎ አይጠረጠርም።ስለዚህ ደገኛው ቅዱስ ያዕቆብ ሐዋርያ በመልእክቱ ብዕልክሙ ጠፍአ አልባሲክሙኒ ቊንቊነ ወርቅክሙኒ ወብሩርክሙኒ ዝሀለ ወዛሁሉኒ ስምዐ ይከውን ላዕሌክሙ፡ ወለሥጋክሙኒ ይበልዖ ከመ እሳት ብሎ ተናግሮ ነበር። ያዕ ም፭ ቍ ፪ ፫።ከሱም ቀጥለው የነበሩት ሊቃውንትና መምህራን ደኸንኑ አብነት አድርገው ብርና ወርቅ አታከማቹ የተከማቸውም ብርና ወርቅ እንደ እሳት ሆኖ በገሃነም ሥጋችሁን ያቃጥለዋል እያሉ ለሕዝቡ ሲያስተምሯቸው ሕዝቡም በጆሮዋቸው ከመስማት በተቀር በግልጽ ሆኖ ባይናቸው አላዩትም ነበር።ነገር ግን ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለምና በአካለ ሥጋ ገልጾ ባንድ መነኩሴ አሳያቸው።ይህስ እንዴት ነው ቢሉ አባ ኤርላርዮስ የሚባል መነኩሴ ባንዲት ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በአት ሰርቶ ማቅ ለብሶ እንዳ ተጐናጽፎ በብሕትውና ይኖር ነበር።ሕዝቡም መንፈሳዊ ነው ብለው ቡራኬ ለመቀበል ወደርሱ ይሔዳሉ ወደዚያውም ለነዳያን መጽውትልን እያሉ ብር ሲያመጡለት ጸሎቴን ስጨርስ በኋላ እመጸውትላችኋለሁና አስቀምጣችሁት ሒዱ ይላቸዋል ከሔዱ በኋላ አግብቶ በሚተኛበት ራስጌ ቆፍሮ ይቀብረዋል እንደዚህ እያደረገ ሲያከማች ኖረ ሕዝቡም ለደኆ ይሰጥ ይመስላቸዋል እንጂ ማከማቸቱን አያውቁም ነበር በኋላ የብሩ ጕድጓድ ሲሞላ መቃብሩን ከብሩ ጕድን ምሶ አደራጅቶ ተቀመጠ ነገር ግን ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከሞት የሚቀር የለምና ጊዜ ሞቱ ሲደርስ እዚሁ ከጸለይሁበት በቃና እኔው በቈፈርሁት መቃብር ቅበሩኝ ብሎ ተናዞ ሞተ በሞተም ጊዜ ብዙ ሕዝብ ከሩቅ አገር ድረስ ተሰብስበው አልቅሰው በቈፈረው መቃብር ቀብረውትንሽ እንደሔዱ መቃብሩ ሲቃጠል አዩ ቢመለሱ ያየተደበቀ ብርና ሥጋው እንደ ፈትልና እንደ ሰም ተስማምቶ ሲቃጠል ብዩ ጊዜ ደነገጡ እኛ ጻድቅ ነው ገንዘብ አይፈልግም ስንል ለካ እንደዚህ ያለ ነው ብለው የሐዋርያውን የያዕቆብን ቃል በግልጽ ተረድተውት በታሪክ ተጽፎ እስከሁን ድረስ ሲነገር ይኖራል ።

አሁንም ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ በየጊዜው የወዳጆቹን ቃል መግለጽ ልማዱ ነውና ቅዱስ ዳዊት ይዘግቡ ወኢየአምሩ ለዘያስተጋብኡ ያለውን ቃል ዳግም በደገኛው ንጉሥ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ በግልጽ ዛሬ አሳየን ። ይኸውም ራስ ኃይሉ በፊት እንደተጻፈው ብርሃንና ሰላም የሰውን ከብት እየወረሱ ደኃ እያስለቀሱ ከልጅነት ጀምሮ እስካሁን ድረስ የሰበሰቡት ብርና ወርቅ ስፍር ቍጥር የለውም ይባላል ገንዘቡም ገቢ ነው እንጂ ወጭ የለበትም ወጭ ማለት ላሽከር ማብላት ፥ ቤተ ክርስቲያን ማሠራት፥ ንዋየ ቅድሳት መግዛት ድልድይና መንገድ ማስበጀት፥ ተማሪ ቤት መክፈት ፥ ለነዳያን መመጽወት ነው ይህ ሁሉ የለባቸውም ፩ድ ፩ድ ጊዜ እንኳ ቢያወጡ በመሸታ የተገዛ ጦር ቢወረውሩት ድፍድፍ ወጋ እንደሚሉ ተረት በዓመፅና በማስለቀስ የተሰበሰበው ገንዘብ ቢወጣ ለደም ማፋሰሻ ለሰው ማስገደያ ሆነ እንጂ ለደግ ሥራ አልወጣም መጨረሻውንም ያየወደዱት ብርና ወርቅ ዓይንዓይኑን ሲያዩት እንደተከማቸ ለሌላ ሔደ ማዕርጋቸውም ለሌላ አለፈ. ስለዚህ የቅዱሱ የዳዊት ቃል በአካለ ሥጋ በግልጽ ስለደረሰና ለወደፊት ልጆች በታሪክ ተጽፎ የሚነገር ስለሆነ ይኸንን ከብዙ በጥቂቱ ከምሉ በክፍሉ ለመጻፍ አሳሰበኝ ። ደግሞ ለዚሁ እንክሮ አንድ መወድስ ቅኔ ጽፌአለሁ ።

መወድስ

በዓመተ ዳንኤል አብ ነቢየ ባቢሎን ፤
ሕልመ ተዋርዶ ርእየ መስፍን ጐጃም ለሊሁ ።
ምሳሌ ብሩር ወወርቅ እንዘ ይቀውም ቅድሜሁ ።
ወዕብነ መንክራት ኃይለ ሥላሴ ፤
ተበትከ ዘእንበለ እድ ይቀጥቅጥ ኪያሁ ።
ለዝርወተ ውእቱ ምስለ ወርቅ ፤ ነፋሰ እግዓዚ ኂሩት እምጣነ ተለም ድኅሬሁ (ዳን ም፪ ቍ ፩ ፴ ፯)
ፍትሕክሂ ኃይለ ሥላሴ ፍትሐ መለኮት ከማሁ ።
እስመ አበኢሁ ለእንተ አፍአ፥ ወለእንተ ውሥጥ አውግኢሁ ።
ዓዲ ይብሉከ ሰብአ ምድረ ጐጃም ናሁ ።
ለዓለም ብሔርነ አንተ ኬንያሁ ።

ዘውገ ወልደ ጻድቅ

በወላጋ አውራጃ ስለ ንግድ መንገድ ሥራ መሰናከል።

ወለጋ አውራጃ በክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ግዛት ቡና ጭኖ ወይም ተሸክሞ የሚነግድ ነጋዴ የመንግሥት ጉምሩክ በቆመበት ሰዮ ድረስ አምጥቶ በጉምሩኩ ጉርድ እያስቀረጠ እንዲነግድ እንጂ ባረብ ወይም በሌላ መንገድ ወስዶ እንዳይሸጥ ስለተከለከለ ለጊዜው ደኅና ምክር መሆኑ ታይቶን ነበር። አሁን ግን በ፲፱፻፳፩ ዓ ም ከጥቂት ቀን በፊት ከጕሬና ከሰዮ አሜሪካን ሚሲዮኖች ሶስት ልጃገረዶች በሸሆጀሌ አልሃሰን አገር አድርገው ወደ ካርቱም ሲወርዱ እኔም አገር ለማየት አብሬ ሔጄ ነበርና ስንሔድም ስንመለስም ነጋዴዎች ብዙ ጭነት ቡና ሲየወርዱ አይቼ ስቆረቆር አንድ ቀን እጉምሩክ ላይ አንዱን ነጋዴ ቡና በዚህ በኩል እንዳይወርድ ክልክል አይደለምን እንደምን አመጣችሁት ብዬ ብጠይቀው ስለ መንገዱም በጋልኛ የሚገጥም ትንሽ ተረት ጨምር ወዲያውም አከታትሎ ስላገራችን ጉዳት እያስተዛዘነ የሚከተለውን ቃል መለሰልኝ ። አዬ ወንድሜ ሆይ ድኃና ጅብ መንገድ ያጣልን ግን መንገዳችን በዱርና በጨለማ ስለሆነ ለመንፈቅ ያሰብነው ሱሬ ባንድ ወር ያልቅብናል እንጂ መሹለኪያ መንገድስ እናጣምና ይልቅስ ስላገራችን ጉዳት እጅግ የሚያሳዝነውን ነገር ልንገርህ በሰዮ አውራጃ ያሉ የውጭ አገር ነጋዴዎች ከኛ ትርፍ ለማግኘት እንጂ ለመንግሥታችን ወይም ለሕዝባችን ጥቅም እንዳልተቀመጡ የታወቀ ነውና መቼም መንገዱም ክልክል ነው እንደ ፈቃዳችን እንገዛለን እንጂ ወዴት ያደርሱታል ሲሉ የቡናው ዋጋ ከዚህ አይለፍ ያቡጀዲውና ያሸበው ዋጋ ከዚህ አይነስ እያሉ ባንዲት ሰዓት ወረቀት ተላልከው ከዳር እስከ ዳር አድመው ይቆዩና ነጋዴው ጭነቱን አምጥቶ ካንዱ ሱቅ ሲያራግፈው መዝኖ አይቶ ሙሉውን ቁንጣር ጕደሎ ትርፍ ያለበትን አንድ ቁንጣር ነው ዋጋውም ይህን ያህል ነው ይለዋል ። ከሕዝባችንም ከተማረው ያልተማረው ይበዛልና ቍጥሩን ከለማወቁ የተነሣ ሚዛኑ ይህን ያህል ነው ብሎ መከራከር ስላልተቻለው እንዱ አብልጦ ይሰጠኝ መስሎት ወዳንዱ ሱቅ ይወስዳል ። መቼም ነገሩ የተመከረ ነውና ከዳር እስከ ዳርም ቢያዞረው ቃላቸው አንድ ሁኖ ይገኛል ። ይልቁንም ቅድም ከወጣበት ቤት የመለሰው እንደሆነ ከፊተኛው ቀንሶ ሊገዛ ይፈልጋል ፡ ይኸን ጊዜ ድኃው ነጋዴ ወደ ገምቤላ አውርዶ በመርከብ ወደ ውጪ አገር ወስዶ እንዳይሸጥ ዓቅም አጥቶ በከብቱ ጭኖ ወደ ሌላ አገር እንዳይወስድ መንገድ አጥቶ በይኑ አልቅሶ በጁ አብሶ ሲቸግረው እነሱው በቈረጡለት ዋጋ ሊሸጥ የግድ ይሆንበታል ብሎ የጓደኞቹንና የራሱን ችግር ስላዋየኝ ። እኔም ደግሞ ብርሃንና ሰላም የሁሉም ሐሳብ መግለጫ ነው የሚለውን ቃል ከጋዜጣ ስላነበብሁ በዚህ መካከል የታየኝን ሁለት ጉዳት በደካማው ሐሳቤ ጽፌ ለማስታወስ ፈቀድሁ። ፩ኛው ድኃው ነጋዴ በተደለደለው በንጉሡ ጐዳና ቀን ለቀን ቀረጥ እየከፈለ ወደ ወደደበት ሔዶ እንደ መንገድ ሌሊት ዱር ጥሶ ጨለማ ለብሶ እግሩን ዕንቅፋት ልብሱን ጋሬጣ እየፈጀው ወይም ጆኒያው ተቀዶ ቡናው ፈሶ ያከስረዋል።ወደመንግሥቱ፣ገቢ ተጨምሮ ለተማሪ ቤት ወይም ላገር ጥቅም ለሚሆነው ሁነኛ ሥራ ይረዳ የነበረውን ገንዘብ በከንቱ ያስቀረዋል ። ስለዚህም መንግሥት መክሮ ድኃው ቀረጥ ከፍሎ ጕርዱን ተቀብሎ ወደ ወደደበትም ሔዶ እንዲነግድ ቢያደርጓለት ለድኃውም ለመንግሥቱም የሚሻል መስሎ ቢታየኝ ስለ የብርሃን መንገድ መሪ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ስለ ለምለምዋ አገራችን ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር ያለ እውቀት በሞኝነት ያለ ፍርሃት በድፍረት አመለክታለሁ ። ማሞ ጮርቃ ።

ስለ ከተማ ዘበኞች ትጋት ።

ከፊታውራሪ ተፈሪ ቤት በነሐሴ ፳፭ቀን ሌሊት ግምጃ ቤታቸውን ሌቦች ሰብረው ገብተው አንድ ባለድግን መትረየስ ከ፱፻፹ጥይት ጋራ በሣጥን እንደሆነ አንድ ረሽ ጠመንጃ ከ፴ጥይት ጋራ፥ አንድ ወጨፎ ጠመንጃ፥አንድ ሽጉጥ፥ አንድ ጥንግ ድርብ ሌላም ይህን የመሰለ ብዙ እቃ በያይነቱ ስለ ሰረቁ የዚህ እቃ መሰረቅ በማግሥቱ በነሐሴ ፳፮ ቀን በዘበኛው አለቃ በኩል ከተሰማ በኋላ በየክፍሉ ላሉት ለከተማ ዘበኞች ትእዛዝ አልፎ ነበርና ባንድ ወገን ያሉት የክፍል ዘበኞች በመትጋትና በስለላ የሌቦችን ፍለጋ ተከታትለው ይዘው የተሰረቁትንም መሣሪያዎችና ዕቃዎች ጭምር በጳጉሜ ፫ቀን ከጥዋቱ በ፫ሰዓት በዘበኛ አለቃ በኩል ወደክቡር ከንቲባ ዘንድ ቀርበው ሌቦቹ ቢመረመሩ በየነ ፥ በጋለ ፥ ሙላቱ ፥ ረጄሳ ፥ ለመይ ፥ ሙዘይን፥ ገብረ ሕይወት የሚባሉት ሰባቱ የመስቃንና የሲልጢ አገር ሰዎች ግምብ ሰብረው መስረቃቸውን ስላመኑ ይልቁንም እነዚህኑ የጦር መሣሪያዎች አርዳሽስ ለሚባለው የወርቅ ሠራተኛ የአርመን አገር ሰው ሸጠውለት ኖሮ ከአርዳሽስ ቤት አግኝተው የተሰረቁትን የጦር መሣሪያዎች በመጡዋቸው ጊዜ ከሌቦቹ ጥፋት ይልቅ በትምህርትና በሥራ የሠለጠነ መስሎ ከብዙ ሕዝብ ጋራ የንግድ ሥራ ይሠራ የነበረው የአርዳሽስ ጥፋት በጣም የጐላ ሆነ ። እጅግ የሚያስደንቀው የዘበኞቹ ትጋት የመትረየሱን ሣጥን ሌቦች ሰብረው ካነደዱት በኋላ ከዚያቴንሽ የተረፈ ምልክት አግኝተው በዚያ ምልክት የተሰረቁትን ዕቃዎች ሁሉ ለማግኘት መብቃታቸው ነው። ሌቦቹ እንደተናገሩት ሁሉ የሰርቆታቸውንና ያከሄዱትን አኳኋን ዘርዝረን ለመጻፍ ስፍራ ይወስድብናል በማለት ትተነዋል እንጂ ዘርዝረን ብንጽፈው ኖሮ ለሰሚዎች እጅግ ያስደንቅ ነበረ። ደግሞ ልብስ ተቀምጦበት የነበረውን ሣጥን (ሻንጣ)ሌቦቹ ሰባብረው ከወንዝ ውሥጥ ከጣሉት በኋላ ዘበኞቹ ተፈላልገው በውሃ ውስጥ ማግኘታቸው በትጋት ላይ ትጋት እንደጨመሩና የከተማውን ጥበቃ ሥራ ከልዩ ልዩ ጥንቃቄ መሥራታቸውን ይገልጻል።እነዚሁም ሌቦች በዚሁ ምርመራ የተነሣ በሌላ ጊዜ የሰረቁትን ሁሉ ተናግረው ከተሰረቁትም ዕቃዎች ለምልክት አንዳንድ ተገኝተዋልና ስለዚህ አሁን ለጊዜው ይህን ብቻ ስለጻፍን ወደፊት የመጨረሻውን ምርምርና ሌላም ይህን በመሰለ በከተማ ዘበኞች ትጋት አሁን በነሐሴ ወር ውስጥ የተገኘውን ጥቅም ሁሉ ለመግለጽ በሐሳብ ተዘጋጅተናል ።

የአይሮፕላን አደጋ በድሬ ዳዋ ።

በሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓመተ ምሕረት በድሬ ዳዋ የአደሮፕላን ተማሪ ቤታችን እስከሁን ድረስ የአደሮፕላኑ ቤት ባለመሠራቱና አየሮፕላኑን ዝናምና ፀሐይ የሚያበላሸው ስለሆነ ከጉምሩክ አስቀምጠነው ቆይቶ ነበረ ፤ የአይሮፕላኑ ቤት ከተሠራ በኋላ አስተማሪያችንንም እኛን ተማሪዎቹንም ደስ ብሎን አደሮፕላናችንን ወስደን አስተማሪያችን ሙሴ ቤዶል በደስታና እጅግ በበዛ ትጋት ያስተምሩን ጀመሩ እንዲሁም ስንማር ሳለን እኔ ፴፰ ጊዜ፥ ልጅ ደመቀ ተክለ ወልድም ፺ ጊዜ፥ እንደበረርን ባ፺፩ኛው ላይ ከማታው በ፲፩ ሰዓት ጀምረው ሙሴ ቤዶል ልጅ ደመቀ ተክለ ወልድን ሲያስተምሩ ከመብረራቸው በፊት አይሮፕላኑ ሲሞከር ኩንትቱሩ ማለት የመኪናውን ልክ መሥራት አበረጅው ልክ ይሠራ ነበረ ከተሞከረም በኋላ ፩ት ጊዜ እያሳረፉና እያስነሱ ሲበሩበት የመኪናው(ማለት)የሞተሩ ድምጽ ኩንትቱሩ ደህና ሲሠራ ቆይቶ በምስተኛው ከመሬት ተሺከርከረው ወዳዩር ከበረሩ በኋላ ሞተሩ ድምጽ ለወጠባቸው።ወዲያው ተመልሰው ለማረፍ ጊዜ ሳይሰጣቸው ቤንዚን አቀባዩ ድንገት በሄሊሱ ኃይል በተወረወረ ድንገተኛ ነገር የከቢሮውን ቀዳዳ ስለደፈነው ቤንዚን አላቀብል ብሎ ሞተሩ ቆመባቸው። ይኸም ሲሆን ከመሬት ወደላይ በግምት ፴፫ ሜትር ያህል ከፍ ብለው ነበረ ። ከተነሱበትም ሜዳ ፫፻ ሜትር የሚያህል እንደራቁ ከናይሮፕላናቸው ተምዘማዝዘው ከወንዝ ውሥጥ ወደቁ አወዳደቃቸውም እንዲህ ነው በፊት አይሮፕላኑ በጭንቅላቱ ወድቆ ከወዳደቁ ንረት የተነሣ በጀርባው ተገለበጠ። ከመውደቃቸውም በፊት ሙሴ ቤዶል እንደሚቻላቸው መጠን ከደህና ስፍራ ለመውደቅና አይሮፕላኑንና ተማሪያቸውን ራሳቸውንም ለማትረፍ ደከሙ ነገር ግን በግንባራቸው ዛፍና ገደል ጉራንጉር ብቻ ስለሆነባቸው የማይቀር አደጋ ስለሆነና አይሮፕላኑም ሲወድቅ ስለተገለበጠ ግራ ቀኝ ከንፉና ነፋስ ሳቢ ሄሊሱ ትራንዳቴርዘዥ የቤንዚን ጋን ተሸካሚውና የቤንዚን ጋኑ ፈጽሞ ተሰበረ እኛም አለቁ ብለን ከየነበርንበት እየሮጥን ብንደርስ ልጅ ደመቀ ተ ወ የራሱን ጉዳትና ድንጋጤ ከምንም ሳይቆጥረው ከከር ላንጉ ውሥጥ ወጥቶ አስተማሪው የታሠሩበትን የአደሮፕላኑን ውሥጥ መጠበቂያ ፈትቶ ከከር ላንጉ ጐትቶ አውጥቶ ደግሞ የተበላሸውን እያገላበጠ ሲያይ ደረስንባቸው ሰውነታቸው ትጉድቶ ይሆናል ብለን ብንያቸው ሙሴ ቤዶል እጃቸው ቲንሽ ቆስሎ ማጅራታቸው ቲንሽ ተቀጥቅጦ ልጅ ደመቀ ተ ወም አፍንጫውና ትከሻው ጉልበቱና ቅልጥሙ ቲንሽ ቲንሽ ቆስሎ ራሱን ሬዝቧል መትቶት ብራኳውንም የመቀመጫው መደገፊያ ጥቂት አሸቶት ሕይወታቸው ተርፎ አገኘናቸው እግዚአብሔር ይመስገን የከተማው ሕዝብ ይኸን በሰማ ጊዜ ከያለበት ባንድ ጊዜ ተሰብስቦ መጥቶ ሕይወታቸው በመትረፉ ደገረምና ድንጋጤው እንዴት እንዳደረጋቸው ይመለከት ነበረ ። እነርሱ ግን ምንም በከፉ አወዳደቅ ቢወድቁ ከወንበር የመውደቅ ያህል እንኳ ፊታቸው አልተለወጠም ነበረ ።

ይህም አደጋ በሆነ ማግሥት የተሰበረውን አይሮፕላን ከወንዝ ውስጥ ለማውጣት በተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ ፊት ልጅ ደመቀ ተ ወ ይህነን ዲስኩር ተናገረ፡ ይህ አደጋ ስላገኘን ልትረዱን የመጣችሁ የኢትዮጵያ ልጆችና የውጭ አገር ተወላጆች ከዚህ ቀጥዬ የምናገረውን ቃል እንድትፈቅዱልኝ እለምናለሁ በገራችን እጅግ ያልተለመደ ስለሆነ የአይሮፕላን አደጋ ከሁሉ የሚያስፈራ ይመስላችኋል እንጂ በኤሮጳ ግን እንደማናቸውም አደጋ የተለመደ ነው እኔም ከናስተማሪዬ ይህ ስላገኘኝ አካላታችን አልጐደለም ሕይወታችን አልጠፋምና ምንም ከከፉ አደጋ አንቆጥረውም ግርማዊ ጌታችንም የተሰበረችውን አይሮፕላን ከምንም ሳይቆጥሩ እኛ በመትረፋችን በጣም ደስ እንዲላቸውና ደግሞ አዲስ አይሮፕላን በፍጥነት አስጥተው ትምህርታችንን እንዲያስፈጽሙን በርግጥ አውቃለሁ። ወደፊትም በድንገተኛ አደጋ ከፉ አሟሟት ብንሞት እንኳ ተማሪዎች እየተተኩ ትምህርቱም እየሰፋ እንዲሔድ ጥርጥር የለውም ያይሮፕላን አደጋ ላይን ከፉ መስሎ ይታያል እንጂ ቀኑ የደረሰ በትንታና በወለምታም ይሞታል ኢትዮጵያን እናታችንን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ንጉሣችንን ዘለዓለም ያኑርልን ለሀገር ለመንግሥታችን በሞት በሕይወት ለማገልገል የዘተጋጀን ነን ለምኞታችን ምጽኒያ ጊዜያችን ሳያልፍብን በቶሎ አይሮፕላን እንዲሰጡን አረጋግጠን እናምናለን። የኢትዮጵያ አንድነት ለዘለዓለም ያጽናልን ብሎ ሲጨርስ ፫ጊዜ ተጨበጨበለት ።

ዕድሜ ለኢትዮጵያ ብርሃን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንኳን የወንድማችንና ያስተማሪያችን ሕይወት ተረፈእንጂ ለተሰበረ ሙስ አይሮፕላን መለወጫ መጥቶለት ይታደሳል ነገር ግን ባንድ አይሮፕላን ተማሪ ቤት ማቆም የተሻለ አይደለም። ይኸውም ዕድልነው ከዚህ ቀደም በዚችው ባንድ አይሮፕላን አራት ተማሪዎች ተምረው መጨረሻቸውና ደግሞ ሁለታችን መጀመራችን ይኸውም ዕድልነው ። አዲስ መኪና አይደለም ከዚህቀድሞም ገና ወደኛ ሳይመጣ ተሰርቶበታል አዲስም ቢሆን በተሰበረ ጊዜ መለወጫና ሌላም ፪ት ፫ት አይሮፕላን ያስፈልጋል የአይሮፕላን ሥራ አደጋ ይበዛዋልና ይልቁንም ፕሮፌሰሩና ሜካኒሲያኑ ጠንቃቆች ካልሆኑ ሁለት ሶስት እንኳ ቢሆን ባንድ ሰሞን ይረግፋል ይኸን አሁን የተሰተበረውን አይሮፕላን ሙሴ ቤዶል አጥብቀው ባይጠነቀቁለት እስከሁንም ባልቆየ ነበር ስለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት የዓለምን ሥልጣኔ መከተል በጣም የሚያስገድደው ስለሆነ ለአይሮፕላን ትምህርት የሚያስፈልገውን መሣሪያ መስጠትና ሥራውንም ያለማቋረጥ እንዲኪያሄድ ማድረግ በጣም ያስፈልጋል የአይሮፕላን አስተማሪና ተማሪዎች ሥራ እንዳይፈቱና ጊዜያታቸውን በከንቱ እንዳያሳልፉ ። ኃይለ ጊዮርጊስ ሀ ማ የአይሮፕላን ተማሪ ድሬዳዋ ።

ስለ ጃንጥራር ገብረ እግዚአብሔርና ስለ ወይዘሮ አሳመነች ሞት በማዘኔ ። እላለሁ እናልቅሶ በሥላሴ ቅኔ ።

ማኅዘኒት ጠማረ ሞት በወይዘሮ አሳመነች (አየለ) ቀስመ ወርቅ ፣ ዘተጽሕፈት ዮም ለፍዳ ፤ ኀበ ጃንጥራር ወልድየ ። ተፈነወት ብሂላ አብዝኃት ብከየ ።
እቴጌ መነን ራሔል በቤታ (ማቴ ፪ ፲፯ና፲፰) ወአመ በጸግ ጸለየ እምአከዓብ ሞት እምድኅረ ጉየ (መጽሐፈ ነገ ቀዳ፲፯ ፭-፱)

ኃይለ ሥላሴ ኤልያስ ፤ ሥልጣና እርእየ ።
በአዝንሞ እሳተ ወማየ።(መጽ ነ ቀ ፲፰ ፩።)´መጽ ነ ከ ፩ ፲ ፲፮)

ለወርቁ በአዝንሞ እሳተ ወማየ ማለት ፤ የመርዶው ቃል በተሰማ ጊዜ ወዲያው ያ እሳት የጐረሰ መድፍ በመተኰሱና ከሰው ዓይን የእንባ ዝናም በመዝነሙ ነው። አለቃ ዳንኤል።

ቅኔ

ያለማቋረጥ በየጊዜው በሚነገረው ስብሐተ እግዚአብሔር ውሥጥ የጻድቃንና የሰማዕታትን ገድል፥የነገሥታትንም ክብር የሚገልጸውን ከሊቃውንቱ የሚገኘውን ቅኔ ብርሃንና ሰላም በየሳምንቱ ተግቶ ላንባቢዎች ሁሉ በማስገኘቱ ፤ የተለ የምስጋና ይገባዋል የሚሉ ብዙ ሊቃውንት አሉ።ይህንም ያሳሰበኝ በነሐሴ ፳፬ ቀን የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ክብር ስለነበረ በዚሁ ቀን በዓሉን ለማክበር ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በመኳንንቱና በሠራዊቱ ታጅበው ወደቤተ ክርስቲያኑ ሔደው ነበርና ፤ የደብሩ ሹም አለቃ ወልደ ትንሣኤ የተቀኙትን ቅኔ ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን ።

ክብር ይእቲ

ግዕዘ ተባርዮ ኢተርፈ በኀበ ወልድ፤ወኀበ መስቀል ልዑል።
ህየንተ መስቀል ተፀውረ ዲበ መትከፉ ለቃል ።
ድኅረ አረፍተ ጽልዕ ተነሥተ ውስተ እውደ ጽኑዕ ቀትል።
ለዋሕድ ቃል እምጣነ ያሮ ፤ ዲበዘበኑ መስቀል ።

ዕጣነ ሞገር

በኀሚሠ ልሕኵት ዘዔው ለፈውሰ ሕሙማን ማያት ።
ፃመወ ኤልሳዕ እምነቢያት ።
ባሕቱ እምሊባኖስ ማየ ተክለ አሚን መርዓት ።
ትወፅእ ለሕይወት ፤ እምጣነ ሕማማ ለጢሮስ ማየ ሊባኖስ ገነት ። ሖረ ኀበ ኢያሪኮ ኬልቄዶን ስፍሕት ።
ለቢታንያ ትዕግሥት ሕሊናከ ፤ ኢየሩሳሌም ቅርብት።
በኃሚሠ ትእምርት ብዙኅ እስመ ይትወሀብ ትእምርት ።
ኃይለ ሥላሴ ወልደ ዳዊት፤ወሥሉጥ ስምከ ንጉሠ ነገሥት።
ሀኀቤነ ወኵሉ ፍጥረት ።

የበዓላትና የአጽዋማት ማውጫ ።

በ፲፱፻፳፭ ዓ ም በዘመነ ማቴዎስ መስከረም ፩ቀን እሑድ ይውላል ። ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ቢቈጠር ፯ሺ ፬፻፳፭ ዓመት ሆነ ይኸነንም ፲፱ኙን እየተዉ ከ፳ው ፩እየያዙ ቢቈጥሩት ፲፭ ይተርፋል እንዱን ለዘመን ትቶ ፲፬ወንበር ይሆናል ። ፳፮ መጥቅ፥ ፬አበቅቴ ይሆናል።፩መዓልት፥ ፩ሕፀፅ፥ ፬አበቅቴን ቢያገናኙ ፮ ሌሊት ፬ጨረቃ ቢያክሉበት ፲ጨረቃ ይሆናል።

ጥር ፳፱ቀን ጾመ ነነዌ ። የካቲት ፲፫ቀን ዓቢይ ጾም ። መጋቢት ፲ ቀን ደብረ ዘይት።ሚያዝያ ፩ቀን ሆሣዕና።ሚያዝያ ፮ ቀን ስቅለት።ሚያዝያ ፰ቀን ትንሣኤ። ግንቦት ፪ ቀን ረክበ ካህናት።ግንቦት ፲፯ቀን ዕርገት።ግንቦት ፳፯ቀን ጰራቅሊጦስ። ግንቦት ፳፰ ቀን ጾመ ሐዋርያት።ግንቦት ፴ ቀን ጾመ ድኅነት ይሆናል

ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች የሕይወትና የሰላም ዓመት ያድርግላችሁ ይህንንም ጾም ለመጾምና ለየክብረ በዓሉ በሰላም ያድርሳችሁ ብሎ ይህችን ትንሽ ዕውቀቴን አክፍላለሁ ።

ቆም ጸሐፊ ገብረ ጻድቅ ።

የሞት መርዶ ።

ቀኛዝማች ወልደ ሥላሴ የልዑል ራስ መንገሻ ዮሐንስ የእናታቸው ልጅ ታናሽ ወንድማቸው መልከቸው ያማረ ጅግና ጸሎተ ወዳጅ ሰው አክባሪ ነበሩ።ግዛታቸውም ከትግሬ አውራጃ ከሽሬ ከፍ ያለውን ክፍል ይገዙ ነበር።በወንድማቸው በደጃች ግርማይና በጓታቸው ኃዘን ምክንያት ሰውነታቸው ስለ ተጐዳ አራት ወርያህል ታመው በተወለዱ በ፶፱ ዓመት በግንቦት ፳፪ ቀን ሙተው ቄየጻ በሚባል ገዳም በብዙ ክብር ተቀበሩ። ሁለተኛ በዓድዋ ከተማ ሰኔ ፲ቀን መኳንንቱና ሊቃውንቱ ካህናቱና ወይዛዝሩ ባላገሩ ከየአውራጃው ተሰብስቦ ክቡር ልጅ ፋሲል ሥዩም ተረድተው ታላቅ ልቅሶ ተደረገ። ደግሞ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ ነሐሴ ፴ቀን ልዑል ራስ ሥዩምና ክብርት ወይዘሮ አልማዝ፥ ክብርት ወይዘሮ አስቴር ተረድተው ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ተሰብስበው ታላቅ ኀዘን ተደረገ። ልጅ አበበ ተሰማ ነሐሴ ፲፪ቀን ስለሞቱ በዚሁ ቀንም ደግሞ ልዕልት ወይዘሮ ዓፀደ አስፋው ተረድተው ዋሉ።ልጅ አበበ ተሰማ ገና ጐበዝ የ፴፫ዓመት ዕድሜ ነበሩና እናታቸው ልዕልት ዓፀደ ሲያለቅሱ ላያቸው ያለ ልክ ያሳዝናሉ ልዑል ራስ ሥዩምና ልዕልት ባለቤታቸው ወይዘሮ ዓፀደ በሐዘን ስለ ሰነበቱ በአዲስ አበባ ያለው ዘመድ ወዳጃቸው ሲያስተዛዝናቸው ሰነበተ መቸም ለኀዘንም ለደስታም ጊዜ አለውና ልዑል ራስ ሥዩምንና ልዕልት ዓፀደን፥ ክብርት ወይዘሮ አልማዝንና ክብርት ወይዘሮ አስቴርን የቀሩትንም ኀዘንተኞች ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናቸው እላለሁ ።

ባላምባራስ በርሄ ዘደብረ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ።

የአቶ ደገፉ የሕይወት ታሪክ ባጭሩ ።

ንጉሥ ዘምቶ ነጋሪት ባልጮኸበት ባንዲራ ባልታየበት አገር ሁሉ፥ መንግሥት ካገለገሉትና ከደከሙት ሰዎች አንዱ አቶ ደገፉ ነበሩ። በሱማሌ፥ በኢሳ፥ በአዳል በርሃ ተርታ ነጋዴ እየመሰሉ ለሱማሌና ለአዳል ትንባሆና ግልድም ጉቦ እየሰጡ ሲዋጉም እየተዋጉ ሱሪ ቀርቶ አዳልና ሱማሌ መስለው ግልድም ታጥቀው ጋሻ ይዘው አባ ሚካኤል ሳበው የሚባል ጠመንጃ ተሸክመው አንድጊዜም ከደንከሉ እየሆኑ ከኢሳና ከሱማሌ እየተዋጉ ወደ ባሕር ያልፉ ነበር።የውጪ አገር ዕቃ ብርቅ በነበረ ጊዜ ለወንድ መሣሪያ ለሴት ጌጥ እያመጡ ሕዝቡን ደስ ያሰኙ ነበር ከባሕር ሲመለሱ አገር እያመሰገነ የአንኰበር አውራጃ ልጆች ሁሉ በዚሁ ጌጥ ይዘፍኑ ነበር።ዘፈኑም ይህ ነው

በረሃው አካሌ በረኸኛው። እንኳን ደህና ገባህ ልማደኛው።

በ፲፰፻፸፬ ዓ ም ሙሴ ቢሬም የሚባሉ ፈረንሳዊ በአንኰበር ስለነበሩ ሥራና ጥበብ እንዲማር ብለው ጃንሆይ አፄ ምኒልክ ሰጧቸው ብዙ ጊዜም ከቆዩ በኋላ ከሙሴ ቢሬም ተለይተው ከዶክተር ናርሲኒ ጋር ወደ አሰብ ሄደው ኖሩ ከዚያም በኋላ የመንግሥት ዕቃ ጭነው ከነአቶ መርሻ ጋር በዳዌና በዉፋ በኩል አድርገው ወደ አንኰበር መጡ። ከዚያም ተመልሰው

ወደ ሮማ ሒደው ብዙ ጊዜ ተቀመጡ ከብዙ ጊዜም በኋላ ወደ አገራቸው ተመልሰው ጃንሆይ አፄ ምኒልክ ባልደረብነታቸውን ለቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ሰጧቸው መጀመሻ ያራዳ ወህኒ ሲቆም ይኸንኑ አዲስ ሥራ ለማሠልጠን ዘበኞች ተመልምለው ፪፻ብረት ጨምረው ፣ሻንበል አድርገው ከቤተ መንግሥት በወጣ በማዕርግ ልብስ ሾሟቸው ከሐረርጌ ከመጡ ሱማሌዎች ጋር እየዞሩ ወስላታውንና ቀጣፊውን እየያዙ ለአራዳ ወህኒ አለቃ ሆነው ቆዩ።በ፲፰፻፺፰ ዓመተ ምሕረት ሙሴ ኢድልቢ በኢትዮጵያ ያለውን የላስቲክ ሞኖፖል ከጃንሆይ ከአፄ ምኒልክ ተቀብለው በወሰዱ ጊዜ ለዚሁ ሥራ ከፈረንጆች ጋራ ሆኖ የሚችል ሰው ሲፈለግ ጃንሆይ አፄ ምኒልክ አቶ ደገፋን መርጠው በመንግሥት በኩል ዋና ሹም አድርገው በገንዘቡና በወለጋ ሾሟቸው ባለውሎችም ወደ መንግሥት ያቀረቡትን አቶ ደገፋ ከመንግሥት ሆነው ተከራክረው መልሰዋል።ከዚሁም ሥራ ጋር በከርቴም በገንቤላ ለሚመጣ ለንግድ ዕቃ ሁሉ ከመንግሥት በኩል ዋና ሹም አደረጓቸው ይልቁንም ዲልቢ አቡዝዲድ በከርቴም በር በመጣ ጊዜ ባቶ ደገፋ ነበር በ፲፱፻፫ ዓ ምሕ በልጅ ኢያሱ ጊዜ ቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ የደጃችጆቴን አገር ተሹመው ልጅ ኢያሱ ከጊሚራ በኢልባቦር ወደደጃች ጆቴ አገር ሲያልፉ አቶደገፋ በሚገዙት አገር ውስጥ ሰዮ ላይ ሰፈር አደረጉ አቶ ደገፋ ያመጡትን የመስተንግዶ ብዛት አይተው የስንት መኳንንት መስተንግዶ ነው ብለው ጠየቁ የመሰቡ ልብስና የገንበው ልብስ መለዮ የተጻፈበት ስም የተነቀሰበት ደገፋ ደገፋ የሚል ስለሆነ የሳቸው ብቻ መሆኑ ታውቆ ለተከታዮቻቸው መኳንንትና ሠራዊት ተርፎ አደረ ። በዚሁ ምክንያት አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ የደጃች ጆቴን አገር ከቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ለደጃችጆቴ ሲመልሱ አቶ ደገፋ በርና ገባያን በስልክ ነጋድራስ ተብለው ደጅ ሳይጠኑ ተሾሙ።በ፲፱፻፯ ዓመተ ምሕረት ነጋድራስ ኢድልቢ ለሐረርጌ አውራጃ ነጋድራስነትና የድሬዳዋ ገጋ በተባሉ ጊዜ ሙሴ ኢድልቢ የውጭ አገር ሰው በመሆናቸው አቶ ደገፋ ሙሉ እንደራሴ ሆኑ ከዚህም ወዲህ የንግድ ሥራ ጀምረው ሲሰሩ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በሥራው ደግ ለሚሠራና ሐሳቡን በሥራ መንፈስ ላዘነበለ ሁሉ ረዳት ስለሆኑ አቶ ደገፋን በጀመሩት በንግድ ሥራቸው ለማጠንከር እርዳታ ለማድረግ በጠየቁትና በለመኑት ሁሉ ያለችግር ያቀኑላቸው ነበር ሆንም ንግድ አንድ ጊዜም ከጣራ አንድ ጊዜም ትርፍ ቢሆን እንደ ብዙ ሰዎች የጀመሩትን እንደማይጨርሱት ያሰቡትን እንደማይፈጽሙት ሳይሆን በያዙት ሥራ የሚደክሙ ናቸው ከምጽዋም ብዙ ሺህ ጆንያ ጨው ያስመጡ ነበር ።

በጂማም የንግድ ቤት ከፍተው እንደ ፈረንጅ ነጋዴ የንግድ ሥራ አቁመው ጀምረው ነበር በሚኖሩበትም ጊዜ ሁሉ የተጣላው ተሰብስቦ መታረቂያውና መስማሚያው እሳቸው ዘንድ ነበር ለትልቁ እንደወንድም ለትንሹ እንደ አባት ነበሩ ለአገራቸው ሰው በችግሩ ገቢና ረዳት በሥራ የሚያነቃቁ ነበሩ በአዲሱ ሥልጣኔ የተመሩና ከሰውም በስምምነት ከመኖር በተቀር ሥራ በያዙበት ሁሉ በፍቅር መኖር ስጦታቸው ነበር ። በኖሩበትም ዘመን ሰውን በፍቅር ለመሳብ በመብልና በመጠጥ በቤታቸው አኳኋን በድግሳቸው ማማር ግብዣቸው ለብዙ ጊዜ ይጠራል።ይልቁንም በየዓመቱ የመቤታችን ማኅበር በሆነ ጊዜ ድግሱ ሳያቋርጥ ከ፫ቀን እስከ ፲፫ቀን ይቆያል ይኸንኑም ድግስ ከልክ አሳልፈው የሚያደርጉት ምክንያቱ ከጨዋታና ከምሳሌ በተቀር ለሰው አልገለጹትም እንጂ ዕድሜአቸው ስለጸና እንደቁም ተስከር ያህል ነበር ።የመብሉና የመጠጡ የቤታቸው ሥርዓት ከአገራችን ይልቅ በአዲሱ ሥልጣኔ አኳኋን የሚዘጋጀው ልዩ ልዩ ዓይነት ስለሆነ ወዳጅ ዘመዳቸውን ደስ ያሰኝ ነበር ።ይኸውም ድግስ በሆነ ጊዜ የውጭ አገር ሰዎች እየተጠሩ በፈረንጅ ሥርዓት ተጋብዘው ስለደስታቸውም ብዛት በኤሌትሪክ ብርሃን በተዘጋጀው ቤት ዳንስ ተጫውተው በደስታ ይሔዱ ነበር ። ይኸውም ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን አገራቸውንም ማስመስገን ነው ። በመጨረሻውም ጊዜ የሐምሌ ወር የእመቤታችን ድግስ እቤታቸው ሆኖ ድግሱ ከልክ ያለፈ ነበር ። እሳቸውም እንደጨዋታ እያደረጉ የቁም ተስካሬ ነው እያሉ በጨዋታ ይናገሩ ነበር ። ከዚህ በላይ እንደ ተጻፈው የውጭን አገር ሰዎች በመልካም ጋብዘው ዳንስና ጨዋታ ተደርጎ ድግሱ የበረከተ ሆኖ ነበር ። ይኸውም ድግስ ከሆነ ወር ሳይሞላ ከዚህ በፊት በልስላሰ የቆየ የሱካር በሺታ የሚባል ስለነበረባቸው ይኸውም በሽታ ውሃ የሚያስጠማ የኩላሊት በሺታ ስለሆነ የሚመገቡት እህልና ውኃ እሆዳቸው ከገባ በኋላ በሽንታቸው ውሥጥ ወደሱካር ባሕርይ እየተለወጠ ሱካር እየሆነ ይወጣል ሐኪሞች በየጊዜያቱ ሽንታቸውን ሲመረምሩት ሱካር ይሆናል ። ይኸው በሽታ ከጥቂት ዓመት ጀምሮ ያማቸው ስለነበረ የዳኑ መስሏቸው ጥቂት ጊዜ ሳይታከሙ ቆይተው በእውከታ ምክንያት የተነሳ እንዠታቸው ቈሰለ ። ባንድሬትም ስርቅታና ነስር ስላፈታባቸው የጥንቱን በሽታ አስነስቶ ኃይል ሰጠው በዶክቶር በራ ሆፒታል ተኝተው በታመሙ በ፲ቀን በተወለዱ በ፶፫ዓመት ተመንፈቅ ሰኞ ነሐሴ ፳፫ቀን በ፮ሰዓት አረፉ ። መቃብራቸውም በዚሁ ዕለት ጴጥሮስ ወጳውሎስ ስለነበረ ቃሬዛው በወርቅ በተሰናዳ በማረጋሬ ሆኖ በመቶ አምሳ ያህል አቶሞቢል ታጅቦ በመቃብሩ ለዚሁ ሐዘን ተከፋይ በነበሩ ወዳጆቻቸው ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፥ ክቡር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት የገንዘብ ሚኒስትር፥ክቡር ብላቴን ጌታ ወልደ ማርያም ያገር ግዛት ሚኒስትር፥ ዋና ዲሬክተርና የውል መርማሪ፥ክቡር ብላታ አየለ ገብሬ የልዩ ፍርድ ቤት ዋና ዳኛ፥ ክቡር አቶ በላቸው የምድር ባቡር ተቆጣጣሪ፥ ሌሎችም ቊጥራቸው የበዛ ሴት ወይዘሮና መኳንንት ሆነው በታላቅ ክብር ተቀበሩ።

ሁሉም በወገኑ ሲመክ ሲሰፋፉ ። እኔን የሚረዳ ደገፋዬ ጠፋ ። እናት አባት ብዬ በልቤ እያሰብሁህ። እንግዲህ ቀረህ ወደ ደገፋዬ ስልህ ። ለብዙ ሰው ሁሉ ነበረ ደገፋ ። ከዛሬ ቀን እንተን የሚያድንህ ጠፋ ። ለሁሉ ደገፋ የነበርህ ሰው። ሳያስበው ደርሶ ቀን አፈረሰው። ሐሳባችን ሁሉ ሆነብን እንደ ሕልም ። ምንም ብናስብህ ቀን አይመልስህም ።

አስተምረው ያሳደጉት ልጃቸው ኪዳነ ማርያም

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት

ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር	
የቅ ዮ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር	
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፰	ብር	
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር	
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲	ብር	
፫ቱ መጻሕፍተ መነኮሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪	ብር	
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪	ብር	
ዶስታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፱	ብር	
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር	
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር	
የዓለም ጅዮግራፊ ከነካርታው	፯	ብር	
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፯	ብር	
ድርሳነ ሚከኤል	፯	ብር	
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር	
ጎሀ ጽባሕ	፭	ብር	
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር	
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር	
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪	ብር	፳መ
የእርሻ ትምህርት	፩	ብር	፳መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ እጅግ ያማረ	፪	ብር	
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር	
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር	
የቍጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩	ብር	
የአማርኛ ሰዋስው	፩	ብር	
መንግሥትና የሕዝብ አስታዳደር	፩	ብር	
የነግ ደንብ ከነተጨማሪው	፩	ብር	፳መ
የብድር ደንብ	፩	ብር	
የጦር መሣሪያ ደንብ አዲስ	፩	ብር	፳መ
የገዳም ደንብ	፩	ብር	
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩	ብር	
ዮሐንስ ቡንያን	፩	ብር	
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፭	ብር	
የ፪ኛ	፳	ብር	
የ፫ኛ	፲፭	ብር	
የ፬ኛ	፲	ብር	
የ፭ ኛ	፯	ብር	
የ፮ኛ	፯	ብር	
የ፯ኛ	፯	ብር	
፳፬ ካርት ፖስታል	፩	ብር	
የረኮማንዴ ደብተር	፫	ብር	
ሕገ መንግሥት	፭	ብር	
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳	መሐ	
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን ነገ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፳	መሐ	
አጭር የዓለም ታሪክ	፳	መሐ	
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተስማማ	፳	መሐ	
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፳	መሐ	
ያማርኛ ምሳሌ	፳	መሐ	
አሳብና ምኞት	፲	መሐ	
የፍቅር መላክት	፲	መሐ	
ትምህርተ ሕፃናት	፰	መሐ	
የምሕረት አዋጅ	፲	መሐ	
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪	መሐ	
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪	መሐ	
የንቍጣጣሽ ግጥም	፪	መሐ	
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፪	መሐ	
፩ ጋዜጣ	፪	መሐ	
አርስጣላብ	፲	መሐ	
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፲	መሐ	
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለውዘድ	፲	መሐ	
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፭	መሐ	
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፭	መሐ	
ካላንድሬ	፳	መሐ	
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪ	፭	መሐ	
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፳	መሐ	
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፲	መሐ	

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት እጥፍ ። ነጠላ በያይነቱ ። እርሳስ መንኮልና ብረት ብርዕ ቀለም በያይነቱ። የካርት ቢዚት እንቦልብና ካርት ቢዚት በያይነቱ ። እንቦልብ ትልቅና ትንሹ በያይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር አ ብሩንስ በፊት በድሬ ዳዋ ማዘጋጃ ቤት የመንግሥት ሐኪም የነበረ ዛሬ በአዲስ አበባ መጥቶ የሕክምና ሥራ መሥራት መጀመሩን ለሕዝብ ሁሉ ያስታውቃል። ማከሚያ ቤቱም አራዳ እሙሴ ዛሳን ጕን ቀድሞ ዶክተር ማየቤርገር እሚሰራበት ቤት ውሥጥ ነው የሚገኘውም ጧት ከ፫ ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩል ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲ ሰዓት ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደዱም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ ፥ የደረት የጕበት ፥ የኩላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቍቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አስናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወከሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት።ከዚሁም አንዱ አርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዳች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ካገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ እስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃማሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪል ነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፴፰
8me ANNE. № 38

ሐሙስ መስከረም ፭ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 15 Septembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሓፊነቱ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የዘመን መለወጥ ።

በየዓመቱ በመስከረም ፩ቀን የዘመን መለወጫ ቀን ይበላል ። የኢትዮጵያና የግብፅ ሊቃውንት መስከረምን የዓመት መጀመሪያ አድርገውታል ፥ የሮፓ ሊቃውንት ግን ጥርን የዓመትመጀመሪያ አድርገውታል ። በእኛም በነሱም ዘንድ በዚህ በዘመንመለወጫ ቀን እንኳን ከዚህ አደረሳችሁ እየተባባለ ዘመድ ከዘመዱ፥ ሎሌ ከጌታው፥ ወዳጅ ከወዳጁ ይጠያየቃል ። በዚሁም በአዲስ ዓመት አዲስ ታናሽ ስጦታ ይሰጣጣል ። ይህም ታናሽ ስጦታ ደስ የሚያሰኝ አዲስ ስጦታ ይስጥህ ብሎ እንደመመረቅ ነው እንጂ የጥቅም ስጦታ አይደለም ። ዛሬም በዚሁ ልማድ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንኳን ከዚህ ዓመት አደረሰዎ ለማለት የሚመጡትን መሳፍንቱንና መኳንንቱን ሕዝቡንና ሠራዊቱን ለመቀበል በታላቁ አልፍኝ በመንበረ ዳዊት ተቀምጠው በሌላው ጊዜ አልፍኝ ለመግባት ያልተፈቀደለት ሁሉ ተፈቅዶለት ሲገባ መቸም የአማርኛ ቋንቋችን ሰምና ወረቅ ሁኖ እንደቅኔ በሁለት ወገን ይተረጐማልና በየዓመቱ የሚነገረውን አስመስሎ እንኳን ከዚህ አደረሰህ እየተባባለ ይጫዋወት ነበር። ምሥጢሩን የሚሰማውም ይደነቅ ነበር። ምሥጢሩንም የማይሰማ ለአዲሱ ዓመት የሚነገረውን ቃል የተነገረ መስሎት አሜን ብሎ ያልፍ ነበረ ። እንግዲህ ወደቁም ነገሩ እንመለስ ። በላይኛው መስመር እንደአመለከትነው እነሱቹ አበባውንም ሥዕሉንም እየያዙ የሚበዙትም እንዲያው ባዶ እጃቸውን እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገረዎ ይሉ ነበር። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም የያዙትንና ያልያዙትንም አሜን እናንተንም እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገራችሁ እያሉ በደስታ ሰላምታ ይሰጡ ነበር ። ሕዝቡም እየተሰናበተ ከአልፍኝ ከወጣ በኋላ ጃንሆይ በታላቁ አዳራሽ ተቀምጠው ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለሊቃውንቱና ለሠራዊቱ ታላቅ ግብር አድርገው ዋሉ ። የሆዳቸውን ልክ የማያውቁትም ሰዎች ከአዳራሽ ወጥተው በየቤታቸው ሲመለሱ በባቡር መንገድ ለሚሔደው ሰው ሁሉ ትያትር ሁነው አመሹ ይልቁንም ከሹማምት ወገን የሆኑ ወታደሮቻቸውን አስከትለው ከፍ ከፍ ባሉ በቅሎዎቻቸው ተቀምጠው እንደ ሕፃናት በግራና በቀኝ ተገድፈው እየተዘናበሉ ሲሔዱ እጅግ ያስደንቅ ነበር ። እወን ከዚህ የበለጠ የሚያስደንቅ ነገር የት ይገኛል ። ድሀስ እቤቱ የሌለው ጥሬት የቋጠረሁ መስሎት ቢሰክር መቸም ድሀ ነውና አይፈረድበትም ሀብት ያለው ከቤቱ የሚገኘውን ከሰው ቤት ሲአገኘው በኋላ አገኘው ይሆናልና አሁን የሰው ገንዘብነቱን ብቻ ተመልክቶ በመጠጡ ብጨክንበት ነውሬን ይገልጽብኛል ኢማዕርጌም ያዋርደኛል አለማለቱ በእንዴት ያለ መከደኛ ተከድኖ በእንዴት ያለ ማሽጋ ልቡ ተደፍኖ ተመርጎ ይሆን የቸገረ ነገር ሆን ግብር ይቅር እንዳይባል የወታደሩ ልብ የተሰቀለበት ነውና አይሆንም።ለክቶ መጥኖ እንዳይሰጡት የሆዳቸውን ልክ ለማያውቁ ሰዎች የንፍገት ሊመስላቸው ሆነ ።

እንደዚሁ እንዳለው ይቆይና ከሠራዊቱ ልኩን የሚአውቀው ሲበዛ ይተወዋል ። ልኩንሳ እንዲአውቅ ምን ማድረግ ይሻላል ትለኝ እንደሆነ ልጅ ልጁን በየተማሪቤቱ አግብቶ ደህና ደህና የኢትዮጵያን መምህራን ቀጥሮ ማስተማር ነው ። ለታላላቁ ግን ደህና ደህና ሰባኪ አቁሞ የጥቅምንና የጉዳትን ነገር ለይቶ የሚአስታውቅ ማድረግ ነው የሰው ተፈጥሮው ፭ነው ብልሓው ግን ከማየትና ከመስማት የተነሣ ነውና የጀግኖችንም ታሪክ የሀገርንም ፍቅር ቢሰብኩለት ጥቅም መሆኑ የማይጠረጠር ነገር ነውና በዚህ ነገር የጦር ሚኒስትሩ ቢተጉበት ለሀገር መጠቀሚያ ለሚኒስትርም ለዘለዓለም መታሰቢያ መሆኑን እናሳስባለን ።

ለሰሚው ግራ ።

የቀድሞ ተረት ተልባ በቅባኑግ ለሰሚው ግራ ነው ለበዩ መልክም ነው ተብሎ ሲተረት አሰት ይመስለን ነበር ለካስ እውነት ኑሯል።ተልባ ቅባት አለው ቅባኑግም ጣፋጭ ቅባት አለው በዩ ለውዬ ሁለቱንም አደባልቆ ቢበላ ቅባት ተጨመረለት እንጂ ጉዳት አላገኘውም ማለት ነው።ይህንም ያልነበትን ምክንያት ቀጥለን እንጽፋለን። አንድ የውጪ አገር ሰው በውጪ አገር ቋንቋ ከተጻፉት መጻሕፍት ደህና ደህናዎችን ወደ አማርኛ ተርጕሚ ፭፻ ሺህ ብር ስጡኝ ብሎ ለጃንሆይ አስታውቆ ነገሩ የሚጠቅም እንደሆነ መክራችሁ አስታውቁኝ ስላሉ ለዚሁ

ጉባኤ ሰዎች ተመርጠው ነገሩን ጀምረውታል ። ደገርማል አማርኛ አያውቅ ቢአውቅ እንኳ አማርኛ እንኳን ለውጪ ሰው ለተወለዱበት ሰዎች እንኳ ልቡ አልገኝ ብሎ ወዲህ ሲሉት ወዲያ እየዞረ አስቸግሮአል ። አሁን ይህ ሰው ይህን ውል ቢአገኝ የኢትዮጵያን ልጆች በጥቂት በጥቂት ዋጋ ቀጥሮ የተቻላቸውን ያህል ተርጕመው ሲሰጡት ያነን ሰጥቶ የቀረውንም ጨርስ ሲሉት በቆንስሉ ብሎ ጠበቃውን ገዝቶ ተሟግቶ ገንዘቡን ቋጥሮ ወደ አገሩ ሲገባ ምን ይደረጋልን።

በልዩ ልዩ ሞኖፖሎች በናዝን ደግሞ ቋንቋችንን ሞኖፖል ሊአደርግብን በማሰቡ ተደንቀን ዳፍን እንጂ እነዚህ ለዚህ ነገር ጉባኤ የሆኑት ሰዎች ብልሆች ከጥቅማቸው ይልቅ ለሀገራቸው አሳቢዎች መሆናቸውን አጥተነው አይደለም ። ይልቁንስ የሚአሳዝነን ብዙ ሥራ ያላቸው ሰዎች በዚህ በማይረባው ነገር ፫ ፬ ቀን ሥራ መፍታታቸው ነው ። የኢትዮጵያ መንግሥት ብዙ ገንዘብ አጥፍቶ ያስተማራቸው ልጆቻችን አሉ ። ይልቁንስ መልከም መልከም በታና ደህና ደመወዝ ሰጥቶ ማሰራት እንዲሻል ጥርጥር የለበትም ነገር ግን ገንዘባችን ሁልጊዜ ከዘመድ ወደባዕድ እያደላ አስቸግሮአልና ምናልባት ደቀናው ይሆን? የሰውዩውን ስምና አገሩን ለዚሁ ሥራ የተመረጡትን ሰዎች ስም ይህ አሳብ በተፈጸመጊዜ እናስታውቃችኋለን ።

ማስጠንቀቂያ ።

ይድረስ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎችና ወዳጆች ደግሞ ዕውቀት ለሞላቸው መኳንንቶች ዕድሜና ጤና ፥ ፍቅርና ምስጋና ይስጣችሁ እግዚአብሔር አሜን ብዬ የምጽፈው ከመቶ ቃል አንድ ቃል ይገኝበታል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነው።የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ ፈረንጆች ገንዘባቸውን ነስንሰው ነጭ ለብሰው በኢትዮጵያ ምድር ሲመላለሱ እየዩዋቸው እንደነሱ ሊሆኑ ዘመዶቻቸውን ትተው በከርቱም ዓባይን ተከትለው ወደ ምስር ብተው ሥራ ይፈልጉና ሥራ ሲያጡ በችግርና በማጣት ምክንያት ወደገጠር እየወጡ ዘመድ ይፈልጋሉ ዘመድም በመት አንድ ቀን ሁለት ቀን እንጂ በሁልቀን አይገኝም በልጆቻችን ብዛትና ስለ ዘመድ መፈለጋቸው እጅግ የሚያሳዝን ነበረ በዚሁ ልማድ ወርቁ ደስታ የሚባል ልጅ ከጅቡቲ በመርከብ ተደብቆ ወደ ምስር ገባ ። ሁለት ዓመት ሁኖት ነበር ነገር ግን የኢትዮጵያ ዜግነቱን የሚያስታውቅለት ከጅቡቲው ቆንስል ፓስፖር አምጥቶ ነበር ይህም ልጅ ሥራውን ጨርሶ በቡና ቤት ተቀምጦ ሳለ እንግዳ ሰው እየፈለጉ ወዳገሩ የሚሰዱ ዘበኞች እሱንና ከከርቱም የመጣ ወንድሙን ገብረ መስቀልን በሰኔ ፲፪ ቀን ያዙዋቸውና እኔ ሰምቸ ሂጄ ነገሩን ብጠይቃቸው የውጭ አገር ልጆች ናቸው አገራቸው ልንሰዳቸው ትእዛዝ አለብን አሉን የያዘውንም ፓስፖር ብናሳያቸው በግድ የሚሳፈር ነው አሉን በ፲፱ ሰኔ ወደ ሐከማዶር ሔድን አሳቸውም ከፖርት ሰዒድ እስከ ስዊስ የዘበኛ አለቃ ናቸው የወርቁን ፓስፖር አቀረብሁላቸው እኔ እንግዳ እንዳይገባ ዘበኛና የዘበኛ አለቃ ነኝና ወደ ካይሮበወዛራት ደክሊያ በቴሌፎን ልጠይቃቸው በሰኔ ፳ቀን ሰኞ ናና ከምስር የመጣልኝን ለምስተር ሴቢ እነግርልሃለሁ አሉኝ እንደ ቀጠሮዋችን የፓስፖር ዘበኞች ሔጄ ስለ ወርቁ ደስታ ምን ወሬ አገኛችሁ ብዬ ብጠይቃቸው የመጣልን ትእዛዝ የኛ ልጆች ሥራ አጥተው በችግር ሳሉ የውጭ ሰው እንዳይሠራ ወዳገሩ እንዲመለስ ከብዙ ወራት ጀምረን ያቆምነው የረጋ ደምብ ነውና ወዳገራቸው መልሱዋቸው የሚል ቃል ስለ መጣላቸው በሰኔ ፳ ቀን ወደ ጂቡቲ ሰደዱዋቸው ከዚህ በምስራውያን እጅ ተይዘው ወደ ጅቡቲ የሔዱትን የጅቡቲ ቆንስል እንዳይቀበልዋቸው የሚረጋ ደንብ ያስፈልጋቸዋል በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን የነበሩ ቆንስል አቶ ዮሴፍ ስለሁለት ሰዎች ፓስፖር እንዲልኩልን ጽፌንላቸው ነበር ያለ ፈቃድ የወጣውን አናውቀውም ይህ በኢትዮጵያ መንግሥት የረጋ ደንብ ነው ብለው ጽፈውልኝ ነበር ሁለተኛ ደግሞ ያለ ፓስፖር የእንግሊዝ መንግሥት ወደምስር ሊገቡ የሚፈቅድላቸው የምስር መንግሥት ከደረታቸው ከሐልፋ ሳይመልሳቸው አገራቸው ከገቡ እያሠሩ ቢሰዱዋቸው ከማራቸውን እንዲችሉ ቶሎ ብሎ ወደፊት ረግቶ የሚኖር ደምብ ማቆም ያስፈልገናልና አሁንም ከከርቱም ሐልፋ ከሐልፋ አስዋን የሚባል ሁለት በሮች አልፈው በፖርት ሰዒድ በር ተይዘው ወደጂቡቲ እንዳይወርዱና የፈረንሣዊ መንግሥት የፓስፖር ዘበኛ እንዳይቀበላቸው ተቀብሎ እንዳያወርዳቸው ከዛሬ ወደፊት የሚረጋ ደምብ ማቆም የግድ አለብን ከጂቡቲ ወደፖርት ሰዒድ ከመለሱዋቸው ከሐልፋና ከስዋን በር አልፈው ወደምስር ሊገቡ አይፈቅዱላቸውም ይህን ነገርም ለምስር መንግሥት በጣም ማስጠንቀቅ ያስፈልገናል ከምስር ወደፖርት ሰዒድ እየመጡ ወደ ምስር ይመለሳሉ ከማስርት የፈሩ በኩለ ቀን ገብተው ሲመሽ ይመለሳሉ ማደርያና የሚባሉት እያጡ ስናያቸው ድካማቸውንና ኀዘናቸውን እንካፈላለን አሁንም እኛ ባይናችን ከምናየው መንግሥት በልቡ የሚያየው ይበልጣል ።

ማርቆስ ወልደ ጊዮርጊስ ዘፖርት ሰዒድ ።

ስለ ትምህርት

ኢትዮጵያን ለማሠልጠን በየዓመቱ ብዙ ልጆች ወደ አውሮፓና ወደ አሜሪካ መስደድ ያስፈልጋል ይኸንንም ለማድረግ የሚከተሉት ሶስት ዋና ነገሮች ያስፈልጋሉ ።

መጀመሪያ ዩኒቬርሲቲ የሚያስገባ ተማሪ ቤት ማቆም ወይም የቆሙትን ተማሪ ቤቶች እዚያ ደረጃ ማድረስ ።

ሁለተኛ ፤ ብልሆች ልጆች በትምህርታቸውና በፈተና መምረጥ ።

ሶስተኛ ፤ በዓመት በዓመቱ ከውጭ አገር ሒደው ለሚማሩ ተማሪዎች የሚያስፈልገውን ገንዘብ መቁረጥና በትክክል መስደድ ።

፩ኛ ፤ ለኢትዮጵያ ማሠልጠኛ በአውሮፓ ደንብ ተማሪ ቤት ተተከፈተ ብዙ ቀን ነው ነገር ግን እስካሁን ድረስ አንድም ተማሪ እንኳ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ተማሪ ቤት የጨረሰ የለም። ተማሪ ያንዱን ዓመት ትምህርት ሶስት አራት ዓመት ያጠፋበታል ምክንያቱም በመጀመሪያው ዓመት ይህን

ይጨርሳል፣ በሁለተኛው ዓመት ይህን ይጨርሳል ተብሎ የተወሰነ የትምህርት ደንብ ስለሌለና ደህና የሚችሉ አስተማሪዎችና አስኪያጆች ስለሌሉ ነው እንጂ ሌላ ምክንያት የለውም ።

ታሁን ቀድሞ በጋዜጣችን በልዩ ልዩ ሥፍራና በአዲስ አበባም ብዙ የትምህርት ቤቶች መከፈታቸውን አንብበናል፣ ነገር ግን የትምህርት ቤቶቹ አስኪያጆቹና አስተማሪዎቹ ፊደል የቆጠሩና አንድ ሁለት የውጭ አገር ቋንቋ ማልኰስኰስ የቻሉ ስለሆኑ ማለት በጭሩ አስተማሮቹ እነርሱ ራሳቸው ማይምን ስለሆኑ ተማሮቹ ምንም እንደማይጠቀሙ ማንም ያየዋል፣ ይህንንም ማለቴ የአገሬን ልጆች ለማስተማር የቻሉትንና ከውጭ አገርም ሰዎች ተቀጥረው የሚያስተምሩትን ለመስደብ ስላማረኝ አይደለም ነገር ግን እውነት ትምህርት እንዲሰፋ ሕዝባችን እንዲሠለጥን የምናስብ እንዲሁ ዩኒቬርሲቲ የጨረሱ አስተማሮች መቅጠር የግድ እንዳለብን ለማስረዳት ነው እንጂ አለበለዚያ የማብር ይውጣ ሥራ ይመስልብናል ዕውር ዕውርን ቢመራ ተያይዞ ገደል ነው ስለዚህ አሁን የሚያስፈልገን ደህና ደህና ዩኒቬርሲቲ የጨረሱ አስተማሮች ለልዩ ልዩ ተማሪ ቤቶች መንግሥት ቀጥሮ ማስተማርና ቢያንስ ቢያንስ ከዚያ ለሚጨርሱ ተማሪዎች በአውሮፓና በአሜሪካ በማነኛውም ዩኒቬርሲቲዎች የሚያስገባ የምስክር ወረቀት መስጠት ያስፈልጋል። ይህ የሆነ እንደሁ የአገራችን ልጆች በአራት ዓመት ማንኛውንም ሥራ በዩኒቬርሲቲ ጨርሰው ለመመለስ ይችላሉ እንደቀድሞ አሥር አሥራ ሶስት ዓመት ያህል መድከምና ብዙ ገንዘብ ማከሰር ይቀራል ።

፪ተኛ ፤ መንግሥት ወደውጭ አገር የሚሰዳቸውን ተማሪዎች ፊት በተማሪ ቤት ሳሉ በትምህርታቸው በጣም ብልሆች የሆኑትንና የተለዩ ፈተና ያለፉ ብቻ ነው እንጂ እንዲያው ብጋጣሚ ያለፈተና ወይም በማላጅ ብዛት አይሆንም የማይችሉ ተማሪዎች የሔዱ እንደሁ በየጊዜው እየወደቁ በትምህርታቸው ሳይቀናቸውና ብዙ ዓመት ኖረው የመንግሥትም ገንዘብ ብዙ ፈሶላቸው በመጨረሻውም ምንም ሳይዙ ይመለሳሉ ከተመለሱም በኋላ እነሱን ያየ ሕዝብ ምን ተምረው መጡ እንዲያው በከንቱ የመንግሥት ገንዘብ ጠፍቶላቸው መጡ እያለ መንግሥትን ያጸከማል ትምህርትንም ለሚጣረሩ ሰዎች ደጋፊ ይሆናል ልዩ ልዩ ጉዳቱ ግልጽ ነው ለመንግሥትም ለሕዝብም ከዚህ በተረፈ ደግሞ በፈተና ያለፉና የተመረጡ ብልሆች ልጆች ሁሉ ሳይሔዱ በሐኪም ጤናቸውን ተመርምረው የጤንነት ምስክር ወረቀት መቀበል ያስፈልጋቸዋል ጤናቸው ደህና ያልሆኑ ልጆች ወደውጪ አገር ከሄዱ በኋላና ብዙ ገንዘብ ከጠፋላቸው በኋላ ማንኛውም ቀላል በሽታ ቢይዛቸው ጠንካሮች ስላልሆኑ ይሞታሉ ጉዳቱ ለሕዝብና ለመንግሥት መሆኑን ማንም ያየዋል ።

፫ተኛ ፤ በውጭ አገር ሔደው ለሚማሩ ልጆች ባመት ይህን ያህል ገንዘብ ተብሎ መቁረጥ ያስፈልጋል ከዚህ በኋላ ለተማሮቹ ወደያሉበት የያንዳንዱን ዓመት ኪሣራ በዓመት አንድ ጊዜ በተቆረጠ ቀን መላክ ነው ይህም የሆነ እንደሁ ወደውጭ አገር የሚሔዱትን ተማሮች በየጊዜው ለማብዛት በቀላል ይቻላል ማለት ተማሮች ጨርሰው ሲመለሱ በነሱ ሥፍራ ሌሎች መስደድ ይቻላል ለምን መንግሥት አንድ ጊዜ ለትምህርት የቆረጠው ገንዘብ የታወቀ ስለሆነ ነው ከዚህም በቀረ ለያንዳንዱ ተማሪ የዓመቱ ኪሣራ አንድ ጊዜ የሔደለት እንደሁ ተማሪው ከብዙ ሥጋትና ገንዘብ በማጣት ከዩኒቬርሲቲው ወጥቶ ያለትምህርት ጊዜያቱን ከማጥፋት መቀጮ ከመከፈል በሚገባውም ጊዜ የሚጨርሰውን ትምህርት በገንዘብ የተነሣ እዩተጓጉለ ዓመት ሁለት ዓመት ከማጥፋት ይድናል፤ ይህ ለኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ትልቅ ጉዳቱ ነው ይህን መጻፌ ጊዜ ማጥፋትና ጋዜጣ መጻፍ ስላማረኝ አይደለም በዚህ ሥራ ውስጥ ያሉ ሹማምንት ነገሩን ቀስ ብለው በጥንቃቄ እንዲያስቡበትና ወደፊቱ ደግሞ ለሕዝባቸውና ለመንግሥታቸው የበለጠ ጉዳት እንዳይሆን ነገሩን በፍጥነት እንዲያስተካክሉት ነው እንጂ ይህንንም በደስታ እንዲያደርጉት በፍጹም ልቤ አምናለሁ ።

መኰንን ደስታ ።

ሠርግ።

በነሐሴ ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም ልጅ ተፈራ የሙሴ ማብሪከስ የቁማር አጫዋች ከወይዘሮ ፈለቀች ካሣ ጋራ ሲጋቡ የድግሱ መበርከት የባልንጀሮቹ መብዛት ከልክ ያለፈ ሁኖ ከዚህ በላይ ከጻፍኩት ቀን እንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ዘወትር ገፈርሳ በአቶሞቢል እየሔዱ ሲመለሱ ከተማውን በቀን አሥር ጊዜ ይዞሩታል ። ቤታቸውም የተሰናዳ የእቴጌ ሳንቃ በሚሸጥበት ውሥጥ ፫ቱን ክፍል ፎቅ በሙሉ ግቢውን ይዘውት ወጪና ወራጁ እነሱን በማየት በመንገዱ ሰው ሊተላለፍ አቃተው ሙዚውም አቶ ብዕዓት ገዝሙ ስለ ሆነ ወይዘሮ ነገደን ለሙሽሪዋ አጫዋች አድርጎ የገንዘቡ አለማለቅ አዝማሪ በአቶሞቢል እያመላለሰ ሲያጫውታቸው ይውላል ምናልባት የቤቱ ጠጅ ቢያልቅ እንኳን ከውጪ በቀን እስከ ሃያ ብር ድረስ እየተገዛ ይኸውም በአቶሞቢል ነው የሚመላለሰው የደስታቸው ብዛት አቶሞቢሉ ውስጥ ጠጅ በብርሌ ይጠጣል ደግሞ ያሉበት ቤት ለባልንጀሮቹና ላገልጋዮቹ የማይበቃ ስለሆነ ሌላ ቤት ለመከራየት አሳብ አድርጓል ። ልጅም ወልደው ከብደው በፍቅር እስኪያረጁ ድረስ ያኑራችው እያልሁ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አስታውቃለሁ ።

ስሜ እንደሻው ።

ስለ ጥና ምርመራ ዘበኞች ትጋት

የጥና ምርመራ ዘበኞች ከዚህ ቀደም በየጊዜው በብርሃንና ሰላም እንደተነገረው ሁሉ በትጋታቸው ላይ ትጋት እየጨመሩ በእውቀት እየደረጁ ለከተማው ሕዝብ የሠሩትን ውለታ ሳይበዛ ባጭሩ እንደሚከተለው እናሳያለን ።

፩ኛ ፤ በነሐሴ ፫ቀን ከቀኑ በ፲፩ሰዓት ወልደ ማርያምና የሱፍ ማሞ የሚባሉትን ሌቦች ከሙሴ ከምቷር ቤት ፶ጣቃ አቡጀዲድ ሰርቀው ከሙጃ ውስጥ ከደበቁት በኋላ ሳይውል ሳያድር የዚያኑለት የምርመራ ዘበኞች የሌቦቹን ፍለጋ ተከ-

ታትለው የተሰረቀውን ጣቃና ሌቦቹን ባንድነት ይዘው መስረቃቸውን ከምኑ በኋላ ወደፍርድ ቤት አሳልፈዋቸዋል ።

፪ኛ ፡ ሙሄ የሚባል የዱባሰን የዝናብ ልብስ ሠርቆ ይዞ ሲሄድ ይዘዋል ።

፫ኛ ፡ በነሐሴ ፳፫ቀን ጉዶታ የሚባለው ሌሊት የሰው ቤት ሰብሮ ሊገባ ግና ሲቆፍር በድንገት ደርሰው ይዘውታል

፬ኛ ፡ በነሐሴ ፳፬ቀን ባልቻና ተስፋ የሚባሉት የኩሊን ጫማ ሠርቀው ሲሄዱ ይዘዋቸዋል።

፭ኛ ፡ በነሐሴ ፳፬ቀን አየለ ቀጭኑ ወልዴና ግርማ መሐመድ እነዚህ አምስቱ ከላይኛው ግቢ ዕቃ ሠርቀው ሲሔዱ በጥርጣሬ የዋና ምርመራ ዘበኞች ይዘው ቢመረምሩዋቸው መስረቃቸውን አምነዋል ።

፮ኛ ፡ አሰሰና አዲቶ የሚባሉት ሙሉ ልብስ ሠርቀው ለመሸጥ ሲያስማሙ ተይዘዋል ።

፯ኛ ፡ ፍሪሲዶ የሚባል ሌባ ደስታ የሚባለውን ሰው ሱሪ ሲሠርቅ በምርምር አግኝተው ይዘውታል ።

፰ኛ ፡ ወልደ ሚካኤል የሚባለው ሙሴ ከከሬን ለሥራ ያቀረቧቸውንብዙ አያሌ ብረታ ብረቶች ሠርቆ ለገብረ ሰንበት ሲሸጥ አግኝተው ይዘውታል ።

፱ኛ ፡ በነሐሴ ፴ቀን ሌሊት መርጊያ የሚባለው ሌባ የቀድሞ ጌታው የነበሩትን የሙሴ ማግስ አዝናውርያንን ቤት በሚያውቀው ስፍራ መሬ ሆኖ ከብዙ ጓደኞቹ ጋራ ሰብሮ ዕቃውን ሁሉ ሠርቆ ሲወጣ ከበሩ ላይ የዋና ምርመራ ዘበኞች በድንገት ደርሰው ተያዝ ቢሉት አልያዝም ብሎ ሲሸሽ በሽጉጥ ስለመቱት የሰረቀውን ዕቃ እንደያዘ ሞቶ ተገኝቷል ይህነንም የትጋት ሥራ በመሥራታቸው የ ተገባ ሽልማታቸውን እንዲያገኙ ተፈቅዶላቸዋል

እንግዲህ የዋና ምርመራ ዘበኞች ከዚህ በላይ እንዳመለከትነውና ይልቁንም ከዚህ ቀደም በብርሃንና ሰላም እንደተነገረው ሁሉ ይህነን የትጋት ሥራ ለመሥራት የበቁት አለቃቸው የሰለላውን ሥራ በልዩ ልዩ ብልሃት እያስረዳ ለትጋቱ ሥራ መሬ ስለሆናቸውነውና ስለዚህ የዋና ምርመራ ዘበኞችን አለቃ ትጋት ማሳሰብ ይገባናል ።

ከዚህ ሌላ ደግሞ ስለ ከተማ ዘበኞች ትጋት ።

ከሁን ቀደም በ፳ኛው ዓመት በቍጥር ፴፯ብርሃንና ሰላም እንደ አመለከትነው ሁሉ ሙላቱና ሙዛይ ቦጋለ የሚባሉ ሌቦች ለጊዜው ሳይያዙ ቆይተው ነበርና በጳጉሜ ፫ቀን የሌሎች ሌቦች ምርመራው ከተፈጸመ በኋላ ለስለላ ታዘው የነበሩት ዘበኞች እነዚህኑ ሙላቱና ሙዛይ ቦጋለ የሚባሉትን ፫ቱን ሌቦች ይዘው ወደዘበኛው አለቃ ዘንድ ባቀረቧቸው ጊዜ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ያደረጉትን የስርቆታቸውን እኳኋን ለዘበኛው አላቃ እንደተናገሩት ሁሉ ከዚህ ቀጥሎ ጽፈነዋል ።

፩ኛ)ከፈታውራሪ ተፈሪ ቤት ከሠረቅነው መሣሪያ ሌላ ከዚህ በፊት ከመሐመድ አሊ ኩምፓንያ ቤት ፫ትልልቅ ምን ጣፍ ፪የጥጥ ፍራሾች ፪ያልጋ ልብሶች ፅድንኳን ሰረቅን ምን ጣፉን እስተሊዮ ለሚባል ግሪክ ሸጠነዋል ።

፪ኛ ፡ ከወይዘሮ አበበች መሸሻ ቤት በያይነቱ የወንድ መሣሪያዎችና የሴት መሣሪያዎች ሌሎችንም ልዩ ልዩ ዕቃዎች ሰርቀናል ።

፫ኛ ፡ ጉስሌ ያለቃ ልሳነ ወርቅን ፪አህዮች ሠርቀናል ብለው ፫ቱም ሌቦች ባንድ ቃል አስረድተው ቅጣታቸውን እንደ ደንቡ እስቲቀበሉ ድረስ በዘብጥያ ታስረው እንዲቆዩ ወደዘብጥያ ዘበኞች ተላልፈዋል ። የተሠረቁትም ዕቃዎች ከተሸጡበት ቤት ጥቂቶች ያህል እየተገኙ ተይዘዋል ።

ጠቅላዩ ዋናው የዘበኞች አለቃና የምሥጢር ሰላዮች አለቃ በዚህ ነገር እጅግ ተግተው እንደተራ ዘበኞች ሁሉ እየሆኑ በልዩ ልዩ ብልሃት ደስ የሚያሰኘውን የሥልጣኑ ሥራ ሠርተው የተሠወረውን ስርቆት በመግለጻቸው ለከተማው ሕዝብ ሁሉ መመኪያ ሆነውታልና እንግዲህ ያሁኑን ትጋታቸውን ወደፊት ስንመለከት የሌቦቹ ኃይል እየተቀነሰ የከተማ ዘበኞችና የዋና ምርመራ ዘበኞች ትጋት እየጉለመሰ መልክም እርምጃ የሚየሳይ መሆኑን እናያለንና ስለዚህ በአዲስ አበባ ከተማ ኑዋሪለሆኑት ሕዝቦች ሁሉ በከተማ ዘበኞችና በዋና ምርመራ ዘበኞች ላይ ታላቅ እምነት አድርገዋል ብንል በሰሚዎቹ ዘንድ የሚያሳፍር አይደለም ።

ስለ ወይዘሮ የሺሐረግ ባልቻ ዕረፍት ።

ወይዘሮ የሺሐረግ ባልቻ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የእናታቸው የወይዘሮ የሺመቤት የታናሽ እኅታቸው የወይዘሮ ማሚቴ ልጅ የደጃዝማች መንገሻ አበዬ ባለቤት ቀይ መልከ ቀና እጅግ ጠባየ መልካም ነበሩ ። ከደጃዝማች መንገሻ አበዬ ከተጋቡ በዓለም በደስታ ብዙ ጊዜ ቈይተው ነበር ። መቸም የዚህ ዓለም መጨረሻው መራራ ነውና በብርቱ ሕማም ታመው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከእኅትነታቸው ደልቅ አብሮ አደጋቸው ስለሆኑ እጅግ ይወዷቸው ነበሩና ብዙ እርዳታቸውን ጨምረው እንዲታከሙ ባለቤታቸውን ደጃዝማች መንገሻ አበዬን ጨምረው ወደ ምስር ከተማ ሰደዱዋቸው ። ሔደውም የጃንሆይ ወዳጅ ዮሴፍ ሱሉማንፓሻ ወደ ኢጣልያ ሐኪም ቤት አገቧቸው ሐኪሙም ዶክቶር ጋሌዎ የሚባሉ በዚያ አገር ስመ ጥሩ ነበሩና ፫ ወር ያህል ከአከሟቸው በኋላ በጎ ሁነው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። ሐኪሙም የደዌአቸውን ብርታት አይቶት ሁለተኛ እንዲመለስባቸው ተረድቶት ለወዳጆቹ አስታውቆ ነበር ይባላል ። ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ ፯ ወር ያህል ጤና አግኝተው ነበር ነገር ግን መቸም አጥፊአቸው ነውና ሁለተኛ ተመልሶባቸው ቢታመሙ በከብት ሲጓዙ ብዙ ጊዜ ደቂያሉና ደዌ ትንዳይጸናባቸው ከባለቤታቸው ከደጃዝማች መንገሻ አበዬ ጋራ በአይ

ሮፕላን አስመጪቸውና ሁለተኛ ወደ ምስር ከተማ ሰደድዋቸው ተመልሰውም ቀድሞ ወደታከሙበት ሆስፒታል ሁለት ወር ያህል ታክመው የመዳን ተስፋ ስለሌላቸው ሐኪሙ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ስለአዘዘ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው እንደታመሙ ፩ወር ያህል ቈይተው በጳጕሜ ፬ቀን እዚሁ አዲስ አበባ አርፈው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊትእቴጌ ልዑላን መሳፍንትና መኳንንት ወይዛዝር ብፁዓን ጳጳሳትና ሊቃውንት ካህናትና ሠራዊት ተሰብስበው አልቅሰውላቸው በመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበሩ ዳንሆይም እጅግ አዘኑላቸው ዕድሜአቸውም ፴፰ ዓመት ነበረ ባለቤታቸው ደጃዝማች መንገሻ አቡዬበዚሁ መከራቸው ፩ቀን ሳይለዩ መከራቸውን ሳይሰለቹ በማስታመማቸው የማይደነቅና የማያመሰግናቸው ሰው የለም እውነት ነውና ባልና ሚስት አንድ አካል ናቸው ተብሎ እንደተጻፈው እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ አለመለየታቸው እውነተኛ ክርስቲያን መሆናቸውን ያስረዳል ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ባለቤታቸውን ደጃዝማች መንገሻ አቡዬንና እኅታቸውን ወይዘሮ አስካለ ባልቻን ልጆቻውንና ዘመድ ወዳጃቸውን እግዚአብሔር ያጽናቸው እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል ።

እጅግ የሚያሳዝን የባልና ሚስት ሞት ።

ልጅ በቀለ ሀብተ ማርያምና ወይዘሮ ጥሩ ወርቅ ወልደ ሥላሴ በዚሁ በአዲስ አበባ ከተማ ተወልደው ነዋሪዎች ነበሩ በ፲፱፻፳፫ ዓ ም በሚያዝያ ፳፫ቀን በኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ደምብ በሥርዓት ተክሊል ተጋብተው በደብረ ጊዮርጊስ ሥጋውን ደሙን ተቀብለው በሕጋቸው ጸንተው ልጅ በቀለም በዚሁ በደብረ ጊዮርጊስ መቅደስ በዲቁና እየቀደሰ በተጋቡ በ፩ዓመት ከ፫ወራቸው ሁለቱም በድንገት ታመው ጉለሌ ሆስፒታል ገብተው ሕማማቸው ስለፀና ልጅ በቀለ በነሐሴ ፳ቀን ሙቶ እጅግ ባማረ ጉዞ ፍታት ተፈትቶ በደብረ ጊዮርጊስ ተቀበረ ። ወይዘሮ ጥሩ ወርቅም ሕመሟ ስለፀና ሐኪሙ ለማዳን አልቻለም ነበርና እናቷ አቤታቸው አምጥተዋት በነሐሴ ፳፰ቀን ለ፱ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ተሣሀለነ እግዚአብሔር ኪዳን ለመድገም ስትጀምር ሲመስለን ለካ ነፍስዋ ከሥጋዋ ስትለይ ኖሮ ወዲያው ልክ ፱ ሰዓት ሲሆን ነፍስዋ ከሥጋዋ ተለይ ። እጅግ ባማረ ጉዞ ፍታት ተፈትታ በደብረ ጊዮርጊስ ተቀበረች ። እነዚህ ገና ወጣቶች በኦርቶዶክስ ሃይማኖት የፀኑ ልጆች ባጭር በመቀጨታቸው እጅግ ያሳዝናሉ ። ልጅ በቀለም ከተወለደ ገና ፳፪ ዓመቱ ነበረ።ወይዘሮ ጥሩ ወርቅም ገና ፲፱ ዓመቷ ነበር ይልቁንም ለቤተ ዘመዶች ዋና ለጐረቤቶችዋ ፀፀት የሆነባቸው በሆድዋ ፅንስ ነበርና ዘር ሳትተው በመሞቷና ደግሞ ሁል ቀን በነግህ ተነሥታ ውዳሴ ማርያምና መዝሙረ ዳዊት ትደግም ነበረ ። ዓርብ ዓርብ ቀን ሕማማተ መስቀል ታሔድ ነበርና ስለዚህ ኃዘናቸው የጸና ሆነ ይህም ስለሆነ ፍርሀዋ ለኃጢአት ኢትፍርሀዎ ለሞት ነውና እንደ ክርስቲያን ደምብ በተክሊል ተጋብተው በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጸንተው ገና በልጅነታቸው በትዳራቸው ተበሳጭተው መፋታትን ሳያስቡ ገና ፍቅራቸውን ሳይጨርሱ በ፩ዓመታቸው ስለሞቱ የዚህን አሟሟት ለተመለከተው ዓለም ማለት ነው።

ከወገኖቿ አንዱ ሙሉጌታ ወሥ።

ክፉ ጨካኝ ሞት

ክንፈ ሚካኤል የሚባል የአዲስ አበባ መካነ ሥላሴ ሊቀ ዲያቆን በሕፃንነት ጀምሮ በዲቁና በመካነ ሥላሴ ሲያገለግል ኖሮ በኋላም ሊቀ ዲያቆንነት ተሾሞ ይኖር ነበር በ፲፱፻፳፬ ዓ ም ፯ ቀን ያህል ታሞ ሰንብቶ ነበርና ጳጕሜን ፫ ቀን አረፈ። ዕድሜውም ፴፫ ዓመት ነበረ ስንኳን የሚአውቀው ይቅርና የማያውቀው መንገድ አላፊው ሁሉ ደግነቱና ቅንነቱን የሰማ አለቀሰለት፤ ይልቁንም በቤተ እግዚአብሔር ቅጽር አጠገብ ወድቀው የሚኖሩት ነዳያን ደግነቱን እያሰቡ ብዙ ሲያለቅሱ ዋሉ ለፍታቱ ከየአድባራቱ የመጡት ካህናቱም ከፍታቱ ይልቅ ልቅሶቸው እጅግ በዝቶ ዋለ ። አሁንም ቤተዘመዶቹን ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ እያልሁ የልቅሶ እንጉርጉሮ እጽፋለሁ

ይኸ ሞት አያረጅ ስሙ አይረሳ ። በዓለም ላይ ሲሔድ በክንፉ ተነሣ ። ዘወትር የማያርፍ የማይደክም ሞት ። ክንፉን ጠቀለለ በዚሁ ወራት ።

ብርሃኑ አልፍነህ።

ማስታወቂያ ።

በኢትዮጵያ ውሥጥ የሚሠሩ ዕቃዎች ከዚህ በታች የተጻፉት ናቸውና እንደደምቡ በአራዳ ጉምሩክ ውሥጥ እየገቡ ቀረጥ መክፈል ይገባቸዋል ።

ሳሙና ። ዘይት በየይነቱ ። ባሕር ዓረብ ። መከሮኒ ። ምንጣፍ ። ሎሲዮን ሺቱና አምበሬ ጭቃ ። ሱካር (ቦንቦን) መስተዋት።

ይህ ማስታወቂያ በብርሃንና ሰላም ከወጣበት ቀን ጀምሮ ወደፊት ይጸናል ።

የንግድ ሚኒስቴር።

AVIS

Pour les marchandises fabriquées en Ethiopie et énumérées ci-après les droits de douane doivent être payés à la Douane de l'Arada.

Savon.
Huile de toutes sortes.
Baharareb
Maccaronis.
Tapis.
Lotions; parfum; pommades.
Bonbons.
Miroirs.

Cet avis sera mis en vigueur le jour de sa publication dans le jousnal « Birrhanna Salam ».

Le Ministre du Commerce.

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት

ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር	
የቅዱ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፱ ብር	
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፭ ብር	
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር	
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲ ብር	
፫ቱ መጻሕፍተ መነኰሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪ ብር	
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፱ ብር	
ዶስታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፰ ብር	
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር	
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር	
የዓለም ጅዖግራፊ ከነካርታው	፯ ብር	
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፮ ብር	
ድርሳነ ሚካኤል	፮ ብር	
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር	
ጎህ ጽባሕ	፭ ብር	
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር	
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ ብር	
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪ ብር	፶መ
የእርሻ ትምህርት	፩ ብር	፶መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ እጅግ ያማረ	፪ ብር	
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር	
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር	
የቊጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩ ብር	
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር	
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር	
የነፃ ደንብ ከነተጨማሪው	፩ ብር	፶መ
የብድር ደንብ	፩ ብር	
የጦር መሣሪያ ደንብ አዲስ	፩ ብር	፶መ
የገዳም ደንብ	፩ ብር	
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር	
ዮሐንስ ቡንያን	፩ ብር	
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፭ ብር	
የ፪ኛ	፳ ብር	
የ፫ኛ	፲፭ ብር	
የ፬ኛ	፲ ብር	
የ፭ ኛ	፯ ብር	
የ፮ኛ	፯ ብር	
የ፯ኛ	፯ ብር	
፳፬ ካርት ፖስታል	፩ ብር	
የረኮማንዴ ደብተር	፫ ብር	
ሕገ መንግሥት	፭ ብር	
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፶ መሐ	
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን ነገ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፶ መሐ	
አጭር የዓለም ታሪክ	፶ መሐ	
የቡገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተስማማ	፶ መሐ	
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፶ መሐ	
ያማርኛ ምሳሌ	፶ መሐ	
አሳብና ምኞት	፬ መሐ	
የፍቅር መላክት	፬ መሐ	
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ	
የምሕረት አዋጅ	፬ መሐ	
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ	
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ	
የንቊጣጣሽ ግጥም	፪ መሐ	
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፪ መሐ	
፩ ጋዜጣ	፪ መሐ	
አርሰማላብ	፬ መሐ	
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፬ መሐ	
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለውዘድ	፬ መሐ	
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፩ መሐ	
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፩ መሐ	
ክላንድሬ	፶ መሐ	
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪያ	፩ መሐ	
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፶ መሐ	
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፬ መሐ	

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት እጥፍ ። ነጠላ በያይነቱ ። እርሳስ መንጕልና ብረት ብርዕ ቀለም በያይነቱ።የካርት ቢዚት እንቦልብና ካርት ቢዚት በያይነቱ ። እንቦልብ ትልቅና ትንሽ በያይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር እ ብሩንስ በፊት በድሬ ዳዋ ማዘጋጃ ቤት የመንግሥት ሐኪም የነበረ ዛሬ በአዲስ አበባ መጥቶ የሕክምና ሥራ መሥራት መጀመሩን ለሕዝብ ሁሉ ያስታውቃል። ማከሚያ ቤቱም አራዳ እሙሴ ዛሓን ጐን ቀድሞ ዶክተር ማየ ቤርዠር እሚሰራበት ቤት ውሥጥ ነው የሚገኘውም ጧት ከ፫ ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩል ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲ ሰዓት ነው ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበሰል ፥ የልብ ፥ የደረት የጕበት ፥ የኩላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቁቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዛና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መበለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፯ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቆሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጎበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመንብኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚከኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፤ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ካገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሜሉር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለፅንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፴፱
8me ANNE. № 39

ሐሙስ መስከረም ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 22 Septembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የአጤ መስቀል ።

ይህ የአጤ መስቀል በዓል በየዓመቱ ይከበራል ። ይከበራልም ስለ አልን እንደሌሎች ታላላቆች በዓላት ሕዝቡ ሥራ አይፈታም ። ሊቃውንትና ካህናት የክብር ልብሳቸውን ለብሰው ቀሳውስትና ዲያቆናትም ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ጽና መስቀል ይዘው በየዓመቱ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ማኅሌት ያደርጋሉ ። ዘንድሮም በዚሁ ልማድ በመስከረም ፲ ቀን የአጤ መስቀል በዓል ተደርጎ ነበር ። ስለዚሁም በዓል ክብር ታላቁ ሰገነት እጅግ አምሮ ተነጥፎ ጥሩ ጥሩ ወምበር ተደርድሮበት ነበር። በመሐከሉም የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዙፋን ተዘርግቶ በዙፋኑ ላይም በወርቅ የተከፈፈ ምንጣፍ ተነጥፎበት ነበር።በግርጌና በራስጌም በወርቅ ያጌጡ መከዳዎች ተደርገውበት በላዩ የወርቅ አጐበር ተዘርግቶ በወርቅ የተከፈፈ የሐር መጋረጃ ተጋርዶ ነበር ። ከ፬ ሰዓት በኋላ መጋረጃው ተገለጠ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በዚሁ በተዘጋጀው ዙፋን ላይ ተቀምጠው ታዩ።የከር ዲፕሎማቲክ ሰዎችም በዙፋኑ ቀኝ በተዘጋጀላቸው ወምበር ተቀመጡ ። በዙፋኑ በግራ ወገንም የኢትዮጵያ ጳጳስ አቡነ ሳዊሮስና ታላላቆች መሳፍንት ተቀመጡ ። ከዚህ በኋላ መኳንንቱ እጅ እየነሡ ገቡ ። ሊቃውንቱና መኳንንቱም በየማዕርጋቸው ተቀመጡ ። ከዚህ በኋላ ካህናቱ ተዘጋጅተው ቀረቡ።የመሪነቱም ተራ የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ካህናት ነበረ።እነሱም ጥሩ ጥሩ የማዕርግ ልብስ ለብሰው ነበር። ዲያቆኑ ባማረ ድምፅ ምሥጢሩ የተስማማውን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ምስባክ ሰበከ።

ኵሉ ይገኒ ለስምከ ዓቢይ ። እስመ ግሩም ወቅዱስ ውእቱ ። ክቡር ንጉሥ ፍትሐ ያፈቅር ። መዝሙር ፺፰። ይህም ሶስት ጊዜ ከተመላለሰ በኋላ እጅግ የረጉ አስተዋይ ካህን ወንጌል ቅዱስ ብለው የወርቅ ወንጌል ይዘው በጥንቃቄና በማስተዋል በቀረቡ ጊዜ እጅግ ደስ አሰኙ። የተነበበውም ከማቴዎስ መኳንንት ምዕራፍ ፳፪ ቍጥር ፭ ነበረ። ወንጌሉንም ካህኑ ለአቡነ ሳዊሮስ ሰጥተው አቡነ ሳዊሮስ ለጃንሆይና በግራና በቀኝ ለነበሩ ታላላቆች ወንጌሉ አሳሙ። ከዚህ በኋላ ፪ ድምጸ መልከከሞች ደብተሮች መሪና ተመሪዎች ሁነው ቀረቡ።መሪው ደብተራ ገብረ. አምላክ፡ ተመሪው ደብተራ አስፋው ነበሩ ። የቀለም ማስተካከላቸውና የድምጻቸው ማማር እጅግ ተደነቀ ። የመጀመሸ አንሽዎች የአዲስ ዓለም ካህናት ነበሩ ። የሁለተኛ አንሽዎች የእንጦጦ ማርያም ካህናት ነበሩ ። እንግዲህ ክርሞ ለሚደረገው በዓል መሪዎች አዲስ ዓለሞች ካህናት፤ በሁለተኛው ዓመት ለሚደረገው በዓል መሪዎች የእንጦጦ ማርያም ካህናት ይሆናሉ ። እንገርጋሪው መቸም የተለመደ ነው ። እስመ ለዓለሙ እግዚእ ዘኵሎ ትሬኢ. የሚለው ነበረ። የዚህን ወደ መጨረሻው ወገን ያለውን ወርበው ብዙኃን መኳንንት ይሰግዱ. ለከ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘአንተ ጸዋዕከ በጽዋዔ ወለተ ጊዮርጊስ አድኅነነ በወልድከ አምኃ ሥላሴ ወራሲ መንግሥት እያሉ ሲአሸበሽቡ እጅግ አማረባቸው። ዕዝሉ የተለመደው ነው። ተቀጸል ጽጌ ኃይለ ሥላሴ ሐጼጌ በተባለ ጊዜ አበባ ታደለ።አቡኑ ዘዮም መስቀል ነበረ።ሁለተኛ አራራይ እስመ ለዓለም የሐንፃ ኃይለ ሥላሴ ለቀራንዮ ኢየሩሳሌም ። ሰላም ጽድቅ ቃሉ የሚለው ነበረ ። ማኅሌቱ ከተፈጸመ በኋላ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ስብከት ሰብከው መርቀው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱ ። ከዚህ በኋላ ከማጆር ፖሊ ሰልፍ ከተማሩት ጥቂቶች ወታደሮች ጥሩምባ ነፊዎች በፊት እየመሩዋቸው ባማረ ሰልፍ ሁነው ከአለቃቸው ከባላምባራስ መኰሸ ባንቲ ደርጉ ጋራ ብቅ ባሉ ጊዜ እጅግ አማሩ ። ሰልፋቸውንም አሳይተው ሰላምታ ሰጥተው ተመለሱ። ከዚህ በኋላ ታላቅ ግብር ለካህናቱና ለመኳንንቱ ተደርጎ ዋለ።

የአይሮፕላን ጥቅም።

የአይሮፕላን ጥቅም መልካምነቱ ለሁሉ ታወቀ ከዚህ ቀድሞ ፖስጣ በማመላለስ ታላቅ ጥቅም አድርጓል። አሁንም ለሚአስቸኵል ነገር ሁሉ መልእክተኞችን አፋጥኖ በማመላለሱ ታላቅ ጥቅም አድርጓል።በመስከረም ፯ ቀን ባላምባራስ ግርማ ያየህ ይራድንና ነጋድራስ ወዳጆ አሊን ከጐጃም ከደብረ ማርቆስ ከተማ ይዞ መጣ። መንገዱም ሩቅ ሳለ በ፩ ሰዓት ከሐያ ደቂቃ ይደርሳል። ይልቁንም ዓባይን ያህል ውኃ አለችግር መሻገሩ ዋና ጥቅም ነው።

የተሸሸገ መገለጥ ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል የተሸሸገ ሳይገለጥ የተከደነ ሳይከፈት አይቀርም ይላል። ነገር ግን ምንም የመጽሐፍን ቃል ቢአነቡትና ቢአውቁት አድራጊዎች ጥቂቶች መሆናቸው እጅግ ያስደንቃል ያስገርማል።የአድራጊዎችስ ማነስ ዘምን ምክንያት ይመስላችኋል?አንባቢዎች በተቻላችሁ ጊዜ ትገልጹልናላችሁ እኛ ግን የመሰለንን እንድንገልጽላችሁ ፍቀዱልን። ሰሎሞን በምድር ላይ ከንቱ ነገር አየሁ ኃጢአተኛ ።ኃጢአቱ ሲጠቅም ጻድቅም በጽድቁ ሲጐዳ ስለዚህም የሰው ልጆች ኃጢአት በምድር ላይ በዛ አለ። እውነቱ ነው። የጻድቃን ዋጋ በሰማይ ብቻ ሆነ። ኃጢአተኞች ግን እገሌና እገሌ እንደዚህ ያለ ቤት ሠሩ እንደዚህ ያለ ርስት ገዙ እያለ ሰይጣን በሰዎች ልብ ውሥጥ እየሰበከ ከምድር ላይ ጻድቃንን ሊአጠፋ ጥቂት ቀረው። ነገር ግን እውነተኛው ዳኛ እግዚአብሔር ሳይቸኰል በዝግታ የበጎችን ለምድ ለብሰው (ጻድቃንን መስለው) ቃላቸውን አለስልሰው በአደባባይ የሚከበሰበሱትን ሰዎች ሁሉ በየጊዜው ኃጢአታቸውን ሲገልጽባቸው ያችን ታናሽቱን የድካማቸውን ፍሬ የሚበሉትን የጻድቃንን ልብ ከኀዘኑ ያጸናናዋል። ይህንም ያልንበት ምክንያት በራስ ጕግሣ ወሌ ጦርነት ጊዜ የጥይት ቤቱ ሹም መልከ መልከሙ አነጋገረ ለስላሳው ግራዝማች አዝምታቸው ነበሩና በዚያን ጊዜ በብዙ ዘመን ከሮፓ እየተገዛ የተሰበሰበውን የቤተ መንግሥቱን ጥይት በብዙ ሰርቀው ሸጠው ሀብታም ለመሆን ስለአሰቡ ከጭፍሮቻቸው ከጸሐፊዎችና ከዘበኞች ከቁልፍ ያዦዎች ጋራ ተስማምተው የቸሬ ክልስ በሚባለው አለሥርዓት በተሠራው ጥሩውን ጥይት ለውጠው ለዘመቻ እንዲሆን ብዙ ክልስ ልከው በጦርነቱ ጊዜ አልተኰስ እያለ በጠላቶቻቸው እጅ ወድቀው የቀሩ ብዙ ናቸው ይባላል ። በላይኛው መስመር እንዳስታወቅነው የተሠራ ሳይገለጥ አይቀርምና ተገልጦባቸው።ግራዝማች አዝምታቸው ከተባበሩዋቸው ጋራ ተይዘው ነበር የከተማ ቦታቸውም ቤታቸውም ተይዞ ነበር። ነገር ግን በዘመድ ብዛት በጃንሆይ ምሕረት ተፈትተው ቤታቸውም ቦታቸውም ተለቀቀላቸው። ግራዝማች አዝምታቸውንም ሥራህን አስረክብ ብለዋቸው ሲአስረክቡ ከሚቈጥሩት ጥይት አንዱን ጥቅልል በጕያቸው ሸሽገው ሲወጡ በላጋራቸው አስያዘባቸው።

የጃንሆይ ምሕረት መቸም ብዙ ነውና ምረዋቸው ወደ አገር ቤት ርስታቸው እንዲቀመጡ ፈቅደውላቸው በደህና ተቀምጠው ከርመው እግዚአብሔር የተሰወረውን በሚገልጽበት ጊዜ አሽከሮቻቸውን አለልክ ስለገረፏቸውና ብዙ ጊዜ ስለአሰሯቸው በዚህ ነገር ተናደው ወደ አዲስ አበባ መጥተው እኛን እንዲህ አድርገው በደሉን የቤተ መንግሥቱንም ጥይት ሰርቀው በሁለት ማጥን ሞልተው እቤታቸው ቀብረውታል መቅበራቸውንም የሚአውቁ ሰዎች እገሌና እገሌ የሚባሉ አሽከሮቻቸው ናቸውና እነሱ ይጠየቁ ብለው ስለ ከሰሱ በጃንሆይ ፈቃድ አጋፋሪ ከኣከሌ የላይኛውን ግቢ አጋፋሪ ባላምባራስ አላምነህን ከዘበኛ ጋራ ከሳሾችን ጨምረው ልከው አሽከሮቹ ያመለከቱት በቃ ቢቈፈር ሁለት ማጥን ጥይት ተቀብሮ ተገኘ። ይህ ኃፍረት ለታመኑት ሁሉ ነው እንጂ ለግራዝማች አዝምታቸው ብቻ አይደለም። ወይ ግሩም ከጨዋታ ታላቅ ቁም ነገር ይገኛል ። አንድ ብልህ ሰው ስርቆሽ በር በሚባለው በታላቁ ግቢ በር ሲገባ አይቶ አንዱ ወዳጁ ሊአናግረው ምነው በስርቈሽ በር ትገባለህ? ወንድሜ ቢለው ብዙ ሰዎች ሲከብሩበት አይቼ ነዋ ብሎ መለሰለት እውነት ነው በዚሁ በስርቆሽ በር ብዙ ሰዎች ሲከብሩ ይታያሉ።ነገር ግን ፍጻሜአቸው ሲከፋ እንጂ ሲአምር አላየንምና የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ ከዚህ በር ሰም አጥብቃችሁ እንድትሸሹ ብርሃንና ሰላም አጥብቆ አደራ ይላችኋል።

የግራዝማች አዝምታቸውም ኃጢአት ተደጋግሞ ነበረ። ነገር ግን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትዕግሥት እጅግ ብዙ ስለሆነ በየጊዜው ምሕረት ይደረግላቸዋል። መጀመፘ በቤተ መንግሥቱ የታወቁት በመንግሥትና በሕዝብ ዘንድ የተወደዱት ወንድማቸው ፊታውራሪ ወልደ ገብርኤል ከሞቱ በኋላ በንግሥት ዘውዲቱ መንግሥት በጃንሆይ አልጋ ወራሽነት ጊዜ የአልፍኝ አስከልካይነቱን ሁለተኛ ማዕርግ ሹመት ደህና አድርገው ሸልመው ቢሾሙአቸው የመጀመፘው ካልሆነልኝ ብለው ቀሚሳቸውን አውልቀው ማቃቸውን ለብሰው እንኳን ደስ አለህ ለማለት የተሰበሰበውን ዘመድ ወዳጃቸውን ሁሉ በትነው ወደቤታቸው ሒደው ሹመታችሁን አልፈልግም አሉ ። ይህም አልታዘዝ ማለት በቀድሞ ነገሥታት ጊዜ ሁኖ ቢሆን ታላቅ ቅጣት ነበረ ። የዛሬ መንግሥት የምሕረት መንግሥት ስለሆነ ምሕረት ተደረገላቸውና የአገር ግዛት ሚኒስቴር ዲሬክቴርነት ተሹመው ነበር ። ቀጥለውም የሰይፍ ጃግሬን ሹመት ተሹመው ነበር።ቀጥለው ደህን የጥይት ቤት ሹመት ተሹመው በላይኛው መስመር እንዳመለከትነው ጥይት ሰርቀሃል ተብለው ቢከሰሱ ይህ ነገር በውጭ የተሰማ እንደሆነ ታላቅ ኃፍረት ነውና ነገሩ ተሰውሮ እንዲቀር ብለው ጃንሆይ በሁለት ታላላቆች ሰዎች ፊት ብቻ ነገሩ እንዲመረመር አዝዘው ነበር ። ግራዝማች አዝምታቸው እውነቱን አላወጣ ስለአሉ ነገሩ ወደ አደባባይ ወጥቶ በአደባባይ ተረትተው በጦር ጊዜ መሣፘ መስረቅ ለጠላት መርዳት ነውና ሞት ይገባዋል ተብሎ የሞት ፍርድ ቢፈረድባቸው በመጀመፘ እንዳልነው የጃንሆይ ምሕረት ብዙ ስለሆነ ምሕረት አደረጉላቸው ። ደግሞ ዕቃውን ለማስረከብ በገቡ ጊዜ ታላቅ ሰው ሁነው ታናሽ ነገር በኪሳቸው ሸሽገው ሲገኙ የነገሩ ፍጻሜ ያው ነበረ።ነገር ግን የጃንሆይ ምሕረት ወሰን የለውምና ምሕረት አድርገውላቸው ርስታቸው ላይ ከተቀመጡበት በነዚህ ድሆች አሽከሮቻቸው መጨከን አይገባቸውም ነበር ። ሰርቀውም እንደሆነ ከቤት የተማሩትን ነው ከዳትም አስበው እንደሆነ ያው ነው።ይልቁንስ እኔ በቤተ መንግሥት የታመንሁት ሰው እንደዚህ ያለ ጥፋት ተገኝቶብኝ ሁሉን ማድረግ የሚቻላቸው ንጉሥ ምሕረት ካደረጉልኝ እኔም ከበታቼ ላሉት አጥፊዎች ምሕረት ማድረግ ይገባኛል ብለው ምሕረት ሊአደርጉላቸው ይገባ ነበር።ነገር ግን ረቂቁ አምላክ የተሸሸገውን ለመግለጽ ስላሰበ ልባቸውን አጸናባቸው ። ደግሞ ወደፊት የሚደረገውን እንጽፍላችኋለን ።

ስለ ከተማ ዘበኞች ትጋት ።

ከፊታውራሪ ተፈሪ ቤት ግምጃቤታቸውን ሌቦች ሰብረው ገብተው ሰርቀው መያዛቸውን ባለፈው እሙስ ፲፱፻፳፩ ዓ ም ጳጉሜ ፫ ቀን ብርሃንና ሰላም አስውታውቋል።የምርምሩን መጨረሻ በዚሁ ምርምር ከሌላ ዘንድ ሰርቀው መገኘታቸውን ወደፊት እናስታውቃለን ተብሎ ስለ ነበረ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ጽፈናል።መጀመሪያ የምርመራው አኳኋን በምሥጢር ስለላ ቢሮ በኩል ሁለትና ሶስት የሚሆኑ ሰላዮች እንደተሰጣቸው ደምብ ትጋታቸውን ጨምረው ተላልፈው ሲሰልሉ ባለድግሩን መትረየስ አይቻለሁ የሚል አንድ ወፍ አገኙ ይኸኑም ወፍ አለቃቸው አልጅ ኃይለ መስቀል ዛማኤል ዘንድ አድርሰውት ልጅ ኃይለ መስቀልም ከዘበኛ አለቃው ከግራዝማች አማረ ዘንድ አደረሰ ይኸኑ ወፍ እርግጥ አይተሀልን ቢሉት መትረየሱን አይቻለሁ ሌቦቹንም አውቃቸዋለሁ አለ ከተሰረቀው እቃ በፊት ሌቦቹን ብንይዝ እቃው እየራቀ ሌቦቹ ለደኅንነት ይጣጣሩብናልና አስቀድመህ መትረየሱን እንድንይዝ አድርግ ከሌቦቹ ዘንድ መቅረቢያ የመትረየሱን መግዣ ይዘህ ገዥ ሁነህ ቅረብ ብለው የሚበቃ ገንዘብ ሰጥተውት ሔደ ሌቦቹም ጥርጣሬ አላቸውና መትረየሱን ሳያሳዩ በቃል የገንዘብ ክርክርና በሌላም በኩል ለራሳቸው ጥቅም ከሚፈልጉ ሰዎች ጋር አጋጥመው ጨረታ አደረጉ ሌቦቹ ጥርጣሬአቸውን አልተዉ ኖሮ ከብዙ በጥቂቱ የሰጠነን እንቀበል አርመን ይሻለናል ብለው ለአርዳሽስ ሸጡ ዋጋውን ተቀብለው ተከተማ ለመጥፋት ማሰባቸውን ወፉ ለይቶ ከሁለት አንዳቸውን ሳንይዝ ሌቦቹ የሚአመልጡን ሆኑ ብሎ ምክር ቢአቀርብ ሌቦቹ እንዳያመልጡ ተይዘው ለመስረቃቸው አስገድደን መጠየቅ ይሻላል ተብሎ ቃስበ የሌቦቹን ቤት ወፍ አሳይቶ ሔደ የወፍና የሰላዮች ሥራ እስከዚህ ነው ። የልጅ ኃይለመስቀልና የግራዝማች አማረ ትጋት ሌትም ቀንም ሳይለያዩ ባንድነት እስከ ሶስት ቀን የወፍና የሰላዮችን ዱካ እየተከተሉ ሲመረምሩ ሰንብተው አሌቦቹ ቤት ቢሔዱ በየን የሚባለውን ብቻ አገኙ የሰረቃችሁትን እቃ አምጣ ቢሉት እንደደረሱበት ተረድቶት የወደፊት ብቆሐት ማቆየቱ መስሎት ከዚህ ቅጣት ልታድኑኝ ግራዝማች አማረ ይግዘቱ ልጅ ኃይለ መስቀል ጣቱን ያጥብኝ ብሎ ጣቱንም ጠባ አስግዘተም፡ የተሰረቀውን ሽጠነዋል አሲዘለሁ አለ ላሁን የሚሆን ምልክት ስጠን ቢሉት ለኛ ገንዘብ የማይሆነንን ጥለነዋል አሳያለሁ ብሎ ከአልያንስ ተማሪቤት በታች ከገደል ከወንዝ ውሥጥ ከጣሉበት መርቶ አሳዬ ራሳቸው ግራዝማች አማረና ልጅ ኃይለመስቀል መልከም የማዕርግ ልብሳቸውን እስከ እግር ጉልበታቸው ከማጥ ከጭቃ ገብተው ጆለል ያለበሰውን ፈንቅለው አንድ ሽንጣና የጥይት ከረታ አመጡ ይህ ትጋታቸውን ያስረዳል ።

ዳግም ማክረጃ በየን ብቻ ተይዞ የቀሩት የማይገኙላቸው ቢሆን በየን ከተያዘበት ቤት ውሥጥ ዘበኞች አስቀምጠው ከዚህ የሚመጣ ሰው ያዙ ከኛም ዘንድ ሳታደርሱ አትልቀቁ ብለው አሲዝዋቸው ተቀምጠው ሲጠባበቁ ሌቦቹ ቤታችን ነው በማለት እየመጡ አገቡ ሲሉ ዘበኞችም አለን እያሉ የመጡላቸውን እየሰበሰቡ ከንድ እስከ ፫ሌባ ይዘው አቀረቡ ከዚህ በላይ የተጻፈውን በምሥጢር ሰርተው ለግልጽ ጥያቄ አደረሱ።

ግልጽ ጥያቄ በየነ ሙዘየን ለመይ ረጂከ የሚባል የስልጤ ሰዎች በቦጋለ መሬነት ከፊታውራሪ ተፈሪ ቤት ድግን መትረየስ፡ ግንጥል ጠመንጃ፡ወጨፎ ጠመንጃ፡ ጥንዳ ድርብ፡ ሶስት መቶ ጥይት ሌላም እቃ መስረቃቸውን አምነው መትረየሱን ደነቀ አጋጣሚ ሆኖ ለአርዳሽስ ሸጠነዋል አሉ ። አርዳሽስም ተጠይቆ አልገዛሁም ብሎ ተክዶ በኋላ ቆንስሉ መጥተው ቤቱ የሚፈተሽ ቢሆን አውጥቶ ሰጠ ። ሌቦቹን ደነቀ አጋጣሚ የሆናችሁ በምን ምክንያት ነው ቢሉአቸው ከዚህ በፊት በሐምሌ ወር የመሐመድ አሊን ካቃቂ ወፍጮ ቤታቸው በረጂከ መሬነት ሁለት ትልልቅ ምንጣፍ ጀፍራሽ ሁለት የጠረጴዛ ልብስ ሌላም እቃ ሰርቀን ይኸኑ እቃ የገዛና ያሸጠልን ደነቀ ነበረ። ቤታችንም ጉረቤት ነን በዚሁ አውቂያ መትረየሱን አሸጠልን ብለው ተመረመሩ ።

ደነቀም መትረየሱን እንዳይታወቅ በባሕር ዛፍ ጠቅሎ ቅጠል ነው አሰኝቶ ቀን ከአርዳሽስ ቤት ማድረሱንና ለራሱ ጥቅም የመትረየሱን ማንገቻ ጠፍር ፈትቶ መውሰዱን በጁም መገኘቱን የመሐመድ አሊን አንዱን ምንጣፍ እስቲሎ ለሚባል በ፴ ብር ማሸጡን አመነ ። እስቲሎም መግዛቱን አምኖ ምንጣፉን መልሶ ለባለገንዘቡ ተመለሰ።ገብረሕይወት የሚባለው ሌባ የፊታውራሪ ተፈሪን ቤት ለመስረቅ ሲሔዱ አሞኛል ብሎ መቅረቱን ቦጋለም የፊታውራሪ ተፈሪን ቤት መምራቱንና አንደኛውን ቀን ስለነቁባቸው መመለሱን አምኑዋል። ለመስረቅ በሔዱበት ቀን ጓደኞቻቸው ለሁለቱ መስከረውላቸዋል በዚሁ ቀን ግን ከቤት አላደሩም ሁለት አህያ ሰርቀው አምጥተው ያህዮቹን ዋጋ ከመትረየስ ከጠመንጃ ከድርብ ከጥይቱ ዋጋ ጋራ ቀላቅለው ለመከፈል መስማማታቸውን ተማምነዋል ። ሙዘየን የሚባለው ሶስተኛ የወይዘሮ አበበች መሸሻን ቤት ሰብሮ እቃ መስረቁን አመነ ኒሰረቀም ፩ ወር ያህል ሆኖታል ከ፫ ዓመት በፊት አሊ ከሚባል ጓደኛው ጋራ በፋኖስ ውሐ በሚሔድበት ፉካ ውሥጥ ወደ ነጋዴ ሱቅ መሬት ቆፍሮ ሲሔድ ግራዝማች ሣህሌ በዘበኛ አለቅነታቸው ጊዜ በሽጉጥ አቁስለው ይዘውት የነበረ ሆኖ ተገኘ። ሙላት የሚባለው ከፊታውራሪ ተፈሪ ቤት ይህን እቃ አብሮ መስረቁን አመነ ይልቁንም ምሥጢር ሰርቆ ተገኘ የምሥጢሩ ዓይነት እልጅ ኃይለ መስቀል ዘንድ ጠጋ ብሎ ስለተከታተለ ሌብነቱን ያውቃልና የሌባን ሥራ ሌባ ያውቀዋል በማለት እሽልምሀለሁ ብሎ ይህን ምሥጢር ነገረው የሰረቁትን ሌቦች አላጣቸውም ብሎ ለመሰለያ አምስት ብር ተቀብሎ የምሥጢር ሰላይ ሹም መንቃቱን ተረድቶት ራሱ ያልሰረቀ መስሎ ይህን ምሥጢር ሰርቆ ሔደ ይኸኑም በጥያቄው ላይ አምኑዋል ዘበኞችም ትጉዎች ስለሆኑ የያዙቸው የመንግሥት አምላክ ነው ። ይህን ሥራ የሠሩ ሌቦች ብድራቸውን ለመከፈል በታላቁ አደባባይ በጃን ሆይ ችሎት ቀርበው ታላቅ ቅጣት ተፈርዶባቸዋል ። ዘበኞቻችን በጣም ተግተዋልና ሌቦች ሁሉ ከተማችንን ለቃችሁ ሠርታችሁ ብትበሉ ይሻላችኋል ።

ትእዛዝን ባለማክበር የሚመጣ ጉዳት።

ፊታውራሪ ተፈሪ ሀብተ ሥላሴ የባሌን ወሰን ለመጐብኘትና የድኃውንም ችግር የግብሩንም ችግር እንዲመረምሩ ከግርማዊ ንጉሥ ነገሥት አፄ ኃይለ ሥላሴ ታዘው የባሌንም ሠራዊት አስከትለው ይዘው ወርደው ነበር።ነገር ግን ከነዚሁ ከባሌ ሰዎች ውሥጥ ከሻንበሎቹ ቀኛዝማች ኃይሉ አባ ፋርዳ፥ ፊታውራሪ ተሰማ፥ ቀኛዝማች እንዲሮ፥ ቀኛዝማች በላቸው ይርጉ ይልቁንም የጊንር አውራጃ አበጋዝ ፊታውራሪ ይልማ ሥዩም የሚባሉት ንጉሠ ነገሥቱ መርጠ የበላይ ያደረጓቸውን ትከትለው ፈቃድ እንደመፈጸም ባልሆነ ስብከት ሰውን አሳድመው አዝማቻቸውን እዚያው አበረሀ ውሥጥ ትተው ወደ ከተማ ስለተመለሱ ይህ የሠሩት ሥራ አገርንም መንግሥትንም የሚጐዳ በመሆኑ ከባሌ ተጠርተው መጥተው ከፊታውራሪ ተፈሪ ጋራ ተቃርበው ቢጠየቁ በቃላቸው አምነው መስከረም ፲፩ ቀን በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ችሎት ቀርበው ያመኑበት ቃል ተነበ እንደገናም አምነው ከተፈጠመ በኋላ ይፈረድ ተብሎ ፍርድ ሳይጀመር ዋና አሳዳሚ የሆነው ቀኛዝማች በላቸው ይርጉ ከመጀመሪ እስከ መጨረሻ ጥፋቴን አውቄዋለሁና እቀጣለሁ አለ ።

የቀሩት ግን አያስቀጣንም ስላሉ ቀኝና ግራ የቆመው ወታደርና ሽማግሌ የተቀመጡትም መኳንንቶችና ወምበሮቹም ባንድ ቃል ሙሉ ቅጣት ፈረዱባቸው የጦር ሠራዊት ጉዳይ ስለሆነ ሲጋባውም ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል የሠራችሁት ሁሉ የሚገባ ሥራ አይደለምና ሙሉ ቅጣት ትቀጣላችሁ ብለው ፈረዱ ።ንጉሥ በሚፈርዱበት ጊዜ የጦር ሚኒስትሩ ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የናንተን ልጅ መሆን ሳያዩ ያባቶቻችሁን ውለታ ለመመለስና እንዳባቶቻችሁ ለመንግሥታችሁ እንድትረዱ ብለው ጃንሆይ በቸርነታቸው ለታላቅ ማዕርግ ቢያበቋችሁ መንግሥትን በቅንነት እንደማገልገል ይህንን ሁሉ ሥራ ከሠራችሁ የናንተ ተንኰል አንሶ የከፋ ሥራ መሬ መሆናችሁ ነውና ቀኛዝማች በላቸው አውቀህ አቀጣለሁ ብለሃል የቀራችሁት ግን ትቀጣላችሁ። አንዱ ማደሪውንና ሹመቱን ይለቃል ብለው ከፈረዱ በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አንተም ይልማ ሥዩም በፊት ሌላ ግዛት ነበር የሰጠሁህ በኋላም ስላባትህ ስለራስ ሉል ሰገድ ውለታ ጊንር የደጃች ወልደ ገብርኤል ይዞታ የነበረውን ግዛትና ማዕርግ ባልደረባም ሰጠሁህ።

ኃይሉም በፊት ሐረርጌ ማደሪ ይዘህ፡በኋላም የፊታውራሪ አባ ፋርዳ ያገልጋይ ልጅ በመሆንህ አባትህ ይዞት የነበረውን ማደሪ እንድትይዝ ወደ ባሌ አዛውረን ታላቅ ትዳርና ሻንበልነት ሰጥተንህ ነበር።ወደ ዘመቻውም የሰደድናችሁ አገሩ ቢለማ ወሰኑ ቢጠበቅ ጥቅሙ ለናንተው አገሩን ለምትገዙት እንዲሆን ብለን አልነበረምን? ። እንግዲህ ሰው መልካም ውለታ ሲያደርጉለትና ሲያስቡለት እንደዚህ ያለ ከፉ ሥራ በመሥራት አገሩንም መንግሥቱንም በድፍረት ሲበድል እንዶምን ለመታገሥ ይቻላል ብለው የሚያሳዝን ቃል ተናግረው ለዚሁ ነገር ዋና አሳዳሚ የሆነው ቀኛዝማች በላቸው የሚባለው ሙሉ ቅጣት ተቀበለ። የቀሩትም የሚገባቸውን ቅጣት ሊቀበሉ በወህኒ ታስረው ቈይተዋል።

እንባቢ ሆይ።

እነዚህ በታላላቅ ማዕርግ ላይ የቆሙት ሰዎች ይቅርና ከኢትዮጵያ ተወላጅ ውሥጥ ዘመቻ በሆነ ጊዜ ማናቸውም ተራ ሰው ቢሆን እንኳን ታዞና ሳይታዘዝም ቢሆን ፋኖ እየሔደ ላገሩ መሞቱና መርዳቱ የታወቀ ነበረ። እነዚህ ሰዎች ግን ያለቃቸውን ፈቃድ ባለመፈጸም እንደዚህ ካለ ጉዳት ላይ መውደቃቸው ያሳዝናል።

ዕንቍጣጣሽ

ከሌገነት አዲስ አበባ ።

ለምለም አገራችን ኢትዮጵያ በነፃነት ተከብታ የእውቀት ቤቷን አሰፋፍታ ወርቁ ንጉሣችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ጤንነታቸው ተጠብቆ ጠላታቸው ወድቆ ከልዑላን መሳፍንቶቻቸው ከክቡራን መኳንንቶቻቸውና ከኃያላን ወታደሮቻቸው ጋር ከ፲፱፻፳፪ ዓ ም ወደ ፲፱፻፳፫ ዓ ም ልዑል አምላክ በሰላም ስላሻገራቸው ደስታዬን ለመግለጽ ለሀገር ለንጉሥ ለጳጳስ ለመሳፍንት ለሴት ወዘዝር ለወንድ መኳንንት ለኃያላን ወታደሮችና ለመላ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ከ፲፱፻፳፫ ዓ ም ወደ ፲፱፻፳፬ ዓ ም በሰላም ያሻገራችሁ ልዑል አምላክ እንዲሁም ወደ ፊት ረጅም ወራት ሰፊ ዘመናት ከየወሩና ከያመታቱ በሰላም ለመሻገር እንዲያበቃችሁ እውነተኛ ምኞቴን እየገለጽሁ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ዕንቍጣጣሽ አቀርባለሁ ።

(፩ለሀገር)ለምለም ኢትዮጵያ እንኳን ደህና ደረሽ ለአዲሱ ዘመን ። ልጅሽን አክሪነሽ የሚወድሽን ። ሕመምተኛ ሆነች እያሉ ሲያሙሽ ። በሥላሴዎች ኃይል ከሕመም ዳንሽ በዓለም ላይ ታውቋል መልካም ጠባይሽ ። ረዳት ሆኖሻል ብርቱው ጸሎትሽ። (መዝሙረ ዳዊት ፷፰ ቍጥር ፴፩ ።

(፪ለንጉሥ) ጃንሆይ እንኳን ልዑል አምላክ ከዘመን አዘመን ያሻገረዎ ። እንክትክት ብሎ ወድቋል ጠላትዎ ።ይጐና ፀሩ እስኪ የጽድቅ ልብስዎን ። መሐሪ ነዎና ከሩ አድራጊዎን እንደርስዎ ማን አል ትእዛዝ ጠባቂ ፈሪ አምላክዎን ። ሲያከብሩ እናያለን የሚጠላዎን ። (ማቴዎስ ም ፭ ቍጥር ከ፴፫-፴፮)።

(፫ለጳጳሳት) ብፁዓን ጳጳሳት ወዳዲሱ ዘመን እንኳን ደረሳችሁ ሰላምና ብርሃን ስንመኝላችሁ ። ጠበል ስብከታችሁ ደስ አለው ሁሉን ። ፈውስም ሆነላቸው ለዓረማውያን ። ለዓረማውያን ያስፈልጋል ትምርት ። በእውቀት ተባብረን እንድሆን አንድነት ። እንደምን ደስ ይለው ጌታችን መምህሩ ። የለፋችሁበት ሲገለጽ መከሩ ። ሕጉን ጠብቃችሁ በትጋት ስትሠሩ ። ብሎ ያዘዘውን ሑሩ ወመሀሩ ። ጳጳስ ብቻ አይደለም ስማችሁ በክንቱ፡ አንትሙ ለዓለም ብርሃኑ ውእቱ ። (ማቴዎስ ም፭ ቍጥር ፲፬-፲፮። ም ፳፰ቍ ፲፱ ማርቆስ ም፲፮ ቍ፲፭ ።)

(፬ለመሳፍንት)ልዑላን መሳፍንት እንኳን ደረሳችሁ ላዲሱ ዘመን ። ተጨናንቀን ኖረን ስፍራ ተጣበን ። ሀብታችሁ መልካም ነው አስፉ ወሰን ። አባት ስንል ከርመን እኛ ሞኝ ሆነን።

ልጅ ሆኖ ተገኘ መልካም መኰንን ። አጥባቃችሁ ያዙ መተባበርን ። ደግ ምኞት ተመኙ እንደሰሎሞን ።

(መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ም ፫ ቁ ፭ ፲፬።)

(፭ለሴት ወይዛዝር)ክቡራት ወይዛዝር እንኳን ልዑል አምላክ ወዳዲሱ ዘመን ያሸጋገራችሁ። መነን መሰለችኝ መልካሟ ልብሳችሁ (መጽሐፈ አስቴር ም ፪ቁ ፲፯)የአውቀት አለባበስ ዛሬስ ተማራችሁ ።(በየዳር አገሩ) በውጭ ያሉትም አይቅርባቸው ። እንደዚሁ ሁሉ አስተምሩአቸው።ደግ ነገር ለመሥራት እውነት ለመናገር በርታ ጠንክር በሉ ይጽናም እምነታችሁ። ሐና አስተዋይ አለች ለናንት ምሳሌያችሁ ።

(መጽ ሳሙ ቀ ም ፪ ቁ፩-፴፮(መጽ ምሳ ም ፴፩ ቁ ፲-፴፩)

(፮ለወንድ መኳንንት)ክቡራን መኳንንት እንኳን ደስ ያላችሁ ። ወዳዲሱ ዘመን በመሸጋገራችሁ ። የሚያስደንቅ ሆነ ይሸማ ኃይላችሁ ። ዓለም አስደነቀ ጸንቶ አንድነታችሁ ። ሕግን መሥራት ሆነ መልካሙ ምክራችሁ ። ክቡራን መኳንንት ጥገት የምትገዙ ። ደህና መራርጡ እንጂ ከወገኑ አታብዙ ። ቅን ዋሉ ቅን ሥሩ ሀገርን ውደዱ ተገዙ ለንጉሥ ። ይጽና እምነታችሁም እንደ መርዶክዮስ ።

(መጽሐፈ አስቴር ም ፪ ቁ ፲፩ ም ፲ (ሮሜ ም ፲፫ ቁ ፩-፬)

(፯ለበጎ ሕዝቦች)ሰላም ለናንት ይሁን ድኅነት ለሁላችሁ። ወዳዲሱ ዘመን እንኳን ደረሳችሁ። እነሆ ምስጋና ለበጎ ሥራችሁ ። የሚገባችሁ ነው ማሰብ ላገራችሁ። በእምነት ማገልገልም ለየጌቶቻችሁ ። እንዲህ ስታደርጉ ብዙ ነው ዋጋችሁ።

(ሮሜ ም ፪ ቁጥር ፯)

(፰ለክፉ ሕዝቦች)ሰይጣን ለወዳጁ ምነው የለው እምነት ። ከሜዳ ይጥላል ሳያስቡት ድንገት ። እንዳትታመኑ በኃይሉ ጥግነት። የማይደርስበትን እሆናለሁ ማለት፡፡እስኪ ተመልከቱ ከታማኞች ወገን ሲለይ ከመላእክት። ይህ አያስደንቅም ከሃዲ ነው ከጥንት ። ሰይጣን አቅም አንሶት ከቤት ውጧል አሉ ። መላወስ አይችልም ተለይቶት ኃይሉ። አያድርስባችሁ ሲያምኑት የሚከዳ ። ገንዘብ ልቡን ነስቶት እንደነ ይሁዳ።(ማቴ ም ፳፮ ቀ፥ ፲፬ ፲፮ ማር ም ፲፬ቀ፥ ፲ ፲፪ ሉቃ ም ፳፪ ቀ፥ ፪ ፮ ዮሐ ም ፲፫ ቀ፥፪ ፳፯። መዝ ፪ ቀ፥ ፪ ፲፪)

(፱ለክፉዎች ፀር)ጭፍሮች ተሰብስበው ሲያንገራግሩን። የሥላሴዎች ኃይል በታተነልን ። ተልከስክሶ ቀርቶ ሰውን እንዳያስት ፈልን መርምሮ ማጥፋት ነው ። መልከስከሱ አይቀርም ሰይጣን ክፉ ሰው ነው ። ሳያወላውሉ ሳይጠራጠሩ በሥላሴዎች ኃይል ከታመኑባቸው ። ሰይጣናትን ሁሉ ለማጥፋት ይችላል በልዑል ስማቸው።በቀልዱ በዋዛው ከመከራከሩ።እኛ ምንቸገረን እንሒድ አምሩ።በቀልድ ነበር እንጂ ሕዝቡ መቸገሩ።በምሩማ ጊዜ ቀጥ ይላል ነገሩ። ይህ ቀልድና ዋዛ ለሰው ምን ጥቅሙ ነው፤፤ ጌታውን የሚወድ ፈቃድ መፈጸም ነው።(ማርም ፲፯ ቀ፥ ፲፰ ዮሐ ም ፲፬ ቀ፥ ፲፭።)

እንዲያው በጠቅላላው ክፉ በጎ ሳልል ። እምኑልዬሙ ኃትጉ ሕሱማን ሕዝብ አያልኩ በርግበ ኖኅ አምሳል ።

ኦሪት ዘፍጥረት ም ፰ቁ ፲ ፲፪።

አበባ አየርባለሁ ኃ ጊ ወልደማኤል ።

ስለ ወይዘሮ ዓፀደ ሞት ።

ወይዘሮ ዓፀደ የአዛዥ ሸብሩ ባለቤት ድሀ ወዳጅ እንግዳ ተቀባይ ነበሩ አዛዥ ሸብሩ ከሞቱ የልጆቻቸውን ርስት ጠብቀው ልጆቻቸውን አደባባይ ሳያወጡ በመሬት ባላንጣ ቢነሳባቸውም እንደወንድ ወጥተው ወርደው በአደባባይ ባላንጣቻቸውን ረትተው ይመለሱ ነበር ። ልጆቻቸውም ፬ት ናቸው ። ከመጀመሬ ባላቸው ወይዘሮ ደስታን ወልደዋል ። ከአዛዥ ሸብሩ ፫ ልጆች ወልደዋል ። ስማቸውም ይህ ነው። ወይዘሮ ላቀች፥ልጅ ሰብስቤ፥ ወይዘሮ አልታሺ ወርቅ ናቸው።በድንገተኛ ሕማም ታመው ወደ ሆስፒታል ወስደዋቸው ነበር።መቸም ቀኑ የደረሰውን ሰው አያድነውምና በመስከረም ፬ ቀን ሙተው መሳፍንትና መኳንንት፥ ወይዛዝር፥ ሊቃውንትና ካህናት አልቅሰውላቸው በአዲስ አበባ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበሩ።ብርሃንና ሰላም ልጆቻቸውንና ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ኃዘኑን ይገልጻል።

ስለ ፊታውራሪ ገብረ ሥላሴ ሞት ።

ፊታውራሪ ገብረ ሥላሴ የአፈ ንጉሥ ነሲቡ የታናሽ ኑኋታቸው ልጅ አፈ ንጉሥ ያሳደጓቸው ነበሩ። ኋላም ከወንድማቸው ከራስ ደምሰው ጋራ ይኖሩ ነበር። ራስ ደምሰውም አክብረው የፊታውራሪ ማዕርግ ሰጥተው ከፍ ያለ አገር ሰጥተዋቸው ይኖሩ ነበር። ራስ ደምሰው ከሞቱ በኋላ መንግሥትና ሕዝብ የወደዳቸው ጠባየ መልካም ጀግና ተኵስና ፈረስ አዋቂ ስለነበሩ ከማዕርጋቸው አልተዋረዱም ነበር። ደጃዝማች ዓምዴም በማዕርግ ይዘዋቸው ነበር። ግዛታቸው ወደ ወለጋ ድምበር አቅራቢያ ስለነበረ ለከተማው ሩቅ ነውና ወደ ከተማ ሲሔዱ የሳል ሕማም ስለ ነበረባቸው በብርድ ምክንያት ተነሥቶባቸው ወደ ከተማ ሳይደርሱ ከወንድማቸው ከደጃዝማች ደበይ ቤት ታመው ተኝተው በሐምሌ ፭ ቀን ሞቱ ብለው ለአፈ ንጉሥ መኰንን ደምሰው አርድተዋቸዋል። ዕድሜአቸውም ፵ ዓመት ይሆናል።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኀበር ቀጥሎ ያሉትን የበለ ዕዶቹን ቦታ ወደፊት በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል።

የክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደውን ፪ ቦታ አጥቢያው ሩፋኤልና ቂርቆስ ስፋቱ ፺፻ ሜትር ካሬና ፹፭ሺ፺፻፴፪ ሜትር ካሬ። ያቶ ታዬ ቦታ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፭ሺ፺፻፸፭ ሜትር ካሬ ። የፊታውራሪ በዳኔ አሸግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፱፻፲ና ፲ሺ፺፻፵፩ ሜትር ካሬ። የነጋድራስ ተፈራ ንጉሤ አጥቢያው ቂርቆስ ስፋቱ ፺ሺ፴፻፳ ሜትር ካሬ። የፊለቀችና የበጋለች ካሣ አጥቢያው ሩፋኤል ስፋቱ ፱ሺ፻፷ ሜትር ካሬ።

ያቶ ወንድማገኘሁ በዛብህ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፫፻፴፮ ሜትር ካሬ። ሽያጩም የሚደረገው በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ ነው። የሚሸጥበትን ቀን ወደፊት ከዚህ ቀጥሎ በሚወጣው ጋዜጣ እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

የዳግማዊ ምኒልክ፥ የተፈሪ መኰንን ፥ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ የቅዱስ ጊዮርጊስ፥ የእቴጌ መነን ትምህርት ቤቶች ስለ ዕረፍት ተዘግተው ስለቆዩ ለአዲሱ ዓመት በ፲፩ መስከረም ሺ፱፻፳፭ ዓመተ ምሕረት ይከፈታሉና በዚሁ በተወሰነው ቀን አስተማሪዎቹና ተማሪዎቹ ሥራቸውን እንዲጀምሩ እናስታውቃለን፡፡

የትምህርትና የጥበብ ሚኒስቴር ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት

ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
የቅዱ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፭ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲ ብር
፫ቱ መጻሕፍተ መነኰሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪ ብር
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪ ብር
ደስታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፱ ብር
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጅዖግራፊ ከነካርታው	፯ ብር
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፯ ብር
ድርሳነ ሚካኤል	፯ ብር
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኅሀ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪ ብር ፶መ
የእርሻ ትምህርት	፩ ብር ፶መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ እጅግ ያማረ	፪ ብር
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
የቊጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የነጻ ደንብ ከነተጨማሪው	፩ ብር ፶መ
የብድር ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ አዲስ	፩ ብር ፶መ
የገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
ዮሐንስ ቡንያን	፩ ብር
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፭ ብር
የ፪ኛ	፳ ብር
የ፫ኛ	፲፭ ብር
የ፬ኛ	፲ ብር
የ፭ ኛ	፯ ብር
የ፮ኛ	፯ ብር
የ፯ኛ	፯ ብር
፳፬ ካርት ፖስታል	፩ ብር
የረኮማንዴ ደብተር	፫ ብር
ሕገ መንግሥት	፭ ብር
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን ነገ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተሰማማ	፳ መሐ
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፳ መሐ
ያማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
አሳብና ምኞት	፲ መሐ
የፍቅር መላከት	፲ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፱ መሐ
የምሕረት አዋጅ	፲ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የንቁጣጣሽ ግጥም	፪ መሐ
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፪ መሐ
፩ ጋዜጣ	፪ መሐ
አርስጣላብ	፲ መሐ
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፲ መሐ
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፲ መሐ
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፩ መሐ
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፩ መሐ
ካላንድሬ	፳ መሐ
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪ	፩ መሐ
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፳ መሐ
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፲ መሐ

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት እጥፍ ። ነጠላ በያይነቱ ። እርሳስ መንኰልና ብረት ብርዕ ቀለም በያይነቱ፡የካርት ቢዚት እንቦልብና ካርት ቢዚት በያይነቱ ። እንቦልብ ትልቅና ትንሽ በያይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ስለሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሲጊያን ዘንድ ይገኛል ። ደህነኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተኩል ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው፡፡

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበሰል ፥ የልብ ፥ የደረት የጕበት ፥ የኩላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቁቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዳሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

እስከ መስቀል ድረስ አንድ የቤተ ሰብ መኪና የገዛ ሰው ደህና ሽልማት ያገኛል ።

በርቱ ይኽ እድል አያምልጣችሁ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ፡ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

በሲሊምስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፵
8me ANNE. № 40

ሐሙስ መስከረም ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 29 Septembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጠውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የመስቀል በዓል አከባበር

ታሪኩን እንደምታውቁት የመስቀል በዓል በየዓመቱ ይከበራል።ከዚህ ታሪክ ጥቂት ለሕፃናቱ እናመለክታለን። ዕሌኒ የግሪክ ንግሥት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል አይሁድ ቀብረውታል የሚባል ወሬ ስለሰማች ወደኢየሩሳሌም ሒዳ የጌታዬ መስቀል የተቀበረበትን አሳየኝ ብላ ከአይሁድ ሽማግሎች ብዙ ዕድሜ ያለውን አሥራ ብትመረምረው ምንም በዚያ ጊዜ ባልኖር በዚህ ወገን ሲባል እሰማለሁ ብሎ ስለነገራት የምትረዳበት ነገር ቢቸግራት ብዙ ዕንጨት ሰብስባ ደምራ ብዙ ዕጣን ሰብስባ ጸሎት አስደርጋ ዕጣኑን ለእሳቱ ብትጨምረው የዕጣኑ ጢስ የመራትን ቦታ ብታስቈፍር የጌታችንን መስቀል አገኘች።የመስቀሉንም ምልክት በልጓምና በጦር መሣሪያ ላይ አሠርታ ለልጅዋ ለንጉሥ ቈስጠንጢኖስና ለመኳንንቱ ፈረስ ብታስደርገው አሕዛብን ሁሉ ድል ነሣ ይባላል። ስለዚሁም ኢትዮጵያ በየዓመቱ ደመራዋን አዘጋጅታ ድል መንሣቷ በመስቀል ነው ስትል አርበኞቿን የጦር መሣሪ አልብሳ የጦር ሰልፍ ማሳየቷ ስለዚህ ነው።ይህንም የኢትዮጵያ አዋቆች ታጡታላችሁ ብለን አይደለም ነገር ግን ሕፃናቱና የውጪ አገር ሰዎች የመታሰቢአውን ምክንያት ስለጠየቁን የሰማነውን ጽፈናል። አዋቆች ይህን ታሪክ ለማግኘት ብትፈልጉ ከባለ ዜማው ከያሬድ መጽሐፍ ታገኙታላችሁ ። ዘንድሮም በዚሁ ልማድ በመስከረም ፲፮ቀን በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አጠገብ ደመራ ተደምሮ ታላቅ ሰልፍ ተደርጎ ነበረ። በደመራው ፊት ለፊት ድንኳኖች ተቀጣጥለው ተተክለው በመሐከሉ የጃንሆይ መንበረ ዳዊት ከነአጐበሩ ተዘርግቶበት ነበር ።

ነገር ግን ስለ ዝናሙ ጃንሆይ ከደመራው ራቅ ባለ ፎቅ ላይ ሁነው ይመለከቱ ነበር ። ከጃንሆይ ጋራም ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት፣ልዑል ራስ ካሣ፣ የኢትዮጵያ እልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ፣ክቡር ራስ ደስታ ዳምጠው ፣ ልዑል መኰንን ፣ ክቡር ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ የምክር ቤት አለቃ (ፕሬዚዳን) የውጪ አገር መኳንንት፣ ሌሎችም የኢትዮጵያ መኳንንት ነበሩ ። በድንኳኑ ውስጥ ግን ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትር፣ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ሌሎችም ታላላቅ መኳንንት ነበሩ ። ነገር ግን ሠራዊታቸውን አስከትለው በየተራ ደመራውን እየዞሩ ሰልፋቸውን እያሳዩ የተቀመጡ ነበሩ እንጂ እንዲያው ለማየት ብቻ አልተቀመጡም ነበር ። ስለ ኃዘን ምክንያት ሽልማት ጐድሎ ነበር እንጂ ሰልፉ ግን የሁሉም መልካም ነበር ። የከተማ ዘበኞችና በማጆር ፖሊ ውሥጥ ያሉት ወታደሮች በሰልፋቸው ማማር እጅግ ተመሰገኑ ። ጃንሆይና መሳፍንቱ፣ መኳንንቱ ፣ ሕዝቡና ሠራዊቱ ታላቅ ጭብጨባ አደረጉላቸው።በማግሥቱም በታላቁ አዳራሽ ታላቅ ግብር ሁኖ ዋለ አስቀድሞም ስለ በዓሉ ብዙ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ነበረ ። ብርሃንና ሰላም እንኳን ከዚህ አደረሳችሁ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ስለ ጀርመን ሚኒስትር መግባት ።

እንግዳው የጀርመን መንግሥት ሚኒስትር ሙሴ ፀሮን ፎንሼዌን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የታመኑ አማካሪ ነበሩ። ቀድሞም በሽንና በጃፖን በሜክሲኮ አገር በጀርመን ሌጋስዮንና አምባሳድ አማካሪነት ብዙ ጊዜ የቈዩ ናቸው ። በመስከረም ፲፫ ቀን ወደአዲስ አበባ በገቡ ጊዜ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ክቡር ከንቲባ መኰንን ተቀበሏቸው።ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለመገናኘት ቀጠሮ የተቀበሉበት በመስከረም ፲፯ ቀን ስለሆነ በዚሁ ቀን ዘበኛውና ወታደሩ በቀኝና በግራ ተሰልፎ የመገናኛውም ቦታ ታላቁ ቤተ መንግሥት አምሮ ተነጥፎ ይጠባበቅ ነበር ። ከእንግዳው ቀደም ብለው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አምሮ በተዘጋጀው ዙፋን ላይ ተቀምጠው ነበር። ለጀርመን ሚኒስትርም ጃንሆይ የቤተ መንግሥቱን ሊጋባ ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤልንና የውጭ ጉዳይ ዋና ጸሐፊውን አቶ ወልደ ጊዮርጊስን በአማረ አቶሞቢል ላከውላቸው ከጀርመን ሌጋስዮን ጀምረው በአንድ አቶሞቢል ግራና ቀኝ ሆነው የቀሩት የሌጋስዮን መኳንንትም በሌላ አቶሞቢሎች ሆነው መጥተው ከጃንሆይ ተገናኙ።ከፍቅር ሰላምታም በኋላ የጀርመን መንግሥት ሚኒስትር የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ።

በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘንድ የጀርመን መንግሥት ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሆኜ መሾሜን የሚያስረዳ የጀርመን ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ወደ ግርማዊነትዎ በእ

ጃቸው የጻፉትን ደብዳቤ ላስረክብዎ መታዘዜን ላስታውቅዎ ይፍቀዱልኝ ።

በጀርመን መንግሥትና በኢትዮጵያ መንግሥት በሕዝባችንም መካከል ያለችግር ሳያቋርጥ ጸንቶ የቈየውን ወዳጅነት ማጠንከርና ማስፋት ሥራዬ ስለሆነ በሥራዬ ሁሉ ሙሉ እምነትዎን እንዲሰጡኝ ግርማዊነትዎን እለምናለሁ ።

ይህነን ደብዳቤ ለግርማዊነትዎ ላስረክብ የጀርመን ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳንና የጀርመን ሕዝብ በኔ አማካይነት ለግርማዊነትዎና ለግርማዊነትዎ ቤተ ሰብ የሚያቀርቡትን ሰላምታና ለኢትዮጵያ ልማትና ሰላም የሚመኙትን ጥልቅ የሆነ ምኞት ለግርማዊነትዎእንድገልጽ ይፍቀዱልኝ ። ላደረጉልኝም ክቡር አቀባበል እጅግ ከፍ ያለ ምስጋናዬን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በማክበር አቀርባለሁ ።

ከዚህም በኋላ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚከተለውን የዲስኩር ቃል መልሰው አነበቡ።

ክቡር ሚኒስትር ።

የጀርመን ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን እርስዎን በእኛ ዘንድ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር አድርገው የሾሙበትን ደብዳቤ ስንቀበል ደስ ይለናል። ከብዙ ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያና በጀርመን መንግሥት በሁለቱም አገሮች ሕዝብ መካከል ሳያቋርጥ በመታደል ጸንቶ የቈየው የወዳጅነት መገናኛ ከዚህ የበለጠ እንዲጠነክርና እንዲሰፋ ለማድረግ ሙሉ አሳባችን ስለሆነ ተመርጠው የተላኩበትን ከፍ ያለውን ሥራዎን ለማከናወን እንዲችሉ የተገባውን እርዳታ እናጐድልብዎትም ።

የጀመርን ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን በእርስዎ አማካይነት ለእኛና ለቤተ ዘመዳችን ለኢትዮጵያም የሚመኙትን መልካም ምኞት ስለ ገለጹልን ምስጋናችንንና ወደ አገራችን እንኳን ደህና ገቡ እያልን እኛም በወገናችን ለጀርመን ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን ጤና ለጀርመን ሕዝብ ደስታ ለመንግሥቱም ልማት እንዲሆን የምንመኘውን ምኞት እንዲያደርሱልን እንለምንዎታለን ።

ስለ ጀርመን መንግሥት ሚኒስትር ክብር ብዙ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ። ምንም ከጀርመን ሕዝብ ሰነፍ ባይኖር አዲሱ ሚኒስትር እጅግ ብልህ ናቸው ይባላል ። ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ የተመሠረተውን የሁለቱን መንግሥታት ፍቅር እንዲአሰፉ ተስፋ እናደርጋለን።

የመልክም ዋጋ አመላለስ።

ፊታውራሪ ተፈሪ ሀብተ ሥላሴ በባሌ አውራጃ አዝማች ሁነው ወርደው ለኢትዮጵያ ወሰን ቀናተኛ ተጠባባቂ መሆናቸውን ሥራቸው ስለመሰከረላቸው ለዚሁ ለድካማቸው ዋጋ በሙሉ እስቲአገኙ ድረስ ለጊዜው የተቀበሉትን ዋጋ ቀጥለን ጽፈነዋል።

ሽልማት ።

በወርቅ ያጌጠ ቀሚስ ፥ ጥሩ ድርብ ፥ የሥላሴን ኒሻን ፥ ባለወርቅና ባለጉሜ ጐፈር፥ባለወርቅ አንፋሮ፥ ወርቅ ጋሻ ባለ ፈርጥ፥ ወርቅ ሙጣ፥የተንቈጠቈጠ ጐራዴ፥ ባለወርቅ መጣምር ፈረስ፥ በቅሎ ከነሥራቷ ተሸልመው በአደባባይ ብቅ ባሉ ጊዜ ወጣቶች ሁሉ መልከም አገልግሎት እንዲጠቅም ተረዱት።

የከፉ ዋጋ አመላለስ ።

አስቀድመን በብርሃንና ሰላም በባሌ አውራጃ ከነበሩት ሹማምንት የአለቃቸውን የፊታውራሪ ተፈሪን ትእዛዝ አንሰማም በማለት አለቃቸውን በውጋዴ በረሀ ጥለው ወደ ከተማ ስለሔዱ የአንዱን ጽፈን የቀሩትን ፍርድ በሚከተለው እናስታውቃለን ብለን ነበርና እነሆ የተፈረደባቸውን ቅጣት ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን።

ፊታውራሪ ተሰማ ሁለት ሺህ ብር መቀጫ ከፍለው ገሙ በደጃዝማች አበበ ዳምጠው ግዛት ፫ ዓመት እንዲታሠሩ ተፈርዶባቸዋል።

ፊታውራሪ ይልማ ሥዩም ሦስት ሺህ ብር ከፍለው ከምባታ በቢትወደድ ጌታቸው ግዛት ፫ ዓመት እንዲታሠሩ ተፈርዶባቸዋል ።ቀኛዝማች ኃይሉ አበፉርዳ አምስት ሺህ ብር መቀጫ ከፍለው ጐፋ በደጃዝማች በየነ መርዕድ ግዛት አምስት ዓመት እንዲታሠሩ ተፈርዶባቸዋል ። ቀኛዝማች እንዳሮ አምስት መቶ ብር መቀጫ ከፍለው ፯ ወር በሐረር አውራጃ በደጃዝማች አባ ሻውል ግዛት እንዲታሠሩ ተፈርዶባቸዋል ።

ቀኛዝማች በላቸው ይርጉ በሌላ መቀጫ ስለተቀጡ ፪ት ዓመት በአስበ ተፈሪ በአዛጋር ወርቅነህ ግዛት እንዲታሠሩ ተፈርዶባቸዋል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ፥ የነዚህን ሰዎች ነገር ብትመለከቱት በመታዘዝ የሚገኘውን ጥቅም፥ በአለ መታዘዝ የሚገኘውን ጉዳት መርምራችሁ መታዘዝን እንድትመረምሩ ብርሃንና ሰላም ያስጠነቅቃችኋል።

ስለትምህርት ።

ተሁሉ ነገር ኢትዮጵያን ዛሬ ወደኋላ ያስቀራት እውቀትን ማጣት ነው የሃገራችን ሰው ዛሬ በቅሎውን ትቶ ቢዩክ (በአቶሞቢል) ላይ ቂጥ ማለት፤ በርኖሱንና ኩታውን ትቶ ከት መልበስ፤ የሳር ጐጆውን ትቶ በግንብ ቤት መኖር፤ በጄ መብላቱን ትቶ በማንከና በሹካ መብላት፤ በጭፉ ገንዘቡ ሊገዛው የቻለውን ለማግኘት አላቃተውም። እነሆ ዛሬ ዋና ለሀገራችን ሰው መታወቂያ ምልክታችን የፈረንጅ ዕቃ ለመግዛት በመጓጓታችን ነው። ይህንንም የሚያስረዳ ጃንሆይ በልጋወራሽነታቸው ዘመን ወደአውሮፓ የሔዱ ጊዜ አብረዋቸው ተከትለው ከሔዱት መሳፍንት አንዱ ወደአንድ የፋብሪካ ቤት ገብተው ሲያዩ ለአስተናጋጃቸው የሚከተለውን ምኞታቸውን ገላጹ።

የናንተ ሀገር እንዲህ መሆኑዋ ይህ ይህ ቢኖራችሁ ነው የኛም ሀገር እንደናንተ ለመሆን ትበቃ ነበር ይህንን ገዝተን በሀገራችን ብናቆም ይህንን በተናገሩ መስፍን ሐሳብ የመኪና መኖር ወይም መኪናውን ለመግዛት መቻል የሀገር መልማት መሠልጠን ነው፥ ግን እኒያ መስፍን ዕድል በማጣት ተመኪናው በኋላ ያለውን ራስ አላዩም እንዲሁም ከኢትዮጵያ ሰዎች በየጊዜው በመንግሥትም መልእክት ሆነ ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ወደአውሮፓ በመጡ ጊዜ፥ በሆቴላቸው በረንዳ ላይ ሆነው የሚያደንቁት የአውቶሞቢሉን ብዛት የመንገዱ

መስፋትና ማማር፡ የቤቱን ማብለጭለጭና ጥዳት፡ የውሥጡን ምቾት፡የሮቁን ርዝመት ነው እንጂ የመንግሥቱን መትጋት፡ የሕዝቡን ሥራ መውደድ ከዚያ ሁሉ አውቶሞቢልና ከዚያ ሁሉ ከሚያምር መንገድና ቤት በኋላ ያለውን ራስ አያስተውሉም። ያልተማሩት ሰዎች ይቅሩና በትምህርት ምክንያት እንኳ ከወጣነው መሐከል ብዙዎች ይህን መኪና በሀገራችን ገዝተን ብናቆም ብዙ ሥራ ልንሠራበት ያቻላል እያለ ያመኛል እንዱ ጓደኛዬ በኢትዮጵያ ላይ የሬዲዮ ጣብያ በየቦታው ገዝቶ ለማቆም ዋጋውን እንደጠየቀና ዳግም ተቆመ በኋላ የሚገኘውን ጥቅም አስረድቶኛል ።

እኔ ግን በኢትዮጵያ መኪና ገዝተን ብናቆም ሬዲዮ ብንዘረጋ ጥቅም እንዳለው አላጣሁትም ነገር ግን ይህን መጻፌ እንግዛው እንጂ እንሥራው የሚል መንፈስ ከትልልቆች ጀምሮ እስከ እኛ እስከ ሕፃናቱ ድረስ ስላላገኘሁ ነው እንጂ ። አንዱ ወንድሜ ከአዲስ አበባ ሲጽፍልኝ ዛሬ አዲስ አበባ እንደወትሮው አትምሰልህ በጣም ሠልጥናለች የአውቶሞቢሉ ብዛት መንገድ አጣቧል፡ሕዝቡ የፈረንጅ ልብስ መልበስ፡ ጫማ ማድረግ ጀምሯል እያለ እንዲህም የመሰለ ብዙ ጽፎልኛል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ አውቶሞቢል ማብዛት፡የፈረንጅ ጠባይ መከተል፡የነሱን ምግብ መብላት ፤ የነሱን ልብስ መልበስ ክፋት የለውም ለምን እነሱ በጣም ከኛ በማነኛውም ነገር የተሻሉ ናቸውና ነገር ግን እኔ ላስታውቃችሁ የምፈልገው ዛሬ እንዲህ በደረጋችሁ ቁጥር የሃገራችሁን ሃብት ለሰው ሃገር ሰው መስጠታችሁ መሆኑንና የውጭ ሃገር ሰዎች አክብራችሁ ኢትዮጵያን ማደህዬታችሁን ላስረዳ ነው እንጂ ስለዚህ ዋና መድኃኒቱ ቢዩክ ኦቶሞቢል በመግዛት ፈንታ ልጆቻችሁን ማስተማር፡እናንተ በበቅሏችሁ መሔድ ትምህርት ቃለ ሒዳችሁም ያያችሁትን በጆሯችሁም ሰምታችሁ የምታደንቁትን በልጆቻችሁ እጅ እየተሠራ ሁሉንም ልታገኙት ልታዩት ትችላላችሁ ትምህርት ቃለ ሁሉ በቀስታ ይመጣል ያለትምህርት ሌላም እናገኝም ያለንንም እንዳናጣ በጣም ያስፈራናል ያለትምህርት በጭሩ ኢትዮጵያ መዳኛ የላትም።

የሰውን ባሕርይ የመረመሩ ሊቃውንት ዛሬ የሰው ጠባይ ከመቶው ዘጠና ስምንት እጁ የእንስሳ ባሕርይ መሆኑን አስረድተዋል ሰው ምንም ዛሬ በሰማይ ቢበር በምድር ቢሽከረከር ባሕርን ቀዶ ቢሔድ አረማዊነቱን አልለቀቀም በእንስሳ ዓለም ደግሞ ብርቱ ደካማውን አጥፍቶ ምግቡን ነጥቆ ቦታውን ይዞ ሊኖር ይፈልጋል ። በጭሩ ብርቱ እንጂ ደካማ ሊኖር አይችልም እንዲሁም ደግሞ ኢትዮጵያ ከሠለጠኑ ሕዝብ ተወዳዳሪና እኩል ሆና ነፃነቷን ጠብቃ ለመኖር ብትፈልግ በማነኛውም ነገር ከነሱ እኩል መሆን የግድ አለባት ፤ ሃገራችን በሀብት ረገድ ሁሉ ነገር አላት ፤ ያለትምህርት በቀር የጐደላት የለም ያለትምህርት ደግሞ የሚያድናት የለም ይህች ዓለም ለብርቱ ለተማረ ለሠለጠነ እንጂ ለደካማና ለአልሠለጠነ አይደለችምና ያለትምህርት ከርስታችን መነቀል የሚያስፈራ መሆኑ ጥርጥር የለበትም ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ባላባትና ከህናት፡ መኳንንትና መሳፍንት፡እጨጌና ጳጳሳት ስለምትወዱዋት ርስታችሁና ሃገራችሁ እርሱ፡ቆፍሮ፡ገብሮ፡ደሙን አፍሶ አስከብሮ፡ጌቶች አድርጎ ስለሚያኖራችሁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብላችሁ፡ ስለሚያስገዛችሁ ስለሚያስነዳችሁ ስለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብላችሁ ትምህርትን ውደዱ አትስነፉ ልጆቻችሁን አስተምሩ የግብር ይውጣን ሥራ ትታችሁ በቅን ልብ ትምህርትን የኢትዮጵያን መዳኛ ፈልጉ ለሚያልፍ ደስታ ብላችሁ የማታልፍ ጥበብን አትጡ።

መኰንን ደስታ ።

ሕክምናን መውደድና ማመስገን ይገባል ።

ይህንን ያልሁበት ምክንያት አሁን ባለፈው ሳምንት ነሐሴ ፲፱ቀን የባላምባራስ ዓለማየሁ ደርቤን ባለቤት ወይዘሮ መና አድማሱን በጠና ታመው ከነበሩበት ቤት አሽሽተው ከደጃዝማች ወንድ ይራድ ቤት ወስደዋቸው ነበረ።ሲአሸሹዋቸውም ስለሕመማቸው ብዛት ምንም አያውቁም ነበረ፡ሕመማቸውም ትኩሳት ስለሆነ ትኩሳታቸው እስከ አርባ አንድ ደርሶ ነበረ።ሕመማቸው ስለጸና ጃንሆይ በቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ገብተው እንዲታከሙ ስላደረጉ በታመሙ በስድስተኛ ቀናቸው ወደቤተ ሳይዳ ሆስፒታል ገብተው ቤተዘመዶቻቸውና አባታቸው ደጃዝማች አድማሱ፡ አጐታቸው ደጃዝማች አያሌው ከልክ ያለፈ ኃዘን አዝነው ነበረ፡ጃንሆይና መኳንንቱ ሚኒስትሮችም እየተመላለሱ ይጠይቋቸው ነበረ ብልሁ ዶክቶር ሐኔርም በትጋት ሲአክሙአቸው ሰንብተው መቸም የሰው ኃዘን ከብዙ መከራ ደሰውራልና ለሞት የሚጠበቁት ሴት ዛሬ ከሞት ድነው በጎ መሆናቸውን ስላየሁ ሆስፒታል ላቋሙልን ንጉሣችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ብዬ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እመለከታለሁ ።

ፍሥሐ ቀለመወርቅ።

የምስራች ።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ተማሪ ቤት ጅማ የተሠራው በ፲፱፻፳፫ ዓ ም ግንቦት ፳፩ቀን ተመሠረተ የግምቡና የክዳኑ ሥራ በ፲፱፳፬ ዓ ም በጥቅምት ወር አለቀ በሩና መስኰቱ የሉህ ንጣፉ ሰኔ ፲፭ ቀን አለቀ አሁን የዘይትና የቀለም ቅቡ ሁሉ አለቀ ። ግምቡን ሙሴ ማሪያናኪስ ሠራው የንጨቱን ሥራ ግን አባ ቡልቲ የሚባል የኢልባቦር ሰው ሠራው ይኸውም አባ ቡልቲ የሚባለው አናጢ የእውቀቱ ነገር ያስደንቃል ብረት ይሠራል ትንንሹን መፈልፈያና የጌጥ ማውጫውን እሱ በጁ ይሠራዋል እንጂ ተውጭ አይገዛም የእንጨትም ሥራ ሲሠራ ከበንያኖች ይበልጣል እንጂ አያንስም መኪና ይሰፋል ማንኛውንም ዓይነት ኰትና ሌላውንም ሁሉ ሲቀድና ሲሰፋ ያስደንቃል የተበላሸ ብረት መሣሪ ሲያድስ የእሱ ሥራ ነው ተብሎ አይጠረጠርም ይህሰው በዋና ከተማ ቢቀመጥ እንዴት እውቀቱ እየሰፋ በሄደ? ሳይማር ይኸን ዕውቀት ማግኘቱ አቶ ለገሠ ቸሩ የተፈጥሮን እውቀት ማመስገኑ የተፈጥሮን እውቀት ማድነቅ መገባቱን ይመሰክርለታል ይኸን ስላልሁ የተማሩትን መንቀፌ አይደለም ይኸውም ተማሪ ቤት

የፈጀውን ገንዘብ አሰናድቼ በየክፍሉ ላስታውቃችሁ ፍጹም ሐሳቤ ነው።የሥራውን መዋጣትና ማማር ግን በኔው በአሠሪው አፍ እንዳይሆን በሌሎቹ ባዩት ሰዎች ትሰሙታላችሁ ይኸውም ተማሪ ቤት በፍጥነት ሥራው በመፈጸሙና በመቃናቱ ምስጋና የሚገባቸው ለትክክለኛው ለብልሁ ባልደረባዬ ለክቡር ብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ ነው። በመንግሥቱ ሥራ ክፍል ሁሉ እንደ ብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ ያለ የሥራ መሪ ባልደረባ ባገኝ ሠራተኛው ሁሉ እንዴት ዕድለኛ በሆነ እኔም በመጀመሪያ ለመንግሥቱ ሥራ ስታመን እንደዚህ ያለውን ባልደረባ በማግኘቴ ዕድለኛ ነኝ ብዬ ለራሴ ለመመስከር እደፍራለሁ ። ያግሉ አባ ወሎ።

መወድስ ።

በእግረ ሐተታ የዐርግ ደብረ ምሥጢራት፤ ልቡና ብእሲ ጠቢብ እንተ ኢየዐርፍ እምረዊፅ ።
ወበእግረ ንዴት ይወርድ ኀበ ታሕታይ ግብፅ ።
እከኑ ኢይበውእ ብዕል ወብዝኀ ጥበብ በዋሕድ አንቀጽ
ባሕቱ ኢይጤየቅ ከመ በእንተ ምንት ከነ ፡ ተኀርዮተ ቢጽ እምነ ቢጽ ።
ዘንተሰ ኅዲገነ ፡ በውስተ ቀዳማይ ገጽ ።
ናስተሐይጽ በጥንቃቄ ከመ እግዚአብሔር ኢይዔምፅ ።
መልክዐ ፍጡራን ያንጽሕ እሞተ ኃጢአት ለምፅ ።
ለውሂበ ሀብት ወጥበብ እምጣነ ተሰቅለ ዲበ ዕፅ ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ።

የመረረ ሞት

ምንም ለጊዜው ሞት በሰው ላይ የጣፈጠ ባይሆን በሕፃናትና በጕልማሶች ላይ ሲሆን እጅግ የመረረ ሞት ይባላል ከመዝኑ ሞት መሪር እንዲል እንደዚህም ያልንበት ምክንያት ተስፋዬ ሽሬፍ የሚባል የወይዘሮ ማሚቴ ልጅ እናቱ ወይዘሮ ማሚቴ በተወለዱ በ፫ ዓመታቸው እናት አባታቸው ቤት ሳሉ ያባታቸው እኅት ወይዘሮ ሳካሜለሽና ባለቤታቸው ባላምባራስ ሽሬፍ ልጅ የሌላቸው መካን ነበሩና ከአባታቸው ለምነው ወስደው በመከባከብና በብዙ ማዕርግ አሳድገው አከለ መጠን ሲደርሱ ለባል ድረዋቸው ባመቱ ይኸን ልጅ ወለዱ ወደዚያው መካን ሰው መቸውንም መጓጓቱን አይተውምና ደግሞ ባላምባራስ ሽሬፍ ወይዘሮ ሳካሜለሽለዓይናችን ማረፊያ አገኘን ብለው ወስደው አሳደጉት ለትምህርት ሲደርስ ወስደው ከዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት አግብተውት ይማር ጀመረ ሲማርም ለሕይወቱና ለትምህርቱ ሥራ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ እየሰጡት ተማረ ስለዚህ ተስፋዬ ሽሬፍ ተብሎ ይጠራል እሱም በትጋት ተምሮ የፈረንሳዊ ቋንቋ አውቆ ነበር ሒሳብም እጅግ ያውቅ ነበር ያስተዳደጉም ነገር ዕለት ዕለት እያደገ ያድር ነበር ላየው ሰው ሁሉ ያስገርማል የ፴ ዓመት ጕልማሳ ይመስላል እንጂ የ፲፯ ዓመት ልጅ አይመስልም ነበር ለናቱም ፩ እሱ ብቻ ነበር ነገር ግን አምላክ ሲጠራው የሚቀር የለምና በድንገተኛ ሕመም ታሞ በመስከረም ፲፩ ቀን በተወለደ በ፲፯ ዓመቱ አረፈና ዘመድ አዝማድ ፣ወንድ መኳንንትና የሴት ወይዛዝር ተሰብስበ ታላቅ ልቅሶ ተደርጎ ዕንባ በዕንባ ተራጭቶ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በብዙኀ ክብር ተቀበረ ለወለዱት ለወይዘሮ ማሚቴ ላሳደጉት ለባላምባራስ ሽሬፍ ለወይዘሮ ሳካሜለሽ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ። የኀዘን ተካፋይ ዘውገ ወልደ ጻድቅ ።

የኀዘን መወድስ

በወይዘሮ የሺሐረግ ሞት ስላዘንሁ ይህን የሚከተለውን መወድስ አጽፋለሁ ።

ለበትረ አዳም ሞት ዘመደ ሥጋን፥ አንተ ይሔውጾን ዘልፈ ንዘንግዖ ለለ ዕለቱ ።
እንዘ በበ ዕለት ንሬኢ፥ ዕለተ ግርምት ምጽአቱ ።
እስመ ንብል ኵለሄ እንግዳ ውእቱ ።
ወእንዘ የኃልፍ በፍኖቱ ።
ዜና መዓዛ ሞት ንጸልእ፥ እንዘ ዜና ሕይወት ንፈቱ ።
ንኃፍርኒ ለትዝምደ ሞት ዘንጸልኦ በከንቱ ።
መቃብራተ ሰብእ መጻሕፍት እስመ ለስምዐ ሞት ይትከሠቱ ።
ወለ የሺሐረግ ዓባይ ሐረግ ልደቱ ።
በዘሰሐባ ለሞተ ሥጋ፥ ይትዓወቅ ተዘምዶቱ ።
ዘአለቃ ዳንኤል ደስታ ።

አቦማልተን
ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

ኦቦማልቲን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው። ኦቦማልቲን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል ኦቦማልቲን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ስ አ፡ ቤርን ናቸው። በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው።

ኦቦማልቲን አዲስ አበባ ባሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ሣጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

ማስታወቂያ ።

የራስ ኃይሉን ገንዘብ በፍርድ መንግሥት ስለወረሰ በራስ ኃይሉ ላይ ያለውን ዕዳ የሚከፍል መንግሥት ነውና ራስ ኃይሉ ላይ ገንዘብ አለን የምትሉ ሰዎች ሁሉ የገንዘባችሁን ልክ በዝርዝር ጽፋችሁ ለገንዘብ ሚኒስቴር አዲስ አበባ ላይ ለማቅረብ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ኅዳር ፳ ቀን ድረስ ቀጠሮ ተሰጥቷችኋል ።

ይህ የተወሰነው ቀጠሮ ከተፈጸመ በኋላ ግን የገንዘብ ሚኒስቴር አቤቱታችሁን አይቀበልም ። የምትፈልጉትንም ገንዘብ ለማግኘት አትችሉም ።

ስለ የገንዘብ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር።

AVIS

En vertu j'un jugement les biens du Ras Haïlou ayant été confisques au benefice du Gouvernement Ethiopien, il est porte a la connaissance du public qu'il se charge du paiement de toutes les dettes du condamne. Par conséquent il invite tous les créanciers du Ras Haïlou a présenter en détail leurs créances en les appuyant des pièces justificatives, au bureau du Ministère des Finances, et cela jusqu'au plus tard le 20 Hedar 1925 (29 Novembre 1932) inclus. Passe ce delai, aucune demande ni réclamation ne sera prise en considération.

Addis-Abeba, le 18 Maskerem 1925
(28 Septembre 1932.)

Pour le Ministre des Finances.
Le Directeur Genéral.

ማስታወቂያ ።

ስለ ሕዝብ ጥቅም ስንል አዲስ አበባ ውሥጥ ያሉት መድኃኒት ቀማሚዎች እሑድ እሑድና በበዓል ቀን ለዘወትርም ሌሊት ተራ ገብተው አንድ አንድ መድኃኒት ቤት ክፍት ሆኖ በድንገተኛ ሕመም ጊዜ ሕዝቡ ለበሽተኞች መድኃኒት ለመግዛት እንዲችል ለመድኃኒት ሻጭዎች ትእዛዝ ስለተሰጠና ሥራውም በተራ ስለተጀመረ ። ሁለተኛም በተራ ክፍት የሚሆነውን የመድኃኒት ቤት ሕዝቡ ለማወቅ እንዲመቸው ብለን በሳምንት ውሥጥ ክፍት የሚሆኑትን መድኃኒት ቤቶች የሚያመለክት ማስታወቂያ እሑድ እሑድ በፖስታ ቤት በር ላይ እንዲለጠፍ አድርገናልና ሕዝቡ እንዲያውቁ በብርሃንና ሰላም እናስታውቃለን ። ያገር ግዛት ሚኒስቴር።

ስለሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሲጊያን ዘንድ ይገኛል ። ይህንኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተሩብ ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

እመቤቴ ፥

ከሁለት ሳምንት ወዲህ አራዳ መዳረሻው ላይ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቦታ በተባለው ሰፍራ ሒደው እንደሆነ በጋሌዝ ሆቴል ጥግ በፖስታ ቤት አጠገብ የተከፈተውንና ሠፈሩን ያሳመረውን የመድኃኒት ቤት የሚአምረውን ዓይንዎም ሳያየው አልቀረም ።

ይኸነን የመድኃኒት ቤት ከግቢም ከውጭም ሲያዩት ለጊዜው ኑሮ እንደሚስማማ ሆኖ ለመቆም መቻላችንን ያለጥርጥር ያስረዳዎታል ።

የሚአክምዎም ሐኪም የሚአስፈልገውን ልዩ ልዩ ነገር በኔ ዘንድ ሊአገኝ ይችላል የሚአዘውም ትእዛዝ በትክክል ከእውቀት ሥራ ተከናውኖለት መድኃኒቱም በልከኛ ዋጋ ይሸጣል ። ደግሞም በኔው ዘንድ ሽቶም ሆነ ሌላም የጌጥ ነገር ሊአገኙ ይችላሉ።

በጥበብ ለሚመረመር ነገር ሁሉ በልዩ አውቃለሁ። ደግሞም ወደ መንገድ ስለሚሔዱ ሰዎች የመድኃኒት ሣጥናቸውን ለመቀበልና የሚአስፈልገውን መድኃኒት በውስጡ አሰናድቼ ለመስጠት እችላለሁ ።

በዚሁ ሰፍራ በየሳምንቱ ልዩ ልዩ ማመልከቻ እጽፍልዎታለሁ ።

እመቤቴ የማክበር ሰላምታዬን በምንት ይቀበሉኝ። ይላል አገልጋይዎ ኤም ማትሳኪስ ።

በሣንትራል ፋርማሲ መድኃኒት የሚቀምምና የሚሸጥ የፈረንሳይ የእንግሊዝ የኢጣልያን የግሪክ የዓረብ ቋንቋ እነጋገራለሁ ።

በሣንትራል መድኃኒት ቤት የሚያስፈልግ መድኃኒት መገኘቱንና በዚሁም መድኃኒት ቤት ከስድስት ሰዓት በኋላ ከሰበት እስከ አሥር ሰዓት ሐኪም ክልፋስ በሽተኞችን ለማከም መቀበላቸውንና ደግሞ ሐኪም ፊንያ ኪሊያ ከሥር እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት በሽተኞችን ለማከም መዘጋጀታቸውን አስታውቃለሁ ኤም ማትሳኪስ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ዕዳቹን ቦታ ወደፊት በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል ፡

የክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደውን ፪ ቦታ አጥቢያው ሩፋኤልና ቂርቆስ ሰፋቱ ፯፻ ሜትር ካሬና ፹፫ ሺ. ፯፻፹፪ ሜትር ካሬ ። ያቶ ታዬ ቦታ አጥቢያው ጊዮርጊስ ሰፋቱ ፫ ሺ. ፯፻፸፫ ሜትር ካሬ ። የፊታውራሪ በዳኔ አሸግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ሰፋቱ ፱፻፲ና ፲ሺ.፯፻፺፩ ሜትር ካሬ። የነጋድራስ ተፈራ ንጉሤ አጥቢያው ቂርቆስ ሰፋቱ ፯ሺ.፰፻፹ ሜትር ካሬ። የፊለቀችና የበጋለች ካሣ አጥቢያው ሩፋኤል ሰፋቱ ፬ሺ.፻፯ ሜትር ካሬ ።

ያቶ ወንድማገኘሁ በዛብህ አጥቢያው ጊዮርጊስ ሰፋቱ ፫፻፴፯ ሜትር ካሬ ። ሽያጩም የሚደረገው በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ ነው ። የሚሸጥበትን ቀን ወደፊት ከዚህ ቀጥሎ በሚወጣው ጋዜጣ እናስታውቃለን ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት

ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር	
የቅ ዮ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር	
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፫ ብር	
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር	
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲ ብር	
፫ቱ መጻሕፍተ መነኮሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪ ብር	
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪ ብር	
ዶስታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፱ ብር	
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር	
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር	
የዓለም ጅዖግራፊ ከነካርታው	፯ ብር	
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፮ ብር	
ድርሳነ ሚካኤል	፮ ብር	
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር	
ኅሀ ጽባሕ	፭ ብር	
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር	
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ ብር	
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪ ብር	፶መ
የእርሻ ትምህርት	፩ ብር	፶መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ እጅግ ያማረ	፪ ብር	
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር	
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር	
የቍጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩ ብር	
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር	
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር	
የነጋ ደንብ ከነተጨማሪው	፩ ብር	፶መ
የብድር ደንብ	፩ ብር	
የጦር መሣሪያ ደንብ አዲስ	፩ ብር	፶መ
የገዳም ደንብ	፩ ብር	
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር	
ዮሐንስ ቡንያን	፩ ብር	
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፫ ብር	
የ፪ኛ	፳ ብር	
የ፫ኛ	፲፫ ብር	
የ፬ኛ	፲ ብር	
የ፭ ኛ	፯ ብር	
የ፮ኛ	፯ ብር	
የ፯ኛ	፯ ብር	
፳፬ ካርት ፖስታል	፩ ብር	
የረኮማንዴ ደብተር	፫ ብር	
ሕገ መንግሥት	፭ ብር	
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፶ መሐ	
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን ነገ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፶ መሐ	
አጭር የዓለም ታሪክ	፶ መሐ	
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተስማማ	፶ መሐ	
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፶ መሐ	
ያማርኛ ምሳሌ	፶ መሐ	
አሳብና ምኞት	፴ መሐ	
የፍቅር መላክት	፴ መሐ	
ትምህርተ ሕፃናት	፴ መሐ	
የምሕረት አዋጅ	፴ መሐ	
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፳ መሐ	
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፳ መሐ	
የንቍጣጣሽ ግጥም	፳ መሐ	
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፳ መሐ	
፩ ጋዜጣ	፳ መሐ	
አርስጣላብ	፴ መሐ	
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፴ መሐ	
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፴ መሐ	
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፩ መሐ	
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፩ መሐ	
ካላንድሬ	፶ መሐ	
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪ	፩ መሐ	
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፶ መሐ	
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፴ መሐ	

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት እጥፍ ። ነጠላ በያይነቱ ። እርሳስ መንኰልና ብረት ብርዕ ቀለም በያይነቱ።የካርት ቢዚት እንቦልብና ካርት ቢዚት በያይነቱ ። እንቦልብ ትልቅና ትንሽ በያይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥የደረት የጕበት ፥ የኵላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቍቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቴክኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቆሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭፈረስዊስኪ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመንብኘት ።

ማስታወቂያ ።

እስከ መስቀል ድረስ አንድ የቤተ ሰብ መኪና የገዛ ሰው ደህና ሽልማት ያገኛል ።

በርቱ ይኸ እድል አያምልጣችሁ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ካገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪል ነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና እስመጭ

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
8^{me} ANNE. № 41

ሐሙስ መስከረም ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 6 Octobre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣዙት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numéro 2 piastres

የኢጣልያ ንጉሥ ወደ አስመራ መግባት ።

ግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ቪክቶር ኢማኑኤል በአለፈው ሳምንት ወደ አስመራ ገቡ ይባላል። ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢጣልያ ንጉሥ ወደ አስመራ መምጣታቸውን አስቀድመው አስታውቀዋቸው ነበርና የወዳጅነት አቀባበል እንዲቀበሉዋቸው የትግሬን መሳፍንት ልዑል ራስ ሥዩምንና ልዑል ራስ ጉግሣን ልከውላቸው ነበርና በመስከረም ፲፮ ቀን ከአዲስ አበባ በልዩ ባቡር ተሳፍረው በጁቡቲ በኢጣልያ መርከብ ተሳፍረው ከኢጣልያ ንጉሥ ጋራ አብረው አስመራ ገቡ ። እነዚህ የጃንሆይ መልእክተኞች መሳፍንት ከኢጣልያ ንጉሥ ጋራ በፍቅር በመገናኘታቸው ለንጉሡ እጅግ ደስ ሳያሰኛቸው አይቀርም ።

የክቡር ራስ እምሩ በደኅና መግባት ።

ክቡር ራስ እምሩ ወደ ሮማ ከሔዱ ሰንብተው ነበር የተላኩበትን ጉዳይ ፈጽመው በመስከረም ፳፬ ቀን በልዩ ባቡር ወደ አዲስ አበባ ስለ ገቡ እጅግ ደስ ብሎናል። ብርሃንና ሰላም እንኳን ደኅና ገቡ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

የመስቀል ግብር።

የኢትዮጵያ መኳንንት በየዓመቱ ለመስቀልና ለፋሲካ ለጭፍሮቻቸው ግብር ያደርጋሉ። ምክንያቱም አብረን እንደ በላን መስቀሉንም (መከራውን) አብረን እንቀበላለን ማለት ነው። ለፋሲካም ግብር መደረጉ ትንሣኤውንም አብረን እንነሣለን ማለት ነው ይባላል። ይህንም የምትጠራጠሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመከራው በፊት በጸሎተ ሐሙስ ለደቀ መዛሙርቱ ግብር እንደ አደረገላቸው ከአርባዕቱ ወንጌላውያን ታገኙታላችሁ። ሕዝቡ የሆዱን ልክ አውቆ መጥና ቢጠጣ ደግ ነበር አልን እንጂ አብሮ ያልበላ አብሮ አይሞትም ብለው ወታደሮች ይተርታሉና ከተቻለ ግብር ማብላት ክፉ አይደለም። ዛሬም በዚሁ ልማድ የንግድ ሚኒስትር ነጋድራስ ኃይሌ ወልደ ሩፌ በመስከረም፳፬ ቀን ታላቅ ግብር አድርገው በከተማ ኑዋሪዎችንና በድንገት ከየዳር አገር የመጡትን የጉምሩክ ሠራተኞችንና በየዳር አገር የተሾሙትን በሥራ ምክንያት ወደከተማ የመጡትን ነጋድራሶችንም ከየሥራው ክፍልም ዲሬክተሮች ወዳጆቻቸውን ጠርተው ነበር። በከተማ ኑዋሪዎች ነጋዴዎችንም ጠርተው ነበር። ከውጭ አገር ሰዎችም ጥቂቶች ነበሩ። የግብርውም አኳኋን እጅግ መልካም ነበር። ድንኳኑም እጅግ ሰፊ ነበር። ነገር ግን ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ እስከ አራት ጊዜ በየተራ እየገባ ተጋበዘ። በዚህም ጊዜ ሁሉ ድምጻቸውና አነጋገራቸው ያማረ አዝማሪዎች ነበሩና በልባችን ያለውን ሁሉ እንደ ሐኪሞች በጣጥም እያወጡ ያሳዩን ነበር። ግጥሙ ስለበዛ በሙሉ ልንጽፍላችሁ ጊዜ አላገኘንምና ጥቂቶችን ግጥሞች ጽፈንላችኋል።

ለመስቀል ጠጅ ማለት ከጥንት የመጣ ነው ።
የበጠበጠውን ማር ያሉት ለምን ነው ።
እያቈጠቈጠ ቀረበው ቤቱን።
ያን እሾህ ከሥሩ ሳንነቅለው ቀርተን ።
እባክህ ጌታዬ እወቅ በጠጅህ ።
ማር ማር እያለ ነው የሚአታልልህ ።
በላስታ በወሎ በጐጃም በጐንደር በዛ ደጅ ጠኚው።
ምን ያታክተዋል የጁን ላያጣው ።

እንዲህ እንዲህ እያሉ ሲአሰሙን ጊዜውን ሳናውቀው መሼ። ከዚህ በኋላ ሽምጋኝ ቀረበና ነጋድራስ ደስታና አንድ ሰው በየተራ እየተነሡ መልካም መልካም ዲስኩር ተናገሩ። ከዚህም በኋላ ወጣቱ ልጅ ደምሴ ወልዳማኑኤል በወረቀት ጽፎ ያነበበውን ዲስኩር ቀጥለን ጽፈንላችኋል ።

ክቡር የንግድ ሚኒስትር ጌታዬ ሆይ ።

በክቡርነትዎ ፊት ለመቆም ጊዜ ስላጋጠመኝ ጥቂት ቃል ለመናገር ታዛዥዎ ያሰብኩትን ክቡርነትዎ ይፈቅዱልኝ ዘንድ እለምንዎታለሁ ።

ክቡር ሚኒስትር ሆይ፤ ክቡር ዲሬክተር ሆይ፤ ጌቶቼ ሆይ።

ከቀድሞ አባቶቻችን ሲያያዝ እንደመጣው ልማድ አለቃ ለጭፍራው ግብር ከሚገኝባቸው በዓላት የመጀመሪያው በዓል ይህ የመስቀል በዓል ነው እንደዚህ ያለው አካሔድ አለቃ ለጭፍራ ፍቅሩን ለመግለጽ የታዛዦቹን ልብ በፍቅር የሚያስርበት ሰዓት ነውና ይህ መልካም ልምድ ለወደፊቱም ሳይነቀፍ ሊኖር የተገባው ነው ።

ክቡር ጌታዬ ሆይ፡አባት ልጆቹን በማዕዱ ዙሪያ እንዲሰበስብ እንዲሁም ክቡርነትዎ የጉምሩክ ሹማምንትንና ሠራተኞችን ከተመሰገነው ግብዣዎ መጥራትዎ ይህ ሁለተኛ ጊዜም ሆነ

ምንም የደግነትዎን ዝና ቀድሞ የታወቀ መሆኑን ብንሰማ የንግድ ሚኒስቴርን ክፍል ከያዙ ጀምሮ ከሰማነው የበለጠ ፍቅርዎንና ደግነትዎን በማግኘታችን የምንሠራው በየክፍላችን ያለው ሥራ ሁሉ እየተቃና ሔዷል ፤ ለዚህም ማስረጃ እንደኛው ምንም ሰዓቱ ንግድ የተበላሸበት ዓመት ቢሆን ንግድ ደምቆበት በነበረው ዓመታት የነበረውን ገቢ በልጦ በመገኘቱና በወጭም በኩል እያነሰ መሄዱ ትጋትዎንና ዕድልዎን ጭምር የሚገልጽ ስለሆነ ይህ ደስታ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሳይሰማቸው አይቀርም ።

ሁለተኛም የሂሳብ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ማቆማችሁ ጉምሩኮችን ሁሉ እንደሠለጠኑት አገሮች የሂሳብ ሥራ አከሔድ አሠልጥኖ ሂሳባቸውን በየጊዜው በደምብ መሰብሰቡ ለንግድ ሚኒስቴር መልካም እርምጃ ሆነው።የሥልጣኔውም ደረጃ አዲስ አበባ ውሥጥ ካሉ መሥሪ ቤቶች ሁሉ ተቀዳሚ ያደርገዋል ።

ጌታዬ ሆይ ፥ ታዛገርዎችዎንም ሁልጊዜ ብሩህ ገጽዎና ደግነትዎ ሲጐበኘን ሥራችን እንቅፋት አያገኘውም ስንል እንተማመንብዎታለን፤ ከዚሁም ሁሉ በላይ የበለጠ ፍቅርዎን ይገልጹልን ዘንድ በየዓመቱ ከማዕድዎ ዙሪያ እንድንገኝ በማሰብዎ መልካም ስምዎን ከኛ ጋራ ያስረዳልና የታዛጋርዎችዎ ናፍቆት በሄዱበት ይከተለዎታል መልካም ስምንም ለኋላ መታሰቢያ መተውን የሚበልጠው እድል አይገኝም ።

ጌታዬ ሆይ እንደዚህ ያማረ ማዕድ አዘጋጅቶ ክቡርነትዎ በመልካም ፈቃድ መሰብሰቡ ለታዛጋርዎችዎ ክብራችን ነውና ይህን ጠልቆ የሚሰማንን ደስታ ለጌታችን ለመግለጽ ይቸግረናል ። አሁንም በንግድ ሚኒስቴር ጠቅላይ ጽሕፈት ቤትና በሂሳብ ጠቅላይ ቤት ያሉት ሠራተኞችም ያላቸውን ደስታ እገልጽላቸው ዘንድ የለመኑኝን ለጌታዬ ካስታወቅሁ በኋላ ልዑል እግዚአብሔር ለጌታዬና ለክቡሩን ቤተሰብዎችም ዕድሜና ጤና ከዚህም የበለጠ ሀብት እንዲያድልዎ እየተመኘሁ በጉምሩክ ታናናሽ ሠራተኞችና በኔም በራሴ ስም ሆኘ ከልብ የመጣ የተለዩ ምስጋናዬን ለክቡርነትዎ አቀርባለሁ ።

ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፥ ኢትዮጵያን በነፃነቷ ለዘለዓለም ይጠብቅልን ።

ስለመልካሚቱ አገር ።

ጠቢባን ሰዎች ስም ቢያጡላት ማን አህሎሽ የሚሏት አንዲት ወይዘሮ ነበረች ። ከ፲፱፻ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ እስከ ፲፱፻፳፱ ዓመተ ምሕረት ደመና ጋርዷት ፀሐይ ተከልክላ ትኖር ነበር የባሏም ስም ያየው አይድን ይባል ነበር በ፩ ግምብ የሚኖሩ ፬ቱን ማዕዘን የሚዞሩ ፲ አዳኞች ነበሩት የቀበሮ ግልገል ይዘው አምጥተው ቢሰጡት ስሙን (መስሌ) እንደኔ ብሎ ሰይሞ ለማዳ ይሁን ብሎ በሚገዛው ሀገር ቢለቀው መኳንንቱን ለመዳቸው ደኅን ከእግዚአብሔር በቀር የሚወደው የለምና ድሆችን ግን የማይለምዳቸው ሆነ።ድሆችን እየነጠቀ እየወሰደ ችግር የሚባል ዋሻ አለ ከዚያ አያገባ መኳንንቱ ድሆችን በደለብን ብለው እንዳይጣሉት የድኆችን በጎች በየበዓላቱ ይልቁንም ቅዳሜና እሁድ በየሀገሩ ላሉ መኳንንት ፳፭በግ ሳያገባ አይውልም ነበረ።እኔም ይህን በየሁ ጊዜ ይህ ቀበሮ እንጂ የሠለጠነ ብርሃን ፀሐይ ባይደምቅ ነው ብዬ አዘንሁ የአናብስት ግልገሎች ስንኳ ኃይለኞች ሲሆኑ በጨለማ ምግባቸውን ነጥቀው ፀሐይ ከወጣ በኋላ ወደጕድጓዳቸው ገብተው ይውላሉ።ሰውም ከጧት እስከማታ ሥራውን ይሠራል ብሎ ነቢዩ ተናግሮ ነበር።ፈጣሪዬ ሆይ እንዲህ ያለውን ፀሐይ ለማየት አብቃኝ እያልሁ መሰላል በቆመበት በታ ተቀምጬ ለእግዜር ሳመለክት በ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት በ፪ኛው ሠርቀ ወርኅ በ፳፫ኛው ሠርቀ ዕለት ያ የተመኘሁት ፀሐይ በዓለም ላይ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሆኖ ሲአበራ አይቶ ያ ቀበሮ ሲሸሽ ከመንገድ ዳር ቆሜ አገኘኝ የጠሉት ይወርሳል የፈሩት ይደርሳል እንዲሉ እኔን ነጥቆ ወስዶ ችግር ከሚባል ዋሻ ፪፻፴፭ ለርቢ የተቀበልኋቸው የባለጸጋ በጎች ነበሩ ነጥቆ ወስዶ ለመኳንንቱ ሰጥቶ ሲመለስ እኔም ችግር ከሚባልዋሻ ከጨለማ ለመዳን ወጥቸ ስሮጥ ቀበሮውም ፪፻፴፩ በጎች ለመኳንንቱ ሰጥቶ ተመልሶ ሲከተለኝ ያብሩህ ፀሐይ ከወጣበት በደረስሁ ጊዜ ጥቂት ሰዎች አገኘሁ ያድኑኛል ብዬ ብጠጋቸው እንደኔ ያሉ ፈሪዎች ኑረው ፈርተው አስፈሩኝ።ምንም ቢሆን ቀበሮው የፀሐዩን መድመቅ አይቶ በከተማ የፈረሰ ግምብ አይታጣምና ከዚያ ገብቶ የምደርስበትን ገና ይመለከታል እኔ ግን ከድን ጋዬ ብዛት የተነሣ የቀን ብርድ ይዘኝ ስመኘው የኖርሁትን ፀሐይ እንዳልሞቅ በመስኮቱ አጠገብ ፍሬ የማይለያቸው ዛፎች አሉ ጥላቸውን ጥለውብኝ ብርሃኑን እያየሁ ሙቀቱን ስለተከለከልሁ እግዚአብሔር ከደዌ ኃዘንህ አድኖ ለተመኘሁሽው ፀሐይ ያብቃህ ብላችሁ አዘኑልኝ ስል ለብርሃንና ሰላም ልጆች ጓደኞቼን አመለክታለሁ። ይኄይስ ዘደብረ ወርቅ።

አለባበስ ቢያርሱ ባረም ይመለሱ ።

አቶ ማርቆስ ወልደ ጊዮርጊስ በብርሃንና ሰላም መስከረም ፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ቁጥር ፴፰ የጻፉት ማስጠንቀቂያ የሚከተለውን ለመጻፍ አሳሰበኝ። እውነት ነው ትምህርት ቤቶች እንዳሁኑ ጊዜ ሳይሆኑ አቶ ማርቆስ ወልደ ጊዮርጊስ እንዳሉት «ከዘመዶቻቸው ተለይተው» ከልዩ ልዩ አውራጃዎች ተነሥተው የትምህርትን እውቀት ለመፈለግ ወደ ዋናዋ ከተማ ገብተው ያገኙዋትና ሠርተው የሚያሳዩባት ብዙ ናቸው ። ከነዚሁም ደግሞ ወደ ካርቱምና ወደ ምስር ከአፍሪቃም ውጪ የተሰደዱ ነበሩ።

አቶ ማርቆስ ወልደ ጊዮርጊስ እንደጻፉት፤ እነዚህ ልጆች ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ የተባለውን ነገር እያስታወሱ፤ መቸም እናታችን ኢትዮጵያ ትሕትናውን እጅግ ታበዛዋለችና እንግዳ ተቀባይና አክባሪ ብቻ ሆና ትቀር መስሏቸው «እንደነሱ ለመሆን ሲሉ» ተሰደዱ፤ ግን ማን እንደሷ ሊቀበልላት ይችላል።

አሁን ትምህርት ቤቶች በመላ ኢትዮጵያ ቢከፈቱልንና ቢሰበክልን እንደዚህ ያለው ሕዝብ ወሰኑ የት ይሆን። እግዚአብሔር ይመስገን ሁሉም ተግተውበታልና ምንም ያህል አልቀረውም።

አቶ ማርቆስ ወልደ ጊዮርጊስ ስለ ልጆቹ ስደት ሙሉ ማስረጃ ለመስጠት ሲችሉ ስለምን አለባበሱት ይሆን? ይገባቸዋል ምናልባት አንድ ሰው ተነሥቶ ያለ ሥራህ ገብተሃል ብሎ ቢቃወማቸው ለሱ መልስ ሲያሰናዱ ሥራ እንዳይፈቱ አስበው ይሆናላ። ቢሆንም ሕልም ፈርቶ ሳይተኙ አያድሩምና መልከም አሳብን መግለጽ እንጂ መሸፋፈንስ አይገባም።

ከሰው ስሕተት፥ ከብረት ዝገት አይታጣም፥ ብርሃንና ሰላም ሆይ ምናልባት ሁሉም አያንዳንዱ ብልህ ነውና የተሰጠውን ይሥራ እንጂ ምክር አያስፈልግም ትለኝ እንደሆነ የማይቻል ነው፥ እንደምን ብትል፥ እጅና እግር በሥራ የተለያዩ ሲሆኑ በሕፃንነታችን ወራት ድኸንባቸው እዚህ ደርሰናል፥ ይልቁንም ዛሬ በዳገትና በቊልቊለት እንፏግርባቸዋለን።ይኸም ብቻ ሳይሆን የዚህ ዓለም ሁለተኛው ፈላስፋ፥ ብልህን ምከረው ብልሃት እንዲጨምር ብሎ ሰው በብልሃት ፍጹም አለመሆኑን ይመሰክራልና እነሆ ምክር ያስፈልጋል። ይልቁን ብልሆች ነን ሲሉ በብልሃታቸውና በራሳቸው አሳብ ብቻ የጠፉ ስንት ናቸው። እንግዲህ ረዳት የሌለውና ብቻውን የሚሔድ በዳገትና በቊልቊለት ተሰብብሮ መቅረቱን አትዘንጋው። የቀረውን የብርሃንና ሰላም ተመልካቾች እንዲጨምሩበት ተስፋ አለን።

የእእምሮ ደጅ ጠኚ ብርሃኑ መስቀል አየለ።

ስለ ክብር ዘበኛ የመስቀል ዕለት ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሁልጊዜ ረጅም ምኞታቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሥልጣኔና ላገራቸው ጥቅም ስለሆነ ሰሎሞን ከዕንቍ ጥበብ ትበልጣለች እንዳለ ለወታደሮቻቸው በብዙ ገንዘብ ቀጥረው የወታደር ትምህርት ደህና አድርገው የሚያውቁ አስተማሪዎች አስመጡላቸውና በሥልጣኔ ዘብ ለመጠበቅ መንግሥታቸውንና ባንደራቸውን ለማክበር ለኢትዮጵያ ደማቸውን ለማፍሰስ ሥጋቸውንለመጣል እንዲችሉ እንደ አውሮፓ ደምብ የከበሬታ አሰጣጥና የጦር ትምህርት ይማራሉ ያለ ግድ በውድ ያለጥርስ በድድ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ተከትለው ወደአገራቸ የመጣውን ጠላታቸውን ለመከላከል የተዘጋጁ ናቸው።ለምሳሌ ውኃ ሙላትና ጦርነት አንድ ነው በውኃ ሙላት ላይ ዋነተኛ ዋኝቶ ያለ አደጋ ለማለፍ ይችላል ዋና የማያውቅ ግን ለማለፍ አይችልም በጦርነትም ላይ ድል ለማድረግ ኃይልና ብዙ ጥበብ የሚያስፈልግ ነው የክብር ዘበኞች ቅዳሜ በየሳምንቱ ለባንዲራችን ደማችንን ለማፍሰስ ሥጋችንን ለመጣል የተዘጋጀንልሽ ነን ኢትዮጵያ እናታችን ዘለዓለም ኑሪልን እያሉ ለባንዲራቸው ትልቅ ምስጋና ያቀርባሉ ሙዚቀኞች የኢትዮጵያን ሕዝብ ማርሽ እንዲህ ብለው ይነፋሉ ።

ኢትዮጵያ ሆይ ደስ ይበልሽ ።
በአምላክሽ ኃይል በንጉሥሽ ።
ተባብረዋል አርበኞችሽ ።
ብዙ ናቸውና ተራሮችሽ ።
አይነካም ከቶ ነፃነትሽ ።
ድል አድራጊ ንጉሣችን ።
ይኑርልን ለክብራችን ።

ስላገር ፍቅር

መጀመሪያ የሚመነጭ ምንጭ ቢጠጡት አይጥምም የዱሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ እንደ ዳግማዊ ምኒልክና እንደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቀንና ሌሊት እንቅልፍ አጥተው ሐሳባቸው ሁሉ ሕዝባቸውን ጥበብ ለማጥገብና አገራቸውን ከዓለም ሁሉ የበለጠች ለማድረግ ታላላቅ መንገዶቹዋ እንዲሰፉና ብርሃን እንዲገባላት ቢሆን ምኞታቸው ኢትዮጵያ ለምለም አገራችን በሥልጣኔና በጥበብ የተጌጠች ትሆን ነበር።አሁን ግን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ረጅም ሐሳባቸው ላገራቸው ፍቅርና ለሕዝባቸው ጥቅም ስለሆነ ለኢትዮጵያ ብርሃን ጠባቂ ሁነው ሕዝባቸው እንዲጠቀምና እንዲከብር ችግር ማቅለያውን ጥቅም ማብገሯውን ቀንና ሌሊት እንቅልፍ አጥተው ስላሰቡልን የጠራ ምንጭ እንላቸዋለን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጥበብን አጠጥተን ለመጥገብና አንድነት እንደተሳሰረ ብረት በፍቅር ለመተሳሰር የሚያበቃው ንጉሣችን ስሙ ዘለዓለም የተደነቀ ይሁን። እኛም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ እናታችን ስለኛ እጆቹዋን ወደ አምላክ ስለዘረጋችና ብርሃን መንግሥት ስለሰጠችን በፍቅር ተሳሥረን እናታችንን ልዘለዓለም ደስ ለማሰኘትና አገራችን ከዓለም ሁሉ የበለጠች ትሁን እያልን ለማመስገን በብዙ ሕይወት ለመኖር ያብቃን ።

እላለሁ መንገሻ ገብረማርያም ።

ያማረ ክርስትና ።

የግብጽ መንግሥት ለጋሲዮን ዋና አነጋጋሪ ሙሴ ሐና ከሕግ ሚስታቸው የወለዷት ሴት ልጃቸውን መስከረም ፭ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም በሊቀጳጳሱ ግቢ በተሠራው በአቡነ እንጦንስ ቤተ ክርስቲያን ተጠምቃ ክርስትና ለመነሣት እንደተለመደው ሥርዓት የሚደረገው ቀን ነበረና የክርስትናው እንሺ ልዕልት ዓፀደ አስፋው ስለሆኑ በሊቀ ጳጳሱ ግቢ ከጥዋቱ በአንድ ሰዓት ባማረ አቶሞቢል ሁነው ተከታዮቻቸው በየአቶሞቢሎቻቸው እንደሆኑ መኳንንትና ወይዛዝር አስከትለው እቤተ ክርስቲያኑ ገቡ ቤተክርስቲያኑም አምሮ ተነጥፎ በሐር መጋረጃ ተጋርዶ የተዋበ ነበረና ከህናቱ አቡነ ያዕቆብና አቡነ ማርቆስ ሥርዓቱን አድርሰው ሕፃኒቱን አጥምቀው ቀድሰው አራት ሰዓት ተኩል ሲሆን ሥራውን ፈጽመው ሕዝቡንና ክርስትና አስነሺዎችን አሰናበቱ ። ከዚያ በኋላ በየአቶሞቢሎቻቸው ተቀምጠው የሕፃኒቱን ወላጆች ሙሴ ሐናና ማዳም ሐና ከዚያውም የነበሩት መኳንንቶችና ወይዛዝር ልዕልት ዓፀደ አስፋውን አጅበው ወደ ወላጆች ቤት ገብተው እንደ ማዕርጋቸው ወደተሰናዳው ማረፊያ ቤት ገብተው ተቀመጡ ከዚያ በኋላም ቻይና ጣፋጭ ብስኩት ተጋብዘው ተመራርቀው ልዕልት ወይዘሮ ዓፀደና ተከታዮቻቸው የቤቱን ሥርዓት እያመሰገኑ ሔዱ።፯ሰዓት ተኩል ሲሆን የቀረው ዘመድ ወዳጆቻቸውን እኳኋኑ በሚያስደንቅ ግብዣ ጋብዘው ሰውን ደስ አሰ

ኟተው ዋሉ ። እኔም ተጠርቼ ሒጄ ነበረና ግብዣውንና ሥርዓቱን አይቼ አኳኋኑን ለተወደዳችሁ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እጽፍላችሁ ዘንድ ወደድሁ ።

በነምባራስ በርሄ ዘደብረ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ ።

የሥልጣኔ እርምጃ።

የከተማ ዘበኞች የከተማ ዘበኝነት ከተመሠረተ ጀምሮ እስከሁን ድረስ እንደ ኤሮፓ ሥርዓት ሁሉ ሰልፋቸውን እያሳዩ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ሲያልፉ ምስጋና ክብር እያገኙ በሥልጣኔ ላይ ሥልጣኔ እየጨመሩ የምስጋና ተቀዳሚ ሆነው መቈየታቸውን አስተዋይ ሕዝብ አይስተውም። አሁንም እነዚሁ የከተማ ዘበኞች የዘበኝነቱ ሥራ ሳይጐድልባቸው የሰልፍ ትምህርታቸውን እንደ ኤሮፓ ደምብ ሁሉ እያሻሻሉ በትጋት እንዲማሩ አድርገው ክቡር ከንቲባ መኰንን ትእዛዛቸውን አሳልፈውላቸው ነበርና ደልቁንም በየጊዜው የትምህርትንና የሥልጣኔን ጥቅም እየሰበኩ ወደ በጎው ፈቃድ ስለመሯቸው የከተማ ዘበኞች እንደ ልማዳቸው ሁሉ በዘንድሮው መስቀል ተሰልፈው በንጉሠ ነገሥቱና በመኳንንቱ በዲፕሎማቲክ ሰዎች ፊት ባለፉ ጊዜ የሥልጣኔን ጥቅም ከሚያውቁት ወገኖች እነዚህ የከተማ ዘበኞች በዛሬው በዓል ያሳዩት የሰልፍ ትምህርት እንደ ኤሮፓ ወታደሮች ሁሉ ሙሉ ሥልጣኔ ያለው ደስ የሚያሰኝ ነውና ስለዚህ የታላቁ ንጉሠ ነገሥት ዕድል በጣም የገነነ ነው። ይህንንም የሰልፍ ትምህርት በሙሉ ተምረው ለማሳየት የበቁት በከንቲባውና ባስተማሪአቸው መሪነት ስለሆነ የከንቲባውንና ያስተማሪአቸውን ትጋት ሳናስታውስ እንዘለውም ብለው ተናግረዋል።

እንግዲህ የከተማ ዘበኞች በሥራቸው ተግተው ለከተማው ሕዝብ የሠሩትን ውለታ በየጊዜው መነገሩን ካሳሰብን በኋላ አሁንም ደግሞ ከላይ እንዳመለከትነው ሁሉ የሰልፍ ትምህርታቸውን አሻሽለው በደህና ሥልጣኔ ተምረዋል የሚል የምስጋና ቃል ካዋቂዎቹ ዘንድ ስለ ሰማን ያዋቂዎቹ ምስጋና ለሥልጣኔአቸው ምስክር የሚሆናቸው ነው በማለት ጽፈነዋል ።

ሹም ሽር ።

ልጅ በቀለ ሀብተ ገብርኤል ለመንግሥት የታመነ አገልጋይ ስለሆነ ይልቁንም አስቀድመን እንዳስታወቅናችሁ ሁለት ወምበዶች ይዞ በችሎት ስለአቀረበ ሽልማት አግኝቶ ነበር አሁንም የነጋድራስ ጽጌ የነበረውን የአሩሲን ነጋድራስነት ተሾመ።

የመከር ወሬ።

ዘንድሮ በኢትዮጵያ እጅግ አዝመራው አምሮ ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኝቶታል። አንበጣም የለም የዝናሙ ወራትና የበራው ወራት በመተካከሉ እህሉ አፍርቷል።ፍሬውን በማየት ገበያችን ጠግቧል። ከየዳር አገር የመጡት ሁሉ በየአውራጃው የአህሉንና የሳሩን አበቃቀል እጅግ ያደንቁታል ። በከተማችን ዙሪያ ያለው አዝመራ ሁሉ እጅግ ደስ አሰኝቷል። ዝናም እስከ መስቀል ድረስ የዘነመ እንደሆነ ለአዝመራ መልካም ነው እንደሚባለው ልክ እመስቀል ድረስ ዘንሞ በራ።የደመራና የመስቀል ዕለት ግን አጥብቆ ስለዘነመ ገፍ ሊሆን መስሎት ሕዝቡ ሁሉ እጅግ ፈርቶ ነበር ቸሩ አምላክ መቸም ለፍጥረቱ አዛኝ ነውና ሕዝቡ እንደ ሚወደው አደረገለት። ይህንም የጻፍንላቸው በውጪ አገር የሚኖሩ የኢትዮጵያ ተወላጆችና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ ደስ እንዲላቸው ነው እንጂ በአገሩ የሚኖር ሰው ይህን ደስ የሚአሰኝ ወሬ ሳያውቀው ይቀራል ብለን አይደለም ።

ማስታወቂያ ።

በክሳራ ስም በተጠራው በቤኒዳስ ኔምቻንድ ነገር ሁለተኛው ክፍያ ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም እንዲደረግ መታሰቡን እየአመለከትን ማስረጃቸውን የአላቀረቡ ገንዘብ ፈላጊዎች ወደ እንግሊዝ ቆንስላ እየመጡ ከዚህ በታች በግርጌው ፊርማውን እፈረመው ሰው ዘንድ እስከ ዕረቡ ኅዳር ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ድረስ የአላቀረቡ እንደሆነ በክፍያው ውሥጥ የማይገቡ መሆናቸውን እናስታውቃለን።

መስከረም ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ተጻፈ አ አ።
ቴ ዲ አየር አፊሲዮል አሲኚ።

የሚሸጥ ቦታ ።

ማጀስቲክ ሆቴል አጠገብ ከሙሴ ሃርዲ ፊት ለፊት መሐመድ አሊ ከሠራው አዲስ ፎቅ በታች ጥሩ ጥሩ ቤት የተሠራበት በወሩ እስከ መቶ ብር ድረስ ክራይ የሚያመጣ ጥሩ የሚሸጥ ቦታ አለና የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ አቡጀዲድ ገበያ ላይ ወችራጅ የሚባል ሒንዲን ጠይቁ።

አበማልተን
ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

አበማልተን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው። አበማልተን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል አበማልተን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፥ ቤርን ናቸው። በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው።

አበማልተን አዲስ አበባ ባሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ማጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

ማስታወቂያ ።

የራስ ኃይሉን ገንዘብ በፍርድ መንግሥት ስለወረሰ በራስ ኃይሉ ላይ ያለውን ዕዳ የሚከፍል መንግሥት ነውና ራስ ኃይሉ ላይ ገንዘብ አለን የምትሉ ሰዎች ሁሉ የገንዘባችሁን ልክ በዝርዝር ጽፋችሁ ለገንዘብ ሚኒስቴር አዲስ አበባ ላይ ለማቅረብ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ኅዳር ፳ ቀን ድረስ ቀጠሮ ተሰጥቷችኋል ።

ይህ የተወሰነው ቀጠሮ ከተፈጸመ በኋላ ግን የገንዘብ ሚኒስቴር አቤቱታችሁን አይቀበልም ። የምትፈልጉትንም ገንዘብ ለማግኘት አትችሉም ።

ስለ የገንዘብ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር።

AVIS

En vertu j'un jugement les biens du Ras Haïlou ayant été confisques au benefice du Gouvernement Ethiopien, il est porte a la connaissance du public qu'il se charge du paiement de toutes les dettes du condamne. Par conséquent il invite tous les créanciers du Ras Haïlou a présenter en détail leurs créances en les appuyant des pièces justificatives, au bureau du Ministère des Finances, et cela jusqu'au plus tard le 20 Hedar 1925 (29 Novembre 1932) inclus. Passe ce delai, aucune demande ni réclamation ne sera prise en considération.

Addis-Abeba, le 18 Maskerem 1925
(28 Septembre 1932.)

Pour le Ministre des Finances.
Le Directeur Genéral.

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሴጊያን ዘንድ ይገኛል ። ይህንኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተኩል ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

ፋርማሲ ሣንትራል ተናግሮት የነበረውን በገዛ ዓይንዎ አይተው ስለተረዱት በጣም ደስ አለኝ ፤ መጥተው ስለተረዱ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ወደፊትም እየመጡ እንዲሁ እንዲረዱልኝ እመኛለሁ ።

እንደ ተባባልነው ስለ መልክዎ ጥንቃቄ አሁን ጥቂት እመክርዎታለሁ ።

የመልክን ቆዳ ስለሚአበላሹ በሺታዎች የተቀመሙትን ሳሙናዎች ሲወስዱ መልካም ሆኖ በረቂቅ ሺታ የተሰናዳውን የውበት ሳሙና ይውሰዱ ። ፊትዎን አልፎ አልፎ ጭረት ስለሚአደርገው በሺታ ኤፌሌን የሚባለውን መድኃኒታችንን እንዲአደርጉ አጥብቀን እንመክርዎታለን ። በጥቂት ቀን ደህና እንዲሆኑ ይኸንን መድኃኒት ማድረግ ነው። እስከሁን ድረስ እሱን የሚተካከል ሌላ መድኃኒት አልተገኘም ።

በፊትዎ ላይ ስለሚአደርጉት የሽቶ ዱቄት ወዝ ለሌለው መልክ «ኮልድ ክሬም» የምንለው መድኃኒታችን መልካም ነው፤ወዝ ላለው ፊት ግን «ሌቢርዠናል» የሚባለው መድኃኒታችን ነው የሚሻለው ስል እመክርዎታለሁ ።

ደግሞ በያይነቱ የተሰናዳውን የሩዝ ዱቄት ሺቶ «የኮቲም»ሆነ«የፒቤርትም»ሆነ ሌላም በያይነቱ ለማየትና ለመምረጥ ይችላሉ፤ እንዲሁም ለከንፈር ቀለም የሚሆን እርሳስ ለያይነቱ አለኝ ዘወትርም ስለ አሚታሹበት ኦዲክሎኝ ይልቁንም ከድካም ባረፉ ጊዜ የሚታሹበትን ከኔ ዘንድ እንዲወስዱ አምናለሁ በዚሁ በፋርማሲአችን ውስጥ ለፊትና ለገላ ማሻ የላስቲክም ሆነ የውነተኛውም ኤፓንገር ሆነ አለን ብለን አስታውቀንዎታልና ሁለተኛ መናገር ያስፈልግ አይመስለኝም ።

ደግሞም በያይነቱ በአውቀት ጥበብ ስለሚመረመር ነገርና ስለ መንገድ መድኃኒት ማሰናዳት በልዩ ማወቄን እንዳይረሱ አስታውሳለሁ አገልጋይዎ ኤም ማትሣኪስ ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ዕዶቹን ቦታ ወደፊት በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል ፡

የክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደውን ፪ ቦታ አጥቢያው ሩፋኤልና ቂርቆስ ስፋቱ ፺፻ ሜትር ካሬና ፹፭ ሺ ፺፻፹፪ ሜትር ካሬ ። ያቶ ታዬ ቦታ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፭ ሺ ፺፻፸፭ ሜትር ካሬ ። የፊታውራሪ በዳኔ አሸግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፱፻፲ና ፲ሺ ፺፻፺፩ ሜትር ካሬ። የነጋድራስ ተፈራ ንጉሤ አጥቢያው ቂርቆስ ስፋቱ ፺ሺ ፹፻፹ ሜትር ካሬ። የፈለቀችና የበጋለች ካሣ አጥቢያው ሩፋኤል ስፋቱ ፬ሺ ፻፺ ሜትር ካሬ ።

ያቶ ወንድማገኘሁ በዛብህ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፫፻፴፺ ሜትር ካሬ ። ሽያጩም የሚደረገው በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ ነው ። የሚሸጥበትን ቀን ወደፊት ከዚህ ቀጥሎ በሚወጣው ጋዜጣ እናስታውቃለን ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት ማስታወቂያ

* * *

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር	
የቅ ዮ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር	
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፭	ብር	
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር	
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲	ብር	
፫ቱ መጻሕፍተ መነኮሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪	ብር	
የወንጌለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪	ብር	
ዶስታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፱	ብር	
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር	
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር	
የዓለም ጅዖግራፊ ከነካርታው	፯	ብር	
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፯	ብር	
ድርሳነ ሚካኤል	፯	ብር	
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር	
ኀሀ ጽባሕ	፭	ብር	
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር	
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር	
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪	ብር	፰መ
የእርሻ ትምህርት	፩	ብር	፰መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ እጅግ ያማረ	፪	ብር	
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር	
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር	
የቊጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩	ብር	
የአማርኛ ሰዋሰው	፩	ብር	
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር	
የነጋ ደንብ ከነተጨማሪው	፩	ብር	፰መ
የብድር ደንብ	፩	ብር	
የጦር መሣሪያ ደንብ አዲስ	፩	ብር	፰መ
የገዳም ደንብ	፩	ብር	
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩	ብር	
ዮሐንስ ቡንያን	፩	ብር	
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፭	ብር	
የ፪ኛ	፳	ብር	
የ፫ኛ	፲፭	ብር	
የ፬ኛ	፲	ብር	
የ፭ ኛ	፯	ብር	
የ፮ኛ	፯	ብር	
የ፯ኛ	፯	ብር	
፳፬ ካርት ፖስታል	፩	ብር	
የረከማንዴ ደብተር	፫	ብር	
ሕገ መንግሥት	፭	ብር	
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፰	መሐ	
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን ነገ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፰	መሐ	
አጭር የዓለም ታሪክ	፰	መሐ	
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተስማማ	፰	መሐ	
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፰	መሐ	
ያማርኛ ምሳሌ	፰	መሐ	
አሳብና ምኞት	፬	መሐ	
የፍቅር መላክት	፬	መሐ	
ትምህርተ ሕፃናት	፬	መሐ	
የምሕረት አዋጅ	፬	መሐ	
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪	መሐ	
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪	መሐ	
የንቁጣጣሽ ግጥም	፪	መሐ	
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፪	መሐ	
፩ ጋዜጣ	፪	መሐ	
አርስጣላብ	፬	መሐ	
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፬	መሐ	
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፬	መሐ	
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፩	መሐ	
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፩	መሐ	
ካላንዴሬ	፰	መሐ	
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማጀ	፩	መሐ	
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፰	መሐ	
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፬	መሐ	

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት እጥፍ ። ነጠላ በየይነቱ ። እርሳስ መንኮልና ብረት ብርዕ ቀለም በየይነቱ።የካርት ቢዚት እንቦልብና ካርት ቢዚት በየይነቱ ። እንቦልብ ትልቅና ትንሽ በየይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ ፥ የደረት የጕበት ፥ የኲላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቍቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዣና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወኪሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዶች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው፡ ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቊረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጐብኘት ።

ማስታወቂያ ።

እስከ መስቀል ድረስ አንድ የቤት ሰብ መኪና የገዛ ሰው ደህና ሽልማት ያገኛል ።

በርቱ ይኸ እድል እያምልጣችሁ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዮ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

በሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዘር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና እስመጭ

ስምንተኛ ዓመት ቊጥር ፵፪
8me ANNE. № 42

ሐሙስ ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 13 Octobre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያን ልጆች የሚያኰራ ወሬ ።

እኔ ከሀገሬ ከወጣሁ አሥራ ሁለት ዓመቴ ነው ከወጣሁም ጀምሬ እስከ አሁን ድረስ በአሜሪካ ነው የምኖረው። ወደውጭ አገር ለትምህርት ከወጡት ከሀገሬ ልጆች ብዙዎችን አላውቃቸውም ነበር። አሁን ከሁለት ዓመት በፊት ሦስት ኢትዮጵያውያን ለትምህርት ወደአሜሪካ መጡ የሚል ወሬ በጋዜጣ አነብብሁ፤ ካለሁበት ከተማ እነሱ ወደነበሩበት ርኅቀቱ ከስድስት መቶማይል የበለጠ ስለሆነ ላገኛቸው አልቻልሁም ።

ከነዚሁም አንዱ ልጅ መኰንን ደስታ የሚባለው በትልቁ በአሜሪካ ከሁሉ ከሚበልጠው ስመ ጥሩ ዩኒቬርስቲ ሐርበርድ ከሚባለው ገብቶ በመማሩ እኔም እንደኔም ለመሰሉ አሜሪካን ለሚያውቁ ሰዎች አስደንቆናል። ምክንያቱም በዚያ ተማሪቤት የሚገቡ ልጆች ሁሉ በትምህርት ምርጥና ብርቱዎች እንጂ ማንም ሊገባበት አይቻልምና። አንድ ተማሪ አገኘሁና ስለርሱ ብዙ ጨዋታ አጫወተኝ በትምህርቱ ብዙኅ ብልህ ስለሆነ በሀርበርድ ዩኒቬርስቲ ሊግ ኦፍኔሽንዝ የሚባለው ማኅበር ተመርጦ ገብቷል፡ ወደፊት ደግሞ ከማኅበረተኞቹ ደኅና ደኅና ልጆች መርጦ ወደኦውርጳ ባለው ዋነኛው ሊግ ኦፍኔሽንዝ ዩኒቬርሲቲው በግዛ ከሳራው ተማሪዎችን ይሰዳልና እሱ ምናልባት ከሚመረጡት አንደኛው ሳይሆን አይቀርም ቢለኝ እጅግ ደስ አለኝ። በተረፈ ደግሞ በጋዜጣ ቦስቶን በሚባለው ከተማ በብዙ ቦታ ሊቃውንቶችና ፈላስፋዎች በተሰበሰቡበት ላይ ስለ ኢትዮጵያ በየጊዜው የሚያስደንቅ ንግግር መናገሩንና ሰው ሁሉ ግሩም ማለቱን በነበብሁ ጊዜ በደስታ ፈነደቅሁ። አንድ ጊዜ እንዲሁ ተለምኖ በሬዲዮ ሲናገር መላ አሜሪካ ከጠረፍ እስከጠረፍ ሰማው ይኸንንም መጻፌ ስራው ሁሉ በጣም ደስ ስላለኝ ነው። እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግሥት ለወደፊቱ ቶሎ ቶሎ ብሎ አገራቸውን የሚያስታውቁ ሕዝባቸውንና መንግሥታቸውን የሚያስከብሩ በብልህነታቸው የሚያስደንቁ ላሉም ለሚመጡም መኩሪያ የሚሆኑ ልጆች ሰዶ እንዲማሩና ኢትዮጵያን በዓለም ባሉ ሕዝብ እንዲያስመሰግኑዋት ምኞቴ ነው ።

ዘውዴ በየነ አሜሪካ ።

እውነተኛ ትጋትን የሚገልጽ አገልግሎት።

ሰው መሀይምንም ድኃም ቢሆን ለመንግሥቱና ለውዲቱ አገሩ ኢትዮጵያ ሲል የፍቅር ቅናት አሳብ የማይቈረቈረው እንደሌለ አስተዋዮች ሰዎች የሆኑ ሳያውቁት እንደማይቀሩ ጥርጥር የለበትም። እንዴት ማለት ያ ድኃ የሆነ ሰው ስንፍናን አርቄ በድኅነት ጉልበቴ የምሠራውን ሥራዬን በእውነት እያገለገልሁ መንግሥቱን ደስ አሰኛለሁ። አገሬን የሚፈልግ የውጪ ጠላት ቢመጣ ለአገሬ ነፃነት ስል ሕይወቴን ለመሠዋት አሳልፌ ደሜን አፈሳለሁ ብዬ ነው እንጂ ያጨከኝ ጠላት ሲመጣ ለነፍሴ ወደኋላዬ አፈገፍጋለሁ እንዳይል የንጉሡ መልክም ቸርነትና የአገሩ ነፃነት ፍቅር አእምሮውን በትዝብት ይወቅሰዋል ። እንደዚሁም ጌታ የሆነ ሰው ከመንግሥቱ ዘንድ የተቀበልሁትን እውነተኛ ታማኝነት ወገኖቼን ለራሴ ጥቅም ብቻ ብዬ እንዳልጐዳቸው የንጉሜን ርኅራኄና ደጉን አርአያቸውን በተሾምሁባቸው ሰዎች ላይ እያስረዳሁ በቅን አገዛዝ ልገዛቸው ይገባኛል ብሎ ከቀን እስከ ሌሊት ይጣጣራል። ከልብም የሆነ እርግጠኛ የአገር ፍቅር ያድርበታል ሕሊናውም ለአገሩ ውለታውን እንዲአቀልላት ያነቃቃዋል፥ ፈጽሞም የራሱን ጥቅም ብቻ ሽቶ ድሆችን እንዳይበድል ያስገነዝበዋል። ሌላውም ሀብታም የሆነ ሰው ከአገሬ ውሥጥ ያፈራሁትን ገንዘቤን እንደምን አድርጌ ለራሴ ጥቅም ብቻ እንዲሆነኝ አስባለሁ እያለ ከልቡም ላይ የገንዘብ ስስትን ፍቅር ማስወገድ ይሞክራል ። ቢዘገይ እንኳ በአገሩ ውሥጥ ለሚነሡት ትውልድ መታሰቢያውን ሊተውላቸው ማሰቡ ምንም ቢሆን ከሕሊናው አይሰወርም ።

እንደዚያው ሁሉ ክቡር ደጃዝማች ዓምደ ሚካኤል በላይኞቹ መስመሮች የተጻፉትን ቃላት ለመፈጸም ቊርጥ አሳብ ኑሮዋቸው ያን ከጥንት የቆየላቸውን ዋና ታማኝነታቸውን እንዲት ደቂቃ ስንኳ ሳያቋርጡ በተሾሙበት አገር ላይ ብዙ ውለታ አድርገዋል ፤ መጀመሬ ለአገር ሕዝብ ዋና እንቅፋት ሁነው በአፈርሳታ ምክንያት ገበሬውን ከእርሻው ፡ ነጋዴውን ከንግዱ ሌሎችንም በዚሁ ረገድ ያስተጓጉሉዋቸው የነበሩት ወንበዴዎችንና ሌቦቹን ከያሉበት ጕሬያቸው ውሥጥ አስለቅ

መው ክፋታቸው አለመጠን የበዛው ተቀጥተው እስከ ተመደበላቸው ዓመት ድረስ እወህኒ ቤት ገብተው በእግር ብረት እንዲታሠሩ ፤ ጥፋታቸውም እጅግ ያልበዛው ደግሞ በሚገባ ተቀጥተው ተመክረው ንስሓቸውን እንዲቀበሉ አድርገው የአገሩን ሕዝብ ከቀድሞ ጭንቅ ስጋት አሳርፈዋቸዋል። ስለዚህ ሁሉ አሁን በግዛታቸው ውሥጥ ወንበዴዎች ሌቦች ዱካቸው ጠፍቶ መልካም ገጋር ለሰደዱልን ንጉሣችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዑል ፈጣሪያችን ብዙ ዕድሜ አድሎአቸው በላያችን ያኑርልን እያሉ ባላገሮች ደስታቸውን በሔዱበት በታ ይገልጻሉ ። ሁለተኛ እግዚአብሔር አጥብቶ የሚወደውን እውነተኛ የሚሆን ቅን ፍርዳቸውን ሳያጓድሉ በመፍረዳቸው ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኝተዋቸዋል ። ከዚሁም ሁሉ በላይ ባልና ሚስት ተጣልተው ወደችሎታቸው ሲመጡ በፍርድ ብቻ አሸኘቸዋለሁ ሳይሉ እንደሽማግሌ በምክር ገሥፀዋቸው ሁለቱ እንዲታረቁ ያደርጋሉ ። ምናልባት በኑሮ ወገን ተበድለው እንደሆን ሁለቱ እንዲስማሙ ከጓዳቸው የገንዘብ እርዳታ ሰጥተው ወደቤታቸው በሰላም እንዲሔዱ ያሰናብቷቸዋል ። ተስፋ ላጡትና ለችግረኞች ሁሉ ችሮታቸውን አላጓደሉም ። ይልቁንም የአገሩ ሕዝብ እንደዚህ እንደአሁኑ ውጥናቸውማ ለልጆቻችን የእውቀት በር መክፈቻ ትምህርት ቤት በአገራችን ውሥጥ ሳያቆሙልን አይቀሩም ብለው በፅኑ ናፍቆት ተይዘዋል ። እንግዲህ እግዚአብሔር ለመልካም መሪያችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ረጅም ዕድሜ ከብዙ ጤና ጋር ሰጥቶ በላያችን ሺህ ዓመት ያንግሥልን ፤ ኢትዮጵያንም ከነፃነት በንዲራዋ ጋራ ለዘላለም ያኑራት ፤ እኛም ሁላችን በአፍ ብቻ ሳንወተውት በያለንበት እንበርታ በእውነተኛም አገልግሎት አገራችንን አገልግለን የድንቁርናን ቀምበር እንድናስጥላት መበርታት ያስፈልገናል ።

ጎመቹ ከረዩ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት
ቤት አስተማሪ ለቀምት (ወለጋ) ።

የጥያቄ መልስ

ይድረስ ለክቡር አቶ ሞገሴ ሰላም ለርስዎ ይሁን ።

፯ሺ፬፻፳፩ ኛ ዓለም በ፲፱፻፳፩ ዓ ም ሰኔ ፪ ቀን የተጻፈ ልዩ ልዩ ጥያቄ ያለበትን ክቡር ደብዳቤዎን ብርሃንና ሰላም የሚባል መልክተኛ ሰኔ ፫ ቀን በክብር አደረሰልን እጅግም ደስ አለን ።

ስለሆነ ግን ለዚሁ ጥያቄዎ አርመው አስተካክለው መልሱን የሚያቀርቡልዎ አቶ በቀለ ዘለቀ ነበሩ። ዳሩ ግን እሳቸውም እንደ ሰው ሁሉ ወረተኛ ሆኑና ያሁኑ ያዲሱ ሥልጣኔ የብረት ብዕር አልሰማማቸው ሲል ጊዜና እንደ ቀድም አያታቸው ለመሆን ሲመኙ መቃብር ብነው ሔዱ ከሔዱም ብዙ ቀን ሊሆናቸው ነው ። እኛም አቶ በቀለ ዘለቀን ተመልሰው እስቲመጡ ድረስ መልሱን ሳንሰጥ እንቆይ ብለን ስናስብ አመይመጽአን እንደመጠበቅ ያህል ሆነብንና ከብዙ በጥቂቱ እንጽፍልዎ ዘንድ ሕሊናችንን አሳሰበን ይህንኑም በተከታዩ መስመር ጽፈንልዎታል ።

፩ኛ ፤ ትምህርት በራሱ ምንድር ነው? ስለ ተባለው ጥያቄ ትምህርት ጥቅሙ የጋራ ሲሆን የድንቁርናንና የዕውርነትን ዓይን የሚከፍት የጠመመውን አቅንቶ የረቀቀውን አጕልቶ በኑሮህ ውሥጥ ያለውን ጉደሎነት ሁሉ ገልጦ የሚያሳይ የእውቀት መነጥር የሀብት ክብረት ነው ።

፪ኛ ፤ የትምህርት ዓይነታው ፍሬ የቱ ነው? ስለ ተባለው ጥያቄ ። የትምህርት ዓይነተኛው ፍሬ ወንድማማችነት ነው ። ይኸውም ሰዎች ሊያደርጉላችሁ እንደምትወዱ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው በሚል ቃል ይፈጸማል ።

፫ኛ ፤ ሰው መማሩ ለምንድር ነው? ለማን ሲል ነው? ትምህርት አነጣጥሮ የሚነግረን ነገሮች እነማን ናቸው? አእምሮ ተኩሮ የሚያየው የትምህርት ዋና ይላማው ምንድር ነው? ስለ ተባለው ጥያቄ ሰው ተምሮ ካወቀ በኋላ አነጣጥሮ ትኩር ብሎ ተሩቅ የሚመለከተው ዋና ይላማው በመጨረሻ የሚያገኘው የድካሙ ዋጋ ነው ።

፬ኛ ፤ ሰው በመማሩ በማወቁ ምን ሁኖ እንዲታይ ነው? ስለ ተባለው ጥያቄ ። ሰው ተምሮ በማወቁ በሥጋዊም ይሁን በመንፈሳዊ ላገሩና ለመንግሥቱ መልካም ምሳሌ ሁኖ እንዲታይ ነው ።

፭ኛ፤እውነት ስለእውነትነቷ መፈለግ መታወቅ ይገባታልን ወይስ ለሰው ጥቅም በመሆንዋ ብቻ ሰው ይወቃት ? ወይስ ይፈልጋት? ስለ ተባለው ጥያቄ ። እውነት ስለ እውነትነቷ መፈለግ መታወቅ ሲኖራት ተፈላጊ ነች እንጂ ፈላጊ አልነበረችም ዳሩ ግን የእውነት ወዳጆች መስለን እውነትን ተጠግተን እውነትን የምናጠፋ ሰዎች አያሌ ስለሆንን እውነት ስለ እውነትነቷ መፈለግ ልታስታውቅ አልተቻላትም ። ስለምን? ባለ እንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚል ቃል ጐድሎብታልና ።

፮ኛ፤ እውነት ምንድርነው እውነት በራሱ አለ ወይ ወይስ ሰው ሠራሽ ነውን ስለ ተባለው ጥያቄ እውነት ማለት ከቅንነት ምንጭ የሚፈልቅ አንድ ጥሩ ፈሳሽ ነበረ ። ነገር ግን እውነት ራሱ በየሰው ልብ ደጅ አፍ ኳ ኳ አድርጎ የሚከፍትለት ሲያጣ ጊዜ እዬ ምን ጊዜም አይከፈትልኝ በማለት ተስፋ ቈረጠና እውነት እውነትም ሰው ሠራሽ ሁኖ ቀረ ።

፯ኛ፤ ሰው ለሥራ ይሻልን ወይስ ሥራ ለሰው ይፈለጋል ስለ ተባለው ጥያቄ ሥራና ሠራተኛ አለ ጊዜው ቢፈላለጉ ምን ጊዜም አይገናኙ ስለምን የሥራ ጊዜ አልደረሰምና ሲላቀሱ ይኖራሉ ። አሁን ለምሳሌ አንድ ትጉህ ገበሬ አለ ። ይህነኑ ትጉህ ገበሬ ሥራ ከመውደዱ የተነሣ አለ ቀኑ ዘርቶ አለ ጊዜውም አጭዶ ከምሮ አለ ጊዜው ወቅቶ አምርቶ ልበልጥግ ቢል የማይሆንለት ሆነ ። እንደምን? አለ ጊዜው ሠርቷልና ። ስለዚህ በሐምሌ ሊዘራ፤በኅዳር ሊያጭድ፤ በታኅሣሥ ሊአመርት ግድ ይሆንበታል ። ሥራና ሠራተኛ አለ ጊዜው ቢፈላለጉ ምን ጊዜም አይገናኙም ያልንበት ስለዚህ ነው ። አሁን ግን ዓይናችን እንደሚያየውና ጆሮዋችን እንደሚሰማው ሠራተኛ ሥራን ይፈልጋል እንጂ ሥራ ሠራተኛኙ ኍ ይፈልግም ።

፰ኛ? ከሀብት፡ከኃይል፡ከዋርነት፡ ከውነት የሚያምር ነገር ከሁሉ ምንድር ነው?ከነዚሁስ ማናቸው ያምራል? ቁንጅ ውብ የሚአምር የሚያሰኝ ከነዚህ ውሥጥ ለአአምሮ የሚበልጥበት የቱ ነው? የሚመረጥበትስ ምክንያት ግድ የሚለው ምንድር ነው? ስለ ተባለው ጥያቄ። ከነዚሁ ሁሉ የሚበልጠው ጉድፍ የሌለበት ጥሩ ሕሊና ነው በዚሁ በቅን ሕሊናም ከሞት በኋላ አብሮ የማይቀበረው ነዋሪ የሚባል የዘለዓለም ፫ም ይገበይ በታል። ዘደቤውም እውነት ይባላል ። ሀብትና ክብረት በጊዜው ይጠፋሉ ። ደግ ስም ግን ትል የማይበላው ሌባ የማሰርቀው ነዋሪ ገንዘብ ነው ። ከሁሉ ይልቅ ቅን ሕሊና ደበልጣል ያል ንበት ስለዚህ ነው ።

፱ኛ፡ ሥራ ከትምህርት ጋራ ኅብረት እንዲኖረው ግድ ደላልን ወይስ ትምህርት ከሥራ ጋር አንድ መሆን ይገባዋል። ስለ ተባለው ጥያቄ ሥራና ትምህርት አንድ ላይ ሲገናኙ ቡናና ወተት አንድ ላይ አድርጎ እንደመጠጣት ያህል ነው ። ስለዚህ ሥራና ትምህርት ኅብረት ሊኖራቸው በግድ የሚያስፈልግ ሆነ ስለምን የሥራ ሁሉ መሠረት ትምህርት ነውና ።

፲ኛ ፤ ደምብ በሁሉ ላይ ሥልጣኑን አጥምዶ ይይዛል ወይስ ሕግ ነውን ስለ ሁሉ የሚገኝ ማንኛው ነው ሥልጣኑ ወሰን የሌለው? ስለ ተባለው ጥያቄ። ደምብ በተቀጠው ዓቅሙ መጠን ለጊዜው ይሠራል እንጂ ለሥልጣኑ ወሰን የሌለውስ ሕግ ነው ።

፲፩ኛ፤ሰው ሕግን ደጠብቃልን ወይስ ሕግ ሰውን የሚጠብቅ ነው? ስለ ተባለው ጥያቄ። ሰው ሕግን ይጠብቃል እንጂ ሕግ ሰውን አይጠብቅም። ሕግም ማለት ወርዱና ቁመቱ ትክክል ሁኖ የተሠራ እስከ መቼውም ድረስ የማይፈርስ አንድ ቀዋሚ ነገር ነው። ሕግ ማለት የኑሮ ሁሉ መወሰኛ ነው። ሕ ማለት ደኃና ሀብታም የሚተካከሉበት እውነተኛ ሚዛን ነው ሕግ ማለት የማይፈርስ ድምበር ነው። ሕግ ማለት በጌታና በሎሌ በመምህርና በተማሪ በባልና በሚስት በነዚህ ሁሉ መካከል የሚኖር የኑሮ መወሰኛ ሐውልት ነው። ሕግ ከሌለ ሰላማዊ ኑሮም የለም ስለዚህ ሰው ሕግን ይጠብቃል እንጂ ሕግ ሰውን አይጠብቅም ።

፲፪ኛ፤ ሰው ጊዜን ይወስነዋልን ወይስ ጊዜ ሰውን ይወስነዋል።ሰው በጊዜ ውሥጥ ይገኛልን ወይስ ጊዜ በሰው ውሥጥ ይገኛል? ስለ ተባለው ጥያቄ። ከዚህ በላይ በ፯ኛው ክፍል ውሥጥ እንደተናገርነው ጊዜ ሰውን ይወስነዋል እንጂ ሰው ጊዜን ለመወሰን አይችልም። ሰው ሁሉ ጊዜን ለመወሰን የሚቻለውስ ኑሮ ሐሳቡን ሳይፈጽም የሚቀር አንድ ስንኳ ባልተገኘም ነበር። ስለዚህ ጊዜ ሰውን ይወስነዋል እንጂ ሰው ጊዜን ለመወሰን አይቻለውም ።

ከቡሩን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ ወንድማችን አቶ ሞገሴ ከ፲፪ላይ ከፍለው የተገባ ጥያቄ ማድረጋቸው የሐሳባችን ተከፋይ እንዲሆኑ በማለት ነውና ለነገ ሳትሉ ከኛ ይልቅ አር ማችሁ አስተካክላችሁ አስፍታችሁ እንድትጽፉላቸው ብርሃንና ሰላም ያሳስበኛል ። ተማኙ ረምሃ ።

የሰው ወርቅ አያደምቅ።

ብርሃንና ሰላም በልጅነቱ ደፋር የነበረ ሲያድግ ሲገለምስ ዓይነ አፋር ሆነ የኢትዮጵያ ልማት ለኢትዮጵያዊ ሁሉ የኢትዮጵያ ጉዳት ለኢትዮጵያዊ ሁሉ ነውና ዕውቀት ያላቸው በሰፊ ዕውቀታቸው ዕውቀትም ያነሳቸው እንደየዕውቀታቸው መጠን ዘሆንንም ጥንቸልም ሆድ ነውና ሁሉም እኩል ወንዝ ወረዱ እንደሚባለው የአገር ፍቅር ትልቅ፡ትንሽ፡ አዋቂ አለአዋቂ አያሰኝምና እንደመጠናቸው የሚጽፉ ብዙዎች ነበሩና በብርሃንና ሰላም አስታዋሽነት ከብዙው በጥቂቱ ጥቅም ያላቸው ነገሮች ተፈጽመውበታል።አሁን ሳይጨልም ገና ማለዳ በብርሃን ግጭት ስለበዛ እንዲህ ብዬ ብጽፍ እንዲህ ቢሉኝሳ በማለት መልከከሙ ለአገር ጥቅም የሚሆነው ሐሳብ ሁሉ ታምቆ ስለ ቀረ ዓይነ አፋር አልሁት። አላይ እንደተባለው ዕውቀት ያላቸው በሰፊው ዕውቀታቸው የምጽፈውን ይነቅፉብኛል በማለት ሐሳቤን አላቋርጥምና ቀጥሎ ያለውን እጽፋለሁ ።

የውጭ አገር ንግድ ወደሷ ከመዝለቁ በፊት ኢትዮጵያ በልብስ አረገድ ከውጭ ምንም የማያስፈልጋት ራሷን የቻለች ነበረች ይኸውም እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ ስለነበር የዕድሜ ባለፅድሎች ከዚያን ጊዜ እንሥተው እስከ አሁን የቆዩ ሽማግሎች አንድ አንድ ነበሩና የተረኩልን ቃል ከታሪኩ መጽሐፍ ጋራ የተባበረ ብዙ ነገር ይገኛልና ይህነንም ከማመን አያዝንፈንም አስቀድሞ ኑሮአችን ሴቶቻችን ለነሳቸው ልብስ የዘወትርና የክት ለኛም እንደዚሁ የዘወትርና የክት ሰናፊላችንን (ሱሪ) መቀነታችንን ሳይቀር ፈትለው ያለብሱን ነበር።በገራችን ስንፈት ሲገባ ለመሥራት የማያቅተንን ነገር ተባሕር መርፌ እያመጣን እንገዛ ጀመር።ቆይቶም ትሊ የሚባል ጨርቅ ወጣ በኋላም አቡጀዲ ወጣ ሌላውም ጨርቅ ከመጣ ወዲህ ብርቅና ድንቅ ሆኖብን ለጌጥ ስንል እንለብሰው ነበር እንጂ እንደአሁኑ በአገራችን የተሠራ ልብስ በመታጣቱ አልነበረም እያሉ የተረኩልንን እርግጡን ለመረዳት ብንፈልግ የውጭ አገር የንግድ እቃ ወደኢትዮጵያ መዝለቅ የጀመረበትን ዘመን አስበን ከዚያ በፊት የኢትዮጵያ አኑዋኑዋር ችግር የሌለበት እንደነበር ታሪክ ያስረዳናልና በልብስ እርግጥ ራሱዋን የቻለች ከውጭ የማትፈልግ ኑራለች ። ለዚሁም ማስረጃ ምስክር የምትሆን መንዝ ቀርታለችና የቀድሞ ሥራዋን ሳታቋርጥ ራሷን ችላ ለሌላ የምትተርፍ መንዝ ብቻ ናት መንዝ ከሸዋ አውራጃ አገሮች አንደኛይቱ በግምት ፲ሺ የሚያህል ነዋሪ ሕዝብ ያለበት እሱዋው ባረባችው በግ ጠጉሩን ፈትላ ለመላ ኢትዮጵያውያን ታለብሳለች ከመንዝ የተሠራ የበግ ጠጉር ጨርቅ (ዝተት) የብርድ ልብስ፡የኃዘን ልብስ፡የጌጥ ልብስ ነው መናኛውም ድንኳን የሚሆን ነው።እንደዚህ ያለ በአገራችን የሚሠራ ጥሩ ጨርቅ (ዝተት) እያለ ሱፍ የሌት ልብስ እያልን ከውጭ አገር ለመጣው የሌት ልብስ አራት አምስት እጥፍ ዋጋ እናወጣለን ። የዝተት ጨርቅ ከውጭ አገር የሚመጣቢ ሆን ለሙቀቱም ለጌጡም ሲባል ለሌላው ጨርቅ እንደሚወጣው ሁሉ ስንት እጥፍ ገንዘብ በወጣ ነበር።እንዴትስ ብርቅ በሆነብን ነበር ለኛ የሌት ልብስ በ፳ በ፴ ብር የሚሸጡልን የ

ውጭ አገር ነጋዴዎች የዝተት ጨርቅ በሙቀትም በጥንካሬም ከሱፍ የሌት ልብስ መብለጡን ዋጋው በጣም ማነሱን ተመልክተው በምስት በስድስት ብር እየገዙ የሌት ልብስ ያደርጉታል ። ለብርድ ጊዜም ልብስ ዝተቱን ኰበርት እያሰፉ መልበስ ጀምረዋል ። ይህን ዝተት የሚሠሩ መንዞች በልብስ እራሳቸውን የቻሉ ናቸው ። ምነው የመንዝ ባላገር አቡጀዲ እየገዛ ይለብስ የለምን የሚለኝ ቢኖር የመንዝ ባላገር ለሱ ሰናፊል ለሚስቱ ቀሚስና ጠሊት አቡጀዲድ የሚገዛው ሚስቱ በፈተለችው እሱ በረገጠው በዝተቱ ሺያጭ ብር ነው እንጂ በእህል ሽማች ብር አይደለምና ስለዚህ መንዞች በልብስ ራሳቸውን የቻሉ ናቸው ለማለት ይቻላል ። የመንዝ ባላገር በመሬቱ የሚገብረው ግብር ዝተት ብቻ ቢሆን ከኛ ተርፎ ለውጭ አገር ንግድ የሚተርፍ ነበር የሥልጣኔን ጥቅም ወሬውን ያልሰሙ የመንዝ ሴቶች በትጋታቸው ራሳቸውን ችለው ሲኖሩ የሥልጣኔን ጥቅም ወሬውን የሰሙ ያዩም የጀመሩም እየገዙ መልበስ ይደንቃል መድነቅም ብቻ አይደል ያስቆጫል ሥልጣኔ ሥራን እያበላለጡ አዲስ አዲስ ዓይነት ለመሥራት ነው እንጂ ቀድሞ የሚያውቁትን ሥራ ትቶ ሌላው የሠራውን ለመግዛት የመምረጫ እውቀት ማግኘት አይደለምና የአገራችንሙያ እንዲስፋፉ ወጭ ገንዘባችን እንዳይበዛ ድሩም ማጉም የኛ ሆኖ ጥበብ ጥበቡን ብቻ እንግዛ ። ይህን ለመጻፍ ያሰሰበኝ አቶ መኰንን ደስታ እንግዛው እንጂ እንሥራው የሚል መንፈስ ታጣ ያለውን ተመልክቼ እውነትም ነገሩ ስለገረመኝ ነው እንጂ ከቡራት ወይዛዝር ገረዶቻቸውን እንዲያስፈትሉ ሌሎችም ሴቶች እንዲፈትሉ ለመምከር አልደፍርም ምክር ብጽፍም ድፍረት አይሆንብኝም ነገር ግን ሲያውቅ የተኛ ቢጠሩት አይሰማምና ብጽፍም ከንቱ ነው።

ማህሉ ጽጌ ።

ቋንቋ ከሥራ መልክም አዝመራ።

ብዙ ቋንቋ ማወቅ፥ ከጐረቤት ለመቃረቢያና ከተቃረቡ በኋላ ብዙ የተሠወረ ነገር ለመጠያየቂያ፤በፍቅርም ለመገናኛና ለመሳነቢያ ዋና ጥቅም ነው። ይልቁንም ሙሴ እገሌ ምን እሱ ይሆን እያሉ ከስማ በለው ለመዳኛ ዓይነተኛ ጥቅም መሆኑ እርግጥ ነው። ከዚህም የበለጠ በልዩ ቋንቋ የተጻፈውን የጥበበኞችን ታሪክ አንብቦ እነሱን በመምሰልና ሥራቸውን በሥራ በመከተል ብዙ የዕውቀት ማስረጃና ምሳሌ ያስገኛል።ነገር ግን እጅ ቢሠራ ነው እንጂ እጅ ካልሠራ በቃል ብቻ የሚሆን ነገር ሁሉ ዝርው ስለሆነ በሥራ ሳይሰበሰብ ተበትኖ ይቀራልና በቋንቋ ብቻ ብዙ ነገር ከመናገር በእጅ ጥቂት ሥራ ሠርቶ ማሳየት የሀገርን ጥቅም ይወልዳል። ለአባታችን ለአዳም ስንኳ ጌታ ብላዕ በሐፈ ገጽከ ብሎ የሥራን ጥቅምነት ነገረው እንጂ ብላዕ በብዝኀ ልሳንከ አላለውም። በሐፈ ገጽከም ማለት ማረስ መቈፈር ተክል መትከል እህል ማብቀል ብቻ አይደለም። በዚሀ አንጻር በልብ ታስቦ፥ በቃል ተነቦ፥ በእጅ ተጨብጦ፥ በእግር ተረግጦ፥ ተቀጥቅጦ ተጨፍልቆ፥ ተጠርቦ ተሰንጥቆ፥ ተዘውሮ ተሽከርክሮ፥ ይህንም በመሰለው ዓይነት ሁሉ የሚሠራውን የብልሃት ሥራ ሠርተህ፥ ወዝህን አፍስሰህ፥ ብላ ማለቱ ነው እንጂ ይህም ብላዕ በሐፈ ገጽከ የተባለ ዕፁ አዋጅ በአዳምና በልጆቹ ዘመን ጥቂት ጥቂት እያለ ሲሠራ ቈይቶ ወደ ፍጹም የዕውቀት ሥራ ደረሰ። ዛሬም የሠለጠኑት አገሮች የከበሩበት ይህኑ የማይፈርስና የማይጣስ አዋጅ አዕንተው በልባቸው ቢመረምሩ በእጃቸው ቢሠሩ ነው እንጂ በቃላቸው ብቻ ብዙ ቋንቋ ቢናገሩ አይደለም እንደበትስ ነገር አብዝቶ ሲናገር ቢውል ከመላሸት በቀር አንድ መኪና ስንኳ ለማቆም አይችልም። ነገር ግን ቋንቋ ከጐረቤት ጋራ አቃርቦ የተበተነውን ልሳን ሰብስቦ ለብልህ ካሳየ በኋላ ሥራና ቋንቋ በብልህ ዘንድ ተባብረው ሲገኙ ሥልጣኔና ሀብት መገኛቸው ያን ጊዜ ነው ።

በሀገሩም ለሚሰበከው ትምህርት መሠረቱ ያገር ቋንቋ ነው እንጂ የቤትን ነቅፎ የውጭን አቅፎ ለመኖር አይደለም። የራስንስ ቋንቋ ቸል ብሎ የሰውን ቋንቋ ብቻ ማጠንከር ያንን ከናቱ ጡት ጀምሮ ያደገበትን ቋንቋ ረስቶ እንደ ባዕድ ሁኖ ኋላ በስማ በለው ለመነጋገር ይመስላል። ስለምን ቢሉ ከቶ የራሱን መላስ ቈርጦ ጥሎ በሌላው መላስ መነጋገር የሚችል የለምና። ለሀገራችንም ቋንቋ መሠረቱ ግዕዝ ነውና የፊደልን መልክና ድምጽ ከወቁ በኋላ የግዕዝን አመል ማወቅ ያስፈልጋል ምነዋ ለዚህማ መጻፍ ቅዱስ በማርኛ ተጽፎልኝ የለምን ግዕዝ ለምን ያስፈልገኛል ትለኝ እንደሆነ ስሙን አያውቅ አገሩን አይጠይቅ እንዲሉ የመጣበትን ሳታውቅ አማርኛውን አነባለሁ ብትል ዘይቤው እየተቃወሰ ምሥጢሩ እየተፋለሰ ለልቡናህ ጨለማ ለአንደበትህ ዕንቅፋት እየሆነ አላላውስ ይልሀል። ሰዋስው ያልተሠራለት አንደበት የመጽሐፍ ቅዱስን ምሥጢር መርምሮ ከድንቍርና ለመሸጋገር አይችልምና። የሆነ ሁኖ እኔ የተነሣሁበት ምክንያት ቋንቋን ከሥራ ጋራ የሚአገናኝ ምክር ለመስጠትና ያገርን አማርኛ ከግዕዙ ጋራ በመጀመሪያ አድርጎ የቀሩትን ከውጭ አገር የመጡትን ቋንቋዎች ተከታይ ለማድረግ የሚገባ መስሎ ስለታየኝ ነው እንጂ ቋንቋን ለመንቀፍ አይደለም። ቋንቋስ እንዳይነቀፍ ከአዋቂዎች ጋራ እያገናኘ ብዙ ጥቅም ሲአስገኝ እናየዋለን። ነገር ግን ከሥራ ከተለየ ጥቅምነቱ አጭር ነው። ከሐልዮ ነቢብ፥ ከነቢብ ግቢር እንዲበልጥ ማንም አይዘነጋውምና።

ደግሞም ገንዘብ ካለኝ እጄ ባይሠራ ምን ቸገረኝ የፈለግሁትን በገንዘቤ ገዝቼ አገኘዋለሁ ለማለት ይገባም አይመስለኝ ከቡሆቃዋ እርሾ ከምድጃዋ ምጣድ ከጋንዋ ጥንስስ ከአገልግልዋ ጥዋና እንዝርት አጥፍታ የገበያ እንጀራና ወጥ የገበያ ልብስና መጠጥ በመግዛት የምትኖር ሴት ከሰነፎች ትቈጠራለችን ወይስ ከልባሞች። ይህን ነገር አስተዋይ ልቡና ቢአስተውለው ከመግዛት መሥራት እንዲበልጥ ሳይረዳው አይቀርም። እጅ ሥራ ለመሥራት እንጂ ለከንቱ አልተፈጠረምና። በቃል ብቻ ሠርቶ መፈጸም የሚቻለው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው ከእግዚአብሔርም በታች ለንጉሥ ነው።በቃሉ አዝዞ ሁሉን ለማስደረግ ሥልጣን አለውና ለሁሉም ነገር መታመን ያስፈልጋል።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ።

ስለ ወይዘሮ ሙሉነሽ ሀብተ ሥላሴ ዕረፍት ።

ወይዘሮ ሙሉነሽ ሀብተ ሥላሴ እናታቸው ወይዘሮ አቻም የለሽ ማህለ ሥላሴ ነበሩ ። አጼ ምኒልክም ከዝምድናቸው ይልቅ እጅግ ያምኑአቸው ነበርና ሙዋቹን ልጃቸውን እንዲአሳድጉላቸው ሰጥተዋቸው ነበር ። ልጁንም ሎዛ በምትባል በአንኮበር አቅራቢያ አሳድገው ለፈረስ ሲደርስ አምጥተው ሰጥተው ታላቅ ምስጋና ተቀብለው ነበር ። ብዙ ዕድሜ አግኝተው አለችግር ሲኖሩ መቸም በዚህ ዓለም መሰንበት እንጂ መቅረት አይጠረጠርምና በ፲፱፻፳፬ ዓ ም በሐምሌ ፳፯ ቀን ዐረፉ ። ዕድሜአቸውም ፹፰ ዓመት ነው ምንም ጊዜው ቢተላለፍ የታላቅ ሰው መታሰቢያ እንዳይቀር ብለን አትመነዋል ። ደግሞ ሰው ምንም ዕድሜ ጠግቦ ቢሞት ለዘመዱና ለወዳጁ ማሰዘኑ አይቀርምና የልጆቻቸውን የልቅሶ ዜማ ግጥም ቀጥለን ጽፈንላችኋል ።

ዙረን እንዳናየው አገራችንን ።
እከተማ ቀረሽ ቤት እናታችን። እኛ በከተማ ተሰደን ስንኖር። መሬአችን ጠፋች ወይ እንዳንገባ ሀገር ። እንዳምሌ እንደናሴ ባመት አትመለስ ። ተለይተን ቀረን ዋ እስከ ወዲያው ድረስ። አንች አልነበርሽምወይ የሰው ሁሉ አገሩ ። ታጥሪው ነበረ ሁሉን በየግብሩ። ልቅሶን ለሸዋን ላንች አትልቀቁላት ፈርሶብና ልና የሁላችን ቤት። የማህለ ሥላሴ ያቻምየለሽ ልጅ ። የሸዋ ባላልጋ እሥር ባለጡጅ ። እመቤትነትሽ መሠረት ነው እንጅ። ሽግግሌው አልቆ ልጁ እየዘገየ። የዝምድና ነገር ቀረ ተለያየ። በግራና በቀኝ ተከበሽ ባባት። የሚአድንሽ ጠፋ ከግባ መሬት።

ማስታወቂያ ።

በመስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም በ፫፻፳፱ ገጽ ማጀስ- ቲክ ሆቴል አጠገብ ከሙሴ ሃርዲ ፊት ለፊት መሐመድ አሊ ከሠራው አዲስ ፎቅ በታች ቤትና ቦታ ይሸጣል ብሎ ስለአስታወቀው ስለ አለበት ብዙህ ዕዳ ከርታውን በኛ እጅ አስይዞልና ስለዚህ ይኸነን በታና ቤት የኛን ገንዘብ ጨርሶ ሳይከፍል ሊያስይዝና ሊሸጥ አለመቻሉን እናስታውቃለን ።

መሐመድ አሊ ኩባንያ።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሚናክ ፓርሴጊያን ዘንድ ይገኛል ። ደህንኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተሩብ ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

ፋርማሲ ሣንትራል ተናግሮት የነበረውን በገዛ ዓይንዎ አይተው ስለተረዱት በጣም ደስ አለኝ ፤ መጥተው ስለተረዱ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ወደፊትም እየመጡ እንዲሁ እንዲረዱልኝ እመኛለሁ ።

እንደ ተባባልነው ስለ መልክዎ ጥንቃቄ አሁን ጥቂት እመክርዎታለሁ ።

የመልክን ቆዳ ስለሚአበላሹ በሺታዎች የተቀመሙትን ሳሙናዎች ሲወስዱ መልከም ሆኖ በረቂቅ ሺታ የተሰናዳውን የውበት ሳሙና ይውሰዱ ። ፊትዎን አልፎ አልፎ ጭረት ስለሚአደርገው በሺታ ኤፊሊን የሚባለውን መድኃኒታችንን እንዲአደርጉ አጥብቀን እንመክርዎታለን ። በጥቂት ቀን ደህና እንዲሆኑ ይኸነን መድኃኒት ማድረግ ነው። እስከሁን ድረስ እሱን የሚተካ ሌላ መድኃኒት አልተገኘም ።

በፊትዎ ላይ ስለሚአደርጉት የሽቶ ዱቄት ወዝ ለሌለው መልክ«ኮልድ ክሬም» የምንለው መድኃኒታችን መልከም ነው፤ወዝ ላለው ፊት ግን«ሌቢርዠናል» የሚባለው መድኃኒታችን ነው የሚሻለው ስል እመክርዎታለሁ ።

ደግሞ በያይነቱ የተሰናዳውን የሩዝ ዱቄት ሺቶ «የኮቲም»ሆነ«የፒቬርትም»ሆነ ሌላም በያይነቱ ለማየትና ለመምረጥ ይችላሉ፤ እንዲሁም ለከንፈር ቀለም የሚሆን እርሳስ በያይነቱ አለኝ ዘወትርም ስለ እሚታሹበት ኦዲኮሎኝ ይልቁንም ከድካም በረፉ ጊዜ የሚታሹበትን ከኔ ዘንድ እንዲወስዱ እምናለሁ በዚሁ በፋርማሲአችን ውስጥ ለፊትና ለገላ ማሸ የላስቲክም ሆነ የውነተኛውም ኤፓንገር ሆነ አለን ብለን እስታውቀንዎታልና ሁለተኛ መናገር ያስፈልግ አይመስለኝም ።

ደግሞም በያይነቱ በእውቀት ጥበብ ስለሚመረመር ነገርና ስለ መንገድ መድኃኒት ማሰናዳት በልዩ ማወቄን እንዳይረሱ አስታውሳለሁ እገልጋይዎ ኤም ማትጣኪስ ።

ኦቦማልቲን
ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

ኦቦማልቲን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው። ኦቦማልቲን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል ኦቦማልቲን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፥ ቤርን ናቸው። በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው።

ኦቦማልቲን አዲስ አበባ ባሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ማጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት

ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
የቅ ዮ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፭ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲ ብር
፫ቱ መጻሕፍተ መነኰሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪ ብር
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪ ብር
ደስታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፱ ብር
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው —	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
የዓለም ጂዮግራፊ ከነካርታው	፯ ብር
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፯ ብር
ድርሳነ ሚካኤል	፯ ብር
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኀሁ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪ ብር ፶መ
የእርሻ ትምህርት	፩ ብር ፶መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ እጅግ ያማረ	፪ ብር
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
የቍጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩ ብር
ያማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የነፃ ደንብ ከነተጨማሪው	፩ ብር ፶መ
የብድር ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ አዲስ	፩ ብር ፶መ
የገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
ዮሐንስ ቡንያን	፩ ብር
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፭ ብር
የ፪ኛ	፳ ብር
የ፫ኛ	፲፭ ብር
የ፬ኛ	፲ ብር
የ፭ ኛ	፯ ብር
የ፮ኛ	፯ ብር
የ፯ኛ	፯ ብር
፳፬ ካርት ፖስታል	፩ ብር
የረኮማንዴ ደብተር	፫ ብር
ሕገ መንግሥት	፭ ብር
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፶ መሐ
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፶ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፶ መሐ
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተስማማ	፶ መሐ
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፶ መሐ
ያማርኛ ምሳሌ	፶ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
የፍቅር መላክት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የምሕረት አዋጅ	፬ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የንቍጣጣሽ ግጥም	፪ መሐ
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፪ መሐ
፩ ጋዜጣ	፪ መሐ
አርስጣላብ	፬ መሐ
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፬ መሐ
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፬ መሐ
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፩ መሐ
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፩ መሐ
ካላንድሬ	፶ መሐ
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪ	፩ መሐ
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፶ መሐ
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፬ መሐ

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት እጥፍ ። ነጠላ በያይነቱ ። እርሳስ መንኰልና ብረት ብርዕ ቀለም በያይነቱ።የካርት ቢዚት እንቦልብና ካርት ቢዚት በያይነቱ ። እንቦልብ ትልቅና ትንሽ በያይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ ፤ የደረት የጕበት ፤ የኩላሊት ፤ የጅማት ፤ የጨብጥ የቂጥኝና ፤ የቋቁቻ ፤ የሚያዋልድ ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪክ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አስናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዶች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኪንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

እስከ መስቀል ድረስ አንድ የቤት ሰብ መኪና የገዛ ሰው ደህና ሽልማት ያገኛል ።

በርቱ ይኸ እድል እያምልጣችሁ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ካገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪል ነው።



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዛር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ቁ ፲ ፳፳ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
8me ANNE. № 43

ሐሙስ ጥቅምት ፲ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 20 Octobre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታናሽ እምባጓሮ በደብረ ማርቆስ የጐጃም ከተማ ።

አስቀድመን እንዳስታወቅናችሁ የጐጃምና የዳሞት የአገው ምድርና የሜጫ የዘጌና የአቸፈር ገገር ራስ ኃይሉ በንጉሠ ነገሥቱና በመሰፍንቱ፥ በመኳንንቱና በሙሉ በኢትዮጵያ ሕዝብና ሠራዊት ዘንድ እጅግ የከበሩ ነበሩ ። ነገር ግን በመልክም ፈንታ ክፋትን ፥ ከመወደድ መጠላትን ፥ ከመከበር ውርደትን ፥ መርጠው የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ ለማፋጀት ቢነሡ እጃቸው ተይዞ የሞት ፍርድ ከተፈረደባቸው በኋላ ጳጳሳትና ሊቃውንት አማልደው መቸም የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምሕረት ብዙ ነውና የሞት ፍርድ የተፈረደባቸውን ምረው በእሥራት አስቀምጠዋቸዋል ። ራስ ኃይሉም የገንዘብ ፍቅር ይፀናባቸው ነበርና በማይገባ ብዙ ገንዘብ ሰብስበው ያስቀመጡትን ተወረስን ተቀማን ለሚለው ድኃ ገንዘቡ ተመልሶለት የተረፈው ገንዘብ ለመንገድና ለድልድይ መሥሯ እንዲሆን ተዘጋጅቶ ነበረ ። መቸም የዓመፃ ገንዘብ ለመልክም መታሰቢያ አይሆንምና በጐጃም ከተማ በደብረ ማርቆስ የተቀመጠውን ገንዘብ በአንድ ወገን ለጥፋት ይረዳቸው የነበረው ፊታውራሪ አድማሱ የሚባለው ልጃቸው ለመዝረፍ አስበ ወምበዴዎቹን ሰብስቦ በመስከረም ፳ ቀን አደጋ ጥሎ በክንቲባ ማተቤና ከዚህ በሔዱት በመንግሥት ሹማምት አስተዞሰባቸው በመከከላቸው እምባጓሮ ተነሥቶ ነበረ ። ከዚያም በኋላ ሽማግሎች ገላግለው ከመንግሥት የሔዱትን ሰዎች አስወጥተው በዚያ ዓመፃ ገንዘብ ጐጃሞች እርስ በርሳቸው ተጐዳዱ ይባላል ። ገንዘቡ ከአለቀ በኋላ ፊታውራሪ አድማሱን አብሮት የነበረው ሕዝብ ይከዳው ጀመረ ። ከዚህ በኋላ እጄን እሰጣለሁና ይማሩኝ ብሎ ወደጃንሆይ ሽማግሎች ላከ ። ጃንሆይም መቸም የሕዝቡን ጥፋት አይወዱምና የእርቁን ነገር የሚፈጽሙ ሽማግሎች ክቡር ደጃዝማች ወዳጆንና ክቡር ሊቄ ገብረ ክርስቶስን ልከው የእርቁንነገር አከናወኑት። እሱም ከክቡር ደጃዝማች ወዳጆ ጋራ በጥቅምት ፫ ቀን በአይሮፕላን ወደ አዲስ አበባገባ።በማግሥቱም ዓርብ የጃንሆይ ችሎት ነበረና በቍራኛና በዘበኛ ሁኖ ታላቅ ደንጊያ ተሸክሞ አጥፍቻለሁና ይማሩኝ ብሎ በጃንሆይ ዙፋን ፊት ለፊት በአደባባዩ ወደቀ። ጃንሆይም ሌላውን ቅጣት ምረውት እንዲታሠር ቈይቷል።

ቸሩ አምላክ ዘንድሮ ጐጃምን ኃይሉን አሳይቶ ማራት ወደ ጐጃም የታዘዘው ጦር ልክ አልነበረውምና እንኳን ሰው በጐጃም ቅጠል አይተርፈውም ነበር። ጉዳቱም ለመላ ኢትዮጵያ ነበር እንጂ ለጐጃም ብቻ አልነበረም። አገረ ገገርው ክቡር ራስ እምሩም ጥቅምት ፰ ቀን ወደ ጐጃም ከተማ ወደ ደብረ ማርቆስ ገቡ ። ጦሩ ግን እርቅ ስለተደረገ እንዲመለስ ታዝዟል።ክፉ ካልኖረ መልክም አይገኝም። አደጋም ካልሆነ ሕዝብ አይጠነቀቅምና ይህ የፊታውራሪ አድማሱ መክዳት ለአባይ ድልድይ ሥራ የሚአተጋ ሳይሆን አይቀርም ። እሱንም ሰይጣን አታሎት ነው እንጂ የራሱ ሐሳብ እንዳልሆነ ሕዝብ ሁሉ ተረድቶታል።የሆነ ሁኖ ኃጢአቱን አውቆ ይቅርታ በመለመኑ በኃጢአት ላይ ኃጢአት በአለመጨመሩ ደስ አሰኝቶናልና እጅግ አንወቅሰውም። ልጅ መቸም ስም አስጠሪ ነውና የተረሳውን የራስ ኃይሉን ስም በማስጠራቱ ወገኖቻቸውን ቅር ሳያሰኝ አይቀርም። እንዲህም እርቅ ሲሆንና የሰው ደም በርከት ብሎ መፍሰሱ ሲቀር ያ ሰይጣን እንዴት ያዝን ይሆን ? ። የሆነ ሁኖ መቸም ቢሆን ራስ ኃይሉ ከጥፋት አልዘለሉምና ብንፈርድባቸውም ያው ነው እንጂ ይህን የመሰለ ልጃቸውን ወደ ከተማ አምጥተው በተማሪ ቤት ቢአሳድጉት እንዲህ ባልሆነም ነበር ። ዕውር ምነው ይደፍራል ቢለው የሰው ፊት ባያይ እንጂ ነው ብሎ መለሰለት ይባላል ። ሰው የሰውን አደባባይ ካላየ ቢሆንም ካልተማረ ዓቅሙን ያውቃል ወይም ለስሙ ይፈራል ተብሎ አይጠረጠርም ። እነዚህ በምግዚት የሚሾሙ የባላበት ልጆች የዘለዓለም ጥፋት እንዲአመጡ አይጠረጠርም ፡ ዕውቀቱና ሥራው ተገምቶ ካልተሾመ በትውልድ ታገኘው መመከቱ እንዴት ይቀራል?፥ ለዚህ ሁሉ በአለሥራዎች ያውቃሉ እኛም አላስችለን ስለአለ የዓቅማችንን እንለፈልፋለን ።

ሀብት የኃጢአት መሠወሪያ ነው።

ስለዚህ ማስረጃ አንድ ጸሐፊ ወዳጄ የነገረኝን ተረት ልንገርህ ግን ተረት ብልህ ተረት አይደለም እውነተኛ ነገር ነው ።

አንድ ሰው በኮንስታንቲኖፕል ከተማ ይኖር ነበር ። ሥራውም ወሮበላነትና ፈታልነት (አቃጣሪ)ነበረ ። በእንደዚህ

ያለው ሥራ የታወቀ ስለሆነ ስሙን ያገሩ ሰዎች ወሮበሌ ወይም ፈታሌ ይሉት ነበረ ። እሱም ሥራው ስለሆነ መጠሪያ ስሙ (የሥራ ስሙ) መሆኑን አውቆ ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት ይል ነበረ። እንደ ነውርም አልቆጠረውም ነበረ በኋላ ግን ሰው ጠላው አገር ናቀው የሚገድሉት ቢሆን ወደ አሜሪካ ኰብልሎ ሒዶ በአሜሪካ በዚያው አዋቂ በሆነበት ሥራው ባለ ብዙ ገንዘብ ሆነና በጣሙ በለጸገ መበልጸግና መክበርም በሰው አገር አይደምቅምና ሀብቱንና ብልጽግናውን ይዞ ወደ ተወለደበት አገሩ ወደ ክንስታንቲኖፕል ተመለሰ። አንድ ቀንም በሆቴል ያጌጠ ልብሱን ለብሶ እብነ በረድ ጠረጴዛውን ተገድሮ ቁጭ ብሎ ጋዜጣ ሲአገላብጥ አላፊ አግዳሚው ይህ ሰው ማነው ከየት መጣ ያ ፈታሉ አይደላምን ያ ወሮበሌው አይደለምን ሞቷል ስንል ከየት ዱብ አለ እያሉ ገልጸው እንዳይጠይቁትም የጌትነት ልብሱ አሳፍሯቸው ሲተማሙ አብሮ አደግ ደፋር ነውና አንድ አብሮ አደጉ እተቀመጠበት ሒዶ እንዴት ዋልህ ጌታዬ አረ አውቅህ አውቅህ ይመስለኛል አለው ።

አረ ከማወቅም አብሮ አደግ ነበርን ስሜን አረሳኸውን አለው ።

አዎን ጌታዬ ይቅር በለኝ ስምህን የረሳሁት ይመስለኛል አለው ስሜንስ አልረሳኸውም ታውቀዋለህ እኔም አሁን ስትተማሙብኝ ሰምቼአለሁ ስለዚህ ያለፍርሃት በዚያ በምታውቀው ስሜ ጥራኝ ግድ የለም አትፈር አለው አረ በጣም ዘንግቼዋለሁ መሰለኝ አለው። የጥንቱ ስምህ የሚጀመርበት ፊደል አቶ ወ ወይም አቶ ፈ እንዲህ ይመስለኛል ባላሳስት ቢለው አዎን ልክ ነው አይዞህ አቶ ፈታሌ ወይም ወሮበሌ በለኝ እኔ ተጠሪው ሳላፍር አንተን ጠሪውን ምን አስፈራህ አየህ እኔ ነኝ ያ ፈታል ያ ወሮበላ የምባለው ሰው አለው ።

ደግሞ ከዚህ ሌላ የስሜን ነገር ምን ላስረዳህ አንተ እንዲህ ቈሸሽህ በድኅነት ትኖራለህ እኔ ግን መሔድና ማየት መልካም ነውና ከመሔድ የተነሣ ውበት ጌትነትን አግኝቼ መጣሁ ።

ያ ጓደኛው ካንተ ውበትና ጌትነት አግኝቶ መምጣት የኔው መልካም ስምን ይዞ በድህነት መቀመጥ ይሻላል አለው ደግሞ ድህነት ነውር ሆነና ትሰድበኛለህን ሞኝላቃ ሌባ ወሮበላ ይህ ፈታል ምናምንቴ ነውረኛ ቢለው ተሳዳቢው ወሮበሌ ወይም ፈታሌ ብለህ ብትሰድበኝ ከቁም ነገር አልቆጥረውም ደስ እንዲለኝና ስድቤን እንዳውቀው በዚህ ቀለም እዚህ እነጩ እብነ በረድ ላይ በጉልህ ጻፈውና አላፊ አግዳሚው ያንብበው አለው። ተሳዳቢውም እንደ ታዘዘ በእብነ በረድ ላይ በጉልህ በፊት የሰደበውን ስድብ ጻፈው ከዚህ በኋላ ተሰዳቢው ወሮብሌ ወይም ፈታሌ ተኪሱ ባንክ ኖቱን (የገንዘብ ወረቀቱን) መዘዝ መዘዝ አደረገና ስድቡ በተጻፈበት እብነ በረድ ጠረጴዛ ላይ ሙሉውን ዘረጋውና እስቲ ጌታው ተሳዳቢ የጻፍኸውን ስድብ አንብበው አለው ።

ያም ተሳዳቢ አሁንማ በባንክ ኖት ሸፍነኸው እንዴት ላንብበው አለው ።

ወሮበሌ ቂሉ ደኸውልህ ገንዘብ እንደዚህ ነውርን ይሸፍናል ያንተን ድምጻዊ ስድብ ድምጽ የለሽ ባንክ ኖት ሸፈነው ስለዚህ የክፋትም የበጎነትም መሠረት ገንዘብ መሆኑን እንድትረዳልኝ እለምንሃለሁ ። በል ደህና ዋል ወንድሜ ተባ ብለው ተለያዩ ።

የብርሃንና ሰላም ደጀጠኒ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጋምቤላ ።

መልካም ምክር ለሀገር ጥቅም።

ክቡራን የሀገሬ መኳንንትና መሳፍንት ወይዛዝርና እመቤቶች እኔ በእናንተ በጌቶቼ ፊት እንደ አንዲት ሰናፍጭ ቅንጣት ነኝ ከዚህ በታች ያለውን ቃል ለክቡራን ጌቶቼ ለማመልከት ያነሣሣኝ በሀገራችን ፍቅር እያነሰ ፥ ምቀኛ እየጐለመሰ ስለ ሔደ ስለዚህ በፊታችሁ ሞገስ አግኝቼ ላመለክታችሁ በፊታችሁ ቁሜያለሁ (ማለት) እንዳትንቁኝና እንዳትነቅፉኝ ያለቁጣ በትዕግሥት እንድታደምጡኝ ከጫማችሁ በታች ወድቄ እለምናችኋለሁ።

፩ኛ፤ ክቡራን ሆይ ልጆቻችሁን በተማሪ ቤት ብታስደጓቸውና ጥበብና ዕውቀት በልቡናቸው ቢአድርባቸው እጅግ መልካም ነበር። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው እንደተባለ አትስቱትም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያድርባቸዋል። ደሀ ከመበደል ሀገር ከማጥፋት ለመንግሥት ከአለመገዛትና በንጉሥ ላይ ጠብና ክርክር ከማምጣት ከዚህ ከድንቁርና ተከልክለው ወደ ጥበብ መንገድ ቢመለሱ ለሀገር ጥቅም ነበር።

፪ኛ፤ እነሱንም እጅግ ጥፋት ያገኛቸዋል ይኸው ትምህርታቸው የሚአመጣባቸው መሰቀልና መገረፍ መታሰርና መዋረድ ይህን የመሰለ ክፉ ቅጣት ያመጣባቸዋል ከነዚህ ከአራቱ አንዱ ገንዘባቸው መሆኑ ያለ ጥርጥር የታወቀ ነው። ለንደነዚህ ያለ ጥፋተኛና ዓመፀኛ መቅጫ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነገሥታት ሰይፍ ተቀብለዋል ። ከዚህ ሁሉ እንዲሰውሩቸው ከተማሪ ቤት ገብተው ለመንግሥታቸውና ለሀገራቸው የሚጠቅመውን ጉዳና ቢከተሉ መልካም ይመስለኛል።

፫ኛ፤ ክቡራን ጌቶቼ ግን ጥበብን ንቃችሁ ድንቁርናን አክብራችሁ ልጆቻችሁ በተማሪቤት ቢገቡ ጥበብን ቢማሩ የተጠቁና የተጎዱ መስሏችሁ ከትምህርት ተከልክለው በድንቁርና ተሸፍነው ወደ ጥበብ የሚመራቸውን ዕውቀትን ንቃችሁ ስንፍናን ገንዘብ አድርጋችሁ ለልጆቻችሁ ጨለማን ማውረሳችሁ እጅግ ያሳዝናል።

፬ኛ፤ ልጆቻችሁን በጠጅና በጮማ እያቀማጠላችሁ በመጋረጃ ውሥጥ ታሳድጓቸዋላችሁ እነዚህ በጠጅና በጮማ ሲቀማጠሉ ያደጉ ልጆች በትምህርት ጉዳና አልሔዱምና ከቀን ብዛት የተለመደው ግብራቸው ሲቀርባቸው ያባቶቻቸውን ቦታና ርስት እየሸጡ የተለመደ ግብራቸውን ይፈጽሙበታል ይኸውም ባይበቃቸው በዱር ገብተው ከመንግሥት ፈቃድ ወጥተው መቀማት ሃገር ማጥፋት ደሀውን ማስለቀስ መንግሥትን ማሳዘን በሀገራቸው ላይ ክፉ መምከር ይህንን የማይገባ ሥራ ለምደው ይቀራሉ። እንደዚህ ያለውን ያልተገባ ሥራ ሲሠሩ መንግሥት አሲይዞ ያመጣቸዋል ከአደባባይ

ቀርበው ተፈርዶባቸው ሲቀጡ ብታዝኑና ብታለቅሱ ተፈቱ ከማሳደግ ጠንቀቅ አድርጎ ነበረ እንጂ ኋላ በከንቱ ብታዝኑ ጥቅም የለውም እንደዚህ ያለው ጥፋት በእናንተ እንደሆነ የታወቀ ነውና ተመልከቱት ።

፫ኛ ፡ ጌቶቼ ሆይ ንጉሣችን ርኅሩኁ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኀይለ ሥላሴ ለሀገራችን ልጆች ብለው የእውቀት መጉልመሻ የትምህርት ቤት በየሀገሩ ከፈቱልን ከዚያ ያለ ሐሳብ እንደ ልባቸው እየበሉና እየለበሱ የጥበብን ጕዳና ቢከተሉ በጣም ጥቅም ያገኛሉ። እናንተም ጌቶቼ በየክፍላችሁና በየአውራጃችሁ ተማሪ ቤት እየከፈታችሁ ሀብታምና ደሀ ሳትለዩ ሕፃናቱን ብታስተምሩ ለሀገራችሁና ለመንግሥታችሁ በጣም ጥቅም ነው ። ገንዘባችሁን በከንቱ ለውጭ አገር ሰዎች ብታፈሱላቸው ምን ትርፍ ይገኝበታል ወጭ ከሚበዛ ገቢው ቢበዛ ጥቅሙ ለማን ነው፥ ሕዝባችሁን ብታስተምሩትና ብታሠለጥኑት የምትፈልጉት መሣሪና ዕቃ ሁሉ ከአገራችሁ ይገኝ አልነበረምን። ነገር ግን የቋንቋ ትምህርት ብቻ ለሀገራችን አይጠቅምም የእጅ ጥበብ ብረት ሥራ እናጺነት ፡ ድንጊያ ማለዘብና መንገድ መጥረግ ደኅን የመሰለ ሥራ ለሀገራችን ይጠቅማል እንጂ የአፍ ጥቦብ ገንዘባችን አይደለም(ማለት) የቋንቋ ትምህርትን ለመንቀፍ ብዬ አይደለም የእጅ ጥበብም ቢጨመርበት ሁለቱ እየተደጋገፉ ለሀገራቸው ይጠቅማሉ ብዬ ነው እንጂ የእጅ ጥበብ በሀገራችን እየበዛና እየሰፋ ቢሔድ ለሀገር ይጠቅማል እንጂ አይጐዳም። መማርና ማወቅ ሳሉ ከትምህርት አዝመራ ልጆቻችሁን መከልከላችሁ እጅግ ያሳዝናል ከትምህርት የሚገኙ ፍሬዎች ፍቅር፥ ትዕግሥት፥ ስምምነት፥ ለሀገር ማሰብና ለመንግሥት መታዘዝ፥ እንደ ነዚህ ያሉ መልካሞች ነገሮች ይገኛሉ ። ከድንቁርና የሚገኙ መራራዎች ፍሬዎች ምቀኝነት ፡ተንኰል፥ ትዕቢት፥ ጠብና ክርክር እንደነዚህ ያሉ መጥፎዎች ነገሮች ይገኛሉ።እነዚህን መራሮችን ፍሬዎች አጥፍታችሁ መልካሞቹን ፍሬዎች በሀገራችን እየበዙና እየሰፉ ቢሔዱ አገራችን እየበለጸገች መንግሥታችን እየከበረ ወደከፍተኛው ደረጃ ለመድረስ የግድ ነበር ። ነገር ግን ድንቁርናና ጨለማ ትዕቢትና ጠብ እነዚህ ካልጠፉ ፍቅር አትገኝም። ጌቶቼ ሆይ አሁን ሕዝቡ እንዲማርና አገራችን እንዲሰፋ መንግሥታችን እንዲከብር ብታደርጉ ፍቅርን ገንዘብ ታደርጉ ነበር። ክቡራን ሆይ የነደደው ብዙ ያናገራልና ነገር ሳላስተካክል ስሕተትና ግድፈት መሆኑን አይታችሁ በጥፋቱ እንድትምሩኝ እለምናችኋለሁ ከደኃ ጥፋት ከጌታ ምሕረት ስጦታ ሲያያዝ የመጣ ነውና።

አሰፋ አበበ በፍሬር ተማሪ ቤት ኢየሩሳሌም።

ከእውነት ስለ አለ መሳሳት ።

ቀን በሰዓት፥ ዓመት በወራት ይለዋወጣል ፡ ቀን በሰዓት ጡዋት በቀትር ፤ ቀትር በማታ ይለወጣል ። ዓመት በወራት፥ ሐጋይ በክረምት ፤ ክረምት በመጸው ፡ መጸው በጸደይ እንደሚለወጥ፥ ሕፃንነት በጐልማሳነት ። ጐልማሳነት በሽምግልና ሽምግልና ፤ በአርጅና እንደሚለወጥ ባሕርይም እንደዚሁ የሕፃንነት ባሕርይ በጐልማሳነት ባሕርይ፥ የጐልማሳነት ባሕርይ በሽምግልና ባሕርይ ምንም ተለዋዋጭ ቢሆን በበጐነት ወይም በክፋት ለሰው አንድአንድ የተለየ ባሕርይ ይሰጠዋል፥ ባሕርይ በትምህርት ይለወጣል፥ ባሕርይ በምክር ይለወጣል በማግኘት በማጣት ይለወጣል ፡ አጥቶ በማግኘት ይለወጣል ። አግኝቶ በማጣት ይለወጣል፥ በጊዜ ማግኘት ይለወጣል፥ ደጉን ባሕርይ ወደክፋት ለመለወጥ ቢመከር የማይለወጥ አለ፥ ክፉውን ባሕርይ ወደበጐነት ለመለወጥ ቢመከር የማይለወጥ አለ፤ ባሕርይ በጥቂቶች ዘንድ ሳይለወጥ ጸንቶ ይኖራል። በትምህርትም በምክርም በጊዜም የማይለወጡ ተፈጥሮን ተመክሮ አያስጥለውም የሚባለው ነው ፡ ባሕርይ በብዙዎች ዘንድ ተለዋዋጭ ይሆናል ይኸውም ተጥንት የቆየ ነው፥ ይሁዳ ከበጐነት ወደክፋት፥ ጳውሎስ ከክፋት ወደበጐነት ተለዋውጠዋል። ደጉ ባሕርይ ለክፋት ክፉው ባሕርይ ለበጎነት ተለዋዋጭ ነውና ሰው ለጊዜው የያዘውን ባሕርይ ተመልክቶ ክፉውን የክፋቱን ዝና፥ ደጉን የበጎነቱ ዝና ይናገሩዋል እንጂ ፡ እንዲህ ነበር ብሎ ማውጋት ከእውነት ያሳስታል፥ ነበር ከማለት ነው ማለት ይሻላል ።

ማህሉ ጽጌ

የተረሳ ምክር ።

አስተዋዩ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ስለሀገር ፍቅር ባመነጩት የመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደርበሚባለው መጽሐፍ ይልቁንም በ፳ተኛው ምዕራፍ ውሥጥ ከውጭ አገር የሚመጣውን በመግዛት ባገር ውሥጥ የነበረው ሥራ እየተረሳ ሲሔድ መሆኑንና በዚሁም ምክንያት የሚያገኘንን ጉዳት አስረድተው መክረውናል ። ይኸውም ከተጻፈ ጊዜው ቈይቷል ። ይህነኑ የሚጠቅም ምክራቸውን በየልባችን አጥንተነውና ተጠንቅቀንበት ይሆንን አይመስለኝም። እንዲያው እንዳለፈ ታሪክ እያነበብንና እየተደነቅን አልፈነው ደሆናል እንጂ ምክራቸውን ተኪታትለነውና ተጠንቅቀንበት ቢሆንስ ባገር ውሥጥ የሚሠራው እየበዛ ከውጭ የሚመጣው እያነሰ ሲሔድ ይታይ ነበር።

ከዚህ በፊትም ባገር ውሥጥ የነበሩት ጥቅሞችና ሥራዎች ምንም ደስ የማያሰኙን ቢሆኑ ሌሎቹ ላዲሱ ሥልጣኔ የምንመኛቸው ለመሠራት እስኪቻሉ ድረስ እነዚያኑ መሠረት አድርገን እያሻሻልናቸው ወደምንመኛቸው ብንደርስ ይሻለናል እንጂ የተለመዱት ቢተዉና ቢረሱ ከብርታት ቢታረፍባቸው ጥቅማችን አለመሆኑን እናስብበት ። በዚህ ወራት ከገር ዘንግና ቀንድ የተሠሩ ከዘራዎች በጥቂቶች ሰዎች እጅ አይቼ ደስ ብሎኛል የባለክፍሉ ሚኒስቴርም የዚህን ከዘራ ሥራና ይህነንም የመሰለ የጥበብ ሥራ ሁሉ ለሚጀምሩ ላገር ልጆች የማትጊያ ሽልማት እንዲያስብላቸውና ሕዝቡም ባገር ልጆች የሚሠሩትን ዕቃዎች እንዲገዛና እንዲያከብሩቸው ስብከት እንዲያደርግላቸው እመኛለሁ ። እንደዚህ ሲሆንም ጥበብን ለሚመለከቱ ለሀገር ልጆች ሁሉ ብርታትና መፅናናት ይሰጣቸዋል ለሀገር ልማትና ለሕዝብ ብልጽግናም እረዳት ይሆናል ስል ያንኑ ከብልሁ መጽሐፍ ያነበብሁትን ላንባቢዎችና ላስረጂዎች አስታውሳለሁ ። ተፈራ ይፍሩ።

ያለው ሥራ የታወቀ ስለሆነ ስሙን ያገሩ ሰዎች ወርበሌ ወይም ፈታሌ ይሉት ነበረ ። እሱም ሥራው ስለሆነ መጠሪያ ስሙ (የሥራ ስሙ) መሆኑን አውቆ ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት ይል ነበረ። እንደ ነውርም አልቆጠረውም ነበረ በኋላ ግን ሰው ጠላው አገር ናቀው የሚገድሉት ቢሆን ወደ አሜሪካ ኮብልሎ ሒዶ በአሜሪካ በዚያው አዋቂ በሆነበት ሥራው ባለ ብዙ ገንዘብ ሆነና በጣሙ በለጸገ መበልጸግና መክበርም በሰው አገር አይደምቅምና ሀብቱንና ብልጽግናውን ይዞ ወደ ተወለደበት አገሩ ወደ ኮንስታንቲኖፕል ተመለሰ። አንድ ቀንም በሆቴል ያጌጠ ልብሱን ለብሶ እብነ በረድ ጠረጴዛውን ተገድሮ ቁጭ ብሎ ጋዜጣ ሲአገላብጥ አላፊ አግዳሚው ይህ ሰው ማነው ከየት መጣ ያ ፈታሌ አይደላምን ያ ወርበሌው አይደለምን ሞቷል ስንል ከየት ዱባለ እያሉ ገልጸው እንዳይጠይቁትም የጌትነት ልብሱ አሳፍሯቸው ሲተማሙ አብሮ አደግ ደፋር ነውና አንድ አብሮ አደጉ አተቀመጠበት ሒዶ እንዴት ዋልህ ጌታዬ እረ አውቅህ አውቅህ ይመስለኛል አለው ።

እረ ከማወቅም አብሮ አደግ ነበርን ስሜን እረሳኸውን አለው ።

እዎን ጌታዬ ይቅር በለኝ ስምህን የረሳሁት ይመስለኛል አለው ስሜንስ አልረሳኸውም ታውቀዋለህ እኔም አሁን ስትተማሙብኝ ሰምቼአለሁ ስለዚህ ያለፍርሃት በዚያ በምታውቀው ስሜ ጥራኝ ግድ የለም አትፈር አለው እረ በጣም ዘንግቼዋለሁ መሰለኝ አለው። የጥንቱ ስምህ የሚጀመርበት ፊደል አቶ ወ ወይም አቶ ፈ እንዲህ ይመስለኛል ባላሰበት ቢለው አዎን ልክ ነው አይዞህ አቶ ፈታሌ ወይም ወርበሌ በለኝ እኔ ተጠሪው ሳላፍር አንተን ጠሪውን ምን አስፈራህ አየህ እኔ ነኝ ያ ፈታል ያ ወርበላ የምባለው ሰው አለው ።

ደግሞ ከዚህ ሌላ የስሜን ነገር ምን ላስረዳህ አንተ እንዲህ ቈሽሽህ በድኅነት ትኖራለህ እኔ ግን መሔድና ማየት መልካም ነውና ከመሔድ የተነሣ ውበት ጌትነትን አግኝቼ መጣሁ ።

ያ ጓደኛው ከንተ ውበትና ጌትነት አግኝቶ መምጣት የኔው መልካም ስምን ይዞ በድህነት መቀመጥ ይሻላል አለው ደግሞ ድህነት ነውር ሆነና ትሰድበኛለህን ሞሽላቃ ሌባ ወርበላ ይህ ፈታል ምናምንቴ ነውረኛ ቢለው ተሳዳቢው ወርበሌ ወይም ፈታሌ ብለህ ብትሰድበኝ ከቁም ነገር አልቆጥረውም ደስ እንዲለኝና ስድቤን እንዳውቀው በዚህ ቀለም እዚህ እነጩ እብነ በረድ ላይ በጉልህ ጻፈውና አላፊ አግዳሚው ያንብበው አለው። ተሳዳቢውም እንደ ታዘዘ በእብነ በረድ ላይ በጉልህ በፊት የሰደበውን ስድብ ጻፈው ከዚህ በኋላ ተሰዳቢው ወርበሌ ወይም ፈቶሌ ተኪሱ ባንክ ኖቱን (የገንዘብ ወረቀቱን) መዘዝ መዘዝ አደረገና ስድቡ በተጻፈበት እብነ በረድ ጠረጴዛ ላይ ሙሉውን ዘረጋውና እስቲ ጌታው ተሳዳቢ የጻፍኸውን ስድብ አንብበው አለው ።

ያም ተሳዳቢ አሁንማ በባንክ ኖት ሸፍነኸው እንዴት ላንብበው አለው ።

ወርበሌ ቂሉ ደኸውልህ ገንዘብ እንደዚህ ነውርን ይሸፍናል ያንተን ድምጻዊ ስድብ ድምጹ የለሽ ባንክ ኖት ሸፈነው ስለዚህ የክፋትም የበጎነትም መሠረት ገንዘብ መሆኑን እንድትረዳልኝ እለምንሃለሁ ። በል ደህና ዋል ወንድሜ ተብ ብለው ተለያዩ ።

የብርሃንና ሰላም ደጀጠኒ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጋምቤላ ።

መልካም ምክር ለሀገር ጥቅም።

ክቡራን የሀገሬ መኳንንትና መሳፍንት ወይዛዝርና እመቤቶች እኔ በእናንተ በጌቶቼ ፊት እንደ አንዲት ሰናፍጭ ቅንጣት ነኝ ከዚህ በታች ያለውን ቃል ለክቡራን ጌቶቼ ለማመልከት ያነሣሣኝ በሀገራችን ፍቅር እያነሰ ፥ ምቀኛ እየጐለመሰ ስለ ሔደ ስለዚህ በፊታችሁ ሞገስ አግኝቼ ላመለክታችሁ በፊታችሁ ቁሜያለሁ (ማለት) እንዳትንቁኝና እንዳትነቅፉኝ ያለቂጣ በትዕግሥት እንድታደምጡኝ ከጫማችሁ በታች ወድቄ እለምናችኋለሁ።

፩ኛ፥ ክቡራን ሆይ ልጆቻችሁን በተማሪ ቤት ብታሳድጓቸውና ጥበብና ዕውቀት በልቡናቸው ቢአድርባቸው እጅግ መልካም ነበር። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው እንደተባለ አትስቱትም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያድርባቸዋል። ይህ ከመበደል ሀገር ከማጥፋት ለመንግሥት ከአለመገዛትና በንጉሥ ላይ ጠብና ክርክር ከማምጣት ከዚህ ከድንቁርና ተከልክለው ወደ ጥበብ መንገድ ቢመለሱ ለሀገር ጥቅም ነበር።

፪ኛ፥ እነሱንም እጅግ ጥፋት ያገኛቸዋል ይኸው ትምህርታቸው የሚአመጣባቸው መሰቀልና መገረፍ መታሰርና መዋረድ ይህን የመሰለ ክፉ ቅጣት ያመጣባቸዋል ከነዚህ ከአራቱ አንዱ ገንዘባቸው መሆኑ ያለ ጥርጥር የታወቀ ነው። ለንደነዚህ ያለ ጥፋተኛና ዓመፀኛ መቅጫ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነገሥታት ሰይፍ ተቀብለዋል ። ከዚህ ሁሉ እንዲሰውራቸው ከተማሪ ቤት ገብተው ለመንግሥታቸውና ለሀገራቸው የሚጠቅመውን ጐዳና ቢከተሉ መልካም ይመስለኛል።

፫ኛ፥ ክቡራን ጌቶቼ ግን ጥበብን ንቃችሁ ድንቁርናን አክብራችሁ ልጆቻችሁ በተማሪቤት ቢገቡ ጥበብን ቢማሩ የተጠቁና የተጐዱ መሰሏችሁ ከትምህርት ተከልክለው በድንቁርና ተሸፍነው ወደ ጥበብ የሚመራቸውን ዕውቀትን ንቃችሁ ስንፍናን ገንዘብ አድርጋችሁ ለልጆቻችሁ ጨለማን ማውረሳችሁ እጅግ ያሳዝናል።

፬ኛ፥ ልጆቻችሁን በጠጅና በጮማ እያቀማጠላችሁ በመጋረጃ ውሥጥ ታሳድጓቸዋላችሁ እነዚህ በጠጅና በጮማ ሲቀማጠሉ ያደጉ ልጆች በትምህርት ጐዳና አልሔዱምና ከቀን ብዛት የተለመደው ግብራቸው ሲቀርባቸው ያባቶቻቸውን በታና ርስት እየሸጡ የተለመደ ግብራቸውን ይፈጽሙበታል ይኸውም ባይበቃቸው በዱር ገብተው ከመንግሥት ፈቃድ ወጥተው መቀማት ሃገር ማጥፋት ደሀውን ማስለቀስ መንግሥትን ማሳዘን በሀገራቸው ላይ ክፉ መምከር ይህንን የማይገባ ሥራ ለምደው ይቀራሉ። እንደዚህ ያለውን ያልተገባ ሥራ ሲሠሩ መንግሥት አሲይዞ ያመጣቸዋል ከአደባባይ

ቀርበው ተፈርዶባቸው ሲቀጡ ብታዝኑና ብታለቅሱ ተፈቱ ከማሳደግ ጠንቀቅ አድርጎ ነበረ እንጂ ኋላ በከንቱ ብታዝኑ ጥቅም የለውም እንደዚህ ያለው ጥፋት በእናንተ እንደሆን የታወቀ ነውና ተመልከቱት ።

፫ኛ ፡ ጌቶቼ ሆይ ንጉሣችን ርኅሩኁ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ለሀገራችን ልጆች ብለው የእውቀት መገልመሻ የትምህርት ቤት በየሀገሩ ከፈቱልን ከዚያ ያለ ሐሳብ እንደ ልብቻው እየበሉና እየለበሱ የጥበብን ጉዳና ቢከተሉ በጣም ጥቅም ያገኛሉ። እናንተም ጌቶቼ በየክፍላችሁና በየአውራጃችሁ ተማሪ ቤት እየከፈታችሁ ሀብታምና ደሀ ሳትለዩ ሕፃናቱን ብታስተምሩ ለሀገራችሁና ለመንግሥታችሁ በጣም ጥቅም ነው ። ገንዘባችሁን በከንቱ ለውጭ አገር ሰዎች ብታፈሱላቸው ምን ትርፍ ይገኝበታል ወጭ ከሚበዛ ገቢው ቢበዛ ጥቅሙ ለማን ነው፥ ሕዝባችሁን ብታስተምሩትና ብታሠለጥኑት የምትፈልጉት መሣሪያና ዕቃ ሁሉ ከአገራችሁ ይገኝ አልነበረምን። ነገር ግን የቋንቋ ትምህርት ብቻ ለሀገራችን አይጠቅምም የእጅ ጥበብ ብረት ሥራ አናፂነት ፥ ድንጊያ ማለዘብና መንገድ መጥረግ ይኸን የመሰለ ሥራ ለሀገራችን ይጠቅማል እንጂ የእፍ ጥበብ ገንዘባችን አይደለም(ማለት) የቋንቋ ትምህርትን ለመንቀፍ ብዬ አይደለም የእጅ ጥበብም ቢጨመርበት ሁለቱ እየተደጋገፉ ለሀገራቸው ይጠቅማሉ ብዬ ነው እንጂ የእጅ ጥበብ በሀገራችን እየበዛና እየሰፋ ቢሔድ ለሀገር ይጠቅማል እንጂ አይጐዳም። መማርና ማወቅ ሳሉ ከትምህርት አዝመራ ልጆቻችሁን መከልከላችሁ እጅግ ያሳዝናል ከትምህርት የሚገኙ ፍሬዎች ፍቅር፥ ትዕግሥት፥ ስምምነት፥ ለሀገር ማሰብና ለመንግሥት መታዘዝ፥ እንደነዚህ ያሉ መልካሞች ነገሮች ይገኛሉ ። ከድንቁርና የሚገኙ መራራዎች ፍሬዎች ምቀኝነት ፡ ተንኰል፥ ትዕቢት፥ ጠብና ክርክር እንደነዚህ ያሉ መጥፎዎች ነገሮች ይገኛሉ።እነዚህን መራሮችን ፍሬዎች አጥፍታችሁ መልካሞቹን ፍሬዎች በሀገራችን እየበዙና እየሰፉ ቢሔዱ አገራችን እየበለጸገች መንግሥታችን እየከበረ ወደከፍተኛው ደረጃ ለመድረስ የግድ ነበር ። ነገር ግን ድንቁርናና ጨለማ ትዕቢትና ጠብ እነዚህ ካልጠፉ ፍቅር አትገኝም። ጌቶቼ ሆይ አሁን ሕዝቡ እንዲማርና አገራችን እንዲሰፋ መንግሥታችን እንዲከብር ብታደርጉ ፍቅርን ገንዘብ ታደርጉ ነበር። ክቡራን ሆይ የነደደው ብዙ ያናገራልና ነገር ሳላስተካክል ስሕተትና ግድፈት መሆኑን አይታችሁ በጥፋቱ እንድትምሩኝ እለምናችኋለሁ ከደጋ ጥፋት ከጌታ ምሕረት ከጥንት ሲያያዝ የመጣ ነውና።

አሰፋ አበበ በፍሬር ተማሪ ቤት ኢየሩሳሌም።

ከእውነት ስለ አለ መሳሳት ።

ቀን በሰዓት፥ ዓመት በወራት ይለዋወጣል ፡ ቀን በሰዓት ጡዋት በቀትር ፤ ቀትር በማታ ይለወጣል ። ዓመት በወራት፥ ሐጋይ በክረምት ፤ ክረምት በመጸው ፤ መጸው በጸደይ እንደሚለወጥ፥ ሕፃንነት በጕልማሳነት ። ጕልማሳነት በሽምግልና ሽምግልና ፤ በእርጅና እንደሚለወጥ ባሕርይም እንደዚሁ የሕፃንነት ባሕርይ በጕልማሳነት ባሕርይ፥ የጕልማሳነት ባሕርይ በሽምግልና ባሕርይ ምንም ተለዋዋጭ ቢሆን በበጎነት ወይም በክፋት ለሰው አንድአንድ የተለየ ባሕርይ ይሰጠዋል፥ ባሕርይ በትምህርት ይለወጣል፥ ባሕርይ በምክር ይለወጣል በማግኘት በማጣት ይለወጣል ፡ አጥቶ በማግኘት ይለወጣል ። አግኝቶ በማጣት ይለወጣል፥ በጊዜ ማግኘት ይለወጣል፥ ደጉን ባሕርይ ወደክፋት ለመለወጥ ቢመከር የማይለወጥ አለ፥ ክፋውን ባሕርይ ወደበጎነት ለመለወጥ ቢመከር የማይለወጥ አለ፤ ባሕርይ በጥቂቶች ዘንድ ሳይለወጥ ጸንቶ ይኖራል። በትምህርትም በምክርም በጊዜም የማይለወጡ ተፈጥሮን ተመክሮ አያስጥለውም የሚባለው ነው ፡ ባሕርይ በብዙዎች ዘንድ ተለዋዋጭ ይሆናል ይኸውም ተጥንት የቆየ ነው፥ ይሁዳ ከበጎነት ወደክፋት፥ ጳውሎስ ከክፋት ወደበጎነት ተለዋውጠዋል። ደጉ ባሕርይ ለክፋት ክፋው ባሕርይ ለበጎነት ተለዋዋጭ ነውና ሰው ለጊዜው የያዘውን ባሕርይ ተመልክቶ ክፋውን የክፋቱን ዝና፥ ደጉን የበጎነቱ ዝና ይናገሩዋል እንጂ ፡ እንዲህ ነበር ብሎ ማውጋት ከእውነት ያሳስታል፥ ነበር ከማለት ነው ማለት ይሻላል ።

ማህሉ ጽጌ

የተረሳ ምክር ።

አስተዋዩ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ስለሀገር ፍቅር ባመነጩት የመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደርበሚባለው መጽሐፍ ይልቁንም በ፰ተኛው ምዕራፍ ውሥጥ ከውጭ አገር የሚመጣውን በመብዛት ባገር ውሥጥ የነበረው ሥራ እየተረሳ ሲሔድ መሆኑንና በዚሁም ምክንያት የሚያገኘንን ጉዳት አስረድተው መክረውናል ። ይኸውም ከተጻፈ ጊዜው ቈይቷል ። ይህነኑ የሚጠቅም ምክራቸውን በየልባችን አጥንተነውና ተጠንቅቀንበት ይሆንን አይመስለኝም። እንዲያው እንዳለፈ ታሪክ እያነበብንና እየተደነቅን አልፈነው ይሆናል እንጂ ምክራቸውን ተከታትለነውና ተጠንቅቀንበት ቢሆንስ ባገር ውሥጥ የሚሠራው እየበዛ ከውጭ የሚመጣው እያነሰ ሲሔድ ይታይ ነበር።

ከዚህ በፊትም ባገር ውሥጥ የነበሩት ጥቅሞችና ሥራዎች ምንም ደስ የማያሰኙን ቢሆኑ ሌሎቹ ላዲሱ ሥልጣኔ የምንመኛቸው ለመሥራት እስኪቻሉ ድረስ እነዚያኑ መሥረት አድርገን እያሻሻልናቸው ወደምንመኛቸው ብንደርስ ይሻለናል እንጂ የተለመዱት ቢተዉና ቢረሱ ከብርታት ቢታረፍባቸው ጥቅማችን አለመሆኑን እናስብበት ። በዚህ ወራት ካገር ዘንጋና ቀንድ የተሠሩ ከዘራዎች በጥቂቶች ሰዎች እጅ አይቼ ደስ ብሎኛል የባለክፍሉ ሚኒስቴርም የዚህን ከዘራ ሥራና ይህነንም የመሰለ የጥበብ ሥራ ሁሉ ለሚጀምሩ ላገር ልጆች የማትጊያ ሽልማት እንዲያስብላቸውና ሕዝቡም ባገር ልጆች የሚሠሩትን ዕቃዎች እንዲገዛና እንዲያከብራቸው ስብከት እንዲያደርግላቸው እመኛለሁ ። እንደዚህ ሲሆንም ጥበብን ለሚመለከቱ ለሀገር ልጆች ሁሉ ብርታትና መፅናናት ይሰጣቸዋል ለሀገር ልማትና ለሕዝብ ብልጽግናም እረዳት ይሆናል ስል ያንኑ ከብልሁ መጽሐፍ ያነበብሁትን ላንባቢዎችና ላስረጂዎች እስታውሳለሁ ። ተፈራ ይፍሩ።

ያንድ ሰው ትንሽ ምክር ወደፊት ለሚመጣው ማሰብ ይገባናል።

የሌላ ሰው ጥቅም ለኛ ምን ይሆናል ትንሹ ትልቁን ቢያፈቅር ቢያከብር ሳይንቃቀፍም ተባብሮ ቢኖር ወደ ትልቁ ደረጃ ይወጣ ነበር ።

መጀመርያ የጥበብ ምንጩ፡ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አባታችንና የሕይወት ምንጭ የምትሆን ኢትዮጵያ እናታችንን ማክበር ይገባናል ። ሁለተኛም አሽከር ጌታውን እንዲያከብር ታዞዋል ጌታውንም አክባሪና ታዛዥ ቢሆን በጌታው ቤት እንደተከበረ ይኖራል ጌትዮውም ደህና አሽከር አለው እየተባለ እንደተከበረ ይኖራል ከጌታውም ቤት ከወጣ በኋላ ጌታውን አክባሪ ነው ታማኝ ነው እየተባለ እንጀራ ይወጣለታል ።

ሁለተኛም ሴት ባልዋን እንድታከብር ታዟል ባልዋንም ያከበረች እንደሆን የገሌ ሚስት ጠንቃቃ ነች ቆምነገረኛ ነች ባልዋንም ታከብራለች ለቤትዋም ታስባለች እየተባለች እስዋም እንደተከበረች ትኖራለች ።

ሶስተኛም ልጅ አባቱንና አባቱን የመሳሰሉትን ሽማግሌዎችን ማክበር ይገባዋል አባቱንም ያከበረ እንደሆነ ልጁ እንጀራ ይወጣለታል። አንድ ክበርቴ ሰው ሽማግሌ አባት ነበሩት አንዳንድ ትንሽ ልጅ እረኛ አድርጎ ከብቶች ያስጠብቃቸው ነበር ከብቶቹም የጠፉ ወይም እህል የበሉ እንደሆነ አስተኝቶ ይገርፋቸው ነበር። አንድ መነኰሴ መጡና ምነው በሽምግልና እረኝነት ይሆናልን ከብቶችዎን አሽከር ቀጥረው እያስጠበቁ ቤተ ክርስቲያን መሳም ይገባዎ ነበረ እንጂ አልዋቸው ሽማግሌውም መለሱ ከብቶቹ የኔ አይደሉም የልጄ ናቸው የጠፉ እንደሆነ ይጣላኛል እህልም የበሉ እንደሆነ ይገርፈኛል ብለው ተናገሩ። ቀኑስ ከብት ይጠብቃሉ ሌሊትስ ምን ይሠራሉ አልዋቸው ሌሊትስ ሥራ የለኝም ተኝቼ ሳስብ አድራለሁ አልዋቸው እንግዲያስ ሌሊት ሌሊት እየሔዱ ሰባት ቀን ቤተ ክርስቲያን ይሳሙና ድንጋዮችን በአእምሮ ያናገረ አምላክ ይመልስለዎታል አሏቸው። የመነኰሴውንም ቃል በሰሙ ጊዜ ሰባት ቀን ሌሊት ሌሊት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሔዱ ይስሙ ጀመር በሰባተኛውም ቀን ልጃቸው ወንድ ልጅ ነበረውና ልጁን ታቅፎ ሲያጫውት አሁን እንደዚህ አድርጌ አሳድጌ ምን ታደርግልኝ አለህ አለው ልጁም መለሰና አባቴ ሆይ ለትልቁ አባቴ እንደምታደርግለት አደርግልሀለሁ አለው ከዚህም በኋላ በሆዱ ጸጸት ገባና አባቴን ጥሩልኝ አለ አባቱም በተጠሩ ጊዜ ምን አድርጌ ይሆን እያለ በኃዘን እያለቀሰ መጣ አባቴ ሆይ እስከ አሁን ባጠፋሁት ይቅርታዎን ይስጡኝ ብሎ የክት ልብሱን ከሳጥን አውጥቶ አልብሶ በመዓርግ ቦታ አስቀመጣቸው አሁንም እኛ በኛ ካልተከባበርንና ካልተባበርን የውጭ አገር ሰው መጥቶ ሊያከብረንና ሊተባበረን አይቻልምና እርስ በርሳችን እንድንከባበር ከፉውን እርቀን መልካሙን መንገድ እንድንከተል በትንሽ ሐሳቤ አመለክታለሁ።ይህነን ማሰቤ በራሴ ስለተረዳሁት ነው ።

ዓለማየሁ ኃይለ ማርያም ።

የሺሚስት ሠራተኞች ትጋት ።

በመስከረም ፯ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም የሕዝብ ጤና ተጠባባቂ አቶ መሸሻ ይኸንኑ ሥራ ለመሥራት አብረን ወደ ውጭ ስንሔድ አንድ አህመድ ሻድ የሚባል ዓረብ የሕዝብ ጤና የሚጐዳ ሀሺሽ የተባለውን ቅጠል በአረቂ ቤት እያዞረ ሲሸጥ ይዘን ወደ ዋናው መድኃኒት መመርመሪያ ቤት አቅርበን ሺሚስቱ ዶክቶር ኤቤርት እርግጥ ሀሺሽ መሆኑን ለማወቅ በትልቁ ሚክሮስኮብ በሚባለው መኪናና በሌላም ዓይነት መኪና ቢመረምሩት እርግጥ ሀሺሽ መሆኑን ካወቁ በኋላ የተዘጋጀ እራፖራቸውን ጽፈው ለክቡር ቢትወደድ ጌታቸው ለአገር ግዛት ሚኒስትር ቢአቀርቡ ክቡር ቢትወደድ ጌታቸውም በደስታና በብርሃን ልቡናቸው የሚገባውን ፍርድ ከሺሚስቱ ጋር አብረው ሆነው ፍርዱን አስፈጽመው ፲፫ቀን እንዲታሰርና አምሳ ብር መቀጮ እንዲከፍል አደረጉ። አሁንም ይኸንን ፍርድ ቢቀበል ይኸ አህመድ ሻድል የሚባል ዓረብ የኢትዮጵያ መንግሥት የከለከለውን ሕግ ተላልፎ የሚአደነዝዙና የሚአሰክሩ መድኃኒቶች ሲሸጥ ከተገኘ የኢትዮጵያ መንግሥት እንዳቆመው ደምብ እንደሌሎች ሰዎች ሁሉ መቀጮ ከፍሎ ከአገር ቢወጣ መልካም ይሆን ይመስለኛል። ይኸንንም ያልኩበት እላይ እንዳልነው ሰው የለመደውን ሥራ መሥራቱ አይቀርምና ብዬ ነው ። ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ሆይ በተሳሳተኝ እርማችሁ እንድትጽፉልኝ ስል በማክበር እለምናችኋለሁ ። የሺሚስት ሠራተኛ ኪዳኔ ወልደ ዮሐንስ ።

ስለ ልጅ ማሞ ሞት ።

ልጅ ማሞ የግራዝማች ከልክሌ የፖስታ ቤት ሹም የነበሩት ልጅ ነው። እሱም የመልካም አባቱን በሕርይ ሳይለቅ በፖስታ ቤት ባ፩ኛው ክፍል ሠራተኛ ነበር። ከለቆቹና ከጓደኞቹ ጋራ ዘወትር ደስ ለማሰኘትና ትሕትና ለመሥራት ስንዱ ነበር፥ በተወለደ በ፳፪ ዓመቱ በጥቅምት ፬ ቀን ዓርብ ከማታው ባ፲፩ ሰዓት ዐርፎ ቅዳሜ ባ፬ ሰዓት በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ። የልጁን አወጣጥና መልካም ሰውነት ለተመለከተው እጅግ ያሳዝናል። የልቅሶ ዜማ ፡፡ ማሞን ግነዙት ቀበሩት። ከጓደኞቹ ለዩት። ምነው ለምልመህ አብበህ። ፍሬህን ሳታይ ቀረህ።

ከጓደኞቹ አንዱ አድምቄ ገብረ ወልድ የማዘጋ ቤት ሠራተኛ።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ ጊዜ እንዳስታወቀው የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ቃዶችን ቦታ ጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል።

የክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደውን ሁለት ቦታ አጥቢያው ሩፋኤልና ቂርቆስ ስፋቱ ፪፻ ሜትር ካሬና ፹፰ሺ. ፪፻፳፱ ሜትር ካሬ።

የፊታውራሪ በዳኔ አሸግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፱፻፲ና ፲ሺ.፪፻፺፮ ሜትር ካሬ።

የነጋድራስ ተፈራ ንጉሤ አጥቢያው ቂርቆስ ስፋቱ ፪ሺ. ፰፻፰ ሜትር ካሬ።

የቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ አጥቢያው አማኑኤል ስፋቱ ፰፬ሺ. ፰፱ ሜትር ካሬ።

ያቶ ወንድማገኘሁ በዛብህ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፫፻፴፮ ሜትር ካሬ ። ሺያጩም የሚደረገው በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ ነው።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሲጊያን ዘንድ ይገኛል ። ይህንኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተኩል ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

የሚሸጥ ቦታ

ማጀስቲክ ሆቴል አጠገብ ከሙሴ ሃርዲ ፊት ለፊት መሐመድአሊ ከሠራው አዲስ ፎቅ በታች ጥሩ ጥሩ ቤት የተሠራበት በወሩ እስከ መቶ ብር ድረስ ኪራይ የሚያመጣ ጥሩ የሚሸጥ ቦታ አለና የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ አቡጀዲድ ገበያ ላይ ወችራጀ የሚባል ሂንዲን ጠይቁ።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

ፋርማሲ ሣንትራል ተናግሮት የነበረውን በገዛ ዓይንዎ አይተው ስለተረዱት በጣም ደስ አለኝ ፤ መጥተው ስለተረዱ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ወደፊትም እየመጡ እንዲሁ እንዲረዱልኝ እመኛለሁ ።

እንደ ተባባልነው ስለ መልክዎ ጥንቃቄ አሁን ጥቂት እመክርዎታለሁ ።

የመልክን ቆዳ ስለሚአበላሹ በሺታዎች የተቀመሙትን ሳሙናዎች ሲወስዱ መልክም ሆኖ በረቂቅ ሺታ የተሰናዳውን የውበት ሳሙና ይውሰዱ ። ፊትዎን አልፎ አልፎ ጭረት ስለሚአደርገው በሺታ ኤሬሊን የሚባለውን መድኃኒታችንን እንዲአደርጉ አጥብቀን እንመክርዎታለን ። በጥቂት ቀን ደህና እንዲሆኑ ይኸንን መድኃኒት ማድረግ ነው ። እስከሁን ድረስ እሱን የሚተካ ሌላ መድኃኒት አልተገኘም ።

በፊትዎ ላይ ስለሚአደርጉት የሽቶ ዶቄት ወዝ ለሌለው መልክ«ኰልድ ክሬም»የምንለው መድኃኒታችን መልክም ነው ፤ ወዝ ላለው ፊት ግን«ቬቢርዢናል»የሚባለው መድኃኒታችን ነው የሚሻለው ስል እመክርዎታለሁ ።

ደግሞ በያይነቱ የተሰናዳውን የሩዝ ዶቄት ሺቶ «የሎቲም»ሆነ«የፒቬርትም»ሆነ ሌላም በያይነቱ ለማየትና ለመምረጥ ይችላሉ ፤ እንዲሁም ለከንፈር ቀለም የሚሆን እርሳስ ፲ያይነቱ አለኝ ዘወትርም ስለ አሚታሹበት አዲከሎኝ ይልቁንም ከድካም ባረፉ ጊዜ የሚታሹበትን ከኔ ዘንድ እንዲወስዱ አምናለሁ በዚሁ በፋርማሲአችን ውስጥ ለፊትና ለገላ ማሻ የላስቲክም ሆነ የውነተኛውም ኤፓንገር ሆነ አለን ብለን አስታውቀንዎታልና ሁለተኛ መናገር ያስፈልግ አይመስለኝም ።

ደግሞም በያይነቱ በእውቀት ጥበብ ስለሚመረመር ነገርና ስለ መንገድ መድኃኒት ማሰናዳት በልዩ ማወቄን እንዳይረሱ አስታውሳለሁ አገልጋይዎ ኤም ማትሣኪስ ።

በዚሁም መድኃኒት ቤት የፈረንሳይ ፤ የእንግሊዝ ፤ የጣሊያን ፤ የዓረብ ቋንቋ ይናገራሉ ።

አበማልተን
ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

አበ ማልተን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው። አበማልተን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል አበማልተን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል፡ የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፡ ቤርን ናቸው። በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው።

አበማልተን አዲስ አበባ ባሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ማጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር	
የቅ ዮ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር	
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፭	ብር	
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር	
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲	ብር	
፫ቱ መጻሕፍተ መነኮሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪	ብር	
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪	ብር	
ደስታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፱	ብር	
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር	
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር	
የዓለም ጆዖግራፊ ከነካርታው	፯	ብር	
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፯	ብር	
ድርሳነ ሚካኤል	፮	ብር	
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር	
ጎሀ ጽባሕ	፭	ብር	
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር	
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር	
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪	ብር	፳መ
የእርሻ ትምህርት	፩	ብር	፳መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ እጅግ ያማረ	፪	ብር	
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት፥ ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር	
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር	
የቍጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩	ብር	
የአማርኛ ሰዋሰው	፩	ብር	
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር	
የነፃ ደንብ ከነተጨማሪው	፩	ብር	፳መ
የብድር ደንብ	፩	ብር	
የጦር መሣሪያ ደንብ አዲስ	፩	ብር	፳መ
የገዳም ደንብ	፩	ብር	
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩	ብር	
ዮሐንስ ቡንያን	፩	ብር	
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፭	ብር	
የ፪ኛ	፳	ብር	
የ፫ኛ	፲፭	ብር	
የ፬ኛ	፲	ብር	
የ፭ ኛ	፯	ብር	
የ፮ኛ	፯	ብር	
የ፯ኛ	፯	ብር	
፳፱ ካርት ፖስታል	፩	ብር	
የረኮማንዴ ደብተር	፫	ብር	
ሕገ መንግሥት	፭	ብር	
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳	መሐ	
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን ነገ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፳	መሐ	
አጭር የዓለም ታሪክ	፳	መሐ	
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተስማማ	፳	መሐ	
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፳	መሐ	
ያማርኛ ምሳሌ	፳	መሐ	
አሳብና ምኞት	፬	መሐ	
የፍቅር መላከት	፬	መሐ	
ትምህርተ ሕፃናት	፬	መሐ	
የምሕረት አዋጅ	፬	መሐ	
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪	መሐ	
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪	መሐ	
የንቍጣጣሽ ግጥም	፪	መሐ	
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፪	መሐ	
፩ ጋዜጣ	፪	መሐ	
አርስጣላብ	፬	መሐ	
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፬	መሐ	
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፬	መሐ	
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፭	መሐ	
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፩	መሐ	
ካላንድሬ	፳	መሐ	
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪያ	፩	መሐ	
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፳	መሐ	
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፬	መሐ	

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት እጥፍ ። ነጠላ በየይነቱ ። እርሳስ መንኰልና ብረት ብርዕ ቀለም በየይነቱ።የካርት ቢዚት አንቦልብና ካርት ቢዚት በየይነቱ ። አንቦልብ ትልቅና ትንሽ በየይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፤ የደረት የኰበት ፤ የኵላሊት ፤ የጅማት ፤ የጨብጥ የቂጥኝና ፤ የቋቁቻ ፤ የሚያዋልድ ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፤ የርሻ የፋብሪክ ፤ የደን ፤ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዞና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገን ብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፯ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወከሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዷል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዘዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመኀብኘት ።

ማስታወቂያ ።

እስከ መስቀል ድረስ አንድ የቤት ሰብ መኪና የገዛ ሰው ደህና ሽልማት ያገኛል ።

በርቱ ይኸ እድል አያምልጣችሁ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፡ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

ቁ ፲ ፸፫ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፵፬
8me ANNE. № 44

ሐሙስ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 27 Octobre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ በደረክተሩ በአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታላቅ መታሰቢያ ያለው ቀን ።

ቀድሞ የጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ከተማ እንጦጦ ሳለ ልዑል ራስ መኰንን በበታንነት የተመሩት ከዚያው ቀጥሎ ባላባቱ ያወረሳቸው ልምላሜና ከረፍታ ያለው ቦታ አለ። ከዚያም ቀጥሎ ከነበሩት ባለቦታዎች ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እየገዙ አስፍተዉት መልከም መልከም ቤቶች ተሠርተውበት ውኃው በቧምቧ ገብቶ ብዙ አታክልት በቀለውበታል የአቶሞቢልም መንገድ ተሠርቶበት እጅግ ደስ የሚአሰኝ ቦታ ስለሆነ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጥቅምት ፲፫ቀን በዚያ ቦታ በዓል ለማድረግ ስለፈቀዱ በዚሁ ቀን የከር ዲፕሎማቲክን ሰዎች ደስ ለማሰኘት ለምሳ ጠርተዋቸው ነበር። ግብታ ተዘርግቶ ብርጭቆው ጠርቶ ተዘጋጅቶ ሲጠበቅ ገና ፯ሰዓት ሳይሆን ትጉሆች ሰዎች መምጣት ጀመሩ ። ፯ሰዓትም ሲሆን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ግርማዊት እቴጌ መነን መጡ። ከዚህም በኋላ የተጠሩት መኳንንትና ወይዘዝር ገቡ፥ቀጥሎም የከር ዲፕሎማቲክ ሰዎች ገቡ። ከኢትዮጵያ ታላላቆች መኳንንትና ወይዘዝር ወገን የነበሩት ቀጥለው የተጻፉት ናቸው ። የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ባለቤት ልዕልት ወለተ እስራኤል ፣ የክቡር ራስ ደስታ ባለቤት ልዕልት ተናኘ ወርቅ፥ የክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ባለቤት ልዕልት ዘነበወርቅ፥ የክቡር ፊታውራሪ ብሩ ባለቤት ክብርት ወይዘሮ ቀለመ ወርቅ ነበሩ ።

ልዑል ራስ ካሣ፥ የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፥የጦር ሚኒስትር ፊታውራሪ ብሩ ። ክቡር ራስ ደስታ ዳምጠው ። ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነበሩ ። ከዝቅተኞችም መኳንንት ጥቂቶች ነበሩ። ከ፯ት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት የምግብና የጨዋታ ጊዜ ነበረ ። ከዚያ በኋላ በሸምፓኝ ተመራርቀው ተነሡ።

ከዚህ በኋላ የልዑል ራስ መኰንን ቤት በነበረበት ተራራ ላይ ታላቅ ድንኳን ተተክሎ በኢትዮጵያ ዓላማ አጊጦ በውሥጡ መልከም መልከም ምንጣፍ ተነጥፎበት ጥሩ ጥሩ ወምበር ተደርድሮብት እጅግ ወደ እሚያአምረው ቦታ ሔድን፥በዚያም ቦታ እንማድር ፓሊ ያዘጋጁት ዓላማ ነበረ የዓላማውም አኳኋን አስቸጋሪ ነበረ። አኳኋኑም እንዲህ ነው ። ሁለት ወታደሮች በካብ ሥር ተሸሽገው አንዱ አብሮት ያለው ወታደር ፉጨት ሲአሰማው በመኪናው ላይ የተድበለበለ ላስቲክ ወደ ሰማይ ይጉናል።በዚያ ጊዜ ተኳሹ ተጠንቅቆ ቈይቶ በሁለት አፍ ረሽ ሁለት ጊዜ ይተኩሳል ። ከሮፓውያን የፈረንሣዊ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ሚኒስትር ዓላማውን መቱ ፥ ከኢትዮጵያውያንም ግራዝማች በቀለ አየለ ፩ጊዜ፥ቀኛዝማች ተፈራ በለው ሁለት ጊዜ መትተዋት ተጨበጨበ።ከዚህ በኋላ እንደ ገና ወደ ድንኳኑ ገብተን የሻይ ግብዣ ተደረገና የከር ዲፕሎማቲክ ሰዎች ተሰነባብተው ሔዱ፥ከዚህ በኋላ ጃንሆይና እቴጌ ጥቂት መንገድ በእግር ሒደው ወደ አቶሞቢል ገቡ።መንገድ ሲጀመርም ፀሐይ ጠልቃ ነበረች እንዲሁም ያቺ ቀን ፩ በመሆንዋ ለሕዝቡ ሳትጠቅመው አለፈች።

የከር ዲፕሎማቲክ ሰዎችም የዝምድና አኳኋን በአለውጥሬ ተጠርተው ደስ በሚአሰኝ ቦታ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋራ በመዋላቸው እጅግ ደስ ብሏቸዋል። እውነት ነው ። ንጉሠ ነገሥቱ ከቤተ ዘመዶቻቸው ጋራ ዕረፍት በአደረጉበት ጊዜ ከቤተ ዘመዶቻቸው ጋራ በመቈጠራቸው ይህችን ቀን የፍቅር መታሰቢያ መሆኑዋን አይዘነጉትምና በአርእስቱ ታላቅ መታሰቢያ ያለው ቀን ብለን መጻፋችን ስለዚህ ነው ።

ማስታወቂያ ።

መንገሻ ገብረ ማርያም የሚባል ወጣት ጉበዝ የመስቀል ዕለት የክብር ዘበኞች ደስ ስለአሉት ታሪካቸውን ጽፎ ብብርሃንና ሰላም ሲአሳትም ደግሞ ደስ ያሰኘውን ከኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር የፈለገውን ያህል አወጣጥቶ ሌላም ጨምሮ ነበርና የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ተለውጧልን ወይስ በምን ምክንያት ነው ይህ የታተመው ብለው ሙሴ ናልባድያን ስለጠየቁ እሱ እንደሐሰበ ከጻፈው ላይ የፈለገውን ያህል ጠቃቀሰለት እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር አለመለወጡን እናስታውቃለን ።የመዝሙሩም ቃል ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ኢትዮጵያ ሆይ ደስ ይበልሽ። በአምላክሽ ኃይል በንጉሥሽ ። ተባብረዋል አርበኞችሽ ። አይነካም ከቶ ነፃነትሽ ። ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ። አትፈሪም ከጠላቶችሽ።ድል አድራጊው ንጉሣችን። ይኑርልን ለክብራችን።



አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ።

ስለ አቶ ገብረ ክርስቶስ ሞት ።

አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ገና በልጅነታቸው እተማሪ ቤት ገብተው የኢጣልያ ቋንቋ ተምረው ፡መጽሐፍ ቅዱስ መምህር ሁነው በአስመራ ከተማ ይኖሩ ነበር ። ደጃዝማች ነሲቡ የአስመራ ቆንስል በነበሩ ጊዜ ለኢትዮጵያ ተቈርቋሪ ስለ ነበሩ ገሥግሠው ወደ አዲስ አበባ መጡ ። በ፲፱፻፲፬ ዓመተ ምሕረት በላይኛው ጣቢ የማኅተም መኪና በመጣ ጊዜ ወደ መንግሥት ሥራ ገቡ ። በሥራቸውም እጅግ ትጉህ ስለሆኑ ሥራቸው እየተቃና ሔደ። በእምነትና በትጋት ስላገለገሏቸው ጃን ሆይ አልጋ ወራሽ በነበሩ ጊዜ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ዲሬክቴር ሾሟቸው ። መቸም ይህች ዓለም የእንግድነታችን እንጂ የመኖሪያ ርስታችን ስለአልሆነች በድንገተኛ ሕማም ሦስት ቀን በቤታቸው ታመው በቤተ ሣይዳም ሆፒታል በተኙ በ፮ኛው ቀን በጥቅምት ፲ ቀን በዚሁ በቤተ ሣይዳ ሆፒታል ሞቱ በማግሥቱ በጥቅምት ፲፩ ቀን ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር እጅግ ብዙ ሕዝብም ተሰብስበው አልቅሰውላቸው በጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበሩ።ዕድሜአቸውም ፴፱ ዓመት ነው ።

አቶ ገብረ ክርስቶስስ ሥራቸውን ሠርተው ተመስግነዋል።እጅግ የሚአሳዝኑ ባለቤታቸውና ልጆቻቸው ናቸውና ብርሃንና ሰላም እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ኀዘኑን ይገልጻል። የቅኔውም ባለቤት አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ስለኀዘኑ ዕናት የሚከተለውን ቅኔ ጻፈላቸው።

ሥላሴ ።

ብከዩ ላዕሌኪ ፥ ኢየሩሳሌም ቤተ ማኅተም
እስመ ገብረ ክርስቶስ ንጉሥ ዘአምኖ፥በላዕለ ኵሎን ግብራት
ጌጋየ በኢያአምሮ ተቀንየ ለሞት ።
ወለቤተ ማኅተም እንከ፥ ይቄስፆ ዎ በምንት ።
እስመ ለስሐ ብኑ በሞተ ጣብት ።
ጣዕመ ገብረ ክርስቶስ ጥዑም ሄወ ጥበባት ።
ዘአጥዐሞ ለልሱሕ ኪነት ።

የአቶ ገብረ ክርስቶስ የሕይወት ታሪክ።

አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት በሐምሌ ወር በ፲፰፻፹፱ ዓ ም በሐማሴን ውሥጥ አባታቸው አስተማሪ ሁነው ይኖሩባት በነበሩ ወኪ በምትባል አገር ተወለዱ። ዕድሜአቸውም ለትምህርት ከበቃ በኋላ አስመራ ላይ ባለው በሽዊድን ሚስዮን ትምህርት ቤት አደጉ። የ፳፮ ዓመት ሰው ሲሆኑም ሲማሩበት በነበሩ ትምህርት ቤት ለአስተማሪነት ተመረጡና ሥራ ጀመሩ። በ፲፱፻፰ ዓ ም የካቲት ፲፫ ቀን በሕግ ወይዘሮ ይኅደጋን አገቡ።

ያስተምሩበት በነበሩ ትምህርት ቤትም በትጋታቸውና በረዳትነታቸው በጣም ተመሰገኑ ። ከዚያ በኋላም የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በሚውለበለብባት ንጉሠ ነገሥት በሚኖርባት በልዩ ልዩ ሥራ ያሉ ሚኒስትሮችና ክቡራን መኳንንት ለነፃነታቸውና ለተወደደች አገራቸው ደማቸውን ለማፍሰስ የተሰናዱ የኢትዮጵያ አርበኞች የሚታዩባት አዲስ አበባን ለማየትና በርስዋም ውሥጥ ለመኖር ስለጐመጁ የተወደደ የሕግ ሚስታቸውንና ልጆቻቸውን ትተው ከሥራ ለመሰናበትም ሳይመቻቸው ቀርቶ እንዲያው ተነሥተው በዓድዋ በመቀሌና በወሎ በኵል ባለው መንገድ ወደ አዲስ አበባ ገቡ።

ወይዘሮ ይኅደጋም ልጆቻቸውን ይዘው የርሳቸውና የባለቤታቸው አገር ስለ ሆነ ካስመራ ወደ አኵስም ተሻግረው ነበሩና እንደገና አቶ ገብረ ክርስቶስ ካዲስ አበባ በጐጃም በበጌምድርና በጸለምት በኩል አድርገው አኵስም ገብተው ባለቤታቸውን ይዘው መጀመርያ በመጡበት መንገድ ወደአዲስ አበባ ተመልሰው ገቡ።በሚስዮን ሥራም አንድ ዓመት ያህል እንደ ተቀመጡ የመንግሥትን ሥራ ያዙ ወደ ማተሚያ ቤቱ እንዳንድ አጋዥ ሠራተኛ ገብተው ሥራውን ማወቃቸውንና ትጋታቸውን አይተው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የማተሚያ ቤቱን ዲሬክተርነት ሾሙዋቸው። ሥራውም እጅግ ተስፋፋ የታተሙና ያልታተሙ አያሌ መጻሕፍትም ጻፉ በሥራቸው ላይም ብርሃንና ሰላምን ጋዜጣ ጀምረው ብዙ ዘመናት

ሕስኬዱት ይህም ለዘላለም መታሰቢያቸው ነው ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም በየጊዜው ብዙ ሽልማትና ሦስት ልሻን ተሸለሙ። ከሥራቸው ሁሉ የሚበልጠውም ያገኙትን እውቀት ሁሉ ሠራተኞቹ እንዲያውቁትና የሌሉ ጊዜም ሥራው ያለ ሁኖ እንዲኖር ጣሩ። ከሠራተኞችም ብዙዎቹ እንደ አስተማሪያቸው ሆኑ። የእውነተኛው ያገር ልጅ ሥራ እንደዚህ ነው።

ከሌላ በብዙ ዘመናት የማይገኘውን እውቀት ለብዙ ወንድሞቻቸው በጥቂት ጊዜ አስረከቡ ። በዚሁም ላይ በትጋታቸውና ሰዓትን በመጠበቃቸው ጊዜን በማክበራቸው አብነት ሆኑ ። አዲስ አበባ ላይም በ፲፱፻፲፭ ዓ ም እናትህ ሙተዋል ብለው ቢያረዱዋቸው አንድ ቀን እቤት ሳይውሉ ወደ ሥራቸው ስለ ሔዱ ሊጠይቋቸው የመጡ ሰዎች አጥተዋቸው በመመለሳቸው የሚያደንቁ ብዙ ናቸው። በ፲፱፻፳፬ ዓ ም አባታቸው ሙተዋል የሚል የስልክ ቃል አግኝተን ልናረዳቸው ሔደን ጥቂት ደቂቃ አልቆሰው እኔ እዚሁ ብቀር ብዙ ሰዎች ሥራ እንዳይፈቱ ሲሉ እኛን እያለቀስን ትተውን ሔደው የጐደለውን ሞልተው የተከፈተውን ዘግተው ተመለሱ ። አብዝተው ሥራውን ለማስፋፋት ከጨረሱ በኋላ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁኖ የዘሩት እንዳበበ የመከሩ ጊዜ ሳይደርስ ባላሰቡበት ቀን ድንገት በብርቱ ትኩሳት ታመው በቤት ማይዳ ተኝተው ነበሩና በታመሙ በዘጠኝ ቀናቸው ጥቅምት ፲ ቀን በ፱ ሰዓት አረፉ ። በሚቀበሩበት ጥቅምት ፲፩ ቀን የኢትዮጵያ መኳንንትና ሚኒስትሮች ወይዛዝሮችም ወዳጆቻቸውም ሁሉ ኀዘናቸውን እያሳዩ በብዙ ክብር በጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ።

ክፍለ እግዚእ ደኅደን።

፲፱፻፳፬ ዓ ም ጳጉሜን ፭ ቀን ስለ ሐረር ከተማ መሻሻል ።

ሐረር ጥንት ከተማ መሆኑዋን ማንም አይስተውም በዳግማዊ ምኒልክና በልዑል ራስ መኰንን ጊዜ በእግዚአብሔር እርዳታ ተቀናች እንሥቶ ለጤና የተስማማች ነች ። ነገር ግን በከተማዋ ብዛትና በቤቱም መጠጋጋት የተነሣ ለወስላታና ለሌላም ትመች ነበረች አሁን ግን የሐረር ማዘጋጃ ቤት ሹም ክቡር ግራዝማች ዓዘው ከተማ ይኸን ስለተረዱት መንገዱንም በከተማ ውሥጥ ካሚዮንና አቶሞቢል እንደሚያስኬድ ለማድረግ ተነስተዋል ተመሸም በኋላ ሰው ያለፋኖስና መብራት እንዳይሔድ ከልክለዋል ። ይኸውም ወስላታን ለማጥፋት ብርሃን ለመግለጽ መሆኑን ያስረዳል ። ይልቁንም በተሾሙበ፬ ወራቸው ብዙ ወስላቶችና ሌቦች እየመረመሩ አስይዘው ወደ ታላቁ ፍርድ ችሎት ወደ አገረ ገዢው ወደ ደጃዝማች ገብረ ማርያም ችሎት ማቅረባቸውን ላየው ሰው በጣሙን ያስደንቃል ወይ ጉድ የከተማ ልጅ በከተማ ሲሾም ምንኛ ደስ ይላል የትጋታቸውን ፍጻሜ ያሳየኝ ስል ምኞቴን ባለማቋረጥ እገልጻለሁ ።

የሐረር ማዘጋጃ ቤት ፍርድ ጸሐፊ መምሬ ይገዙ ፈለቀ።

ለሀገር ስለ መቁርቁር ።

ክቡራን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል እንደሚባል እኛም በምናየውና ልብ አድርገን በምንመለከተው ሁሉ ምንስ በትልቅ ማዕርግና ደረጃ ብንደርስ ሰው እንዳቅሙ እህል እንደቀርሙ ነውና አሁንም እኔ ያቅሜን ያህል የመሰለኝን ለመጻፍ ያሳሰበኝ ይህ ነው ፤ አቶ ማርቆስ የሚባሉ በፖርት ሳዒድ የሚኖሩት ወንድማችን በብርሃንና ሰላም በ፰ኛ ዓመት በቍጥር ፴፰ መስከረም ፭ ቀን ስለ ሁለት የኢትዮጵያ ልጆች ወደ ግብፅ አገር ሔደው በብዙ ችግር ሲጐሳሉ ከንዱ ወዳንዱ አገር ሲንከራተቱ በዘበኛ ተይዘው ከገር እንዲወጡ የተባለውን ነገር ሳነብ የነዚህን መከረኞች ችግር ባሰበው በጣም አሳዘነኝ ። እኒህ ወንድሞቻችን ካገራቸው ሲወጡ የሚደርስባቸውን መጉላላት ሳያስቡ ምናልባት ትምህርት ፈልገው ሔደው ተም/ን ራሳችንን ችለን ወንድሞቻችንን ረድተን እንኖራለን ብለው አስበው ይሆናል።ነገር ግን ያሰበው በፍጹም የሚከናወንለት ከሰር አንድ አይሆንም።እኔም ይህንን ነገር በልቤ ውሥጥ ሲገባ ሲወጣ የነበረውን ሐሳብ ለመጻፍ አሳሰበኝ ምነው ሰው ካያሌ ዓመታት ጀምሮ በቤቱ የፈቀደውንና የወደደውን ሊያስገባ የጠላውንና የማይሰማማውን ሊያስወጣ ምሉ ሥልጣን አለው ። ስለዚህ የምስር መንግሥት ስላገሩ ጥቅም ባቆመው አዲስ ደንብ ዘበኞቹን አዝዞ የወደደውን ቢያስገባ የጠላውን ቢያስወጣ ያገሩንም በረከትና ሥራ ባዕዶችን እያስከለከለ ላገሩ ሕዝብ ጠቀሜታ ብቻ ቢጫስን ያስመሰግነዋል እንጂ አያስነቅፈውም ።

ረዳ ጻድቅ ።

መወድስ ።

በመጠነ ፀሐይ ወወርኃ ብርሃናተ ራማ፡ ኵለሄ ታበርህ ሀገረ ምኒልክ ኢትዮጵያ ።
እኮኑ ትኔጽር ማኅቶተ ጥበብ ነያ ።
በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘነግሠ በገነተ ጽጌ ከዊኖ ዕበያ።
እስከነ በአማን ይትኄሠያ ።
ኵሎን አህጉር፥ አዋልደ ግብፅ ወዕርያ ።
ዕበ ነሥአሂ በትረ ዳዊት፥ ወበትረ ሲራክ ኬንያ ።
ደንገፀ አርዌ ምድር ወተሀውከ ሐራውያ ።
ወኃይለ ሥላሴ ተከሥተ በዘሰሎሞን አርአያ ።
መሠረተ ጽድቅ ተፋቅሮ እስከነ ታፀንዕ ሰማርያ ።

መወድስ ።

ማዕረረ ትርጓሜኪ በጽሐ በኃይለ ሥላሴ ፤ ሠርፀ ንባብኪ ቅድመ እመ በምኒልክ በቈለ ።
ወሥርወ ጥበብኪ ወይን፥ በኃይለ ሥላሴ ተተክለ ።
ዓለመ እስከ አስተፍሥሐ ወኵሎ አብፀለ ።
አዲስ አበባ ገራህተ ጽድቅ፥በሐውያትኪ ሰብአ ዘኢተሐፅዒ መዋዕለ ።
ብርሃንሂ መዋዕልኪ ዘያስተፌሥሕ አሕባለ ።
ጽልመተ ኢያእምሮ ፍጹመ አሰሰለ ።
ወቅድመ መኰንን ዳዊት፥ ለእመ እግዚኡ መሐለ ።
ንጉሥኪ ኃይለ ሥላሴ በመንበረ ዳዊት ተለዐለ ።

ሰሎሞን በተወለደበት ወራት

ዘመኑ ዘመነ ሰላም ሁኖ ጥበብና እውቀት ሰፋ (መዝሙር ፸፪ቍጥር ፯) በዘመኑ እውቀትና ጥበብ ለመለመ ዓዘ-

መን ምሉ ፍቅርና ሰላም ሆነ። ቍጥር ፲፮፡ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ ለፍጥረቱ ሁሉ አምባ መጠጊያ ሆነ ጥበቡና ድርሰቱ ከዛፍ ፍሬ ከሶድር ማዕር በዛ ። ዛሬም ምግባር ሃይማኖቷ የፀና ኢትዮጵያ መጻሕፍትን በየክፍላቸው፥ጥበብና ዕውቀትን በየስልታቸው ልትገልጽ ፈቃድዋ ቢሆን እጅዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ ብርሃኑዋን ኃይለ ሥላሴን ተቀበለች።ኃይሏ ብርሃኑዋ ኃይለ ሥላሴም (መዝሙር ፷፯ ቍጥር ፴፩) ወርቅ ብር ባእሳት እንዲፈተን በምግባር በሃይማኖት የተፈተኑ ወገኖቿ በጠላት እጅ እንዳይወድቁ የቀርከሀ እባብ ጠላቶቿን አጠፋላት በበትረ መንግሥቱ ገላለጻላት ።

ቀኝ ጌታ ተክለ ሚካኤል ዘገነተ ጽጌ
መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ።



አብርሃም ባራኪ ዘብሔረ ሐማሴን ።

የሚያሳዝን ሞት ።

አብርሃም ባራኪ የሚባል የሐማሴን ተወላጅ የክቡር ደጃዝማች ነሲቡ አሽከር ነበር ። ታማኝነቱን ስለተረዱት በጥንቃቄ እንዲሠራላቸውና ከግዛታቸው ውሥጥ ሁኖ ገንዘባቸውን እንዲተሳሰብላቸው በግዛታቸው አገር ላለው ገንዘባቸው ሁሉ ተቈጣጣሪ አድርገዉት ነበርና እርሱም ጌታዬ ቢገቡልኝ ሚስቴንና ልጆቼን አስመጥቼ በደስታ እኖራለሁ፣ እያለ በሥራው የታመነ ሁኖ ሲሠራ ከንድ ከተማ ገበያ አድሮ ወደሚኖርበት አገር ሲሔድ ከቀኑ በ፰ ሰዓት ጠላቶች በመንገድ አድብተው ቈይተው ሮምታ ተኵሰውበት በ፫ ጥይት ቈስሎ ወደቀ ። ወዲያው እንደወደቀ ሊገፉት ሲመጡ ከገዳዮቹ አንዱን በሽጉጥ አቍስሎ ሞተ የሚል የስልክ ቃል ሰምተን አዘን ። ይልቁንም የሞተበት ምክንያት ስላልታወቀና ደመኞቹን የሚፈላለጉለት ጌታው ወደ ውጭ አገር በተላኩበት ወራት ስለሆነ የወገኖቹና የተወላጆቹ ኃዘን ከልክ ያለፈ ሆነ ። ነገር ግን ምንም ቢያዝኑ የሞተው አይመለስምና ኃዘንተኞችን እግዚአብሔር ያጥናቸው። ዕድሜውም ፴፱ ዓመት ነበር ።

ተ ሚ ኃ ።

ማስታወቂያ

የራስ ኃይሉን ገንዘብ በፍርድ መንግሥት ስለወረሰው በራስ ኃይሉ ላይ ገንዘብ አለኝ ስለሚለው ሰው ሁሉ በኮሚሲዮን የሚያዩ ሰዎች ታዘዋልና በመስከረም ፲፱ ቀን በጋዜጣ እንዳስታወቅነው እስከ ተወሰነው ቀን ድረስ ጉለሌ ራስ ኃይሉ ቤት ማስረጃችሁን ለልጅ ውብሸት ወልደ ዮሐንስ እንድታቀርቡ ይሁን ።

የገንዘብ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር።

AVIS AU PUBLIC

En vertu d'un jugement rendu, les biens du Ras Haïlou étant confisqués par le Gouvernement, nous avions informé Messieurs les Créanciers du Ras Haïlou, qu'il a été nommé une commission chargée d'examiner les diverses réclamations.

Tout créancier est tenu de présenter les pièces justificatives qu'il détient à Lidje Woubechét Woldé Johannés se trouvant à Goullalé, immeuble du Ras Haylou. La présentation des pièces justificatives sera valable dans le délai prévu à lavis publié le 19 Meskaram.

Signé : Balambaras Achénie
Directeur Génerel des finances

የካህናት ሹም ሽር

መምህር ጽጌ የአዲስ አበባ ቅዱስ ገብርኤልን አለቅነት ተሾሙ ።

አለቃ ገብረ አጋእዝት የደብረ በግዕን አለቅነት ተሾሙ

መምህር በላይ የዑራኤልን አለቅነት ተሾሙ ።

መምህር እርገጤ የአንኮበር ቅደስ ሚካኤልን አለቅነት ተሾሙ ።

ሹመት ያዳብር እያለ ብርሃንና ሰላም ደስታውን ይገልጻል ።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ ጊዜ እንዳስታወቀው የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ዕዳዎችን በታ ጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል።

የክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደውን ሁለት በታ አጥቢያው ሩፋኤልና ቁርቆስ ስፋቱ ፯፻ ሜትር ካሬና ፹፰ሺ. ፯፻፳፱ ሜትር ካሬ።

የፊታውራሪ በዳኔ አሻግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፱፻፲ና ፲ሺ.፯፻፺፩ ሜትር ካሬ።

የነጋድራስ ተፈራ ንጉሤ አጥቢያው ቁርቆስ ስፋቱ ፯ሺ. ፫፻፹ ሜትር ካሬ።

የቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ አጥቢያው አማኑኤል ስፋቱ ፳፱ሺ. ፳፱ ሜትር ካሬ።

ያቶ ወንድማገኘሁ በዛብህ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፫፻፴፯ ሜትር ካሬ ። ሺያጩም የሚደረገው በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በርበት ክፍል ቢሮ ነው።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሴጊያን ዘንድ ይገኛል ። ይህነኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተኩል ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

የሚሸጥ በታ

ማጀስቲክ ሆቴል አጠገብ ከሙሴ ሃርዲ ፊት ለፊት መሐመድአሊ ከሠራው አዲስ ሮቅ በታች ጥሩ ጥሩ ቤት የተሠራበት በወሩ እስከ መቶ ብር ድረስ ኪራይ የሚያመጣ ጥሩ የሚሸጥ በታ አለና የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ አቡጀዲድ ገበያ ላይ ወችራጀ የሚባል ሂንዲን ጠይቁ።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

ፋርማሲ ሣንትራል ተናግሮት የነበረውን በገዛ ዓይንዎ አይተው ስለተረዱት በጣም ደስ አለኝ ፤ መጥተው ስለተረዱ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ወደፊትም እየመጡ እንዲሁ እንዲረዱልኝ እመኛለሁ ።

እንደ ተባባልነው ስለ መልክዎ ጥንቃቄ አሁን ጥቂት እመክርዎታለሁ ።

የመልክን ቆዳ ስለሚአበላሹ በሺታዎች የተቀመሙትን ሳሙናዎች ሲወስዱ መልክም ሆኖ በረቂቅ ሺታ የተሰናዳውን የውበት ሳሙና ይውሰዱ ። ፊትዎን እልፍ አልፍ ጭረት ስለሚአደርገው በሺታ ኤፊሊን የሚባለውን መድኃኒታችንን እንዲአደርጉ አጥብቀን እንመክርዎታለን ። በጥቂት ቀን ደህና እንዲሆኑ ዮኸንን መድኃኒት ማድረግ ነው። እስከሁን ድረስ እሱን የሚተካ ሌላ መድኃኒት አልተገኘም ።

በፊትዎ ላይ ስለሚአደርጉት የሽቶ ዱቄት ወዝ ለሌለው መልክ«ኮልድ ክሬም»የምንለው መድኃኒታችን መልክም ነው፤ወዝ ላለው ፊት ግን«ሌቢርሄናል» የሚባለው መድኃኒታችን ነው የሚሻለው ስል እመክርዎታለሁ ።

ደግሞ በያይነቱ የተሰናዳውን የሩዝ ዱቄት ሺቶ «የሎቲዮ»ሆነ«የፒቤርትም»ሆነ ሌላም በያይነቱ ለማየትና ለመምረጥ ይችላሉ፤ እንዲሁም ለከንፈር ቀለም የሚሆን እርሳስ ባያይነቱ አለኝ ዘወትርም ስለ እሚታሹበት አዲኮሎኝ ዮልቁንም ከድካም ባረፉ ጊዜ የሚታሹበትን ከኔ ዘንድ እንዲወስዱ እምናለሁ በዚሁ በፋርማሲአችን ውስጥ ለፊትና ለገላ ማሻ የላስቲክም ሆነ የውነተኛውም ኤፓንገር ሆነ አለን ብለን አስታውቀንዎታልና ሁለተኛ መናገር ያስፈልግ አይመስለኝም ።

ደግሞም በያይነቱ በእውቀት ጥበብ ስለሚመረመር ነገርና ስለ መንገድ መድኃኒት ማሰናዳት በልዩ ማወቄን እንዳይረሱ አስታውሳለሁ እገልጋይዎ ኤም ማትማኪስ ።

በዚሁም መድኃኒት ቤት የፈረንሳይ ፤ የእንግሊዝ ፤ የጣሊያን ፤ የዓረብ ቋንቋ ይናገራሉ ።

አበማልተን
ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

አበማልተን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው። አበማልተን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል አበማልተን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፥ ቤርን ናቸው። በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው።

አበማልተን አዲስ አበባ ባሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ማጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት

ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
የቅዱ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፭	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲	ብር
፫ቱ መጻሕፍተ መነኮሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪	ብር
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪	ብር
ዶስታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፱	ብር
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
የዓለም ጂዮግራፊ ከነካርታው	፯	ብር
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፯	ብር
ድርሳነ ሚካኤል	፮	ብር
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር
ኅሀ ጽባሕ	፭	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪	ብር ፶መ
የእርሻ ትምህርት	፩	ብር ፶መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ እጅግ ያማረ	፪	ብር
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
የቍጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩	ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የነፃ ደንብ ከነተጨማሪው	፩	ብር ፶መ
የብድር ደንብ	፩	ብር
የጦር መማሪያ ደንብ አዲስ	፩	ብር ፶መ
የገዳም ደንብ	፩	ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩	ብር
ዮሐንስ ቡንያን	፩	ብር
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፭	ብር
የ፪ኛ	፳	ብር
የ፫ኛ	፲፭	ብር
የ፬ኛ	፲	ብር
የ፭ ኛ	፯	ብር
የ፮ኛ	፯	ብር
የ፯ኛ	፯	ብር
፳፬ ካርት ፖስታል	፩	ብር
የረከማንዴ ደብተር	፫	ብር
ሕገ መንግሥት	፭	ብር
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፶	መሐ
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንነገ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፶	መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፶	መሐ
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተሰማማ	፶	መሐ
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፶	መሐ
ያማርኛ ምሳሌ	፶	መሐ
አሳብና ምኞት	፴	መሐ
የፍቅር መላክት	፴	መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፴	መሐ
የምሕረት አዋጅ	፴	መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፳	መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፳	መሐ
የንቍጣጣሽ ግጥም	፳	መሐ
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፳	መሐ
፩ ጋዜጣ	፳	መሐ
አርስጣላብ	፴	መሐ
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፴	መሐ
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፴	መሐ
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፭	መሐ
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፭	መሐ
ካላንድሬ	፶	መሐ
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪ	፭	መሐ
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፶	መሐ
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፴	መሐ

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት እጥፍ ። ነጠላ በያይነቱ ። እርሳስ መንኰልና ብረት ብርዕ ቀለም በያይነቱ። የካርት ቢዚት እንበልብና ካርት ቢዚት በያይነቱ ። እንበልብ ትልቅና ትንሽ በያይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኀኒት ቤት በያይነቱ መድኀኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኀኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት የጉበት ፥ የኩላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቍቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ኀርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሡ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋናታኪስ ወከሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዶች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመኀብኝት ።

ማስታወቂያ ።

እስከ መስቀል ድረስ አንድ የቤተ ሰብ መኪና የገዛ ሰው ደህና ሽልማት ያገኛል ።

በርቱ ይኸ እድል አያምልጣችሁ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን (ሱዊስ) በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ቁ ፤ ፳፱ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፵፭
8me ANNE. № 45

ሐሙስ ጥቅምት ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 3 Novembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ በጸሐፊነቱ በአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ፡ መጣፊት ለፊደገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሁለተኛው ዓመት የዘውድ በዓል አከባበር ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥቱን አልጋ በወረሱ በስምንተኛው ወር የሮፓን ነገሥታትና የኢትዮጵያን መሳፍንት ጠርተው በጥቅምት ፳፫ ቀን ታላቅ በዓል አድርገው የንጉሠ ነገሥቱን ዘውድ የጫኑበት፤ ግርማዊት እቴጌ መነንም የእቴጌነታቸውን ዘውድ የጫኑበት በዚሁ በጥቅምት ፳፫ ቀን ስለሆነ በየዓመቱ እንዲከበር ተደርጓልና ዘንድሮም በዓምናው ልማድ በዚሁ ቀን ታላቅ ክብር ተደረገ። አኳኋኑንም በሚከተለው መስመር ታገኙታላችሁ ።

፩ኛ፤ ለዘውዱ በዓል የተደረገው አከባበርና አቀባበል፤ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን እንሥቶ የኢትዮጵያ የጦር አለቆች ሠራዊቱን ሰብስበው ከጧቱ ባ፩ ሰዓት በመንገዱ ግራና ቀኝ በየተሰጣቸው ቦታ ክፍል አሰልፈው ቆሙ ። የክብር ዘበኞችም ከቤተ መንግሥቱ እንሥቶ እተወሰነላቸው ቦታ ድረስ እንደዚሁ ቆሙ ። ከክብር ዘበኞችም ቀጥለው የከተማ ዘበኞች ቆሙ።

በ፪ ሰዓት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊት እቴጌ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሒደው ለዘውዳቸው በዓል ዓመት ላደረሳቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርበው ወደቤተ መንግሥቱ ተመለሱ ።

፪ተኛ ፤ ስለ ዘውዱም በዓል የተደረገው አቀባበል በቤተ መንግሥቱ ከ፬ት ጀምሮ ፭ ሰዓት ተኩል እስቲሆን ድረስ የኢትዮጵያን መሳፍንትና መኳንንት፤የውጭ አገር ሚኒስትሮችንና ቆንስሎችን በከተማው ያሉትንም ታላላቆች ሰዎች ለዚህ በዓል በተለየ የተጠሩትን ተቀበሉ ።

፫ተኛ፤የሕግ መወሰኛና መምሪያ አማካሪዎች ወደቤተ መንግሥቱ በ፭ ሰዓት ተሩብ መጥተው በተዘጋጀላቸው ስፍራ ቆዩ።

ሊቀጳጳሳቱም የኢትዮጵያ መኳንንቶችም በዚሁ ሰዓት መጥተው በተዘጋጀላቸው ቦታ ቆዩ ።

ባ፭ ሰዓት ተኩል የሕግ መወሰኛና መምሪያ ምክር ቤት አማካሪዎች ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው በተዘጋጀላቸው ስፍራ ተቀመጡ ።

ከዚህ ቀጥሎ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ።

በእግዚአብሔር ቸርነት ላገራችን ለኢትዮጵያ ልማት ለሕዝባችን ሥልጣኔና ብልጥግና እንዲሆን አስበን ያቆምነውን ሕገ መንግሥት ተከትላችሁ ባለፈው ዓመት በሕግ መምሪያና በሕግ መወሰኛ በሕጉ ማስፈጸሚያ ምክር ቤት የሠራችሁትን ሥራ ብንገምተው ፍሬ የሚገኝበት መሆኑን ስለተረዳነው ስለዚህ ደስታችንን እንገልጽላችኋለን ደግሞ የተዘራ ሁሉ አይበቅልም።መቸውንም ቢሆን ለመንግሥት ሁለት ኃይል ያስፈልገዋል ፡ አንደኛው እስካሁን በአገራችን በኢትዮጵያ እንደ ተለመደው የጦር ኃይል ነው ።

ሁለተኛውም የፍቅር ኃይል ነው ። ነገር ግን ባገር ውስጥ ዘወትር የጦር ኃይል ማድረግ ደም እያፈሰሰ የሕዝብን ቁጥር እያሳነሰ የሚሔድ ስለሆነ ላገር ውስጥ ከጦር ኃይል ይልቅ የፍቅር ኃይል የሚሻል መሆኑን ስለተረዳነው ዋናው ሥራ እየተመከረበት እንዲሠራ ፈቅደን ሕገ መንግሥት አቆምን።

በዚህም ባለፈው ዓመት እንደ ሕገ መንግሥቱ ቃል በምክር ቤቶች በሠራችሁት ሥራ ፍሬ ነገር ስለ አገኘንበት ዛሬም የሁለተኛውን ዓመት ምክር ለመክፈት ስንፈቅድ ደስ ይለናል።

ወደፊትም ገበሬ በርሻውና በግብሩ ነጋዴ በንግዱና በቀረጡ ወታደር በሰልፉና በማደሪያው ደስ ብሎት የሚኖርበትን የኢትዮጵያም ነፃነት ተጠብቆ የሚኖርበትን፤ ትምህርት የሚሰፋበትን ፤ ፍርድ የሚተካከልበትን ፤ ይህንም የመሰለውን ሁሉ በትጋት እንድትሠሩና ካለፈው ዓመት አብልጣችሁ የሥራ ፍሬ እንድታሳዩን ተስፋ በማድረግ እምነታችንን በላያችሁ አድርገን አደራ እንላችኋለን። ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም።

ከዚህ ቀጥሎ የሕግ መወሰኛ ፕሬዚዳን ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ ጃንሆይ የምክር ቤቱ እንዲከፈት ስለመፍቀዳቸው የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ግርማዊ ሆይ።

ለኢትዮጵያ ልማት ለሕዝብዎ ሥልጣኔና ሀብት እንዲሆን አስበው ያደረጉት ውለታ ከሁሉ የበለጠ ነው። ይኸውም

፭ኛ፤ ለዚሁ ቀን ከማታው በሁለት ሰዓት የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት፤ የውጭም አገር የዲፕሎማቲክ ሚኒስትሮች ወይዛዝሮችም ራት ተጋበዙ ።

ከራትም በኋላ ለሲሬ የተጠሩት በከተማው ያሉ ታላላቅ ሰዎች በ፬ሰዓት መጡ ።

የንጉሡ በዓል ሲኒማና ወደ ሰማይ እየተወረወረ የሚተኰስ ፊደአርቲፌስ ታየ ።

፮ኛ፤ጥቅምት ፳፬ቀን ሐሙስ በተለየ ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ለምክር ቤቱም አማካሪዎች ለጦር አለቆችና ለሠራዊቱም ሁሉ ታላቅ ግብር ተደረገ ።

ምንም ቢጠም መንገድ፥ ምንም ቢጠሉት ዘመድ።

ብዙ ሰዎች ከሀገራቸው ሰው ወደ ውጭ አገር ሰው ፍቅራቸው የሚያዘነብል እምነታቸው የሚስፋፋ የሀገራችንን ሰው የሚያሳንሱ እነዚያን የሚያከብሩ ለሀገራቸው ሕዝብ ክብረትን የማይወዱ አይታጡም ይመስለኛል። እንደምን ማለት አንድ የኢትዮጵያ ሰው ልዩ ልዩ ሸቀጦች ለንግድ አስመጥቶ ወይም በእጁ በሠራቸው ንግድ ቢያቆም እነዚህንም ሸቀጦች ዋጋቸውን የውጭ አገር ነጋዴዎች ከሚሸጡበት በጣም አሳንሶ ለመሸጥ ቢያስብ ያገራችን ሰው ምንም ቢሆን እሱ ዘንድ ገብቶ ለመግዛት የሚያስብ ይኖር አይመስለኝም። ይህም ብቻ ሳይሆን ምንም ያገራችን ሰው የሠራውን ነገር ከመናቅ ከማኰሰስና ከማዋረድ በተቀር ለሠራቸው ልዩ ልዩ ሥራዎች የሚገባው ምስጋና ስለአጣ እነዚህኑ ሠራተኞች ስንፍና የሚባል ትልቅ ባለጋራ ሊተናነቃቸው ጀምሮአል እነሱም ረዳት ስለአጡ ሳይሸነፉ ይቀሩ አይመስለኝም። እንግዲያማ ለሀገራችን ሕዝብ ዕውቀት ምን አንድና ሁለት ነበረው ፥ አሁን ከብዙ ሠራተኞች ማረሻ፥ ወገል፥ ዶማ፥ መጥረቢያ፥ ቢላዎ እነዚህንም የመሰሉ ሁሉ እየሠሩ ከሀገራችን ሰው የሚገዛቸው ቢያጡ ለውጭ ሀገር ነጋዴዎች እከተማ ድረስ አምጥተው ይሸጣሉ። ደግሞም አንዳንዶቹ በገበያ ቀን እገበያ የሚሸጥልን እየመሰላቸው ቢያመጡ ሕዝቡ ከዚያው ከውጭ አገር ነጋዴ በተቀር ከአገሬ ሰው ልግዛ ብሎ አያስብም።

ከቡራን የኢትዮጵያ ተወላጆች ሆይ ፥ እኛ በሠራነው የውጭ ሀገር ሰው ሲያስተርፍበት እንዴት የሚያሳዝን ነው። እንደኔማ ቢሆን ከውጭ አገር ሰው ይልቅ ያገራችንን ሰው ማክበር የተገባ ይመስለኛል። ዳግም አንድ ሳይበል ሁለት ወይም ሦስት ለማለት የማይቻል ነውና በዚሁ በሀገራችን ውሥጥ ከዚህ ቀድሞ በሚሠሩት ልዩ ልዩ ሥራዎች ሠራተኞቹን ቢያበረታቷቸው ብዙ ዓይነት ሊሠሩ ይችሉ ነበር። አሁን ለምሳሌ የውጭ አገር ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ዕቃ ለመግዛት ወይም ወደ ቡና ቤት ለመግባት ቢያስቡ ወደ ዚያው ወደ ሀገራቸው ሰው ዘንድ ይሔዳሉ እንጂ የሀገራቸው ተወላጅ ወደማይሆነሰው ዘንድ ሒደው ለመግዛት ፈጽመው አያስቡም። ይኸውም ሁለት ነገር ያስረዳል። መጀመሪያ ገንዘባችን እሌላ እባዕድ ሰው ዘንድ ከሚገባ አገራችን ሰው ዘንድ ቢገባ ይሻላል በማለት፤ሁለተኛ የሀገር ፍቅር በልባቸው እለተቀረጸባቸው ያስረዳል።

ይልቁንም ይህን ቃል ለመጻፍ ያሳሰበኝ በጐሬ አንድ ቱጃር የሆነ ፈረንጅ ነበር ብዙም የሀገራችን ሰዎች ገንዘባቸውን አስቀምጠውበት ነበረ ። ገንዘቡም ከስልሳ ሺሕ የሚበልጥ ነው ይኸውም ፈረንጅ የንግድ ገንዘብ አነስ ቢልበት ከሰርሁ ብሎ ስለሔደ ብዙ ሰዎች ያለቅሳሉ ነገር ግን ለነዚህ ሰዎች ምንም ሊታዘንላቸው አይገባም እንደ ምን ማለት የታመነ ማስቀመጫ ባንክ ነበረ ። ደግሞም ይህ ቀርቶ እንደ ዱሮው ልማድ ከዚያው ከፈሩ ቢያገናኙት በፈለጉት ጊዜ አግኝተውት ከአሁን ጊዜ ልቅሶ ይድኑ ነበር ። ይልቁንም አንድ መነኵሴ ስድስት መቶ ብር አስቀምጠውበት ነበረና አሁን እሳቸው ከዚህ ሁሉ ገንዘብ ነፃ ወጥተው ልመናን አዘውትረዋል ። ይገርማል አሁን ግን ደጉ ርኅሩኁ ብርሃኑ ንጉማችን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ባንክን ለሕዝባቸው ስለገዙ ባለ ገንዘብ ሁሉ ገንዘባችሁ በከንቱ ከሚቀር እባንክ ብታስቀምጡ ከንደዚህ ያለ ቅሚያ ሁሉ ትድናላችሁ ያለዚያ ገንዘብን ለውጭ ሀገር ሰው እያስረከቡ ብር ጠፋ ማለት ኃጢአት ይሆናል።

ሥዩም ወልደ መስቀል ጐሬ።

ለማወቅ መጠየቅ

የማያውቁትን ነገር ከሚያውቅ ለመጠየቅ በማፈር ብዙ ነገር ይጐድላልና ከዚህ ቀጥሎ የተጻፉትን ነገሮች ባለማወቄ ምሁሮችና ብልሆች የብርሃንና ሰላም ወዳጆች የሆናችሁ እንድታስረዱኝ ስለፈለግሁ ጥያቄዬን ጻፍሁ ።

ሰነፍ ገበሬ በትጉህ በሬ፤ ትጉህ ገበሬ በአባያ በሬ ከሚያርሱት ለማናቸው ፈር ይወድቅለታል?

ጥሩውን ዕቃ በአሻሻጡ ኰርቶ በርካሽ ከሚሸጥ ነጋዴ መናኛውን ዕቃ በትሕትና ውድ አድርጎ ከሚሸጥ ነጋዴ ለማንኛው ወረት ይገባለታል ?

ብዙ ትምህርት ተምሮ በተማረው ዕውቀቱ ከማይሠራ ሳይማር በመቅረቱ ከሚጸጸት ማናቸው ብልጫ አላቸው

ዕውቀት እያሁ ቤት አለማወቅ ከሀብታም ቤት ሁኖ ሀብታም ይህ ሁሉ ገንዘቤ ቀርቶብኝ ምነው ዕውቀት በገኘሁ ብሎ ቢመኝ አዋቂው ደሀ ይህ (የተማርኩት) ዕውቀቴ ቀርቶብኝ ምነው ሀብት ባገኘሁ ብሎ ቢመኝ የማናቸው ምኞት ይሻላል ።

ሀብታም ሁኖ በገንዘቡ ቀዋሚ ነገር ከማይሠራ የዕለት ምግብና ልብስ ካላጣ ከደሀ ጋራ ልዩነታቸው ምንድንነው።

ዛሀሉ ጽጌ ።

ስለ ደጃዝማች ኃይለማርያም ወሌ ሞት

ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ወሌ የራስ ወሌ ልጅ በልጅነታቸው ከአባታቸው ከራስ ወሌ ቤት ወጥተው ወደ አክስታቸው ወደ እቴጌ ጣይቱ መጥተው እቴጌም በመልካም ተቀብለዋቸው ነበር ። የእቴጌ ጣይቱ ዘመን ከአለፈ በኋላ በልጅ ኢያሱ ጊዜ በደጅ ጥናት ተጉላልተው ሲኖሩ መቸም ይህ ዓለም ተላላፊ

ነውና ። ደግሞ የልጅ ኢያሱ ዘመን አለፈና ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ በነገሡ ጊዜ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም አልጋ ወራሽ በሆኑ ጊዜ ወንድማቸው ራስ ጉግሣ ከእሥር ተፈትተው ሲሾሙ የአዲስ አበባ ደጅጥናት ስልችቷቸው ነበርና ከወንድሚ ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋራ ደሸለ ኖል ፡ ለው ከንግሥት ተሰናብተው ከወንድማቸው ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋራ አብረው ሔዱ ወንድማቸውም አክብረው ደጃዝማች ብለው ምልክም አገር ሹመዋቸው ሲኖሩ ራስ ጉግሣ ወሌ ከመንግሥት ከድተው ከራስ ሙሉ ጌታ ጋራ በተዋጉ ጊዜ ከጦርነቱ ተማርከው ተከተማ ውጭ ታሥረው ቈይተው የቍርጥማት በሽታ ነበረባቸው ና እየባሰባቸ ስለሔደ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሐኪም እንዲያያቸው ጃንሆይ ፈቅደውላቸው በዳግማዊ ምኒልክ ሆፒታል ብዙ ጊዜ ታክመው በጥቅምት ፲፩ ቀን ዐርፈው እቴጌ ጣይቱና ደጃዝማች አመዴ ወሌ በተቀበሩበት በእንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን መሳፍንቱና መኳንንቱ ወይዛዝሩ ተሰብስበው አልቅሰውላቸ በብዙ ክብር ተቀበሩ ዕድሜያቸውም ፵፬ ዓመት ይሆናል ልጃቸውን ውቤ ኃይለ ማርያምንና ባለቤታቸውን እኅቶቻቸውንና ዘመድ ወዳጆቻቸውን የቀሩትንም ኃዘንተኞችን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኃዘኑን ይገልጻል ።

የሚያአሳዝን መርዶ።

ፊታውራሪ ኃይሌ በረደድ የራስ ቢትወደድ ተሰማ የልጅ ልጅ በአለፈው ዓመት ፊታውራሪ ተብለው ታላቅ ማዕርግ ያለው ሽልማት ተሸልመው ጉራፋርዳንና ቤንሾ የሚባለውን የሸንቅላን አገር ተሹመው እንኳን እሳቸውን ወዳጅ ዘመዳቸውን ሁሉ እጅግ ደስ ብሎት ወደ ተሾሙበት አገር ሒደው ቤተ ክርስቲያንም አሠርተው አገሩንም ገና መልመድ ሲጀምሩት በተሾሙበት አገር በእብጠት ሕማም ፫ ወር ያህል ታመው በመስከረም ፲፫ ቀን ሙተው በዚያው ተቀበሩ የሚል የመርዶ ወረቀት ለአክስቶቻቸው ለወይዘሮ አበነሽና ለወይዘሮ ጌጤነሽ ለከቡር ከንቲባ መኰንንና ለቀሩት ዘመዶቻቸውና ወዳጆቻቸው ሁሉ መጥቶላቸው በጥቅምት ፰ ቀን ታላቅ ልቅሶ ተርጎ ነበር ። በማግሥቱም የጉባኤ ልቅሶ ተደርጎ ከቤታቸው አጠገብ ባለው ሜዳው ታላቅ ድንኳን ተተክሎ መኳንንትና ወይዛዝር ካህናትና ሠራዊት ተሰብስበው ታላቅ ልቅሶ አለቀሱላቸው እሳቸው መልከመልካም ጠባየ መልካም በዓለጋርማ ነበሩ ። ዕድሜአቸውም ፵፫ ዓመት ነው ። በራስ ቢትወደድ ተሰማ ወገኖች ልቅሶና ኃዘን በዛባቸው እያለ የሚደነቅ ሰው አለ ለአዋቂ ሰው ግን እጅግ አያስደንቅም የሞት ብዛት የትውልድ ብዛት መሆኑ አይጠረጠርምና ። ጥቂቶች ዘመዶች ያሉት ጥቂት አልቅሶ ይረሳል ብዙ ዘመድ ያለው ግን የተራቸው ቀን በደረሰ ቍጥር ተራው እስኪደርስ እንደአለቀሰ መኖሩ አይጠረጠርም ። ይልቁንም ይህን የሚአደርገው ምክንያት በአንድ አገር በመኖርና የትውልዱ መታወቅ ነው ። ይህንም ያሳሰበን ምክንያት በነሐሴ ፳፱ ቀን የራስ ቢትወደድ ተሰማን የአክስታቸውን ልጅ ፊታውራሪ ባልቻ ጉግሣን ተረድተው ነበር አሁን ደግሞ እንደዚህ ያለ መርዶ መጣባቸው እያሉ ሰዎች ሲነጋገሩ ሰምተን በንጠይቃቸው የፊታውራሪ ባልቻን ታሪክና ትውልድ ነገሩን ብዙ ልጆች ያሉአቸው ታላቅ ሽማግሌ አርበኛ ነበሩ ። በ፹፬ ዓመታቸው ሞቱ ። በዕድሜአቸውም ብዛት የአልዘነጉ በዓለአእምሮ ሰው ነበሩ ብለው እሚወቱን ከላይ እንደአልነው በዘር መብዛትና በመተዋወቅ ነው እንጂ መርዶ የበዛባቸው ሞት ሌላውን ምሮ በእነሱ ቤት ብቻ የሚመላለስ አይመስለንም ።

የሆነ ሁኖ ዋና ኃዘናችን ለፊታውራሪ ኃይሌ በረደድ ነውና ኃዘንተኞቹን ሁሉ ብርሃንና ሰላም እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ኃዘኑን ይገልጻል ።

የሚያሳዝን ሞት።

መቸም ሞት ምሕረት እንደሌለው የብድር ገንዘብ ነው፤ እስቲከፈልም ድረስ ሲአሳስብ ይኖራል ፤ ከተከፈለም በኋላ በዚህ ዓለም ላይ ምንም ሐሳብ የለምና ዕረፍት ይሆናል። ይህንንም ያጻፈኝ ንጋቱ ወልደየስ የሚባል አወጣጡ ያማረ እንኳን ለተወለደው ለወደደው እንዲያውም ላየው የሚያሳዝን ታናሽ ወንድም ነበረኝ፤ በየካቲት ወር ታሞ በሕመሙ መጠንከር ስንጨነቅ ሰንብተን በታመመ በ፯ ወር በተወለደ በ፳፫ ዓመት ከ፯ ወር በጥቅምት አንድ ቀን ዐርፎ ብዙ ወዳጆቹና በየአድባራቱ ያሉ ካህናት ልብሰ ተክህና ለብሰው መጥተው በሚያስደንቅ ጉዞ ፍታት ተፈትቶ በቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበረ። የሚያሳዝን ሞት ብዬም አርእስት ያደረግሁበት ምክንያት አባታችን በሕፃንነቱ እተማሪ ቤት አግብተውት ሳለ በተማሪ ቤት የሚሠራውን ቅንነት ባለተማረውና አብረው በሚማሩ ጓደኞቹ እንደበት ሲነገር ቈይቶ ወዲያው ዓቅመ አዳም አድርሶ ቤት ንብረት ከያዘ በኋላ በተማሪ ቤት ያገኘው ቅንነት እንደልብስ ሁኖ እንኳን በሚያውቀውና በማያውቀው ሰው ላይ ቢሆን ላገልግሎትና ሰላምታ ለመስጠት ይፋጠን ነበር። እኔም ወንድሜ ሆይ የዚህ ዓለም ኑሮ ያለገንዘብ እንዳይገፋ የታወቀ ነው፤ በገንዘብ የማይገዛውን በሕርይ አስማምቶ ከሰጠህ ምንም የዚህ ዓለም የማይሳካ ቢሆን ኑሮትህ እንዳይሰናከልብህ እንደኛ ሥራ ይዘህ ለምክንያት የወር ቀለብ ብታገኝ ይሻላል ሥራውም ሳትደክም ተገኝቶልሃል ብዬ አስገድጄ ብመክረው በማያስፈልገው ነገር በከንቱ ደክመህል እንዳያት እንዳባቶቼ ቤተ እግዚአብሔር አገለግላለሁ እንጂ ሌላ ሥራ ስመለከት በተማርኩት ትምህርት ሳላገለግል ጊዜዬን በከንቱ አላሳልፍም እንዲያውስ የዚህ ዓለም ኑሮ የለት ራት ከተገኘ ምን ያስፈልጋል «ቅዱስ ዳዊት ይዘግቡ ወኢየአምሩ ለዘያስተጋብኡ ብሎ የተናገረውን ዘነጋኸውን» ስለዚህ በቤተ እግዚአብሔር አገለግላለሁ እንጂ ሌላ ሥራ አልፈልግም ብሎ ቁርጥ አሳቡን መለሰልኝ ከዚህ ወዲያ ከቤተ ክርስቲያን አለመለየቱና ቅንነቱ ብኔ እንደበት ሊነገር አይቻልም።

እንግዲህ የሚያሳዝን ሞት ብዬ አርእስት ያደረግሁት መጀመሪያ ገና በሕፃንነቱ የገንዘብን ፍቅር ንቆ ቤተ ክርስቲያንን በመውደዱ ነው ። ፍርድ ጸሐፊ ደምሴ ወልደየስ።

አቦማልተን
ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

አቦማልተን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው። አቦማልተን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል አቦማልተን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፡ ቤርን ናቸው። በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው።

አቦማልተን አዲስ አበባ ባሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ማጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት

ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር	
የቅ ዮ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር	
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፭	ብር	
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር	
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲	ብር	
፫ቱ መጻሕፍተ መነኮሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪	ብር	
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪	ብር	
ዶቦታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፱	ብር	
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር	
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር	
የዓለም ጂዮግራፊ ከነካርታው	፯	ብር	
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፮	ብር	
ድርሳነ ሚካኤል	፮	ብር	
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር	
ኅሀ ጽባሕ	፬	ብር	
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር	
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር	
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪	ብር	፳መ
የእርሻ ትምህርት	፩	ብር	፳መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥራዙ እጅግ ያማረ	፪	ብር	
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር	
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር	
የቍጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩	ብር	
የአማርኛ ሰዋሰው	፩	ብር	
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር	
የነፃ ደንብ ከነተጨማሪው	፩	ብር	፳መ
የብድር ደንብ	፩	ብር	
የጦር መሣሪያ ደንብ አዲስ	፩	ብር	፳መ
የገዳም ደንብ	፩	ብር	
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩	ብር	
ዮሐንስ ቡንያን	፩	ብር	
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፭	ብር	
የ፪ኛ	፳	ብር	
የ፫ኛ	፲፭	ብር	
የ፬ኛ	፲	ብር	
የ፭ ኛ	፯	ብር	
የ፮ኛ	፯	ብር	
የ፯ኛ	፯	ብር	
፳፬ ካርት ፖስታል	፩	ብር	
የረኮማንዴ ደብተር	፫	ብር	
ሕገ መንግሥት	፬	ብር	
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳	መሐ	
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ን ነገ የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፳	መሐ	
አጭር የዓለም ታሪክ	፳	መሐ	
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተስማማ	፳	መሐ	
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፳	መሐ	
ያማርኛ ምሳሌ	፳	መሐ	
አሳብና ምኞት	፱	መሐ	
የፍቅር መላከት	፱	መሐ	
ትምህርተ ሕፃናት	፱	መሐ	
የምሕረት አዋጅ	፱	መሐ	
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪	መሐ	
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪	መሐ	
የንቍጣጣሽ ግጥም	፪	መሐ	
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፪	መሐ	
፩ ጋዜጣ	፪	መሐ	
አርሰጣላብ	፱	መሐ	
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፱	መሐ	
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፱	መሐ	
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፭	መሐ	
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፩	መሐ	
ካላንድሬ	፳	መሐ	
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪ	፩	መሐ	
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፳	መሐ	
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፱	መሐ	

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት እጥፍ ። ነጠላ በያይነቱ ። እርሳስ መንኰልና ብረት ብርዕ ቀለም በያይነቱ።የካርት ቢዚት እንቦልብና ካርት ቢዚት በያይነቱ ። እንቦልብ ትልቅና ትንሽ በያይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ ጊዜ እንዳስታወቀው የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ዕዶችን ቦታ ጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል።

የፊታውራሪ በዳኔ አሸግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፱፻፲ና ፲ሺ፯፻፺፬ ሜትር ካሬ።

የቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ አጥቢያው አማኑኤል ስፋቱ ፳፬ሺ ፳፱ ሜትር ካሬ።

ያቶ ወንድማገኘሁ በዛብህ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፫፻፴፮ ሜትር ካሬ ። ሺያጩም የሚደረገው በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ ነው።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሴጊየን ዘንድ ይገኛል ። ይህነኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተኩል ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

የሚሸጥ ቦታ

ማጀስቲክ ሆቴል አጠገብ ከሙሴ ሃርዲ ፊት ለፊት መሐመድ አሊ ከሠራው አዲስ ፎቅ በታች ጥሩ ጥሩ ቤት የተሠራበት በወሩ እስከ መቶ ብር ድረስ ኪራይ የሚያመጣ ጥሩ የሚሸጥ ቦታ አለና የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ አቡጀዲድ ገበያ ላይ ወችራጀ የሚባል ሂንዲን ጠይቁ።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

ባለ መናገሬ ብዙኅ ተደንቁ ባሁኑ ጊዜያት ሌሎችም ሰዎች እንደ ታመሙት እኔንም በቲኒሹ አሞኝ ነበረ ይኸውም የጥቢ ወር መጀመሪ ልዩ ልዩ የሆኑ ሕመሞች ስለሚያመጣብን በትንሹ መጸጸት ይገበናል ግን ከክረምት አበጋው ስለ ደረስን ፀጣም ደስ ይለናል፤ ባሁኑም ጊዜ ተላላፊው በሽታ ባከተማችን ውስጥ ብዙህ በርትቷል ትልልቅም ጥንቃቄ የሚያስፈልገው በንደዚህ ያለች በድንገት በምትደርስ ተላላፊ ሕመም ነው፤ባሁኑም ሰዓት ያልበሰለ ያታክልት ምግብ መብላትና ተፈልቶ ያልተነጠረ ውሀ መጠጣት የማይስማማ መሆኑን ባለኝ እውቀቴ አስረዳችኋለሁ

የቅባትና የዱቄት መድኃኒት ደግሞ ሌሎችም መድኃኒቶች አፋርማሲ ሳንትራል መገኘታቸውን በጻፍኩልዎት ማስታወቂያ አሳስብዎታለሁ.

እነዚሁም መድኃኒቶች ብዙኅ ጊዜ የተመዘዘኑናቸው ባለፈውም አንበንሮ በመንግሥት ፈቃድ ብዙኅ መድኃኒቶች ሒደው ነበረ።

ለጊዜውም ጤንነት የሚሰጥ ለማበርታት የሚችለውንና ይህንኑም ሕመም ለመዳን ለሚፈቅዱ ሰዎች ሔትማገሮን የሚባለውን መድኃኒቴን እልክልዎት እችላለሁ ለመንገድና ለጉዞ የሚቀሉ መድኃኒቶች ለማሰናዳት የተዘጋጀሁ መሆኔን አሁንም ደግሜ አሳስብዎታለሁ

በጻፍኩልዎት ደብዳቤ በሚመጣው ሳምንት ደግሞ አስታውቅዎታለሁ ።

ታዛዥዎ ኤም ማቅሳኪስ ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ ፥ የደረት የጕበት ፥ የኵላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቁቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪክ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዘ ገንዘብ ማበደር

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፯ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወከሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዳች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመኀብኘት ።

ማስታወቂያ ።

እስከ መስቀል ድረስ አንድ የቤተ ሰብ መኪና የገዛ ሰው ደህና ሽልማት ያገኛል ።

በርቱ ይኽ እድል አያምልጣችሁ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚክኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ካገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ፡ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

ቁ 1 [illegible] በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፵፮
8me ANNE. № 46

ሐሙስ ኅዳር ፩ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 10 Novembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለጸሐፊቱና ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ፡ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ክቡር ራስ እምሩ አቀባበል በጐጃም።

ክቡር ራስ እምሩ በባሕርያቸውና በአገዛዛቸው እጅግ የተመረጡ ፍርዳቸውም ለሕዝቡ የመጠነ መሆኑን ከአሁን ቀደም በገዙት አገር ላይ ሰላምና ጸጥታን ከማብዛት በቀር ከድኃና ከመኳንንት ጋር እንደሌሎች አገረገዦች በየጊዜው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት መከሰስና መወቀስ የለባቸውም። ስለዚህ በሕዝቡ ዘንድ አጥብቀው የተናፈቁ ናቸው። ይህንኑ በመገንዘብ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሰላምና ፍቅርን በተራቆተው ጐጃም እንደሾሟቸው፤ ወዲያው ለመንግሥቱ ጉዳይ ወደ ሮፓ ተልከው ቈይተው ነበርና የጐጃምም ሕዝብ በውነት አገሩን የሚወድ ሁሉ ዝናቸውን እየሰማ ምነው አንድ ጊዜ መጥተው ዓይናቸውን ባየነው እያለ ይናፍቅ ነበር። ያገር ፍቅር የሌለበት አጋሚዶ (ሽፍታ ወሮበላ) የሚባለው ግን የራስ ኃይሉን ልጅ ፊታውራሪ እድማሱን በፖለቲክ ለጥፋት መሪ አድርጎ በጐጃም ላይ ታላቅ ሁከት አስነሥቶ ወተበርበረት ታቦት ሕግነ ወተሄወጠ ክህናቲነ እንዲል ቤተ ክህነቱም ፤ ቤተ መንግሥቱም ተበረበረ፣ ብዙዎቹም ተጐዱ። በነዚህ ሰዎች ኃይልና ጥጋብ ጐጃም በፍጹም ለጥፋት ታዝዞ ነበር። በነነዌ ለጥፋት የታዘዘው እሳት በእንጨቶቹ ላይ ውሎ አድሮ ከልመና ብዛት እንደ ተመለሰ፡ የርኅሩኁ ንጉሠ ነገሥት ሠራዊት ጐጃምን ለማጥፋት በዓባይ ዙሮ ተንጠርቦ ይታይ ነበርና፡ለዘጸፍዐከ መልታሕቴከ ሚጥ ሎቱ ከልእታሂ ብሎ በቅዱስ ወንጌል እንደ ተነገረ፡ በደሉ በደል ሳይሆን ቀርቶ አይደለም ወደፊት የሚሆነውን ጥፋት በመገንዘብ ርኅሩኁ ንጉሠ ነገሥት በይቅርታ አሳለፉት። ይህንን ጸብ በመስማት ሰላማዊው ክቡር ራስ እምሩ ከሮፓ በተመለሱ በ፫ኛ ቀናቸው ከብዙ ሠራዊት ጋር ወደ ጐጃም ጉዞ ጀመሩ። በ፲ኛው ቀን በዋናው ከተማ ማርቆስ ጥቅምት ፲፱ ቀን ደረሱ። የራስ ኃይሉ ግቢ ለጤንነት የማይስማማ ስለሆነ የሸዋና የጐጃም መኳንንት መክረው ለክቡር ራስ እምሩ ማረፊያ የሚሆን ለጊዜው ከከተማ ውጭ አሰናድተው ነበር። ከማረፊያውም በታች ዝቅ ብሎ ኃይሉ ገበያ ከሚባለው አጠገብ ለክቡር ራስ እምሩ መቀበያ ታላቅ ድንኳን ተተክሎ በግራና በቀኝ የሸዋ ወታደር ተሰልፎ ነበር።እልፎ እልፎ በሰልፉም መሐል አንዳንድ መትረየስ ነበር። ጐጃም መኳንንትና ሠራዊት የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ በግንባር እተሰናዳው ቤት ድረስ ተሰልፈው ነበር። ሦስት ሰዓት ተኩል ሲሆን ክቡር ራስ እምሩ በአርበኞቻቸውና በክብር ዘበኞች ታጅበው ወደ ተሰናዳው ድንኳን አጠገብ ደርሰው ከበቅሎ ሲወርዱ የሸዋ መኳንንት እንኳን ደህና ገቡ እያሉ ሰላምታቸውን ካቀረቡላቸው በኋላ አምሮ በተሰናዳው ቦታ ሒደው በወንበር ተቀመጡ። በዚያን ጊዜ የክብር ዘበኞች በግንባር ተሰልፈው ሰላምታ ሰጡ። ከዚህ በኋላ የኢጣሊያ መንግሥት ቆንስል ከሐኪሙ ጋር መጥተው ሰላምታቸውን አቀረቡ። ቀጥሎም የጐጃም መኳንንት በፊታውራሪ አላምረው አቀራቢነት እየመጡ ተገናኙ። ካህናቱም በመልአከ ፀሐይ ተገኝ መሪነት በግንባር ተሰልፈው ቀርበው፤ የለበሱት ዲያቆናት እግዚኦ በኃይልከ ይትፌሣሕ ንጉሥ ወበዙኅ ይትኃሠይ በአድኅኖትከ፡ ፍትወተ ነፍሱ ወሀብኮ ብለው ከሰበኩ በኋላ፤ የለበሱት ቄሶች ወንጌል ብለው በረድም ዜማ አንቀረቀሩት፡ወንጌሉም ማቴ ፲፩ ፯ ነው፡ «ምልጣን» ወአንተኒ ትክለ ሃይማኖት ነቢየ ልዑል ትሰመይ ዓርኩ ለኃይለ ሥላሴ ትሰመይ ወእጼሙዱ በሥጋ ኅሰረ ተፈኖከ ታርኁ አናቅጸ ጽድቅ። ይኸውም ምሥጢሩን ለተረዳው እጅግ አርጎ ደስ ያሰኛል። «እስመ ለዓለም» (ለዘብ) እምሥራቀ ፀሐይ እስከ ዓረብ ይትአኰት ስሙ ለኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ጸልዩ ጻድቃን ደቂቀ ማርቆስ መምህረ ዓለም። አመ ይመጽእ ውስተ ደብረ ፀሐይ በዘዚአሁ ስብሐት ንርከብ ገጸ በኀቤሁ ወንርከብ ሞገሰ በቅድሜሁ ለተክለ ሃይማኖት ብለው አሸብሸበው ከጨረሱ በኋላ የለበሱት ካህናት ቀርበው መስቀል አሳለሟቸው ። ወዲያውም ያብሣ ማርያም አለቃ የሆኑት እንደ በተ ርቱዑ አለቃ ዓለማየሁ ሽፍ ያለፈውን በጐጃም የተነሣውን ሁከት የሚነክና የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን ርኅራኄ የሚ አጕላ ከወንጌል እየጠቀሱ፤ ቀጥሎም ኢታደሉ ለገጽ የተባሉትን የክቡር ራስ እምሩን ፍርድና እውነተኝነትን እንደሰማነው ዓባይ አይለውጥብን ብለው ታላቅ የሆነ ደስ የሚያሰኝ ዲስኩር ተናግረው ሕዝቡን ሁሉ በጣም ደስ አሰኙት ። ከዚህ በኋላ ክቡር ራስ እምሩ በማረ አጀብ ሆነው ወደተሰናዳላቸው ቤት በእልልታና በእምቢልታ በሰላም ገቡ ።

ያለቃ ዓለማየሁ ሻሹ ዲስኩሩም ይህ ነው። ነአምር ከመራትዕ ብእሲ አንተ ወበጽድቅ ትሜህር ፍኖተ እግዚአብሔር ወኢታደሉ ለገጽ(ትርጓሜውም፤) ቀና፤ እውነተኛ ሰው እንደሆንህ እናውቃለን በውነትም የእግዚአብሔርን መንገድ የምታስተምር የሰው ፊት አይተህ የማታደላ ማለት ነው ። ዳግመኛም ለእመ ኮነት ቀዳሚሃ ቅድስተ ከማሁ ብሑእኒ ቅዱስ ውእቱ፡ ወለእመ ኮነ ሥርዋ ቅዱሰ ከማሁ አዕፁቂሃኒ ቅዱስ አሉ። (ትርጓሜውም) እርሾው ያልመጠጠ ያልኰመጠጠ እንደሆነ ዳቦው ያማረ የተወደደ ይሆናል።ሥሩም የሚጣፍጥ የሆነ እንደሆነ ጫፉም የሚጣፍጥ ይሆናል ማለት ነው ። እንዲህ ማለት ባፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሁሉ ያማረ የተወደደ ይሆናል ። ጠማማው ይቀናል ። ሐሰት ይደከማል ። እውነት ይበረታል፤ ሕዝቡ ሁሉ ንጉሡ የሚሠራውን ይሠራሉ ። የሚወደውን ይወዳሉ ማለት ነው ።

ወበከመ በጌጋየ ፩ዱ ብእሲ ተኰነነ ኵሉ ዓለም ከማሁ በጽድቀ ፩ዱ ብእሲ ይጸድቅ ኵሉ እጓለ እመሕያው። (ትርጓሜው) ለ፩ድ ሰው በደል በሁሉ እንደተፈረደበት ባንድ ባፄ ኃይለ ሥላሴ ቸርነት ሁሉ ዳኑ ማለት ነው ።

ወከዕበ በእንተ ዓሊዎቱ ለ፩ዱ ብእሲ ብዙኃን ኮኑ ኃጥአነ ወበተአዝዞቱ ለ፩ዱ ብእሲ ብዙኃን ኮኑ ጻድቃነ።(ትርጓሜውም) ባንድ ሰው መከዳት ብዙ ሰዎች ሞቱ ፤ ተጐዱ ፥ ባፄ ኃይለ ሥላሴ ቸርነት ራስ እምሩ ታዝዘው በመምጣታቸው ግን ብዙ ሰዎች ከሞት ዳኑ ማለት ነው። ዳግመኛም ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብእሴ ዘዘርአ ሠናየ ዘርአ ውስተ ገራህቱ ፤ ወእንዘ ይነውሙ ሰብኡ መጽአ ጸላኢሁ ወዘርአ ክርዳደ ፤ ወሰበ በቈለ ሣዕሩ ወፈረየ ፍሬ አሜሃ አስተርአየ ክርዳድኒ ወይቤልዎ አግብርቲሁ ለበዓለ ገራህት አኮኑ ሠናየ ዘርአ ዘራእከ ውስተ ገራህትከ እምአይቴ እንከ ዝንቱ ክርዳድ ወይቤሎሙ ጸላዒ ገብረ ዘንተ ወይቤልዎ አግብርቲሁ ትፈቅድኑ ንእርዮ ወንጸሕዮ ወይቤሎሙ ኅድጉ አልቦ እንዘ ትፈቅዱ ትእርዩ ክርዳደ ኢትምሐው ምስሌሁ ሥርናየኒ ፤ ኅድግዎሙ ይልኅቁ ኅቡረ (ትርጓሜውም) የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በርሻው ያማረ ሥንዴ የዘራ ሰውን ትመስላለች።ሰዎቹ ሲተኙ ጠላት መጥቶ እንክርዳድ ዘርቶ ሔደ፤ቡቃያ ሆኖ ባፈራ ጊዜ እንክርዳድ መሆኑ ተለይቶ ታወቀ ፤ ሎሌዎቹ ባለአዝመራውን እንዲህ አሉት፥መልካም ሥንዴ ዘርተህ ነበረ ይህ እንክርዳድ ከወዴት መጣ አሉት እሱም ጠላት እንዲህ አደረገ አለ፥ ከወደድህስ እየነቀልን እንጣለው አሉት፤እሱም አይሆንም እንክርዳዱን ስትነቅሉ ሥንዴዩን እንዳትነቅሉ ተዉዋቸው እንክርዳዱና ሥንዴው ባንድነት ይደጉ አላቸው ። አፄ ኃይለ ሥላሴም የበደለውን አጠፋለሁ ስል ያልበደለውን ሀገሬን፥ ያልበደለውን ሕዝቤን አጠፋለሁን ብለው መግራታቸው ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰላቸው እጅግ ያስደንቃል። የቀደሙ ነገሥታት ፊቱ ወዛ ከብቱ በዛ ብለው ይወርሱ ነበር ደግሞም ከዚህ አገር ከብት ረብቷል እህል በቅሏል ብለው ሒደው ዘርፈው ገፈው ወረው ወግተው ለሠራዊታቸው ያተርፉለት ነበር ። አሁን ግን ሰዎቹን ቢወጉበት ቤቱን ቢበረብሩበት ገንዘቡን ቢዘርፉት የሚምር ንጉሥ ያስነሣልን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ።

እርስዎም ክቡር ጌታዬ ራስ እምሩ ይህን ታሪክ የተረክሁ ወትዕግሥትየኒ ዘእምኀቤከ ውእቱ ብሎዋል የትዕግሥተኛ ሎሌ ዕጉሥ ነው፤የቸር ሎሌ ቸር ነውና ብንበድልዎ እንዲምሩን እንዲችሉን ያድርግዎ፡ መዓስበ ናዝዝ፡ እጓለ ማውታ ተወከፍ ሚሩያነ በምሕረትከ እንጽሕ፡ዓብዳነ አጥብብ፤ ወኅጉላነ ሚጥ፡ እለ ውስተ ሞቅሕ አድኅን ወለኵልነ ኩን ፀወነ እስመ ለከ እግዚኦ መንግሥት ቡሩክ አሜን። ባልዋ የፈታት ፥ ልጆችዋ ያልላቁላት ለሥራ ያልደረሱ ለሙብልም ያላነሱ የሚረዳት የሌላት ጉጃምንም አዕናት አይዞሽ በላት ይህ የተባረከ መንግሥት ለተባረከው ንጉሥ ለአፄ ኃይለ ሥላሴ ነውና ፤ ዳግመኛም ያፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት በመዓልት ከፀሐይ በሌሊት ከጨረቃ ከከዋክብት ባንድነት ያኑርልን፥ልጅዎ የልጅ ልጅዎ በዙፋንዎ ሲአበራልን ይኑር ።

ክቡር ጌታዬ ራስ እምሩ የሰማነውን ምግባርዎን እንደ ናየው ያድርገን አሜን ብለው ጨረሱ ። ውሂብ ወ ማ ።

የሚገባ ነዋ ።

ሟቹ አቶ ደገፋ ማደርያ ሥራቸው ንግድ ስለነበረ የንግድም ሥራ የሚሔደው በማበደርና በመበደርም ገንዘብን ከአንዱ ወደ አንዱ በማመላለስ ስለሆነ አቶ ደገፋም በዚሁ ሥራ ሲኖሩ ከጥቂት ጊዜ በፊት ጀምሮ ያደረባቸው ሕመም በድንገት በርትቶባቸው ወደ ሞት መቅረባቸውን ባለቤታቸው ወይዘሮ ቅጅነሽ አይተው ባላቸው ይሠሩት የነበረው የንግድ ሥራ የሒሳብ መዝገብና ሰነድ የተባለ ሁሉ ከየቦታው እንዳይታጣና እንዳይሰክር አስበው የአቶ ደገፋን ሕመም ለመጠየቅ የመጡትን ወዳጆቻቸውን የሒሳቡ መዝገብና ሰነዱ ያለበትን የጽሕፈት ቤታቸውን ዘግተው በሁሉም ፊርማ እንዲያሽጉት ለመኑዋቸው ። እነዚሁም ሽማግሎች አቶ ደገፋ ለሞት መቅረባቸውን ስለ አዩ በወይዘሮ ቅጅነሽ ልመና ቃል ተቀብለው ፲፪ የሚሆኑ ሽማግሎች ቢሮውንና የቁም ሣጥኑን ዘግተው በፊርማቸው አሽገው ቁልፉን ከነርሱው መካከል ላንደኛው አደራ ሰጥተው ከጽሕፈት ቤቱ ሲወጡ አቶ ደገፋ አረፉ ። ከጥቂት ቀን በኋላ ልጃቸው በቀለ ደገፋ ከአገር ቤት መጥቶ ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ቅጅነሽ ጋራ ተማክረው የጽሕፈቱን ቤት ያሸጉ ሽማግሎች ተሰብስበው እንዲከፍቱና ከነርሱ መካከል ሰባቱ ያህል ሽማግሎቹ የሒሳቡን መዝገብና ሰነዱን እያዩ እንዲመረምሩና ሒሳቡን ሁሉ አጣርተው እንዲለዩላቸው የባለቤቷንና የልጁንም ክፍያ ለየራሳቸው የሚደርሳቸውን ድርሻቸውን አደላድለው እንዲለዩዋቸው በጽፈት ለመኑዋቸው ። እነዚያም ሽማግሎች ስለወዳጃቸው ስለ አቶ ደገፋ ቁም ነገር ሲሉ ልመናቸውን እሺ ብለው ተቀብለው የየራሳቸውን ሥራ ፈትተው በሳምንት ሁለት ቀን እየተሰበሰቡ ሒሳቡን ሲመረምሩ ቆይተው ሳይጨርሱ የሞቱበት አርባ ቀን ደረሰ ። አርባውም ከወጣ ከሦስት ቀን በኋላ የአቶ ደገፋ ባለቤትና ልጃቸው የአቶ ደገፋን አገልጋዮች ወንዱንም ሴቱንም የሴቲቱ ፈንታ ሳይከፈል በነዚሁ በሽማግሎቹ ፊት ሰብስበው መንግሥት ስለ ባሮች አስተዳደር በአቆመው ሕግ እንደተጻ-

ፈው ቃል ጌታችሁ ከሞቱ ባርነት የለባችሁምና ነፃ ናችሁ ። መሔድ የምትፈልጉ አስታውቁንና ነፃነታችሁን የሚመሰክርላችሁ ፈርማችንን እየሰጠናችሁ፥ ሒዱ ብለው በግልጥ አስታወቁዋቸው ። አገልጋዮቹም ቃሉን ሰምተው የጌታችንን ሙት ዓመት እያወጣን ከዚያ በኋላ ብንወድ ከጌታችን ሚስት ወይም ከልጃቸው ጋራ እንቀመጣለን ብንጠላ እንሔዳለን ብለው፥ ወንዶቹም ሴቶቹም ሁሉም ባንድ ቃል ተናገሩ ። ቍጥራቸውም ፵ ይሆናል ።

እንደዚሁም ባለ ባርያ የሆኑ የኢትዮጵያ ሰዎች ሁሉ ሲሞቱ፥ ወራሾቻቸው ያቶ ደገፋ ባለቤትና ልጅ እንዳደረጉት እያደረጉ ለባሮቻቸው አርነት በመስጠት የመንግሥቱ አዋጅ ተጠብቆ ይፈጸምና ኢትዮጵያ በባርያ ምክንያት ከመታማት ትድናለች በማለት ብርቱ ተስፋ እናደርጋለን ። ነገር ግን ምንም የባሮች ነፃነት ለሁሉም ደስ የሚያሰኝ ቢሆን ባሮች በባርነት ስም እየተጠሩ በጌታቸው አሳብ መኖራቸው ለነርሱ ጥቅም ነውና በጌታቸው ሞት ነፃ ሁነው በሚኖሩት ኑሮ የሚያገኛቸው ችግር ባርያ ተብለው ከኖሩበት ኑሮ ይልቅ የሚከፋ እንዳይሆንባቸው የሚያሰስብ ሳይሆን አይቀርምና ለወደፊት ለኑሮዋቸው በሚያስፈልጋቸው ነገር መንግሥትን እንደገና ማሳሰቡ የማይቀር ይመስለናል ። ብ ጠ ።

ስለ ክቡር ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኔል ከሮፓ መግባት።

ክቡር ደጃዝማች ነሲቡ ተልከው ወደሮፓ ከሔዱት መኳንንት ጋራ ሒደው ብዙ ጊዜ ቈይተው ነበር የሔዱበትን መልእክት ፈጽመው በጥቅምት ፳፱ ቀን በማክሰኞ ባቡር አዲስ አበባ ገቡ ። የተቀባዩም ብዛት እጅግ የሚያስደንቅ ነበረ ። ከታላላቆች መኳንንትና ከሚኒስትሮች ብዙ ነበሩ የከተማው ሰው ብዛትማ ምን ይነገራል? ሕዝብ ከመብዛቱ የተነሣ ሊቀበል ከመጣው ብዙው ሰው ሳያገኛቸው ተመለሰ ። ተሹሞ መወደድ እጅግ ያስደንቃል ። ሽማግሌ ሲተርት ዕገሌ ደህና ሰው ነው ቢለው ተሹሞ አይተሽዋልን አለው። ዕገሌ ወዳጄ ነው ቢለው በመከራህ ቀን አይተሽዋልን አለው ይባላል ። ሹመት የጠባይና የአባት መመርመሯ ስለሆነች በሹመት የሚኖሩት ሰው እንዲህ አድርገው በሕዝብ ዘንድ መወደዳቸው እጅግ ያስደንቃል። የተቀባያቸውን ብዛት ለአየ ሰው ለአገር ግዛት የመጡ ይመስላል እንጂ ከውጪ አገር ወደ አገራቸው የተመለሱ አይመስሉም ነበር ። ብርሃንና ሰላም እንኳን በደኅና ገቡ እያለ ደስታውን ይገልጻል።

የአይሮፕላን ማገልገል ።

አይሮፕላን የመጣ ጊዜ በወጪ ማብዛት ምክንያት ጕዳት እንጂ ጥቅም የለበትም ያለ ብዙ ሕዝብ ነበር ነገር ግን ከመጣ ጀምሮ አገልግሎቱን ያወቅን ሰዎች በወጪው ገንዘብ ብዛት ደስ ይለናል እንጂ አይከፋንም በዚሁ በአገልግሎቱ ብዛት ዓርብ ከንቲባ ማተቤን ከጕጃም፥ ቅዳሜ የሙዋቹን የጃንጥራር ገብረ እግዚአብሔርን ባለቤት ከወሎ ይዞ መጣ። አገልግሎቱ ብዙ መሆኑ ምንም ቀድሞ የታወቀ ቢሆን ለታመመና ቶሎ ለሚፈለግ ሰው ሁሉ ፍጥነቱ የሚጠቅም መሆኑ እጅግ ደስ ብሎናል መንገደኞችንም ብርሃንና ሰላም እንኳን ደኅና ገባችሁ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ነፋስ መለወጥና አገር ማየት ።

ጥቅምት ፳፰ ቀን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ግርማዊት እቴጌ መነን፥ ልዑል አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንና ልዕልት ተናኘ ወርቅ፥ ልዕልት ዘነበ ወርቅ፥ ልዕልት ፀሐይ፥ ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ፥ ክቡር ራስ ደስታ፥ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጕግሣ፥ ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ እነዚህን አስከትለው ባሥራ ሁለት ሰዓት ተነሥተው የመንገዱን ሥራ እያዩ ወሊሶ ፍል ወኃ ካለበት ስፍራ ባራት ሰዓት ተኩል ደረሱ ። በደረሱም ጊዜ ፍል ወኃውን አዩና ለጊዜው በፊት እንደነበረው እንደ አገር ልማድ ነበረና የተሠራው ቤትና ዋጋ አከፋፈሉ ምን ያህል እንደሆን የሚቀበሉት የርሻ ሚኒስቴር ሠራተኛ እዚያው ነበረና ጠየቁት፥እሱም ከደኅና ሰው አራት ቤሳ፥ ከቂጥኛም በሽተኛ ሩብ እንቀበላለን ብሎ መልስ ከሰጠ በኋላ ለደሀቸው ተጨናቂ የሆኑ ንጉሣችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህ ፍል ወኃ ቤትና ቦታ በመልክም ሁኖ እስቲሠራ ድረስ ሳይሠራ በወኃው ብቻ ከደኅነኛውም ከበሽተኛውም ቢሆን ዋጋ አታስከፍሉት በነፃ ይጠመቅ ብለው ወደግምጃ ቤታቸው የሚገባውን ገንዘብ ለደኃው ጥቅም ሲሉ አስቀሩለት።

ከዚያም ተመልሰው አምስት ሰዓት ተሩብ ሲሆን አምቦ ወደተዘጋጀው ድንኳን ገቡ በ፮ሰዓት ተኩልም የምሳ ግብዣ ሆነ። በዘጠኝ ሰዓት ወደ ጅማ የሚሔደውን መንገድ የሚሠራውን መኪና ለማየት ሔዱ።ከዚያ ተመልሰው ከጠበሉ በላይ ባለው ከፍተኛ ቦታ ላይ ወጥተው አገር ሲያዩ አመሹ።በማግስቱ ማክሰኞ ጠዋት የውኃውን ሙቀት ለማስለካት ሔዱ።ከዚያ በኋላ ጭቱ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ከተማ የነበረውን ጐብኝተው ተመለሱ። ከዚያም በኋላ የምሳ ግብዣ ሆነ። ከምሳ በኋላ ፫ አይሮፕላኖች መጥተው ነበርና ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ፥ ራስ ደስታ፥ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጕግሣ፥ ሙሴ ኰርገር በሚነዱት ፋርማን በሚባለው አይሮፕላን፤ ልዑል አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን፥ ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ ሚሽካ በሚነዳው ፖቴዝ በሚባለው አይሮፕላን፥ የሽቃ በልሁ፥ አቶ ታደሰ መሸሻ አስፋው አሊ በሚነዳው ፖቴዝ በሚባለው አይሮፕላን ሁነው ፲ሰዓት ከ፲ደቂቃ ሲሆን ተነሥተው አምሳ ደቂቃ ያህል በአየር ላይ ከወሊሶ በታች ያለውን አገር ጊቤን ተሻግረው ጐብኝተው በ፲፩ሰዓት በሰላም ተመልሰው እሰፈሩበት ቦታ ወሊሶ ከአይሮፕላን ወርደው፥ ቻይ ግብዣ ተደረገ ።

በእግዚአብሔር ቸርነት ይህ ለሕዝብና ለሀገር ሀብት የሚጠቅም መንገድ በትጋት ተሠርቶ ተጅማ ጕሬ ተሻግሮ በወሬ የምንሰማውን አገር በዓይን ለማየት የኢትዮጵያን ከፍታ የግርማዊ ንጉሣችንን ደስታ ለማየት ምኞታችን ነው ። በጥቅምት ፴ቀን ከጥዋቱ ለ፲፪ ሰዓት ፳ደቂቃ ሲቀረው ተነሥተው

አዲስ አበባ ከተማ በ፫ ሰዓት ደርሰው እችሎት ተቀመጡ ። ብርሃንና ሰላም እንኳን በደኅና ገቡልን ይላል ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ሚኒስቴር ።

ማስታወቂያ ።

በሮፓ ቍጥር በነሐሴ ፳፩ቀን ፲፱፻፴ ዓ ምሕረት ፓሪስ ላይ ስለ ተፈረመው የጦር መሣሪያ ውል ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቅደው በግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት ስለጦር መሣሪያ እንደቆመው ደምብ መሣሪያ ለማስመጣት ፈቃድ ለሚጠይቁ ሰዎች የጽሕፈት ቤቱ ከቀድሞው በታ ተዛውሮ ወደላጋር መሔጃ ከመንገድ በላይ ከራስ ተሰማ በታ ከነበረው አዲስ ከተሠራው ቤት መቆሙን እናስታውቃለን ።

ሹምሽር ።

አለቃ ወልደ ሰማያት ቀድሞ በያዙት ሥራ ላይ ማደሪያ ተጨምሮላቸው ባላምባራስ ተብለው ተሾሙ። ነጋድራስ ሓሬ ሰማይ የሲዳሞን ነጋድራስነት ተሾሙ ። አቶ ወልደ ጻድቅ አስረስ የወላሞን ነጋድራስነትና የነጋድራስ ሓሬ ሰማይ የነበረውን ሹመት ሁሉ ተሾሙ ። አቶ ደምሴ ፋሪስ የጅማን ማዘጋጃ ቤት ተሾሙ ብርሃንና ሰላም ሹመት ያዳብር እያለ ደስታውን ይገልጻል።

ስለ አለቃ ገረመው ሞት።

አለቃ ገረመው አገራቸው ቤገምድር አፈረዋናት ነው። አባታቸውም ብላታ ወንድም ይባሉ ነበር። በአገራቸው የተከበሩ የታፈሩ ሽማግሌ በጉዛምነት የከበሩ ሀብታም ነበሩ። አለቃ ገረመውም የዜማ ትምህርትና የቀለም አነጋገር ጣዕም የተሰጣቸው አነጋገራቸውም የጐላ ነበረ ። ከአዲስ አበባ አድባራት የካ ሚካኤልን ፤ ከአገራቸው አድባራት ግላውዴዎስን ተሹመው ይኖሩ ነበር ። ደግሞ ሥርዓት አዋቂ ስለ ሆኑ በወንጀለኛ ቅጣት ፍርድ ቤት ዳኛ ሁነው እውነትን በመድፈራቸው ሕዝብ ሁሉ እጅግ ይወዳቸው ነበር።ነገር ግን ሰው ምንም ቢወድ ከሞት አያድንምና በድንገተኛ ሕማም ታመው በጥቅምት ፲፱ ቀን ሙተው ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር ካህናትና ሠራዊት ተሰብስበው አልቅሰውላቸው በዚያው በደከሙበት በየካ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበሩ ። ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስም ከጥንቱም አባታቸው ወዳጃቸው ነበሩና እጅግ የሚአሳዝን ስብከት ሰብከው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱ።የአለቃ ገረመው ዕድሜ ፶፫ ዓመት ነው ። ብርሃንናሰላም ኃዘንተኞችን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ኃዘኑን ይገልጻል ።

ማስታወቂያ ።

አቶሞቢል ነጂ የነበረው አቶ ዑመር የበታዬን ካርታ አሲዞ ከርሻና ከንግድ ማስፌያ ከኢትዮጵያ ማኅበር በ፲፱፻፳፪ ዓ ም በኅዳር ወር ገንዘብ ሲበደር እሱም በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን በታና ባገር ቤት ያለውን ርስት ፈርሞ አሲዞል የተበደረውን ገንዘብ እስካሁን ስላልከፈለ የርሻና የንግድ ማስፌያ ስለዋስ የያዘውን የኔን በታ በሐራጅ ሊሸጥ በብርሃንና ሰላም ጽፎ ስላስታወቀ እኔም ለዚሁ ዕዳ አቶ ዑመር መያዣ አድርጎ ፈርሞ ያሲያዛቸውን ርስቶች እንደውሉ ቃል ሽጬ ዕዳውን ልከፍል ቀጥሎ የተጻፈውን የከተማ በታና ያገር ቤት መሬት ኅዳር ፲፫ ቀን አሸጣለሁ ።

፩ኛ፤ ከሥላሴ አጥቢያ አቶ ዑመር ይቀመጥበት የነበረውን ቤት ከናታክልቱ ።

፪ተኛ፤ ወደ ኢትዮጵያ ባንክ መሻገሪያ በዋናው መንገድ ዳር ፫ ደጃፍ ሱቅ ቆርቆሮ ክዳን ከነማድ ቤቱ ።

፫ኛ፤ ከቤተ መንግሥቱ ወደ ላይኛው ግቢ በወጣው በትልቁ መንገድ ዳር አዲስ የተጀመረ ቆርቆሮ ቤት ያለበትን በታ።

፬ኛ፤ ወልመራ ፩ ጋሻ መሬት ግብሩ ሐያ ብር ብቻ ።

፭ኛ፤ ገነት የጋሻ ግሚስ መሬት ግብሩ ባመት ፲ ብር ብቻ የሆነ።ይሽንን በታና መሬት ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ከኅዳር ፲፫ ቀን አስቀድሞ ከኔ ጋራ ተነጋግሮ ሊገዛ ይችላል ።

ነጋድራስ ተፈራ ንጉሤ ።

ማስታወቂያ

የራስ ኃይሉን ገንዘብ በፍርድ መንግሥት ስለወረሰው በራስ ኃይሉ ላይ ገንዘብ አለኝ ስለሚለው ሰው ሁሉ በኮሚሲዮን የሚያዩ ሰዎች ታዘዋልና በመስከረም ፲፱ ቀን በጋዜጣ እንዳስታወቅነው እስከ ተወሰነው ቀን ድረስ ጉለሌ ራስ ኃይሉ ቤት ማስረጃችሁን ለልጅ ውብሸት ወልደ ዮሐንስ እንድታቀርቡ ይሁን ።

የገንዘብ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር።

AVIS AU PUBLIC

En vertu d'un jugement rendu, les biens du Ras Haïlou étant confisqués par le Gouvernement, nous avions informé Messieurs les Créanciers du Ras Haïlou, qu'il a été nommé une commission chargée d'examiner les diverses réclamations.

Tout créancier est tenu de présenter les pièces justificatives qu'il détient à Lidje Woubechét Woldé Johannés se trouvant à Goullalé, immeuble du Ras Haylou. La présentation des pièces justificatives sera valable dans le délai prévu à lavis publié le 19 Meskaram.

Signé: Balambaras Achénie
Directeur Générel des finanesc

ማስታወቂያ ።

ሐኪም ፌሊፕ ዓይንና ጆሮ አፍንጫና ጕሮሮ ዋና መንግሥታዊ በሎንዶን ያከሙ የነበሩት አዲስ አበባ ገብተዋል። በቅዱስ ሚካኤል መድኃኒት ቤት ራስ ደስታ ሱቅ እስከ ፫ት ሳምንት ድረስ ያከማሉ። ጥቅምት ፴ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ ጊዜ እንዳስታወቀው የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ዕዶችን ቦታ ኅዳር ፲ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ብአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል።

የፊታውራሪ ፀዳኔ አሻግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፱፻፲ና ፲ሺ፲፪፻፶፩ ሜትር ካሬ።

የቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ አጥቢያው አማኑኤል ስፋቱ ፰፻ሺ ፰፱ ሜትር ካሬ።

የነጋድራስ ተፈራ ንጉሜ አጥቢያው ቂርቆስ ስፋቱ ፯ሺ፫፻፳ ሜትር ካሬ።

የወይዘሮ ዓመተ መንፈስ ቅዱስ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፬፻፸፪ ሜትር ካሬ።

የወይዘሮ ወለተየስ ሀብቴ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፩ሺ፫፻፹ ሜትር ካሬ።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምፓንያ) አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምፓንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሲጊያን ዘንድ ይገኛል ። ይህንኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተኩል ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

የሚሸጥ ቦታ

ማጀስቲክ ሆቴል አጠገብ ከሙሴ ሃርዲ ፊት ለፊት ሙሐመድ አሊ ከሠራው አዲስ ፎቅ ቤት ጥሩ ጥሩ ቤት የተሠራበት በወሩ እስከ መቶ ብር ድረስ ኪራይ የሚያመጣ ጥሩ የሚሸጥ ቦታ አለና የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ አቡጀዲድ ገበያ ላይ ወችራጅ የሚባል ሂንዲን ጠይቁ።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

በዚሁም ጊዜያት ጠቅላላውን የሴቶችና የወንዶችን ውበቶች በሚያስረዳበት ጊዜ ግን ውቢቱ እመቤቴ ቀልጣፋና አቋቋመ መልከም እንደትሆን ይኸውም እየራመዘመናት ይፈቅዳል በሚያሳዝነው አቀማመጣቸው ብዙ ሰዎች በሽተኞች ናቸው ። ደግሞም በምግባቸው እኑዋኑዋር እንዲሁም በጨካኝነትና ችግረኛ በመሆናቸው ለመዳንም አይችሉም ። ለነዚሁም ሰዎች ብዙ ጊዜ የተወደደና በእውነት የማይሳሳተውን መድኃኒት እንሰጣቸዋለን። ሲፖቶዴን የሚባለውን በጥቅልል ያለውን መድኃኒቴን በጣም ሲያስጨንቅዎትና ሲያምዎት ቢሞክሩት ሕመምዎን በማቅለሉ ብዙ ደስ ያሰኝዎታል በአዲስ አበባ ውሥጥ ግዙፎችንና ሰውነተ ቁጡ ለሆኑ ሰዎች እየሩ አለመሰማማቱን ይልቁንም ከኔ የበለጠ ያውቁታል።ይልቁንም ደግሞ ዋና ማስረጃ እንቅልፍ ለሌለውና ለሚባንን ሰው ነው ።

ለነዚሁም ሰዎች ፈጽሞ የሚከለክልላቸውን ዲአል ኮምፕሬሜ የሚባለውን መድኃኒታችንን በጣሙ የጠራውን ከምንሰጣቸው በቀር ሌላ የማያስፈልግ መሆኑን እናስታውቃችኋለን ። ደግሞ ከዚህ በኋላ የሰውነት ሥራቸውን ተስማምተው ያለ ሐሳብ ሌሊቱን በደስታ ያልፉታል ስል ባለኝ እውቀቴ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አሳስባለሁ

ታዛዥዎ ኤም ማትሳኪስ ።

አቦማልቲን ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

አቦ ማልቲን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው። አቦማልቲን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል አቦማልቲን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፡ ቤርን ናቸው። በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው።

አቦማልቲን አዲስ አበባ ባሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ማጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
ማተሚያ ቤት ታትመው የሚሸጡ መጻሕፍት
ማስታወቂያ

ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር	
የቅዱ አፈወርቅ ተግሣፅ ብቻ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር	
,, ,, ,, ተግሣፅና ድርሳን ,, ,,	፲፭	ብር	
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር	
፲፬ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜ	፲	ብር	
፫ቱ መጻሕፍተ መነኰሳት ንባቡ ከነትርጓሜው	፳፪	ብር	
የወንጀለኛ መቅጫ (ፍትሐ ነገሥት)ደንብ	፲፪	ብር	
ደብታና ክብር የአውሮጳ መ ታሪክ	፱	ብር	
ሲራክና ሰሎሞን ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር	
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር	
የዓለም ጅዖግራፊ ከነካርታው	፯	ብር	
፬ቱ ወንጌልና ግብረ ሐዋርያት ነጠላ ትርጓሜ	፯	ብር	
ድርሳነ ሚካኤል	፯	ብር	
፲፬ ቅዳሴ ነጠላ ትርጓሜ	፭	ብር	
ጎህ ጽባሕ	፭	ብር	
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር	
መጽሐፈ ቅኔ በፊደል ተራ የታተመ	፫	ብር	
የሕይወት ታሪክ (ቢዮግራፊ)	፪	ብር	፳፭መ
የእርሻ ትምህርት	፩	ብር	፳፭መ
ዳዊት በኪስ የሚያዝ ጥሬዙ እጅግ ያማረ	፪	ብር	
ኪዳንና ትምህርተ ኅቡአት ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር	
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር	
የቍጥር ትምህርት (አሪቲሜቲክ	፩	ብር	
የአማርኛ ሰዋስው	፩	ብር	
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር	
የነግ ደንብ ከነተጨማሪው	፩	ብር	፳፭መ
የብድር ደንብ	፩	ብር	
የጦር መማሪያ ደንብ አዲስ	፩	ብር	፳፭መ
የገዳም ደንብ	፩	ብር	
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩	ብር	
ዮሐንስ ቡንያን	፩	ብር	
የ፩ኛ ዓመት ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ተጠርዞ	፳፭	ብር	
የ፪ኛ	፳	ብር	
የ፫ኛ	፲፭	ብር	
የ፬ኛ	፲	ብር	
የ፭ ኛ	፯	ብር	
የ፮ኛ	፯	ብር	
የ፯ኛ	፯	ብር	
፳፬ ካርት ፖስታል	፩	ብር	
የሬኮማንዴ ደብተር	፫	ብር	
ሕገ መንግሥት	፭	ብር	
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳	መሐ	
የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት የአደን መንገዳቸው ታሪክ	፳	መሐ	
አጭር የዓለም ታሪክ	፳	መሐ	
የበገና ሰላምታ ከመጻሕፍት የተሰማማ	፳	መሐ	
ስለ ነቀርሳና ሳል ምክር	፳	መሐ	
ያማርኛ ምሳሌ	፳	መሐ	
አሳብና ምኞት	፬	መሐ	
የፍቅር መላከት	፬	መሐ	
ትምህርተ ሕፃናት	፬	መሐ	
የምሕረት አዋጅ	፬	መሐ	
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪	መሐ	
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪	መሐ	
የንቍጣጣሽ ግጥም	፪	መሐ	
ስለ አውሮጳ መንገድ የምክር ቃል	፪	መሐ	
፩ ጋዜጣ	፪	መሐ	
አር፡ ማላብ	፬	መሐ	
የጃንሆይ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፬	መሐ	
የእቴጌ ፎቶግራፍ ባለዘውድ	፬	መሐ	
ትንሽ ማስታወሻ ሌጣ	፩	መሐ	
የአለቃ ገብረ መድኅን መታሰቢያ	፩	መሐ	
ክላንድሬ	፳	መሐ	
ትንሽ ደብተር የማብዛት መማሪ	፩	መሐ	
የኪስ ማስታወሻ የነገሥታት ታሪክ ያለበት	፳	መሐ	
ስለ ሕገ መንግሥት ስብከት	፬	መሐ	
☛ ሁለተኛ የ፲፱፻፳፫ ዓመት ምሕረት የሕገ መንግሥት ስብከት	፬	መሐ	

ደግሞ የደብዳቤ ወረቀት እጥፍ ። ነጠላ በያይነቱ ። እርሳስ መንገልና ብረት ብርዕ ቀለም በያይነቱ። የካርት ቢዚት እንቦልብና ካርት ቢዚት በያይነቱ ። እንቦልብ ትልቅና ትንሽ በያይነቱ በርካሽ ዋጋ ታገኛላችሁ ።

ማስታወቂያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ ፥ የደረት የጉበት ፥ የኵላሊት ፥ የጅማት ፥ የጨብጥ የቂጥኝና ፥ የቋቁቻ ፥ የሚያዋልድ ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ኀርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዣና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርከፍ ቤት ይገኛል ።

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቆሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋናታኪስ ወከሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዶች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና ብዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቀሩረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

እስከ መስቀል ድረስ አንድ የቤተ ሰብ መኪና የገዛ ሰው ደህና ሽልማት ያገኛል ።

በርቱ ይኸ እድል አያምልጣችሁ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል ። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል ።

ከአገራቸውም ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሁሉ ሥራቸውን መጀመራቸውን ለሕዝብ ያስታውቃሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ካገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሜሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪሉ፤ው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዘር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና ነስሙሬ

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፵፯
8me ANNE. № 47

ሐሙስ ኅዳር ፰ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 17 Novembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ፡

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ሀገር ፍቅርና ስለመንግሥት እርዳታ

ባለፈው ዘመን የውጭ ነገሥታት ታላቅ ጦርነት አድርገው በነበሩ ጊዜ ፩የመንግሥት አገልጋይ ስለሀገሩ ፍቅር የሠራው ሥራ እጅግ የሚያስደንቅና የሚያስመሰግን ነው።በጠረፍ ከተማ አቅራቢያ ፲ሜትር ከፍ የሚሆን በሲሚንቶ የተገነባ የኤሌክትሪክ መብራት ማቆሚያ ከባሕር ውስጥ ስለአለ መርከቦች ሲተላለፉ ኤሌክትሪኩ ይበራ ነበርና ከዚያው ከባሕር ውስጥ ሰውዬው ዓሣ አጥማጅ እየመሰለ ብቻውን በጀልባ እየሔደ ግምቡን ሰርስሮ ውስጡን መደብ ለብዙ ቀን የሚበቃውን ስንቅና መሣሪያውን ይዞ ጀልባውን ጠቅልሎ ፩ ራሱን ገባ።የሰረሰረውም ግምብ እንዳይታወቅበት የሚመስለውን ቀለም ቀብቶታልና የሚተላለፉት መርከበኞች አይጠረጥሩትም ነበር ይባላል። ፪ኛ፡ ከዚህም በኋላ የጦርና የንግድ መርከቦች የሚተላለፉት በዚያው መንገድ ስለሆነ ለጦር ሚኒስቴሩ መርከብ ማለፉን በቴሌግራፍ ሳንፊል ሲአሳልፍና የሳንፊሉ መኪና በቆመበት ቦታ ሁሉ ቃሉ እየተጻፈ ስለተገኘ ሰውየው ያለበትን ቦታ ለመመርመርና ለማወቅ በብዙ ድካም ፈልገው ስለአጡት የከተማውን ሰው በብዙ ይመረምሩት ነበር ይባላል።ሰውየው ግን ከትዳሩና ከዘመዶቹ ይልቁንም ከሕይወቱ የሀገሩ ፍቅር የሚበልጥበት ስለሆነ ጦርነቱ ተጀምሮ እስኪጨረስ ድረስ እርዳታውን አላቋረጠም ። ሐሳቡ ሁሉ ለመንግሥቱ መቆምና ለሀገሩ ልማት እንጂ ለራሱ ከቶ ምንም አያስታውስም ነበር ይባላል። ይህነኑ በእንደዚህ ያለ ትጋት የጀመረውን ሥራ በእግዚአብሔር ኃይል ፈጽመና ወደ ሀገሩ ሲገባ በብዙ ደስታና ለዘለዓለም በሚሆን በማይረሳ መታሰቢያ ተቀበሉት።ታላቅ ሐውልትም ሊሠሩለት ነው ይባላል። ፫ኛ፥ የውጭ ሀገር መኳንንት ስለሀገራቸውና ስለመንግሥታቸው እርዳታ በማያውቁት ሀገር በአፍሪካ ዞሯ ያየናቸውና የምንሰማቸው በሐሩርና በበሽታ ቅላታቸውን ለጥቁረት፥ ክብረታቸውን ለችግር፥ ደስታቸውን ለንዴት፥ ተድላቸውን ለጕስቍልና፥ ሕይወታቸውን ለሞት ለውጠው ከረማውያንና ከራዊት ጋራ ታግለው የበሉትን በልተው የለበሱትን ለብሰው፥የሞቱት ሙተው የተረፉት ያበቶቻቸውን ጅምር ሥልጣኔ እስከ መጨረሻው ያደርሱታል፥በየተሰጣቸውም ማዕርግ ሀገር እንዲቀና፥ ሕዝብ እንዳይበደል ሥራ ለሌለው ሥራ እየሰጡ ሀገሩ የሚሰጠውን ጥቅም የተራሮችን አቀማመጥ ልዩ ልዩ ለሞተርና ለአትክልት የሚሆኑ የብዙ ወንዞች ፈሳሾች እንዴት እንዲሆኑ ፥ የታላላቆች ሜዳዎችና ረግረጎች ምን እንዲሰጡ የቆላውና የደጋው አየር ለምን እንደሚስማማ በበረሃ ያለ ከሁሉ የሚበልጥ ጥቅም መኖሩን በየጊዜው በራፖር ያስታውቃሉ። እንደዚህም መሆናቸው ስለሀገራቸው ፍቅርና ስለመንግሥታቸው እርዳታ ነው። ፬ኛ፥ ሰው ሁኖ ተፈጥሮ ባለው ዓቅሙና በሚቻለው ነገር ሁሉ ሀገሩንና መንግሥቱን ለመርዳት ቢጣጣር የከበረችና የተመሰገነች ሀገሩን በጣም ደስ ያሰኛታል።ከልጅም ከአትክልትም ከማናቸውም ሁሉ ሀገር ትበልጣለችና።፭ኛ፥ የኢትዮጵያ ወዳጆች ሆይ ሀገራችን ኢትዮጵያ በጸሎቷና በተራሮቿ ይልቁንም በከፍታዋ የምትኰራ ሌላ የማታውቀው የድንግሊቱ አገልጋዮች ፍቅር ማለት መጀመሪ እግዚአብሔርን መፍራትና ሀገርን መጥቀም፥መንግሥትን መውደድ ነው። እርስ በርሳችን መስማማትና ነፋስ እንዳይገባን በአንድነት ሁነን ለምለሚቱ አገራችንን ለመርዳት ማሰብ እንዲገባ ማወቅ ነው።ድር ቢአብር አንበሳ ያስር እንደሚሉት ሁሉ ይህም በየጊዜው ሁከት እያደረግን ደጉ ንጉሣችንን ሥራ ማስፈታት በጣም ይጐዳናል እንጂ አይጠቅመንም። በፍቅርና በአንድነት ተሳስራ የምትኖረውን ኢትዮጵያን በሐሰተኛ ፖለቲካ እርስ በራሳችን ያለመስማማት በጣም ያሰዝነናል። የፖለቲክንም መንገድ ለወደፊቱ ማወቅና መጠንቀቅ ያስፈልገናል። ፊታውራሪ ፈንታ ።

ሥራ ለማግኘት እውጭ አገር እየሔዱ ስለሚኰላሉ የኢትዮጵያ ሰዎች ።

አገራችን ላለ ሰው እውጭ አገር ያሉት የኢትዮጵያ ሰዎች በጣም ጥቂቶች ይመስሉታል ። እኛም እንዲሁ ይመስለን ነበር። ነገር ግን አሁን እያየነው ይህ ሐሰት መሆኑን ተረዳነው። እውጭ አገር ያሉት ኢትዮጵያውያን ብዙ ናቸው፥ የሚበልጡት ኢትዮጵያውያንም የሚገኙባቸው አገሮች ትሪፖሊ፥ሱዳን፥ ግብፅ፥ኢየሩሳሌም ናቸው። አውሮፓ ያሉት ብዙ አይደሉም እነዚህ ኢትዮጵያውያን እውጭ አገር ያሉበትን ምክንያት ብንፈልግ ሁለት ዋነኞች እናገኛለን ።

፩ኛ ፤ ለትምህርት ።
፪ኛ ፤ ሥራ ለመፈለግ ።

ለትምህርት የሚወጡት ሰዎች ታገር ተዘመድ ተለይተው መማራቸው በኋላ አገራቸውን የሚያገለግሉ ስለሆነ ለሚበልጡት መንግሥት ነው የሚከፍልላቸው።ስለዚህ ጉዳት አያገኛቸውም ለማለት ይቻላል ።

ሥራ ለመሥራት የሚወጡት ብዙዎች ናቸው አውጭ አገር መሔዳቸውም ተዱሮው የበለጠ ሥራና የበለጠ ደመወዝ እናገኛለን ብለው ነው ። እነዚህ ሰዎች እውነት ተዱሮአቸው ይበልጥ ደልቷቸው ይኖራሉን ። እንኳን ሊደላቸው የለት ምግባቸውንም በመከራ ነው የሚአገኙት። ታንድ አንዶቹ በቀር ታገራቸው ተወጡ ሐያ ሠላሳ ዓመት የሚሆናቸው ሌሎቹ እየተራቡና እየተከዙ ይኖራሉ ። ብዙዎቹም በራብና በብርድ ያልቃሉ ። አንድ የኢትዮጵያ መኰንን በመጣ ጊዜ ከአረፈበት ሆቴል ሔደው እንደ ተስከር ቤት የሚከቡት ስንቶች ናቸው? እየተማሪቤቶቻችን እየመጡ አጠጡን አብሉን አልብሱን እያሉ ሲያሳዝኑን ያለንን ሰጥተን ሔዱ ያልናቸው እንደሆን እንሔድም ብዙ ገንዘብ ስጡን ወደ ሀገራችንም መልሱን ይሉናል ። እንዲህ ሀገራችንን ስትወዷት ለምን ጥላችኋት መጣችሁ ያልናቸው እንደሆን ይህን መቼ እናውቅ ነበር ። የመጣን ጊዜ እግራችንን በቆረጠው ብለው ታገራቸው ተመጡ የደረሰባቸውን መከራ ያወሩልናል ያገኛቸውንም ሁሉ ለማውራት አንድ መጽሐፍ ስለማይበቃኝ ክቡራን አንባቢዎችን ፈቃድ ጠይቄ የሦስት ኢትዮጵያውያን ታሪክ እጀምራለሁ ።

መጀመሪያ አንድ ቀን ከእስክንድርያ ወደ ባላገር ለመናፈስ ታስተማሪዎቻችን ጋር ሔደን በስድስት ሰዓት እዛፍ ሥር ምሳችንን ስንበላ ከኋላችን በኢትዮጵያ ንግግር ጤና ይስጥልኝ የሚል ድምጽ ሰማን ። በድንጋጤ መለስ ብንል አንድ ጥቁር ሰው ባዶ እግሩን ያለቀ ልብስ የለበሰ አየን ሰላምታም ከተሰጣጠን በኋላ አንድ ትልቅ ወረቀት ነጥሎ የግብፅ ንጉሥ ሥዕል ያለበትን አሳየን ወዲያው እኔ ነኝ የሣልኩት አለን። በሥዕሉም ማማር ስንደቅ ቢያየን ኑ ሌላ አሳያችኋለሁ ብሎ ወደ አንድ ቤት ወሰደን ቤቱም በውጭ ቆሻሻ ይመስላል ። ነገር ግን ብንገባ እውነተኛ ቤተክርስቲያን ውሥጥ ያለን መሰለን (ማለት) ውሥጡ በጌታችን በመቤታችን በሚከኤልበገብርኤል በሌላም ታቦታት ሥዕሎች አምሩዋል ይኸነንም እኔ ነኝ የሣልኩት አለን እንደዚህ ያለ ሥዕል ሣይሁነህ ለምን ታገርህ ወጣህ እዚህስ እንደምንድነው ያለኸው አልነው የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አሽከር ሁኜ ለቤተ ክርስቲያን ሥዕል እሥል ነበር ጌታዬ ቢሞቱ ዓለም በቃኝ ብዬ መጣሁ እዚህም የቡና ሻጭ አሽከር ሁኜ ስኒ አጣቢ ነኝ ጌታዬም የሚበቃኝን ያህል መብልና መጠጥ አይሰጡኝም እያለ ይበሳጭ ጀመር ። አገርህ መመነኛ ስፍራ አጥተህ ነውን ወደዚህ ድረስ የመጣኸው አልነው ። የመጣሁበት ቀን የተረገመች ትሁን እያለ ያማርር ጀመር እኛም ያለንን መሐለቅ ሰጥተነው አሮጌ ልብስም መጥቶ እንዲወስድ ነግረነውና ይህ ሰው አገሩ ቢቀመጥ እንዴት ተመችቶት በኖረ ነበር እያልን እያዘንን ሔድን።

ሁለተኛ እግብፅ አገር የመንፈሳዊ ትምህርት ለመማር ወጥተው በጉዳት ምክንያት አገራቸው ከተመለሱት አንዱ እተማሪ ቤታችን መጥቶ ሰላምታ ሰጠን። እኛም አልተመቸንም አገራችን መልሱን ብትሉ ደጉ ንጉሣችን ልመናችሁን ፈጽመውላችሁ ነበር አሁንም ተመለስ እዚህ ምን ትሠራለህ አልነው እሱም እንዲህ አለን ጃንሆይ ትምህርት የሚፈልግ ይማር የሚሠራም ይሥራ ብለውን ነበር ባልንጀሮቼም ግማሾቹ ይሠራሉ ግማሾቹም ይማራሉ እኔ ግን እውጭ አገር እሠራለሁ ብዬ መጣሁ ተመጣሁም ፫ ወር ነው ። እፖርትሳይድ ሳህን አጣቢ ነበርኩ አሁን ተዚያ አስወጥተውኝ ሥራ ባጣ እንድትፈልጉልኝ ብዬ መጣሁ ። አንተስ ምንም አታሳዝን ብትፈልግ ተማር ብትፈልግ ሥራ የሚል የማይገኝ ንጉሥ አገር ጥለህ ተጐዳሁበት አልሀበት አገር ተመልሰህ በመምጣትህ እብድ ያሰኝሀል እዚህ ዘመድ ስለሌለን ምንም ልናደርግልህ አንችልም አልነው ።

ሦስተኛ፡ ተእስክንድርያ ወደ ፈረንሣዊ አገር ትምህርቴን ለመቀጠል ስሔድ እመርከብ በተሳፈርሁበት ማግስት ጡዋት ፀሐይ እየሞቅሁ እውጭ ቁሜ ሳለሁ አንድ ጠይም ሰው በማርኛ እንዴት አደርህ አለኝ እኔም እዚያ እውጭ ከሰዎች መሀል አንድ ኢትዮጵያዊ በማግኘቴ በጣም ደስ ብሎኝ ሰላምታ ተሰጠሁት በኋላ ወሬውን ጠየቅሁት እሱም እንዲህ አለኝ ወንድሜ ሆይ ይኸው እህል ውኃ ተቀመስሁ ሁለተኛዬ ቀን ሊሆን ነው። እባሕር ላይ ሁኜ ውኃ ሲጠማኝ በጣም ይገርመኛል። ዘልዬም ለመጥለቅ ይቃጣኛል ትኒሽ ስቆይ ሳላደርገው አልቀርም በኪሴም አንድም ቤሳ የለኝም አለኝና ወዲያው እመብል ቤት ወስጄ የሚበላውና የሚጠጣውን ገዝቼ ሰጠሁት እስቲ እየበላህ ወሬህን ጨርስልኝ አልኩት። እግብፅ አገር ሁኜ የአናጺነትን ሥራ እሠራ ነበር አሁን ግን ጌታዬ አልፈልግም ብሎ ቢያሰናብተኝ እፈረንሣዊ አገር ሥራ አገኛለሁ ብዬ መምጣቴ ነበር በሣጥኔ ውሥጥ ልብሴን የይለፍ ወረቀቴን ስምንት ወርቅ አድርጌ እመርከብ መሳፈሪያ ደርሼ አቃዬን አጉምሩክ ለማሳዮት ስሔድ አንድ ዓረብ ሁሉንም በደንቡ አስደርጌ የይለፍ ወረቀትህንም አስፈርሜ አመጣልሀለሁ አንተ እመርከብ ላይ ቆዬኝ አለኝ እውነት ነው አገሩን በጣም አላውቀው ምንም ነገር ሳላደርግ መርከቡ ያመልጠኛል እንግዳ እንደዚህ በመቀበላችሁ እግዚአብሔር ይባርካችሁ ብዬ ሣጥኔን ሰጥቼው እኔም ሰው እንደሚለኝ እመርከብ መውጫ ባሥር ፍራንክ ገዝቼ እመርከብ ገባሁ ግን ያ ጺድቅ የመሰለኝ ዓረብ ለካ ሰይጣን ኑሩዋል ብጠብቀው ብጠብቀው ሳይመጣ መርከቡ እላዩ እንደሆንሁ ተነሥቶ ሔደ። ብሎ ይህንን ባወራልኝ ጊዜ ምንም ሰውዬው ቢያሳዝነኝ ለመሳቅ አልተመለስሁም እግብፅ አገር ሥራ ብታጣ እፈረንሣዊ አገር አገኛለሁ ብለህ ኑሩዋልን እፈረንሣዊ አገር እንደብዙዎቹ አገሮች የውጭ አገር ሰው ሥራ እንዳይዝ መከልከሉን አታውቅምን አልሁት። አላውቅም ነበር ነገር ግን የአናጺነት ሥራ ባጣ ያለ ሽበ ስልክ ሥራ አውቃለሁ በዚህ አገኛለሁ መስሎኝ ነበር። መጀመሪያ ዲፕሎም የለህም ቢኖርህም እዚያ ልትሠራ አትችልም የይለፍ ወረቀት ስለሌለህና የመርከብ ዋጋ ስላልከፈልህ ሹማምንቶቹ ይይዙሀል እስከዚያ ድረስ ለስንቅ የሰጡኝን እየተከፈልንእንቀመጣለን አልሁት። በሁለተኛው ቀን የመርከቡ ሰላይ ያዘውና ወደ ካፒቴኑ ወስዶት ሌባ መስሏቸው ሊያጉላሉት ሲ-

ሆን ለመርከቡ አለቃ አለመስረቁንና ሌባ አለመሆኑን አስረዳሁት እሱም ይህ ሰው ሁለት ጊዜ ጥፋተኛ ነው አለኝ፡፩ኛ በፈረንሳዊ መንግሥት በኩል የይለፍ ወረቀት ስለሌለው። ፪ኛ በመርከቡ ማኅበር በኩል መሳፈሪያውን ስላልከፈለ፡አሁን ምን ታደርጉታላችሁ ብለው አሥረን እመጣበት እግብፅ አገር መልሰን ለመንግሥቱ እናሳልፈዋለን የግብፅ መንግሥት ስድስት ወር አሥሮ ይለቀዋል አለኝ እኔም ምንም ለማድረግ ስላልቻልሁ እያዘንሁ ሔድሁ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ሰው የሚሔድበትን አገር አስተዳደርና አኑዋኑዋር አይጠይቅምን ? እነዚህ ሦስት ሰዎች አንደኛው ያለሽበ የስልክ ሥራ እያወቀ፤ሁለተኛው የሥዕል ነገር እያወቀ፤ ሦስተኛው ሥራ ወይም ተማር ሲሉት ትቶ ተመችቷቸው የሚኖሩበትን አገር ትተው እውጭ አገር ሔደው ሲጉላሉ ያሳዝናሉ ።

ይህንም መጻፌ መጀመሪያ በየጠረፉ ላሉ ክቡራን አገረገዦች ጥበቃውን ማጠንከር ማስፈለጉን ለማሳሰብ ነው የሚበልጡት ኢትዮጵያውያን እላይ እንዳልሁት እትሪፖሊ፡ሱዳን፤ግብፅ፤ ኢየሩሳሌም ነው ያሉት (ማለት ወደኢትዮጵያ ቀረብ ያሉ አገሮች እነዚህም ኢትዮጵያውያን የይለፍ ወረቀት ሳይረኙቸው እፈረንሳዊ ወይም እንግሊዝ አገር እንሔዳልን ብለው በእግራቸው ደነማሉ ቴንሽ እንደሔዱ ያችው የያዙዋት ገንዘብ ታልቅ ባቸውና እዚያው እደረሱበት (ሱዳን ግብፅ መቅረት የግድ ይሆንባቸዋል።

ሁለተኛ ለክቡራን ብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እውጭ አገር እሔዳለሁ ለሚለው ሰው ሁሉ ሁሉንም ነገር እንዲያስረዱት የፈረንጅ አገር ገንዘብ ማፈሻ እንዳይደለ ዲፕሎም የሌለው ሰው ለመሥራት አለመቻሉን ዲፕሎምም ቢኖር ለውጭ አገር ሰው በሚበልጡት አገሮች ሥራ አለመፈቀዱን እንዲያስታውቁ ለመለመን ነው ።

አክሊል ሀ ወ ።

ስለ ወይዘሮ ባፈና ዕረፍት።

ወይዘሮ ባፈና የደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ልጅ የልዑል ራስ መኰንን እናት የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አክስት በጠባያቸው እጅግ የተመሰገኑ ነበሩ ። ደኅና ደኅና ልጆችም አሏቸው ። የልጆቻቸውም ስም ቀጥሎ የተጻፈው ነው። የመጀመሪያ ልጃቸው ወይዘሮ ከፈይ። ሁለተኛው ልጃቸው ፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴ። ሦስተኛው ፊታውራሪ ወዳጆ። ፬ኛ፥ ወይዘሮ ታየች። ፭ኛ፥ ልጅ ለማ። ፮ኛ፥ ወይዘሮ ላቀች። ፯ኛ፥ ወይዘሮ ሙላተ ወርቅ ናቸው።ባለቤታቸው የፊታውራሪ ገብረየስ ልጅ ፊታውራሪ ዘርፉ ነበሩ። እጅግም መንፈሳዊት ነበሩ። ዕድሜአቸውም ፹፱ ዓመት ነው። ወይዘሮ ባፈናም ደኅና ጠባይ ስለነበራቸው ከዘምድናቸው ይልቅ በጠባያቸው ማማር በጃንሆይ ዘንድ እጅግ የተወደዱ ስለሆኑ በላይኛው ግቢ አቅራቢያ ቤት ተሠርቶላቸው ሲኖሩ በድንገተኛ ሕማም ታመው በኅዳር ፫ ቀን ዐርፈው ጃንሆይና እቴጌ ጳጳሳትና መሳፍንት፥ ካህናትና ሊቃውንት፥ ወይዛዝርና መኳንንት ሕዝብና ሠራዊት አልቅሰውላቸው በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበሩ። ብርሃንና ሰላም እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን፤ ልጆቻቸውንና ኀዘንተኞችን ሁሉ ያፅናናል ።

ሹም ሽር ።

ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ በታዘዘበት ቦታ ሁሉ ጌታውን ደስ ስለአሰኘ በአንድ ዓመት ብዙ ክብርና ሽልማት ተቀብሎዋል።ነጋድራስ ተብሎ ማዕርግ ተቀብሎ ወደጎጃም እንደሔደ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሁሉ ታውቃላችሁ ። አሁንም በስልክ ተጠርቶ በአይሮፕላን በኅዳር ፫ቀን መጥቶ በማግሥቱ ማዕርግ ያለው ሽልማት ተሸልሞ የማዘጋጃቤትን ዲሬክተርነት ተሾመ።ተረት ቢሰነብት ይሆናል እውነት እንደተባለው ከሰማይ አውርዶ ሰጠው ተብሎ መልካም ስጦታ በተቀበለ ሰው የሚተረተው ተረት እውነት ሁኖ ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊን በአይሮፕላን አስመጥተው ጃንሆይ ስለሾሙት ሕዝብ ሁሉ ተደነቀ፥ ብርሃንና ሰላም ሹመት ያዳብር እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ወይዘሮ ቀለመ ወርቅ አባ ፋርዳ ።

ስለ ክብርት ወይዘሮ ቀለመ ወርቅ ሞት ።

አባቷ ፊታውራሪ አባ ፋርዳ የትልቁ ያቶ በዛብህ ልጅ ነበሩ ያቶ በዛብህንም ታሪክ ከብዙ በጥቂቱ እንጽፋለን። አቶ በዛብህ በኢትዮጵያ የታወቁ አርበኛ ነበሩ የፈረሶቻቸውም ስም ቦሬ ጠለፉ የጦሮቻቸውም ስም አንዱ ተልባ መጠጥ አንዱ ሰው በሌ ነበር ይባላል።በእነዚህም ጦሮች ከፈረስ ላይ እንዳሉ በጨ

በጣ ይወጉባቸው ነበር እንጂ አይወረውሩአቸውም ነበር ይባላል። በጀግንነት አረመኔን አስፈርተው አርበኞቻቸውን አንቀተው ሲኖሩ ነበር። ልጃቸውም ፊታውራሪ አባ ቶርዳ ለፈጣሪአቸው ተገዥ፤ ለመንግሥታቸው አገልጋይ፤ ሰው አክባሪ እግዚአብሔርን ፈሪ፤ ደግ ሰው ነበሩ፤ ከደግነታቸውም የተነሣ እንኳን ልጆቻቸውን የቤት አሽከሮቻቸውን እንኳ አይማቱም ነበር ይባላል

የወለዷቸውም ልጆች ፭ ሴቶችና ፲ ወንዶች ነበሩ ፤ ከነዚሁም ልጆች ያዕቆብ ከልጆቹ ሁሉ ዮሴፍን እንዲወድ ቀለመ ወርቅን ከሁሉ አብልጠው ይወዷት ነበር እርሷም ገና ሕፃን ሁና አባቷ አረፉ ። እናቷም በዚያው ዓመት ዐረፉ ። ከዚያም ወዲህ ቀኛዝማች ኃይሉ አባ ቶርዳ እንደአባት፤ ወይዘሮ አስከለ እንደናት ሁነው አሳድገው ለዓቅመ አዳም ስትደርስ ለቀኛዝማች ኤፍሬም ዘውዱ ድረዋት በሕግ ጸንታ ስትኖር ወይዘሮ አስካለ እኅቷ በድንገት ስለታመሙ እየተመላለሰች ስትጠይቅ ውላ አድራ በጥቅምት ፱ ቀን ታማ እሑድ ወንድ ልጅ አስወርዳት በታመመች በ፰ ቀን፤ በተዳረች በ፰ ዓመት፤ በተወለደች በ፲፱ ዓመት በጥቅምት ፲ ቀን ዐርፋ ባሏና ወንድሞቿ በአቶሞቢል ወስደው ከእናት ከአባቷ መቃብር ደብረ ሊባኖስ በክብር ተቀበረች ።

አብረው ከተወለዷቸውም የሞቱት ስለበረከቱ የእሷንም ሞት ወይዘሮ አስከለ በሕመማቸው ሰዓት የተነሣ አልተረዱም ነበረና ባረፈች በ፰ ቀን ሰሙ ። ከሁን በፊትም በየጊዜው የሞቱት ወይዘሮ ደስታ፤ወ ዠማነሽ፤ወ ላቀች፤ ልጅ ደምሴ፤ልጅ እየለ የእነዚህ ሁሉ መቃብራቸው አንድ ላይ ነው ። እኅቷም ወይዘሮ አስከለ ከዚህ በታች ያለውን የልቅሶ ግጥም ገጠሙ።

አባቴም እናቴም እኅቶቼም ወንድሞቼ ሁሉም አለቁብኝ። ከላንቺ አልቀረኝም እኅቴ አትረቂኝ ። ሞትሽን ብሰማ ልቤን ውጋት ያዘኝ ። ዛሬስ አልቻለውም በጣም ደነዘዘኝ ። ዘመዶቼ ሁሉ ሔዱ በጐዳና ። ልጅ እንኳን አልወለድሁ ልቤን የሚያጽናና ። እኔማ አለች ብዬ ጥሩልኝ እላለሁ ። እንደዚህ መከዳቷን መሔዷን የት አየሁ።እንዲያው ምን እላለሁ ጠንክሬ ናት ነፍሴ። ዓይኔም እጄም እግሬም ሙቷል ልጅ ደምሴ ። እንደምን ደስ ባለኝ ቀንና ሌሊት ። ከመቃብር ወጥታ እቴን ባገኘኋት ። ማርታና ማርያም አማልዱ እባካችሁ ። ከመቃብር ወዲያ ወንድም ከሰጣችሁ። ዓይንሽ ተከደነ ተገነዘ ጣትሽ ። የማልቀር ነኝና አንቺን እያለብኩሽ፤በጭንቅ ታምሜ አላየችኝም።መጥታ አልጠየቀችኝ ብዬ ስቀየም። ተለያይተን ቀረን እስከዘላለም። እትሽ የናትሽ ልጅ እንከን የሌለብኝ ። በቁርጥ ስትሔጂም ነው ሳትልኪብኝ ። አባትና እናትሽ እቶችሽም ሁሉ ሳይድሩሽ ቀርተዋል ብለን ስናማቸው ። ቤት ማያ ጠሩሽወይ ዜጋመል ቤታቸው ። ሰኞ ሔድሽ አሉ ሰኞ ተጠርተሽ። ምነው ቀለመ ወርቅ ለመሔድ ፈጠንሽ ። ባንድ ቀን ደረሽ ወይ ያን እሩቅ መንገድ ። እንዳንች በቀሎ ነወይ ሁሉ የሚሔድ ። ኃዘን መጣች አሉ ቤቷን አደራጅታ ። ደስታ ከጠፋች ብዙ ቀን ሰንብታ ። አባቴ ተጐዳሁ እናቴ ተጐዳሁ ብዙ ልጅ ወልደው ። ያ ይከተለኛል ያንን ስወጣው ፤በሰው ተራ ለፋሁ ለኔስ ቀን ማነው ። ምነዋ ዘነጋሽ ምነዋ ሰነፍሽ ። ወየው ቀለመ ወርቅ አለፈ አዝመራሽ ። ዘር ከተላለፈ የት ይገኝ መስሎሽ ። ወደስታ ወ ዠማነሽ ወ ላቀች አፈርና ድንጋይ አይችል አንገታችሁ። መጣች ቀለመ ወርቅ ትራስ ልትሆናችሁ ። ከናንተማ ይልቅ ቲኒሹዋ አወቀች ። ላባቴም ለናቴ ለቴ ለወንድሚ ትራስ ልሁን አለች ።

ከኃዘንተኞች አንዱ ።

ስለ ቀኛዝማች ቡኔ ዕረፍት።

ቀኛዝማች ቡኔ ከልጅነታቸው ጀምረው የልዑል ራስ መኰንን አሽከር ነበሩ። ጌታቸውም እጅግ ይወዷቸው ነበሩና የእኅታቸውን ልጅ ድረውላቸው ብዙ ልጆች ወልደው ነበር። የሞቱት ሙተው አሁንም ደኅና ደኅና ልጆች አሏቸው። ታላቁ ልጃቸው ቀኛዝማች ተሰማ ቡኔ በታላቅ ታማኝነት ሥራ ተቀምጠዋል። መቸም የቀድሞ ሰዎች ደጅ ጠኚዎች ናቸውና በደጅ ጥናት ምክንያት አዲስ አበባ ከርመው በድንገተኛ ሕማም ታመው በጥቅምት ፳፪ ቀን ዐርፈው በማግሥቱ በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ። ቀኛዝማች ቡኔ እጅግ ጠባየ መልካም ስለነበሩ ሰው ሁሉ ይወዳቸው ነበርና ልጆቻቸው በሌሉ ጊዜ በመሞታቸው እጅግ አዘኑ። አንዱ ልጃቸው ልጅ ግዛው ቡኔ ግን የዘበኛ አለቃ ሁኖ ወደ ጐጃም ሔዶ የነበረው በኅዳር ፫ ቀን ከነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ ጋራ በአይሮፕላን መጣ። የቀሩት ልጆቻቸው ገና አልመጡም።

ደግሞ የፊታውራሪ ላንቻ ይደሩ ልጅ ወይዘሮ ፀዳለ ማርያም መልከ መልካም ጠባየ መልካም ነበረች። አባቷም እጅግ ይወዷት ነበር። በድንገተኛ ሕማም ታማ በኅዳር ፩ ቀን ሙታ በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በብዙ ክብር ተቀበረች። ዕድሜዋ ገና ፲፰ ዓመት ነው። ብርሃንና ሰላም የመቅሠፍት ጊዜ በመሆኑ የልቅሶው ጽሕፈት ብዙ ቦታ ስለያዘበት እያዘነ ኀዘንተኞችን ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ ይላል።

ደግሞ የአቶ ጠገዬ ልጅ በታመመ በ፱ተኛ ቀን በማይታወቅ በሽታ በኅዳር ፫ ቀን ሙቶ በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ ። ሕፃኑም ብልህ ነበረ ይባላል ዕድሜውም ገና ፱ ዓመት ነው።

☞ ማስታወቂያ።

ሺ፱፻፳፭ ዓመተ ምሕረት ኅዳር ፲፩ ቀን እሑድ ከእኩለ ቀን በኋላ ልክ በ፰ት ሰዓት ተኩል በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት በአለው የቴአትር ቤት የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ተማሪዎች ቴአትር የሚአሳዩ ስለ ሆነ በዚሁ ቀን መሳፍንቱና መኳንንቱ ፤ ወይዛዝሩም ሁሉ እንዲመጡ ቀጠሮ ተደርጓልና ይህንኑ ቴአትር ለማየት የምትፈቅዱ ሰዎች የተቈረጠውን ጥቂት ዋጋ እየከፈላችሁ ገብታችሁ ለማየት ትችላላችሁ። የሚታየውም የቴአትር ዓይነት ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው።

መጀመሪያ፤ ዳዲ ቱራ (የጋሎች ደንብ በአማርኛ ቴአትር)

ሁለተኛ፤ ክቡር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ያወጡት ቴአትር በበጎችና በአውሬዎች ምሳሌ ሁኖ የሰውን ሁኔታ የሚአሳይ።

ሦስተኛ፤ እመት እታላይ ባላቸውን እያ መታለያን እንዳስታመሙ እነዚህ ሦስቱ ቴአትሮች ይታያሉ።

ዋጋውም ከሦስት ተከፍሏል።

፩ኛ ማዕርግ ፫ ብር።
፪ኛ ማዕርግ ፪ ብር።
፫ኛ ማዕርግ ፩ ብር። ቁመጡ ለሚያዩት ግን ፩ ሩብ ብቻ ተቈርጧል።

ይህንኑ የፈቃድ ወረቀት ለመግዛት የፈለገ ሰው በቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ይሸጣልና ከ፪ ሰዓት እስከ ፮ት፥ ከ፰ት እስከ ፲፩ ሰዓት ሊገዛ የሚቻል መሆኑን እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ ።

፩ኛ፤ጥንት የቈየውን ሕግ ተከትሎ ለጨርጨር አውራጃ የተሰጠው ደንብ ማንም ሰው ቢሆን ስለርስቱ ለመንግሥት የሚገባውን ግብር በየመቱ ሳይገብር እስከ ፫ ዓመት ያስታጉለ እንደሆነ ርስቱ ንቅል መሆኑን ባምሰ አምስት(፶፭)ገጽ ባሥር(፲) አንቀጽ ወስኖ አስታውቋልና ስለዚህ በጨርጨር አውራጃ ርስት ያለው ሰው የ፫ ዓመት ወይም ከዚህ በላይ ውዝፍ ግብር ያለበት በኅዳር ፴ ቀን ድረስ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ግብሩን ከነመቀጫው ለማግኘት መሬቱን በሐራጅ መሸጣችንን እናስታውቃል።

፪ኛ፡መሬቱ በሐራጅ ሲሸጥ መንግሥት ከሚፈልገው ግብር በላይ ገንዘብ የተገኘ እንደሆነ ለባለ መሬቱ ይሰጣል፡ አዛዥ ወርቅነህ።

ማስታወቂያ

ከዚህ በታች በዝርዝር የተጻፉት ከሰፈሩ ወደሰፈሩ የማይዘዋወሩ የሚ፡ቱ የባንማሊ ቢርጂ ንብረቶች ቀዳሚ ታኅሣሥ ፳፪ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም በሐራጅ ይሸጣሉ ።

በአዲስ አበባ ከተማ ውሥጥ ወደለጋር በሚወስደው መንገድ አጠገብ ባለው በባንማሊ ቢርጂ ግቢ ሰባት ቤቶች ከነዚሁ ሁለቱ ፎቆችና ሁለቱ የሰቃ ቤቶች ናቸው ።

በአቡጀዲ ተራ የሺህ አሊ የነበረው አሁን የባንማሊ ቢርጂ የሆነ አንድ ሱቅ ።

በድሬ ዳዋ ከተማ ውሥጥ ከወደፊት ሱቅ ከወደኋላ ያትክልት ቦታ ያለበት አንድ ጥሩ ቤት ።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጻፉት ቤቶች ሁሉም ጥሩ ጥሩ ስለሆኑ ዋጋቸውም እንደጥራታቸው መጠን ነው ።

በአዲስ አበባ ያሉትን ቦታና ቤቶች ተራ በተራ ለመሸጥ ሐራጅ ተብሎ ጨረታ የሚጀመረው ከዚህ በላይ በተጻፈው ቀን ከእኩለ ቀን በኋላ ልክ በ፰ ሰዓትነው።እነዚሁ ቦታና ቤቶች የሚሸጡበትን የመጨረሻውን ዋጋ ከዚህ በታች በሻርጌው ፊርማውን የፈረመው ሰው ይወስናል ።

እነዚሁ ቦታና ቤቶች የሚሸጡት ከተወሰነው ዋጋ በላይ አብልጦ ለሰጠ ሰው ነው። ጨረታው የሚቆምበት የገንዘብ ልክ አስቀድሞ ከተወሰነው ዋጋ የአነሰ እንደሆነ ግን ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጥ እስኪገኝ በነገሩ ይታሰብበታል እንጂ ጨረታው በቆመበት በዝቅተኛው ዋጋ ነገሩ አይጨረስም ።

የነገሩ መወሰኛ ገዢ የሆነው ሰው አስቀድሞ የሚከፍለውን የቃብድ ገንዘብ ከሰጠ በኋላ ቀሪውን እስከ ሐያ አራት ሰዓት ጨርሶ የከፈለ እንደሆነ ነው የሚፈለግበትን ገንዘብ እስከ ሐያ አራት ሰዓት በሙሉ የአልከፈለ እንደሆነ ግን ቃብድ ሰጥቶበት የነበረው ቦታና ቤት እንደገና ሐራጅ ይባላልና በዚሁ ምክንያት የሚወጣው ገንዘብ ቃብድ ከተሰጠው ላይ ተነሥቶ ከዚህ ሌላ ደግሞ ከዚያው በቃብድ ስም ከተሰጠው ገንዘብ ላይ መቀጫ አንድ መቶ ብር ተነሥቶ ቀሪው ለባለገንዘቡ ይመለሳል ።

ከዚህ በላይ እንደተባለው ከተወሰነው ዋጋ በላይ አብልጦ በመስጠት ገዢ የሆነው ሰው የገዛበትን ዋጋ ጨርሶ እንደከፈለ የገዛውን ቦታና ቤት ወዲያው ይረከባል፤ በከርታውም ውሥጥ የሚያስፈልገው የቃል ጭማሪ ተደርጎ በስሙ ሊዛወርለት ይቻላል ።

እነዚሁኑ ቦታና ቤቶች የገዛ ሰው አሁን ያሉትን ተከራዮች ለማስወጣት የፈለገ እንደሆነ ከሦስት ወር በፊት ማስታወቅ አለበት ተከራዮቹም የሚከፍሉትን ኪራይ ግዢው ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ለገዢው ይሰጣሉ ።

ሻጩ፡ እነዚሁኑ የሚሸጣቸውን ቦታና ቤቶች አሁን እንደአሉበት አኳኋን ሸጦ ለገዢው ከአስረከበ በኋላ አስቀድሞም ቢሆን ወይም ግዢው ከተፈጸመበት ቀን ወዲህ የተበላሸ ነገር ቢገኝ ሊጠየቅ አይቻልም ።

በጨረታው ውሥጥ የሚጨመረው የገንዘብ ብልጫ በ፲፣ በ፳፣ በ፴ና እነዚህን በሚመስሉ ቍጥሮች እየተበላለጠ ይሄዳል እንጂ ከነዚህ ከተባሉት የአነሰ ቁጥር ቢጨመር ከብልጫ አይቆጠርም ።

በድሬ ደዋ ለአለው ቦታና ቤት ጨረታ የሚደረገው እዚያው ድሬ ደዋ ላይ ነው ሻጮቹም በድሬ ደዋ ያሉት እነሜስርስ ጂ ። ኤም ። ሞሐመዳሊና ኩባንያው ናቸው እንጂ ከዚህ በተቀር የሽያጩ አኳኋን ከዚህ በላይ እንደተጻፈው መሆኑን እናስታውቃለን ።

ጥቅምት ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም ተጻፈ አዲስ አበባ ።
ቲ ። ዲ አየር ።
የሚ፡ቱ የባንማሊ ቢርጂ ንብረት አድሚኒስትራተር

የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ሚኒስቴር
ማስታወቂያ ።

በሮፓ ቍጥር በነሐሴ ፳፩ቀን ፲፱፻፴ ዓ ምሕረት ፓሪስ ላይ ስለ ተፈረመው የጦር መሣሽ ውል ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቅደው በግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓመተ ምሕረት ስለጦር መሣሪያ እንደቆመው ደምብ መሣሪያ ለማስመጣት ፈቃድ ለሚጠይቁ ሰዎች የጽሕፈት ቤቱ ከቀድሞው ቦታ ተዛውሮ ወደላጋር መሔጃ ከመንገድ በላይ ከራስ ተሰማ ቦታ ከነበረው አዲስ ከተሠራው ቤት መቆሙን እናስታውቃለን ።

Ministère de la Guerre du Gouvernemet Ethiopien

AVIS

D'après le traité conclu a Paris le 21 Août 1930 nous portons à la connaissance du Public, que le Bureau de Réglementation du Trafic des Armes est trensféré à l'endroit où se trouvait la Propriété du Ras TASSAMA et à coté de l'avenue de la Gare à droite en venant de la ville (Immeuble tout neuf.)

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ ጊዜ እንዳስታወቀው የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ዕዳዎችን ቦታ ኅዳር ፲ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም ከጧቱ በ፬ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል።

የፊታውራሪ በዳኔ አሸግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፬፻፲ና ፲ሺ፯፻፶፩ ሜትር ካሬ።

የቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ አጥቢያው አማኑኤል ስፋቱ ፳፬ሺ ፳፱ ሜትር ካሬ።

የነጋድራስ ተፈራ ንጉሤ አጥቢያው ቂርቆስ ስፋቱ ፯ሺ፫፻፳ ሜትር ካሬ።

የወይዘሮ ዓመተ መንፈስ ቅዱስ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፬፻፷፯ ሜትር ካሬ።

የወይዘሮ ወለተየስ ሀብቱ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፪ሺ፫፻፹ ሜትር ካሬ።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ) አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሴጊያን ዘንድ ይገኛል ። ይህነኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተኩል ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

የሚሸጥ ቦታ

ማጀስቲክ ሆቴል አጠገብ ከሙሴ ሃርዲ ፊት ለፊት መሐመድአሊ ከሠራው አዲስ ርቅ በታች ጥሩ ጥሩ ቤት የተሠራበት በወሩ እስከ መቶ ብር ድረስ ኪራይ የሚያመጣ ጥሩ የሚሸጥ ቦታ አለና የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ አቡጀዲድ ገበያ ላይ ወችራጅ የሚባል ሂንዲን ጠይቁ።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

በዚሁም ጊዜያት ጠቅላላውን የሴቶችና የወንዶችን ውበቶች በሚያስረዳበት ጊዜ ግን ውቢቱ እመቤቴ ቀልጣፋና አቋቋመ መልክም እንድትሆን ይኸውም አየራመዘመናት ይፈቅዳል በሚያሳዝነው አቀማመጣቸው ብዙ ሰዎች በሽተኞች ናቸው ። ደግሞም በምግባቸው አኑዋኑዋር እንዲሁም በጨካኝነትና ችግረኛ መሆናቸው ለመዳንም አይችሉም ። ለነዚሁም ሰዎች ብዙ ጊዜ የተወደደና በእውነት የማይሳሳተውን መድኃኒት እንሰጣቸዋለን። ሊፖቶዴን የሚባለውን በጥቅልል ያለውን መድኃኒቴን በጣም ሲያስጨንቅዎትና ሲያምዎት ቢሞክሩት ሕመምዎን በማቅለሉ ብዙ ደስ ያሰኝዎታል በአዲስ አበባ ውሥጥ ግዙፎችንና ሰውነተ ቁጡ ለሆኑ ሰዎች አየሩ አለመስማማቱን ይልቁንም ከኔ የበለጠ ያውቁታል።ይልቁንም ደግሞ ዋና ማስረጃ እንቅልፍ ለሌለውና ለሚባንን ሰው ነው ።

ለነዚሁም ሰዎች ፈጽሞ የሚከለከልላቸውን ዲአል ኮምፕሬሜ የሚባለውን መድኃኒታችንን በጣሙ የጠራውን ከምንሰጣቸው በተቀር ሌላ የማያስፈልግ መሆኑን እናስታውቃችኋለን ። ደግሞ ከዚህ በኋላ የሰውነት ሥራቸውን ተስማምተው ያለ ሐሳብ ሌሊቱን በደስታ ያልፉታል ስል በለኝ እውቀቴ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አሳስባለሁ

ታዛዥዎ ኤም ማትሳኪስ ።

አበማልተን
ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

አበ ማልተን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው። አበማልተን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል አበማልተን ከቁርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፥ ቤርን ናቸው። በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበበ ናቸው።

አበማልተን አዲስ አበባባሉ በዋና ምግብ ሸጮችና በመድኃኒት ሸጮች ቤት ይሸጣል። ሣጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

Japanise Dentist
ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፯ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቆሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

WHITE HORSE
WHISKY

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋናታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በከዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሬ ቤት እንዲጎበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመንገኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክተር ሚካኤል ።

በሞንፐሊዬ ኡኒበርሲቴ ።

ስለውሥጥና የሴት በሽታ ፤የቍስልና ፤የዓይን በሽታ የሴት አዋላጅነት ሕክምና የተመሰከረላቸው ድር ራስ መኰንን ድልድይ ቤታቸውን ትተው ወደ ጉለሌ መንገድ ሙሴ ሙራዲያን ቤት አጠገብ ቤት መለወጣቸውን ለወዳጆቻቸው በማክበር ያስታውቃሉ ።

ሁሉ ቀን ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፮ሰዓት ደግሞ ከ፰ ሰዓት እስከ ፲፩ ሰዓት ይገኛሉ ።

ሐሙስ ዕለት በጧቱ በሽተኞች አለዋጋ ያክማሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

በሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጳሚሴር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

ቁ ፤ ፻፵፰ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቊጥር ፵፰
8^me ANNE. № 48

ሐሙስ ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ.ም
Jeudi 24 Novembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ልዕልት የሻሽ ወርቅ ይልማ ።

ታላቅ ሽልማት ።

ልዕልት የሻሽ ወርቅ ይልማ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የታላቅ ወንድማቸው የደጃዝማች ይልማ መኰንን ልጅ ዘንድሮ በተደረገው በዘውዱ በዓል ቀን በወርቅ የጠለቀ የሐር ቀሚስ፥ጥሩ ድርብ፥ ጥሩ ባለፈርጥ ካባላንቃ ፥ ጥሩ የወርቅ አክሊል ተሸልመው በወጡ ጊዜ ዘመድ ወዳጆቻቸውን ሁሉ እጅግ ደስ አለው።ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴንም መረቃቸው። በዚሁም ምክንያት ታላቅ በዓል አድርገው ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰንን፥ ልዑል ራስ ካሣን፥ ልዕልት ተናኘወርቅን፥ልዕልት ወለተ እስራኤልን፥ ክቡር ፊታውራሪ ብሩን፥ክቡር ራስ ደስታን ፥ የምክርቤቱ ፕሬዚዳን ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅን፥ ከዚህም ቀጥሎ በ፫ኛው ቀን ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር ቤተ ዘመዳቸውንም ጠርተው የሚእምር ግብዣ አደረጉ ። ብርሃንና ሰላም ልዕልት የሻሽ ወርቅ ይልማን እንኳን ደስ አለዎ ይላል ።

ሹም ሽር ።

ክቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትር የቀድሞው የጦር ሚኒስትር ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ይገዙት በነበረው ላይ ማረቆና ቶኬ በበረና ፈንታ ተጨምሮላቸው እጅግ የሚአስደንቅ ባለፈርጥ ላንቃ፥ባለወርቅ አጫዋች ግምጃ ሱሪ፥ ጥሩ ድርብ፥ታላቁን ኒሻን ተሸልመው፥ ማዕርጉ ከፍ ያለ ራስ ወርቅ አሥረው በታላቅ ክብር በነጋሪት ተሾሙ።

ክቡር ራስ ደስታ ዳምጠው እንደገና ታላቅ ማዕርግ ያለው ሽልማት፥በወርቅ የጠለቀ ቀሚስ፥በወርቅ የጠለቀ ግምጃ ሱሪ፥በወርቅ የጠለቀ ላንቃ፥ ታላቅ ኒሻን ተሸልመው፥በደስታ ላይ ደስታ ተጨምሮላቸው ራስ ወርቅ አሥረው ሲዳሞንና ቦረናን በነጋሪት ተሾሙ ።

ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ወላሞን ለግዛት፥ቈጫንና ክዶን ለቈራጪነት ተሾሙ ።

ክቡር ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ማዕርግ ያለው ሽልማት ተሸልመው ከምባታን ተሾሙ ።

ክቡር ደጃዝማች መልኬ የቀድሞ አገራቸውን እንደያዙ የጐንደርን ከንቲባነት ተሾሙ ።

ልጅ መልአኩ ታየ ከጉራጌ አገር ማደርያ ተደርጎለት ቀኛዝማች ተብሎ ተሾመ ። ብርሃንና ሰላም ሹመት ያዳብር እንኳን ደስ አላችሁ እያለ ስደታውን ይገልጻል ።

ከሮፓ በደኅና መመለስ ።

ክቡር ብጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ የፖስታና የቴሌግራም የቴሌፎን ሚኒስትርና በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም ራይስ(መምህር)ወልደ ሚካኤል በኅዳር ፱ ቀን አዲስ አበባ ገቡ።ደግሞ አቶ ፋሲካ ሀብተ ሚካኤል ለራሳቸው ጉዳይ ወደሮፓ ሒደው ከርመው ነበርና በኅዳር ፮ ቀን አዲስ አበባ ገቡ።ብርሃንና ሰላም እንኳን በደኅና ገባችሁ ይላል ።

ስለከተማ ዘበኞች ትጋት ።

ዘውዴ የሚባል ሰው ለአዛጋር ገብረ ወልድ በአሽከርነት ተቀጥሮ ሲኖር በኋላ ሳይሰናበታቸው ጠመንጃቸውን ይዞ ስለከዳቸው ሌሎቹን ደርቤና ተፈራ ኪዳኔ ፥ የሚባሉትን

እንዲይዙላቸው አሽከሮቻቸውን አዝዘዋቸው ድንገት እንዳጋጣሚ ይኸው ዘውዴ የሚባል ሰው ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ባለው መንገድ ሲተላለፍ በኅዳር ፲ ቀን አግኝተውት ጌታችን አዛዥ ገብረ ወልድ ዘውዴን ያገኛችሁት እንደሆን ያዙ ብለው አዘውናልና ና ወደጌታችን እንሒድ ቢሉት እሺ መሔዱን እሔዳለሁ ነገር ግን አቶ ገብረ ማርያም ከሚባል ሰው ቤት እቃ አስቀምጫለሁና ሒደን እናምጣ ብሎ የፖሊቲክ ተስፋ ሰጥቷቸው እነሱም እውነት መስሏቸው ከሱ ጋራ ሔዱ። እቤትም እንደደረሱ አቶ ዘውዴ ለክ በሆዱ ክፉ ሐሳብ አድርበት ኑሮ ከዚያ ቤት ውሥጥ ለበን ጠመንጃ ይዞ ወጥቶ ለማምለጥ ሲጐላመም ወደጌታችን እንሒድ እኮ ቢሉት እኔ አልሔድም ብሎ ሲሸሽ ተያዝ ቢሉት አልያዝም ብሎ በንጉሥ እያለ ሲከታተሉት ደርቤ የሚባለውን ተኩሶ መታው። ሁለተኛ በዚያው ቀን ባ፲ረኛው ክፍል በኩል ብዙ ሕዝብ ለአፈርሳታ ተሰብስቦ ነበረና ለሌላ ቀን ተቀጥሮ ሕዝቡ ሲበተን ለጊዜው ወዳጅ ተገኝ የሚባል ቤቱ ከነእቃው ተቃጥሎበት አፈርሳታ አብሮ ያስወጣ የነበረውና ደግሞ አየለ የሚባለው ወደኋላ ቀርተው እዚያው ክፍል ካለው ከቢቶደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ቦታ አጠገብ የጩኸት ድምፅ ሰምተው ለርዳታ ከዘበኞች ጋራ ተከታትለው ቢሔዱ ሁለቱንም በ፪ጥይት ወዲያው ገደላቸው ዘበኞቹ ግን አለቆቻቸው እንዳስተማሯቸው የጦር ትምህርት ተኝተው ሁለቱ የክፍል ዘበኞች ተኩሰው አንዱ ከጉልበቱ ፩ዱ ከክንዱ ላይ መትተውት ተያዘ ።

እንደተመታም ሌላ ሰው ለማበላሸት አልበዘነም ነበር። ከተመታም በኋላ ፮ያህል ጥይት ተኩሷል ነገር ግን በዘበኞቹ ብርታት ተይዞ ሳለ ወዲያው የከተማ ዘበኞች ጠቅላይ አለቃ ግራዝማች አማረ ይህን ሰምተው በፍጥነት ሔደው ከዚያው ክፍል ካለው መጠባበቂያ ቤት ገብተው ይኸንኑ ዘውዴ የሚባለውን በምን ምክንያት እነዚህን ሰዎች ገደልካቸው ብለው ቢጠይቁት ደርቤና ተፈራ የሚባሉት እመንገድ አግኝተውኝ ጌታችን አዛዥ ገብረ ወልድ ፈልጉና ያዙ ብለውናልና እንሒድ ቢሉኝ ወደ ሰው ቤት ዕቃ አስቀምጫለሁና ሒጄ ያንን ይዤ እንመለሳለን ብዬ ሔደን ነበረ ። በኋላ ግን ጠመንጃዬን አጥጬ ስሔድ ተያዝ ቢሉኝ አልያዝም ብያቸው ስሸሽ ቢከታተሉኝ መጀመሪያ ደርቤን አቁሰልሁት፥ በኋላም ወዳጅ ተገኝና አየለ ለርዳታ መጥተው ሊይዙኝ ቢሉ ሁለቱንም ገድያቸዋለሁ ብሎ አምኖ እንደታሠረ ቈይቷል።

ለማ ወ ማ።

ስለ መልካሙ ተማሪ በደኅና መግባት

ባሕሩ ከባ የሚባል የወለጋ ልጅ በልጅነቱ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት በጠባዩና በትምህርቱ እጅግ የተመሰገነ ሁኖ ሲኖር በኋላ ጃንሆይ የወታደር ትምህርት እንዲማሩ አስመርጠው ባሕሩንና ጒበናን ወደ ሮፓ ልከዋቸው ጒበና ለወታደር ትምህርት አይሆንም ልጅ ነው ስለተባለ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ገብቶ በትምህርቱና በጠባዩ የተመሰገነ ሁኖአል ። ባሕሩ ከባ ግን መጀመሪያ ሳንሲር በሚባለው የወታደር ትምህርት ቤት ፪ዓመት ተምሮ ሱሊዬተና ሆነ። ፪ኛ በቤርሳይ በጦር አይሮፕላን ትምህርት ቤት ፩ዓመት ተምሮ ብሬቤ ዶብሴርባተር የሚባለውን ዲፕሎም(የምስክር ወረቀት) ተቀበለ ። ፫ተኛ በአቦር ከተማ ባለው የአይሮፕላን ትምህርት ቤት ፰ወር ተምሮ ብሬቤ የሚባለውን የምስክር ወረቀት ተቀበለ ። ፬ኛ በቡገር ባለው የአይሮፕላን ትምህርት ቤት ፭ወር ተምሮ ሊየተና ሆነ የአይሮፕላን ሜካኒስያንነት አለው ። በአይሮፕላን ላይ ሁኖ ፎቶግራፍ ማንሣት፥ መትረየስ መተኰስ፥ ቦምብ መጣል ይችላል ተብሎ ተመስክሮለት ይህን ሁሉ የምስክር ወረቀት ይዞ በባቡር ወደ አዲስ አበባ ገባ ። ባልንጀሮቹና ወንድሞቹ የሰውቀት ወዳጆቹ ሁሉ በናፍቆት ተቀበሉት ። በደኅና ስፍራ ላይ የተዘራው ገንዘብ ደኅና ፍሬ በማፍራቱ ይልቁንም እንደዚህ ያለውን ፍሬ የሚሰጠውን ተማሪ ብዙ ገንዘብ አፍስሰው ስለአስተማሩ ብርሃንና ሰላም ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እጅግ ያመሰግናል ።

የቤተ ክርስቲያን በዓል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሁኖ ከሠራቸው ከብዙ ቸርነቶቹ አንደኛው ከሄሮድስ መሰደዱ ነው ። ይህም በክርስቲያን ዘንድ የማይረሳ መታሰቢያ ሁኖ ከመስከረም ፳፭ እስከ ኅዳር ፮ ቀን ድረስ የሚችል እየጾመ የመቤታችንንና የጌታችንን ስደት እያሰበ እሑድ እሑድ ለአገልግሎትና የእግዚአብሔርን ምስጋና ለመስማት ከሌሊቱ ቀድሞ እያለ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሒዶ ያድራል ። ዘመኑም ወርኅ ጽጌ ስለሆነ የሚነገረው ምስጋና ሁሉ እመቤታችንንና ጌታችንን በዕፅና በጽጌ ምሳሌ እያደረገ ነው ። በፍጻሜውም በኅዳር ፮ ቀን በዓል ይደረጋል ። በዚሁም ልማድ ዘንድሮ ኅዳር ፭ ቀን አዲስ አበባ ወደ አለው መንበረ ንግሥት ቍስቋም በከተማ ያሉት ሊቃውንት ሁሉ ወጥተው ነበርና በሚያምር አኳኋን የዋዜማው ምስጋና በተነገረ ጊዜ የደብሩ ዋና ሹም አለቃ መርሻ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኙ ።

ዋዜማ ።

መስተገብረ ምድር ጽምእተ ማይ፤ ዘርአ አፃብዕ ደመ በፍናወ ግብፅ ዘርአ ።
ወዕቅፍት ኅላፌ ፍኖት ረሰየ መብልዐ ።
ላቲ ዐቀብተ ከመ ኢይሚም እግዚአ ።
እስመ ካልአ ሰብአ አቅረበ ወአርኅቀ ሰብአ ።
ተዘኪሮ እንተ ዮሴፍ ግፍዐ ።

በነጋውም ኅዳር ፯ ቀን ከሌሊቱ ከሀናቱ ቀደም አድርገው ማኅሌቱን ጀምረው እንደሚገባ አደረሱ ። የቀለሙ ማማር፥ ያነጋገራቸው መተባበር እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር ።

ይልቁንም አለቃቸው ጣዕም ባለው ዜማ ወረቡን እያስማሙ ሲወርቡና ሲአሸበሽቡ ያምሩ ነበር ። ሲነጋጋም በብዙ ሠራዊት ታጅበው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፥ ግርማዊት እቴጌ መነን፥ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ፥ ሌሎችም መኳንንትና ሠራዊት በዓሉን ለማክበር ተሰብስበው ነበር። ከቅዳሴውም በኋላ በዕጣነ ሞገር ጊዜ አለቃ መርሻ (ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን) እንዲህ ብለው ተቀኙ ።

ክብር ይእቲ

በኵረ ድንግል ሜም በንፍስ፡ ወሥጋ፡ እንተ አልብከ ኀፀፅ።
እንበይነ ዘአምረርከ ቅድመ ማየ አፍላጊሃ ለግብፅ ።
ኢይትርፍ ብከ ዘግብፃውያን ተግሣፅ።አምረሩ ብከ ጣዕመ
ማይ መስተሓውዛን አብያጽ ።

ፅጣን ሞገር

ለሀገረ ግብፅ ዘውዕየ በዋዕየ ፀሐይ ፅዱል። እንዘ እምኔሁ ይትኀጣእ ትእምርተ ጠል።
እሳተ ነሢአኪ ዘትረድኢ ድንግል ።
ተራድኦ ዘመድ ኢይመስል ።
ተዋሕዶ መብረቅ ወነድ አኮኑ በውስተ አሐቲ አባል ።
እንበሌኪ ሀገረ ክርስቶስ ኢሀሎ ዘይክል ።
አሠረ ንጉሥ። በምንት ይከውን ተአምሪሁ ለምጽአተ ክርስቶስ ቃል ።
እስመ ግብረ ክርስቶስ መጽአ ቅድሜሁ እንዘ የሐውር መስቀል ።
በደመና ሰማይ ምስለ ኃይል ።
ኃይለ ሥላሴ ትጉህ ዘውግ ሱራፌል ።
ኀበ ኵሉ ኀቤከ ቀሊል ።

ከዚህም በኋላ ዑደት ተደረገና ከዑደት በኋላ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ እመቤታችን ደብረ ቍስቋም ገብታ ከመንገድ ድካም እንዳረፈች፡ ጌታችንም በታይቱን እንደባረከትና ሌላም ብዙ የታምራት ሥራ እንደሠራበት፡ ከዚያም ወዲህ ብዙ ድጋፃ መነኰሳት እንደኖሩበት መልክም ስብከት ሰብከው ሕዝቡን ባርከው አሰናበቱ ።

ተስፋዬ ኢዮቤድ።

በቅን ለመንግሥት ማገልገል ምንጊዜም ዋጋን አያሳጣም።

አያሌ ሰዎች በማያውቁት ነገር እየገቡ በየሰዉ ላይ የሚሆነውን ጥቅም ጉዳት፡ ጉዳቱን ጥቅም በማስመሰል ልዩ ልዩ ወሬ ያወሩና ነገሩ በተገለጠ ጊዜ አስቀድሞ ነገራቸውን በሰሙ ሰዎች ፊት ያቀላቸዋል (ማለት) ሥራ ለሠሪው እንደተባለው ማናቸውንም ሥራ ከሠራተኛው በቀር የሚያውቅ እጅግ አይገኝም ። እነሆ ገበሬ የንጉሥን ፤መበለት የቄስን፤ ነጋዴ የጸሐፌን እነዚህንም የመሳሰሉት ልዩ ልዩ ሠራተኞች ያንዱን ሥራ አንዱ ይህ እንዲህ ነው ብሎ ለማሳየት እጅግ ድፍረትና ቅሌት ነው። የስጦታንም ነገር ትንሽና ትልቅነቱን የሚያውቁት ሰጭና ተቀባይ ብቻ ናቸው እንጂ አሻግሮ የሚያይና የሚሰማ ሰው እንደ መሰለ እንደመሰለው ከማውራት በተቀር ፈጽሞ ለማወቅ አይቻለውም ።)ይኸንንም (ሚያስረዳ ነገር መንግሥት በቅን ያገለገሉትን ከከፍተኛ ደረጃ ለማውጣትና ሥራውን ለማሻሻል፡ ጥቅም ላነሰውም ጥቅም ለመስጠት ሹመቱንና ሥራንም ቢያዘዋውር አንድ አንዱ በሹመት ወይም በሥራው ሌላ ሰው ገብቶበት እሱ ከፍ ላለው ደረጃ ታጭቶ በታው ሰላልተደራጀለት ጥቂት ጊዜ የቈዩ እንደሆነ ከላይ እንደተጻፈው በማያውቁት ነገር ለመንቀፍ የተደራጁ ሰዎች የተዘዋወረው ለጥቅሙ እንደሆነ ሳያውቁ አገሌእንጂተጋዘ እያሉ ነገሩ እስኪ ገለጥ ድረስ የዚያን ሰው ጠላቶቹን ደስ ያሰኛሉ ወዳጆቹንም ያሳዝናሉ

እነሆ አሁን በቅርቡ ክቡር አለቃ ገብረ አጋዕዝት ገብረ ሚካኤል የደብረ ብርሃን ሥላሴን አለቅነትና የመላ ተጉለትን ምስለኔነት ተሹመው መንግሥትን በቅን ስላገለገሉና ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ጠፍቶ የነበረውንም የደብረ ብርሃንን ከተማ በማደስና ልዩ ልዩ ቀዋሚ ሥራንም በመሥራት እጅግ ሲመሰገኑ አሁን ሹመታቸው ለሌላ ሰው ስለ ተሰጠ ብዙ ሰዎች የታሰበላቸውን ሹመትና ማዕርግ ሳያውቁ የማያስፈልገውን ወሬ ያወሩ ነበር።አሁን ግን ከላይ እንዳልሁት ጊዜው ሲደርስ ትልቁን ገዳም ደብረ ባዕን ተሾሙ እኔም ባለ አቅሜ አገልግሎታቸውንና ወረታቸውን ከብዙ በጥቂቱ በዚህ በወረቀት አገልጻለሁ። ምንጊዜም ለሀገራቸው ለደብረ ብርሃን ብዙ ፍቅር ነበረባቸውና እግዚአብሔርና መንግሥት የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ ስለሆነ ቀድሞ አበታቸው ይዘውት የነበረውን የደብረ ብርሃን ሥላሴን ቤተ መቅደስ በሰጡቸው ጊዜ ልጅ በመሆናቸው እንደምን ሊያውቅበት ነው ሲባሉ መቅደሱን ማስከበራቸውና ሥርዓታቸውን ሁሉ ከቀድሞዎቹ አለቆች እያስበለጡ ለመንግሥት እያስታወቁ ብዙ ሕግ አቆሙ።ዮልቁንም አሁን በቅርቡ ጊዜ ለደጉ ንጉሣችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አስታውቀው ያስደረጉት ብዙ እርዳታ እጅግ ያስደንቃል።ለቤተ መቅደሱማ በየጊዜው የሠሩትን ሥራ ቁጥሩን ለመጻፍ ጊዜ አላገኘሁምና ወደ መጀመሪያው ልመለስ ከዚያም ወዲህ ደብረ ብርሃን የዘርአ ያዕቆብን ከተማ ለማደስ ፈቃድ ተቀብለው መጀመሪያ ወኃ በከተማው ችግር ስለሆነ የመዘውር ውኃ እንዲገባ ፈቃድ አስደረጉ። ፪ተኛ የከተማው ሰው ገበያ ስለራቀውና ከተማውም እንዲለማ ፈቃድ ተቀብለው እከተማው ላይ ገበያና ጉምሩክ አስቆሙ ፤ ፫ተኛ በከተማው ስልክ አለመግባት ብዙ ችግር ነበረና አስፈቅደው ስልክ አስገቡ ፤ ፬ተኛ ቤተ መንግሥቱን ለማስፋት ከቀድሞው አልፍኝ አዳራሽ ሥራ አስበልጠው ዕፁብ ድንቅ የሆነ አዳራሽና ሌላም በያይነቱ ለቤተ መንግሥት የሚገባ ስድስት ማለፊያ ቤት አሠሩ) ፭ተኛ የተጉለት ሕዝብ በወር ተራ መጫን ምክንያት ብዙ ጉዳት ነበረበትና ለወር ተራ የሚጫነውና ሌላውም ሁሉ የከሚዎን መንገድ ተሠርቶ በከሚዎን እንዲመላለስ ፈቃድ አስደረጉ ፤ ፮ተኛ በደብረ ብርሃን ከተማ መታደስ የተጀመረውንና ሀገራችንን ለመጐብኘት እንዲመጡልን ከደጉ ንጉሣችን ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሙሉ ፈቃድ ተቀብለውልን ነበር ፤ ፯ተኛ ስለ ጃንሆይ ዘውድ በዓል የሠሩትሥራ ብዙ የሚያስደንቅ ነው ፤ ፰ተኛ በደብረ ብርሃን ከተማ ለማናቸውም ሥራ የእንጨት ችግር በጣም ስለበዛ በቤተ መንግሥቱ በምድረ ግቢው ሁሉ ዙሯ ሁለት ሺህ የሚሆን የባሕር ዛፍ አስተከሉ፤ ፱ነኛ በደብረ ብርሃን ለሚተላለፈው ዘመድ ወዳጅ ለሌለው እንግዳና ደካማ ማረፊያ ብለው በጣም ትልቅ የሆነ ቤት አሠርተዋል፤ ፲ረኛ ለጥር ሥላሴ ጃንሆይን ለመቀበያ ተብሎ የተደረገው የቅጥር ካብና አጥር የቤቱ መታደስና ዕዳት ተነግሮ አያልቅም ። ነገር ግን ይህ ሁሉ ስለሆነ ዋና ዋናውን ጻፍሁ እንጂ ያለቃ ገብረ አጋዕዝት ለመንግሥት እርዳታቸውና የደብረ ብርሃንን ከተማ ለማደስ ፥ ሕዝቡንም ለማሠልጠን

ምኞታቸው ብዙ ነበር) አሁን ለተሾሙት ለደብረ በዓሉም ይሆን የመሰለ እርዳታቸውን ያጕድሉብናል ብለን እንጠራጠርም በሀገራችን የተጀመረውም ሥራ ሁሉ ፈጽሞ ስለ አላለቀ ክቡር ቀኛዝማች ባልቻንና ክቡር አለቃ አምባዬን እግዚአብሔር አትግቶልን እርሳቸው የወጠኑትን ሥራ ሁሉ ይፈጽሙልናል በማለት ብዙ ተስፋ አለን)

የደብረብርሃን አውራጃ የርሻና የመሥሯ ቢሮ ጸሐፊ
ዮሐንስ ወልደ ማርያም

ታላቅ ርኅራኄ ።

እንደኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ልማድ በኅዳር ፲፪ ቀን በሚካኤል ቤተክርስቲያን በዓል ይደረጋል ። ዛሬም በዚሁ ልማድ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊት እቴጌ፥ ልዑላን መሳፍንትና ጳጳሳት፥ መኳንንትና ወይዛዝር ሠራዊት ተሰብስበው በየካ ሚካኤል በዓል የሚያደርጉ ስለሆነ ትጉሁ አጋፋሪ ከልክሉ ወርቁ ማልደው ወደ የካ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ሒደው የጃንሆይን መምጣት ሲጠባበቁ ከሐረር የመጣች አንዲት ሴት ነበረች አባቷ አቶ ስለአምሳው ይባሉ ነበር በሐረር የታወቁ ሰው ነበሩ ይባላል ።

መቼም ሰው ሲቸገር ለምን እንጂ ሠርቶ ልብላ ማለት በብዙ ሰዎች ዘንድ ቀርቷልና ደልቶንም ለምኖ መብላት ታላቅ ኀፍረት መሆኑን ብዙ ሰዎች ረስተውታልና ሲቸግራት ጊዜ ከሐረር ወደ አዲስ አበባ መጥታ እየዞረች ስትለምን በዚህ ቀን ብዙ ምጽዋት ለማግኘት ተስፋ አድርጋ ማለዳ መጥታ በቤተ ክርስቲያን ዙሯ እየዞረች ስትለምን የመውለጃዋ ቀን ሳታውቀው ደርሶ ኖሮ በዚያው በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ምጥ ተይዛ ለቤተ ክርስቲያን የሔዱ ሴቶች አገላግለዋት ሕፃኒቱና እናቲቱ በፀሐይ ላይ ወድቀው ርኅሩኁ አጋፋሪ ከልክሉ አይተው ያቺን ያልታደለች ድኻ ከሕፃኒቱ ጋራ በአቶሞቢል አሳፍረው ወደቤታቸው ሰደድዋቸው ።

ሰዎችም ቢጠይቋቸው እግዚአብሔር ነውና ያጋጠመኝ ሕፃኒቱም በመልክ አስተዳደግ አሳድጋታለሁ እናቲቱም እሺ ብትለኝ ባል አጋብቶ ሠርታ እንድትበላ አደርጋለሁ ብለው ለኋላ እንኳ የሚጠቅም ምኞት ስለተመኙላት የሰማው ሰው ሁሉ በአጋፋሪ ከልክሉ ርኅራኄ እጅግ ተደነቀ ። ከተሰበሰቡትም አንዱ ብልህ እንዲህ አለ በመቆየት ብዙ ነገር ይታያልና መቆየቱን እወዳለሁ በዚህ ምክንያት ነው የቀድሞ አጋፋሪዎች አዋቂና ሕፃን፥ ሽማግሌና ክህን ሳይለዩ ያገኙትን ሁሉ ሽመላቸው እስቲሰበር መደብደብ ነበረ ዛሬ በደግ ንጉሥ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን ርኅራኄ ያለው አጋፋሪ ያሳየኸኝ አምላክ ክብርና ምስጋና ይግባህ ብሎ እግዚአብሔርን አመሰገነ ።

ታሪክና መታሰቢያ ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ባለፈው ወር ቍ፴፬ የክቡር አቶ ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖትን ሞት ብርሃንና ሰላም ኃዘኑን ገልጾ በታላቅ ቃል ጮሆ አሰምቷችኋል ። ከ፲፱፻፲፬ ዓመተ ምሕረት ከነሐሴ ወር ጀምሬ እስካሁን በሞት እስከተለዩበት ቀን ድረስ ታዝዣቸው ሁኜ ዓሥር ዓመት አብረን ስለሠራን ያሥር ዓመት ታሪካቸውን በጭሩ እጽፋለሁ ።

አቶ ገብረ ክርስቶስ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ፥ ሥራቸውን የሚያከብሩ ፥ ንጉሣቸውን በሥራ ደስ አሰኝተው የታመኑ፥ ስለ ሀገራቸው ስለ ኢትዮጵያ ደማቸውን ለማፍሰስ የተዘጋጁ፥ ስለ ሀገራቸው ቀናተኛ፥ ስለ ሀገራቸው ተቈርቋሪ፥ የሀገራቸውን ልማትና ክፍታ ፈላጊ፥ የሥልጣኔ ወዳጅ፥ የእውነት ማደሪያ፥ የተማሩ ደግ ሰው ነበሩ ።

ነገር ግን ያችን የተወሰነችዋን ቀን ማለፍ የማይቻል ስለሆነ በተጠሩባት ሰዓት ከድካም ጋራ እንደተስማሙና እንደ ተፋቀሩ ከዚህ ዓለም ወደማያልፈው ዓለም ተሻገሩ ። ሥራቸውን ሌሊትና ቀን ሠሩ፥ በጌታቸው ትእዛዝ ብዙ መጻሕፍትን በትጋት አትመው በኢትዮጵያ ላይ ዘሩ፥ ያንን በመመልከት ያገራቸው ልጆች በዕውቀት ጐለመሱ ።

ደግሞ በንጉሠ ነገሥቱ አሳብ ብርሃንና ሰላምን መሠረቱ ብርሃንና ሰላምም በኢትዮጵያ ብርሃኑን ገለጸ ። አቶ ገብረ ክርስቶስ ሥራቸውን አሳምረው እርምጃውን ከፍ ወዳለው ደረጃ ያደረሱት በመልካም ወንበር ተቀምጠው፥ የሚያምር ጠረጴዛ ተደግፈው በመመልከት አይደለም ። ማዕርግ የሚመስለውን አዋርደው፥ የሥራ ልብሳቸውን ለብሰው እንደ አንድ ሠራተኛ እየሠሩ ሥራቸውን ከፍ ከፍ አደረጉት እንጂ የመቀመጥ ጊዜ አልነበራቸውም ።

አቶ ገብረ ክርስቶስ በሥራ ቀን ምሳቸውን በቤታቸው በልተው አያውቁም ዘወትር ምሳቸው በሚዛን ተንጠልጥሎ እሥራቸው ድረስ መጥቶ ይበሉ ነበር ። ይኸንም ማድረጋቸው በዚያ ጊዜ ወደ ቤት የሔዱ እንደሆነ የሥራ ጊዜ ይተላለፍብኛል የማለት አሳብ ስለነበራቸው ነው እንጂ ከባለቤታቸውና ከልጆቻቸው ጋራ በገበታቸው ቢጋበዙ ጠልተው አይደለም። እንዲያውም ሥራ በበዛባቸው ጊዜ ሁለትና ሦስት ወር ቤታቸውን ሳያዩ ሌሊትና ቀን ሥራቸውን ይሠሩ ነበር። ሠራተኞቹም የሳቸውን ፍለጋ ተከትለው ለሥራ የተጉ ሁነዋል። ከአቶ ገብረ ክርስቶስ ጋራ ሲሠሩ የነበሩ ሠራተኞች በማናቸውም ሥራ ቢዘዋወሩ ሥራቸውን በጥንቃቄ ያስኬዳሉ ይልቁንም የሥራ ጊዜአቸውን ሰዓት በመጠበቅና በማክበር በጣም የተጉ ናቸው።

ደግሞ አዲስ ሠራተኛ ወደ ሥራ ሲገባ የምስክር ወረቀት(ሴርቲፊካ)እንዳለው ወረቀቱን አቅርቦ ወረቀት እንደሌለው በሥራ ተፈትኖ ዕውቀቱን ካሳየ በኋላ እንደ ሥራው መጠን ደመወዙን ይቈርጡለታል እንጂ ደጅ ጥናት በጭራሽ ገንዘባቸው አልነበረም ። ደግሞ ጉቦ የሚበላውን ፈጽመው አያውቁትም ነበር ። እንዲያውም ልጅ ወልደው በደስታቸው ቀን ለክርስትና በጠሩን ጊዜ ጠባያቸውን የምናውቀው ስለሆነ አንዲት ቤሳ እንኳን ሳንሰጥ የተዘጋጀውን ድግስ ተመግበን መርቀን በደስታ ወደቤታችን እንመለስ ነበር ። አንዳንድ ጠባያቸውን የማያውቁ ሰዎች ግን ገንዘባቸውን ከኪሳቸው አውጥተው ሲያቀርቡ አቶ ገብረ ክርስቶ እያዘኑ እየተጨነቁ ይህ ነገር የማይገባ መሆኑን በስብከት እያስረዱ ገንዘባቸውን ወደ ኪሳቸው እንዲያደርጉ ያስገድዷቸዋል ። እነዚያም እየተ

ጆነቱ ምስጋና እያቀረቡ ገንዘባቸውን ይዘው ወደ የቤታቸው ይመለሳሉ ።

ለአቶ ገብረ ክርስቶስ አንዲት ቤሳ እንኳን ጉቦ ሰጥቸአለሁ የሚል አንድ ሰው እንኳን ቢገኝ እኔ አንገቴን እሰጣለሁ። ምንም ሐሰተኛ ቢሆን ይኸንን ውሸት ደፍሮ ለመናገር የሚያስብ እንደበት ቢኖር እንደማዘጋ አምናለሁ።ይህስ ይቅርና በጣም የሚያፈቅሩት ወዳጃቸው ላንድ ሰው አማላጅ ሁኖ ቢሔድ የማያደርጉትን ነገር ያደርጉለታል ተብሎ አይፈተንም አንድ ሠራተኛ ለጉዳዩ የተከተላቸው እንደሆነ ይጨነቁና መንገዳቸውን ትተው ይቆሙና መልስ ሰጥተው ይመልሱታል።

አቶ ክፍለ እግዚአ ይኅደጎ እንደጻፉት የእናታቸውንና የአባታቸውን ሞት ተረድተው የሚያፅናኑዋቸውን አፅናንተው ተጫወቱ ሰዓት ደረሰብኝ ብለው በሰዓቱ ወደ ሥራቸው ገብተው ሲሠሩ መዋላቸውን እናውቃለን ፤ ደግሞ አሁን በቅርብ ጊዜ አንዱ ዓርብ አንዱ በማግሥቱ ቅዳሜ ሁለቱ ልጆቻቸው ተከታትለው ሙተውባቸው ሁለቱንምቀን የልጆቹ ሬሳ እቤት እንደሆነ በሰዓቱ ወደ ሥራቸው እየገቡ እገሌና እገሌ ሥራችሁን ሥሩ ፤ እገሌና እገሌ ወደ መቃብር ሒዱ ብለው ከተመለሱ በኋላ ሬሳው ወደ መቃብር ሔደ፤በዚያ ቀን ሁላችንም አምተናቸው ነበር፤ በእውነተኛው አሳባችን ነገሩን መርምረን ስናስተውለው ግን ሥራቸውን ማክበራቸው ይሰማናል።የሠሩት ሥራ ሁሉ ለታሪክ ጸሐፊ የተመቸ፤ ደስ የሚያሰኝ፤ እንደልብ የሚያናግር ነውና እኔም ይህቺን አጭር ታሪካቸውን ስጽፍ እውነት ነገር ስለሆነች ልቤ በደስታ እየኰራ ተናገርኋት ።

አቶ ገብረክርስቶ ሰዓት፤ በመጠበቅ፤በጥንቃቄና በትጋት፤በቅንነት፤ በመታመን ሌሊትናቀን በመሥራት እጅግ ትጉህ ነበሩ፤ እንደዚህ አድርገው መንግሥታቸውን አገልግለዋል፤የድካማቸውን ዋጋ መንግሥት ለልጆቻቸው እንዲከፍላቸው እናምናለን።በማናቸውም ሥራቸው ቢሆን እውነተኛ ታሪካቸውን እንደሚገባቸው ለመናገር ብዙ ጊዜ ይወስድብናል ብለን በጭሩ ትተነዋል ። ባቶ ገብረ ክርስቶስ ሞት የተጐዳ መንግሥት ነውና መንግሥትንና ሠራተኞቹን እግዚአብሔር ያጥናቸው።

ትንሽ የኃዘን መዝሙር ። እሑድ ቀን ተዘግቶ የማያውቀውን ። ሐሙስ ዘግቶት ጠፋ ማተሚያ ቤቱን ። ጌታዬ ምን ላርግህ ምን ልበልህ እኔ። ወዳንተ መጭ ነኝ እኔውም በቀኔ። ማተሚያ ቤታችን በኃዘን ቈሰለ ። ብርሃንና ሰላም መዝሙሩን ቃኘልህ ሞተ ሞተ እያለ ። ማተሚያ ቤት ነበር ጥላው የደመቀ ። እንጣዲህስ እንጃ ወርክችን ወደቀ ።መሬትን ተመርቶ ጠም ከማሳደሩ ። እንዳንተ ማወቅ ነው የማትጠፋዋን ስም እየዘሩ ። ሌትና ቀን ሠርቶ የተንከራተተ። ሌትና ቀን አይቶ የተንከራተተ። ብርሃናችን ጠፋ ሞተ ተከተተ ። ዓይኔ ከጠፋብኝ ላልቅሰው በምኔ።ወይኔ ተጐዳሁ ወይኔ ወይኔ።

ከጕዳተኞቹ አንዱ ደምሴ ወልደ ገብርኤል።

ስለ ወይዘሮ ፈትለ ወርቅ ይግለጡ ሞት ።

ወይዘሮ ፈትለ ወርቅ አባትዋ አቶ ይግለጡ ይባሉ ነበር እናትዋም ወይዘሮ ንግሥት አርአያ የሁለተኛው አቡነ ሰላማ የኢትዮጵያ መንግሥት ሊቀ ጳጳሳት አሽከር የበጅሮንድ አርአያ ልጅ ናቸው።አገራቸውም በትግሬ ውሥጥ ገንደብታ ይባላል ። ይህችውም ወይዘሮ ፈትለ ወርቅ ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፫ ዓመተ ምሕረት ተወለደች።መስከረም ፳፭ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓመተ ምሕረት በ፶፰ ዓመትዋ በወሊድ ምክንያት ሙታ በብዙ ልቅሶና ኃዘን በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረች ። እናቷም ወይዘሮ ንግሥት አርአያ ብዙ የልቅሶ ግጥም እየገጠሙ የተሰበሰበውን ሰው ሁሉ እንባ በእንባ ያራጩት ነበር።ከገጠሙትም ግጥም ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን።

ማናቸው ይሻላል ብናደላድለው ። በልጅ ከሞተና እግዜር ከገደለው ። የኔስ እናትነት ያንችስ ልጅነትሽ በምን ይታወቃል ። አስጠሪኝ ፈትለ ወርቅ ስፍራውም ይበቃል ። የፈትሉ ባለቤት የስፌት መምር ። እንዴት ያነን ጣትዋን ይዛው ትቀበር ። መስከረም ሲጠባ ያልመጣሽ እንደሆን ። አንችም ልጅ አይደለሽ እኔም እናት አልሆን ።

እናትዋን ወይዘሮ ንግሥት አርአያንና ወንድሞችዋን እግዚአብሔር ያጥናቸው። ገብረ ሩፋኤል ወልደ ማርያም ።

ማስታወቂያ

አዲስ አበባ በአቡጀዲ ተራ መደዳውን የአሉት በከማራ ስም የተጠራው የቤኔዳስ ኤምቻንድ አራት ጥሩ ጥሩ ሱቆች ታኅሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ ም ቅዳሜ ከኩለ ቀን በኋላ ልክ በ፱ ሰዓት በሐራጅ ይሸጣሉ ።

ነገሩን የሚፈጽም ከዚህ በታች በግርጌው ፈርማውን የፈረመው ሰው ነው ። በጨረታው ውሥጥ የሚጨመረው የገንዘብ ብልጫ በ፲፻፳ በ፴ና እነዚህን በሚመስሉ ቍጥሮች እየተበላለጠ ይሔዳል።

ገጋር የሆነው ሰው እንደገዛ የሚፈለግበትን ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ያለማዘግየት የከፈለ እንደሆነ የገዛቸውን ሱቆች ወዲያው ይረከባል።በከርታውም ውሥጥ የሚአስፈልገው የቃል ጭማሪ እንደሚገባ ተደርጎ በስሙ ሊዛወርለት ይቻላል ስንል እናስታውቃለን።

ቲ።ዲ።አየር
አሬሲዬል አሲኝ ።

የሚሲዮን መጽሐፍ መሸጫ ቤት ።

የሱዳን ኢንቴሪዎር ሚሲዮን ዶክቶር ለምቢ ዲሬክቶር ወደ ራስ መኰንን ድልድይ በሚወስደው መንገድ ማጅስቲክ ሆቴል የሚባለውን አለፍ ብሎ መሐመድ ኦሊ ኩባንያ አዲስ ሱቅ አሰራበት አጠገብ የመጽሐፍ መሸጫ ቤት መክፈቱን ያስታውቃል ።

ከዚያ በያይነቱ የጽሕፈት መጣሪያና በፈረንሣዊ በአማርኛም በእንግሊዝም በሌላም ቋንቋ የታተሙ መጽሐፍ ቅዱስና ደግሞም ማለፊያ ማለፊያ መጽሐፎች ይገኛሉ ።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ ጊዜ እንዳስታወቀው የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለዕዶችን ቦታ ኅዳር ፲ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ከጧቱ በ፬ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል።

የፊታውራሪ በዳኔ አሸግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፴፻፲ና ፲ሺ፺፻፺፮ ሜትር ካሬ።

የቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ አጥቢያው አማኑኤል ስፋቱ ፹፬ሺ ፹፱ ሜትር ካሬ።

የነጋድራስ ተፈራ ንጉሜ አጥቢያው ቂርቆስ ስፋቱ ፯ሺ፫፻፳ ሜትር ካሬ።

የወይዘሮ ዓመተ መንፈስ ቅዱስ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፬፻፸፯ ሜትር ካሬ።

የወይዘሮ ወለተየስ ሀብቴ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፪ሺ፫፻፲ ሜትር ካሬ።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሴጊያን ዘንድ ይገኛል ። ይህንኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተሩብ ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

የሚሸጥ ቦታ

ማጄስቲክ ሆቴል አጠገብ ከሙሴ ሃርዲ ፊት ለፊት መሐመድአሊ ከሠራው አዲስ ፎቅ በታች ጥሩ ጥሩ ቤት የተሠራበት በወሩ እስከ መቶ ብር ድረስ ኪራይ የሚያመጣ ጥሩ የሚሸጥ ቦታ አለና የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ አቡጀዲድ ገበያ ላይ ወችራጅ የሚባል ሂንዲን ጠይቁ።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

በዚሁም ጊዜያት ጠቅላላውን የሴቶችና የወንዶችን ውበቶች በሚያስረዳበት ጊዜ ግን ውቢቱ እመቤቴ ቀልጣፋና አቋቋመ መልካም እንድትሆን ይኸውም እየራሙ ዘመናት ይፈቅዳል በሚያሳዝነው አቀማመጣቸው ብዙ ሰዎች በሽተኞች ናቸው ። ደግሞም በምግባቸው አኑዋኑዋር እንዲሁም በጨካኝነትና ችግረኛ ፥ መሆናቸው ለመዳንም አይችሉም ። ለነዚሁም ሰዎች ብዙ ጊዜ የተወደደና በእውነት የማይሳሳተውን መድኃኒት እንሰጣቸዋለን። ሊፖቶዴን የሚባለውን በጥቅልል ያለውን መድኃኒቱን በጣም ሲያስጨንቅዎትና ሲያምዎት ቢሞክሩት ሕመምዎን በማቅለሉ ብዙ ደስ ያሰኝዎታል በአዲስ አበባ ውሥጥ ግዙፎችንና ሰውነተ ቂጡ ለሆኑ ሰዎች እየሩ አለመሰማማቱን ይልቁንም ከኔ የበለጠ ያውቁታል፡ይልቁንም ደግሞ ዋና ማስረጃ እንቅልፍ ለሌለውና ለሚባንን ሰው ነው ።

ለነዚሁም ሰዎች ፈጽሞ የሚከለክልላቸውን ዲአል ኮምፕሪሜ የሚባለውን መድኃኒታችንን በጣሙ የጠራውን ከምንሰጣቸው በተቀር ሌላ የማያስፈልግ መሆኑን እናስታውቃችኋለን ። ደግሞ ከዚህ በኋላ የሰውነት ሥራቸውን ተስማምተው ያለ ሐሳብ ሌሊቱን በደስታ ያልፉታል ስል ባለኝ እውቀቴ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አሳስባለሁ

ታዛዥዎ ኤም ማትሳኪስ ።

አቦማልተን
ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

አበማልተን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው። አበማልተን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል አቦማልተን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፥ ቤርን ናቸው። በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው።

አቦማልተን አዲስ አበባ በሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ማጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

Japanise Dentist
ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፯ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኪዎርከፍ ቤት ይገኛል ።

WHITE HORSE
WHISKY

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቀ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ሲንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም እንደኛው ሲንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፉና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቁረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሲንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክተር ሚክኤል ።

በሞንፐሊዬ ኡኒቨርሲቴ ።

ስለውሥጥና የሴት በሽታ ፤የቁስልና ፤የዓይን በሽታ የሴት አዋላጅነት ሕክምና የተመሰከረላቸው ድሮ ራስ መኰንን ድልድይ ቤታቸውን ትተው ወደ ጉለሌ መንገድ ሙሴ ሙራዲያን ቤት አጠገብ ቤት መለወጣቸውን ለወዳጆቻቸው በማክበር ያስታውቃሉ ።

ሁሉ ቀን ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፮ሰዓት ደግሞ ከ፱ ሰዓት እስከ ፲፩ ሰዓት ይገኛሉ ።

ሐሙስ ዕለት በጧቱ በሽተኞች አለዋጋ ያክማሉ ።

ለኢትዮጵያውያን ማስታወቂያ ።

ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ ከገሩ ይወጣል

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ስትገዙ የኢትዮጵያ ገንዘብ በአገሩ ይቀራል ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ የኢትዮጵያ ሥራ ነው ።

ይልቁንም ከውጭ አገር የመጣውን ቢራ ስትገዙ ለባዶው ጠርሙስ ቢያንስ አንድ አላድ ትከፍላላችሁ ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራን ገዝታችሁ ጠርሙሶቹን ብትመልሱ የጠርሙሶቹን ዋጋ አትከፍሉም የቢራውን ዋጋ ብቻ ትከፍላላችሁ እንጂ

ኢትዮጵያውያን ከወዳጆቻችሁ ጋራ የቅዱስ ጊዮርጊስን ቢራ ብቻ ጠጡ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

ቁ ፤ ፲፱፻፭ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፵፱
8me ANNE. № 49

ሐሙስ ኅዳር ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 1 Decembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie
Un an 5 Thalers
Etranger
Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የኢትዮጵያን ባንክ መሠረታዊ ደንብ የሚያፀና ሕግ።

በሕገ መንግሥቱ በ፶ነኛውና በ፶፪ኛው ክፍሎች የተወሰነውን ነገር ተመልክተን በ፳፫ ነሐሴ ፲፱፻፳፫ ዓ ም የተደረገውን አዋጅ ለመፍቀድ የሕግ መምሪያ ምክር ቤትና የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት መክረውበት የቈረጡትን ነገር ተመልክተን የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የቈረጠውን ነገር ስለፈቀድን ቀጥሎ የተጻፈውን እናውጃለን ።

ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።
አ ዋ ጅ ።

፩ኛ ክፍል፤ በኢትዮጵያ የባንክ ሥራ የሚሠራበትን አኳኋን ለመወሰንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ባንክ ለማቋቋም በ፳፫ ነሐሴ ፲፱፻፳፫ ዓመት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ያደረጉት አዋጅ በዚህ ሕግ የተፈቀደ ሁኗል። ሕግነቱም የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሁኖ በፍጹም እንዲከበር የፀና ሁኗል ። ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የጽሕፈት ሚኒስቴር ።

የፈረሶች መቀዳደም በጃን ሜዳ ።

በኅዳር ፲፱ቀን የፈረሶች መቀዳደም ነበረ ። ይህነኑ የፈረሶችን መቀዳደም ለማየት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልዑላን መሳፍንትንና መኳንንትን አስከትለው እንደማስታወቂያው ቃል በ፰ሰዓት ወደጃን ሜዳ መጥተው ነበረ ። የጃንሜዳም ዙሯ በወታደር ተከቦ ነበረ።ጃንሆይ የሚቀመጡበትም ቦታ በወርቅ በተከፈፈ ከፋይ አጐበር ተጋርዶ በመካከሉም በወርቅ ያጌጠ መንበረ ዳዊት ተዘርግቶበት ነበረ። ከዚህ በኋላ የፈረሶቹ መቀዳደም ተጀመረ።

የመጀመፘው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ፩ሺ ሜትር ነበረ ። በዚሁ መቀዳደም ዋቅኬኔ ቡሎ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነና ዋንጫና ዓርባ ብር አሰጠ ። ፪ኛ ሮቢ ጥርኝ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነና ፴ብር አሰጠ።፫ኛ ዳንት ቡሎ የኢጣልያ ሌጋሲዮን ፈረስ ሆነና ፲፭ ብር አሰጠ ።

የሁለተኛው መቀዳደም የሚዳው ርኅቀት ሺ፫፻ ሜትር ነበረ ። በዚሁም መቀዳደም መጀመፘ የሆነ ፪ ዋንጫ እንዲአስገኝ ደምብ ተደርጎ ነበር ። የተቀዳደሙትም ሮፓውያን ብቻቸውን ነበሩ።በዚሁም መቀዳደም ቡልቲም ጥርኝ የኮንት ፌዲቸለሬ ፈረስ ሆነ።፪ኛ ኮን ጥርኝ እንዲሁ በላይኛው የተጻፉት የኮት ፈረስ ሆነ። ፫ኛ በላክ ናይት ጥቁር የሰር ሲድኒይ ባርተን ፈረስ ሆነ ።

የ፫ኛው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ፪ሺ ሜትር ነበረ ።

በዚሁም መቀዳደም የመጀመፘው ሽልማትና ፺ብር የሁለተኛው ፴፭ብር የሦስተኛው ፳፭ብር እንዲአስገኝ ደምብ ተደርጎ ነበረ ። በዚሁ መቀዳደም ፩ኛ ሱዳን ጥርኝ ። ፪ኛ ራብር ጥርኝ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረሶች ሆኑና የተጻፈላቸውን አስገኙ።፫ኛ ዠፒቴር ቡሎ የሙሴ ፖስቶ ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ።

የአራተኛው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ፫ሺ፪፻ሜትር ነበረ።ታላቅ ለዝላይ የተሰናዳ ድምበርም ነበረበት።በዚሁ መቀዳደም የመጀመፘው ዋንጫና ፺ብር፤የሁለተኛው ፲፭ብር፤የ፫ኛው ፳፭ብር እንዲአስገኝ ደምብ ተደርጎ ነበረ ።

መጀመፘ ሻፓኝ ጥርኝ የሙሴ ደረፌ የፈረንሳዊ ሚኒስትር ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ ። ፪ኛ አረውን ዠክ ቡሎ የሰርሲድኒይ ባርተን የእንግሊዝ ሚኒስትር ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ ። ፫ኛ ኒቦድ ጥርኝ የማዠር ቤንቴግ ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ ።

የአምስተኛው መቀዳደም ።

የሚዳው ርኅቀት ሺ፪፻ሜትር ነበረ ። በዚሁ መቀዳደም ፩ኛው ዋንጫና ፺ብር፤፪ኛው ፴፭ብር፤ ፫ተኛው ፳፭ብር እንዲአ

ስገኝ ተወስኖ ነበረ።በዚሁ መቀዳደም ዳምጠው ጥርኝ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ። ፪ኛ ቲፎን ቡሎ የሚስ ባርተን ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ ።

፫ኛ ሰገሌ ጥርኝ የግርማዊት እቴጌ ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ ።

የስድስተኛው መቀዳደም ።

የሜዳው ርኀቀት ሺ፭፻ሜትር ነበረ ። በዚሁ መቀዳደም ፩ኛው ሰማንያ ብር፥ ፪ኛው ፵ብር፥፫ኛው ፳፭ብር እንዲያስገኝ ተወስኖ ነበረ።በዚሁ መቀዳደም አውራሬስ ቡሎ የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ፈረስ ፩ኛ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ ። ፪ኛ ኤሬን የማድሙዜል ባርተን ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ ። ፫ኛ ጁፒተር የሙሴ ፖስቶ ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ ።

የሰባተኛው መቀዳደም ።

የሜዳው ርኀቀት ሺ፫፻ሜትር ነበረ ። ፩ኛው ፪ዋንጫ፥ ፪ተኛ ፵ብር፥፫ኛው ፳፭ብር እንዲያስገኝ ተወስኖ ነበረ።በዚሁ መቀዳደም የማስተር ደአተሌ ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ።

፪ኛ ዚራንት ጥቁር የሰር ሴድኒይባርተን ፈረስ ሆነና የተጻፈለትን አስገኘ ። ፫ኛው ቀርቷል ዋጋ አልሰጡትም ። የፈረሶችን መቀዳደም እያየን ስንደነቅ ውለን ደስ ብሎን ነበር።ነገር ግን እማሆይ ስምን ተስፍራው ጠፍቶ እንዳሉት በፈረሶች መጽሐፍ የጃንሆይና የእቴጌ የልጆቻቸው ስም ብቻ ተጽፎ ስናይ ምንም ከመንግሥታችን ስም የበለጠ ደስታ ባይኖር ከዚህ ዕድል የመኳንንቶቻቸው ስም በመለየቱ ቅር አለን ። ወይ ፈረስ ጋራውን ዞሮ ወንዙን ተሻግሮ ባቀናው አገር እንደ ጉንዳን አንድ መንገድ ይዞ የሚሔድ ይህ አቶሞቢል የሚባለው ዘመናይ መኳንንቱን ሲቀማው እንዴት ድርቅ ብሎ ያዝን ይሆን? ነገር ግን በአንዱ ድክም አንዱ መግባቱ ከጥንት፤ የመጣ ነውና እጅግ የሚያስደንቅ አይደለም። በሸዋ የነበሩት የጀግኖች አለቆች እነራስ ጐበና ዳጨው (ዳጬ) እንዲህ አድርጎ በመኳንንቱ ዘንድ ፈረስ ተንቆ ከአጥር ውጭ በወታደሮች ቤት ጭብጥ ገለባና እፍኝ እህል የሚሰጠው አጥቶ እህህ ሲል ቢሰሙት እንዴት በገረማቸው ? የሞተ ሰው እስከ ዓለም ፍጻሜ አለመነሣቱ በእንደዚህ ያለ ጊዜ ያገለግላል ከዚህ ቀደም ብርሃንና ሰላም በዚህ ነገር ተቈርቍሮ መኳንንት የፈረስን ነገር እንዳይረሱ አስታውቆ ነበር ። ነገር ግን ብርሃንና ሰላም እንኳን ሊሰማና ተነበብም አይመስለኝም ። ተነበስ ቢሆን የጥንት ወዳጃቸውን አይረሱም ነበር ። አምስት ፈረሰኞች አስከትሎ እሱ ከፍ ባለው ድንጉላ ተቀምጦ ከሚሔድ ጌታና በአቶሞቢል ተቀምጦ ከሚሔድ ጌታ ማን ይከብር ይመስላችኋል?

ከድንገተኛና ከበሽተኛ በቀር ለኛ እደሚመስለንስ ፈረሰኞች ይሻላሉ ። ነገር ግን እኛን አሁን ቅር ያሰኘን ። የራስ እገሌ የደጃዝማች እገሌ የፊታውራሪ እገሌ ፈረስ የሚል ከመጽሐፉ ሳይኖር የሙሴ እገሌና የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና የእቴጌ የልጆቻቸውም ስም ብቻ በመጽሐፍ ተጽፎ የታላላቆች መሳፍንትና መኳንንት ስም በአለመጻፉ ነውና እንግዳ አለብን ማለት እንኳ ቢረሳ ለመቀዳደሚያ የሚሆኑ ሁለት ሦስት ፈረሶች በመቀዳደሚያ መጽሐፍ ስማቸውን ስናገኘው እጅግ ደስ ይለናል በማለት ነው የጻፍነው ።ጌቶቻችንን ያስቀይምብን ይሆን? ። ተዘጋጁ አትቀደሙ ማለት የሚአስቀይም ከሆነ መቸስ ምን እናደርጋለን።ነገር ግን ለሰው ቢሆን ልቀደም ባይሆንም ልከተል ማለት የሚገባ ይመስለናል።ከሁለቱ ሐሳብ የተለየ ሰው እንደ አልነበረ መስሎ ቢታየን ደንግጠን ይህን ለመጻፍ አሰብን

የማታ ማታ እውነት ያረታ ።

ይህን ተረት ምንም ቀድሞ ብትሰሙት እንደ ዛሬው ጊዜ አጋጥሞት በአደባባይ ቁሞ አላያችሁትምና ማስረጃውን ጨምረን ጽፈንላችኋልና ተጣታችሁ ስታነቡት ደስ ይላችኋል በማለት ተስፋ አድርገን ጽፈንላችኋል ። ይህም የተባለበት ምክንያት ፊታውራሪ አድማሱ ኃይሉ የአባቱን ገንዘብ ለማዘረፍ በአባቶቹ ከተማ በተነሣ ጊዜ ሕዝብ እንዲአብርለት ለጕጃም ይረዳል ይጠቅማል ብለው ጃንሆይ የሰጡን ዳኛ ከንቲባ ማተቤ ሚስቴን ቀሙኝ ብሎ አስወርቶ ነበርና የዚህ ነገር በአዲስ አበባ ከተማ ተወርቶ እንዲህ ሲበደል ምን ያድርግ? ቢበደልስ ከሶ ያስቀጣቸው ነበር እንጂ መንግሥትን መክዳት የት ይገባው ነበረ እያሉ ከሁለት የተከፈሉ የሕዝብ ወሬ እንሰማ ነበር ።ነገር ግን ምንም እውነት ለጊዜው ቢሞት ተቀብሮ አይቀርምና በኃጢአታቸው የተያዙ ፳፱ኙ በጕድሩ ገጋር በደጃች ደስታ እሸቴ እጅ ሦስቱ ባዛጋር ይርዳው እጅ ፩ዱ በአውሮፕላን በድምሩ ፴፪ ሰዎች ተይዘው መጥተው በኅዳር ፲፯ቀን በጃንሆይ ችሎት ቀርበው ከንቲባ ማተቤና ነጋድራስ ወዳጆ ዓሊም በአንድነት ቁመው ነበር ። ከዚህ በኋላ ነጋድራስ ወዳጆዓሊ የሚከተለውን የክስ ቃል አነበበ ።

ጃንሆይ ።

እግዚአብሔር ያሳይዎ ፊታውራሪ አድማሱ ላነሣው ጠብ መሥራቾችና አጋገሮች ተዋጊም ሁነው የተዋጉት እነዚህ ፊታውራሪ ዘውዴ እንግዳና ፥ ፊታውራሪ ዓለሙ ተድላ ፥ ቀኛዝማች አንተነህ ንጉሤ ፥ ቀኛዝማች ስብሓቱ ፥ ቀኛዝማች አከለ ባለህ ፥ ግራዝማች አያሌው ንጉሤ ፥ የሻቃ ምን ውዬለት ፥ የሥራህ ተገኘ ፥ ግራዝማች አጥናፉ ፥ ፊታውራሪ ተገኝ መሸሻ፥ አስፋው ዋሴ ፥ የሚባሉት ናቸው ።

እነዚሁም ፊትም የነገሩ መሥራቾች ሁነው ከግቢው እነከንቲባን ወግተው አስወጥተው ኋላም የውሽ ድረስ በግምጃ ቤቱ የነበረውን ጥይትና መሣሪ በየአለቃው ለወታደር አድለው መትረየሱን ከነተኳሾቹ ይዘው ካብ ሠርተን ቦታ ይዘን ከዮቤ እንዳንሻገር የጃንሆይ ትእዛዝ አልፎልን ነበርና ስንጠባበቅ በተጠባበቅንበት በኩል ሳይመጡ ፊታውራሪ አላምረውና፥ ቀኛዝማች ደምሴ ፥ በተሰለፉበት በጀርባ አደጋ ጥለው የተዋጉን የጦሩ አበጋዞች እነዚህ ናቸው ። በጦርነቱም ውሥጥ የሞቱት ብዙዎች ናቸው ከነዚሁም አንዱ ሟች ዋና ሰዎችን ቀኛዝማች ደምሴ የሚባል ነው ።

፪ኛ ፤ ከነዚሁም የጦር አበጋዞች ጋር ቅዳሜ መስከረም ፳፰ ቀን ከጧቱ ካንድ ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት ተኩል ተዋግተን በጃንሆይ ግምባር ብንመልሳቸው ከማታው በ፲ ሰ

ዓት ይሆናል።ዳግም ፊታውራሪ ዓለሙ ተድላና ፥ ቀኛዝማች እንተነህ ፥ በሰልፍ መጥተው እስኪጨልም ድረስ ተታኵሰን። ከዚህ ሁሉ በኋላም ጃንሆይ ምሕረት ልማድዎ ነውና የሞት ፍርድ ይገባቸው የነበረውን ትተው የሞቱን ፍርድ ምሬአለሁ ከእንግዲህ ወዲህ ከፊታውራሪ አድማሱ አትቀላቀሉ የሚል አዋጅ ቢነገርላቸው በዋጁ ቃል እንደመግባት ከጦርነቱ በኋላ አዋጁን አፍርሰው ከፊታውራሪ አድማሱ ጋር ተቀላቅለው ከግምጃ ቤቱ የተረፈውን ገንዘብ ዘርፈው የቀበሩትን ቈብረው ፊታውራሪ አድማሱ እጁን ለደጃች ወዳጆ እሰጠ ድረስ አብረው ሰንብተው በኋላ በየጫካው ገብተው ሳለ አገር ከበ የሚወጋቸው ቢሆን ወደ ክቡር ራስ እምሩና ለከንቲባም ምረናችኋል የሚል ማኅተም ስጡንና እንጣበ እያሉ በየዘመዶቻቸው በኩል እየተላላኩ ገቡ ።

፫ኛ ፤ በገቡም ጊዜ ምሕረት ለምነው የገቡ ሳይመስሉ ጕራዴና ሽጉጣቸውን ታጥቀው እየነቀነቁ ደጅ አጋፋሪዎችን እየገለመጡ እጅ ነሱ ። ከዚህ ሁሉ ጥፋታቸውም በላይ ሳይታገሡ በአደባባይና በግብርም ጊዜ ተከፉው ሥራቸው ያልተደበለቁትንና በሐሳባቸውም ያልመሰሏቸውን ሁሉ እኛስ ምን ተጐዳን እናንተስ ምን ተጠቀማችሁ የምንኖርበትም ባንድ አገር ነው ጊዜ ያገናኘናል እያሉ ሥራቸው ሁሉ መዘባበት ቢሆን ቀድሞውንም ጃንሆይ የሞቱን ፍርድ የማሯቸው የሚታገሡ መስሏቸው ነበር ።

እነሱ ግን ምሕረቱን ራሳቸው አፍርሰው ከጣሉት በጃንሆይ ፊት ባደባባይ ቀርበው ጃንሆይ እንዳወቁ ያድርጓቸው በማለት ታስረው ወደዚህ የተላኩት በዚህ ምክንያት ነው ።

ግርማዊ ሆይ ።

በግምጃ ቤቱም ውስጥ የነበረውን ሁሉ ሰብረው ጥይቱንና መሣሪያውን ብሩንም የዘረፉት ዋናዎቹ እነዚህ ናቸው ።

፬ኛ ፤ ከዚህ በላይ ስማቸውን ጠርተን የጻፍናቸው የውሽ ድረስ ጦር ከተው መትረየስ ይዘው ከንድ ሁለት ላይ ተከፍለው የወጉንን ለመለየት ነው እንጂ ፊታውራሪ አድማሱ የሌብነት አደጋ ጥሎ የገንዘብና የጥይቱን ቤት ሰብሮ አግቢው ከገባበት ቀን ጀምረው በከፉ ሥራ ሳይለዩ መከሬና ጦር ሰዳጅ ዘበኛም ሁነው ፊታውራሪ አድማሱ በደጃች ወዳጆ እጅ እውሮፕላን እገባ ድረስ ሳይለዩ የነበሩትንም ስማቸውን ቀጥሎ ባለው እናስረዳለን።ፊታውራሪ ደርሰህ በፈቃዱ፥ፊታውራሪ በዛብህ ይመር ፥ ፊታውራሪ ዘውዴ መኰንን ፥ ፊታውራሪ ደምሰው ይመር ፥ ፊታውራሪ ንጉሤ ኑርልኝ ፥ ፊታውራሪ እምቢአለ ፥ ፊታውራሪ ንጉሤ ዘገየ ፥ ቀኛዝማች ሰውነቱ ፥ ቀኛዝማች ንጋቱ ደስታ ፥ ቀኛዝማች ደስታ ወንዴ ፥ ቀኛዝማች ሽፈራው ዓለሙ ፥ ቀኛዝማች ይርሳው ዓለሙ ፥ ቀኛዝማች እንዳርጌ ዓለሙ ፥ አሳላፊ ንጋቱ ፥ ባሻ ብርሃኔ ፥ ሻቃ መንገሻ ፥ ሻቃ ልመንህ ፥ አዛዥ ሁነኛው ፥ አዳም ሰገድ ፥ ቀኛዝማች መሸሻ ዓሥራቴ ፥ እንደዚሁም ሌሎቹ አሉ ። በመጀመሪያው ጊዜ እንደተመለከተው ከገንዘቡ ዘረፋ ሳይለዩ ሰንብተው እነዚሁም ፊታውራሪ አድማሱ እጁን በሰጠ ጊዜ ያዋጁን ቃል ሳይፈጽሙ በየጫካው ገብተው በኋላ የመጡ ናቸው ከጦርነቱ ቦታ ደርሰው አይዋጉ እንጂ ሥራቸው ሊነገር የማይገባ ሁኖ ካልተውነው በቀር ከተዋጉትስ ይልቅ የነዚህ በደል የከፋ ነው።

ግርማዊ ሆይ ።

፭ኛ ፤ ከነዚሁም የጥቂቶችን እናመለክታለን ፊታውራሪ ደርሰህ በፈቃዱ ፥ በክረምቱ ውስጥ ፊታውራሪ አድማሱን በውሮፕላን ልትሔድ ነው ማለትን ሰምቻለሁና አሞኛል እያልክ ተኛ እያሉ ቀኛዝማች እንተነህንና ፊታውራሪ ዓለሙ ተድላን ፥ ከቤታቸው እየጠሩ ያማማሉና ነገሩን የጨረሱ እንደኛው እርሳቸው ናቸው ። ኋላም ፊታውራሪ አድማሱን የከዳህ ብለው አዋጅ አናግረዋል ።

፮ተኛ፥ፊታውራሪ ደምሰው ይመርም ጃንሆይ ዓርብ ዕለት ይህኑ ጦብ ስለሰሙ በዘሚ ስልክ ስልኩን እንዳይበጠስ እየጠበቅህ ለስልከኞቹም ዘበኛ ሁነህ እነከንቲባ ማተቤ ተቸግረዋል ማለትን ሰምቻለሁና ጦር ይዘህ ድረስላቸው የሚል ቃል ቢደርሳቸው ከዘሚና ከሊበን አውራጃ በጃንሆይ ቃል ጦሩን አዘው ወደ ማርቆስ ሲሔዱ ሳለ ጨሞጋን ተሻግረው ዓባይ ከሚባል ቦታ ሲደርሱ እነከንቲባን አግኝተው አመጣጣቸውም በትእዛዝ መሆኑን ሳይገልጹ ተሰልፈው እነርሱን አሳልፈው ከነጦሩ ማርቆስ ከፊታውራሪ አድማሱ ጋር ተቀላቅለው ከእሑድ እስከ ማክሰኞ አብረው ሰንብተው ፊታውራሪ ተገኝ መሸሻ፥ ቀኛዝማች ደስታ ወንዴ፥ ፊታውራሪ ደስታ ቢረሳው፥ ፊታውራሪ ደምሰው ሆነው አንድ ሣጥን ጥይት ተቀብለው ፊታውራሪ ተገኝ መሸሻ በጥይቱ የውሽ ድረስ መጥተው ወጉን እርሳቸው ተማርከዋል፤ ፊታውራሪ ደምሰው ግን በዕርቅ አመካኝተው ሊሰልሉን መጥተው ሳለ ተይዘው ነበርና ለመመለስ ጊዜ ስለአጠራቸው ከጦርነቱ አልዋሉም እንጂ መንግሥቱን የበደሉ ዓይነተኛው እርሳቸው ናቸው።

፯ተኛ፥ ቀኛዝማች አድገህ ቢሰውርም ውዝፍ ያጋ ሆነው የሚኖሩና በተለይም ያገር ምስለኔ ናቸው ለሹመታቸውም ጃንሆይ በቸርነትዎ በራስ ኃይሉ ጊዜ የያዛችሁትን እንደያዛችሁ ራስ እምሩ እስኪመጣ አገራችሁን ጠብቁ የሚል ለሁሉም በዋጅ ስላስታወቁት የያዙትን ይዘው ተከብረው የተቀመጡ ሰው ናቸው፥ እንዲህም ታምነው ጃንሆይን ሳይከዱ በሥዕልና በመስቀል ተገዝተው የተቀመጡት ሰውዬ ፊታውራሪ አድማሱ መሃላውን አፍርሶ ቢከዳ እርሳቸውም መሃላውን አፍርሰው ከሱ ጋራ ከዱ ከዳታቸውንም ለማስታወቅ ያልከዱውን ታማኙን ጕጃምን ከዳተኛ አድርገው፥ጕጃሞች ከድተናችኋልና አገራችንን ልቀቁልን እናንተም ሸዋን መስላችሁ ኑ እኛም ጕጃምን መስለን እንቆያችኋለን ብለው ስለ ተናገሩ ይህማ ከሆነ ወዳጅ ጠላታችንን አልፍ ብለን ሰፍረን እንለየው በማለት ከንቲባ የማርቆስን ከተማ ለቀው የውሽ የመጡበት በዚህ ምክንያት ነው ይኸውም ነገር በክቡር ራስ እምሩ ፊት ተመስክሮባቸዋል። ሁለተኛም መልክተኛ መስለው በተመላለሱበት ጊዜ ሁሉ ፊታውራሪ አድማሱን ከመርዳት አልተመለሱም። አንድ ሣጥን ጥይትም ተቀብለዋል። አሁን ክቡር ራስ እምሩ ከገቡ በኋላ የልጃቸው ባል ቀኛዝማች አከለ የውሽ ድረስ መጥቶ ተማርኮ አዲስ አበባ መጥቶ ስለነበረ ለጃንሆይ

እኔ ልሠር ብለው ስላስታወቁ በአውሮፕላን መልሰው ልከውት ነበርና በዚሁ በቀኛዝማች አከለ ላይ ሌላ ነገር ተሰምቶበት ለመጠየቅ ያቀርቡ ቢባሉ ከቤቴ ከሔደ ሦስት ቀን ሁኖታል የለም ብለው በሐሰት ተፈጠሙ። ከተፈጠሙ በኋላ ግን ዘበኛ ከቤታቸው ቢሔድ ከልፍኛቸው ተቀምጠ ተገኙ፣ እኒሁም ቀኛዝማች አድገህ አዲስ አበባ በአውሮፕላን ከፊታውራሪ አድማሱ ጋር ቢመጡ የፊተኛውን ጥፋትና ተንኰላቸውን ታግሠው ሦስት መቶ ብር ሰጥተው አክብረው ቢመልሷቸው የጃንሆይ ሀብት የተንኰለኞችን ሥራ ገላጭ ነውና ቀኛዝማች አከለን ከልፍኛቸው ሸሽገው በመፈጠማቸው ያለፈውን ተንኰል ሥራ ሁሉ ገለጹባቸው ።

፰ተኛ፡ ቀኛዝማች መሸሻ ዓሥራቴም ግራ ወምበርሁነው የሚኖሩ ናቸው ይህን ሹመታቸውን እንደያዙ በክብረት ቄይተው ሳለ ሊነገር የማይገባ የሐሰት ወሬ በሕዝቡ መከከል ሰባኪ ሁነው ተማክረው የሕዝቡን አእምሮና ሐሳብ የለወጡ እኒህ ናቸው።

፱ኛ፡ ደህም ድልነሣሁ የሚባል ሰው ዓርብ ፊታውራሪ አድማሱ ዓምጃ ቤቱ ላይ አደጋ ጥሎ በገባ ጊዜ እሱም በበኩሉ የግምጃ ቤቱን ሰብሮ የራስ ኃይሉን ፎቶግራፍ አውጥቶ ይዞ ራስ ኃይሉ ተፈትተው መጥተውልሃልና ጐጃም አውራሁን ተቀበል እያለ ሌላም ለጆሮ የሚከብድ ጸያፍና ሐሰት የመላበት ነገር እየሰበከ ሕዝቡንና ገንዘቡን ያስጨረሰው አንዱ እሱ ነው። ይኸውም ድልነሣሁ ባዋጁ ሳይገባ ከከተማ ስለራቀ ካለበት ቦታ ሰው ታዞ ሒዶበት ነበርና ተታኵሶ ነው የተያዘው።

፲ኛ፡ ይህን ሁሉ መሥራታቸው ሳይታሰባቸውና በጥፋታቸውም ሳይጸጸቱና ሰላማዊ ሁኖ የሚኖረውን ደገኛውን የጐጃምን ሕዝብ አእምሮውንና ባሕሪውን ለመለወጥ ሐሳባቸው ተነሣስቶ ደግሞ ደም ለማፍሰስ ባደባባይና በቤተ ክርስቲያንም የትዕቢት አነጋገር ሲናገሩ ይሰሙ ነበር።

ግርማዊ ሆይ።

፲፩ኛ፡ አሁን ግን እኛ የምንጠይቃቸው የሞቱን ፍርድ በቸርነትዎ ምሬአችኋለሁና ከፊታውራሪ አድማሱ ጋር ዳግም እንዳትቀላቀሉ ብለው ባዋጅ ቢያስታውቋቸው ከጦርነቱና ከዋጁም በኋላ ወደኛ እንደመምጣት ከፊታውራሪ አድማሱ ጋር ተመልሰው ተቀላቅለው የፊታውራሪ አድማሱም እጅ ከደጃች ወዳጄ እጅ ገብቶ በውሮፕላን ከመጣ በኋላ እንደ አዋጁም ቃል በከተማ ሳይቈዩ በየጫካው ሰንብተው ባዋጁ ሳይሆን በመላከት ከገቡ አዋጁን በገዛ እጃቸው እነርሱ አፍርሰውታልና ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ በሠሩት ኃጢአት ይቀጡልን ስንል አቤቱታችንን እያቀረብን ፍርዱን እንጠብቃለን።

ከንቲባ ማተቤም የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ለግርማዊ ማስታወሻ

ወደ ጐጃም ስሔድ በአውሮፕላንም ቢሆን በቶሎ ሒጄ ፈቃድዎን ልፈጽም ማለቴ በሞቴ ቈርጬ ነው ግንቦት ፳፫ ቀን ተነሥቼ ፳፰ ቀን ማርቆስ ከተማ በጧት ገብቼ ያዋጁንም ቃል አናግሬ የተጻፈውን የጃንሆይን ማኅተም ሁሉ በያድራሻው ሰጥቼ ለጊዜው ከከተማ ላልተገኘውም ያዋጁን ቃል እየጨመርኩ በመልክተኛ በየሃገሩ ሰድጄ ካህናቱንም፣መኳንንቱንም፣ሕዝቡንም በሥዕል በመስቀል አምየ በቄስ አስገዝቼ ትልልቁን ሰው ሁሉ አስፈርሜ በተቻለኝ አውቀቴ ሰብኬ አገሩ አንድ ልብ ሁኖ ልጅ ኢያሱን ለመያዝ በቆላ በደጋ ታዞ ሒዶ ሰኔ ሁለት ቀን በምክንያት ለማፋረስ የወይዘሮ ሰብለ ወንጌል አሽከሮች ተኵሰ ቢአነሡ በግቢው ውሥጥ በተኵሱ መከከል እኔው ራሴ ገብቼ የተኰሱትን ሁሉ አስይገር የሚገባ ቅጣታቸውን ሰጥቼ ወህኒ ብሰዳቸው ወስላታውም ሁሉ ደነገጠ፤ ልጅ ኢያሱም ወዲያው ተያዙ የግርማዊነትዎ ዕድል በርትቶ እኔም በሔድኩበት ባለማፈሬ ጠላትዎም በመያዛቸው ፈጣሪዬን በብዙ አመስግኜ ደግሞ ወደፊት የምታዘዘውን ስጠባበቅ ሰኔ ፲፱ ቀን አገሩን ለራስ እምሩ ሰጥቸዋለሁና አዋጁን አስነግር ላንተም ያሰብኩትን አስታውቅሀለሁ የሚል የግርማዊነትዎ ቃል በቴሌግራም ቢአልፍልኝ እንኳን ንጉሠ ነገሥት ማናቸውም ጌታ ቢሆን ላሽከሩ የሰጠውለት ያስታውቀዋል እንጂ ይህን ያህል ተስፋ ለኔ ማስታወቃቸው ለማንም ያልተሰጠ ከክብር ሁሉ የበለጠ ነው ብዬ ደስ ብሎኝ በተስፋው ምድር ስሜ ያዘዙኝንም ሠርቼ ይህንኑ የፈራሁትን ሐሜታ ያመለጥኩ መስሎኝ ወደጌታዬ ለመምጣት ብነሣ እኔ ሳልጠራህ አትምጣ የሚል ቃል ስላላፈልኝ ጌታዬ እንኳን አልከለከሉኝም ብኔ ምክንያት ወጭ እንዳይበዛና ገንዘብ እንዳይበላሽ ብዬ በመንግሥት ሹማምንቶች ከተሠራው ከመኳንንቶችዎ ጋር ኅብር ጠብቄ በልቼ ራሴንና ሥራዬን የጠበቅሁ መስሎኝ ብርዝ ጠጥቼ እግሬን እንኳን ቢያመኝ እሳት እያስነደድኩ ከችሎት ሳልለይ እነዚሁ ላጥፊነት የተነሡ ሰዎች ፊ አድማሱ ከቸፈር ሳይነሣ ጀምረው ውኃ ሳይሞላ ማርቆስ እንዳትገባ በአውሮፕላን አዲስ አበባ ሊሰዱህ ነው እያሉ ልከውብት ኑሮ በሐምሌ ገባ ዕለቱን የገባ ዕለትም በሌላውም ቀን እጁን ለመያዝ ባስብ አድማው በሙሉ መሆኑን አይቼ ጀልባው በትክክል እስቲዘረጋ አውሮፕላንም የሚመጣበት ወር እስቲደርስ ብናቄየው ይሻላል አሁን በውኃ ሙላት እንያዘው ያልን እንደሆነ በገንዘቡ ምክንያት ጐጃም ሁሉ ይከዳናል ረዳትም አውሮፕላንም እንዳይመጣልን ሐምሌና ነሐሴ ነው እርሱን አምለን አስገዝተን አሽከሮቹን አሰናብተን ቢቆይ ይሻላል ብለን አብረውኝ ካሉት መኳንንቶች ጋር መከረን በመንግሥትዎ ክፉ ነገር እንዳያስብ ማርቆስ አግብተን አምለን ወንጀል ካልተገኘበት በሰውወሬ ላላሥረው በመስከረም ወደጃንሆይ ሊመጣ እኔንም አምሎኝ ወደ ጃንሆይም ልምጣ ብሎ ጽፎልዎ ነበር በመስቀል ግብት ምክንያት እንኳን አምባገር እንዳይነሣ ተጠንቅቄ የጠበቅሁትን ቀን ሁሉ አስተላልፎ ባልታሰበ ቀን የሌብነት አደጋ ጥሎ የገንዘብና የጥይቱን ቤት ያዘብን ቀድሞም ከሸዋ ዘበኛ አለመታዘዙ ጐጃምን አምነው ለሀገሩ አዝነው ነበር የታመነው ጐጃም ከድቶ በኛ ላይ እየተኰሰ ገንዘቡንም ጥይቱንም ተካፈለው የራስ እምሩ ሰዎች እንኳን በየሃገሩ ለሥራ ተበትነው ከኔና ከቀኛዝማች ወልደየስ ጋር የሚያድሩ አሽከሮችና ከነጋድራስ ወዳጆ ጋር የሔዱ ዓርብ አንድ ዘበኛ ሁነን ከጧት ጀምረን እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ድረስ ተታኵሰን

ኸወዲያውም ከወዲህም ሰው ከመጕዳት በቀር ገንዘቡን ለማዳን የማንችል ሆነ።በውጭ ተቋርጠው ተቀሩት ከኛም ሰው ጭምር ጕጃሞችም ሁነው ሙታችኋል ብሎ አገሩ ተጨንቆ ነበር ነፍሳችሁ ከለ ከግቢው ውጡልንና ጕጃም ያያችሁ እንደሆን በመንግሥት ስም የተቀመጣችሁትን ተስፋ አድርጎ ሁሉም ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይረዳል ።

ገንዘቡም ርቆ ሳይሔድ እርሱም ከግቢው ሳይወጣ ከበን እህልና ውኃ ከልክለን እንያዘው እናንተ የሞታችሁ እንደሆን ግን ማንን ተከትሎ ለመንግሥት ይረዳል ጕጃምም በሙሉ መከዳቱ ነው ጃንሆይም አገሩን ሲአጠፉት ብዙ ጕዳት እንዳይሆን ወጥታችሁ ከነደጃዝማች ገሠሠ፥ ከናዛጋ ደስታ፥ ከነፊታውራሪ አሳምረው ጋር ተገናኝታችሁ ጕጃም ይያችሁና ወገን ይለይ ስላሉን እነሱ ለተንኰል አሰበው ሠርተውትም እንደሆን በኛም በኩል ብንመለከተው የተቈረጠውን ስልክ ቀጥለን የአይሮፕላን ማረፊያ አሰናድተን ለስልኩና ለጀልባ ዘበኛ አቁመን ለግርማዊነትዎ እየመለከትን ወገን ለይተን ትእዛዝዎን ብንቀበል ይሻላል እንጂ ገንዘቡና ጥይቱ ከሔደ በኋላ እጃችንም ቢያዝ እርሱ ኃይል ማግኘቱ ነው ብንሞትም ያሸከርቱ ደም የፈሰሰበት ብለው ጥቅም እንዳይገኝበት ገጾዮች ገበሮቻችን ስለሆኑ በኛ ሞት ተቈጥተው ጕጃምን ሲአጠፉት ለበዕድ ደስ ማሰኘት ይሆናል በማለት ተመልክተን አኳኋናችንን ብናመለክትዎ ጠላትዎን የሚጐዱበት፥ አማኝዎን የሚያድኑበት ኃይለኛ ሥልጣንዎ በየቀኑ ወደኛ በመተላለፉ መስከረም ፳፰ ቀን ከቀን ሁለት ጊዜ የመጣውን ጦር ድል አድርገን ከወጣንበት ከተማ ጥቅምት ፫ቀን ተመልሰን መጣባታችን ትንፋሽም የመልአክ ሰይፍ በመሆኑ እኔም ጌታዬን አመሰግናለሁ።ጌታዬም እንዲህ አድርጎ ሙሉ እንደራሴነት የሰጥዎ እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑት ይገባል። ይህም አሳቤን ከተጠቀለለ በኋላ ለኔ የመሰለኝ ምንም አቅም እንደሌለኝ ባውቀው በመንግሥትዎ ስም ነበርና የተቀመጥኩ ከውቀቱ ጉልበቱ ከጉልበቱ እውቀቱ የተሰማማ ሁኖ ከንቲባ ማተቤ መልከም ሥራ ሠራ ተብዬ በሰሩው ምስጋና አገኛለሁ ።ስሜም በብርሃንና ሰላም ይነሣል በማለት ነው ነገር ግን ከላይኛው አርእስት እንደጻፍኩት ይኸው የፈራሁት ሐሜታ ተከትሎኝ በድማሱ የተነሣ ሚስቱን ቢቀማው ነው ተባልኩ ለዚህም ጕጃም ሳለሁ እንዳሳለፍኩልዎ ቢሥልጣንዎ የሚመረመር ነው አድማሱን ጡት ማጥባቱ ግን አዲስ አበባ ስሔድ ከሰርስዎ የማውቀው ዘመድ የለኝምና ጡት ያጥቡኝ ብሎ ከጫማዬ ላይ ቢወድቅ ጋብቻው ይከለክላል ብዬ እንኳን ምክንያት ባደርግበት ሊቃውንቱን ጠይቆ ዝምድናው ለሁላታችሁ ነው አይከለከልም ስላሉ ልቡን ወደ ሰላም የመራሁት መስሎኝ ጡት ማጥባቱ እውነት ነው ከዚህም የቀረውን በቃሌ አመለክታለሁ ።

ከዚህ በኋላ በምን ምክንያት አዋጅ አፍርሳችሁ አገር ልታጠፉ አሰባችሁ ? ብለው ጃንሆይ ቢጠይቋቸው ከነዚህ ከአጥፊዎች መኳንንት አንዱ ቀኛዝማች አንተነህ የሚባለው ያኑ ያወሩለትን የሐሰት ወሬ ይዞ የፊታውራሪ አድማሱን የልጅ እናት ከንቲባ ማተቤ ቢቀሙ ነዋ አለ ። ከንቲባ ማተቤም ። ይህን የሐሰት ወሬ ሲአወሩብኝ እየሰማሁ ከኔ በላይ ያሉትም ታላላቆች ጌቶች ይታማሉ መቸስ በሐሜት ምን አደርጋለሁ ብዬ ትቸው ነበር ዛሬ የኃይለ ሥላሴ አምላክ አውጥቶ ከናገረልኝ እንግዲህ ይርታኝና እንኳንስ መገናኘት መልኳን ያውቃታል ብሎ ምስክር ቢመሰክርብኝ መልኳን በማወቄ ብቻ ልረታና ልቀጣ አሉ ።

ከዚህ በኋላ ደጃዝማች ወዳጄ ተነሥተው መንግሥት አምኖ ሹሞ ልኮታል ከፉ ሥራስ ሠርቶ እንደሆነ ከንቲባ ማተቤ ይከሰሳል እንጂ መንግሥት ይከዳልን ብለው ጠየቁ። ከቡር ፊታውራሪ ብሩ የጦር ሚኒስትርም ተነሥተው እኛ መኳንንቶቻችንን የምናምናቸውን ሹመን ብንልክ ጦር አንሥታችሁ ወጋችኋቸው አሁን ደግሞ በማን ምስክር ልትነጣጠሩ ነው ብለው ጠየቁ ። ከዚህ በኋላ ከሥረኞቹ አንዱ መልከቸው ሞኝ የሚመስል ቀኛዝማች አድገህ የሚባሉ ብልህ ሽማግሌ ጃንሆይ እነዚህን ሹማምት እንደ ዓይንዎ እንደልብዎ አድርገው ልከዋቸዋል። እኛ የማይገባ ነገር አድርገን እንደሆነ የታሠርንበት ሰንሰለት ወደ መቃብር ታውርደን እነሱም ያላጠፉነውን አጥፊ አስመስለው ጽፈውብን እንደሆነ መቸስ ምን ይደረጋል እንደአደረጉን መሆን ነው እንጂ ጃንሆይ ዓይኔ ልቤ ብለው ከሰደዷቸው ሰዎች ጋራ ተሟግተን ምን እንጠቀማለን አሉ ። ለጃንሆይና ለመኳንንቱ ለሰማውም ሰው ሁሉ ይህ ቃል እጅግ ደስ አሰኘ ። ጃንሆይም የሽማግሌ ቃል እንዲህ ነው ቀድሞም የአክልን ቅጣት ምሬአችሁ ነበር አሁንም ቃሌን አላለውጠውም ምሬአችኋለሁ ከእሥር ተፈትታችሁ በሰጡኋችሁ ቦታ ተቀምጣችሁ ክፉታችሁም ደግነታችሁም እየደረ ይመረመራል ባሉ ጊዜ እሥረኞችና ዘበኞች ሁሉም በንድነት እልል አሉ ። ስለ ከንቲባ ማተቤም ነገር ይህ የምታወሩት ነገር እውነት ነውን ብለን ፊታውራሪ አድማሱን ብንጠይቀው ለጠብ ማነሻ ብዬ አስወራሁት እንጂ ከንቲባ ማተቤ እንዲያውም የሚስቴን መልኳን አያውቋትም ብሎ መስክሮዋልና ጥፋቱን አውቀናል ብለው ጃንሆይ በግርማዊ ቃላቸው በመሰከሩ ጊዜ እንኳን ከንቲባ ማተቤንና የእውነትን ወዳጅ ሁሉ እጅግ ደስ አለው ። እሥረኞቹም ተፈቱ እውነትና ንጋት እያደረ ይገለጻል ብሎ የተረተው ሽማግሌ መልክም ተናገረ። ከንቲባ ማተቤ በራስ ጉግሣ ወሌ ጦርነት ጊዜ በግሥገሣ ተልከው መልእክታቸውን ፈጽመው መጡ ዛሬ ደግሞ በድንገት ተልከው ቸሩ አምላክ ከሞት አትርፎዋቸው ቢመለሱ በእንደዚህ ያለ ክፉ ስም ሊአጠፉአቸው ነበር። ጃንሆይ በረቂቅ ሐሳባቸው እውነተኛውን ነገር መርምረው ስለአገኙላቸው የኔ ለት ይኸው ነው የሚል በዓለአእምሮን ሁሉ እጅግ ደስ የሚአሰኝ ነው ።

ጥቅም የሚገኝበት የሐሳብ ውጥን ።

ኢትዮጵያ በወርቋ ብዛት ስሟ ሲጠራና ሲተረክ የዘመኑ ልክ አይታወቅም ፥ ያገሩም ሕዝብ ምንም በያመቱ መጠን የሌለው ወርቅ እያጠበ ወደ ውጪ አገር እየሰደደ ቢሸጥ እስከ ዛሬ ድረስ የወርቁን አገር በጥበብ አካሒድ መርምሮ የብልጽግናውን ልክ ያወቀ ሰው የለም ስለዚህ የኢትዮጵያ

አያሌ ሰዎች ተማክረው የወርቁን አገር በጥበብ አካሔድ አስመርምረው ብዙ ወርቅ መኖሩን ከተረዱ በኋላ ወርቅ የሚያወጣ የኢትዮጵያ ማዕደን ማኅበር ለማቋቋም ቍርጥ አድርገዋል።

በዚህ ማኅበር ውሥጥ ለመግባት የሚፈቅድ ማንኛውም ሰው አክሲዮኑን ለመግዛት ይችላል።ያንዱም አክሲዮን ዋጋ ሐያ ብር ነው ። ስለሚቋቋመውም ማኅበር ሁነው አክሲዮኑን የሚሸጡ ቀጥሎ ያሉት የማኅበር ቤቶች ናቸው።የኢትዮጵያ ባንክ፤የእርሻና የንግድ ማስፊያ ማኅበር (ሶሲዬቴ ናሲዮናል ዴቲዮፒ) የኢትዮጵያ የንግድና የሥራ ማኅበር (ሶሲዬቴ ኢቲዮፒየን ዶኮሜርስ ኤዴንዱስትሪ) ናቸው፡ስለ ማኅበሩም አቋቋም ለማወቅ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ከነዚህ ከሦስቱ ቤቶች መጠየቅ ይቻላል።

INITIATIVE INTERESSANTE

Depuis des temps immémorables l'Ethiopie est reputée, comme un pays riche en or et malgré que les habitants lavent l'or en Ethiopie et une grande quantité de ce minerai précieux est exporté tous les ans, jamais encore personne n'a fait des prospections systématiques des régions aurifères.

Plusieures personnalités Ethiopiennes ont decidé la formation d'une Societé Minière Ethiopienne qui aura pour but l'étude systématique des terrains reconnus aurifères et décidera la création éventuelle d'une Societé d'exploitation si ces terrains son suffisamment riches en or.

Les personnes desireuses de souscrire aux actions de la Societé Minière Ethiopienne dont la valeur nominale est de thalers vingt chaque, peuvent avoir tous les renseignements à la Bank of Ethiopia, à la Societé Nationale d'Ethiopie et à la Societé Ethiopienne de Commerce et d'Industrie.

አቦማልቲን ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

አቦማልቲን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው፥አቦማልቲን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል አቦማልቲን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኀይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፥ ቤርን ናቸው።በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው ።

አቦማልቲን አዲስ አበባሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ማጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

Japanise Dentist
ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፯ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

ALL AIR EXTRACTED
The Old Blend Whisky of the White Horse
ዊስኪ

WHITE HORSE
WHISKY

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናኚ በኢትዮጵያና በጅቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወከሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ ጊዜ እንዳስታወቀው የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ቆዶችን ቦታ ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፫ዓ ም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ብአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል።

የፊታውራሪ ባዴኔ አሻግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፱፻፲ና ፲ሺ፯፻፶፩ ሜትር ካሬ።

የቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ አጥቢያው አማኑኤል ስፋቱ ፳፬ሺ ፳፱ ሜትር ካሬ።

የባሻ ወልዴ ዮሐንስ አጥቢያው ማርያም ስፋቱ ፲፩ሺ ፯፻፳፬ ሜትር ካሬ ።

የወይዘሮ ዓመተ መንፈስ ቅዱስ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፬፻፹፯ ሜትር ካሬ።

የወይዘሮ ወለተየስ ሀብቴ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፪ሺ፫፻፹ ሜትር ካሬ።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሴጊያን ዘንድ ይገኛል ። ደህነኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተሩብ ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

የሚሸጥ ቦታ

ማጅስቲክ ሆቴል አጠገብ ከሙሴ ሃርዲ ፊት ለፊት መሐመድ አሊ ከሠራው አዲስ ፎቅ በታች ጥሩ ጥሩ ቤት የተሠራበት በወሩ እስከ መቶ ብር ድረስ ኪራይ የሚያመጣ ጥሩ የሚሸጥ ቦታ አለና የምትፈልጉ ሰዎች ሁሉ አቡጀዲድ ገበያ ላይ ወችራጅ የሚባል ሂንዲን ጠይቁ።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

በዚሁም ጊዜያት ጠቅላላውን የሴቶችና የወንዶችን ውብቶች በሚያስረዳበት ጊዜ ግን ውቢቱ እመቤቴ ቀልጣፋና አቋቋመ መልክም እንደትሆን ይኸውም እየራመዘመናት ይፈቅዳል በሚያሳዝነው አቀማመጣቸው ብዙ ሰዎች በሽተኞች ናቸው ። ደግሞም በምግባቸው አኑዋኑዋር እንዲሁም በጨለኝነትና ችግረኛ መሆናቸው ለመዳንም አይችሉም ። ለነዚሁም ሰዎች ብዙ ጊዜ የተወደደና በእውነት የማይሳሳተውን መድኃኒት እንሰጣቸዋለን። ሲፖቶዴን የሚባለውን በጥቅልል ያለውን መድኃኒቱን በጣም ሲያስጨንቅዎትና ሲያምዎት ቢሞክሩት ሕመምዎን በማቅለሉ ብዙ ደስ ያሰኝዎታል በአዲስ አበባ ውሥጥ ግዙፎችንና ሰውነተ ቄጠ ለሆኑ ሰዎች አየሩ አለመስማማቱን ይልቁንም ከኔ የበለጠ ያውቁታል፡ይልቁንም ደግሞ ዋና ማስረጃ እንቅልፍ ለሌለውና ለሚባንን ሰው ነው ።

ለነዚሁም ሰዎች ፈጽሞ የሚከለክልላቸውን ዲአል ኮምፕሬሜ የሚባለውን መድኃኒታችንን በጣሙ የጠራውን ከምንሰጣቸው በተቀር ሌላ የማያስፈልግ መሆኑን እናስታውቃችኋለን ። ደግሞ ከዚህ በኋላ የሰውነት ሥራቸውን ተስማምተው ያለ ሐሳብ ሌሊቱን በደስታ ያልፉታል ስል በለኝ እውቀቴ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አሳስባለሁ

ታዛዥዎ ኤም ማትሳኪስ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም እንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕያወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመንብናት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክተር ሚክኤል ።

በሞንፐሊዮ ኡኒበርሲቴ ።

ስለውሥጥና የሴት በሽታ ፣የቍስልና ፣የዓይን በሽታ የሴት አዋላጅነት ሕክምና የተመሰከረላቸው ድሮ ራስ መኰንን ድልድይ ቤታቸውን ትተው ወደ ጉለሌ መንገድ ሙሴ ሙራዲያን ቤት አጠገብ ቤት መለወጣቸውን ለወዳጆቻቸው በማክበር ያስታውቃሉ ።

ሁሉ ቀን ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፮ሰዓት ደግሞ ከ፰ ሰዓት እስከ ፲፩ ሰዓት ይገኛሉ ።

ሐሙስ ዕለት በጧቱ በሽተኞች አለዋጋ ያክማሉ ።

የሚሲዮን መጽሐፍ መሸጫ ቤት ።

የሱዳን ኢንቴሪዮር ሚሲዮን ዶክቶር ለምቢ ዲሬክቶር ወደ ራስ መኰንን ድልድይ በሚወስደው መንገድ ማጅስቲክ ሆቴል የሚባለውን አለፍ ብሎ መሐመድ አሊ ኩባንያ አዲስ ሱቅ አሰራበት አገጠብ የመጽሐፍ መሸጫ ቤት መክፈቱን ያስታውቃል ።

ከዚያ በያይነቱ የጽሕፈት መሣሪያና በፈረንሣዊ በአማርኛም በእንግሊዝም በሌላም ቋንቋ የታተሙ መጽሐፍ ቅዱስና ደግሞም ማለፊያ ማለፊያ መጽሐፎች ይገኛሉ ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

በሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው

ወደፈለጉት እንጨቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

ቁ ፤ ፯፻፹፯ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፶
8me ANNE. № 50

ሐሙስ ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓም
Jeudi 8 Decembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ ባ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ጥቅም ያለው የትያትር መጽሐፍ ።

ይህን ጥቅም ያለው የትያትር መጽሐፍ ክቡር በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ጽፈው ለሕፃናት አስጠንተው በ፲፱፻፲፫ ዓመተ ምሕረት በሙሴ ቴራስ ሆቴል የትያትሩን ጨዋታ አሳይተው ጥቂቶችን ሰዎች እንጂ ብዙዎችን ሰዎች ደስ ለማሰኘት አልሆነላቸውም ነበር።ምክንያቱም በዚያ ዘመን ከአዋቂዎች ይልቅ አለአዋቂዎች በኃይል ስለበዙ ነው ። ይህንም ደስ የሚያሰኝ መጽሐፍ ከላይ እንደአመለከትነው የአለአዋቂዎች ኃይል ስለበዛ እንዲጠፉ መክረው የታተሙትን ብዙዎችን መጻሕፍት አጠፉአቸው።

ነገር ግን ምንም በረዶ ቢመታው አንበጣም ቢበላው የተዘራ ፍሬ ለዘር ያህል በጭራሽ አይጠፋምና ከደኅና በታ ተጠግተው ተመከሬ የዳኑ ጥቂቶች መጻሕፍት ተገኙ።ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ይስጥልን እንጂ ጊዜው እጅግ የተሻሻለ ለሆነ እነዚህን ስደተኞች መጻሕፍት በጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት ፈልገው አጠራቅመው ለቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንዲአስጠና ለዲሬክተሩ ለአቶ ዮፍታሔ ንጉሤ ሰጥተውት ተማሪዎችም ደኅና አድርገው ካጠኑት በኋላ በኅዳር ፲፩ ቀን በዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት ተደረገና የተሰበሰቡትን ሰዎች እጅግ ደስ አሰኘ። ነገር ግን ለተማሪ ቤት እርዳታ ተብሎ ጥቂት የሚከፈል ገንዘብ ነበርና ከታወቁት ሰዎች ብዙዎቹ ስለቀሩ የተሰበሰበው ሕዝብ እጅግ አዘነባቸው። የትያትሩንም ቃል በአንድ ጊዜ ለማተም ስፍራ የማይበቃ ስለሆነ ጥቂት ጥቂቱን በየሳምንቱ እናትምላችኋለን ። የመጀመሸውም ቃል የሚከተለው ነው ።

መቅድም ።

ኮሶና ቁም ነገር ይመሳሰላሉ።ያለ ማጣፈጫ እጅግ ይመራሉ ። ኮሶን ለልጅ መስጠት በማር ጠቅሎ ነው ። ማሩ እየጣፈጠው ኮሶው እንዲያድነው ። ይኸን ስለ ማለት እኛም የታየንን ። በተረት፡በቡአልታ፡ ባውሬ እያስመሰልን ። በውሥጡ ቁም ነገር ይኸው ጻፍንላችሁ ። ያገራችን ልጆች በረከት እንካችሁ።በርቱና ተማሩ በቃላችሁ አጥኑ ። እየተማራችሁ ልባችሁን አቅኑ ።

ፌንጣና ጕንዳን ።

እመቲቱ ፌንጣ በበጋ ስትዘፍን ። እንክዬ ጕንዳኒት አንድ ቀን ሳትበዝን።ቤቷዋን ስታደራጅ ቀርሱዋን ስታከማች፡ ለትዳር ስትቃትት ስትማስን ነበረች ። በጋም አለፈና ክረምትም ገባና ። እመቲቱ ፌንጣ ቆፈን ያዛትና ። እንኳን የምትለብሰው የምትጐርሰው አጣች። ኋላም ወደ ጕንዳን እንዲህ ስትል መጣች ። ክረምትና በጋ እንዴት ልዩ ናቸው ። ራብና ቆፈን አንድ ላይ ሆኑብኝ። ጠሜን ዕራቁቴን እንዴት ልቻላቸው። እንግዲህ ምን ይብጀኝ በምን ፈረደብኝ። እንክዬ ጕንዳኒት ከቤትሽ አግብተሽ ።የምድሩ አላፊ ነው የሰማዩን አይተሽ። ሌላው ቢቀር እንኳ ብታሞቂኝ ጥቂት ። አስጠቅምሽ ነበር በላይኛው መንግሥት ። አረገኝ እቴሆይ ይኸንን ደፈርዋል። ክረምት ሳይገባ ዝናብ ሳያከፋ ። የማንን ጕፈሬ ታበጥሪ ኖሮአል ። አንቺ ለምን በዘንሽ እኛ ስንለፋ ። የሙቀቱ ጊዜያት ስዘፍን አለፈ ። ክረምት ሳላስበው ድንገት ደረሰብኝ ። አበባው ቅጠሉ በቶሎ ረገፈ። አባክሽ ወዳጄ ወቀሳ አታርጊብኝ። እህ እንዲህ ነው ደግ ሞያ ሠርተሻል። ታዲያስ አሁን አንቺ ምንድን ያስፈራሻል፡ብርድና ራብ እንጂ ምን ይመጣብሻል። በጋውን ተዘፈንሽ አሁንም ጠንክሪ።ክረምቱንም ደግሞ ሒጂ እዚያው ጨፍሪ።

ዝንጀሮና መስተዋት ።

አንድ ቀን ዝንጀሮ እያመነታታች።ጌጥ አገዛ ብላ ከመደብር ገባች። ሰፋፊ መስታወት የጠራ የማረ።ከመደብሩ ውሥጥ ተሰቅሎ ነበረ።መለስ ቀለስ ብላ እቃ ስታማርጥ።መልኳን አገኘችው ከመስታዋቱ ውሥጥ።ኋላም በመደነቅ እንዲህ ተናገረች ። ወደ መስታዋቱ ትኩር ብላ እያየች። እረገኝ ይህቺ ምንድን ነች እንዲህ ያለች ፍጥረት።አጉል የተሠራች ሰው አይሉዋት አውሬ።ላስተያየቱዋ እንኳ ጥቂት የለው እፍረት ። አይቻትም አላውቅ እኔስ ያለ ዛሬ።እንዴት ያስቀይማል የደረቱዋ ቅላት።ተገርራቱዋስ በቃች ደግሞ ምን ጠበሳት። ምነው በቀረችው ጥንቱን ሳትፈጠር።እኔስ እሱዋን ብሆን ታንቄ እሞት ነበር። (አሁን በዝንጀሮ ምን ያስተርተኛል መልኩን የሚያራክስ ምን ፍጡር ይገኛል)

ሉልና አውራ ዶሮ ።

አንድ ሉል ከዘውድ ውሥጥ ጠብ ብሎ ኑሮ።አውራ ዶሮ አገኘው ሲጫጭር ከንሮ። የሚበላ መስሎት ለቀም አደረገው።

ኋላ ግን እየና ታፉ አውጥቶ ጣለው ። ይኸን ገንዘብ ብዬ ደርሶ ሳልቸገር ። ያተር ፍሬ መስሎኝ ቋምጬለት ነበር ። እሱስ ከንቱ ኑሮአል ጥቅም የሌለበት ። መልኩን አሳምሮ እኔን ሊያሞኝበት ። እንደዚህ እያለ ጌታው አቶ ዶሮ ። ሉሉን ጥሎ ሔደ ኩኩሪኩ ብሎ ። ስለዚህ ይመኙዋል አስቀድሞ እውቀትን ። እውቀት ቃለ ወዲያ በኋላ ማግኘትን ።

ወርቅና ሰንበሌጥ ።

ወርቅ ሰንበሌጥን መቅጠኑዋን እየና ። እንዲህ ተናገራት እጅግ ናቃትና ። አሁን ለምን አንቺን እግዚአብሔር ፈጠረሽ። ተቁመት አላደግሽ ተጐን ስፋት የለሽ ። የነፋስ ሽውታ ያሽ ቈጠቍጥሻል። ጤዛ እንኳ ሲያርፍብሽ ያስጐነብስሻል ። እዩው ቀና ብለሽ የኔን አፈጣጠር ። የቁመቴን መርዘም የግንዴን መወፈር ። የጥላዩን ስፋት የሥሬን መጠንከር ። ሰማይ ቢሰበር ምድር ቢሰነጠቅ ። ያፈቀደው ቢሆን እኔ አልንቃነቅ ። እኔን ተጠግተሽ ብትበቅሊ ተጥንቱ ። ዘወትር በነፋስ ተመንገላታቱ ። አይሻልም ኑሮአል ብሆንልሽ ተገን ። ታሳዝኚኛለሽ እጅግ ያለ መጠን ። ለኔ ተማዘኑ ጌታው አቶ ወርቅ ። ይልቅስ በኃይልህ እጅግ አትመካ። እግዚሐር ባይሰጠኝ እንዳንተ ውፍሬ ። እኔ መች ጠላሁት የሰጠኝን ባሕሬ ። በዚሁ ደስ ብሎኝ እንዳቅሚ ታደርሁኝ። መቅጠንና ማጠር ነውርም አይሆንብኝ ይኸንን ሰንበሌጥ ገና ተማለቱዋ ። ተቀኝም ተግራም እንደዚ ነፈስ ። ማዕበል ተነሣ ጨለመች መሬቱዋ ። ሰማዩም ጠቈረ ጥቀርሻ ለበሰ።በምድር ያለ ፍጡር እጅጓ ተጨነቀ። በየጐሬው ገብቶ ሁሉም ተደበቀ ። እንደ ነፋሱ ኃይል እንዳጨላለሙ ። እኛስ መስሎን ነበር አልፈት የደረሰች ። ሰንበሌጥም ተኛች ገና ተቀድሞ ። ተምድር ልክክ አለች ቀጠሉዋን ለበሰች ። ወርቅ ግን ሲመካ እንዲያ በጕልበቱ ። ነፋስ ነቅሎ ጣለው ተነመሠረቱ ። (ይህ ያሁኑ ተረት ምሳሌም አያሻ ። ሰዎች አትመኩ በጕልበት በጋሻ ።)

ከዚህ የቀረው በሚከተለው ይታተማል።

የጥያቄ መልስ ።

ብርሃንና ሰላም ፮ኛ ዓመት ቍጥር ፵፫ ወንድማችን ልጅ ማህሉ ጽጌ የማያውቁትን ነገር ከሚያውቅ ለመጠየቅ በማፈር ብዙ ነገር ይጐድላል ብለው በጻፉት አርእስት ሐሳባቸውን በጥያቄ ስለ አቀረቡልን እኔም ሐሳቤን በማፈር ብተወው የማይገባ ስለሆነ ወደፊት የብርሃንና ሰላም ሊቃውንት አምልታችሁ አስፍታችሁ በምር እስክታስረዱን ድረስ አሁን ለጊዜው የተቻለኝን ያህል ምላሽ ለመጻፍ በድንቍርናዬ እሞክራለሁ።

፩ኛ ፤ ሰነፍ ገበሬ በትጉህ በሬ ፤ ትጉህ ገበሬ በሰነፍ (በአባያ) በሬ ከሚያርሱት ለማናቸው ፈር ይወድቅለታል ለተባለው ጥያቄ ፤ መቸም የአዛዥና የታዛዥ ፤ የአድራጊና የተደራጊ፥ የሠሪና የተሠሪ ረድፋቸው ለየቅሉ ነው ። እንዴት ብለን ብንመረምር በምሳሌ ልንረዳ እንችላለን ፤ አሁን በአንድ አገር ጦርነት ቢነሣ የጦር አበጋዙም ሰነፍ ወይም ፈሪ ቢሆን ሕዝቡን ፈርቶ ያስፈራቸዋልና በድንጋጤ ድል ይሆናሉ ። ሁለተኛ ምሳሌ፥ አንድ ተረት አለ በገዛ አረሟ እባብ ይዛ አስፈራራች እያሉ ሽማግሎች ሲተርቱ እንሰማለን ። እንግዲህ አድራጊዎችና አስደራጊዎች ትጉሃን ሊሆኑ ይገባል ። ግን አድራጊዎች በስንፍና ገመድ ተይዘው ቸል ካሉ ተደራጊዎች ምንም ሊሆኑ እንደ ማይችሉ የታወቀ ነው ።እነሆ መርከብ፥ባቡር፥አውቶሞቢል፥አውሮፕላን፥እነዚህን የመሰሉ ሁሉ መጓጓዣዎች ሞተር (መዘውር) ካላንቀሳቀሳቸው ምንም ሊሠሩ አይችሉም እንደዚህም ሁሉ ለማናቸውም ሥራ አድራጊዎቹ ካልተጉበት ተደራጊዎቹ በገዛ ራሳቸው ሊዘጋጁ አይችሉም። ግን ሰነፍ(አባያ)በሬ በትጉህ ገበሬ እጅ ከሆነ ዘንድ ምንም እንደሌሎቹ ጥማዶች ደስ ባያሰኝ በትጉሁ ገበሬ ጥረትና ትጋት ቀስ ቀስ እያለ እያደር ሥራ መልመዱ አይቀርም ፤ የኋላ ኋላም ገበሬው ትጉህ ነውና በገመድ ስቦ ቀምበር አሸክሞ አበያ ቢቀና ቤት ያቀና እንደሚባለው ተረት እንዲሠለጥንና እንዲያርስ ያደርገዋል ።

፪ኛ ፤ ጥሩውን ዕቃ በአሸሸጡ ኰርቶ በርካሽ ከሚሸጥ ነጋዴ መናኛውን ዕቃ በትሕትና ውድ አድርጎ ከሚሸጥ ነጋዴ ለማንኛው ወረት ይገባለታል ለተባለው ጥያቄ ፤ ነጋዴ ንግድ ማቆሙ ትርፍ ሊያገኝበት ነው እንጂ እንዲከስርና ጕድለት እንዲያገኘው አይደለም ። እንግዲህ ኰርቶ ጥሩ ጥሩውን ዕቃ ያለ ዋጋው በርካሽ ከሸጠው ወረት (ጥቅም) አገኘ ለማለት እንዴት እንችላለን ። ይሁንና ኩሩ ነጋዴ ጥቅም ያገኛል ለማለት ፈጽሞ አይቻልም ። ስለምን ቢባል በተጓዳጅነቱ ገበያተኛ ይጠላዋልና እየራቀው ይሔዳል ። ገበያተኛም ከራቀው ዘንድ ገቢው እያነሰ ሀብቱ እየተቀነሰ ጕድለት ያገኘዋልና ወደ ችግር ይወድቃል ። ትሑት ነጋዴ የሆነ እንደሆነ ዝናው ከሀገር ወደ ሀገር በደግነትና በትሑትነት እየተነገረለት ከፍትፍቱ ፊቱ እንዲሉ ገበያተኛ ይገባለታል ንግዱ ይነግለታል ። ከዚህም የተነሣ ቱጃር (ሀብታም) እስከ መሆን ይደርሳል ። እንግዲህ መናኛውን ዕቃ በውድ የሚሸጥ ትሑት ነጋዴ ይበልጣል ለማለት እንደፍራለን ።

፫ኛ፤ ብዙ ትምርት ተምሮ በተማረው እውቀቱ ከማይሠራ፥ ሳይማር በመቅረቱ ከሚፀፀት ማናቸው ብልጫ አላቸው ለተባለው ጥያቄ ፤ ይህ ሁለት ዓይነት ነገር አለበትና ለትርጓሜ ያስቸግራል ፤ ቢያስቸግርም ጀምረነዋልና በተቻለን ረገድ እንፈጽመዋለን ። አንደኛው ተምሮ ስለ በተማረው እውቀቱ የማይሠራው በአርግጥ በልግምና በምን አለብኝ እንደሆነ ፤ ስለ ድንቍርናው እየተፀፀተ የተቻለውን ያህል ያለ ልግም የሚሠራ ያልተማረው ይበልጣል ። ግን በላይኛው መስመር ሁለት ዓይነት ነገር አለ ብለን ነበርና ሁለተኛው ይህ ነው ፤ ምናልባት የተማረው ሰውዬ ለሀገሩና ለመንግሥቱ ጥቅም በትክክል ለመሥራት ሲፈቅድ የበላዮች ሥልጣን እያሰናከለው ሥራውን ባያስኬድ የመብት ኃይል ባለማግኘት ነውና ልንወቅሰው አይገባንም ። ማለት በዓለም ላይ በእንደዚህ ያለ ኑሮ እየተበሳጩ ሕይወታቸውን ያሳለፉ አይታጡም ።

፬ኛ ፤ እውቀት አድኃ ቤት አለማወቅ አሀብታም ቤት ሁኖ ፤ ሀብታም ይህ ሁሉ ገንዘቤ ቀርቶብኝ ምነው እውቀት ባገኘሁ ብሎ ቢመኝ ፤ አዋቂው ድኃ ይህ የተማርኩት እውቀቴ ቀርቶብኝ ምነው ሀብት ባገኘሁ ብሎ ቢመኝ የማናቸው ምኞት ይሻላል ለተባለው ጥያቄ ። እነዚህ ምኞቶች በጥልቅ

ሕሊና ላልመረመረ ግልጾች አይሆኑም ፥ ማለት የዚህ ዓለም ድካምና ጥረት ፍጻሜው ዕዱኛን ለመሻት ነው ማናቸውም የእውቀት ሥራ ቢበዛም ቢያንስም ዋጋ የሚያስገኝ ስለሆነ የሁለቱም ምኞት ወደ ማግኘት ያዘነበለ ይመስላል ። የሆነ ሁኖ የእውቀት ሥልጣኔ በገባበት አገር የሆነ እንደሆነ አዋቂ ሰው ተወዳጅ ነውና ምንም በእውቀቱ ራሱ እንኳ ለጊዜው ባይ ጠቀም ሕዝቦቹ (ወገኖቹ) ብልሆች ስለሆኑ የእውቀቱን ፋራ እየተከታተሉ ይሔዳሉና ። የትምርቱ ፍሬ አገርን የሚጠቅም መንግሥትን የሚረዳ ከሆነ ዘንድ ገንዘብን ለማግኘት ምኞት ከማድረግ ጥበብን ለማግኘት መጣጣር ይሻላል ። ግን የእውቀት ሥልጣኔ ባልገባበት አገር የሚበዙቱ አላዋቂዎች ስለሆኑ ብልህንና አዋቂን እንደ ባላጋራ ያዩታልና ፥ ብልሆም ሥራ ለማስኬድና በሥራው ድካም ዋጋ ለማግኘት ጭንቅ ስለሚሆንበት ፥ በዚያ አገር ገንዘቡን በከንቱ ያደለበ አላዋቂ ሀብታም ይሻላል ።

፫ኛ ፥ ሀብታም ሁኖ በገንዘቡ ቀዋሚ ነገር ከማይሠራ የሰለት ምግብና ልብስ ከላጣ ድኃ ጋራ ምንድነው ልዩነታቸው ለተባለው ጥያቄ ። ይህ ቃል እርግጥ ነው በእግዚአብሔር ጸጋ የተገኘ ገንዘብን ለአዝማሪ፥ለዘዋሪ፥ ለዳንዴ፥ለወምበዴ፥ቢሰጡት (ቢዘሩት) አያስመሰግንም ፥ በውሥጡም የሀገር ጥቅም የለበትም ። ግን ገንዘብን ለቀዋሚ ነገር ቢያደርጉትና አብያተ ክርስቲያናት ቢታነፁበት፥የድኆች ልጆች ቢያድጉበት፥ ተማሪ ቤት ቢቆምበት፥ ሆስፒታል ቢከፈትበት መንገድና ድልድይ ቢሠራበት ስም ያስጠራል አገርን ያስከብራል ።

ሁለተኛም የጦር መሣሪያ ቢያደረጁበት ለጀግና ቢያበሉት ቢያጠጡት፤አገራችሁን ልቀቁ፥ሃይማኖታችሁን ከዱ የሚል ጠላት በተነሣ ጊዜ የጀግኖች አሳዳሪ እነ እገሌ በፊት፥ እነ እገሌ በኋላ፥ እነ እገሌ በቀኝ እነ እጌሌ በግራ ሁናችሁ ጠላታችንን እንግጠመው በተባለበት ቀን እነዚያ የበሉ የጠጡ አርበኞች አብሮ የበላ አብሮ ይሞታል ከጌታችን ፊት እንሞታለን እያሉ እሳት ለብሰው እሳት ጐርሰው ዘገር ነቀው ብቅ ባሉ ጊዜ ጌታቸውን አስከብረው ጠላታቸውን አሳፍረው አገራቸውን ጠብቀው ይኖራሉ ።እንደዚሁ ሁሉ ግብር ከሚያበሉና ከሚያጠጡ መኳንንቶች እነ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስን ፥እነ ራስ አባተን፥ እነ ራስ ደምስን ፥ የገንዘብ ፍቅር ስለ ሌለባቸው በማብላታቸውና በማጠጣታቸው የጀግኖችንም መሣሪያ እያደራጁ በመስጠታቸው፤ ከሞቱ በኋላ እስከሁን ድረስ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዝናቸውን ሲናገር እንሰማለን ። ገንዘብና ጌትነት እንደዚህ ለቀዋሚ ነገር ሲሆን ደስ ያሰኛል ።ግን ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ሳይሆን ወይም ለጀግና ምግብ ወይም ለቀዋሚ ሥራ ሳይሆን በየከበርቴዎቹ እጅ እየተሰበሰበ ሥራ ፈትቶ የተቀመጠው በጣም ያሳዝናል። ገንዝብ ኃላፊ ጠፊ ነው ደጋግ ነገር ካልሠሩበት ረብ የለውም በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ክቡር ራስ ወሌ በአዲስ አበባ ቤት አልሠሩም ነበርና እኅታቸው እቴጌ ፀሐይቱ ይኸነን ሰምተው ዓሥር ሺ ብር ለቤት መሥሪያ ቢሰጡዋቸው አርበኞቻቸውን ጠርተው ዕለቱን አከፋፈሏቸው ይባላል ። እቴጌ ፀሐይቱም ቤት እንዳልተሠራበት ወሬ ሰሙና ራስ ወሌን አስጠርተው፣ ቤት እንድትሠራ ዓሥር ሺ ብር ሰጥቼህ ነበር አሁን ብጠይቅ ጎጆ እንኳን አላቆምህም አሉ ብለው ቢጠይቋቸው ክቡር ራስ ወሌ ሲመልሱ እቴጌ ሆይ የሰው ነገር አይስሙ ሠርቼበታለሁ የሠራሁትንም ቤት ነገ አሳይዎታለሁ ብለው ወደ ሰፈር ሔደው ከደሩ በኋላ ፥ በማግሥቱ እቴጌ ወደ እንጦጦ ማርያም ሲወጡ ራስ ወሌ ሠራዊታቸውን ግራና ቀኝ አሰልፈው አርበኞቻቸውን በፈረስ በፈረስ ላይ እንደሆኑ አስከትለው፤ይኸውና ያነን የሰጡኝን ገንዘብ እንደዚህ ያለ ቤት ሠርቼበታለሁ ብለው አርበኞቻቸውን ቢያሳዩዋቸ እቴጌ ፀሐይቱ እውነትም ላንድ ቀን እንግዳ ማስተናገጃ የሚሆን ቤት ሠርተሀልናል አሏቸው ይባላል አሁን ይህን መታሰቢያ አድርጌ መጻፌ ቤት መሥራት ከስንፍና ይቈጠራል ለማለት አይደለም ። ብሎም ገንዘብ ላለው ከድንጋይ ቤት የሰው ቤት መብለጡን ለማሳሰብ ነው ። ዘበ እዝነ ሰሚዐ ለይስማዕ (ጆሮ ያለው ይስማ) ልጅ ማህሌ ጽጌ በጥያቄያቸው አሳሰበውን ስለጻፍሁ ስሕተት ቢገኝበት ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እለምናችኋለሁ ።

በቀለ አበዬ

ስለ ውል መቀበል ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና የጃፓን ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ሂሮሂቶ በሁለቱ የንጉሠ ነገሥት መንግሥቶች መካከል ያለው ወዳጅነት እንዲፀናና በሁለቱም አገሮች መካከል ያለው የንግድ ሥራ እንዲሰፋ ለማድረግ አስበው የንግድና የወዳጅነት ውል ለመዋዋል ቍርጥ ስላደረጉ ባንድ ወገን ዛሬ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት ያን ጊዜ ግን ዋና ዲሬክተር የነበሩት ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ በሁለተኛውም ወገን የጃፓን ንጉሠ ነገሥት ልዩ መላክተኛ ክቡር ኢዛቡሮ ዮሺዳ ሆነው በኅዳር ፲ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ላይ የተፈራረሙትን ውል ግርማዊ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ግርማዊ የጃፓን ንጉሠ ነገሥት ሂሮሂቶ ወደው ስለተቀበሉትና ስለፈረሙበት እንደውሉ ቃል በፓሪስ ሌጋሲዮን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት ክቡር በጅሮንድ ዘለቀና ፓሪስ ያሉት የጃፓን ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ክቡር ናጋኦካ በነሐሴ ፳ ቀን ፲፱፻፳፬ ዓ ም (በፈረንጅ ቍጥር ነሐሴ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፪) ፓሪስ ላይ ተቀባብለዋል። ሁለቱም የንጉሠ ነገሥት መንግሥቶች የተዋዋሉት የንግድና የወዳጅነት ውል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው።

መጀመሪ፥ ከፍ ያሉት ተዋዋዮች መንግሥቶች አንደኛው በአንደኛው አገር የዲፕሎማቲክ እንደራሴ ለማስቀመጥ ይችላሉ ።

ሁለተኛ፥ የሁለቱ ከፍ ያሉት ተዋዋዮች መንግሥት ዜጎችና የንግድ ዕቃ አንዱ ወደ አንዱ ሲመላለስና ሲገባ ለዜጎቻቸውም አትዋኑዋር ቢሆን ለንግድም ለቀረጥም ቢሆን ከዚህ ቀድሞ ለሌላ መንግሥት ዜጎችና የንግድ ዕቃ አብልጦ እንደተፈቀደው ወደፊትም እንደሚፈቀደው በሁለቱም ወገን ሳያበላልጡ በትክክል ያኖሯቸዋል ።

ምስተኛ፤ይህን ውል እንደተቻለ መጠን በቶሎ አደላድለው ይቀበሉታል። አደላድለው የሚቀበሉበትንም ወረቀት ፓሪስ ላይ ይቀባበላሉ ። አደላድለውም የተቀበሉትን ወረቀት ከተቀባበሉበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ወር በኋላ ውሉ ለአምስት ዓመት የፀና ይሆናል ። ይህ ውል ፀንቶ የሚቈይበት አምስቱ ዓመት ሊፈጸም ዓሥራ ሁለት ወር ሲቀረው ከሁለቱ መንግሥቶች አንደኛው ውሉ ይፍረስ ብሎ ለአንደኛው መንግሥት በጽሕፈት ያላስታወቀው እንደሆነ፥ ይህ ውል እንደገና አንድ ዓመት ድረስ ይረጋል ። ከዚያም በኋላ አንደኛው መንግሥት ለሁለተኛው መንግሥት ይፍረስ ብሎ ያስታወቀው እንደሆነ፥ ይፍረስ ብሎ ካስታወቀበት ቀን ጀምሮ አንድ ዓመት ድረስ እንደፀና ይቈያል ። ይህንንም ውል የሁለቱ መንግሥታት እንደራሴዎች ፈርመው አትመውበታል ። ይህ ውል በአዲስ አበባ ከተማ በኢትዮጵያ ቁጥር በኅዳር ፭ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም በጃፓን ቁጥር በሾዋ አምስተኛ ዓመት በዓሥራ አንደኛው ወር በዓሥራ አምስተኛው ቀን ከሁለት ላይ ተጽፏል ።

ፊርማ ።

ብላቴን ጌታ ኅሩይ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ዋና ዲሬክተር ።

ኢዛቡሮ ዮሺዳ ልዩ
አምባሳደር።

Sa Majesté l'Empereur d'Ethiopie
Haïle Sellassié Ier
et
Sa Majesté l'Empereur du Japon
Hirohito

Animés du désir de resserer les relations amicales existant entre Leurs Etats et de développer Leurs rapports commerciaux avaient décidé à l'an de Grâce 1923 (calendrier éthiopien) de conclure un Traité d'Amitié et de Commerce et avaient nommé à cet effet pour Leurs Plénipontentiaires, savoir :

Sa Majesté l'Empereur d'Ethiopie

Son Excellence le Blaten-Guéta Herouy Welde Sellassié Ministre des Affaires Etrangères, alors Directeur Général.

Sa Majesté l'Empereur du Japon

Son Excellence Monsieur Isaburo Yoshida, Ambassadeur Extraordinaire et Plénipotentiaire.

Ce Traité ayant été approuvé et ratifié par Sa Majesté l'Empereur Haïle Sellassié d'une part et par l'Empereur du Japon Sa Majesté Hirohito d'autre part, le 20 Nehassié de l'an de Grâce 1924 (26 Août 1932) se sont réunis à Paris et ont opéré à déchange des ratifications, Son Excellence le Bedjirond Zelleke, Envoyé Extraordinaire et Ministre Plénipotentiaire à Paris de Sa Majesté l'Empereur d'Ethiopie, et Son Excellence Monsieur Nagaoka, Envoyé Extraordinaire et Ministre Plénipotentiaire du Gouvernement Impérial du Japon à Paris.

Le Traité d'Amité et de Commerce conclu entre les deux Gouvernements est le suivant.

Article I. — Chacune des Hautes Parties Contractantes pourra envoyer des représentants diplomatiques accrédités auprès de l'Autre.

Article II. — Les ressortissants et les produits de Chacune des Hautes Parties Contractantes continueront à jouir réciproquement dans l'Autre du même régime et des mêmes avontages, en matière d'établissement, de commerce et de douane, que ceux qui sont actuellement accordés ou qui seraient accordés dans l'avenir aux ressortissants et aux produits de la nation la plus favorisée.

Article III. — Le présent Traité sera ratifié aussitôt que faire se pourra et l'échange des ratifications aura lieu à Paris. Il entrera en vigueur un mois après l'échange des instruments de ratification et restera exécutoire pendant 5 ans.

Dans le cas où aucune des Hautes Parties Contractantes n'aurait notifié, un an avant la fin de la dite période de cinq années, Son intention d'en faire cesser les effets, le présent Traité demeurera obligatoire jusqu'à l'expiration d'une année à partir du jour où l'Une ou l'Autre des Hautes Parties Contractantes l'aura dénoncé.

En foi de quoi les Plénipotentiaires respectifs ont signé le présent Traité et y ont apposé Leurs sceaux.

Fait en double exemplaire à Addis-Abeba le 5 Hedar de l'an 1923 d'après le calendrier éthiopien, correspondant au quinzième jour du onzième mois de la cinquième année de Showa.

Signé :

Bellaten-Guéta HEROUY
Directeur Général du
Ministère des Affaires
Etrangères

ISABURO YOSHIDA
Ambassadeur Extraordinaire

ስለሙሴ ያዕቆብ ባግዳሳርያን ሞት

ሙሴ ያዕቆብ ባግዳሳርያን ለኢትዮጵያ መንግሥት የታመኑ አገልጋይ ዋና የክብር ዘውድ የሚሠሩ ነበሩ። ይልቁንም ደግሞ በሃገር ጥቅም ለሥልጣኔ እርምጃ መጀመሻ የሚሆን በንጉሠ ነገሥታችን መልክ የብር ማተሚያ ቤት መሥርተው ለዚሁ ቤት ዋና ዲሬክተር ነበሩ።በሃገራችንም ከተመሠረተው የሥራ ቤት ሁሉ የብር መኪና ቤት ሥራውን እያከናወ ይሠራል ።

ወደ ኢትዮጵያ የመምጣታቸው ታሪክ እንዲህ ነው።አስቀድመው አጼ ምኒልክ አስፈልገው በልዑል ራስ መኰንን በኩል ከሃገራቸው አስመጧቸው ሙሴ ያዕቆብም ልዑል ራስ መኰንንን ይወዱ ነበርና ምንም በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ቢመጡም ለጊዜው በሐረር ተቀማጭ ሆኑ ወዲያው የወርቅ ብርጭቆ ሠርተው ለልዑል ራስ መኰንን ሰጡ ልዑል ራስ መኰንንም ይህ ለጃንሆይ የሚገባ ነው ብለው አምጥተው ለጃንሆይ በሰጡ

ጊዜ ጃንሆይ ሥራውን አይተው በጣም ተደነቁ ይላሉ። ወዲያው ይህነን የሠራ ሰው ወዴት ይገኛል ብለው ልዑል ራስ መኰንንን ቢጠይቋቸው በጃንሆይ ፈቃድ መጥቶ እኔ ዘንድ ተቀምጧል አሏቸውና ወደኔ ይምጣልኝ ብለው ከሐረር አስመጧቸው። ሙሴ ያዕቆብም ከሐረር መጥተው አዲስ አበባ ሲገቡ ለጊዜው ጃንሆይ አፄ ምኒልክ ወደ አዲስ ዓለም ከተማቸው ሔደው ነበርና መምጣታቸውን በሰሙ ጊዜ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የክብር ሰላምታ ላኩላቸው ።

ሙሴ ያዕቆብ ባግዳሳርያን ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ምኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ይድረስ ከያዕቆብ እንዴት ሰንብተሃል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ሠርተህ የሰደድህልኝም መለኪያ ደረሰልኝ እጅግ ማለፊያ ነው። ደግሞ እዚያ ስመጣ ልኩን አሳይህና ማለፊያ ኩባያ ትሠራልኛለህ። ታኅሣሥ ፫ ቀን ፲፰፻፺፫ ዓመተ ምሕረት አዲስ ዓለም ሰፈር ተጻፈ።ከዚህ በኋላ ጃንሆይም በክብር ተቀብለው በከፍተኛ ማዕርግ አስቀመጧቸው በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ንጉሠ ነገሥቱን ደስ አሰኝተው ሳለ ሙሴ ያዕቆብ ፈጽመው ለኢትዮጵያ ሐሳቢ ስለሆኑ በንጉሠ ነገሥቱ መልክ ገንዘብ ቢሠራ ለኢትዮጵያ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ለጃንሆይም ለዘላለም መታሰቢያም ይሆናል ብለው ለንጉሠ ነገሥቱ ቢያማክሯቸው ጃንሆይም አጥብቆ ደስ አላቸውና ወዲያው መኪናውን እንዲያመጡ የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ሰጥተው ወደአውሮጳ ልከዋቸው ሔደው መኪናውን ይዘው መጥተው ይኸውና እንደምናዬው ለመንግሥታችን ጥቅም የሚሆን መሠረት ያለው ሥራ ሠርተዋል በሥራቸውም ደስ ስላሰኙ አፄ ምኒልክ በኢትዮጵያ ያልኰልን ሞኖፖል ሰጥተዋቸው ነበር በዚያውም ሥራቸውን በትክክል መሥራታቸው የሐረርና ያውራጃውን መዓድን ሥራ ተቀብለው ነበር። ከንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ደጋግመው ኒሻን እየተሸለሙ በየጊዜው ማዕርግ ተቀብለዋል አሁንም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የሙሴ ያዕቆብ ባግዳሳርያን መታመንና አገልግሎታቸው ስለታወቀላቸው የዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ተቀብለው ወደአውሮጳ ተልከው የተላኩበትን የመንግሥት ጉዳይ በትክክል ፈጽመው ስለተመለሱ ተመስግነው የክብር ኒሻን ደጋግመው ተሸልመዋል ሙሴ ያዕቆብ ባግዳሳርያን ዋናው መታሰቢያቸው ያገልግሎታቸው ታሪክ እስከ ፫፻የሚሆኑ የኢትዮጵያን ልጆች የሥልጣኔ ሥራ የጅ ጥበብ አስተምረው ቤተ መንግሥትን የሚያገለግሉ ሁነዋል።ሙሴ ያዕቆብ በመንግሥት ፈቃድ ወደአውሮጳ በሚላኩበት ጊዜ ሁሉ ደስ አሰኝተው ያገለግሉ ነበር ስለምግባራቸውም መልካምነት ከኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት ከሕዝቡም ሁሉ ፍቅረኛና ፈቃድ ፈጻሚ በማናቸውም ነገር የተስማሙ ነበሩ። ኢትዮጵያንም እንደተወለዱባት አገር አድርገው ማፍቀራቸውን እንኳን መንግሥትና የከተማው ሕዝብ ሁሉ ይመሰክርላቸዋል ለኢትዮጵያ መንግሥት በመታመን ፴፪ዓመት ያገለገሉ መሆናቸውን ይኸውና የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ማኅተም መሰከረላቸው።ንባቡ የሚበዛ ቢሆን ባጭሩ ተውሁት እንጂ ሙሴ ያዕቆብ ለመንግሥታችን ያገልግሎታቸው ታሪክ ብዙ ነበር ። ሙሴ ያዕቆብ ባግዳሳርያን ፈጽመው ከኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ የተባበሩ መሆናቸውን የሚያስረዳን ከወገናችን ከኢትዮጵያዊት ሴት የወለዷቸው ልጆቻቸው ወንድሞቻችን ለመንግሥት የታመኑ አገልጋዮች ጉልማሶች አድርሰው የታመነ ሥራቸውን ለመንግሥት ትተው ወደዘላለም ቤታቸው ሔዱ። ዕድሜያቸውም ፷ ዓመት ነው። ኅዳር ፲፫ ቀን ዐርፈው በኅዳር ፲፬ቀን የኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት የውጭአገርም ብዙ ታላላቅ ሰዎች ተሰብስበው በክብር ተቀበሩ።

ባለቤታቸውንና ልጆቻቸውን ዘመዶቻቸውንም ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ እላለሁ። መክብብ ደስታ ።

ስለሙሴ ማዩ አዲስ አበባ መግባት ።

ሙሴ ማዩ የመጀመሪያው አይሮፕላን ነጂ በኢትዮጵያ የነበሩት አገልግሎታቸውን ጨርሰው ተሰናብተው ወደ አገራቸው ከሔዱ ብዙ ጊዜ ቈይተዋል ነገር ግን አገራችንን ስለወደዱ ወደኢትዮጵያ ለመግባትና ወዳጆቻቸውንና የባለቤታቸውን ወዳጆች ለማየት ከመንግሥት አስፈቅደው ኮደር በሚባለው አይሮፕላን ከአገራቸው ከፓሪ ተነሥተው ከባለቤታቸው ከመዳም ማዩ ጋራ በኅዳር ፳፫ ቀን አዲስ አበባ ገቡ። የአገራቸው ሰዎች ፈረንሳውያንም በታላቅ ደስታ ተቀበልዋቸው ።

የእንግዶች በአይሮፕላን መምጣት።

በኅዳር ፳፫ ቀን ዶክተር ፉስባንና ባለቤታቸው ማዳም ፉስባን ክሌም በሚባል በጀርመን አይሮፕላን ባል ከሚባለው ከሱዊስ ከተማ ተነሥተው በማርሰይ በኒያፕል በቱኒዝ በትሪፖሊ በቤጋዚ በሜርዛም አትሩ በካይሮ በአስዋን በባዲ ሐልፋን ባትባራ በባር ሱዳን በምጥዋ በጂቡቲ አድርገው አዲስ አበባ ገቡ። እኒህም ሰዎች ኤሮፕላን ነጂዎች አይደሉም በጀርመን አገር አቢዮ (ድእሶፖር) በትንሽ አኢሮፕላን ወደ እሩቅ አገር የደረሰ ሽልማት ያገኛል ተብሎ ማስታወቂያ ስለ ተደረገ ማዳም ፉስባን ከልጅነታቸው ጀምረው አይሮፕላን መንዳት ተምረው በሱዊስ አገር ከወንዶቹ ጋር ተቀዳድመው

በመቅደማቸው ሽልማት አግኝተዋል። በጀርመንም አገር እንዲሁ ሰባት ጊዜ ውርርድ እያደረጉ ሃብልሜቻቸውን ሽልማት ሰባት ጊዜ አግኝተዋል። አሁንም ዶክቶር ፋስባንየአገር ካርታ እየተመለከቱ ማዳም ፋስባን እየነዱ ወደ አዲስ አበባ የመጡበት ምክንያት ይህ ነው።ይልቁንም ባልንጀራቸው አብሮ አደጋቸው ማዳሟዜልትሩዲ ሸኔበሊ ከሱዊሶ አገር ወደኢትዮጵያ ሥዕል ለመሣል ስለመጡ እሳቸውን ለማየት ነው። እንግዲህም የሚሔዱበት አገር አልታወቀምና ሲነሡ እናስታውቃለን።

ማስታወቂያ።

በከተማ ውሥጥ በየመንገዱ ላይ በሽተኛ ውሻ ስለበዛ ማዘጋጃ ቤት ለማጥፋት አስቧልና ውሻ ያለው ሁሉ ውሻውን ከቤቱ እንዲያስር እናስታውቃለን። ነገር ግን ከ፲፱፻፳፫ ዓ ም ከኅዳር ፴ ቀን በኋላ ውሻውን ሳያስር ቀርቶ ውሻው አደጋ ቢያገኘው ባለቤቱ ለመጠየቅ አለመቻሉን አስቀድመን እናስጠነቅቃለን። ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም።

የአዲስ አበባ ከንቲባ።

አቦማልተን ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

አቦ ማልተን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው።አቦማልተን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል ኦቦማልተን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፤ ቤርን ናቸው።በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው ።

ኦቦማልተን አዲስ አበባባሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ሣጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

Japanise Dentist
ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቆሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

WHITE HORSE
WHISKY

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤክስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በከዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ ጊዜ እንዳስታወቀው የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ቆዶችን በታ ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ከጧቱ በ፬ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማከበር ያስታውቃል።

የፊታውራሪ በዳኔ አሻግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፱፻ና ፲ሺ፪፻፶፩ ሜትር ካሬ።

የባሻ ወልዴ ዮሐንስ አጥቢያው ማርያም ስፋቱ ፲፬ሺ ፪፻፷፬ ሜትር ካሬ ።

የወይዘሮ ዓመተ መንፈስ ቅዱስ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፬፻፸፪ ሜትር ካሬ።

የወይዘሮ ወለተየስ ሀብቱ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፩ሺ፫፻፳ ሜትር ካሬ።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ) አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሴጊያን ዘንድ ይገኛል ። ይህነኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተኩል ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

ማስታወቂያ።

ለኢትዮጵያ ሰው የሚሸጥ ርስት ።

የባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ሂሳብ አጣሪዎች በ፫ሺ፱፻፹፩ ቍጥር የተጻፈውን ርስት ስፋቱ ሺ፯፻፺፯ ሜትር ካሬ ፥ አጥቢያው ሥላሴ ከደጃዝማች ከበደ ጎንቦልና ከንቡረ እድ አድማሱ በታ ጉረቤት ጥንት የባለዕዳችን የዋኅ ሥዩም ግርማይ ርስት የነበረውን ለመሸጥ ስላሰበ ይኸንን ማስታወቂያ ለሕዝብ ይገልጻል ። ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ባንክን ለመጠየቅ ይችላሉ።

ስለ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ሂሳብ አጣሪ ፈርማ።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

በዚሁም ጊዜያት ጠቅላላውን የሴቶችና የወንዶችን ውበቶች በሚያስረዳበት ጊዜ ግን ውቢቱ እመቤቴ ቀልጣፋና አቋቋመ መልከም እንድትሆን ይኸውም እየራሙ ዘመናት ይፈቅዳል በሚያሳዝነው አቀማመጣቸው ብዙ ሰዎች በሽተኞች ናቸው ። ደግሞም በምግባቸው እኑዋ ኑዋር እንዲሁም በጨካኝነትና ችግረኛ መሆናቸው ለመዳንም አይችሉም ። ለነዚሁም ሰዎች ብዙ ጊዜ የተወደደና በእውነት የማይሳሳተውን መድኃኒት እንሰጣቸዋለን። ሊፖቶዴን የሚባለውን በጥቅልል ያለውን መድኃኒቴን በጣም ሲያስጨንቅዎትና ሲያምዎት ቢሞክሩት ሕመምዎን በማቅለሉ ብዙ ደስ ያሰኝዎታል በአዲስ አበባ ውሥጥ ግዙፎችንና ሰውነተ ቁጡ ለሆኑ ሰዎች አየሩ አለመስማማቱን ይልቁንም ከኔ የበለጠ ያውቁታል፡ይልቁንም ደግሞ ዋና ማስረጃ እንቅልፍ ለሌለውና ለሚባንን ሰው ነው ።

ለነዚሁም ሰዎች ፈጽሞ የሚከለክልላቸውን ዲአል ኮምፕሬሜ የሚባለውን መድኃኒታችንን በጣሙ የጠራውን ከምንሰጣቸው በተቀር ሌላ የማያስፈልግ መሆኑን እናስታውቃችኋለን ። ደግሞ ከዚህ በኋላ የሰውነት ሥራቸውን ተስማምተው ያለ ሐሳብ ሌሊቱን በደስታ ያልፉታል ስል ባለኝ እውቀቴ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አሳስባለሁ

ታዛዥዎ ኤም ማትሳኪስ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ናት።ከዚሁም እንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን እንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም እንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቊረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሎት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጐብኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክተር ሚካኤል ።

በሞንፐሊዬ ኡኒቨርሲቴ ።

ስለውሥጥና የሴት በሽታ ፣የቀዶስልና ፣የዓይን በሽታ የሴት አዋላጅነት ሕክምና የተመለከረላቸው ድሮ ራስ መኰንን ድልድይ ቤታቸውን ትተው ወደ ጉለሌ መንገድ ሙሴ ሙራዲያን ቤት አጠገብ ቤት መለወጣቸውን ለወዳጆቻቸው በማክበር ያስታውቃሉ ።

ሁሉ ቀን ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፮ሰዓት ደግሞ ከ፰ ሰዓት እስከ ፲፩ ሰዓት ይገኛሉ ።

ሐሙስ ዕለት በጧቱ በሽተኞች አለዋጋ ያክማሉ ።

የሚሲዮን መጽሐፍ መሸጫ ቤት ።

የሱዳን ኢንቴሪዎር ሚሲዮን ዶክቶር ለምቤ ዲሬክቶር ወደ ራስ መኰንን ድልድይ በሚወስደው መንገድ ማጀስቲክ ሆቴል የሚባለውን አለፍ ብሎ መሐመድ አሊ ኩባንያ አዲስ ሱቅ አሰራበት አገጠብ የመጽሐፍ መሸጫ ቤት መክፈቱን ያስታውቃል ።

ከዚያ በያይነቱ የጽሕፈት መሣሪያና በፈረንሣዊ በአማርኛም በእንግሊዝም በሌላም ቋንቋ የታተሙ መጽሐፍ ቅዱስና ደግሞም ማለፊያ ማለፊያ መጽሐፎች ይገኛሉ ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሉር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዘር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ-

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፶፩
8me ANNE. № 51

ሐሙስ ታኅሣሥ ፮ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 15 Decembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የአፄ ምኒልክ መታሰቢያ ።

አፄ ምኒልክ ዕድለ መልካም ስለሆኑ መታሰቢአቸው እስከ ዛሬ ደኖራል።ታላቂቱ ልጃቸው ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱም ታላቅ መታሰቢያ ቤት አሥርተው የእግዚአብሔር አብንና የበአታን ታቦት አግብተው ለቤተክርስቲያኑም አገልጋዮች ከሀናት ብዙ ርስት ተክለዋል። የቤተክርስቲያኑንም ማማር ብዙ መሐንድሶች ተደንቀውበታል ። በሞቱበት ቀንም በዓመት በዓመት በታኅሣሥ ፫ቀን በበአታ ምክንያት ታላቅ በዓል ተደርጎ የበአታ ታቦት ወጥታ ጃንሆይና መሳፍንቱ መኳንንቱ ተሰብስበው ውደት ይደረጋል ። ዘንድሮም በዚያው ልማድ ታላቅ በዓል ተደርጎ ነበር። በዚሁም በታኅሣሥ ፫ቀን ለከሀናቱ ታላቅ ግብር ተደርጎ ነበር። በማግሥቱም ለመሳፍንቱና ለመኳንንቱ ለሠራዊቱም ታላቅ ግብር ተደርጎ ዋለ ። አፄምኒልክ ከሞቱ ፲፱ነኛ ዓመት ነው ። የደግሰው መታሰቢያ ለዘለዓለም መኖሩን የዓለም ሰዎች ቢረዱት ከዛሬው ይልቅ የኋላውን እያሰቡ ተክሉ ሥራ ይመለሱ ነበር ። አሁን ይህን ያልንበት ምክንያት አፄ ምኒልክ ከሞቱ ፲፱ነኛ ዓመት ሲሆን እስከ ዛሬ ሕዝቡ አብረውት እንደአሉ ይቄጥሩትዋልና የደግሰው መታሰቢያ ለዘለዓለም ደኖራል ያልንበት ስለዚህ ነው። እንኳን የወንድማቸው ልጅ አፄ ኃይለ ሥላሴ ማንም ቢሆን የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ ሁሉ የአፄ ምኒልክን መታሰቢያ አይረሳም ።

የግርማዊ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
የቢሾፍቱን የእርሻ ሥራና ሆቴል መጐብኘት ።

ቢሾፍቱ ጣቢያ አጠገብ ያለው (የእርሻ መኪና) ፈርምና ሆቴል ከዚህ በፊት ተሰናድቶ የነበረው በመሀከሉ ሥራው እንደ መቆም ብሎ ነበረና ግርማዊ ጃንሆይ በ፲፱፻፳፬ ዓም በመጋቢት ወር ለንግድ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ለአቶ መኰንን ሀብተ ወልድ ሥራውን ስለሰጡአቸው አንድ ዓመት ሳይሞላ ሆቴሉና ሥራውታድሶ ለማየት እጅግ የሚያስገመጅ ልዩ ልዩ ሥራዎች አሠሩላቸው ።

ይህንንም ሥራ ለመጐብኘት ጃንሆይ ከግርማዊት እቴጌ መነን ጋራ ሁነው በኅዳር ፳፩ ቀን ማታ በባቡር ወርደው ነበረ። የተከተሉአቸውም ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን፣ ልዕልት ወለተ እስራኤል፣ ክቡር ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ፣ ልዕልት ዘነበ ወርቅ፣ ልዕልት ፀሐይ፣ ልዑል መኰንን ፤ ክቡር ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል፣ ክቡር ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ ናቸው ።

የሆቴሉም ስም ተለውጦ ሆቴል ዘማየ ባሕር (ሆቴል ዲላክ)ስለተባለ በጕልህ ፊደል ተጽፎ በበሩ ላይ ይታይ ነበረ። ሆቴሉም አለመጠን እጅግ አምሮና ተሰናድቶ ውጭውና ግቢው በኤሌክትሪክ መብራት አጊጦ ነበርና እጣቢያ እንደደረሱ በሩቅ ሲታይ የመብራቱ ማማር ደምቆ ለዓይን ደስያሰኝ ነበር ።ጃንሆይም ከጣቢያው ባውቶሞቢል ተጋብተው ከሆቴሉ ደጃፍ ሲደርሱ ማርሽ ተፈፈ ተመታ።ቀጥሎም ከስዊስ አገር ለዚሁ ለሆቴሉ ሥራ በተለየ ተመርጠው የመጡት የሆቴሉን ባለቤት ማዳም ሆሴንን አቶ መኰንን አቅርበው ከጃንሆይ አስተዋወቁ ። ከዚህም በኋላ መጀመሬ ሆቴሉን ቀጥሎ የመኝታ ቤቱንና የመታጠቢያ ቤቱን፣ የወጥቤቱንም ስፍራ ሁሉ እየዞሩ አዩ።

የዚህም ሆቴል ጥዳትና ማማር ልክ እንደመርከብ ሆቴል ነው።መኝታ ቤቱ ፥ መታጠቢያ ቤቱ ፥ ወጥቤቱም ፥ በረንዳው ሁሉ በጌጠኛ ሲሚንቶ ሸክላ ተነጥፎአል። ግርግዳውም በኢታርሬት ተመቷል።መታጠቢያ ቤቱም ለወንድና ለሴት የተለየ ሁኖ ሙቅና ቀዝቃዛ ወኃ አለበት ። ጃንሆይም ይህንን ሁሉ እየዞሩ ካዩ በኋላ አምሮ ወደ ተዘጋጀው ማረፊያ ቤት ገብተው ጥቂት እንደቄዩ ወደ ሆቴሉ ተመልሰው ራት ተጋበዙ።

በማግስቱም ግርማዊት እቴጌ መነን ባውቶሞቢል ሁነው ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል አጅበዋቸው የፈርሙን(የእርሻውን መኪና) ጤፍና በያይነቱ እህል የተዘራውን የቃሊቲን ሁዳድ ለማየት ሔደው ተመለሱ ። ጃንሆይም በባሕሩ ዳር ለዳር የተተከለውን ወይን ለማየት ሔዱ ። የዚህም የወይን አዝመራ አወጣጡ አለመጠን የሚያጓጓ ሁኑዋል። ጃንሆይም አዝመራውን አይተው ሲመለሱ በሆቴሉ ምሳ ተጋበዙ ። ፱ ሰዓትም ሲሆን ጃንሆይና እቴጌ ፈርሙን(የእርሻውን መኪና) ለማየት ሔዱ። የፈርሙም የየክፍሉ ሹማምቶች ዶክቶር አሴንት የእርሻ

ው መሐንዲስ ሙሴ ጳውሎስ፡ሙሴ ረዲፍ፥ ዶክቶር ባሬቶ የከብቶች ሐኪም ። ሚካኒሲያው ሙሴ ቶብቻይን በተራ እየቀረቡ የሚገባ ሰላምታ እያቀረቡ ከጃንሆይ ተዋወቁ ።

ወዲያውም በየክፍሉ እየዞሩ የቅቤውን መኪና የተሠራውን ቅቤ ልክ እንዳውሮፓ የተሠራውን አይብ በያይነቱ አሳዩአቸው ፡በፈርሙም ውሥጥ ብዙ ላሞችና ጥጆች አዩ ከነዚሁም የምታስደንቀውን አንዲትላም የዚያው አገር ተወላጅ ባንድ ቀን ሰባት ሊትሮ ወተት የምትታለበውን አሳዩአቸው ይህም የሆነው በመልካም ከመመገብና በጥንቃቄ ከመጠበቅ ነው።

ቀጥሎም እንቍላል የሚፈለፍለውን መኪና፡፲፻ እንቍላል እንደታቀፈ አዩ ። ይህም መኪና ባንድ ጊዜ ስድስትና ፯መቶ እንቍላል ይፈለፍላል። ወዲያውም በሆቴሉ አጠገብ ያለውን ትልቁን ባሕር ወኃ ለመሙላት የተቈፈረውን ክናል በውሥጡም ቱኔል(የሲሚንቶ በምባ)እየቀበሩ የተሠራውን አዩ። ይህም ወኃ የመጣበት ፬ኪሎ ሜትር ከሚሆን ርቀት ከወንዝ የበዩ አዘቅት ፯ና ስምንት ሜትር የሚሆን እየተቈፈረለት የመጣ ነው።ይህም ወኃ በጥቂቱ ተቀንሶ ወደሆቴሉ ሒዶ በመኪና ፎቅ እየወጣ ያገለግላል ። ቀጥሎም ዳርና ድምበሩ ላይን የማይደረሰውን በያይነቱ እኅል የተዘራውን ሁዳድ እየዞሩ ከዩ በኋላ ደስ ብሎአቸው ወደሆቴሉ ተመልሰው ሻምፓኝ ተጠጣ። በኋላም ጃንሆይ ለሹማምንቶች ባዩት ሁሉ ደስታቸውንና ወደፊትም የተጀመረውን ሥራ ሳያቋርጥ እንዲተጉበት ደስ የሚያሰኝ የሚያተጋ የምክር ቃል ተናግረው ከሆቴሉ ሲወጡ ማርሽ ተፈሪ ተመታና ተሰነባብተው ከተከተሉአቸው ጋራ በደኅና ተመልሰው አዲስ አበባ ከተማ ገቡ ።

ጃንሆይ እንደዚህ የሚያምረውን በትጋት የተሠራውን ሥራ መጐብኘታቸው ሥራው ወደፊት እንዲገፉ ኃይል ይሰጠዋል ። ትጉሁ ዲረክተርም ለሥራቸው ብርቱ ናቸውና ለሚመጣው ዓመት አዝመራውና አትክልቱም ሌላውም ሥራ ሁሉ በጣም እንዲለማ ያደርጉታል ማዳም ሆሴንም እውቀተኛ ሴት ስለሆኑ የሆቴሉን ሥራ ያሰፉታል ይባላልና ሆቴል ዘማየ ባሕር (ሆቴል ዲላክ) የተባለው መልካም ማረፊያና በውነት የደላታ ባሕር እንዲሆን እንመኛለን ። አሰፋ ደርቤ ።

የዘመድ መልእክት።

ይድረስ እተማሪ ቤት ካለህ ወንድሜ ልጅ ብርሃኑ እንደ ምን ሰንብተሃል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። መጀመሪያ ከዚህ ቀጥዬ እምጽፍልህን በዓይን ብቻ ሳይሆን በልብህም አንብበው። ይልቁንም አለመመልከት ማየት፥ አለ ማድመጥ መስማት፥ እንደማይጠቅም በጣም ልብ አድርግ። ለትምህርት ሒደህ የተቀመጥህበት አገር ከተወለድህበት አገር ምንም የራቀ ቢሆን ከዘመድ ተለየሁ ብለህ ሆድህ አይባባ አትዘን ። አዘመድ መካከል ተቀምጬ ትምህርት እማራለሁ ማለት እያማገጠ ጊዜ ይወስዳልና በቶሎ ትምህርት ያስጨርስ አይምሰልህ። ባለህበት ተማሪ ቤት ድኃ መስለህ ተማር እንጂ ጌታ መስሎ መማር አይመርህ ጌታ መስሎ ወይም ጌታ ሁኖ መማር ለወጣት ልጅ ተማሪ ገንዘብ ያባክናልና ስለዚህ በሰው አገር ተማሪ ቤት ጌታ መስሎ መታየት ነው እንጂ ድኃ መስሎ መታየት አያሳፍርህ። ይልቁንም ድኃ ማለት የአክልና የአመል ነው እንጂ የገንዘብ ድኅነት ብቻ ይጎዳ አይምሰልህ በእግዚአብሔር ታምነህ እሱን ተስፋ አድርገህ ትምህርትህን ብቻ አስብ በጥበብህና በእውቀትህ ደስ ይበልህ። በጥበብ ማደግ የሚፈልግ ብዙ ትዕግሥት ያሻዋል ። ከስንፍናና ከዐዘን ብትለይ በክፉ የሚወራውንም ወሬ ከመስማት ብትርቅ መልካም ለመሥራትና ለመትጋት የሚበቃና የሚመች ጊዜ ታገኛለህ። ይልቁንም አመለ መልካምና ተመስጋኝ ትሆን ዘንድ እመኝልሃለሁ። በተማሪ ቤትም ያለ ጡብ መኖርና በስተማሪዎችና በተማሪዎች መካከል ተመስግኖና የታመነ ሁኖ መገኘት ትንሽ ነገር አይምሰልህ። ይኸውም አመልህ አብሮህ ቢያድግ እስከ ጊዜ ሞትህ ደስ ብሎህ ለሰውም ደስ አሰኝተህ ትኖራለህ ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ሕፃንም በትምህርት ይፈተናል በእግዚአብሔር እንጂ ተስፋህን በሰው አታድርግ ምንም የተወደደና የሚጠቅም ቢሆን በተሰባሪና በሚሻች ሰው ላይ ታላቅ የተፈጸመ እምነት ማድረግ አይገባም። ከሰው ይልቅ በራስህ እውቀትና ሥራ ታመን እውቀት ካለህና ሥራ ከወደድህ የማንም ወዳጅ ትሆናለህ። በዚሁም ላይ ሰው መውደድን ጨምርበት ሥራ ሁሉ አለ ፍቅር አይፈጸምም በፍቅር የሚደረግ ሁሉ ምንም ትንሽ የተናቀ ቢሆን ሁሉም ፍሬ ያለው ይሆናል።ሥራ በእጅ እንጂ በቃል አይደረግምና ለሥራ የተገባ የሚመስል የመራቀቅን የሰዎችን አነጋገር ብትሰማ ሥራ መስሎህ አታድንቅ ቃሎች ቃል ከመሆን በቀር ቃሎች ምን ይሆናሉ?የተማረና ታላቅ ጥበበኛ መሆን ብትፈልግ የማታደርገውን አትናገር እንዳታገኘውና የማይገባህ እንደሆን ስታውቀው ይህን ለማየት ለምን በከንቱ ጊዜህን እያጠፋህ ትደክማለህ የሥጋ ፈቃድ ጠባዩዋ ሁል ጊዜ ወደ ምኞት ትስባለች ነገር ግን በምኞት ሕሊናን ከማዘርና ጊዜ ከማጥፋት በኋላ ከሕሊና ማበሳጨትና ልብ ከመበተን በቀር ምን ትርፍ ይገኝበታል? ብዙ ጊዜ ሰው የሚሻት አንዲትን ነገር ለማግኘት በብዙ ያስባል ። ነገር ግን ፈቃዶች ካንዱ ወዳንዱ ይጋፋሉ እንጂ ባንዱ ብቻ የሚፀኑ አይደሉምና ወደዚያው በደረሱ ጊዜ ሌላ ማሰብ ይጀምራሉ። እንዲህ ከሆነ ምኞትን በትንሹ መግታት ትንሽ ነገር አይደለም። ብዙ ሰዎች በሐሳብ መመሠጥንና መመስገንን ሲፈልጉ ይታያሉ ነገር ግን ደግሞ ሌላ ያስባሉ እንጂ የሚፈልጉት እንዲፈጸም አይተጉም። ወንድሜ ሆይ ከክፉ ነገር ሁሉ ራስህን ካላራቅህ የተፈጸመች ነፃነትን ለማግኘት አትችልም ክፉ አሳብና የተንኰል ነገር ሁሉ የራስም የሰላምና የሀገር ጠላት መሆኑን አስብ። በቅን ልቡናና በእውቀት ሥራ መሥራት ነው።ነገር ግን እውቀት ሁሉ እግዚአብሔርን መፍራት ካልተደባለቀበት የሚፀናና የሚጠቅም አይምሰልህ፡ወንድሜ ሆይ በሔድክበት አገር ጠንክረህ ተማር ለትምህርት ሔድህ እንጂ ለመዐዘን አይደለም። ለትጋት ሔድህ እንጂ ለስንፍና አይደለምና ተጠንቀቀህ ተማር። ለጨዋታ ዝግጁ እንደምትሆን ለትምህርትም ዝግጁ ሁን። የዚህም ዓለም ሀብት በብርታት እንጂ በስንፍና፥ በብልሃት እንጂ በድንቁርና አለመገኘቱን በጣም አስብ ። ሌሎችም ሰዎች በክብር ከፍ ከፍ ያሉና የበለጡ ብታይ እኔም ዛሬ ተዋርጄ

ተምሬ ኋላ እንደነሱ ካለ ክብር አደርሳለሁ ብለህ አስብ እንጂ በሕፃንነትህ ወራት ሀብት አጣሁ ብለህ አትዘን በሕፃንነት ወራት የተገኘ እውቀት ነው እንጂ በሕፃንነት ወራት የተገኘ ሀብትና ገንዘብ ሥራ እንደማይዝና እንደማይጠቅም የታወቀ መሆኑን እወቅ ።

ንቁ ተማሪ የታዘዘውን ሁሉ በመልካም ይቀበላል ይፈጽማልም ሰነፍና ቸል ባይ ሀኬተኛ ተማሪ ግን ውሥጣዊ መፅናናት አይችልምና ትምርት ጭንቅ መስሎ ይታየዋል እንጂ የኋላው የትምህርቱ ፍሬ አይታሰበውምና ስለዚህ እዚህ እንደሰነፎች ተማሪዎች አትሁን ሰነፍ ልጅ ላበቱ ኀፍረት ነው ያለውን የሲራክን ተግሣፅ አስብ ። ወንድሜ ሆይ ትምርትህንም በጨረስህ ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠህን እውቀት ተጠንቅቀህ መሳሪ አድርገው እንጂ በማናቸውም እውቀትህ ራስህን ከፍ ከፍ አታድርግ ለራስህም ብዙ ብልሃት የምታውቅ ቢመስልህ ደግሞ የማታውቃቸው ብዙ ዓይነት እውቀቶች እንዳሉ አስብ በእውቀትህም ሥራበት እንጂ አትታበይበት መማርና ማወቅም መሥራት ነው እንጂ መኩራት አይደለም እውቀትም ሲሰሩበት ነው እንጂ ሲኩሩበት አያኰራም። ደልቁንም በያይነቱ ብዙ ፈላስፎች እንዳሉ ማሰብን አትርሳና ራስህን ለማብለጥ አትድከም ለብልህ ሰውም የሚገባው ሥራው ብልህ ሲያደርገው ነው እንጂ ራሱን ራሱ ብልህ ቢአደርገው ደስ እሚአሰኝ አይምሰልህ በትምህርትህም ቢሆን ወይም በዕድል በማናቸውም ረገድ እግዚአብሔር የሰጠህ ጌትነት የጸጋ እንጂ የባሕርይ አይደለምና ሀብትህም ጌትነትህም ከሌሎቹ አልፎ ላንተ እንደደረሰ እንዲሁ አንተም አልፈህ ሀብትህም ጌትነትህም ደግሞ ካንተ አልፎ ለባለተራዎች ይሔዳልና እንዲህ ከሆነ በሚአልፈው ጌትነትህና ሥልጣንህ ወንድምህን ጥቀምበት እንጂ ለመጕዳት አታስብበት ። የዚህም ዓለም ሀብት ወንድምን ቢጐዱበት መልሶ ራሱን እንደሚጐዳ የሉቃስ ወንጌልም ፲፮ ቍ ከ፲፱ እስከ ፴፩ ተመልከት ወንድሜ ሆይ ለጊዜው ይኸን ከዚህ በላይ የጻፍኩልህን ምክር አንተ በእውቀትህ ጕልምስህ እስትትጨምርበትና እስትታሻሽለው ድረስ አብሮህ እንዲቈይ እለምንሃለሁ ።

ወንድምህ ነጋድራስ አበበ ወልዴ ።

ሙሴ ማዬን ስላገኛቸው የአኤሮፕላን አደጋ ።

ዓርብ ኅዳር ፴ ቀን ከማታው ፲ሰዓት ተኩል ሲሆን ሙሴ ማዬ ከፈረንሣዊ አገር በመጡበት አኤሮፕላን ወዳጆቻቸውን ሁሉ እየያዙ በየተራ ሲበሩ ቈይተው በዘጠነኛው ከሙሴ ሻኑአ ጋራ ሁነው ሲበሩ አኤሮፕላኑ ታውኮ ግርማዊት እቴጌ መነን ባሠሩት የሴቶች ትምህርት ቤት ፊት ለፊት አንድ ቤት ወድቆ ያላንድ አደጋ ሙሴ ሻኑአም እሳቸውም ተረፉ ። አኤሮፕላኑም በወደቀበት ቤት ውሥጥ አንድ በሽተኛ ተኝቶ ነበርና በእግዚአብሔር ቸርነት ተረፈ አኤሮፕላኑ ግን በጭራሽ ተሰብሯል ።

ይህነንም ከሰማን በኋላ ይህ አደጋ የሆነው በምን ምክንያት ነው ብለን ሙሴ ማዬን ብንጠይቃቸው ፤ቀጥሎ ያለውን ምላሽ ሰጡን ።

አኤሮፕላኔ በመልካም ሁኖ መሥራቱን ለማሳየት ብዙ ጊዜ እያረፍሁ ፤ ብዙ ጊዜም እየተነሣሁ ሳሳይ ፤ በመጨረሻ ከበረርሁ በኋላ ፤ ለማረፍ አኤሮፕላኔን ወደ መሬት በዘቀዘቅሁ ጊዜ ኃይለኛ ነፋስ ተነሥቶ ስላወከኝ እንደገና ለአኤሮፕላኑ ኃይል ሰጥቼ ወደላይ ለመነሣት ግድ ሆነብኝ ። ይህነኑም ያደረግሁበት ምክንያት ለማረፍ መሬቱ ወደታች ስለራቀብኝ ነበር ። ነገር ግን አኤሮፕላኔን ወደ መሬሁበት ያለው ቦታ በዛፍ የተከበበና ብዙ ቤት ያለበት ስለሆነ ፤ አኤሮፕላኑም ሙሉ ኃይሉን አላገኘም ነበርና ካሊብቱሱን ተሻግሬ ለመሔድ የማልችል መሆኔን ተረዳሁት ከዚህ በኋላ አደጋም ቢያገኘኝ ባያገኘኝም አኤሮፕላኑን መለስ አድርጌ ማዞር ይሻለኛል ብዬ አሰብሁ ። ነገር ግን ይህንም ባደርግ አበታቹ ብዙ ሰው አይ ነበርሁና ምናልባት እነሱ ላይ የወደቅሁ እንደሆነ የባሰ አደጋ እንደሆነ ፈራሁ ስለዚህ የሆነውይሁን በማለት አላይኛውግቢ አጠገብ ባለው ወታደሮች በሚማሩበት መስክ ላይ መድረስና ማረፍ ይሻላል ብዬ አሰብኩ ። ይህም የማይሆንልኝ መሆኑን ከወቅሁ በኋላ እንደተቻለኝ አኤሮፕላኔን ዘቅዝቄ ወደ መሬት ለማቅረብና በሰው ላይ አደጋ እንዳላመጣ ብቻ ቍርጥ አሳብ አደረግሁ ። ከዚህ በኋላ የሆነውን እናንተም አይታችሁታል እሉን ።

በእውነትም አኤሮፕላኑ እንደወደቀ ሰዎቹ እንደተረፉ ለተመለከተው ሰው እጅግ ያስገርማል።እግዚአብሔር በተአምራት አተረፉቸው እንጂ እንደሰውስ ፍርድ የሚቻል አይመስልም ።አደጋ በሁሉ ነገር ሊመጣ ይችላል ስለዚህ ለአኤሮፕላን መንዳት የተመረጡ የኢትዮጵያ ልጆች ይህነን አደጋአይተው አሳባቸውን ያቋርጥባቸዋል ብለን አንጠረጥርም ። ይልቅስ ይህ ሁሉ ትምህርት ይሆናቸዋል ብለን እናምናለን ። ሙሴ ሻኑአንም ሙሴ ማዬንም ።አኤሮፕላኑ በወደቀበት ቤት ውሥጥ የነበሩትን ሰዎች ሁሉ እንኳን እግዚአብሔር ከአደጋ አዳናቸው

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

መተባበርን ለማጥፋት ስለ እሚጥሩ ሰዎች ።

አንዳንድ ሰዎች የአንድነት ወጥመድ ለመሆን እመሸታ ቤት ገብተው ጠጅ እየጠጡ ከጋለሞቶቻቸው ጋራ የሚጫወቱት ሲያጡ መሰንቆ ገዝጋዦቻቸውና ከራር ደብዳቢዎቻቸው ከመገዝገዝ ሲያቋርጡ በዚህ መካከል ከነሱ አንዱ የተማረ ሊመስል የሃይማኖትን አካሔድ ያነሣና እገሌና እገሌ ፍራማሶን ናቸው እገሌና እገሌ እስላሞች ናቸው ሰው ሁሉ ሃይማኖቱን ትቶታል እንቺና እኔ ብቻ ነን ክርስቲያኖች ይላታል። እርስዋም መቸም ምልክታቸው ይህ ነውና እረ ካልህስ እሊህ አሁን የቈጠርሀልኝ ሰዎች ሁሉ ሰውነታቸውም ደወፍር ጀመረ ጽሕማቸውንም ይላጫሉ ከሰው ጋራም መነጋገር ትተዋል። ጠጅም እንዲጠጡ እመሸታ ቤት አይገቡም ትለዋለች። እስዋም የምትፈልገው የሚያነጋግራትን ነውና እንዲህ እየተባባሉ ወዲያው የ፪ የ፫ ብር ጠጅ እየጠጡ እንደ አሕዛብ ሲሆኑ ከሕግ ወጥተው ደገኛ ሥራ ሳይሠሩበት ሰዓቱ በከናባቸው ይገኛል።

ከዚህ በኋላ እርሱም በልማድ መሪነት እየተመራ ከመልአከ ዑቃቤው ተለይቶ በየመንገዱ ከሰው ጋራና ከየእንስሳው ከየስልክ ዕንጨቱና ከየአቶሞቢሉ ጋራ እየተጋጨ ሰው ሁሉ እየሸሸው ለዘበኞችም አስቸግሮ ዓይኑን አፍጥጦ፥ ጥርሱን አግጥጦ፥ መልኩ ተለውጦ፥ እንደምንም እቤቱ ይገባል። ሚስቱም እሰይ መጣ በማለት ፈንታ መከራዬ መጣ የት ልደርስ ብላችሁ ቤቱን ክፈቱልኝ በሩን ሰፋ አርጋችሁ። እያለች ትቃወ ትሸሻለች። እርሱም ገብቶ ይወድቃል። መቸም የሚያስፈልገውን ሁሉ በውጭ አግኝቶ ውሉዋልና ከሚስቱ ጋራ ሳይተዋወቁ አድረው ይገኛሉ። እርስዎም እንኳን እንዲህ ያለምክንያት አግኝታ እንዲያውም በየጊዜው ወንድ ቢለዋወጥላት ነው የምትወድና እርስዎም አባቷም ያልተማሩ የሆኑ እንደ ሆነ ላባቷ አፋታኝ ብላ ትነግረዋለች። የተማሩስ ቢሆኑ ወይከውኑ ፪ሆሙ ፩ደ ሥጋ እንከሰኬ ኢኮኑ ፪ኢተ አላ ፩ ሥጋ እሙንቱ ዘእግዚአብሔር አስተጻመረ ሰብእ ኢይፍልጥ የሚለውን ወይም ደግሞ ወእመኒ ብእሲት ባቲ ምት ወኢየአምን ወያፈቅር ብእሲቶ ወይፈቅድ ይንበር ምስሌሃ ኢትኅድግ ምታ፥ የሚለውን ያስቡ ነበረ። አባቷም በየወሩ ብዙ ትርፍ ያገኝባታልና ደስ ብሎት እንዲህ እያለ ያነጋግራታል። ልጄ ሆይ መቸም ቤት አይደለምን እኛም እንደዚህ ነን። አይዞሽ ግድ የለሽም ይኸ ማሠሪያው ምንም ያህል ያስቸገረ አይደለም እንፈታዋለን፥ ከገባሽ ምን ያህል ቀን ሆነሽ ይላታል። እርሷም ፫ ወር ሆነኝ ትለዋለች፥ አባቷም ደግም አላደረግሽ ፪ተኛው ወርስ ለመጀመሪያ ወር ማደናቀፊያ ይሆናል፥ ፫ተኛውን ወር ግን በከንቱ አሳልፈሽዋል ደግሞ ከሌላ ዘንድ ጥሎሽ የምንቀበልበትን እያለ ብርስዋ እየፈረደ ልጁን ያፋታል መቸም የሚፈልገው በየቀኑ መጋባትን በየወሩ መፋታትን ነውና እንዲህ የሚያደርጉት ሰዎች እኛ ብቻ ጻድቃን ነን፥ ሰው ሁሉ ኃጥእ ነው እያሉ ዝምድና ለማጥፋት የሰውን ሃይማኖት እያቃለሉ የነሱን ሃይማኖት ያከብራሉ።

ይኸውም የሆነው ውሎ ያደረና የሰነበተ አይደለም በ፲፱፻፳፩ ዓ ም ነሐሴ ፱ ቀን እናቱ የኛ ወገን ኢትዮጵያዊት ትመስላለች አባቱ ግን ምናችንም አይደለም ምናልባት በግምት ዓረባዊ ይመስላል፥ይኸው ክልሱ (ክልስልሱ) ሰው የሚገኘው ከጋለሞታ ጋራ እጠጅ እመሸታ ቤት ነው፥ አንዳንድ ጠጅም የማይጠጡ ጠላም የማይጠጡ ልባቸውን የሚያማቸው ኢትዮጵያውያን አልፈው አልፈው ጾምም ቢሆን ለንስሓ አባታቸው እየነገሩ ሕመማቸውም ጥቂት ገለል ሲልላቸው ንስሓ እየተቀበሉ መቸም ሌላ የሚቀምሱት መብልና መጠጥ ስለሌለ ወተት ይጠጣሉ፥ ምናልባት በደል እንኳ ቢሆንባቸው ንስሐሰ ትሬስዮ ለዘአበሰ ከመ ዘኢአበሰ ይላልና።

ይኸም ስካርና ዝማዌ ሐሜትም ገንዘቦቹ የሆኑት ሰው ያለሥራው ገብቶ እሊህን ሕመምተኞች ሰዎች ሃይማኖትም የላቸው እያለ ሃይማኖታቸውን ያስተናንሳል እርሱን ግን አንተ ሃይማኖትህ ምንድር ነው አንድነትና ሦስትነት በምን በምን ነው ብሎ ቢጠይቁት ምላሽ አያገኝም እንኳን ያላባቱ ሥራ ምሥጢረ ሥጋዌ ሊደርስ የዚህን ሰው ታሪኩን ሁሉ ጽፈን ስሙንም ገልጸን እናስታውቃችኋለን። አሁን ግን ስካርንና ዝሙትን ሐሜትንም ገንዘብ ካደረገ ሰውና በሕመማቸው ጊዜ ለነፍስ አባታቸው ነግረው እየፈሩ አንድ አንድ ቀን ወተት ከሚጠጡት ሰዎች የማንኛው ሃይማኖት ጐደለ? እስቲ እሊህን ሰዎች ፍረዱዋቸው በዚህ ሥራቸው ሃይማኖተ ጐደሎዎች ይባላሉን። ነገር ግን ምግባሩ ክፉ የሆነ ብርሃንን አይወድምና በብርሃንና ሰላም በመገለጹ ሐሜተኛው ሳያዝን አይቀርም።

የተ መ ተ ቤ አ መ በ ።

በባቡር መግባት ።

ክቡር ብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ የትምህርትና የጥበብ፥ የዋናውም የሕግ መወሰኛው ምክርቤት ዲሬክቱር ለታላቅ ጉዳይ ተልከው ከመኳንንቱ ጋራ ሔደው የተላኩበትን ፈጽመው በኅዳር ፳፫ በዓርብ ባቡር አዲስ አበባ ገቡ ። ከወዳጆቻቸውም ብዙ መኳንንትና የውጪ አገር ሰዎችም፥ በየክፍሉ ካሉት ሠራተኞችም ወዳጆቻቸው በባቡሩ መቋሚያ ተሰብስበው ይጠባበቋቸው ነበሩና ባቡሩ መጥቶ በቆመ ጊዜ በብዙ ናፍቆት ተቀበልዋቸው ። ይልቁንም በውሥጣቸው ያሉ የትምህርትና የጥበብ ሠራተኞችና ተማሪዎች እንደ ሙሽራ አበባ ይዘው ተቀበልዋቸው ። ከባቡሩ መቋሚያ ወጥተውም በአቶሞቢል ሁነው ወደቤታቸው ጉዞ በጀመሩ ጊዜ ብላቴን ጌታ ሣህሌ ፀዳሉ በተቀመጡበት አቶሞቢል በፊትና በኋላ በአቶሞቢሎች ፊት ያማረ ያማረ አበባቸውን አስቀድመው ሲአጅቡእጅግ አማሩ። ብርሃንና ሰላም እንኳን በደኅና ገቡ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ነጋድራስ ሐራሰማይ ።

ስለነጋድራስ ሐራሰማይ ሞት

ነጋድራስ ሐራሰማይ እጅግ ብልህ የሀገር አካሔድ አዋቂ ለጌታው የታመነ አገልጋይ ነበረ ገና በልጅነቱ የፍርድ ጸሐፊ ነበረ ኋላም በወላሞ አውራጃ ዋና ጸሐፊ ሁኖ ነበር፥ ቀጥሎም

በወንጀለኛ ቅጣት ፍርድ ቤት ዳኛ ሁኖ ነበር ቀጥሎም በወላሞ፥ በቈጫ፥በበረዳ፥ በገሙ፥ ነጋድራስ ተብሎ ተሹሞ ነበር። አዲስ ለቆመውም የምክር ቤት ከየሀገሩ ደኅና ደኅና ሰው ባላገሩና መኳንንቱ ሠራዊቱ እየመረጠ ወደአዲስ አባባ እንዲልክ በታዘዘ ጊዜ የወላሞና የበረዳ ባላገርና መኳንንት ሠራዊት ነጋድራስ ሐራሰማይን መርጠናል ብሎ ፈርሞ ወደ መንግሥት ስለላከ ወደ ምክር ቤት ገብቶ ሲመክር ቈይቶ ተሰናብቶ ወደ ወላሞ ሔዶ ነበር።ደግሞ ከወላሞ ከፍ ባለው በሲዳሞ ነጋድራስ ተብሎ እዚያው እንደሆነ ተሹሞ ነበር። ነገር ግን ተላላፊ በሽታ ከቤቱ ገብቶ ነበርና ባለቤቱና ልጁ ቤተሰቦቹም ታመው ወላሞ ካለው ሆስፒታል ገብተው ቈይተው እነዚያን ሲአስታምም ሰንብቶ እንደ ታዘዘው በኅዳር ፯ቀን ከወላሞ ተነሥቶ በኅዳር፲፪ ቀን ሲዳሞ ገብቶ ገና ሥራውን በሥርዓት ሳይረከብ ታሞ በታመመ በ፫ኛው ቀን በኅዳር ፳፮ ቀን ሙቶ በዚያው በሲዳሞ ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ክብር ተቀበረ የሚል የስልክ ቃል መጥቶ እኅቶቹና ዘመዶቹ፥ ወዳጆቹም ሁሉ ተረድተው በአዲስ አበባው ቤቱ ታላቅ ልቅሶ ተደረገ። ዕድሜውም ፵፩ ዓመት ነው ያውም አልተፈጸመም አስተውሉ በሚሠራበት ጊዜ መሞቱ እጅግ ያሳዝናል በ፲፰፻፹፬ ዓመተምሕረት ተወልዶ በ፲፱፻፳፭ ዓመተ ምሕረት በኅዳር ፳፮ ቀን ሞተ ወይ ሰው መውጣቱን እንጂ መውረዱን ሳያስብ መኖሩ እጅግ ያስደንቃል ። መቸስ ምን ይደረጋል ልጁንና እኅቶቹን፥ዘመድ ወዳጆቹን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ እያለ ብርሃንና ሰላም ኀዘኑን ይገልጻል።

የሙሴ ፖል ዱሜር የፈረንሣዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን መገደል (ሞት።)

በፓሪስ ከተማ ግንቦት ፯ቀን ታላቅ መጥፎ ሥራ ተሠራ የፈረንሣዊ መንግሥት ፕሬዚዳን ሙሴ ዱሜርን ገደሉት። ዓለም ሁሉ በዚሁ ነገር ተነቃነቀ ። የገደሉበትም አኳኋን በዚህ ቀን በባሮን ሮትሽልድ ግቢ አዲስ መጽሐፍ መታየት ስለነበረ ሙሴ ዱሜር ከዚያ ለመሔድ ፈቃድ አድርጎ ነበረና ይህንን ገዳዩ ፓዌል ጎርጉሎብ አውቆ ስለነበረ ከዚያ ጠበቀው። ፕሬዚዳንም በተከታዮቹ ተከቦ ወደተዘጋጀው ስፍራ በገባ ጊዜ አንድ ሰው አክሉ ግዙፍ የሆነ ፈጥኖ ወደርሱ ቀረበና በጣም በተጠጋ ጊዜ ከኪሱ ሽጉጥ አውጥቶ አምስት ጥይት ተኩሶ መታው ፕሬዚዳንም ቈሰለና ሊወድቅ ሲል የከበቡት ሰዎች ደገፉት ወዲያውም ሐኪሞች ከዚያ ኑረው በፍጥነት የሚያስፈልገውን ሕክምና አደረጉለት። ከዚህ በኋላ በቅርብ ባለው አንድ ሆፒታል ወሰዱት ቍስሉቹም እጅግ የበረቱ ስለነበሩ የመዳን ተስፋ የሌለበት መሆኑን ተረዱት ሐኪሞች ግን በተቻላቸው ሁሉ ሕይወቱን ለማቈየት ኦፔራሲዮን በማድረግና ልዩ ልዩ መድኃኒቶች በማድረግ እጅግ ደከሙ በመጨረሻው የማዳን ነገር ፈጽሞ የማይቻል ሆነና ሌሊቱን ሁሉ በፃዕር አድሮ በማግሥቱ ጧት ሞተ።

የዚህ ኃጢአት ሥራ ምክንያቱ ምን ነበር ? ነፍሰ ገዳዩ ተይዞ በአደባባይ በተመረመረ ጊዜ ተናገረ። » እኔ ይኸንን ሰው ሁሉ የሚወደውን ፕሬዚዳን በራሴ ጉዳይ በኩል ምንም የጠላሁበት ምክንያት የለኝም። » ደግሞ በዚሁ ነገር የፖለቲክ ምክንያት እንደሌለበት በፍርዱ አደባባይ ታየ። ስለዚህ ምናልባት ይህ ገዳይ እብድ እንደሆነ በማለት ሐሳብ ተደርጎ ነበረ ግን በሐኪሞች ዋና ምርመራ እብደት እንደሌለበት ተገለጸ። እንደገና አደባባይ እየወጣ ቢመረመር ብዙ አዲስ ነገር ተገኘ ይህ ሁሉ ስለ ተደረገ እውነተኞች ምክንያቶች ሁሉ አልተገለጹም ነበር ስለሆነ ይህ ሰው ከመስኮብ አገር ሲወጣ ለሕይወቱ የሚሆነውን ገንዘብ የሚያገኝበት ከሆነ ማናቸውንም ሥራ ለመሥራት ባለፈቃድ መሆኑ ታወቀ።በመስኮብ አገር ከታላላቅ ኮሚኒስቶች ጋራ የሚሠራ እንደነበረ የመጀመሪዋ ሚስቱ ተናገረችበት በፍርዱም ጊዜ አንድ ኰዛክ ላዛሬብ የተባለ መጣ (በዚሁ ጊዜ ይኸ ሰው ኑሮው በፈረንሳዊ አገር ነበር) ይኸውም ላዛሬብ ኰሚኒስት ቼኪስት (ቼኪስት ማለት ቦልሾቢክ ማለት ነው።) በጐርጉሎብ ባየው ጊዜ አወቀውና ከዚያ በፊት በ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት በሮስቶብ በተባለ ከተማ እኔን እንደዚሁ ለመግደል አቍስሎኝ ነበር ብሎ ተናገረ።ጐርጉሎብ ከመስኮብ አገር ሲወጣ ወደ ቼኰስሎባክ አገር ሔደ። ከዚያም በኡኒቤርሲቲ ተማሪ ቤት ገብቶ የሕክምና ሥራ ተምሮ ዶክተር ተብሎ ወጣ። ግን ለእንደዚህ ያለ ሥራ ሰውዬው መጥፎና የማይገባ መሆኑ ከታወቀ በኋላ የሕክምና ሥራ እንዳይሠራ ተከለከለ። ከዚህ በኋላ ወደ ፈረንሳዊ አገር ሔደ። ከዚያም ክፉ ባሕሬ ስለነበረበት የፈረንሳዊ መንግሥት ከአገሩ እንዲወጣ አዘዘ። እጅግ የሚያስደንቁ መጻሕፍቶች እያሳተመ ያላንድ ሥራ ከቤተ ሰዎች ጋራ ያለችግር በመልካም አኳኋን ይኖር ነበር ግን ለዚህ ሁሉ የሚሆነውን ገንዘብ ከምን እንደሚያገኘው አይታወቅም ነበር። በመጨረሻውም ብዙ ታላላቅና እውነት ያላቸው ሰዎች ሁሉ የዚህን እውነተኛውን ምክንያት እናገኝበታለን ብለው በብዙ አኳኋን ቢጠይቁትና ቢመረምሩት ከቶ ምሥጢሩን ለማግኘት የማይቻላቸው ሆነና ብዙ ነገር እንደ ተደበቀበት ቀረ። ለሞትም ፍርድ በተፈረደበት ጊዜ እንደ ዕብድ ሆነ ይህንንም ያደረገው በአውሮፓ ዕብድ ይሙት በቃ እንደማይፈረድበት ያውቅ ነበርና ይተውት ስለመሰለው ነበር፥ ግን ሐኪሞች ምንም የዕብደት ምክንያት እንደሌለበት መስከረውበት ነበር።

ስለዚህ በፍርዱ አደባባይ ይሙት በቃ ተፈረደበትና በመስከረም ፬ ቀን በጊሊ ኦቲል መኪና አግብተው ገደሉት። ግን ወደ ሞት ሲሔድ ሁሉ ከቶ ማን ለዚህ ሥራ እንዳዘዘውና ወይም ይህንን ደግ ሰው ሁሉ የወደደውን ፕሬዚዳን በምን ምክንያት እንደገደለው ፈጽሞ አልተናገረም በልቡናውም የነበረውን ምሥጢር እንደያዘው ወደ መቃብር ገባ።

ኦልጋ ንጊን።

መሰናበቻ ።

የኢትዮጵያ መኳንንትና ወይዛዝር ወዳጆቼ ሆይ ሁለት ዓመት ተመንፈቅ አብረአችሁ ስለተቀመጥሁ በጣም ደስ ብሎኛል አሁንም ኰንትራቴ ስላለቀ ወደሃገሬ መመለሴ ስለሆነ በየቤታችሁ እየመጣሁ እንዳልሰናበታችሁ ጊዜ የለኝምና በሚመጣው ሳምንት ከባለቤቴ ጋራ እንሳፈራለንና የሚገባችሁን ሰላምታየን እየሰጠሁ በማክበር አመለክታለሁ።ምንጊዜም

ቢሆን ፍቅራችሁና ውለታችሁ ከልቤ አይጠፋም አገሬም ከደረስሁ በኋላ ካገራችሁ ጋራ ደኅንነታችሁን እንድሰማ ተስፋ አለኝ ። ታኅሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም ሙሴ ቢዶል ።

ማስታወቂያ።

በማናቸውም ምክንያት የመንግሥት ገንዘብ ተበድራችሁ ያልከፈላችሁ ሰዎች ከዚህ ቀደም የገንዘብ አስገቢው ሹም አቶ ወሰን የለህ እንድታገቡልን እያለ በየጊዜው በጽሕፈት ጠይቋችሁ እስከሁን ጨርሳችሁ ስላልከፈላችሁ ከንግዲህ ወዲህ የተበደራችሁትን ገንዘብ እስከ ፲፱፻፳፭ ዓመት ታኅሣሥ ወር መጨረሻ ድረስ በገንዘብ አስገቢው ባቶ ወሰን የለህ በኩል አምጥታችሁ ጨርሳችሁ ወደ ዋናው ገንዘብ ቤት እያገባችሁ የደረሰኝ ከዋናው ገንዘብ ሹም ከቶ ወልደ ጻድቅ እንድትቀበሉ። እስከዚህ ወር መጨረሻ ድረስ ጨርሳችሁ ሳትከፍሉ ብትዘገዩ ግን በከተማና በውጭም አገር ያለው ርስታችሁ በሐራጅ ተሽጦ የተበደራችሁት ገንዘብ ተከፍሎ እንዲያልቅና የተረፈው ገንዘብ እንዲመለስላችሁ ማድረጋችንን እንድታውቁት ይሁን። የገንዘብ ሚኒስቴር።

AVIS

Nous constatons avec regret, que diverses personnes, ayant contracté une dette envers le Gouvernement, s'obstinent à n'en pas faire le réglement, malgrè des injonctions réitérées, qui leur ont été faites par ato Wossenéleuh, notre préposé à la liquidation des créances du Gouvernement.

Nous invitons, pour une dernière fois, messieurs les débiteurs du Gouvernement, à s'acquitter de leur dette, jusqu'à fin tahessas 1925 (décembre 1932.) Pour ce faire ils devront se présenter à ato Wossenéleuh, qui les conduira à ato Wold-Sadik, notre trésorier central ; ce dernier leur délivrera l'acquit de leur dette Passé ce délai, le ministère des finances, se truvera dans l'obligation de rentrer dans ses créances, en vendant aux enchères toute propriété du débiteur, se trouvant en ville et ailleurs.

En cas où le produit de la vente présenterait un solde, après le réglement de la dette, cette somme sera retournée au propriétaire.

Le Ministre des Finances.

ማስታወቂያ ።

በአዲስ አበባ ላሉ ቤት ሥራ ለሚሠሩ ሰዎች አናጢነትና ማናቸውንም ሥራ ለተባለው ሁሉ ለሚሠሩ ሠራተኞች አረቢያን ታሬዲንግ ኩምፓንያ ባለበት ግቢ ውሥጥ አንድ አዲስ ቤት ሥራ ተጀምሮ ሥራው ሳያልቅ ግማሹ ተሠርቶ ግማሹ ስለ ቀረ ሠራተኞች የሆናችሁ ሥራውን ለመሥራት ብትፈልጉ መጥታችሁ አይታችሁ ገምታችሁ ግምቱን ስታስታውቁን ትዋውለን ሥራውን ለመስጠት ይቻላል። አረቢያን ትሬዲንግ ኩምፓንያ ። ታኅሣሥ ፫ ቀን አ አ ፲፱፻፳፭ ዓ ም

Japanise Dentist

ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፯ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።



ባለንጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለንጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ ጊዜ እንዳስታወቀው የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ዕዶችን ቦታ ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፰ዓ ም ከጧቱ በ፬ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል።

የፊታውራሪ በዳኔ አሽግሬ አጥቢያው አቃቂ መድኃኔ ዓለም ስፋቱ ፬፻፲ና ፲ሺ፮፻፶፩ ሜትር ካሬ።

የባሻ ወልዴ ዮሐንስ አጥቢያው ማርያም ስፋቱ ፲፬ሺ ፯፻፷፬ ሜትር ካሬ ።

የወይዘሮ ዓመተ መንፈስ ቅዱስ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፬፻፸፯ ሜትር ካሬ።

የወይዘሮ ወለተየስ ሀብቱ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፪ሺ፫፻፹ ሜትር ካሬ።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሲጊያን ዘንድ ይገኛል ። ደህነኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተኩል ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

ማስታወቂያ።

ለኢትዮጵያ ሰው የሚሸጥ ርስት ።

የባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ሂሳብ አጣሪዎች በ፫ሺ፬፻፹፬ ቊጥር የተጻፈውን ርስት ስፋቱ ሺ፯፻፵፯ ሜትር ካሬ ፥ አጥቢያው ሥላሴ ከደጃዝማች ከበደ ጓንጉልና ከንቡረ እድ አድማሱ ቦታ ጉረቤት ጥንት የባለዕዳችን የዋጣ ሥዩም ግርማይ ርስት የነበረውን ለመሸጥ ስላሰበ ይኸንን ማስታወቂያ ለሕዝብ ይገልጻል ። ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ባንክን ለመጠየቅ ይችላሉ።

ስለ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ሂሳብ አጣሪ ፊርማ።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

በዚሁም ጊዜያት ጠቅላላውን የሴቶችና የወንዶችን ውብቶች በሚያስረዳበት ጊዜ ግን ውቢቱ እመቤቱ ቀልጣፋና አቋቋመ መልካም እንድትሆን ይኸውም እየራመዘመናት ይፈቅዳል በሚያሳዝነው አቀማመጣቸው ብዙ ሰዎች በሽተኞች ናቸው ። ደግሞም በምግባቸው አኑዋኑዋር እንዲሁም በጨካኝነትና ችግረኛ በመሆናቸው ለመዳንም አይችሉም ። ለነዚሁም ሰዎች ብዙ ጊዜ የተወደደና በእውነት የማይሳሳተውን መድኃኒት እንሰጣቸዋለን። ሊፖቶዴን የሚባለውን በጥቅልል ያለውን መድኃኒቴን በጣም ሲያስጨንቅዎትና ሲያምዎት ቢሞክሩት ሕመምዎን በማቅለሉ ብዙ ደስ ያሰኝዎታል በአዲስ አበባ ውሥጥ ግዙፎችንና ሰውነተ ቁጡ ለሆኑ ሰዎች እየሩ አለመሰማማቱን ይልቁንም ከኔ የበለጠ ያውቁታል፡ይልቁንም ደግሞ ዋና ማስረጃ እንቅልፍ ለሌለውና ለሚባንን ሰው ነው ።

ለነዚሁም ሰዎች ፈጽሞ የሚከለከልላቸውን ዲአል ከምፕሬሜ የሚባለውን መድኃኒታችንን በጣሙ የጠራውን ከምንሰጣቸው በተቀር ሌላ የማያስፈልጋ መሆኑን እናስታውቃችኋለን ። ደግሞ ከዚህ በኋላ የሰውነት ሥራቸውን ተስማምተው ያለ ሐሳብ ሌሊቱን በደስታ ያልፉታል ስል ባለኝ እውቀቴ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አሳስባለሁ

ታዛጋርዎ ኤም ማትሳኪስ ።

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው ብምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች።ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ከንድ ቀን አንድ ቀን እየተዋበች ሔዳች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው፡ ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወሰዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ተማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው ፡፡

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመጎብኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክተር ሚክኤል ።

በሞንፐሊዬ ኡኒበርሲቴ ።

ስለውሥጥና የሴት በሽታ ፤የቍስልና ፤የዓይን በሽታ የሴት አዋላጅነት ሕክምና የተመሰከረላቸው ድሮ ራስ መኰንን ድልድይ ቤታቸውን ትተው ወደ ጉለሌ መንገድ ሙሴ ሙራዲያን ቤት አጠገብ ቤት መለወጣቸውን ለወዳጆቻቸው በማክበር ያስታውቃሉ ።

ሁሉ ቀን ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፮ሰዓት ደግሞ ከ፱ ሰዓት እስከ ፲፩ ሰዓት ይገኛሉ ።

ሐሙስ ዕለት በጧቱ በሽተኞች አለዋጋ ያክማሉ ።

የሚሲዮን መጽሐፍ መሸጫ ቤት ።

የሱዳን ኢንቲሪዎር ሚሲዮን ዶክቶር ለምቢ ዲሬክቶር ወደ ራስ መኰንን ድልድይ በሚወስደው መንገድ ማጅስቲክ ሆቴል የሚባለውን አለፍ ብሎ መሐመድ አሊ ኩባንያ አዲስ ሱቅ አሰራበት አገጠብ የመጽሐፍ መሸጫ ቤት መክፈቱን ያስታውቃል ።

ከዚያ በያይነቱ የጽሕፈት መሣሪያና በፈረንሣዊ በአማርኛም በእንግሊዝም በሌላም ቋንቋ የታተመ መጽሐፍ ቅዱስና ደግሞም ማለፊያ ማለፊያ መጽሐሮች ይገኛሉ ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ባሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሚሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት እንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራየሚሆን መኪና አስመጭ

ቁ ፤ ፪፻፯ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስምንተኛ ዓመት ቍጥር ፶፪
8^me ANNE. № 52

ሐሙስ ታኅሣሥ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፭ ዓ ም
Jeudi 15 Decembre 1932

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል።
Hébdomadaire paraisant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ኢሉባቦር አሌገንት ከተማ የተደረገ የዘውድ በዓል መታሰቢያ ።

በጥቅምት ፳፫ ቀን ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የነገሡበት ቀን ስለሆነ ይኸንኑ የሁለተኛውን ዓመት የዘውድ በዓል ለማክበር ክቡር ራስ ሙሉጌታ የማይዘነጉ መሆናቸው ስለ ታወቀ ለኢሉባቦር አቅራቢያው ከሆኑት አገሮች ብዙ ታላላቅ ሰዎች ወደ ገንት ከተማ ወጥተው ነበር። ከነዚሁም ዋናዎቹ ከጋምቤላ የሱዳን መንግሥት የጋምቤላ የውሰት ቦታ ምስለኔ ምትክ (አዶኒስታንስ) ሚስተር ሂመር፥ ከዋቢኮ ፊታውራሪ ክፍሌ፥ ከወለጋም ብዙ ታላላቅ ሰዎች መጥተው ነበሩ። በዓሉም ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው እኳኋን ተከበረ። ጥቅምት ፳፪ ቀን ከከተማው አቅራቢያ ያሉ ካህናት በዓሉን ለማክበር ተሰብስበው ነበርና በሰባት ሰዓት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ዋዜማ ቆሙ። ወዲያው ባ፲ ሰዓት ፊታውራሪ በፊ.ቃዱ. ከባልደረቦቻቸው ጋራ ለካህናቱ ታላቅ ግብዣ አደረጉ። ለበዓሉም አኳኋን ከረቡዕ እስከ እሑድ በየቀኑ የሚደረገውን ሁሉ የሚያመለክት ፕሮግራም ተጽፎ ለየሰዉ ታድሎ ነበር። ጥቅምት ፳፪ ቀን ማታ የጐሬ ንግድ ማኅበሮች በክቡር ራስ ናደው ሆቴል ክቡር ራስ ሙሉጌታንና ሌሎችንም መኳንንትና ሹማምንት ራት ጋበዙ። ወዲያውም በማግሥቱ ጥቅምት ፳፫ ቀን እንደ ፕሮግራሙ ከጧቱ በ፫ ሰዓት ተኩል ክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ራስ ወርቃቸውንና ከርዶን ኒሻናቸውን አድርገውና በሚያስፈራ ግርማ ሆነው ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱ ከተማዋ በደስታ ማሸብሸብ ጀመረች። ወዲያው በከተማው ያሉ ያውሮፓ ወይዛዝርና መኳንንት ታላላቆችም ነጋዴዎች ሁሉ በዚሁ ሰዓት ሰልፉን ለማየት ወደ ተዘጋጀው ድንኳን መጥተው እንደተቀመጡ መጀመሪ የኢትዮጵያ መንግሥት ተማሪ ቤት ሹም አቶ ንጋቱ ማህሌ ከስተማሪዎቹ ጋራ ተማሪዎቹን ደስ በሚያሰኝ መለዮ አሰልፎ ሲያልፍ ዳምጤ እሰማኸኝ የሚባለው ተማሪ በክቡር ራስ ሙሉጌታ ፊት እጅግ ደስ የሚያሰኝ ቃል ተናገረ። ከዚህ በኋላ መኳንንቱና ወታደሩ ሁሉ የማዕርግና ያርበኝነት ልብሱን እየለበሰ በየተራው እየተሰለፈ ሲያልፍ ደስ ያሰኝ ነበር። እንደዚሁም ሰልፉ ሲታይ ቈይቶ ሰባት ሰዓት ሲሆን ያውሮፓ ወይዛዝርና መኳንንት ክቡር ራስ ሙሉጌታን እየተሰናበቱ ወደየቤታቸው ሔዱ። ክቡር ራስ ሙሉጌታም ወደ ግቢ ጒዞ በጀመሩ ጊዜ ነጋሪቱ ሲያጓራ፥ ጥሩምባ እምቢልታውና መለከቱ ሲንጫጫ ያጀቡ አኳኋን ዕፁብ ድንቅ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ከተማዋ በመላ በለመለመ ዘንባባና ደስ በሚያሰኝ አበባ አጊጣ በኢትዮጵያ ባንዲራ ተሸፍና ነበር።በዚህም ቀን ሕዝቡ ሁሉ እንደዚህ ባለ በታላቅ ደስታ ዋለ።

ሁለተኛ ጥቅምት ፳፬ ቀን ሐሙስ ክቡር ራስ ሙሉጌታ ለኢትዮጵያውያን መኳንንትና ወታደር ታላቅ ግብር አድርገው ነበርና መኳንንቱ ሁሉ የማዕርግ ልብሱን ለብሶ ወደ ግቢ እየገባ ለማረፊያ በተዘጋጀው ስፍራ እንዳረፈ ብፁዕ አባታችን አቡነ ሚካኤል ኮርዶን ኒሻናቸውን አድርገው መጥተው በታላቁ አዳራሽ በክቡር ራስ ሙሉ ጌታ አጎበር በስተቀኝ አረንጓዴ ሐር አጎበር ተደርጎላቸው ነበርና በዚያው ገብተው ተቀመጡ በዚሁም ቀን የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል ካፒቴን ኢ. ኤን ኤርስኪንና ሚስተር ሂመር ግብሩን ለማየት መጥተው ስለነበረ በክቡር ራስ ሙሉጌታ አጎበር በስተ ግራ ስፍራ ተዘጋጅቶላቸው ነበርና አራት ሰዓት ሲሆን መጥተው በተዘጋጀላቸው ስፍራ ተቀመጡ። ወዲያው ግብሩ ተጀመረና መኳንንቱና ወታደሩ ሁሉ መልካም ግብዣ ሲጋበዝ እስከ ፲ሰዓት ውሎ በሰላም ወደ የቤቱ ገባ ። ማታውንም ነጋድራስ ወልደ ሰማዕት ስለበዓሉ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል ካፒቴን ኢ. ኤን ኤርስኪንና ሚስተር ሂመርን፥ ልጅ ዓሥራት ሙሉጌታን ሌሎችንም የዲፕሎማቲክ ሰዎችና የኢትዮጵያን ሹማምንት ራት ጋብዘው ነበር ።

ሦስተኛ፥ ጥቅምት ፳፭ቀን ዓርብ እንደፕሮግራሙ ክቡር ራስ ሙሉጌታ የፈረሶችን መቀዳደምና ጉግስ ጨዋታ ለማዬት ከጧቱ በ፫ሰዓት ወደ አስፋ ወሰን ሜዳ ሒደው በተዘጋጀው ስፍራ እንደ ተቀመጡ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ካፒቴን ኤ ኤን ኤርስኬንና ሚስተር ሂመር ሌሎችም አውሮፓውያን መኳንንትና ታላላቆች ሁሉ መጥተው በተዘጋጀው ስፍራ ተቀመጡና የሠለጠኑት ዘበኞች ሰልፍ ጥቂት ከታዬ በኋላ የፈረሶች ጨዋታ ተጀመረ። ወዲያው የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ክቡር ካፒቴን ኤ ኤን ኤርስኪንና ልጅ ዓሥራት ሙሉጌታ

በፈረሶቻቸው የኔ ይቀድማል የኔ ይቀድማል በማለት ተወራርደው የልጅ ዓሥራት ፈረስ አዲስ አበባ፥ የቆንሲል ፈረስ ሎንዶን ሁለቱ ብቻ ሽርጥ ገብተው ሲቀዳደሙ የልጅ ዓሥራት ፈረስ አዲስ አበባ ሎንዶንን ቀደመና ተጨበጨበለት።ከዚህ በኋላ ሌሎች ፈረሶች ሲቀዳደሙ በመጀመሸው መቀዳደም ከዓሥር ፈረሶች መሐል አሊ የክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ፈረስ ቀደመ በሁለተኛው መቀዳደም ከስምንት ፈረሶች መሐል ገነት የክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ፈረስ ቀደመ ከዚህ በኋላ ባለው መቀዳደም የፊታውራሪ ዳርጌ ፈረስ፥ የፊታውራሪ ክፍሌ ፈረስ የፊታውራሪ አበበ ፈረስ ሌሎችም የብዙ መኳንንት ከሥርም ከስድስትም ፈረሶች መሐል ስለቀደሙ በመጨረሻ የቀደሙት ባንድነት ሁነው ይቀዳደሙ ስለተባለ የቀደሙት የቀደሙት ባንድነት ሁነው ሲቀዳደሙ ከሥራአምስት ፈረሶች ማሀል አሊ የክቡር ራስ ሙሉ ጌታ ፈረስ ቀደመና ተጨበጨበለት ከዚህ በኋላ የፈረሶች መቀዳደም ተፈጸመና ሁሉም በሰላም በታላቅ ደስታ ወደየቤቱ ገባ።በዚሁም ቀን ማታ ስለበዓሉ ያሜሪክን ሚስዮን ሐኪም የዲፕሎማቲክን ሰዎችና የኢትዮጵያን ሹማምንት ራት ጋብዘው ነበር ።

፩ተኛ፥ ጥቅምት ፳፯ቀን ቅዳሜ ክቡር ራስ ሙሉጌታ ስለበዓሉ በከተማው ያሉትን የዲፕሎማቲክን ሰዎችና ሌሎችንም የአውሮፓ ወይዛዝርንና መኳንንት የኢትዮጵያንም ሹማምንት በስድስት ሰዓት ምሳ ጋብዘው ነበርና ሁሉም በተጠሩበት ሰዓት ተሰብስበው በታላቁ አዳራሽ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ምሳ ተደረገና በሻምፓኝ ጊዜ የኢሉባቦር አውራጃ ጉምሩክ ዲሬክተር አቶ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደማኤል ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ዲስኩር ተናገረ ።

ክቡር ጌታዬ ራስ ሙሉጌታ ።
ክቡራን ወይዛዝርና መኳንንት ሆይ ።

ከዓለም ነገሥታት ሁሉ ወደላይም ወደታችም ብንመለከት እንደ ክቡር ዳዊት ያለ ንጉሠ ነገሥት እንዳልተነሣ እናያለን ማለት ሌሎቹ ነገሥታት በታሪካቸው እንደተመለከትነው ኃይለኛነትና ብልህነት ቢሰጣቸው ደግነትና ታጋሽነት ይቀራቸዋል እንዲሁም ደግነትና ታጋሽነት ቢሰጣቸው ኃይለኛነትና ብልህነት ይቀራቸዋል ግን ክቡር ዳዊት ኃይለኛነት ብልህነት ደግነት ታጋሽነት ይልቁንም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት በመሆኑ ነቢይነት ይህ ሁሉ የተሰጠውና ከዚህም በቀር ርኅሩኅ ስለነበረ ሕዝቡ ሁሉ የዚህን የደግ ንጉሠ ነገሥት ፍቅር እንደሸማ ለብሰው ይኖሩ ነበር ሲባል በታሪክ ስለተጻፈ ዓለም በመላው እንደዚህ ያለውን ንጉሠ ነገሥት ለማግኘት ሲመኝ ይኖራል ያገኘ የለም፡ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በዚሁ በደጉ ንጉሠ ነገሥት በክቡር ዳዊት አድሮ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር ብሎ የተናገረው ትንቢት ሲፈጸምና የኢትዮጵያም ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሲደርስ ዳግማዊ ዳዊት የሆኑ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴን ልዑል እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ አስነሣለት እነሆ ዳግማዊ ዳዊት የሆኑ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ለኢትዮጵያና ለዝሕቧ ከነገሡላት ዛሬ ሁለተኛው ዓመት ስለሆነ ዘወትር የሚያደርጉልን ደግነትና ቸርነት በልባችን ተቀርጾ ደስታችን በልባችን ስለሚገነፍል በያመቱ ይኸን የተባረከ የዘውድ በዓል ለማክበር ይገፋፋናል።

ክቡራን ሆይ ምናልባት ዳግማዊ ዳዊት የሆኑ ንጉሠ ነገሥት ብዬ የተናገርኩበት ቢያስደንቃችሁ የክቡር ዳዊትን የሕይወት ታሪክና የኢትዮጵያ ብርሃን የቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴን እስካሁን ያለውን የሕይወታቸውን ታሪክ ብታመዛዝኑት የተናገርኩት ቃል እውነተኛ መሆኑን ትረዱታላችሁ ማለት ክቡር ዳዊት ይጌይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር እም ተአምኖ በእጓለ እመሕያው ብሎ እምነቱን በእግዚአብሔር በማበርታቱ ከብዙ ልዩ ልዩ መከራ እንደ ዳነ እንዲሁም በእምነታቸው ብርታት ከብዙ ልዩ ልዩ መከራና ፈተና ድነዋል የቀረውን አእምሮአችሁ እንደዚሁ ያመዛዝነው ስለዚህ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ዳግማዊ ዳዊት ቢባሉ ትክክለኛ ስማቸው መሆኑን በዚህ እንረዳ ።

ክቡር ሆይ፥ከደጉ ንጉሠ ነገሥት ከዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከልጅነት ጀምረው በእምነት አገልግሎትዎ የታወቀ በመሆኑ በቤተ መንግሥቱ ያልታዘዙበት ሥራ አይገኝም ይኸንኑም የሚታዘዙበትን ሥራዎን ሁሉ በእምነት እየፈጸሙ በመሔድዎ ይኸው ከማዕርግ ማዕርግ እየጨመሩ እስከዚህ ደረሱ አሁንም የንጉሠ ነገሥትዎን ክብር የተወለዱበትን የነገሡበትን የዘውድ በዓል ያለመዘንጋት በያመቱ ተጠንቅቀው በሚያስደንቅ አኳኋን በማክበርዎና በማስከበርዎ ይህ ደግ አድራጎትዎ ዋጋ አያሳጣዎትምና ስለዚህ ከራስዎ የሚተርፈውን ብድርዎን በልጆችዎ እንዲያገኙት አይጠረጠርም ። እኛም የንጉሠ ነገሥቱን ክብር አጥብቆ የሚወድ አገረ ገዥ ባለበት አገር በመሆናችን ዕድላሞች ነን ለማለት እደፍራለሁ ። ክቡር የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል ካፒቴን ኤ ኤን ኤርስኪን ለንጉሠ ነገሥታችን በሚደረገው ክብር ደስታዎ የበዛ መሆኑን እያዩን በጣም እናመሰግንዎታለን ። ደግሞም ባለፈው ዓመት የጋምቤላ ሙፈትሽ ክቡር ካፒቴን ሞሪስ ይኸንኑ የዘውድ በዓል ለማክበር መጥተው እንደነበረ አሁንም የሳቸው ረዳት የሆኑት ክቡር ሚስተር ሂርመን በዓሉን ለማክበር በመምጣታቸው በጣም ደስ ብሎናልና ስለዚህ ለሳቸውና እዚህ ላሉት ላውሮፓውያን ወይዛዝርና መኳንንት የሚገባቸውን ምስጋና ካቀረብሁ በኋላ ዛሬ የቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴን የዘውድ በዓል የሁለተኛውን ዓመት እንዳከበርን እንዲሁም ወደፊት በያመቱ ሁሉ ለማክበር በፍጹም ልቤ እመኛለሁ ። ዕድሜ ለቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ፥ ዕድሜ ለዕድለኛይቱ እቴጌ መነን ፤ ለልዑላን መሳፍንት ሁሉ ለምለሟ ሀገራችን ኢትዮጵያ በነፃነት ለዘለዓለም ትኑር ብሎ በጨረሰ ጊዜ ተጨበጨበለት ።

ቀጥሎ የተማሪ ቤት ሹም አቶ ኀጋቱ ሣህሌ ደስ የሚያሰኝ ዲስኩር ተናገረ ።

ቀጥሎም የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል ካፒቴን ኤ ኤን ኤርስኪን እጅግ ደስ የሚያሰኝ ዲስኩር ተናገሩና ሦስት ጊዜ ተጨበጨበ ። ከዚህ በኋላ የአውሮፓ ወይዛዝርና መኳንንት ሁሉ ክቡር ራስ ሙሉጌታን እየተሰናበቱ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴን እያመሰገኑ ወደ የቤታቸው ሔዱ በዚሁም ቀን ማታ

አቶ ኃይለጊዮርጊስ ወልደ አማኑኤል ስለዘውድ በዓል አክባሬዎች ማኅበረተኞች ሁኖ ክፒቴን ኤ ኢ ን ኤርስኪንና ሚስተር ሂመርን፥ ነጋድራስ ወልደ ሰማዕትንና ልጅ ዓሥራት ሙሉጌታን ሌሎችንም የአውሮፓ መኳንንትና ወይዛዝር ፡ የኢትዮጵያንም ሹማምንት ራት ጋብዘ ነበርና በታላቅ ደስታ አመሹ ።

አምስተኛ ጥቅምት ፳፯ ቀን እሑድ ነጋድራስ ወልደ ሰማዕት ስለ በዓሉ በከተማ ላሉት ነጋዴዎችና ለመንግሥት ሹማምንትና ሠራተኞች ፥ ለክቡር ራስ ሙሉጌታ ሹማምንት ጭምር ምሳ ግብዣ አድርገው ነበር በዚሁም ቀን ፊታውራሪ በፈቃዱ ለባልደረቦቻቸው ግብር አድርገው ነበር ማታውንም የእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ስለ በዓሉ ክብር ክቡር ራስ ሙሉጌታንና ሌሎችንም መኳንንት ራት ጋብዘው በታላቅ ደስታ አመሹ።በዓሉ ከረቡዕ እስከ ሰኞ በእንደዚህ ያለ አኳኋን ተከበረ ይህ ሁሉ ሲሆን በከተማ የተደረገው ዘንባባና አበባ ባንዲራውም እንዳለ ነበር ግን ጽሕፈት እንደዓይን አያስረዳም እንጂ ወታደሩ ለሰልፉ ሳይጠራ በዓሉን አውቆ አስበ መሰብሰቡን የየመኳንንቱም መሣሪያ ዕዳትና መዘጋጀት ላየው ሰው በጣም ደስ ያሰኝ ነበር ክቡር ራስ ሙሉጌታም ኢሉባቦር በሥልጣኔ ካዲስ አበባ ተከታይ እንድትሆን መጣራቸው በጣም የሚያስመሰግናቸው ነው ማለት ከሁን ቀድሞ ኢሉባቦር ከመጡ ከሠሩት ከታላላቁ ሥራቸው ባላይ በኢሉባቦር ያለ ከህን ማደሪ ስላልተቀበለ በድኃው ላይ ነበርና አሁን በክቡር ራስ ሙሉጌታ ብርታት በኢሉባቦር አውራጃ ላለው አድባራት ሁሉ ስለማደሪው ቀላድ ስለሰጡት ካህኑም የተካከለ ማደሪ በመቀበሉ ድኃውም አንድ ሸክም ስለወረደለት ደስታቸው ከልክ ያለፈ ሁኖአል እንዲሁም ደግሞ ወታደሩ ሁሉ ለኛም እንደዚሁ ማደሪችንን ያስተካክሉናል እያለ በተስፋ ይጠባበቃል ። እንዲያውም ኢሉባቦር እስከ ዛሬ ርስቱ የፀና አልነበረምና ዛሬ በሳቸው ጊዜ ቀላዱ ተተክክሎ ባላባት ሚሰውን ክህንና ወታደር ማደሪውን ከተደላደለ የኢሉባቦር ርስት የፀና ይሆናልና ስለዚህ ክቡር ራስ ሙሉጌታ ለኢሉባቦር የሥልጣኔ መሪዋ ናቸው ሊባሉ የሚገባቸው ነው ሕዝቡም በመላ በዚህ በሁለት ዓመት ውሥጥ የሠሩትን መልካም ነገር ሁሉ እየተመለከተ ወደፊት ከዚህ የበለጠ ዓመት ሲቀመጡ እንደምን ያለ ሥራ ይሠሩ ይሆን እያሉ የማያስብና የመልካም ሥራቸውን ፍጻሜ ለማዬት የማይመኝ የለም የበጎ ሠሪዎችና የጌታቸውን ክብር ወዳጆች ክብራቸው ሊገለጽ የሚገባ ነው ።

ፍሬ ሕይወት ተክለአብ ።

ስለ ክቡር ደጃዝማች አያሌው ብሩ ሽልማትና ወዳገራቸው መግባት ።

ክቡር ደጃዝማች አያሌው ብሩ ለቀ ኃ ሥ በየበሩ የሚጠመዱ የጦር አርበኞቻቸውና የታመኑ አገልጋይ ናቸውና ባለፈው ጥር ፲፱፻፳፪ ዓ ም ክቡር ደጃዝማች አያሌው ወደ አዲስ አበባ እንድመጣ የግርማዊነትዎን ፈቃድ እለምናለሁ ብለው ልከው ነበርና ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ፈቃድ አልፎላቸው የፈቃዱ ቴሌግራም እንደደረሰላቸው በብዙ ደስታ በፍጥነት ወደ አዲስ አበባ ጉዞ ጀመሩ ክቡር ደጃዝማች አያሌውም በራያና በዘብል ሽፍታውን ለመውጋት ታዝዘው ስምንት ወር ዘመቻ አድርገው ሽፍታውን ወግተው አሳምነው ሲመለሱ ባንችም ጦርነት የመኳንንቱና የወታደሩ ከብቱም አልቆባቸው በጦርም በበሽታም ብዙ ሰው ተጉድቶባቸው ነበርና ቸሩ ንጉሣችን ቀ ኃ ሥ የሰዉን ጉዳት ስለ ተረዱት ሰውህ አከተማ ላይ እንዳይጉላላና እንዳይቸገር ሁለተኛ ዘመቻ እንዳይሆንበት ጥቂት ራስክን ሆነህ በመርከብ ብትመጣ ደግ ነው የሚል ቃል አልፎላቸው ደጃዝማች አያሌው ብሩ ጥቂት መኳንንት አስከትለው በመርኪብ ጉዞአቸውን አሳምረው አዲስ አበባ ገቡ። አዲስ አበባም ከገቡ በኋላ ሐምሌ ፲፮ ቀን ጃንሆይ የተወለዱበት ቀን ነበርና በዚያ ቀን ደጃዝማች አያሌው ብሩን ጃንሆይ እንደ ፀሐይ የሚያበራ ሙሉ ሽልማት ሸለሟቸው የሽልማቱም ዓይነት ቀጥሎ የተጻፈው ነው በወርቅ ያጌጠ ማለፊያ ቀሚስ፤ እንደ ካባ ላንቃ ሁኖ የተሠራ በወርቅ ያጌጠ አንበሳ በወርቅ ያጌጠ አንፋሮ ታላላቆች ሚኒስትሮች የሚሸለሙት ባለወርቅ ሰገባ ጐራዴ በወርቅና በፈርጥ ያጌጠ ጋሻ ማለፊያ መውዜር እስከ ወርቅ ዝናሩ ጥይቱ እንደሞላ ይኸን ተሸልመው ከንዳ ብቅ ባሉ ጊዜ ዘመድ ወዳጆቻቸው ሁሉ ደስ ብሎት እልልታውና እምቢልታው እየቀለጠ ወደ ቤታቸው ገቡ ። በዚሁም ቀን ሸፓኙ የሐምሌን ጉርፍ መስሎ አደረ ። ሁለተኛ መስከረም ፲፮ ቀን መስጠት የማይሰለቻቸው ቀ ኃ ሥ በወርቅ ያጌጠ የራሶች ቀሚስ በወርቅ የተጠለፈ ሐር ሱሪ፥ ማለፊያ ድርብ የራሶች ባልማዝማና በወርቅ የተሠራ ካባ ላንቃ፥ በፈርጥ የተንቈጠቈጠ ጐራዴ፥ ባለፈርጥ ጋሻ፥መውዜር፥የወርቅ ዝናር ጥይቱ እንደሞላ፥ ሳይን የሚአንጸበርቅ የወርቅ እቃ የተጫነች በቅሎ ጥሩ ፈረስ ባለ ወርቅ መጣምር ይኸን ሁሉ አንድ ጊዜ ተሸለሙና ብቅ ባሉ ጊዜ የከተማው ሰው መደነቅና መገረም በዛበት እውነት ነው ምነው ቢሸለሙ አያሌው ብሩ በሱማሌ አያሌው ብሩ በሰገሌ አያሌው ብሩ በሜጫሶ፥በራያ በዘብል ፤ ባንችም፥ አያሌው ብሩ ነው እያለ ብዙ ሰው ደስ አለው ከዚህም በኋላ ወደ አገርህ ሒድ ብለው ጃንሆይ ሦስተኛ የጃቸውን መትረየስ ሸልመው አሰናበቱዋቸው መንገዳቸውም የተፈቀደላቸው በአይሮፕላን ነበርና በጥቅምት ፲፯ ቀን አይሮፕላኑ ተዘጋጅቶ ጉዞአቸውን ሲጀምሩ ታላላቆች መኳንንት ለመሸኘት ጃንሜዳ መጥተው ነበር አይሮፕላኑም ከአዲስ አበባ ተነሥቶ ሁለት ሰዓት ከርባ ደቂቃ ሲሆን ክቡር ደጃዝማች አያሌው ከተማ ዳባት ከሚባለው ደረሰና የከተማው ሰውና ያገሩ ሰው ደስታው ከልክ ያለፈ ሆነ የአይሮፕላኑም አቀባበል ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ጧት አይሮፕላኑ ወደዳባት መሔዱን ለባለቤታቸው ለወይዘሮ ማን ያህልሻል ካሣና ለሹሞቻቸው የክቡር ደጃዝማች አያሌው መላክተኛ ፊታውራሪ ነጋሽ መርሴ አስታውቀው ነበርና መጀመሪ እንደትእዛዙ የተሰናዳው ሜዳ አራት ማዘን ነበር ዙሪያውን ፳፱ ያጌጡ ባንዲራዎች በመሐሉ ጽሕፈት ያለባቸው ተተክለው ከባንዲራው ላይ የተጻፉት ቃሎች ዕድሜ ለቀ ኃ ሥ የኢትዮጵያ ነፃ የሚል ነበር ባንዲራዎቹም በነፋስ ሲውለበለቡ ላያቸው ሰው ንባባቸውን በማንበብ ብዙ

ደስ ያሰኝ ነበር ። ከባንዲራው ውጪ ውጪውን ካኪ ለባሽ የሠለጠነ ዘበኛ ዙሯውን ተሰልፎ ነበር ።

ከዘበኛውም ውጭ ደግሞ ነጭ ለባሽ ወታደር ተሰልፎ ነበር ከሜዳውም ራስጌ ከዳር ከፍ ካለ ቦታ ላይ ማለፊያ ድንኳን ተተክሎ ምንጣፉ አምሮ ተነጥፎ ያማረ ያማረ ወንበር ግራና ቀኝ ተደርድሮ ታላላቆች መኳንንት ካባ ካባቸውን ለብሰው በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ይጠባበቁ ነበር ። በስተቀኝም የደብረ ሕይወት ገብርኤልና የከተማው አድባራት ካህናት የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው በደስታ ወረብ እያለዘቡ ይጠባበቁ ነበር ቀጥሎ ግራና ቀኝ መትረየሶች ተጠምደው ላያቸው ሰው ያስፈሩ ነበር ።

ደጅ አጋፋሪዎቹና የጦር አለቆቹም ሰሙን በየሰልፉ ለማዘጋጀት ይፋጠኑ ነበሩ የከተማው ሠራዊት በያፋፋና በየመንገዱ ሲታይ ብዛቱ ከልክ ያለፈ ሁኖ ይታይ ነበር ከዲስ አበባ አይሮፕላኑ የመነሣቱን ወሬ ሰምተው የሚጠባበቁት ያ ሁለት ሰዓት ከርባ ደቂቃ ሁለት ዓመት መስሎ ታያቸው ምን ጊዜ በደረሰልን እያሉ ይጠባበቁ ነበር የዚህን ጊዜ ሁለቱ አይሮፕላኖች እያንዣበቡ ብቅ ባሉ ጊዜ ገና ከመሬት ሳያርፉ ከተማውን እየዞሩ ሳለ የእልልታው መድመቅ መሬት የተሰበረ መሰለ በተሰናዳውም ሜዳ ባረፉ ጊዜ ሰው ለመገናኘት ይሽቀዳደም ነበረ ። የዚህን ጊዜ የሠለጠኑ ዘበኞች አንድ ጫማም እልተራመዱም ሜዳውን ከባንዲራው ውጭ ቆመው ዙሪያውን ይጠባበቁ ነበር ። የዘበኛው አለቃ እንዲህ አለ ናፍቆትና ደስታው ይልቅ የኛ ይበልጣል ግን ከታዘዝነው ሕግ መተላለፍ የለም ይልቅስ ሹም ያልጠራው ሰው እንዳይተላለፍ ጠብቁ አለና ቃሉን ዘለግ አድርጎ ተናገረ ። ከዚህ በኋላ ደጃ አያሌው ብሩ ከተሰናዳው ድንኳን ዘማለፊያ ወንበር ተቀመጡና መኳንንቱን መገናኘት ጀመሩ ሰውም ባለቃ ባለቃው እየመጣ ይገናኝ ተባለ ሹሞቹም ትእዛዝ ሰጥተው ነበር ግን በዚያን ሰዓት ደስታና ፈንጠዝያ ስለሆነ እንደ ፈቃዱ እየመጣ ተገናኘ እንጂ ትእዛዝ አልፈጸመም ነበር የሰውም ደስታና ፈንጠዝያ ላየው እዚያ ለነበርነው ሰዎች እጅግ ያስገርማል ለካ ብዙ ደስታ እንባ ይሆናል ሊገናኝ የመጣ ሴትና ወንዱ እንባ እያነቀው ተመስገን የጌታችንን ዓይን ያሳየኸን አምላክ እያለ ለእግዚአብሔር ምስጋና እየሰጠ ነው የሚገናኝ ሴቱም ወንዱም ሽማግሌውም አያሌው ብሩ መጣህልን የደኃ እናት የከብታችን እረኛ የሌባ ዳኛ መጣህልን እያለ ሴት ወንዱ ደስታውን ዘለግ አድርጎ ይናገር ነበር የዚያን ጊዜ ከሩቅ አገር የመጣ ሽማግሌ እንዲህ አለና ተናገረ ደጃች አያሌው ለመንግሥታቸው ታማኝ አገልጋይ የወታደር ወዳጅ መሆናቸውን ነው እንጂ እንደዚህ አገር እንደሚወዳቸውና ደኃ ጠባቂ መሆናቸውን ዛሬ ተረዳሁት የዛሬ መንገዴ ይኸን ሊያሰማኝ እንኳን አመጣኝ አለ አብሮት ያለ ሰው አሰዎ ሰሙዎ ይኸን ሳያውቁ የትኖራሉ የደጃዝማች አያሌው ብሩን ዳኝነት በጌምድርና በትግሬ ጐረቤታቸውን መጠየቅ ነው አለና መለሰ ምን አጠያየቀኝ ያገሩን ደስታ ባይኔ እያየሁ አለና ሁለተኛ መለሰለት ። ከዚህ በኋላ ደጅ አጋፋሪው ፊታውራሪ ገሠሠ ቀረቡና ለግብር ጊዜ ይመሽብናል ዘመድዎንና ሠራዊትዎን ባንድ ቀን ተገናኝተው የሚያልቅ አይደለም አልዋቸው እሺ ደኅና ነው መግባቴን ለጃንሆይ ላስታውቅ አሉና ተነሥተው ወደ ስልክ ቤት ገቡ ካዲስ አበባ ጃንሆይ ቀዳ ኃ ሥ አይሮፕላኑ መንገዱን አያውቀውም ብለው አሳብ ሁኖባቸው ክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስን በስልክ ተጠባበቅና መድረሱን አስታውቀኝ ብለው አዝዘዋቸው ነበርና ክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ በስልክ ይጠባበቁ ነበር ። ወዲያውም ክቡር ደጃዝማች አያሌውና ክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ ተገናኙና ክቡር ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስም ደኅና መግባትዎን ለማስታወቅ ወደ ጃንሆይ እሔዳለሁ እስዎም ወደ ቤትዎ ይግቡ ብለው ለጃንሆይ ሊያስታውቁ ገቡ ። ክቡር ደጃዝማች አያሌውም ደብረ ሕይወት ገብርኤልን እጅ ነሥተው ገቡ ወደቤታቸውም ገብተው ትልቅ ግብዣ ሁኖ ሲበላ ዋለ።በዚህም ቀን ክቡር ደጃዝማች አያሌው ቆሙ ፤ የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ የኢትዮጵያ ብርሃን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጃንሆይ የሚውሉልኝ ውለታ እኔ ከማገለግላቸው ሺህ ጊዜ እጥፍ ድርብ ይሆናል እንኳን እኔ ራሴ ሒጄ በመላክተኛዬ በፊታውራሪ ነጋሽ መርሴ እጅ እሚልኩልኝ በያመቱ ይዘት የሚመጣው መሣሪያና ሽልማት እናንተም የምታዩትና የምታውቁት ነው እኔም በወረቀት እንጂ በቃሌ ማድረስ አይቻልም ። እኔም ብሔድ በየቀኑ በየወሩ የተሸለምሁት የምስራች እያልኩ የምልክባችሁን ወረቀት ቁጥሩን ታገኙታላችሁ እኔም ከመግዛቴና ከወዳጅነቴ ይበልጥ ይልቅ ደስ ያለኝ ላገራችን ለኢትዮጵያ ታላቅ ፀሐይ ወጥቶላት ብርሃንዋ በዲስ አበባ እንደደመቀ ስላየሁ ይህን ላሳየኝ አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው ብዬ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ።

እኔም ለገናናው ጌታዬ ለቀዳ ኃ ሥ እንደጐርፍ የሚፈሱ ወታደሮች ይዤ ወረታ ለመመለስ የተዘጋጀሁ ነኝ ። ዕድሜ ለቀዳ ኃ ሥ ዕድሜ ለእቴጌ መነን ዕድሜ ላልጋወራሽ ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑር ብዬ ጽዋዬን አነሣለሁ ባሉ ጊዜ ባዳራሹ የሞላው ሰው ከዳር እስከዳር ቢያጨበጭብ መትረየስ የተተኰሰ መሰለ ። ስብሐት ዘገየ ዘሀገረ ስሜን ።

በአለፈው ሳምንት የተደረገ ሹምሽር ።

ክቡር ቢትወደድ ወልደ ጻድቅ የምክር ቤቱ ፕሬዚዳን (አለቃ) የምክር ቤቱን አለቅነት እንደያዙ እናጂሊሙን ተሾሙ። ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ዘቡልንና ራያን ተሾሙ። ክቡር ከንቲባ መኰንን ደጃዝማች ተብለው የአገር ግዛት ሚኒስትር ሁነው ሲቡን በዓዛት ጉዳየን በቄራጭነት ተሾሙ፡ ክቡር ደጃዝማች ነሲቡ ባሌን ከናውራጃው ተሾሙ። ክቡር ደጃዝማች መታፈሪያ የወህኒ አዛዥ ተብለው አንኮበርን ከናውራጃው ተሾሙ። ክቡር ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅ የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አለቅነት ተሾሙ ። ክቡር አዛዥ ጤና ጋሻው ከንቲባ ተብለው የአዲስ አበባን ከንቲባነት ተሾሙ።ክቡር ፊታውራሪ ካሣ መስፍን ደጃዝማች ተብለው አቸፈርንና ጉባዬን ተሾሙ።ክቡር ፊታውራሪ ዓለምአየሁ ተድላ

የደጃዝማች ተድላ የልጅ ልጅ ተራስ ኃይሉ በአለመስማማታቸው ተአገራቸው ወጥተው በጣዘት ወደዳር አገር ሲኖሩ ጃንሆይ ምሕረት አድርገውላቸው ደጅ ሳይጠኑ ደጃዝማች ተብለው ከአገራቸው የደጃዝማች አገር ተሾሙ።ግራዝማች ኃይለ ማርያም ወልደ ገብርኤል ሊቀ መኳስ ተብለው ፈረስ ጥፍርን ተሾሙ። ቀኛዝማች ዘውዱ አባኰራን ፌታውራሪ ተብለው በቆጫ ግዛታቸው ላይ የከዶን ቆራጭነት ተሾሙ። ነጋድራስ ሡርፀ ወልድ የጕጃምንና የዳሞትን የቀረውንም የነጋድራስ ወዳጆ ዓሊ የነበረውን ማደሪያና ሹመት ተሾሙ። ፊታውራሪ ግዛው ወለጋ የነጋድራስ ተፈራ ንጉሤ የነበረውን ነጋድራስነት ተሾሙ ።

በአሁኑ ሳምንት የተደረገው ሹም ሽር ።

ክቡር አፈ ንጉሥ መኰንን ደምሰው ቢትወደድ ተብለው ሌቃንና ወለጋን በግዛት፥ ጉድሩ ወረዳን በቆራጪነት ተሾሙ።

ክቡር ፊታውራሪ ጣሰው የግቢ ምኒስትርነትንና የሜጫን አበጋዝነት ተሾሙ። ክቡር አዛጋር ይርዳው በግርማዊት እቴጌ መነን ቤት ዋና አዛጋርነቱን ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም እንኳን ደስ አላችሁ ሹመት ያዳብር ተጌታችሁ ፈቃድ አያውጣችሁ እያለ ደስታውን ይገልጻል ። ሌሎችም የተሾሙ አሉ ስፍራ ቢጠበን ነውና የተውነው ለሚመጣው ጊዜ እንጽፍላችኋለን ።

ስለ ሐውሳ መሬት ሀብት ማስታወሻ ።

የሐውሳ መሬት ሀብታምነቱ ባዋሽ ውኃ ነው አዋሽ ምንጩ ከወርቃ ስለሆነ ሐውሳ እስኪደርስ በመራረዱ ቀኝና ግራ ካሉት ሀገሮች ለመሬት የሚሆነውን ቅባት በክረምት ጕርፍ ሰብስቦ ለሐውሳ ሀብት የሆነ ወንዝ ነው። የሐውሳ መሬት ከምስት አንዱ ያዋሽን ወኃ እያጠጣ የሚታረስ ነው አንድ ጊዜ መሬቱ ወኃ ጠጥቶ ከተዘራ ቡቃያዎች ሳይጠወልጉ ሥራ ሳያስፈልጋቸው አፍርተው ገበሬዎች ያለድካም ሰብላቸውን ይሰበስባሉ አንድ ሰው ሁለት እግር 'ጥጥ ተክሎ በመሬቱ ደግነት በመሰላል ስለተለቀመ ያገሩ ሰዎች ጥቅም አዋቂ ያየብን እንደሆነ አገራችንን ያስበዋል በማለት አጥፍቢሉት ነቅሎ ጣለው ከቶውንም ከማሽል በቀር ሌላ እህል እንዳይዘራ አታክልትም እንዳይተከል ከልክለዋል ይባላል ። የሐውሳ ባላባት ሙሐመድ አንፈሬ የሚባል ነበር ድርቅ በሆነ ዘመን አበሩበሬፋጌ ከሚባለው አገር ቃጥሮ በሚወርድበት ቦታ በታናናስ መሣሪዎች በጦርና በንክሴ ቈፍሮ ያዋሽን ወንዝ ሰብሮ ሁለት ሺህ ጋሻ መሬት በሚሆን ሜዳ ላይ ወሃውን አፍስሶ ሳር እያበቀለ ከብቶቹን ጉዳት ሳያገኛቸው በምቾት ይኖሩ ነበር ይባላል ። ይህ ጥቅም ያለው ቦታ እንደቀድሞ ሣር በማብቀል ብቻ ይኖራል ሣር በማብቀል ተወስኖ ከሚኖር ለመንግሥት አትክልት ቢተከል እህል ቢዘራ ሁለተኛም አትክልት ለሚተክል ገበሬ በግብር ቢሰጡት በጥቅሙ ግናንነት ባታክልቱ ውበት አውሳ ተገኘ ገነት በኃይለ ሥላሴ መንግሥት ተብሎ ስሙ ተሰይሞ ጥቅሙ ለመላዋ ኢትዮጵያ በተሰማት ነበር ። ስሙን የሰየምኩበት ምክንያት ገነት ወደምሥራቅ እንደሆነች አሪት ዘፍጥረት ም፪ ቊ፰ ነግሮናል ምሥራቅ ዘወትር ብርሃን እንደምታፈራ እንዲሁም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘመነ መንግሥታቸው ሰላምነት ጭለማ የማያቋርጠው ለቀሳሚዎች ላገልጋዮች ዋጋቸውን የሚሰጥ ብርሃን ስለሆነ እኛም ለመንግሥት ጥቅም የሚሰጠውን የሚታወቀንን እያመለከትን ላገልጋሎት መታጠቅ ይገባናል።ከባቲ ወደ ሐውሳ ለመንዝ በዝግታ የስድስት ቀን መንገድ ነው ከባቲና ከሐውሳ መከከል እንደሆ ከሚባል ቦታ ላይ ራስ ይመር ከተማ አሰርተውበት ራሳቸውም ነበሩበት እሳቸውም በሌሉ ጊዜ ብዙ ዘበኞች ይቀመጡበት ነበር ለዘበኞቹቀለብ የሚሰጥ እህል ካውሳ ነበር አውሳ ውሥጥ ለሰው ለሕይወት የሚስማማ ቦታ አግኝተው ሁለተኛ ከተማ ለመሥራት ሲያስቡ ወደትግሬ ተሹመው ሔዱ ማለትን እንሰማለን።አሁን የጠረፍና ያውሳ አበጋዝ ተብሎ የተሾመው ሹም ይህን በመልካም ስም የጠራነውን ጠቃሚውን አገር የሹመት አባቱ ያገር ፍቅር ያደረባቸው ሲደክሙበት የነበረውን የተጀመረውን ከተማና ሥራ እያየ ያገሩ ተወላጆች ዘወትር ሲነግሩት ባላፌነት የተቀበለውን ሥራ ለማስፋት ጥቅሙን ለማሳየት የጀመረውን አልሰማንም አላየንም ።

ስለ ንግድ ሥራ

በሐሰብና በትጁሬ በጠረፍ በሮች በወጭና በገቢ የንግድ ዕቃ ቀረጥ በባቲ በር ብቻ በቀድሞው ሠራተኞች ፈቃድ ሲሠራ በነበረ ጊዜ ንግዱ ከሁን በጣም የተሻለ ነበር በዚያው ጊዜ ባመት ካንድ ወ፡ ፲፪ሺ ፻፺፩ ብር ፯መሐለቅ ካንድ ቤሣ ገቢ ነበር።አሁን እኛ ሥራውን ከጀመርን ያንድ ዓመት ካንድ ወር ገቢ ፵፰ሺ፰፻፰ ብር ፯መሐለቅ ገቢ ስለሆነ ካለፈው ጋራ ብናመዛዝነው ብልጫው ፴፮ሺ፰፻፴፯ ብር ካንድ ቤሣ ሆነ ።፪ኛ በደወይ በር የቀድሞ ገቢ ያ፲፩ ወር ፩ሺ ፫፻ ፸፫ ብር ፫መሐለቅ ከቤሣ ነበር እኛ ሥራውን ከጀመርን ያ፲፩ ወር ፲ሺ፫፻፷፩ ብር ፩ መሐለቅ ሆነ ካለፈው ጋራ ብናመዛዝነው ብልጫው ፱ሺ፫ብር ፲፫ መሐለቅ ከቤሣ ሆነ ይኸውም ገቢ ያገባነው የመጀመሯ ጊዜያት ቢሆንም ንግዱ እየሰፋ መሔዱን አስረድቷል ነጋዴዎችም ባቀራረጡ ትክክለኛ ደምብ መሆኑን በውነት ሥራ መሠራቱን ስላወቁት ደስ እያላቸው ነው።

ለጠባቂው ማስታወሻ

ሐሰት አፉን ከፍቶ ያሻውን ቢያወራ።ፍሬውስ ያውልህ
ማንም ማን አይፈራ። ኃይለ ሥላሴ ነው በቀኝም በግራ።
ሁሉም በቅሉ እንዲገኝ እውነት የሚዘራ።ቡቃያው አማረ
እጅግ ፍሬ አፈራ ።

ተፈራ ለወጠኝ።

ማስታወቂያ።

በማናቸውም ምክንያት የመንግሥት ገንዘብ ተበድራችሁ ያልከፈላችሁ ሰዎች ከዚህ ቀደም የገንዘብ አስገቢው ሹም አቶ ወሰን የለህ እንድታገቡልን እያለ በየጊዜው በጽሕፈት ጠይቋችሁ እስካሁን ጨርሳችሁ ስላልከፈላችሁ ከንግዲህ ወዲህ የተበደራችሁትን ገንዘብ እስከ ፲፱፻፳፭ ዓመት ታኅሣሥ ወር መጨረሻ ድረስ በገንዘብ አስገቢው ባቶ ወሰን የለህ በኩል አምጥታችሁ ጨርሳችሁ ወደ ዋናው ገንዘብ ቤት እያገባችሁ የደረሰኝ ከዋናው ገንዘብ ሹም ካቶ ወልደ ጻድቅ እንድትቀበሉ።እስከዚህ ወር መጨረሻ ድረስ ጨርሳችሁ ሳት

ክፍሉ ብትዘገዩ ግን በከተማና በውጭም አገር ያለው ርስታችሁ በሐራጅ ተሽጦ የተበደራችሁት ገንዘብ ተከፍሎ እንዲያልቅና የተረፈው ገንዘብ እንዲመለስላችሁ ማድረጋችንን እንድታውቁት ይሁን። የገንዘብ ሚኒስቴር።

AVIS

Nous constatons avec regret, que diverses personnes, ayant contracté une dette envers le Gouvernement, s'obstinent à n'en pas faire le réglement, malgré des injonctions réitérées, qui leur ont été faites par ato Wossenéleuh, notre préposé à la liquidation des créances du Gouvernement.

Nous invitons, pour une dernière fois, messieurs les débiteurs du Gouvernement, à s'acquitter de leur dette, jusqu'à fin tahessas 1925 (décembre 1932.) Pour ce faire ils devront se présenter à ato Wossenéleuh, qui les conduira à ato Wold-Sadik, notre trésorier central ; ce dernier leur délivrera l'acquit de leur dette Passé ce délai, le ministère des finances, se truvera dans l'obligation de rentrer dans ses créances, en vendant aux enchères toute propriété du débiteur, se trouvant en ville et ailleurs.

En cas où le produit de la vente présenterait un solde, après le réglement de la dette, cette somme sera retournée au propriétaire.

Le Ministre des Finances.

ኦቦማልቲን
ጤና ይሆናል።

OVOMALTINE
c'est la Santé

ኦቦ ማልቲን ለልጆች የተሻለ ጤና የሚሰጥ ምግብ ነው። እንደዚሁም ለበሽተኞችና ለገመምተኞች ለፀነሱ ሴቶችም ጤና የሚሰጥ ሁነኛ ምግብ ነው፤ኦቦማልቲን የብርታት ምንጭ ነው። ማናቸውም ቢሆን አንድ ፍንጃል ኦቦማልቲን ከቍርስ በፊት ቢጠጣ የቀኑን ሥራ ያለ ድካም እንዲፈጽም ኃይል ይሰጠዋል። የሚሠሩት ዶክቶር አ ዋንደር ሰ አ፡ ቤርን ናቸው።በኢትዮጵያ ወኪሎች ዶክቶር ኤሪክ ዋይንስንጀር አዲስ አበባ ናቸው ።

ኦቦማልቲን አዲስ አበባባሉ በዋና ምግብ ሻጮችና በመድኃኒት ሻጮች ቤት ይሸጣል። ሣጥኑ ፪፻፶ ግራምና ፭፻ ግራም ይይዛል።

Japanise Dentist
ምስተር ኤስ ኢማይ

የጃፓን ዋና የጥርስ ሐኪም ስለሕክምናው የተመሰከረለት የሕክምና ሥራውን በጥንቃቄ እየሠራ በርካሽ ዋጋ የሚያክም ከጧቱ በ፫ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ ሰዓት ከእኩለ ቀን በኋላ ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስከ፲፪ ሰዓት ድረስ ወደ ሕክምና ቤቱ የሚመጡትን ሰዎች ሁሉ በትሕትናና በደስታ እየተቀበለ ያክማል ቤቱም ወደ ባቡር ማቋሚያ በሚወርደው በትልቁ መንገድ አጠገብ የአቶ ማርቆስ ቤት ነው ።

WHITE HORSE WHISKY

ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን ልትጠጣ ብትፈልግ ባለትልቅ ምልክት ኤኮስ ባለነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና በጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወከሎታል በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በክዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

ከዚህ ቀድሞ ብዙ ጊዜ እንዳስታወቀው የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር ቀጥሎ ያሉትን የባለ ቆዶችን ቦታ ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፫ዓ ም ከጧቱ በ፬ ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት በርስት ክፍል ቢሮ በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ በማክበር ያስታውቃል።

የባሻ ወልዴ ዮሐንስ አጥቢያው ማርያም ስፋቱ ፲፩ሺ ፯፻፳፬ ሜትር ካሬ ።

የወይዘሮ ዓመተ መንፈስ ቅዱስ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፩፻፴፯ ሜትር ካሬ።

የወይዘሮ ወለተየስ ሀብቱ አጥቢያው ጊዮርጊስ ስፋቱ ፪ሺ ፫፻፲፫ ሜትር ካሬ።

ስለ ሙዚቃ ሸክላ ማስታወቂያ ።

የመንግሥት ሙዚቃ አስተማሪ ሙሴ ኬ ናልባንዲያን ያወጡት የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙርና የተፈሪ ማርሽ የሙዚቃ ሸክላ (ከኮሎምቢያ ኩምባንያ)አስመጥተዋልና ይኸውም ሸክላ የኩምባንያ ወኪል ሙሴ አርሜናክ ፓርሴጊያን ዘንድ ይገኛል ። ይህንኑ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ዋጋው አራት ብር ተኩል ነው ሱቁም ከግሪክ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ፊት ለፊት ነው።

ማስታወቂያ።

ለኢትዮጵያ ሰው የሚሸጥ ርስት ።

የባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ሂሳብ አጣሪዎች በ፫ሺ፱፻፳፬ ቍጥር የተጻፈውን ርስት ስፋቱ ሺ፮፻፶፯ ሜትር ካሬ ፡ አጥቢያው ሥላሴ ከደጃዝማች ከበደ ጓንጕልና ከንቡረ እድ አድማሱ ቦታ ጕረቤት ጥንት የባለዕዳችን የዋጣ ሥዩም ጓርማይ ርስት የነበረውን ለመሸጥ ስላሰበ ይኸንን ማስታወቂያ ለሕዝብ ይገልጻል ። ለመግዛት የሚፈልጉ ሰዎች አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ባንክን ለመጠየቅ ይችላሉ።

ስለ ባንክ ኦፍ አቢሲኒያ ሂሳብ አጣሪ ፊርማ።

ፋርማሲ ሣንትራል

መድኃኒት ቤት አዲስ አበባ B. P. N. 254

Pharmacie Centrale

ውድ እመቤቴ ።

በዚሁም ጊዜያት ጠቅላላውን የሴቶችና የወንዶችን ውብቶች በሚያስረዳበት ጊዜ ግን ውቢቱ እመቤቴ ቀልጣፋና አቋቋመ መልካም እንድትሆን ይኸውም አየራሙዘመናት ይፈቅዳል በሚያሳዝነው አቀማመጣቸው ብዙ ሰዎች በሽተኞች ናቸው ። ደግሞም በምግባቸው አኑዋኑዋር እንዲሁም በጨካኝነትና ችግረኛ በመሆናቸው ለመዳንም አይችሉም ። ለነዚሁም ሰዎች ብዙ ጊዜ የተወደደና በእውነት የማይሳሳተውን መድኃኒት እንሰጣቸዋለን። ሊፖቶዴን የሚባለውን በጥቅልል ያለውን መድኃኒቴን በጣም ሲያስጨንቅዎትና ሲያምዎት ቢሞክሩት ሕመምዎን በማቅለሉ ብዙ ደስ ያሰኝዎታል በአዲስ አበባ ውሥጥ ግዙፎችንና ሰውነተ ቁጡ ለሆኑ ሰዎች አየሩ አለመስማማቱን ይልቁንም ከኔ የበለጠ ያውቁታል።ይልቁንም ደግሞ ዋና ማስረጃ እንቅልፍ ለሌለውና ለሚባንን ሰው ነው ።

ለነዚሁም ሰዎች ፈጽሞ የሚከለክልላቸውን ዲአል ኮምፕሬሜ የሚባለውን መድኃኒታችንን በጣሙ የጠራውን ከምንሰጣቸው በተቀር ሌላ የማያስፈልግ መሆኑን እናስታውቃችኋለን ። ደግሞ ከዚህ በኋላ የሰውነት ሥራቸውን ተስማምተው ያለ ሐሳብ ሌሊቱን በደስታ ያልፉታል ስል ባለኝ እውቀቴ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አሳስባለሁ

ታዛዣዎ ኤም ማትሳኪስ ።

BRITISH MUSEUM 21 38

ሴንጀር የስፌት መኪና ኩባንያ

ሕይወት ሁሉ ጊዜ ያለችና ለብልሆች በጊዜአቸው በምድር ላይ እንዲአሻሽሏት የተዘጋጀች ነች። ከዚሁም አንዱ እርሻና ማሻሻል ነው ይመስገን ለብልሆችን ሕይወታችን ካንድ ቀን እንድ ቀን እየተዋበች ሔደች ቀጥሎም አንደኛው ሴንጀር ኩባንያ ነው ጊዜ የማያጠፋና ድካም የሌለው ለሕይወት የሚስማማ የስፌት መኪና ለዓለም የሚአቀርብ ለቤተሰቦች ፩መኪና በዱቤ እስከ ፴ወር እንዲወስዱ ይፈቅዳል የቤተሰብ መኪና የሚገዛ ሁሉ መቍረጥ መስፋትና መጥለፍ የቀረውንም ሥራ ሁሉ አለገንዘብ መማር ይችላል። የከበሩ መኳንንቶችና ወይዛዝሮች በታቻላቸው ጊዜ መጥተው የሴንጀር የስፌት መኪና ትማሪ ቤት እንዲጐበኙና ደምቡንና ትምህርቱን እንዲረዱ ሙሉ ፈቃዳቸው ነው።

ሕይወታችሁንና ንብረታችሁን የቤተሰብ መኪና ገዝታችሁ አሻሽሉት ብዙ ጥቅምና ትርፍ ታገኙበታላችሁ ። አትዘግዩ ለመንብኘት ።

ማስታወቂያ ።

ዶክተር ሚካኤል ።

በሞንፐሊዬ ኡኒቨርሲቴ ።

ስለውሥጥና የሴት በሽታ ፤የቀዶ-ስልና ፤የዓይን በሽታ የሴት አዋላጅነት ሕክምና የተመሰከረላቸው ድሮ ራስ መኰንን ድልድዩ ቤታቸውን ትተው ወደ ጉለሌ መንገድ ሙሴ ሙራዲያን ቤት አጠገብ ቤት መለወጣቸውን ለወዳጆቻቸው በማክበር ያስታውቃሉ ።

ሁሉ ቀን ከጧቱ ከ፫ ሰዓት እስከ ፮ሰዓት ደግሞ ከ፱ ሰዓት እስከ ፲፩ ሰዓት ይገኛሉ ።

ሐሙስ ዕለት በጧቱ በሽተኞች አለዋጋ ያክማሉ ።

የሚሲዮን መጽሐፍ መሸጫ ቤት ።

የሱዳን ኢንቴሪዮር ሚሲዮን ዶክቶር ለምቢ ዲሬክቶር ወደ ራስ መኰንን ድልድይ በሚወስደው መንገድ ማጅስቲክ ሆቴል የሚባለውን አለፍ ብሎ መሐመድ አሊ ኩባንያ አዲስ ሱቅ አሰራበት አገጠብ የመጽሐፍ መሸጫ ቤት መክፈቱን ያስታውቃል ።

ከዚያ በያይነቱ የጽሕፈት መሣሪያና በፈረንሣዊ በአማርኛም በእንግሊዝም በሌላም ቋንቋ የታተሙ መጽሐፍ ቅዱስና ደግሞም ማለፊያ ማለፊያ መጽሐፎች ይገኛሉ ።

በየዓይነቱ የኪስና የእጅ ሰዓት የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ።

ማስታወቂያ ።

በሲሊዎስ አስላኒዲስ በአዲስ አበባ ጃሜሌር ሱሚስ ዋልድ ቤርን(ሱዊስ)በተለየ ወኪልነው



ወደፈለጉት አንሥቶ ለማዞር የተመቸ መጋዝና ለዕንጨት ሥራ የሚሆን መኪና አስመጭ

ቁ ፤ ፪፻፳ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።